أمهري

ለደስተኝነት የሚያበቃ መንድ

የደስተኝነት ልበለድ

ግራ ያጋቡ ጥያቄዎችና ... የሕይወት ፍልስፍና

ልበለድ

ዶ/ር ዐብዱላህ ብን ሳሊም ባህማም

2014 - 1435

ልበለድ
የደስተኝነት ልበለድ
ግራ ያጋቡ ጥያቄዎችና ... የሕይወት ፍልስፍና
ዶ/ር ዐብዱላህ ብን ሳሊም ባህማም

የደስተኝነት መንገድ

ግራ ያጋቡ ጥያቄዎችና … የሕይወት ፍልስፍና

www.path-2-happiness

بسم الله الرحمن الرحيم

ሽማግሌው

www.path-2-happiness.com

1 ሽማግሌው

ሽማግሌው

(1)

ለብዙ ጊዜ አብሮት የቆየው ከባድ ጭንቀትና መደበት ከጎበኘው በኋላ ለመወሰን ቆረጠና ወረቀት አውጥቶ የሚከተለውን ማስታወሻ ጻፈ ፡-

‹‹ካትሪና የኔ ፍቅር መሄዴ ነው አልመለስም፡፡ አብሮኝ የኖረው ዕድለ ቢስነትን እንዲያበቃ አደርጋለሁ፡፡ እቅጩን ልናገርና መኖሬን አበቃለሁ፤ራሴን አጠፋለሁ፡፡ አንቺም ይቅርታ አድርጊልኝ፣ ልጆቼም ይቅርታ ያደርጉልኝ››፡፡

መንገዱን ቀጠለ . .

ከራሱ ጋር ደጋግሞ የመከረ ቢሆንም እያመነታ ነበር፡፡ ካለበት ስቃይ ለመገላገል ሕይወቱን ከማጥፋት ውጭ ሌላ መፍትሔ አልታየውም፡፡ ‹እውን እኔ ሕመምተኛ ነኝ ማለት ነው? ካትሪናማ ዘውትር እንደዚያ ነው የምትለው! ሁሌም እምነትና እርግጠኝነት እንዲኖረኝ ስትጎተጉተኝ ነው የኖረችው፣ አዘውትራም ፡-

- አንተ ጆርጅ፣ጥርጣሬ'ኮ በሽታ ነው፣ፈጽሞ እጅ አትስጠው፡፡ ትለኛለች›

እያለ ከራሱ ጋር እያወራ በአዝጋሚ እርምጃ ይራመድ ነበር፡፡

ሌላው ቀርቶ አባቱ እንኳ ሕመምተኛ ነው ብሎ ስለሚያምን፣ የጥርጣሬ በሽታ በዘር የሚተላለፍ እንደሆነና ከናቱ ቤተሰቦች ወደርሱ የተላለፈ መሆኑን እፊቱ ደጋግሞ እየተናገረ ካላቆመ መጨረሻው የአእምሮ ሕሙማን መታከሚያ ማእከል እንዳይሆን ይመክረው ነበር! የሥራ አለቃው ይሁዳዊው ካኸም እንዲሁ ብዙ ጊዜ ይስቅበታል፡፡ አዘኔታና ፌዝ በተቀላቀለበት ቅላጼ ፡-

- ወዳጄ ጆርጅ፣እኔ በጣም ነው የማዝንልህ፡፡ ፋይዳ በሌለው ነገር ራስህን ታሽቸግራለህ፡፡ የሚያስጨንቅህና የምታሰላስለው ነገር ሀብትህን አይጨምረውም፣ይብሱንም በሕይወት እንዳትደሰት ነው የሚያደርግህ፣ይለዋል፡፡

ጆርጅ የሰላሳ ስምንት ዓመት ጎልማሳ ሲሆን እንደሱው እንግሊዛዊት የሆነችውን ካትሪናን ነው ያገባው፡፡ እሷ ግን በዘር ግንዷ ትውልደ ሕንዳዊ ነች፡፡ ከተጋቡ አስር ዓመታቸው ሲሆን ሦስት ልጆች ወልደዋል፡፡ ትልቋ

www.path-2-happiness.com

ማሪ (ዛሬ ዕድሜዋ አስር ዓመት ይሆን የነበረና በሰባት ዓመቷ የሞተች)፣ ማይክል (ስምንት ዓመት)፣ ሳሊ (ስድስት ዓመት) ናቸው። ትልቋ ልጁ ማሪ በመኪና አደጋ ከሞተች ወዲህ፣ስለ ሕይወትና ሞት ምንነት በማያቋርጥ ሁኔታ የሚያስብና ሁሌም የሚያሰላስል በመሆኑና ለፍልስፍና ባለው ፍቅርና በብሩህ አእምሮው ምክንያት እውስጡ የሚጉላሉ ጥያቄዎች በእጅጉ በዝተዋል። ጆርጅ የመጽሐፍ ቀበኛ የሆነ አንባቢ ሲሆን ፍልስፍናን፣ታሪክንና ሃይማኖቶችን የሚመለከቱ ርእሰ ጉዳዮችን ማንበብ ይወዳል። ምናልባትም የስነ መለኮት አስተማሪ የሆነቸውን ካቶሊኳን ካትሪና እንዲያገባ የገፋፋው ይኸው ሳይሆን አይቀርም።

ጆርጅ ፕሮቴስታንት ቢሆንም ያጣውን እምነትና እርግጠኝነት እርሷ ዘንድ መኖሩን ያውቅ ነበር። እርሱ ከሞላ ጎደል ሁሉንም ነገር የሚጠራጠርና ጥያቄ የሚያበዛ ሲሆን ጥርጣሬዎቹን አሜን ብላ መቀበሏ በጣም ይገርመዋል። ይሁን እንጂ አማኟ ካትሪና ሊኖራት የማይችል ብሩህ አእምሮ፣ንቁ ሕሊናና ሎጂክ ስላለኝ ነው ይህን የምታደርገው ብሎ ነው ሁሌም የሚያስበው። ከርሷ ጋር ብዙ ጊዜ ተወያይቷል። ውይይቶቹ በርሱ በሚወከለው አእምሮና በርሷ በሚወከለው እምነትና አሜን ብሎ መቀበል መካከል፣ አሊያም በርሱ በሚወከለው ተጨባጭ እውነታና በርሷ ተምሳሌታዊ ተምኔት መካከል የሚደረጉ ውይይቶች ሆነው ነው የሚታዩት። ለካቲሪና ግን ወይይቶቹ በርሷ በሚወከለው አምኖ የመቀበል እርግጠኝነትና በርሱ በሚወከለው የጥርጣሬ በሽታ መካከል የሚደረጉ ሆነው ነው የሚወሰዱት። ውይይቶቹ ብዙውን ጊዜ የሚያበቁት በረዥም ዝምታ ሲሆን ሁለቱን የሚያስተሳስራቸው ፍቅር በመካከላቸው ባይኖር ኖሮ ገና ድሮ ነበር የሚፋቱት።

ዳሩ ግና ልጁ ከሞተች በኋላ ጆርጅ ዘንድ እየጨመረ የመጣው ጥርጣሬ፣በመካከላቸው የሚደርጉትን እነዚያ ውይይቶች የበለጠ ጠጣርና ጠባብ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ታላላቆቹ ጥያቄዎችም ‹‹ለምን ዓለማ ተፈጠርን?››፣ ‹‹ለምንድነው የምንኖረው?›› መጨረሻችንስ ወዴት ነው?›› የሚሉ ሆነዋል። ሀሳቡ በሙሉ በዚህ ተይዞ እእምሮው ተወጥሯል። ጥያቄዎቹ ተራና ቀላል ቢመስሉም ከባድና በጣም የተወሳሰቡ ናቸው። ለዚህም ነው የሕይወትንና የፍጥረተ ዓለም ጽንሰ ሀሳቦችን የቀመሩ ባለ ብሩህ አእምሮ ፈላስፎች ብዙ ትኩረት የሰጧቸው። ለጆርጅ እነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ አገኙ ማለት የሰው ልጅ የሕሊና እርጋታ፣የመንፈስ እርካታና ደስተኝነትን አገኘ ማለት ነው።

ራሱን ለመግደል በሚሄድበት ጊዜ ብዙ የሕይወቱ ትእይንቶች ከፊቱ ይደቀኑ ነበር። ትልቋ ልጁ በሆስፒታሉ የድንገተኛ አደጋ ክፍል ውስጥ ሞትን ስትታገል፣ተሸንፋ ውበቷን፣ ሕይወቷንና ነፍሷንም በሞት ስትነጠቅ ታወሰው። ከለታት አንድ ቀን በሥራ ጫና ድክምክም ብሎት በተቀመጠበት ልጁ ማይክል እንዲህ ሲል የጠየቀውም ትዝ አለው :-

- አባዬ በየቀኑ ወደ ሥራ የምትሄደው ለምንድነው?
- ሕይወቴ ተልእኮና ዓለማ እንዲኖረውና ላንተም የሚያስፈልግህንና የምትወደውን ነገር ለማሟላት ነው።
- የሕይወቴ ተልእኮና ዓለማ ስትል ምን ማለትህ ነው ?!
- ሰዎችን ማገልገልና የሰውን ልጅ መጥቀም ማለቴ ነው።
- ለምን ?!

ጥያቄው ውስጡን እያራደው መሆኑ የተሰማው ጆርጅ ብድግ አለና :-

- ነገሩ ከባድ ነው፣ምናልባት አንተም እኔም አናውቀውም !
- አባዬ አንተ ትልቅ ሆነህ ይህን አታውቅም ! እኔ ግን ትልቅ ስሆን ሁሉንም ነገር አውቃለሁ፣ሳላውቀው የምተወው ምንም ዓይነት ትልቅ ነገር አይኖርም።
- ውድ ልጄ ማይክል . . በቃ እርሳው . .

ከዚያም ስቆ ‹‹እነኚን ጥያቄዎች እርሳቸውና በሕይወትህ ተደሰት›› ይህማ ዘውትር በየቀኑ የሚነገረኝ ምክር ነው አለ ለራሱ። ቀጠለናም እንዲህ አለው :-

- አይዞህ፣ አንድ ቀን መልሱን እነግረሃለሁ።
- አባዬ አንተ ትምህርትህን ጨርሰሃለህ፣ብዙ ታነባለህ፣ ግን አታውቅም !
- ውዴ የቤት ሥራህን ጨርሰሃል ?
- አዎ።
- እሺ ደህና እደር።

እርምጃዎቹ እየከበዱት በመሄድ ላይ እያለ ከራሱ ጋር ማውራቱን ቀጠለ፡ ፡ ካትሪና እንደምትለው ሁሉ ሕመምተኛ ሳልሆን አልቀረሁም፣ወይም ካኽ እንደሚለው ሕይወቴን በከንቱ የማባክን ሞኝ ተላላ ነኝ፣አሊያም አባቴ እንደሚለኝ የተወሰወስኩ ነኝ። . . ወይም ደግሞ . . ወይም ማይክል እንዳለው ማይም ነኝ ! ምናልባት ማይክል ትክክለኛ ሊሆን ይችላል። የሚያስቀው ግን ሌሎች ለኔ የሚሰጡኝን የ‹‹በቃ እርሳው›› መልስ ለርሱም የሰጠሁት መሆኔ ነው። ሌሎች ሰዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ እኔም ወደፊት መሸሽን ሳልማር

www.path-2-happiness.com

አለቀረሁም !

ሕይወቱን ለማጥፋት ወደሚፈልግበት ቦታ እያመራ ከባድ የጭንቀትና የመደበት ስሜት ተጠናውቶት እስኪሰክር ድረስ የጠጣበትን ዕለት አስታወሰ፡፡ በዚያ ቀን መኪናውን እየነዳ መጥቶ ከግድግዳ ጋር ተላተመ፡፡ ይዞት የነበረውንና ‹‹የደስተኝነት ፍልስፍና›› የሚል ርእስ ያለው መጽሐፍ በእጁ ይዞ እየተንገዳገደ ከመኪናው ወረደ፡፡ የትራፊክ ፖሊሱ ያዘውና እንዲህ አለው ፡-

- ይኸ የደስተኝነት ፍልስፍና ነው ወይስ ራስን የማጥፋት ፍልስፍና ነው?! ሰክሮ መንዳት ሕገ ወጥ መሆኑን አታውቅም?!

ካትሪና ከትራፊክ ፖሊስ በዋስትና አስለቀቀችውና እንዲህ አለችው ፡-

- ሰክረህ መንዳት አይገባህም ነበር፡፡

በማፌዝ መለሰላት ፡-

- ሁሌ የምትመክሪኝ ‹‹በቃ እርሳው›› እያልሽ አይደል?!
- በዚህ ዓይነቱ አይደለማ፡፡
- አንቺ በየቀኑ እያመሸሽ ለምን ትጠጭያለሽ ?
- እኔ የምጠጣው ኢየሱስን ለማገልገል በቤተክርስቲያን የሚፈጸመውን ስነ ስርዓት ለማክበር ነው፡፡

በሴረኝነት ስሜት እንዲህ አላት ፡-

- ቅዱስ የመጠጥ ጽዋና የተባረከ ስካር ነው፣ ወይስ ሸሽት በሌላ መልኩ ነው?!
- ካንቺ ጋር መከራከር አድካሚ ሆኗል፡፡ ማሰብና ማስተንተንን ስለምትፈሪና ልክ እኔ እንዳደረኩት ሁሉ በመጠጥና በማምሸት ትሸሸጊያለሽ፡፡ ልዩነቱ አንቺ ለድርጊቱ የቅድስና ካባ መደረብሽ ብቻ ነው፡፡

የጆርጅ ቃላት በጣም ጠጣር ነበሩ፡፡ በሀዘንና በተጎዳ ስሜት ተነሳችና ፡-

- ቢያንስ እንዳንተ የአእምሮ ሕሙማን ሐኪም አያስፈልገኝም ! አለችው፡፡
- ምናልባት! ማን የውቃል?!

(2)

በዚህ በጣም ረዥም መስሎ በታየው ጉዞው፣ በመከታተል አእምሮውን በሚያጨናንቁ ሀሳቦችና ትውስታዎቹ ምክንያት ጭንቅላቱ ሊፈነዳ ምንም ያህል ባልቀረበት ጊዜ፣ የማመንታትና ግራ የመጋባት ሁኔታው አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በዙሪያው ያለውን የሰዎች እንቅስቃሴ ሲመለከት ሕይወትም ሆነ ትርጉም የሌላቸው ዕቃዎች የሚንቀሳቀሱ ሆኖ ይታየዋል፡፡ የሰው ልጆች ወደ ሕይወት አልባ እቃዎች መለወጥን እንዴት በጀ ብለው ይቀበላሉ ብሎ ራሱን ጠየቀ፡፡ ድል በተመታ መንፈስ ጉዞውን እንደቀጠለ ዕድሜው በሰባዎቹ ውስጥ የሚገኝ አንድ አረጋዊ ሽማግሌ ደስተኝነት በተሞላው መንፈስ ከልጅ ልጁ ጋር ሲጫወት ተመለከተ፡፡ የሽማግሌው የዋህነት፣ፈገግታውና ሳቅታነቱ ትኩረቱን ሳበውና ቀረብ ብሎ እንዲህ አለው ፡-

- በማቋረጤ ይቅርታ፣ደስተኛ ነዎት?

ሽማግሌው በአግራሞት አየውና ፡-

- አዎ . . ብሎ ከልጅ ልጁ ጋር ወደ መጫወቱ ተመለሰ፡፡

ጆርጅ እንደገና አቋረጣቸውና ፡-

- እንዴት? ማለቴ ለምን ደስተኛ ሆኑ? ለምንድነው የሚኖሩት?

ሽማግሌው ትኩር ብሎ ተመለከተውና ፡-

- ጥያቄህን አንተው ራስህ መልሰሃል አለው፡፡
- እንዴት?
- ለምን እንደምኖር ስለማውቅ ደስተኛ ነኝ፣በአጭሩ ይኸው ነው፡፡
- ለምንድነው እምኖረው? እባክዎን ይንገሩኝ፡፡
- ራስህን ጠይቅ! ይህን ጥያቄ እኔ ልመልስልህ አልችልም፡፡ ያንተው መንፈስና ያንተው ሕይወት እንጂ ማንም አይመልሰውም፡፡
- አደራ ብይዎታለሁ፣እባክዎን ይንገሩኝ፡፡
- ነገርኩህ እኮ ይህን ጥያቄ በቀላሉ የሚመልሰው መንፈስና ሕይወት ነው፡፡ መንፈስህና ሕይወትህ አምነው የማይቀበሉትን ነገር ልነግርህ አልችልም፡፡

በቁርጠኝነት ስሜት ቀጠለና ፡-

- ስለ ሕይወትና ስለ ፍጥረተ ዓለም ያለኝን አመለካከት ባንተ ላይ እንድጭን የምትፈልገው አንተ ልጅ ሆነህ ነው? ወይስ በሌሎች ላይ የመመርኮዝ የጥገኝነት ልማድ የተጠናወተህ ሰው ነህ? መልካም ፈቃድህ ይሁንና

www.path-2-happiness.com

ከልጁ ጋር እንዳልጫወት አታውከኝ?

-በድጋሜ ይቅርታ ያድርጉልኝና መንፈሴና ሕይወቴ እንዴት አድርገው ነው ምላሽ የሚሰጡኝ ?

-አነጋገርህ ከልብ መሆኑ ይሰመኛል፣አንድ ነገር ልንገርህ ፡- የአንገት ጌጥን ብትመለከት ውብ ሐብል ለመሆን እርስ በርሱ መሰናሰል ይኖርበታል:: የኛ ሕይወትም እንዲሁ በእውቀት ሰንሰለት የተሰናሰለ መሆን ይኖርበታል:: የምንኖርበትና . . ደስተኛ የምንሆንበት ምክንያትም ይኸው ነው::

-እንዴት ነው? እባክዎን ይንገሩኝ !

-እውነተኛ ከሆንክ የመልሱን መክፈቻ ቁልፍ የምታገኘው በምርምር በጽናት፣በፍለጋና በቁጠኝነትና ወደ ግቡ ለመድረስ ጥረት በማድረግ ነው::

-ወደ የትኛው ግብ ለመድረስ ?

-ወደ ደስተኝነት!

-እንዴት?

-ወደ ደስተኝነት የሚያደርሰውን መንገድ ፈልግ ! ነፍስህ ትጽናናለችና፣ያንተ ሕይወትና ፍጥረተ ዓለሙም ትርጉም ይኖራቸዋልና! ይቅርታ ጊዜዬን አታቃጥልብኝ፣ከአያቴ ጋር መጫወት እፈልጋለሁ::

-እሺ . . ደግ ነው:: እኔ የደስታን መንገድ አላውቅም:: ይሁንና ቀድሞ ነገር መኖሩ እውነት ከሆነ፣ምናልባት እርስዎ እንደሚሉት በጥረትና በትጋት ወደ ደስታ መንገድ እደርስ ይሆናል!

-መኖሩማ እርግጥ ነው:: ባይኖርማ ኖሮ ሕይወት ትርጉም የለሽ በሆነች ነበር:: ለማንኛውም መልሱን በምታገኝበት ጊዜ የምስራቹን ንገረኝ:: ጽናትና ቁርጠኝነት ካለህ ታገኘዋለህ:: መንፈስህና ሕይወትህ ምላሽ ይሰጡሃል ማለት ምን ማለት እንደሆነም ትረዳለህ:: ለያንዳንዱ የሕይወትህ ነጠላ ጉዳዮች ትርጉም የሚሰጥህን ገመድ ጫፍም ደርሰህ ትጨብጣለህ::

-እንዳሉት እንዲሆን ምኞቴ ነው፣ ግን ስምዎን ማን ልበል? የሚኖሩትስ የት ነው?

-በሕይወት ከቆየሁ በየሳምንቱ ዐርብ በዚህ ሰዓት እዚህ ቦታ ላይ ታገኘኛለህ: : አድራሻህን ስጠኝና አድራሻዬን በኋላ እልክልሃለሁ::

ሽማግሌው ቀጠሉና ወደ ልጅ ልጃቸው ዞር ብለው ኳሱን ወረወሩ:: ጆርጅ በአድናቆት ተሞልቶ ፡-

-በጣም አመሰግናለሁ ይኸውና አድራሻዬ፣አላቸው::

ትቷቸውም ሄደ . .

ትንሽ ሄደት እንዳለ፣ የሥራ ጫና በሚበዛበት ጊዜ እንኳ ተሰምቶት በማያውቅ ሁኔታ ከባድ ድካም ይሰማው ጀመር:: ንቃትና ጥንካሬውን በጥቂቱም ቢሆን ለማስመለስ ትንሽ ለመጠጣት ወሰነ:: ጭንቅላቱ ሲፈነዳ ምንም ያህል እንዳልቀረው እየተሰማው ብሶበት መንገዳገድ ጀመረ:: በዙሪያው ያሉ ነገሮች ምንነት መለየት እስኪያቅተው አዞረው:: በመጓዝ ላይ እያለ አጥወለወለውና ጎዳናው ላይ ራሱን ስቶ ወደቀ:::

ሰዎች በዙሪያው ተሰበሰቡና አንስተው ሲሸከሙት እንደ ምንም ብሎ ቀና ብሎ የቤቱ አድራሻ ነገራቸው::

በራፉ ላይ ካትሪናን እያለቀሰችና እየጮኸች አገኛት:: ገና ስታየው እያለቀሰች ሮጣ ደረቱ ላይ ስትወድቅ ፡-

-ይኸው አለሁ አልሞትኩም አላት::

-ጌታ የተመሰገነ ይሁን፣እንኳን ተረፍክ:: በጣም ነበር የፈራሁት:: ራስህን ለመግደል ለምን ታስባለህ?

-ጆርጅ ከሚባለው ተንቀሳቃሽ እቃ ራሴን ለመገላገል ! የመኖር ትርጉምና የሕይወትን ዓለማ ምንነት ከማያውቀው፣ በየሰከንዱ መንፈሱ ሞቶ ነፍሱ ከሚድነው ከዚያ እቃ፣ከዚያ የመገልገያ መሳሪያ ለመገላገል ነበር: : መንገድ ላይ ያገኘሁት ሽማግሌ ባይኖር ኖሮ፣መጠጥ ባልጠጣ ኖሮ ከሕይወት ተገላግዬ ነበር !

-ሽማግሌው ደግሞ ማነው?

-አላውቀውም፣ግና ደስተኛ ነበር! (በማፌዝ ቀጠለና) ለምን እንደሚኖርም ያውቃል ?!

-ስለምን እንደምታወራ አልገባኝም፣ለማንኛውም ግን በሰላም የመለሰህ ጌታ የተመሰገነ ይሁን::

-ለኔ ለራሴም አልገባኝም፣ የገባኝ ነገር ቢኖር ወደ ደስታ መንገድ ለመድረስ ቁርጠኝነት ፍለጋና ጽናት የሚያስፈልግ መሆኑን ብቻ ነው::

-የደስታ መንገድ ! የኔ ፍቅር ወደዚያ ትደርሳለህ:: ዋናው ነገር ለኛ ታስፈልገናለህና ለሕይወትህ ግድየለሽ አትሁን::

www.path-2-happiness.com

- አህ፣ለሕይወቴ ግድየለሽ ላለመሆን እሞክራለሁ። መልሱን እስከማገኝ ድረስ ፍለጋውንና ምርምሩን ለመቀጠልም ስል፣ያኔ እንደ ሽማግሌው ደስተኛ እሆናለሁ።

ካትሪና በገጽታው ላይ በጣም እንደ ደከመው አስተውላ እጁን ይዛ ወደራሷ አስደገፈችው። ወደ መኝታ ክፍሉ ሲደርሱ አልጋው ላይ ተዘረገፈ። የዕለቱ ገጠመኝ ዝርዝሮች እንደ አስበርጋጊ ጽላሎቶች ጭንቅላቱ ውስጥ እየተወራጩ እንቅልፍ አሸንፎት ጭልጥ ሳተ።

ግራ ያጋቡ ጥያቄዎች!

www.path-2-happiness.com

2 ግራ ያጋቡ ጥያቄዎች!

ግራ ያጋቡ ጥያቄዎች!

(1)

አብረው ሲመለከቱት የነበረው ፊልም እንዳበቃ ካትሪና ወደ ጆርጅ ፊቷን አዞራ ካለበት የሀሳብ ዓለም አባነነቸው :-

-ጆርጅ . . ጆርጅ፣ካለህበት ነገር መገላገል አትፈልግም?

-ምን ማለት ፈልገሽ ነው?! አዎና እፈንዴታ!

- አዲሷ ጎረቤታችን ቶም አሪክሰን የተባለ ታዋቂ የስነ ልቡና ሐኪም መኖሩንና እርሱ ዘንድ መታከሚን አንስታልኝ ነበር።

የተናጋ ስነልቦናዊ ነውጥ መኖሩን የሚያመለክት የተምታታ ስሜት ከፊቱ እየተነበበ ፊቱን ወደርሷ አዙሮ ተመቻችቶ ተቀመጠና በምጸት፡-

-መልካም . . ወደ ስነ ልቦና ሐኪም የምሔደው እባክህን ለምን እንደ ተፈጠርኩና ለምንስ እንደምኖር የማላውቅ መሆኔን እንዴት እንምረሳ አስተምረኝ ብዬ ልጠይቀው ነው?

-ሳይሆን ለምን እንደ ተፈጠርኩና ለምንስ እንደምኖር እንዴት ማወቅ እችላለሁ ብለህ ልትጠይቀው ነው።

-ምላሹን ላውቀው !!

-አዎ።

-ጆርጅ ራሱን ወደ ኋላ ዘንበል አደረገ፤ወዲያውኑ በተለመደ ውስጣዊ ጉትጎታው ተጠልፎ ነጎደ። ጭንቀትና ስነ ልቦናዊ ነውጡ አገረሸበት። በውጥረቱ ማዕበል እየተናጠ ሳለ ጭንቀትና ነውጡ ዳግም ቢሶበት ቢሆን እንጂ በዚህ ሁኔታ ዘንግቷት ጭልጥ እንደማይል ከሁኔታው ያስተዋለችው ካትሪና ጎላ ባለ ቅላጼ :-

- ጆርጅ! አለች።

-አዎ . . አዎ . . ሐኪሙ ዶክተር ቶም ፕሮትስታንት ነው? ወይስ እንዲህ መጓጓትሽ በሌላ ምክንያት ነው? ብዬ ልጠይቅሽ ነበር።

-ጆርጅ የኔ ፍቅር . . ጉጉቴ ደስተኞች ሆነን አብሬን እንድንኖር ነው፣እኔ ከገዛ ራሴ ሆን ብዬ የምሸሽ መሆኔን በሚመለከት ምናልባት ትክክለኛ ልትሆን ትችላለህ፣ግና አንተ ከምትመራው የመደናገርና የጥርጣሬ

www.path-2-happiness.com

ሕይወት የተሻለ አይመስልህም ?!

- መልካም፣የደስተኝነትን መንገድ ፈልጌ ለማግኘት ወስኛለሁ፣ ከዛሬ ጀምሮ መልስ ለማግኘት ጥረት አደርጋለሁ እንጂ ከራሴ አልሸሽም . . ፈገግ አለና ቀጠለ :- ነገር ግን መንገዱን ከካቶሊክ ቄስ ዘንድ ለማግኘት ፍለጋ አልሄድም፣ቆይኝማ መጀመሪያ ስለዚህ ሐኪም ልጠይቅ::
- አጠያይቀን እንፈልገዋለን፣ፈውስህን በርሱ እጅ ያደርግ ዘንድ ለጌታ እጸልያለሁ::
- አሃ፣እናም እኔ ሕክምና የሚያስፈልገው ሕመምተኛ እንጂ ለጥያቄው ምላሽ የሚያፈላልግ ፈላስፋ አይደለሁም ማለት ነዋ !
- መታከሙ ራሱ ወደ ምላሹ ለመድረስ እንጂ ታማሚ ስለሆንክ አይደለም . . በዐይኗ ጠቀስ አድርጋ ደረቱ ላይ በመለጠፍ :- ተስማማን የኔ ፍቅር? አለች::
- ተስማምተናል !

(2)

ጆርጅ ለመታየት ቀጠሮ ከመውሰዱ በፊት ስለ ሐኪም ቶም ለማወቅ ጉጉ ነበርና ወደ ፌስቡክ ገጹ ገባ:: ስለሚሳተፍባቸው ጉባኤዎች፣ስለሚያቀርባቸው ወረቀቶችና ጥናቶች ዓይነት አነበበ፤ በታካሚዎቹ ስለሱ የሚጽፉትንም አነበበ:: በዚህም የመጠቀ አእምሮ፣የጠለቀና የሰፋ ዕውቀት ባለቤት፣የፍልስፍና አፍቃሪና ዘመናዊ ሕክምናን ከተለያዩ የፍልስፍና ጎራዎች ጋር ማጣመር ስለቻለው ዓለም አቀፍ ዝና ስላለው የስነልቦና ሐኪም ከሞላ ጎደል ግልጽ የሆነ ሥዕል አእምረው ውስጥ መቅረጽ ቻለ::

የዶክተሩ ታካሚዎች የሚሰጡትን አስተያየቶችና ሀሳቦች ይከታተል የነበረው ጆርጅ፣ሐኪም ቶም ወጣ ያለ ሰብእና ያለው፣ ዕውቀቱና ሙያው ከግላዊ ስነምግባሩ ጋር የሚጻረር መሆኑን፣ በተለይም ከእንስት ሕሙማን ጋር ባለው ግንኙነት የተዛባ ባህሪ እንዳለው ለመገንዘብ ችሏል:: እንደገመተው ካቶሊክ አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን በሁሉም ሃይማኖቶች የማያምን ኤቲስት መሆኑንም ጭምር አስተውሏል::

ጆርጅ ሐኪሙ ዘንድ ቀጠሮ እንዲያዝለት የማድረጉን ዛሬ ነገ እያለ ያዘገይ ነበር:: የገዛ ራሱን ጋር የማይጣጣም ሐኪም ዘንድ ለመሄድ ምንም ዓይነት ፍላጎት አላደረበትም:: እንደሚሄድ ለካትሪና ቃል የገባላት ቢሆንም ማንገራገሩን ቀጥሎበታል:: አንድ ቀን ከሰዓት አስር ሰዓት ላይ ቀጠሮ የያዘችለት

መሆኗንና አብራው እንደምትሄድ ድንገት ስትነግረው በዚህ ሐኪም ደስተኛ ባይሆንም እሺ አላት:: የማይሳካ ጥረት ቢሆንም የሚጎዳኝ ነገር የለም፣ ከካትሪና ጭቅጭቅም እገላገላለሁ በሚል መንፈስ ነበር የተቀበለው::

ጆርጅና ካትሪና ወደ ዶክተሩ ክሊኒክ አመሩ:: ጸጥ ያለ፣ በውድ ቁሳቁሶች የተዋበ፣ማራኪና አስደሳች በሆኑ ቀለማት ያሸበረቀ ክሊኒክ ነበር:: የቦታውን ውበት የሚያረብሽ ነገር ቢኖር እንግዳ መቀበያ ክፍሉ ውስጥ የተጎለተው እይታውና የፊቱ ሰንበሮች

የማያስደስቱ ግለሰብ ብቻ ነበር:: ጆርጅ ቀጠሮ እንዳለው ሲነግረው፣በጣም ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ :-

- ስሜ በራድ ነው፣ከዚህ በፊት አይቼህ አላውቅም፣ዶክተሩ አሁን ሥራ ያላቸው ይስለኛል፣ አለው::

ጆርጅ ወደ ካትሪና ዞር ብሎ :-

- ቀጠሮ አልያዝሽልንም ነበር? አላት::
- ይዣለሁ እንጂ ! ከሦስት ቀናት በፊት መጥቼ ነው ቀጠሮ የተቀበልኩት:: በራድ ብስጭት ብሎ መለሰ :-
- አዎ . . አዎ . . ይቅርታ ቀጠሮ ወስደሻል፣ኑ ግቡ እየጠበቋችሁ ነው::

ጆርጅ በበራድ ሁኔታ እየተገረመና እየቀፈፈው ከካትሪና ጋር ወደ ውስጥ አመራ:: ሐኪሙ ዘንድ ገቡና ተቀብሏቸው ከሁለቱም ጋር በየግል ለመነጋገር ጠየቃቸው::

ጆርጅ መለሰ :-

- ግን እኮ ቀጠሮው ለኔ ብቻ ነው የተያዘው !
- ካትሪና ባለቤትህ ነች፣ ከሁሉም ይበልጥ ቅርብህ ናት፣ ሁኔታህን ለመረዳት ብዙ ልትጠቅመኝ ትችላለችና በቅድሚያ ከርሷ ጋር ለጥቂት ደቂቃዎች ተነጋግሬ ከዚያ ካንተ ጋር እቀመጣለሁ::

ጆርጅ ወደ እንግዳ መቀበያ ሳሎን በመሄድ አንደኛው ወንበር ላይ በጭንቀት ተውጦ በዝምታ ተቀመጠ ሳለ በራድ እንዲህ አለው :-

- ቶም ከካትሪና ጋር ነዋ !
- ስሟን እንዴ ማወቅ ቻልክ ?
- ከሦስት ቀናት በፊት የመጣችው እሷ አልነበረችም . . አለና በምጸት ፈገግ አለ:: ቶም ለብቻው ከርሷ ጋር ይቀመጣል፣ዶክተር ቶም መቼም በጣም እድለኛ ነው፣ መልከ መልካም ሎጋ ወንድ የምሥራቅ መስህብነት ካላት ውብ ሴት ጋር . .

www.path-2-happiness.com

ጆርጅ ንዴትና ብስጭቱን ዋጥ አድርጎ አንዱን መጽሔት አንስቶ ከበራድ ለመገላገል ያህል አየት አየት በሚያደርግበት ጊዜ ቶም እርሱ ዘንድ ለመታከም ከሚመጡ ሴት ደንበኞቹ ጋር ያለው አጠራጣሪ ግንኙነት ታወሰውና ለማስመሰል ከሚያሳየው እርጋታው ውጭ ለመሆን ተቃረበ:: ነገር ግን ራሱን ያዝ አደረገና ንዴትና ቁጭቱ እየጨመረ ቢመጣም ትንሽ ለመታገስ አእምሮውን ለማሳመን ሞከረ:: ከአስር ደቂቃ በኋላ ካትሪና ፈገግ እያለች ደረሰችና ባሏን ጠራችው:-

- የኔ ፍቅር ዶክተሩ አንተን እየጠበቀ ነው፣አሁን ቤተክርስቲያን ቀጠሮ ስላለብኝ እኔ መሄድ አለብኝ::

ጆርጅ ወደ ዶክተሩ ክፍል ገባ:: እፊቱ ላይ እንደነበረ አይቶት የነበረው የፈገግታ ዱካ ጥፍት ብሎ ሐኪሙ ጭፍግግ ባለ ገጽታ ተቀበለውና :-

- ማን እንደ ፈጠረህ፣ለምን ዓለማ እንደምትኖርና መጨረሻህ ምን እንደሚሆን ማወቅ የምትፈልገው ለምንድነው? አለው::
- መንፈሴና ሕይወቴ ተቀናጅተው ዓላማና ትርጉም ያለው ሕይወት እንዲኖረኝ ስለምፈልግ ነው::
- አሀ፣ ልዩና የብሩህ አእምሮ ባለቤት የሆነ ምሁር ሁኔታ ያጋጠመኝ መሰለኝ፤ለምን የፍልስፍናዊ አስተሳሰብ መንገዶችን አትጠቀምም?
- ማለት የፈለከው ነገር አልገባኝም?
- አንተ ፈላስፋ እንዴት ነው ያልተረዳኸው! በፍልስፍናዊ መንገድ መልስ ስንሰጥ እያንዳንዱ መልስ ምላሽ ለመስጠት በሚያግዙ ጥቅል ጥያቄዎች ላይ የሚሞረከዝ ይሆናል::

ከአፍታ ዝምታ በኋላ ቀጠለ :-

- ለጥያቄዎችህ ምላሽ ለማግኘት ሌሎች ጥያቄዎችን አቀርብልሃለሁ:: ለምሳሌ :- መልሱን ከዬት ማግኘት እንችላለን? ወደ ምላሹ ተልቀን ከመግባት ፈንታ ከየት ልናገኘው እንችላለን? ትክክለኛ ስለመሆናቸው መለኪያቸው ምንድነው? የሚለውን እንመልከት:: ይኸኛው ምክንያታዊና ፍልስፍናዊ የሆነ አርኪ መንገድ አይመስልህም?
- ምናልባት !
- ምላሹን ከውስጥህና ከመንፈስህ ውስጥ ለማስወጣት ይህ መንገድ በጣም ምርጥ ነው:: ፈገግ ብሎ ቀጠለና :- እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ነገሮችን አእምሮን ሳይጠቀሙ እንዳው አምኖ በመቀበል ላይ ከተመሰረተው የካቶሊክ መንገድም ያለ ጥርጥር የተሻለ ነው! ቀጠሯችን መጪው ሳምንት ነው::

ቀጥሎ ላሉት ሁለት ጥያቄዎች መልስ ይዘህልኝ ለመምጣት ሞክር:: ወደ መልሱ መድረስ የምንችለው በየት በኩል ነው? ለምላሹ ትክክለኛ መሆንና አለመሆን ዋስትናው ምንድነው? ተስማማን?

- ስለ ካቶሊካዊነት የተናገርከው መጥፎ ከመሆኑም ጋር ሎጂካዊና ምክንያታዊ ነውና ተስማምተናል::

ጆርጅ የዶክተሩን ክፍል ለቆ ሲወጣ ዓይኖቹ በራድ ላይ አረፉ:: በራድ መሰሪ ፈገግታ አሳየውና :-

- መልካም የሕክምና ጉብኝት፣ ሰላምታዬን ለካትሪና አድርስልኝ !

(3)

የቶም ጥያቄዎች፣የአነጋገር ስልቱ፣አስተሳሰብና ሎጂኩ፣ . . እነዚህ ሁሉ በጆርጅ አእምሮ ከሚመላለሱ ሃሳቦች ብዙውን ክፍል ይዘዋል:: በነበሩኝ ጥቄዎች ላይ ቶም ጥያቄዎችን ጨመረልኝ፤የሐኪሙ ፋይዳ በጥያቄዎቼ ላይ ጥያቄ መጨመር ነው ማለት ነው ! ብሎ ከራሱ ጋር እየተነጋገረ መኪናውን ይነዳ ነበር::

በቅርበት ወደሚገኘው ካፌ አመራና ቡና አዘዘ:: አስተናጋጁ አቀረበለትና ጠረጴዛው ላይ አኖረለት:: ጆርጅ ያላየው መሆኑን ያስተዋለው አስተናጋጅ ማቀረቡን ለማሳወቅ ድምጹን ቢያሰላም ጆርጅ በሃሳብ ዓለም የነጎደ በመሆኑ ትቶት ሄደ:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ ጠረጴዛው ላይ የቀዘቀዘ ፍንጃን ቡና መኖሩን ሲመለከት አስተናጋጁን ጠራና ጠየቀው :-

- ቡናውን አቅርበህ ማስቀመጥህን ጭራሽ አላወቅኩም ብልህ ታምናለህ፤ አንዳንድ ጊዜ ውስጣዊ ጥያቄዎቻችን የገዛ ራሳችንንም እንድንረሳ ያደርጉናል !
- ውስጣዊ ጥያቄዎች የንቁነትና የብልህነት ምልክት ናቸው፤ ይሁን እንጂ . . ሲበዙ ግን ውስጣዊ ትግል፣ የሃሳቦችና የእምነቶች የርስበርስ ፍጭት መኖሩን የሚጠቁም ምልክት ይሆናሉ::

ጆርጅ በአስተናጋጁ ንግግርና በትንተናው ተደንቆ ምልልሱን ቀጠለ :-

- ባንተ ግምት የነዚህ ፍጭቶች ወይም ቅራኔዎች ምክንያት ምንድነው?
- ምክንያቶቹ በርካታ ናቸው፤ከዋነኞቹ መካከል፣ ለምንድነው የተፈጠርነው? የምንኖርለት ዓላማ ምንድነው? መጨረሻችንና መመለሻችንስ ወዴት ነው? የሚሉትን የመሳሰሉ ታላላቅ የሕይወት ጉዳዮችን በተመለከተ ባለቤቱ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ላይ ገና ያልደረሰ መሆኑ አንዱ ነው:: ችግሩ

ያለው ነገሮችን ውስብስብ በማድረጉ ላይ ነው:: ነገሮችን ቀለል አድርጎ መውሰድ ለጥያቄዎቹ፣ በአብዛኛው ከአፍአዊነት የማያልፈው ውስብስብነት የማይሰጠንን ጥልቀት ያለው ምላሽ ይሰጣናል!

ጆርጅ በአግራሞት ተውጦ ዐይኖቹን ፈታና :-

- ለነዚህ ጥያቄዎች እንዴት ነው በቀላሉ ምላሽ ማግኘት የምንችለው?
- ብዙዎች በአልባሌ ነገር፣በመጠጥ፣ወይም በወሲብና በሌሎች ነገሮች ውስጥ ከምላሹ ይሸሻሉ:: ጥያቄው በራሱ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ የሕሊና ንቃት ምልክቶች አንዱ ነው፤ግና . .

ሌላ ደንበኛ ስለጠራው አስተናጋጁን አጠር ያለ ውይይታቸውን አቋርጦ ጆርጅን ይቅርታ ጠየቀና የቡናውን ሂሳብ ተቀብሎት ሄደ::

የአስተናጋጁን ንግግር መርሳት የተሳነው ጆርጅ በሃሳብ ባዝኖና ግራ ተጋብቶ የሚሄድበትን ሳያውቅ መኪናውን ይዞ ወጣ:: አስተናጋጁ ውስጣዊ ስሜቱን ኮርኩሮ ልቡን ነክቶታል:: የቡናውን ዋጋ አስር ጊዜ ከፍሎት አስተናጋጁ የጀመረለትን ምልልስ ቢያሟላ ኖሮ ይመኝ ነበር:: ይህ አስተናጋጅ ተራ ሰራተኛ ከመሆኑ ጋር ባሳደረበት የደስታ ስሜትም ይገረም ጀመር:: ከቁመናውና ከተክለ ሰውነቱ ምናልባት ግሪካዊ ወይም የግሪክ አሊያም የላቲን የዘር ግንድ ያለው ሳይሆን እንደማይቀርም ገምቷል::

ጆርጅ ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ አካባቢውን ሳይለቅ እዚያው በነበረበት ሰፈር እያሽከረከረ መሆኑ ትዝ ብሎት ዳግም ወደ ነበረበት ካፌ ለመመለስ ወሰነ:: መጥቶ ተቀመጠና የተለመደ ቡናውን አዘዘ:: ቡናውን ሌላ አስተናጋጅ ሲያቀርብለት ከርሱ አስቀድሞ የነበረው አስተናጋጅ የት እንደሆነ ጠየቀው::

- ጌታዬ ማንን ማለትዎ ይሆን?
- ከግማሽ ሰዓት በፊት መጥጬ ያስተናገደኝ ሌላ ሰው ነበር::
- ምናልበት ካት ወይም አደም ይሆናል፤ተራቸው ከአንድ ሰዓት በፊት አብቅቶ አሁን የኛ ተራ ነው::

ጆርጅ ቡናውን ቶሎ ቶሎ ፉት አደረገና ለመሄድ ሲነሳ አስተናጋጁን ጤቀው :-

- የካት ወይም የአዳም ተራ መቼ ነው የሚጀምረው?
- ነገ ጧት ከሦስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አስራ አንድ ወይም አስራ ሁለት ሰዓት ድረስ ነው::
- አመሰግናለሁ::

(4)

ጆርጅ ወደ መኖሪያ ቤቱ ተመለሰ:: ሁለት ሕጻነቱ ተቀበሉት:: እናታቸው የት እንደሆነች ሲጠይቃቸው አሁንም እዚያው ቤተክርስቲያን መሆኗንና ምናልባትም እስከ ሌሊት ድረስ ትንሽ መዘግየቷ እንደማይቀር ማይክል ነገራት::

ካትሪና ከበቤተክርስቲያኑ እስክትመጣ ሳሎን ቤት ቁጭ ብሎ ጠበቃት:: ሰክራ ራሷን ባትስትም ደካክማና ብትንትኗ ወጥቶ አልኮል አልኮል እየሸተተች ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ደረሰች:: ገና ጆርጅን ስታይ ጠየቀችው :-

- የዶክተሩ ነገር እንዴት ሆነ ?
- በመጠኑ አሳማኝ ቢሆንም እንግዳ ባሕርያት ያሉት ሐኪም ነው:: ከዚያም ወደ ካትሪና ፊቱን አዞረና ጠበቅ ባለ አነጋገር :- ለብቻችሁ በተቀመጣችሁ ጊዜ ካንቺ ምን የፈልግ ነበር?
- የኔ ፍቅር አላውቅም፤ተቀበለኝና ራሱን አስተዋውቆ ችሎታውን ነገረኝ፤ከዚያም ስለ ሥራዬና ስለ ኑሮዬ ጠየቀኝ . . ስልጡንና በጣም የተገራ ሰው ነው::
- መልከ መልካም ሎጋም ነው! ስለኔ ምንም አልጠየቀሽም?
- ልወጣ ስል ጠይቆኝ የሕይወትን ምንነት የሚመለከቱ ጥያቄዎችህ እንደሚያስጨንቁህ ነገርኩት::
- ይኸው ብቻ ነው ? !
- ይኸው ብቻ ነው፤አብዛኛውን ጊዜ ስለራሱና ስለኔ ነበር የሚናገረው:: እንዴት ያለ ጨዋ መሰለህ!
- አይ፣በሃይማኖቶች የማያምንና ሃይማኖተኝነትን የሚዋጋ፣ ሃይኖማቶችን በሽታ አድርጎ የሚመለከት ኤቲስት ከመሆኑ ጋር፣ስለርሱ የምትናገሪው የሚገርም ነው:: እንደሚመስለኝ ጋጠ ወጥ ባለጌም ነው !
- ጆርጅ ! ከኔ ጋር እጅግ በጣም ጨዋና ትሁት ነበር! የስነ መለኮት መምህርት መሆኔን ካወቀ በኋላ እንኳ ስለ ሃይማኖት በጭራሽ አላነሳልኝም:: ለማንኛውም አንተ ወደርሱ የሄድከው ለሚሰጠው ሕክምና እንጂ ለሃይማኖቱም ሆነ ለስነ ምግባሩ ብለህ አይደለም !
- ያመሸሽውና ስትጠጭ የነበረው ከማን ጋር ነው?!
- ተቆጣጣሪዬ አይደለህም፤መልስ አለመስጠት መብቴ ቢሆንም ለማንኛውም በቂሱ ቡራኬ ሰጭነት በተመራ ድግስ ላይ ነበርን::

የካትሪና፣ማምሸትና አልኮል መጠጣቷ ጆርጅን ብዙ ጊዜ ያሳስበዋል፤ጊዜና ጥረቷን የሰጠችውን ሃይማኖተኛነት የሚጻረር መሆኑንም ያምናል:: ይሁንና ምናልባት ትንሽ ጠና ያለባት መስሎ ታሰበውና የጨዋታውን ርእስ መለወጥ ፈልጎ በቀልድ መልክ :-

- የጥያቄዎች ስብስብ ነበረኝ፣እርሱም በጥያቄዎቼ ላይ ጥያቄ በመደናገሬ ላይ ሌላ መደናገር ነው የጨመረልኝ !
- እንዴት !
- ለጥያቄዎቼ መልስ እንደመስጠት ሌሎች ጥያቄዎችን ጠይቆኝ መልስ እንድሰጥባቸው ጠየቀኝ::
- ሌሎች ጥያቄዎችሌሎች ጥያቄዎች !
- አዎ፣ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ የምናገኘው ከየት ነው? መልሶቹ ትክክል ስለመሆናቸው ዋስትው ምንድነው? የሚሉ ናቸው::
- ጥያቄዎቹ እንግዳ ከመሆናቸውም ጋር ምናልባት እውነቱን ሊሆን ይችላል!
- ይህን እርሽው፣ ዛሬ እውስጤ ጠልቆ ስሜትን ከነካ ሌላ አስደናቂና ሰው ጋር ተገናኘ፣ሐኪሙ ዘንድ በሄድኩበት ያው ጉዳይ ላይ ባልጠበኩት አጋጣሚ አነጋገረኝ!
- በዚያው ርእስ ላይ!
- ይህ መቼም እጅግ የሚገርም አጋጣሚ ነው!
- ምን አለህ ?!
- በትክክል ይህ ነው ማለት አልችልም፣ከኔ ጋር የጀመረውን ውይይት አልቋጨውም:: ይሁን አንጂ ከቶም በተቃራኒ ሃይማኖተኛ ሰው ይመስለኛል:: ጥያቄዎቹን ውስብስብነት በሌላው ቀለል በሆነ ሁኔታ ስለመመለስ፣ቀለል ማድረግ ጥልቀት ያለው ስለመሆኑ፣ስለ ሕይወት ትርጉምና ስለ ደስተኝነት ይናገር ነበር:: ዓይኖቿን ትኩር ብሎ እየተመለከተ :- ሰዎች ከምላሹ በመሸሽ አስካሪ መጠጥ በመጠጣት፣ በማምሸት፣በመጨፈርና በመሳሰሉት ውስጥ ራሳቸውን ከራሳቸው ለመሸሸግ የሚሞክሩ ስለ መሆናቸውም ሲናገር ነበር !
- ሃይማኖተኛ በመሆኑ ንግግሩ መልካም ሲሆን፣ሰዎች ከምላሽ መሸሻቸውን በተመለከተ ግን ምናልባት ትንሽ ያከረረ ሳይሆን አልቀረም ! ‹‹አፈገገችና›› :- ምናልባት ካቶሊካዊ ይሆናላ ! የኔ ፍቅር ምናልባት ስለደካከመህ በምትናገረው ጉዳይ ላይ ትኩረትህን መሰብሰብ አልቻልክም !
- ምናልባት . . አዎ ምናልባት፣ለማንኛውም ግን ውስጣዊ ስሜቴን ነው

በጥልቀት የቀሰቀሰው:: አሁን እንተኛ፣ነገ ብዙ ሥራ አለብኝ::

ጆርጅና ካትሪና ወደ መኝታ ቤት አመሩ:: ለመተኛት እንደ ተዘጋጁ የካትሪና ስልክ አቃጨለ:: በተረበሸ ስሜት ተመለከተችውና አንስታ አጠር ባሉ ፈጣን ቃላት መልስ ከሰጠች በኋላ ረዘም ላለ ጊዜ በዝምታ ስታዳምጥ ቆይታ ጥሪውን አበቃች :-

- ቀጠሮአችን ረቡዕ ምሽት ሁለት ሰዓት ነው፤ቤተክርስቲያኑ ውስጥ አብረን እናመሻለን::
- ማነው የደወለው?!
- ካቶሊካዊነትን መማር የሚፈልግ ሰው ነው::
- በምሽት ድግስ ነው የሚማረው !
- ቤተክርስቲያን ውስት የሚደረግ የምሽት ድግስ እንጂ የመሸታ ቤት የብልግና ጭፈራ አይደለም! በመካነ መቃቢር እንዲማር ትፈልግ ኖሯል ! ተወንና አሁን እንተኛበት፣ በጣም ስሱ ሆነሃል::

(5)

- ጆርጅ ጧት ከካትሪና ቀድሞ ነቃ:: በመጀመሪያ ከፊቱ ድቅን ያለው ለምን ወደርሱ እንደሚሳብ ምስጢሩን ማወቅ ያልቻለው አስተናገጅ ነበር:: ዳግም ከርሱ ጋር ለመገናኘት ወደ ካፌው ለመሄድ ወሰነና የማታው የስልክ ጥሪ ታወሰው:: የካትሪናን ሞባይል ወስዶ በመክፈት ሌሊት የደወለላትን ሰው ቁጥር ከወሰደ በኋላ ወደ ቦታው ለምን እንደመለሰ አያውቅም::
- ጆርጅ ወደ ሥራው አማልዶ ሄደ:: ትናንት ሐኪም ቤት ለመሄድ ፈቃድ ወስዶ ስለነበር ብዙ የተወዘፉ ሥራዎች ነበሩት:: ወደ ቢሮው ገብቶ ሥራው ላይ እንዳቀረቀረ የቢሮ ስልኩ ጮኸ:: የሥራ አለቃው ካኽ ነበር :-
- ሠላም ደህና አደርክ::
- ሠላም ደህና ነኝ::
- የትናንቱ የሐኪም ቤት ውሎህ እንዴት ነበር?
- ምንም አይልም፤ገና በጅምር ላይ ስለሆነ አድሮ ውጤቱ ወደፊት ይታወቃል::
- መልካም፣ግና ጊዜህንና ገንዘብህን ነው የምታባክነው፤ስለነዚህ ጉዳዮች ማሰብና መጨነቅ ጊዜን ማቃጠል ነው:: ለኔማ የበለጠ የሚከፍለኝን ሰው ብትነግረኝ ከፈለክ አምላኬ አድርገዋለሁ . . ክተክት ብሎ ሳቀና :- ትናንት የመጣ አስቸኳይ ሥራ ስላለን ወደቢሮዬ ብትመጣ ትሩ ነው፣ አለው::

www.path-2-happiness.com

- ጥሩ፣እመጣለሁ ከተቻለ ግን ካንድ ሰዓት በኋላ ነው::
- መልካም፣ ካንድ ሰዓት በኋላ::
- ጆርጅ ሌሊት ተደውሎበት ወደነበረው ስልክ ቁጥር ከራሱ ሳይሆን ከሌላ ስልክ ደወለ:: ከሌላኛው ጫፍ የሰማው ድምጽ የቶም ነበር:: ተለይቶ የሚታወቀውን ድምጽ ጆርጅ መለየት አላቃተውም:: ሃሎ . . ሃሎ . . ማነም ልበል? ይሰማሃል? ሲል አዳመጠና ወዲያውኑ ስልኩን ዘጋው:: ንድድ አለው፤ካትሪና የደወለው ቶም መሆኑን ለምን አልነገረችውም? ለምንስ ተረበሸች? . . ለምን? . . ሕይወት በጥቅሷ ውስብስብ ጥያቄዎች ብቻ ነች ማለት ነው ! !

ጆርጅ ወደ ሥራው ተመልሶ አቀረቀረና ስብስብ ሥራዎችን በፍጥነት ለማገባደድ ሞከረ:: ልክ ካንድ ሰዓት በኋላ ወደ ካኽ ቢሮ ሲደርስ ተነስቶ ተቀበለው :-

- ወዳጄ፣ሐኪሙ የሚወሰውስህን አከመህ ወይ? ተፈወስክ ?
- እኔ የተወሰወስኩ አይደለሁም፤አልታመምኩምም:: ወደ ዶክተሩ የሄድኩት ለጥያቄዎቼ መልስ እንዳገኝ ይረዳኝ ዘንድ ነው::
- ነገሩ ሳንተ የምር ይመስላል፤ሳጫውትህ መቀለዴ ነው፤የኔን አቋም በሚገባ ነው የምታውቀው፤ጉዳዩን እርሳውና ሀብትህን ለመጨመር በኑሮህ ለመደሰትና ሕይወትን ለመቅጨት ትጋ . . ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስና ካንተ ጋር ለመገናኘት የፈለኩት ሕንድ የሚገኘው የሠራተኛ አስቀጣሪ ኩባንያ የኛን መመዘኛዎች መቀበሉን ሳለ አሳወቀን ነው:: እኛም ከነሱ ዘንድ ብዛት ያላቸውን ሠራተኞች በአስቸኳይ መቅጠር ያስፈልገናል:: እዚያው ሕንድ አገር ከሚገኘው የሶፍትዌር አከፋፋይ ኩባንያ ጋርም ትብብራችንን ማጠናከር እንፈልጋለ:: ስለሆነም በሁለት ሳምንታት ውስጥ አንዳችን ወደ ሕንድ መጓዝ የግድ ሆኗልና አንተ ዝግጁ ነህ ወይ?
- በዚህ ጥድፊያ?!
- ከይቅርታ ጋር አዎ፤እንደምታውቀው የባለ ንብረቶች ቦርድ ስበሰባ ከሁለት ሳምንት በኋላ በመሆኑ እኔ መሄድ አልችልም::
- የራሴን ሁኔታዎች አይና ከሰሞኑ ስለጉዞዬ አሳውቀሃለሁ:: የውሎቹንና የስምምነቶቹን የተሟላ ቅጂ በውስጥ መረብ ላይ አድርግልኝና አንብቤ ልመርምራቸው:: ነገሮች ግልጽ ከሆኑልኝ በኋላ በመጪው ሳምንት እንገናኝ::
- እናም ቀጠሯችን መጪው ሳምንት ነው:: ራስህን ለጉዞው ዝግጁ

እንድታደርግ ምኞቴ ነው . . መሰሪ ፈገግታ አሳየና ሐኪሙን ወዲያ በለውና መጪው ሳምንት የሚነገርህ ድንገተኛ የምስራች እኔ ዘንድ ታገኛለህ::

- ጆርጅ ግራ እየተጋባ ወደ ቢሮው ሄደ:: ካኽ በኩባንያው የውስጥ መረብ ላይ ያስቀመጣቸውን ውሎችና ስምምነቶች ተመለከታቸው:: ወደ ሕንድ ለመጓዝ ፍላጎት ያለው ቢሆንም አእምሮው በሦስት ጉዳዮች ተይዟል :- በአስተናጋጁ፣በሐኪሙና በካትሪና !

ገና ገማለዳው ጀምሮ ዛሬ አስተናጋጁን ለመጎብኘት ወስኖ ነበር ያለው:: ከሐኪሙ ጋር ያለው ቀጠሮ ግን ከጉዞው በፊት በመሆኑ የሚቀጥለው ቀጠሮ እንደሚዘገይ ሊነግረው ይችላል:: የካትሪና ጉዳይ ግን . . ሃይማኖተኛዋ ባለቤቱ ከኤቲስቱ ቶም ጋር ክህደት ትፈጽምበታለች ተብሎ እውን ሊታሰብ ይችላል?! እንዴት ተደርጎ . . ሊሆን የማይችል ነው !!

ከሥራ ሰዓት በኋላ ጆርጅ የትናንቱን አስተናጋጅ አግኝ እንደሆ ብሎ ወደ ካፌው አመራ:: ሲያየው ራሱን መልሶ ባስገረመው ሁኔታ ደስታ ተሰማው:: ቦታ ይዞ ሲቀመጥ አስተናጋጁ ወደሱ መጣ :-

- ጌታዬ ምን ልታዘዝ?
- መልካም ፈቃድህ ከሆነ ቡና . . ይቅርታ አንዴ . . ስምህ ካት ነው ወይስ አደም?
- ጌታዬ አደም ነኝ::

አስተናጋጁ ቡናውን ለማቅረብ ሄደ:: ይዞለት ሲመጣ ጆርጅ ተፐሎ ብሎ :-

- አብረን እንድንጫወት መቀመጥ ትችላለህ?
- ጌታው ይቅርታ፣እርስዎን ማገልገል ደስ ባለኝ ነበር፤ግና መፈጸም የሚገባኝ የሥራ ኃላፊነት አለብኝ::
- የሥራ ሰዓትህ ሲያበቃ በመኪና እንዳደርስህ ትፈቅድልኛለህ?
- ይህ የርስዎ ደግነት ነው፤እኔ ፈቃደኛ ነኝ . . ቢያንስ አውቶብስ አልሳፈረም ማለት ነው . . ተራዬ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ያበቃል::
- እስከዚያ ቡናዬን እጠጣለሁ፤አንተን ለማድረስ ደስተኛ ስለመሆኔ እርግጠኛ ሁን::
- አመሰግናለሁ፤ይፍቀዱልኝ::

ጆርጅ ቁጭ ብሎ ቡናውን በዝግታ ፉት ማለት ጀመረ:: ውስጣዊ ስሜቱን የኮረኮሩ የአደም ቃላትን በማስታወስ ይህ አስተናጋጅ የሚያስደንቅ

www.path-2-happiness.com

ነው፤የማያውቀኝ እየሆነ እንዴት በአፍታ ውስጥ ሊረዳኝ ቻለ? ስለ ዋነኞቹ የሕይወት ጥያቄዎች በማሰላሰል እንደምጨነቅና መልሳቸውን ለማወቅ እንደምስገበገብ እንዴት ሊደርስበት ቻለ? . . ጥልቀት በቅለት ውስጥ፣ ምንኛ ድንቅ ፍልስፍና ! እያለ ከራሱ ጋር ማውራቱን ቀጠለ::

አደም የሥራ ልብሱን ቀይሮ መጥቶ ጆርጅን ከነጎደበት የሃሳብ ዓለም አባነነውና :-

- ተዘጋጅቻለሁ፣እንሂድ? አለው::
- እኔም ዝግጁ ነኝ፣ወደ ቤትህ መሄድ ትፈልጋለህ? ወይስ እዚህ ካፌ ፍንጃን ቡና? ወይስ በቅርበት በሚገኝ ሬስቶራንት እራት ልጋብዝህ?
- ምርጫው የኔ ከሆነ፣ሦስተኛውን ነው የምመርጠው::
- እዚህ ቅርብ ያለው የደስተኝነት ሬስቶራንት አመቺ ሊሆን ይችላል::
- በጣም አመቺ ነው፣ስሙ ይማርከኛል::ደስተኝነት በግራ መጋባት፣በጥርጣሬና በዕድለ ቢስነት ዘመን፣በአሳዛኝ መልኩ ብዙዎች የተነፈጉት ውብ መንፈስ ነው!
- የአዳም ቃላት ጥልቅ ስሜቱን የነኩት፣ውስጡን የኮረኮሩትና የከበቡት መሆናቸው ቢሰማውም ጆርጅ ግን ዝምታን ነው የመረጠው::

(6)

ጆርጅና አደም ወደ ደስተኝነት ሬስቶራንት ገቡ:: እንደስሙ ደስተኝነት የሚያሳብቅ ሆኖ ነበር ያገኙት:: ማራኪና ውብ ዲኮሩ፣የመብራቶቹ ብርሃን ሕብረ ቀለማት፣ይህ ሁሉ የአእምሮ እፎይታ እርካታና ደስተኝነትን ይናኛሉ::

ያንዱን ትግ ጠረጴዛ ይዘው ተቀመጡ:: የምግብ ቤቱ አስተናጋጅ ሜኑ ሲያመጣ ጆርጅ ለአደም :-

- በል የምትፈልገውን እዘዝ፣ አለው::
- የዓሳ ጥብስ ከአረንጓዴ ሰላጣ ጋር ይሁንልኝ::
- ለኔ የበሬ እስቲክ ከድንች ጋር አምጣልኝ::

አስተናጋጁ እንደሄደ ጆርጅ ለአደም :-

- እነሆማ አንተ እንደምትለው፣በግራ መጋባት፣ በጥርጣሬና በዕድለ ቢስነት ዘመን . . ብዙዎች በተነፈጉት የደስተኝነት ምግብ ቤት ውስጥ ነን፣ አለው::
- እህ፣አዎ፤ጥርጣሬና ግራ መጋባት ሕይወትን ትርጉም ስለሚያሳጡ፣ ሰዎች ወደ ግዑዝ እቃነት፣ እንቅስቃሴው ትርጉምም ሆነ ጣዕም ወደ ሌለው፣ ደስተኝነትና ተድላን መኖር ቀርቶ ማወቅ እንኳ ወደማይችል መገልገያ ቁሳቁስነት ይለወጣሉ::
- እናም አንተ ከግራ መጋባትና ከጥርጣሬ ወደ ጭፍን አምኖ መቀበል መሸሽን ከሚደግፉ ወገኖች ነህ ማለት ነው::
- ፈጽሞ . . ፈጽሞ፣ ያልሆነውን መስሎ ለመታየት ቢሞክር እንኳ ሽሽት የባለቤቱን ሁኔታ ይበልጥ የከፋ ያደርጋል:: የመጀመሪያው ራበኝ ብሎ የሚጮህ ረሃብተኛ ሲሆን፣ ሁለተኛው ለመተኛት የሚጮህ ረሃብተኛ ነው !
- አሃ፣እናም ሁለቱም የተራቡ ናቸው !
- ሆኖም የመጀመሪያው የገዛ ራሱን ነፍስ አያያዝ በተመለከተ ከሁለተኛው የበለጠ አእምሮና ብልህነት አለው::
- በእውነተኝነት መልስ ስጠኝማ:: አንተ ደስተኛ ነህ ወይ?
- ቀላል መልስ ትፈልጋለህ :- አዎ፣ደስተኝነት ማለት እኛ ራሳችን ስለራሳችን፣ስለ ሕይወትና ስለ ፍጥረተ ዓለም የሚኖረን አመለካከት ውስጣዊ ስሜትና ግንዛቤ ነው::
- ያንተ ደስተኝነት እንደ አንተው ሃይማኖተኛ የሆነችው ባለቤቴ ደስተኝነት - ባንተ አባባል መልሶቹን ላለመፈለግ በመጠጥና በምሽት ጭፈራ ውስጥ ራስን መደብቅ ! - እንዳይሆን እሰጋለሁ:: ከአጭር ዝምታ በኋላ :- ባንተ አመለካከት የሕይወት ትርጉም ምንድነው? ሲል አስከተለ::
- ለታላቆቹ ጥያቄዎች ምላሽ መፈለግን የሚሸሽ ሰው፣ አስመስሎ ቢተውን እንኳ የደስተኝነት ስሜት ሊኖረውና ደስተኛ መሆን አይችልም:: የሕይወት ትርጉምን የሚመለከተው ጥያቄህ፣ለምን ዐላማ ተፈጠርን? ለምንስ እንኖራለን? መጨረሻችንስ ወዴት ነው? የሚሉ የሦስቱ ጥያቄዎች ሌላ ቅንብር ነው::
- የሦስቱ ጥያቄዎች መልስ ምንድነው?
- የደስተኝነት ስሜት የሚሰማው፣ጣዕሙን የሚየውቅና መዓዛውን የሚያሸት ሆኖ የነዚህን ጥያቄዎች ምላሽ የማያውቅ ሰው ይኖራል ብለህ ታምናለህ ?!
- በግልጽ መልስልኝ፣የነዚህን ጥያቄዎች መልስ ታውቀለህ ወይ?
- ለኔ በጣም ግልጽና አሳማኝ የሆኑ መልሶች አሉኝ ብዬ ነው የማምነው:: ነገር ግን መልስ ማለት አራሴን አመለካከት ባንተ ላይ ማንቆርቆር ማለት

www.path-2-happiness.com

አይደለም። እንደሚመስለኝ አንተ ከኔ ይበልጥ ታውቃለህ። እኔ በሃይኖቶች ጥናት መስክ ገና የዩኒቨርሲቴ ተማሪ ስሆን አንተ ግን ትልቅ ኢንጂነር ነህ . . ደግሞም መልስ ማለት የገዛ መንፈሳችንና የገዛ ሕይወታችን የሚሰጠን መልስ ነው። የትኛውንም ምላሽ ቢሰጥህ እንኳ የገዛ ራስህ መንፈስና የአስተሳሰብህ አካል እስካልሆነ ድረስ ምን ትርጉም ሊሰጥህ ይችላል?

- መንገድ ላይ ያገኘሁትንና ደስተኛ መሆኑን የነገረኝን ሽማግሌ አስታወስከኝ። ልክ አንተ አሁን የምትለኝ ነበር ያለኝ።
- የሕይወት ተሞክሮና ዕውቀት ያለው ሰው የሚናገረውን ዓይነት መናገር የምችል ጥበበኛ ነህ ብለህ ገመትከኝ ወይስ ትርጉም የሌለው ነገር በመናገር የምፈላሰፍ አደረከኝ! ለማንኛውም መልሱ ወደ መልሱ ለመድረስ በቁርጠኝነትና በጽናት ጥረት ማድረግ ነው።
- ልክ የሽማግሌው ዓይነት አነጋገር ! ምን ለማድረግ ነው ቁርጠኛ የምሆነው?
- እነዚህን ጥያቄዎች መልሰህ በሕይወትህ ደስተኛ ለመሆን ቆርጠህ ትነሳለህ . . የጆርጅን ዓይኖች ትኩር ብሎ አየና ፦ እስኪ ጥያቄ ላቀርብልህና ከየት ነው ምላሹን የምናገኘው?
- ወደ ሐኪሙ ንግግር ተሸጋገርክ! ልክ እንደ ዶክተሩ ሆንክ !
አደም ሳያስብ ሳቀና ቀጠለ ፦
- አሃ፣አንተ እኮ የእንቆቅልሾች ስብስብ ነህ፣ስለ የትኛው ሐኪም ነው የምትናገረው? ሽማግሌው ሐኪም ነው?
- ይቅርታ፣በጣም የታከተኝ መሰለኝ፣አይደለም ሽማግሌው አይደለም። ደስተኝነትን ለማግኘት አንድ ሐኪም ዘንድ ሕክምና እየተከታተልኩ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች ብዙ አደከሙኝ፣አንከራተውኛል፤ጭንቀትና ውጥረት ውስጥ ከተውኛል።
- በጥያቄዎቹ ምክንያት የደረሰብህ ጭንቀትና ሃሳብ ሐኪም እስከ ማስፈለግ ደረጃ አደርሶሃል ማለት ነው?! አሁንም ደግሜ አረጋግጥልሃለሁ፣ከራስህ መንፈስና ከሕይወትህ ውጭ የሚመጣ መልስ የለም። ለመሆኑ የሐኪሙን ንግግር የሚመስለው ምኑ ነው?
- መልስ ለመፈለግ ከመነሳታችን በፊት መልሱን ከየት ማግኘት እንደምንችል መወሰን አለብን ነበር ያለው።
- በኔ አመለካከት ይህ በጣም ጥሩና ቀለል ያለ አቀራረብ ነው። ቀለል ያለ አቀራረብ የስኬትና ወደ እውነታ የሚያደርስ መክፈቻ ቁልፍ ነው። ውስብስብነት የውድቀት፣ የደካማነትና የግራ መጋባት ምልክት ነው።

ያንተ ሐኪም ምክንያታዊና በጣም ጥሩ ሰው ይመስላል፣እንደዚያ ነው ወይ?

- እርግጥ ምክንያታዊ ነው፣በጣም ጥሩ ሰው ግን አይመስለኝም፣ የማይመች ዓይነት ሰው ከመምሰሉም በላይ ጨዋነትም የሚያንሰውም መስለኛል።
- ታዲ ምን ልታድርግ አሰብክ?
- አላወኩም፣ውጤቱን እስከማይ ድረስ ከርሱ ጋር ለመቀጠል አስቤያለሁ። ይሁንና መልሱን ከዬት ነው የምናገኘው? መልስልኝ
- ይቅርታ፣ሐኪሙን መቃረን አልፈልግም፤ሐኪሙ ምን አለህ?
- ጆርጅ በአደም መልስ ሳቀ። ከሁሉም አቅጣጫ እየመጣበት ወደ ምላሽ ፍለጋው የሚገፋፋው መሆኑ የተሰማው ቢሆንም፣አደም መልስ ለመስጠት ባለመፈለግ በዙሪያው እየተሽከረከረ አልጨበጥ ማለቱ አስደሰቶታል። ወይም እንደደዚያ መስሎ ታይቶታል። ግና ለምን ይሆን ?!
- አንተ ራስህ ፈልግአለኝ አለኝ። መልሱን ከየት እናገኛለን? መልሱ ትክክለኛ ስለመሆኑ ዋስትናው ምንድነው? የሚል ትያቄ አቀረበልኝ።
- ውብ፣ድንቅ፣ቀለል ያለና ጥልቀት ያለው ጅምር ነው። የሐኪሙን አመለካከት ለመገምገም እኔ ሐኪም አይደለሁም!
- መልሶቹን ከየትነው ማግኘት የሚቻለን?
- ሃይማኖቶችን በመመርመር በገዛ መንፈስህ ውስጥ ፈልግ።
- በሃይማኖቶች ውስጥ !!
- አዎ . . በሃይማኖቶች ውስጥ። በሃይማኖቶች ውስጥ ካልሆነ በኤቲዝም ውስጥ እንድንፈልግ ትፈልግ ኖሯል?!
- ሃይማኖት አልቦነትን . . ኤቲዝምን አምርሬ ነው የምጠላው! የአእምሮና የዕውቀት እንከን ነው።
- ስለዚህም በሃይማኖቶች ውስጥ መፈለጉ ግዴታ ነው ማለት ነው።
- በተለያዩ አመለካከቶችና ሃይማኖቶች ወደ ተሞላችው ሕንድ የሚጓዝበት አጋጣሚ ሳይኖረኝ አይቀርም። ወደዚያ የማደርገው ጉዞ ከተለያዩ የእምነት ስልቶች ጋር ለመተዋወቅ ይረዳኝ ይሆን?
- ለመተቸት ወይም ትክክል ነው ለማለት እኔ ዶክተር አይደለሁም፣ዶክተሩን መጠየቅ ትችላለህ። የራሴን ግልጽ አስተያየት ግን ሊነግርህ እችላለሁ : - የተለያዩ ርእዮቶች፣ ሃይማኖቶችና ጎራዎች ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡበትን መንገድ መተዋወቅ በጣም ጥሩ ነገር ነው። መንገዱ ቀላል፣ገር፣ምክንያታዊ፣ተጨባጭና መንፈስና ሕይወትን የሚያረካ በሆነ መጠን መልሱ ለትክክለኛነት ይበልጥ የቀረበ ይሆናል።

www.path-2-happiness.com

- አመለካከቶችንና ሃይማኖቶችን መመርመር የምችለው እንዴት ነው?!
- የኔ አስተያየት በመጀመሪያ አጠቃላይ የሆነ ምልከታ እንድታደርግ ነው::
- እንዴት ማለት?!
- ሁለት ስልቶችን ማየት እንችላለን:: ከአፍታ በፊት እንደ ተነጋገርነው በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ስልትና በኤቲዝም ላይ የተመሰረተ ስልት ናቸው:: እኔ ያለ አንዳች ማመንታት በሃይማኖት ላይ ከሚመሰረተው ስልት ጋር ነኝ፣የሃይኖቶች ጥናት ተማሪ ነኝ ብየህ የለም?
- አስተናጋጁ ምግቡን ይዞ መጣ:: ጆርጅ እንግዳውን ላለማስከፋት ሲል ውይይቱን ለማብቃት መረጠ:: ይህን ለመጀመሪያ ጊዜ አብሮት የተቀመጠ ቢሆንም ከረዥም ዘመን ጀምሮ የሚያውቀው ይመስል በጣም የቀረበውን እንግዳውን ስሜት ለመተበቅ ፈለገ::
- የቀረበውን ምግብ እንዳትበላ ላውክህ አይገባም:: የበዛሁብህ መሰለኝ፤እውነቱን ለመናገር እገዛህ ለኔ በጣም አስፈጊ ነው:: ምናልባት ግንኙነታችን ገና አዲስ ስላንተ ያለኝ እውቀትም ጠለቅ ያላለ ነው:: ይሁን እንጂ በንግግርህ በጣም የተደሰትኩ በመሆኔ ምቾት እንዳልነሳህ ተስፋ አድርጋለሁ::
- አይ፣በፍጹም ምቾት አትነሳኝም:: የተደረገልኝ የራት ግብዣ ብቻ በቂዬ ነው፣በተለይ ደግሞ ግብዣው በደስተኝነት ሬስቶራንት ! ዋናው ነገር መብላትህ ነውና፣ብላ::

በመመገብ ላይ እያሉ ጆርጅ የጨዋታውን አካሄድ ለመለወጥ ፈለገና የከበባቸው የፍልስፍና አየር ቀስ በቀስ እየቀለለ ይመጣ ዘንድ ስለ ምግብና የሚበሉ ነገሮች ማውራት ትሩ አጋጣሚ ሆኖ ታየው . . ዳሩ ግና የውይይቱን ርእስ እንደገና ወደ መጀመሪያው ለመመለስ ጊዜ አልወሰደበትም . . ስለ አደምና በመልስ አሰጣጥ ላይ ስለሚከተለው ጠንቃቃ ስልቱ ብዙ ነገር አእምሮው ውስጥ እየተመላለሰ ነበር::

- የሃይማኖቶቹ ስልት ከኤቲዝም ስልት የተሸለ የሚሆነው ለምንድነው? በነገራችን ላይ ሐኪሜ ሁሉንም ሃይማኖቶች የሚያስተባብልና የሚሳለቅባቸው ኤቲስት ነው::
- ከአነጋገርህ እንደገባኝ ምርጥ ሐኪም ከመሆኑ ጋር፣ ኤቲስቶች ከሰው ሁሉ ይበልጥ ዕድለቢሶችና ከገዛ ራሳቸው ራሳቸው የሚሸሹ ሰዎች ስለመሆናቸው ግን በታም እርግጠኛ ነኝ:: ለምን የሃይማኖት ስልት ሆነ የኤቲዝም ስልት ለምን አልሆን የሚለውን በተመለከተ ዝርዝሩ ብዙ ሲሆን በሚከተሉት ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል :- አንደኛ ለምን እንደ ተፈጠርን የሚያውቅ

ከፈጣሪያችን ውጭ ማን ሊያውቅ ይችላል? በሌላ አገላለጽ እኔም ሆንኩ አንተ፣ከራሱ ከፈጣሪው ካልሆነ በስተቀር ለምን እንደ ተፈጠርን ማወቅ አንችልም ማለት ነው:: የኤቲዝም ስልት የፈጣረን ጌታ አምላክ መኖሩን ያስተባብላል:: ሁለተኛ :- ኤቲዝም በሚያቀርባቸው ነገሮች ሁሉ ራሱን በራሱ ይቃራናል:: ፍጥረተ ዓለሙ እጅግ በተራቀቁ፣የጸኑና የማይለወጡ በሆኑ ሕግጋት ይመራል፣ይህ የተራቀቀ ሥርዓት ያስገኘው ፈታሪ ሳይኖር በአጋጣሚ የተፈተረ ነው ብሎ ያምናል:: ሦስተኛ:- ኤቲስቶች ብዙውን ጊዜ በፈጣሪ ማመናቸውን እውስጣቸው ይደብቃሉ፤አደጋ ሲደርስባቸውና ችግር ሲያጋጥማቸው ግን መጀመሪያ የሚያድርጉት ያድናቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር

- መወትወት ነው:: አራተኛ:- ግልጽ ባለ ሁኔታ ልጠይቅህና ኤቲዝም እውነታ ነው ወይስ ወደ ከንቱነትና ወደ መንፈስ ባዶነት የመሸሽና የመፈርጠጥ ሙከራ ነው?
- ከነዚህ አንዱ እንኳ በቂ ሲሆን ሦስቱም ተጠቃለው አንድ ላይ ሲገኙ ምን ሊኮን ይችላል ! ሙሉ በሙሉ ካንተ ጋር የምስማማ ይመስለኛልና መቀጠል አያስፈልግህም:: ኤቲዝም ባለቤቱ ራሱን ከግንዛቤ ውጭ በሆነው የማያምን ሳይንሳዊ አድርጎ የሚወስድ ቅዠት ሲሆን እውነታው ግን አእምሮና ዕውቀትን የሚጻረር ሌሎችን ከመዋሸት በፊት ራስን መዋሸት የሚያሰፍን መሆኑ ነው:: ዋነኛው ጉዳይ ግን ከሃይማኖቶች መካከል የትኛውን እንከተል? የሚለው ነው:: የሃይማኖቶች ቁጥር በሕይወት የሚገኙ ሰዎች ቁጥር ያህል ነው . . ሳቀና :- ምናልባት ከዚያም ሳይበዛ አይቀርም !
- ሙሉ በሙሉ ካንተ ጋር እስማማለሁ:: አሁን ያሉት ሃይማኖቶች ቁጥር ከአስር ሺህ በላይ ነው ይላሉ:: እንደ ክርስትና ባለ አንዱ ሃይማኖት ውስጥ ብቻ 33830 የተለያዩ ሴክቶች (ፈለጎች) ይገኛሉ:: ይሁንና በአጠቃላይ ምልክታውን ብንቀጠልበትስ ?!
- ምን ማለት ነው የፈለከው?
- በአጠቃላይ ምልከታው ስልቶቹን አማኞችና ኢአማኝ ኤቲስቶች ብለን በሁለት ከፍናል፣አይደለም?
- ልክ ነው::
- በአጠቃላይ ምልከታው መሰረት ሃይማኖቶችና እምነት በሁለት ይከፈላሉ :- ወይ ስልታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ናቸው፣ወይ ደግሞ ስልታቸው ሰው ሰራሽ የሆነ ምድራዊ

www.path-2-happiness.com

ሃማኖቶች ናቸው::

- ማለት የፈለከው ገብቶኛል:: ባንተ አስተያየት ከሁለቱ የትኛው ነው የሚሻለው?
- የኔን አስተያየት ወደ ጎን በለውና ወደ ሕንድ እጓዛለሁ ብለህ የለ?
- አዎ፣ታዲያ ከርእሳችን ጋር ምን ያገናኘዋል?
- አገረ ሕንድ በምድራዊና መለኮታዊ አመለካከቶች፣ ሃይማኖቶች፣ፈለጎች፣ጭፍሮችና ቡድኖች የበለጸገች ናት:: በመሆን እዚያ በመለኮታዊ ሃይማኖቶች ተከታዮችና በምድራዊ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል ንጽጽር ማድረግና በገለጻ ሳይሆን በተጨባጭ እውነታውን ማየት ትችላለህ::
- በዚህ ነጥብ ላይ የጠራ አመለካከት ቢኖረኝም፣ጉዳዩን ከሕንድ እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ ማዘግየቱ ችግር አይኖረውም:: ነገር ግን ይህ አቀራረብና ስልት ወደ ምላሹ ሊያደርሰኝ ይችላል ብለህ ታምናለህ?
- ወደ እውነት መመራት፣ለዚያ መታደልና እርግጠኝነትን መጎናጸፍ የእግዚአብሔር ችሮታና ጸጋ ነው:: በፍለጋህ ፍጹምና እውነተኛ ከሆንክ ወደምትፈልገው ትደርሳለህ ብዬ አምናለሁ:: ዋናው ነገር እውነተኛ ፍላጎት እንዲኖርህና ቆርጠህ በጽናት መቀጠልህ ነው:: ነገሮችን በተወሳሰበ ሁኔታ ሳይሆን ቀለል ባለ ሁኔታ፣በትካዜ ሳይሆን በደስተኝነት ስሜት የምታስኬድ ስለመሆንም እርግጠኝነት ይኑርህ::
- ወደ አረጋዊው ሽማግሌ አነጋገር ተመለስክ !
- ይህን ሽማግሌ ዬት ይሆን የማገኘው? በታም አጓጋሀኝ::
- አላውቅም፣በውነት አላውቅም:: በታም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ስለነበርኩ አርሱ ነበር ስልክ ቁጥሬን የወሰደውና እደውላለሁ ያለኝ፤እኔ አድራሻውን አልተቀበልኩትም:: በነገራችን ላይ ቁጥርህንና ኢሜይልህን ትሰጠኛለህ?

አደም ይዞት ከነበረው ትንሽ የማስታወሻ ደብተር ትንሽ ወረቀት ገነተጠለና የስልክ ቁጥሩን፣ኢሜይሉንና የፌስቡክ ገጹን አድራሻ ጽፎባት ለጆርጅ ሰጠው::

- አዝናለሁ፣እንደምታውቀው እኔ ተራ አስተናጋጅ ነኝና የምሰጥህ ቢዝነስ ካርድ የለኝም !
- ግድየለም፣ከሕንድ እንደተመለስኩ ወዲያውኑ እንገናኛለን፣ ተስማማን?
- ተስማምተናል::

የክህደት ጥርጣሬ . .

www.path-2-happiness.com

3 የክህደት ጥርጣሬ . . .

የክህደት ጥርጣሬ . . .

(1)

ካትሪና እንደ ልማዷ ቤተክርስቲያን አላመሸችም ነበርና ወትሮ ከሚመለስበት ሰዓቱ የዘገየውን የጆርጅን ለመጠበቅ ቁጭ ብላለች:: እንደ ደረሰ በሩ ላይ ተቀበለችውና ለምን እንደ ዘገየ ጠየቀቸው . . ዓይኑና ዓይኗ ሲጋጩ ከቶም ጋር ያላትን ግነኙነትና መደወሉን ከርሱ መደበቋን አስታወሰ:: ሆኖም መጠየቅ ተወና ለሌላ ጊዜ ለማዘግየት ወሰነ::

-ባለፈው ጊዜ ወደነገርኩሽ አስተናጋጅ ሄጄ አብረን እራት በላን::

-ውይይታችሁ እንዴት ነበር? ስለርሱ ያለህ አስተያየት እንደነበረ ነው ያለው ?

-ግሩም ድንቅ ውይይት ነበር:: ትምህርተ መለኮትን የሚያጠና ተማሪ ነው:: ይሁን እንጂ ቀለል ባለ ገርና አሳማኝ . . በሆነ መንገድ ነው የሚናገረው::

-በቃ . . በቃ፣ይህ ሁሉ ሙገሳ ምንድነው ! ከፍተኛ አድናቆት ያሳደረብህ ይመስላል:: እህ፣ነገሩማ በጣም የተለመደ ነው፣ትምህርተ መለኮትን የሚያጠና ሰው የግድ እንደዚያ መሆን ይኖርበታል:: ግን ምን አለህ ?

-ንግግሩ ራሴን ለማጥፋት አስቤ በነበረበት ጊዜ አግኝቼው የነበረውን ሽማግሌ ንግግር ይመስላል፤አስታወስሽው ?

-አዎ ! ! !

-ከኤቲስቱ ሐኪም ከቶም አነጋገር ጋርም ይመሳሰላል ! ሃይማኖተኛ ሆኖ ንግግሩ ከኢአማኝ ኤቲስት ንግግር ጋር መመሳሰሉ አይገርምም ? !

-ሐኪሙን በኤቲስትነት ስትገልጸው አላግባብ እየተጫንከው ይመስለኛል፤በአብሬው ተቀምጫለሁ፣ይህን ፈጽሞ አላየሁበትም::

-አብረን በሄድን ጊዜ ክሊኒኩ ውስጥ የነበረወውን ግንኙነት ማለትሽ ነው፣ወይስ ሌላ ግንኙነት ነበር ? !

-አንተ ጆርጅ ! አዎና የክሊኒኩ ግንኙነት ነው:: በቤተክርስቲያን የሙሉ ጊዜ የትምህርተ መለኮት አስተማሪ መሆኔን ነግሬው ምንም ትችት አልሰነዘረም፣እንዲያውም አድናቆቱን ነበር የገለጸው::

www.path-2-happiness.com

- ኤቲስት በመሆኑም ይኩራራል፤ከፈለግሽ በፌስቡክ ገጹ ላይ ማየት ትችላለሽ . . ትኩረቱን አሰረፈባትና ፡- በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ካንቺ ጋር መለሳለሱ ከጀርባው ያቀደው ነገር ስላለ ይመስለኛል።
- ምን እያልክ ነው ? ! !
- ምንም . . ምንም አይደለም፣ እንዳው አእምሮዬ ውስጥ ሽው ያለ ግምት ነው። ዋናው ነገር ምናልባት ወደ ሕንድ ልጓዝ እችላለሁና ምን ትያለሽ ?
- ግሩም፣መቼ ነው ?
- ከአስር ቀናት በኋላ።
- ጆርጅ፣የዘር ግንዴ ከሕንድ በተለይም ከደልሂ መሆኑን መቼም ታውቃለህ . . ሕንድ የድንቃድንቅ አገር ነች። ብዙ ችግሮችን ታስረሳሃለች፣ዘና እንድትልም ታደርገሃለች። ይሁንና የሐኪም ቀጠሮውን እንዴት ታደርጋለህ ?
- መጪው ሰኞ ቀጠሮ ስላለኝ ቀጣዩን ቀጠሮ እንዲያዘገይልኝ እጠይቀዋለሁ።
- በጣም ጥሩ።

(2)

ጆርጅ፣ ካትሪና ከቶም ጋር ያላትን ግንኙት ካወቀ በኋላ ራሱን ለማረጋጋትና ግድ የሌለው አድርጎ ራሱን ለማሳመን ቢሞክርም፣ ውስጡ እየተረበሸ መጥቷል። ረቡዕ ጧት ግን ከካትሪናና ቶም የስልክ ምልልስ ሰምቶት የነበረውን የዛሬ ምሽት ሁለት ሰዓት ቀጠሯቸውን ጠብቆ በድንገት ለመያዝ አሰበና ቶሎ ብሎ ወደ ዶክተር ቶም ክሊኒክ ስልክ ደወለ። የእንደግዳ መቀበያ ሰራተኛውን በራድን የሚቻል ከሆነ ቀጠሮው ወደ ዛሬ ምሽት እንዲሸጋሸግለት ጠየቀ።

- ዛሬ ማድረግ አይቻልም።
- ለምን ?
- ኣ፣ዶክተር ዛሬ ሁለት ሰዓት ላይ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ ቀጠሮ ያለው በመሆኑ ።
- እስከዚህ ድረስ በጣም አስፈላጊ ነው?
- ምናልባት፣ዋናው ነገር ቀጠሮውን ወደዚህ ማሸጋሸግ የማይቻል ነው። ቀጠለና ጎላ ባለ ድምጽ ሳቀ።
- አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ወደ ክሊኒኩ እመጣና ባለ ቀጠሮው ታካሚ ምናልባት ከዘገየ በርሱ ፈንታ እኔ እገባለሁ።

- አይ፣አይቻልም አልኩ'ኮ፣ደግሞም የዶክተሩ ቀጠሮ እዚህ ክሊኒክ ውስጥ አይደለም . . ልክ በዚህ ሰዓት መምጣት በጣም ያሳሰበህ ትመስላለህ፣ የምትፈልገው ይገባኛል!! አለው በማፌዝ። ቀጠለና ፡- ለማንኛውም መምጣት ተችላለህ፣ና የምትፈልገውን ሁሉ በትክክል እነግረሃለሁ፤ችግርህን ሁሉ እፈታልሃለሁ . . ዳግም ከፍ ባለ ድምጽ ሳቀና ፡- እጠብቀሃለሁ እንዳትቀር፣አለው።
- ጆርጅ የሥራ ሰዓቱ ሲያበቃ አደምን ለማግኘት እየተቻኮለ ወጣ። የቶምና የካትሪና ጉዳይ በጣም ስለ አሳሰበው በጉዳዩ ላይ አደምን የማማከር ሀሳብ አድሮበታል። መኪናውን ካፌው ፊትለፊት አቁሞ አዳም ከሥራ የሚወጣበትን ሰዓት መጠባበቅ ጀመረ። ከተዋወቁ ገና ጥቂት ቀናት ብቻ የተቆጠሩ እየሆነ የግል ሕይወቱን ጉዳይ እስከማማከር ደረጃ ድረስ ይህ ሰው ልቡ ውስጥ መግባት እንዴት እንደቻለ ራሱን ደጋግሞ ጠየቀ።
- አደም የጆርጅ መኪና መቆሟን አየና ተራው ሲያበቃ የሥራ ልብሱን ቀይሮ ወዲያውኑ ወደ ጆርጅ አመራ። ጆርጅ ሲያየው ወደ ቤቱ ያድርሰው ዘንድ እንዲገባ ጠየቀውና አደም እሺ ብሎ ገባ።
- አደም . . በጣም በሚቀርብህ ሰው ላይ ጥርጣሬ አድሮብህ ታውቃለህ?
- ፈጽሞ አላጋጠመኝም፣በጣም ከባድ መሆኑ ግን ይሰማኛል።
- ባለ ትዳር ነህ?
- አይደለሁም።
- ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለህ የፍቅር ግንኙነትስ እንዴት ነው?
- ከተቃራኒ ጾታ ጋር ምንም ዓይነት የፍቅር ግንኙነት የለኝም ! ጆርጅ ምንድነው የፈለከው?
- የኔ ሐኪም ጨዋነት የጎደለው ሰው ነው አላልኩህም ነበር?
- ብለሀኛል !
- ባለቤቴ ሃይማኖተኛ ከመሆኗ ጋር ጠጪና ጥርጣሬን በሚጭር ሁኔታ በምሽት ድግሶች ላይ ታመሻለች ብየህ አልነበረም?
- ብለሀኛል !
- ወየውልኝ፣በርሱና በባለቤቴ መካከል ኢሞራላዊ የሆነ ግንኙነት ይኖራል ብዬ መጠራጠር ጀምሬያለሁ፣ዝም ብዬ እየተወሰወስኩ ይሆን?

አደም ትካዜ የሚነበብበትን የጆርጅ ፊት እያስተዋለ ጥቂት ጊዜ በዝምታ ካሳለፈ በኋላ ፡-

- ምን እንደምል አላውቅም፣ምን እንደሚሰማህ እረዳለሁ . . በመሰረቱ

www.path-2-happiness.com

ሰዎች ላይ ቅን አመለካከት ልኖረንና በበጎ ልቦና ልናያቸው ይገባል:: እርግጠኛ እስካለሆንክ ድረስ እንዲየው ዝም ብለህ ሰዎችን ለመጠራጠርና ለመወንጀል አትቻኮል::

- ዛሬ ከርሱ ጋር ለማምሸት ቀጠሮ ይዛለች !
- እርግጠኛ ነህ?! ደሞም ብዙ ጊዜ እንደሚትጠጣና እንደምሚታመሽ ነግረሀኛል፣ከቶም ጋር ማምሸትን ከሌላው ጋር ከማምሸት ምን ለየው?
- ቶም ከሴት ታካሚዎቹ ጋር ያለው ግንኙነት የሚያስጠረጥረው ሲሆን ሰውየው ጨዋ ስነምግባር የሌውም:: ካትሪናም እንዲሁ ማምሸቷ የሚያስጠረጥራት ነው:: በተጨማሪም ግንኙነቱን ሆን ብላ ከኔ ሸሽጋለች:: የ . . የበራድ አነጋገርም በጣም እንግዳ የሆነ አነጋገር ነበር!
- በራድ የምትለው ደሞ ማነው?
- የቶም ጸሐፊ ነው:: ፈጽሞ የማይመች ዓይነት ሰው ነው:: የሚረብሹና የተድበሰበሱ ነገሮችን ይጠቋቁመሃል!
- አሁን ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ነው፣ለካትሪና ደውለህ በአንድ ታዋቂ ሬስቶራንት ለራት ግብዣ ብትጠራት ምን ይስለሃል?
- እሞክራለሁ !

ጆርጅ ለካትሪና ደወለ:: ከድምጹ ቅላጼ የሚገኝበትን ስሜታዊነት እንዳታውቅ የተቻለውን እየሞከረ አደም የነገረውን ሀሳብ አቀረበላት:: በዝነኛ ሬስቶራንትና አብረው ቢሚያሳልፉት ውብ ምሽት ልቧን ለማማለል ሞከረ:: ይሁን እንጂ ደግማ ደጋግማ ይቅርታ በመለመን ግበዣውን ለሌላ ቀን እንዲያስተላልፈው ጠየቀች:: የቤተክርስቲያን የድግስ ሥርዓት በመሆኑ መቅረት የማትችል መሆኗን ነገረቸው::

- ይኸውልህ በቤተክርስቲያን የምሽት ድግስ በማሳበብ እምቢ ብላለች::
- እናማ የቤተክርስቲያን የድግስ ሥርዓት ከሆነ ዘንዳ ለምን ትወነጅላታለህ?
- የቤተክርስቲያን የምሽት ድግስ ቀይ ቅሌቶች እጅግ አሳፋሪና ጠረናቸው ከርቀት የሚረብሽ ነው !
- ምናልበት እኔ ላላውቃቸው እችላለሁ !

ጆርጅ ወደ አደም መኖሪያ ቤት ደረሰ፤ለትህትናውና ላደረገለት እገዛ አመሰገነውና . .

- በግላዊ ጉዳይ ለምን እንደ ረበሽኩህ አላውቅም ! እባክህን ይቅርታዬን ተቀበለኝ::
- ይቅርታ መጠየቅ አያስፈልግህም፣የማደርግልህ አንዳች ነገር ቢኖር

እንዴት ደስ ባለኝ ነበር:: በል በቸር እንገናኝ . . አንድ ነገር ብቻ ልነግርህ እፈልጋለሁ :- ስለርሱ የነገርከኝን ያን በራድ ያልከውን ሰውዬ ተጠንቀቅ:: በጥርጣሬና በግራ መጋባት ስንጠመድ በከፍተኛው የድክመት ደረጃችን ላይ ስለምንሆን በስሜትህ እንዲጫወት አትፍቀድለት::

- ድክምክም ብሎኛል፣ ከሁለት ሰዓት በፊት የግድ መፍትሔ ማግኘት ይኖርብኛል ! ፈቃድህ ይሁንና እኔ ልሂድ::

(3)

የጆርጅ ስልክ አቃጨለ . . የደወለው በራድ ነበር:: ጆርጅ ግን የሚረብሹ አስተያየቶችን ከርሱ ለመቀበል በሚፈቅድለት ሁኔታ ላይ አልነበረም:: ይሁን እንጂ ደጋግሞ መደወሉ ስልኩን እንዲያነሳና ምን እንደሚል እንዲያውቅ ገፋፋው::

- ሃሎ . . የት ነህ? አንተን በመጠበቅ ላይ ነኝ:: ቶም ወደ አስፈላጊ ቀጠሮው ሄዷል !
- ወዴት?
- ወደ ቀጠሮው ነዋ ! ምኑን ማወቅ ነው የፈለከው?
- እባክህን እኔ ታክቶኛል !
- ኣ፣ ለማንኛውም ወደኔ ና፣ ለችግርህ ከኔ ዘንድ መፍትሔ ታገኛለህ::
- መፍትሔ አንተ ዘንድ ይገኛል? ! እንግዲያውስ አሁኑኑ እመጣለሁ::

ጆርጅ ወደ ክሊኒኩ ሲደርስ በራድ እየተጠባበቀው ነበርና ጠንከር ባለ አነጋገር ያናግረው ገባ . .

- ቶም የትነው ያለው?
- ከአፍታ በፊት ወጥቶ ሄዷል::
- ከማን ጋር?
- ከማን ጋር እንደሆነ ታውቃለህ:: ይልቅ ቶም ክሊኒክ ውስጥ እንቀመጥ፣አረፍ በል !
- እኔ የማውቀው ምንም ነገር የለም፣ከኔ ምንድነው የምትፈልገው?
- ቶም የወጣው ከካትሪና ጋር ነው::
- እየዋሸህ ላለመሆንህ ዋስትናዬ ምንድነው?
- እኔ አልዋሸሁም !

የሚያደርገው ጠፍቶት ጆርጅ ራሱን አቀረቀረ፤ከዚያ ቀና ሲል ዓይኖቹ በድንገት ጠረጴዛው ላይ ባለው ትንሽ የሴት ቦርሳ ላይ አረፉ:: ከካትሪና ቦርሳ

www.path-2-happiness.com

ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ በራድ ላይ ጮኸ ፡-

- ይኸ ምንድነው?
- እህ፣የማይታመን ነው ካትሪና ቦርሳዋን ረሳች? ! የተናገርኩት እውነት ስለመሆኑ ይኸውልሃ ማስረጃው፡፡
- ወዴት ነው የሄዱት?
- የምሽት ፕሮግራም አላቸው . . እዚያው ቤተክርስቲያን መሰለኝ፡፡
- ቶም 'ኮ ኢአማኝ ነው፣ኤቲስት ነው . .
- ለምን አብረሃቸው አልሄድክም? ወይስ አንተ ባለህበት የማይፈጸም የተለየ ጉዳይ ኖሯቸው ነው? በከፍተኛ ድምጽ ሳቀ . . ከዚያም ቀጠለና ፡- ወዳጄ ያለህበትን ሁኔታ አስቸጋሪነትና ስሜትህን እረዳለሁ፡፡ ከዚህ የስነልቦና ጫና የሚያሳርፍህ ነገር አለኝ፡፡
- ምን ይሆን?
- አንዲት የደስተኝነት እንክብል ናት፡፡ ምናልባት ስለ ሄሮይን አደገኛነት ሰምተህ ይሆናል፡፡ ግና ተጠቃሚው የሚሰማው የደስተኝነት ስሜት ምን ያህል እንደሆነ አንተ እንደማታውቅ እኔ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ፡፡ አንዷ እንክብል ብቻ በፍለጋ የምታሳድደውን ደስተኝነት ታጎናጽፈሃለች፣ ትፈልጋለህ?
- አንዷ እንክብል ብቻ !

ጆርጅ ውስጡ ድል የተመታና እጅ የሰጠ መስሎ ስለተሰማው፣ በራድ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ጠብቀኝ፣የደስተኝነት እንክብል ይዤልህ እመጣለሁ፣አልቆይም ብሎት ወጣ፡፡ ጆርጅ በዚህ ጊዜ በስነልቦና ጫናው ምክንያት መንፈሱ እንደተናደ ሲሆን በራድ እንደ ወጣ ባዶነት ተሰማው . . ሞባይሉን አውጥቶ በመጨረሻ ያደረጋቸውን ጥሪዎች ተመለከተ፡፡ የበራድ፣የካትሪናና የአደምን ቁጥሮች ነበሩ፡፡ ወዲያውኑ ለአደም ደወለ፡፡

- ሃሎ፣ጆርጅ፡፡
- የነገርኩህ ነገር እርግጠኛ መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡
- ነገሮችን ቀለል አድርገህ ውሰዳቸው፡፡ አብረው መውጣታቸውን ብታረጋግጥ እንኳ፣ያ ማለት ባንተ ላይ ክህደት ትፈጽማለች ማለት ነው?
- አደም እኔ በጣም ተንከራትቻለሁ፡፡ በራድ ውጥረቴን የሚቀንስና መንፈሴን የሚያረጋጋ ነገር ሊያመጣልኝ ለጥቂት ደቂቃዎች ትቶኝ ሄዷል፡፡
- የሚያዝናናህና ውጥረትህን የሚያረጋጋው ምንድነው?
- አንዲት የደስተኝነት እንክብል ብቻ ነች ነው ያለኝ !

- አደንዛዥ እጽ ! አብደሃል'ንዴ? በግራ መጋባትና በጥርጣሬ ጊዜ ሌሎች በቀላሉ ይጫወቱብናል አላልኩህም ነበር . . ጆርጅ ምን ነካህ? ይኸ ሽሽት ነው፡፡ በሽሽት ደስተኝነትን አገኛለሁ ብለህ ታምናለህ? እባክህን አሁኑኑ በቀጥታ ወደኔ መምጣት አለብህ . .
- ሞራሌ ምን ያህል ድባቅ እንደ ተመታ ልነግርህ አልችልም፤ ሰውየውም ገና አልመጣም፣ እሺ . . መልካም፣መጣሁ፡፡

ጆርጅ ወደ አዳም መኖሪያ ቤት ሲደርስ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነበር፡፡ አዳም ተቀበለውና ወደ ውስጥ እንዲገባ ጋበዘው፡፡ የአዳም ቤት ትንሽ ሆና በሥርዓት የተያዘችና ቀለል ያለች ቤት ናት፡፡ ጆርጅ አንዱ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ አደም ሻይ አዘጋጀለት፡፡ ሲጠጣም ትንሽ የመዝናናት ስሜት ተሰማው፡፡

- ነገሮቹ አሁን እንዴት እየሄዱ ናቸው? አብረን የአካል እንቅስቃሴ ብናደርግ ምን ይመስለሃል?
- እስፖርት ! አሁን ጊዜው ነው ብለህ ነው?
- በየለቱ ከ3-5 ኪሎ ሜትር በእግር የመጓዝ ወይም ሶምሶማ የመሮጥ ልማድ አለኝ፡፡ ዛሬ ገና አልተጓዝኩምና በል ጆርጅ ከጎኔ ሁን፣ቤቴ ለእግር ጉዞ አመቺ ቦታ ላይ ነው የሚገኘው፡፡
- እሺ . . ይሁን፣ምንም አይደለም !

አብረው በመጓዝ ላይ እያሉ አደም ወደ ጆርጅ ፊቱን አዙሮ ስለ አካል እንቅስቃሴ ጥቅሞች፣መንፈስን ለማነቃቃትና የስነልቦና ሁኔታን በማሻሻል ረገድ ስለሚጫወተው ሚና በማውራት ላይ እያለ ሳያስብ የጆርጅ ዓይኖች ሲያነቡ ተመለከተ፡፡

- ሚስቱ በሌላ ወንድ እቅፍ ውስጥ ባለችበት ጊዜ አካላዊ እንቅስቃሴ ለሚያደርግ እንዳኔ ላለና ሞራሉ ለተንኮታኮተ ሰው፣እስፖርት ደስታ ሊያስገኝለት ይችላል ብለህ ታምናለህ?
- እስፖርት ሞራል ያነቃቃል፣መንፈስን ያድሳል፡፡ ይሁን እንጂ ብቻውን ማንንም ደስተኛ አያደርግም፡፡ ደስተኝነት ከውስጣችን እንጂ ከየትም አይመነጭም፤ሊመጣ የሚችለው ከውስጣችን ብቻ ነው፣አደንዛዥ እጽና አስካሪ መጠጦች ቀርተው እስፖርትም ሊያመጣው አይችልም !
- በድክመት ሁኔታ ላይ ነበርኩ፣በራድ መጫወቻ ሲያደርገኝ ነበር፡፡
- በድክመታችን ጊዜ ወንጀለኞች በኛ እነዲጫወቱ እድል ልንሰጣቸው አይገባም !

www.path-2-happiness.com

-ካንተ ጋር በመጓዝ ላይ እያለሁ ውስጤ ሲናድና ድል ስመታ፣መንፈሴ በየሰከንዱ ሲሞት ይሰማኛል::
-ሀሳብ ጭንቀትና ውጥረት ሲያጋጥምህ ቀደም ሲል ምን ታደርግ ነበር? !
-ትዝ አለኝ፣የዱሮው ሐኪም የሰጠኝን የሚየረጋጋ አስታጋሽ እንክብል እወስድ ነበር . . ግን እንቅልፍ እንድተኛ ያደርገኛል::
-የማስታገሻ እንክብል ከወንጀለኛ ሳይሆን ከእስቴሽያሊስት ሐኪም ከሆነ ደግ ነው፣እንክብሎቹን አሁን ይዘሃቸዋል?
-አዎ መኪና ውስጥ አሉ::
-ወደ ቤት እንመለስና አንዱን ፍሬ ትወስዳለህ::
-ወደ ቤቴ እሄድና አወስደዋለሁ::
-እዚሁ ውሰደውና እኔ ዘንድ ተኛ::
-ካትሪና የት እንዳለች አላውቅም አንተ ዘንድ እተኛለሁ ! !
-ጥርጣሬህን የወንጀሏ ማስረጃ አድርገህ አትውሰድ፣ምናልባት ከቶም ጋር የሆነችው እሱን ወደ ክርስትና ለመጥራት ሊሆን ይችላል !
-ሊሆን ይችላል፤እርግጠኛ ብሆን እንዴት ደስ ባለኝ፤አሁን ካለሁበት ጥርጣሬ ይሻለኝ ነበር::

የወሰደው እንክብል መስራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ጆርጅ ረዘም ላለ ጊዜ አንቀላፋ . . ጧት አራት ሰዓት ላይ ሲነቃ አደም ቁርስ አዘጋጅቶለት አገኘው . .

-እንደምን አደርክ፣ቁርስ ተዘጋጅቷል::
-ስንት ሰዓት ሆነ?
-አራት ሰዓት ነው::
-አዝናለሁ፣አንተን ከሥራህ አስቀረሁ፣እኔም ከሥራዬ ተስተጓጎልኩ::
-ምንም አይደለም፣እኔ አስፈቅጃለሁ፤አንተ ምክትል ዳይሬክተር በመሆንህ አንድ ቀን መቅረት ችግር አያስከትልብህም::

ጆርጅ ከአደም ጋር ቁርሱን በልቶ ላደረገለት መስተንግዶና ላሳየው ትሕትና አመሰገነው:: ሁኔታው ትናንት ከነበረበት በጣም የተሻለ ሲሆን ጥሩ ውስጣዊ መረጋጋትም ተሰምቶታል::

-በጣም ጥሩ፣የበለጠ ልትረጋጋ ይገባሃል:: ከፍተኛ ጭንቀትና ያልተጠበቁ ለውጦች ብዙውን ጊዜ ውስጣዊ ደስተኝነትን ይነሳሉ::
-ምን ማለትህ ነው?
-ለዋነኞቹ ጥያቄዎችህ እልባት ካገኝህ ለሌሎች ችግሮችህ የተሻለ አያያዝ ማድረግ ትችላለህ:: የሚያጋጥሙህን ጫናዎችና ችግሮች ለመቋቋም የበለጠ የመንፈስ ጥንካሬና ብቃት ይኖረሃል::
-የካትሪና ጉዳይ ቀላል ነው እያልከኝ ነው?
-አይደለም፣ማለት የፈለኩት ውስጣዊ ደስተኝነት ጥርጣሬያችንን ያስወግዳል፣ትናንሾቹን ችግሮቻችንን ይፈታል፤ስለዚህም ትኩረትህ በደስተኝነት ፍለጋውና ለጥያቄዎችህ ምላሽ በማግኘት ወደዚያ የሚያደርሰውን መንገድ በመከተሱ ላይ ይሁን ነው:: ይህን ስታደርግ ሕይወት እንደገና እንዴት እንደሚቀመርና ለሕይወት ያለህ አመለካከት ሙሉ በሙሉ እንዴት እንደሚለወጥ ታያለህ::
-ከተናገርከው ውስጥ ያልተረዳሁት ነገር ቢኖርም ያልከውን ለማድረግ ቃል እገባልሃለሁ::
-ንግግሬ ግልጽ ነው:: ቅለትና ጥልቀት ባለው ስልት በዋነኛው ጉዳይህ ላይ አትኩር:: ያን ስታደርግ ደስተኝነት ከውስጥህ ከራስህ መንፈስ ይመነጫል፣ይህ ሲሆን ለችግሮችህ ሁሉ መፍትሔ ታገኛለህ::
-ምናልባት . . አመሰግናለሁ:: ከኔ ጋር ለፍተሃል . . አሁን ወደ ሥራ እሄዳለሁ፣በተጨማሪም ዛሬ ከሐኪሙ ጋር ቀጠሮ አለኝ::
-በካትሪናና በቶም ላይ ከተለመደው የተለየ ነገር ላለማሳየት ሞክር:: በቅርብ ወደ ሕንድ መሳፈርህ ነውና ከጉዞው ስትመለስ የሚሆነው ይሆናል:: ነገሮችን የምትወስዳቸው ቀለል አድርገህ ሳታወሳስብ፣በደስተኝነት መንፈስ እንጂ በትካዜ ላለመሆኑ እርግጠኛ ሁን::
-እሞክራለሁ::

(4)

ጆርጅ በቀጠሮው መሰረት ማታ ወደ ቶም ክሊኒክ ሄደ:: ሲገባ በራድ በክፉ ፊት ተቀበለው . .

-ትናንት ወዴት ነው የፈረጠጥከው?
-አልፈረጠጥኩም፣ሥራ ነበረኝ::
-ለምን አልጠበቅከኝም?
-አደንዛዥ እጽን እጠላለሁ፣ከራሴ ችግሮች መሸሽንም እጠላለሁ::
-ነው’ንዴ! . . ጥሩ፣ችግሮችህን ተጋፍጠሃላ?
-ከቶም ጋር ቀጠሮ አለኝ፣አለ ወይስ ትቼ ልሂድ?
-እህ . . አለ፣የደስተኝነት እንክብል እንደሚያስፈልግህ ግን እርግጠኛ

ነኝ፣አንድ ቀን ለመፈለግ መመለስህ አይቀርም:: ሐኪሙ እየጠበቀህ ነው፣የካትሪናን ባል ለማግኘት በጣም ጓግቷል መሰለኝ፣ በል ግባ!

ጆርጅ ሲገባ ቶም ፊቱ ጨፍግጎና የታከተው ሆኖ ተቀበለውና ሻይ አቀረበለት:: እስከ ሌሊቱ መጨረሻ አካባቢ በማምሸቱ ትንሽ ድካም የተሰማው መሆኑን ገልጸለት ይቅርታ ጠየቀ . . ሐኪሞች በተለምዶ ማምሸትን የሚከለክሉ በመሆኑ ጆርጅ በቶም አነጋገር የመገረም ስሜት ቢያሳይም ቶም ግድ የሌለው በመምሰል ወዲያውኑ አርእስቱን ቀየረው:: በመቀጠልም መልሱን እንዳላገኘ በመገመት ለጆርጅ ጥያቄ አቀረበ :-

- ለበቀደሙ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተሃል?
- አግኝቻለሁም፣አላገኘሁምም::
- እንዴት? መልካም ፈቀድህ ከሆነ አብራራልኝ?
- በጣም አሳማኝ የሆነ ምላሽ አለኝ፣ነገር ግን የተሟላ አይደለም::
- ጥሩ፣መልሱን ከየት ነው የምናገኘው?
- መልሱ :- ጥያቄዎቹን በቅለት እንጂ በአስቸጋሪነታቸው አለመመልከት ነው፤ይህን ስናደርግ መልሱ በቀጥታና ቀለል ባለ ሁኔታ ግልጽ ይሆናል::
- ፍልስፍናዊው መንገድ በአብዛኛው - የሰላ አእምሮ ያለንና በጥልቀት የምንገነዘብ መሆናችንን ለማሳያት ሲባል - ነገሮችን በማወሳሰብ ላይ የተመሰረተ ነው::
- የበለጠ ጥልቀት ያለው ግን በማቅለል ውስጥ ነው:: ለጥያቄዎች በጥልቀት ምላሽ የሚሰጥ ከሆነ ይበልጥ ተመራጭ አይደለምን? !
- በጉዳዩ መፈላሰፍ የጀመርክ መሰለኝ . . እስኪ አድርገው በሚል ቅላጼ :- ነገሩን እንዳሻህ አቅልለውና ለጥያቄዎቹ መልሱን ከየት ታመጣለህ?
- ከፍጥረታት ለማግኘት ፈላልጌ ከግዑዝ አካላትም ሆነ ከእንስሳት ዘንድ ማምጣት እንደማንችል ተገንዝቤያለሁ . . እናም ምን ቀረ?
- ጆርጅ ዓይን ዓይኑን እያየ ቁርጥ ባለ አነጋገር :-
- አሃ፣ ሰዎች ቀሩ ልትለኝ ነዋ!
- ልክ ነህ፣ከሰዎች ወይም ከጌታቸውና ከፈጣሪያቸው ዘንድ ነው::
- የሰዎች ፈጣሪ ጌታ መኖሩን አላምንም !
- ታድያ ፍተጥረታት እንዴት ሊገኙ ቻሉ? !
- በአጋጣሚ እንበል፣ራሳቸውን በራሳቸው ፈጠሩ እንበል፣በሆነ ሌላ ነገር ነው እንበል ! በዚህ ጥያቄ ራሴን ምቾት መንሳት አልወድም::
- ፈላስፋው ! ይህማ የፈላስፎች ስልት ሳይሆን ከጥያቄዎቹ የመሸሽ ስልት

ነው:: የጠቀስካቸው መላምቶች ሁሉ ምክንያታዊ አይደሉም:: አንድ ነገር ራሱን በራሱ ይፈጥራል ብሎ የሚቀበል አእምሮ የለም:: አጋጣሚም እንዲህ የተራቀቀና የተቀናጀ ሊሆን አይችልም:: ሌላ የምልህ ነገርም የለኝም . . ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ቀጠለ :- ባንተ መንገድ ልጓዝና ወዴት እንደምንደርስ እናያለን፣መጀመሪያ ላይ አሳማኝ መስሎ ቢታየን እንኳ ወደ እውነታው እስኪያደርሱን ድረስ ጥያቄዎቹን መለጎም የለብንም::

- ጥያቄዬን አልመለስክልኝም . . ለጥያቄዎቹ መልስ የምናመጣው ከወዴት ነው?
- ከሰዎች ፈጣሪ ዘንድ፣ከማንም በላይ የሚያውቃቸው እርሱ ነውና::
- ቶም ለረዥም ጊዜ ራሱን አቀርቅሮ ቆየና ቀና ብሎ :-
- የተናገርከውን ባልስማማበትም አደንቀዋለሁ፣በመሆኑም በተናገርከው ላይ አልከራከርም፤ይሁን እንጂ ጥያቄዎችን ማቅረብ እቀጥላለሁ:: ስህተትህን የሚገልጹ ጥያቄዎች አቀርብልሃለሁ:: አንተ የምትለውን እውነት ነው ብለን እንቀበለውና . . ምላሽ የሚሰጠን የሰዎች ፈጣሪ ጌታ ቡድሃ ነው፣ጸሐይ ነች፣ወይስ መንፈስ ቅዱስ፣ወይስ ሌላ ነው . . ? የሰዎች አማልክት የተለያዩና የሚለዋወጡ ናቸውና ከመካከላቸው እውነተኛው አምላክ የቱ እንደሆነ እንዴት ማወቅ እንችላለን? የሃይማኖቶች ቁጥር በጣም ብዙ መሆኑን ታውቅ የለ ? !
- ልክ ነህ ከ10000 የሚበልጡ እምነቶች ይገኛሉ:: ከነዚህ አንዱ የሆነው የክርስትና ሃይማኖት ብቻ 338830 የተለያዩ ሰክቶችና ፈለጎች ይገኙበታል::
- ያጋጠመኝ የሞቀ ክርክርና ጥልቅ እውቀት ያለው ግለሰብ ነው:: መልሱን ትክክለኛ ነው ብለን በመውሰድ ጥያቄውን እናሚላውና :- መልሱ ትክክለኛ ስለመሆኑ ዋስትናው ምንድነው?
- በቀላሉ ለመመለስ አጠር ያለ ቀላልና ውስብስብ አለመሆኑ፣ደስተኝነትን የሚያጎናጽፈን፣ከአእምሮና ከሎጂክ ጋር የማይቃረን፣ወይም ከሳይንስ ጋር የማይጋጭና እርስ በርሱም የማይጻረር መሆን፣ሁሉንም የሕይወት ፈርጆች የሚሸፍን መሆን ነው::
- ቀለል ያለ ጥልቀት ያለውና ትክክለኛ የሆነ መልስ . . ስትል ማንኛውም መልስ ትክክለኛ ሆኖ ቢገኝና ደስተኝነት የማያጎናጽፈን ወይም አእምሮና ሎጂክን የሚጻረር ከሆነ፣ወይም ውስብስብና ሁሉንም የሰው ልጅ የሕይወት ፈርጆች የማይሸፍን ከሆነ አንቀበለውም ማለትህ ነው !

www.path-2-happiness.com

- አዎ . . በትክክል እንደዚያ ነው !
- ግሩም ነው ! እንዲህ ያለው ምላሽ ከተገኘ እኔ ካንተ ጋር ነኝ። ከዚያም ፈገግ ብሎ ቀጠለ ፦ የመልሳችንን ትክክለኛነትና የተከተልነው ስልት ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ መሆን አለመሆኑን የሚያሳዩ አዳዲስ ጥያቄዎችን እሰጠሃለሁ . . አሁንም አፈገገና ቀጠለ ፦ የኤቲዝም ማስረጃና እግዚአብሔርን መካድ ተራ ዝቅጠት በመሆኑ ላይ ካንተ ጋር ብስማማም፣አሁንም አምላክ የለም የሚል እምነት አለኝ . . ለማንኛውም ወዴት እንደሚያደርሰን በማናውቀው መንገድ አብረን እንጓዛለን። የማቀርብልህ ጥያቄ ግን ፦ መልሱን የምታገኝበት አምላክ የትኛው ነው? በየትኛውስ ሃይማኖት መንገድ ነው?
- ጉዳዩን ቀላል እናድርገውና ሁለት የሃይማኖቶችና የአመለካከቶች ጎራዎች ይገኛሉ። የመለኮታዊ ሃይማኖቶች ጎራና የምድራዊ ሃይማኖቶች ጎራ። ስለ የትኛው ስብስብ ይሆን የምትጠይቀው?
- ልክ ነህ . . ሃይማኖቶች ብዙ ናቸው። ለማቅለል ሲባል በዋነኛ ምድቦች ብቻ መክፈሉ የግድ ነው። ይህን አላሰብኩም ነበር። አንተ ወደ ሕንድ መሄድህ ነውና ጥያቄውን ፦ ከሃይማኖቶች ውስጥ የተሻለው መለኮታዊው ነው ወይስ ምድራዊው ሰው ሰራሽ? ወደሚለው እንለውጥ። ለጥያቄው በምትሰጠው ምላሽ ላይ ተመርኩዘን ከሁለት ሳምንታት በኋላ ስትመለስ በሚኖረን ቀጠሮ ዝርዝሩን እንመለከታለን። በአገረ ሕንድ እኔ ወዳለሁበት ኢአማኝ ኤቲስትነትና ሁሉንም እርግፍ አድርጎ ወደ መተው የሚያደርሱ ሃይማኖቶች ያጋጥሙሃል ብዬ አስባለሁ።
- ወደ ሕንድ ትጓዛለህ ! እንዴት አወቅህ?
- ቶም ተርበትብቶ አንደበቱ ተሳሰረ፤መውጫ ለመፈለግ ቢሞክርም መጣፊያ አጠረው !
- ከ . . ከካትሪና ነው ያወቅኩት . . ድንገት ቤተክርስቲያን ውስጥ . . በአጋጣሚ አይቻት ነበር።
- ፈጣሪ አምላክን የሚያስተባብል ኤቲስት ወደ ቤተክርስቲያን መሄዱ ደግ ነገር ነው !
- ወደ ቤተክርስቲያን የሄድኩት የአማኞችን ባህሪና ስነ ልቦናቸውን ለማጥናት እንጂ ለአምልኮ አይደለም።
- አሃሃ፣የካትሪናን ስነልቦናዊ ሁኔታ እንዴት አገኘኸው?
- በአመለካከቷ፣በመንፈሷ፣በገጽታዋ፣በተክለ ሰውነቷ ምስራቃዊ መስህብነት

የሚስተዋልባት ሴት፣ ብልህና ሃይማኖተኛ ሴት ሆና ነው ያገኘኋት።
- ትኩረትና አድናቆትህን የሳበች ይመስላል? !
- እውነቱን ለመናገር በሃይማኖት አጥባቂነቷና በእርግጠኛነቷ ተደንቂያለሁ። ያንተ በመሆኗ እንኳ ደስ አለህ እለሃለሁ፣ደሞም በጣም ነው የምታፈቅርህ . .
- ኢአማኝ ኤቲስት ሆኖ ሃይማኖተኝነትን ማድነቅ አስደናቂ አይደለም? !
- ‹‹ምናልባት›› አለና ርእሱን ለመቀየር ሞከረ ፦ የሕንድን ውበት አልጠገብክምና ነው ወደ ሕንድ መጓዝ የምትፈልገው?
- አልገባኝም።
- የካትሪና ውበት አላረካህምና ነው በሌሎች የሕንድ ቆነጃጅት ለመደሰትና ከነሱ ጋር ለመጫወት የምትሻው? !
- ይህን ወዲያ በለው . . እኔ የምሳፈረው የተለያዩ ሃይማኖቶችንና ርእዮቶችን ለማወቅና የሥራ ውል ለመፈራረም ነው። በል ደህና ሁን፣ቀጠሮአችን ከሁለት ሳምት በኋላ ነው።
- ተስማምተናል። ገና ስትቀርባቸው ሁሉንም ሃይማኖቶች ችላ እንደምትል እርግጠኛ ነኝ። መልካም ሕንዳዊ ጥቅምና መደሰቻ እንዲገጥምህ እመኝልሃለሁ።

(5)

ካትሪና ጆርጅ መምጣቱን ስታውቅ በፍጥነት ተነስታ በሩ ዘንድ ተቀበለችው . . የሞቀ ሰላምታዋን በቀዘቀዘ መንፈስና ደስተኛ አለመሆኑን በሚያሳብቅ ቅላጼ መለሰላት . . ራሷን ለማዋደድም ሞከረች . .

- ከባድ ሃሳብ ላይ ነው የጣልከኝ፣ትናንት ዬት ነበርክ፣እቤት አላደርክም? !
- ትናንት በጣም አምሽተሸ እንጂ አልመጣሽም፤እቤት ወይም ውጭ ማደሬ ላንቺ ምንሽም አይደለም።
- አዎ፣ትናንት ቤተክርስቲያን ውስጥ በጣም አምሽተን ነበር፣በጣም አስፈላጊና ድንቅ የሆነ የቤተክርስቲያን የምሽት ድግስ ነበር።
- እርሱ የተሳተፈበት በመሆኑ ድንቅ ነበር።
- ማንን ማለትህ ነው?
- በምሽት ፕሮግራሙ ላይ ካንቺ ጋር የነበረው ማነው?
- ብዙ ናቸው፣በጣም ብዙ።
- ከተገኙት መካከል እኔ የማውቀው ማን አለ?

- ጆርጅ፣እየመረመርከኝ ነው? ለማንኛውም መልስ ልስጥህና ቄስ ሞሪስ፣ሳሊ፣ፒተር፣ሄላሪ፣ሲምፕሰን፣ እና . .
- መልከ መልካም ሎጋው ቶምስ?
- አዎ . . ሐኪም ቶምም ተገኝቶ ነበር። በጌታ ያለውን እምነትና እርግጠኝነት ለማጠናከር ነው የመጣው፣የቅዳሴ ሥርዓቱን በሙሉ ከኛ ጋር ተሳትፏል!
- እጅግ በጣም ጥሩ ነው . . ሃይማኖት የለሽ ኤቲስት የመጣው በቅዳሴ ሥርዓት ላይ ለመሳተፍ ነው ወይስ በመጠጥና በምሽት ጭፈራ ድግሱ ለመዝናናት? !
- እኔን እያዋረድከኝ ነው፣ቤተክርስቲያኒቱንም እያዋረድካት ነው፣ምን ለማለት ነው የፈለከው? እርሱ በምሽት ድግሱ ላይ ማለቴ በቅዳሴ ሥርዓቱ ላይ መሳተፉን ማን ነገረህ?
- የለም፣አንቺን አላዋረድኩም፣ቤተክርስቲያኑንም አላዋረድኩም። እርሱ ራሱ ነው ከማራኪዋ ካትሪና ጋር በማምሸቱ መደሰቱን የነገረኝ። እምነቱን መጨመርና ማጠናከር የሚፈልገው ቶም ነው በጉዞዬ በሕንድ ሴቶች ውበት እንድደሰትና ከነሱ ጋር እንድዝናና በመምከር የገፋፋኝ !
- እንደዚህ አለ !
- አዎ፣ምኑ ነው የሚያስደንቀው?
- ምንም ! ግን . .
- በጣም ደክሞኛልና መተኛት እፈልጋለሁ፣ፍቀጅልኝና ወደ መኝታ ክፍል እሄዳለሁ።

ጧት አማልዶ ወደ ሥራ ሲሄድ ካኽ እሱን በመጠባበቅ ላይ ነበር . .

- የምሥራች ንገረኝ እስኪ፣ጆርጅ የመጨረሻ ውሳኔህ ምንድነው?
- በመካከላችን ያሉትን የሥራ ስምምነቶች ካጠናቀቅን በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ወደ ሕንድ እጓዛለሁ፣በራሴ በኩል ያለውን አመቻችቻለሁ።
- በጣም ግሩም፣የሚፈለጉ ዝርዝር ውሎችንና የሀገሩን ሰዎች ዝርዝር የስነ ልቦና ሁኔታ ለማወቅ ረዣዥም የሁለትዮሽ ስብሰባዎች ያስፈልጉናል።
- ካንድ ሰዓት በኋላ ለሦስት ሰዓት የሚቆይ ስብሰባ ለመጀመር አንተ ዘንድ እሆናለሁ፣ነገም እንደዚሁ ይኖረናል።

ከሕንድ ኩባንያዎች ጋር የሚፈረመው ስምምነት ማስገኘት በሚችለው የገንዘብ ጥቅም ዝርዝር ላይ፣ ካኽ ከፍተኛ ጉጉት አድሮበታል። ለዚህም

ነው ከጆርጅ ጋር የሥራ ግንኙነት የሚያደርጉ ግለሰቦችን ዝርዝር የስነ ልቦና ሁኔታ ለጆርጅ ግልጽ ለማድረግ የፈለገው። ስለያንዳንዱ ግለሰብ የሚያውቀውን ትልቅ ትንሹን ሳይል ሁሉንም ዝርዝሮ ነበር ያስረዳው።

- የምትፈልገው ተጨማሪ ማብራሪያ አለህ?
- የለም፣ነገሮች ከሞላ ጎደል በሚገባ የተብራሩ ይመስለኛል። ለሁለቱም ወገኖች ቁሳዊ፣ ሕሊናዊና መርሃዊ ጥቅሞችን በሚያስገኙ መሰረቶች ላይ የሚፈጸሙ የውል ስምምነቶች ከረዥም ጊዜ አኳያ ይበልጥ ጠንካራና ይበልጥ የጠበቁ ናቸው የሚል እምነት ቢኖረኝም ሁሉም ነገር ግልጽ ነው።
- ማትረፍ ማለት በአነስተኛ ክፍያ የተቻለህን ያህል ከፍተኛ ጥቅም ማግኘት ነው . . በመቀጠል ፈግግ ብሎ :- የገንዘብ ጥቅም ለኔ ይሁን፣መርሃዊና መንፈሳዊ ጥቅም ደግሞ ላንተ ይሁን።
- ተስማምተናል ! !
- የደበቅኩትን ድንገተኛ የምስራች ሳልነግርህ ረስቼ።
- የምን ምስራች? !
- ጥያቄዎችን የሚያስረሳህ፣ሐኪምህንም ጭምር የሚያስረሳህ የምነግርህ ድንገተኛ የምስራች አለኝ ብየህ አልነበር ?
- ምን ይሆን?
- የሕንድን መደሰቻ ቀምሰህ እየው።
- የትኛውን መደሰቻ ማለትህ ነው?
- አንዳንዴ በጣም ደደብ ትሆናለህ፣የሕንድ ሴቶችን ውበት ቅመስ፣ተደሰት እያልኩህ ነው፣ ለሁሉም ጥያቄዎችህ ምላሽ ይሰጡሃል . . የነገርኩህ የሠራተኛ አስቀጣሪ ኩባንያው ዳይሬክተር ማክል ሁሉንም ነገር ያመቻችልሃል . . የሹፈት ሳቅ ለቀቀና :- ማይክል በጣም ሃይማኖተኛ የሆነ ክርስቲያን ነው ብየህ የለም?
- ለመሆኑ ቶምና ካኽን ያመሳሰላቸው ምክንያት ምን ይሆን ! የሥጋዊነትና የኢአማኝነት ባህሪያቸው ይሆን? ወይስ ሁለቱም ከእውነታ የሚሸሹ የመሆናቸው ሁኔታ? . . ጆርጅ ራሱን ጠየቀ። ይህች እውነታ ምንኛ አደናጋሪ ነች ! ! የፈለገውንም ቢሆን ወደርሷ ለመድረስ ቆርጫለሁ . . እያለ ከራሱ ጋር አወራ።

www.path-2-happiness.com

-ጉዞዬ ረቡዕ ጧት ነው፣ከኔ የምትፈልገው ሌላ ነገር አለ?

-መልካም ጉዞ፣መርሃዊ ሳይሆን፣ቁሳዊ የገንዘብ ጥቅም የሚያስገኙ ስምምነቶች፣አስደሳችና ማራኪ ሴቶች፣ . . እመኝልሃለሁ፤ደህና ሁን::

ጆርጅ፣ስግብግብነትና ጭልጥ ያለ ቁሳዊ አመለካከትን በአለቃው በካኽ ላይ ብዙ ጊዜ አስተውሏል:: በተለይም የሕንድ ጉዞውን አስመልክተው ባደረጓቸው የመጨረሻዎቹ ስብሰባዎች ላይ:: በሕንድ ስላሉት የሶፍትዌር መሸጫዎች እንዲያውቅና ርካሽ የሆነ የቴክኒክ ባለሙያ የሰው ኃይል በማስገኘት ላይ እንዲያተኩር ሲያሳስበው ነበር:: መቼም ሕንድ በሕዝብ ቁጥሯ ብዛት ትልቅ ገበያ መሆኗን፣የተትረፈረፈ ርካሽ የሰው ኃይል የዚህ ግዙፍ ገበያ ዓይነተኛ መለያ መሆኑን ካኽ ሲደሰኩርለት ጆርጅ በጸጥታ ያዳምጠው ነበር:: ከገንዘብና ከወሲብ ውጭ ከሕይወት ውስጥ ለምንም ግድ ባልነበራቸውና በሁለቱ ዙሪያ ብቻ በሚሽከረከሩ የካኽ ቃላት ላይ ሀሳብ ለመስጠት ግን ፍላጎት አልነበረውም::

-የሕንዱ ዓለም አቀፍ የሠራተኛ አስቀጣሪ ኩባንያ ዳይሬክተር ማይክል፣አይሮፕላን ጣቢያ ተገኝቶ አቀባበል እንደሚያደርግለት ነግሮት፣ጥብቅ ሃይማኖተኛ መሆኑን አስጠነቀቀውና በመቀጠል፡-

-በውሉ የመለወጥና የመቀየር እድል እስከሰጠን ድረስ . . የፈለገውን ቢሆን ጉዳያችን አይደለም:: የፌዝ ሳቅ እየሳቀ በመቀጠል ፡- ብልጥ ሃይማኖተኝነት እንዲህ ነው፣በኔ በኩል ይበልጥ አትራፊ፣ይበልጥ ተጠቃሚና አስደሳች የሚያደርገኝን ሰው ለማምለክና ለማገልገል ዝግጁ ነኝ !

-ጨርሰው ለመውጣት ሲነሱ ካኽ ጆርጅን ጠቀሰውና የመጨረሻ ማሳሰቢያው ፡- በሕንዳዊ ውበት መደሰት እንዳያመልጠውና አልፎ አልፎ ብቻ የሚገኝ ውበት መሆኑን ነገረው:: ጆርጅ በቸልተኝነት ስሜት ፡-

-የትኛውን ውበት ማለትህ ነው?

-የሕንዳውያቱ ውበት ነዋ ! የምሥራቆቹ ጭፈራ ነዋ !

-ጆርጅ በማናናቅ ስሜት ከንፈሩን መጠጠና ተሰናብቶት ወዲያውኑ ሄደ::

ጆርጅ እቤቱ ሲደርስ በጣም ደካክሞት ነበር:: ካትሪና አለወትሯ ስትጠብቀው አገኛት:: ዛሬ እንደ ልማዷ አላመሸችም . . በፈገግታና በናፍቆት ስሜት ተቀበለችው . .

-የኔ ፍቅር በጣም ዘገየህ፤ለሁለት ሰዓታት ስጠብቅህ ነበር? !

-ስለ ጉዞው ጉዳይ ከካኽ ጋር ረዣዥም ስብሰባዎች ነበሩኝ::

-ልክ ነው ! ዘንግቸው ነበር:: ትናንት ከሐኪም ቶም ጋር የነበረህ ቀጠሮ እንዴት እንደ ነበረ አልነገርከኝም?

-የአስተናጋጁን መልሶች ነው የሰጠሁት ! እኔን አሳምኖኛል፣ ለሱም እንደዚሁ አሳማኝ ሆነዋል::

-በጣም ጥሩ . . ዋናው ነገር በመንገገዱ እየተጓዛችሁ መሆኑ ነው::

-ተጨማሪ አዳዲስ ጥቄዎችም ሰጥቶኛል !

-አዳዲሶቹ ጥያቄዎች ምንድነው?

-መልሱን የምናገኝበትን የተሻለ ሃይማኖት እንድለይና ምላሽ የሚሰጠን ፈጣሪ አምላክ የትኛው እንደሆነ እንድነግረው ነው የጠየቀኝ::

-መልሱ በጣም ግልጽ ነው:: አብ፣ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው፣ሦስትም አንድ ናቸው፤ሰዎችን የፈጠሩት እነሱ ናቸው:: ከዚህ ውጭ የሚያምን ሰው ከሃዲ ኢአማኝ ነው . . በመቀጠልም ልቅ ሳቅ መሳቅ ጀመረች::

-ወደ ሕንድ ስሄድ ሃይማኖቶችን እንድመረምርና ከንጽጽሮሽ በኋላ በመጀመሪያ ከመለኮታዊ ሃይማኖቶችና ከሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች የትኞቹ እንደሚሻሉ እንድወስንም መክሮኛል::

-ተጓዝ ሕንድ ውስጥ አስበህ የማታውቃቸውን ድንቃድንቅ ነገሮች ታያለህ:: በእርግጥ የአግራሞት አገር ነች:: የነገርኩህ ሁሉ እውነት መሆኑን እርግጠኛ ሆነህ ነው የምትመለሰው::

-በሕንዳዊያት ቆነጃጅት እንድደሰት ከቶም የተሰጠኝን ምክርሳ? !

ካትሪና መረበሿን ለመሸሸግ ሞከረች . .

-የኔ ፍቅር በዚህማ ቃሉን አትፈጽም::

-ትጠረጥሪኛለሽ? !

ካትሪና ፈገግ አለች፤ ርእሱን የማስቀየሻ አጋጣሚ አገኘች . . ራሷን ቀና አድርጋም ወደ ጆርጅ ተመለከተች . .

-የዘር ግንዴ ከሕንድ ነው፣ይሁን እንጂ ከሃያ ዓመታት ወዲህ ሕንድን አላየሁም:: ከሕንድ ስጦታ ልታመጣልኝ ትችላለህ?

-በጣም ደስ እያለኝ . . ምን ላምጣልሽ?

-የሕንድ የእጅ ሥራ የሆነ መስቀል እፈልጋለሁ::

www.path-2-happiness.com

- ምርጥ የሆነ የሕንድ መስቀል ይመጣልሻል፣ ግን ከቀላል ግዴታ ጋር ነው።
- በል አቅርብ።
- ዛሬ ለየት ያለ ሌሊት እንዲኖረን እፈልጋለሁ . . በይ ወደ መኝታችን ክፍላችን እንሂድ።

ሕንድ . . የድንቃድንቅ አገር



www.path-2-happiness.com

4

ሕንድ . . የድንቃድንቅ አገር

ሕንድ . . የድንቃድንቅ አገር

(1)

ጆርጅ የአይሮፕላን ማረፊያውን የቪዛ ሂደት ጨርሶ ሲወጣ፣ሊቀበለው የመጣውን ማይክልን አገኘው:: በኢሜል አድራሻው ልኮለት ከነበረው ፎቶግራፉ ለይቶ ያወቀው ማይክል ሞቅ ያለ አቀባበል አድርጎለት ወደ ሆቴሉ መሄድ ወይም በከተማው አጭር ጉብኝት ማድረግ ይፈልግ እንደሆነ ጠየቀው::

- አመሰግናለሁ፣በጉዞውና በሰዓት ለውጡ ምክንያት ድካም ስለተሰማኝ ወደ ሆቴሉ ውሰደኝ:: ምናልባት ወደ ቢሮ ከመሄዳችን በፊት ነገ ጧት ትንሽ ዞር ዞር ማለት እንችል ይሆናል::

ጆርጅ የማይክልን እስከ መጨነቅ ደረጃ የሚቀርበውን የበዛ ሽቅርቅርነትና የሰለጠነ ምግባሩን አስተውሏል:: በውድ መኪናው አብሮት ሲጓዝም በዚህ በድሆች በተጨናነቀች አገር ውስጥ የሀብታም ቱጃሮች መደብ አባል መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም::

ጆርጅ ሌሊቱን በቂ እንቅልፍና እረፍት ካገኘ በኋላ፣ በቀጣዩ ቀን ጧት ልክ አንድ ሰዓት ላይ ንቁ ሆኖ ከክፍሉ ወጣ:: ማይክልን ሆቴሉ እንግዳ መቀበያ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲጠብቀው አገኘው:: ትናንት እንዳየው ሁሉ ትኩረት የሚስብ የተሟላ ሽቅቅርነቱን እንደ ጠበቀ ነበር:: ሠላምታ አቅርቦለት ወደ መኪናው ገብተው ሄዱ::

- ለአንድ ሰዓት ያህል ዞር ዞር ብለን ብንጎበኝ ምን ይመስለሃል? ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ወደ ቢሮ እንደርሳለን::
- መልካም ነው፣ሕንድን ማወቅ እፈልጋለሁ::

ማይክል፣ሕንድ ጥንታዊትና ታሪካዊት አገር በመሆኗ እየተኩራራ ሕንጻዎችንና አብያተክርስቲያናትን ሲያስተዋውቅና ማብራሪያ ሲሰጥ ነበር ሙሉውን ጊዜ ያሳለፈው:: ጆርጅ ጥያቄ ቢያቀርብም ማይክል ስለ አንዳንዶቹ ግዙፍ ሕንጻዎች መናገርን ሆን ብሎ የሚሸሽ መሆኑን ጆርጅ አስተውሏል:: በየቦታው ስለሚገኙት የቡድሃ ማምለኪያ ሐውልቶችም ምንም ከመናገር ይቆጠብ ነበር:: ጆርጅ ካንድ ጊዜ በላይ ጠይቆት፣ሕንድን የክርስትና አገር ብቻ አድርጎ ለማቅረብ የሚፈልግ ይመስል መልስ ሳይሰጠው አድበስብሶ አልፎታል:: ጆርጅ ምንም ሀሳብ ሳይሰጥ በመመልከት ብቻ ተወሰነ፣ማይክል

www.path-2-happiness.com

አክራሪ ካቶሊክ መሆኑን ካኽ ነግሮት እንደነበረ ትዝ አለው::

ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ጆርጅና ማይክል ወደ ቢሮው ደርሰው በሥራዎቹ፣በፕሮጀክቶቹና በውል ስምምነቶቹ ላይ በውይይት ተጠምደው እስከ አምስት ሰዓት ቆዩ:: በጅርጅ አካሄድ እርካታ የተሰማው ማይክል ድንገት ራሱን ቀና አደረገና እንዲህ አለው ፦

-አንተም እንደኔ ክርስቲያን ነህ፣ይሁዲው ካኽ የሁሉንም ተቀጣሪ ውሎች እንዲያጭበረብር ለምን እንፈቅድለታለን:: የማዛባቱ ነገር በሕንዱዎች፣በቡድሂስቶችና በሙስሊሞች ላይ ብቻ የተወሰነ እንዲሆንና የክርስቲያኖች ውል ከሁሉም የተሻለ እንዲሆን ብናደርግ ምን ይመስለሃል፣ይህ ይሁዲ እንዲሰርቀን አልፈልግም !

-ሕንዱውን ቡድሂስቱንና ሙስሊሙን መስረቅስ ፍትሐዊ ነው? !

ማይክል ተሸማቆ ዝም አለ . . ያከናውኑት ወደ ነበረው ሥራ ተመልሰው እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ ቀጠሉ:: ሰባት ሲሞላ በጣም ደክሞት ነበርና ጆርጅ ዕረፍት ጠየቀ::

ወደ ሆቴሉ ለመሄድ በመጡበት መንገድ ተመለሱ:: አንድ ትልቅ ሕንጻ ሲመለከት ጆርጅ ሆን ብሎ ለማይክል በድጋሜ ጥያቄ አቀረበ ፦

-ይህን ውብ ሕንጻ ማነው የገነባው?

-ሙስሊሞቹ ናቸው . . ወራሪዎቹ ሙስሊሞች::

-ይኸኛውስ ምንድነው?

-ኋላ ቀር የሆነ የቡድሂዝም ቤተ መቅደስ ነው . . በድንጋዮችና እንደኛው ባሉ ሰዎች ያመልካሉ ! !

ማይክል በነዚህ ጥያቄዎች ደስተኛ አለመሆኑን ስላወቀ፣ጆርጅ ቀሪውን መንገድ በዝምታ እያዳመጠው መጓዙን መረጠ . .

(2)

ማይክል አስር ሰዓት ላይ ለምሳ አብረው ለመሄድ እንደሚመጣ ለጆርጅ ነግሮት ተስማምተዋል:: ቀለል ያለ ግን ለአቀባበሉ በቂ የሆነ ድግስ አዘጋጅቶለታል:: ጆርጅ ከመኝታ ክፍሉ ወደ መኪና እንደገባ ማይክል በመገረም ስሜት ጠየቀው ፦

-ካኽ ወደኛ በሚመጣበት ጊዜ የሚጠይቃቸው የተለመዱ ነገሮች አሉ፤አንተ ግን ስትጠይቅ አላየሁም !

-ምንድን ይሆን?

-ወደ ሬስቶራንቱ እስክንደርስ ድረስ መልሱን እናቆየው፣ በሚጠብቅህ ያልተጠበቀ ነገር ትደሰታለህ ብዬ አምናለሁ !

ወደ ታጅ ኦፍ ኢንዲያ ሬስቶራንት ደረሱ:: በሁሉም ገጽታው ታላቅነትንና ታሪካዊነትን የሚያንጸባርቅ ሲሆን፣የቦታው ውበትና አስደናቂነቱ የጆርጅን ትኩረት ስበዋል:: ባህላዊ አሠራሩ መስህብነቱን ጨምሯል:: ጆርጅ በልማዱ የማይወደው ቢሆንም እንኳ ቦታውን ያወደው የሕንድ ዑድ ሽቶ መዓዛ አስደስቶታል:: ማይክል አንዳች መልክት የሚያስተላልፍ ፈገግታ አሳየውና ለርሱ የተያዘለት ልዩ ክንፍ ከዚህ ይበልጥ ውብና ማራኪ እንደሚሆን ነገረው::

በሬስቶራንቱ ልዩ ክንፍ ውስጥ፣ጆርጅ ዕድሜያቸው ሃያ ዓመት አካባቢ የሚገመት ሁለት ውብ ኮረዶችን አየ:: ወደርሱ እየተመለከቱ ፈገግታ ያሳዩ ነበር:: እሱም በአጸፋ ፈገግታ እያሳየ ጨበጣቸው:: ማይክል በዓይኑ ጠቀስ አድርጎት ደጋግሞ ትከሻውን ቸብ ቸብ አደረገና ፦

-ያልተጠበቀውን አስደሳች ዱብዳ እንዴት አየኸው? አለው::

-ግሩም ድንቅ ነው::

-ካኽ በመጣ ቁጥር ለምሳ ወደዚህ ቦታ ነው ይዤው የምመጣው:: ከዚያም ሁለቱን ኮረዶች ወይም አንደኛዋን አስደሳች ሌሊት በአብሮነት ለማሳለፍ ወደ ሆቴሉ ይዞ ይሄዳል::

የመከፋት ስሜት የሚስተዋልበት የጆርጅ ፊት ጨፍገግ ብሏል፣በቀዘቀዘ አነጋገር መለሰለት ፦

-እኔን በተመለከተ ግሩም ድንቁ አስደሳች አጋጣሚ የቦታው ውበት ብቻ ነው ::

-የሚገርም ነው፣ኮረዶቹ አልተመቹህም? !

-በእርግጥ ሁለቱም ውብ ቆነጃጅት ናቸው:: የምትገርመው ግን አንተው ነህ ! እኔ ካኽ አይደለሁም !

-እንዴት ማለት?

-ካኽ የሚሰራው ጥሩ ነገር ሆነና ነው እኔም እንደሱ የምሰራው? !

-በዚህ መንገድ እንጅ ካኽ ውሎቹን ጭራሽ አይፈርማቸውም !

-እናም ውሎቹን እንድፈርም የቀረበልኝ ጉቦ ነው ማለት ነዋ !

-ይቅርታ፣ምንድነው የምትፈልገው?

-እኔ ባለትዳር ነኝ፣በባለቤቴ ላይ ክህደት መፈጸም አልፈልግም:: የኔማ ማይክል ክርስትና ይህችው ናት? !

-ልክ ነህ . . ልክ ነህ !

-አስተናጋጁ የምግብ ሜኖውን አምጥቶ ለማይክል አቀረበና በሕንድኛ

ከተነጋገሩ በኋላ ሄደ:: ሁለቱ ኮረዶችም ተከትለውት ሄዱ:: ፈገግታ ለማሳየት እየሞከረ ወደ ጆርጅ ዞር አለና ፦

- በራሴ ምርጫ ልዘዝ ወይስ አንተ ራስህ ትመርጣለህ?
- ምግቡን ከኔ ይበልጥ ስለምታውቀው አንተ ምረጥ::
- ጆርጅ የሰፈነውን የውጥረት አየር ለመቀየር ሲፈልግ፣ከሕንድ መስቀል እንዲያመጣላት ደጋግማ የጠየቀችውን ካትሪና አስታወሰ:: ከሕንድ የሚመጣላት መስቀል፣ክርስቲያኖች ሕንድ ውስጥ በሙስሊሞች ላይ የተቀዳጁትን ድል፣ፓክስታን ከሕንድ ባንግላዴሽ ከፓኪስታን የተገነጠሉበትን ሁኔታ የሚያስታውሳት ስለመሆኑ የነገረችው ትዝ አለውና ለማይክል እንዲህ አለው ፦
- በእጅ ስለሚሰሩት ምርጥ መስቀሎች ከማንም ሰው በላይ ታውቃለህና ለባለቤቴ መስቀል መግዛት የምችልበትን ቦታ ልታመለክተኝ ትችላለህ?
- ሆቴል ክፍልህ ድረስ ይመጣልሃል . . በመቀጠልም ፦ ደሞም ዋጋውን ስለምነግርህ ጉቦ አይደለም ! ሲል አከለ::
- ታውቃለህ፣እኔ ፕሮቴስታንት ክርስቲያን ብሆንም ክርስትናን አላውቅም:: እስከገባኝ ድረስ አንተ ሃይማኖተኛ ነህና ስለ ሃይማኖቴ ልታሳምነኝ ትችላለህ? !
- ክርስትና ከእግዚአብሔር የተላለፈ መለኮታዊ ሃይማኖት እንጂ እንደ ሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖት አይደለም::
- የትኞቹን ሃይማኖቶች ማለትህ ነው?
- ቡድሂዝም፣ሕንዱ፣ዞረስትሪያንና የመሳሰሉትን ማለቴ ነው:: በመቶዎች የሚቆጠሩ መሰል ሃይማኖቶች ሕንድ ውስጥ ይገኛሉ::

ጆርጅ ከአደም ጋር ያደረገው ውይይት ወደ ትውስታው ሲመጣ፣ ስለ ሃይማኖቶች ያለውን አመለካከትና መገኘታቸውን እንዴት እንደሚተነትን ለማወቅ፣ጥያቄዎቹን ለማይክል ማቅረቡን የመቀጠል ፍላጎት አደረበት::

- ክርስትና ወይም ሌላው ምድራዊ ሳይሆን መለኮታዊ ሃይማኖት ስለመሆኑ ማረጋገጫው ምንድነው?
- ይህን የሚያረጋግጠው ታሪክ፣ሲወርድ ሲዋረድ የተላለፈ ማስረጃና ምስክርነት ናቸው:: የሕንዱ እምነት ተከታይን ብትጠይቀው ክርስትና መለኮታዊ ሃይማኖት ነው፣ህንዱ ሰዎች በየጊዜው የሚያሻሽሉት ሃይማኖት ነው . . ይለሃል::
- ነገሮችን በማቅለል ስልት መለኮታዊ ሃይማኖቶች ከምድራዊ ሃይማኖቶች ይበልጥ ትክክለኞች መሆናቸው ማወቅ የሚቻል ይመስለኛል::

- ማቅለል የሚለው ውብ ቃል ነው:: አዎ ይበልጥ ትክክለኞችም ናቸው፣በዚህ ጥርጣሬ አለ? !
- ይህ የሁሉም ክርስቲያኖች አቋም ነው:: እኔ በቀላሉ የምፈልገው ግን ያንን በራሴ ማረጋገጥና በገዛ ዓይኔ ማየት ነው::

በሁነቶችና በውይይቶች የተሞላና የተጨናነቀ ቀን ካሳለፈ በኋላ ጆርጅ ወደ ሆቴሉ ሄደ:: ገብቶ በጆርባው እንደተዘረረ ያሳለፈውን ሁሉ ማጠንጠን ያዘ:: ‹‹ነገሮችን በቅለት እንጂ በውስብስብነት፣ በደስተኝነት እንጂ በትካዜ ላለመመልከትህ እርግጠኛ ሁን›› የሚለውን የአደም አነጋገር ሲደጋግም ራሱን አገኘ::

- በሕንድኛ የሚቀርብና የእንግሊዝኛ መግለጫ ያለው ፕሮግራም ለማግኘት ቴሌቪዥን ከፈተ:: የሕንዱ ሃይማኖትንና ሞራላዊ ትምሕርቶቹን አስመልክቶ ይቀርብ የነበረው ፕሮግራም፣የሕንዱ ሃይማኖት ለተፈጥሮ ኃይላት ቅድስናን በመስጠት ላይ የተመሰረተው የኣርያኖች ሃይማኖትና በአመዛኙ የጥንት ሕንዶች ይወዷቸው በነበሩ ነገሮች ላይ የሚያተኩረው የቀደምት ሕንዶች ሃይማኖት ቅይጥ መሆኑን ያረጋግጣል:: ከጊዜ በኋላ ማሻሻያ ተደርጎ አንድ ዓይነት የመዋሐድ ሁኔታ ተከሰተና - ያንዳንድ ማሕበራዊ መደቦች ልዩ መብቶች እንዳይጠፉ በመስጋት - እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከቱ እሳቤዎችን በጽሑፍ ማስፈር ጀመሩ:: የእሳቤዎቹ ስብስብም ኋላ ላይ ቪዳ ወይም ወይዳ ተብሎ ተሰየመ:: ወይዳ የተባለው በሕንዱዎች ዘንድ ዋነኛው ቅዱስ መጽሐፍ ሲሆን ትርጉሙ ሕግ ወይም ጥበብ ማለት ነው:: እነዚህን ሕጎች በጽሑፍ አስፍረው ማኖሩን የቀጠሉ ሲሆን፣የሕጎቹ ዓለማ የቆዳ ቀለሙ ነጭ የሆነው አናሳው የኣርያን ዘር መደብ፣የቆዳ ቀለሙ ጥቁር በሆነው የብዙኃኑ መደብ ላይ ልዩ መብቶች እንዳሉት ማረጋገጥና መብቶቹን ማስከበር ነው:: ለአናሳው መደብ ማለቂያ የሌላቸው ልዩ መብቶች የሚሰጡ እነዚህ ሕጎች እየበዙና እየገዘፉ በመሄዳቸው በቃል ጠብቆ ማቆየት ከማይቻልበት ደረጃ ሲደረስ ጽፈው ማኖር ጀመሩ:: የመጻፉ ሂደትም ለአስር ምእተ ዓመታት ማለትም ለአንድ ሺ ዓመት የቆየ ሲሆን፣ካሁን በኋላ ምንም ነገር አይጨመርበት የሚል የሕንዱ ካህናት ጠቅላይ ጉባኤ ውሳኔ እስካስተላለፈበት ጊዜ ድረስ ቀጥሏል:: ውሳኔው ባይተላለፍ ኖሮ ጭማሬው እንደቀጠለ ይቆይ ነበር:: መጽሐፉ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ጥራዞች ያሉት ግዙፍ መጽሐፍ ነው:: ከሁሉም በላይ የጆርጅን ትኩረት የሳበው የሕንዱ ሃይማኖት ሕንድ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ብቻ የሚያገለግል፣ሕንዱዎች በሃይማኖት መሪዎቻቸው

ጉባኤ ላይ እምነቱ የሕንዶች ብቻ መሆኑንና የሕንዱ አማኝ ከሕንድ አገር ውጭ በሚሆንበት ጊዜ ሕንዱ መሆኑ እንደሚቀር መወሰናቸውን የሚያመለክተው የቲቪ ፕሮግራሙ ክፍል ነበር:: ለቦታ ሳይቀር ጠባብ ወገንተኛ በሆነው በዚህ አስገራሚ ሃይማኖት የፌዝ ሳቅ ሳቀ፤ሆኖም ራሱን ያዝ አደረገና ፦

- ለማንኛውም ይህ የሰብአዊ ፍጡራን ገዳይ እንጂ መለኮታዊ አይደለም:: በቀላሉ ይኸው ነው! . . የፍለጋየን ውጤት ማየት የጀመርኩ ያህል ነው የተሰማኝ:: ይሁን እንጂ ይህ ብቻ በቂ አይደለም . .

(3)

- ጧት ሁለት ሰዓት ላይ ማይክል በቀጠሮው መሰረት ጆርጅን በእንግዳ መቀበያ ሳሎን ሆኖ በመጠባበቅ ላይ ነበር:: ገና ጆርጅን ሲያይ ፈገግ እያለ ሰላምታ አቀረበለትና በቁርጠኝነት ቅላጼ ፦
- ዛሬም ልክ እንደ ትናንቱ የተራዘመ ሥራ እየጠበቀን ነው፣ዝግጁ ነህ?
- በትክክል፣ የመጣሁት ለዚህ ነውና::

ወደ ቢሮ በመጓዝ ላይ እያሉ የቡድሃን ሐውልት የማይመስል እንግዳ የሆነ ሐውልት ተመለከተና አትኩሮ ለማየት ራሱን ዘንበል አደረገ:: ማይክል ቀድሞት ሳቀና ፦

- ምን ሆንክ? ይኸ ከአማልክቱ ውስጥ አንዱ አምላክ ነው:: ምድራዊ ሃይማኖቶች በየቀኑ አዲስ አምላክ ይቀረጽላቸዋል አላልኩህም ነበር?
- የነዚህ ምድራዊ ሃይማኖቶች አማኝ ከሆነ ሰው ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ::
- አሃ፣ዛሬ ከኩባንያችን የኦፕሬሽን መምሪያ ሥራ አስኪያጅ ጋር ነው ምሳ የምትበላው፣አጥባቂ የቡድሂዝም ሃይማኖት ተከታይ ናት::

ወደ ኩባንያው መሥሪያ ቤት ደረሱና በሥራ ተጠመዱ:: ጆርጅ ሙሉ በሙሉ ከካኽ እንደሚለይ ማይክል እያስተዋለ መጥቷል:: ጆርጅ ለሃይማኖት ትኩረት የሚሰጥ ስለ እምነቶች የሚጠይቅና የማወቅ ጉጉት ያለው ሲሆን፣በተጨማሪም የሚያከብረውና የሚመራበት መርህ ያለው ሰው ነው:: ካኽ ግን በተቃራኒው ከገንዘብና ከወሲብ ውጭ የሚያሳስበው ምንም ነገር የለም:: ስድስት ሰዓት አካባቢ ሥራውን ሲያጠናቅቁ ማይክል ወደ ጆርጅ ትንሽ ቀረብ ብሎ ለስለስ ባለ ቅላጼ ፦

- ከጨርሰን ዘንዳ፣አእምሮዬ ውስጥ የሚመላለስ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ፣አለው::
- በል ንገረኝ::

- ሁለታችሁም ካንድ ኩባንያ ብትሆኑም፣አንተ ካኽን ፈጽሞ አትመስለውም::
- አሃ፣የሬስቶራንቱን ኮረዶች ማለትህ ነው?
- ይኸኛው አንዱ ብቻ ነው፣ሌሎችም ብዙ አሉ::
- መልካም፣የነዚህ ልዩነቶች መንስኤ በአንተ አስተያየት ምንድነው?
- መንስኤው በቀላሉ ሃይማኖት ነው::
- አንተ ሃይማኖተኛ እየሆንክ የካኽን ፍላጎት ታስፈጽም የለ?
- ምናልባት፣ይሁን እንጂ . . እኔ የምፈጽመው ነገር ሁሉ የግድ ትክክለኛ ነው ማለት አይደለም::

ማይክል ለመሄድ ተነስቶ እንደ ቆመ ፊቱን ወደ ጆርጅ መለሰና ፦

- ጂዮስቲናን ማግኘት አትፈልግም?
- ጂዮስቲና ማን ነች?
- ቡድሂስቷ የኦፕሬሽን መምሪያ ሥራ አስኪያጅ ነች . . ጂዮስቲና ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ?
- አላውቅም::
- ትርጉሙ የጨረቃ ብርሃን ማለት ነው:: ፈገግ አለና ፦ እህህ፣ግና ዕድሜዋ አሁን ወደ ስልሳ ዓመት ነውና ጉቦ አይደለችም::
- ልክ ነህ፣ላገኛት እፈልጋለሁ፣ዛሬ አስር ሰዓት ላይ በሆቴል ከኔ ጋር ምሳ መብላት ትችላለች ?
- ይቻላል፣ከርሷ ጋር ከተገናኘህ በኋላ የክርስትናን ጸጋ ትረዳለህ . .

ጆርጅ ለምሳ ቀጠሮው ከክፍሉ ሲወጣ ዕድሜዋ ትንሽ ገፋ ያለ፣ የሕንድና የቻይና ዝርያ ቅልቅል ገጽታ ያላት፣ወይም እንደዚያ የመሰለችው ሴት ቁጭ ብላ እየጠበቀችው ነበር:: ጠጋ ብሎ ሰላምታ አቀረበላት ፦

- ወይዘሮ ጂዮስቲና እንኳን ደህና መጣሽ::
- እንኳን ደህና መጣህ፣ካንተ ጋር በመገናኘቴ ደስተኛ ነኝ::

በሆቴል ቤቱ ሬስቶራንት ክፍት ቡፌ ለምሳ ጋበዛት:: አመሰገነችው:: ትሁትና በጣም ጨዋ ሴት መሆኗ በግልጽ ይታይ ነበር::

ጆርጅ ለመቀመጫ ወደ ጥግ ያለውን ጠረጴዛ መረጠ:: በድጋሜ እንኳን ደህና መጣሽ አላትና ፦

- ማይክል ስላንቺ ብዙ ብዙ ነግሮኛል::
- ስላንተም እንዲሁ ማይክል ብዙ ነግሮኛል:: ስለ ቡድሂዝም ማወቅ ስለምትፈልግ ከኔ ጋር ምሳ ለመብላት መጠየቅህንም ነግሮኛል !
- ልክ ነው::
- ወደ ውይይቱ ከመግባታችን በፊት አንድ ነገርህ ትኩረቴን ስቧል፣እኔ ብቻ

www.path-2-happiness.com

ሳልሆን መላው የኩባንያው ሠራተኞች ይህንኑ ነው የሚናገሩት፡፡
- ምንድን ይሆን?
- እንደ ካኽ አለመሆንህ ነው፡፡
- እንዴት አወቁ?
- በክርስቲያኖች፣በቡድሂስቶች፣በሕንዱዎችና በሙስሊሞች መካከል በቅጥር ውል ስምምነት ልዩነት ማድረግንና ኮንተራቶቹን ማጭበርበርን እምቢ አልቀበልም የማለትህ ወሬ በስፋት ተሰራጭቷል፡፡ ሁለቱን ቆነጃጅት ኮረዶች አለመቀበልህና ሌሎችም ሰራተኛው ዘንድ ተዳርሰዋል፡፡
- ይህ ያስደስታቸዋል ማለት ነው?
- ቢያንስ ለኔ እንደ ቡድሂስት፣ . . እጅግ በጣም ያስደስተኛል፡፡
- ውሎችን ማጭበርበርና ማዛባትን መቃወም ግልጽ ነው፣ በትዳር ላይ ክህደት መፈጸም ግን እንዴት ይታያል?
- እኛ ቡድሂስቶች ክህደትንና ለሥጋዊ ፍላጎት መረታትን እንጠላለን፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የእኩይ ነገሮች ሁሉ መሰረት ሦስት ነገሮች መሆናቸውን እናምናለን፡፡ የመጀመሪያው ፦ ለሥጋዊ ፍላጎት መንበርከክና ተገዥ መሆን ነው፡፡ ከቡድሃ ትእዛዛት መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን ፦ ‹‹ሕይወት ያለውን ነገር አታጥፋ፣አትስረቅ፣አትናደድ፣አትዋሽ፣አስካሪ መጠጥ አትጠጣ፣ዝሙት አትፈጽም፣ያለ ጊዜው የበሰለውን ምግብ አትብላ፣አትጨፍር፣በጭፈራም ሆነ በዘፈን ድግስ ላይ አትገኝ፣ሐኪም አትጠቀም፣ፍራሽም ሆነ ምንጣፍ አይኑርህ፣ ወርቅም ሆነ ብር አትውሰድ››፡፡
- እጅግ በጣም ድንቅ የሆኑ ትእዛዛት ናቸው፣መልካም ፈቃድሽ ከሆነ ግን አንዳንድ ጥያቄዎች አሉኝ ፦ በሐኪም የማትጠቀሙት፣ ወይም ወርቅም ሆነ ብር የማትወስዱት ለምንድነው? ፍራሽም ሆነ ምንጣፍ የማይኖራችሁስ ለምን ይሆን? ሶሻሊዝም ነው ወይስ ምንድነው ?
- ዓለማዊ ሕይወትን ችላ ማለትና ምናኔ ከዋነኞቹ የቡድሂዝም መገለጫዎች አንዱ ነው፡፡ ይህም ከጋብቻ መራቅ፣ሀብት ማካበትን መተው፣ራስን ችላ ማለትንና የሰማሃቸውን የመሳሰሉ ሌሎች ጉዳዮችን ያካትታል፡፡ ዓለማዊ ሕይወት የክፋት ሁሉ እናት ነውና፡፡
- የቡድሂዝም ሃይማኖት ዋነኛ መገለጫ ይህን ዓለማዊ ሕይወት እንዳንኖርና እንዳንደሰት ማድረግ መሆኑ አስገርሞኛል፡፡ ገንዘብ መውደድና ወደ ተቃራኒ ጾታ መሳብ የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው . . ለመሆኑ ቡድሃ ማነው?

- ዓለማዊ ሕይወት የክፋት ሁሉ እናት ነው ብየሃለሁ፡፡ ምናኔና ዓለማዊ ሕይወትን ችላ ማለት የመልካም ነገሮች ሁሉ እናት ነች፡፡ ቡድሃ ማነው? ለሚለው ይህ ለመመለስ የሚያስቸግር ጥያቄ ነው !
- ቡድሃ ማነው የሚለውን መመለስ እንዴት ነው አስቸጋሪ የሚሆነው? አምላካችሁ፣ወይም መልክተኛችሁ፣ወይም የምትጠሩበት አዳኛችሁ አይደለም ወይ? !
- አስቸጋሪ ከሆነው ግማሹን አግኝተሃል፡፡ ነብይ ነው፣አዳኝ ነው፣አምላክ ነው ወይስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፣መምህር ነው ወይስ ሌላ ? . . በሚለው ላይ ከስምምነት የተደረሰበት አንድ አቋም የለንም፡፡
- አይታመንም፣እንዴት ሊሆን ይችላል? !
- በዚህ ጉዳይ ላይ ሰሜን ቻይና ከደቡቡ፣በርማና ሲሪላንካ ፈጽሞ የተለያየ አቋም ነው ያላቸው፡፡ ለማንኛው ዋናው ጉዳይ ይህ አይደለም፡፡ ዋነኛው ጉዳይ ቡድሂስት ለመሆን መንፈሳዊ ምጥቀትና ልቀት እንዲኖርህ ነው፡፡
- ነፍስን ማጥራትና መንፈስን ማላቅ ጋብቻና ሀብትን በመተው፣በአለባበስ ራስን በማስቸገር ነው? !
- አዎ፣አትስርቅም፣አትዋሽም፣አትሰክርም፣አትገድልም፡፡

ጆርጅ ከጂዮስቲና ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ውድና ማራኪ የሆነው ልብሷ ከእይታው ውጭ አልነበረምና ሳሪዋን በትኩረት እየተመለከተ ሆን ብሎ ጥያቄ አቀረበላት ፦
- ቡድሂስቶች በዚህ ተገዥዎች ናቸው?
- አዎ . . ፈገግ አለችና ፦ በተወሰነ ደረጃ፣የሕይወት ውጣ ውረድ በነዚህ ጥበባዊ ትእዛዛት መሰረት እንድንኖር አያስችሉንም፡፡
- እናም ሞራላዊ ምክሮች ብቻ እንጂ ሌላ አይደሉም፣ ለአብዛኛው ሕዝብ ሕይወት የተመቹ አይደሉም ማለት ነዋ? !
- አሁንም በተወሰነ ደረጃ አዎ . . እናንተም ብትሆኑ እንደዚያው ናችሁ፡፡
- ምን እያልሽ ነው?
- ግልጽ ልሁንና ማይክል በጣም ሃይማኖተኛ ነው፤ሆኖም ግን በየጉብኝቱ ቆነጃጅት ኮረዶችን ራሱ ለካኽ ያቀርብና የኮንትራት ስምምነቶችን ያጭበረብራል! አስካሪ መጠጥ የሚጠጡ ብዙ ክርስቲያኖችንም አውቃለሁ፡፡ እነዚህ ስህተቶች እናንተ ዘንድም ይገኙ የለም ወይ?
- ትክክል ነሽ፣ግን የኔ ትኩረት በራሱ በሃይማኖት ላይ ነው፡፡
- ለኔ ልዩነቱ ብዙ አይደለም፣ሁላችንም የምንመሳሰል ይመስለኛል፡፡ በመቀጠል ተመግባ ማብቃቷን ለማመልከት አፏን ማበስ ያዘች፡፡ ጆርጅ

www.path-2-happiness.com

አስተናጋጁን ጠርቶ የሕንድ ጣፋጭ እንዲያቀርብላት አዘዘና ውይይቱን ቀጠለ ፦

- በአምላካችሁ ወይም በነብያችሁ ወይም በ . . ላይ ስምምነትና የጋራ አቋም የላችሁም:: በሕግጋት፣ በድንጋጌዎችና በትእዛዛት ላይ ስምምነት አላችሁ?
- እኛ እነዚህን ትእዛዛት በየጊዘው፣በየዘመኑና በየአገሩ እናሻሽላቸዋለን . .
- ታሻሽላላችሁ !!
- አዎ፣ቡድሂዝም ከጊዜ ጋር የሚሻሻል ሃይማኖት ነው:: ክርስትናን በተመለከተ እናንተ እንደምትሉት መለኮታዊ ሳይሆን የኛ የእጅ ሥራ ውጤት ነው:: አንዳንዶች መለኮታዊ መሰረት ነበረው የሚሉ ቢሆንም እኔ ግን እጠራጠራለሁ::
- ትንሽ የሚያሸማቅቅ ቢሆን እንኳ ቀጥተኛና ቀላል የሆነ ጥያቄ እንዳቀርብልሽ ትፈቅጂያለሽ?
- ቡድሂስቶች ሁሌም ማቅለልን ያፈቅራሉ፣አቅርብ::
- መለኮታዊ ሃይማኖት ከሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖት የተሻለ ነው ብለሽ ታምኚያለሽ?

ጂዮስቲና ራሷን ትንሽ አቀርቅራ ለጥቂት ጊዜ ዝም ካለች በኋላ ራሷን ቀና አድርጋ መናገር ያዘች ፦

- ላለመዋሸት ስል . . መለኮታዊ የሆነው በላጭ ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም . . ይህ ከመርህ አኳያ ነው:: በስተቀር ብዙ ቁጥራቸው የበዛ የመለኮታዊ ሃይማኖቶች ተከታዮች በጣም እኩይ ሰዎች ናቸው . . ፈገግ ብላ አከለች ፦ ለምሳሌ ያህል ይሁዲውን ካኽን፣ ከርሱ አነስ ባለ ደረጃ ደግሞ ክርስቲያኑን ማይክልን ውሰድ:: ሁለቱ የሰዎችን ገንዘብ ያጭበረብራሉ፣ ይሰርቋቸዋልም !
- አውነት ነው . . ትክክል ነሽ፤ግን መለኮታዊ ሃይማኖትን ተቀብለሽ ጥሩ ለምን አልሆንሽም?
- ቡድሂስት ከሆኑ ወላጆች ነው የተወለድኩት፣በመሆኑም እኔ ቡድሂስት ነኝ:: ግን ማን ያውቃል !! ምናልባት ከሞትኩ በኋላ ይሁዲ፣ሙስሊም ወይም ክርስቲያን እሆን ይሆናል::
- ከሞትሽ በኋላ? !
- አዎ . . እኔ ከሞትኩ በኋላ መንፈሴ ወደ ሌላ ግለሰብ ትዛወራለች፣አሁን እድሜዬ ስልሳ ነው::
- የሙታን መንፈስ ለአዲስ ሕይወት ወደ ሌሎች ተሸጋግሮ ይወለዳል ብለሽ

ታምኚያለሽ?
- አላምንም፣ግን ሃይማኖታችን ውስጥ አለ::

በውይይቱና በእሰጣ አገባው ምክንያት ጂዮስቲና ድካም እንደተሰማት ፊቷ ያሳብቃል:: በተለይ ደግሞ ሳታርፍ ከሥራ እንደወጣች በቀጥታ የመጣች በመሆኗ ከዚህ በላይ መቀመጥ ስለሚሳናት ውይይቱን የመቋጨት ፍላጎት አሳየች::

- ሌሎች ጥያቄዎች ወይም የማቀርብልህ አገልግሎት አለ?
- የለኝም፣አመሰግናለሁ:: ብዙ ነው ያገለገልሽኝ፣ካንቺ ብዙ ነገር ተምሬያለሁ:: ተሰናብቷት ሄደች::

ማይክል በቀኑ መጨረሻ ላይ ለጆርጅ ደውሎ፣የጠየቀው መስቀል እንግዳ መቀበያ ያለው ሰራተኛ ዘንድ የተቀመጠለት መሆኑን ነገረው:: ትንሽ ቀልድ ብጤም አስከተለና ፦ ደሞም ጉቦ ነው ብለህ እንዳትጠራጠር በሆቴሉ ቢል ላይ ተሞልቷል!

ጆርጅ አመሰገነውና አብረው ሳቁ::

- ንገረኝማ፣ከጂዮስቲና ጋር ከተገናኘህ በኋላ የክርስትናን ጸጋ አወቅህ አይደል?
- ከሞላ ጎደል::
- ውይይታችሁ ቢራዘም ኖሮ ጸጉር የሚያሸብቱ ጉዳጉዶችን በሰማህ ነበር:: ስለ ምናባዊ እሳቤዎቻቸውና ስለ ፍልስፍናዎቻቸው ነግራሃለች?
- ምናባዊ እሳቤዎቻቸው ! . . አልነገረችኝም::
- አሀ፣ይሻላል፣ክርስትና የተሻለ መሆኑን ለማወቅ የነገረችህ ብቻ በቂ እንደሚሆን ብገምትም፣ያንን ብትነግርህ ኖሮ ሁለተኛ ወደ ሕንድ አትመለስም ነበር::
- ሁሉንም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ማላትህ ነው?
- እንደዚያ ነው የሚታየኝ፣ወዳጄ በል ደህና ሁን፣በቸር እንገናኝ::

ጆርጅ እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስ፣አልጋው ላይ ተንጋሎ የኢንተርኔት ድረ ገጾችን እየጎበኘና ቲቪ እየተመለከተ በሆቴል ክፍሉ ውስጥ አሳለፈ:: ለርሱ አድካሚ የሆነ ቀን ነበር:: አካላዊ ድካም ሳይሆን በተልእኮውና በሚፈጽማቸው ዝርዝር ጉዳዮች ጎን ለጎን ወደ ሕንድ እንዲመጣ በዋናነት በገፋፋት የግል ጥያቄዎቹ አእምሮው ተወጥሯል:: በዚህ ሁሉ ማዕበል መሀል ‹‹ነገሮችን የምትወስዳቸው ቀለል አድርገህ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሁን›› የሚለው የአደም ማሳሰቢያ ከትውስታው አልተለየም:: ዛሬ የሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች መደናበርና ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር የመጻረራቸው ሁኔታ በከፊል ግልጽ

ሆኖለታል። እምነቱም ይኸው ነበርና እንደኛ ያለ ሰብአዊ ፍጡር ለምን ዓለማ እንደተፈጠርን እንዴት ልነግረን ይችላል?! በመሆኑም ብዙም ሳይቆይ ትልቅ እፎይታና ውስጣዊ እርካታ ተሰማው።

(4)

በቀጣዩ ቀን ጧት ጆርጅ ወደ ትልቁ የዴልሂ የኮምፒዩተር ገበያ አመራ። በሕንድ የትልቁ የኮምፒዩተርና የሶፍት ዌር መሸጫ መረብ ባለቤት ወደ ሆነው የሙጢዕ ቢሮ ለመሄድ በአሳንሰር ወደ አምስተኛው ፎቅ ወጣ።

ቢሮው የተለመደ ዓይነት ሆኖ አገኘው። ግና ከውበቱና ከማራኪነቱ ጋር ቀለል ያለ ነው። አካባቢው በሕንድ የዑድ ሽቶ መዓዛ ተሞልቷል። የሙጢዕ ቢሮ የት እንደሆነ እንግዳ ተቀባይ ሠራተኛውን ሲጠይቅ ፦

- ሸይኽ ሙጢዕ፣በቀኝ በኩል ነው። በቀኝ በኩል የመጨረሻው በር ላይ የጸሐፊውን ቢሮ ታገኛለህ፣አለው።

ሸይኽ ሙጢዕ፣ሸይኽ ! ምን ማለት ይሆን ? ! ብሎ በመገረም ራሱን እየጠየቀ ወደፊት ቀጠለ። ኮምፒዩተር ላይ ይሰራ ለነበረው ጸሐፊ ሰላምታ አቅርቦለት ራሱን አስተዋወቀና ቢዝነስ ካርዱን ሰጠው። ከሙጢዕ ጋር ቀጠሮ እንዳለውም ነገረው።

- ይግቡ፣ሸይኹ ከአምስት ደቂቃ ጀምሮ እርስዎን እየጠበቁ ነው።

ጆርጅ ሰዓቱን ሲመለከት በእርግጥም ከሁለት ተኩል አምስት ደቂቃ አልፏል። ጆርጅ ከትልቅነቱ ጋር ዝብርቅርቅ መስሎ ወደሚታየው ቢሮ ሲገባ መጢዕ ብድግ ብሎ ተቀበለው። ስለ ትሕትናው አመስግኖ የሥራ ጉዳዩን ወደ መነጋገር ገቡ።

- መመስረት የምንችለው የትብብርና የአጋርነት አድማስ እስከ ምን ድረስ ሊሆን እንደሚችል ብታብራራልኝ?
- በቀላሉ ለኔና ለናንተም ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል በማንኛውም ነገር ሊሆን ይችላል።

ጆርጅ በዚህ ቀለል ያለ ግን ጥልቀት ባለው አነጋገር ተደስቶ ሙጢዕን ጨበጠው። እየሳቀም ቀጠለ ፦

- ተስማምተናል . . ይህ በታሪክ እጅግ ፈጣኑ ስምምነት ነው። ይሁንና ሁላችንንም የሚያረካ መንገድ የቱ እንደሆነ ማወቅ ይገባናል።
- እነዚህን ዝርዝር ጉዳዮች ወንድሜ ከሪሙ‐ሏህ ከኔ ይበልጥ የሚያውቃቸውና የተሻለ የሚገነዘባቸው ስለሚመስለኝ፣ከርሱ ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። ለጊዜው እርሱ ስለሌለ ነገ ጧት ሦስት ሰዓት ተገናኙና የውል ስምምነት

ዝርዝሩን አብራችሁ አዘጋጁ . .

- ደልሂንና አካባቢውን ጎብኝተሃል? ካልሆነ አንደ እንግድነትህ የማስተናገድ ግዴታ ስላለብን የጉብኝት ፕሮግራም አመቻችልሃለሁ።
- ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል አጭር ጉብኝት አድርጌያለሁ።
- አይ፣ምንም አላየህም ማለት ነው፤ሕንድ በጣም ሰፊ ታሪክ ያላት ጥንታዊት አገር ነች . . እንድናስተናግድህ ትፈቅድልናለህ?
- በጣም ደስ እያለኝ።
- መልካም እንግዳውስ ተዘጋጅ፣በአላህ ላይ ተወከል።
- ወዴት ነው?
- የጉብኝት ጉዞ ነው፣በታጅ መሐል እንጀምራለን።

ጆርጅ ከሙጢዕ ጋር ከግል ሾፌሩ ጋር ወደሚጠብቃቸው የሙጢዕ ባለምቾት መኪና አመሩ። ሙጢዕ ከኋላ ከጆርጅ ጋር ተቀመጠ።

- ወደ ታጅ መሐል የሚወስደው መንገድ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል የሚፈጅ ሲሆን በዚህ ጊዜ የትራፊክ መጨናነቅ የለበትም። መንዱ በራሱ አንድ ሽርሽር ነው፣ታጅ መሐል ደግሞ ከዓለማችን ድንቅ የኪነ ሕንጻ ጥበብ ቅርሶች አንዱ ነው። ራስህ ስለምታየው በኔ ገለጻ አላበላሽብህም።
- ማነው የገነባው?
- ንጉሥ ሻህ ጅሃን ነው። በአገረ ሕንድ የእስላማዊ ኪነ ሕንጻ ድንቅ ሞዴል ነው።
- እስላማዊ? !
- አዎ።
- ይቅርታ፣ግና ሙስሊሞች የሕንድ መሬት በጉልበት የነጠቁ፣ አጥፊ አረመኔ ሕዝቦች አይደሉም እንዴ? !

ሙጢዕ ፈገግ አለ . .

- አዎ . . ሕንድን ሰርቀናታል፣ሕዝቡንም ገድለናል፣ሀብቷንም ዘርፈናል !
- ኦ ይቅርታ፣አንተ ሙስሊም ነህ?
- አዎ ነኝ፣የምታውቅ መስሎኛል።
- ለጥያቄዬ ይቅርታ አድርግልኝ፣ስለሙስሊሞች የምንሰማው ግን ይኸው ነው።
- ምንም አይደለም፣እኔም ሆንኩ የተቀሩት ሙስሊሞች ሀብቷን ለመዝረፍ ከውጭ የመጣን ሰዎች አይደለንም . . እኔ ከነዘር ምንዛሬ ሕንዳዊ የሕንድ ልጅ ነኝ። ሕንድን ማን እንደሰረቃት ለማወቅ ከፈለግህ ወደ ታጅ መሐል ስትደርስ የሕንጻውን የከበሩ እንቁዎች ቆራርጦ የወሰደው ማን እንደሆነ

ጠይቅ::

- ማነው?
- ስንደርስ የቱሪስት አስጎብኚውን ጠይቀው . . የምትሰማው መልስ እንደማያሸማቅቅህ ተስፋ አድርጋለሁ:: በሙስሊሞች ላይ የሚወራውን ቅጥፈት ሁሉ ስለማውቀው ምላሽ ለመስጠት ግድ የለኝም:: በሕንድ ታሪክ ላይ አጭር ንባብ ማድረግ ብቻ፣ ማለት የፈለኩትን ነገር ግልጽ የሚያደርግ ይመስለኛል::
- እንዴት?
- ኢንተርኔት ላይ በየትኛውም ሰርች ኢንጂን ‹‹የሕንድ ታሪክ›› ብለህ በመጻፍ ሕንድን ማን ወሮ እንደያዛትና ማን እንደ ሰረቃት፣ሙስሊሞች የአገሪቱ ነባር ወይም መጤ ሕዝብ መሆን አለመሆናቸውን ማወቅ ትችላለህ:: በሙስሊሞች አገዛዝ ስር ሌሎች መደቦች እንዴት እንደኖሩም ግንዛቤ ታገኛለህ . . እየሳቀ ቀጠለና ፦ በእርግጥ ብዙ የተሳሳቱ ነገሮችም ነበሩ፣ከነዚህ ውስጥ አሁን የምንሄድበት ታጅ መሐል የታነጸው ለንጉስ ሻህ ጂሃን ሚስት መካነ መቃብርነት መሆኑ አንዱ ነው::
- በጣም ቀለል ባለ መንገድ ነው የምትናገረው !
- ሕይወትን ቀለል ባለ መንገድ ማየት አንዱ የደስተኝነትና የእርካታ ምልክት ነው::

ጆርጅ በጉዞው በጣም ተደስቷል:: የከበሩ ዕንቁዎች የቅርስ ስርቆት በሕንጻው ላይ የተፈጸመው በእንግሊዞች የቅኝ አገዛዝ ዘመን መሆኑን ሲያውቅ መደንገጡ ባይቀርም ሙጢዕ የእንግዳውን ስሜት መጉዳት ባለመፈለጉ ሊነግረው አልፈገም ነበር:: ጆርጅ በሙጢዕ ፈገግታና በቅን ልቦናው እጅግ የተማረከ ቢሆንም ያስተዋለበት አንድ ነገር ግን ብዙም አልተዋጠለትም:: በዚህ ጉዞ ላይ ሙጢዕ ሦስት ጊዜ ‹‹ጠብቀኝ ሰግጄ እመለሳለሁ›› እያለው ትቶት ሄዷል:: ለሥርዓት አለመጨነቅና ነገሮችን እንደመጡ የማስኬድ ባህሪም በሁሉም ነገሩ ውስጥ ጎልተው ይታያሉ::

የሙጢዕ የጉብኝት ፕሮግራም አብቅቶ ጆርጅ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ወደ ሆቴሉ ደረሰ:: በጣም ደክሞት ነበርና ሙቅ ሻወር ወስዶ ወደ መኝታው ሄደ:: አልጋው ላይ እንደ ተዘረጋ ከሙጢዕ ጋር የሚደረገው ስምምነት ምን መልክ መያዝ እንዳለበት ማይክልን የማማካር ሀሳብ መጣለት::

- ሃሎ . . ደህና አመሸህ . . ትንሽ ነገር ላማክርህ ነው:: ሙጢዕ ለስምምነት በጣም ገር ይመስላል:: የማታለያ ገርነት ይሆን?
- ሙጢዕ ለኔ የሚመቸኝ ባይሆንም ሐቀኝነት ያለው እውነተኛ ሰው

ይመስለኛል:: በሥራዎቹ ላይ ቅንጅት ያንሰዋል፣ራሱን በሥርዓት ቢያቀናጅ የተሻለ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ የሚችል ሰው ነው::

- ካኽ ግን ውስብስብና አስቸጋሪ ሰው ነው ይለኝ ነበር:: ሆኖ ያገኘሁት ግን ተቃራኒውን ነው::
- አዎ፣በሃይማኖቱ ውስብስብ ነው:: በበይነ ሰባዊ ግንኙነቱና በሥራ ግንኙነቶች ላይ ገር፣ቀለል የሚያደርግና የሚመች ሰው ነው:: ሳቀና ቀጠለ ፦ በሥጋዊ ፍላጎቶቹና በኮረዶቹ ለካኽ ታዛዥ ባለመሆኑ ውስብስብ ነው:: ለዚህ ነው ብዙ ረዣዥም ስብሰባዎች አብረው ቢቀመጡም ካኽ ከርሱ ጋር መስማማት የተሳነው:: እንደኔ ሃይማኖተኛ የሆነ ሰው ቆነጃጅት ኮረዶችን ለካኽ የሚያቀርብበትን ምክንያት አሁን የተረዳህ ይመስለኛል !
- ነገ ከርሱ ጋር ውሉን ለመፈራረም ስለምሄድ የምትሰጠኝ የተለየ ምክር ይኖራል?
- ፈጽሞ . . ምንም ነገር የለም:: መንፈስ ቅዱስ ይጠብቅህ:: ነገ እንዳደርስህ ወይም ለጉብኝት እንድወስድህ ትፈልጋለህ?
- አመሰግናለሁ . . የሚያስፈልገኝ ነገር ካለ እደውልልሃለሁ::
- በቸር ያገናኘን::

(5)

ጧት በሆቴሉ ምግብ ቤት ውስጥ ቁርሱን በመብላት ላይ እያለ፣የተሰባበረ እንግሊዝኛ ከሚነገረው አስተናጋጅ ጋር ምልልስ አካሄደ ፦

- ስምህ ማነው?
- ካቡር::
- ሕንድ የብዙ ሃይማኖቶች አገር ነች ይባላል፣ሃይማኖትህ ምንድነው?
- ሕንዱ ነኝ::
- ግሩም፣ሞራላዊ ሃይማኖት ነው::
- ልክ ነው፣ እንደዚያ ነው::
- በሃይማኖቱ መሪዎች ዘንድ፣ሕንድ ውስጥ ለሚገኝ ሰው እንጂ ለሌላው ሃይማኖቱን መከተል ትክክለኛ አለመሆኑና በዚህ ምክንያት ህንዱ ተብሎ መሰየሙ እውነት ነው?
- አዎ፣እውነት ነው፣ለሕንድ ነዋሪዎች እንዲስማማ አድርገን ነው ይህን ሃይማኖት የሰራነው::
- ሃይማኖት ሰራችሁ !!
- አዎ፣ለኛ እንዲስማማ አድርገን ሰራነው !

www.path-2-happiness.com

- የምታመልኩት አምላካችሁ ማነው?
- እኛ በዓለም ላይ ካሉት እምነቶች ሁሉ በአማልክት ብዛት የበለጸግን ነን !! ቁጥራቸው እጅግ በጣም የበዙ አማልክት አሉን:: ስሞቻቸውን ዘርዝረን ለማስፈር ምናልባት ብዙ ጥራዝ መዛግብት ሊያስፈልግ ይችላል:: ‹‹የስልጣኔ ትረካ›› መጽሐፍ ደራሲ ዎል ዲዮራንት እንዳለው ሁሉ እነኚህን አማልክት ለመመዝገብ የሚያስፈልገው ምናልባት እስከ አንድ መቶ ጥራዝ ይደርሳል::
- በጣም የሚያስደንቅ ነው !
- እንደ ጸሐይ ያሉ ጠፈራዊ አካላትን አማልክት አድርገን እናመልክባቸዋለን:: አንዳንዶቹን አማልክት በመላእክት ባሕርያት አንዳንዶቹን ደግሞ በሰይጣናት ባሕርያት እንገልጻቸዋለን::
- ለሰይጣን ይበልጥ የቀረበ አምላክ !
- አንዳንድ ጠልሰሞች አማልክት ናቸው፤አንዳንድ አእዋፍም አማልክት ናቸው፤አንዳንድ እንስሳትም እንዲሁ አማልክት ናቸው::
- እንስሳ አምላክ !
- ዝሆን ለምሳሌ የሰው ልጅ እንስሳዊ ባህሪ መገለጫ የሆነው ‹‹ጃኒሻ›› አምላክ ነው:: አንድ ጊዜ በመንደፍ ጋዳይ የሆነው እባብም ‹‹ናጃ›› አምላክ ነው:: ለእባቦቹ ወተትና ለውዝ እናቀርብላቸዋለን፤የአምልኮት በዓላትም እናዘጋጅላቸዋለን::
- ለነዚህ ሁሉ አማልክት እንዴት ነው አምልኮት የምታከናውኑት?
- በአማልክቱ ቁጥር ብዛት የተነሳ በሦስት ወይም ሦስት በህርያት ባሉት አንድ አምላክ ውስጥ እናጠቃልላቸዋለን::
- አንድም ሶስትም የሆነ . . ልክ እንደ ክርስትና !
- ሃይማኖታችን በኛው በራሳችን እጅ የሚሻሻል ስለሆነ፣ ምናልባት ይህን ከክርስትና ወስድነው ይሆናል:: ምናልባትም እናንተ ከኛ ወስዳችሁ ይሆናል::
- እህህ፣ቀጥልበትና አሟላው . .
- ለማንኛውም ሦስቱ አማልክት፣ወይም ሦስት በአንድ ወይም ሦስት አምላክ ፦ ፈጣሪ የሆነው ‹‹በራህማ››፣ዓለምን የሚጠብቀው ‹‹ቢሽኖ›› እና የውድመትና የጥፋትና አምላክ የሆነው ‹‹ሺቫ›› ናቸው::
- በድንቃድንቅ የተሞላ አስደናቂ ሃይማኖት ! ነገር ግን ስለ ላም ምንም አላልክም? ! . . ችሁ የምታደርጉ መሆኑን ሰምቻለሁ::
- አሃ፣ጋንዲ እንዳለው ሁሉ ላም አምላካችን ናት፣ከእናቶቻችን ይበልጥ

እንወዳታለን፣እለሃለሁ:: እናቴ አንድ ወይም ሁለት ዓመት ጡት አጥብታኝ ዕድሜ ልኬን አገለግላታለሁ:: ላም ግን እድሜ ልኬን ወተት አጠጥታኝ ከኔ የምትፈልገው መኖዋን ብቻ ነው:: እናቴ ስትሞት የቀብር ስነ ስርዓት ወጭ የምታስወጣኝ ሲሆን፣ላም ስትሞት ግን አጥንቷ እንኳ ሳይቀር ከሁለመናዋ ጥቅም እናገኛለን::
- ይህ የላም አምልኳችሁ ከሞት በኋላ ወደ ገነት ያደርሳችኋል ማለት ነው?
- እኛ ዘንድ ገነትም ሆነ ገሀነም የለም::
- ታዲያ በጎ ሰሪ የሚሸለመውና ክፉ ሠሪ የሚቀጣው እንዴት ነው? ወይስ ሁለቱም እኩልና ተመሳሳይ ናቸው?
- ጥሩ የሰራው ከሞተ በኋላ መንፈሱ ወደ ጥሩ ሰው በመዘዋወር ይሸለማል:: ከዚያም ከመነሻ ጉዞው ከበራህማ አምላክ ጋር ሊዋሐድም ይችላል:: ክፉ የሰራው ሰው ደግሞ ተኮንኖ መንፈሱ ወደ ተኮነነ ክፉ ሰው ይዘዋወራል::
- በዚህ ዓለም ላይ በደጉና በክፉ ሰው መካከል ልዩነት ታደርጋላችሁ?
- አዎ፣አንዳንዶቻችን ከአምላክነት ደረጃ የተወሰነ ድርሻ ይኖረዋል::
- እንዴት?
- ፈጣሪው ‹‹በራህማ›› እያንዳንዱን መደብ ከአካል ክፍሉ ውስጥ ከአንዱ ነው የፈጠረው:: በራህማዎችን ከፊቱ ነው የፈጠራቸው:: ስለዚህም የፍካሬና የጥበብ ሰዎች ናቸው:: ከሽተሪዎችን ከክንዱ ነው የፈጠራቸው፣ስለዚህም የኃይል፣ የማጥቃት፣የጥበቃና የውትድርና ሰዎች ናቸው:: ዌሽን ደግሞ ከጭኑ ነው የፈጠራቸው፣በመሆኑም የሚሰማሩት በንግድ፣ በእንዱስትሪና በምግብ ዋስትና ላይ ነው:: ሾደርን ከሁለቱ ጫማዎቹ ነው የፈጠራቸው፣ስለሆነም አገልጋዮችና ባሮች ሲሆኑ ማገልገል ግዴታቸው ነው፤አምልኳቸውም የመጀመሪያዎቹን ሦስት መደቦች ማገልገል ነው:: ካስቶችን በተመለከተ ግን በነዚህ አራቱ መደቦች ውስጥ አይገቡም፤ በሕንዱ ስብጥር ውስጥም አይካተቱም::
- ሾደር ብሆን ወደ በራህማዎች መደብ ከፍ ማለት እችላለሁ? ከካስቶች ወገን ብሆንስ ወደ ሕንዱ ሃይማኖት መግባት እችላለሁ?
- ፈጽሞ አይቻልም . . የሾደር ሃይማኖትና አምልኮ ሌሎቹን መደቦች ማገልገል ነው፤ካስቶች ደግሞ ሙሉ በሙሉ ከኛ ስብጥር ውጭ ናቸው:: ከመገረም ብዛት የጆርጅ ምላስ ተሳሰረ:: ውስጡ ይህን እኩይ እምነት

ክፉኛ ተጠየፈው፤ይሁን እንጂ ለማስመሰል ያህል ፈገግ አለና ጥቂት ገንዘብ ሰጥቶት ካቡርን አሰናበተው:: ከከሪሙሏህ ጋር ካለው ቀጠሮ እንዳይዘገይ ተቻኩሎ ሄደ::

www.path-2-happiness.com

- በመጓዝ ላይ እያለ የምድራዊ ሃይማኖቶችን አስከፊነት በመጥቀስ ማይክል ከጂዮስቲና ጋር የበለጠ ጊዜ አሳልፎ ቢሆን ኖሮ ሕንድን ይጠላ እንደነበርና ሁለተኛም ወደዚህ እንደማይመለስ የነገረውን አስታወሰ:: በእርግጥም እነዚህ ሃይማኖቶች ከሰብአዊ አእምሮና ከተፈጥሮ ጋር ያላቸው ተቃርኖ የትየሌለ ነው:: ለመሆኑ ይህ የምድራዊ ሃማኖቶች አስከፊ ገጽታ ብቻ ነው? ወይስ ሐኪሙ ቶም ‹‹ሃማኖት የሚባለውን ሁሉ የጠላህ ሆነህ ነው የምትመለሰው›› እንዳለው የሁሉም ሃይማኖቶች የወል መገለጫ ነው? የሃይማኖተኛው ማይክል ባህሪም ያው የካኽ ባህሪ ነው፣ሙጢዕም ቢሆን በሥርዓተ አልበኝነት ጎኑ ከሁለቱ የተሻለ አይደለም ! እውነተኛ ሃይማኖት ከሰው አእምሮ፣ከተፈጥሮም ሆነ ከሎጂክ ጋር ፈጽሞ መቃረን እንደማይችል እርግጠኛ ነው:: ይሁንና እንዲህ ያለ ሃይማኖት አለ ወይስ የለም . . ?

(6)

- ጆርጅ ልክ ሦስት ሰዓት ላይ ወደ ሙጢዕ ጸሐፊ ቢሮ ደረሰ:: ከከሪሙሏህ ጋር ለመገናኘት እንደሚፈልግ ሲነግረው በሸይኹ ቢሮ ውስጥ እየጠበቀው መሆኑን ነገረው:: ሲገባ ሁለቱ ወንድማማቾች ሙጢዕና ከሪሙሏህ ሲነጋገሩ አገኛቸው:: ተነስተው ሰላምታ ተለዋውጠው ተቀበሉት:: ከሪሙሏህን ሲያይ ገጽታው ብዙ ደስ አላሰኘውም:: ለምን የመሸማቀቅ ስሜት እንደተሰማው ግን አላወቀም !
- ወደኔ ቢሮ እንሄድ፣ውሉን ለመጻፍ ተዘጋጅቻለሁ::
  ሙጢዕ አቋረጣቸውና ፦
- ከጨረሳችሁ በኋላ፣ጆርጅ ከመሄድህ በፊት ላገኝህ እፈልጋለሁ::
- እኔም ሳልሰናበትህ መሄድ አልፈልግም::
  ጆርጅ ከከሪም ጋር ወደ ቢሮው አመራ:: ሰፋ ያለና ቀለል ያለ ቢሮ ነበር::
- ለሁለቱ ወገኖች ጥቅም በሚሰጥ ማንኛውም ውል ላይ እንደምንስማማ ወንድሜ ነግሮሃል::
- አዎ ልክ ነው . . ግን አንተ የሆነ ሰው ትመስላለህ . . !
- ኡሳማ ብን ላዲንን ነው የምመስለው ! አሀሃ፣አንተ እንዲህ ያለኝ የመጀመሪያው ሰው አይደለህም::
- እንደሱ እንደማትሆን ተስፋ አደርጋለሁ::
- እኔም እንደሱ ሙስሊም ነኝ:: እርሱ ዐረብ እኔ ሕንዳዊ በመሆኔ ከርሱ እለያለሁ::

- ማለቴ እንደርሱ ገዳይ አሸባሪ አይደለህም ማለቴ ነው::
- ይህን ርእስ ወዲያ በለው፣እናንተን ስለማያስደስትና ከናንተ ጋር ስለማይስማማ ነው አሸባሪ የሆነው::
- እንዴት ? እርሱና ተከታዮቹ አይደሉም ወይ የኛን ባቡሮች ሕንጻዎችና ተቋማት የሚያፈነዱት? !
- አንዳንዶቹ መሪዎቻችሁ እብን ላዲን የገደላቸውን በብዙ እጥፍ የሚበልጡ ሰዎችን ገድለዋል፣ግን አሸባሪዎች አድርጋችሁ አትስዷቸውም:: ምዕራባውያን በወረራ በያዟቸው አገሮች ውስጥ ከዚህ በሺ እጥፍ የሚበልጥ ሕዝብ ፈጅተዋል፣አሸባሪዎች ሲባሉ ግን ሰምተን አናውቅም:: ከዚያም ፈገግ አለና ፦ ጠላታችሁን ሩሲያን ይዋጋ በነበረበት ጊዜ ጀግና እንጂ አሸባሪ አልተባለም ነበር . . መልካም ፈቃድህ ሆኖ ይህን ተወንና ወደ ሥራችን እንግባ::

ጆርጅ በርሱና በከሪሙሏህ መካከል ክፍተት እየጨመረ መሆኑ ተሰማውና ከሥራው ውጭ ሌላ ምልልስ ውስጥ ላለመግባት ወሰነ:: ማድረግ ያለበት ሥራውን በተቻለ መጠን በፍጥነት ማጠናቀቅ መሆኑን እያሰላሰለ፣ቶም እንዳለው ሁሉ እነዚህ ሙስሊሞች በታሪክ ትልቁ አሸባሪ ለሆነው ግለሰብ ይሟገታሉ ልበል ! ሲል ከራሱ ጋር ይነጋገር ነበር::

- መልካም፣ይህ የኛ ርእሰ ጉዳይ አይደለም::
- ያዘጋጀህ የስምምነት ረቂቅ አለህ፣ወይስ የኛን ረቂቅ ልስጥህ ?
- ረቂቅ አለኝ፣ግን ያንተን ረቂቅ ስጠኝና ላንብበው::
- ይኸው እንካ::
- አመሰግናለሁ . . እንዳነበው ጥቂት ደቂቃዎች ስጠኝ::
- ጆርጅ ረቂቁን ማንበብ ጀመረ:: አንቀጾቹ ገርና ቀለል ያሉ መሆናቸውንና በራሱ ረቂቅ ውስጥ ለፍቶባቸው ከጻፈው የተሻሉ ሆነው አገኛቸው:: ሆኖም ግን ረቂቁ ለኩባንያቸው ሰፊ ነጻነት ይሰጣል:: የሆነ መጽሐፍ በማንበብ ተጠምዶ ወደነበረው ከሪሙሏህ ፊቱን አዞረና ፦
- ተስማሚና ባጣም ግሩም ሆኖ ነው ያገኘሁት፣ግን አነስተኛ ማሳሰቢያ ግን አለኝ::
- በል አቅርበው፣ምን ይሆን ?
- ለናንተ ኩባንያ ትልቅ ነጻነት የሚሰጥና ለኛ የሚከፈለውን ገንዘብ የሚያዘገይብን አይመስልህም ?
- ሁለት ነጥቦች ናቸው ማለት ነው:: ነጻነትን በተመለከተ ማሰራጨቱን በስፋት ማካሄድ እንዲያስችለኝ ነው፤ በተጨማሪም እያዘንኩኝ አኛ

www.path-2-happiness.com

በከፍተኛ ደረጃ የተደራጀን አይደለንም፡፡ የገንዘብ ክፍያ የመዘግየቱ ነገር ደግሞ ከናንተ ጋር ከተስማማን በኋላ መዋሸት ስለማንፈልግ ነው፡፡

- መዋሸት አትፈልግም፣እንዴት ?
- ቃል ገብቼ ቃሌን ማፍረስ ነው፡፡ ነጻ ባልሆን በሀሰተኛና ተራ ምክንያቶች ባለመከፈሉ በተደጋጋሚ ይቅርታ ለመጠየቅ እገደዳለሁ፣ይህ ደግሞ እኔም እናንተም የማንፈልገው ነገር ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ መስፈርቶች የናንተን የሽያጭ መጠን ከፍ ስለሚያደርጉ የበለጠ ተጠቃሚ ትሆናላችሁ፡፡ ለክፍያው የተሟላ የባንክ ዋስትና ውሉ ውስጥ ተካቷል፡፡
- ክፍያው በየሦስት ወሩ እንዲፈጸም በማድረጉ ላይ መስማማት እንችላለን?
- ተስማምተናል፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ካኽ ወደኛ እንዳይመጣ ካንተ ጋር ገር መሆን እፈልጋለሁ፡፡
- ካኽን ለምንድነው የማትፈልገው ?
- ይቅርታ አድርግልኝ፣አንተን ላለማስከፋት ስል መልስ አልሰጥህም፡፡
- ፈጽሞ አታስከፋኝም፣ለምን እንደሆነ ንገረኝ ?
- እኛንና አሱንም ለኪሳራ በሚዳርግ ያልተገራ አቀራረብ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ብቻ የሚያስብ ሰው ነው፡፡ የኔ እምነት በመርህ መመራት ሁሉንም ወገን ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም እኛ ልንቀበለው የማንችል ወሲብ ነክ ቃላትን ብዙ ጊዜ ይደጋግማል፡፡ ይቅርታ አድርግልኝና እኛ የምስራቅ ሕዝቦች ወግ አጥባቂዎች ነን፡፡
- ምንም አይደለም፣ከተናገርከው ውስጥ እኔም በብዙው እስማማለሁ፣በውሉ ተስማምቻለሁ፡፡ ውሉ እዚህ ባለው የእንግሊዝ ኤምባሲ ይረጋገጥና ወደ ለንደን ስመለስ እዚያ በሚገኘው የሕንድ ኤምባሲ እንዲረጋገጥ አደርጋለሁ፡፡
- አመሰግናለሁ፣ስለ አለቃህ በተናገርኩት ይቅርታ አድርግልኝ፡፡
- ምንም አይደለም፣ከመሄዴ በፊት ሙጢዕን ሰላም ማለት እፈልጋለሁ
- በል እንሂድ፡፡

ጆርጅና ከሪሙኋህ ወደ ሙጢዕ አርረሕማን ቢሮ ሲገቡ ለጆርጅ የተለየ ሞቅ ያለ አቀባበል አድርጎለት ጥያቄ አቀረበለት ፦

- ውሉን አጠናቀቃችሁ ?
- አዎ፡፡
- እንዳልኩህ ገር ቀላልና ያልተንዛዛ ነበር ?
- በጣም ገርና ቀለል ያለ ነው፡፡
- ገርና ቀለል ያለ ነገር ሁሉ ስኬታማ ነው፡፡ የተወሳሰበና የተንዛዛ ነገር ሁሉ የሰውን አእምሮ ተፈጥሮንና ሃይማኖትን ይቃረናል . . ቀጠለና ፦

ካጠናቀቃችሁ ዘንዳ፣ጆርጅ ከሕንድ ማየት የምትፈልገውና የምንወስድህ ቦታ አለ ? መቼም የድንቃድንቅ አገር በሆነችው ሕንድ ቱሪዝም ማራኪ ነው፡፡

- አመሰግናለሁ . . ዛሬ በጊዜ ወደ ሆቴል መመለስ እፈልጋለሁ፣ኢንተርኔት ላይ ማከናወን ያለብኝ ብዙ ሥራ ይተብቀኛል፡፡
- እንግዲያውስ እንደ ፍላጎትህ ይሁን፣ አለና ከመሳቢያው ውስጥ ውድ የሆኑ ሁለት የሕንድ ዑድ ሽቶ እሽጎችን አወጣ፡፡ ይህ የኔ ስጦታ ነው፣ ብሎ በውብ ኪስ ውስጥ አደረጋቸው፡፡ ወደ ሆቴል ሊያደርስህ ሾፌሩ እየጠበቀህ ነው አለው፡፡
- የትም የማይገኝ ምስራቃዊ መስተንግዶ ነው፡፡ እጅግ በጣም አመሰግነሃለሁ አለና ኪሱን ተቀብሎ ተሰናብቷቸው ወጣ፡፡

(7)

ጆርጅ፣ መምጣቱን የሚጠባበቀውን ሾፌር አገኘ፡፡ መምጣቱን ሲያይ ወደርሱ አመራና ወደ መኪናው ይዞት በመሄድ በሩን ከፈተለት፡፡

- ጌታዬ ይግቡ፡፡
- አመሰግናለሁ፣ስምህ ማነው ?
- እስቲቨን፡፡
- ኦ፣የምዕራባውያን ስም !
- እኔ ክርስቲያን ነኝ፣ለዚህ ነው ስሜ የምዕራባውያን ስም የመሰለው፡፡
- ከመቼ ጀምሮ ነው ክርስትና ሕንድ ውስጥ የኖረው ?
- ለረዥም ዓመታት ነው፡፡
- ቅኝ አገዛዝና የክርስትና ሚሽናሪዎች በዚህ ውስጥ ሚና ነበራቸው ?
- ያለ ጥርጥር፣ባይሆን ኖሮማ ሙስሊሞች ሕንድን ባጥለቀለቁ ነበር፡፡
- ሙስሊሞች ! በሽብራቸው ሕንድን ያጥለቀልቁ ነበር ማለትህ ነው ?
- አይደለም፣አንተ የምድራዊ ሃይማኖቶችን ዝቅጠት አታውቅም፡፡ የዘቀጡ አስቂኝ ሃይማኖቶች ናቸው፡፡ ሚስዮናዊ ዘመቻዎች ባይኖሩ ኖሮ ሰዎች ሁሉ በገዛ ፈቃዳቸው ወደ እስላም በገቡ ነበር፡፡
- አንዳንዶቹን አውቅአቸዋለሁ፣መለኮታዊ ሃይማኖቶችም ከነሱ አይለዩም !
- ይገርማል ! ክርስቲያን ሆነህ እንዴት እንዲህ ትላለህ ? ይህማ የኤቲስቶች አነጋገር ነው !
- ኤቲዝም እርስበርሱ የሚቃረን በመሆኑ እጠለዋለሁ፣ይሁን እንጂ መለኮታዊ ሃይማኖቶችም ከምድራዊ ሃይማኖቶች ብዙ አይለዩም፡፡

www.path-2-happiness.com

- እኛ ክርስቲያኖች ግን የሰው ልጅ ከጥፋት እንዲድን ነው የምንፈልገው። በንጽሕና በሞራል ላይ እናተኩራለን። ስለዚህም በምንም ዓይነት ክርስትናን መተቸት አልቀበልም። ከአንድ ክርስቲያን በኩል ሲመጣ ቀርቶ፣ የግል ሾፌሩ ከመሆኔና አድርጎት የማያውቅ ከመሆኑም ጋር ከሙስሊሙ ከሙጢዕ አርረሕማንም ቢመጣ እንኳ ይህን አልቀበልም። ምናልባት ፕሮቴስታንት ስለሆንክ ይሆናል፣ያም ቢሆን አልቀበለውም !
- ክርስትናን መተቸት አላሰብኩም ! ክርስትያን ሆኜ እንዴት እተቸዋለሁ ! ማለት የፈለኩት በተግባራዊ አፈጻጸም ከምድራዊ ሃይማኖቶች ጋር ይመሳሰላል ነው። እውር መደናበሩም ካንዳንድ ምድራዊ ሃይማኖቶች መደናበር ጋር ይመሳሰላል።
- አልገባኝም !
- ርእሱን ብንቀይርና ቀሪውን መንገድ ስለ ሕንድ ታሪክ ብትነግረኝስ?
- ለመድረስ ብዙ መንገድ አልቀረንም፤በጥቅሉ ፓኪስታን ባንግላዴሽና ሕንድ አንድ አገር ነበሩ፣ፓኪስታን ከሕንድ ተገነጠለች።
- ለምንድነው የተለያዩት ?
- ሙስሊሞች ከሕንዱዎች በኩል ይደርስብናል ባሉት ጭቆና ሲሆን ሳያስተውሉት ከሕንድ እንዲገነጠሉ ተገፋፉ። ያ ባይሆን ኖሮ ሕንድ ዛሬ እስላማዊት አገር በሆነች ነበር።
- ከነሱ ወገን ሳትሆን አንተ ብዙ ጊዜ ለሙስሊሞች ትከራከራለህ ! . . እነሱ ዘንድ ስለምትሠራ ነው ወይስ ስለምትፈራቸው ነው?
- እህ፣ ምናልባት !

ድክመት . . !

www.path-2-happiness.com

5

ድክመት . . !

ድክመት . . !

(1)

ጆርጅ ወደ ሆቴሉ ሲደርስ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ነበር። ወደ ክፍሉ ገብቶ ቶሎ ሻወር ከወሰደና ልብሱን ከቀየረ በኋላ ለምሳ ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ለመሄድ ወሰነ። ከክፍሉ ሊወጣ ሲል ስልኩ ጮኸ። ካትሪና ነበረች . .

- ሃሎ . . የኔ ፍቅር እንዴት ነሽ።
- ጆርጅ እንደምነህ፣የድንቃድንቆቹ አገርስ እንዴት ናት?
- ግሩም ድንቅ ናት፣እኔ እዚህ በጣም ደስተኛ ነኝ። ሥራዬንም አሳክቻለሁ። ሁለት ቀናት ብቻ ናቸው የቀሩኝ፣ ይህችን ውብ ከተማ የበለጠ ለማወቅ እጠቀምባቸዋለሁ።
- በጣም ጥሩ፣የሐኪሙን ጥያቄዎችስ እንዴት አደረግህ?
- ኣህ፣ቶም ወደ ሃይማኖቶች ቀረብ ብለህ ስትመለከታቸው ሁሉንም ችላ ትላቸዋለህ ማለቱ፣አንዳንዴ እውነቱን ነው የሚል ስሜት ያድርብኛል። ቢሆንም ግን በተወሰነ ደረጃ ነገሮች ግልጽ መሆን የጀመሩ ይመስለኛል።
- ካቶሊክ ክርስትና ወደርሱ በቀረብክ ቁጥር የበለጠ ያስደስተሃል፣መንፈስ ቅዱስም ይረዳሃል።
- ይህን እንኳ ተይኝ፣አጥባቂ ክርስቲያኑ ማይክል ነው እንድረካባቸው ኮረዶችን የሚያቀርብልኝ። ማይክልም ካኽም ሁሉም ያው ናቸው፣ከእንግዲህ ማናቸውንም አላምንም።
- ያንድ ክፉ ምሳሌ መኖር ማለት መሰረታዊው እሳቤ ስህተት ነው ማለት አይደለም። እንዲያውም መሰረታዊው እሳቤ ስህተተኛ ላለመሆኑ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል። አንድ ክፉ ምሳሌ ቢገኝ በተቃራኒው በአስርቶች የሚቆጠሩ መልካም ምሳሌዎች ይገኛሉና !
- ልክ ነሽ፣ዋናው ነገር ልጆቻችን ማይክልና ሳሊ እንዴት ናቸው?
- በጣም ደህና ናቸው፣ሁላችንም በጣም ናፍቀህናል።
- እኔም እንደዚሁ በጣም ናፍቄያችኋለሁ።

በሆቴሉ ሬስቶራንት ምሳው ምርጥ ምርጡ በያይይነቱ የተትረፈረፈበት ክፍት ቡፌ ነበር። ሬስቶራንቱ ከተለያዩ አገሮች በመጡ ቱሪስቶች

www.path-2-happiness.com

ተጨናንቋል:: ጆርጅ ፈንጠር ብሎ በሚገኝ ጠረጴዛ ምሳውን ለመብላት ለብቻው በተቀመጠበት፣ዓይኑ ውብና ማራኪ በሆነች ሕንዳዊት ኮረዳ ላይ አረፈ:: ዕድሜዋ በሃያዎቹ መጀመሪያ አከባቢ ይመስላል:: ሐር የመሰለ ጥቅጥቅ ያለ ጥቁር ጸጉር፣የተኳሉ ዓይኖች፣ብርቱካን የመሰሉ ስርጉድ ጉንጮች፣ በፈገግታ የተሞላ ውብ ገጽታ . . በዓይኖቻቸው የሚያሳድዷትን ቱሪስቶች ትቃኝ ነበር:: አንድ ጊዜ ፈገግታ ትለዋወጣለች፣ሌላ ጊዜ ደግሞ በመሽኮርመም ፊት ትነሳቸዋለች::

በውበቷና በመሽኮርመሟ ለምን እንደተማረከ አላወቀም፣ በተደጋጋሚ እይታውን ተክሎባታል:: ከወጥመዷ ለመራቅ በምግቡና ኢንተርኔት ላይ በሚጠብቀው ሥራ ሃሳብ ለመጠመድ ወሰነ:: ግና ሳያስብ ያችን ውብ ኮረዳ ከጎኑ ቁጭ ብላ አገኛት . .

- ስሜ ኦርሜላ ነው፣ የዴልሂ ልጅ ነኝ:: የስሜ ትርጉም ፈታኟ ወይም ማራኪዋ ማለት ነው . . ለብቻህ ተቀምጠህ በዓይኖችህ ስትበላኝ ሳይ አሳዘንከኝ፣ብቸኝነትህን እንዳቃልልህ ትፈልጋለህ?

ጆርጅ ራሱን ቀና አድርጎ ተመለከታት:: በከፊል ራቆቷን ነች፣ ሆዷ ሙሉ በሙሉ ተገልጧል:: ገላዋን ምንም ያህል የማይሸፍን በጣም አጭር የሆነ ጉርድ ነው የለበሰችው:: ፊቷ ሙሉ ጨረቃ ነው፣ ጸጉሯ የሐር ነዶ:: ፈገግታዋ መብረቅ ነው:: ሌሎችን እምቢ ስትላቸው ወደርሱ ጠረጴዛ መጥታ ስትቀመጥ ለምን ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማው አያውቅም . .

- ስሜ ጆርጅ ነው፣ከእንግሊዝ አገር ነው የመጣሁት:: ለበጎ አስተያየትሽ አመሰግናለሁ:: ከዚያም ራሱን ለማሸነፍና ውስጣዊ ትግሉን ለመቋጨት በመፈለግ ዝም አለ:: አብሯት መቀመጥ ውስጡ ይመኛል፣መቀመጡ ግን ሌሎች ጉዳዮችን ማስከተሉ ግልጽ ነው . . አዝናለሁ፣የበዛ ሥራ አለብኝ፣ወደ ሕንድ ከደረስኩ ወዲህ ለብቻዬ ስቀመጥ ይኽ የመጀመሪያዬ ነው::
- ትሕትናህ፣አለባበስህና ገጽታህ ውብ ነው፣አብረን ብንደሰትስ ?
- አቀራረብሽም ውብ ነው፣አሁን ካንቺ ጋር በመነጋገር እየተደሰትኩ ነው፣ከአፍታ በኋላ ግን በሥራ መጠመዴ ነው::
- ይቅርታ . . በተፈጥሮህ ጅል ነገር ትመስላለህ፣እኔ ከኤድስ ነጻ መሆኔን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት አለኝ::

እጇን ዘርግታ እጁ ላይ አሳረፈችና ጠበቅ አድርጋ ያዘችው:: የኤሌክትሪክ ንዝረት ያህል እስከ ልቡ ድረስ ቢሰማውም፣ ልቡንና ስሜቱን አሸንፎ እጁን

ከእጇ በቀስታ አስለቀቀ::

- ገብቶኛል . . አመሰግናለሁ፣አመሰግናለሁ፣እኔ ባለትዳር ነኝ::
- ሚስትህ እዚህ ሕንድ ውስጥ ካንተ ጋር ነች ? !
- አይደለችም፣እንግሊዝ አገር ናት::
- ከአውሮፓና ከአሜሪካ የሚመጡ የተለያየ ሃይኖት ያላቸው ቱሪስቶች አብዛኞቹ ባለትዳሮች ናቸው:: ይሁን እንጂ ሁሉም እዚህ መደሰትና መዝናናትን ይወዳሉ . . ሕንዳዊ ውበት ከሌላው የተለየ ነው::
- አመሰግናለሁ . . አንቺ በእርግጥ ውብና ማራኪ ነሽ:: ግና አመሰግንሻለሁ::
- አንተተ ለየት የምትል ውስብስብ ሰው ነህ:: በሕይወቴ እንዳንተ ያለ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም:: ራሴን ለወንድ አቅርቤ እምቢ አልፈልግም ስባል ይህ የመጀመሪያዬ ነው::

ኦርሜላ ወዲያውኑ ተነስታ ሄደች:: ጆርጅ ለራሱ አጉረመረመ፣ የሚገርም ነው . . ሚስቱን የማይክድ ሰው፣ ለመርህ ተገዥ የሆነ ሰው ውስብስብ ነው፣እህህ ምናልባት . . ሕይወት በየቀኑ ትርጉማቸውን የማናውቃቸው፣ወይም በየራሳችን መንገድ የምንተረጉማቸው ድንቃድንቆችን ታሳየናለች:: ካኽ በኔ ቦታ ቢሆን ኖሮ የቆንጆዎች ቆንጆ ከሆነች ኮረዳ ጋር ምርጥ ሌሊት በማሳለፍ በተደሰተ ነበር ! !

(2)

- ጆርጅ ምሳውን አብቅቶ ሰዓቱን ሲመለከት በሕንድ አቆጣጠር አስር ሰዓት ተኩል ነው:: በለንደን አቆጣጠር ሲያሰላ ከጧቱ አምስት ሰዓት ነው:: ካትሪና ከአራት ሰዓት በፊት ማለትም ከጧቱ አንድ ሰዓት ላይ መደወሏን አስታወሰ:: እንዲህ አማልዶ ከእንቅልፍ መንቃት የካትሪና ልማድ አይደለም !
- ወደ ክፍሉ ሄደና የሚጠብቁትን ሥራዎች ለማጠናቀቅ፣ ኢሜሉንና የፌስቡክ ገጹን ለማየት . . ኮምፒውተሩን ከፈተ:: ከሁለቱ ኩባንያዎች ጋር ውሉ በተሳካ ሁኔታ መፈረሙን በማብሰር ለካኽ ኢሜል ላከ:: የተላኩለትን መልእክቶች አየት አየት ካደረገ በኋላ ከሦስት ቀናት ወዲህ ወዳላየው የፌስቡክ ገጹ ገብቶ በርካታ ቁጥር ያላቸው መጣጥፎች፣ምስሎችና ከወዳጆቹ የመጡ ሊንኮችን አገኘ:: ሐኪም ቶም ወዳጅነት ጠይቆት አገኘውና ከወዳጆች ዝርዝር ውስጥ ከጨመረው በኋላ ወደ ገጹ ሲሄድ አዳዲስ ፎቶግራፎችን የጨመረ መሆኑን ተመለከተ:: ሲከፍታቸው ያልተጠበቀ አስደንጋጭ

www.path-2-happiness.com

ምስል ተመለከተ:: ቶምና ካትሪና አብረው የሚታዩባቸው ፎቶግራፎች ! አብረው ሲመገቡና ሲሲቁ የሚያሳይ ከሥሩ ‹‹ከካትሪና ጋር›› የሚል የተጻፈበት አንደኛው ነበር:: ፌስቡክ ላይ መቼ እንደ ተደረገ ሲያስተውል በለንደን አቆጣጠር አስራ ሁለት ሰዓት ሆኖ አገኘው:: በአንዳንዶቹ ላይ 5፡25 ሰዓት የተጻፈባቸው ሲሆን ቀኑ ግን ያው 15/17 . . ነበር::

-ግራ ተጋባ:: ካትሪና የደወለችው ገና ከማለዳው ነበር፣እስከ አስራ አንድ ተኩል ድረስ ከቶም ጋር ነበረች፣እናም እስካሁን አልተኛችም ማለት ነው ! ደሙ ፈላና ለካትሪና ደወለ:: ስልኳ ዝግ ነው:: ለቶም ሲደውል በተዳከመ ድምጽ መለሰለት ፦

-ሃሎ ጆርጅ፣እንዴት ነህ ? ሁሉንም ሃይማኖቶች ችላ ማለት መጀመርህን ካትሪና ነገረችኝ !

-መቼ ነገረችህ ? ! !

-ስትደውልልህ አብረን ነበርን:: ከዚያ በኋላ ወደ ቤት አደረስኳት፣ታድለሃል:: በጣም ድንቅ ሴት ነች::

-ምን ስታደርጉ ነበር ?

-በቤተክርስቲያን የድግስ ሥርዓት ላይ ነበርን:: በሃይማኖተኞች ላይ ጥናት አካሄዳለሁ ብየህ የለ !

ጆርጅ የስልክ ጥሪውን አበቃና በዚህ ሀፍረተ የለሽ ቅሌት ተገርሞ አልጋው ላይ ተዘረጋ . . ሳያስብ ኮረዳዋን ኦርሜላን ሲፈልግ ራሱን እንግዳ መቀበያው ውስጥ አገኘ:: ሲያጣት የእንግዳ መቀበያ ሰራተኛውን ጠየቀ:: ፈገግ አለና ዛሬ ፈላጊዋ በጣም ብዙ ነው፣ከአፍታ በፊት ወደ ቻይናዊ ቱሪስት ክፍል ሄዳለች፣አለው::

ግንፍል ብሎ በግብዝነት ጠየቀው ፦

-ምን ያደርጋሉ ? !

-እህ፣ምን እንደሚያደርጉ እንዴት ልወቅ ?

ጆርጅ በጥያቄው ተመልሶ አፈረ፣በከፍተኛ ውጥረት ላይ መሆኑን ተገነዘበ:: የሚያደርገው ነገር ጠፋው . . ወደ ክፍሉ ተመልሶ ሄደ . . በዚህ አፍታ የሚታየው ነገር ከሃዲዋን ካትሪና በማንኛውም መንገድ ቢሆን መበቀል ብቻ ነው:: እነዚያን በሬስቶራንቱ ድግስ ላይ እምቢ ብሎ የተዋቸውን ሁለቱን ቆነጃጅት ኮረዶች እንዲያመጣለት ለማይክል ለመደወል ወሰነ:: እስኪ መርሆህ ይጥቀምህ፣እንደ ካኽ ወይም እንደ ቶም ለምን አትሆንም፣እነዚህ መርሆዎች ምን ጠቀሙህ . . ምንም . . ምንም . . አለችው፣ነፍሲያው ::

-ሃሎ . . ማይክል::

-ሃሎ ጆርጅ፣ በሰላም ነው ? በዚህ ጊዜ ደውለህ አታውቅም::

ጆርጅ ባንኖ ሰዓቱን ሲመለከት ገና አንድ ሰዓት ተኩል ነበር . .

-ኦህ፣ይቅርታ እንዲሁ ሰላም ለማለት አስቤ ነው . . በቃ ነገ እደውላለሁ፣ አመሰግናለሁ ማይክል::

-በመደወልህ አመሰግናለሁ፣ነገ እደውልልሃለሁ::

ጆርጅ እየተነጫነጨና በንዴት እያጉረመረመ፣ አንዳንድ ስድብና እርግማን ካፉ እያመለጡ ክፍሉ ውስጥ መንጎራደድ ቀጠለ:: የሚያደርገው ጠፍቶታል:: በሚስቱ ላይ ያደረበት ጥርጣሬና ግራ መጋባት ሰብእናውን ደካማ እንዲሆን አድርጓል . . ከኦርሜላ ጋር ሊበቀላት ቢፈልግም ሊያገኛት አልቻለም:: ከርሱ ያነሰ ግትርና እንዲቆጠብ በሚያደርጉት በነዚያ መርሆዎች ላይ ከርሱ ይበልጥ የሚለሳለስ ሌላ ግለሰብ አንደወሰዳት እርግጠኛ ሆኗል:: እርሱን ቀፍድዶ በመያዝ ሌሎች መጥተው በማራኪ ውበትና በደስታ እንዲዝናኑ በሚያደርገው አጉል የመርህ ተገዥነቱ ተበሳጨ::

-በዚህ አፍታ ውስጥ ካትሪና ቀደም ሲል ከቶም ጋር አምሽታ የነበረችበትን አስታውሶ ኢንተርኔት ላይ ገብቶ የቶምን ድረ ገጽ ከፈተና የቆዩ ፎቶገግራፎችን መፈለግ ያዘ:: የዚያን ምሽት ፎቶግራፍም ቶም ድረ ገጽ ላይ ተደርገው አገኛቸው:: ፎቶግራፎቹ ከሞላ ጎደል ከመጨረሻው የምሽት ድግስ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ ቦታውም ራሱ መሆኑንና ምናልባትም ቤተክርስቲያኑ መሆኑን የሚያመለክቱ ነበሩ:: እንዲህ ያለውን ጋጠ ወጥነት የምትፈቅድ ምን ዓይነቷ ቤተክርስቲያን ትሆን ? ስል ራሱን ጠየቀ ! !

የቀድሞውን ማምሸቷን በምን መልኩ ይዞት እንደነበረና በራድ የአደንዛዥ እጽ ሱሰኛ ሊያደርገው እንዴት እንደ ሞከረ ትዝ አለው:: ‹‹ለዋነኞቹ ጥያቄዎችህ እልባት ስታገኝ ችግሮችህን በተሻለ ሁኔታ መያዝ ትችላለህ፣መንፈስህም ጫናዎችን ለመቋቋም የበለጠ ጥንካሬ ያገኛል››:: ‹‹ጥርጣሬህን የወንጀሏ ማስረጃ አድርገህ አትውሰድ፣ ምናልባት ከቶም ጋር የሆነችው እሱን ወደ ክርስትና ለመጥራት ሊሆን ይችላል !››:: ‹‹ቅለትና ጥልቀት ባለው ስልት በዋነኛው ጉዳይህ ላይ አትኩር፤ ያን ስታደርግ ደስተኝነት ከውስጥህ ከራስህ መንፈስ ይመነጫል፣ ይህ ሲሆን ለችግሮችህ ሁሉ መፍትሔ ታገኛለህ››:: ‹‹በካትሪናና በቶም ላይ ከተለመደው የተለየ ነገር ላለማሳየት ሞክር፣በቅርብ ወደ ሕንድ መሳፈርህ ነውና ከጉዞው ስትመለስ የሚሆነው ይሆናል::

www.path-2-happiness.com

ነገሮችን የምትወስዳቸው ቀለል አድርገህ ሳታወሳስብ፣ በደስተኝነት መንፈስ እንጂ በትካዜ ላለመሆኑ እርግጠኛ ሁን::›› የሚሉትን የአደምን ምክሮች አስታወሰ:: ለመሆኑ ይኸ አደም ከካትሪና ገር ተስማምቷል ? ወይስ እንደሱ ሃይማኖተኛ ስለሆነች ለርሷ እየተሟገተ ነው ? በማለት ራሱን በራሱ ጠየቀ:: ይህ ሰው ከኔ የሸሸገው ምን እንደሆነ ለማወቅ እደውልለታለሁ ! !

- ሃሎ ማን ልበል ?
- ጆርጅ ነኝ፣ ከሕንድ ነው የምደውለው::
- ከምስራቅ የሚደውለው ምዕራባዊ ሰው ! እንደምን አለህ ?
- መጥፎ ሁኔታ ላይ ነው ያለሁት:: ካትሪና እስከ ዛሬ ጧት ድረስ ሌሊቱን ሙሉ ከቶም ጋር ነው ያመሸችው::
- እንዴት ማረጋገጥ ቻልክ ?
- ከራሱ ከቶም ነው ያረጋገጥኩት፣ፎቶግራፎቹን በፌስቡክ ገጹ ላይ አሰራጭቷል፣ለራስህ ገብተህ ማየት ትችላለህ::
- ታዲያ ምኑ ነው አዲስ ?ባለፈው ጊዜም ከርሱ ጋር ማምሸቷን አረጋግጠህ አልነበረም ?
- አዎ ግን . .
- ዋናው ነገር ምን ለማድረግ አስበሃል ? በጥርጣሬና በግራ መጋባት ወቅት ደካማ አትሁን:: ትኩረትህን በሥራህ ላይና የጉዞህ ዓላማ በሆነው በጥያቄዎችህ ምላሽ ፍለጋ ላይ ብቻ አድርግ::
- በማንኛውም መንገድ ቢሆን ካትሪናን መበቀል እፈልጋለሁ::
- በግራ መጋባትና በጥርጣሬ ላይ በምትሆንበት የድክመት ሁኔታ ውስጥ ማንም ሰው እንዲጫወትብህ አታድርግ ብየሃለሁ አስቀድሜ:: አሁንም ደጋግሜ የምልህ በድክመት ሁኔታ ላይ በምንገኝበት ወቅት መርሃችንን መጠበቅ ይሳነናል፣መርሃችንን አጥብቀን በያዝን ቁጥር ደግሞ ይበልጥ ጠንካሮች እንሆናለን::
- በአንድና ከዚያም በላይ በሆኑ የሕንድ ኮረዶች እደሰታለሁ፤ ልቤን እንዳነደደች ልቧን ለማንደድ ከኮረዶቹ ጋር ሆኜ ፎቶግራፎችን እልክላታለሁ::
- በዚህ ራስህን ነው የሚታቃጥለው፣በዚህ መንገድ መበቀል የደካሞች አድራጎት ነው:: ካትሪናን ከምትጎዳት ይበልጥ ራስህንና መርሆህን ነው የምትጎዳው:: ላይሆን ቢችልም ከቶም ጋር ክህደት ፈጸመች ብንል እንኳ ይበልጥ ተጎጂው አንተ ነህ ወይስ እሷ ?
- እኔ ነኝ::

- አይደለም እሷ ነች:: ራሷን መርሆዋን፣ሃይማኖቷንና ስሟን ያቃጠለችው እራሷ ናት:: እኔ አሁንም አንተ እንደ ጠረጠርካት አትሆንም የሚል እምነት ቢኖረኝም አንተ በምንም ነገር ተጎጂ አትሆንም::
- ለምንድነው የምትሟገትላት ? እንዳንተው ሃይማኖተኛ ስለሆነች ነው ?
- አንተ እንደምትለው ክህደት ፈጽማብህ ከሆነች መስላ ለመታየት ብትሞክር እንኳ ሃይማኖተኛ አትመስለኝም:: ክህደት ያልፈጸመችብህ ከሆነ ሌላ ነገር ነው:: እኔ በጭራሽ የማላውቃት እየሆንኩ ለምን ብዬ ነው የምሟገትላት ? ሃይማኖተኛ መሆኗንም አሁን ነው ካንተ የምሰማው:: የነገርከኝ የሚትጠጣና የሚታመሽ መሆኗን ብቻ ነበር:: ሃይማኖተኛ ነች አላልከኝም:: ደሞም በዚህ ምን ጥቅም አገኝበታለሁ ? በተጨማሪም የጠየከኝ አንተ እንጂ እኔ አልደወልኩም !
- አደም ይቅርታ አድርግልኝ፣በጣም ስለተረበሽኩ እንጂ አንተን ማስቆጣት ፈልጌ አይደለም:: ከኦርሜላ ጋር ካትሪናን መበቀል የወሰንኩት በጣም ስለጨነቀኝ ብቻ ነው::
- እኔን ለማስከፋት እንዳላሰብክ አውቃለሁ:: ዳሩ ግን ውጥረቶች ከመርሆዎቻችን ሊያዘናጉን አይገባም:: ኦርሜላ ደግሞ ማን ናት ?
- በጣም የሞማርክ ቁንጅና ያላትና ዛሬ ራሷን አቅርባልኝ እምቢ ያልኳት ኮረዳ ነች:: አሁን ላገኛት ምን ያህል እንደጓጓሁ ልነግርህ አልችልም::
- ለምንድነው እምቢ ያልካት ?
- ለሥጋዊ ፍላጎት፣ለጊዜያዊ ስሜት ወይም ለአላፊ ደስታ ብዬ መርሆዬን ማዋረድ ስላልፈለኩ . . ወይም ሞኝ ተላላ በመሆኔ !
- አሁን መርሆህን ለማራከስ ዝግጁ ነህ ማለት ነው ? !
- ምን ላድርግ ?
- ወደ መርሆህ ተመለስ:: ለታላላቆቹ ጥያቄዎችህ ምላሽ ፈልግ:: በደስተኝነት ጎዳና ተጓዝ:: ከግብህ ትደርሳለህ፣ ፈተናውንም ታልፋለህና !
- ከሁለት ቀናት በኋላ ወደ ለንደን ስለምመለስ ላገኝህ ይገባኛል::
- እኔም እጠብቀሃለሁ::

የሚያደርገውን ያጣው ጆርጅ ስልኩን እንደዘጋ ኮምፒውተሩን ከፈተ:: የአደምን የፌስቡክ ገጽ ከፍቶ የማየት ሀሳብ አደረበት:: በጣም የተለመደው ዓይነት ገጽ ነበር:: መጣትፎቹ በአንጻራዊነት ረዣዥሞች ናቸው:: እንዲህ ያሉ መጣጥፎችን ማንበብ በሚፈቅድለት የስነ ልቦና ሁኔታ ላይ ባይሆንም ‹‹ደስተኝነትን ፍለጋ ከሚኳትነው ወዳጄ የሚቀሰሙ ትምሕርቶች›› በሚል

ርእስ ሥር የተጻፈው መጣጥፍ ትኩረቱን ሳበው:: ከአራት ቀናት በፊት በአደም የተጻፈ ነበር . .

ደስተኝነትን ፍለጋ ከሚኳትነው ወዳጄ የሚቀሰሙ ትምሕርቶች ፦

በቅርቡ የደስተኝነትን መንገድ በጉጉት በመፈለግ ላይ ከሚገኝ መርህ ካለው ግለሰብ ጋር ተዋውቄያለሁ:: ፍለጋው ከልብ የመነጨ እውነተኛ ፍለጋ ነው የሚል እምነት አለኝ:: ያለበት ጫና ግን በጣም ከባድ ነው:: ከርሱና ከታሪኩ ትምሕርት ያገኘሁ በመሆኔ የሚከተሉትን ጠቃሚ ነጥቦች ከናንተ ጋር መጋራት ወደድኩ ፦

1. ደስተኝነትን የሚፈልግ ሰው ወደዚያ የሚያደርሰውን መንገድ ይዞ ለመጓዝ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል:: በገንዘብ፣ በሥልጣንም ሆነ በውርስ ወደዚያ መድረስ አይቻልም:: ደስተኝነትን ለማግኘትና ወደዚያ ለመድረስ ጽኑ ጥረትና የማያቋርጥ ፍለጋ ማድረግ የግድ ነው::
2. በሕይወቱ ውስጥ ለታላላቆቹ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የማይችል ሰው ደስተኛ መሆንም ሆነ ደስተኝነትን ማግኘት ፈጽሞ አይችልም:: ጥያቄዎቹ ፦ ማነው የፈጠረን ? ለምን ዓለማ ነው የተፈጠርነው? ለምንድነው የምንኖረው? መጨረሻችንስ ወዴት ነው? የሚሉ ናቸው:: ለነዚህ ጉዳዮች እልባት መስጠት ያልቻለ ሰው ፈጽሞ ደስተኝነትን መጎናጸፍ አይችልም::
3. አንዳንድ ሰዎች ወደ ደስተኝነት የሚያደርሰውን መንገድ ውስብስብነና አስቸጋሪ ያደርጉትና ተግዳድሮቶቹን ማለፍ አልቻልንም ይላሉ:: ነገሮችን ገርና ቀላል አድርገው ቢወስዱ በቀላሉ መድረስ በቻሉ ነበር::
4. አንዳንድ ሰዎች በመለስተኛ ችግሮችና በጥቃቅን የቅርብ ዓላማዎች ዋናኛ ዓላማቸውን ይዘናጋሉ:: ይህን ሲያደርጉ መሀል መንገድ ላይ ወድቀው ስለሚቀሩ በጭራሽ ወደ ደስተኝነት አይደርሱም::
5. በጉዞው ወቅት መርሆዎቻችንን መጣስ ተገቢም ትክክለኛም አይደለም:: መርሆዎች መሪ የብርሃን ማማዎች ስለሆኑ መጣስ የለባቸውም:: ረግጦ ሊያልፋቸው የሚሞክር ሰው የሚያፈርሰው የገዛ ራሱን ሲሆን እነሱ ግን ባሉበት ይኖራሉ::
6. በፍለጋው ላይ የተሰማራ ሰው ፍለጋው ከልብ የመነጨ እውነተኛ ፍለጋ እስከሆነ ድረስ፣ቁርጠኛና የማያቋርጥ ጥረት በትእግስትና በጽናት ካደረገ መንገዱን ብሩህ የሚያደርጉለት ነገሮች ገር ይሆኑለታል::

ትምህርቶቹ ብዙ ስለሆኑ በሚቀጥለው ጽሑፌ ምናልባት በቅርቡ ለማሟላት እሞክራለሁ::

ከአክብሮት ጋር ፡- አደም

(3)

- ጆርጅ የአደምን ጽሑፍ ካነበበ በኋላ ዘና ያለ ቢሆንም አደም ሳይነግረውና ስሙን እንኳ ሳይጠቅስ ስለርሱ ለምን እንደ ጻፈ ግራ በመጋባት ራሱን ጠየቀ:: አደም በጻፈውና ለኔ በነገረው መካከል ምንም ግጭት የለም:: ከኔ ጋር ግልጽና ቁርጠኛ ነበር:: ለተጎዳ ስሜቴና ላለሁበት የስነ ልቦና ሁኔታዬ ግን ግድ የለውም ! የሄሮዊን እንክብል ብወስድ ወይም ኦርሜላን ባገኝ ኖሮ ያለሁበትን ሁኔታ እረሳ ነበር፣መርሳት የደስተኝነት መንገድ ነው . . አወይ፣እውን እነዚህ ዘዴዎች ከራስ ወደፊት መሸሽ ናቸው ? ወይስ አጋጣሚዎችን የማያበላሹ አስተዋዮች የሚጠቀሙበት ትክክለኛ መፍትሔ ናቸው ? ግራ መጋባቴና መባዘኔ ምነው ከፋ !

የክፍሉ ስልክ አቀጨለና መነጋገሪያውን አነሳ:: የእንግዳ መቀበያ ሰራተኛው ነበር የኦርሜላን መምጣት ሊነግረው የደወለው . .

- ወደ ክፍልህ እንድትመጣ ትፈልጋለህ ?

ጆርጅ ምላሽ ጠፍቶት ለረዥም ጊዜ ጸጥ አለ . .

- አላውቅም !
- ማለት ?
- እኔ ራሴ መጣሁ::
- ከክፍሉ ወጥቶ ወደ እንግዳ መቀበያው ወረደ:: መውረዱ ካትሪናን ለመበቀል ነው ? ወይስ አደም እንደሚለው የገዛ ራሱን ለመበቀል ? ካኽና ቶምን ልታዘዛቸው ? ወይስ አደምን ልታዘዝ ? እያለ ከራሱ ጋር በመሟገት ላይ እያለ አሳንሰሩ እንግዳ መቀበያው ላይ ቆመ:: በሩን ከፍቶ ሲወጣ ኮረዳይቱ ኦርሜላ ከፊትለፊቱ ቆማለች . . አይታው በሰፊው አፈገገች፣ፊቷ ፈክቶ የፈነዳ ጽጌሬዳ መስላለች::
- ሰላም ኦርሜላ፣እዚያ መቀመጫ ላይ ብንቀመጥ ምን ይመስልሻል ?
- አህ፣ይቻላል::

እንደተቀመጠች በፈገግታ ቀደመችው . .

- የእንግዳ መቀበያው ሰውየ ስለኔ እንደጠየቅና እንደፈለከኝ ሲነግረኝ ከፍተኛ ደስታ ነበር የተሰማኝ::
- ለምን ?
- እምቢ ብለህ ስትመለሰኝ ያዋረድከኝና ባንተ ዓይን የምማርክ ውብ ቆንጆ እንዳልሆንኩ ስለተሰማኝ ነው::

www.path-2-happiness.com

-አመስገንኩሽ እንጂ አልዋረድኩሽም። ቆንጆ አይደለሽም አላልኩምም። አንቺ እንደ ስምሽ ውብና ማራኪ ልጅ ነሽ።

-ታዲያ አብረን እንድንደሰት ወደ ክፍልህ ሄደን ለምን አንዝናናም . . ብላ በዓይኗ ጠቀስ አደረገችው።

-መጀመሪያ መነጋገር እፈልጋለሁ።

-ስለምንድነው የምንነጋገረው ?

-በጣም ቀላል የሆነ ለኔ ግን ትልቅ ትርጉም ያለው ጥያቄ ልጠይቅሽ እችላለሁ ? ግን ከኔ ጋር ፍጹም እውነተኛ እንድትሆኚ እፈልጋለሁ።

-ካንተ ጋር የመጨረሻው ፍጹም እውነተኛ እሆናለሁ፣የሆነ ነገር ወዳንተ ለምን እንደሚስበኝ አላውቅም።

-በሕይወትሽ ደስተኛ ነሽ ?

ለአፍታ ጸጥታ ሰፈነ። ኦርሜላ መሬት መሬቱን እያየች ዝምታውን አቋረጠችና . .

-እውነተኛ ለመሆን ቃል ገብቼልሃለሁና ቃሌን አከብራለሁ። እንዲህ ያለውን ጥያቄ አልጠበኩም ነበር። ደስተኝነት ሳቅ ፈገግታና ጫወታ፣ገንዘብና ቁንጅና ከሆነ በጣም በጣም ደስተኛ ነኝ።

-ማለት በውስጥሽ፣የሕሊና ሰላም፣ውስጣዊ ደስታና የመንፈስ እርካታ አለሽ ወይ ? ማለቴ ነው። አንዳንድ ሰው እውስጡ የተየሬለ ሀዘንና ጭንቀት ተሸክሞ በጥርሱ ይስቃል።

-እውነቱን ለመናገር ቃል ገብቼልሃለሁና ልክ እኔን እየገለጽከኝ ነው። በገንዘብ፣በሳቅና በጫወታ፣በጭፈራና በወሲብ ከራሴ፣ ከውስጣዊ ሀዘኔና ከጭንቀቴ እየተሸሸግሁ ነው የምኖረው።

-ውበት ገንዘብና ጤንነት እያለሽ የዚህ ሀዘንና ጭንቀት መንስኤ ምንድነው?

-አላውቅም። ምናልባት የምመራው ትርጉም አልባ ኑሮ ይሆናል፣ሕይወቴ ፈጽሞ ትርጉም የለሽ የሆነ የከንቱነት ሕይወት ነው።

-ሕይወትሽ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ ጥረት ታደርጊያለሽ ? ወይስ ጉዳዩ አያሳስብሽም ?

-አይደለም፣እኔ መልሱን ለማግኘት ምንም ብቃት የለኝም። መልስ ማለት ደስተኝነት ማለት ነው፣ያ ደግሞ እንደኔ ላለ የሚገባ ነገር አይደለም

-ለምን ተገቢሽ አይሆንም ?

-እኔ ቱሪስቶች የሚጫወቱበትና እኔም ለጊዜያዊ ደስታ የምጫወትባቸው ቆንጆ አሻንጉሊት እንጂ ሌላ አይደለሁም።

-ሌላ ሰው ሳይሆን እኔ እየፈለኩሽ መሆኔን ስታውቂ ለምን ደስ አለሽ ?

-ባንተ ላይ ጫወታዬ ስለከሸፈብኝና በዚህ ረገድ ሽንፈት ፈጽሞ አጋጥሞኝ ስለማያውቅ ብቻ ነው።

-ለምን ስፈልግሽ እንደነበረ ታውቂያለሽ ?

-አላውቅም፣ፈገግ አለችና ፦ ይህን ጥያቄ ልጠይቅሽ ነው የፈለኩሽ እንዳትለኝ ብቻ? !

-አይደለም፣ለዚህ እንኳ አይደለም። ባለቤቴ ከሌላ ወንድ ጋር ክህደት ፈጽማብኛለች ብዬ በመጠራጠሬ ካንቺ ጋር በመዝናናት ልበቀላት ፈልጌ ነው።

-እህህ፣እኔ የመጫወቻ አሻንጉሊት ነኝ ብየህ የለ ! ባለቤትህን በመሰሪነት በኔ ልትበቀል ነው ማለት ነዋ፣የኔ ዝቅጠት እስከዚህ ድረስ ነው ማለት ነዋ ? !

-አዝናለሁ፣አንቺኮ እጅግ በጣም ውብና ማራኪ ቆንጆ ነሽ፣ግና መርሆዬ መልካም ጸባዬንና ስነ ምግባሬን የሚጻረር ነገር እንዳልፈጽም ያግደኝ ስለነበረ ብቻ ነው።

-አሁን ግን ለመበቀል ስትል መርሆዎችህን ረስተሃል ማለት ነዋ ! ወይኔ በሰው ዓይን ይህን ያህል ውዳቂ ርካሽ ነኝ ማለት ነው !

-እኔ አንቺን ለማዋረድ አልፈለኩም፣ግን ይኸ የተሰማራሽበት ሥራ ነው።

-ውሸት አልተናገርክም ! የሰው ልጅ አንዳንድ ጊዜ ራሱን ቆም ብሎ አይመለከትም፣በዚህ ሥራ ላይ ከተሰማራሁ ሁለት ዓመት የሞላኝ ከሁለት ሳምንት በፊት ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ራሴን አቅርቤለት እምቢ ያለኝ ወንድ አልነበረም። መጀመሪያ ላይ ለውበቴ ያላቸውን ከፍተኛ አድናቆት በመግለጽ ሲቀባጥሩ ጉዳያቸውን ጨርሰው ለመሄድ ስነሳ በሚናገሩት ቃላትና በሚፈጽሙት ድርጊት ውርደቴና ዝቅጠቴ ምን ያህል እንደሆነ ሲሰማኝ ኖሯል . . ይህን በቀጥታ የሚገልጽልኝና ራሴን በራሴ እንድጋፈጥ የሚያደርገኝ ሰው ሲያጋጥመኝ ግን ይህ የመጀመሪያው ነው።

-ይቅርታ . . አንቺን ለማዋረድ ወይም ስሜትሽን ለመጉዳት ፈልጌ አለመሆኑን ደግሜ ደጋግሜ ላረጋግጥልሽ እፈልጋለሁ።

-ምናልባት ሊሆን ይችላል . . ይሁን እንጂ እውነታው ይኸው ነው !

-ምን ማለትሽ ነው?

-አንዳንድ ጊዜ ከገዛ ራሳችን እንሸሻለን፣ እውነተኛውን ማንነታችንን ባለበት ሁኔታ ማየትን እንፈራለን።

www.path-2-happiness.com

-አልገባኝም !

ጆርጅ እጁን ዘርግቶ እጇን ያዝ አደርጎ ወደራሱ ሊስባት ሲሞክር፣ቀስ ብላ እጇን አላቀቀች። ዓይኖቿ አነቡና እንዲህ አለች ፦

-አልባሌነት፣ከንቱነትና ከሕይወት ሽሽት የፈለገውን ያህል ጀግንነት ቢመስሉ መናጢነት ናቸው።

-ይህን ተይውና በተናገርኩት ነገር ይቅርታ አድርጊልኝ።

-እህህ፣ሚስትህን በኔ ለመበቀል ብለህ መርሆዎችህን አሽቀንጥረህ ትጥላቸዋለህ፣እስከዚህ ድረስ ወራዳ ነኝ ማለት ነው? !

-ምንድነው የምትፈልጊው? ወደ ክፍሌ ወጥተን ከሀዘናችንና ከውስጣዊ ጭንቀታችን ለመሸሽግ አብረን እንድንዝናና አትፈልጊም ማለት ነው?

-አዎ፣አሁን እኔ በተራዬ እምቢ ብያለሁ።

-ሃይማኖትሽ ምንድነው?

-ሃይማኖት የለኝም፣ትክክለኛ ሃይማኖት የሚከተል ሃይማኖተኛ ሰው እኔ የምሰራውን ነገር ይሰራል?

-ባለቤቴ ሃይማኖተኛ ነች፣ከሌላ ወንድ ጋር ክህደት ትፈጽምብኛለች የሚል ጥርጣሬ አለኝ !

-ጥርጣሬና ግምትህ ያለ ቦታው ነው፣አሊያም እርሷ ሃይማኖተኛ ሳትሆን ዋሾ አስመሳይ ናት፤ወይም የተሳሳተና የተዛባ ሃይማኖት ትከተላለች ማለት ነው። የሚያየኝና የሚጠይቀኝ አምላክ እያለኝ ቁጭ ብዬ ወንዶችን የማጠምድ ይመስለሃል? . . በነገራችን ላይ አባትና እናቴ ቡድሂስቶች ናቸው፣እኔ ግን እርስ በርሱ የሚቃረን በመሆኑና በአስቀያሚ መደባዊነቱ ምክንያት ቡድሂዝምን እርግፍ አድርጌ በመተው ሃይማኖት የለሽ ሆኜያለሁ።

-ስለ አያቶሽ ሃይማኖት እንዴት እንዲህ ትናገሪያለሽ?

-ቡድሂዝም ሃይማኖታችን ነው እንደፈለግን እንጨምርበታል፣ እንቀንስበታለን፣እናሻሽለዋለን። ስለዚህም ከፈለክ ሃይማኖት የለሽነትን አዲሱ የቡድሂዝም ማሻሻያ አድርገህ መውሰድ ትችላለህ ! ብዙዎቹ አዳዲስ ፋሽኖች በነባሩ ሃይማኖት ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች ናቸው። ፈጠራ በመጥፎ ጎኑ ቢሆንም እንኳ ድንበር የለውም . . አሁን ሆቴሉን ለቅቄ እሄዳለሁ፣ምናልባትም ሁለተኛ ወደዚህ አልመለስም።

-ለምንድነው የማትመለሺው?

-ለሕይወቴ ትርጉም የሚሰጠኝና ራሴን እንዳከብር የሚያደርገኝ ምክንያት

እስከማገኝ ድረስ አልመለስም፤ዳግም አመሰግነሃለሁ።

-ወዴት ትሄጃያለሽ ?

ኦርሜላ ተነስታ ወጣች፣ለጥያቄው መልስ አልሰጠችም።

(4)

ጆርጅ የማይክል ጥሪ ሲያቃጭል ከእንቅልፉ አርፍዶ ተነሳ . . ድካም በተሞላበት ድምጽ ጥሪውን ተቀበለ . .

-እስካሁን ተኝተሃል? ምን ሆነሃል? ትተኛለህ አርፍደህ ትነሳለህ፣ከካኽ ነው የተማርከው?

-እባክህን ይህን ተወኝና ሕንድ ውስጥ አንድ ቀን ተኩል ቀርቶኛል፣ምንትመክረኛለህ?

-አያሌ መናፈሻዎች፣አብያተ ክርስቲያናት፣ቤተመቅደሶች፣ ሙዝየሞችና ገበያዎች፣ . . ይገኛሉ። የቱን ነው የምትፈልገው?

-አብያተ ክርስቲያናትንና ቤተ መቅደሶችን።

-የቅዱስ ጄምስን ቤተክርስቲያን መጎብኘት አትርሳ፣በጣም ታዋቂና ማራኪ ቤተ ክርስቲያ ነው።

-የሙስሊሞች፣ የሕንዱዎችና የሌሎች የአምልኮ ቦታዎችስ የሉም?

-እኔ ባልወደውም ግንባታው ስድስት ዓመታት የፈጀው ታላቁ የደልሂ ዐቢይ መስጊድም ኪነ ሕንጻው እጅግ ግሩም ነው።

-አመሰግናለሁ፣ቁርሴን በልቼ እነዚህን ሁለት መዳረሻዎች እጎበኛለሁ።

-ከቁርሱ ላይ ከመነሳትህ በፊት ከሆቴሉ እደርሳለሁ።

-አትልፋ፣ ታክሲ እይዛለሁ።

-ኣይ፣የውል ስምምነት ፎርማውን ያጠናቀቅን በመሆኑ ይህ ጉቦ አይደለም፣ከግማሽ ሰዓት በኋላ አንተ ዘንድ ነኝ፣ደህና ሁን።

ጆርጅ፣በሚስቱ ላይ ያደረበትን ጥርጣሬ ለመርሳትና ጥርጣሬውን የሚቀሰቅስበትን ከኦርሜላ ጋር ያደረገውን ምልልስ ለመዘናጋት እየሞከረ ቁርሱን በልቶ ተነሳ። ወዲያውኑ ማይክል ደውሎ እንግዳ መቀበያ ውስጥ እየጠበቀው መሆኑን ነገረው። የቀረውን ሻይ ጨለጠና ወደ ማይክል አመራ . . ሰላምታ ተለዋውጠው ወደ መኪና ገቡና ወደ ቤተክርስቲያኑ አመሩ።

-ትናንት ከሕንዱው የሬስቶራንት ሰራተኛ ጋር ስነጋገር አንተን አስታውሼህ ነበር።

-ሕንዱው እኔን እንድታስታውስ እንዴት አደረገህ?

-አህ፣ስለ ቡድሂስቷ ጂዮስቲና የተናገርከው ትዝ አለኝ። ከዚህ ለበለጠ ጊዜ ከርሷ ጋር ቆጭ ብለህ ኖሮ ሁለተኛ ወደ ሕንድ ለመመለስ አታስብም ነበር፣ብለሀኝ ነበር !

-አሀ፣ትክክል . . ትክክል ነው፣እነዚህ ሃይማኖቶች ሰዎች በስልጣኔና በዕውቀት እጅግ ኋላ ቀር በነበሩበት ዘመን የፈጠሯቸው ናቸው። እያንዳንዱ ሃይማኖት የታለመው አንድ የተወሰነ ችግር ለመፍታት ወይም የተወሰኑ መደቦችን ጥቅም ለማስከበር ነበር። ዛሬ ላይ ሲታዩ ግን የተሻሻሉ አዳዲስ እትሞች ቢሯቸውም . . የዘቀጡ ናቸው። እነዚህን ሃይማኖቶች ወዲያ በላቸውና ከአፍታ በኋላ የምንደርስበትን የቅዱስ ጀምስ ቤተክርስቲያን ላስተዋውቅህ። የታነጸው በ1836 በጀምስ ስክነር ነበር። በቀጠናው ጥንታዊና ልዩ የሆነ የስነ ሕንጻ ጥበብ የሚስተዋልበት ሲሆን አደባባዩም ከውብ አደባባዮች አንዱ ነው።

-በአካባቢው ጥንታዊ የሆነ ቀዳሚ ቤተክርስቲያን ነው? !

-አዎ፣ከ 200 እስከ 300 ዓመታት አካባቢ ይሆነዋል።

-ከ300 ዓመታት በፊት ሕንድ ውስጥ ክርስትና አልነበረም? !

-ክርስትና ወደ ሕንድ የደረሰው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው በቶማስ አማካይነት በአንደኛው ምእተ ዓመት ሲሆን፣ቶማስ በዮሐንስ ወንጌል ከአስራ ሁለቱ የኢየሱስ ሐዋርያት አንዱ ነው። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ከ1500 እስከ 1975 ባሉት ዓመታት በምዕራባውያን ዘመቻዎች አማካይነት ነው። በሕንድ ውስጥ ከሕንዱና ከእስላም ቀጥሎ ሦስተኛው ሃይማኖት ነው። የክርስቲያኖች ቁጥር በ24 ሚሊዮን ይገመታል።

-ብቻ ! ከሕንድ የሕዝብ ቁጥር አንጻር ትንሽ ነው።

-ልክ ነው፣ክርስቲያኖች ከጠቅላላው ሕዝብ 2.3% ናቸው። ሕንዱዎች ክርስትና ከውጭ በገንዘብ ይጫንብናል ብለው ስለሚያስቡ በዚህ አነስተኛ ቁጥር ላይ እንኳ በቁጣ የተሞሉ የተቃውሞ ስልፎችን ያካሄዱበታል።

-አንድን ሃይማኖት በገንዘብ ኃይል በሰዎች ላይ መጫን ተገቢ ነው ?

-ኣሀ፣በተወሰነ ደረጃ ተገቢ ነው፣ሰዎችን ከበሰበሱ የሕንዱ እምነቶች ነጻ እስክናደርጋቸው ተገቢ ይሆናል።

ከቤተክርስቲያኑ ደርሰው የኪነ ሕንጻ ውበቱን ሥዕሎቹን፣ ቅርጻቅርጾቹን፣ጉልላቶቹን እየተመለከቱ ማድነቅ ጀመሩ። በእርግጥም በጣም የሚማርክ ነበር። ይሁን እንጂ ለጉብኝት የተዘጋጀ ታሪካዊ ቅርስ ብቻ ይመስል፣የማምለኪያ ስፍራነቱን የሚያሳይ ምንም ዓይነት የአምልኮ ገጽታ

አይታይበትም። ማይክል ሁሉንም ነገር ከፍ ባለ የደስታ ስሜት ለጆርጅ ሲያስረዳ ቆይቶ ጉብኝቱ ተጠናቀቀና ለመሄድ ወደ መኪና ሲገቡ ፦

-እንዴት አገኘኸው ? አለው።

-በእውነት ግሩም ድንቅ ነው።

-ብየህ አልነበረም ? አሁን ወዴት ነው የምንሄደው ?

-ወደ ደልሂ ዐቢይ መስጊድ ለመሄድ ነው የተስማማነው።

-መልካም ! ቦታውን እኔ ባልወደውም፣ፍላጎትህን ለማክበር ይሁን።

-ለምንድነው የማትወደው ?

-ሙስሊሞች ጨካኝ አረመኔዎች ናቸው።

-እንዴት ማለት ? ሰዎችን በኃይል ወደ እስላም እንዲገቡ ያስገድዳሉ ?

-እውነቱን ለመናገር ወደ አረመኔያዊ ሃይማኖታቸው እንዲገባ ማንንም አላስገደዱም።

-ታዲያ እንደክርስትና በገንዘብ ያታልሏቸዋል ማለት ነው? !

-ማለት የፈለከው ይገባኛል፣ግን ይህንንም አያደርጉም።

-ታዲያ ሰዎች ወደዚህ ሃይማኖት የሚገቡት እንዴት ነው ?

-አህ . . ሰዎች ይህን ሃይማኖት መጀመሪያ የተቀበሉት፣ ለንግድ ወደ ሕንድ ከመጡት ዐረቦች ነበር።

-ማለትም ሰዎች እስላምን የተቀበሉት ወደዱና ፈልገውት እንጂ ተገደው አልነበረም ማለት ነው !

-አዝናለሁ፣ይህ እውነት ነው። ሰዎችን ማታለልና ማጭበርበር ቀላል ሳይሆን አልቀረም። ከዐረብ ነጋዴዎች ጋር መገናኘት በጀመሩበት ጊዜ ከአስቀያሚው የሕንዱ መደባዊነት በመሸሽ ወደ እስላም ይገቡ ነበር። ከዚያ በኋላ በወራሪነት መጡ።

-በወራሪነት? !

-አዎ፣ከዘመቻዎቹ የመጀመሪያው በ700 ዓመተ ልደት አካባቢ ሙሐመድ ብን አልቃሲም አስሠቀፊ በሚባል ግለሰብ የተመራ ነበር።

-ከአንድ ሺ ሦስት መቶ ዓመታት ጀምሮ ማለት ነው !

-እየተበራከቱ መጥተው በሕንድ ሁለተኛው ሃይማኖት ለመሆን ቻሉ።

-ቁጥራቸው ምን ያህል ይሆናል ?

-ቁጥራቸው ከ180 ሚሊዮን ወይም ከሕዝቡ 14.5% ይበልጣል።

-ትልቅ ቁጥር ነው ! ይህ ማለት ፓኪስታንና ባንግላዴሽ ባይገነጠሉ ኖሮ ሙስሊሞች በሕንድ አብላጫውን ቁጥር ይይዙ ነበር ማለት ነው? !

www.path-2-happiness.com

- ልክ ነው፣በሕንዱዎች እንጨቆናለን በማለታቸው ሕዝባዊ ንቅናቄዎች ተጠናክረው በፓኪስታን መገንጠል ተደመደመ:: ፈገግ ብሎ ቀጠለና ፦ ለኛ የሚሻለው ይህ ነው:: መስሊሞች ከ1001 ዓመተ ልደት ጀምሮ ለ300 ዓመታት ያህል ሕንድን ገዝተዋል::
- በዚህ ጊዜ ውስጥ ሰዎች እስላምን እንዲቀበሉ አስገድደዋል ?
- አላስገደዱም:: ግን ግፈኞች ነበሩ፣በድሆችና በደካሞች ጉልበት ታላላቅ ድንቅ ሕንጻዎችን ገንብተዋል::
- ታጅ መሐልን ስንጎበኝ ሙጢዕ አረሕማን ይህን አንስቶልኝ ነበር !
- ይህ የሙጢዕን ሚዘናዊነት ያመለክታል:: ሃማኖታቸውን እንዲቀበሉ ባያስገድዱም በሕዝቡ ላይ በደል ፈጽመዋል:: በእርግጥ ሕንድን የገዙት ስርወ መንግሥታት ሁሉ ግፍና ጭቆና ፈጽመዋል፣ምናልባትም ሕንድን ከገዙት ሁሉ የሙስሊሞቹ አገዛዝ የተሻለ ፍትሓዊነት የነበረው መሆኑን መግለጽ ሚዘናዊነት ነው:: መንግስታቸውን ያስወገዱት የተለየ ዓይነት ምዝበራና አረመኔነት በነበረውና የምሥራቅ ሕንድ ኩባንያ በሚል ሽፋን ወራሪዎቹ እንግሊዞች ነበሩ:: በእንግሊዞቹ ቅኝ አገዛዝ ላይ ሕንዱዎችና ሙስሊሞች በጋራ አምጸዋል::
- ሕንዱዎች የሙስሊሞችን አገዛዝ ይወዱ ነበር ማለት ነው ?
- እህህ፣እያዘንኩ አዎ ይወዱ ነበር:: ሁሉም የሙስሊም ገዥዎች ግፈኞች አልነበሩም፣ግፉ የታየው በመጨረሻው የአገዛዝ ዘመናቸው ነበር:: ግፍ ይፈጽሙ የነበሩ ሙስሊም ገዥዎችም ቢሆኑ ከእንግሊዞቹ የምስራቅ ሕንድ ኩባንያ ግፍና አስከፊ ምዝበራ ጋር ሲነጻጸሩ ፍትሐዊ ገዥዎች ነበሩ . . ይህ ቅር እንደማያሰኝህ ተስፋ አደርጋለሁ::
- ታሪክ መነገር ያለበት እንዳለ ነው እንጂ እኛ በምንፈልገው መንገድ ተቀነባብሮ አይደለም::
- እንግሊዞች ሙስሊሙን ንጉሥ ማርከው ልጆቹን ከገደሉ በኋላ ጭንቅላቶቻቸውን ቆርጠው ምግብ ማዕድ ላይ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ፣በበእንግሊዞች ላይ የተነሳሳው ሕዝባዊ አመጽ ቀጠለ:: ከዚያ በኋላ እስላማዊ ሃይማኖትን መዋጋት፣ትምህርቶቹን ማገድ፣የሕንድን ሀብት መመዝበር በሰፊው ተያያዙት::
- ምን ዓይነቱ ጭካኔና ኢሰብአዊነት ነው . . የሚዘመርለት ሰብአዊ መብት የትገባ? !
- ስለ ሰብአዊ መብት የምንሰማው በጉባኤዎች ላይ፣ በስብሰባ አደራሾች

ውስጥና በሕትመተች ላይ ብቻ ነው:: ተግባርና ተጨባጭ እውነታው ግን ሌላ ነገር ነው:: ዋናው በእንግሊዞች ላይ በተደረገው አመጽ ዋነኛ የመሰባሰቢያ ማእከል ወደ ነበረው ትልቁ መስጊድ ተቃርበናል:: በዚህ መስጊድ ነው የሙስሊም ሊቃውንት በእንግሊዞች ላይ የጅሃድ ፈትዋ ያስተላለፉትና በፈትዋው መሰረት ሕዝቡ የተንቀሳቀሰው . . የጅሃን ነማ ወይም ጃማ መስጊድ ተብሎ ይጠራል:: ግንባታው ረዥም ጊዜ የፈጀ ሲሆን የተጠናቀቀው በ1656 ዓመተ ልደት ነው:: እንዲገነባ ያዘዘው መንጎሊያዊው ንጉሥ ነገስት ሻህ ጂሃን ሲሆን፣ በአንድ ጊዜ 25000 ሰጋጆችን የሚይዝ የኤስያ ክፍለ አህጉር ትልቁ መስጊድ ነው ::

- ጥንታዊና ታሪካዊ መስጊድ ነው ማለት ነው !
- ምናልባት ይሆናል፣በመንጎላዊ ስነ ሕንጻ ሞዴል የተገነባና ሦስት ጉልላቶች ያሉት ነው:: ይኸው ከፊትህ የሚታየው ነው፣ ደርሰናል::

ወረዱና የኪነ ሕንጻ ውበቱን በአድናቆት ተመለከቱ . . እሱን ላለማስከፋት ብሎ እንጂ በማይክል ፊት ላይ ያለ መደሰት ስሜት ይስተዋል ስለነበረ፣ጆርጅ የተባበረውን የማይክል ስሜት ለመጠበቅ ሲል የመስጊዱን ጉብኝት ቶሎ አጠናቀቀ::

- ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ትፈልጋለህ ?
- አመሰግናለሁ፣አሁን ጊዜው ትንሽ የሄደ ይመስለኛል::
- ግና ሚዘናዊ አልሆንክም !
- ለምን ?
- ቤተክርስቲያኑን አየህ፣ መስጊድም አየህ፣ የሕንዱዎችን ቤተመቅደስ ግን አላየህም !
- ማየት እወድ ነበር፣ግን ብዙ አለፋሁህ::
- ቤተመቅደሱ ከምንሄድበት መንገድ ቅርብ ነው፣ማየት ትፈልጋለህ ?
- በትክክል፣ከሥራ የማያስተጓጉልህ ካልሆነ ደስ ይለኛል:: ጉዞዬ ነገ ስለሆነ ካሁን በኋላ ጓዜን ስለማዘጋጅ ብዙም አልወጣም::
- የቤተ መቅደሱ ስም አክሻርዳም ነው:: በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ያገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ይጎበኙታል:: በደልሂ ውስጥ ትልቁ የሕንዱ ቤተ መቅደስ ነው:: ግንባታው በ2000 ተጀምሮ በ2005 ነው የተጠናቀቀው:: አዲስ ቤተ መቅደስ ሲሆን የኪነ ሕንጻ ውበቱ ድንቅ ነው:: በግድግዳዎቹ ላይ የአማልክቶቻቸው ምስሎች ተቀርጸውበታል::
- እንስሳቱና ሌሎቹም አማልክት ተቀርጸውበታል ?

www.path-2-happiness.com

- አህ፣አዎ እንስሳትንና ዘፋኞችን የመሳሰሉ ሁሉም አማልክት የተቀረጹበትና የ20000 አማልክት ቅርጾች ያሉበት ቤተ መቅደስ ነው:: ሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች አስቂኝ ናቸው ብየህ የለም ? እንደሚመስለኝ ደስ የሚላቸውን ወይም የሚገርማቸውን ነገር ባዩ ቁጥር አምላክ ያደርጉታል:: የምትገኘው በድንቃድንቆቹ አገር ነው:: አይጦችን ቤተ መቅደስ ሰርተውላቸው የሚያመልኩ አሉ:: እባብና ዘንዶዎችን ቤተ መቅደስ ሰርተውላቸው የሚያመልኩ አሉ:: ለማንኛውም ወደ ሕንዱው ቤተ መቅደስ ደርሰናል::
- በጣም ውብ የሆነ ሕንጻ ይመስላል::
- ልክ ነህ:: የተገነባው በጽጌሬዳማ የአሸዋ ድንጋይ (ሳንድስቶን) ሲሆን ብረትም ሆነ ኮንክሪት አገልግሎት ላይ አልዋለም:: በተለያዩ የተረቀረጹ ጌጦች በከፍተኛ ደረጃ አጊጧል:: እንዳይረፍድብህ ቶሎ እንውረድ::

በውስጡ የታጨቁት የአማልክት ቅርጻቅርጾች ብዛት ቢያሸማቅቁትም ጆርጅ በሕንጻው ውበት በጣም ተደንቋል . . በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለአጭር ጊዜ ፈጣን ጉብኝት አድርገው ወጡ:: በመልስ ገዟቸው ላይ ፦

- ሕንጻው ግሩም ድንቅ የሚባል ነው፤ቅርጻቅርጾቹና ብዛታቸው ግን አስጠሊ ነው !
- ልክ ነው . . እውነትህን ነው::
- የገረመኝ ነገር ግን ቤተክርስቲያኑም ጭምር ቅርጻቅርጾች አሉበት:: መስጊዱ ግን ምንም ምሥልም ሆነ ቅርጻቅርጽ የለበትም !
- የቤተክርስቲያኑ ምሥልና ቅርጻቅርጽ ግን የኢየሱስ እንጂ የእንስሳት አይደለም::
- አህ፣ ልክ ነህ:: ለማንኛውም በጣም ነው የማመሰግነው፣ የዛሬው ጉብኝት እጅግ በጣም የተዋጣለት ነው::

በዛሬ የጉብኝት ፕሮግራሙ ድባብ ውስጥ ጆርጅ የካትሪናና የቶምን ጉዳይ ትንሽ የረሳ ከመሆኑም በላይ መጠነኛ የደስታና የመረጋጋት ስሜት ተሰምቶታል:: ‹‹በዋነኛ ጉዳይህ ላይ አትኩር›› . . የሚለው የአደም ቃል ወለል ብሎ ታይቶታል:: ይህ ጉብኝት ለርሱ ወደ ደስተኝነት በሚደረገው ጉዞ ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ነበር:: ሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት ፋይዳ የሌላቸው መሆኑ ግልጽ ሆኖለታል:: የሌላቸውንና የማያውቁትን ነገር እንዴት ሆኖ ሊመልሱ ኖሯል? ሌላው ቀርቶ ወደሚፈልጉት ሃይማኖታዊ መረጋጋት ለመድረስ እንኳ ራሳቸውን

እንደ ሁኔታውና እንደ አስፈላጊነቱ የሚያሻሽሉና የሚለዋውጡ ናቸው . .

ለአደም መልእክት የመላክ ሀሳብ መጣለትና ኮምፒውተሩን ከፈተ ፦

‹‹ወዳጄ አደም . . ስለ ምክርህ አመሰግናለሁ፣ላልተገባ አነጋገሬ ይቅርታ አድርግልኝ::

አውነቱን ልንገርህና በምክርህ ብዙ ብዙ ተጠቅሜያለሁ:: ሕሊናዬን ተቆጣጥሮ የነበረውን የብቀላ ፍላጎትም መርታት ችያለሁ:: ትኩረቴን በዋነኛው ጉዳዬ ላይ በማድረጌ ሀሳቤ በንኡሳን ጉዳዮች ላይ ከመበታተን ድኗል:: ሙሉውን ቀን በቁርጠኝነትና በጽናት በዚህ ላይ በማተኮሬ ያንተንና የሐኪሙን ጥያቄ በግልጽ መመለስ ችያለሁ:: ምድራዊ ሃይማኖቶች ለየትኛውም ጥያቄ ምላሽ የላቸውም:: እኛን ያልፈጠሩን ሰብአዊ ፍጡራን ሀሳቦች ብቻ እንጂ ሌላ ምንም አይደሉምና ለምን እንደ ተፈጠርን እንዴት ማወቅ ይችላሉ ? . . ምስጋናዬ በድጋሚ ይድረስህ:: ነገ ወደዚያ ስለሚመለስ እንገናኛለን፣ አሁንም አመሰግናለሁ::

ወዳጅህ ጆርጅ::

ከዚያም በሳለፈው ቀንና ወደ ዐቢይ ግቡ ጉዞ በመጀመሩ ደስተኝነት እየተሰማው አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋለለ . .

(5)

ጆርጅ አማልዶ ከእንቅልፉ ተነሳና የሚያነቃቃ ሙቅ ሻወር ወሰደ . . ሰዓቱን ሲመለከት ወደ አይሮፕላን ማረፊያ ለመሄድ አራት ሰዓት ቀርቶታል:: በቀሪው ጊዜ ምን ማድረግ እንደምችል አያለሁ፣መጀመሪያ ግን ቁርሴን ልብላ . .

ለቁርስ በተቀመጠበት ትናንት አነጋግሮት የነበረውን ሕንዱ አስተናጋጅ ካቡርን አየና ጠራው . .

- አቤት ጌታዬ ! ሠላም አደሩ ?
- እንደምነህ፣ባለፈው ጊዜ አራዝሜብህ ነበር፣አሁንም መልካም ፈቃድህ ከሆነ ሌሎች ጥያቄዎች አሉኝ ?
- ችግር የለውም:: ለሕንዱ ሃይማኖት ብዙ ትኩረት የሰጡ ይመስላል . . ይህ አዲሱ የምዕራባውያን ፋሽን ነው::
- ሕንዱይዚም ፋሽን ነው ?

- አዎ፣ሕንዱይዚምና ቡድሂዝም እናንተ ዘንድ በአውሮፓና በአሜሪካ ፋሽን ሆነዋል:: በመሰረቱ ወደዚህ የሚመጡት ሰዎችን ወደ ግዑዝ መሳሪያነት ከለወጠው እርጉሙ ማቴሪያሊዝም ለመሸሽ ነው:: ከግዑዝ ቁሳዊነት ሸሽተው የሆነ መንፈሳዊነትና ሞራላዊነትን ለመፈለግ እንጂ ስለ ሃይማኖቶቹ የሚያውቁት ምንም ነገር የለም::
- ጥሩና ግልጽ ነው:: እኔ ግን አንድ ጥያቄ ላቀርብልህ እፈልጋለሁ:: አንተና ሕንዱዎችም በአጠቃላይ ደስተኞች ናችሁ ?
- ምናልባት ሰዎችን የሚጨቁኑና የሚመዘብሩ በራህማዎች፣ ናቸው ብዬ ባላስብም ደስተኞች ይሆኑ ይሆናል:: እኔ ግን ከመደቦች አንጻር ከሾደሮች ማለትም ከአገልጋዮች መደብ ነኝ:: እምነትን በተመለከተ እኛ ከሃይማኖታችንና ከአማልክታችን ብዛት፣ከዓለማዊ ሕይወትም ሆነ ከአምላክ ጭምር ነጻ በሆኑ መንፈሳዊ ሞራላዊ ክንውኖች ራሳችንን እናሸሻለን:: ስለ ጋንዲ ሰምተህ አታውቅም ?
- ሰምቻለሁ፣ድንቅ ሰብእና ነበር::
- በሕንዱይዚም ላይ ማመጽ ፈልጎ አክራሪ ሕንዱዎች የገደሉት አመጺ ሰብእናም ነበር::
- ለምንድነው በገዛ ሃይማኖቱ ላይ የሚያምጸው ?
- ሃይማኖታችን እንዳለ ሆኖ እኩል ሆነን መኖር ስለማንችል ነው:: ግን ይቅርታ ምናልባት - እንደ ፋሽኑ - በሕንዱይዝም ተማርከህ ከሆነ እያበላሸሁብህ እንዳልሆን::
- ሃይማኖትህን ለምን አልለወጥክም ?
- አባቴና እናቴ ሕንዱዎች ናቸው፣ሕንዱ ሆኜ ነው የተወለድኩት . . በመቀጠል ፈገግ አለና ፦ እኤም ሌላው ጋንዲ እንዳልሆን ማመጽ አልፈልግም::
- ይህችን የገንዘብ ስጦታ ተቀበለኝ፣ ጊዜህን ብዙ ተሻምቻለሁ::
- አመሰግናለሁ::

ወደ ክፍሉ ተመልሶ ሄደና ዕቃዎቹን መሰብሰብና ጓዙን ማዘጋጀት ጀመረ:: ይህን በማድረግ ላይ እያለ ስልኩ አቃጨለና አነሳው:: ከሪሙሏህ ነበር . .

- ጆርጅ እንደምነህ፣ከሪሙሏህ ነኝ::

- ሃሎ፣ከሪሙሏህ::
- ትናንት ሠላም ልልህ መጥቼ አላገኘሁህም:: በተስማማነው መሰረት ሕንድ በሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ የተረጋገጠውን የውሉን ሰነድ እንድግዳ መቀበያ አስቀምጫለሁ:: መቼ ነው የምትሳፈረው ?
- በጣም አመሰግናለሁ፣ልረሳው ነበር:: አሁን እቀበለዋለሁ፣ ጉዞዬ ከሁለት ሰዓት በኋላ ነው . .
- ወደ አይሮፕላን ማረፊያ እንዳደርስህ ትፈልጋለህ ?
- አመሰግናለሁ:: መኪና እንዲያዘጋጅልኝ ከሆቴሉ ጋር ተስማምቻለሁ::
- ይቅርታ፣ለንደን በሚገኘው የሕንድ ኤምባሲ የተረጋገጠውን የውሉን ቅጂ እጠብቃለሁ፣ደህና ሁን::
- ጆርጅ መነጋገሪያውን አስቀምጦ ወዲያውኑ ወደ እንግዳ መቀበያ ደወለና ወረቀቶቹን እንዲያመጡለት ጠየቀ . . መነጋገሪያውን አስቀምጦ አሰበ ፦ ምንም መጥፎ ነገር ሳያይበት በከሪሙሏህ ውስጡ የማይደሰተው ለምን ይሆን ? እብን ላዴንን በመምሰሉ ምክንያት ይሆን ? ወይስ በድርድር ላይ ንቁና በጥበብ የተካነ በመሆኑ ? ወይስ ስለ አለቃው ስለ ካኽ በመናገሩ? ወይስ ገና ባላወቀው ሌላ ምክንያት ይሆን ? አስገራሚ የሆነ እንግዳ ስሜት ነው . . ምናልባት የለንደኑን ሜትሮ የባቡር ፍንዳታዎችን መርሳት አልቻለም:: ምናልባት ደግሞ መገናኛ ብዙኃን በሳደሩበት ተጽእኖ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ አያስደስተኝም፣ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም . .

ከእንግዳ መቀበያ ክፍል የመጣው ወረቀት ሲደርስ ከነጎደበት የሀሳብ ዓለም ተመለሰ . . አገላብጦ አያቸው:: በትክክል እንደፈገው ሆነው አገኛቸው:: የቀረው ነገር ቢኖር ለንደን ቢገኘው የሕንድ ኤምባሲ እንዲረጋገጥ ማስደረግ ብቻ ነበር:: ሰዓቱን ሲመለከት ወደ አይሮፕላን ማረፊያ የመሄጃ ሰዓት ደርሷል::

ለእንግዳ መቀበያ ክፍል ደወለና የመውጫ ሂደቱን እንዲያጠናቅቁለትና ያልተጠበቀ ነገር ወይም የትራፊክ መጨናነቅ እንዳያጋጥመው፣ ቢቻል መኪናው ግማሽ ሰዓት አስቀድሞ እንዲዘጋጅለት ጠየቀ . .

ወደ አይሮፕላን ማረፊያው ሲጓዝ በመኪናው መስኮት የደልሂን መንገዶች

www.path-2-happiness.com

እየቃኘ ነበር። ጎዳናዎቹ በቅርጻቅርጾች የተሞሉ ናቸው። ድንጋዮችን ወይም ሰብአዊ ፍጡራንን ማምለክም ሆነ ለጥያቄዎቹ ከነሱ ምላሽ ማግኘት ሊሆን የማችል ጉዳይ ነው . . ወደ መጀመሪያው የደስተኝነት መንገድ ለመራችኝ ሕንድ ምስጋና ይድረስ። ካሳለፍኳቸው ነገሮች ሁሉ ጋር አስደሳች ጉዞ ነበር . . እያለ ከራሱ ጋር እያወራ ተጓዘ።

ቀጠሮ ከሽብርተኝነት ጋር . .

www.path-2-happiness.com

6

ቀጠሮ ከሽብርተኝነት ጋር . .

ቀጠሮ ከሽብርተኝነት ጋር . .

(1)

ጆርጅ ከሕንድ ተመልሷል። ጉዞው በጣም አመርቂ ቢሆንም የተሟሟቀ፣በመረጃዎች፣በውይይቶችና በጥያቄዎች የተሞላ ነበር። ለሥራ ጉዳይ ሲላክ ይህ የመጀመሪያ ጉዞው አልነበረም። ሆኖም ግን ትልቅ ስኬት ያስመዘገበበት የመጀመሪያው ጉዞ ነው። ውሎችን በዚህ ብቃትና በዚህ ፍጥነት ማጠናቀቅ የቻለበት የመጀመሪያው የሥራ ጉብኝት ነበር . . ሕንድ በእርግጥ የድንቃድንቆች አገር ናት። የጉዞውን ዝርዝር ሁኔታዎች አይሮፕላኑ ውስጥ ሆኖ አስታወሳቸው። ከሃይማኖቶቿና አእምሮ ከማይቀበላቸው አፈተረታዊ እምነቶቿ ብዙውን ቢጠላም፣ሕንድና ሰዎቿን የመውደድ ስሜት አድሮበታል። ይህ ውዴታ ከጥያቄዎቹ ጥቂቱን ሕንድ ስለመለሰችለት ይሆን? ሕንዳዊ የዘር ግንድ ላላት ካትሪና ካለው ፍቅር የመነጨ ይሆን? ካትሪናን በተመለከተ ገና ያልጠገገ ቁስል ልቡ ውስጥ በመኖሩ ለዚህ ይሆናል የሚለውን ግምት ወዲያውኑ ተወው።

አይሮፕላኑ ለንደን ደረሰ። ሻንጣዎቹን ይዞ ወደ መውጫው ሳሎን ሲያመራ፣ካትሪና ከሁለቱ ልጆቻቸው ጋር እሱን ለመቀበል እየተጠባበቀች ነበር። ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶት ወደ ቤት እስኪደርሱ ድረስ ከቤተሰቡ ጋር ሲስቅና ሲጫወት መንገዱን ዘለቀ . .

- አልነገርከንም እኮ . . የኔ ፍቅር ሕንድ እንዴት ነች ?
- እጅግ በጣም ድንቅ ናት፣አገሩም ሰውም ድንቅ ናቸው።
- ውብ መስላ ታይታህ ይሆናል።
- በእውነትም ውብ አገርና ውብ ሕዝብ ነው። በሕይወቴ ካደረኳቸው ጉዞዎች ሁሉ ግሩም ድንቅ የሆነ ጉዞ ነበር።
- በጣም ጥሩ፣እሽ ከዚህ ጉዞ የወደድከው ምኑን ነው ?
- ጉዞው በሁሉም ጎኑ በጣም ጥሩ ነበር። የሚገርመው ግን ከዚህ ጉዞ ውስጥ በተለይ የወደድኩት ነገር ምን እንደሆነ ለይቼ አላውቅም . . ምናልባት ሰዎቹ ጥሩዎችና የሚመቹ በመሆናቸው ምክንያት፣ወይም በኔና ባንቺ ፍቅር ምክንያት . . ምናልባት ደግሞ የኩባንያውን የውል

www.path-2-happiness.com

ስምምነቶች በፍጥነትና በብቃት በማጠናቀቄ . . እኔ እንጃ . . ዋናው ነገር በጣም ነው የተደሰትኩበት።

ወደ ልጁ ወደ ማይክል ዞር አለና . .

- ታውቃለህ ? ሕንዳዊውን ማይክል ታስታውሰኛልህ፣ካንተ ጋር በስሙና በተክለ ሰውነቱ የሆነ ተመሳሳይነት አለው . . ፈገግ ብሎ ቀጠለ ፦ አንተ ውዴ ግን ከርሱ ይበልጥ ውብና በብዙ ከርሱ የተሻልክ ነህ . . ሳሊ አንቺ ደግሞ ቁንጅናሽ የኦርሜላን ቁንጅና እንዳስታውስ ያደርገኛል።

ወደ ቤት ሲደርሱ ጊዜው ሄዶ ነበር። አባታቸው የጉዞውን ዝርዝር ነገ ሊያወራላቸው ቃል ከገባላቸው በኋላ ሁለቱ ሕጻናት ለመተኛት ወደ ክፍላቸው ሄዱ። . . ጆርጅም ወደ መኝታ ክፍል ሲሄድ ካትሪና ተውባና አምራ እየጠበቀችው ነበር . .

- ሳሊን ትመስላለች ያልካት ኦርሜላ፣አሳሳቿ ቆንጆ ከረዳ ነች ?
- አዎ . . ልክ ነሽ።
- እንዴት አወቅሃት? ! የቶምና የካኽን ምክር ሰምተሃል ማለት ነው ?
- መጀመሪያ ልትነግሪኝ የሚገባው አንቺ ነሽ . . ከዚህ ቶም ከሚባለው ጋር መቼ ነው የተገናኛችሁት? !
- አልተገናኘሁትም . . ከሁለት ቀን በፊት በቤተክርስቲያን ስነ ሥርዓት ላይ ነው ያገኘሁት። ከኔ ጥያቄ ለምን ትሸሻለህ፣ ኦርሜላ ማን ናት ?
- ኦርሜላ ሆቴል ውስጥ በአጋጣሚ ያገኘኋት ልጅ ነች። በጣም ቆንጆ ነች። የስሟ ትርጉም ውብ ማራኪ ማለት ነው አለችኝ . . ግና ከቶም ጋር እስከ ስንት ሰዓት እንዳመሸሽ ንገሪኝ ።
- እስከ ሌሊቱ መጨረሻ አካባቢ ነው ያመሸነው። ይሁንና ኦርሜላን ያገኘሃት በአጋጣሚና በእግረ መንገድ ነው ብዬ እንዳምንልህ ትፈልጋለህ ? በአጋጣሚ ተገናኝታችሁ ስሟን ከነትርጉሙ አልረሳህም ማለት ነው ?
- አዎ በአጋጣሚ ነው፣ይሁንና አንቺስ የቤተክርስቲያኑ ስነ ሥርዓት እስከ ጧቱ አንድ ሰዓት የዘለቀ ነበር ብዬ እንዳምንሽ ትጠብቂያለሽ ?
- እስከ ንጋት ማምሸታችንን ማን ነገረህ? ! ስለምትጠረጥረኝ ትከታተለኝ ነበር ? ከዚህ ይልቅ ከቆነጃጅት ጋር ያለህን ግንኙነት መከታተል የነበረብኝ እኔ አይደለሁም ? !
- መልካም ፈቃድሽ ሆኖ አሁን መተኛት እፈልጋለሁ . .

ጆርጅ ጀርባውን ለካትሪና ሰጥቶ ተኛ። የተለዋወጧቸው ቃላትና ውይይታቸው ለፍንዳታ ምንም ያህል ያልቀራቸው ስለነበር በእንቅልፍ

ለመሸሸግ የመረጠ ይመስላል . . ካትሪናም ይህንኑ በማድረግ ጀርባዋን ሰጥታው ተኛች . . ያንቀላፋ የመሰለው ጆርጅ ከራሱ ጋር መነጋገር ጀመረ . . በአነጋገሬ ጠንከር ብዬባቸው ይሆን? እውነት በቤተክርስቲያን ስነ ሥርዓት ላይ ነው የነበረችው? ክብሯን ነክቼ ይሆን? አስከተለና ፦ ምናልባት አድርጌ ይሆናል፣ግን የሚገባት መቀጣጫ ነው፣በኔ ውስጥ እንደዘራችው አእምሮዋ ውስጥ ጥርጣሬ ዘርቼ ተበቅያታለሁ፣ብሎ በማሰላሰል ላይ እያለ እንቅልፍ ይዞት ጨለጠ።

ጧት ከእንቅልፉ ሲነቃ ካትሪና የሚወደውን ዓይነት ቁርስ አዘጋጅታለት ነበር . . የሌሊቱን ቁጣ የተዘናጋ በመምሰል ፈገግ አለላት . .

- የኔ ፍቅር በል ና።
- ፍቅሬ አመሰግናለሁ። የኔ ፍቅር ስጦታውን አልሰጠሁሽም፣ . . ለአፍታ ጠብቂኝ የጠየቅሽውን መስቀል ልስጥሽ . .
- ውዴ በጣም አመሰግናለሁ . . ታድዬ በጣም ያምራል ! ትረሰዋለህ ብዬ ነበር!
- የፍቅሬን ጥያቄ እንዴት አድርጌ እረሳለሁ፣ ከሕንድ ማምጣት የፈለኩት ዋነኛው ነገርም እሱ ነበር።
- ይህን መስቀል ይዘህ ስትመጣ የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ካንተ ጋር ነበር። በነገራችን ላይ የጥያቄዎችህ መልስ ጉዳይ እንዴት ሆነ?
- ከተለያዩ ሃይማኖቶች፣እምነቶችና፣አመለካከቶችና ፈለጎች ጋር የተዋወቅኩበት ግሩም ድንቅ ጉዞ ነበር።
- የቅዱስ ጄምስን ቤተክርስቲያን ጎብኝተሃል? ኪነ ሕንጻው በጣም ማራኪ ነው!
- አዎ ጎብኝቻለሁ . . በእርግጥ በጣም ድንቅ ነው። በነገርሽ ላይ ክርስቲያኖች ሕንድ ውስጥ በቁጥር ብዙ ይመስሉኝ ነበር። ቁጥራቸው በጣም ውስን መሆኑን ሳውቅ በጣም ገረመኝ።
- አዎ . . ልክ ነህ። አሳዛኝ እውነት ነው፣ሰዎች ወደ አሸባሪዎቹ ለመለወጥ እንጂ የሕንዱ ሃይማኖታቸውን በቀላሉ አይቀይሩም። ቤተክርስቲያን ይህን ሁኔታ ለመለወጥ እስትራቴጂዋን ለመቀየር እያሰበች ነው።
- አሸባሪዎቹ ! ! ሙስሊሞችን ማለትሽ ነው?
- አዎ፣ጨካኝ አረመኔዎቹን ማለቴ ነው።
- ከኩባንያችን የውል ስምምነቶች ፊርማ መካከል አንዱ ከሙስሊሞች ጋር ከመሆኑ፣ከመልካም አያያዛቸው፣ ከተጋግባቢነታቸው፣ከሐቀኝነታቸውና

www.path-2-happiness.com

የመርህ ተገዥ ከመሆናቸው ጋር፣ ስሙ ከሪሙሏህ የሚባል አንደኛቸውን ልቤ ፈጽሞ ሊቀበለው አልቻለም፣ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም !

-በጎ ነገር አፍቃሪ የሆነው ንጹህ ልብህ ግድያና ውድመት አፍቃሪ የሆነ ልብን መውደድ አይችልም::

-ሊሆን ይችላል:: ግን ሕንድ ውስጥ ካጋጠሙኝ ሰዎች ሁሉ ሙስሊሞቹ፣ገሮች ከሁሉም ይበልጥ የሚመቹና ለመርሆዎቻቸው ተገዥዎች ናቸው::

-እንዴት! ከክርስቲያኖች ጋር አልተገናኘህም?

-ተገናኝቻለሁ:: ሃይማኖተኛውን ማይክልን አግኝቼዋለሁ:: ስነ ምግባሩ መጥፎ ቢሆንም ልቤ ለምን እንደ ወደደው ግን አላውቅም !

-እኩይ ስነ ምግባር ያለው ሃይማኖተኛ ? !

-አዎ . . በጣም በጣም ሃይማኖተኛ ብቻ ሳይሆን አክራሪም ነው:: በዚህ ላይ ግን ስነ ምግባሩ የተዛነፈ ነው:: ካኽ የውል ስምምነቶቹን እንደሚፈለገው ለማጭበርበር የሕንድ ቆነጃጅት ኮረዶችን ለኔ እንዲያዘጋጅ ጠይቆት እሺ ብሎ ትእዛዙን ፈጽሟል::

-ወየው ጉድ !! ሃይማኖተኛ ሆኖ ኮረዶችን ለዝሙት የሚያቀርብ !

-አዎ . . በጣም የሚገርመው ደግሞ እምቢ በማለቴ በጣም መደነቁ ነው::

-የሌሎችን መብት እየሰረቀ ለዝሙት ጥሪ ያደርጋል! የኔ ፍቅር እንዲህ ያለው ክርስትናን አይወክልም:: ክርስትናንና ክርስቲያኖችን ለያይተን ማየት ይኖርብናል::

-ልክ ነሽ . . ያለ ምንም ጥርጥር ይህ በሁለት ጎኑ ትክክል ነው:: በአንድ ጎኑ - እንዳልሽው ሁሉ - አመለካከቶችንና ሃይማኖቶችን ከአራማጆቻቸው ለያይተን መመልከት ይኖርብናል፤ተከታዮቹ ለፈጸሙት ስህተት ሃይማኖቱን ተጠያቂ ማድረግ የለብንም:: በሌላ በኩል ግን የሰዎች ድርጊት የሚመነጨው ከአመለካከታቸውና ከሃይማኖታቸው አይደለም ወይ ? የሆነ ነገር ከመጠን አልፎ ጎልቶ ሲታይባቸው ከስር መሰረቱ በሃይማኖታቸውና በአመለካከታቸው ውስጥ ችግር መኖሩን አያመለክትም ወይ ? !

-ነው፣ግን የወዳጅህ የማይክል ሁኔታ የተለየ ነው::

-ምናልባት ይሆናል . . የሁሉም እምነት ተከታዮችም ይህንኑ ይላሉ::

-የሐኪሙ ጥያቄዎች ምላሽ ጉዳይስ እንዴት ሆነ?

-መልሶቹ ለኔ ግልጽ የሆኑልኝ ይመስለኛል::

-ታዲያ . . ከችግሩ ተገላግለናላ ?

-የተገላገልነው የሐኪሙን ጥያቄዎች ምላሽ በሚመለከተው ብቻ ነው:: መልሱን የምናገኘው መለኮታዊ ሃይማኖቶችን ካስተላለፈው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ለታላላቆቹ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት መንገዱን የያዝን ይመስለኛል፣ ከዚያም ለደስተኝነት እንበቃለን ማለት ነው::

-የኔ ፍቅር ቀጥል ትደርስበታለህ . . የሐኪሙን ጥያቄዎች ምላሽ ትክክለኛነት እንዴት አወቅህ . . ማለቴ መልሱ መምጣት ያለባት ከመለኮታዊ ሃይማኖት መሆኑን እንዴት እርግጠኛ ሆንክ?

-መልሱ ብዙ ማሰብ የሚያስፈልገው አልነበረም፤መለኮታዊ ያልሆኑ አያሌ የሕንድ ሃይማኖቶችን ያወቅኋቸው ሲሆን ለመላው የሰው ዘር የሚበጁ መሆን ቀርቶ ለራሳቸው ተከታዮች እንኳ የሚበጁ ከመሆን በጣም የራቁ ናቸው:: ከሰው ልጅ ተፈጥሮ፣ከፍትሕና ከጥበብ ጋር ተጻራሪ በሆነ መንገድ የሚጓዙ ሃይማኖቶች ሆነው ነው ያገኘኋቸው:: እኛ በምዕራቡ ዓለማችን ለነዚህ ሃይማኖቶች ያለን ግንዛቤ በጣም ውስንና ከእውነታው ጋር የማይጣጣም መሆኑንም ለማስተዋል ችያለሁ:: ለማንኛውም ይኸ የኔ አስተያየት ነው፣የቶም አስተያየት ምን እንደሆነ ስንገናኝ ነው የማውቀው::

-ቀጠሯችሁ መቼ ነው?

-ከአራት ቀናት በኋላ ነው:: . . የሥራ ሰዓት ረፈደብኝ፣የኔ ፍቅር አንቺንም አስረፈድኩብሽ::

-ዛሬ እንደማልመጣ ነግሬ አስፈቅጄያለሁ፣አንተም ዛሬ ወደ ሥራ የማትሄድ መስሎኝ ነበር::

-የለም . . ለጥቂት ሰዓታትም ቢሆን ሄጄ የማስረክበው ሥራ አለኝ . . የኔ ፍቅር ፍቀጂልኝና ልሂድ ስመለስ እንገናኛለን::

(2)

ጆርጁ ወደ ሥራ ሄደ . . መጀመሪያ ቀጥታ ያመራው ገና ሲያየው ተነስቶ ሞቅ ያለ አቀባበል ወደ አደረገለት ወደ አለቃው ካኽ ቢሮ ነበር . .

-በዚህ ጉዞ ያስመዘገብካቸው ስኬቶች እንዴት ሊሆኑ ቻሉ? ! በጣም የምትገርም ሰው ነህ !

-በእርግጥ ስምምነቶቹ እኛ በምንፈልገው መንገድ ነው የተፈጸሙት:: ግን እንዴት አወቅክ? !

-ማይክል የምሥጋና ደብዳቤ ልኮልን ስምምነቱ መፈጸሙን ነግሮናል . . ማይክል ሃይማኖተኛም ቢሆን ጥሩ የሥራ ሰው፣የሰውን ፍላጎትና ስሜቱን

www.path-2-happiness.com

የሚረዳና ምላሽ የሚሰጥ ሰው ነው . . (ፈገግ ብሎ) ሙጢዐረሕማን ግን ለምንም የማይመች ደረቅ እንጨት ነው፣ከርሱ ጋር ያለውንስ እንዴት አደረግህ?

- ተስማምተን ሁሉንም ውሎች ተፈራርመናል፤ይኸው ሕንድ በሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ ማህተም ተረጋግጦ ለንደን የሚገኘው የሕንድ ኤምባሲ ማረጋገጫ ብቻ ይቀረዋል፡፡
- ዓይኔን አላምንም? ከርሱ ጋር እንዴት መስማማት ቻልክ? !
- ከርሱ ጋር የተደረገው ስመምነት ምናልባት በዓለም ላይ በታም ፈጣኑ ስምምነት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ቅንጅት የሚጎድለው ቢሆንም ግትር ያልሆነ ንቁና ሁሉንም ተጠቃሚ በሚያደርግ መንገድ የሚያስብ ገር ሰው ነው፡፡ የውል ስምምነቱን ወንድሙ ከሪሙሏህ እንዲፈጽመው ነበር ያስተላለፈለት፡፡ ወንድምየው ብዙ ደስ የማያሰኝ ቢሆንም ሰብሰብ ያለ የተግባር ሰው ነው፡፡
- ስምምነቶቹ ከፊትለፊቴ የተቀመጡ ቢሆንም የምትናገረውን ማመን ተስኖኛል፡፡ ለኔ መጢዐረሕማንም ሆነ ከሪሙሏህ አይመቹኝም፡፡ ሕይወትን እንዴት እንደሚመለከቷት አላቅም፣ልክ ውጊያ ሜዳ ያሉ ነው የሚመስለው፡፡ ምናልባትም ሙስሊሞች ስለሆኑ በእምነታቸው ባሕሪ ምክንያት ሊሆን ይችላል . . ለመሆኑ የኔን ቆነጃጅት ጉዳይ እንዴት አደረግህ? አንተ ጆርጅ ከኔ ሴቶች ጋር መተኛት ትንሽ እንኳ አላፈርክም ማለት ነው?
- ካንተ ሴቶች ጋርም ሆነ ከሌሎች ጋር አልተኛሁም፡፡
- ታዲያ . . ማይክል ወራዳ ነበር በተለምዶ ለኔ እንደሚያደርግልኝ ላንተ አላደረገም፣ በደንብ አላስተናገደህም በለኛ?
- በተቃራኒው ለኔ በጣም ጥሩ ነበር፣ቆነጃጅቱን እምቢ ብዬ የመለስኳቸው እኔ ነኝ፡፡
- አእምሮ ያለው ሰው እንዲህ ያለውን የማይገኝ አጋጣሚ ያበለሻል ብዬ አላምንም፡፡ የኩባንያው የቦርድ ስብሰባ ባይኖር ኖሮ ከቆነጃጅቱ ጋር ለመዝናናት እኔ ራሴ ብገዝ ደስ ይለኝ ነበር፣ እንዴት ያሉ ማራኪዎች መሰሉህ፡፡ አንተ ሕይወትን መቼ እንደምትኖራትና ድንቅ አጋጣሚዎችን መቼ እንደምትጠቀም አላውቅም፡፡ ሁሉንም ውሎች ተፈራርመህ ጨርስህ ባትመጣ ኖሮ ጭራሽም መኳዝህን እጠራጠር ነበር ! ያለ ሕንዳውያት ቆነጃጅት ኮረዶች ወደ ሕንድ መሄድ ምን ትርጉም አለው? እውነቱን

ለመናገር ማይክል ከሚያቀርባቸው እንቡጦች የሚበልጥ ምን ውበት አለና ነው የተውካቸው? !

- አዎ አለ፣ሆቴሉ ውስጥ ራሷን ያቀረበችልኝ ኦርሜላ በብዙ እጅ የበለጠ ውብ ቆንጆ ነች፤ግና እምቢ ብዬ ነው የተውኳት፡፡
- እኔ እንጃ፣ለመሆኑ ሕይወትንና ዓለማዊ ደስታን እንዴት ነው የምትመለከተው? !
- ዕድሜያችንና ጊዜያችንን ከራሳችን ሸሽተን በሥጋዊ ፍላጎታችንና በጊዜያዊ ደስታ ውስጥ የምንደበቅ ከሆነ፣የሕይወት ትርጉም ምንድነው? የመኖር ዓለማ ምንድነው? የተፈጠርነውስ ለምን ዓለማ ነው?
- አሃ፣ለሐኪምህ ልታቀርበው የሚገባ ድንቅ ሌክቸር ነው፡፡ አሁን ይህን እንተወውና ከነዚህ ስምምነቶች በኋላ ቀጣዩን ሥራ የሚመለከቱ ሂደቶችን መጀመር ይጠበቅብናል፡፡ ኩባንያው ለስኬታማ ክንውንህ ያለውን አክብሮትና አድናቆትቱን ከምስጋና ጋር ያቀርባል፡፡
- ሂደቶቹን እጀምራለሁ፣በመጪዎቹ ጥቂት ቀናት ውስጥ አጠናቅቃቸዋለሁ፡፡ እኔም ኩባንያውን ማመስገን እፈልጋለሁ፣ ጉዞዬ በጣም አስደሳች ነበር፡፡
- ለአንተ አስደሳችነቱ ምኑ ላይ እንደሆነ ባይገባኝም፣ከፈለግህ ካሁኑ የበለጠ አስደሳች ጉዞ እየጠበቀህ መሆኑን ስነገርህ በጣም ደስ እያለኝ ነው፡፡
- ሌላ ጉዞ ? !
- አዎ፣ወደ ቅድስት አገር የሚደረግ ጉዞ፡፡
- የትኛዋ ቅድስት አገር?
- እኔ ቅድስናዋን ባልቀበልም የሦስቱ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ተከታዮች ግን ‹‹ቁድስ›› ወይም ‹‹ኢየሩሳሌም›› ወይም ‹‹ቴልአቪብ›› ቅዱስ አገር መሆኗን ያምናሉ፡፡ ቤተሰቦቼ ሁሉ እዚያ ይኖረራሉ፣ወደዚያ እንድመጣ ሁሌ ይወተውቱኛል፡፡ እኔ ግን ከሚገባው በላይ ሃይማኖት አጥባቂዎች እነደሆኑ ነው የሚሰማኝ ! እናቴ ይሁዳዊት ናት፣ለኔ ግን ሁሉም ሃይማኖቶች አሳማኝ አይደሉም፡፡ የኦርሻሌም ሴኩሪቴ ኩባንያ የላክንላቸውን የቴክኒካል ውል ሀሳብ ተቀብለዋል፣ከፈለግህ አንተ ትሄዳለህ አለዚያ እኔ እሄዳለሁ፡፡ ውሎችን ለማሳካት ከኔ የተሻልክ ስለሆነ አንተ ብትሄድ እመርጣለሁ . . የሁለት ሳምንት ጊዜ አለህና አስብበት፡፡
- ጥሩ፣አስቤበት እነግረሃለሁ፡፡

www.path-2-happiness.com

(3)

ጆርጅ ከሥራ በኂላ በቀጥታ ወደ ቤቱ ተመለሰ . . መንገዱ ከወትሮ በተለየ ሁኔታ የትራፊክ መጨናነቅ ነበረበት። በተለምዶ ከአርባ አምስት ደቂቃ በላይ ያልነበረው ከሥራ ቦታ እስከ መኖሪያ ቤቱ ያለው መንገድ ዛሬ ሁለት ሰዓት ተኩል ወስዶበታል። . . ወደ ቤት የደረሰው ድካም እየተጫጫነው ነበር። ካትሪና ተጣድፋ ተቀበለችው . .

-እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣እንኳን ደህና መጣህ የኔ ፍቅር፣በጣም ተጨንቄ ነበር።

-ዛሬ ምን እንደተፈጠረ እንጃ በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት መንገዱ ሁለት ሰዓት ተኩል ነው የወሰደብኝ !

-ዛሬ የምድር ውስጥ ባቡር መንገድ ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል።

-ለምን?

-በሜትሮ በደረሰው የሽብር ጥቃት፣ጌታ ይመስገን እንኳ በማእከላዊው ቦታ አልሆነ እንጂ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በሞቱ ነበር።

-የተጎዳ ሰው አለ?

-ከሁለት ቀናት በፊት የተጋቡ ባልና ሚስት የተገደሉ ሲሆን ሁለት ወንዶች፣አንዲት ሴትና አንድ ሕጻን በፍንዳታው ተጎድተዋል። እነዚህ አሸባሪ ሙስሊሞች ምን ዓይነት ጨካኝ ልብ ይሆን ያላቸው !

ዜናውን በቲቪ ለመከታተል ጆርጅ ሪሞቱን ወሰደ . .

-ሙስሊሞች መሆናቸውን እንዴት አወቅሽ? እሱን ተይና ዜናውን በቲቪ እንከታተል።

-ይህን ጥቃት ለመፈጸም ከነርሱ በስተቀር በጭካኔ የተሞላ ልብ ያለው ሌላ ሰው አይኖርም።

ጆርጅ የሚዲያ ሽፋኑን በቲቪ ተከታተለ፣ፍንዳታው የደረሰው ከአራት ሰዓት በፊት ሲሆን ሁሉም ተንታኞች ጥቃቱን የፈጸሙት ሙስሊም አሸባሪዎች ናቸው በሚለው ላይ ሙለ በሙሉ ተስማምተዋል። ይሁን እንጂ እስካሁን ድረስ በይፋ የተሰጠ የውንጀላ መግለጫ ለም። የእንግሊዝ የፖሊስና የጸጥታ ኀይሎች በከፍተኛ የተጠንቀቅ ሁኔታ ላይ ናቸው። ሁሉም ሰው ወደ ቤት መመለስ ይፈልጋል፣መንገዶች ግን ሙሉ ለሙሉ ዝግ ናቸው።

-ሀሳብሽ ልክ ሳይሆን አይቀርም፣እስካሁን ድረስ በይፋ የተሰጠ መግለጫ ባይኖርም፣ጥቃቱን ያደረሱት አሸባሪ ሙስሊሞች ናቸው።

-እመነኝ ርህራሄ ያልተፈጠረባቸው ልበ ደረቆች ከነዚህ አሸባሪዎች በስተቀር ማንም የለም፣ይህን ማድረግ ሃይማኖታዊ አምልኮ አድርገው ይቆጥሩታል።

-ለሃይማኖታዊ አምልኮና ለጽድቅ ብለው ሰዎችን ይገድላሉ? !

-አዎ . . ‹‹ጅሃድ›› ብለው የሚጠሩት ነገር አላቸው፣በርሱ አማካይነት ሰዎችን መግደልና ማሰቃየትን የአምልኮ ሥራ አድርገው ይቆጥራሉ። በዚህ የሽብር ሃይማኖትና በክርስትና ገርነትና ፍቀር መካከል ያለውን ልዩነት ተመልከት። ኢየሱስ ለሰው ልጆች ብሎ ራሱን ሰዋ፣ተከታዮቹም እንደዚሁ። የሙሐመድ ተከታዮች ግን ከመግደል በስተቀር ሌላ አያውቁም።።።።

-የነኚህ ሙስሊሞች ነገር የሚገርም ነው። ምናልባት ከሪሙሏህ ፈጽሞ የማይመቸኝ በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

-ሰይገድሉህ ወይም ሳያፈነዱህ ከነሱ ዘንድ በሰላም በመውጣትህ እዝግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

-ወየው ጉድ፣ይታይሽ ሙጢዑረሕማን ፈንጂ ጠምዶብኝ ሲያፈነዳኝ . . እውነቱን ለመናገር ግን ገርና ምቹ ሰው ነበር፣ በተጨማሪም የሕንድ ዑድ ሽቶ በስጦታ አበርክቶልኛል።

-ችግር የሌለው መሆኑን ሳታረጋግጥ አትጠቀመው፣የተመረዘ ሊሆን ይችላል።

-እኔ የዑድ ሽቶ አልወድም፣ለአስተናጋጁ ለአደም ነው ያመጣሁት። ዝንእንዳመጣለት ጠይቆኝ ነበር፣ወዳጄ አደምን የሚጎዳ ነገር እንደሌለበት ግን ማረጋገጥ አለብኝ።

-ለወዳጅህ ከማበርከትህ በፊት ነጻ መሆኑን አረጋግጥ፣እነዚህ አሸባሪዎች ፈጽሞ የሚታመኑ አይደሉም።

-አስታወስሽኝ . . ከተመለስኩ ወዲህ አደምን አላኘሁትም፣ ከሕንድ ስመለስ እጎበኘሃለሁ ብየው ነበር።

-ለመሆኑ እርሱ ፕሮቴስታንት ነው ወይስ ካቶሊክ?

-ባይገርምሽ አላውቅም ! አልጠየኩትም፣እሱም አልነገረኝም። ነገ ላገኘው እሞክራለሁ፣ምናልባት እጠይቀው ይሆናል . . ዛሬ እናመሻለን ወይስ በቀጥታ ወደ መኝታ ነው?

-ከተወዳጅ ፍቅሬ ጋር ማመሸቱን እመርጣለሁ።

በነጋታው ጆርጅ ወደ ሥራ ላለመሄድና ሥራውን እቤት ሆኖ በስልክና

በኢንተርኔት አማካይነት ለመከታተል ወሰነ:: የውስጥ ለውስጥ ባቡር መንገዱ በከፊል ብቻ እንጂ ሥራ ስላልጀመረ የትራፊክ መጨናነቁ አሁንም አልቀነሰም:: ለአደም ደጋግሞ ቢደውልም ስልኩ ዝግ ነው:: የፍንዳታውና የአሸባሪዎቹ ነገር ከምን እንደደረሰ ለማወቅ ቲቪ ከፈተ . . መንግስት የተቀረውን የምድር ውስጥ ባቡር መንገድ ከፍቷል፣በለንደን የሚኖሩ የሕንድ የፓኪስታንና የዐረብ ዝርያ ያላቸው በርካታ ሙስሊሞችም እንግሊዛውያን ሙስሊሞችንም ጨምሮ በቁጥጥር ሥር ውለዋል:: ከሽብር ጥቃቱ በስተጀርባ ሙስሊሞች መኖራቸውን የሚገልጹ ትንተናዎች አሁንም እየጎረፉ ነው:: ከጥቃቱ ሰለባዎች አንዱ ሕንዳዊ ሙስሊም ሲሆን በባቡር ጣቢያው የመገኘቱ ሁኔታ ጥርጣሬ አሳድሯል:: በዚያው ቦታ ላይ የአንድ ሌላ ፓኪስታናዊ መታወቂያ ካርድ የተገኘ ሲሆን ግለሰቡን ለማግኘት ፍለጋው ቀጥሏል . . በተጨማሪም ዜጎችና ነዋሪዎች ሕዝብ በሚሰባሰብባቸው ቦታዎች ላይ ሻንጣ መሰል ነገር ትቶ የሚሄድ ሰው ካጋጠማቸው በተለይም ሙስሊም ከሆነ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉና ለሚመለከተው ክፍል ወዲያውኑ እንዲያስታውቁ መንግስት በጥብቅ አሳስቧል . .

ጆርጅ ዜናውን ተከታትሎ እንዳበቃ ለባብሶ አደምን ለማግኘት ወደ ካፌው አመራ . . ግን አላገኘውም:: ሌላውን አስተናጋጅ ሲጠይቅ ለአምስት ቀናት ፈቃድ መውሰዱን ነገረው::

-ከመቼ ጀምሮ ነው ፈቃድ የወሰደው? ለምን እንደወሰደ ታውቃለህ?
-ለዩኒቨርሲቲው የሚያቀርበውን የመመረቂያ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ጊዜ ለማግኘት ብሎ ነው፤ከሦስት ቀናት በፊት ነው የወሰደው::

ጆርጅ ወደ አደም ቤት ሄዶ ሲያንኳንኳ የከፈተለት ሰው አልነበረም፣መጥቶ እንዳላገኘው የሚገልጽ ማስታወሻ በሩ ላይ ትቶለት ወደ ቤቱ ተመለሰ . . ሲመጣ ካትሪናን ዜና እየተከታተለች አገኛት . .

-የሜትሮውን ፍንዳታ የተመለከተ አዲስ ነገር አለ?
-ምንም አዲስ ነገር የለም:: የአሸባሪው ፓኪስታናዊ ፍለጋ አሁንም እንደቀጠለ ነው:: ዋነኛው ስጋት ግን ለንደን ሌላ አዲስ ፍንዳታ እየጠበቃት እንዳይሆን ነው::
-ዛሬ ባገኙትና ሰው ከስጋት ቢገላገል እንዴት ጥሩ ነበር:: እነዚህን አሸባሪዎች ምን ዓይነት ጨካኝ ልብ ፈጥሮባቸው ይሆን?!
-ዛሬ ወደ ሥራ ሄደሃል?
-አልሄድኩም፣ሜትሮው ጧት በከፊል ዝግ ነበር:: ወደ ወዳጄ አደም

ዘንድ ነበር የሄድኩት፣ግና ለመመረቂያ ጽሑፉ ዝግጅት ዕረፍት ስለወሰደ አላገኘሁትም::
-ነገስ ወደ ሥራ ትሄዳለህ?
-አዎ . . አንዳንድ ሥራዎች ስላሉኝ አለጥርጥር እሄዳለሁ፣ ከዚያ ለሐኪም ቶም ቀጠሮ አወጣለሁ::
-አሁንማ ለሐኪሙ ጥያቄዎች ግልጽ ምላሾች ይዘህለት የለም?
-አዎ፣እንደ እድል ሆኖ በመጀመሪያውና በአሁኑም ዙር ወደ ምላሾቹ የተመራሁ ሆኖ ይሰማኛል::
-አንተ ሁሌም ስኬታማ ነህ፣መንፈስ ቅዱስ ካንተ ጋር ነው፣ያግዝሃል::
-አሁንም አዳዲስ ጥያቄዎች እንዳሉት ነው የማውቀው::
-ታውቀዋለህ? !
-አዎ፣አማራጭ እየጠበበኝ የመጣ መሰለኝ:: በአጋጣሚ ይሁን ወይም በቶም የተቀነባበረ አሊያም አንቺ እንደምትይው በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ይሁን ግን አላውቅም::
-እንዴት ማለት?
-መጀመሪያ ላይ ምርጫው መልሶቹን ከየት ነው የምናመጣቸው የሚል ነበር:: መምጣት የሚችሉት ከፈጣሪ በኩል ብቻ ስለመሆናቸው ለኔ እጅግ በጣም ግልጽ ነበር:: የኤቲዝም አመለካከት ወዴትም የማያደርስ የሸሸት አመለካከት መሆኑን አውቅ ነበር:: ሥርዓትን ከሥርዓት አልበኝነት መፍጠር እንዴት ይቻላል? ከፈጠረን በስተቀር ሌላው ለምን እንደተፈጠርን እንዴት ማወቅ ይቻለዋል? ኤቲዝም ምሁራን ነን ብለው ራሳቸውን የሚገምቱ አንዳንድ ሰዎች የሚከተሉት ቢሆንም እንኳ ሰብአዊ አእምሮን፣ ተፈጥሮንና ሃይማኖትን የሚጻረር አዝማሚያ ነው:: ከዚያ የሚቀጥለው ጥያቄ ደግሞ ፈጣሪው ማነው? የሚለው ነበር:: ሃይማኖቶችና ሰዎች ስለ ፈጣሪ ያላቸውን አመለካከት ለመረዳት፣ ምድራዊ ሰው ሰራሽ ሃይማኖቶችና መለኮታዊ ሃይማኖቶች ብለን በሁለት ጎራዎች ከፈልን:: ምድራዊ ሰው ሰራሽ ሃይማኖቶች፣ለሰው ልጅ ጥያቄዎች ምላሽ ማቅረብ ቀርቶ ከሰው ተፈጥሮና ከተከታዮቻቸው ተፈጥሮ ጋር መጣጣም የማይችሉ መሆናቸው በተለይም ከሕንድ ጉዞዬ በኋላ ለኔ በጣም ግልጽ ነበር:: ብቃት ማጣታቸው ብቻ ሳይሆን ለመኗኗር የማይመቹ አጉጉል እምነቶች ናቸው:: በመሆኑም አሁን ጥያቄው መሆን ያለበት ከሳይንሳዊና ሰብአዊ እውነታዎች ጋር የሚጣጣም ሎጂካዊ ምላሽ የሚሰጠው ከመለኮታዊ

www.path-2-happiness.com

ሃይማኖቶች ውስጥ የትኛው ሃይማኖት ነው? የሚለው ነው።

- ክርስትና የሰው ልጅ መድህን ነው ብየህ የለም?
- ይሁድናስ? እስላምስ?
- የኔ ፍቅር አንድ ቀን በምድር ውስጥ ባቡር መንገድ ላይ የፈንጂ ቀበቶ የታጠቀ ሙስሊም ሆነህ አየሃለሁ ማለት ነው?
- ምናልባት ! ማን ያውቃል፣ወይም ሀብት ከማግበስበስና ከወሲብ በስተቀር ምንም ሀሳብ እንደሌለው ካኽ ያለ ይሁዲ እሆን ይሃናል።

(4)

በሥራ ላይ እያለ ጆርጅ ካንድ ጊዜ በላይ ለአደም ቢደውልም ሞባይሉ ዝግ ነበር። ሀሳብ ገባው፣ወደ ሐኪም ቀጠሮው ከመሄዱ በፊት ሊያገኘው ይፈልግ ነበር . . ‹‹ከሕንድ ተመልሻለሁ፣ስጦታ ያመጣሁልህ ስለሆነ ባገኝህ ፍላጎቴ ነው። ከቻልክ ደውልልኝ›› የሚል አጭር የጽሑፍ መልእክት ቢልክለትም ምላሽ አላገኘም . .

የሐኪም ቀጠሮው ስለደረሰ ጆርጅ ወደ ክሊኒኩ አመራ። እንግዳ መቀበያ ውስጥ ተቀምጦ የነበረው በራድ ጆርጅን ሲያይ በሰላምታ ተቀበለው . .

- ሕንድንና ቆነጃጅቷን እንዴ አገኘሃቸው?
- ወብና አስገራሚ አገር ነች . . ቀጠሮዬ ደርሷል ወደ ቶም ልሂድ።
- የቸኮልክ ትመስላለህ፣ወይስ ከኔ ጋር መነጋገር አልወደድክም . . ግዴለም!
- ልግባ ትፈቅድልኛለህ?
- ግባ . . ግባ፣የሆነ ሆኖ ግን አንድ ቀን ወደኔ መመለስህ አይቀርም።

ጆርጅ ሲገባ ቶም ሞቅ ባለ ሁኔታ ተቀበለው። የዛሬው ከተለመደው በጣም የበዛ አቀባበል ነበር። እርሱን በማየቱ ቶም በጣም ደስተኛ መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር። እንዲህም አለው ፦

- በመገናኘታችን ምን ያህል እንደተደሰትኩ ልነግርህ አልችልም። አመለካከትህን፣አስተያየትህንና ምላሾችን ለመሰማት በጣም ነው የጓጓሁት።
- የኔን ምላሽና አስተያየት በናፍቆት እየተጠባበቅክ ነው ማለት ነው? !
- ምናልበት አነጋገሬ ያስገርምህ ይሆናል . . ግን እውነት ነው . . አዎ እየጠበቅሁ ነው። ያንተ ፍልስፍና ከኔ ሳይንሳዊና ፍልስፍናዊ አካሄድ ጋር የተጣጣመና በሃይማኖት ላይ የማደርገውን ምርምር ከመጀመሬ ጋር የተገጣጠመ ይመስለኛል። ለዚህ ነው አንዳንድ ሃይማኖታዊ ስነ ልቦናዊ ጥናቶችን ለማካሄድ ቀጣይ በሆነ ሁኔታ ወደ ቤተክርስቲያን የምሄደው .

. ፈገግ አለና ቀጠለ ፦ ለማንኛውም ይህን እንተወውና ከሕንድ ጉብኝት በኋላ እኔ እንደጠበቅሁት ሁሉንም ሃይማኖቶች ችላ አላልክም ወይ?

- ያለ ጥርጥር አዎ . .
- አላልኩህም እንደ ጠበቅኩት ሆነ፣ ግሩም ድንቅ።
- መልካም ፈቃድህ ሆኖ ተወኝና ልጨርስልህ፣አዎ ሁሉንም ምድራዊ ሃይማኖቶች ችላ ብያለሁ።
- ምን ማለትህ ነው?
- ለትላልቆቹ ጥያቄዎች ምላሽ ማፈላለግ ያለብን በመለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥ በቀረበው መሰረት ከፈጣሪ አምላክ በኩል ብቻ ነው ማለቴ ነው።
- በምን መብት ነው መለኮታዊ ሃይማኖቶችን ከምድራዊ ሃይማኖቶች የምታስቀድመው?
- መለኮታዊ ሃይማኖቶችን እኔ ከራሴ ተነስቼ አላስቀደምኩም፣ የምድራዊ ሃይማኖቶች ተከታዮች ራሳቸው ሃይማኖቶቻቸው የራሳቸው እጅ ሥራ መሆናቸውንና በየጊዜው እያሻሻሏቸው መሆናቸውን ያውቃሉ።
- እያሻሻሏቸው? !
- አዎ በየጊዜው ያሻሽሏቸዋል ! ምድራዊና ሰው ሰራሽ መሆናቸውንም አምነው ይቀበላሉ። ደሞም ለታላላቆቹ ጥያቄዎቻችን እንደኛ ያሉ ሰብአዊ ፍጡራን እንዴት አድርገው መልስ ያመጣሉ ! ምናልባትም እኛ ከነሱ የተሻለ ግንዛቤና ዕውቀት ሳይኖረን አይቀርም። በተጨማሪም የሆነ እንስሳ ሊፈጥራቸው ቀርቶ ራሳቸውን በራሳቸው መፍጠር እንኳ የማይቻል እንደ መሆኑ፣ የሰው ልጆች የፈጠራቸው ፈጣሪ አምላክ ሳይኖር ለምን እንደተፈጠሩ እንዴት ማወቅ ይችላሉ? ! እነዚህ ምድራዊ ሃይማኖቶች በዓለም ላይ ለሚታየው የኤቲዝም እንቅስቃሴ መፈጠር ዋነኛ መንስኤዎች መሆናቸው አይታህም?
- ልክ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ምንም ጥርጥር የሌለባቸው እውነታ እንደሆኑ አድርገህ ነው የምትናገረው !
- እኔ እንጃ . . ጥያቄህ ከመለኮታዊና ምድራዊው አንዱን መምረጥ የሚመለከት ነበር። በዚህ ረገድ ፈጽሞ ጥርጥር የለም።
- ሁለቱን አማራጮች ያስቀመጥከው አንተ እንጅ እኔ አይደለሁም።
- አምነህ ተቀብለህ ጥያቄውንም ያሻሻልከው አንተ ነህ። ባልወደውም በትክክለኛ ሳይንሳዊ መንገድ እየተጓዝን ነው። ስለዚህም በማንኛውም አፍታ መለኮታዊ ሃይማኖቶችንም ችላ ልትላቸውና አብረን ልንተዋቸው

እንችላለን፣ያኔም ወደ ወደ ኤቲዝም እንመለሳለን::

- ያ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም:: ኤቲዝም ወደ ደስተኝነት የማያደርስ የጨለማ መንገድ ነው፤ለዚህ ነው ብዙዎቹ ኤቲስቶች ራሳቸውን የሚያጠፉት::
- አሃሃ፣አንተም በቅርቡ ራስህን ትገድላለህ እያልከኝ ነው? ታዲያ የሃይማኖት አማኞችስ ለምን ራሳቸውን ያጠፋሉ?
- የኤቲዝም መንገድ ጨለማ መሆኑን ታውቀዋለህ ብዬ ነው የምገምተው፣ለዚህም ነው በሃይማኖቶች ላይ የምታደርገውን ጥናት የጀመርከው:: ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች ለምን ራሳቸውን ይገድላሉ ለሚለው መልሱን እኔ የግድ ማወቅ ያለብኝ አይመስለኝም::
- ሊሆን ይችላል፣ዋናው ነገር እኛ አሁን መለኮታዊ ሃይማኖቶችን እናጥናና ሁሉም ወደምንፈልገው ምላሽ የማያደርሱን ከሆኑ ሌላ መፍትሔ እንፈልጋለን:: ከኤቲስትነቴም ጋር ስለ ኤቲዝም የምትናገረውን ብዙውን እጋረሃለሁ:: ይሁን እንጂ ምናልባት የግድ መኖር ያለበት አማራጭ በመሆኑ አማራጮቼን ሁሉ ሙሉ በሙሉ እርግፍ አድርጌ መተው አልፈልግም::
- ሦስት ሃይማኖቶች ብቻ ናቸው የቀሩት::
- አሸባሪውን እስላምም እናጠነዋለን ማለት ነው?
- እኔ እንጃ፣ግና አማራጮችን ውድቅ ማድረግ አልወድም ብለህ የለ? !
- አዎ . . እውነትህን ነው:: ግና እንደ እብን ላዴን በቶራ ቦራ ተራሮች ውስጥ ስትደበቅ ታየኝ::
- ሽብርተኝነትን አምርሬ ከመጥላቴና አእምሮ አልባነት ፣ሃይማኖት የለሽነትና ጭካኔ ስለመሆኑ እርግጠኛ ከመሆኔ ጋር ሚዘናዊ የሆነ ሳይንሳዊ አካሄድ በጥናቱ ውስጥ እንድናካትተው ያስገድደናል::
- ጊዜ ለመቆጠብ ያህል አሁን ከፊትህ የሚጋፈጥህ ፈታኝ ጉዳይ ከሦስቱ ሃይማኖቶች አንደኛውን የመምረጡ ነገር ነው:: እኔ የማቀርበው ሀሳብ በሁሉም ዘንድ ስምምነት በተደረገበት ሃይማኖት ጥናቱን እንድትጀምር ነው::
- ሦስቱም ሃይማኖቶች ስምምነት የተደረገባቸው ናቸው::
- ማለት የፈለኩት አይሁዳዊነትን ነው:: ሙሴ አይሁዶች፣ክርስቲያኖችና ሙስሊሞችም ያምኑበታል::
- ገባኝ፣የዚህ ተቃራኒና ግልባጭ ከሆነ ሌላ አቅጣጫ መመልከትም የሚቻል

ይመስለኛል::

- እሽ ፈላስፋው፣ እንዴት ማለት ነው?
- ሙስሊሞች በሙሴ በኢየሱስና በሙሐመድ ያምናሉ:: ክርስቲያኖች ግን በሙሴና በኢየሱስ ብቻ ነው የሚያምኑት:: አይሁዶችን ከወሰድን ደግሞ በሙሴ ብቻ ነው የሚያምኑት::
- ከተቃራኒ አቅጣጫ ትክክለኛ የሆነ አመለካከት ነው፤ይሁን እንጂ የመለኮታዊ ሃይማኖቶች አንጋፋ ከመሆኑ አንጻር በአይሁዳዊነት እንጀምር በሚለው ሀሳቤ አሁንም እንደጸናሁ ነኝ::
- ሙሉ በሙሉ በሀሳብህ እስማማለሁ::
- በአንድ ጊዜ ስለ ታሪክ፣ስለ ፍልስፍና፣ ስለ ርእዮት፣ ስለ ሃይማኖትና ስለ ተጨባጩ ሁኔታ የምታጠና ስለሆንክ፣ ለያንዳንዱን ሃይማኖት በቂ ጊዜ ሰጥተህ እንደምታጠና ተስፋ አደርጋለሁ:: አይሁዳዊነትን አውቀህ ስትጨርስ ክርስትናን ከማወቅህ በፊት ውድቅ አታደርገው ወይም አትቀበለው:: ጊዜ ወስደህ ክርስትናን ካወቅህ በኋላም እስላምን ከማወቅህ በፊት ውድቅ አታደርገው ወይም አትቀበለው . . ፈገግ ብሎ ቀጠለና ፦ ወደ ቶራ ቦራ ተራሮች ለመሄድ ገፍተህ ከቀጠል ማለቴ ነው !
- መልካም ግን እነዚህን ሃይማኖቶች ለማወቅ ተመራጩ ዘዴ ምን ይመስለሃል?
- ማንበብ፣ ማነጻጸር፣ ማጥናትና መመራመር የማያልቅ ሀብት ነው:: እያንዳንዱን እምነት ከሃይማኖቶቹ ሊቃውንት ማወቅ ከቻልክ ተመራጭና ጠቃሚ መሆኑ ጥርጥር የለውም . . ወደ ሕንድ እንደ ሄድክ ሁሉ አይሁዳዊነትን በቅርበት ለማወቅ ወደ ቴልአቪቭም ብትጓዝ ጥሩ ነበር::
- በሚገርም አጋጣሚ በቅርቡ ወደ ቴልአቪብ የሚደረግ አጭር የሥራ ጉብኝት ቀርቦልኛል:: ይሁን እንጂ እስካሁን ለመሄድ ፈቃደኝነቴን አልገለጽኩም::
- ሰሞኑን ከሕንድ የተመለስክ በመሆንህ የግል ሁኔታህን ባላውቀውም ወደ ቴልአቪብ የመሄድ ዕድሉ ካለ ወደዚያ መጓዝህ በጣም ጠቃሚ ይሆናል . . ክርስትናን በምታጠናበት ጊዜ ደግሞ ወደ ሮማ ተጓዝ:: እስላምን ለማጥናት ወደ መካ ሂድ፣ግና አሸባሪዎቹ ወደ መካ እንድትገባ አይፈቅዱልህም !
- አነጋገርህ የቴልአቪቩን ጉዞ እንድቀበለው ስሜቴን አነሳስቷል፤ነገሩን አስብበትና ውሳኔዬን እነግረሃለሁ::

- ዕድለኛ ነህ፣አይሁዳዊያት ሴቶች ማራኪዎች፣ አጫዋቾች፣ የተለያየ የዘር ግንድ ያላቸውና ቁንጅናን በየዓይነቱ የተጎናጸፉ ናቸው:: ከሕንዳዊያት ቆነጃጅት በኋላ እነሆማ በአይሁዳዊያቱ ልትዝናና ነው፤ታድለሃል !

ጆርጅ በሐኪሙ አነጋገር ተከፋና ሊያፋጥጠው ፈለገ . .

- አንተም የተለያየ የትውልድ ሐረግ ባላቸው ሴት ታካሚዎችህ ትደሰትባቸው የለ? ! የተለያየ ዝርያ ባላቸው አማኝ ሴቶች ላይ የምታካሄደውን ጥናትህን ለማሟላት በቤተክርስቲያን ድግሶች ላይ ትዝናና የለም ወይ? !
- ማለት የፈለከውን በሚገባ ተረድቻለሁ:: ካትሪና ግሩም ድንቅ ናት፣ድንቅነቷ ግን ግራ ቀኝ ሳትል በፍጹምነት ሃይማኖቷን ብቻ ማገልገሏ ነው::
- ምናልባትም በሕንዳዊያት መደሰት ስለምትወድ ይሆናል፣አስቸጋሪውን ጥናትህን ሌሊቱን ሙሉ እስከ ንጋት ድረስ የማታቋርጠው::
- አሁንም ማለት የፈለከው በደንብ ገብቶኛል:: እስከ ንጋት የቆየነው ቤተክርስቲያኑ አጠገብ ባለው ሕንጻ ላይ በተነሳው የቃጠሎ አደጋ ምክንያት ነው . . (ወደ ጆርጅ ፊቱን አዞረና በምር አነጋገር ቀጠለ)) ፦ በሴቶች የመጫወት ረዥም ታሪክ ቢኖረኝም ካትሪና ግን ሙሉ በሙሉ ከሁሉም የተለየች ናት:: ካቶሊክ ሃይማኖቷንና እሱን ከመስበክ ውጭ በሌላ ነገር ፈጽሞ የማታስብ ሴት ናት::
- ሁል ጊዜ ስትገናኙና ስታመሹ ስለ ሃይማኖት፣ስለ ክርስትናና ስለ እምነት ብቻ ነው የምትወያዩት ብዬ እንዳምንልህ ነው የምትፈልገው? !
- በእርግጥ አይደለም፣ቤተክርስቲያኑ የተለያዩ የምሽት ድግሶችን የሚያዘጋጀው ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን ለመሳብና ሃይማኖት ለማስተማር ነው
- በነዚህ የጭፈራ ድግሶች ውስጥ ነዋ ብዙዎቹ የፍቅር ትረካዎች የሚጀምሩት? !
- ይህ እውነት ነው:: ካትሪና ግን ከቁንጅናዋ ጋርም የተለየች ሴት ናት:: ዓላማዋ ቁልጭ ያለ ነው፣ከዚያ ውጭ ስለምንም ነገር አታስብም:: ብቸኛ ግቧ ካቶሊካዊነትን ማገልገል፣ሰዎች በኢየሱስ ያላቸውን እምነት እንዲጨምሩ ማድረግ ነው፤ድንቅነቷም በዚህ ነው::
- አሃ፣ለዚህ ነዋ እስክትሰክሩ አብራችሁ የምትጠጡት፣ እምነታችሁ ጨምሮ ለሰው ልጆች ስትሉ ልትሰው? !

- አካሄድህ ፈጽሞ የማይዋጥልኝ ቢሆንም፣ካትሪና የዋለችልኝን ውለታ በከፊል መመለስ የሚገባኝ ይመስለኛል፤ከአስራ አምስት ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ልቤ ውስጥ እምነትን ቀስቅሳለች . . ልክ ነው በቤተክርስቲያኑ ድግስ ላይ መጠጥ ጠጥቻለሁ፣እኔ እንኳ ኤቲስት ነኝ፣ሃይማኖት አጥባቂዋ ካትሪና በመጠጣቷ ግን ተገርሜያለሁ::
- እምነት ሞልቶ ሲፈስ፣ለሰው ልጆች መድህን ራስን አሳልፎ መስጠት ከጫፉ ሲደርስ፣ጨዋታው ደርቶ፣ሞቅታውና ስካሩ ከመጨረሻው ደረጃ በደረሰ ጊዜ ምን ይሆን የተከሰተው ! !
- እውነቱን ለመናገር ካትሪና ብዙ ላለመጠጣት ብትጥርም፣ ከተከሰተው የእሳት አደጋ ችግር ከተገላገልን በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተለመደው በላይ በመጠጣቷ ተዳክማ ነበር::
- ያኔ አንድ ላይ በመንፈስ መጠቃችሁ፣ተዋሀዳችሁ ማለት ነዋ !
- እንዴ አንተ ጆርጅ ! ምንም አስነዋሪ ነገር በመካከላችን አልተከሰተም:: ግን መጠጡን ትንሽ ከልክ አሳልፋ ስለነበር አዞራትና ወደ መኪና ተሸክሜ ወስጄ ራሷን እስክታውቅ ድረስ ጠበቅኋት:: በዚህ ምክንያት ነው እስከ ንጋት የዘገየነው:: ከነቃች በኋላ በሁኔታው ሀፍረት ተሰምቷት አጥብቃ አመሰገነችኝ:: ለምስጋናዋ ምላሽ ሳምኳት፣ግን በአድራጎቴ መከፋቷ በግልጽ ይታይ ስለነበር መሳሳቴን ወዲያውኑ ተገነዘብኩ::::
- በጣም ጥሩ . . ድንቅ የፍቅር ትረካ ነው፣ሳጨበጭብላችሁ ይገባል !
- ወዳጇና ጎረቤቷ ሳሊ ሙሉውን ጊዜ ከኛ ጋር ስለነበረች የነገርኩህን ሁሉ ከርሷ ማረጋገጥ ትችላለህ:: የዚያ ሌሊት ፎቶግራፎች በሙሉ እዚያ ላይ ስለሚገኝ ከኔ የፌስቡክ ገጽም ማረጋገጥ ትችላለህ:: ይህን ሁሉ እንድነግርህ ያስገደደኝ ሰው የለም፣አቀራረብህ አፋጣጭ ቢሆንም፣እኔ ላንተ ግልጽ መሆን ስለፈለኩ ብቻ ነው የነገርኩህ:: ከሌላው ሰው በተለየ መንገድ አንተን ለምን እንደማይህ አላውቅም፣ምናልባት እኔም ያንተው ዓይነት ጉዳይ ስላለኝ ወይ በሌላ ምክንያት ሊሆን ይችላል::
- የኔው ዓይነት ጉዳይ? !
- በምነግርህ ነገር ትገረም ይሆናል፣የቆየ ውስጣዊ ሀሳብና ጭንቀት አለብኝ:: ምክንያቱን ሳላውቅ ካንድ ዓመት ወዲህ በጣም ተባብሶብኛል:: በጣም የሚደንቀው አንተ ጥያቄዎችን ይዘህ ወደኔ ከመጣህና ሃይማኖትን

www.path-2-happiness.com

ማጥናት ከጀመርኩ በኋላ ግን ለምን እንደሆነ እንጃ ጭንቀቱ መቀነስ ጀምሯል:: በጥያቄዎቹና በመልሶቹ ምክንያት ይሆን? ወይስ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄዴ ወይም በሁለቱም ምክንያት ይሆን? በነገራችንን ላይ ያንተው የጭንቀትና የመደበት ችግር አሁን እንዴት ነው? እየሰፈረብህ የሚያስቸግርህ የጥያቆዎችህ ማዕበልስ አሁን እንዴት ነው?

- አሁን አሁን በጣም እየቀነሰ መጥቷል:: ምናልባት ወደ ደስተኝነት መንገድ ለመድረስ በሚያስችሉ መልሶች ፍለጋ በመጠመዴና በሕንድ ጉዞዬ ምክንያት ሊሆን ይችላል ጭንቀቱን እንድረሳ ያደረገኝ::

- ‹‹የደስተኝነት መንገድ›› የሚለው ውብ አገላለጽ ነው::

- ልክ ነው፣አንድ ጊዜ መንገድ ላይ ያገኘሁት ሽማግሌ የነገረኝና በአንድ ካፌ ያገኘሁት አስተናጋጅ እውስጤ ያስጸረሰው አባባል ነው::

- ሁሉም ሰው በደስተኝነት ጎዳና መጓዝ ይፈልጋል:: እንዲያውም ሁሉም በዚያ ጎዳና ላይ እንዳለ አድርጎ ራሱን ይቆጥራል:: እውነታው ግን እውነታነቱን እንደጠበቀ ይቆያል::

- ምን ማለትህ ነው?

- የያንዳንዱ ሃይማኖት፣ቡድን፣ጎራ ወይም ፈለግ ተከታዮች በደስተኝነት ጉዳና ላይ ነን ብለው ይገምታሉ፤በደስተኝነት መንገድ ላይ ያሉት እነሱ ብቻ መሆናቸውን ያምናሉ !! (ፈገግ ብሎ ቀጠለ) ፦ ይህ መቼም አስቂኝ አጋጣሚ ነው !!

- ይሁንና እኔና አንተ ግን ያለ ጥርጥር በደስተኝነት መንገድ ላይ አይደለንም፣ብንሆን ኖሮ አሁን ባለንበት ጭንቀትና ሀሳብ ውስጥ ባልኖርን ነበር !

- ለማንኛውም አብረን ያደረግነውን በከፊል ጠቅለል እናደርገው . . ደስተኝነት የሚገኘው ለታላላቆቹ ጥያቄዎች በሚሰጡ ምላሾች ውስጥ ነው፣የኤቲዝምን አመለካከት ውድቅ በሚያደርግ ሁኔታ መልሶቹ መገኘት ያለባቸው ከሰው ልጅ ሳይሆን ከፈጣሪው በኩል ነው በሚለው ላይ ተስማምተናል:: ከዚያም ይህ ፈጣሪ አምላክ ያስተላለፈው ምድራዊ ሃይማኖት ሳይሆን መለኮታዊ ሃይማኖት ነው በሚለው ላይም ተግባብተን፣አሁን ይህ መለኮታዊ ሃይማኖት የትኛው እንደሆነ በመወሰን ሂደት ላይ እንገኛለን::

- የዚህ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው በደስተኝነት መንገድ ይጓዛሉ ተብለው

የሚታሰቡት:: ካትሪና ከመጀመሪያው ወዳለችኝ አቅጣጫ ወደሚያደርሰኝ እየተጓዝኩ ነው የሚል እምነት አለኝ:: ይሁን እንጂ ተጣድፌ እርከኖችን ማምከን አልፈልግም:: አሁን አሁን የነዚህ ጥያቄዎች ጫናና ውስብስብነት እየቀነሰልኝ መጥቷል፤ታላላቆቹን ጉዳዮች በጥልቀትና ሳላካብድ ቀለል ባለ መንገድ እያስኬድኩ መሆኔ ይሰማኛል::

- በጌታ መንገድ ሁሉንም ነገር የሰዋችው ካትሪና ትክክለኛ መሆን የሚገባት ነው፤ይሁን እንጂ በጀመርነው መንገዳችን እንዝለቅ፤ከቴልአቪብ የምትመለስበትን ጊዜ እጠብቃለሁ፣ ስትመለስ ውይይታችንን እንቀጥላለን::

- ተስማምተናል፣ዛሬ አራዝምብሃለሁ ይቅርታ አድርግልኝ . . መልካም ፈቃድህ ከሆነ ወደ ቴልአቪብ ከተጓዝኩ ቀጠሯችን ከሁለት ሳምንት በኋላ ነው፣ካልተጓዝኩ ግን መጪው ሳምንት ይሆናል::

- ስለ አይሁዳዊነት ለማንበብ በቂ ጊዜ እንድናገኝ ቀጠሯችን ከሁለት ሳምንት በኋላ ነው:: መረጃህን ለማበልጸግ ወደ ቅድስት አገር መጓዙን ችላ አትበል::

- ‹‹ቅድስት አገር›› የሚለው ውብ አገላለጽነው !

- አዎ፣ለሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ቅድስት አገር ነች:: በዚህ ምክንያት ነው በውስጧና በአካባቢዋ ሁሌ ጦርነቶችን የምናስተውለው::

- ለመጓዝ ጥረት አድርጋለሁ፣እስኪ እንዴት እንደማደርግም አስብበታለሁ::

ጆርጅ ከቶም ዘንድ ሲወጣ በራድ መሰሪ ፈገግታን በተላበሰ ፊት ከውጭ እየጠበቀው ነበር . .

- ካትሪና እንዴት ነች? ትተሃት ወደ ቶራ ቦራ ልትሄድ ነው?

- ቶራ ቦራ? ! !

- ሰው ሁሉ በአጭር ቃላት የሚጫወትብህ ተራ ሞኝ አትሁን !

- ምን ማለት ነው?

- ምንም አይደለም፣ካትሪና ማራኪ ቆንጆ ናት፣ቶምም መልከ መልካም ሎጋ ነው:: መሳፈር ትችላለህ ግን ብልህ አስተዋይ እንጅ ሞኝ ተላላ አትሁን::

ጆርጅ መልስ አልሰጠም፣ወዲያውኑ ነው በንዴት ጥሎት የሄደው:: በቶምና በበራድ አነጋገር መካከል ያስተዋለው ይህ መመሳሰል አእምሮው ውስጥ እየተመላለሰ ነው . . ለመሆኑ በራድ ከቶም ጋር የተነጋገርኩትን

www.path-2-happiness.com

ሰምቶ ይሆን? ወይስ ልብ ለልብ መናበብ የሚሉት ነው?!

(5)

ጆርጅ ለአደም መደውሉን ቢቀጥልም ምላሽ አላገኘም። ምን ነክቶት ይሆን ብሎ በጣም አሰበ፣ሰጋለት። ካንድ ጊዜ በላይ ወደ ቤቱ ሄዶ አላገኘውም . . ካትሪናም የጆርጅ መጨነቅ ተሰምቷታል . .

- በጣም የተጨነቅህ ትመስላለህ . . ምንድነው ነገሩ?
- አስተናጋጄን ወዳጄን አደምን ማግኘት አልቻልኩም። ብዙ ጊዜ ደወልኩ፣ወደ ቤቱም ካንድ ጊዜ በላይ ተመላልሻለሁ!
- በሽብር ጥቃቱ ምክንያት ጉዳት እንዳያገኝህ ስጋት ነበረኝ። ተጨንቀህ ሳይህ አሳሰበኝ። አደምን በጣም ትወደዋለህ ማለት ነው? !
- ቀለል ያለ የማይከብድ የማያካብድ ሰው በመሆኑ ብዙ ጠቅሞኛል፣የሚናገረው ሁሉ በጣም ያረካኛል።
- የሥራ ባልደረቦቹ ምን ይላሉ?
- የዩኒቨርሲቲ ወረቀቱን ጽፎ ለማጠናቀቅ ፈቃድ ላይ ነው ይላሉ፣ቀደም ሲል እንደነገርኩሽ ሃይማኖቶችን የሚያጠና ተማሪ ነው።
- ፈቃዱ መቼ ነው የሚያበቃው?
- ከነገ ወዲያ ያበቃል። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ላማክረው ስለፈለግሁ ላገኘው ቸኩያለሁ . . በነገራችን ላይ ወደ ቁድስ ወይም ቴልአቪቭ ወደሚባለው አገር ለሥራ እንድጓዝ ጥያቄ የቀረበልኝ በመሆኑ ላማክርሽ ፈልጌ ነበር።
- ወደ ቅድስት አገር? !
- አዎ፣ኩባንያችን ካንድ የአይሁድ የደህንነት ኩባንያ ጋር የሥራ ውል ለመፈራረም ይፈልጋል።
- ገና አሁን ነው ከጉዞ የተመለስከው፣ሳታርፍ ሌላ ጉዞ አድካሚ እንዳይሆንብህ ስጋት አለኝ።
- አድካሚ አይሆንም፣ይሁን እንጂ ካንቺ ከማይክልና ከሳሊ ጋር ተጨማሪ ጊዜ ማሳለፍ ነበር ፍላጎቴ። ጉዞው ብዙም አልሳበኝም ነበር፣ዛሬ ከቶም ጋር ስገናኝ ግን እንዳልቀር በጣም አበረታቶ ገፋፋኝ።
- ለምን?

- የአይሁድን ሃይማኖት በቅርበት ለማወቅ መልካም አጋጣሚ ይሆናል ነው የሚለው።
- በዚህ ልታምነው ይገባል። ይህ ብቻ ሳይሆን የሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ቅድስት አገር በመሆኗ ሦስቱንም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ለማወቅ መልካም አጋጣሚ ነው።
- አንቺስ ምን ትያለሽ?
- ቶም ያነሳው ነጥብ ትዝ አላለኝም ነበር፣ይጠቅመኛል ብለህ የምታምን ከሆነ ተጓዝ፣ከጠቀመህ ደስተኛ ነኝ፤እኔና ልጆቼ በሰላም ተመልስህ የምትመጣበትን በጉጉት እንጠባበቃለን።
- ቶም ያነሳው ነጥብ አሳማኝ ቢሆንም ብዙ ጉጉት አላሳደረብኝም ነበር፣ለማንኛውም ጉዞው በታጣም አጠር ያለ እንዲሆን ለማድረግ እሞክራለሁ።
- አንተ ዕድለኛ ነህ ወደ ድንቃድንቆቹ አገር ተጉዘህ አሁን ደግሞ ወደ ጦርነት ፍጥቻዎችና የፍልሚያዎች አገር ትጓዛለህ!
- ዕድለኝነቴማ በድንቋ ባለቤቴ ባንቺ ነው።
- እኔም አንድ ገጸ በረከት ላቀርብልህ እፈልጋለሁ።
- ምን ይሆን?
- ከጉዞህ ተመልሰህ ትንሽ ካረፍክ በኋላ ፈቃድ ትወስድና ሁላችንም አንድ ላይ ወደ ሮም እንጓዛለን። በዚህም የድንቃድንቆችን አገር፣የጦርነት ፍጥጫዎችን አገርና የአብያተ ክርስቲያናትን አገር ያዳረስክ ትሆናለህ። ካቶሊክን ወደ አገሩ ሄደህ በቅርበት በማየት የደስተኝነት መንገድ የምትለውን ነገር ትተዋወቃለህ።
- እዚያ ሆኜ ቶም እንደሚፈልገው ክርስትናን ይበልጥ ማወቅ እችላለሁ። . . ለመጓዝ የተስማማሁ መሆኔን ነገ ለካኽ ሳልነግር አልቀርም፣ይህ አስጨናቂ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሳይነሳ ባልሄድ ግን ደስ ይለኛል . . ለደህንነታችሁ እርግጠኛ ሳልሆንና ወንጀለኞቹ አሸሪዎች ለፍርድ ሳይቀርቡ አልጓዝም።
- የፍንዳታው ዋነኛ ተጠያቂ ነው ተብሎ የሚገመተው ፓኪስታናዊ አሁንም ገና አልተያዘም፣ወዳጆቹና በዙሪያው የሚገኙ ሙስሊሞች ግን ቁጥጥር ሥር ውለዋል።

www.path-2-happiness.com

- የት አባቱ ያመልጣል፣ዛሬ ወይም ነገ ጋማውን ይይዛሉ:: ሽብርተኝነትንና ግድያን በሁሉም ገጽታዎቹ እንዴት እንደምተጠላው ልነግርህ አልችልም !

ጆርጅ ወደ ሥራ ቦታው እንደ ደረሰ ጉዞውን መቀበሉን ለማሳወቅ ወደ ካኽ ቢሮ አመራ:: ጉዞው አጠር ያለና ከአራት ቀናት ያልበለጠ እንዲሆንም ጠየቀው::

- አራት ቀን በጣም በቂ ነው::
- ተልእኮዬ በግልጽ ተዘርዝሮና ተለይቶ ተቀምጧል?
- አዎ . . የኦርሻሌም ሴኩሪቲ ኩባንያ የኤሌክትሮኒክስ ደህንነት ጥበቃ ውሎችን ከኛ ጋር ይፈራረማል፣ከሞላ ጎደል በሁሉም ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ከስምምነት ደርሰናል::
- መሄድ ሳያስፈልግ ለምን ውሎቹን ብቻ አንልክላቸውም?
- የኩባንያው የቴኒክ መምሪያ ኃላፊ መመለስ የሚገባቸው ብዙ ጥያቄዎች አሏት፣በጣም ብዙ ዝርዝር ማብራሪያዎች ትጠብቃለች:: እሷን በአካል ተገኝቶ ማሳመን ግዴታ ነው:: የስምምነቱ ዋነኛ ተቀናቃኝ እሷ ናት:: የመጨረሻው ውሳኔ የርሷ ነው፣በጉዳዩ ላይ የመወሰን መብት ያላት የመጨረሻው ሰው ናት::
- እንዲህ ከሆነ በዝርዝር ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ በቂና የተሟላ ግንዛቤና መረጃ ሊኖረኝ ይገባል:: የተለዋወጣችሁትን ዝርዝር የተቃውሞ ነጥቦቿን የግድ ማንበብ ይኖርብኛል::
- ልክ ነህ፣ይህ በጣም አስፈላጊ ነው . . ወደዱም ጠሉ በመጨረሻ ውሉን መፈረማቸው ግን አይቀሬ ነው::
- በጣም እርግጠኛ የሆንክ ትመስላለህ !
- በብዙ ምክንያት፣አንደኛ፦ እስራኤላውያን የአሸባሪው ሐማስ ፎቢያ አለባቸው፣ሌላው ቀርቶ ለቴክኖሎጂ አቅሙ እንኳ ስጋት አላቸው፤በመሆኑም የደህንነት ጥበቃ ውሎችን ከኛ ጋርም ሆነ ከሌሎች ጋር ለመፈራረም አያመነቱም::
- እውነት አላቸው፣አሸባሪዎች ርህራሄ የላቸውም፣እኛ ራሳችን ሰሞኑን እዚህ ለንደን ውስጥ ያለንበትን ሁኔታ አታይም? !
- ግና አይሁዶች ከሐማስም ሆነ ከሌላው ሁሉ የከፋ አሸባሪዎች ናቸው !

- እንጃ ሊሆን ይችላል፣የማውቀው ነገር ቢኖር አሸባሪዎች ለንደን ውስጥ ያለ አንዳች ርህራሄ፣ሃይማኖትም ሆነ ሕሊና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የመግደል ፍላጎት የነበራቸው መሆኑን ነው !
- አሁን ስለ ሽብርተኝነት ተወኘና . . ሁለተኛው ምክንያት ፦ የቴክኒክ መምሪያ ኃላፊዋ ሌቪ አይሁዳዊት፣አለቃዋም አይሁዳዊ መሆናቸው ነው::
- አልገባኝም፣የርሷና የአለቃዋ ይሁዳዊ መሆን ውሉን እንዲፈርሙ እንዴት ያደርጋቸዋል?
- ሁለቱም ይሁዲዎች እንደ መሆናቸው እኔ ከማንም በላይ አውቃቸዋለሁ:: አለቃዋ ቤንያሚን ለራሱ የግል ጥቅም ብሎ ውሉን ከኛ ጋር መፈራረም ይፈልጋል:: የቴክኒክ ኃላፊዋ ደግሞ ከርሱ ፍላጎት ውጭ መሆን አትችልም፣ አለዚያ የርሷን ጥያቄዎች ውድቅ ያድርግባታል፣ከሃይማኖት ተነስታ ነው ቃሉን የምትፈጽመው::
- አንተስ አይሁዳዊ አይደለህምን?
- እናቴ አይሁዳዊት ናት፣ስለዚህ እኔም አይሁዳዊ ነኝ ማለት ነው:::: ይህ ሦስተኛው ምክንያት ነው:: ለዚህ ነው ከኔ ጋር ስምምነቱን ለመፈራረም የተስማሙት . . አለዚያማ እኔ ሀብትና መዝናኛን የሚያስገኝልኝ ካልሆነ በስተቀር ስለ ሃይማኖት ምንም ደንታ የሌለኝ ሰኩላሪስት ዓለማዊ ሰው ነኝ . . ኣ፣በነገራችን ላይ ሌቪ ገና የ25 ዓመት ጉብል ናት፣የዓለም ውብ ቆንጆ ነች:: ከርሷ ጋር ለመዝናናት ከፈለግህ ለቤንያሚን ንገረውና ወዲያውኑ ትቀርብልሃለች:: ቤንያሚንን በተመለከተ ውሉ እንዲፈጸም ካደረገ ለግሉ አንድ መቶ ሺ ዶላር ለመስጠት ነው ቃል የገባሁለት::
- አንድ መቶ ሺ ዶላር አልበዛም? !
- በጣም ብዙ ነው፣ግና በመደበኛው የስምምነቱ አጠቃላይ ዋጋ ላይ አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ዶላር ጨምሬ ስለተስማማ ነው በመቶ ሺው የተስማማሁለት::
- ምን ዓይነት ወራዳነት ነው ጃል !! ይህ በኩባንያውና በአገርም ላይ የሚፈጸም ክህደት ነው፣ቢዝነስ አይደለም !
- ገንዘብ እኛ ዘንድ ሌላ ነገር ነው፣እኛ አይሁዶች አውነተኞቹ ነጋዴዎች ነን:: በዚህ ምክንያት ነው በመላው ዓለም ንግድና ቢዝነስ በኛ ቁጥጥር ሥር የሆነው፣በፍቅረ ነዋይም ሆነ በንግድ ሥራ ማንም ከኛ አይወዳደርም::

www.path-2-happiness.com

-አነጋገርህ የአይሁድ ሃይማኖትንና የአይሁዳዊ ሰው ሰብእናን ከሩቁ እንድፈራ አድርጎኛል።

-አሃሃ፣‹‹አንድን አይሁዳዊ ሰላም ብለህ ከጨበጥክ ከሰላምታው በኋላ ጣቶችህን ቁጠራቸው፣ሙሉ ሆነው ካገኘሃቸው በትክክል መቁጠር ስለመቻልህ እርግጠኛ ሁን›› ተብሎ አይደል የሚተረተው . . ዋናው ነገር ለቤንያሚን መቶ ሺውን ስጠውና ነገሮች እንዴት ቀላል እንደሚሆኑ ታያለህ።

-ስለ ስምምነቱና ስለ ባሕርያቱ የውል ስምምነቱን ረቂቅና ተያያዥ ጽሑፎቹን ካነበብኳቸው በኋላ ተነጋግረን እናጠቃልላለን።

-መልካም . . ለቀጣዩ ሳምንት የአይሮፕላን ቦታ አስይዛለሁ፣በዚህ ሳምንት ስምምነቶቻችንና ስብሰባዎቻችንን እንጨርሳለን።

ጆርጅ የውል ስምምነቱን ረቂቅና ተያያዥ ጽሑፎችን ከዝርዝር ቴክኒካዊ ጉዳዮች ጋር በማንበብ ላይ ተጠምዶ እስከ ሥራ ሰዓቱ ማብቂያ ድረስ ከቆየ በኋላ ንባቡን ባይጨርሰውም ዘግይቶ ወጣ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሞባይሉ ዝግ ወደ ነበረው አደም ደጋግሞ ደውሎ ነበር . . ወደ ቤት ተመለሰና የዕለቱን ዜና መከታተል ጀመረ፤ከጉዞው በፊት ፓኪስታናዊው ቁትጥጥር ሥር ቢውል ምኞቱ ነበር።

የፍንዳታውን ፈጻሚ በተመለከት አዳዲስ ግምቶች መሰጠታቸውን፣ተጨማሪ ሰዎች መያዛቸውንና የተያዙት ከእስላማዊ ሽብርተኝነት ጋር ግንኙነት የሌላቸው የተገንጣዩ ሲታ ቡድን አባላት መሆናቸውን በዜናው አዳመጠ . . ምን አዲስ ነገር እንዳለ እየጠየቀች ካትሪና ከጎኑ ተቀመጠች . .

-አስደናቂው የሽብር ጥቃቱ ዜና፣ ፈጻሚዎቹን በተመለከተ አዲስ መረጃ መሰጠቱ ነው !

-ለማስመሰል የሚደረግ ባዶ አነጋገር ነው፣ከአሸባሪዎቹ ሙስሊሞች በስተቀር ይህንን ማንም ሊፈጽም አይችልም።

-ተገንጣዩ የሲታ ንቅናቄ ነው አዲሱ ተከሳሽ።

-ምናልባት አሸባሪዎቹ ጥንቃቄአቸውን ቀንሰው ዘና በማለት እንዲዘናጉ በማድረክ ፓኪስታናዊውን ቁጥጥር ሥር ለማዋል ሲባል የተሰጠ የማሳሳቻ መግለጫ ሊሆን ይችላል።

-በፖለቲካ ዓለም ሁሉም ነገር ሊሆን ይችላል !

(6)

በቀጣዩ ቀን ጆርጅ በጉዞው ጉዳይና የውል ስምምነቶቹን በማዘጋጀት ላይ ተጠምዶ ቢውልም ለአደም መደውሉን አላቋረጠም፤ይሁን እንጂ የአደም ስልክ አሁንም እንደ ተዘጋ ነው . . ኢሜል ላከለት፣በፌስቡክ ገጹም መልክት አስቀመጠለት። ከሥራ ባልደረባው አስተናገጅ ማወቅ እንደተቻለው ፈቃዱ ዛሬ ስለሚያበቃ ወደ ሥራ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል። ከጉዞው በፊት መገናኘት ጽኑ ፍላጎቱ ነው፣ለጆርጅ ይህ ብዙ ማለት ነው . .

ከሥራ ሰዓት በኋላ . . ጆርጅ በካፌው በኩል አልፎ አደም መምጣት አለመምጣቱን ጠየቀ . . አላገኘውም !

-ዛሬም አልመጣም።

-የወሰደው ፈቃድ ገና አላበቃም?

-አብቅቷል ግን አልመጣም፣ አልደወለምም፣ ይሄ ልማዱ አልነበረም !

-መቼ ይመጣል ብለህ ትገምታለህ?

-አላውቅም፣ዛሬ ሥራ መጀመር ነበረበት፣የሌለ ሰው ችግሩን እራሱ ነው የሚያውቀው።

-አመሰግናለሁ፣ከመጣ ጆርጅ ብዙ ጊዜ ተመላልሶ ፈልጎህ ነበር ብለህ ንገርልኝ።

-እሸ ጥሩ እነግረዋለሁ።

ጆርጅ ወደ መኖሪያ ቤቱ የተመለሰው የአደም ጉዳይ በእጅጉ እያስጨነቀው ነበር፣በድንገት መሰወሩ ስጋት አሳድሮበታል፣እሱን ለማግኘት ያልተጠቀመው የመገናኛ ዘዴ የለም፤ስልክ፣ኢሜል፣ ፌስቡክ፣ ወደ ቤቱና ወደ ካፌው በተደጋጋሚ መሄድ . . ፈጽሞ ሊያገኘው አልቻለም !

-እንደምን ዋልክ የኔ ፍቅር፣ወዳጅህን አደም አገኘህ?

-አላገኘሁትም። የወሰደው ፈቃድ ያበቃ ቢሆንም ዛሬም ሥራ አልገባም !

-በሽብር ጥቃቱ ምክንያት ጉዳት ደርሶበት እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

-እኔም ተስፋዬ ነው፣አዲስ ነገር አለ? ሽብርተኛው ተያዘ?

-የሚያሳዝን ነው አልተያዘም . . ቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ዛሬ መለቀቃቸው ከአፍታ በፊት በዜና ታውጇል!

-ወንጀለኞቹ ተለቀቁ !

-በምርመራ የተረጋገጠው ፍንዳታውን ያደረሱት የተገንጣዩ የሲታ ንቅናቄ አባላት መሆናቸው ነው።

-አሃሃ፣ፊቱ ምንም ምቾት ያልሰጠኝ ሰውየ ከሪሙሏህ ያለኝን ነገር አስታወሰሽኝ ፦ ‹‹ሽብርተኛ ከናንተ የፖለቲካ ዓላማ ጋር የማይስማማ ነው፣ከናንተ ጋር ከተስማማ አሸባሪውም ጀግና ነው›› ነበር ያለኝ፣እውነቱን ይመስለኛል . . !

-እኔ ማመን አልችልም፣የፍንዳታ ጥቃቱን ያደረሰው ፓኪስታናዊው ነው ብዬ አምናለሁ። መጀመመሪያ ላይ ማንነቱን በደህንነት ካሜራዎች አማካይነት መታወቁን ነግረውን አልነበረም?

-ከሪሙሏህ ምናልባት እውነቱን ሳይሆን አይቀርም የተናገረው። የሲታ ንቅናቄ ተጠርጣሪዎቹን ቁጥጥር ሥር አውለዋል?

-አዎ፣ጥቃቱ ፖለቲካዊ የወንጀል ድርጊት እንጂ ሽብርተኝነት አይደለም እያሉ ነው።

-ወንጀለኞቹ ተለወጡና ወንጀሉ ከሽብርተኝነት ወደ ፖለቲካ ወንጀልነት ተለወጠ ማለት ነው? !!

-ፈጻሚው ሙስሊም ከሆነ ሽብርተኝነት ይሆናል።

-አሃሃ፣ይህማ በትክክል የከሪሙሏህ አባባል ነው። ዋናው ነገር እውነተኞቹ ወንጀለኞች በቁጥጥር ሥር በመዋላቸው ለንደን አስተማማኝ ሰላም ማግኘቷ ነው።

የጆርጅ ስልክ ሲጮህ ፈጥኖ አነሳው፣ደዋዩ አደም እንዲሆን ምኞቱ ነበር፣በእርግጥም አደም ነበር . . በደስታ ሲቃ አነጋገረው . .

-አንተ አደም በመጨረሻ ተገኘህ፣መጥፋትህ በጣም ነበር ያሳሰበከኝ።

-አዎ፣አጭር ጉዳይ ነበረኝ ካፍታ በፊት ነው ያጠናቀኩት።

-ጥናትህን አበቃህ?

-ጥናትና ምርምሬ ይበልጥ ጥልቀት እዲኖራቸው ነው የተደረገው፣ይህን እንተውና አንተ እንዴት ነህ?

-ጥሩ ሁኔታ ላይ ነኝ፤ላገኝህ እፈልጋለሁ፣አሁን ልምጣ?

-በሥራው ምክንያት ትንሽ ስለ ደካከመኝ ነገ ከሥራ ሰዓት በኋላ ብትመጣ

ምን ይመስለሃል?

-ጥሩ ከአስራ አንድ ሰዓት በፊት አንተ ዘንድ እሆናለሁ። በደስተኝነት ሬስቶራንት ለእራት ግብዣ ጠርቼሃለሁ።

-ተስማማን፣ነገ እጠብቀሃለሁ።

ጆርጅ ስልኩን ዘጋ፣ፊቱ በደስታ ፈክቷል . .

-አስተናጋጁን አግኝተህ በማናገርህ በጣም የተደሰትክ ትመስላለህ!

-አዎ፣በአነጋገሩ እውነተኝነት፣አላማካበድና ጥልቅነት ለምን እንደሚሰማኝ አላውቅም !

-ይሁዲ ነው ወይስ ክርስቲያን ነው? ካቶሊክ ይሆን ወይስ ፕሮቴስታንት ?

-እኔ አልጠየኩትም . . ሳገኘው በዚህ ጥያቄ ነው የምጀምርለት . .

በተስማሙበት የቀጠሮ ሰዓት ካፌው ፊት ለፊት መኪናው ውስጥ ጠበቀው፣ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አደም መጣና ወደ መኪናው ገባ።

-አንተ ሰውየ የት ገብተህ ነው፣በጣም ነው ያሰብኩት?

-ይህ ያንተ ሰናይነት ነው፣በጣም ይቅርታ እጠይቃለሁ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ለመልክቶችህ ምላሽ መስጠት አልቻልኩም . . የደስተኝነት መንገድ ፍለጋው ዬት እንደደረሰ አብስረኝ፣የጥያቄዎችህ መልሶችስ እንዴት ሆኑ? የሕንድ ጉዞህስ? . .

-የሕንድ ጉዞዬ በጣም የተሳካና በመረጃ የበለጸገ ነበር። በጣም ተደስቼበታለሁ . . ወደ ሬስቶራንቱ ስንደርስ ጨወታንን እንቀጥላለን . .

-ግዴለም . . የተቃረብን መሰለኝ . .

ሬስቶራንቱ ውስጥ ጆርጅና አደም ለሁለት ሰዎች የተዘጋጀ ጠረጴዛ ይዘው ተቀመጡ። አስተናጋጁ የምግብ ሜኑ ይዞላቸው መጣ . . አደም ጆርጅን እያናገረ ሜኑውን ማገላበጥ ያዘ . .

-ይህ ውብ ሬስቶራንት ነው . .

-ተመራጭ ሬስቶራንትህ ይመስላል . .

-ስሙ ያስደስተኛል። ደስተኝነትን እወዳለሁ። የሁሉም የምድራችን አስተዋዮች የጋራ ግብ ሆኖ ይታየኛል። በነገራችን ላይ የሬስቶራንቱ ባለቤት የሌላ አገር ዜጋ ይመስላል፣ከየትኛው አገር ይሆን?

-እንግሊዝ አገር የማሌዝያ ሬስቶራንቶች ጥቂት ናቸው፣ይህ የማሌዝያ

www.path-2-happiness.com

ሬስቶራንት ነው፤ማሌዢያን ጎብኝተህ ታውቃለህ?

- አልሄድኩም . .
- ማሌዢያ መጎብኘት ከምፈልጋቸው አገሮች አንዷ ናት፣እስካሁን አላየኋትም:: ተፈጥሯ ልክ እንደ ሕዝቧ ተፈጥሮ ማራኪ ነው ይባላል:: ሕዝቡ በጣም ቀለል ያለ በጣም ገር የሆነ የሚመች ሕዝብ ነው::
- ማቅለልና አለማካበድ አንዳንድ ጊዜ ጥልቅነትን የሚያመለክት ሲሆን አንዳንዴ ደግሞ ጅላጅልነትና ጅንፈልነትን ያመለክታል::
- እዚህ ግን ጥልቅነትን ነው የሚያሳየው:: ማሌዢያ ወደፊት የተራመደች በተለይም በቴክኖሎጂ መስክ ፈጣን ዕድገት በማስመዝገብ ላይ የምትገኝ አገር ነች::
- ጥልቀት ያለው ቀላልነት ያስደስተኛል:: (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ ወይም በሌላ አባባል ቀለል ያለ ጥልቅነት . . እሺ የሕንድ ጉዞ ጫወታህን ቀጠል . .
- መጀመሪያ ምግቡን እንዘዝ . .

ጆርጅ አስተናጋጁን ጠራና ሁለቱም ትእዛዛቸውን ነገሩት . . አስተናጋጁ ትእዛዛቸውን ተቀብሎ ሄደ . .

- የሕንድ ጉዞው ጥያቄዎቼን በጉልህ መልሷል፤ወደ ደስተኝነት መንገድ እየተጓዝኩ ነኝ የሚል እምነት አለኝ::
- በጣም ጥሩ !
- ጉዞው ከነገርኩህ የቶምና የካትሪና ጉዳይ በስተቀር ምንም ዓይነት እንከን አልነበረበትም:: ለለገሰገኝ ምክር ከፍተኛ አክብሮት አለኝ:: በጣም አስቸጋሪ በሆነ የስነ ልቦና ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ:: የነገርከኝ ነገር ትክክለኛ እንደነበር አሁን ለመረዳት ችያለሁ ማለት እችላለሁ::
- የትኛው ነገር?
- ጥርጣሬህ ትክክለኛ ላይሆን ይችላል ብለኸኝ ነበር:: ቶም ጉዳዩን በዝርዝር ነግሮኛል፣አሁን ለምን አምኜ እንደተቀበልኩትና ለምን ከቀድሞ የተለወጠ መስሎ እንደታየኝ ግን አላውቅም::
- ዕድሉን ከሰጠናቸው ሰዎች ሁሉ ሊለወጡና ሊሻሻሉ ይችላሉ . . (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ መለኮታዊ ሃይማኖቶችን ከሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች

ጋር የማነጻጸሩ ነገርስ እንዴት ሆነ?

- ያለ ምንም ጥርጥር መለኮታዊ ሃይማኖቶች ተቀዳሚና ተመራጭ ናቸው::
- በልበ ሙሉነት እርግጠኛ የሆንክ ትመስላለህ !
- አዎ፣በሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች ውስጥ ይሆናል ተብሎ በማይገመት ሁኔታ መደናበር መኖሩን ነው ያስተዋልኩት:: (ሳቀና ቀጠለ) ፦ እስኪ ይታይህ በአይጦች የሚያመልኩ፣በጥንዝዛ የሚያመልኩ፣በቅርጻቅርጽና በድንጋይ የሚያመልኩ . . ሰዎች በዚህ ዓለም ላይ መኖራቸው በጣም አስገራሚ ነው:: በእርግጠኝነት ለጥያቄዎቼ ምላሽ የሚሰጠኝ አምላክ አይጥ፣ጥንዚዛ፣ጣዖት ወይም ሌላ እንስሳ ሊሆን አይችልም::
- ስለዚህም መለኮታዊ ሃይማኖት ብቻ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሆነሃል ማለት ነው?
- በትክክል ከመለኮታዊ ሃይማኖቶች ከአይሁዳዊነት፣ ከክርስትናና ከእስላም መካከል በአንዱ ውስጥ ብቻ ነው ማግኘት የሚቻለው . .
- የሚቀጥለው እርምጃህ ምድነው የሚሆነው?
- ከመለኮታዊ ሃይማኖቶች ጋር አንድ በአንድ መተዋወቅ ይሆናል:: በአይሁዳዊነት እጀምራለሁ . . በነገራችን ላይ ወዳጄ ሃይማኖትህ ምንድነው?
- ምን ይሆናል ብለህ ነው የምትገምተው? ስሜ አደም ነው፣የሰው ልጆች ሁሉ አባት:: የአባቴ ስም ደግሞ የነብያትና የሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች አባት ስም የሆነው ኢብራሂም ነው::
- እንዴት ማለት?
- አደም የመላው ሰው ዘር አባት ስም ነው:: ኢብራሂም ደግሞ የነብያት አባት ስም ነው፣ሙሴ ኢየሱስና ሙሐመድም የኢብራሂም ልጆች ናቸው::
- አንተ ከነብያቱ መካከል ማንን ነው የምትከተለው?
- ሦስቱንም ሃይማኖቶች ለማወቅ አብረን ብንጓዝ ምን ይመስለሃል፣ምናልባት ሃማኖቴን እለውጥ ይሆናል!
- እንደ ባለቤቴ ካቶሊካዊ ትመስላለህ . . ኦ፣ምግቡ ደርሷል . . በዚህ ነገር ተጽእኖ ያሳደርክብኝ ይመስለኛል:: የፍልስፍና ባሕሪ አንዳንዴ ነገሮችን ማቅለል ሳይሆን ማወሳሰብ ቢሆንም . . ይህን የማቅለል ፍልስፍናህን

www.path-2-happiness.com

አዘውትሬ ስደጋግመው ነው ራሴን ያገኙሁት:: እንግሊዛዊ ጠባያችን ሆኖ አንዳንዴ ነገሮችን ከማቅለል ይልቅ ማካበድና ማወሳሰብ ይቀናናል::

- ማቅለል፣ገርነት፣ፈገግታና ደስተኝነት ሁሌም የተያያዙ ቃላት ናቸው::

- በዚህ ልክ ደግሞ ማወሳሰብ፣ እርስ በርስ መቃረን፣ አስቸጋሪነት፣ደካማነትና መናጢነት እርስ በርሳቸው የተያያዙ ቃላት ናቸው . . አልነገርኩህም ሐኪም ቶም ወደ ቴልአቪብ እንድሄድና አይሁዳዊነትን በቅርበት እንዳውቅ ሀሳብ አቅርቦልኛል:: በዚህ ላይ ምን ትላለህ?

- በጣም ጥሩ ነው፣ወደ ቅድስት አገር ትጓዛለህ ማለት ነው !

- ካቶሊካዊ ነህ ብየህ የለም?

- ጉዞው አይሁዳዊነትን ብቻ ሳይሆን ሦስቱንም ሃይማኖቶች ለማወቅም ጠቃሚና አጋዥ ሊሆን ይችላል::

- ወደ ቴልአቪብ እንደምሄድ ስነግራት ካትሪናም ልክ እንደዚሁ ነበር ያለችኝ::

- ይህን ለማለት የግድ ካቶሊካዊ መሆን የለብኝም:: ይህ ሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው . . አገሩ በርካታ የጦርነት ውሎዎችን ያስተናገደ ምድር ነው:: ጉዞህ አይሁዳዊነትንና ሌሎቹንም በይበልጥ ለማወቅ በጣም ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ:: ያ ማለት ግን ስለ ሃይማኖቶቹ ማንበብን ይተካል ማለት አይደለም::

- ምን ማለት ነው?

- ለጉዞው ስንት ቀን ቀረህ?

- አራት ቀናት::

- እንድታነብ ነው ሃሳብ የማቀርበው፣እኔም ካንተ ጋር ስለ ትልቁ ሃይማኖት ስለ አይሁዳዊነት በብዛት አነባለሁ::

- አይሁዳዊነት ትልቅ ሃይማኖት ነው ! አንተ አይሁዳዊ ነህ እንዴ?

- የሦስቱም መለኮታዊ ሃይማኖት ተከታዮች በሙሴ ያምናሉ፣ይህ ግን አይሁዳዊ ለመሆናቸው ማስረጃ አይሆንም:: ያላንዳች ቅድመ ውሳኔ ለምን አናጠናቸውም፣ ምናልባት አይሁዳዊ ወይም ክርስቲያን አሊያም ሙስሊም ልሆን እችላለሁና ለኔ ሃይማኖት ምንነት አትቸገር !

- እስላምን ስታነሳ ትዝ አለኝ፣ይህ ከሕንድ እንዳመጣልህ የጠየከው የዑድ

ሽቶ ነው::

- ዋጋው ስንት ነው?

- ኣይ፣በነጻ ነው፣ካንድ ሙስሊም በስጦታ የተበረከተልኝ ነው:: ካትሪና እንዳስጠነቀቀችኝ ፈንጂ ተጠምዶበት ወይም ተመርዞ ከሆነ ግን እኔ ተጠያቂነት የለብኝም::

- ታዲያ ሽቶውን በምጠቀምበት ጊዜ እኔም አሸባሪ ልሆን ነው ማለት ነዋ?

- ሰሞኑን እዚህ ለንደን ውስጥ በሽብር ጥቃት ምክንያት አስፈሪ ቀናትን አሳልፈን በኋላ ግን ፍንዳታው የሽብርተኝነት ሳይሆን የወንጀል ፍንዳታ ነው ተባልን::

- ለምንድነው የሽብርተኝነት ሳይሆን የወንጀል ፍንዳታ የሆነው?

- አላውቅም ግን በጣም አስቂኝ ነገር ነው:: ነገሩ ሕንድ ውስጥ አንዱ ሙስሊም ‹‹ሽብርተኛ ከናንተ ጋር የማይስማማና የማትፈልጉት ሰው ሁሉ ነው›› ያለኝ እውነት ሳይሆን አይቀርም አሰኝቶኛል::

- ሽብርተኝነት ሽብርተኝነት ነው፣ሃይማኖት የለውም፣አገር የለውም:: የትኛውም ሃይማኖትም ሆነ አገር በሽብርተኝነት ሊፈረጅ አይችልም:: በዕለታዊ ድርጊቶቻችን ውስጥ ለሚስቶቻችንና ወይም ለልጆቻችን በምናደርገው አያያዝ አንዳንዴ ሽብርተኞች መሆናችንን አላስተዋልክም? አገሮችም እንደዚሁ ሽብርተኝነትን የሚዋጉት ራሳቸው የአሸባሪነትን ስልት በመጠቀም ነው:: የኃይል እርምጃ፣ሁከትና የጭካኔ ግድያ በማንም ይሁን በማን ቢፈጸም፣፣ከሰብአዊ አእምሮና ከሃይማኖት ሀሁ ጋር የሚጋጭ እኩይ ተግባር ነው !

- በሰሞኑ ፍንዳታ አንዳንድ ሙስሊሞች ሙስሊም በመሆናቸው ብቻ ያለ ኃጢአታቸው ስለ መታሰራቸው ጉዳይ የምትናገር ነው የሚመስለው::

- በትክክል፣ከፍንዳታው ሙሉ በሙሉ ነጻ መሆናቸው ቢረጋገጥም እስካሁንም ድረስ ብዙዎቹ እስር ቤት እየማቀቁ ነው:: ታዲያ ይህ ሽብርተኝነት አይደለም ትላለህ? !

- ነው፣ግን ብዙ ጊዜ ሙስሊሞች አሸባሪዎች ናቸው ብዬ ለምን እንደማስብ አላውቅም::

- ይህ አዝማሚያ በጣም የተለመደ ነው፣እኔም አንተም የሽብር ሚዲያና የሽብር ፖለቲካ ኢምፓይሮች ሰለባዎች ነን::

www.path-2-happiness.com

- እንዴት ማለት? ምን ማለት ነው የፈለከው? !
- እነዚህ ኤምፓይሮች እያወቅንም ሆነ ልብ ሳንለው ለሌሎች ያለንን አመለካከትና አቋማችንን በፈለጉት መንገድ ይቀርጹታል። ወራሪዎች ተወራሪ ሕዝቦችን የሚመለከቱት መገደል የሚገባቸው አረመኔዎች አድርገው አይደለም ወይ? ! ሕዝቦች ሌላውን ሕዝብ የሚያዩት ገዳይ ወንጀለኞች አድርገው አይደለም ወይ?! ሃይማኖቶች ሌሎች ሃይማኖቶችን ገዳዮችና አሸባሪ ወንበዴዎች አድርገው አይደለም የሚመለከቱት? !
- ልክ ነህ፣ግን በጣም ስሜታዊ የሆንክ ትመስላለህ . . (ከዚያም ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ አንተ ሙስሊም ነህ እንዴ?
- እናማ አንተን ከነሬስቶራንቱ እንዳላፈነዳህ ጠንቀቅ በል!
- ውድ ወዳጄ ቀልዴን ነው።
- እኔም፣ብንሄድና እቤት ብታደርሰኝስ?
- በል እንሂድ።

ኢየሩሳሌም የሃይማኖቶችና የፍጥጫ አገር



www.path-2-happiness.com

7

ኢየሩሳሌም የሃይማኖቶችና የፍጥጫ አገር

ኢየሩሳሌም የሃይማኖቶችና የፍጥጫ አገር

(1)

ጆርጅ ሌሊቱን ከልጆቹና ከባለቤቱ ጋር ለማሳለፍ በቂ ጊዜ በመፈለጉ ለጉዞው የሚያደርገውን ዝግጅት ያጠናቀቀው በጊዜ ነበር። ከሕንድ ከተመለሰ ወዲህ ተደራራቢ ሥራ፣የስምምነቶቹን ዝርዝር ጉዳዮች የሚመለከቱ ረዣዥሞቹ የካኽ ስብሰባዎችና ከመጓዙ በፊት ስለ አይሁዳዊነት ለማንበብ መወሰኑ ለቤተሰቡ መስጠት የነበረበትን ጊዜ ሲሻሙበት ቆይተዋል። የጉዞውን ዓላማ በሥራ ተልእኮው ላይ ብቻ ሳይወስን ለትላልቅ ጥያቄዎቹ ምላሽ ፍለጋ ለሚያደርገው ጥረትም አጋጣሚውን ለመጠቀም ወስኗል።

- ጣፋጯ ካትሪና . . ከቴል አቪብ እንዲመጣልሽ የምትፈልጊው ነገር ይኖራል?
- የትንሣኤን ቤተክርስቲያንና የቅድስት ማርያምን ቤተክርስቲያን ጎብኝተህ በውስጣቸው ጸሎት እንድታደርስ ነው የምፈልገው።
- ስለ ትንሣኤ ቤተክርስቲያን ብዙ ነገር አንብቤያለሁ። ቤተክርስቲያኑን በ335 ዓመተ ልደት ያሳነጸችው የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት እሌኒ ናት። ቤተክርስቲያኑ የተሰራው ኢየሱስ የተሰቀለበት ነው የሚባለው እንጨት ተገኘበት ተብሎ በሚታሰበው ኮረብታ ላይ ነው። ሥራው 270 ዓመታት የፈጀ ሲሆን ከዚያ በኋላ ፐርሽያውያን አገሩን በያዙ ጊዜ ተቃጥሎ ነበር። በ617 ሞደስቲ በተባለ የገዳም መነኩሴ አማካይነት እንደገና ተሰራ። ከዚያ በኋላ በተደጋጋሚ በተለይም በቆስጠንጢኖስ ዘመን በ1048 እድሳት ተደርጎለታል። ወራሪዎቹ መስቀላውያን ቅድስት አገርን በ1099 ሲይዙ ሁሉንም ቤተ አምልኮዎች አንድ ላይ በማሰባሰብ አሁን ባለው ቤተክርስቲያን እንዲሰባሰብ አደረጉ። ቤተክርስቲያኑ በኛ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ የተቀደሰ ባይሆንም ላንቺ ስል ጎብኝቼ እጸልይበታለሁ። የማርያም ቤተክርስቲያንንም እንዲሁ እጎበኛለሁ። ሌላ የምትፈልጊው ነገር የለም ?
- አመሰግነሃለሁ፣ስለ ቅድስት አገር ብዙ አንብበሃል ማለት ነው።
- በጣም ብዙ የሚባል አይደለም፣አሁንም ገና በማንበብ ላይ ነኝ።
- ቅድስት አገር የአይሁዶች ሳይሆን የክርስቲያኖች ብዙ ታሪካዊ ስፍራዎች

www.path-2-happiness.com

ያሉባት አገር ነች። ከኢየሱስ ታሪክ ጋር የተያያዙ ብዙ ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናትም ይገኙባታል።

- የእስራኤል ቆይታዬ በጣም አጭር ቢሆንም፣የክርስቲያን ታሪካዊ ሥፍራዎችን ለመጎብኘትና ከክርስቲያኖች ጋር ለመገናኘት ጥረት አደርጋለሁ።
- ወይኔ! . . እነዚህን ታሪካዊ ቦታዎች መጎብኘትና በአካል ሄጄ ለጌታ መጸለይ ምን ያህል እንደምመኝ ሊነግርህ አልችልም።
- ለምን አብረን አንጓዝም ?
- አሁን እንኳ ብዙ የቤተክርስቲያን የሥራ ቀጠሮዎች ስላሉብኝ አልችልም። ምናልባት ከአይሁዶች በኩል አሁን የሚደርስብን ግፍ ከቆመ በኋላ ወደፊት እንሄድ ይሆናል።
- ግፍ ?!
- አይሁዶች በቅድስት አገር የሚገኙ ክርስቲያናዊ ቅርሶችን ከማድበስበስና እዚያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትንና ክርስቲያኖችን ከማጎሳቀል ተቆጥበው አያውቁም።
- የቅድስት አገር ታሪክ ስሜት የሚነካ ነው። የመለኮታዊ ሃይማኖቶች የትግልና የፍጥጫ ሜዳ ሆና ነው ለዘመናት የኖረችው። ሁለት ጊዜ ለውድመት ተጋልጣለች። 23 ጊዜ ተከባለች። 52 ጊዜ ጥቃት ተሰንዝሮባታል። 44 ጊዜ ተወራ ሕልውናዋን አጥታለች። አሁንም ድረስ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ግዙፍ የሆኑ ታላላቅ ውጊያዎችን ገና ታስተናግዳለች ብለው ይጠብቃሉ። ቁድስ በእርግጥም የጦርነት ፍጥጫዎች ምድር ናት። አነጋገርሽ ግን አስገርሞኛል . . ለአይሁዶች አሳልፋ ያስረከበቻት እንግሊዝ ናት! ከዬት ስለ መጣው በክርስትና ላይ ያነጣጠረ ጭቆናና ግፍ ነው የምትናገሪው ?
- በጣም አሳዛኝ ቢሆንም ልክ ነህ። አንተ ማለት የፈለከውና ‹‹የበልፎር ቃል ኪዳን›› እየተባለ የሚጠራው አያሌ ፖለቲካዊ መንስኤዎች ያሉትና በኃያላን አገሮች መካከል የነበረውን ትግል የተንተራሰ ነው።
- እንዴት ማለት ? የተባሉት መንስኤዎችስ ምንድናቸው ?
- ከምክንያቶቹ መካከል ፦ የእንግሊዝ ወደ አንደኛው የዓለም ጦርነት (1914-1918) መግባት አንዱ ሲሆን፣በዚህ ወቅት የአይሁዶች ፖለቲካዊና ሳይንሳዊ ድጋፍ ለእንግሊዞች በጣም ወሳኝ ነበር። የጽዮናዊነት ንቅናቄ ደግሞ በዚሁ ተመሳሳይ ወቅት በፍሌስጥኤም ምድር ላይ የአይሁድ ብሔራዊ መንግስት ለመመስረት የሚያራምደውን ዓለማ የሚደግፍለት

ወገን ይፈልግ ነበር።

- የመጠቃቀም ነገር ብቻ ነበር ማለት ነው? !
- አይደለም፣ሌሎች አውሮፓዊ ምክንያቶችም ነበሩ። አንዱና ዋነኛው አይሁዶችን ከአውሮፓ ምድር አስወጥተው ለመገላገል በአውሮፓውያን ዘንድ የነበረው ብርቱ ፍላጎት ነው። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አይሁዶች፣ ከሚኖሩባቸው ሕብረተሰቦች ጋር ተሰባጥረውና ተጣጥመው መኖር ባለመቻላቸው በሚገኙባቸው አገሮች ሁሉ ከአገሩ መንግስት የተነጠለ እንግዳ አካል ተደርገው ይወሰዱ ነበር።ግብጽና አፍሪካን የኤስያ ዐረብና ሙስሊሞችን የሚያገናኝ ድልድል በሆነችው ፍልስጥኤም የተለያዩ ኃይሎችን መትከልም ሌላው ምክንያት ነበር። በተጨማሪም አውሮፓውያን እንደ አደጋ ይመለከቱት በነበረው በቱርክ ዑሥማናዊ ኸሊፋ መንግስት ውስጥ አይሁዶች አንዳንድ ወሳኝ የሥልጣን ቦታዎችን ይቆጣጠሩ ስለነበር የቱርክ ኤምፓይርን የመውረስ ዓላማ የነበራት እንግሊዝ የአይሁዶችን ትብብር መፈለጓ ሌላው ምክንያት ነበር።
- በእንግሊዞች ላይ ትንሽ ጫን ያልሽ መሰለኝ!
- ፈጽሞ፣ጫናዬ የሃይማኖትን ጉዳይ ግምት ውስጥ በማያስገባው ፖሊሲ ላይ ነው። ኢየሩሳሌምን ተቆጣጥረው የክርስትና መዲና ማድረግ ይገባ አልነበረምን ?
- እናማ መሆን የነበረበት በይሁዳዊው ወረራ ፈንታ ሌላ ዓይነት ክርስቲያናዊ ወረራ ነው ማለት ነው!! በዚህ ላይ ካንቺ እለያለሁ፣የቤልፎር ቃል ኪዳን በከፊል ሃይማኖታዊ ነበር የሚል እምነት አለኝ።
- በአንተ አመለካከት ሃይማኖታዊው ምክንያት ምንድነው ?
- ለክርስትና ትምህርቶች የተሰጡ የተሳሳቱ ትርጓሜዎች፣ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የጽዮናዊነት አቀንቃኝ መስመር በስፋት እንዲስፋፋና በሃይማኖት ስም ዘረኝነት እንዲሰፍንና የጦርነት ወንወጀሎች እንዲፈጸሙ አድርገዋል።
- ይቅርታ፣ይህ በካቶሊኮች ዘንድ የለም።
- ልክ ነሽ፣ይህ ደዌ በስፋት የሚስተዋለው እኛ -ፕሮቴስታንት - ዘንድ ነው። በ1948 የእስራኤል መንግስት መመስረት፣በብሉይና ሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ትንቢቶች ለመሙላት የግድ መሆን የነበረበት ጉዳይ መሆኑና ይህም ኢየሱስ ዳግም ወደ ምድር ድል አድራጊ ንጉሥ ሆኖ እንዲመጣ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን የሚያምኑ አያሌ የፕሮቴስታንት

www.path-2-happiness.com

አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: ጽዮናውያን ክርስቲያኖች የአይሁድን ሕዝብ በአጠቃላይና አይሁዳዊቷን አገር ደግሞ በተለይ መጠበቅና መከላከል ክርስቲያናዊ ሃይማኖታዊ ግዴታችን ነው ብለው ያምናሉ:: (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ እውነቱን ለመናገር አንቺ እንግሊዝን ሳይሆን ፕሮቴስታዊነትን የምትኮንኚው ለዚህ ነው:: ለማንኛውም እስራኤል አሁን እውን ሆናለች::

- ይሁንና ግን ቤተ ክርስቲያኖቻችን፣ቅዱሳን ቦታዎቻችንና ቀሳውስቶቻችን እንዳይጨቆኑ ይገባል::
- ግፍና ጭቆና አይሁዳዊም ይሁን ክርስቲያናዊ በሁሉም መልኩና በሁሉም ገጽታው እኩይ ተግባር ነው:: ክርስቲያኖች በአይሁዶች ሲጨቆኑ ይህ የመጀመሪያው አይደለም፣ልክ አይደለም ? !
- ልክ ነው፤በአይሁዶች ከተገደለውና ራሱን ለሰው ልጆች ቤዛ ካደረገው ከኢየሱስ ጀምሮ፣ከርሱ በኋላ በተከታዮቹ ላይ የተፈጸመው ግፍና ሰቆቃ፣ዛሬ በቅድስት አገር በወንድሞቻችን ላይ የሚደርሰው ጭቆናም የዚህ አካል ነው::
- እህህ፣ወደ ኢየሩሳሌም ከመድረሴ በፊት በሃይማኖቶች ጦርነትና በፍጥጫዎቹ ውስጥ የገባሁ መሰለኝ:: በይ ጊዜ ሄዷል አሁን እንተኛ:: ከእኩለ ሌሊት በፊት ወደ አይሮፕላን ማረፊያ ማምራት አለብኝ::

(2)

ጆርጅ ከጧቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ቴል አቪብ ደረሰ . . ብንያምን ነበር አቀባበል ያደረገለት:: ብልጠትና መሰሪነትን ከብንያምን ዓይኖች ውስጥ ጎልተው ታት . .

- ሰላም . . ወደ ቅድስት አገር ወደ ኢየሩሳሌም እንኳን ደህና መጣህ::
- ሰላም፣ወደዚች ቅድስት ምድር በመምጣቴ ደስታዬ ወደር የለውም::
- ጉዞህ አጭርና ለአራት ቀናት ብቻ መሆኑን ካኽ ነግሮኛል::
- አዎ፣ለኔ ተከታታይ ጉዞ በመሆኑ ረዥም እንዲሆን አልፈለኩም:: ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት ሕንድ ነበርኩ:: ካኽ ነው የገፋፋኝና ቅድስት አገርን እንድጎበኝ ያደረገኝ::
- ሁሉንም ነገር አሰናድቻለሁ፤ውሉ በሁለት ቀናት ውስጥ ይፈረማል:: በዚህ ረገድ ምንም የሚያሳስብህ ነገር አይኖርም:: እዚህ መገኘትህ ውሉ የተፈረመው በመደበኛው ሂደት ውስጥ አልፎ መሆኑን ለማረጋገጥ ብቻ ነው::

- በጣም ጥሩ ነው::
- ወደ ሆቴል ወይስ ወደ ኩባንያው እንሂድ ?
- ወደ ሆቴሉ እንሂድና ሻንጣዬን አስቀምጬ ከዚያ በቀጥታ ወደ ኩባንያው እናመራለን::
- መልካም፣ተነገወዲያ ቅዳሜ ስለሆነ ሌቪ ሰንበት ቀን አትሰራም:: በመሆኑም ዛሬና ነገ ከርሷ ጋር መገናኘት ያስፈልግህ ይሆናል:: ሌቪ በጣም ሃይማኖተኛና የወጣላት የቴክኒክ ሰው ስለሆነች የደህንነት ሶፍትዌሩ ከሽብርተኞች ጥሶ የመግባት አቅም ይበልጥ ጠንካራ ሆኖ መገኘቱ ዋነኛ ትኩረቷ ነው::
- ያቀረብንላችሁ የሰኩሪቲ ፕሮግራም እጅግ በጣም ጠንካራ ሶፍትዌር በመሆኑ በዚህ በኩል ምንም የሚያሳስባችሁ ነገር የለም::
- ከሌቪ ጋር ስትገናኝ ትኩረትህ በዚህ ነጥብ ላይ ይሁን:: ለእስራኤል ደህንነትና ጸጥታ በጽኑ የምታስብ መሆንህን አሳያት:: በጣም የሚያሳስባት ነገር ይህ ነውና:: እንዲያውም ከርሷ ጋር በሚኖርህ ቆይታ ውይይታችሁ ከቴክኒካዊ ገጽታው ሌላ ሃይማኖታዊና ፍልስፍናዊ ገጽታ ይዞ ሊያስገርምህ ይችላል::
- ሃይማኖታዊና ፍልስፍናዊ ?!
- አዎ፣ይህ ከመጥፎ ጸባይዋ አንዱ ክፍል ነው:: ለማንኛውም ከርሷ ጋር በሚኖረው ነገር ችግሮች ካጋጠሙህ ትነግረኛለህ:: (ፈገግ ብሎ ቀጠለ) ፦ ሞገደኛ ብትሆንም ከኔ ቃለል ፈጽሞ አትወጣም::
- በጣም ጥሩ::

ወደ ሆቴሉ ደረሱ፣ጆርጅ ወደ ክፍሉ ሄዶ ሸንጣዎቹን አስቀመጠና ወደ ብንያምን ተመልሶ መጣ:: ተያይዘው ወደ ኩባንያው ቢሮ ሄዱ . . የኩባንያው ሕንጻ ትልቅና ትኩረት የሚስብ አልነበረም፣መካከለኛ ሆኖ በሠራተኞች የተጨናነቀ ነው:: በሰፈሩ መግቢያ ኬላ ላይ ጥበቃው በጣም የተጠናከረ ሲሆን በኩባንያው መግቢያ በር ላይም እንደዚሁ ነበር::

ወደ ብንያምን ቢሮ አመሩ፣እንደ ደረሱ ብንያምን ለሌቪ ደውሎ እንድትመጣ ጠየቃት . .

- ችግር አሁን ትመጣለች::
- ችግር ! እንዴት ?
- የሃይማኖት አክራሪነቷ ሕይወትን በተገቢው መንገድ እንዳትረዳ ያደርጋታል:: እንደዚሁም ክርክር ትወዳለች፣አይሰለቻትም፣በመጨረሻ

www.path-2-happiness.com

ግን በጫና ትለሰልሳለች::

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በጣም ቆንጆ የሆነች ኮረዳ ብቅ አለች:: የለበሰችው ልብስ የጨዋ ሊባል የሚችል ቢሆንም ወበቷን የሚደብቅ አልነበረም:: ብንያምን ከጆርጅ ጋር አስተዋወቃት ፦

- ሌቪ የኩባንያችን የቴክኒክ መምሪያ ኃላፊ ናት . . (ወደ ጆርጅ እያመለከተ) ፦ ይህ ጆርጅ ነው፣እንግሊዝ አገር የሚገኘው የተራቀቀ የኤሌክትሮኒክስ ማምረቻ ኩባንያ የፕሮግራሚንግ መምሪያ ኃላፊ ነው::
- እንኳን ደህና መጣህ፣እዚህ በመምጣትህ አመሰግናለሁ:: ብዙ ቴክኖሎጂያዊና ቴክኒካዊ ጥያቄዎች አሉኝ::
- ለመመለስ ደስተኛ ነኝ::
- ከፈለጋችሁ በመሰብሰቢያው ክፍል ውስጥ ሆናችሁ ስብሰባችሁን ማካሄድ ትችላላችሁ::
- መልካም፣ሚስተር ጆርጅ እባክህን ወደ ክፍሉ እንሂድ::

ጆርጅና ሌቪ ወደ ስብሰባ ክፍሉ ሄዱ:: ትንሽ ክፍል ብትሆንም በሥርዓት የተደራጀችና ምቹ ክፍል ናት . .

- ግባ::
- አመሰግናለሁ፣ኩባንያችን ባቀረበው የሰኩሪቲ ሶፍትዌር እምብዛም የረካሽ አትመስይም ?
- አይደለም፤እንደዚያ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ አርኪና አስተማማኝ እንዲሆን ስለምፈልግ ብቻ ነው:: እንደ አይሁድ ደህንነታችንና ጸጥታችን ከምንም ነገር በላይ ያሳስበኛል::
- ፕሮግራሙ አሁን ካሉት የሰኩሪቲ ፕሮግራሞች ሁሉ እጅግ ጠንካራው ነው:: በደህንነትና በጥበቃ ጉዳይ ላይ ከሚገባው በላይ እንድታከሩ የሚያደርጋችሁ ፎቢያ እንዳለባችሁ ነው የሚሰማኝ::
- እንዴት ማለት?
- የሰፈር ጥበቃ፣የሕንጻ ጥበቃ፣በሕይወቴ እንዲህ ያለውን አይቼ አላውቅም!
- እኛ ለዘመናት ጭቆና ስር የኖርን ሕዝብ ነን፤በመሆኑም በተቻለኝ አቅም ሁሉ ይህን ሕዝብ መጠበቅ ኃላፊነቴ ሆኖ ይሰማኛል::
- መልካም፣የኔም ኃላፊነትና ተልእኮም በዚህ ረገድ ቴክኒካዊ እገዛ ለናንተ ማቅረብ ነው::
- ታግዘናለህ ! ለምንድነው የምታግዘን ?
- አልገባኝም! አሁን በምንፈራረምበት በዚህ ልዩ የሆነ የደህንነት ጥበቃ

ፕሮግራም አግዛችኋለሁ::

- ይቅርታ አድርግልኝና የለመድኩት ሰዎች ሁሉ የኛ የአይሁዶች ጸር መሆናቸውን ነው::
- እኔ እንግሊዛዊ ፕሮቴስታንት ክርስቲያን ነኝ:: ይህን አገርና ይህን መሬት ለናንተ የሰጣችሁ እንግሊዛዊው ፕሮቴስታንት ክርስቲያን ቤልፎር አይደለምን?
- ይህች አገራችንና መሬታችን ናት፤ማንም አልሰጠነም::በመሆኑም እኛው ራሳችን ልንጠብቃት ይገባል::
- ክርክር ወዳድ ትመስይያለሽ፤ግልጽነትን ትወጂያለሽ ?
- ክርክር እወዳለሁ፤አፈቅራለሁ፤ግልጽነትንም እወደዋለሁ፤ እፈልጋለሁ::
- እንደምትዪው ግልጽነትን የምትወጂ ከሆነ ከዬት ነው የመጣሽው ? ገጽታሽ አውሮፓዊ ይመስላል?!
- እኔ ከእስራኤል ነኝ::
- አባትና እናትሽም እስራኤል ውስጥ ነው የተወለዱት?
- ወላጆቼ በ1970 የመጡ ነምሳውያን ሲሆኑ እኔ እዚህ እስራኤል ውስጥ ነው የተወለድኩት:: በመሆኑም የነምሳ ዜግነት ቢኖረኝም እኔ እስራኤላዊ ነኝ::
- እናም አንቺ የእስራኤልን ደህንነት የምትጠብቂ ነምሳዊት ነሽ፤እኔ ደግሞ የደህንነት ጥበቃ ሶፍትዌር የማቀርብልሽ እንግሊዛዊ ነኝ ማለት ነው::
- እኔ አይሁዳዊት ስሆን፣አንተ ግን ፕሮቴስታንት ነህ!
- አባትሽ ይሁዲ ነው?
- አይደለም፣አባቴ ኤቲስት ክርስቲያን ነበር፤አይሁዳዊነት የሚመጣው ከእናት በኩል እንጂ ከአባት አይደለም::
- ግልጽ ልሁንና ወደ ኢየሩሳሌም የመጣሁት ለሁለት ነገር ነው:: አንደኛው ውሉን ለመፈራረም ሲሆን፣ሁለተኛው የአይሁድ ሃይማኖትን ለማወቅ ነው:: ምናልባት አይሁዳዊ ልሆን እችል ይሆናልና በሃይማኖት ጉዳይ ላይ በጥልቀት ብንወያይ ምን ይመስልሻል ?
- በጣም ደስ እያለኝ፣ይሁን እንጂ እናትህ አይሁዳዊት እስካልሆነች ድረስ አይሁዳዊ መሆን አትችልም::
- እንዴት ማለት?
- እኛ ምርጥ ሕዝብ ነን፤በዝርያውና በእምነቶቹ በእግዚአብሔር የተመረጥን ሕዝብ ነን::

www.path-2-happiness.com

- ስለዚህምሌሎችሃይማኖታችሁንእንዲቀበሉጥሪአታደርጉም፣አታስተምሩም ማለት ነው ?
- ፈጽሞ አናደርግም፤ጥሪ የምናደርገውና የምናስተምረው ሌሎች ይህን ምርጥ ሕዝብ እንዲያገለግሉ ብቻ ነው።
- ሌላው የናንተ አገልጋይ እንዲሆን ብቻ ነው ማለት ነዋ!!
- ዋጋ የማይከፈልበት አገልግሎት የለም።
- የደህንነት ጥበቃ ውሉን ስትፈርሙ ለኛ የምንስማማበትን ዋጋ ትከፍሉናላችሁ። ይኸ አገልግሎት አይደለም ! ሽያጭና ግዥ፣ግብይት ነው።
- የናንተ ኩባንያ ዳይሬክተር አይሁዳዊ ባይሆን ኖሮ፣ የሰኩሪቲ ሶፍትዌሩን ለኛ ለማቅረብ ኩባንያችሁ ባልተመረጠ ነበር።
- ካኽ ግን ሴኩላሪስት ነው !
- ቢሆንም ከምርጡ ሕዝብ የወጣ አይሁዳዊ መሆኑ አልቀረም . . አንተ ግን ሃይማኖተኛ ትመስላለህ !

በዚህ ወቅት አስተናጋጅ በሩን አንኳኳ። ምን እንደሚወስድ ሌቪ ጆርጅን ጠየቀች . .

- ውሃና ቡና . . ጉዳዩን ከመነሻው ብንጀምር ምን ይመስልሻል ?
- ይሁን ቀጥል፣የሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች እናት የሆነው ሃይማኖት ትኩረትህን የሳበ ትመስላለህ።
- የመለኮታዊ ሃይማኖቶች እናት ስትይ፣አይሁዳዊነትና ሙሴ አይሁዶች፣ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የሚያምኑበት ነው ማለትሽ ነው ?
- አዎ፣ክርሱ በኋላ በመጡት ላይ ስምምነት አልተደረገም። አይሁዶች በኢየሱስ፣ክርስቲያኖች ደግሞ በሙሐመድ አያምኑም።
- ሙስሊሞች በሁሉም ያምናሉ ማለት ይቻላል፤አይሁዶች ግን ከራሳቸው ነብይ ከሙሴ በስተቀር በየትኛውም አያምኑም . . አሁን ይህን ተይውና ከመለኮታዊ ሃይማኖቶች ጥንታዊ ስለሆነው እምነት በዝርዝር ማወቅ ስለምፈልግ ልታግዢኝ ትችያለሽ ?
- የፕሮግራሚንግ ሳይሆን የሃይማኖተቶች ኤክስፐርት ነው የምትመስለው ! መቀጠል ትችላለህ።

ጆርጅ ፊትለፊት ለመጋፈጥና ስለ አይሁዳዊነት የሚታውቀውን ሁሉ እንዲትነግረው ሊያግባባት ወሰነ። መሰረታዊ ያልሆነ ፍሬ አልባ መረጃ ሳይሆን እውነታውን ማወቅ ነው ዋነኛ ዓለማው . .

- አይሁዶች በእግዚአብሔር ያላቸው እምነት ምን ይመስላል? እንዴት ነው የሚገልጹት? እንዴት ነው ብለው ያስተዋውቁታል?
- ማለት የፈለከው አልገባኝም? ጌታ አምላክ ግን ፈጣሪና ሲሳይ ሰጭ አምላክ ነው።
- የእግዚአብሔር ባሕርያት በአይሁዶች ዘንድ እንዴት እንደሚገለጽ ለማወቅ ብዙ ነገሮችን ያነበብኩ ሲሆን ብዙ ጥያቄዎችን እንዳነሳ አድርጎኛል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካነበብኩት መካከል አንዱ እንዲህ ይላል ፦ ‹‹የእግዚአብሔርም ቃል ፦ ሳኦል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና፣ትንቢቴንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት ጸጸትሁ ብሎ ወደ ሳሙኤል መጣ።›› አሪት ዘ ጸአት ውስጥ ደግሞ ፦ ‹‹የልቅሶአቸውን ድምጽ ሰማ፣እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አሰበ።›› የሚል አነበብኩ። መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ወስጥም ፦ ‹‹አሁን ሄደህ አማሌቅን ምታ፣ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣አትማራቸውም ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ሕጻኑን በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል።›› የሚለውን አነበብኩ። ይህንን የመሳሰሉ ሌሎች ብዙ ብዙ ነገሮች አሉ። የኔ ጥያቄ እግዚአብሔር ይጸጸታል? ይረሳና ያስባል? ያለ ምሕረት ሕጻናትንም ጭምር እንዲገደሉ ያዛል?! እንዲህ ያለው አምላክ ምን ዓይነት አምላክ ነው?!
- ጥሩ አንባቢ ትመስላለህ፤ግን ቁንጽል አንባቢ ነህ። ያልከው ነገር ትክክል ነው። ከዚህም ሌላ ብዙ ይኖራል፤ይሁን እንጂ ይህ በአይሁዳዊነት ብቻ የተወሰነ ነው ወይ? እናንተም ብትሆኑ የዚህ ዓይነት እጥፍ ድርብ አላችሁ።
- እህህ፣ልክ ነሽ ተመሳሳዩ እኛ ዘንድም በብዛት ይገኛል፤ግን እኔ ወደ ይሁዳዊነት ለመለወጥ ስለማስብ ነው። ወደፊት ስለ አይሁዳዊነት እምነቶች የጀመርነውን ብንቀጥልበት ምን ይመስልሻል? ዛሬና ነገ የስምምነት ፊርማውን ጉዳይ ብጠናቅቅ ደስታዬ ነበር፤ተነገወዲያ ቅዳሜ ስለሆነ እናንተ አትሰሩም።
- ልክ ነህ፣ቅዳሜ የዕረፍትና የአምልኮ ቀን ነው። ሰንበትን ማክበር ከአስርቱ ትእዛዛት አንዱ ነው። እግዚአብሔር ሰማያትና ምድርን ፈጥሮ ያረፈው ቅዳሜ ዕለት ነው።
- ያረፈው?!
- አዎ፣ሰንበት ነው ያረፈው። እግዚአብሔርን በሚመለከቱ አንዳንድ ቃላት

www.path-2-happiness.com

ላይ ስሜታዊነትን ታንጸባርቃለህ፤መቼም ይህ ያንተ ችግር ነው፡፡

-ሊሆን ይችላል፣ዋናው ነገር በውል ስምምነቱ ላይ የምናደርገውን ውይይት በሁለት ቀን ውስጥ እንድናጠቃልል ነው፡፡ አሁን ድካም ተሰምቶኛል፣ከአይሮፕላን ማረፊያ እንደመጣሁ ሳላርፍ ነው በቀጥታ ወደ ኩባንያው የመጣሁት፡፡

-አሁን ሄደህ ማረፍ ትችላለህ፣ከፈለግህ ማታ መቀጠል እንችላለን፡፡

-ከአስር ሰዓት ተኩል በኋላ በሆቴሉ ብንቀጠል ያስቸግርሻል?

-ፈጽሞ . . አስር ተኩል ላይ ወደ ሄቴሉ እመጣልሃለሁ፡፡

-መልካም አብረን ምሳ እንበላለን፤ምናልባትም ይበልጥ ተረጋግተሽ ሳታፋጥጭኝ እንጨርስ ይሆናል፡፡

-ማለት የፈለከው አልገባኝም? ! ዛሬ እንኳ አፋጣጩ አንተ ነበርክ፤አስቀይመህ ከሆነ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

-አፋጣጭ ሆኘ ከነበረ እኔ ነኝ ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ፡፡ እንዳች ያለችን ቆንጆ መፋጠጥና መቀየም አይገባትም፡፡

-ይህ ያንተ ትሁትነት ነው፣ግን የቀድሞ ማፋጠጥህን ካሁኑ ማሽኩርመምህ ይበልጥ እወደዋለሁ . . ፈገግ ብላ ቀጠለች ፦ እኔ የምኖረው ሕይወቴን በሙሉ ለጌታ ሰጥቼ ነው፡፡

-ከመሄዴ በፊት ብንያምን ብሰናበት ደስ ይለኛል፡፡

-በል እንሄድለት፡፡

-ወደ ብንያምን ቢሮ አብረው አመሩ፡፡ ተሸቀዳድሞ ስለ ስብሰባቸው ጠየቃቸው . .

-ውይይቶቹ መልካምና ባለ ብዙ ፈርጅ ነበሩ፡፡

-ፍቀዱልኝና እኔ ወደ ሥራዬ ልመለስ፡፡

-እሽ ሌቪ፣ግና ጆርጅ እንግዳችን ስለሆነ በሚገባ ሊስተናገድ ይገባል፡፡

-ጥሩ ነው፣በሉ ደህና ሁኑ፡፡

-ትንሽ ዕረፍት ለማድረግ ወደ ሆቴሉ እንድሄድ ነው የተስማማነው፡፡ ድርድሩን ለመቀጠል ሌቪ በኋላ ወደ ሆቴሉ ትመጣለች . . ውሉን ለመፈራረም በትንሹ ለምን ሁለት ቀን እንደሚያስፈልገን አሁን ተረድቻለሁ፤ክርክርና ማስፋት ትወዳለች፡፡

-ውይይቱን በሆቴሉ ውስጥ የመቀጠል ሀሳቡ ግሩም ሀሳብ ነው፤ከይፋዊ የሥራ መንፈስ ወጣ ባለ ስሜት ዘና ብላችሁ እንድትቀጥሉ ይረዳል፡፡

-ልክ ነህ፤ሌቪ ግን ትንሽ አስቸጋሪ ብጤ ነች !

-ከአስቸጋሪነቷም ጋር ጥሩና ቆንጆም ናት፡፡ ዛሬ ወዳንተ ከመምጣቷ በፊት ግትርነቷንና የማክረር አካሄዷን እንድትቀይር እነግራታለሁ፡፡

-መልካም፣ፍቀድልኝ ትንሽ እየደካከመኝ ነው፡፡

-በል ሂድ፣ሾፌሩ ወደ ሆቴል ያደርሰሃል፡፡

(3)

ጆርጅ ሰባት ተኩል ላይ ወደ ሆቴሉ ደረሰ፡፡ ወደ ክፍሉ ገብቶ አልጋው ላይ ተጋደመና እንቅልፍ ወስዶት ጭልጥ አለ፡፡ የነቃው አስር ሰዓት ከሩብ ላይ ነበር . . በችኮላ ፊቱን ተጣጥቦ ልብሱን ሲቀይር የክፍሉ ስልክ እያቃጨለ ነበር . . የእንግዳ መቀበያ ሠራተኛው ሌቪ የተባለች ሴት እየጠበቀችው መሆኑን ነገረው . .

ጆርጅ በፍጥነት ወደ እንግዳ መቀበያው ወረደ፡፡ ሌቪ ወርቃማ ጸጉሯን ለቃ፣ትንሽም ቢሆን ጨዋነት ያላጣና ወደ እራት ምሽት ልብስነት የቀረበ ልብስ ለብሳ አምራ ደምቃ አገኛት . . ጨበጣት፡፡ ቀልብ የሚሰልብ ውበቷን ይበልጥ ያጎላ ፈገግታ ቦግ አደረገችበት . .

-ጧት ከነበርሽበት ይበልጥ ውብ ሆነሻል !

-ለምርጫህ አመሰግናለሁ፡፡

-በይ ወደ ምግብ ቤቱ እንሂድና ምሳ እየበላን ውይይታችንን እንቀጠል፡፡

ወጣ ብሎ የሚገኘውን ጠረጴዛ መረጡና ፊትለፊት ሆነው ተቀመጡ . . ጆርጅ አስተናጋጁን ጠራና የሚፈልጉትን አዘዘ . .

-ስንበላ ስለ ሥራ ባናወራ ምን ይመስልሻል?

-እንዳሻህ፡፡

-እጅግ በጣም ቆንጆ ነሽ፤ባለትዳር ነሽ?

-አይደለሁም፣ገና ነኝ፡፡ ከካኽ ትለያለህ የሚል ግምት ነበረኝ፡፡

-እንዴት ማለት?

-አንተ ለሃይማኖት ለኦሪትና ለወንጌል ትኩረት ትሰጣለህ፡፡ ካኽ ግን ጭንቀትና ሀሳቡ ሁሉ ገንዘብና ሴት ብቻ ነው፡፡

-ልክ ነው፡፡ የምንመሳሰልበት ነጥብስ?

-ገንዘብን ብዙ የማትወድና ውበትም የማያሳስብህ መስሎኝ ነበር . .

-ገንዘብና ቆንጆን የማይወድና የማያሳስበው ሰው ማን አለ? ይሁን እንጂ ማለት የፈለክሽው ነገር አልገባኝም !

-አንተ ከሄድክ በኋላ ስብሰባው በሆቴል እንዲሆን የተደረገበትን ዓላማ

www.path-2-happiness.com

ብንያምን ነግሮኛል።
- ምን ማለትሽ ነው?
- አንተም እንደ ካኽ መደሰትና መዝናናት ትፈልጋለህ . . መደሰት ብቻ።
- በይበልጥ አብራሪው !
- ራስህን ብዙ አታጃጅል፣እኔ ዝግጁ ነኝ።

ጆርጅ ሆን ብሎ ለመጃጃል ፈለገ። ማለት የፈለገችው ያልገባው መስሎ ለመታየት ሞከረ . .

- ውይይቱን ለመቀጠል እኔም ዝግጁ ነኝ፤ግና ምሳዬን ተመግቤ ካበቃሁ በኋላ ነው።
- መልካም፣ሞቅ ያለ ውይይት እንዲሆን ትፈልጋለህ?
- አንቺን ደስ እንዳለሽ።
- ብንያምን የጠየቀኝን ነገር እምቢ ማለት አልወድም፤ስለዚህ አንተ እንደፈለከው ይሁን።
- ብንያምንን ከውይይታችን ጋር ምን አገናኘው? !
- እቅጩን ልናገርና . . እናንተ ወንዶች ስትባሉ ከወሲብ በስተቀር የሚያሳስባችሁ ነገር የለም።
- እኔ የምናገረው ሌላ፣አንቺ የምታወሪው ስለ ሌላ ነገር መሰለኝ !
- ጆርጅ ይበልጥ መረዳት፣የሌቪን ንግግር ከካኽና ከብንያምን አነጋገር ጋር አያይዞ ማስተዋል ጀመረ። ከምግብ ቤቱ ሲወጡ ወደ ሆቴሉ የውጭ መናፈሻ አመራና ፦
- የሚስማማሽ ከሆነ በሆቴሉ መናፈሻ ውስጥ እንድንቀመጥ ሀሳብ አቀርባለሁ።
- መናፈሻ ውስጥ !! ደስ እንዳለህ ይሁን !!
- ቦታው አስደሳች ነው፤ለግልጽነትም የሚመች ይመስላል።
- ልክ ነው፤አስደሳች ነው፣ግን ለሰው ዓይን የተጋለጠ ግልጽ ቦታ ነው። ምንድነው የምትፈልገው?
- ውይይታችንን መቀጠል ነው የምፈልገው።
- መጫወቻ እያደረግከኝ ነው'ንዴ? ብንያምን እንደነገረኝ ነግሬሃለሁ፣እኔ ዝግጁ ነኝ።
- እኔም ውይይቱን ለመጀመር ዝግጁ ነኝ፤ብንያምን በተሳሳተ መንገድ የተረዳኝ መሰለኝ፣እኔ ካኽ አይደለሁም።
- ከብንያምን የተረዳሁት ሁለታችሁም አንድ መሆናችሁን ነው፤ለዚህ ነው

እንደምታየኝ ዝግጁ ሆኜልህ የመጣሁት።
- መሸኮርመም አልወድም፤ሕይወቴን በሙሉ የምኖረው ለእግዚአብሔር ነው ብለሽኝ አልነበረም?!
- እኔ . . እኔ በነገሩ የተስማማሁት እግዚአብሔርን ለማገልገል ዓላማ ነው።
- እግዚአብሔርን ለማገልገል ዓላማ!! እንዴት ሆኖ?
- እኛ ዘንድ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ዋነኛው አምልኮና አገልግሎት፣የእስራኤልን መንግስት ማገልገል እና የእግዚአብሔርን ምርጥ ይሁዳዊ ሕዝብ መጥቀምና ማገልገል ነው።
- አዝናለሁ፤አንቺ ባጣም ርካሽ ነሽ!! ቢያንስ ቢያንስ ለሰብእናሽ እንኳ ቅንጣት ክብር አትሰጭም?!
- በአጥቂነት የጀመርክ ብትሆንም በግልጽነት ነው የምናገረው። በአይሁዳዊነት ውስጥ ሴት ልጅ ያላት ቦታ የተለየ ነው፤እንደ ወንድ አትታይም . . በዚህ ላይ መናገር ደስ አይለኝም። መልካም ፈቃድህ ሆኖ ርእሱን ብትቀይረው?
- አልገባኝም?! ሳትወጅ እንድትናገሪ አልፈልግም። ግን ውይይትና ክርክር እወዳለሁ ብለሽኝ አልነበር? !
- ውይይት እወዳለሁ ግን በተሳሳተ መንገድ እንዳትረዳኝ እፈራለሁ . . በትክክለኛው መንገድ እንደምተረዳኝ ተስፋ አደርጋለሁ።
- እባክሽን ቀጥይ።
- ወሲብና ሴት በአይሁድ ሃይማኖት ውስጥ ያላቸውን ቦታ ለማወቅ ትንሽ ዘርዘር አድርጎ ማየት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ያህል እኛ ዘንድ ትክክለኛው ተፈጥሯዊ ወሲብ በባልና ሚስት መካከል ልጅ ለመውለድ ዓላማ ተብሎ የሚደረገው ብቻ ነው። ይሁን እንጂ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ሴት የተዋረደችና እንደ ሕጻን ወይም እንደ እብድ ወይም እንደ እንስሳ ነው የሚያዩዋት። ወንድን ለማስደሰት ብቻ የተፈጠረች ናት። ቴልሙድ ውስጥ ፦ ‹‹ሴት በዓይነምድር የተሞላች እቃ ናት›› . . የሚል ሰፍሯል። (በቁጣ ዞር አለችና) ፦ ይኸን ነው የፈለከው?! ወይስ ያለህን ነገር ከፈትለፊትህ በተቀመጠች በዚች የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማራገፍ ትፈልጋለህ?!
- አስከፍቼሽ ከሆነ ይቅርታ አድርጊልኝ፤በእውነቱ ይህ የከፋ አድልዎና ጭቆና ነው የሚል እምነት አለኝ። ዘና ባለ መንፈስ እንድናሟላ እሻለሁ። እንዲያ እንድትሆኚ የሚያስገድድሽ ነገር ምንድነው?
- ብንያምን ነው ! ትእዛዙን መፈጸም ግዴታዬ ነው !
- አልገባኝም ! የተነሳውን ነገር ለብንያምን ትእዛዝ በፍጹምነት ተገዥ

www.path-2-happiness.com

ከመሆን ጋር ምን ያገናኛል?

-ብንያምን የናቴ ባል ነው።

-አባትሽ !

-አይ፣አይደለም፤አባቴ ባንድ ወራዳ ሙስሊም አሸባሪ ፍንዳታ ነው የተገደለው . . አጎቴ እናቴን ወረሳት፣ሚስቱ ሆነች። ኦሪት ዘዳግም ውስጥ ባል የሞተባት ሴት የባልዋን ወንድም ማግባት አለባት የሚል ሰፍሯል።

-እናትሽን አጎትሽ ወረሳት! የምትወረስ እቃ ነች ማለት ነው ?!

-አዎ፣በጣም የሚያሳዝነው የባልዋን ወንድም ለማግባት ትገደዳለች።

-ይቅርታ አድርጊልኝ፤አንቺን ማስተባበሌ አይደለም፣ግን የምትናገሪውን ማመን ይከብደኛል ! አክራሪ አይሁዳዊት ነኝ እያልሽም ኦሪትን ከሚገባው በላይ እየወረፍሽ ነው የሚመስለኝ !

-ዋይ፣ምናልባት ሞቅ አድርጌ ተናግሬ ይሆናል ! ለነገሩ በዚህ ጉዳይ ላይ ማውራት አልወድም፣አንተ ነህ የፈለከው ! (ቀና ካለች በኋላ እንደ ገና አቀርቅራ) ፦ እስካሁን ብዙውን ላለመናገር ራሴን ቆጥቤያለሁ።

-ከተናገርሽው ይበልጥ የከፋ ነገር አለ ማለት ነው?!

የሌቪ ውብ ዓይኖች በእንባ ተሞሉ፤ቀጠለች . .

-እስከ ጠየከኝ ድረስ፣አዝናለሁ አዎ አሉ ! ያንድ መቶ ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል ነው ! ሴት ሳይጣናዊ ፍጡር ናት፣በፍጥረቷ ከወንድ ያነሰች ናት ! . . ተልሙድ ውስትጥ እንደተመለከተው ሁሉ ፦ ‹‹ወንድ በሁለት ሴቶች መካከል፣ወይም በሁለት ውሾች መካከል፣ወይም በሁለት አሳሞች መካከል መተላለፍ የለበትም። ሁለት ወንዶችም ሴት ወይም ውሻ ወይም አሳማ በመካከላቸው እንዲያልፍ መፍቀድ የለባቸውም።›› እኔ ሴት ስለሆንኩ በየዕለቱ ማለዳ ላይ በመንፈሳዊ ስሜት ተናንሽ ፦ ‹‹በፈቃድህ መሰረት የፈጠርከኝ ጌታ አንተ የተባረክ ነህ›› ብየ እጸልያለሁ። ወንዱ ግን ‹‹ጣዖት ወይም ሴት ወይም አላዋቂ አድርገህ ስላልፈጠርከኝ አንተ የተባረክ ጌታ ነህ›› ብሎ ነው የሚያመሰግነው።

ጆርጅ ውቧን ሌቪና የሚያነቡ ሰማያዊ ዓይኖቿን በአዘኔታ ስሜት እየተመለከተ ነበር። ባላሰበው ሁኔታ ከርሷ ጋር ለተጣበቀው የገዛ ልቡና ዓይኖቹም እንዲሁ ማዘናቸው አልቀረም። ከአፍዋ በሚወጣ እያንዳንዱ ቃል ስሜቱ ተነክቷል . .

-ይቅርታ አድርጊልኝ . . ርእሱን እንለውጥ ይሆን? በጣም

አደከምኩሽ፣በማስቸገሬ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

-ከመጀመሪያው ብየህ ነበር።

-መቼም እነዚህ ነገሮች ሁሉ በእርግጥ ለአይሁዳዊት ሴት ብቻ አይሆኑም !

-ፈጽሞ . . ይህ ለአይሁዳዊቱ ብቻ ነው። አይሁዳዊት ያልሆነችው ሴትማ ጉዳዩዋ ሌላ ነው!! እንደማትናደድና እንደማትከፋ ተስፋ አደርጋለሁ፤ሴት ቴልሙድ ውስጥ (ከኦሪት ቀጥሎ ሁለተኛው የአይሁዶች መጽሐፍ ነው) የሚከተለውን እናገኛለን ፦ ‹‹ከእስራኤል ሕዝብ ወገን ያልሆነች ሴት እንስሳ እንጂ ሌላ አይደለችም። ስለዚህም ከርሷ ጋር ዝሙት መፈጸም ወንጀል ተደርጎ አይቆጠርም፣የእንስሳት ዝርያ ናትና።››

-ምን ዓይነት ዘረኝነት ነው ! እንዴት ያለ አድልዖና ጠባብነት ነው! አሁንም እደግማለሁ የምትይውን ነገር አምኖ መቀበል ይከብደኛል። ስለ አይሁዳዊነት አንብቤያለሁ፣ኦሪትንም አብዛኛውን አንብቤያለሁ፤ይሁን እንጂ ምናልባት አንቺ ራስሽ ኦሪትን እንዳሻሽ እየተረጎምሽ ነው የሚመስለኝ።

-እንዲወጣልኝና እንዲቀለኝ በዝርዝር ለምን እንደነገርኩህ አላውቅም! ለግንዛቤ ያህል እናንተ ፕሮቴስታንቶች ወንጌልን እንደምታነቡት እኛ ኦሪትን አናነብም።

-እንዴት?

-ኦሪት የአምላክ መልክት ሲሆን ቴልሙድ ደግሞ የኦሪት ትንታኔና ማብራሪያ ነው። ኦሪትን ከቴልሙድ ለይተን በተናጠል መረዳት ትክክለኛ ተደርጎ አይወሰድም።

-ቴልሙድን ማነው የጻፈው?

-በአንድ ሺህ ዓመታት ውስጥ የተጻፈ ሲሆን ጸሐፊዎቹም እጅግ ብዙ ናቸው። ለምን ጠየቅህ?

-በጣም ስለ ተከፋሁና የሴቶች ጉዳይ በጣም ስለ አሳዘነኝ ነው። ከይቅርታ ጋር ስለ ሴቶች የነገርሽኝን ነገር አምኖ መቀበል ከብዶኛል።

-የነገርኩህ በአብዛኛው በቀጥታ ከኦሪት የተጠቀሰ ነው። ከቴልሙድ እንዲነግርህ ትፈልጋለህ? የቴልሙድ መጽሐፎች ጠቅላላ ድምር ስልሳ አራት ጥራዝ ነው። በውስጡ ከሰፈሩት ነገሮች ውስጥ ጥቂቱን መስማት ትፈልጋለህ?

-የሚያስከፋሽ ካልሆነ እባክሽን ንገሪኝ።

www.path-2-happiness.com

-እንግዲያውስ ድንቃድንቁን አዳምጥ . . በአንደኛው የቴልሙድ መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለውን ታነባለህ ፦ ‹‹ሴት ሕጻን መሬት በማጽዳት ላይ እያለች ለማዳ ውሻ ዘሎባት ብልቱን አስገብቶ ቢገናኛት የረከሰች ተደርጋ አትቆጠርም፤እስከ ከፍተኛ ደረጃ ሓኻም ድረስ እንዲያገባት ይፈቀድላታል!›› ለሴት ልጅ ወሲብ መፈጸም የሚፈቀድላትን የዕድሜ ገደብ ቴልሙድ በሦስት ዓመት ከአንድ ቀን ይወስናል!! በዚህ ዕድሜ ላይ ያለች ሴት ሕጻን የሓኻም (የሃይማኖቱ ከፍተኛ ሊቅ) ሚስት መሆን ችላለች::›› ወንድ ልጅ ወሲብ መፈጸም የሚፈቅድለትን ዕድሜ በተመለከተ የቴልሙድ ጸሐፊዎች በዘጠኝ ዓመት ከአንድ ቀን ይወስናሉ:: አንዳንዶቹ ሓኻሞች ደግሞ ስምንት ዓመት ከአንድ ቀን ያደርጉታል:: ቴልሙድ ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል ፦ ‹‹አንድ ወንድ ዕድሜዋ ከሦስት ዓመት ከአንድ ቀን በታች ከሆነች ሴት ሕጻን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ወሲብ ተደርጎ አይቆጠርም!! ይህ ሰውየው በልጅቷ ዓይን ውስጥ ጣቱን እንዳደረገ ብቻ ነው የሚቆጠረው!! ዕድሜው ከዘጠኝ ዓመት ከአንድ ቀን በታች የሆነ ልጅ ከደረሰች ሴት ጋር ወሲብ ቢፈጽም በእንጨት ስንጥር እንደ ወጋት ያህል ስለሚወሰድ ዝሙት ተደርጎ አይቆጠርም!! በእንስሳት ወሲብ መፈጸም ዝሙት ተደርጎ አይቆጠርም፣አድራጊውም አይቀጣም ! ከእንስሳት ጋር ወሲብ የፈጸመች ሴትም ዝሙተኛ አይደለችም፣መቀጫም አይጣልባትም፣የሚቀጣው እንስሳው ነው! ቀጥ ብሎ ባልቆመ ብልት ግንኙነት መፈጸምም እንደዚሁ ከዝሙት አይቆጠርም፣ቅጣትም አያስከትልም !

-ይቅርታ፣ይቅርታ ይበቃል:: ይህ አነጋገር አቅለሸለሾኛል:: አሁንም ለግልጽነቴ ይቅርታ አድርጊልኝና አንድ ጥያቄ አለኝ ፦ ለመሆኑ አንቺ ሃይማኖተኛ ነሽ ወይስ በአይሁድ ሃይማኖት ላይ ቂምና ቁጭት ያለሽ ሰው ነሽ?! በድጋሚ ይቅርታ አድርጊልኝና ሁሉም አይሁዶች እንደዚህ አይመስሉኝም !

-ልክ ነው . . ሁሉም አይሁዶች እንዳልኩህ አይደሉም፤እንደ ወዳጅህ እንደ ካኽ ያሉና ኦሪትም ሆነ ቴልሙድ ግድ የማይሰጣቸው ሴኩላሪስቶች አሉ:: ሌሎች ብዙ የተለያዩ ሴክቶችም ይገኛሉ:: አሳዛኝ ሆኖ እኛ ግን በጣም አጥባቂ ከሆነ ሃይማኖተኛ ቤተሰብ ነን፤እኔም ሃይማኖተኛ ነኝ:: እናም ያልኩትን ሁሉ ለምን እንደነገርኩህ አላውቅም! ምናልባት ወጥቶልኝ እንዲቀለኝ ፈልጌ፣ወይም ተሳስቼ፣አሊያም ራሴን ላንተ ለማቅረብ መጥቼ

እምቢ ስትለኝ የተዋራጅነት መንፈስ ተሰምቶኝ ራሴን ለመከላከል አድርጌው ይሆናል::

-ፈጽሞ አንቺን ለማዋረድ አልፈለኩም፤ይህ ጠባየም አይደለም:: ለመሆኑ ብንያምን አንቺን ወደኔ ሲልክሽ ምን ፈልጎ ነው?

-በትክክል ምን እንደሆነ አላውቅም:: የማወቀው ነገር ቢኖር ገና ያልሰጠኸው ገንዘብ አንተ ዘንድ እንዳለ ነው:: እኔ በገላዬ አንተን እስካላዝናናሁ ድረስ ገንዘቡን እንደማትሰጠው አድርጎ ያመነ ይመስለኛል::

-ገላሽ ውብና ግሩም ድንቅ ነው፣ብደሰትበት በጣም ደስ ባለኝ ግና . . እኔ ባለትዳርና ለመርሆዬ የምገዛ ሰው ነኝ:: ምናልባት ከሚገባው በላይ አጥባቂ ሆኜ ይሆናል:: ይቅርታ አድርጊልኝና ብንያምን በተሳሳተ መንገድ ተረድቶኝ ይሆናል:: እኔ ፈጽሞ እንዲህ አላልኩትም፣እንደዚያ ማለትም ፈጽሞ ተገቢዬ አይደለም::

-አዝናለሁ፣መቼም እኔ የመገልገያ ሸቀጥ ነኝ . . (ዓይኖቿ እንባ አቀረሩ፣ራሷን መቆጣጠር ተስኗት ለቅሷ ፈነዳ) . . ምናልባት በካኽ ምክንያት እንደዚያ ገምቶህ ይሆናል::

-እባክሽን ተረጋጊ . . ካኽ ከተፈጠረው ነገር ምን ግንኙነት አለው?

-ካኽ በመጣ ቁጥር ለብንያምን ይነግረውና አንድ ወይም ሁለት ቀን አብሬው አድራለሁ:: ካኽ ይሁዲ ነው፣ለዚህ ነው ኮንትራቱም ሴቱም ገንዘቡም ለርሱ የሚደረገው:: በመሆኑም የካኽ መልክተኛም ልክ እንደ ካኽ ሊስተናገድ ይገባል ማለቱ ነው፣ዋይ ውርደቴ ! ዋይ ቅለቴ !

ጆርጅ የሌቪን እንባ ሲመለከት የሚናገረው ጠፋው . . ማራኪ ውበቷንና ትኩስ እንባዋን እየተመለከተ በዝምታ ቆየ:: ከልብ አሳዘነችው፣ገላው ወደ ገላዋ ሲሳብ ተሰማው:: እንደሷ ላለች ሴት አዋራጅና አስቃቂ የሆኑ ቃላት እንዲትናገር ስለ ገፋፋት የአጥፊነት ስሜት ተሰማው . .

-ሌቪ እባክሽ እንባሽን ጥረጊ . . በጣም አዝናለሁ፣ሁለተኛ እንዲህ ያለውን ነገር አላነሳመም:: ፍንጃን ቡና ቢመጣልሽስ?

-ይቅርታ አትጠይቅ . . አንተ ምንም አላጠፋህም::

ወደ ሆቴሉ ካፌ አብረው ሄዱ:: ጆርጅ የጨዋታውን ርእስ ለመለወጥና ከሥጋዊ ስሜቱ ራሱን ለማራቅ ቆርጧል . .

-ከኩባንያችን ጋር የደህንነት ጥበቃ ውሉን መፈረም በተመለከተ ያለሽ ስጋት ምንድነው?

-ምንም ስጋት የለኝም::

www.path-2-happiness.com

-ላንቺ ጥያቄዎችና ለስጋቶችሽ መልስና ማብራሪያ እንድሰጥ ስለ ተጠየቀ ነው ከእንግሊዝ አገር የመጣሁት::

-አይ፣እውነቱ እንኳ ለብንያምን የሚሰጠውን ገንዘብ ይዘህ እንድትመጣ ስለ ተፈለገ ብቻ ነው:: ገንዘቡን አምጠተህ ለብንያምን አስረክበህ ከሆነ ውሉ እንደተፈረመ አድርገህ ቁጠረው::

-በእርግጥ ገንዘቡን ይዣለሁ፣ላንቺ ላስረክብ ወይስ ለብንያምን ልስጥ ?

-ለብንያምን ስጥ . . (በአዘኔታ መንፈስ ፈገግ አለችና) ፦ አንተም ጭምር ከመርሆህ ጋር ተጻራሪ ቢሆን እንኳ ለብንያምንና ለካኸ አገልግሎት ለመስጠት ትሰማራለህ ማለት ነው !

-በጣም አዝናለሁ፣የምትናገሪው ሁሉ እውነት ነው:: መወዳደር የነበረብን በምርታችን ጥራት እንጂ በጉቦና በሙስና መሆን አልነበረበትም . .

-እናም አይሁዳዊነት ከክርስትና የከፋ አይደለም ማለት ነዋ !

-ሊሆን ይችላል፣ይህን ያህል ለኔ ግልጽ ከሆንሽልኝ ዘንዳ እውነታውን እንድነግርሽ ፍቀጂልኝ::

-የትኛውን እውነታ ነው ? !

-ለትላልቆቹ ጥያቄዎቼ ምላሽ ማግኘት ባለመቻሌ ምክንያት ለጭንቀትና ለውጥረት ከተጋለጥኩ በኂላ በደስተኝነት ፍለጋ ጉዞ ላይ እገኛለሁ:: ለዚህም ሃይማኖቶችን መመራመር ጀመርኩ:: አሁን አይሁዳዊነትን በመመርመር ላይ እገኛለሁ፤ከዚያ ክርስትናንና እስላምን አስከትላለሁ::

-‹‹ደስተኝነት›› ግሩም ድንቅ ቃል ነው፣ዳሩ ግና በአይሁዳዊነት ውስጥ በተለይ ለወንዶች ብቻ የተወሰነ ነው የሚመስለው፣ወንድ በሆንኩ ብዬ ሁሌም እመኛለሁ !

-ደስተኛ ለመሆን አይደለም እንዴ ሃይማኖተኛ የሆንሽው ?

-ነበረ፣ግና የወዳኛው ዓለም ደስተኝነት ብቻ ነው መሰለኝ::

-ሃይማኖትሽን ለምን አልለወጥሽም ?

-አይሁዳዊነት ከክርስትና እና ከእስላም የተሻለ ነው:: ጥንታዊው ሃይማኖት ከመሆኑም በላይ የአይሁድ ሕዝብም ምርጡ ሕዝብ ነው:: የተናገርኩት ሁሉ ምናልባት የተሰማኝን የተዋራጅነት ስሜት ከራሴ ለማባረር ሊሆን ይችላል:: ይቅርታ አድርግልኝና መርሆዎችህን ተጻርረህ ጉቦ ስትሰጥ ግን የተዋራጅነት ስሜት አይሰማህም ?!

-አዎ ይሰማኛል፤ሕይወት ብዙ ጊዜ ወደ ሰዎች መጫወቻ እቃነት ትለውጠናለች:: ግና ተጫዋቾቹ በሙሉ አይሁዶች መሆናቸውን

አላስተዋልሽም?!

-እህህ፣ይህማ ትክክለኛና ተፈጥሯዊ ነገር ነው:: እኛ ምርጡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን . . እናም ይህን ተመራጭነት ይህን አይሁዳዊነት እንድተው ትፈልጋለህ?!

-ውበትሽ በድጋሜ ቦግ እንደማለቱ፣የውሉ ጉዳይ እና ጥቄዎችሽም እልባት ያገኙ እንደ መሆናቸው፣በአይሁዳዊነት ላይ የጀመርነውን ውይይት ብንቀጠል ቅር ይልሻል? የሴቶችን ጉዳይ አናነሳም፣ይህን ዕድሜ ጠገብ ሃይማኖታችሁን ይበልጥ ማወቅ እፈልጋለሁ::

የጆርጅ ስልክ አቃጨለ፣ብንያምን ነበር የደወለው:: ለማናገር ሌቪን ይቅርታ ጠየቀ . . ከሌቪ ጋር ምን ላይ እንደ ደረሱና ግንኙነታቸው እንዴት እንደ ነበረ ለመጠየቅ ነበር የደወለው . .

-ደህና ነኝ፣ሌቪም ደህና ነች፤ሥራችንን በተመለከተ አሁንም በመወያየት ላይ ነን::

-እንዴ ! እስካሁን አላጠናቀቃችሁም ?

-ገና ነው . . ምናልባት ዛሬ እንጨርሰው ይሆናል::

-ከፈለክ ዛሬና ነገ በሆቴሉ ማሟላት ትችላላችሁ፤እኛ የምትፈልጉትን ሁሉ ለመታዘዝ ዝግጁ ነን::

-መልካም፣ከተቻለ ግን ነገ ሳገኝህ እፈልጋለሁ፤ውሉን እንድንፈራረም ላንተ የሚሰጥ ቼክ ይዣለሁ::

-ከሌቪ ጋር ከጨረሳችሁት እኔ በፈለከው ሰዓት ታዛዥ ነኝ::

-አመሰግናለሁ፣ሰዓት ለመቀጣጠር እደውልልሃለሁ::

-ስልክህን እጠብቃለሁ፣ከፈለክ ሌቪ ነገ በቅድስቷ ከተማ አንዳንድ ቦታዎችን ለመጎብኘት ልትወስድህ ትችላለች::

-በዚህ ላይ ከርሷ ጋር እንመካከራለን . .

-በሉ እንግዲህ፣ጌታ ይባርካችሁ::

ጆርጅ የስልክ ጥሪውን አበቃ:: ወደ ሌቪ ውብ ሰማያዊ ዓይኖች ተመለከተ..

-ብንያምን የቼኩን ጉዳይ ማረጋገጥ ነው የፈለገው::

-ከኔ የተፈለገውን ሁሉ መፈጸሜንም ማረጋገጥ ነው የፈለገው::

-አንድ ጥሩ ሀሳብ አቅርቦልኛል::

-ጥሩ ሀሳብ ያመነጫል ብዬ አልገምትም፣ምን አለ ?

-ነገ ወደ ቅዱሳን ሥፍራዎች ለጉብኝት እንድንሄድ ነው::

-መልካም ነው . . ግን እንግዳ ነገር ነው:: አንዳንድ ጊዜ ካልተጠበቀ ሰው

www.path-2-happiness.com

ጥሩ ሀሳብ ይቀርባል::

-አሁን አስራ ሁለት ሰዓት ነው፣ከፈለክ ስለ አይሁዳዊነት የጀመርነውን እንቀጥለሳለን:: ነገ ደግሞ የአይሁድ ቅዱሳን ሥፍራዎችን ለመጎብኘት በጧት እጠብቀሃለሁ::

- መልካም፣አሁን በውይይታችን እንቀጥልና የቅዱሳን ስፍራዎች ጉብኝታችን ተነገወዲያ ማለትም ቅዳሜ ይሁን እላለሁ:: (በመቀጠል በማፈር ስሜት ፈገግ አለችና) ፦ ቅዳሜ ለጉብኝት እንሄዳለን፣ሌላ የምትፈልገው ነገር ካለ ዛሬ ወይም ነገ ነው::

-ሌላ ነገር . . ገባኝ፣በእርግጥ ውበትሽ ተፈታታኝ ነው::ይሁን እንጂ እኔ ባለትዳር ነኝ፣መርሆዬ ይከለክለኛል ብየሻለሁ::

-የበለጠ ግልጽ ለመሆን፣ባለትዳርና ሃይማኖተኛ የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው እንዲህ ያሉ ነገሮችን እምቢ የማይሉት::

-ልክ ነው . . አዝናለሁ እውነትሽን ነው:: እኔ ግን በባለቤቴ ላይ ክህደት መፈጸም ስለሆነ ለኔ ተገቢ አይደለም የሚል እምነት አለኝ፤እሷ እንድትፈጽም እንደማልቀበል ሁሉ እኔም አልቀበልም::

-የማስመሰል ሳይሆን አንተ በእውነት ድንቅ ሰው ነህ፣ላንተ ያለኝ አክብሮት የበዛ ነው::

ግልጽ በሆነ የአድናቆት ስሜት ሁለቱም ዓይን ለዓይን መተያየቱን ቀጠሉ:: ሳያስብ እጁ ለስላሳ እጇን ያዝ አደረገ፤ግን ወዲያውኑ ነቃና እጁን አላቆ በማፈር ስሜት እንዲህ አላት . .

-ምስጋና የሚገባው ላንቺ ነው:: እኔ መመስገን ያለብኝ አይመስለኝም:: ዋናው ነገር አንቺ እንዳልሽው ጉብኝታችን ቅዳሜ ቢሆን መልካም ነው ባይ ነኝ::

-ጥሩ . . ውይይታችንን እንቀጥል::

-ኦሪትንና ተልሙድን ይበልጥ ለማወቅ እፈልጋለሁ::

-እንዳልኩህ ሁሉ ኦሪት ከእግዚአብሔር የተላለፈ ነው ብለን ነው የምናምነው:: ተልሙድ ግን የኦሪት ማብራሪያዎች፣ትንታኔዎችና ሕግጋት ዝርዝር ሲሆን ቀደም ብሎ በቃል ሲተላለፍ ቆይቶ ኋላ ላይ በጽሑፍ የተጠናቀረ ነው::

-ቴልሞድ የሰዎች ቃል ነው ማለት ነው !

-አዎ፣ግን በርሱ አማካይነት ብቻ እንጂ ኦሪትን መረዳት አይቻልም:: ቅድም እንዳልኩህ እኛ እንደ ክርስቲያኖች አይደለንም::

-ኦሪት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል በቀጥታ ለምን አትወስዱትም?

-ላንተ ፍጹም ለመሆን ቃል ገብቻለሁ፤እውነቱን ለመናገር ኦሪት ራሱ ብዙ ችግሮች አሉበት:: ምናልባት ስለ ሴቶች የሚናገረውን አንብበህ ይሆናል::

-የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ችግር ይኖርበታል? አልገባኝም!

-በጣም ያሳዝናል፣እኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ ነው እንላለን፤ዳሩ ግን የመዛባትና የመለዋወጥ ሁኔታ የደረሰበት መሆኑን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች ይገኛሉ::

-ስለ መዛባቱ ማስረጃ ?! ኦሪጂናል ቅጂው ዬት ነው ያለው ?

-የኦሪት ኦሪጂናል ቅጂ ጠፍቷል:: ያሉት ሦስት የተለያዩ ቅጂዎች ናቸው:: አንዳንዶቹ ጭማሬ ያለባቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ እርስበርስ የሚጋጩ ነገሮች አሉባቸው:: ከሦስቱ ቅጂዎች አንዱ የሆነው የግሪክ ቅጂ እስከ አስራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት ተሰጥቶት የቆየ ቅጂ ነው:: በዚያን ጊዜ ውስጥ የዕብራይስጡን ቅጂ የተዛባና ተአማኒነት የጎደለው አድርገው ይቆጥሩት ነበር:: የግሪክ ቅጂ በግሪክ ቤተክርስቲያንና በተቀሩትም የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አሁንም ድረስ ተቀባይነት ያለው ቅጂ ነው:: የዕብራይስጡ ቅጂ ደግሞ በአይሁዶችና በፕሮቴስታንቶች ዘንድ ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን 39 መጽሐፎችን ያካተተ ነው:: እስከ አስራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የግሪኩ ቅጂ በክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት የተቸረው ትክክለኛው ቅጂ ተደርጎ ሲወሰድ የቆየ ሲሆን፣የዕብራይስጡ ቅጂ ግን በወቅቱ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት በነበረው በግሪኩ ቅጂ ላይ ጥርጣሬ ለማሳደር ዓላማ ሆን ተብሎ በአይሁዶች እጅ በ130 ዓመተ ልደት እንዲዛባ ተደርጓል ተብሎ ይታመናል:: ማዛባቱ ከክርስቲያኖች በተጨማሪ ሳምራውያን አይሁዶችንም ዒላማ ያደረገ ነበር:: በአስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የፕሮቴስታንት እምነት ከመጣ በኋላ ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነና ፕሮቴስታንቶች ለዕብራይስጡ ቅጂ ትክክለኛነት ዕውቅና በመስጠት የግሪኩ ቅጂ የተዛባና ተአማኒነት የሌለው ነው የሚል አቋም ማራመድ ጀመሩ:: ሦስተኛው የሳምራዊው ቅጂ ነው:: ሳምራ በናፖሊስ ተራሮች የሚኖሩ አይሁዶች ጭፍራ ሲሆን ይህ ቅጂ ከብሉይ ኪዳን ሰባት መጽሐፎችን ብቻ የሚያካትት ነው:: ከሰባቱ ውጭ ያሉት በሳምራ አይሁዶች ዘንድ የተዛባና መሰረት የሌለው ጭማሬ ነው:: ቅጂው በሌሎች ቅጂዎች ውስጥ የማይገኙ ዐረፍተ ነገሮችንና አንቀጾችን ያቀፈ

www.path-2-happiness.com

ሲሆን አንዳንድ የፕሮቴስታንት ተመራማሪዎች ከዕብራይስጡ ቅጂ ያነሰ አድርገው ቢወስዱትም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከዕብራይስጡ ቅድሚያ ይሰጡታል።

- በጣም የሚገርም ታሪክና ትኩረትን የሚስብ መፋለስ ነው። ይሁንና የዚህ መዛባትና ኢተአማሚነት መገለጫዎች ምንድናቸው ? . . ማለቴ ከሴቶችና ከወሲብ ርእስ ጉዳይ ውጭ ያሉት ?
- በጣም ብዙ ናቸው! ከነዚህ መካከል ጧት ያነሳነውና ፈጣሪ አምላክን ተገቢው ባልሆኑ ባህርያት መግለጽ አንዱ ሲሆን፣ ነብያትን በኃጢአት ሥራዎች ፈጻሚነትና በእኩይነት መግለጽም ይገኙበታል። ሌሎች ብዙ ብዙ ነገሮችም . .
- ይቅርታ ላቋርጥሽና . . ነብያትን በኃጢአት ሥራዎች ፈጻሚነትና በእኩይነት መግለጽ ነው ያልሽው? !
- ታውቃለህ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው እንደዚህ የምናገረው! እውነቱን ለመናገር ሁኔታዬ ለኔ ለራሴም በጣም አስገርሞኛል። ይሁን እንጂ ይህን በማድረጌ ከውስጤ ደስታ ይሰማኛል፤አንድ ዓይነት የስሜት ማስተንፈሻ መንገድ ይሆን ወይስ የሰይጣን ጉትጎታ?! እኔ እንጃ ግና ይህን በማድረጌ ደስተኛ ነኝ። ምሳሌዎችን ልስጥህ ፦ ኦሪት ውስጥ የእግዚአብሔር ነብይ ኖሕ አስካሪ መጠጥ ጠጥቶ ራቆቱን እንደሆነ ተደርጎ ሲገለጽ እንዲህ ተብሏል ፦ ‹‹ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ፣ወይንም ተከለ። ከወይን ጠጅም ጠጣና ሰከረ፤በድንኳኑም ውስጥ ዕወራቆቱን ሆነ።›› ነብዩ ሎጥን በተመለከተም ፦ ‹‹ሎጥም . . ከሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ጋር በተራራ ተቀመጠ፤በዋሻም ከሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ጋር ተቀመጠ። ታላቂቱም ታናሺቱን አለቻት ፦ አባታችን ሸመገለ፣ በምድርም ሁሉ እንዳለው ልማድ ሊገናኝን የሚችል ሰው ከምድር ላይ የለም፤ነዪ አባታችንንም የወይን ጠጅ እናጠጣውና ከእርሱ ጋራ እንተኛ፤ከአባታችንም ዘር እናስቀር። አባታቸውንም በዚያች ሌሊት ደግሞ የወይን ጠጅ አጠጡት፤ታናሺቱም ገብታ ከእርሱ ጋር ተኛች፤እርሱም ስትተኛና ስትነሣ አላወቀም። የሎጥም ሁለቱ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው ፀነሱ። ታላቂቱም ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ሞዓብ ብላ ጠራችው፤እርሱም እስከ ዛሬ የሞዓባውያን አባት ነው። ታናሺቱም ደግሞ ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ፦ የወገኔ ልጅ ስትል አሞን ብላ ጠራችው፤እርሱም እስከ ዛሬ የአሞናውያን አባት ነው።›› የሚል ሰፍሯል። ሌሎችም ብዙ ብዙ መሰል ነገሮች አሉ። ለጊዜው እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች

በቂ ይመስሉኛል።

- ሌቪ ይቅርታሽን፣ትተን ባለፍን ቁጥር ለምንድነው ወደ ወሲባዊ ጉዳዮቹ ዳግም የምትመለሺው?
- ሳንተ ፍጹም እውነተኛ ለመሆን ለራሴ ቃል የገባሁ በመሆኔ ነው፤የጠየከኝ ደግሞ አንተው ነህ።
- ወደ ሌላ ርእስ ጉዳይ መሄድ እፈልጋለሁ።

ሌቪ ፈገግ አለች፣ጉንጮቿ በሀፍረት ቀሉ። ቁንጅናዋና ፍካቷ ይበልጥ ደመቀ . .

- እሺ፤በል ቀጥል ጥያቄዎችህን ወደ ወሲብና የሴቶች ጉዳይ እንደማትለውጥ ተስፋ አደርጋለሁ።

የጆርጅ ከጾታዊ ጉዳዮች የመራቅ ጥያቄ፣ከፊትለፊቱ በተቀመጠችው እንቡጥ ጽጌሬዳ ኮረዳ ውበት ምክንያት ዓይኖቹ በአካሉ ላይ ከሚያደርጉት ጉትጎታ ለመሸሽ እንጂ ሌላ አልነበረም። ከፊቱ ከተቀመጠው ፈታኝ ውበት ተጎንጭቶ የመርካት ብርቱ ጥማትና ጥልቅ ፍላጎት እያደረበት የመጣ አካሉን ጆሮው እንዲጎተጉተው አይፈልግም። በካትሪና እና በመርሆው ላይ ክህደት እንዳይፈጽም ስጋት አድሮበታል። ሕይወት ምንኛ ወራዳና ምንኛ አስቸጋሪ ናት! ‹‹ደስተኝነት ነገሮችን አቅልሎ በመውሰድ ውስጥ ነው›› የሚለው የኣደም ተደጋጋሚ ብሂል ትዝ አለው። በውስጡ አጉተመተመና ‹‹ወይኔ ከመርሆዬ ጋር በቀላሉ መኖር በቻልኩ›› ብሎ ርእሱን ለመቀየር ሞከረ . .

- መሰረትሽ ከኦስትሪያ ነው ብለሽኛል።
- ኣይ፣ከእስራኤል ነኝ ነው ያልኩት።
- አዎ፣ማለቴ ወላጆችሽ ከኦስትሪያ የመጡ ናቸው። ይቅርታ አድርግልኝና በእንግሊዝ አኃዛዊ መረጃ መሰረት በ1945 በፍልስጥኤም ውስጥ የአይሁዶች ቁጥር 38%፣የሙስሊሞች ቁጥር 58%፣የክርስቲያኖች ቁጥር ደግሞ 8% ነበር። ዛሬ ያለው የአይሁዶች ቁጥር ከፍ ያለው ከ500000 እስከ 600000 የሚደርሱና አይሁዶች ነን የሚሉ ሰዎች ከ1920 እስከ 1945 ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ መጥተው በመስፈራቸው ምክንያት ነው። ታዲያ ከውጭ መጥታችሁ መሬታቸውን በወረራ የያዛችሁት እናንተ ስትሆኑ እንዴት ነው ሙስሊሞችንና ክርስቲኖችን ሽብርተኞች አድርጋችሁ የምትወስዱት?!
- ይቅርታ . . ወራሪዎቹ እናንተ እንግሊዞች ናችሁ፣እናንተ ናችሁ

www.path-2-happiness.com

መሬታችንን የሰጣችሁንና መብታችንን የመለሳችሁልን::

-እንግሊዞች አንቺ እንደምትይው መብታችሁን የመለሱላችሁ ለምንድነው ? ለናንተ ነጻ ግልጋሎት ለማበርከት ዓላማ ብቻ ይሆን?!

-የኔ ጉዳይ መሬታችን መሆኑና ለኛ የተመለሰልን መሆኑ ነው:: እንግሊዝ ለኛ አገልጋይ ለምን ሆነች ? የሚለው ላንተ እንጂ ለኔ የሚቀርብ ጥያቄ አይደለም . . እንግሊዝና አውሮፓ እንደ አገለገሉን ሁሉ በአስከፊ ሁኔታ ጨፍጭፈውናል፣ይህን አታውቅም?!

-ሆሎኮስትን ማለትሽ ነው?!

-እኛ ለዘመናት ብዙ የተጨቆን ሕዝብ ነን:: ሆሎኮስትም በኛ ላይ ከተፈጸሙት ኢሞራላዊ ግፎች የቅርብ ዘመኑ አንዱ ምዕራፍ እንጂ ሌላ አይደለም::

-ወደዚህ በመጣሁበት ምሽት ካቶሊካዊቷ ባለቤቴ አይሁዶች በክርስቲያኖች ላይ ስለ ፈጸሙት ግፍና ጭቆና ስትነግረኝ ነበር:: ሁሉም የዓለም ሕዝቦች ተጨቁነናል ይላሉ ማለት ነዋ!

-ልክ ነህ . . ሌላው ቀርቶ አባቴን የገደሉት አረመኔዎቹ ሙስሊሞች እንኳ ተጨቁነናል ይላሉ:: ዳሩ ግና ታሪክና ተጨባጩ ሁኔታ እውነታውን ይሰጡሃል::

-ክርክር እንደምትወጂና ግልጸኝነትም እንደማያስጨንቅሽ ነግሬሽኛል:: ታዲያ ሙስሊሞች መጨቆናቸው፣መሬታቸው በወረራ ተወስዶ ከገዛ አገራቸው መባረራቸው፣መገደላቸውና መሰደዳቸው እንዴት አልታየሽም?!

-ለአሸባሪዎች ይህና ከዚህም የከፋ ይገባቸዋል:: ደሞም ይህን ያደረገው ማን ሆነና! ከኛ በፊት እናንተው ናችሁና እኛን አትተቹን::

-ወደ አጥቂነት ተሸጋግረሻል፣ልክ ነው ከናንተ በፊት ለናንተ ስንል እኛ አድርገነዋል:: ይሁንና ግፍ የተዋለባቸው ጭቁኖች መሆናቸው እንዴት አይታሽም ?

-ነገርኩህ እኮ፣ይህና ከዚህም የከፋ ነገር ይገባቸዋል:: አረመኔዎች፣ኋላ ቀሮች፣ጨካኞችና አሸባሪዎች ናቸው . .

-ፍልስጥኤም ውስጥ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችም ተጨቋኞች ናቸው !

-ፍልስጥኤም ሳይሆን እስራኤል ማለትህ ነው::

-አዎ፣ክርስቲያኖች እስራኤል ውስጥ ከአይሁዶች በኩል ግፍና ጭቆና ይፈጸምባቸዋል !

-አትቆጣ፣ክርስቲያኖች አያያዛችን ካላማራቸው ወደ አውሮፓና ወደ አሜሪካ ወይም ወደ ፈለጉት ቦታ መሄድ ይችላሉ!

-እህህ፣ይህ ጨካኝ ቁርጠኛ አነጋገርሽ ከቁንጅናሽ ጋር ይጋጫል:: አንቺን የመሰለች ውብ ቆንጆ እንዲህ ያለውን ጭካኔ የተሞላበት ግርድፍ ነገር ትናገራለች ብዬ ማሰብ ይከብደኛል!

-እኛን ለማገልገል ዝግጁ ያልሆነ ሁሉ እኛ ዘንድ የሚጠብቀው ግድያ ብቻ ነው! ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ነው::

-የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች እንዲህ ናቸው ማለት ነው ?!

-አዎ፣ኦሪት ውስጥ የሚከተለው ሰፍሯል ፦ ‹‹የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦ የእናንተ ሰው ሁሉ ሰይፋን በወገቡ ላይ ይታጠቅ፣በሰፈሩም ውስጥ በዚህና በዚያ ከበር እስከ በር ተመላለሱ፣የእናንተም ሰው ሁሉ ወንድሙን ወዳጁንም ጎረቤቱንም ይግደል አላቸው::›› በተጨማሪም ፦ ‹‹እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ ፦ እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤ሽማግሌውንና ጎበዙን ቆንጆይቱንም ሕጻናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ፤›› ይላል:: ብሉይ ኪዳን ሌላ ቦታ ላይ ፦ ‹‹አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ፣ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣አትማራቸውም፤ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ሕጻኑን በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል::›› ይለናል:: እነዚህ ጥቅሶች ይበቁሃል ወይስ ልጨምርልህ?

-ይቅርታ . . አስከፋሁሽ መሰለኝ:: ትንሽ ተረጋጊ . . ይኸ ማንም ልሰማው የማይችል ሽብርና ሽብርተኝነት ነው !

-እኔ የተረጋጋሁ ነኝ:: የነገርኩህ ግን ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሰፈረውን የእግዚአብሔር ቃል እንጂ የራሴን ቃል አይደለም !

ጆርጅ አስተናጋጁን ጠራና የብርቱካን ጭማቂ እንዲያመጣለት አዘዘ . . ውጥረቷንና ስሜታዊነቷን ለመሸሸግ ስትሞክር ወደነበረቸው ሌቪ ዞር አለና . .

-ይበልጥ ለመረጋጋት ምን ይምጣልሽ ?

-መልካም ፈቃድህ ከሆነ የሎሚ ጭማቂ::

ጆርጅ ወደ ሌቪ እተመለከተ፣በውበቷ ልስላሴና በመግደል፣በማፈናቀልና በምትናገረው ርህራሄ አልባ ጭካኔ መካከል ያለውን ተቃርኖ እያስተዋለ ለአፍታ በዝምታ ቆየ . . አቀርቅራ የቆየችው ሌቪ እያነባች ራሷን ቀና አደረገች . .

www.path-2-happiness.com

- አባተ ሞተ፣እኔም የብንያምን መጫወቻ ሆንኩ:: ይህ ሁሉ ለዘመናት የተጨቆን በመሆኑ ምክንያት ነው:: እናም እነዚያ አሸባሪዎች ተጨቋኖች መሆናቸውን አምኜ እንድቀበል ነው የምትፈልገው?!
- በይ ሎሚውን ጠጭው . . የሚረብሽሽ እስከሆነ ድረስ ይህን ርእስ ተዪው..
- አይረብሸኝም፣መቀጠል ትችላለህ፤አሁን በጣም ተረጋግቻለሁ::
- ግልጽ ሆነሽ እውነቱን ንገሪኝና አሁን የጠቀስሽያቸውን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች አምነሽ ትቀበያለሽ ?
- ግልጽ ሆኜ እውነቱን ለመናገር . . አልቀበልም::
- ለምን ?
- ብሉይ ኪዳን በስህተትና በመዛባት የተሞላ ነው ብየህ አልነበረም? እንዲህ ዓይነቱ ጭካኔ ከርህሩሁ እግዚአብሔር አምላክ ዘንድ የተላለፈ ሊሆን አይችልም !
- እውነትሽን ነው . . እግዚአብሔር ርህሩህ አዛኝ ነው::
- እንደገና ወደ ወሲብና ሴቶች ጉዳይ ልመልስህና የሚከተለውን የብሉይ ኪዳን ጥቅስ አዳምጥ ፦ ‹‹አሁን እንግዲህ ከልጆቹ ወንዱን ሁሉ ግደሉ፣ወንድንም በመኝታ የሚያውቁትን ሴቶች ሁሉ ግደሉ:: ወንድን የማያውቁትን ሴቶች ልጆችን ሁሉ ግን ለራሳችሁ አድኑአቸው::›› (በድጋሜ ፈገግ አለችና) ፦ ከፈለክ ይህን ጥቅስም አክልበት ፦ ‹‹የብንያምንም ልጆች እንዲህ ብለው አዘዙአቸው ፦ ሂዱ በወይኑም ስፍራ ተደበቁ፤ተመልከቱም፣እነሆም፣የሴሎ ሴቶች ልጆች አታሞ ይዘው ለዘፈን ሲወጡ ከወይኑ ስፍራ ውጡ፣ከሴሎም ሴቶች ልጆች ለየራሳችሁ ሚስት ንጠቁ፣ወደ ብንያም ምድርም ሂዱ::›› (በሹፈት ሳቀችና) ፦ አሁንም ወደ ወሲብና ወደ ሴቶች ተመለስን፣ያሁኑ ግን በግድያና በጠለፋ መልኩ ነው ! ርእሰ ጉዳዩን እርግፍ አድርገን እንድንተወው ትፈልጋለህ ?
- በጣም የሚገርም ነው ! የምሰማውን ለማመን እየተቸገርኩ ነው ! አዎ፣ርእሱን ብንተው ይመረጣል:: መልካም ፈቃድሽ ከሆነ ግን የሴሎ ሴት ልጆች ማን ናቸው ? ሴሎስ ማነው ?
- ሴሎ ማለት እኛ ዘንድ በሚሰራባቸው ትንታኔዎች ክርስቶስ ወይም መሲሑ ማለት ነው:: ዋናው ነገር የተጠቀሱት አይሁዳዊያት ያልሆኑ የናንተንና የሙስሊሞችን ሴቶች የመሳሰሉ ሴቶች ናቸው:: ይቅርታ አድርግልኝና አስበርግገህ ሚዛኔን አሳጣሀኝ::

- ምንም አይደለም፣አሁን ጊዜው በጣም የሄደ ይመስለኛል፤እንድትረጋጊ እራት ልጋብዝሽ::
- ኦህ . . ለካስ ሳይታወቀኝ በጣም መሽቷል፤አሁን ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ሆኗል:: ትእዛዝህ ከሆነ እሽ እቀበላለሁ፤ አለዚያ ግን መልካም ፈቃድህ ከሆነ መሄድ እፈልጋለሁ::
- እንዲህ ዓይነት አነጋገር አያስደስተኝም፣እኔ አንቺን ለማዘዝ አልመጣሁም:: ግልጸኝነትሽ በጣም እንዳስደሰተኝ ነግሬሻለሁ:: መታደልን ፍለጋ በማደርገው ጉዞ ላይ ብዙ ትጠቅሚኛለሽ፣ ያንቺ ፍላጎት ከሆነ ብቻ ነው ካንቺ ጋር መወያየት ደስ የሚለኝ::
- ለትህትናህ በጣም አመሰግናለሁ፣እናም ነገ እንገናኝ::
- የምንገናኘው ተነገ ወዲያ ቅዳሜ እንዲሆን ተስማምተናል !
- የአይሁድ ቅዱሳን ስፍራዎችን የምንጎበኘው ተነገ ወዲያ ነው:: ከፈለክ ግን ውይይታችንን ነገ መቀጠል ይቻላል::
- ነገ ጧት ብንያምንን ለማግኘት ስመጣ እንገናኛለን:: ከተቻለ ግን የትንሣኤ ቤተክርስቲያንን እና የማርያምን ቤተክርስቲያን መጎብኘት እፈልጋለሁ::
- የትንሣኤ ቤተክርስቲያን ግን የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን አይደለም፣ፕሮቴስታንት ነኝ ብለህ የለ? . . (መስህብነትን በተላበሰ የመሽኮርመም ስሜት ቀጠለችና) ፦ ወይስ እያታለልከኝ ነው ?
- ለምን አታልልሻለሁ? እጎበኛለሁ ብዬ ለካቶሊካዊቷ ባለቤቴ ቃል ስለ ገባሁ እጎበኛለሁ::
- ባለቤትህን በጣም ትወዳታለህ ማለት ነው:: ወደ ብንያምን ቢሮ እንዲያደርስህ ጧት ሁለት ሰዓት ላይ ሾፌሩን እልክልሃለሁ:: ነገ ዓርብ ስለሆነ ሁለቱን ቤተክርስቲያኖች ለመጎብኘት በጊዜ መውጣት ይኖርብሃል::
- ዓርብ ነው ስትዪ ምን ማለትሽ ነው?
- ማለቴ በሁሉም መንገዶች ላይ የፍተሻ ኬላዎች ይኖራሉ:: አሸደባሪዎቹ ለዓርብ ጸሎት ሲሄዱ የሽብር ጥቃት እንዳይፈጽሙ እርግጠኛ ለመሆን ሲባል ፍተሻዎች ይበዛሉ::
- ወደ ቢሮው ለመሄድ ሁለት ሰዓት ላይ ዝግጁ ሆኜ እጠባበቃለሁ . . ብድግ ብሎ ሌቪን ጨበጣትና ዓይን ዓይኗን እያየ ፦ በጣም ነው የማመሰግነው፤ስለ ረበሽኩሽ ይቅርታ አድርጊልኝ::
- ለትሕትናህ፣ለጨዋነትህ፣ለግልጽነትህ፣ለባለቤትህና ለመርሆህ ታማኝ በመሆንህ ማመስገን ያለብኝ እኔ ነኝ::

www.path-2-happiness.com

- አንቺ ግሩም ድንቅ ሰው ነሽ !
- አንተ በምትጓዝበት የደስተኝነት ጎደና ካንተ ጋር ብጓዝ ምነኛ ደስ ባለኝ ነበር! ጻሩ ግና ያለሁበት ሁኔታ አያስችለኝም።
- ማን ያውቃል? ሊሆን ይችላል . . ለማንኛውም አንቺ ቆንጂት ጧት እንገናኛለን።
- ሌቪ ከሄደች በኋላ ጆርጅ እራቱን በችኮላ በላ። ምስሏ ግን ከአእምሮው አልጠፋ ብሎታል . . ከፍተኛ የሆነ የቅርበት ስሜት አሳድራበታለች፤ለምን እንደሆነ ግን አያውቅም። በተፈታታኝ ውበቷ ምክንያት ይሆን ? ወይስ ለርሱ በጣም ግልጽ በመሆኗ? ወይስ ስለ አሳዘነችው ይሆን? . . ግራ የመጋባት ስሜት ውስጥ ነው። ፈገግታዋ፣እንባዋ፣ቁጣዋና ስሜታዊነቷ . . ሁሉ ነገሯ ትዝ ትዝ ይለዋል . . ሁለመናዋ ከፊቱ ድቅን ይላል። ከልብ አዘነላት . . የተዛባ ጨቋኝ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ሰለባ ነች . . በእግዚአብሔር አምላክ ስም የሚፈጸምባትን ይህን ሁሉ ግፍና ጭቆና ይህች ሚስኪን ሴት እንዴት ሆና ትቋቋማለች !!
- ሌቪንና ውበቷን ለመርሳት እየሞከረ ወደ ክፍሉ ሄደና ዜና ለመስማት ቲቪ ከፈተ። የለንደኑ ፍንዳታ ዜና ጋብ ብሏል፤የፍንዳታው ተጠያቂ የሲታ ተገንጣይ ቡድን መሆኑ፣ሲፈለግ የነበረው ፓኪስታናዊ የተያዘ ቢሆንም ፈርቶ ከመደበቁ ውጭ ከፍንዳታው ጋር ምንም ግንኙት የሌለው መሆኑ በመረጋገጡ በነጻ መለቀቁን ተረዳ። . . ‹‹አንተ ከሪሙሏህ ነጻ መሆንህ ተረጋገጠ!›› አለ ለራሱ። ከዜናዎቹ አንዱ የእስራኤል መንግስት ለነገው የዕለተ ዓርብ የሙስሊሞች ጸሎት ዕድሜያቸው ከሃምሳ በታች የሆኑትን ሙስሊሞች የሽብር ጥቃትን ለመከላከል ሲባል በአል አቅሷ መስጊድ እንዳይሰግዱ መከልከሉን የሚመለከት ነበር . . ቲቪውን ዘግቶ ኢሜይሉን ከፈተ። ለአዳዲስ መልክቶች መልስ ከሰጠ በኋላ ሌቪ ከነገረችው የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ውስጥ አንዳንዶቹን ጽፎ ለቶምና ለኣደም ለመላክ ወሰነ . . መልእክቱን ከላከላቸው በኋላ ሰዓቱን ሲመለከት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ነበር። ለመተኛት ወደ አልጋው ሄደ፣ግና የሌቪን ሀሳብ ከአእምሮው ማራቅ አልቻለም። ምሽቱን ከርሱ ጋር እንዳታድር ባለማድረጉ ተሳስቶ እንደሆን ራሱን ጠየቀ ! አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣እሽ ብሏት ኖሮ፣እንዴት ያለ አዝናኝና አስደሳች ሌሊት ይሆን ነበር። እርሷ ለሁሉም ነገር ዝግጁ መሆኗን ገልጻለት ነበር፤ ከዚያ በፊትም ከካኽ ጋር ፈጽማው ነበር። በዓለማዊ ሕይወት ከመደሰትና አዝናኝ ሕይወትን መኖር የሚከለክል

መርህ የምን መርህ ነው?! ካትሪና ከቶም ጋር ክህደት ፈጽማብኛለች ብሎ በገመተ ጊዜ ተሰምቶት የነበረው የቅናትና የቁጣ ስሜት በዚህ ጊዜ ለምን እንዳስታወሰ አያውቅም። ‹‹ምን ዓይነት የግጭትና የመፋለስ ሁኔታ ውስጥ ገባሁ›› ሲል በውስጡ አጉረመረመ። ለራሴ ክህደት መፈጸም እፈልጋለሁ፣በኔ ላይ ሲፈጸም ግን እናደዳለሁ፤ጉቦ እሰጣለሁ፣ጉቦ የሚቀበል ሰው መርህና ስነ ምግባር የጎደለው ሰው ነው የሚል አቋም አራምዳለሁ። መንፈሴ፣ነፍሴ፣አመለካከቴ፣ሕይወቴ፣ደስተኝነቴና መርሆዎቼ ጽናት ያላቸው እንዲሆኑ ስንቴ እመኛለሁ . .

(4)

ጆርጅ ጧት ከሁለት ሰዓት አስቀድሞ ነበር ቁርሱን በልቶ ሾፌሩ እስኪመጣ ድረስ ወደ ክፍሉ የተመለሰው። ልክ ሁለት ሰዓት ከእንግዳ መቀበያ ተደውሎ ሰው እየጠበቀው መሆኑ ተነገረው። ሲሄድ ባልጠበቀው ሁኔታ የመጣው እንደ ተባለው ሾፌሩ ሳይሆን ሌቪ ራሷ ነበረች። በጣም ደስ ብሎት በፈገግታ ጨበጣት . .

- አንቺን ማስቸገር አልፈለኩም ነበር።
- ተገቢህ ነው . . ውይይትህም በጣም ነው የሚያረካኝ።
- ለበጎ ግምትሽ፣ለጸባይሽና ለመልካም ስነ ምግባርሽ ምስጋናዬ የላቀ ነው። ብንያምን አሁን እቢሮው ይኖራል ?
- አዎ፣እቢሮው ይጠብቀሃል፣እንደምትመጣ ነግሬዋለሁ።
- አመሰግናለሁ፣ረስቼ አልደወልኩለትም ነበር።
  ፊቷን በፍካት ያሸበረቀ ማራኪ ፈገግታ አሳየችው . .
- ካንተ ዘንድ ወጥቸቼ ወደ ቤት ከመድረሴ በፊት ካንተ ጋር ማደሬን ለማረጋገጥ ብንያምን ሲደውልልኝ ነበር። አንተ ካኽ አለመሆንህን እና እኔን የማትፈልግ መሆንህን አምኖ አልተቀበለም። ጧት ወዳንተ ስለሚመጣ ከርሱ ከራሱ ማረጋገጥ ትችላለህ ነበር ያልኩት።
  በቁርጠኝነትና በምር እየተመለከታት እንዲህ አላት ፦
- አይፈልግሽም ያለው ማነው?!
  ሌቪ ውስጧ ተረበሸ። የስሜቶቿ፣የአመለካከቶቿ፣የሥጋዊ ፍላጎቶቿ . . ውስጣዊ ግጭቶች ከገጽታዋ በግልጽ ተነበቡ . .
- ምን እያልክ ነው? እኔ ከሄድኩ በኋላ የተለወጠ ነገር አለ'ንዴ?
- ኣይ፣ዕውቀትሽን፣ብሩህ አእምሮሽን፣መንፈስሽን፣ጸባይና ስነ ምግባርሽን

www.path-2-happiness.com

እፈልጋለሁ:: ገላሽ ግን እንደ ዕንቁ ለእይታና እንደ ጽጌሬዳ ለመዓዛው የሚያጓጓ ነው:: ግና ሴትን ከሴትነቷና ከገላዋ አንጻር ብቻ መመልከት አሳፋሪ ተግባር ነው:: አንቺን ማጣት ወይም የራሴን መርሆ ማጣት አልፈልግም::

እንደ ስሜቷ ሁሉ ባልተረጋጋ እንቅስቃሴ የጸጉሯን ዘለላዎች ከፊቷ ላይ ከፍ ስታደርግ ግንባሯን በግራ እጇ አባበሰች::

- ወይኔ . . ለምን ብዙ እንደፈራሁ አላውቅም ?
- እርሱ ባቀረበው ሀሳብ መሰረት ቅዱሳን ስፍራዎችን ለመጎብኘት እንደምንሄድ ነግረሽዋል ?
- አልነገርኩትም፣አንተ ንገረው::
- እውነቱን ለመናገር ብንያምን ብዙም አያስደስተኝም፣መርሆዬን ረግጬ ጉቦ ስሰጠው ውርደት ይሰማኛል:: ይሁን እንጂ ወደዚህ አገር ከመምጣቴ በፊት በጉዳዩ ላይ አላሰብኩበትም እንጂ አስቀድሜ አስቤበት ቢሆን ኖሮ አልቀበልም ነበር:: ለማንኛውም ለአሁኑ ነገሩን እዚህ ላይ እንቋጨውና ስመለስ የሚሆነው ይሆናል::
- መልካም፣አንተ ገንዘቡን ባታስረክበው ኖሮ ብንያምን የተሰጠኝን ሥራ በአግባቡ እንዳልተወጣሁ አድርጎ ይረዳ ነበር::
- የሰው ልጅ ለገንዘብ፣ለወሲብ ወይም ለሥልጣን ብሎ መርሆዎቹን የሚጥስበት ሕይወት ወራዳ ሕይወት ነው !
- ራሴን በራሴ ተጻርሬ ሊሆን ይችላል፤ይሁንና ሰዎች መርሆዎቻቸውን ለገንዘብ፣ለወሲብና ለሥልጣን ብለው ወደ ጎን ባይሉ ኖሮ እስራኤል ባልተመሰረተችና ሕልውናዋን ጠብቃ መቀጠልም ባልቻለች ነበር::
- ጉቦውን ለመስጠት ወደዚያ ሳመራ የሕይወት ወራዳነትና የራሴ የግሌ ወራዳነት ጠልቆ እየተሰማኝ ነው:: ካኽ ሲነግረኝ በጉዳዩ ላይ እንዴት ሳላስብበት እንደቀረሁ አላውቅም !
- ለማንኛውም ኩባንያው ይኸውና ደርሰናል፣የውል ስምምነቱን ሰነድ ለፊርማ ዝግጁ ሆኖ ብንያምን ዘንድ ታገኘዋለህ::
- በፍጥነት እንድንጨርሰው እፈልጋለሁ፤ካጠናቀኩ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያኖቹ ለጉብኝት የሚወስደኝ ሾፌር ያስፈልገኛል::
- ይቅርታ አድርግልኝ . . እኔ ነገ ወደ ቤተክርስቲያኖቹ ልወስድህ አልችልም፤ሾፌሩ ይጠብቀሃል::

ጆርጅና ሌቪ ወደ ብንያምን ቢሮ ሲገቡ ብንያምን ብድግ ብሎ ሞቅ ያለ

አቀባበል በማድረግ ጆርጅን በፈገግታ ጨበጠው . .

- ትናንት ቀናችሁን እንዴት አሳለፋችሁ? አዳራችሁስ እንዴት ነበር?
- ከሌቪ ጋር ብዙ ሥራዎችን ያጠናቀቅንበት ጥሩ ቀን ነበር::
- አዎ . . ውሉን ለመፈራረም ዝግጁ መሆንህንና ለቴክኒካል ስጋቶቿ ምላሽ የሰጠህ መሆንህን ሌቪ ነግራኛለች:: (ወደ ሌቪ ዞር ብሎ) ፦ ከጆርጅ ጋር ውሉን ተፈራርመን እስክንጨርስ ድረስ አንቺ ወደ ሥራሽ መሄድ ትችያለሽ::
- አንዳንድ ሥራዎች ስላሉኝ እሄዳለሁ . . (ወደ ጆርጅ ዞር ብላ) ፦ እንደ ጨረስክ ሾፌሩን ታገኘዋለህ::
- ለምን ሾፌር ? ሌቪ ራሷ ልትወስድህ ትችላለች ? አልተመቸችህም እንዴ ? አልማረከችህም ?
- አንተ ባቀረብከው ሀሳብ መሰረት ነገ አብረን በቅዱሳን ስፍራዎች ጉብኝት ለማድረግ ተስማምተናል፤ዛሬ ግን ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናትን ነው የምጎበኘው::
- ሌቪ ትናንተ ካንተ ጋር እንዴት ነበረች?
- ግሩም ድንቅ ሰው ናት::
- ማታ ሦስት ሰዓት ተኩል አካባቢ ደውዬላት ወደ ቤቷ ለመድረስ እንደ ተቃረበች ስትነግረኝ በጣም ነው የገረመኝ:: ግሩም ድንቅ ናት ካልክ የበለጠ ጊዜ ወስደህ አብረሃት ማሳለፍ ትችል ነበር::
- ውይይታችንን ማታ ሦስት ሰዓት ላይ ስናበቃ ነው የሄደችው:: ውሉን ለመፈራረም አንተን ለማግኘትና ጉዳዩን ለመጨረስ በስልክ ነግረህ ነበር . . ይህ ከካኽ የተላከልህ ቼክ ነው::
- አንተንም ካኽንም አመሰግናለሁ:: ይኸውና ውሉ ለፊርማ ተዘጋጅቷል::
- ጨረስን ?
- አዎ የውሉን ጉዳይ አጠናቀናል:: ግና ከኛ ጋር ሦስት ቀናት አሉህ፣እኔና ሌቪ ለአገልግሎትህ ዝግጁ ነን::
- ስለ መስተንግዶህ አመሰግናለሁ::
- ነገ ከጉብኝታችሁ በኋላ አብራችሁ ለማምሸት ወደ ሆቴልህ እንድትመጣልህ ከፈለክ እንኳ እርሷ ዝግጁ ነች::
- ከጉብኝቱ በኋላ ይደካክመኛል ብዬ አስባለሁ፣በመሆኑም ለማረፍ በጊዜ መተኛት ስለሚያስፈልገኝ ማምሸት አልችልም !!
- እህህ፣ሌቪ በማዝናናት እንድታሳርፍህ ሞክር . . ካኽ ውል ለመፈረም

www.path-2-happiness.com

ሲመጣ ሌቪ አዝናንታው ካላስደሰተችው በስተቀር ፈጽሞ አይረካም ነበር::

-አሁን ውሉን ተፈራርመን ጨርሰናል:: ከውሉ ጋር ግንኙነት በሌለው ሌላ ጉዳይ ላይ ካንተ ጋር ሀሳብ ብንለዋወጥ ምን ይመስለሃል ?

-ማለት የፈለከው አልገባኝም . . በል ቀጠል . .

-በግልጸኝነት ያለ ማሸማቀቅ ልናገርና ውሉን ለመፈረም ገንዘብ የምትቀበለው ለምንድነው? ይህ ጉቦ አይደለም ወይ ?

-እህህ፣ግልጸኝነትን የምትወድ ከሆነ አንተና ካኽም ውሉን ለመፈረም ለምንድነው በሌቪ የምትደሰቱት? ይሄስ የወሲብ ጉቦ አይደለም?!

-ልክ ነህ ወሲባዊ ጉቦ ነው፣አምቢ እንድል ካደረጉኝ ምክንያቶችም ይህ አንደኛው ነው::

-ካኽ ግን እምቢ ብሎ ራሱን አቅቦ አያውቅም፤እንዲያውም በግልጽና በይፋ ይጠይቅ ነበር:: አንተም ብትሆን ትናንተ በተዘዋዋሪ መንገድ ጠይቀሃል፤እንደምትለው በሌቪ ሳትደሰት ቀርተህ ከሆነ ይህ ያንተ ችግር ነው:: ደሞስ እንደምትለው ጉቦ ከሆነ ለምን ሰጠኸኝ?!

-ጉቦ ከሆነ ለምን ትከፍላለህ የሚለው አነጋገርህ ትክክለኛና ምክንያታዊ ነው . . ለማንኛውም ገንዘብና ወሲብ ደስተኝነትን ያጎናጽፉሃል ?

-ያለ ጥርጥር ዓለማዊ ደስታ የሚገኘው በወሲብ በገንዘብና በሥልጣን ነው . . (ተመቻችቶ በመቀመጥ ቀጠለና) ፦ እነዚህ መደሰቻዎች ራሳቸው እርግማን የሚያመጡብን ቢሆኑም እንኳ . .

-አልገባኝም፣የሕይወት መደሰቻዎች ተመልሰው እንዴት መርገምት ይሆናሉ?!

-ወዳጄ ይህ የሕይወት ተጻራሪ ገጽታ ነው:: ወሲብ ገንዘብና ሥልጣን የቁሳዊ ሕይወት ዋነኛ መደሰቻዎች ሲሆኑ አንዳንዴ ግን መንፈሳዊ ሕይወታችንን በመጉዳት መርገምት ይሆናሉ:: ልክ ከደስታ ስሜት እንደራቁትና ሁሌም በሀዘን ድባብ ውስጥ ብቻ እንደሚከበሩት የኛ የአይሁዶች በዓላት ማለት ነው:: በዓላት በሕይወታችን ውስጥ በጣም አስደሳች ጊዜያት መሆን አለባቸው ተብሎ አይደለም የሚጠበቀው? አዎ ብየ ነው የምመልስልህ፤ግና እኛ ዘንድ በዓላት የሀዘን ቀናት ናቸው::

-እንዴት ?

-ሌቪ ከኔ በተሻለ ልታብራራልህ ትችላለች . . እህህ፣ ከሁሉም በላይ ቆንጆም ናት፣ውይይቱን ከርሷ ጋር በሚመችህ ቦታና አኳኋን መቀጠል ትችላለህ::

-እንግዲያውስ አመሰግነሃለሁ::

ጆርጅ ብንያምንን ተሰናብቶ ሲወጣ ጸሐፊውን የሌቪን ቢሮ እንዲያሳየው ጠየቀና ወደዚያ አመራ . . ሲገባ በመጓጓት ስሜት ጠየቀችው ፦

-ምን ተባባላችሁ?

-ውርደት ነው የምሰማኝ፣ጉቦውን ሰጥቼው ውሉን ተፈራርመናል::

-ስለ ጉቦው ወይም ስለኔ ከርሱ ጋር ተነጋግረሃል?

-አዎ፣ስላንቺ ብዙ ነው የተነጋገርነው፤አዝናለሁ እንድዝናናበት አሁንም ገላሽን ለግብዣ እያቀረበልኝ ነው . . (ፈገግ አለና) ፦ አዲስ ነገር ቢኖር፣ለአንዳንድ ጉዳዮች ካንቺ ማብራሪያ እንድጠይቅ ሀሳብ ያቀረበልኝ መሆኑ ብቻ ነው::

-ከኔ ነው ማብራሪያ የምትጠይቀው?!

-ስለ ጉቦው ባነሳሁለት ጊዜ አንተና ካኽም ጉቦ ትቀበላላችሁ፣ የናንተ ጉቦ ግን ገንዘብ ሳይሆን የወሲብ አገልግሎት ነው ብሎ አፋጠጠኝ:: እኔ ያመጣሁለትን ጉቦ እርሱ የተቀበለው በመሆኑም ሁለታችንም እኩል ነን በማለት ምላሽ አሳጣኝ::

-መቼም ያሳዝናል፣የሰው ልጅ አንዳንዴ በክርክርና ለጥፋቶቹ ፍልስፍናዊ ማመካኛ በማቅረብ የተካነ ነው::

-ማንን ማለትሽ ነው ?!

-ብንያምንን ማለቴ ነው፤አቀርቅራ ላፍታ ዝም ካለ በኋላ ፦ ራሴንም ማለቴ ነው፣ይቅርታ አድርግልኝና አንቴንም ማለቴ ነው::

ጆርጅ በሀዘን ስሜት ጣሪያውን እየተመለከተ ፦

-እውነትሽን ነው . . መቼ ይሆን ፍልስፍናችን የጥፋትና የጉቦ ማመካኛ ፍልስፍና ከመሆን ወጥቶ የደስተኝነታችንና የዕድገታችን ፍልስፍና የሚሆነው ?

-ከኔ ማብራሪያ ስለምትጠይቅበት ጉዳይ ግን አልነገርከኝም::

-ብንያምን የሚለው ይህ የሕይወት ባህሪ ነው፣ውስብስብ ሕይወት ነች፤ደስታና ተድላዋ ለመንፈሳችን መርገምት ነው፤ምሳሌዋ የደስታ ቀናት ይሆናሉ ተብለው እንደሚጠበቁትና ግና የሀዘን ቀናት እንደሆኑት አይሁዳዊ በዓሎቻችን ምሳሌ ነው::

-ምናልባት ይህ ቀደም ሲል ከተነጋገርንባቸው የማዛባት መገለጫዎች አንዱ ሊሆን ይችላል:: አይሁዳዊነት ውስብስብ ሃይማኖት ነው:: ችግሩ ያንተ የግንዛቤ ችግር ሳይሆን የአይሁዳዊነት እውነታ ውስብስብነት ነው::

ዋናው ነገር የአይሁዶች በዓላት በአብዛኛው የደስታና የፈንጠዚያ ሳይሆኑ የሀዘንና የለቅሶ በዓላት ናቸው::

-እንዴት ማለት ?

-በዓላት ከአምልኮ ጋር የተያያዙ ሲሆን የአይሁዶች አምልኮ ለቅሶና ሀዘን ነው:: የማልቀሻ ግንብ ስለሚባለውን የአይሁድ አምልኮ ስፍራ ሰምተህ የለ?! የሰንበቶች ሰንበት ብለን በምንጠራውና ከፍ በዓላት ሁሉ ዋነኛው በሆነው የምሕረት ቀን በዓል ጊዜ፣ቀንና ሌሊት በተከታታይ ለሃያ አራት ሰዓት እንጾማለን:: ከአምልኮ ውጭ ምንም ነገር አንሰራም:: በአጠቃላይ ብዙ በዓላት ያሉን ሲሆን አብዛኞቹ አይሁዶች በተለይም ሴኩላሪስቶቹ ከቅርጽ ያለፈ ይዘት የሌላቸው አምልኮ አልባ በዓላት አድርገው ያከብራሉ::

-ይኽ ብዙም አስፈላጊ ነጥብ አይደለም፤ግና ሕይወት ደስተኝነትን ለእርግማን በሚዳርገን ነገር ውስጥ ብቻ እንጂ ማግኘት እስከማንችልበት ደረጃ ድረስ ውስብስብ መሆን ትችላለች ማለት ነው? !

-ይህ ጥያቄ ሁሌ አእምሮዬ ውስጥ ይመላለሳል:: ኦሪትና ተልሙድንም በጥልቀት ያጠናሁና የመረመርኩ ቢሆንም ምላሽ ማግኘት አልቻልኩም:: ምናልባት ይህ የሆነው በአይሁዳዊነት ወይም በአይሁድ ሃይማኖት የአስተሳሰብ ውስብስብነት ባህሪ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: አሊያም ወደ መልሱ ለመድረስ የበለጠ ዕውቀት ስለሚያስፈልገኝ ሊሆን ይችላል::

-እኔ እንጃ . . እኔ ግን ውስብስብነትንና ማወሳሰብን እጠላለሁ:: ማወሳሰብ ወደ እርግማን እንጂ ወዴትም ማድረስ አይችልም የሚል እምነት አለኝ::

-እኔም ማወሳሰብን እጠላለሁ፣ዳሩ ግን ተነክሬበታለሁ:: ለማንኛውም አራት ሰዓት ነው፣ጊዜ እንዳያጥርህ፣ከዶክተር ሐበቢብ ዘግይተህበታል፣ውጭ እየጠበቀህ ነው::

-ዶክተር ሐቢብ ማነው?

-የሃይማኖቶች ተመራማሪ የሆነ ካቶሊክ ክርስቲያን ነው . . ካንተ ጋር መሆን የሚገባውንና የሚመችህን ሰው ስለማውቅ እኔ ራሴ ነኝ በጉብኝቱ ላይ ባልደረባህ እንዲሆን የመረተጥኩልህ::

ጆርጅ ለአፍታ በዝምታ ቆየ:: ከርሷ መለየት አልፈለገም ነበርና በውበቷ ዓይኖቹን ለመሙላት ሞከረ . . በትከሻዋ ላይ በተዘናፈለው ጸጉሯ፣በሚንቦገቦጉ ዓይኖቿ፣በተሰረጎዱ ጉንጮቿ፣ በማራኪ ተክለሰውነቷና በእንቅስቃዋ፣በሁለመናዋ . . የሥጋዊ ፍላጎቴን ጥማት የሚያረካ ሌሊት አብሬያት ባለማሳለፌ ተሳስቼ ይሆን? ብንያምን ‹‹የገላ እርካታ የመንፈስ

መርገምት ነው›› ያለው እውነት ይሆን? ወይኔ በዚህ ነጥብ ላይ ረስቼ ሳልከራከረው ቀረሁ!

ጆርጅ የተከለባት የእይታ ጨረራ በያንዳንዱ የገላዋ ክፍል ላይ እያረፈ መሆኑ ሌቪ ተሰምቷታል:: በዚህ እይታ የመነሳሳትና የትኩሳት ስሜት ለምን እንዳደረባት አታውቅም:: ከርሱ ጋር ለመደሰት ፈልጋ ከሆነ ለምን ተወች? የተወችው ራሷን ለማስወደድና እንዲከተላት ፈልጋ እርሱ ስላላደረገ ይሆን? እሱስ ቢሆን እንዲህ በዓይን እይታ እየበላት ለምን ተዋት? ሀሳቡን ቀይሮ ይሆን? ማን ያውቃል፣የልቧን አውጥታ ነግራው ዛሬ አብራው ትደር ወይስ ምንታደርግ ?!

-በጣም ነው የማመሰግነው፣ነገ ጧት ሁለት ሰዓት ላይ እጠብቅሻለሁ::

-ጆርጅ እኔም አመሰግናለሁ::

ጆርጅ ወጥቶ ለዶክተር ሐቢብ ሰላምታ አቀረበ፣ተያይዘው ወደ መኪናው ሄዱ . .

-መጀመሪያ የምናመራው ወደ ትንሣኤ ቤተክርስቲያን ነው:: ዛሬ ዓርብ ስለሆነ መንገዶች ሁሉ በፍተሻ የተጨናነቁ ናቸው፣ሁለት ሰዓት ሊወስድብን ይችላል::

-ሁለት ሰዓት?!

-አዝናለሁ፣አዎ ሁለት ሰዓት:: በሌላው ጊዚ የአርባ አምስት ደቂቃ መንገድ ነበር፤ዛሬ ዓርብ ስለሆነ በፍተሻ ኬላዎች ብዛት መንገዶች ሁሉ የተዘጋጉ ናቸው::

-የጊዜ ብክነትና አስቸጋሪነቱ ከፍተኛ ቢሆንም ሽብርተኝነት በሰው ዘር ላይ ያንዣበበ አደጋ በመሆኑ ነገሩ ተገቢ ነው::

-ስለ የትኛው ሽብር ነው ምታወራው?

-ስለ ዐረብ ሙስሊሞች ሽብር ነዋ !

-ይቅርታ፣እኔ ዐረብ ካቶሊካዊ ክርስቲያን ነኝ፣ሙስሊም አይደለሁም:: እውነተኛው ሽብር ግን የአይሁዶቹ መንግስታዊ ሽብርተኝነት ነው:: ሰዎች በመስጊዶቻቸው ተገኝተው እንዳይሰግዱ ለምንድነው የሚከለከሉት? በመስጊዳቸው መስገድ ምኑ ላይ ነው ሽብር የሚሆነው?!

-ይቅርታ፣እኔ የታሪክ፣የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖቶች ኤክስፐርት አይደሰለሁም:: ያገጠመኝ ሰው ባለሞያ መሰለኝ፣ለመሆኑ አይሁዶችን ለመግደል ራሳቸውን በማፈንዳት ባቡሮችንና አውቶቢሶችን የሚያፈነዱት ሙስሊሞች አይደሉም? !

www.path-2-happiness.com

- ልክ ነህ ያደርጋሉ፣አንድን ሰው ራሱን ወደ መግደል የሚያደርሰው ምንድነው ብዬ ብጠይቅህ ምን ትላለህ?
- በተለምዶው አንድ ሰው መሞትን ከመኖር ከሚመርጥበት ሁኔታ ላይ ካልደረሰ በስተቀር ራሱን አይገድልም ብዬ አስባለሁ፡፡
- እዚህ አገር ሙስሊሞችን ከዚህ ሁኔታ ላይ ምን አደረሳቸው?
- እኔ እንጃ፣ምንድነው ያደረሳቸው?
- ግፍ፣ጭቆና፣ወረራና የተዋራጅነት ስሜት ነው፡፡
- ለሙስሊሞች በጣም የወገንክ ትመስላለህ፡፡
- በፍጹም፣እኔ ሙስሊም አይደለሁም፡፡ ግና ያገሩ ባለቤት ለሆኑት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መብት እወግናለሁ፡፡ ክብራቸው ተዋርዷል፣መሬታቸውን እና መብታቸውን ተነጥቀዋል፡፡ ታውቃለህ እኛ የፍልስጥኤም ክርስቲያኖችም ከመሬታችን እንባረራለን፣እንሰደዳለን፣ቅዱሳን ስፍራዎቻችን ይዋረዳሉ፡፡
- ግን እንደ ሙስሊሞቹ ራሳችሁን አላፈነዳችሁም?
- እኛ በቁጥር አናሳ ነን፡፡ ይሁን እንጂ እያዋረዱንና እየጨቆኑንም ከሙስሊሞቹ የተሻለ አያያዘ ያደርጉልናል፡፡ ይህም ለኛ ተብሎ ሳይሆን የዓለም ክርስቲያኖችን ስሜት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡
- የዓለም ሙስሊሞችን ስሜት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለሙስሊሞች የተሻለ አያያዝ ለምን አይደረግላቸውም?
- በግልጽና በአጭሩ ለማስቀመጥ ለኃይልና ለኃይል ብቻ አክብሮት በሚሰጥ ዓለም ላይ ነው የምንኖረው . . ይህን ተወኝና የትንሣኤን ቤተክርስቲያን ታውቃለህ?
- በተወሰነ ደረጃ አውቃለሁ፣በርሱ ላይ ብዙ አንብቤያለሁ፡፡
- መልካም ነው፣ሌቪ እንደነገረችኝ ፕሮቴስታንት ነህ፡፡
- ልክ ነህ፣ ሌቪ ስለሁሉም ነገር የነገረችህ ይመስለኛል፡፡
- ሌቪን ለአምስት ዓመታት ያህል አውቃታለሁ፤ላንተና ለምቾትህ ትኩረት የሰጠችውን ያህል ለሌላ ሰው ስትሰጥ አይቼ አላውቅም፡፡
- ሌቪን ያወቅኋት በዚህ ሰሞን ነው፣ይህን ያደረገችው በተገራ ጠባይዋና በመልካም ስነ ምግባሯ ነው . . አንተ ከሌቪ ጋር የተዋወከው እንዴት ነበር?
- አይሁዳዊነት ሰልችቷት ነበር ወደ እኔ የመጣችው፡፡ ክርስትናን ለመቀበል ታስብ ስለነበረ በካቶሊካዊነት ዙሪያ ከኔ ጋር ለመከራከር ነበር አመጣጧ፡፡ ክርክርና ውይይት በጣም ትወዳለች፡፡

www.path-2-happiness.com

- ክርስትናን ተቀበለች?!
- በእርግጥ አልተቀበለችም፣በጣም ሃይማኖተኛ ከመሆኗም ጋር ካቶሊካዊነትንም ሆነ አይሁዳዊነትን አሳማኝ ሆኖ አላገኘችም፡፡ ከአክራሪ አይሁዶች ቤተሰብ የተወለደች በመሆኗ ክርስትናን ብትቀበል ሊትገደል፣ልትታሰር ወይም የሆነ ዓይነት ጥቃት ሊፈጸምባት ይችላል፡፡
- ካቶሊካዊነትን እንድትቀበል እንዴት ልታሳምናት አልቻልክም?
- ምናልባት በውስጡ ባሉት ግጭቶች ምክንያት፣አሊያም በአይሁዳዊነት ውስብስብ ባህሪ ምክንያት ሊሆን ይችላል !
- ምናልባትም በራሱ በካቶሊካዊነት ውስብስብ ባህሪ ምክንያትም ሊሆን ይችላል፡፡
- እህህ፣ሊሆን ይችላል፡፡
- የሃይማኖቶች ጉዳይ ተመራማሪ መሆንህን ሌቪ ነግራኛለች፡፡
- አዎ . . በዩኒቨርሲቲ የሃይማኖቶች ታሪክ ኮርስ የማስተምር ዶክተር ነኝ፡፡
- የሃይማኖቶች ታሪክ በፍልስጥኤም ምን እንደሚመስል ልትነግረኝ ትችላለህ?
- በፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ውስብስቦች የታጠረ ቢሆንም ነገሩ በጣም ቀላል ነው፡፡
- ማቅለልንና አለማካበድን አፈቅራለሁ . . እባክህን ቀለል ባለ መልኩ ንገረኝ፡፡
- ቀለል ባለ መልኩ . . ያለ ጥርጥር ከሃይማኖቶች በፊት በዚህ መሬት ላይ ሰዎች ይኖሩ ነበር፡፡ ሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች በዚች ቅድስት አገር ውስጥ አልፈዋል፡፡ አይሁዳዊነት ከክርስትና እና ከእስላም ይቀድማል፡፡ ከሁሉም ሃይማኖቶች በፊት ግን ነዋሪዎች ነበሩ፡፡ ወደዚህ አገር የደረሱ ሃይማኖቶች ሁሉ ከመሬቱና ከአገሩ ጋር እየተቀላቀሉ ይሰባጠሩና ተቻችለው ይኖሩ ነበር፡፡ ከቅርብ ዘመን ወዲህ አይሁዶች ከየአገሩ እየመጡ ነባሮቹን ቀደምት ነዋሪዎች እየገደሉ እያባረሩና እያፈናቀሉ በመስፈር መሬቱን በወረራ መያዝ እስከጀመሩበት ጊዜ ድረስ ሁሉም እምነቶች በአብሮነት በሰላም የኖሩባት አገር ነበረች፡፡
- ቀደም ሲል ሙስሊሞች ሌሎቹን አላባረሩም ነበር?
- ፈጽሞ፣እውነቱን ለመናገር ዑመር ብን አልኸጧብ ወደዚህ ሲገቡም ቤተክርስቲያኖቻችን እንደነበሩ ነው የቀጠሉት፣ ምንም ዓይነት ጉዳት ደርሶባቸው አያውቅም፡፡

-የመስቀል ጦርነቶችስ?

-የመስቀል ጦርነቶች በሁለት ሃይማኖቶች መካከል፣በነባሮቹ ሙስሊም ነዋሪዎችና ከነሱ ጋር ነባሮቹ የአገሩ የተወሰኑ ክርስቲያኖች በአንድ በኩል ሆነው ከአውሮፓ የመጡ መስቀላውያንን ወረራ ለመመከት የተደረጉ ጦርነቶች ናቸው:: ከአውሮፓ መስቀላውያን መምጣት በፊት ሕዝቡ በፍቅርና በመቻቻል ይኖር ነበር::

-ክርስቲያኖችስ አይሁዶችን አልጨቆኑም?

-እኔ ክርስቲያን ነኝ፣አይሁዶች በቅርቡ ዘመን የተጨቆኑት አውሮፓ ውስጥ እንጂ ፍልስጥኤም ውስጥ አይደለም:: ይህች ምድር ግን የመቻቻል ምድር ነች . . የጥንቱን ዘመን በተመለከተ የሮማውያን መንግስት ከኢየሱስ መምጣትና አይሁዶች ካስተባበሉት በኋላ እልቂት አድርሶባቸዋል፣ደማቸውን አፍስሷል::

-እስላም የዐረቦች ሃይማኖት በመሆኑ፣ከክርስትናህ ይልቅ ዐረባዊነትህ ለሙስሊሞች ተቆርቋሪ እንድትሆን ያደረገህ ትመስላለህ !

-ሊሆን ይችላል፣ግና እስላም የዐረቦች ሃይማኖት አይደለም::አብዛኞቹ ሙስሊሞች ዐረብ አይደሉም:: እኔ ዐረባዊ እንጂ ሙስሊም አይደለሁም፤የአካዳሚክስ ሰው በመሆኔ ግን በተቻለ መጠን መልሴ ሳይንሳዊ እንዲሆን ጥረት አደርጋለሁ:: ዐረቦች ወደ ቅድስት አገር የደረሱት ከእስላም መምጣት በፊት ነበር፤አብርሃም የያዕቆብና የእስማዒል አባት አይደለም?! አብርሃም ደግሞ ከአይሁዳዊነትም ሆነ ከእስላም በፊት ነው የኖረው::

-በማቋረጤ ይቅርታ፣አሁን የደረስንበት አካባቢ ሰፈሩ በጣም ጥንታዊ ይመስላል::

-አዎ፣የትንሣኤ ቤተክርስቲያን ወደሚገኝበት ወደ ጥንታዊው የከተማው ክፍል ተቃርበናል:: እስካሁን ከአስራ አምስት የበለጡ የፍተሻ ኬላዎችን እንዳለፍን አስተውለህ የለም?!

-በፍተሻ ኬላዎቹ ላይ የተኮለኮሉ በእድሜ የገፉ ሰዎችን ሳይ ውስጤ በጣም ነው የተረበሸው፤በጣም አሳዛኝ ነው !

-በፈታሽ መኮንኖች ዘንድ የምታወቅ ክርስቲያን መሆኔ ኬላዎቹን በፍጥነት እንድናልፍ ረድቶናል:: በዕድሜ የገፉ ሰዎች በብዛት ተሰልፈው የሚታዩት እድሜያቸው ከሃምሳ ዓመት በታች የሆኑት ከእለተ ዓርብ ሶላት የተከለከሉ በመሆናቸው ምክንያት ነው . . ይህም ማለት ሕጉ በኛም ላይ ተፈጻሚ

ቢሆን ኖሮ እኔና አንተም ወደ ትንሣኤ ቤተክርስቲያን መድረስ እንከለከል ነበር ማለት ነው::

-አሮጌው ከተማ የክርስትና ታሪካዊ ቅርሶች ማእከል ሳይሆን አይቀርም !

-ልክ ነህ ለሙስሊሞችም እንደዚሁ::

-ለአይሁዶችም ጭምር::

-እነሱ ይላሉ፣ታሪክና ተጨባጩ ሁኔታ ግን አይደግፋቸውም . . (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፥ የጫካ ሕግ በሰፈነባት ዓለማችን ላይ ዋነኛ የሆነው ኃይልና ጡንቻ ግን ይደግፋቸዋል::

-በአይሁዶች ላይ በጣም የምትጫን ትመስላለህ!

-ይህን ያረጋገጠው ሳይንሱ ነው፤መሬቴን ስለ ነጠቁ፣መብቴን ስለጣሱ፣ነጻነቴን ቀምተው ከአምልኮቴ ስለ ከለከሉኝ አምርሬባቸው ሊሆን ይችላል::

-ሁሉም ሃይማኖት እንደዚህ ስለሚናገር ይህን እንተውና ወደ ቤተክርስቲያኑ የደረስን መሰለኝ?

-ልክ ነህ፣ጉልላቶቹንና መስቀሎቹን ማየት ትችላለህ፤የተቀረውን መንገድ በእግር እንጓዛለን::

-ሙስሊሞችን አትፈራቸውም?

-ከአይሁዶች ጥቃት ከተረፍክ ከዚያ በኋላ ያለው ነገር ሁሉ ቀላል ነው:: ሙስሊሞች ቁድስ ወይም ኢየሩሳሌም ውስጥ አንድም ክርስቲያን መግደላቸውን ሰምተህ ታውቃለህ?

አብረው ጥቂት በእግር ተጓዙ . . ጥንታዊው የቤተክርስቲያን ሕንጻ ከፊትለፊታቸው ቆሞ አዩት:: የኪነ ሕንጻው ጥበብና ውበት ያስደመመው ጆርጅ በአድናቆት ተውጦ እየዞረ ያስተውለው ጀመር . .

-ወደ ውስጥ ስትገባ ደግሞ ከዚህ በበለጠ በአድናቆት ትዋልላለህ::

-እንግዲያውስ እንግባ . .

ሲገቡ ጆርጅ የኢየሱስን የስቅለት ሥዕል በትልቁ ግድግዳው ላይ ተስሎ ተመለከተ:: ከግርጌው የድንግል ማርያም ትልቅ ሥዕል፣ቀጥሎም የዮሴፍ . .

-ሥዕሎች ይበልጥ ተገቢ የሚሆኑት ለሙዝየሞች ነው የሚል እምነት አለኝ ! እንዲህ ያሉ ሥዕሎች ለአምልኮተ እግዚአብሔር በተዘጋጁ ቤተክርስቲያኖች ውስጥ መደረጋቸው ተገቢ ነው?

-እናንተ ፕሮቴስታንቶች መቼም ይህ የተለመደ ዐመላችሁ ነው:: በአብያተ

www.path-2-happiness.com

ክርስቲያናት ውስጥ ሥዕላ ሥዕሎችን ማየት አትወዱም . . (በምጸት ፈገግ አለና) ፦ በዚህ ረገድ ከሙስሊሞቹ ጋር ትመሳሰላችሁ!

-ለመጀመሪያ ጊዜ ሙስሊሞችን ትመስላላችሁ ስንባል መስማቴ ነው፣የተለመደው አይሁዶችን ትመስላላችሁ የሚል ነበር::

ጆርጅ ከጉልላቱ የሚወጣውንና ወደ አስራ ሁለት ጮራዎች የሚከፋፈለውን የብርሃን ፍንጣቂ በከፍተኛ አድናቆት ትኩር ብሎ ሲመለከት ቆየ . .

-ይህ ከዓለም ድንቃድንቅ ነገሮች አንዱ ነው:: ከጉልላቱ ወደታች የሚወርደው ከአናት ባለው የጉልላቱ ክፍተት መሀል ላይ ብርሃን ያፈነጠቀችውን ጸሐይ የሚወክል ሲሆን፣ከዚህ ብርሃን አስራ ሁለት ጨረሮች ይወጣሉ:: ተምሣሌቱ ግልጽ ነው:: የብርሃን ምንጩ ኢየሱስን ሲያመለክት ጨረሮቹ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት ይወክላሉ:: ብርሃኑ እምነት በምድር ላይ መሰራጨቱን ያሳያል:: ይህ ጉልላት ተሰርቶ የተመረቀው ጃንዋሪ 1997 ነበር::

-በእውነት ግሩም ድንቅ ትእይንት ነው:: እንዲህ ባለ ቦታ ላይ ስትሆን በእምነት የተሞላ መንፈሳዊነት ይሰመሃል::

-እናንተ ፕሮቴስታንቶች ግን ይህን ቦታ ብዙም አትወዱም!

-እህህ፣ኢየሱስ የተሰቀለበት መስቀል አለበት የሚባለውን ቦታ ማን የማይወድ ይኖራል!

-ለዚህ ቤተክርስቲያን የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ካቶሊኮችና ኦርቶዶክሶች ናቸው::

-ቀደም ሲል ሙስሊሞች አፍርሰውት ነበር! አንተ ግን ሙስሊሞች አንድም የአምልኮ ቦታ አላፈረሱም ነው የምትለው!

-ልክ ነህ . . አልሓክም ብአምርልላ የሚባለው የሺዓው ፋጥማዊ ገዥ አፍርሶት ነበር:: በታሪክ እንደምናውቀው ክርስትናን እንዳፈረሰ ሁሉ እስላምንም አፍርሷል . . ሆኖም ግን ካፈረሰ ከአርባ ዓመት በኋላ እንደገና እንዲገነባ ተደረገ . . እኔ ሙስሊም አይደለሁም፣ሙስሊሞች ስለ ፈጸሙት ግፍ መናገር ፈጽሞ አያስጨንቀኝም:: አልፎ አልፎ ተከስቷል፣ይሁን እንጂ ከአይሁዶች ግፍና ጭቆና ጋር የሚነጻጸር በፖሊሲ የተደገፈ አይደለም፤ክርስቲያኖች በአይሁዶች ላይ ከፈጸሙት ግፍ ጋርም አይነጻጸርም:: በነገራችን ላይ ቤተክርስቲያኑን በ336 ለመጀመሪያ ጊዜ የሰራው አውሮፓዊ ሳይሆን ዚኖቢዮስ የተባለ ሶርያዊ መሀንዲስ ነው::

-የሚገርም ነው፣በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ብዙ ሰዎች የሉም::

-እንደሚታውቀው የቅዳሴ ቀን እሁድ ነው:: ዛሬ ዓርብ ሲሆን መንገዱም የተዘጋጋ ነው:: ባይሆን ኖሮ ግን ይህ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተቀደሰና ቦታውም ከሁሉም በላይ የተከበረ ቦታ ነው::

ጆርጅ ለካትሪና የገባውን ቃል ለመፈጸም ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ጸሎት አደረሰ:: ለጥያቄዎቹ መልስ እየሰጠ ከሚያስጎበኘው ሐቢብ ጋር የቤተክርስቲያኑን የተለያዩ ክፍሎች እየተዘዋወሩ አዩ . . ወደ ማርያም ቤተክርስቲያን ለመሄድ ወጡ . . ሐቢብ ሰዓቱን ሲመለከት ለስምንት ሩብ ጉዳይ ሆኗል . .

-ብዙ እንዳልዘገየን ተስፋ አደርጋለሁ፤ወደ ማርያም ቤተክርስቲያን ለመድረስ ከአንድ ሰዓት እስከ አንድ ሰዓት ተኩል ያስፈልገናል:: ለመመለስም የዚያኑ ያህል ስለሚወስድብን ከጸሐይ መጥለቅ በፊት እንመለሳለን በዬ አስባለሁ::

-መልካም፣እንግዲያውስ ትንሽ ስለ ደካከመኝ መኪና ውስጥ ለግማሽ ሰዓት ያህል እረፍት እንዳደርግ ፍቀድልኝ::

-ጥሩ አረፍ በል::

ጆርጅ መቀመጫውን ወደ ኋላ ለቀቅ አድርጎ ተኛና ዓይኖቹን ጨፈነ:: በዚህ ጉዞው የሁነቶች ክስተትና ክትትል በጣም ፈጣን መሆኑ እየታወሰው ነው:: የጉዞውን የመጀመሪያ ዓላማ ቶሎ ማሳካቱ ትዝ አለው:: ሁለተኛ ዓላማው የሆነውን የደስተኝነት መንገድ ፍለጋ ጉዳይን አሰበ:: ከሌቪ፣ከብንያምንና ከሐቢብም ጋር ያደረጋቸውን ውይይቶች አስታወሳቸው:: ይህ ሁሉ የተፈጸመው በአንድ ቀን ተኩል ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው:: በቀሪው የሁለት ቀን ተኩል ጊዜ ውስጥ ምን ሊፈጸም ይችላል? . . ካትሪና፣ቶምና ኣደም ትዝ አሉት:: ሁሉም አብረውት ሆነው ውይይቶቹን ቢሰሙ ምኞቱ ነበር:: በተመለከታቸውና በሰማቸው መረጃዎች ላይ የራሱን ግላዊ አቋም ለመውሰድ እስከ አለመቻል ደረጃ ድረስ የመረጃው መጠን ጭንቅላቱን ያጨናነቀ ሆኖ ተሰማው:: ጥያቄዎቹን አስታውሶ ቀደም ሲል ያስጨንቁት እንደ ነበረው ባለመሆናቸው ፈጣሪውን አመሰገነ . . ይህ የሆነው ወደ ደስተኝነት መንገድ ለመድረስ እየታገለ በመሆኑ ምክንያት ይሆን? ይሁን እንጂ የደስተኝነት መንገድ ፍለጋ ጥያቄዎችና የሰበሰባቸው አያሌ መረጃዎችም አድክመውታል:: በነዚህ የሀሳብና የትግል ማዕበል ውስጥ ሲላጋ ቆይቶ ወደ ሕልም ዓለም ተሸጋገረና አንቀላፋ::

www.path-2-happiness.com

(5)

ጆርጅ ከእንቅልፉ ሲነቃ መቀመጫውን አስተካከለና ወደ ሐቢብ ተመለከተ ፦

- ይቅርታ በጣም ደከመኝ መሰለኝ !
- ሳይሆን አልቀረም።
- ኦህ፣አንድ ሰዓት ሙሉ ነው የተኛሁት ! ወደ ቤተክርስቲያኑ ለመድረስ ምን ያህል ይቀረናል?
- ሩብ ሰዓት ያህል ይቀረናል . . (ፈገግ እያለ ቀጠለና) ፦ ይቅርታ አድርግልኝና ብርቱ ውስጣዊ ግጭቶች ያሉብህ ትመስላለህ። ካትሪና፣ብንያምን፣ቶም፣ሽማግሌው፣ማይክል፣ጆስቲና፣ካኽ፣ሌቪ . .
- እነዚህን ስሞች ከየት አገኘሃቸው?!
- ተኝተህ በእንቅልፍ ልብ ትደጋግማቸው ነበር።
- በእርግጥ ከባድ ድካም አለብኝ ማለት ነው። መረጃዎችና ክስተቶች ጭንቅላቴ ውስጥ ዝብርቅርቅ ብለውብኛል። አካሌንም ጫን ብሎኛል።
- አንድ ሰው ለጉዳዮቹ እልባት ካልሰጠ ነገሮች አእምሮው ውስጥ ተጠላልፈው ስለሚዘበራረቁበት መንፈሱ ሊታወክና አካሉም ሊዳክም ይችላል።
- የኔ ችግር በትክክል ይህ ሳይሆን አይቀርም።
- በነገራችን ላይ ብዙ ጊዜ ስትደጋግመው የነበርከው አንድ አባባል በጣም ማርኮኛል።
- የቱ ይሆን ?
- ‹‹የደስተኝነት መንገድ›› የሚለው ነው፤ደጋግመህ ‹‹የደስተኝነትን መንገድ እፈልጋለሁ›› ስትል ነበር፣ድንቅ አባባል ነው።
- ታድያ በደስተኝነት መንገድ ርእስ ላይ ሀሳብ ብንለዋወጥ ምን ይመስለሃል ? አንድ ጥያቄ ላቀርብልህ እፈልጋለሁ።
- ጥሩ፣ አቅርብ።
- አንተ ደስተኛ ነህ ?
- በጣም ትልቅ ጥያቄ ነው፤መልስ ሊኖረው የሚችል ነው ብለህ ታምናለህ ? !

- አዎ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።
- ሁሉም ሃይማኖቶች፣ርእዮቶችና ቡድኖች ይህን ይፈልጋሉ።
- አንተ የሃይማኖቶች ታሪክ መምህር ነህና ከሃይማኖቶች መካከል ለደስተኝነትና ለተድላ የቀረበው ሃይማኖት የትኛው ነው?
- እንዲህ ያለው ትልቅ ጥያቄ ሲቀርብልኝ ይህ የመጀመሪያው ነው . . መልሱን ለማግኘት የቻልኩትን ያህል ጥረት አድርጌያለሁ፣አሁንም በፍለጋና በምርምር ላይ ነኝ።
- በአንተ አመለካከት መንገዱ ከሃይማኖት ውጭ ሊሆን ይችላል ?
- ያ የማይታሰብ ነው። አብዛኞቹ ኢአማኒያን ኤቲስቶች የስነ ልቦና ወይም የአእምሮ ሕሙማን መሆናቸውንና የውሸት ኤቲስቶች መሆናቸውን ሳይንስ ያረጋግጣል።
- አልገባኝም . . የውሸት ኤቲስቶች?!
- ማለትም ኤቲስቶች መስለው ለመታየት ቢሞክሩም ፈጣሪ አምላክ መኖሩን በውስጣቸው ያምናሉ። እውነቱን ለመናገር ኤቲዝም ከሃይማኖትና ከግዴታዎች ለመገላገል የሚደረግ ሽሽት ነው።
- ሃይማኖት የደስተኝነትና የተድላ ጎዳና ከሆነ የሃይማኖቶች ተመራማሪ የሆነ ምሁር ለምን መልስ ሊሰጥኝ አልቻለም ?
- ይህን ማለት መብትህ ነው። እኔ አሁንም በምርምርና በፍለጋ ላይ ነኝ፤በቅርቡም ወደ መልሱ እደርሳለሁ።
- ይህን መልስ ስታገኝ እንደምትነግረኝ ቃል ግባልኝ።
- ቃል ገብቻለሁ፣ቃሌ ነው። ሌቪ እንዳለችው ሁሉ ለሃይማኖቶች ከፍተኛ ትኩረት ትሰጣለህ።
- እርስበርስ የሚጋጩ ነገሮችን አልወድም፤ውስብስብ ነገሮችንም አልወድም። በአእምሮ፣በመንፈስና በሥጋ መካከል፣በመርሆዎችና በዓለማዊ ደስታ መካከል ሚዛናዊነትና መጣጣም እንዲኖር እፈልጋለሁ። ማካበድን አልወድም፣ጥልቀት ያለው ቅለትን እወዳለሁ።
- ግሩም፣እኔም በትክክል አንተ የወደድከውን እወዳለሁ። ፈላስፋ መሰልከኝ፣በውይይቱ ልንቀጥል ይገባል፣ግና ወደ መግደላዊት ማርያም ቤተክርስቲያን የደረስን መሰለኝ፣ይኸው ከፊትለፊትህ።

www.path-2-happiness.com

- አስደማሚ የሕንጻ ጥበብ!
- ይህ ሩሲያዊ የሕንጻ ጥበብ ነው:: ሩሲያዊው እስክድር ነበር በዚህ ውብ ወርቃማ ጉልላቶች አስውቦ የገነባው::
- የቅርብ ጊዜ ቤተክርስቲያን ነው ማለት ነው?
- ከትንሣኤ ቤተክርስቲያን ጋር ሲነጻጸር ያለ ጥርጥር አዲስ ነው:: ትንሣኤ ቤተክርስቲያን የተገነባው በ335 ሲሆን፣የማርያም ቤተክርስቲያን የተገነባው በ1886 ነው:: በመካከላቸው ያለው ልዩነት የ1500 ዓመት ነው::
- የሚገርመኝ አብዛኞቹ የክርስትና ቅርሶቻችንና ታሪካዊ ቦታዎቻችን ከባለ ታሪኮቹ ሕይወት በኋላ ብዙ ዘመናት ዘግይተው የተመሰረቱ መሆናቸው ነው:: ይህ ደግሞ እውን ቅዱሳን ስለ መሆናቸው ጥርጣሬ የሚያሳድር ነው::
- አዎ ያሳዝናል፣ያልከው ነገር መቶ በመቶ እውነት ነው:: ይህ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተም እንኳ እውነታው ይኸው ነው . . አሁን ደርሰናል በል ውረድ፣የቀረውን ስንመለስ እንጫወታለን:: ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት መመለስ እንድንችል ጉብኝቱን ቶሎ መጨረስ ይኖርብናል::
- ጥሩ፣ቶሎ እንጨርሳለን::

ቤተክርስቲያኑን ቶሎ ቶሎ ሲጎበኙ በድጋሚ የጆርጅን ትኩረት የሳበው በተለይ በውስጥ ጣሪያው ላይ የተሳሉት የሥዕሎች ብዛት ነበር:: በጆርጅ እምነት ሥዕሎችን በአምልኮ ሥፍራ ማኖር ተገቢ አይደለም . . ውብ ጌጦቹና የጸሐይን ብርሃን የሚያንጸባርቁ ሰባቱ ጉልላቶችም ዓይን የሚስቡ ናቸው:: ድንቅ ጥበብ የሚስተዋልበት ሕንጻ ነው:: ጆርጅ በችኮላ ጸሎት አደረሰና ለቀው ወጡ . .

- የሚማርክ እጅግ የተዋበ ሕንጻ ነው::
- አዎ፣ምርጥ ከሚባሉ የኪነ ሕንጻ ጥበቦች አንዱ ነው::
- እናንተ ካቶሊኮች ግን በአምልኮ ቦታዎች ውስጥ ሥዕሎችን ትወዳላችሁ:: እኔ ግን ይህ በአምልኮ ቤት ውስጥ መኖር የሌለበት ተገቢ ያልሆነ ነገር ነው የሚል እምነት አለኝ:: እንዳውም የጣዖት አምላኪዎችን የማምለኪያ ስፍራዎች ያስታውሱኛል::
- በመጀመሪያ ደረጃ ቤተክርስቲያኑ የካቶሊክ ሳይሆን የኦርቶዶክስ ነው:: ሁለተኛ እናንተ ፕሮቴስታንቶች በዚህ በኩል ከሙስሊሞች ጋር

ትመሳሰላላችሁ ብየሃለሁ::

- የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አይደለም?! ታዲያ ባለቤቴ ካትሪና እውስጡ እንድጸልይ ለምን ፈለገች?!
- እኔ እንጃ !
- የሃይማኖቶች ጉዳይ ምሁርና ተመራማሪ እንደ መሆንህ በኦርቶዶክስ፣በካቶሊክና በፕሮቴስታንት መካከል ያሉትን ልዩነቶች በአንተ አመለካከት ምን እንደሆነ ልታብራራልኝ ትችላለህ?
- ለመመለስ አስቸጋሪ የሆነ ውስብስብ ጥያቄ ነው::
- ነገሮችን ማቅለል ትወድ የለ ? ቀለል አድርገህ ንገረኝ::
- እሞክራለሁ ግን . . ጠቅለል ባለ አነጋገር ቁጥራቸው እጅግ የበዙ የክርስትና ቡድኖች፣ጎራዎችና ሴክቶች ይገኛሉ:: ለማቅለል ያህል በጠቀስካቸው ሶስቱ ትላልቅ ቡድኖች ብንወሰን በመጀመሪያ ኦርቶዶክስን እናገኛለን:: ትርጉሙ ትክክለኛው፣እውነተኛው፣የጥንቱ፣ሃይማኖት አጥባቂው፣መደበኛው ማለት ነው:: ኦርቶዶክስ ጥንት መሰረት ሲሆን ካቶሊክ ከ451 ጀምሮ ከርሱ ተገንጥሎ የወጣ ነው:: ትርጉሙ አጠቃላዩ ወይም ዓለም አቀፉ ማለት ነው:: ፕሮቴስታንት ደግሞ ከካቶሊክ የተገነጠለና በአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አውሮፓን ባጥለቀለቀው የሃይማኖት ተሐድሶ ንቅናቄ በማርቲን ሉተር መሪነት የተመሰረተ ነው::
- እናም ጥንተ መሰረቱ ኦርቶዶክስ እንጂ እናንተ ካቶሊኮች አይደላችሁም ማለት ነው?
- አዎ አይደለንም፣ለናንተ ለፕሮቴስታንቶች ግን መሰረት ነን:: ዋናው ነገር የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የምስራቅ ቤተክርስቲያን ወይም የምስራቃውያን ሮም ቤተክርስቲያን ተብሎ ይጠራል:: ተከታዮቹ እንደ ሩሲያ፣የበልቃን አገሮች ያሉ የምስራቅ አውሮፓ አገሮችና ግሪክ ናቸው:: የጥንት ዋና መቀመጫው የቆስጠንጥኒያ (ኮንስታንትኖፕል) ከተማ ስትሆን፣የግብጽ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ፣የአርመንና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያኖች የዚህ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ናቸው:: የኦርቶዶክስ (ምስራቅና ኦሪየንታል) ሃይማኖት ተከታዮች ቁጥር 312 ሚሊዮን ያህል ነው::
- 312 ሚሊዮን ተከታዮች!
- የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ደግሞ የምዕራብ ቤተክርስቲያን ተብሎ

www.path-2-happiness.com

ይጠራል። በምዕራብ ላቲን በኢጣሊያ፣በቤልጂየም፣በፈረንሳይ፣በእስፔን እና በፖርቱጋል የተስፋፋ ሲሆን በአውሮፓ፣በብራዚል፣በሰሜንና ደቡባዊ አሜሪካ አገሮች፣በአፍሪካና በኤስያም ተከታዮች አሉት። የቤተክርስቲያኑ መስራች የሐዋርያት አለቃ የሆነው ጴጥሮስ ሲሆን የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳትን የርሱ እንደራሴ ነው ብለው ያምናሉ። በተጨማሪም የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እናትና አስተማሪ አድርገው ራሳቸውን ሲቆጥሩ የቤተክርስቲያኒቱ ሲኖዶስ የሊቀ ጳጳሱን ፈቃድ የማወጅ መብት አለው። ፓፓው የኢየሱስ ሐዋርያና እንደራሴ የጴጥሮስ ተጠሪ በመሆኑ የፓፓው ፈቃድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ተደርጎ ይታመናል። በመሆኑም የሊቀ ጳጳሱ ፈቃድና ውሳኔ ጥያቄና ክርክር ሊቀርብበት የማይችል መለኮታዊ ፈቃድና ውሳኔ ነው ብለው ያምናሉ። የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ቁጥር አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ያህል ነው።

- መልካም፣የፕሮቴስታንቶችን ደግሞ ቀጥልልኝ ?

- ፕሮቴሰታን ቤተክርስቲያን ወንጌላዊ ማለትም ተከታዮቹ ወንጌልን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት በቀጥታ ለራሳቸው ተረድተው የሚከተሉበት ቤተክርስቲያን ሲሆን ካህናትና የቤተክርስቲያን መሪዎች ከአማኙ የተለየ ግንዛቤና ራእይ አላቸው ብለው አያምኑም። በአጠቃላይ መልኩ በመሰረታዊ የክርስትና እምነቶች የሚምኑ ክርስቲያኖች ሲሆኑ በብዙዎቹ የቤተክርስቲያን ምስጢራት፣ልማዶችና ስርዓቶች፣ በቤተክርስቲያን በተደነገጉ ጸሎቶች፣በጥምቀትና በመሳሰሉት ግን አያምኑም። አንዳንዶቹን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፎችና አያሌ የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ወግና ልማዶችንም አይቀበሉም። የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ቁጥር ከ600 እስከ 800 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል።

- ከክርስትና ውጭ ልታደርጉን ነው የምትፈልጉት? ግድ የለም፣ለመሆኑ በሦስቱ ቡድኖች መካከል ያሉት መሰረታዊ ልዩነቶች ምንድናቸው ?

- ከክርስትና ውጭ ልታደርጉን ነው የምትፈልጉት ስትል መሰረታዊውን ጉዳይ ጠቅሰሃል። እውነቱን ለመናገር በተለያዩት አብያተክርስቲያናት እና ቡድኖች መካከል ያሉት ልዩነቶች፣በአንዳንዶች ዘንድ ራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ ሃይማኖቶች እንጅ በአንድ ሃይማኖት ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች ናቸው ብሎ መውሰድ እስከማይቻልበት ደረጃ እጅግ በጣም የሰፉ ናቸው።

- እንዴት ማለት? ብታብራራልኝ?

- ሁሉም ቡድኖች በሁሉም የክርስትና እምነቶች ላይ ልዩነቶች አሏቸው። ስለዚህም መኪና ውስጥ ሆነን እንዲህ በቀላሉ መዘርዘር አንችልም። በእግዚአብሔር አምላክ ማንነትና ባህርያት ላይ፣በኢየሱስ ማንነትና ባህርያት ላይ፣በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ፣በአምልኮ ደንብና ሥርዓቶች ላይ፣ በሌሎች ብዙ ብዙ ጉዳዮች ላይ ይለያያሉ።

- ልየነቶቹ እስከዚህ ድረስ የገዘፉና የበዙ ከሆኑ እንዴት አንድ ሃይማኖት ሊሆን ይችላል ? የግድ አንደኛቸው ትክክል ይሆናል።

- አንዱ ብቻ ትክክለኛ ነው የሚለው አስተሳሰብ ነው በነዚህ የተለያዩ የክርስትና ቡድኖችና ጎራዎች መካከል ጦርነቶችን የጫረው።

- ጦርነቶችን? !

- አዎ፣ብዙ ሚሊዮኖች ያለቁባቸው ጦርነቶች። ለምሳሌ ያህል ከ1618 እስከ 1648 ባሉት ዓመታት በካቶሊኮች እና በፕሮቴስታንቶች መካከል በአገሮች ደረጃ የተደረገው የሰላሳ ዓመት ጦርነት የብዙ ሚሊዮን አውሮፓውያንን ሕይወት ቀጥፏል። ጀርመን ብቻዋን ግማሽ የሚሆኑ ወንድ ዜጎቿን አጥታለች። የዜጎቿ ቁጥር ከሃያ ሚሊዮን ወደ አስራ ሦስት ሚሊዮን ተኩል አሽቆልቁሏል!

ሽብርተኝነትን እና አክራሪነትን በሁሉም መልካቸው የሚጠላው ጆርጅ ይህን ሲሰማ ስሜቱ ክፉኛ ተነካ። የደስተኝነትና የተድላ መንገድ በደም የተጥለቀለቀና የጨቀየ ሊሆን ይችላል? ሲል ራሱን በራሱ ጠየቀ። ጌታዬ በእዝነትህ እየን፣የሰው ልጅ በዚህ ዓይነቱ አረመኔያዊ ጭካኔ ተድላና ደስታን ማግኘት አይችልም . .

- ምን ዓይነት ጭካኔ ነው?!

- ወደድንም ጠላን፣በእምነት ምክንያት የሚነሱ የከረሩ ልዩነቶች ወደ ግጭቶች የሚለወጡ መሆናቸውን ታሪክ ያረጋግጣል።

- በጣም አስፈሪ የሆነ አሸባሪ ታሪክ ነው!

- አዎ ያሳዝናል፣በአጠቃላይ የሃይማኖቶች ግጭት አይሁዶች በክርስቲያኖች ላይ ካካሄዱት ጦርነትና ከፈጸሙባቸው ግፍ አንስቶ፣ኢየሱስን መግደላቸው፣በኋላ ላይ ደግሞ ክርስቲያኖች አይሁዶችን መጮቆናቸው፣ቀጥሎም ዛሬ አይሁዶች ሙስሊሞችን እና ክርስቲያኖችን መጨቆናቸው በጣም አሳሳቢና አስጨናቂ ነው።

www.path-2-happiness.com

- አሁንም በድጋሚ ሙስሊሞች አይሁዶችን ወይም ክርስቲያኖችን ስለ መጨቆናቸው አላነሳህም !
- በታሪክ መከሰቱን ስለማላውቅ ነው፣አንድ ምሳሌ ልትሰጠኝ ትችላለህ ?
- ሙስሊሞች የትንሣኤን ቤተክርስቲያን ማፍረሳቸው።
- እንዲህ ያሉ ነጠላ ክስተቶች ብዙ ናቸው። እኔ የምናገረው ግን አጠቃላይ ስለሆነ ግፍና ጭቆና ነው። ሰዎችን ስለ መግደልና ሃይማኖታዊ ስርዓቶቻቸውን እንዳይፈጽሙ ስለ ማገድ ነው። እስላም ቤተክርስቲያንና ገዳማትን ማፍረስም ሆነ በጦርነት ውስጥ ቢሆን እንኳ መነኮሳትን መግደል ይከለክላል። በዚህ ረገድ የደረሱ ነጠላ ሁነቶች ፈጽሞ አጠቃላይ ወደ ሆነ የታቀደ ግፍና ጭቆና ደረጃ የሚደርስ አልነበረም።
- በክርስትና ውስጥ የተደበቅክ ሙስሊም ሳትሆን አልቀረም።
- እህህ፣ሊሆን ይችላል፣ማን ያውቃል ምናልባት አንድ ቀን ሙስሊም ወይም ፕሮቴስታንት እሆን ይሆናል። እናንተ እንደነሱ በአምልኮ ቦታ ሥዕልና ቅርጻ ቅርጾችን አትወዱም አላልኩህም ነበር። (ወደ ጆርጅ ዞር አለና) ፦ ወይ ደግሞ ካንተ ጋር በደስተኝነት ጎዳና እጓዝ ይሆናል። ጎሽ አስታወስከኝ . . ‹የደስተኝነት መንገድ› ጉዳይ ምን እንደሆነ አልነገርከኝም፣ምን ይሆን?!
- ‹የደስተኝነት መንገድ› ጉዳይ ታሪኩ በጣም ረዥም ነው።
- ቀለል አድርገህና አሳጥረህ ንገረኝ።
- እውነቱን ለመናገር የሕይወት ትላልቅ ጥያቄዎች ማለትም ለምን ተፈጠርን? ማን ፈጠረን? ለምንድነው የምንኖረው? መጨረሻችንስ ወዴት ነው? የሚሉት በጣም ነው ያደከሙኝ። ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ እሳከገኝላቸው ድረስ ደስተኛ መሆን እንደማልችል ስለ ተረዳሁ የደስተኝነትን መንገድ ለማግኘት ፍለጋ ጀመርኩ። (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ ተኝቼ ሳለሁ ሰማሁ ያልከኝ ስሞች በደስተኝነት መንገድ ፍለጋ ሂደት ውስጥ ያገኘኋቸውና ያጋጠሙኝ ግለሰቦች ናቸው።
- የዚች ቅድስት ከተማ ጉብኝትህ፣ክርክሮችህና ውይቶችህ ሁሉ የደስተኝነት መንገድ ፍለጋ ጥረትህ አካላት ናቸው?
- የመጣሁት ለሥራ ጉብኝት ነው፤እንድመጣ የቀሰቀሰኝ እውነታ ግን አንተ ያልከው ነው።
- ይህን መንገድ መቼ ነው የምታጠናቅቀው ?

- አላውቅም፣ለመድረስ ግን ቁርጠኛ ነኝ። (ፈገግ እያለ ወደሱ ዞረና) ፦ የደስተኝነት መንገድ ፍለጋው ራሱ ደስተኝነት ነው።
- በእኔ በአንተና በሌቪ መካከል ብዙ መመሳሰሎች ያሉ ይመስለኛል።
- እንዴት?
- ከአይሁዳዊነት ውጭ ደስተኝነትን ፍለጋ እኔ ዘንድ መጥታ ካቶሊካዊነት ሊያረካት አልቻለም። እኔ ደግሞ ኦርቶዶክስ ነበርኩ ወደ ካቶሊክነት ተለውጬ አሁንም ድረስ በፍለጋና በምርምር ላይ ነኝ።
- ፕሮቴስታንትን ሞክር . . ምናልባት መፍትሔ ሊሆንህ ይችላል። ለካቶሊካዊቷ ባለቤቴ አዘውትሬ፣ሃይማኖታችሁ በአያሌ መንፈሳዊ ሥርዓቶችና ምክንያታዊ ባልሆኑ ሚስጥራት የተወሳሰበ ነው እላታለሁ።
- ምናልባት ይሆናል፣በደስተኝነት ፍለጋ ጉዞህ ግን የት ደርሰሃል?
- ይቅርታ፣ወደ ሆቴሉ ለመድረስ የት ደርሰናል? አንዳች የጤና መታወክ እየጀመረኝ ይመስለኛል፣ከመጠነኛ ማዞር ጋር ገላዬ ከባብዶኛል።
- አይዞህ በርታ፣ጌታ ይባርክህ፣ሩብ ሰዓት ያህል ብቻ ነው የሚቀረን።
- በጣም ነው የማመሰግንህ፣በብዙ ነገር ጠቅመህኛል።
- ካንተ ጋር ያስተዋወቀችኝ ሌቪ ነች መመስገን ያለባት፤እርሷን አመስግናት። በከፍተኛ ደረጃ ነው ለምቾትህ የተጨነቀችው።
- ልክ ነህ፣ሌቪ በጣም ልዩ የሆነች ሴት ናት፤በጣም አመሰግናታለሁ።
- የምትወዳት ትመስላለህ፣ባለትዳር ነኝ ብለህኝ የለ?
- አዎ ባለትዳር ነኝ፣እሷ በጣም ውብ ኮረዳ ነች፤አሳሳች ቁንጅናና መግናጢሳዊ መስህብነት ቢኖራትም ከገላዋ ይበልጥ መንፈሷን ነው የምወደው።
- ተምኔታዊ አፍቃሪ ትመስላለህ!
- እህህ፣ወይም ብዙዎቹ የሚያውቁኝ ሰዎች እንደሚሉኝ ውስብስብ ሕመምተኛ ነኝ።
- በቁሳዊ ማህበረሰቦቻችን ውስጥ በአምልኮቱና በዓለማዊ መደሰቻው መስክም ከመንፈሳዊ ጎን ይልቅ ቁሳዊ ጎን ቅድሚያ ይሰጣል። በብዙዎቻችን ዘንድ እውነታው ይህ ሲሆን በአይሁዶች ዘንድ ደግሞ ብልጫው የጎላ ነው።
- እንዴት?
- ከክርስትና መገለጫዎች አንዱ ነገሮችን በመንፈሳዊ ጎናቸው መመልከት

www.path-2-happiness.com

ነው:: ይሁን እንጅ ቁሳዊ ሕብረተሰቦቻችን ትኩረት የሚሰጡት ለመንፈሳዊ ደስታዎች ሳይሆን ለሥጋዊ ደስታዎች ነው:: የአይሁዶች ታሪክ ግን ለሁሉም ነገር፣ለአምላክ፣ለወዳኛው ዓለም፣ለሞራልና ለስነ ምግባር . . ቁሳዊ አመለካከት እንዳለቸው ነው የሚያረጋግጠው:: ሁሉም ነገር ሊሸጥ፣ሊገዛና ሊለወጥ ይችላል፣ሽያጭና ግዥ ግብይት ሲባል ሸቀጥ ብቻ ማለት አይደለም::

- በአይሁዶች ላይ ትጫናለህ ብየህ የለ?
- በዚህ ላይ ከሌቪ ጋር መነጋገር ትችላለህ:: ፈታኝና ማራኪ አይሁዳዊት ስለሆነች በአይሁዶች ላይ የምትጫን አትሆንም:: በተጨማሪም ታሪክንና ተጨባጩን ነገር ማየት ትችላለህ::
- እንደልማድህ ረታሀኝ፣በጣም ደከመኝ ደርሰናል?
- ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፣አይዞህ በርታ እንደርሳለን::

የጆርጅ ስልክ አቃጨለ . . የሌቪ ውብ ድምጽ ነበር . .

- ሃሎ ጆርጅ::
- ሃሎ::
- ጉዟችሁ እንዴት ነበር?
- ግሩም ነበር፣እንዴታ ከመረጥሽልኝ ድንቅ ባልደረባ ከዶክተር ሐቢብ ጋር ሆኜ !
- ምርጫዬ በጣም ጥሩ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ::
- እጅግ በጣም ጥሩ እንጂ፣አመሰግናለሁ::
- ጸሐይ ከመጥለቋና ሰንበት ከመግባቱ በፊት ደህንነትን ለማወቅ ነው የደወልኩት::
- እኔ ደህና ነኝ፣በመደወልሽ አመሰግናለሁ:: ለአዘገጀሽልኝ የተመቻቸ ጉብኝትም ምስጋናዬ የላቀ ነው:: ነገ ምን ጊዜ ነው የማገኝሽ ?
- በፈለከው ሰዓት፣እኔም ላገኝህ ጓግቻለሁ::
- እኔም ናፍቂያለሁ፤እንግዲያውስ ትንሽ ስለ ደካከመኝ በቂ እረፍት መውሰድ እፈልጋለሁና ቀጠሯችን ጧት ሦስት ሰዓት ነው::

ጆርጅ ትንሽ የመርበትበት ስሜት አሳየና ስረቅ አድርጎ ወደ ሐቢብ ሲመለከት ፈገግታውን ለመደበቅ ሲሞክር አየው . .

- አይዞህ፣ጌታ በጥበቃው ካንተ ጋር ይሁን፤ሐኪም ላምጣልህ እንዴ ?

- ሌቪ አመሰግናለሁ፣ነገ ሙሉ ንቃቴ ተመልሶ ሦስት ሰዓት ላይ ዝግጁ ሆኜ ታገኚኛለሽ::
- ደህና ሁን . .
- አመሰግናለሁ፣ደህና ሁኚ . .
- . . ሞቅ ያለ የስልክ ጥሪ ነው!!
- ምን ማለትህ ነው ?
- ምንም፣ሌቪ አንተ እንደምትለው ግሩም ድንቅ የሆነች ፈታኝ ቆንጆ ኮረዳ ናት::
- ምን ማለትህ ነው ?
- እየቀለድኩብህ ነው:: አንተ እንደምታደንቃት ሁሉ ሌቪም በጣም የምታደንቅህ ነው የሚመስለኝ:: አንደኛችሁ አድናቆቱን በሌላው መንፈስ፣አመለካከትና ሞራል ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ይሞክራል . . (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ ለመንፈሱ ብቻ ሳይሆን አንዱ ለሌላው ገላም እንዲሁ አድናቂ ነው፣በመሆኑም የመንፈስ አድናቆቱ ወደ ገላ አድናቆት እንዳይሸጋገር ጥንቃቄ አድርግ:: ሌቪ የነገረችኝን መርሆዎቻችሁን ለመጣስ ወደሚዳርጋችሁና ወደማትፈልጉት ነገር እንዳትደርሱ ራሳችሁን ያዝ አድርጉ:: ለማንኛውም ይህውና ሆቴሉ ደርሰናል::
- ከልብ ለመነጨው እውነተኛና አስቸጋሪ ምክር አመሰግናለሁ:: ምሳ ወይም እራት አብረን እንብላ፣እስካሁን ምሳም አልበላንም::
- አንተ በጣም ደክሞሃል፣እኔም እንደዚያው ነኝና ይቅርታ አድርግልኝ::
- አመሰግናለሁ፣ብዙ ነገር ነው ካንተ የተማርኩት:: ይህ የቢዝነስ ካርዴ ነው፣ግንኙነታችን እንደሚቀጠል ተስፋ አደርጋለሁ . . እህህ፣ነገ ሙሉውን ቀን ከሌቪ ጋር ስለሚሆን በመካከላችን ጠባቂ ዘበኛ ብትሆን ችግር የለውም::
- ለባህል፣ለስልጣኔ፣ለእሳቤ እና ለመርህ ያለህን ትኩረት አውቃለሁ:: ግና እርሷንም እንዳስጠነቀቅኩ ሁሉ አንዳንዴ ነገሮች እንዳይደበላለቁብህ እና ሰዎች እንደመሆናችን ስብአዊ ድክመት እንዳለብን ላሳስብህ እወዳለሁ፤አመሰግናለሁ . . ተመልሰህ ከመሄድህ በፊት ለመገናኘት ተስፋ አደርጋለሁ . . ይህውና የቢዝነስ ካርዴ . . የደስተኝነት መንገድ ፍልጋህ የት እንደደረሰ ሁሉ አሳውቀኝ::

ከፍተኛ ድካም እየተሰማው ወደ ክፍሉ ሄደና በመጀመሪያ ሻውር ወሰደ . .

www.path-2-happiness.com

እንደልማዱ ቲቪ ከፍቶ ዜና ተከታተለ። አዲስ ነገር አልነበረም። ኢሜይሉን ለማየት ኮምፒውተሩን ከፈተና ከኣደም የተላከውን የሚከተለውን መልእክት አገኘ ፦

‹‹ከሰላምታ በኋላ ፦

የላክልኝን የተዛቡና የተበረዙ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን አነበብኳቸው፤የሚታመንና ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም። በመላክህ አመሰግናለሁ፤ስትመለስ እንወያይባቸዋለን። እንዲህ ያሉትን መልእክቶች መላኩን ትቀጥላህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፣እጅግ በጣም ይጠቅሙኛል።››

ቀጥሎም ተከታዩን የቶም መልእክት አገኘ ፦

‹‹ከሰላምታ በኋላ ፦

የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን በተመለከተ ቀደም ብዬ ሁሉም ሃይማኖቶች ዋጋ እንደ ሌላቸው ነግሬሃለሁ። ይህ መልእክትህ እስከ ደረሰኝ ድረስ አቋሜን ለማስቀየር ተቃርበህ ነበር፤አሁን ግን የኔን እምነህ መቀበል ጀምረሃል ብዬ ጠርጥሬያለሁ።ክርስቲያኖችም በዚህ በምትተቸው ብሉይ ኪዳን የሚያምኑ መሆናቸውን አትርሳ። በዚህ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ቀጠሮአችን ማክሰኞ ስምንት ሰዓት ነው። ሌሎች ነገሮች ካሉህ ላክልኝ።››

- ጆርጅ ዛሬ ያሳለፈውን ሁሉ ሊጽፍላቸው ፍላጎት ነበረው፣ዳሩ ግን ድካሙ እየተባባሰበት በመሆኑ አልቻለም ። በመሆኑም አንድ ደብዳቤ በአጭሩ ብቻ ሊጽፍላቸው ወሰነ . . ከሰላምታ በኋላ ሚከተለውን አሰፈረ ፦

‹‹መልስህን አንብቤያለሁ፣ዝርዝር ጉዳዮችን አንድ በአንድ እጽፍልሃለሁ። የዛሬው ቀን እንደ ትናንቱ ሁሉ በሁነቶች የተሞላ ነበር። በሃይማኖቶች ውስብስብ ጉዳዮች፣በሃይማኖት ግጭቶች እና ጭቃናዎች፣በተለያዩ የክርስትና ቡድኖች እና አብያተክርስቲያናት መካከል ባሉት ልዩነቶችና ቅራኔዎች . . ላይ ያተኮረ ነበር። ትንሽ ስለ ደካከመኝ የደረስኩባቸውን አንዳንድ ጉዳዮች ነገ እልክላችኋለሁ።››

ኮምፒውተሩን ዘጋና አልጋው ላይ ተንጋለለ። በጣም የደከመውና ድቅቅ ያለ ቢሆንም የሌቪ ምስል፣ደማቅ ፈገግታዋና ሰማያዊ ማራኪ ዓይኖቿ ከሕሊናው ሊጠፉ አልቻሉም። ነገሮች አንዳንዴ ሊደበላለቁ ይችላሉ የሚለው የዶክተር ሐቢብ ቃል ታወሰው። ስጋት ቢኖረውም በራሱ ይተማመናል፣በሌቪም እንዲሁ ይተማመናል።

ሥጋዊ ፍላጎትና መርሕ . .

www.path-2-happiness.com

8

ሥጋዊ ፍላጎትና መርሕ . .

ሥጋዊ ፍላጎትና መርሕ . .

(1)

ጆርጅ ጧት ሁለት ተኩል ላይ ነቃ። የሰራ ገላው በሕመም ስሜት ተወሮ ትኩሳቱ ከፍ በማለቱ ሌሊቱን እንቅልፍ አልወሰደውም። የትኩሳት መቀነሻ እንዲሰጠው ከሆቴሉ ለመጠየቅ ተገደደ። እንደ ምንም ብሎ ለመንቀሳቀስ ሞከረና ተነስቶ ገላውን ሲታጠብ ትንሽ ሻል አለው። ወደ ሬስቶራንቱ ሄዶ ቁርሱን በላና የሕመም ማስታገሻ እንክብሉን በድጋሜ ሲወስድ እፎይታ አገኘ።

ሦስት ሰዓት ከአስር ላይ ወደ ክፍሉ ሲመለስ ስልኩ እየጮኸ ነበር። የሌቪ ውብና የሚያጓጓ ድምጽ ነበር።

- የት ነህ? አሳሰብከኝ፣ደጋግሜ ደውዬ ስልኩ አይነሳም።
- ይቅርታ፣ረስቼ ስልኬን ሳልይዝ ለቁርስ ወጥቼ ነበር።
- ከቀጠሮ መዘግየት ልማድህ አይደለም ብዬ ነው።
- ሳያመኝ አልቀረም፣ሌሊቱን በደንብ መተኛት አልቻልኩም ነበር።
- ጌታ ይፈውስህ፣ሐኪም ቤት እንድወስድህ ትፈልጋለህ?
- የለም አመሰግናለሁ፤ቀጠሮ በማሳለፌም ይቅርታ እጠይቃለሁ። አሁን በጎ ነኝ፣ሻል እያለኝ ነው።

ጆርጅ ወደ እንግዳ መቀበያው ሄደ፤ገላን የሚሸፍን ጨዋ ግን ማራኪ ውበቷን ያልደበቀ ልብስ ለብሳ ሌቪን አያት። ጨበጣትና ሰላምታ ተለዋወጡ . . ጭንቅ ብላ አለችው፦

- ሐኪም ቤት መሄድ አለብህ፣እንዲህ ሆነህ እያየን ዝም ማለት አይገባም።
- ሌቪ አመሰግናለሁ። አሁን ጥሩ ተሽሎኛል፣ቅዱሳን ስፍራዎቹን ለመጎብኘት ብንሄድ ደስተኛ ነኝ።
- እንደ ፈቃድህ ይሁን፤ዋነው ነገር ያንተ ደስተኝነት ነው . . ዛሬ ሁለት ወይም ሦስት ቦታዎችን ትጎበኛል፣ምን ይመስለሃል?
- ይበልጥ አስፈላጊ በሆነው እንጀመር፣ሁለቱን ካደረስን በቂ ነው። ይበልጥ የሚያስፈልገኝ ጉብኝቱ ብቻ ሳይሆን ካንቺ ጋር ቁጭ ብሎ መወያየት ነው።

www.path-2-happiness.com

-ለኔም ዋነኛው ነገር ያ ነው:: መጀመሪያ የምናመራው ወደ ማልቀሻ ግንብና ወደ ዮራ ተራራ ነው:: ከዚያ በጽዮን ተራራ የሚገኘውን የንጉሥ ዳዊትን መቃብር ትጎበኛለህ:: በቂ ጊዜ ከተገኘ ደግሞ በወይራ ተራራ የሚገኙ ጥንታዊ መቃብሮችን ትጎበኛል::

-ተስማሚ ነው፤ድካሙ ሳይመለስብኝ ጉብኝቱን በጊዜ ለማጠናቅቅ ተስፋ አደርጋለሁ::

-ከሐቢብ ጋር የነበረህ ቆይታ እንዴት ነበር?

-ምርጫሽ ግሩም ነው፤በሚገባ የተረዳሽኝ ይመስለኛል::

ዓይኖቸዋ ክብልል ክብልል አሉ፣ስርጉድ ጉንጮቿ ደመቁ፣ፈገግ አለች . .

-ኣ . . ምናልባት በመጠኑ፣ሐቢብ ምሁር ነው፣አእምሮው ብሩህና ክፍት ነው::

-ልክ ነሽ፣በእውቀቱ ብዙ ተጠቅሜያለሁ::

-እሱም ሰለ አንተ እንዲዚሁ ነው የሚለው::

ጆርጅ በአግራሞት ጠየቃት ፦

-እንዴትና መቼ ነው እንደዚህ ያለሽ?

-ማታ ወደ ሆቴል ካደረስህ በኋላ ወዲያውኑ ነበር የደወለልኝ፤ካንተ ጋር ባሳለፈው ቆይታ ብዙ መጠቀሙን በአድናቆት ነገረኝ . . ማንንም ሲያደንቅ ባልሰማሁት ሁኔታ ነው ላንተ ያለውን አድናቆት የገለጸልኝ::

-ይህ መቼም የርሱ ትሕትና ነው እንጂ ሙሉ ጊዘውን ከርሱ ጋር ያሳለፍኩት በውይይት በክርክርና በቃለ ምልልስ ነበር::

-ከኔ ጋር የምታደርገው ዓይነት ውይይትና ምልልስ ከሆነ እጹብ ድንቅ ውይይት ነው!

ከማግኔታዊ ገላዋ ጋር . . ከውብ መንፈሷ ጋር . . ጆርጅ ጣፋጭ ንግግሯን በለስላሳ ድምጽዋ እያዳመጠ መነቃቃት ተሰማው::

-እህ፣ትንሽ ይለያያል፤አንቺ ረቀቅ ያልሽ ውብ ቆንጆ ነሽ፣እሱ ግን አይደለም፤እርሱን ስለ መረጥሽልኝ ግን በጣም አመሰግንሻለሁ፣ላደረግሽልኝ እንክብካቤና ከኔ ጋር በመድከምሽም ምሳጋናዬ የላቀ ነው:: ዋናው ጉዳይ መሰረታዊዎቹ የጉብኝቴ ዓላማዎች ማለትም ስምምነቱን መፈራረምና የደስተኝነት መንገድ ፍለጋውም በስኬት እየተካሄደ መሆኑ ነው::

-ምስጋና የሚገባህ አንተ ነህ፣የውሉን ጉዳይ አሁንም ታስታውሳለህ? እኔ ጭራሽ ረስቼዋለሁ:: በነገራችን ላይ ከቤንያሚን ጋር ያደረከው ቆይታ አእምሮው ውስጥ ዝብርቅርቅ ሁኔታ ሳይፈጥርበት አልቀረም::

-እንዴት?

-እኔ እንጃ፣አንተ ወጥተህ ከሄድክ በኋላ አስጠራኝና ‹‹ይህ ሰው በሕይወቴ ውስጥ ካጋጠሙኝ ሁሉ በጣም አስገራሚው ነው›› አለኝና እንዴት? አልኩት፤‹‹ወይ እብድ ነው፣ወይ ደግሞ ቅዱስ ነው›› አለኝ::

-እህህ፣ሦስተኛ አማራጭ የለም ! እብድ መሆን እንኳ አልፈልግም፤አዝናለሁ ለርሱ ጉቦ እያቀበልኩ ግን ቅዱስ መሆን አልችልም::

-ያልከው ነገር ለምን ተጽእኖ እንዳሳደረበት አላውቅም፣ደጋግሞ ሕይወት ገንዘብ ብቻ ናት ብለን ስናስብ ስህተት እንሰራለን ይለኝ ነበር:: በሕይወቴ እንዲህ ያለውን አነጋገር ከቤንያሚን ስሰማ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው::

-ግልጽ ልሁንና . . የማይመቸኝ ሰው ቢሆንም እርሱም በአነጋገሩ ትልቅ ተጽእኖ አሳድሮብኛል:: እውን የአካል ደስታ የመንፈስ ስቃይ ነው? የአካልና የመንፈስ ደስታን አንድ ላይ ማጣጣም የሚቻልበትና ስቃይ የሚወገድበት መንገድ አይኖርም?

-እንዲህ ያለውን መንገድ ማግኘት የዘውትር ጉጉቴ ነው::

-እናም ሐቢብ እንደነገረኝ ሁሉ አንቺም በደስተኝነት መንገድ ፍለጋ ላይ ነሽ ማለት ነው?

-በጣም ውብ አባባል ነው፤ግና የደስተኝነት መንገድ ምንድነው?

-አሁን ለማግኘት ስትመኚው የነበረውና እኔም ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ፈልጌ ለማግኘት የተሰማራሁበት መንገድ ነው::

-እኔም ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ በፍላጋ ላይ ነኝ . . (ፈገግ ብላ ዓይን ዓይኑን እያየች) ፦ በሁለታችን መንፈስ መካከል እንዴት ያለ መቀራረብ ይሆን ያለው?!

-ሐቢብ ነግሮኛል፣ካቶሊካዊነትን ለምን አልተቀበልሽም?

-ሀሳቤ ከአይሁዳዊነት ውስብስብነትና ከመዛነፎቹ ለመሸሽ እንጂ ውስብስብነትን በሌላ ውስብስብነት፣መዛነፍን በሌላ መዛነፍ ለመለወጥ አልነበረም:: ለዚህ ለዚህማ አይሁዳዊነት ይበልጥ ጥንታዊና ይበልጥ የተቀደሰ ነው::

-እንዳስለመድሽኝ በግልጽነት ንግሪኝ፣ምክንያትሽ ይኸው ብቻ ነው ወይስ ሌሎች ምክንያቶች አሉሽ?!

-እውነቱን ለመናገር ሃይማኖትን መለወጥ ፈጽሞ ቀላል ነገር አይደለም:: ሃይማኖቱን የሚቀይር ሰው በዙሪያው ካሉት ሰዎች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ስታስብ ከቤንያሚን ጋር የሚኖረኝ ግንኙነት እንዴት ይሆናል?

www.path-2-happiness.com

በሥራዬ ላይ ለአንድ ቀን እንኳ የምቆይ ይመስለሃል?

- እናም ከርሱ በኩል ስጋት አለብሽ ማለት ነው?
- ከመጀመሪያውም በካቶሊካዊነት አልረካሁበትም ብየሃለሁ፣ደግሞም ግልጽ ለመሆን ሃይማኖቴን መለወጥ ያስፈራኛል . . ነጻነት ውድ ዋጋ ያስከፍላል . . እጅግ ውድ የሆነ ዋጋ !
- ነጻነታችንን ለማግኘት ግን ይህን ዋጋ መክፈል ግድ ይለናል፣ነጻነትን የሚመስል ምንም ነገር የለም።
- አሁንም ድረስ ትክክለኛውን ውሳኔ ወይም የደስተኝነትን መንገድ በመፈለግ ላይ ነኝ። ያንን በአሳማኝ መልኩ ሳገኝ ምናልባት በድፍረት መወሰን እችል ይሆናል፣ወይም መወሰን እፈራም ይሆናል . . አላውቅም !
- ቤንያሚንን ትፈሪዋለሽ?
- በትክክል ! . . . ድፍረት የተሞላበት ትክክለኛው ውሳኔ ወይም በአንተ አገላለጽ የደስተኝነት መንገድ ወደ ክርስትና የሚወስድ ነው ብለህ ታምናለህ?
- በተከራካሪሽ ላይ መንገድ የመዝጋት ልዩ አቅምና ብቃት አለሽ፣ለምን እንደሆነ አላውቅም?
- መንፈሳችን አብሮ ነው የሚንሳፈፈው ብየህ የለ? ምናልባት በሆነ አፍታ ላይ ተዋህዶ ሊሆን ይችላል።
- አንቺ ቆንጂት ፍጡር እነሆማ ወደ ፈላስፋነት ተለወጥሽ፣መንፈስና መንፈስ እንዴት ነው የሚዋሀደው?
- ኣህ፣አላውቅም፣የማውቀው ነገር ቢኖር አካል እንደሚዋሐድ ሁሉ መንፈስም የሚዋሐድ መሆኑንና የኔ መንፈስና ያንተ መንፈስ አብረው የሚንሳፈፉ መሆናቸውን ብቻ ነው።
- የሚመረጠው ግን በግርታና በጥርጣሬ ከመሆን ፈንታ በተድላና በደስተኝነት አብረው እንዲንሳፈፉ ነው።
- ልክ ነህ፣አሁን ይህን እንተውና ወደ ማልቀሻው ግንብ ወይም ሙስሊሞች እንደሚጠሩት የቡራቅ ግንብ ለመድረስ ጥቂት ደቂቃዎች ይቀሩናል። ከሰሎሞን ቤተ መቅደስ የተረፈ ብቸኛው ቅርስ ነው። በብዙኃኑ የአይሁድ ሃኻሞች አመለካከት ቤተ መቅደሱ ከወደመ በኋላ ወደ ቁድስ ቅጽረ ግቢ መግባት በአይሁዶች ላይ እርም ተደርጓል፣በመሆኑም በዘመነኛው አይሁዳዊ ሕግ መሰረት ግንቡ ለቤተመቅደሱ ቦታ ቅርብ የሆነ አይሁዶች መጸለይ የሚችሉበት ነጥብ ነው። ‹‹የማልቀሻ ግንብ›› የተባለው በግንቡ

አጠገብና በትይዩው በሚደረገው የለቅሶና የሀዘን የጸሎት ስርዓት ምክንያት ነው።

- ከመቼ ጀምሮ ነው?
- ከአስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት አይሁዶች ጸሎቶቻቸውን የሚያደርሱትና ለሰሎሞን ቤተ መቅደስ መውደም የሚያከናውኑትን የለቅሶ ሥርዓት ይፈጽሙ የነበሩት በቁድስ ግቢ አካባቢ በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ነበር። ከዚያ በኋላ በየዓመቱ ቁድስን ከሚከልለው አጥር አቅራቢያ ከሚገኘው ድንጋይ ፊትለፊት መሰባሰብ ጀመሩ። እነሱ የማልቀሻ ግንብ ሲሉት ሙስሊሞች ደግሞ የቡራቅ ግንብ ይሉታል።
- ታድያ የቡራቅ ግንብ ምንድነው?
- ቦታው በሙስሊሞች ዘንድም የተቀደሰ ቦታ ነው። ነቢያቸው ከመካ ወደ ቁድስ ቡራቅ በሚባል እንስሳ ላይ ተቀምጦ የሌሊት ጉዞ ባደረገ ጊዜ ቡራቅን እዚህ ግንብ ዘንድ እንዳቆመው ይናገራሉ።
- ሙስሊሞች በዚህ ቦታ ላይ ሃይማኖታዊ ሥርዓት እንዲያከናውኑ ትፈቅዳላችሁ?
- ሙሉውን የቁድስ ግቢ ትተንላቸውም ይህን ግንብም ከኛ ጋር ይሻማሉ ! ደግሞም ሙስሊሞች በቅርሶች ዘንድ አምልኮ አያካሄዱም፣ሐውልትና ቅርጻ ቅርጾች ጉዳያቸው አይደሉም።
- ሐቢብ፣ፕሮቴስታንቶች እንደ ሙስሊሞች ናችሁ፣ቅርጻቅርጽና ሥልሎችን አትወዱም እያለ ያሾፍብኝ ነበር።
- ከወደመው ቤተ መቅደሳችን የተረፈልን ይኸው ብቻ ነው፣ይህንን የሚያረጋግጡ የቅርስ ማስረጃዎችን ለዓለም ሁሉ ወደፊት እናሳያለን።
- ይህን ሁሉ ዓመታት የምትሉትን አስረጅ ቅርስ ማግኘት አልቻላችሁም፣ካሁን በኋላ እናገኛለን ብለሽ ተስፋ ታደርጊያለሽ?
- አሃ፣ባናገኘው እንኳ እንፈጥረዋለን !
- እናም አንቺ በዚህ አታምኚም ማለት ነው?
- አምንበታለሁ ወይም አላምንበትም አልልም፣በጥርጣሬ ሁኔታ ውስጥ ነኝ። አንዳንድ ጥናቶች የሚያመለክቱት አይሁዶች ግንቡ አጠገብ መጸለይ የጀመሩት በኦትማን ኢምፓየር ዘመን መሆኑን ነው። ቅድም እንዳልኩህ ከአስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት አይደለም። ሙስሊሞች ይህን ግልጽ ውሸት አድርገው ይቆጥሩታል። ለማንኛውም ቦታው እኛ ዘንድ ከሁሉም በላይ የተቀደሰ ቦታ ነው። (ወደ ጆርጅ ዞር አለችና) ፦

መንፈስህን መግራት፣ማንቃትና ደስተኛ ማድረግ የግድ ነው፤እናም ያለ አምልኮ እንድንቀር ነው የምትፈልገው?

- ዛሬ ደግሞ ከትናንቱ ይበልጥ አስደናቂ ትመስልያለሽ::
- ዛሬ የአምልኮ ቀን ነው፣ወደ ማልቀሻ ግንብ እየደረስን ነው:: አሁን ከመኪና ወርደን የቀረውን በእግር መጓዝ ይኖርብናል::
- በዚህ ጸሐይ ውስጥ በእግር የምንጓዘው አጭር ርቀት ብቻ እንዲሆን ምኞቴ ነው፤የድካም ስሜቱ እየተመለሰብኝ ነው::
- አይሁዳዊ አለመሆንህ እንዳይታወቅብህ ይሁን::
- እንዴት?
- ይህን በርኔጣ ወስደህ አድርገው::
- ግዴለም ይሁን፣እህህ፣ግን ይህን አድርጌ ፎቶግራፍ እንዳታነሽኝ፣አለዚያ ካትሪና መቆጣቷ ነው::
- ካትሪናን በጣም የምትወዳት ትመስላለህ !
- አዎ፣ሃይማኖተኛ የሆነች ምሁር ናት፣ልቧም እንዳንቺው የጸዳ ነጭ ነው::
- እንዳንተ ለሃይማኖት፣ለዕውቀትና ለፍካሬ . . አክብሮት የሚሰጥ ሰው ማግኘት እመኛለሁ . . አሁን ወደ ቀኝ ከዚያም እንደገና ወደ ቀኝ እንታጠፍና ሰዎች ተሰብስበው ግንቡ አጠገብ ሲያለቅሱ እናገኛቸዋለን::
- በርኔጣውን ለብሻለሁ፣ለቅሶውን አስመስዬ መተወን ግን አልችልም::
- ችግር የለውም፣ብዙዎች እንዳንተው አስመስለው መተወን አይችሉበትም:: ሌሎች በርካታ ሰዎች ግን ሲያለቅሱ ወይም በሚገባ አስመስልው ሲተውኑ ታገኛቸዋለህ . . የቀረው ያንተ ነው ለሴቶች መግባት የተከለከለ ነው::
- እንዴት? አንቺ ካልገባሽ እኔ አልገባም::
- በል እኔ እዚህ እጠብቀሃለሁ፣ገብቼ እንደውሻ እንድባረር ነው የምትፈልገው? እባክህን በል ግባ::

ጆርጅ ቀሪውን መንገድ ለብቻው ተጓዘ:: የድካም ስሜት እየተጠናወተው ወደ ግንቡ ደረሰ . . የሚያለቅሱ አይሁዶች ቁጥር ብዙ ነበር:: ሌሎች ብዞዎች ደግሞ አሳምረው ማልቀስ የማይችሉ የሚመስሉም ይታያሉ . . እያስተዋላቸው አጠገባቸው ቆመ፤ሆኖም ጭንቀት ስለ ተሰማውና በተለይም ድካሙ እየበረታና ትኩሳቱ እየጨመረ በመምጣቱ ቶሎ መውጣት ፈለገ:: በዙሪው ያሉትን በዓይኖቹ ቃኘ፣አንዲትም ሴት አላየም:: መቆየት አስጠላውና ለመመለስ ወሰነ፣ግና በግድ ነበር የሚራመደው፣የድካም ስሜቱ ከፊቱ በጉልህ ይነበባል፣እግሮቹን መጎተት እየተሳነው ነው:: እንደ ምንም ብሎ

ሌቪ ካለችበት ለመድረስ ቻለ:: መንገድ ላይ ሆና እየጠበቀችው አገኛት . .

- ቶሎ ተመለስክ !
- በጣም ደክሞኛል፣ቶሎ ወደ መኪናው መሄድ እንችላለን?
- ጥሩ ደስ እንዳለህ::
- ወይም መኪናውን እዚህ ማምጣት ትችያለሽ?
- በጣም የተዳከምክ ትመስላለህ . . አዝናለሁ መኪናውን እዚህ ማምጣት የሚቻል አይደለም፣በርታ እኔ ላይ መደገፍ ትችላለህ . .

ጆርጅ ድካሙ በጣም ጎልቶ ይታያል፣ትከሻዋ ላይ እንዲደገፍ ሌቪ እጁን አንገቷ ላይ አደረገች:: እጁን አንስቶ ቀጥ ብሎ ለመራመድ ቢሞክርም ሕመሙ አላስቻለውምና ከአንገቱ ትከሻዋ ላይ ዘንበል አለ:: ነፋስ ጸጉሯን ወደ ፊቱ፣የገላዋን ጠረን ወደ አፍንጫው አንቀሳቀሰ፣ጸጉሯ ከእጁ ስር ነው፤አንዳንዴ ጉንጬ ከጉንጯ ይጣበቃል . .

- አዝናለሁ፣አስቀድሜም አደከምኩሽ፣አሁንም እንደገና እያስቸገርኩሽ ነው . . እንደ ሕጻን እየቀበጥኩ ነው መሰለኝ::
- ግዴለም . . ዋናው ነገር ወደ መኪና ቶሎ መድረሳችን ነው . . በቅርብ ሆስፒታል ስለሚገኝ ወደዚያ እንሄዳለን፤ጤንነትህ አስተማማኝ ከሆነ በኋላ መቅበጡና እሽሩሩው ሊቀጥል ይችላል::

(2)

ሌቪ ጆርጅን በፍጥነት ወደ ሆስፒታሉ ድንገተኛ ክፍል አደረሰችው:: የማስታገሻ መርፌ ተሰጠውና ወዲያውኑ አንቀላፋ . . ስለ ሁኔታው ለመጠየቅ ወደ ሐኪሙ ሄደች . .

- ምን ሆኖ ነው?
- አይዞሽ አትስጊ . . እረፍት እንዲያገኝ የሚያስተኛ ማስታገሻ ሰጥቼዋለሁ:: በሽታውን ከአንድ ሰዓት በኋላ ከምርመራ ውጤቶቹ የምናውቅ ይሆናል . . (ፈገግ አለና) ፦ በጣም የተጨነቅሽለት ትመስያለሽ፣ባለቤቱ ወይስ ጓደኛው ነሽ?
- ወዳጁ ብቻ ነኝ::
- ለማንኛውም በአንድ ሰዓት ውስጥ የምርመራ ውጤቶቹ ይደርሳሉ፣ከዚያ በፊት የሚነቃ የሚስለኛል::

ሌቪ ከጆርጅ አልጋ አቅራቢያ ቁጭ ብላ ያንቀላፋ ፊቱን እያስተዋለች ግንባሩን በመደባበስ በጣቶቿ ጸጉሩን ታፍተለትላለች:: ልቧ በከፍተኛ ሁኔታ

www.path-2-happiness.com

በርሱ እንደተጠመደ ይሰማታል . . ከአፍታ በኋላ ጆርጅ ዓይኖቹን ሲከፍት የሌቪ እጅ ጸጉሩን እየደባበሰ ነበር . .

-ዬት ነኝ?

-በመንቃትህ ጌታ የተመሰገነ ይሁን፣ሆስፒታል ነው የምንገኘው፣አንተም ደህና ነህ::

-ሐኪሙ የታለ?

-በደቂቃዎች ውስጥ የምርመራ ውጤቱን ይዞ ይመጣል:: ጆርጅ እረፍት ውሰድ፣ ራስህን አታድክም::

ጆርጅ ፊቱንና ጸጉሩን እየደባበሰ ያለውን እጇን ያዝ አደረገና እጇን በእጁ በቀስታ ደባበሰ . .

-ሌቪ በጣም ነው የማመሰግንሽ፣እንዲህ አስቸግርሻለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር . .

-እንዲህ አትበል፣ጆርጅ አንተን ለመርዳት ነው እዚህ ያለሁት::

ለተወሰኑ ደቂቃዎች ምንም ሳይናገሩ በዝምታ ቆዩ:: ሐኪሙ ጆርጅን ለማየት እስከ መጣበት ጊዜ ድረስ የእይታና የዳበሳ ቋንቋ ግን ከአንደበት ቋንቋው ይበልጥ ጥልቅ ተሰሚነት ነበረው . .

-ጆርጅ ነቃህ? ፍቅረኛህ . . ይቅርታ ወዳጅህ በጣም ተጨንቃልህ ነበር::

-ዶክተር ምን ይሆን የነካኝ?

-የመጀመሪያው የምርመራ ውጤት ሀይለኛ የቫይረስ ኢንፌክሽን መኖሩን ነው የሚያሳየው:: ሌሎቹ የምርመራ ውጤቶች ነገ ነው የሚደርሱት::

-መቼ ነው መውጣት እምችለው?

-በሚገባ ማገገምህ ከተሰማህ ካንድ ሰዓት በኋላ ወይም ነገ፣እንዳፈለክ:: ስትወጣ ነርሷ መድኃኒቶችን ትሰጠሃለች:: በሉ እኔ ልሂድ . .

-ለጤንነትህ አስተማማኝ ስለሚሆን፣ ጆርጅ እባክህን እስከ ነገ ድረስ እዚህ ቆይ::

ጆርጅ የሌቪን እጅ ጠበቅ አድርጎ ይዞ በጉጉት ተመለከታት . .

-ሌቪ አመሰግናለሁ፣ወደ ሆቴሉ መሄድ እፈልጋለሁ፣ጉብኝቱን ባለ ማሟላቴ ይቅርታ . .

እጇን ጎትቶ ደረቱ ላይ አደረገ፣አነሳናም ሳመው . .

-ይቅርታ አድርጊልኝ::

ሌቪ ብዙ ተርበተበተች፤ውስጧ በደስታ ስሜት ብዙ ቢፈነድቅም በገጽታዋ የሚስተዋለው ግን የማፈር ስሜት ነው:: ፈገግ አለችለት . . ለመውጣት

እንዳይቸኩል ተማጸነችው:: ዛሬ ሰንበት ነው፣ ጸሐይ ገና አልጠለቀችም . .

-የምን ይቅርታ ነው የምትጠይቀው? አትጠይቅ፣ዋናው ነገር ያንተ በጥሩ ጤንነት ላይ መገኘት ነው::

ሌቪ የመውጫ ሂደቱን ጨርሳ የምርመራ ውጤቱንና መድኃኒቶቹንም ተቀብላ ለነገ ጧት አራት ሰዓት ቀጠሮ አስያዘችለት::

-እርሱም መምጣት ይኖርበታል? ወይስ እኔ መጥቼ የምርመራ ውጤቱን ልውሰድለት?

-ሕመሙ ከተመለሰበት አብራችሁ ኑ፣ደህና ከሆነ ግን አንቺ ብቻ መጥተሽ ቀሪዎቹን የምርመራ ውጤቶች መቀበል ትችያለሽ::

-እንግዲያውስ ነገ መጥቼ ውጤቱን እወስዳለሁ:: በአንቡላንስ መኪና ነው ወይስ በኔ መኪና ነው የሚወጣው?

-በራስሽ መኪና ውጡ፣በእግሩ ተራምዶ መሄድ ይችላል . . (ወደ ጆርጅ ዞር አለና) ፦ በል አሁን መሄድ ትችላልህ አለው::

-እንግዲያውስ ጠብቀኝ መኪናዋን ወደዚህ ላቅርብ::

ሌቪ ተመልሳ መጣችና እጁን ይዛ ወደ መኪናዋ አደረሰችና በሩን ከፈተችለት:: አጠገቡ ሆና ተመቻችቶ እንዲቀመጥ አደረገች . . ሰማያዊ ዓይኖቿን ተመለከተ፣ ሁለቱም በርህራሄና በውዴታ የተሞሉ ነበሩ . .

-ሌቪ አመሰግናለሁ፣እንዴት ብዬ እንደማመሰግንሽም አላውቅም . .

ከቁጥጥሩ ውጭ መስሎ በታየው እንቅስቃሴ ወደርሷ ዞሮ በአካሉ ቀረባትና አቅፎ በረዥሙ ሳማት:: ለመሸሽግ የሞከረችው ፈገግታ ፊቷን የሞላ ቢሆንም በከፍተኛ ሁኔታ ተርበተበተች . .

-ይቅርታ ዛሬ ቀኑ ሰንበት ነው፣የአምልኮ ብቻ ነው:: እኔን ማመስገን አያስፈልግህም:: የማደርገው ሁሉ ለሕሊናዬ ብዬ ነው::

-አዝናለሁ፣ችግር ውስጥ ከትቼሽ ይሆናል፤ምስጋናዬንና ላንቺ ያለኝን አክብሮት የሚገልጽበት መንገድ ስለጠፋኝ ነው የሳምኩሽ::

-አሁን ጊዜው አይደለም . . አሁን ዕረፍት ለመውሰድ ሞክር . . (ፈገግ አለችና) ፦ ካኽ ብዙ ጊዜ ስሞኝ ይቅርታ አልጠየቀም ነበር ! እንዴት እጠላው መሰለህ::

-ይቅርታ፣አንቺን ማስከፋት ፈልጌ አይደለም፤ይህን እንዴት እንዳደረግኩ አላቅውም:: ምናልባት በበሽታው ምክንያት የሞራል ድክመት አፍታ ውስጥ ሆኜ ይሆናል፣ወይ ደግሞ ሐቢብ እንዳለው ሁሉ ፦ የውብ መንፈስ አድናቆት ከውብ ገላ አድናቆት ጋር ተደበላልቆብኝ ሊሆን ችላል::

-ወይ ደግሞ ስንነጋገርበት የነበረው የመንፈስ ጥምረት ሊሆን ይችላል፤ለማንኛውም ይህን እርሳውና አሁን እንዴት ነህ?

-አንቺንና ራሴንም እያፈርኩ ነኝ፤በሥጋዊ ፍላጎቴ ፊት ድክመቴን አየሁ:: የልቤን ለመገግለጽ እንጂ እመኚኝ አንቺን ማስቀየም ፈልጌ አይደለም::

-እባክህን ይህን ርእስ ዝጋው:: ካኽ ሳመኝ ብቻ ሳይሆን ካንድ ጊዜ በላይ ደፍሮኝ ይቅርታ እንኳ አልጠየቀኝም ብየህ የለ? የባሰ ውርደቴ ደግሞ ከቆሻሻው ካኽ ጋር ወሲብ ስፈጽም አንዳንድ ጊዜ የደስታ ስሜት ይሰማኝ የነበረ መሆኑ ነው:: ይታይህ መርሆዬን እንድጥስ በመገደዴ እደሰት ነበር ማለት ነው:: ምናልባት ቤንያሚን እውነቱን ይሆናል ስጋዊ ፍላጎታችንን የምናረካው መንፈሳችንን በመበደል ነው::

-ምናልባትም መንፈሳችንና ሥጋችን የሚጣጣሙበትን፣መንፈሳችን አካላችንን አካላችን ደግሞ መንፈሳችንን የሚያረካበትን መንገድ ባለማግኘታችን ሊሆን ይችላል::

-ምናልባት የደስተኝነት ጎዳና ፍለጋ ፕሮጀክትህ ወደዚያ ሊያደርስህ ይችል ይሆናልና ከደረስክበት ለኔም መንገሩን እንዳትረሳ:: ባታደርገው ይቅርታ አላደርግልህም::

-መቼ ይሆን ይህን መንገድ የምጨርሰው? የሚየገኝኝ ሰው ሁሉ ውጤቱን እየተጠባበቀ ነው:: ሌቪ በሆነው ነገር ማዘኔንና ላንቺ ያለኝን አክብሮት ደጋግሜ እገልጽልሻለሁ::

-ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ሆቴሉ እንደርሳለን፤ዛሬ ክፍልህ ውስጥ የተሟላ ዕረፍት መውሰድ ይገባሃል:: የምሳ ሰዓቱን አሳልፈናል፣እራት ክፍልህ ድረስ እንዲመጣልህ አመቻችልሃለሁ:: ቁርስም ጧት እዚያው ይመጣልሃል . . እኔ የምርመራ ውጤቱን ለማምጣት ወደ ሆስፒታሉ ሄጄ ወዳንተ እመጣለሁ፤መቼ ነው የምትሳፈረው?

-አንደበቴን ለጎምሽኝ፣መቼም አመሰግናለሁ፣ጉዞዬ ማታ አስራ ሁለት ሰዓት ነው::

ወደ ሆቴሉ ደረሱ፣ሄዶ እስኪተኛ ድረስ ሌቪ አብራው ወደ ክፍሉ አመሩ . .

-ካንተ ጋር ብቀመጥ ደስ ይለኝ ነበር፣ከቆየሁ ወደ ውይይቱ ገብተህ እንዳይደክምህ ስለምፈራ እሄዳለሁ::

-ካንቺ ጋር ሀሳብ ስለዋወጥ የምሰማኝን እርካታ ልነግርሽ አልችልም፣ግና ብዙ አድክሜሻለሁና አንቺም ሄደሽ ማረፍ አለብሽ::

-አሁን የሰንበት ጸሐይ ጠልቃለች፣ለምን እንደሆነ የማላውቀውን ነገር መስራት እፈልጋለሁ፤ባሻህ መንገድ ልትተረጉመው ትችላለህ::

-አልገባኝም !

ሌቪ ወደ ጆርጅ ጠጋ ብላ አቅፋው በረዥሙ ሳመችው . . ጆርጅ ውሃ ያጠጧት የበረሃ ችግኝ ዓይነት የእርካታና የመንሰራራት ስሜት ተሰማው:: በጣም ቢደካክመውም እቅፉ ይበልጥ የተራዘመና የአካል ቅርርቡም የበለጠ ቢሆን ምኞቱ ነበር . .

-የኛ ሰንበት አሁን አብቅቷል፤ያደረኩትን ነገር ምንነት የመተርጎሙን ነገር ላንተ ትቻለሁ፤እኔ ግን ለምን እንዳደረኩት አላውቅም፣ደህና ሁን::

የሌቪ አድራጎት ለጆርጅ ዱብ እዳ ነበር:: እራሱ ቀደም ሲል ሲስማት ለምን እንዳደረገ እንዳላወቀ ሁሉ እርሷም ለምን እንዳደረገች ማወቅ አልቻለም . . ከፍላጎታችን ውጭ መንቀሳቀስ እንችላለን? ወይስ ምክንያቱ በሽታው ያስከተለበት የሞራል ድክመት ይሆን? ወይስ በመንፈስ ጥምረት ሊተረጎም የሚችል አድራጎት? ወይስ ወሲባዊ ፍላጎትና ኃጢያት ነው? ወይስ ሐቢብ እንዳለው መንፈስን ማድነቅ ሳይታሰብ ገላን ከማድነቅ ጋር ተቀላቅሎ ይሆን? . . ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ድርጊቱ የሰብአዊ ፍጡራንን ድክመት የሚገልጽ ነው . . ምናልባትም ኃጢአታችንን ለማስተሰረይ ኢየሱስ ለምን እንደሚያስፈልገን የሚገልጽ ሊሆንም ይችላል:: ከዚያ ሌቪን በማሰብ፣ከጎኑ በመሆን ያደረገችለትን ድጋፍና እንዴት እንደተጨነቀችለት በማሰላሰል አእምሮው ተጠመደ:: በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ስልኩ ጮኸ፣ካትሪና ነበረች . .

-የኔ ፍቅር ጤንነትህ አሁን እንዴት ነው?

-እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ፣ከሆስፒታል ወጥቻለሁ:: መታመሜን ማን ነገረሽ?

-መታመምህን? የምን መታመም? የማውቀው ነገር ቢኖር ቶም ትናንት በቤተክርስቲያን ስነ ሥርዓት ላይ በላክለት ኢ-ሜይል ትንሽ ድካም እንደሚሰማህ የገለጽክለት መሆኑን የነገረኝን ብቻ ነው::

-አሁንም በድጋሜ ቶም?

-የኔ ፍቅር አሁንም እየጠረጠርከኝ ነው ማለት ነው?

-ፈጽሞ፣አሁን ደህና ነኝ ነገ መምጣቴ ነው፣አይሮፕላኑ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ከዚህ ይነሳል::

-በአንቡላንስ መኪና እንጠብቀሃለን::

-ኣይ፣አስፈላጊ አይደለም::

www.path-2-happiness.com

-ግዴለም ለጤንነትህ ጥንቃቄ ሲባል አስፈላጊ ነው . . አላራዝምብህም፣አሁን በደንብ እረፍት ለማድረግ ሞክር፣ጌታ ይጠብቅህ።

-የኔ ፍቅር አንቺንም ጌታ ይጠብቅሽ።

ጆርጅ ሌቪ ከሳመችው በኋላ በቶም የተሳመችውንና ምን ያህል ተናደባት እንደ ነበረ ሊያስታውሳት ካትሪና የመደወሏ አጋጣሚ እያስደነቀው የስልክ ጥሪውን አበቃ። ምን ዓይነት አጋጣሚ ነው? እውን ሥጋዊ ደስታ ማለት የመንፈስና የመርህ ሞት ማለት ነው? ሁለቱን አንድ ላይ አጣጥሞ ማስኬድ አይቻልም? መጪዎቹ ቀናት ለመተንበይ የሚያስቸግሩ ሁነቶችን ያረገዙ ሳይሆኑ አይቀሩም።

በዚህ ጊዜ ውስጥ አስተናጋጁ እራት ይዞ ወደ ክፍሉ ደረሰ፣ፈገግ እያለ ለጆርጅ ሰላምታ አቅርቦ ገባ . .

-ሴትየዋ በጣም የምትወድህና የምትጨነቅልህ ትመስላለች። የምግቡን ጥራት ራሷ ነች ያረጋገጠችው፤መድኃኒትህን መውሰድ እንዳትረሳ እንድንነግርህ አሳስባናለች። ምግቡን ይዤ ወዳንተ ስመጣ ነው የሄደችው።

-መልካም፣ አመሰግናለሁ።

እራቱን ቶሎ ቶሎ በላ . . ያሳለፈውን ቀን እያጠነጠነ አልጋው ላይ ተንጋለለ። ኢ-ሜይሉን ለማየት ጉጉት ነበረው፣ግና ለነገ ማዘግየቱን መረጠ . .

(3)

ጆርጅ ከእንቅልፉ የነቃው ጧት ሦስት ሰዓት ላይ ቁርስ ይዞለት የመጣው አስተናጋጅ በሩን ሲያንኳኳ ነበር . .

-ይህ ከፍቅረኛህ የተሰጠን መመሪያ ነው፣ቁርስ ማዘጋጀታችንን ለማረጋገጥ ከግማሽ ሰዓት በፊት ደውላ ነበር። ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ላይም መድኃኒትህን እንድትወስድ ደውለን እንድናስታውስህ ለመጠየቅ ደውላ ነበር . . አንተ ዕድለኛ ሰው ነህ፣እንዲህ ያለችውን ማራኪ ቆንጆ ፍቅረኛ ማን ይታደላል?

ጆርጅ አመሰገነው፣ለጥያቄው መልስ ሳይሰጥ ‹‹ማራኪ ቆንጆ ፍቅረኛ›› የሚለውን መደጋገም ያዘ። ቁርሱን በላና ኢ-ሜይል ለማየትና የሚችለውን ያህል ምላሽ ለመስጠት ኮምፒውተሩን ከፈተ። ለቶምና ለአደም መልእክት ጻፈ፣መታመሙን ነግሮ ዛሬ ወደ ለንደን እንደሚመለስ አሳወቃቸው። ስለ መንፈስ ደስታ የሚያውቁት ነገር እንዳለ ጠይቋቸው መንፈስ ደሰታ አለው?

ወይስ ደስተኝነት ለገላና ለገላ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ የመንፈስ እጣው እርግማን ብቻ ይሆን? ሁለቱንም አንድ ላይ ደስተኞች ማድረግ እንችላለን? ወይስ የመንፈስ ደስታን ለማግኘት የግድ አካላችንና ገላችንን ማሰቃየት ይኖርብናል? የሚሉ ጥያቄዎችን ላከላቸው።

ሌቪ የምርመራ ውጤቱን ለመቀበል ወደ ሆስፒታሉ ሄደች። ጆርጅን ያጠቃው ቫይረስ በጣም አልፎ አልፎ ብቻ የሚያጋጥም፣አንጎልን የሚየጠቃ መሆኑም ለመጀመሪያ ጊዜ ገና መታወቁንና እንግዳ የሆነ ሁኔታ የገጠማቸው መሆኑን ሐኪሙ ነገራት። ለአንድ ሳምንት ወይም ለአስር ቀናት ጊዜ ወደ ሆስፒታሉ ተመልሶ እንዲተኛ ሐኪሙ ሀሳብ አቀረበላት። ቫይረሱ በማንኛውም ጊዜ ጥቃት መጀመር ስለሚችል፣የጆርጅ ሁኔታ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል መተንበይ አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም የሐኪም መኖርን ግዴታ የሚያደርግ ድንገተኛ ሁኔታዎች በጤንነቱ ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ። ይህን ስትሰማ ሌቪ አለቀሰች፣የምታድርገው ነገር ሲጠፋት ለሐቢብ ደውላ ወደ ሆስፒታሉ እንዲመጣ አደረገች። ራሷንና ሐቢብን ይህን ሁሉ ከጆርጅ ጋር ያጣበቃት ምን እንደሆነ ትጠይቅ ነበር። አብሯት ወሲብ መፈጸም እምቢ ካላት ወንድ ጋር የሚደረግ የሴትነት በቀል የፈጠረው የሥጋዊ ፍላጎት መጣበቅ ይሆን? ወይስ በአመለካከቱ በስነ ምግባሩና በዕውቀቱ ምክንያት የተፈጠረ መንፈሳዊ መጣበቅ ይሆን? ወይስ የደስተኝነት መንገድ ፍለጋን በተመለከተ ከሚጋሯቸው ተመሳሳይና ተደጋጋፊ እይታዎች የመነጨ ይሆን? እንዲህ እየተብሰለሰለችና ሐቢብም እያረጋጋትና እያጽናናት ተያይዘው ጆርጅ ዘንድ ወደ ሆቴሉ ሄዱ።

ጆርጅ የደረሱትን ኢ-ሜይሎች በማንበብ ላይ እንዳለ የክፍሉ ስልክ ጮኸ፤ሲያነሳ ሌቪ ነበረች ፦

-መልካም ፈቃድህ ከሆነ ወደ ክፍልህ እንምጣ?

-በደስታ፣ግቢ።

ሌቪ ሐዘን ባጠላበት ፈገግታ ገብታ ሰላምታ አቀረበችለትና ጨበጠችው . .

-እንግዳ አለኝ፣ይግባ?

-በመካከላችን መለያ አታድርጊ፣እንግዳሽ የኔም እንግዳ ነው፣እባክሽን አስገቢው።

ሐቢብ ገባ፣ጆርጅ ሞቅ ባለ ሰላምታ ተቀበለው፣ በመምጣቱም በጣም ደስ አለው . .

-የታመምከው በኔ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፣ሕመሙ የጀመረህ ከኔ

www.path-2-happiness.com

ጋር ሆነህ ነበር፣ሌቪ ከዚህ ነጻ ነች።

-ሌቪማ ከማንኛውም እንከን ንጹሕ ነች፣ከራሱ ከንጽሕናም በላይ ንጹሕ ነች።

-እኔ ፊት ይህ ሁሉ ማሽኮርመም ምንድነው?

-ኦህ፣ጠባቂ ዘበኛችን መሆንህን ረስቼ።

በማራኪና ሐፍረትን የተላበሰ ፈገግታ ጆርጅን እየተመለከተች . .

-አልገባኝም ሐቢብ ዘበኛችን ነው ስትል ከምን የሚጠብቅ ዘበኛ ነው?

-ዝም በይው . . ጆርጅ ሊያጣላን ፈልጎ ነው . . (ወደ ጆርጅ ፊቱን አዞረና) ፦ ለጤንነትህ አሁን እንዴት ነህ?

-እንደምታየሁ ጥሩ ሁኔታ ላይ ነኝ፣አሁን በጣም ተሽሎኛል . . ትናንት በጣም ደክሜ ሌቪም ከኔ ጋር ስትደክም ዋለች።

-ፈጽሞ አልደከምኩም፣ምን እንደማደርግም አላወኩም ነበር። እኔ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙኝ ሁሌም እርበተበታለሁ። እንዲያውም አንተን አስቸግሬህ እንዳልሆን እሰጋለሁ። ድካም እንደሚሰማህ በነገርከኝ ጊዜ ጉብኝቱን መሰረዝ ይገባን ነበር፣ምናልባት ምክንያቱ የኔ አለማስተዋል ሳይሆን አይቀርም።

-ፈጽሞ አልተሳሳትሽም፣ያጋጠመኝ ድንገተኛ ሁኔታ ነበር።

-ሐኪሙ ተመልሰህ ለሁለት ሦስት ቀን እነሱ ዘንድ እንድትቆይ ይፈልጋል፣ምን ታስባለህ?

-አይሮፕላኑ የሚነሳው አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ነው፣ማለትም ከሁለት ሰዓት በኋላ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ መንቀሳቀስ ይኖርብኛል፤ሁለት ሦስት ቀን ትይኛለሽ !

-ጆርጅ እባክህን ጤንነትህ አስተማማኝ መሆኑን እስክናረጋግጥ ሁለት ሦስት ቀናት ብቻ !

-አሁን ደህና ነኝ፣የመጨረሻው የሐኪም ውሳኔ እንዴት ሆነ?

-ሌቪ ስጭው፣ውጤቱ ጥሩ ነው፤ ሐኪሙ ግን የበለጠ እርግጠኛ መሆን ይገልጋል።

ጆርጅ የሕክምና ሪፖርቱን ዓይን ዓኗን እያየ ከሌቪ ተቀበለ፤አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለራሱ እንደሚያደርግና ለንደን እንደ ደረሰ ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ቃል ገባላት . .

-ጆርጅ ለንደን ሰትደርስ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል በመሄድ እንድንረጋጋ አድርገን።

-ባለቤቴ ካትሪና መታመሜን አውቃ አንቡላስ መኪና ይዛ አይሮፕላን ማረፊያ እጠብቃለሁ ብላለች፣እንዳታደርገው ብለምናትም እምቢ ብላለች፣ሌቪ እሷም እንዳንቺው ሀይለኛ ናት።

-ካትሪና በጣም ጥሩ ነው ያደረገችው። ሁለት ሰዓት ያህል ስላለን ምሳህን መብላት አለብህ፣ከዚያ ለመጓዝ እቃህን ታዘጋጃለህ።

-ምሳውን ከአንድ ሰዓት በኋላ አብረን እዚሁ ሆቴሉ ሬስቶራንት እንመገባለን፣ተጋብዛችኋልና እምቢ አትበሉ። ከምሳ በኋላ ለመታጠብና ሸንጣዎቼን ለማዘጋጀት ከሩብ ሰዓት በላይ አያስፈልገኝም።

-በሬስቶራንቱ ሳይሆን እንዳትደክም እዚህ አንተ ክፍል ውስጥ ከሆነ ተስማምተናል።

-ኣይ ሌቪ . . ትንሽ መንቀሳቀስ እፈልጋለሁ፣በሬስቶራንቱ ቢሆን ፈጽሞ አያስቸግረኝም።

ሐቢብ ስውሩን የፍቅር ምልልስ ሊያቋርጥባቸው እየሞከረ . .

-ቀሪ ጊዜያችንን ለመጠቀም ያህል የደስተኝነት መንገድ ፍለጋው ጉዳይ እንዴት ሆነ?

-ሐቢብ፣ይህ የደስተኝነት መንገድ ፍለጋ ሁለተኛው ጉዞዬ ነው። ከተለያዩ ሰዎች ጋር ካደረኳቸው ግንኙነቶች፣ ውይይቶችና ስብሰባዎች ሌላ ማለት ነው። ይህ ጉዳይ ረዥም ጊዜና ጥረት ጠይቆኛል፣ጥረቶቼ በድልና በስኬት እንደሚጠናቀቁ ነው ተስፋ የማደርገው።

-ሌቪ ፦ ያንተ ስኬት የሁላችንም ድልና ስኬት ነው። የምተትደርስበትን ውጤት በጉጉት እንጠባበቃለን።

-ሐቢብ ፦ የመጀመሪያ ጉዞህ ወዴት ነበር?

-ቅደም ተከተሉን ካትሪና እንዳስቀመጠቸው ላስቀምጥላችሁና ፦ መጀመሪያ ወደ ድንቃ ድንቆች አገር፣ከዚያ ወደ ፍጥጫዎች አገር፣ ቀጥሎም ወደ አብያተ ክርስቲያናት አገር ነው።

-የድንቃ ድንቅ አገር ሕንድ መሆኗንና የፍጥጫዎች አገር አንተ አሁን ያለህበት መሆኑን አወቅን፤የአብያተ ክርስቲያናት አገር ደግሞ የትኛው ነው?

-ሮምና ቫቲካን ነው። ቀጣዩ የጉዞዬ መዳረሻ ወደዚያ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

-ሐቢብ ፦ ቁድስ የሃይማኖቶች መገኛና ማጣቀሻ፣የእምነት ፍጥጫዎች ማስተናገጃ በመሆኗ ጠቃሚ ተደርጋ መታሰብ ትችላለች። ቫቲካንም

www.path-2-happiness.com

በተለያዩ የክርስትና ጎራዎች ዘንድ ከዋነኞቹ የክርስትና ስፍራዎች አንዷ ከመሆኗ አንጻር ለምን እንደምትጎበኝ መገመት ይቻላል:: የሚገርመው ሕንድ ለምንና እንዴት የመጀመሪያ ሆነች? የሚለው ነው::

-የመጀመሪያ ጥያቄዬ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ይሻላሉ ወይስ ሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች? የሚል ነበር:: ለዚያ ብዬ ነው ወደ ሕንድ የተጓዝኩት:: ቀጣዩ ጥያቄ ደግሞ . .

-ሌቪ ፦ በማቋረጤ ይቅርታ አድርግልኝና የመጀመሪያ ጥያቄ ‹‹ሃይማኖት ነው ወይስ ኤቲዝም ነው የሚሻለው?›› የሚል መሆን የነበረበት::

-ልክ ነሽ፣ይሁን እንጂ ፊትም ሆነ አሁን ኤቲዝም የማመካኛ ፍልስፍናን የሚያስከትል የስነ ልቦና በሽታ ነው የሚል እምነት አለኝ:: ኤቲስቶች በውስጣቸው የአምላክን መኖር ያምናሉ:: ከነሱ የበለጠ በመንፈስ ቀውስና በጭንቀት የሚጠቃ ፍጡር የለም::

ሐቢብ ሌቪን እያየ ፈገግ አለና . .

-ልክ ነህ፣ግና ይህ በገለልተኝነትና በሳይንሳዊ መንገድ መጠናት ይገባው ነበር::

-አጥንቻለሁ፣በእውነት መርምሬያለሁ ! ግና ያንን በአካል ለማየት ወዴት መሳፈር ነበረብህ ብለህ ታስባለህ?

-እህህ፣በማንኛውም ኤቲስት የአእምሮ ጓዳ ውስጥ ተጓዝ፣የምትናገረው እርግጠኛ መሆኑን ትረዳለህ ! ! እነሱ ራሳቸው እንዴት ችለው እንደሚሸከሙት እኔ እንጃ ! !

-ሌቪ ፦ ለዚህ ነው ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ በጭንቀት የሚጠቁና ራሳቸውን የሚያጠፉ የሆኑት::

-ፍቀጂልኝና ልቀጥል፣ሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች አፈተረትና ማጭበርበር መሆናቸውን አረጋግጠን ካበቃን በኋላ ሁለተኛው ጥያቄ፣ ከመለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥ የሚሻለው የትኛው ነው? የሚል ነበር:: ወደ ቅድስት አገር የተደረገው ጉብኝት አይሁዳዊነትን በቅርበትና በጥልቀት ለመመርመር ነበር . . (ወደ ሌቪ ዞር ብሎ) ፦ ጉብኝቱ ባንቺ ባልዳረባነት በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነኝ::

-እናም ከትናንት ወዲያ ክርስትናንና የተለያዩ ጎራዎቹን፣የርስ በርስ ጦርነቶቹንም አስመልክተን ያደረግናቸው ውይቶች ከሦስተኛው ጉዞ የቀደመ ችኮላ ነበር ማለት ነዋ? !

-አዎ፣ይሁን እንጂ ተገቢ የሆነ ችኮላ ነው:: ወደ ቫቲካን የሚደረገው ጉዞ ክርስትናን በተለይም ካቶሊክን በይበልጥ ከቅርበት ለማወቅ ነው::

-የእስላም ሃይማኖትን ማወቅ ብቻ ነው የሚቀርህ::

-(ሌቪ ፊቷ ላይ የመከፋት ስሜት በግልጽ እየተስተዋለ) ፦ የአረመኔዎቹን ሃይማኖት፣እንግዲያውስ ወደ መካ ሂድና እወቀው፤ግና ያሻህን ብታደርግ አያስገቡህም::

-አህ፣አትቆጭ ተረጋጊ፣እውነቱን ለመናገር ቁድስ ውስጥ ከሙስሊሞች ጋር ለመገናኘት ተስፋ አድርጌ ነበር:: እዚህ አብዛኞቹ ነዋሪዎች ሙስሊሞች መሆናቸውን አንዘንጋ፤ይሁንና ጉብኝቱ አጭር በመሆኑና በመታመሜም ምክንያት አልተሳካልኝም:: በአጠቃላይ ግን ወደ ሙስሊሞች አገር መሄድ ላያስፈልገኝ ይችላል::

ሐቢብ የሌቪን ዓይኖች ትኩር ብሎ አየ . .

-ሙስሊም ያልሆነን ሰው ወደ መካ እንዳይገባ ማድረጉ አይሁዶች ሙስሊሞችን፣ወይም አይሁድ ሴቶችን ወደ ማልቀሻ ግንብ እንዳይገቡ በማገድ እንደሚጥሉት ክልከላ ዓይነት ነው:: ወይም ወጣት ሙስሊሞች ዓርብ ቀን በአልአቅሳ መስጊድ ተገኝተው እንዳይሰግዱ በአይሁዶች እንደሚከለከሉት ነው . .

-ጆርጅ ፦ ነገሩን ቀለል አድርገው፤ቀድሞውኑም አንተ የካቶሊክ ጭንብል ያጠለቅህ ሙስሊም ነህ ብየሃለሁ !

-ሌቪ ፦ እህህ፣እርሱ ሁሌም እንደዚህ ነው፤ዶክተር ዛሬ የራስህ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ግለሰብ አንተን ተጻርሮ ለኔ ወግኗል::

-በኔ ላይ የጆርጅን እገዛ አትጠይቂ፣እሱ ዛሬ መሳፈሩ ነው፣እኔና አንቺ ግን ክርክራችን የሚቀጠል ይሆናል:: ይሁንና አንተ ጆርጅ አይሁዳዊነትንና ክርስትናን እንደመረመርክ ሁሉ እስላምንም ማጥናትና መመርመር ፍትሐዊነትና ሚዘናዊነት ነው:: ኤቲዝምን እንኳ እንድትመረምረው ጠይቄህ የለ? እናንተ ዘንድ ኤቲዝም ከእስላም የተሻለ ነው ማለት ነው?

-እህህ፣ምናልባት::

-ጊዜው ሄዷል፣እኛ ቀድመን ሄደን እንጠብቅህ? ወይስ ከኛ ጋር ትወጣለህ?

-ስለሚደክመው ሲወጣ ሊናግዘው ይገባል::

-ሌቪ አመሰግናለሁ፣እናንተ ቀድማችሁ ሂዱ፤መጸዳጃ ቤት ገብቼ እወጣና ቶሎ እደርስባችኋለሁ::

ሌቪና ሐቢብ ወደ ሬስቶራንቱ አብረው ሄዱ፤አመቺ የሆነ ጠረጴዛ መርጠው ጆርጅን ለመጠበቅ ተቀመጡ:: በዚህ ጊዜ ሐቢብ ለሌቪ እንዲህ

www.path-2-happiness.com

አላት . .

-ለርሱ ያለሽ አድናቆት ከሚገባው በላይ እንዳይሆን ስጋት አለኝ::

-ለምን?

-ጣልቃ በመግባቴ ይቅርታ፤ግና የምትለዋወጡት እይታ ጥርጣሬን የሚጭር፣አነጋገራችሁም ልክ የፍቀረኞች አነጋገር ዓይነት ነው::

-እዚህ ደረጃ ላይ ለምን እንደ ደረስን አላውቅም ! እንደ ነገርኩህ ሁሉ ከመጀመሪያው አንስቶ ወሲባዊ ግንኙትን እምቢ ብሎ ባለቤቱን እንደሚወዳትና ይህን ማድረግ ክህደት መሆኑን ነበር የነገረኝ::

-የመንፈስና የስነ ምግባር አድናቆት ከጾታዊ ሥጋዊ ስሜታዊ ፍላጎት አድናቆት ጋር አይምታታብሽ ብየሻለሁ::

-ትናንት እጅግ አስደናቂ የሆነ ነገር ተከስቶ ነበር:: በሕመሙ ምክንያት ተዝለፍልፎ ሲወድቅ ደግፌ ካነሳሁት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከንፈሬን ሳመኝ፤ወደ ክፍሉ ደርሰን አልጋው ላይ ሳስተኛው ደግሞ እኔም መልሼ ሳምኩት::

-በጣም ያሳዝናል፣መሳሳም በሁለታችሁም ባህሎች ውስጥ በጣም የተለመደ ተራ ጉዳይ ነው:: መርሆዎቻችሁን መጣስ ግን ተራ ጉዳይ መሆን የለበትም::

-ለሆነው ነገር ይህ ነው የምለው ትንተና የለኝም:: አንተ እንደምትለው ሊሆን ይችላል፣ወይም ሰብአዊ ድክመት ይመስለኛል::

በዚህ ጊዜ ጆርጅ መጣና ከነሱ ጋር በመቀላቀል አብሯቸው ተቀመጠ . .

-የሬስቶራንቱ ምግብ ክፍት ቡፌ ነውና መልካም ፈቃዳችሁ ከሆነ ተነስተን ምግባችንን እንውሰድ::

እንደገና በጠረጴዛው ዙሪያ ከተቀመጡ በኋላ . . ሐቢብ ውይይቱ እንዲቀጥል ለጆርጅና ለሌቪ ሀሳብ አቀረበ . . ሦስቱ አንድ ላይ የተገናኙበት መልካም አጋጣሚ ነበር . .

-ካቆምንበት እንቀጥላለን፤እኔ እስላምን ለማወቅና ለማጥናት ወደ አንድ ሙስሊም አገር መጓዝ እንዳለብህ ነው የሚታየኝ::

-ብዙ ጊዜ ከርሱ ጋር የማልስማማ ቢሆንም ለእስላም እንደ ሞገተ ሁሉ ለኤቲዝም በመሞገቱ አሁን እኔም ሀሳቡን ተቀብያለሁ::

-እህህ፣ለኤቲዝም ሆነ ለእስላም አልተሟገትኩም፣ የተናገርኩት ወደ እውነት ለመድረስ መከተል ስላለበት ሳይንሳዊ የምርምርና የጥናት ዘዴ ነው::

-ያደረኳቸው ጉዞዎች ሁሉ አሁን የምናደርገውን በመሳሰሉ በርከታ ረዣዥም ውይይቶችና ክርክሮች የታጀቡ፣በብዙ ንባቦች የተደገፉ፣ስመለስም ጥልቅ እሳቤና ምክክሮችን ያስተናገዱ ነበሩ:: በአሁኑ ዙር ግን ጉዞው በጣም የተሳካና የበለጸገ በመሆኑ የመረጃው መጠንና ብዛት ለማስተንተን ካለኝ ጊዜ አንጻር እጅግ የበዛ ነው:: ከተመለስኩ በኋላ ለማስተንተን ተስፋ አደርጋለሁ::

ሌቪ የጆርጅን ዓይኖች በስስት እየተመለከተች . .

-አፋጣጭ እንደማይሆን ተስፋ እያደረኩ አንድ ጥያቄ መጠየቅ ይፈቀድልኛል?

-ጠይቂ::

-አይሁዳዊነት፣ካቶሊካዊነት፣ኦርቶዶክስ ወይም ሌላው ቀርቶ እስላም የምታስሰው የደስተኝነት መንገድ መሆኑን ካረጋገጥክ በቀጥታ እምነቱን ተቀብለህ ተከታዩ ትሆናለህ? ወይስ ትርፍና ኪሳራን ማስላት ትጀምራለህ?

-የደስተኝነትን መንገድ ካወቅሁ የተጣራው ትርፍ ያ በመሆኑ ሁሉም የትርፍና ኪሳራ ስሌት ያከትማል የሚል እምነት አለኝ:: ከዚህ መንገድ ይበልጥ ደስታን የሚሰጥና ይበልጥ ትርፋማ የሆነ ምን ይኖራል? . . ዋናው ነገር መንገዱን ላግኘው::

ሐቢብ ወደ ጅርጅ እያየ በቁርጠኝነት መንፈስ . .

-ታገኘዋለህ፣በእርግጠኝነት ታገኘዋለህ፤ይሁን እንጂ ባልከው ነገር ላይ ጥርጣሬ አለኝ . .

-ምኑን ነው የምትጠራጠረው?

-ያን ማድረግ እንዲሁ በቀላሉ የሚሆን መሆኑን:: የትርፍና ኪሳራ ስሌት የማይኖር ስለ መሆኑ እጠራጠራለሁ:: አንዳንድ ውሳኔዎች ሁሌም ለመወሰን በጣም አስቸጋሪ ይሆናሉ . . ! !

-እንዴት?

-ሀሳቤን ግልጽ ላደርግልህ፣የስኳር ሕመም ያለባቸው ሰዎች ሁሉ ስኳር መውሰድ ጎጂ መሆኑን ያውቁታል ግን ይወስዳሉ:: ትርፍ ክብደት ያለው ሰው ሁሉ አንዳንድ የአመጋገብ ልማዶች ጎጂ መሆናቸው ያውቃል ግን ምግቡን መብላት አያቋርጥም::

-ይህን ካልኩት ጋር ምን ያገናኘዋል?

-ሃይማኖትን መለወጥ የአመጋገብ ልማድን ከመለወጥ ይበልጥ አስቸጋሪ መሆኑ ጥርጥር የለውም:: ሃይማኖትን መለወጥ የሕወትን ትርጉምና

www.path-2-happiness.com

መንስኤውንና አንቀሳቃሽ ሞተሩን የመለወጥ ያህል ነው። (ወደ ሌቪ ዞረና) ፦ ሌቪ ይህን በሚገባ ትረዳለች ብዬ አምናለሁ። ለማንኛውም በእርግጠኝነት መንገዱን ታገኛለህ።

- እንዴት እንዲህ እርግጠኛ መሆን ቻልክ? ታድያ ሁለታችሁም መንገዱን እየፈለጋችሁት ስትሆኑ እስካሁን እንዴት አላገኛችሁም?
- አንተ ይህን ያህል ጽናትና ቁርጠኝነት ሰንቀህ እየፈለከውን ልታጣው አትችልም። በተጨማሪም የፈጣሪ አምላክ ቸርነት ወደ እውነት ለመድረስ የሚጥረውን ሰው አያግዝም ብሎ ማሰብ የማይቻል ነው።
- አንድ ወቅት ላይ አግኝቸው አሁን አንተ ያልከውን ያለኝን ደስተኛ ሽማግሌ እንዳስታውስ አደረከኝ።
- ሽማግሌው ምን አለ?
- በምናገረው ትገረሙ ይሆናል፤ራሴን ለመግደል እየሄድኩ ነበር፣የደስተኝነት መንፈስ ፊቱ ላይ በግልጽ ይነበብ የነበረውን ሽማግሌ መንገድ ላይ አገኘሁትና ደስተኛ ነህ? ብዬ ጠየኩት። አዎ አለኝ፤ደስተኛ መሆን የምችለው እንዴት እንደ ሆነ ጠየኩት። ለማንኛውም ‹‹የደስተኝነት መንገድ›› የሚለውን ብሂል የሰማሁት ከርሱ ነበር።
- መልሱ ምን ነበር?
- ቀጥተኛ መልስ አልሰጠኝም፣ጽናትና ቁርጠኝነት ካለህ ትደርስበታለህ ነበር ያለኝ።
- ከዚያ በኋላ ከርሱ ጋር ግንኙነት አልቀጠልክም?
- አዝናለሁ፣ቁጥሩ ወይም አድራሻውን . . አልወሰድኩም ነበር። ቁጥሬንና አድራሻዬን የወሰደው እርሱ ነው ግን አልደወለልኝም።
- ይቅርታ ጆርጅ ጊዜው እየሄደብህ ነው፣ምሳውን ቶሎ በልተህ ሸንጣዎችህን ማዘጋጀት ይኖርብሃል።
- አልዘገይም . . በሩብ ሰዓት ውስጥ ከናንተ ጋር እሆናለሁ . . ወደ ክፍሉ ሄደ።
- የጆርጅ ድፍረትና ነገሮችን አቅልሎ በጥልቀት የማየት ብቃቱ በጣም ያስደንቀኛል።
- እኔም እንደዚሁ እደነቃለሁ።

- እኔን በተመለከተ እኔ ወንድ ነኝና እንዳሻኝ አደንቃለሁ፣አንቺ ግን ራስሽን ያዝ አድርጊ።
- እናንተ ዐረቦች በወንድና በሴት መካከል ልዩነት ታደርጋላችሁ !
- ዐረቦች ወይስ አይሁዶች? በዚህ ጉዳይ ላይ ክርክራችንን የቋጨን ይመስለኛል፤ይሁንና መካድ የማትችያቸው አንዳንድ ልዩነቶች መኖራቸው የግድ ነው
- ምን የመሳሰሉ?
- እህህ፣እኔ እንዳንቺ ቆንጆ አለመሆኔን፣አንቺ ወንድ እኔ ሴት አለመሆኔን . . የመሳሰሉ። የነገሮችን ተፈጥሮ መለወጥ ትፈልጊያለሽ? የፈለግነውን ብናደርግ መብላት ከመጠጣት የተለየ ነገር መሆኑ ይቀጥላል። ሁለቱም የየራሳቸው የሆነ የተለየ ሚና ይጫወታሉ። አንቺ ውብ ተከራካሪ ኮረዳ እንደሆንሽ ትቀጥያለሽ፣እኔም ወንድ ተከራካሪ ሆኜ እቀጥላለሁ። ሴቶችን እንደ ውሾች፣ቆሻሻዎች ወይም እርኩሶች . . አድርጎ ማቅረብ ግን ተከታዮቹን ከሚያከብር ግለሰብ ወይም ሃይማኖት ሊሰማ የማይገባ እኩይ ነገር ነው።
- ማለት የፈለከውን በሚገባ እረዳለሁ፣ማንጓጠቱጡን ግን ተወት አድርገው።
- ይቅርታ፣ዋናው ነገር አድናቆትሽ ለገላው ሳይሆን ለአመለካከቱ፣ለጽናቱ፣ለመንፈሱና ለመልካም ስነ ምግባሩ ብቻ ሊሆን ይገባል። ለርሱም አስቀድሜ እንዲህ ብየዋለሁ፤የሁለታችሁ ጠባቂ ዘበኛነቴ ትርጉምም ይህ ነው።
- አሃ . . የዘበኛ ትርጉም ገና አሁን ገባኝ . . እንግዲያውስ እጠነቀቃለሁ፣ትናንት የሆነው ይበቃል።

ጆርጅ ቶሎ ተመልሶ ከሆቴል የመውጫ ሂደቱን አጠናቀቀና እየጠበቁት ወዳሉት ሐቢብና ሌቪ መጣ . .

- ጊዘው እየተጣደፈ መሰለኝ . . እንነሳ እንዴ?
- አዎ፣የትራፊክ መጨናነቅ ወይ ፍተሻ ኬላዎች እንዳይኖሩ ፍርሃት አለኝ።
- ጌታ ይጠብቅህ፣ይቅርታ አድርግልኝ ሌቪ ታደርሰሃለች፣ እኔ ቀጠሮ አለኝ። የደስተኝነት መንገድ ፍለጋው ከምን እንደደረሰ ለኛ ማሳወቁን ግን አደራ እንዳትረሳ።
- የዘበኝነት ሥራህን ከጫፍ አታደርሰውም?
- እህህ፣አላደርስም የሚጠብቃችሁ እግዚአብሔር ነው፤ከመርሁ ይበልጥ

www.path-2-happiness.com

የሰውን ልጅ የሚጠብቅ ምንም ዘበኛ የለም።

-ሻንጣዎቹን ለመጫን መኪናውን ወደ ሆቴሉ በር ላስጠጋ።

-ጆርጅ አርክተህናልና አመሰግናለሁ፤ስላንተ ለመስማትም እጓጓለሁ፤ጌታ ይጠብቅህ። ለንደን እንደደረስክ በአቅራቢያህ ወደሚገኝ ሆስፒታል መሄዱን እንዳተረሳ፣ሌቪ ዘንድ ያለውን መርፌ መውሰድም እንዳትዘነጋ።

-የምን መርፌ ነው?

-አይሮፕላን ውስጥ ሕመሙ ቢቀሰቀስብህ እንድትወስደው ሐኪሙ የሰጠን መርፌ ነው።

-ሁለታችሁንም አመሰግናለሁ።

(4)

ጆርጅ ሲወጣ ሌቪ መኪና ውስጥ እየጠበቀችው ነበር። ሻንጣዎቹን ጭናለች፤ ወደ መኪናው ገባና ወደ አይሮፕላን ማረፊያው ጉዞ ቀጠሉ . .

-ጆርጅ ስትለየን በጣም ቅር ይለናል፤ጥቂት ቀናት ብቻ ነው ከኛ ጋር የቆየኸው፤ሆኖም ግን የማይረሳ ጉልህ አሻራ ትተህልናል።

-የሚፍለቀለቅ ፈገግታሽ፣ዕውቀትሽና አስተሳሰብሽን ናቸው እንጂ የማይረሱት። ካንቺ በብዙ ነገር ተጠቅሜያለሁ፣ብዙም አስቸግሬሻለሁ፣እናም ምስጋናዬ ይድረስሽ።

የሌቪ ዓይኖች እንባ አቀረሩ . .

-ክርክሮችህንና ውይይቶችህን . . እይታህንም አጣለሁ፤ወደኖርኩበት የጭቆና አዙሪትም መመለሴ ነው።

-እንደ ቤንያሚን ላለ ሰው ይህ እንባ ተገቢ አይደለም።

-ችግሩ ቤንያሚን ወይም ሁሉም አይሁዶች ሳይሆኑ እውስጤ ያለው እውነታ ነው። የደስተኝነትን መንገድ አላውቅም፤ካንተ ጋር ስንወያይ የበዛ ደስተኝነት ይሰማኝ ነበር።

-የጋራ ውይይቶቻችን ይቀጥላሉ፤ከሐቢብ ጋር የሚኖርሽ ውይይትም ይቀጥላል . . አንቺ እውነት አለሽ ! እኔ በደስተኝነት ፍለጋ መንገድ መጓዝ ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ቀደም ሲል ተለይቶኝ የማያውቀው ጭንቀት ኀብኝቶኝ አያውቅም።

-ይህን በደስተኝነት መንገድ ፍለጋህ የምትደርስበትን ውጤት እንደምታስታውቀኝ የሰጠኸኝ ቃል ኪዳን አድርጌ ነው የምቆጥረው። እኔና

ሐቢብም የምንደርስበትን ውጤት እናሳውቀሃለን።

-ቃል ኪዳን ነው . . ግን ከግዴታ ጋር ነው።

-ግዴታው ምንድነው?

-እንባሽን አብሰሽ ፈገግ ማለት ነው፣በፈገግታ የበራ ፊትሽን ማየት ደስ ይለኛል።

-ተስማምተናል፤ትናንት ስለናበትህ ለሆነው ነገር ይቅርታ አድርግልኝ፤እመነኝ ለምን እንዳደረኩት አላውቅም።

-በሚገባ እረዳሻለሁ፣እኔም እንዳንቺው ሁሉ ከማልቀሻው ግንብ ለቀን ስንወጣ ያንኑ ዓይነት ለምን እንደ ፈጸምኩ አላውቅም . . እህህ፣ምናልባት በማልቀሻው ግንብ አጠገብ ማልቀስ ባለ መቻሌ ሊሆን ይችላል።

-ለምን አላለቀስክም?

-ለምን አላቅሳለሁ? የሚችሉትን ሁሉ አድርገው ስለመኖሩ እስካሁን አንድ ማስረጃ ማግኘት ላልቻሉት ቤተመቅደስ ውድመት አለቅሳለሁ !

-ስለ ሃይማኖቴ ስትናገር ቀይ መስመር እያለፍክ መሆንህ አይሰማህም?

-እህህ፣አዝናለሁ፣የተናገርኩትን ለማካካስ የፕሮቴስታንትን ቀይ መስመር ረግጬ አልፋለሁ፤በአውሮፓ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ካቶሊኮችን የገደሉ ወንጀለኞች ናቸው . . የኔ እመቤት ደስ ብሎሽ ይቅር አልሽኝ?

-የኔ ጌታ ይቅር ብየሃለሁ . . ግን ከግዴታ ጋር ነው።

-ወደኔ መለስሽው፣ግዴታው ምን ይሆን?

-ነገ በኢ-ሜይል ቢሆን እንኳ ስለ ጤንነትህ ሁኔታ እንዳናስብ ታስታውቀናለህ።

-ተስማምተናል።

-እነሆ ደረስን፤ይህ በመጀመሪያው የእስራኤል ጠቅላይ ሚንስትር ስም የተሰየመ የቤንጎሪዮን አይሮፕላን ማረፊያ ነው። ለመረጃ ያህል ይህ አይሮፕላን ማረፊያ በመካከለኛው ምስራቅ ከሁሉም የተሸለ በመሆን የተሸለመ ነው።

ጆርጅ የጉዞ ሂደቶችን ጨርሶ ወደ ውስጥ በር ለማለፍ ሲፈልግ ስትጠብቀው የነበረችው ሌቪ መርፌውን ልትሰጠው እጇን ዘረጋች። አይሮፕላን ውስጥ ድንገተኛ ትኩሳት ወይም ድካም ከተሰማህ እንድትወስደው ከሐኪሙ የተሰጠ መርፌ ነው፣ለንደን እስክትደርስ እፎይታ ይሰጠሃል፣አለችው።

-አመሰግናለሁ ::

የሌቪ ዓይኖች እንባ አቀረሩ፣ጆርጅን ለመጨበጥ እጇን ዘረጋችና ፦ ከኛ ጋር ላሳለፍካት እያንዳንዷ ደቂቃ ከልብ አመሰግነሃለሁ፣አለችው:: ጆርጅም ጨብጧት ሌላኛውን እጁን በእጇ ላይ ሲያደርግ ለዓመታት ከሚያውቅ ወዳጅ የሚለይ ሰው ዓይነት ስሜት ተሰማው፣ይሁን እንጂ ማድረግ ካሰኘው ነገር ራሱን ያዝ ሲያደርግ እሷም በተመሳሳይ ሁኔታ ራሷን ገታ አደረገች . .

-ደህና ሁኚ፣ኢየሱስ ይተጠብቅሽ ::

-ደህና ሁን፣ጌታ አምላክ ይጠብቅህ::

ከጆርጅ በመለየቷ ልቧ እያነባ ወደ ኋላ ዞር አለች::

በሕይወትና በሞት መካከል . .

www.path-2-happiness.com

9 በሕይወትና በሞት መካከል . .



በሕይወትና በሞት መካከል . .

(1)

ጆርጅ ልቡ በሌቪ ሀሳብ እንተወጠረ ወደ አይሮፕላኑ ገባ፡፡ ቆይታው ከአራት ቀናት ያላለፈ ቢሆንም ልቡን መቆጣጠር ችላለች . . ለመሆኑ ምስጢሩ ምን ይሆን?! ጨካኝና ግፈኛ በሆነ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚኖር የተቀደሰ ንጹሕ መልአክ ሆና ነበር ለርሱ የታየችው፡፡ ሴቶችንና አይሁዳዊነት ውስጥ የሚፈጸምባቸውን አስከፊ ጭቆና አስመልክቶ ከሌቪ ጋር ያደረገውን ውይይት በምሬት አስታወሰ፡፡ ሴት ልጅ እንደ እቃ እንዲትወረስ የሚያደርግ ሃይማኖት ምን የሚሉት ነው ! የሕብረተሰቡን ግማሽ አካል እንደ ቆሻሻ፣እንደ ውሻና እንደ እርኩስ ነገር የሚመለከት፣የመውረስ መብት የሚነፍጋትና መብት አልባ ፍጡር የሚያደርጋት ሃይማኖት ! . . ስለ ብሉይ ኪዳን መዛባትና ተአማኒነት ማጣት ያደረጉት ውይይት፣ለአባቷ ገዳይ ሙስሊሞች ያላት የከረረ ጥላቻ፣‹‹የሴሉን ልጆች›› ስለሚገድለው፣ስለሚዘርፈውና ስለሚሰርቃቸው ምርጡ ኤሁዳዊ ሕዝብ ያነሱት ሁሉ ትዝ አለው፡፡ በአካባቢው ላይ ለአይሁዶች ባለመብትነት ማስረጃ ይሆናሉ የተባሉትንና ግን የሌሉ ቅርሶችን በሚመለከት የተለዋወጡት ሀሳብ . . ታወሰው፡፡ ሌቪ ከአይሁዳዊ ውስብስብነት ወደ ካቶሊካዊ ውስብስብነት እንደማትሸጋገር የተናገረችው ትዝ ብሎት ፈገግ አለ፡፡ ከትውስታው ዓለም ባኖ የተመለሰው ከጎኑ የተቀመጠው ተሳፋሪ ሲያቋርጠው ነበር ፦

- ወዳጄ በእጅህ የያዝከው መርፌ ምንድነው?
- ድንገተኛ ትኩሳት ሊያጋጥመኝ ስለሚችል አይሮፕላን ውስጥ በእጄ እንድይዘው በጥብቅ አሳስቦኝ ሐኪም ነው የሰጠኝ ነው፡፡
- እንዳየው ትፈቅድልኛለህ?
- እንካ፣ሐኪም ነህ?

መርፌውን ተቀብሎ አየው፣አብሮት ያለውን የአጠቃቀም መምሪያ ወረቀት አነበበ፡፡

- እኔ ፋርማሲስት ነኝ፣ይህ መርፌ ላንት እጅግ አስፈላጊ ሳይሆን

www.path-2-happiness.com

አይቀርም፣አልፎ አልፎ ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውል መድኃኒት ነው።

-ሐኪሙ አልነገረኝም፣ለምን ሕመም ነው የሚየገለግለው?

-አላውቀውም፣ይህ መርፌ ግን መጥፋት የማይችሉ ቫይረሶችን ለማስታገስ እጅግ በጣም አጣዳፊ ለሆኑ ድንገተኛ ሁኔታዎች ነው የሚታዘዘው።

- ወዳጆቼ ለኔ በመጨነቅ ያደረጉት እንጂ እኔ እንኳ አሁን ጥሩ ሁኔታ ላይ ነኝ።

-ሊሆን ችላል፣ግን አይመስለኝም፣ይህ መርፌ በልዩ የሐኪም ትእዛዝና በድንገተኛ ሁኔታዎች ብቻ እንጂ የማታዘዝና የማይሸጥ ነው።

-ሊሆን ይችላል፤አላውቅም፤እኔ ግን በጥሩ የጤንነት ሁኔታ ላይ ነኝ።

-በእርግጥ ጤንነት ከታመሙ ሰዎች በስተቀር ሌሎች የማያዩትና ጤነኞች ብቻ በራሳቸው ላይ የደፉት ዘውድ ነው። ረብሸህ እንደሆን ይቅርታ።

- ፈጽሞ . . አመሰግናለሁ።

ጆርጅ ዳግም ለትውስታዎቹ እጁን ሰጠ . . ልቡ አሁንም ለሌቪ እየተጨነቀ ነው። ዐረብ ቢሆንም አብሮት በመሆን ብዙ ያስደሰተውንና የተመቸውን ሐቢብን በአድናቆት ሲያስታውስ ደስ አለው። ሙስሊሞችን አስመልክቶ ከርሱ ጋር ባደረገው ውይይት ለሐቢብ ‹‹አንተ የካቶሊክ ጭንብል ያጠለቅህ ሙስሊም ነህ›› ማለቱን አስታወሰ . . ይህ ጉዞ ለርሱ በሁነቶች የተሞላ እጅግ በጣም አስደሳች ጉዞ ነበር . . አስተናጋጇ አቋረጠችው ፦

- ይቅርታ፣ምን መመገብ ይመርጣሉ? ሥጋ ወይስ ዶሮ?

- ሥጋ።

አጠገቡ ያለው መንገደኛ ወደሱ ዞረና ፦

- አእምሮህ ሙሉ በሙሉ በሀሳብ የተወጠረ ትመስላለህ !

- ኦህ . . አዎ፣ያሁኑ ጉዞዬ ግሩም ድንቅና በመረጃዎች የበለጸገ ነበር።

-ኢየሩሳሌም ምን ያህል ቆየህ?

-ለአራት ቀናት።

-ብቻ !

-አዎ፣ግን ብዙ ወራት የቆየሁ ያህል ነው። ያገኘኋቸውን ድንቅ ሰዎች መቼም ቢሆን አልረሳቸውም።በዚች ቅድስት አገር ውስጥ ከነሱ ብዙ ብዙ ነገሮችን ተምሬያለሁ።

-አይሁዳዊ ነህ?

-አይደለሁም . . ለምን?

-እኔ አይሁዳዊ ነኝ . . ይቅርታ አድርግልኝና አገሩ ለነሱ የተዘጋጀ

በመሆኑ በተለምዶ ኢሩሳሌም ውስጥ እርካታ የሚያገኙት አይሁዶች ብቻ ናቸው። ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ግን ያሉበት ሁኔታ የሚያስደስት አይደለም።ስላገኘሃቸው ሰዎች ደስታህንና አድናቆትህን ስትገልጽ አይሁዳዊ መሰልከኝ? !

-ኢየሩሳሌም ውስጥ ኤሁዶችንና ክርስቲያኖችንም አግኝቻለሁ፣ሁሉም ድንቅ ሰዎች ናቸው።

-ምናልባት ይህ አባባል እንግሊዝ አገር ቢነገር አግባብነት ይኖረዋል፣ቴልአቪብ ውስጥ ግን የሰዎች አንቀሳቃሽ ሞተር ሃይማኖት ነው።

-አንተ አይሁዳዊ ነህና አንድ ጥያቄ እንዳቀርብልህ ትፈቅድልኛለህ?

-ጠይቅ።

-የኦሪት ትምህርቶች ላንተ አሳማኝ ናቸው?

-አይደሉም፣ኦሪትን መረዳት የሚቻለው በቴልሙድ ትምህርቶች አማካይነት ብቻ ነው።

-መልካም፣የቴልሙድ ትምህርቶችስ ላንተ አሳማኝ ናቸው?

-እህህ፣አሁንም አይደሉም፣ግና በዚህ መልካቸው ነው ወደኛ የደረሱት።

- ይቅርታ፣በውስጥህ ያለው ይህ ግጭት አያስጨንቅህም?

-ማንንም ቢሆን ያስጨንቃል፤ዳሩ ግን ሰዎች በሚያስጨንቃቸው ነገር ላይ የሚኖራቸው አያያዝ ይለያያል።

-እንዴት?

-እኔ ከዚህ ውስጣዊ ግጭት የምሸሸው ራሴን በሥራዬ በመጥመድ ነው። ከዚህ ግጭት በመጠጥ ወይም በወሲብ ውስጥ ራሳቸውን የሚደብቁ ሰዎችም ይኖራሉ። በነዚህ ጉዳዮች ላይ ሳይንሳዊ ምርምር በማድረግ የሚሸሹና ይበልጥ ሃይማኖተኛ በመሆን የሚሸሹ ሰዎችም ይገኛሉ።

-በጣም ጥሩ፣ከራስህ ጋር በጣም ግልጽ ሰው ትመስላለህ።

-አመሰግናለሁ።

-ይሁንና ‹‹ሽሽት መታደልን ያስገኛል? ወይስ አያስገኝም?›› የሚለው ጥያቄ ይቀራል።

-ያለ ሃይማኖት የሚኖር ሰው የስነ ልቦና ሕመምተኛ ነው በሚለው ላይ ሁሉም አስተዋዮች የሚስማሙ ይመስለኛል። በመሆኑም ሽሽቱ ከኤቲዝም በሽታና ከጽልመቱ፣ በሃይማኖት ውስጥ ካለው ተቃርኖም ለመራቅ የሚደረግ ሽሽት ነው።

-በነዚህ ጉዳዮች ላይ በሚደረግ ሳይንሳዊ ትናት ውስጥ ከሚደበቀው ሰው

www.path-2-happiness.com

በስተቀር፣በዚህ እንስማማለን?

- አዎ፤ግና ለሀሳብ፣ለጭንቀትና ለአእምሮ መዋዠቅ የሚዳርግ በመሆኑ አልወደውም::
- ከሽሽት በስተቀር ሌላ መፍትሔ የለም የምትል ትመስላለህ::
- አዎ፣አይደለምም::
- እህእህ፣እንዴት?
- አዎ የምለው ከሽሽት በስተቀር ሌላ መፍትሔ ስለማላውቅ ነው:: አይደለም የምለው ደግሞ ፈጣሪ አምላክ እንዲሁ ለብኩንነት፣ለውስጣዊ ግጭትና ለሽሽት አሳልፎ ሰጥቶ ሊተወን የማይችል በመሆኑ ነው::
- ፋርማሲስት ሳትሆን ፈላስፋ ትመስላለህ::
- ድካሜ ሁሉ እውነታን ለመፈለግ የማደርገው ምርምር ነው:: ሳይንሳዊው ስልት ከምናገረው ጋር ይቃረናል፤ከፋርማሲ የተማርኩት በሳይንሳዊ መንገድ እንጂ እንዳልናገር ነው::
- ለእውነታ የሚደረገው ፍለጋ ወይም እኔ በምወደው ስያሜ ‹‹የመታደል መንገድ›› ተድላና ደስታን ያጎናጽፋል እንጂ ለእርግማን አይዳርግም::
- ‹‹የመታደል መንገድ›› ጥሩ አገላለጽ ነው::
- ይቅርታ ላቋርጥህና አይሮፕላኑ እየበረደ ነው? ኃይለኛ ብርድ እየተሰማኝ ነው::

ፋርማሲስቱ ትኩሳቱን ለማየት እጁን ጆርጅ ግንባር ላይ አደረገ፣ሙቀቱ ከፍ ብሏል . .

- የያዝከው መርፌ የተሰጠህ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም፣አሁን እንዴት ነህ?
- ቅዝቃዜው እየጨመረ ነው፣ድካም ይሰማኛል፤አታስብ ከአፍታ በኋላ ይሻለኛል:: የመታደል መንገድ ትኩረትህን ስቧል?
- ስለ መታደል መንገድ ተውና መርፌውንና የሕክምና መግለጫ ወረቀትህን ልትሰጠኝ ትችላለህ?
- ይኸው እንካ::

ፋርማሲስቱ አይሮፕላኑ ላይ ሐኪም ይኖር እንደሆነ አስተናጋጇን ጠየቃት፣አለመኖሩን ነግራ መኖር ነበረበት በመዘግየቱ አልደረሰም፣ አለችው . .

- ግዴለም፣መርፌውን እኔው ራሴ እሰጠዋለሁ፤ፋርማሲስት ከመሆኔም ጋር የከፍተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ ስልጠና ወስጃለሁ:: ይሁንና ራሱን ይስታል፣የሚነቃውም ከደረስን በኋላ ስለሚሆን የአንቡላንስ

መኪና አይሮፕላን ጣቢያ እንዲጠብቀን አድርጉ::

- ነገሩ አሳሳቢ ይመስላል፣ባለቤቴ በአንቡላንስ መኪና እየጠበቀችኝ ስለሆነ መኪናው አስፈላጊ አይደለም፣አንተም ትንሽ ያጋነንክ መሰለኝ::
- አላጋነንኩም፣ግና በነገሮች አያያዝ ላይ ሳይንሳዊ ስልቶችን ረግጬ ማለፍ አልሻም::

(2)

ጆርጅ ራሱን ከሳተበት ተመልሶ ሲነቃ ለንደን በሚገኝ ሆስፒታል ውስጥ ራሱን አገኘ:: ካትሪናንም ፈገግ ብላ አጠገቡ አያት . .

- የኔ ፍቅር በሰላም በመምጣትህ ጌታ የተመሰገነ ይሁን::
- አሁን የት ነኝ? ፋርማሲስቱስ የት ነው?
- አንተ ለንደን ሆስፒታል ውስጥ ነህ፣ፋርማሲስቱ ደግሞ ማን ይሆን? !
- ሆስፒታል ውስጥ ነኝ? ! አይሮፕላኑ ውስጥ ከጎኔ የነበረው መንገደኛ የትነው ያለው?
- ኦ ገባኝ፣በአንቡላንስ መኪና ውስጥ አንተን አስረክቦኝ ያለህበትን ሁኔታ ካረጋገጠ በኋላ አድራሻህን ወስዶ ነው የሄደው:: ደህና በመሆንህ ጌታ የተመሰገነ ይሁን::
- ኣህ . . የኔ ፍቅር አንቺ እንዴት ነሽ? በጣም ነው የናፈቅሽኝ፣ስለ አለፋሁሽና ስለ ረበሽኩሽ ይቅርታ አድርጊልኝ:: ነገሮች ወደዚህ ደረጃ ይደርሳሉ ብዬ አልገመትኩም ነበር::
- ሐኪሙ የቀድሞ የሕክምና ወረቀቶችህን አንብቦ የደም ናሙና ወስዷል:: ኤክስሬይም አስነስተው የምርመራ ውጤቱን ነገ እናየዋለን ብለዋል::
- መቼ ነው ወደ ቤት የምንሄደው?
- አላወኩም፣የምርመራ ውጤቱ ከታየ በኋላ መሆን ያለበትን እንወስናለን ነው ያለኝ:: ለማንኛውም እምደሚገምቱት ከአንድ ሳምንት ላላነሰ ጊዜ እዚህ ትቆያለህ::
- ሳምንት? !
- ዋናው ነገር ቆይታህ ሳምንት መሆኑ ሳይሆን፣ጤንነትህ አስተማማኝ መሆኑንና እዚያ ሆፒታል እንድትቆይ ባለመደረጉ መገረማቸውን መናገራቸው ነው::
- ሆስፒታሉ እንኳ እንዳልወታጣ ለማድረግ ጠይቆኝ ብዙ ሞክሯል፣እኔ ነኝ አሻፈረኝ ያልኳቸው . . ሌላ ምን አለ?

-የሥራ ፈቃድ ወስጄ ካንተ ጋር እሆናለሁ፣ካንተ ጋር መቀመጥ ስለናፈቀኝ አብረን ለመሆን ይህ መልካም አጋጣሚ ሳይሆን አይቀርም::

-እኔም በጣም ናፍቄሻለሁ:: የምፈልገው ግን ካንቺ ጋር ወደ ቤት መሄድ ነው::

-የኔ ፍቅር አትጨነቅ በቅርቡ ትወጣለህ . . የትንሣኤ ቤተክርስቲያንን ጎብኝተሃል?

-አዎ . . ለመጎብኘት ቃል ገብቼልሽ የለ? የማርያምን ቤተክርስቲያንም ጎብኝቻለሁ::

-በነዚህ ቅዱሳን ቤተክርስቲያኖች ጸሎት ያደረሰ ሰው ምነኛ ታደለ ! የትንሣኤ ቤተክርስቲያንን መጎብኘት የዕድሜ ልክ ምኞቴ ነው::

-ቃል በገባሁልሽ መሰረት ገብቼ ስላንቺ ጸሎት አድርሻለሁ፣ግና ምኑ ላይ ነው ደስታው?

-ለኔ ወደ እግዚአብሔር አምልኮ ከመቀላቀልህ የሚበልጥ ደስታ የለም::

-አምልኮዎቻቸውና በዓሎቻቸው የሀዘንና የለቅሶ ከመሆናቸውም ጋር ሃይማኖተኛ አይሁዶችም እንዲህ ይላሉ::

- ልክ ነህ፣እነሱ እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በተሻረና በኢየሱስ መገለጽ ሕልውናው ባበቃ ሃይማኖት ነው:: ይህም ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን ተዋግተውታል፣ገድለውታልም፣ተከታዮቹንም አሰቃይተዋል::

-ለመሆኑ ክርስቲያኖች ኦሪትን በብሉይ ኪዳንነቱ ያምኑበታል?

-አዎ ያምናሉ::

-ታዲያ በኢየሱስ መገለጽ ያበቃለት ሃይማኖት ነው የምትይው እንዴት ነው?

-ለአይሁዳዊነት በጥብቅ የወገንክ ትመስላለህ፣እንደ ሃይማኖት አብቅቷል፣ልንመራባቸው ዘንድ የኦሪት ትምህርቶች ግን ቀሪ ናቸው::

-እንዴት አድርገሽ ነው በተዛባና ተአማኒነት በጎደለው ትምህርቱ የምታምኚውና የምትመሪበት?

-የተዛባና ተአማኒነት የጎደለው ! ማነው እንዲህ ያለህ?

-ብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ የሴሎ ሴት ልጆች የሚከተለው ጥቅስ ሰፍሯል ፦ ‹‹የብንያምንም ልጆች እንዲህ ብለው አዘዙአቸው ፦ ሂዱ በወይኑም ስፍራ ተደበቁ፣ተመልከቱም፣እነሆም፣የሴሎ ሴቶች ልጆች አታሞ ይዘው ለዘፈን ሲወጡ ከወይኑ ስፍራ ውጡ፣ከሴሎም ሴቶች ልጆች ለየራሳችሁ ሚስት ንጠቁ፣ወደ ብንያም ምድርም ሂዱ::›› የሴሎ ሴት ልጆች እነማን

እንደሆኑ ታቂያለሽ? እንዲህ ያለው ነገርስ ከእግዚአብሔር የተላለፈ ነው ብለሽ ታምኚያለሽ?

-የሴሎ ሴት ልጆች እነማን እንደሆኑ በሚገባ አውቃለሁ፣በዚህ ላይ መናገር ግን አልፈልግም:: ይህንና የመሳሰለውን ለኛ ማብራራት ያለባቸው ቀሳውስትና ሊቃነ ጳጳሳቱ ናቸው::

- በተጨማሪም ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚከተለውን እናገኛለን ፦ ‹‹የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦ የእናንተ ሰው ሁሉ ሰይፉን በወገቡ ላይ ይታጠቅ፣በሰፈሩም ውስጥ በዚህና በዚያ ከበር እስከ በር ተመላለሱ፣የእናንተም ሰው ሁሉ ወንድሙን ወዳጁንም ጎረቤቱንም ይግደል አላቸው::›› እንዲህ ዓይነቱ ጭካኔ እንዴት ሆኖ ከእግዚአብሔር የተላለፈ ሊሆን ይችላል?

-መልካም ፈቃድህ ሆኖ አርእስቱን እንድትለውጥ እፈልጋለሁ:: እነዚህንና ሌሎች ብዙ መሰል ጥቅሶችን አውቃቸዋለሁ፣ይሁን እንጂ በነሱ ላይ ክርክር መክፈት አልሻም:: ደሞም አሁን እረፍት እንድታደርግ ነው የምፈልገው::

-ለምን?

-በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ መከራከር አልፈልግም ብየሃለሁ . . በሆስፒታል ቆይታህ ለጥናትና ለንባብ ጥሩ ጊዜ ያለህ ይመስለኛል::

-ልክ ነሽ:: ዋናው ነገር ላፕቶፔ ከኔ ጋር መሆኑ ነው:: ስለ ክርስትና እና ስለ ጎራዎቹ ማንበብ ስለምፈልግ አንዳንድ መጽሐፎችን መግዛትም ያስፈልገኛል::

-በጣም ጥሩ፣ምናልባት ወደ ካቶሊክነት ትለወጥ ይሆናል::

-ምናልባት ሊሆን ይችላል::

-ያሁኑ ንባብህ ለጉዞአችን መልካም ቅድመ ዝግጅት ሊሆን ይችላል፣ውዴ ረሳህ እንዴ?

-አልረሳሁም፣በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሆን ነገ ከሐኪሙ ጋር እነጋገርበታለሁ:: ቆይታዬን ራሴን በንባብ ለማጥመድ እንደ መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም እሞክራለሁ::

-ቆይታህ ሊያስጨንቅህ አይገባም:: እኔ ካንተ ጋር እዚሁ ስለምሆን አብረን በመሆንና በመወያየት አስደሳች ጊዜ እናደርገዋለን::

-ካትሪና በጣም አፈቅሪሻለሁ::

-እኔም እንደዚሁ ነኝ:: አሁን ሄጄ ነገ እንድመለስ ትፈቅድልኛለህ?

www.path-2-happiness.com

ከትናንትተት ጀምሮ አዚህ ነኝ፣አሁንም እየመሸ ነው።

- አዝናለሁ፣ከኔ ጋር ለፋሽ፤የኔ ፍቅር ነገ እጠብቅሻለሁ። ዋናው ነገር አንዳንድ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ኮምፒውተሬና ስልኬ ከአጠገቤ እንዲሆኑ እፈልጋለሁ።
- ኮምፒውተርህንና ስልክህን በአቅራቢያህ ባለው ጠረጴዛ ላይ አደርጋለሁ፣ግና ራስህን ካላማድከም ግዴታ ጋር ነው።የኔ ፍቅር እረፍት እንድትወስድ ነው ፍላጎቴ፤ለማንኛውም እስከ ነገ ደህና ሁንልኝ።

ጊዜው ገና በመሆኑ ጆርጅ መተኛት አልፈለገም። ትንሽ ለማንበብ ወስኖ ኢ-ሜይሉን ሲከፍት ስለ ጤንነቱ ሁኔታ እንዲያሳውቃት የሚመማጸነውን የሌቪ መልእክት አነበበ። የደረሰውን ሁሉ ነግሯት ለመርፌው፣ለተደረገለት አቀባበልና ላደረገችለት ሁሉ ልባዊ ምስጋናውን በመግለጽ መልስ ላከለላት። ቃሉን ያልዘነጋ መሆኑን፣ሆኖም ኮምፒውተሩንና ስልኩን የተቀበለው ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ብቻ መሆኑንም ጻፈላት። የመታደልን መንገድ ፍለጋ በተመለከተ የደረሰበትን ለማሳወቅ የገባላቸው ቃል እንደ ተጠበቀ መሆኑን አረጋግጦ ለሐቢብም ምስጋናውን እንድታደርስለት ጠየቃት።

ሌላ መልእክት ከአደም የደረሰው ሲሆን መንፈስን ለጉዳት በመዳረግ ሥጋዊ ደስታን ስለማግኘት ጽፎለት ለነበረው የላከለት መልስ ነበር ፦

‹‹መንፈስና ገላ አብረው ደስተኛ መሆን ካልቻሉ የአካል ደስታ ብለህ የሰየምከው የገላና የመንፈስም እርግማን ነው። ሕይወትን ደስተኝነት የሌለበት መርገምት አድርጎ የሚወስደው ይህ ፍልስፍና ጽልመታዊ ፍልስፍና ነው። ለመሆኑ ለእርግማን ነው? ወይስ ለደስታ ነው የተፈጠርነው?! ለእርግማን ነው የተፈጠርነው የሚለው አመለካከት ለሁሉም ነገር አምላክን ማማረር ለሚቃጣው የኤቲስቶች አመለካከት የቀረበ ነው። ወይም የአምላክን ባህርይ፣የሰውን ልጅ ተፈጥሮና የሃይማኖትን ባህሪ ከመረዳት ለራቁ ምድራዊ ጣዖታዊ ሃይማኖቶች የቀረበ ነው። አልያም በመበረዛቸውና መዛባታቸው ምክንያት በጣኦታዊነት ተጽእኖ ስር ወደ ወደቁ ሃይማኖቶች የተጠጋ ነው። በአጠቃላይ አነጋገር ይህ አመለካከት ከሳይንሳዊ፣ፍልስፍናዊ ወይም ሃይማኖታዊ . . አመለካከትነት ይልቅ የባለቤቱን ውስጣዊ ቅራኔና ግጭት የሚያመለክት ነው። አሁን ተመልሰህ መጥተሃል ብዬ ስለምገምት እረፍት ከወሰድክ በኋላ ተገናኝተን መወያየት እንችላለን።››

- ጆርጅ ደብዳቤውን በድጋሜ ካነበበው በኋላ ከራሱ ጋር ማውራት ጀመረ ፦ ይኸ አደም ትልቅ ፈላስፋ ነው? ፕሮቴስታንት ነው? ወይስ ይሁዲ?

ዕድሜው ገና ወጣት ከመሆኑና የተሰማራበት ሥራ ተራ ከመሆኑ ጋር በአነጋገሩ ውስጥ ነገሮችን ሳወሳስቡ አቅልሎ ማየትና ጥልቅነት አንድ ላይ የተጣመረበት ነገር ለምን እንደሚታየኝ አላውቅም። አደም እውነቱን ነው፣መንፈስም ሆነ አካል ለብቻቸው መታደል አይችሉም፣የሰው ልጅ ወጥና የተሟላ አንድ አሃድ ነውና። ይህን ወጥ አንድ አሃድ መከፋፈል ጥልቅነት ያላቸውን ጉዳዮች ተራ አድርጎ የማየት ያህል ነው። የአካል ጊዜያዊ ደስታ የመንፈስና የገላን በሽታ ያስከትላል። እንደ ቡድሂስቶች ዓይነት በምናኔና ከዓለማዊ ደስታ በመራቅ የሚገኘው ማንኛውም የመንፈስ ደስታም የስነ ምግባር እነጻ ወይም የመንፈስ ምጥቀት ተብሎ ቢጠራ እንኳ፣ የመንፈስና የገላን በሽታ ያስከትላል። የመታደል መንገድ መንፈስና ሥጋ የሚጣመሩበት፣አካልና አእምሮ የሚቀላቀሉበት፣ተድላና ደስታን እንጂ እርግማንና ብኩንነትን በማያስከትል ሁኔታ ሁለቱ የሚዋሐዱበት ጥምረት ነው። አንዳንድ ሃይማኖቶች ገላን በማሰቃየት የመንፈስ ተድላና ምጥቀት ለማግኘት በሚል ከአካላዊ ደስታ ብዙ ይርቃሉ። ሌሎቹ ደግሞ በተገላቢጦሽ ለአካላዊ ደስታ ብቻ ብለው ከመንፈሳዊ ደስታ ብዙ ይርቃሉ። ሁለቱም ግን አካላዊ ደስታንም ሆነ መንፈሳዊ ደስታን ሳያገኙ፣ለነፍስም ሆነ ለሥጋ መታደልን ሳያመጡ በከንቱ ይቀራሉ።

ጆርጅ ሰዓቱን ሲመለከት ሁለት ሰዓት ሆኗል፤ለአደም ደወለ።

- ሃሎ አደም፣ለንደን ገብቻለሁ፣ግን ሆስፒታል ነኝ፤ስለዚህ ላገኝህ አልችልምና ፍልስፍናህንና ውይይታችንን ለመቀጠል ልትጎበኘኝ ትችላለህ?
- ይማርህ . . እጎበኝሃለሁ። በውይይቶቼም ሆነ አንተ እንደምትለው በፍልስፍናዬ ላስቸግርህ ግን አልፈልግም።
- እንደዚያ ማለቴ አይደለም፣እውነቱን ለመናገር ያንተ ውይይትና ፍልስፍናህ የተለየ ደስታ ይሰጠኛል፤በተሳሳተ መንገድ ተረድተህኝ እንደማይሆን ተስፋ አድርጋለሁ።
- እኔም በአነጋገርህ ቅር ተሰኝቻለሁ ማለቴ አይደለም። ነገሩ በጣም ቀላል ነው፣እኔ ማቅለልን ነው የምወደው። ነገ ምሽት ልጎበኝህ እሞክራለሁ።
- አደም እጠብቀሃለሁ፣ውይይቶችህን ናፍቄያለሁ።
- እህህ፣ነገ እንገናኝ። የውይይት ናፍቆትን ከማሰናዳልህ ቡና ናፍቆት ጋር እየቀላቀልክ እንዳትሆን፣ደህና ሁን።

ጆርጅ ወደ አደም እንዲህ የሚስበው ምስጢር ምን እደሆነ እያሰበ ስልኩን ዘጋ . . ከገጽታውና ከተክለሰውነቱ እንግሊዛዊ አለመሆኑ ግልጽ ነው።

ግሪካዊ ወይም ጣሊያናዊ ሊሆን ይችላል :: አልያም ከላቲን አሜሪካ ሊሆን ይችላል::ለማንኛውም ግን ትልቅ ምቾትና ደስታ የሚሰጠው ሰው ነው:: ሌቪ ከአደም ጋር ብትገናኝ ኖሮ እንዴት ታየው ይሆን? እህህ፣ አደም ሰማያዊ ዓይኖቿንና ወርቃማ ጸጉሯን እያየ መታገስ ይችል ይሆን? ወይስ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ እንደኔም ጭምር ወርቃማ ምክሮቹ ባዶ ቃላት ይሆኑና ሌላው ካኽ ይሆን ነበር? ለማንኛውም ነገ ይመጣና ያሳለፍኩትን ሁሉ እተርክለታለሁ . .

(3)

ነርሷ ቁርሱን ጠረጴዛው ላይ ስታድርግለት ጆርጅን በማለዳ ቀሰቀሰችው . .

- ሐኪሙ መቼ ነው የሚመጣው?
- ጧት ሦስት ሰዓት ላይ በክፍሉ የሚገኙ ታካሚዎችን ሁሉ ያያል:: ዋናው ነገር ትኩሳት ከተሰማህ በፍጥነት ንገረን፣የወሰድከው መርፌ ውጤት ከሚያበቃበት ከሁለት ሰዓት ጀምሮ በየሰዓቱ ሙቀትህን እንለካለን::
- አመሰግናለሁ፣የትኩሳቱ ጉዳይ አደገኛና አዙሪቱም ቀጣይ ይመስላል::
- ዋናው ነገር የገላህ ሙቀት ከፍ ካለ ወይም ብርድ ከተሰማህ በፍጥነት እንድትነግረን ይሁን::
- እሺ፣መልካም::

ጆርጅ ቁርሱን ከበላ በኋላ ነርሷ የተናገረችውን ነገር ቁጭ ብሎ አሰላሰለ:: ሌቪ መርፌውን በእጁ ይዞ እንዲገባ ለማድረግ ያደረገችበትን ግፊት አስታወሰ . . ሐኪሙ ሦስት ተኩል ላይ ወደ ክፍሉ ሲደርስ ምን ይዞ ይመጣ ይሆን የሚል ስጋትና ጭንቀት ተሰማው . . ::

- ዶክተር መልካም ፈቃድህ ሆኖ የጤንነቴን ሁኔታ በግልጽ ልታስታውቀኝ ትችላል?
- የኛ የምርመራ ውጤት ኢየሩሳሌም ከተሰጠህ የምርመራ ውጤት የተለየ አይደለም::
- ይቅርታ፣እዚያ የተሰጠውን ውጤት አላውቅም፣ምን ያሳያል?
- ያለ ምንም ቀዳሚ ምልክት በድንገት ወደ አንጎል ሕዋሳት የደረሰ እንግዳ የሆነ ቫይረስ በከፍተኛ ሁኔታ የትኩሳት ደረጃህን ከፍ እያደረገ ነው:: ምንም ችግር ሳይኖርብህ በተለመደው ሁኔታ ላይ የምትገኝ ብትሆንም ሆስፒታል ውስጥ እንድትቆይ ለማድረግ የምንገደደው በዚህ ምክንያት

ነው:: የሰውነትህ ትኩሳት በድንገት ከፍ ሲል ከአንድ እስከ ሁለት ቀን እየሰራ የሚቆይ የሙቀት መቀነሻና የማስታገሻ መርፌ ልንሰጥህ እንገደዳለን::

- እስከ መቼ ነው ሆስፒታል የምቆየው?
- አሁን ማወቅ አልችልም:: ለማንኛውም ገና የምንጠብቃቸው የምርመራ ውጤቶች በመጪዎቹ ሁለት ቀናት ውስጥ ይደርሳሉ:: አዲስ ነገር ካልተከሰተ ቆይታህ በጣም ቢበዛ ከሁለት ሳምንት በላይ አይሆንም::
- የዚህ ቫይረስ መነሻ ምክንያት ምንድነው?
- እስካሁን የታወቀ ነገር የለም፤ይሁንና ማንኛውንም ነገር ስለምናሚላልህና በየጊዜው መረጃዎችን ስለምንሰጥህ የሚያሳስብህ ነገር አይኖርም:: ስለ ሕመምህ እስካሁን የምናውቀው ነገር ይኸው ብቻ ነው::
- ለመልካም አቀራረብህ በጣም አመሰግናለሁ::

ሐኪሙ ተሰናብቶት ሄደ . . ጆርጅ ለረዥሙ የሆስፒታል ቆይታ እቅድ ለማውጣት ኮምፒውተሩን ከፈተ:: የመታደልን መንገድ ፍለጋ ላይ እንደመሆኑ ስለራሱ ሃይማኖት ይበልጥ ለማወቅ አብላጫውን ጊዜ ለንባብ ለማዋል ወሰነ:: ‹‹ሃይማኖቴን ልወቅ ! ክርስትናን እና ጎራዎቹን ልወቃቸው ›› ብሎ በማጉረምረም በራሱ ላይ አፌዘ:: ቀሪውን ጊዜ ደግሞ የክርስትና ምሁር ከሆነችው ካትሪና፣እንደዚሁም ከአደምና ከቶም ጋር ለመወያየት፣ከተቻለም ከሌቪና ከሐቢብም ጋር የኤሌክትሮኒክስ ውይይት ለማካሄድ እቅድ ነደፈ:: ከዚያም በኦርቶዶክስ፣በካቶሊክና በፕሮቴስታንት እምነቶች ላይ ንጽጽራዊ ንባብ በማድረግ ላይ ይሰማራል:: እነዚህ ሦስቱ ዋነኞቹና ታዋቂዎቹ የክርስትና ጎራዎች ሲሆኑ፣ሁሉንም የክርስትና ጎራዎች አንድ በአንድ ለማጥናት ቢፈልግ እድሜ ልኩን ማዳረስ አይችልም::

ከእኩለ ቀን በኋላ ካትሪና ማይክልና ሳሊን ይዛ መጣች:: ናፍቋቸው ስለነበር በመምጣታቸው በጣም ተደሰተ . . ከጎኑ አስቀምጧቸው ሲያጫውታቸው፣ሲያስቃቸውና ሲያስቁት ደስታው ወደር አልነበረውም . . መንፈስና አካልን አንድ ላይ የሚያረኩ መደሰቻዎች ታወሱት . . ከልጆቹ ጋር ጊዜውን ሲያሳልፍ ይህን ጥምር ደስታ እንደሚያገኝ ተገነዘበና አካልና መንፈስን አንድ ላይ ደስተኛ የሚያደርጉትን ነገሮች ሁሉ ምነው ባወቅሁ ሲል ተመኘ:: ይህን ማድረግ መቻል የግድ ወደ የመታደል መንገድ መድረስ ማለት መሆኑ ተሰማው . .

ለሁለቱ ሕጻናት በአእምሮው የሚጉላላውን ጥያቄ አቀረበላቸው . .

www.path-2-happiness.com

-ማይክል በሕይወትህ ከሁሉም በላይ የሚያስደስትህ ነገር ምንድነው?

-ባባ ካንተ ጋር መጫወት ነው፣እግር ኳስንም እወዳለሁ::

-ሳሊ አንቺስ?

-እኔም ባባ ካንተ ጋር መጫወት እወዳለሁ፤በአሻንጉሊት መጫወትም ያስደስተኛል::

-እኔም ከናንተ ጋር መጫወት ያስደስተኛል፣ግና ከጨዋታ በስተቀር የሚያስደስታችሁ ሌላ ነገር አለ?

ማይክል በመገረም ፦

-አንዳንድ ጊዜ ደስታ ይሰማኛል፣ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይከፋኛል፣ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም:: ባባ ለምን ይሆን?

-ማይክል፣ ምክንያቱ ላንተ ምን ይመስለሃል?

-የመደሰቴ ምክንያት ምናልባት ባልደረባዬን ወይም ጓደኛዬን በማገዜ ሊሆን ይችላል:: መከፋቴ ደግሞ በፈጸምኩት መጥፎ ተግባር ምክንያት ሊሆን ይችላል::

በዚህ ድንቅ ቤተሰባዊ ውይይት ካትሪና በሰፊው ፈገግ ብላ ፦ የኔ ቆንጆ ልባችን በደስታ የሚሞላው ሰዎችን ሁሉ ስንወድና መልካሙን ሁሉ ስንመኝላቸው ሊሆንም ይችላል፣አለች::

-ምንም ነገር ባንሠራም እንኳ ለሰዎች መልካሙን መመኘት ብቻ ማለትሽ ነው ማማ?

-አዎ፣በተቃራኒውም ምንም ነገር ባናደርጋቸውም እንኳ ሰዎችን መጥላትና ለነሱ ክፉ መመኘት እኩይ ነገር ነው::

ጆርጅ ውይይቱን ይበልጥ ማጎልበት ወደደና ፦ ታዲያ አንተ ማይክል፣አንቺም ሳሊ፣ይህ ከሆነ ዘንዳ ሰዎች ለምንድነው ራሳቸውን ደስተኞች የማያደርጉት? ለምን መከፋትን ይመርጣሉ?

-ማይክል ፦ ሞኞች ስለሆኑ ነው::

-ሳሊ ፦ ወይም ስለማያውቁ ነው::

-ካትሪና ፦ የኔ ውዶች፣ ወይም በሁለቱም ምክንያት ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪም ወደ መልካም ነገር መመራትና ለሰናይ ተግባርና ለደስታ መታደል የእግዚአብሔር ጸጋ ነው::

-ጆርጅ ፦ ስለዚህ የመታደልን መንገድ ገልጎ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ይሆናል::

-ማይክል ፦ የመታደልን መንገድ ለመፈለግ ወደ ኢሩሳሌም እጓዛለሁ ብለህ

ለናቴ ስትናገር ሰምቻለሁ፤የመታደል መንገድ የሚገኘው ኢየሩሳሌም ብቻ ነው?

-እህህ፣ የኔ ልጅ አይደለም፣እኔ እውነትን ለማግኘት በፍለጋ ላይ ነኝ:: በአጋጣሚ ኮንትራት ለመፈራረም ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዝኩ፤እዚያ ከሰዎች ስማርና ጠቃሚ ዕውቀት ስገበይ ነበር::

-ሳሊ በሕጻን የዋህነት ፦

-የኢየሩሳሌም ነዋሪዎችን አልወዳቸውም::

ጆርጅ በአግራሞት ፦

-ለምን?

-የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ቤተሰቦቿ ወደ እስራኤል እየሩሳሌም እንደሚሄዱና እስራኤል በሰዎች ግድያ፣በእስራትና በማሰቃየት፣እንዲሁም በፍንዳታዎች የተሞላች መሆኗን ትናገራለች:: ስለዚህ እስራኤልን አልወዳትም፣የኢየሩሳሌም ሰዎችንም አልወዳቸውም::

ካትሪና በሴት ልጇ አነጋገር ተገረመችና ፦ ሽብርተኝነትንና ግድያን የሚወድ ጤነኛ ሰው የለም:: ሁሉም ምድራዊና መለኮታዊ ሕጎች ለፍትሕና ለሰናይ ተግባራት ጥሪ ያደርጋሉ፣አለች::

የካትሪና አነጋገር ጆርጅን ስለ ቡድሂዝም የመደብ ሥርዓት፣መግደልን ሴቶችንና የሴሎ ልጆችን ስለሚመለከቱ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት እንዲያስታውስ አደረገው:: ፈገግ እያለ ፦

-ኢየሩሳሌም ውስጥ ከሁሉም ሃይማኖቶች ከሙስሊሞች፣ከክርስቲያኖችና ከአይሁዶችም በጣም ጥሩ የሆኑ ሰዎች ይገኛሉ::

-ሳሊ ፦ ስለዚህ አይሁዳዊቷ ሌቪ ይህን ግድያና እስራት ስለምትወድ እኔ አልወዳትም::

-ጆርጅ ፦ ሌቪ ማን ናት?

-አይሁዳዊቷ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ናት::

-ጆርጅ ፦ ጥሩ አርገሻል፤ልጆቹ በቅርጻቸው ወይም በአገሮቻቸው ምክንያት ሳይሆን፣ሰዎችን መውደድና መጥላት የሚገባን በመርሆዎቻቸውና በመልካም ስነ ምግባራቸው ምክንያት መሆኑ በጣም ጥሩ ነገር ነው::

-ማይክል ፦ እኔም ጓደኛዬን ዴቪድን አልወደውም፤ስለ መጠጥ እንጂ ሌላ ወሬ የለውም::

ጆርጅ በጨረፍታ ካትሪናን አየና ፈገግ አለ . .

-ማይክል፣ መጠጥ ምን ችግር አለው?

www.path-2-happiness.com

-አላውቅም፣የማውቀው የሚጠጣ ሰው አእምሮውን የሚስት መሆኑን ብቻ ነው::

ካትሪና በመረበሽ ስሜት ለልጇ ምላሽ ለመስጠት ተጣደፈች . .

-ማይክል ደግ አድርገሃል፣አስካሪ መጠጥ በሃይማኖታችን በአዲስ ኪዳንም እርም ተደርጓል ፦ ‹‹የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤›› . .

ካትሪና በጆርጅ ገጽታ ላይ የመገረም ስሜት አስተውላ ርእሱን ለወጠች ፦

-ጆርጅ ከሐኪሙ ጋር ተገናኝተሃል?

-አዎ ::

-ምን አዲስ ነገር አለ?

-አዲስ ነገር የለም፤ከቴልአቪብ ሆስፒታል የምርመራ ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነው አለኝ:: የቴልአቪቡ ምርመራ ውጤት ራሱ ምን እንደሆነ ግን እኔ አላውቅም ::

-ይገርማል፣እዚያ ያለው ሐኪም የምርመራ ውጤቱን አልነገረህም ነበር?

-የሄድኩበት ኩባንያ በሰጠኝ አገልግሎት አንዷ ሰራተኛቸው የሕክምናዬን ጉዳይ እንድትከታተል ስለተደረገ፣የምርመራ ውጤቱን ያወቀችው ሌቪ ናት :: ውጤቱን ለማወቅ ጥረት ባደርግም እንዳልረበሽ በማሰብ መሰለኝ ሊታሳውቀኝ አልፈለገችም ::

-የካትሪና ፊት በቅናት ተለዋወጠ፤ያች ሌቪ ቆንጆና ስሜትህ እንዳይጎዳ በጣም የምታትሳሳልህ ትመስላለች ! !

-ሳሊ ፦ ባባ እንደ ጓደኛዬ ሌቪ ዓይነት ከሆነች ግን ቆንጆም ጥሩ ሰውም አይደለችም ::

-ጆርጅ ፦ ያችኛዋ ሌቪ ግን ቆንጆና ጥሩ ሰውም ነች::

-ካትሪና ፦ አይሁዳዊያት ሴቶች በብሉይ ኪዳን እንዳለው ሁሉ ወሲብ ለነሱ በቀላሉ የሚፈጸም ተራ ነገር ነው::

-ማይክል፦ ማማ ብሉይ ኪዳን ወሲብን ያበረታታል?

-ካትሪና ፦ ማይክል እየቀለድኩ ነው፤(ወደ ጆርጅ ዞር አለችና) ፦ ጆርጅ አይደለም እንዴ?

-ልክ ነሽ . . እናትህ ብዙ መቀለድ ትወዳለች . . ሰዎችን መግደል፣ወይም አስካሪ መጠጥን መጠጣት ወይም ልቅ ወሲብን የሚያበረታታ ትክክለኛ የሆነ ሃይማኖት ፈጽሞ የለም::

-ጆርጅ ማይክልን ሲያናግር ማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት ካትሪና ስለተረዳች፣እንደገና አርእስቱን ለመለወጥ ሞከረች ፦

-ጆርጅ፣ስለዘገየን አሁን ልጆቹን ወደ ቤት አድርስና በቀጥታ ወዳንተ እመለሳለሁ::

-የኔ ፍቅር እጠብቅሻለሁ . . (ወደ ሁለቱ ሕጻናት ዞር አለና) ፦ የኔ ጀግኖች! ቢያንስ በየሁለት ቀኑ እንድትጎበኙኝ ይሁን፣እወዳችኋለሁ . . አላቸው::

(4)

ካትሪና ልጆቹን ይዛ ከሄደች በኋላ ብቻውን ሲቀር ጆርጅ ለሀሳቦቹ እጁን ሰጠ:: እንዲህ ሲልም ራሱን ጠየቀ ፦ ዕድሜዬን በሙሉ በአመለካከቶች በፍልስፍናና በሃይማኖቶች ግጭቶች ውስጥ እኖራለሁ ማለት ነው? ! መላው የሰው ዘር ይታደል ዘንድ እነዚህ ሃይማኖቶች እርስ በራሳቸው የተጣጣሙ ለምን አይሆኑም? ! የሰው ልጆች በመላ ውስጣዊ ሰላም አግኝተው ለምን አይኖሩም? ! እርስ በርሳቸውስ ለምን በሰላምና በመቻቻል አይኖሩም? ! (ፈገግ አለና ቀጠለ) ፦ ምናልባት በድንገት ታምኤታዊ ሆኜ ይሆናል፣አስደናቂዋ ሕይወት አንዳንዴ ከአእምሮ ውጭ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ሕልውና ወደሌላቸው ባዶ ተምኔታዊ ምኞቶች ትለውጠናለች ! ጌታ ሰዎችን ሁሉ ያለ ልፋት ወደራሱ ቢያደርሳቸውስ እላለሁ . . ምናልባት ሕይወት አሰልቺ ሳትሆን አልቀረችም:: ሰብአዊ ድክመት የሌለባቸው ሌላ ፍጡር ሆነንም ሊሆን ይችላል:: ብንሆን ኖሮ ክፋት ብቻ ሳይሆን ደግነትም ጭምር አይኖርም:: እንዲያውም የሁለቱ ጎን ለጎን መኖር በዚህ ዓለም ላይ እየኖርን ስለመሆናችን ማስረጃ ነው:: ኣህ . . የሰው ልጅ የመኖሩን ትርጉም፣የመሞቱን ፍቺና መጨረሻው ወዴት እንደሆነ የሚያውቅ ካልሆነ በስተቀር በፍልስፍናዎቹና በአመለካከቶቹ ማዕበል ውስጥ ባክኖ መቅረቱ ነው . .

ከሄደች ምንም ያህል የቆየች ባይሆንም የካትሪናን መመለስና የወዳጁን የአደምን ጉብኝት ሲጠብቅ ነበር . . ኮምፒውተሩን ከፍቶ ኢ-ሜይሉን ሲያይ ሥራውን በስኬት በመጨረሱ አመስግኖት መታመሙን ከባለቤቱ መስማቱን በመንገር ዛሬ ወይም ነገ መጥቶ እንደሚጎበኘው የገለጸለበትን የከካኽ መልእክት አገኘ:: በመቀጠል የአደምን የፌስቡክ ገጽ ጎበኘ:: ስለርሱ የሚጽፈውን ነገር ማንበቡን አደም እንዳይነቃ የጓደኝነት ጥያቄ አላቀረበም . . ‹‹የመታደል መንገድን ፍለጋ ላይ ከተሰማራው ወዳጄ የተቃረመ ትምህርት 2›› በሚል ርእስ ስር የተጻፈ መጣጥፍ አገኘ ፦

‹‹በመታደል መንገድ ፍለጋ ላይ የተሰማራው ወዳጄ አሁንም የደስተኝነትን መንገድ ለማግኘት ጥረቱን በቁርጠኝነትና በጽናት እንደ ቀጠለ ነው:: የሚከተሉትን ትምህርቶች ከርሱ ለመገብየት ችያለሁ ፦

1. መታደልን ፍለጋ የመሳሰሉ ትላልቅ ጉዳዮች ከፍተኛ ጥረትና ብዙ ፈተናዎችን ማለፍ ይጠይቃሉ::
2. ጽናትና ቁርጠኝነት መልካም አጋጣሚዎችን ይፈጥራሉ:: ወዳጄ ጽናትና ቁርጠኝነቱ በጨመረ ቁጥር የመማርና የማወቅ ዕድል ተመቻችቶለታል::
3. -የመታደልን መንገድ ለመፈለግ የሚነሳ ሰው የሚያረጋግጠው ትልቁ ስኬትና ድል፣ የገዛ ራሱን ማሸነፍ እንጂ በሕይወት ሁነቶች ላይ ድል መቀዳጀት አይደለም::
4. ከጽናቱና ከቁርጠኝነት ኃይሉ ጋር ለወዳጄ የሚሰጋለት ነገር የማያሳፈልገውን ነገር ሁሉ ያውቃል፣ይሁን እንጂ በሚያስፈልገው ነገር ላይ በበቂ ሁኔታ ትኩረት የማያደርግ መሆኑን ነው::

የተቀሩትን ትምህርቶች በቅርብ ቀን ይዤላችሁ እመለሳለሁ . . ሠላም ለሁላችሁም ይድረስ:: አደም››

ጆርጅ ጽሑፉን እንደገኛ በጥሞና አነበበው:: አደም አእምሮው ውስጥ የሚመላለሰውን የሚያውቅ መስሎ ተሰማው:: ትልቁ ፈተና ሲል ምን ማለቱ ይሆን? በራስ ላይ ድልን መቀዳጀት ማለቱስ? ሲል ራሱን ጠየቀ:: ወዳጁ ፈተና መውደቁን፣መርሆውን ሸጦ ጉቦ ማቀበሉን አደም ያውቅ ይሆን? ቆንጆ ሴት መሳሙንና ማቀፉንስ? ከርሷ ጋር በሚስቱ ላይ ክህደት ለመፈጸም መፈለጉንስ? ካኽን የመሰለ ስነ ምግባር የጎደለው ብልሹ ሰው ከሚመራው ኩባንያ ለመልቀቅ አለመወሰኑንና ይልቁንም ጉቦ በማቀበል ተባባሪው መሆኑን ያውቅ ይሆን? የመጨረሻው ነጥቡ ትርጉምስ ምን ማለት ይሆን? የማያስፈልገኝን በማወቄና ለሚያስፈልገኝ በቂ ትኩረት ባለመስጠቴ ለምን ይሰጋልኛል? የማልፈልገውን ሁሉ ማወቅ ማለት የግድ የምፈልገውን ሁሉ ማወቅ ማለት አይደለም ወይ? እርግጥ ነው ወዳጁ ብኩን ኤቲስት፣በአፈተረት ውስጥ የሚኖር ቡድሂስትም ሆነ ላም ወይም በሺዎች የሚቆጠሩ ቁሳቁሶችን የሚያመልክ ሕንዱ መሆን አይፈልግም:: ውስበስብ ይሁዲም አይሆንም . . ታዲያ የሚፈልገው ምን ይሆን? የአደም ስጋት ተገቢ ሳይሆን አልቀረም:: ነጻ ሆኖ መጻፉን እንዲቀጥልበት የፌስቡክ ገጹን ያነበበው መሆኑን ሳይነግረውና ምንም ፍንጭ ሳይሰጥ ዛሬ በጉዳዩ ላይ ከርሱ ጋር ለመወያየት ይሞክራል::

ጆርጅ የክፍሉ ቅዝቃዜ የጨመረ መስሎ ተሰማውና የሙቀት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ ብድግ ሲል ድካም ተሰምቶት ተንገዳገደ:: ነርሷ አየችውና በፍጥነት መጣች . .

- ብርድ ብርድ አለህ?
- አዎ ትንሽ፣የሙቀት መጠኑ ዝቅ ብሎ ይሆናል መሰለኝ::
- የሙቀቱ መጠን አልተለወጠም፣ የተረጋጋ ነው:: አልጋህ ላይ አረፍ በል፣ለሐኪሙ እደውልና በፍጥነት መርፌውን ይዤልህ እመለሳለሁ::
 ነርሷ ወጥታ ሄደችና መርፌውን ልትወጋው ፈጥና ተመለሰች . .
- ይህ ሐኪሙ ያዘዘልህ አዲሱ መርፌ ነው::
- አዲሱ? !
- አዎ አዲሱ፣ከመጀመሪያው ይበልጥ ብዙ ጊዜ የሚሰራ ሲሆን ራስህን ግን ያስተዛል:: ይቅርታ አድርግልኝና በአስቸኳይ ልትወጋ የሚገባ ነው፣ክንድህን መዘርጋት ትችላለህ?

ነርሷ መርፌውን ወጋችው፤በጥቂት በደቂቃዎች ውስጥ ሙሉ በሙሉ ራሱን ሳተ::

ካትሪና ስትመለስ ጆርጅን በዚህ ሁኔታ ላይ አገኘችውና እስኪነቃ ድረስ ከአጠገቡ ቁጭ ብላ ጠበቀች:: አልጋው ላይ ለጥ ብሎ ሲተኛ ተመለከተችው:: በካቶሊካዊቷ እምነት እርሷን ከመከራከር ባይገታም፣በጌታ አምኖ እጁን ለመስጠት የማይፈልግ ቢሆንም፣ደግነቱንና ለርሷ ያለውን ፍቅር አስታውሳ ፍቅሩ እነደ አዲስ በውስጧ ይቀሰቀስ ጀመርር . . እያሰበችው ቁጭ አለች . . መልስ እያጠራት የመፋጠጥ ሁኔታ የሚያጋጥማት ቢሆንም ክርክሮቹን በጣም ትወዳለች:: ለብዙ ጥያቄዎቹ ግልጽ ምላሽ የላትም:: ከነዚህ ጥያቄዎችና ክርክሮች ለመገላገል በደፈናው ጌታን አምኖ መቀበል ብቻ በቂ አይደለም? ወይስ ያለ ጥያቄ አምኖ መቀበል ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ ጥያቄውን ላለመመለስ የሚደረግ አንድ ዓይነት ሽሽት ይሆን? እርግጥ ነው የካቶሊክ እምነት ውስብስብነት አንዳንድ ጊዜ ያስቸግራታል:: አይሁዳዊነትና ፕሮቴስታንታዊነትም እንዲሁ በተመሳሳይ ውስጣዊ ግጭቶች የተሞሉ ናቸው፣ምናልባትም ከካቶሊካዊነት በከፋ መልኩ ! ሽሽት ቢሆንም እንኳ ያለ ጥያቄና ያለ ክርክር አምኖ መቀበሉ ለሁለቱም ይበልጥ አትራፊ አይሆንም? በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ሽሽት ኪሳራ ከሚያስከትል መጋፈጥ ተመራጭ ይሆናል:: ኦህ . . አንተ ኢየሱስ ሆይ ይቅር በለኝ፣አንተ አላዳንከንም ማለቴ አይደለም፣ግና . .

www.path-2-happiness.com

ስለ ቆንጆዋ አይሁዳዊት ስለ ሌቪ የተናገረውን አስታወሰች . . በጆርጅ ላይ ጽኑ አመኔታ አላት:: ያለው መርህና የታማኝነት ደረጃው ምን ያህል እንደሆነም ታውቃለች:: ይሁንና ከኢየሩሳሌም ወሲብ ነክ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ብቻ አግበስብሶ የመጣው ለምንድነው? ! ባሳደረባት የቅናት ስሜት ፈገግ አለችና ቶም በሳማት ጊዜ ይህ ቅናት ዬት እንደነበረ ራሷን ጠየቀች:: ታዲያ በዚህ ረገድ ጆርጅ እውነት የለውም? አዲስ ኪዳን የሚከለክል መሆኑን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ለልጆቼም እያስተማርኩ መጠጥ እንዴት ነው እምጠጣው? ! አምላኬ በዚህ ሁሉ ቢከራከረኝ ምን እመልስለታለሁ . .

ካትሪና በራሷ የሀሳብ ዓለም በመዋኘት ላይ እያለች ነርሷን ‹‹አንቺ ቆንጆ ጆርጅ የት ነው?›› የሚል ሰው ድምጽ ሰማች::ነርሷን የሚያይበት ሁኔታ ከቃላቱ ይበልጥ አስቀያሚ ነበር . . ነርሷ ክፍሉን አመላከተቻውና ገብቶ ካትሪናን ጨበጣት::

- እንዴት ነሽ፣የጆርጅ ባለቤት ነሽ?
- አዎ፣ካትሪና እባላለሁ፤እንኳን ደህና መጣህ፣አንተ ማነህ?
- እኔ የጆርጅ የሥራ ባልደረባ ካኽ ነኝ:: ትናንት ደውዬ ሆስፒታል መሆኑን ነግረሽኝ ነበር፣አሁን እንዴት ነው ያለው?
- ደህና ነው . . ትኩሳት አለበት፣የሰውነት ሙቀቱ መጠን ከፍ በማለቱ ሙቀቱን የሚቀንስና የሚያስታግስ መርፌ ስለሰጡት ራሱን ስቶ ተኝቷል::
- አንቺ እንግሊዛዊት አትመስዪም !
- ሕንዳዊ የዘር ግንድ ያለኝ እንግሊዛዊት ነኝ::
- እህህ፣የምሥራቆች ውበት በግልጽ ይታያል፣ጆርጅ ወደ ሕንድ ሲሄድ ያላስፈለገው ለዚህ ሳይሆን አይቀርም::
- ምንድነው ያላስፈለገው?
- የሕንድ ቆነጃጅት ኮረዶች፤እህህ፣ለማንኛውም እንኳን ደስ አለሽ እላለሁ፣ጆርጅን በፍቅርሽ ማርከሽ ሳትፈትኚው አልቀረሽም::

  የካትሪና ፊት በከፍተኛ የመከፋት ስሜት ተወረረ . .
- ለመጀመሪያ ጊዜ ዛሬ ነው ያየሁሽ:: ጆርጅ ውበትሽን ከኔ ይደብቅ ነበር ማለት ነው:: ለማንኛውም ካንቺ በመተዋወቂቴ ዕድለኛ ነኝ:: በፈለግሽው ነገር ለመታዘዝም ዝግጁ ነኝ:: ከኛ ጋር ኩባንያችን ውስጥ ለመስራት ከፈለግሽ ታዛዦች ነን::
- አመሰግናለሁ፣እኔ የሃይማኖት መምህርት ስሆን የቤተክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነኝ::

- የኛ ሥራ የሚያስገኘው ቁሳዊ ጥቅም የተሸለ ነው፣የበለጠ እርካታም ያጎናጽፋል የሚል ግምት አለኝ::
- ሙሉ ጊዜዬን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሰጠሁ በመሆኔ ሥራዬን መለወጥ አልፈልግም::
- አስቢበት ውሳኔው ያንቺ ነው:: እውነቱን ለመናገር ጆርጅ ኩባንያውን በጣም ነው የጠቀመው:: የዳይሬክተሮች ቦርድ ባከናወነው ከፍተኛ ጥራት ያለው ስኬታማ ሥራ ጥልቅ ምስጋና እና አድናቆት ቸሮታል፤በተለይም በመጨረሻ ባደረገው የቴል አቪብ ጉዞው:: ታውቂያለሽ . . በሁለት ተከታታይ ጉዞዎች በያንዳንዱ ተፈላጊውን የውል ስምምነት በላቀ ብቃትና ሁሉንም ደንበኞች ባረካ መልኩ ለመፈራረም ችሏል::
- አንተ አለቃው ስለሆንክ ምናልባት ይህን ማሳካት የቻለው ከአንተ በተሰጠው መመሪያና ድጋፍም ጭምር ሊሆን ይችላል::
- ሊሆን ይችላል፣ግን አይመስለኝም፤በተለይም ሴቶችን በሚመለከት::

  በዚህ አፍታ . . አንድ ሰው የክፍሉን በር አንኳኳ . .
- ይቅርታ . . ይህ የጆርጅ ክፍል ነው?
- አዎ፣የተኛው እርሱ ነው፣ራሱን አያውቅም፣እኔ ባለቤቱ ነኝ፣ግባ አንተ ማነህ?
- እኔ ወዳጁ አደም ነኝ፣ዛሬ ደውሎልኝ ነበር፣በጥሩ ጤንነት ላይ ነበረ፣አሁን ምን አግኝቶት ነው?
- ሕመሙ እየሄደ በድንገት ይመለስበታል:: ትኩሳቱ ከፍ ስለሚል ማስታገሻና የትኩሳት መቀነሻ መርፌ ለመውሰድ ስለሚገደድ ሙሉ በሙሉ ራሱን ስቶ ይቆያል::
- በጣም ነው የማዝነው፣ወዳጄን መርዳት የምችልበት ነገር ይኖር ይሆን?
- ለጥልቅ ስሜትህ አመሰግናለሁ፣አረፍ በል::
- አመሰግናለሁ::

አደም ካኽን ለመጨበጥ እጁን ሲዘረጋ ካኽ በኩራት ተወጣጥሮ ጨበጠው፤አደም በትህትና እንዲህም አለው . .

- ይቅርታ . . አልተዋወቅንም::
- እኔ ካኽ ነኝ፣በኩባንያው የጆርጅ አለቃ ነኝ፤አንተስ ሥራህ ምንድነው?
- አደም እባላለሁ፣በአንድ ካፌቴሪያ አስተናጋጅ ስሆን የጆርጅ ወዳጅ ነኝ::
- አስተናጋጅ? !

  የአደም ፊት ቀላ፣ግን ንዴቱን ዋት አደረገውና በተረጋጋ ቅላጼ ፦

-ሲነቃ ልትጠይቀው ትችላለህ ! ወዳጅነት በስነ ልቦናዊ፣መንፈሳዊና ርእዮታዊ ቅርርብ ላይ እንጂ በሀብትና በገንዘብ ላይ አይመሰረትም የሚል እምነት አለኝ !

በካኽ አነጋገር የተከፋች መሆኗ በግልጽ የሚስተዋልባት ካትሪናም በፍጥነት ጣልቃ ገባች ፦

-አደም ምንም አይደለም፣ጆርጅ ስላንተ በዙ ነገር ነግሮኛል . . በአንተ ወዳጅነት፣በአመለካከትህና በጥበብህ እጅግ በጣም ደስተኛ ነው።

-ይህ የጆርጅ መልካም ስነ ምግባርና የተገራ ባህሪው ማሳያ ነው . . (ወደ ካኽ እያየ ቀጠለ) ፦ ባይሆንማ እርሱ ትልቅ ኢንጂነርና የስነ ቴክኒክ ባለሞያ ሲሆን እኔ አንድ ተራ አስተናጋጅ ነኝ !

-ካኽ በኩራት እንደ ተወጣጣረ ፦

-በትክክል !

-ካኽ እባክህን ለጆርጅ ወዳጅ አክብሮት እንድትሰጥ እፈልጋለሁ።

-እህህ፣ገቢው ከኔ የጽዳት ሰራተኛ ገቢ ለማይበልጥ ሰው ብለሽ ነው እንደዚህ የምትናገሪው?

-የጆርጅ ወዳጅ ነው፤ደሞም ገንዘብ ሁሉም ነገር ማለት አይደለም። የሰዎች ማንነት በገንዘብ ይለካል ብለህ ነው የምታምነው?

-ጆርጅን መሰልሽኝ . . ለኔ ግን ከአስተናጋጅ ጋር መቀመጥ ውርደት ነው። ካትሪና ዋናው ነገር እኛ ዘንድ እንድትሰሪ ያቀረብኩልሽ ግብዣ አሁንም እንደተጠበቀ ነው . . ይህ ቢዝነስ ካርዴ ነው፣ስልኬ አለበት። የሚያስፈልግሽ ነገር ሲኖር ደውይ፤በይ ደህና ሁኚ . . ለጆርጅ ፈውስ እመኝለታለሁ።

-አደም፣ ሰውየው ለተናገረው ሁሉ ይቅርታ እጠይቀሃለሁ።

-ይቅርታ የሚያስጠይቅ አይደለም፣የኔ ማንነትና እሴት ያለው ከውስጤ እንጂ ማንም ስለኔ በሚናገረው ውስጥ አይደለም። ደግሞም አንቺ ምንም ስላልተናገርሽ ይቅርታ መጠየቅ አያስፈልግሽም።

-ጆርጅ ስላንተ የነገረኝ ሁሉ እውነት ነው ማለት ነው።

-አመሰግናለሁ፣ይህ ትህትናውና መልካም ስነ ምግባሩ ነው።

-ስለ ሃይማኖተኛነትህ፣ስለአስተዋይነትህና ስለ ምክሮችህ ብዙ ነገር ነግሮኛል።

-ጆርጅ በፍጹም ልቦና እውነታን በመፈለግ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤ካሰበበት መድረሱም አይቀሬ ነው። ቸሩ ፈጣሪ አምላክ ደግሞ ወደርሱ ለመድረስ የሚፈልግን ሰው አያሳፍርም።

-በእግዚአብሔር ላይ መተማመንና መመካትን በተመለከተ ጥልቅ አነጋገር ነው፤ሆኖም ግን እርስ በርስ መጋጨታቸውን ሲመለከት ሃይማኖቶችን ሁሉ እርግፍ አድርጎ እንዳይተው አያስፈራህም?

-አይመስለኝም።

-ይህ ሁሉ በራስ መተማመን ለምንድነው?

-በእውነተኛ ሃይማኖት ውስጥ እርስበርስ የሚጋጭና የሚቃረን ነገር የለም፤ስለዚህህም መድረሱ አይቀሬ ነው።

-አንተ ካቶሊክ ነህ ወይስ ፕሮቴስታንት?

-መልስ እንዳልሰጥ ትፈቅጂልኛለሽ?

-ዝም ብዬ ነው የጠየኩት፣ውሳኔው ያንተ ነው።

-ጆርጅን ሌላ ጊዜ መጥቼ እጠይቀዋለሁ፣አሁን ፍቀጂልኝና ልሂድ።

-ነገ መጥተህ ብታየው ጆርጅ በጣም ደስተኛ ይሆናል፣እባክህን እንዳትቀር።

-ነገ ወይም ተነገወዲያ ለመምጣት እሞክራለሁ። ለማንኛውም ያለበትን ሁኔታ ለመጠየቅ ነገ እደውልለታለሁ፤ደህና ሁኚ።

የሚያስተኛው መርፌ ሥራውን ቀስ በቀስ እየቀነሰ በመምጣቱ ጆርጅ በጥቂቱ ራሱን ማወቅ ጀምሯል፤ይሁን እንጂ ከፍተኛ የሆነ የመጫጫን ስሜት ስለሚሰማው ዓይኖቹን የሚከፍታቸው በግድ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ በካትሪና በካኽና በአደም መካከል ከነበሩት ምልልሶች ከፊሉን የሰማ ቢሆንም ከፊሉ ተደበላልቆበታል። ከአደም መሄድ በኋላ ትንሽ ሻል ስላለው ዓይኖቹን ለመክፈት ፈለገ፣ወደ ክፍሉ የሚያመራ ጎብኚ ኮቴ ሲሰማ ግን አለመክፈቱን መረጠ። ጎብኚው ሰላምታ አቅርቦ ተቀመጠ፣ሐኪም ቶም ነበር . .

-የፈላስፋችን ጤንነት አሁን እንዴት ነው?

-ቶም እንኳን ደህና መጣህ፣ድንገተኛ ትኩሳት መጥቶበት የማስታገሻ መርፌ ሰጡት፣አሁን ራሱን አያውቅም።

-መልካም ጤንነትና የተሟላ ፈውስ እመኝለታለሁ። ጆርጅ በጣም አልፎ አልፎ ብቻ የሚገኝ ልዩ ሞዴል ነው። ብዙ የምጨቃጨቀው ብሆንም እኔ ከምጠቅመው ይበልጥ ከርሱ በብዙ ነገር ተጠቃሚ ሆኛለሁ።

-አንተ የርሱ ሐኪም ነህ፤አንተ ዘንድ ሕክምና መከታተል ከጀመረ ወዲህ ብዙ መሻሻል አሳይቷል።

-ይልቁንስ መሻሻል ያሳየሁት እኔ ነኝ። ምናልባት አንቺም ሆንሽ ጆርጅ

አታውቁትም እንጂ እኔ ቀልደኛ ሐኪም ነበርኩ:: ዋነኛ ፍላጎቴ ሴቶችን ማጥመድና መዝናናት ነው:: በዚህ ሰሞን የጆርጅ ፍልስፍና በሃይማኖቶች ላይ ያደረኳቸው ንባቦችና ካንቺ ጋር ቤተክርስቲያን መጎብኘቴ ሕይወቴን ለምን እንደለወጠ አላውቅም:: በነገራችን ላይ ባለፈው ጊዜ ስለ ሳምኩሽ ይቅርታ እጠይቃለሁ፣እመኚኝ ሆን ብዬ አቅጄ አልነበረም፣ለምን እንዳደረኩትም አላውቅም::

- ነገሩ አልፏል፣የተረሳ ነገር ነው:: ምናልባት ትልቁ ስህተት ከኔ ለከራሴ ሳይሆን አይቀርም:: በዚያን ዕለት ያን እርጉም መጠጥ አብዝቼ ነበር::
- ለማንኛውም ሰዎች ስንባል ለስህተቶቻችን ‹‹ሳናውቀው ነው ወይም ተገደን ነው›› እያልን ማመካኛ መደርደር እንወዳለን:: ይህን ተይውና ስለ ጆርጅ ጤንነት ሐኪሞች ምን እንዳሉ ንገሪኝ::
- ነገሮች ሙሉ በሙሉ ግልጽ የሆኑ አይመስልም:: የሐኪሞች ቡድን በቀጣዮቹ ሁለት ቀናት ውስጥ ጥርት ያለ ውሳኔ ላይ ይደርሳል የሚል ተስፋ አለኝ::
- ይሻለዋል፣ጌታም ይጠብቀዋል::

ጆርጅ አሁን ገና የነቃ መስሎ አጠገቡ ያሉትን በመጠየቅ ዓይኖቹን ከፈተ . .

- ጆርጅ የኔ ፍቅር ነቅተሃል::
- ከመቼ ጀምሮ ነበር እንደዚህ የነበርኩት?
- ከሦስት ሰዓት ጀምሮ ነው:: ነርሷ እንደ ነገረችኝ እኔ ከመምጣቴ ጥቂት ቀደም ብሎ ነበር መርፌውን የሰጡህ:: በሰላም በመንቃትህ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን . . (ወደ ቶም ዞረችና) ፦ ያንተ ሐኪም ሊጠይቅህ መጥቶ ይኸው እዚህ ይገኛል::
- ጆርጅ እንዴት ነህ?
- ደህና ነኝ፣ዶክተር እንደምን አለህ?
- ደህና ነኝ፣ስለጤንነትህ ካትሪናን ጠይቄ ጥሩ ሁኔታ ላይ መሆንህን ነግራኛለች፤አሁን ላደክምህ አልፈልግም፣ተመልሼ እጠይቀሃለሁ::
- እኔ እንግዲህ ሆስፒታል ነኝ፣መጪው ቀጠሮአችን መቼ ነው የሚሆነው?
- አንተ በፈለከው ቀን፣እዚህ ክፍልህ ውስጥም ሊሆን ችላል::
- መልካም፣እንግዲ;ያውስ በመጪዎቹ ጥቂት ቀናት ውስጥ ይሆናል::
- በሆስፒታል ቆይታህ ጊዜ ካለህ፣ውይይታችን ይበልጥ ጠንከር ያለ እንዲሆን በመለኮታዊ ሃይማኖቶች ላይ የምታደርገውን ንባብ ቀጥልበትና

አጠናቅቅ::

- ጥሩ፣ተስማምተናል::

ካትሪና ጆርጅ አጠገብ ከተደረደሩት መጽሐፎች አንዱን አንስታ ፈገግ እያለች ፦

- ከትናንት አንስቶ ጀምሮታል::
- ጆርጅ፣ ጥሩ አድርገሃል::
- እዚህ ያለኝን ረዥም ቀሪ ወቅት በውይይት ላይ ለማዋል እሞክራለሁ . . (ወደ ካትሪና ዞር ብሎ ፈገግ አለና) ፦ እርሷ ውይይትና ክርክር ስለማትወድ ቶሎ ትዘገዋለች እንጂ::

የካትሪና ፊት ቀላ . .

- ውይይት ላለማቋረጥ ቃል እገባላችኋለሁ::
- እህህ፣በጣም ጥሩ፤ካንተ ጋር ለመወያየትና ሀሳብ ለመለዋወጥ ከተመቸኝ ደጋግሜ እጎበኝሃለሁ:: ፈጣን ፈውስ እመኝልሃለሁ፣ፍቀዱልኝና ልሂድ::

ቶም ወጥቶ ሲሄድ ካትሪና ፈገግ ብላ ወደ ጆርጅ ዞረች ፦

- የኔ ፍቅር ውይይቶችን በማቋረጤ ይቅርታ አድርግልኝ፣ ይህን እንዳላደርግ ግን አግዘኝ::
- መቀለዴ ነበር::
- ሆኖም እውነትም አለህ . . ያንተ አለቃ ነኝ የሚለው ቅሌታም ባለጌ ካኽ ማነው? ብዬ ልጠይቅህ ነበር::
- ካኽ ምን አደረገ?
- ዛሬ እዚህ መጥቶ ነበር፤በጸባዩ፣በስነ ምግባሩም ሆነ በድርጊቱ ጫፍ የነካ ቅሌታም ነው፤አንተን ባላስብ ኖሮ አባርረው ነበር::
- እኔን በማሰብ . . ! ማበረር ትችይ ነበር:: እንዴት እንደምጠላው ልነግርሽ አልችልም:: ግን ምን አድርጎ ነው?
- ዓይኑ፣እይታው፣አነጋገሩ፣አድራጎቶቹ፣መንፈሱ፣ሁለመናው ቅሌታም ወራዳ ነው:: ይታይህ፣እርሱ ማኔጀር ነውና አደምን አስተናጋጅ በመሆኑ አብጠልጥሎ ሲያዋርደው ! ነርሷንም በብልግና ያናገር ነበር !
- አደም መጥቶ ነበር? !
- አዎ፣ካኽ አስከፍቶታልእንጂ:: እርሱ ግን እጅግ የላቀና የተገራ ጨዋነትን ነው ያሳየው::
- አንዳንድ ጊዜ አደም ሙሉ በሙሉ የካኽ ተቃራኒ የሆነ ሰብእና ሆኖ ነው የሚታየኝ::

www.path-2-happiness.com

-ትልቅ ከማይመስለው ዕድሜውና ከተሰማራበት ሥራው በተቃራኒ አነጋገሩ እንደ ዕድሜ ባለጸጋና እንደ ፈላስፋ ነው፡፡
-እናም አስቀድሜ ስለ አደም የነገርኩሽን ማረጋገጥ ችለሻል ማለት ነው?
-ጆርጅ ስለርሱ የነገርከኝን ብቻ ሳይሆን ያልነገርከኝንም እውነት አድርጌ እወስዳለሁ፡፡ ካኽ በተለይ በሴቶች ነገር ላይ ያንተ ተቃራኒ ነኝ ብሎ ነው የነገረኝ፣የርሱን ቅሌታምነትና ያንተን ጨዋነት ግን እርሱ አይነግረኝም፡፡
-ፈታኟ ኦርሜላ፣ውቧ ሌቪስ?
-የኔ ፍቅር እኔ ባንተ በጣም ነው የምተማመነው፡፡ እመነኝ በስነ ምግባርህና በጨዋነትህ ጽኑ እምነት አለኝ፡፡ አንተሳ በኔ ትተማመናለህ?
-አዎ፡፡
-ከቶም ጋር ያሳለፍኳቸውን ምሽቶችስ?
-በመጨዐረሻው ምሽት ላይ በመካከላችሁ ስለተከሰተው ነገር ቶም ነግሮኛል፡፡
-እመነኝ ያ ነገር እንዴት እንደተከሰተ አላውቅም፡፡
-ኦህ . . ብዙ ስህተቶችን እንፈጽማለን፣ግን እንዴት እንተከሰቱ አናውቅም፡፡ የኔ ፍቅር በእምነትሽና በጨዋነት ባህሪሽ እተማመናለሁ፡፡
-ጆርጅ አፈቅረሃለሁ፡፡
ሰዓቷን ተመለከተችና ፦
-አሁን መሄድ አለብኝ፣ነገ እመለሳለሁ፡፡
-ነገ ልጠብቅሽ? ለውይይትና ለክርክር ቃል ጋበተሸልኛል፡፡ ካንቺ ጋር ከማነሳቸው ነገሮች ውስጥ ወንጌል ውስጥ የሰፈረውና ፦ ‹‹የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤›› የሚለው ጥቅስ አንዱ ይሆናል፡፡
-የኔ ፍቅር ተስማምተናል፣በዚህ ነጥብ ላይ ግልጽ ሆኘልህ እቀርባለሁ፡፡
-ፍቅሬ ተስማምተናል፡፡

(5)

ካትሪና ወጥታ ሄደች . . መጀመሪያ ሲነቃ የሰማቸውን ድምጾች ለማስታወስ እየሞከረ ዓይኖቹን ጨፈነ፡፡ ከሌላው ይበልጥ ቶም የተናገረውና ስለ መለወጡና ከጆርጅ ብዙ ፋይዳ ማግኘቱን የገለጸው በጉልህ ታወሰው፤መረጃው ብርቱና አሳማኝ ሆኖ ተሰማው፡፡

ካኽ አደምን በማብጠልጠል ከተናገራቸው ግርድፍና ያልተገሩ ቃላት ጥቂቶቹ ትዝ አሉት፡፡ የአደም ጨዋነትና ትሁት አነጋገሩ ታወሰው፡፡ ውሉን በስኬት በመፈራረሙ ምክንያት ከካኽ በቀረበለት ምስጋና እና ከኩባንያው

ቦርድ በተቸረው አድናቆት በውስጡ ፈገግ አለ፡፡ ከሆስፒታሉ ከወጣ በኋላ ኩባንያውን ለመተውና በካኽ እጅ የሚሽከረከር ኢሞራላዊ መሳሪያ መሆኑን ለማብቃት የመልቀቂያ ደብዳቤ ለማቅረብ በቂ ድፍረት ይኖረው ይሆን? ወይስ የገንዘብና የስልጣን ፍቅር በመርሆዎቹ ላይ ድል ይቀዳጅ ይሆን?

በሀሳብ ባህር በመዋኘት ላይ እያለ የነርሷን ድምጽ ሰማ ፦
-እንደምን ነህ፣የሙቀት መጠኑ አሁን እንዴት ነው?
-አህ፣አሁን ጥሩ ሁኔታ ላይ ነኝ፣ይሻለኛል፡፡
-ከጊዜው በፊት ትነቃለህ ብለን ጠብቀን ነበር፡፡
-በትክክል . . ከአፍታ በፊት ነው የነቃሁት፣ይሁን እንጂ በጣም ደክሞኝ ስለነበር ዓይኔቼን እንደጨፈንኩ ቀጥዬ ነበር፡፡
-ግድ የለም፣የሰውነትህ የሙቀት መጠን አሁን ቆንጆ ነው፤ደህና ሁን፡፡
-አመሰግናለሁ፣ከእንግዳዬ በኩል ለደረሰብሽ ተገቢ ያልሆነ ነገር ይቅርታ አድርጊልኝ፣የሆነውን ነገር ባለቤቴ ነግራኛለች፡፡
-እኔ ሳልሆን ባልደረባዬ ነበረች፡፡ ለማንኛውም እንደሱ ያሉ ያንዳንድ ሰዎች ጋጠወጥነት ስለሚያጋጥመን ለምደነዋል፡፡ በዚህ ራስህን አታስጨንቅ፤ለጨዋነትህ አመሰግነሃለሁ . . ስሜ ዚንታ ነው፣የሚያስፈልግህ ነገር ካለ በማናቸውም ጊዜ ልታስጠራኝ ትችላለህ፡፡
-ዚንታ ስሜሽ ትንሽ እንግዳ ነገር ይመስላል !
-የዘር ግንዳችን ከነምሳ እንጂ ከእንግሊዝ አይደለም፡፡
-እንዳንች ያለች ደግና ትሁት ነምሳዊት አውቃለሁ፡፡
-ይገርማል፣እንግሊዝ ውስጥ የነምሳውያን ቁጥር በጣም ትንሽ ነው፡፡
-ሌቪን እንግሊዝ ውስጥ ሳይሆን ቴልአቪብ ነው የተዋወኳት፡፡
-ይሁዳ ናት ! አይሁዶች አውሮፓን ስለበከሉ ፍልስጥኤምና ኢየሩሳሌምን ሰጥተናቸው ነው ከነሱ የተገላገልነው፡፡
-በአይሁዶች ላይ ያለሽ ስሜት ጠንከር ያለ ይመስላል !
-ሊሆን ይችላል፣ግና አንተ ከአይሁዶች ጋር ብዙ ስላልኖርክ ነው . . ለማንኛውም ከፈለከኝ በማንኛውም ጊዜ አስጠራኝ፤አሁን እራት ስላልበላህ ይመጣልሃል፣በልተህ ማረፍ ይኖርብሃል፡፡
-ስለትህትናሽ አመሰግናለሁ፡፡
-ሚስተር ጆርጅ ምንም አይደለም፡፡

በቀጣዩ ቀን ሰሞኑን አጥቶ የከረመው ንቃትና ብርታቱ ተመልሶለት አማልዶ ከእንቅልፉ ተነሳ፡፡ እዚ መሰንበቱ ስለ ሰለቸው ከሆስፒታሉ

www.path-2-happiness.com

መውጣት በቻልኩ ብሎ ተመኘ:: በጧት የቀረበለትን ቁርስ በልቶ እስከ ዶክተሩ መምጫ ሰዓት ድረስ ጥልቀት ባለው ንባብ ራሱን ለማጥመድ ወሰነ:: በዚህም በአይሁዳዊነትና በክርስትና መካከል አንዳንድ ንጽጽራዊ ምልከታ ያደርጋል:: አይሁዳዊነት ውስጥ ካላት ስፍራ ጋር ለማነጻጸር ሴት በክርስትና ውስጥ ስላላት ስፍራ ያነባል:: በዚህ ርእስ ላይ ከካትሪና ጋር ለመወያየትና ከሐቢብና ከሌቪ ጋር ለመላላክም ይችላል ማለት ነው::

ሐኪሙ መጥቶ ገና ሰላምታ ሲያቀርብለት ጆርጅ ጠየቀ ፦

-የምርመራ ውጤቱን በተመለከተ አዲስ ነገር አለ?

-የለም፣አንዳንዱ ውጤት ሲደርስ አንዳንዱ ደግሞ ገና አልደረሰም፣አትጨነቅ ተረጋጋ::

-እንዲሁ ለመጠየቅ እንጂ ፈጽሞ አልተጨነኩም፣የደረሱት የምርመራ ውጤቶችስ?

-ከመወሰናችን በፊት የቀሩትን ውጤቶች እንጠብቃለን፤አንተን ማስበርገግ አልፈልግም፣ይሁን እንጂ ምናልባት ቀዶ ጥገና ሊያስፈልግህ ይችል ይሆናል::

-ቀዶ ጥገና? !

-አታስብ ብየሃለሁ፣የሚያድነው እግዚአብሔር ነው፣ፈውስም በርሱ እጅ እንጂ በኛ እጅ አይደለም፣እኛ ምክንያት ብቻ ነን::

-ሁኔታዬ እስከዚህ ደረጃ መድረሱ በጣም አስገርሞኝ እንጂ እመነኝ ፈጽሞ አልተጨነኩም::

-አውቃለሁ፣ሁሌ በንባብና በውይይት ተጠመድህ እንጂ ስትጨነቅ ጭራሽ አይታህ እንደማታውቅ ነርሷ ነግራኛለች:: ይኸ እጅግ በጣም ጥሩ ነው . . ውጤቱ ነገ ወይም ተነገ ወዲያ ይደርሳል ብለን እንጠብቃለን::

-ውጤቱን እጠብቃለሁ፣ጥሩ ነገር ይዞ እንደሚመጣ እተማመናለሁ::

-ድንቅ ነው፣ይህ ጥልቅ መተማመን ከምን እንደመጣ ልታብራራልኝ ትችላለህ?

-እግዚአብሔር አምላካችን ከኛ ይበልጥ ለኛ ርህሩህ መሆኑ ጥርጥር የለውም::

-እናም አንተ ሃማኖተኛ ነህ ማለት ነው:: በጥቅሉ ሲታይ ሃይማኖተኞች ለደስተኝነትና ለሕሊና መረጋጋት የበለጠ ብቃት አላቸው:: የሚያስቸግሩን እጣ ፈንታቸውን ይህቺ ዓለማዊ ሕይወት ብቻ መሆኑን የሚያምኑ ኤቲስት ሕሙማን ናቸው::

-ይቅርታ፣ማለት የፈለኩት አንተ ያልከውን አይደለም::ጌታችን በዚህ ዓለም ላይ ከሁሉም በላይ ለኛ ርህሩህ ነው ማለቴ ነው:: በእርግጥ የተናገርከው በጣም ጥልቅ የሆነ ትርጉም አለው:: አማኝ ሰው ከወዲያኛው ዓለም ሕይወት ጋር ራሱን ስለሚያያይዝ ሕይወቱ ቀጣይነት አለው:: ይህ ግን የመለኮታዊ ሃይማኖቶችን ተከታዮች ብቻ የሚመለከት ነው::

-ፈላስፋ መሰልከኝ፤ወዳጄ እኔ ሥራ አለኝ . . ይሁንና ያኛው የቡድሂዝም ወይም የሕንዱ እምነት ተከታይ ይህን ማድረግ ለምን እንደማይችል በአጭሩ ንገረኝ::

-ስንሞት ነፍሳችን ወደሌሎች ፍጡራን ትዛወራለች ብለው ስለሚያምኑ ሌላ መጪ ሕይወት አለ ብለው አይቀበሉም::

-እህህ፣ጥልቀት የሌለው ጥሬ እምነት ነው፤አነጋገርህ ማራኪ ቢሆንም ለመሄድ እገደዳለሁ፤ ደህና ሁን::

ጆርጅ በንባቡና በትንተናው ውስጥ እንደሰመጠ ቀጠለ:: ያቋረጠው ከአደም የተደወለለት ስልክ ነበር . .

-አደም እንደምን አለህ? መጥተህ እንደነበረ ካትሪና ነግራኛለች፣በጣም አመሰግናለሁ::

-ወዳጄ ሆይ ! ሳግዝህ ወይም ሳቀርብልህ የምችለው ነገር ይኖራል?

-ወዳጄ የምትለው ውብ ቃል ነች:: ወዳጄ ላንተ ያለኝ ምስጋና የበዛ ነው:: እመነኝ ካንተ የምፈልገው ነገር ቢኖር እጠይቅህ ነበር . . ኦ ! አዝናለሁ ካንተ የምፈልገውን ነገር አስታወስኩ::

-በል ንገረኝ፤እውነተኛ ወዳጆች መሆናችን እንዲሰማኝ ስለምታደርግ ታስደስተኛለህ::

-የምፈልገው ካንተ ጋር መገናኘት ነው፣ካንተ ጋር የምወያይባቸው ብዙ ርእስ ጉዳዮች አሉኝ::

-ይቅርታ አድርግልኝና ዛሬ ሳይሆን ነገ እመጣለሁ:: ዛሬ አንድ ሰራተኛ ከሥራ ስለቀረ በካፌቴሪያው ድርብ ሥራ አለብኝ::

-መልካም . . ግዴለም ነገ እጠብቀሃለሁ::

ጆርጅ የስልክ ጥሪውን እንዳበቃ ካትሪና ደረሰች:: በደስተኝነት ስሜት ፊቷን በፈገግታ አድምቃ ወደ ክፍሉ ገባች . .

-የኔ ፍቅር ዛሬ እንዴት ይሆን ያደረው?

-ደህና አድሬያለሁ፣በጥሩ ሁኔታ ላ;ይ ነኝ፤አንቺስ እንዴት ነሽ?

-እግዚአብሔር ለፀጋው የተመሰገነ ይሁን::

-ላንቺ የእግዚአብሔር ፀጋ የትኛው ነው?

-የሃይማኖት ፀጋና በቤተክርስቲያን ሥራ መጠመዴ . . እና . . አንተ ባሌ የመሆንህ ፀጋ።

-እናም ሃይማኖተኝነት በአንቺ አመለካከት ፀጋ ነው? !

-ጥርጥር አለው? የምትጽናናበትን ፈጣሪ የሌለህ አምላክ አልባ ከመሆን የከፋ ነገር የለም !

-በአንቺ እምነት የኤቲስቶች ነገር እንዴት ነው?

-በግልጽነትና ያለምንም ዘለም ወለም . . በኔ አመለካከት ኤቲዝም እምነት ሳይሆን ደዌ ነው። የመንፈስና የልቦና በሽታ ነው። የተዛባ አእምሮና ኢምክንያታዊነት ነው። ለፍጥረትና ለፍጡርም በሽታ ነው።

-ሙሉ በሙሉ ካንቺ ጋር እስማማለሁ። ግና ባለቤትሽ በሽተኛ በመሆኑ ፀጋው ምኑ ላይ ነው?

-አንተ ባለቤቴ በመሆንህ ለኔ ፀጋ ነው ማለት እንጂ ያንተ መታመም ፀጋ ነው ማለቴ አይደለም።

-ያም ቢሆን ፀጋነቱ ምኑ ላይ ነው?

-ለሴት ተገቢውን ክብር የማይሰጡና በንቀት ዓይን የሚመለከቱ ብዙ ወንዶች ይገኛሉ። እንደዚህ ዓይነቶቹ ወንዶች እንደ አንተ እንደኔ ፍቅር ለሴቶቻቸው ታማኞች አይደሉም።

-የሴቶችን ክብር ማሳነስና መጨቆን ከሃይማኖተኝነት ጋር በቀጥታ የተዛመደ አይደለም ወይ?

-እንዴት?

-ሃይማኖተኝነት በጨመረ መጠን ሴትን አሳንሶ ማየት ይጨምራል።

-አሁንም ልድገምና ይህን ያለህ ማነው?

-የአይሁድ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ሴቶችን የሚገልጹት እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ ነው።

-ማለት የፈለከው አይሁዳዊነትን ከሆነ ክርስትናን በዚህ ውስጥ ለምን ታጠቃልላለህ?

-ጳውሎስ በቆሮንቶስ 1 ውስጥ ፦ ‹‹ሴቶች በማህበር ዝም ይበሉ፤ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና።›› አላለም ወይ?

-ዛሬ ደግሞ የስነ መለኮት ሊቅ ሆነሃል !

-በሆስፒታል ቆይታዬ በክርስትና ላይ ጥልቅ ንባብ አካሄዳለሁ ብየሽ የለ?

ቶምም እንዲሁ አንቺ እያለሽ ይህንኑ ብሎ አልነበረም?

-መልካም . . ይህ ሃይማኖተኝነትህን ይጨምራል . . ምናልባትም ከፕሮቴስታነት ወደ ካቶሊካዊነት ሊለውጥህም ይችላል።

-ሊሆን ይችላል፤ይሁንና ወደ ርእሳችን እንመለስ። በግልጽ እንነጋገርና የሴት ሁኔታ ክርስትና ውስጥ በአይሁዳዊነት ውስጥ እንዳለው ሁሉ አስከፊ አይደለምን?

-ግልጽ ለመሆንና ውይይቱን ለመቀጠል ቃል ስለገባሁልህ ብጠላውም እቀጥላለሁ።

-የምትጠይውን ነገር እንድትቀጥዪ አልፈልግም፣እርግጠኛ ሁኚ እኔ ምንም ቅር አይለኝም።

-የለም፣ እቀጥላለሁ፤ ለአንተ በጌታ አምነህ እጅ መስጠት እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ለኔ ደግሞ አእምሮና ምክንያታዊ አመለካከት ያስፈልገኛል የሚል ሀሳብ አለኝ።

-ካንቺ ጋር እስማማለሁ። ለእግዚአብሔር ወደው እጅ ሳይሰጡ እምነት ሊኖር አይችልም። ይሁን እንጂ ፍትሕ አስተካካዩ ጌታ ግን እርስ በርስ የሚጣረሱ ወይም አእምሮ ሊቀበላቸው የማይችል ግዴታዎችን ሊጥልብን አይችልም።

-እንዴት?

-እውነተኛ የሆነ ሃይማኖት አእምሮ የማይቀበለውን ነገር ይዞ ሊመጣ ይችላል?

-ምንን የመሰለ ነገር?

-እግዚአብሔር ደካማ ነው፣ወይም ፍጡራን ያስፈልጉታል፣ወይም ሰዎች እንዲገደሉ ያዛልና የመሳሰሉ ነገሮች። እንዲህ ያለው እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል? !

-አንደምታው አደገኛ ቢሆንም አፍ የሚያስዝ አስረጅ ነው።

-የትኛውን አንደምታ ማለትሽ ነው?

-ይህ እንኳ ከርእሳችን ውጭ ነው። ርእሳችን የሴት ስፍራ በክርስትና ውስጥ የሚለው ነው፣አይደለም እንዴ?

-ልክ ነሽ . .

-ግልጽጹን ለመናገር . . ወንድ በሆንኩ ብዬ ብዙ ተመኝቻለሁ። በእርግጥ ሴት ክርስትና ውስጥ ደረጃዋ ከወንዱ ዝቅ ያለ ነው።

-ኦህ፣ልክ እንደ አይሁዳዊነት ማለት ነው?

-ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ከዚያ ቀለል ያለም ሊሆን ይችላል። የተዛቡና ተአማኒነት የሚጎድላቸው ኦሪትና ተልሙድ በጣም አስከፊ የሆኑ ትምህርቶችን አካተዋል፤እንዲያውም ለማሰብ እንኳ በሚከብዱ ወሲባዊ ልቦለዶች የተሞሉ ናቸው . . ወንጌል ውስጥ ግን ሴት ከወንድ ያነሰች መሆኗና የሴቶችን መብት በሚመለከት አንዳንድ መጥፎ ነገሮች ቢኖሩም የአይሁዳዊነትን ያህል የከፋ አይደለም።

-ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚያስበረግጉ ጥቅሶች አጋጥሞኛል።

-እንዴት ያሉ?

-ሴት እንደ ንብረት ትወረሳለች ፦ ‹‹ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ፣አንዱም ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፣የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ፤ነገር ግን የባልዋ ወንድም ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ፣ከእርስዋም ጋር ይኑር።›› ወንድ ወራሽ ከሌለ በስተቀር ሴት ልጅ መውረስ አትችልም ፦ ‹‹ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ፦ ሰው ቢሞት ወንድ ልጅም ባይኖረው፣ርስቱ ለሴት ልጁ ይለፍ፤›› የወር አበባ ያለባትን ሴት አስመልክቶም፦ ‹‹በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች፤የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው። . . መኝታዋንም የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፣በውኃም ይታጠባል፣እስከ ማታም ርኩስ ነው።›› . . ይበቃል ወይስ ልጨምር?

-ይበቃል፣ይበቃል፣ . . እንደ እውነቱ ከሆነ እኛ ዘንድ የሚስተዋለው የሴቶች አስከፊ ሁነታ እንዳለ ሆኖ፣ ክርስትና ሴትን በአይሁዳዊነት ውስጥ ከነበረችበት ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች ነጻ አውጥቷታል፤ሁኔታችንም በአይሁዳዊነት ውስጥ ከነበረው ተሻሽሏል።

-እንዴት?

-ለሴት መብቷን አስከብሯል። ለምሳሌ አይሁዶች በኢየሱስ ዘመን በተራ ምክንያቶች የሰራችው ምግብ ያልጣፈጠ በመሆኑ እንኳ ቢሆን ፍች ይፈጽሙ ነበር። በዝሙት ምክንያት ብቻ እንጂ ፍች እንዳይፈጸም ኢየሱስ አስተማረ። በዚህም በማንኛውም ምክንኛያትና በማንኛውም ጊዜ ይፈታት ከነበረው ወንድ ሥልጣን ነጻ አውጥቷት መዘባበቻው እንዳትሆን አድርጓታል።

-መልካም . . ሌሎች ምሳሌዎችን ማቅረብ ትችያለሽ?

-መጽሐፍ ቅዱስ አንተ በገለጽካቸው ዓይነት ጥቅሶች እንደተሞላ ሁሉ ለሴት አክብሮት በሚሰጡ ሌሎች ጥቅሶችም የተሞላ ነው።

-የሚጋጩና እርስ በርስ የሚቃረኑ እየሆኑ ትክክለኞች ይሆናሉ ተብሎ አይታሰብምና ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፉ ትክክለኞቹ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?

-አስቸጋሪ ነጥብ ነው ያነሳሽው። የውይይቱ መራዘም አድክሞኛል፤ባይሆን ኖሮ ግን እመነኝ ከመወያየት አላፈገፍግም ነበር።

-ሌላ ጊዜ እንወያይበታለን፣ግን አስቸጋሪው ርእስ የቱ ነው?

-ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፉት የትኞቹ ናቸው? የሰዎች የብረዛና የማዛባት እጅ የገባባቸውስ የትኞቹ ናቸው? የሚለው ነው።

-ለአሁኑ ውይይቱን እንቋጨውና ሌላ ጊዜ እንቀጥልበታለን።

-ስለ ትንሣኤ ቤተክርስቲያን አሁን ትነግረኛለህ?

-እንደፈለግሽ፣ቃል እንደገባሁልሽ ወደ ቤተክርስቲያኑ ሄጃለሁ። የሄድኩት ዓርብ ቀን ስለ ነበረ መንገዱ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ነበረበት . .

ጆርጅን ለመጠየቅ የመጣው በራድ አቋረጣቸው . .

-ጆርጅ እንደምን አለህ? . . ካትሪና ሠላም።

-እንኳን ደህና መጣህ !

-መታመምህን ሰምቼ ልጠይቅህ መጣሁ፤ምናልባት አስፈልግህ ይሆናል።

-አመሰግናለሁ።

በራድ ፊቱን ወደ ካትሪና መልሶ መሰሪ ፈገግታ እያሳየ ፦

-ኦ ካትሪናም እዚህ ናትና፣ከቶም ጋር ያለች መስሎኝ።

-ምን ማለት ፈለክ?

-ምንም፣የኔ እመቤት አትቆጪ።

ጆርጅ ተመቻችቶ ተቀመጠና ፦

-ይህ ያንተ ሥራ ወይም አንተን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም።

-ሊሆን ይችላል፤ግና ቶም ስለ ካትሪናና ስለ ውበቷ ብዙ ጊዜ ስለሚናገር እርሱ ዘንድ ትሆናለች ብዬ ገምቼ ነው።

ጆረትጅ ተናደደ ፦

-አንተ ውሸታም ጋጠወጥ ነህ።

-ቶም ወደ ቶራ ቦራ መሄድ እንደምትፈልግ ነግሮኛል፣እርሱም ይዋሻል ማለት ነው?

ካትሪና በአግራሞት ዓኖቿን አፍጥጣ ፦

-ቶራ ቦራ?!

-ከተፈጥሮ ጸባዬ እንድወጣ አታድርገኝማ። በራድ ለጉብኝትህ

www.path-2-happiness.com

አመሰግነሃለሁ፤ሠላም እፈልጋለሁና በል ቶሎ ከዚህ ጥፋልኝ::

-እኔስ እሄድልሃለሁ፣ነገር ግን ቶም ማር በተቀቡ ቃላቶቹ እንዳይሸነግላችሁ፤በቃላት ሽንገላ ኤክስፐርት ነው:: ከፈለጋችሁ የተጫወተባቸውን ሴቶች መጠየቅ ትችላላችሁ . . ጆርጅ እንደምታውቀው ሁሉ ለሁሉም ችግሮችህ ፈውሱ እኔ ዘንድ ይገኛልና ስልክህን እጠብቃለሁ፤ደህና ሁኑ::

በራድ እንደወጣ ካትሪና መናገር እየቃጣት ሶፋው ላይ ተመቻችታ ተቀመጠች . .

-ይህን ሰውየ እጠለዋለሁ::

-እኔንም እንደዚሁ ያስጠላኛል:: መርህም ሆነ ሰብእና የጎደለው ሰው ነው::

-ግና ማለት የፈለገው ምንድነው?

-በየትኛው ጉዳይ?

-እውን ወደ ቶራ ቦራ መሄድ ትፈልጋለህ?

-እህህ፣ቶራ ቦራን ታውቂያለሽ?

-አዎ . . በፓኪስታንና በአፍጋኒስታን የሚገኝ የአሸባሪዎች ተራራ ነው፤ጉዳዩ ምንድነው?

-አንድ እንግዳ ነገር ተከስቶ ነበር:: ከቶም ጋር ስለ ሃይማኖቶችና ስለ እስላም ስንናገር ከሰለምክ ወደ ቶራ ቦራ ትሄዳለህ ብሎ ቀለደብኝ:: ወዲያው ከቶም ዘንድ ስወጣ በራድ ሳላስበው ‹‹ወደ ቶራ ቦራ ትሄዳለህ?›› ሲለኝ ተገረምኩ::

-ጆርጅ፣በራድና ቶም ውሸታሞች ስለሆኑ ስለኔ የሚናገሩትን አትመን::

-የበራድን ውሸታምነት አውቃለሁ:: ቶም ግን አንቺን እንደ ሳመሽ ነግሮኝ ሆን ብሎ ፈልጎ አለማድረጉን ገልጾልኛል::ለምን እንዳመንኩት ግን አላውቅም::

-አዝናለሁ፣ ቶም የተናገረው እውነት ነው:: ይህ ተከስቷል፤ጥፋቱን ከርሱ ይበልጥ የምሸከመው እኔ ነኝ:: ጠጥቼ ባልሰክር ኖሮ ደፍሮ ያደረገውን ባላደረገ ነበር::

-ቶም የፈጸመውን ምናልባት ሳያስበውና እንዴት እንዳደረገው ሳያውቅ ያደረገው ነው ብዬ ልረዳ እችላለሁ:: በጣም የሚገርመው ግን አስካሪ መጠጥ መውሰዱን አሁንም የቀጠልሽበት መሆኑ ነው !

-እውነቱን ለመናገር . .

-ከዚህ ይበልጥ አስገራሚው ደግሞ ፦ ‹‹የወይን ጠጅና የሚያሰክር

መጠጥ አትጠጣ፤›› የሚለውን ጥቅስ ለልጃችን ለማይክል መንገርሽ ነው::

-የሰው ልጅ ለሁሉም ጥፋትና ስህተቱ ፍልስፍናዊ ወይም ምክንያታዊ ትንተና ቢያንስ ለራሱ ለመስጠት ይችላል:: እኔ ግን ለራሴና ላንተም ይበልጥ ግልጽ ሆኜ እናገራለሁ::

-በማቋረጤ ይቅርታ፣ለጥፋትና ስህተቱ ፍልስፍናዊና ምክንያታዊ ትንተና መስጠት ስትዪ ምን ማለት ነው?

-እኛ የማናውቃቸው የሃይማኖት ትምህርቶች ብዙ ናቸው:: የማናውቃቸውና የማንከተላቸው ትምህርቶችም እንደዚሁ በርካታ ናቸው:: ችግሩ ግን ስህተታችንን አምነን መቀበል የማንወድና ጥፋተኞች መስለን እንዳንታይ ሎጂካዊ ወይም ፍልስፍናዊ እንዲያውም ሃይማኖታዊ ትንተና ለመፈለግ የምንባዝን መሆናችን ነው:: ለዚህ ጉልህ ምሳሌ የሚሆነው በክርስትና ውስጥ ያለው የአስካሪ መጠጥ ጉዳይ ነው::

-ይበልጥ ግልጽ ልታደርጊልኝ ትችያለሽ?

-አስካሪ መጠጥ በብሉይና በአዲስ ኪዳንም እርም ተደርጎ የተከለከለ ነው:: በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፦ ‹‹ . . ነገሥታት የወይን ጠጅ ይጠጡ ዘንድ አይገባም፣መሳፍንትም ፦ ብርቱ መጠጥ ወዴት ነው? ይሉ ዘንድ፤እንዳይጠጡና ሕግን እንዳይረሱ፣የድሀ ልጆችንም ፍርድ እንዳያጎድሉ “:: የሚል ሰፍሯል:: በአዲስ ኪዳን ደግሞ ፦ “መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ“ የሚል ተጽፏል::

-በጣም ጥሩ፣እናም በመሰረቱ አስካሪ መጠጥ እርም ነው ማለት ነው:: ግና ከዚህ ክልከላ ውጭ የሆነ እገዳው የማይመለከተው ልዩ ሁኔታ አለ?

-አታሹፍብኝ፤ግልጽ ሆኜልህ ነው የምናገረው:: በእርግጥ ነቢያት አስካሪ መጠጥ ይጠጣሉ የሚል ጥቅስም ሰፍሯል:: እናም ቤተክርስቲያን ውስጥ አስካሪ መጠጥ እንጠጣና ኢየሱስ ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስለራሱ ሲናገር “እውነተኛው የወይን ግንድ እኔ ነኝ“ ብሏል:: ስለ ተከታዮቹም ሲናገር ፦ “እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ “::ብሏል እያልን ፍልስፍናዊ ማመካኛ እንደረድራለን ::የወይን ውሃ ተክሉን ለመመገብ ወደ ቅርንጫፎች እንደሚሰራጭ ሁሉ፣ቅዱስ ደሙ ደማችንና የሰራ አካላችንን ቅዱስ ለማድረግ በደም ሥራችን ውስጥ መሰራጨቱን ለማመልከት ኢየሱስ የወይን ጠጅን በምሳሌነት ተጠቅሟል፣እያልን እንጎነጫለን:: ኢየሱስ ግን የወይን ጠጅን እንድንደሰትበትና እንድንሰክርበት አልሰጠንም:: የሰጠን አማኞች ብቻ እንጂ ሌሎች የማይረዱትና የሚያነጻ ምስጢራዊ ዓለማ

www.path-2-happiness.com

አድርጎ ነው ብለን እንፈላሰፋለን።

- ኦህ . . ድንቅ ፍልስፍናዊ ፈጠራ ነው !
- በኔ መዘባበትህን አቁም፣አለዚያ ውይይቱን አቆማለሁ።
- አህሀ፣መልካም እንግዲያውስ አስካሪ መጠጥ መጠጣት የተቀደሰ ተግባር ሆኗል ማለት ነው !
- ሃይማኖት እንዲሆን ለምንፈልገው ነገር እንዴት ፍልስፍናዊና ምክንያታዊ ትንተና እንደምንሰጥ አየህ?
- እንዲህ ዓይነቱ ነገር ተከታዮቹ ያሻቸውን ነገር ባሻቸው ጊዜ ሊሚፈጥሩለት ሰው ሰራሽ ሃይማኖት እንግዳ ነገር አይደለም። ከእግዚአብሔር ለተላለፈ መለኮታዊ ሃይማኖት ግን ተቀባይነት የለውም።
- ወየው፣አንተ መቼም ክርክር አይሰለችህም፣እኔ ግን ማይክልና ሳሊ መምጫቸው ስለሆነ ወደ ቤት ለመሄድ እገደዳለሁ። እንደገና ተመልሼ ለመምጣት እሞክራለሁ . . ውይይቱንም እንቀጥላለን። ግን እኔ ከውስጥ ራሴን ስለምሟገት በተለይ ደግሞ ግጭቱ በሃይማኖታችን ውስጥ ብቻ ሳይሆን በገዛ ራሳችን ውስጥ ጭምር ስለሆነ ይደክመኛልና ክርክርህን ቀለል አድርግልኝ።
- የኔ ፍቅር መመለስሽን እጠብቃለሁ። አስቀይመሽ ከሆነም ይቅርታ አድርጊልኝ፣ራስሽን እንድታስጨንቂም አልፈልግም። ዛሬ መመለስ ካልተመቸሽም ችግር ለውም።

ካትሪና ግንባርና ግንጮቹን ስማ ወጥታ ሄደች . . በተካሄደው ውይይት በጣም ተደስታለች። ለመጀመሪያ ጊዜ ራሷን እንደ ገለጸችና አእምሮዋ ስሜቷን እንደረታ ታምናለች። ጆርጅም በእጅጉ ተደስቷል። ካትሪና ዝም ብሎ አምኖ በመቀበል ካባ የተሸፈነና ከሚጠበቀው በላይ የሆነ የፍልስፍና፣የሎጂክና የዕውቀት . . አቅም እንዳላት ለመገንዘብ ችሏል። ጆርጅ ካትሪና ከሄደች በኋላ በጆርባ ተኝቶ ከራሱ ጋር መነጋገር ጀመረ ፦ ጥልቅ ውይይትና ክርክር ነበር። ካትሪና አስካሪ መጠጥ ለምን እንጠጣለን ከሚለውን ጥያቄ ሳትፋጠጥ በግሩም ስልት እንዴት ማምለጥ እንደ ቻለች አስታውሶ ፈገግ አለ።

ተስፋና ስጋት

www.path-2-happiness.com

10 ተስፋና ስጋት

ተስፋና ስጋት

(1)

ጆርጅ በክርስትና ላይ የሚያደርገውን ጥልቅ ንባብ ቀጥሎበታል። ትኩረት ያደረገው በብሉይና አዲስ ኪዳኖች ትክክለኛነትና በደረሰባቸው የመበረዝ፣ የመምታታት፣የመዛባትና የጭማሬዎች ጉዳይ ላይ ነው። ይህ ርእስ ስሜት የሚኮረኩር ከመሆኑ አንጻር ወደዚህ ለመግባት ሲያቅማማ መኖሩ ታሰበው። ይሁን እንጂ የራሴ የሚለው ቅዱስ መጽሐፍ ምን ያህል ከመበረዝና ከመለወጥ የተጠበቀ ትክክለኛና ተአማኒ መጽሐፍ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ርእሱን በጥልቀት ማጥናት የግድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እኛ ዘንድ ጥርጣሬ የሚነሳበት ሆኖ መኖሩ በጣም አሳሳቢና አስቸጋሪ ነገር ነው። ምሳ እስከ መጣለት ጊዜ ድረስ ንባቡን የቀጠለው ጆርጅ ምሳውን የበላው እያነበበ ነበር . . በንባቡ ተጠምዶ እንዳለ ሙቀቱን ለመለካት የመጣችው ነርስ እንዲህ አለችው፦

- ፈተና ያለበት ተማሪ ትመስላለህ!
- አህህ፣አዎ የሕይወት ትምህርት ቤት ተማሪ ነኝ። የምፈተነው ፈተናውን አልፌ መታደልን ለማግኘት ወይ ደግሞ ወድቄ ዕድለ ቢስነትን ለመቀበል ነው።
- ፈላስፋ ትመስላለህ!
- ቁም ነገሩ ፈተናውን ማለፌ ነው።
- የሕይወትን ፈተና ማለፍ አስቸጋሪ ነው። የሚያሳዝን ነው አብዛኞቹ ሰዎች ፈተናውን ይወድቃሉ።
- ለምን?
- ለመውደቅ ስለሚፈልጉና ማለፍ ስለማይሹ።
- ወይ እየተፈላሰፍሽ ነው፣ወይ ደግሞ በአስገራሚ ሁኔታ ገሃዱን ሁኔታ እየተጻረርሽ ነው።
- እንግዲያውስ እየተፈላሰፍኩ ነኝ፤ሥራ ስላለብኝ ፍቀድልኝ ልሂድ።

በአነጋገሯና ጥልቅ የሆነ ፍልስፍና እንደ ዘበት ወርወር ካደረገች በኋላ እንዴት ፈጥና እንደ ሄደች ገርሞት ጆርጅ ፈገግ አለ . . አብዛኛው ሰው

www.path-2-happiness.com

የሕይወትን ፈተና ለመውደቅ ይፈልጋል ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ሊሆን ይችላል?! ለማንኛውም እዚሁ ሆስፒታል ውስጥ አብራው ስለላለች ሲያገኛት ማብራሪያ ይጠይቃታል . .

ጆርጅ በንባብ ተጠምዶ እያለ ቶም መጣ . . ጆርጅ ግን ቶም ገብቶ አጠገቡ እስከ ቆመበትና እየሳቀ ትከሻውን መታ መታ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ መምጣቱን አላስተዋለም ነበር . .

- አሁን ክርስትናን ከነፈለጎቹ በሚገባ የግድ አውቀሃል ማለት ነው።
- ቶም . . እንኳን ደህና መጣህ።
- ዛሬ እንዴት ነህ?
- እንደምታየኝ ዛሬ ደህና ነኝ፤ዛሬ ትመጣለህ ብዬ አልጠበኩም ነበር።
- ካትሪና ላትኖር ትችላለች ብዬ ያሰብኩትን ጊዜ መርጬ ነው የመጣሁት።
- ለምን?
- ስለ ሳምኳት የጥፋተኝነት ስሜት የምሰማኝ በመሆኑ ነው፤ለምን እንዳደረኩት አላውቅም፤ከርሷ መገናኘቴ አያስደስትህም ይሆናል፣የምናገረውንም አምነህ አትቀበልኝም ብዬ አስባለሁ፤ይህን ብታደርግ እውነት አለህ።

ጆርጅ ፈገግ አለና፦

- ነገሩ ቀላል ነው፤ግና ለበራድ ካትሪናን እንደምትወዳት፣ሁሌም እንደምትስማትና እንደምትደሰትባት ለምን ትናገራለህ?
- እኔ እንደዚህ ብየው?!
- ይህ ከኔ ሳይሆን የቢሮህ ኃላፊ በራድ ዛሬ ሊጠይቀኝ መጥቶ የነገረን ነው።
- ፊትም አላመንከኝም፣አሁን እንዴት አድርገህ ታምነኛለህ? እርሱ እኮ ውሸታም ወራዳ ነው።
- ይህን የሚናገረው የቢሮህ ኃላፊ ነው። ዛሬ ጧት ካትሪና ባለችበት ነው የተናገረው። እኔ ወደ ቶራ ቦራ እንደምሄድስ አልነገርከውም? ወይስ ይህንንም ፈጥሮ ነው ያወራው?
- ኦህ፣ፍላጎቴ አልነበረም ግን አንዳንድ ነገሮችን ልነግርህ እገደዳለሁ።
- በል ንገረኝ።
- የቢሮዬ ኃላፊ ወይም የኔ ጸሐፊ እኩይና ስነ ምግባር የጎደለው ሰው መሆኑን አውቃለሁ። ቀደም ሲል በሴቶች ስጫወትባቸው ያግዘኝ ስለ ነበረ ዝም ብዬ አልፈው ነበር። እመነኝ ካንተ ጋር ከተገናኘሁበት ቀን ጀምሮ ግን ለምን እንደሆነ እንኳ ተለውጫለሁ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ንባቤ፣ውይይቴና ምርምሬ ሁሉ በሃይማኖቶችና መታደልን በሚያመጡ ርእሰ ጉዳዮች ላይ

ብቻ ያተኮረ ሆኗል። አዲሱ የኔ ሁኔታ በራድን ያላስደሰተው በመሆኑ ብዙ ጊዜ የጨቀጨቀኝ ከመሆኑም በላይ በእጁ የሚገኙና ከአንዳንድ ሕሙማን ሴቶች ጋር የተነሳኋቸውን የቆዩ ፎቶግራፎች ይፋ ለማድረግ አስጠንቅቆኛል። . . በተጨማሪም በኔ ክፍል ውስጥ በምስጢር ካሜራና ድምጽ መቅጃ ማጥመዱን ዘግይቼ ደርሼበታለሁ። በዚህም ለሰዎች የምናገረውን፣የስልክ ጥሪዎቼንና የማደርገውን ሁሉ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በድምጽና በምስል ይቅርጽ ነበር። ይህን የደረስኩበት ከሦስት ቀናት ወዲህ ብቻ ሲሆን የመረረ ጠብ በመካከላችን ተፈጥሮ ከሥራ ለማባረር ስዝትበት እርሱም ፎቶገግራፎቹን ከነድምጼ በቀጥታ ኢንተርኔት ላይ ለመልቀቅ ዝቶብኛል። ይህም የሕክምና ፈቃዴን መነጠቅ ማለት ነው። አሁን ምናባቴ እንደማደርግ ቸግሮኛል። የምናገረውን ታምናለህ?! ባታምነኝም ምክንያት አለህ . .

- በከፍተኛ ደረጃ ልቦለድ ትረካ ቢመስልም እውነት መሆኑን የሚመሰክሩ ማስረጃዎች አሉኝ።
- የምን ማስረጃ?
- ካንተ ጋር በነበረኝ የመጨረሻው ቀጠሮ ከቢሮህ ወዲያው እንደወጣሁ በራድ አግኝቶኝ ስለ ቶራ ቦራ ነግሮኝ ነበር፤አብረን በነበርንበት ጊዚ አንተ ፈጽሞ እንዳልወጣህና እርሱም ወደ ክፍሉ እንዳልገባ እርግጠኛ ነኝ።
- ለምን አልነገርከኝም?
- ነገሩ ከፍተኛ አግራሞት ነበር የጫረብኝ፤ግና ምናልባት አስደናቂ አጋጣሚ ወይም ከሩቅ መናበብ የሚሉት ይሆናል ብዬ ዝም አልኩ።
- እንግዲያውስ ሙሉውን እውነት ነግሬሃለሁ፣ማመን አለማመኑ ያንተ ፈንታ ነው።

ነርሷ በሩን አንኳኳችና በችኮላ ገባች . .

- በማቋረጤ ይቅርታ፣ሐኪሙ ካንተ ጋር በአስቸኳይ መነጋገር ስለሚፈልግ አሁን ወዳንተ እየመጣ ነው።
- ጥሩ ይምጣ፣ግን ነገሩ ምን ይሆን?

ሐኪሙ መጣ . .

- ጆርጅ እንደምነህ? ለድንገተኛ ጉብኝቴ ይቅርታ፣ጉዳዩ አጣዳፊ በመሆኑ ነው።
- እሽ፣ግባ።
- ቀሪዎቹ የምርመራ ውጤቶች ከአፍታ በፊት ደርሰዋል። በጣም አስቸኳይ

የሆነ ቀዶ ጥገና ያስፈልገሃል። ነገ በዚህ ሰዓት መደረግ ይኖርበታል።

-ነገሩ አሳሳቢ ሳይሆን አልቀረም መሰለኝ።

-እውነቱን ለመናገር አዎ ለማለት እገደዳለሁ፤በዚህሰዓት የመጣሁትም በዚህ ምክንያት ነው። ከነገ ስድስት ሰዓት በፊት በጉዳዩ ላይ አስበህበት ስምምነትህን በፊርማህ ለማረጋገጥ ጊዜ አለህ።

-ማሰብና መፈረም . . ማረጋገጥ!

-በዝርዝርና በግልጽ ላብራራልህ ይገባኛል። የሙቀት መጠንህን ከፍ የሚያደርገው ቫይረስ ከያንዳንዱ ከፍታ ጋር ከአንጎልህ ሕዋሳት የተወሰኑ ክፍሎችን እያበላሸ መሆኑን ደርሰንበታል። ትኩሳቱ ነገ ማታ ከሁለት ሰዓት በኋላ ይመጣብሃል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ቀዶ ጥገናውን ከጀመርንልህ በኋላ እንጂ አይመጣም ማለት ነው። የቀዶ ጥገናው የስኬታማነት ዕድል 60% ብቻ ነው።

-ቀሪው 40% ምን ይሆናል?!

-በአንዳንድ የአንጎል ክፍሎች ውስጥ እንከን ይኖራል ማለት ነው።

-ይህ ምን ማለት ነው?

-አዝናለሁ ውጤቱን አሁን መተንበይ አልችልም . . ምንም ነገር ላይከሰትም ይችላል፤ማንኛውንም ሌላ ነገር ሊያስከትልም ይችላል።

-አሁን ከኔ የሚፈለገው መስማማቴን ገልጬ በፊርማ ማረጋገጥ ነው!

-አዎ።

-ቀዶ ጥገናው እንዳይደረግልኝ ባልስማማ ምንድነው የሚሆነው?

-ስምምነትህ ተጠይቆ እምቢ ማለትህን በማረጋገጥ ትፈርማለህ . . ሁኔታው ለኛ አዲስ ቢሆንም ቀዶ ጥገናውን ማድረጉ ላንተ ተመራጭ ነው የሚል እምነት አለኝ። ሌላ ጥያቄ ይኖረሃል?

-በጉዳዩ ላይ ሌሎች ተጨማሪ አስፈላጊ መረጃዎች ከሌሉ ጥያቄ የለኝም።

-ሌላ ነገር የለም፤ያነጋገርኩህ የሕክምና ቡድኑ ተሰስቦ ከወሰነ በኋላ ሲሆን ይህ የሁሉም የጋራ አቋም ነው። ሌላ ጥያቄ ካለህ በማንኛውም ጊዜ ለነርሶቹ ብትነግራቸው ወዲያውኑ ደውለው ስሚነግሩኝ ምላሽ ማግኘት ትችላለህ። በጉዳዩ አስበህበት ከነገ ስድስት ሰዓት በፊት የስምምነት ማረጋገጫ ፍርማህን እንደምታኖር ተስፋ አደርጋለሁ።

-አስቤበትና ተማክሬ መልስ እሰጠሃለሁ።

-እንደ ልማድህ ነገሮችን በማቅለል ሳትጨነቅ መውሰድ አስፈላጊ ነው። ሕይወት፣ሞትም ሆነ ሕመም የሰው ልጆችን ሚያጋጥሙ የተለያዩ

ሁኔታዎች በመሆናቸው እንደ ሁኔታው ልንቀበላቸው ይገባል። አሁን ልሂድ፣ ጧት ሦስት ሰዓት ላይ እመጣለሁ፤ካዚያ በፊት ጥያቄ ካለህ ለነርሷ ንገራትና ይደውሉልኛል።

-አመሰግናለሁ ዶክተር።

ዶክተሩ ወጣ፤የቶም ድምጽ እስካቋረጠው ድረስ ጆርጅ በዝምታ ተዋጠ . .

-ጆርጅ . . የታደልን ደስተኞች ካልሆን በስተቀር ሕይወት ትርጉም የላትም። በዳግም ሕይወትና በምርመራ የማናምን ከሆነም ሞትም ትርጉም የለውም። የሞትና የሕይወት ፍልስፍና ምንኛ አስደናቂ ነው!

-ይልቁንም የመኖርና የሕልውና ፍልስፍና እራሱ በጣም አስገራሚ ነው! ለምን ዓለማ ነው የተፈጠርነው? መጨረሻችንና መመለሻችንስ ወዴት ነው?!

-ታዲያ ምኑን ነው የምታስበው?!

-ሕይወትን ነው ወይስ ሞትን ነው? የምፈልገው ብዬ ሳስብ ነበር።

-ማሰብ አያስፈልግህም፤ሕይወትን የማይፈልግ ማንም ሰው የሌም።

-ታዲያ ሰዎች ለምን ራሳቸውን ይገድላሉ? በዓለም ላይ ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች ቁጥር በየጊዜው እያሻቀበ አይደለም ወይ? እኔ ራሴ ባንድ ወቅት ይህንኑ ተመኝቼ አልነበረምን?

-በተለይ ያንተው አስገራሚ ነው። ራሱን የሚገድል ሰው እድለቢስነቱን ነው በሌላ እድለቢስነት የሚቋጨው። መታደልን ላገኘ ሰው ግን ይህ ፈጽሞ አስፈላጊው አይደለም።

-ራሴን ለመግደል በሄድኩበት ጊዜ ፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ ነው የጠበበኝ፤መጠን በሌለው ጭንቀትና የእድለቢስነት ስሜት ውስጥ ነበርኩ። ልክ አንተ እንዳልከው መከፋቴን በመከፋት ለማክተም እፈልግ ነበር።

-መሞት ነው ወይስ መኖር ነው ምፈልገው ብለህ ለማሰብ አሁንም ባለመታደል ሁኔታ ውስጥ ነህ?

-እውነቱን ለመናገር በመታደል መንገድ ፍለጋ ላይ ከተሰማራሁበት ጊዜ ጀምሮ የመታደል ስሜት እየተሰማኝ ነው። መንገዱን ጀምሬ እንዲህ ከተሰማኝ ጉዞውን ጨርሼ ስደርስበት እንዴት ይሆን? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ።

-እናም ወደ መታደል ለመድረስ ሕይወትን የሙጥኝ ብለህ ያዝ።

-እኔ ሕይወትን እፈልጋታለሁ፤ጥያቄው ግን ሕይወትስ ትፈልገኛለች ወይ? ነው። ልጃችን ማሪ ከሞት ጋር ስትታገል አየኋት፣ግና ሞት አሸነፋት . .

www.path-2-happiness.com

-እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፣እርሱ ይረዳሃል።

-እህህ፣ቶም የሚተማመን ሃይማኖተኛ ወጥቶሃል ማለት ነው!

-ተለውጫለሁ ብየህ የለ? እመነኝ እኔ ራሴ እለወጣለሁ ብዬ ጠብቄ አላውቅም ብቻ ሳይሆን ለመለወጥም እቅድ ኖሮኝ አያውቅም። እንዴት እንደ ተለወጥኩ አላውቅም፣ግን በእርግጠኝነት ተለውጫለሁ።

-በምታየው ሁኔታ ላይ ብሆንም እንኳ ጥያቄ አለኝ፦ ቀደም ሲል በነበርክበት ነው ወይስ አሁን ባለህበት ሁኔታ ነው ይበልጥ ደስተኛ የሆንከው?

-ባለፈው ጊዜ የአካልና የመንፈስ ደስታን አስመልክተህ በኢ-ሜይል ለላክልኝ ጥያቄ መልስ ልሰጥህ እችላለሁ። መንፈሴን ዕድለቢስ በማድረግ ነበር አካሌን ሳስደስት የነበረው፣ይህን በማድረጌም ሁለቱንም መንፈሴንም አካሌንም ለእድለቢስነት እዳርግ ነበር!

-አሁንስ?

-አሁንም ለመታደል አልበቃሁም፣ይሁን እንጂ ቢያንስ ቀደም ሲል በነበርኩበት አስከፊ ሁኔታ ውስጥ አይደለሁም።

-በኔ ቦታ ብትሆን ኖሮ መሞትን ነው ወይስ መኖርን ነው የምትመኘው?

-ያለ ጥርጥር ሕይወትን ነው የምመርጠው። ምናልባት ቀደም ባለው ጊዜ ብትጠይቀኝ ኖሮ መሞትን እመርጣለሁ . . የመሞት መርገምት ለመኖርን መርገምት እልባት ይሰጣል እልህ ነበር።

-ራሴን ለመግደል ስሄድ መንገድ ላይ ያገኘሁት ሽማግሌ በጣም የታደለና ከሕጻን አያቱ ጋር በመጫወት በጣም ደስተኛ እንደነበረ አስታውሳለሁ። አድራሻውን ወስጄ ቢሆን ኖሮ እያልኩ ሁሌ እቆጫለሁ።

-ዋናው ነገር አሁን ሐኪሞች ከኛ የተሻለ ስለሚያውቁ፣ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ተስማምተህ መፈረም አለብህ የሚል ሀሳብ አለኝ። መጀመሪያ ግን ከካትሪና ጋር እንድትመካከር ነው የማሳስብህ።

-ያለ መሳካት ዕድሉ 40% በመሆኑ አንዳንድ ጉዳዮችን ማስተካከል የግድ ቢሆንም የኔም ሀሳብ ይኸው ነው . .

-ወዳጄ መልካሙንና ስኬቱን ብቻ አስብ፣የተመኘኸው ብቻ ነው የሚያጋጥምህ። ሁላችንም ለሁሉም ሁኔታዎች ራሳችንን ማዘጋጀት ችግር የለውም . . ከዚህ በሽታ ተገላግለህ የመታደል ፍለጋ ጉዞህን በድል ታጠናቅቃለህ፤ወደ መታደል ስትደርስ ግን እኔንም መውሰድ እንዳትረሳ . . በጉዳዩ ላይ እንድታስብበት አሁን ትቼህ እሄድና ነገ መጥቼ እጠይቀሃለሁ፣ደህና ሁን።

ጆርጅ በጀርባ ተኝቶ ዓይኑ እያየ ልጁ ማሪ የተጋፈጠችውንና ምናልባትም እርሱም በቅርቡ ሊጋፈጠው ስለሚችለው ሞት ምንነት ማሰላሰል ጀመረ። ለመሆኑ ሞት ራሱ ምንድነው? ሕይወትስ ምንድነው? ሞት ከዚህ ዓለም ጣጣዎች መገላገያ ነው? ወይስ የዚህ ዓለም ደስታ ፍጻሜ ነው? የመጀመሪያው ከሆነ አያ ሞት እንኳን ደህና መጣህ፣ሁለተኛው ከሆነ መታደልን አግኝቶ ምንነቱን አውቋል ማለት ነው። እንዲህ በማሰብ ላይ እያለ በፌዝ ፈገግ አለና ‹‹ወዴትም የማያደርስ ፍልስፍና እየተፈላሰፍኩ ልሞት ነው መሰለኝ›› አለ ለራሱ . .

የስልክ ጩኸት ከሀሳቡ አባነነው። አደም ነበር የደወለው . .

-ሃሎ፣እንደምነህ አደም?

-ጆርጅ እንዴት ነህ? ልጠይቅህ ፈልጌ ነው የደወልኩት። አሁን እንዴት ነው?

-በመኖርና በመሞት መካከል ነኝ፤ለማንኛቸው ይበልጥ ቅርብ እንደሆንኩ አላውቅም።

-አልገባኝም፣እንዴት ማለት?

-60% ሕይወት 40% ደግሞ ሞት ወይም ዘላቂ ጉዳት።

-ምንም አልገባኝም፤እየቀለድክ ከሆነ እኔ ይህን ቀልድ አልወደውም።

-ቀልድ በሆነ፣ግና እውነት ነው . . ምናልባት የመሳካት ዕድሉ 60% የሆነ ቀዶ ጥገና ነገ ሳይደረግልኝ አይቀርም።

-በማንኛውም ሁኔታ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ።

-ዛሬ ብንገናኝ ምኞቴ ነበር።

-አሁን የሕሙማን መጠየቂያ ሰዓቱ ስላለፈ ዛሬ የሚሆን አይመስለኝም፤በጊዜ ለምን አልደወልክልኝም ነበር?

-እኔ እንጃ፣ነገ በጧቱ የመጠየቂያ ሰዓት ልትመጣ ትችላለህ?

-አዎ በሚገባ፣አሁን መምጣት ብችል እንኳ በመጣሁ ነበር። የማረጋግጥልህ ነገር ቢኖር ግን ዕድሜ በእግዚአብሔር እጅ እንጂ አስፈላጊ ምክንያት ቢሆኑም በሐኪሞች እጅ አለመሆኑን ነው።

-ሞትን ፈርቼው ወይም ምንም ቁብ ሳልሰጠው ቀርቼ እንደሆነ አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር የሕይወትን ቅደም ተከተል ሙሉ በሙሉ የሚለውጥ ግዙፍ እውነታ መሆኑን ብቻ ነው።

-አይዞህ አትፍራ፣ተስፋ አትቁረጥ፣እግዚአብሔር ከኛ ከራሳችን እንኳ ይበልጥ ለኛ ርህሩህ አዛኝ ነው።

www.path-2-happiness.com

-እመነኝ ፈርቼ ይሆን ወይስ ተረብሼ? ምን እንደሆንኩ አላውቅም:: የሚሰማኝ ነገር ቢኖር ሕይወቴን ዳግም ሥርዓት ማስያዝ እንዳለብኝ ብቻ ነው . . በራሴ ሳሾፍ አታይም? . .

-የምን ሹፈት ነው?

-ሞትን ስፈራ ሕይወቴን ሥርዓት ለማስያዝ ወሰንኩ:: ገና ወደ ሕይወት በማምራት ላይ እያለሁ እንጂ ሕይወትን ለቅቄ ስሄድ አልነበረም ሕይወቴን ሥርዓት ማስያዝ ይበልጥ ተገቢ ይሆን የነበረው?

-ቀደም ብሎም ሕይወትህን ሥርዓት ለማስያዝ ጥረት በማድረግ ላይ ነበርክ፣ምን ያህል እንደቀረ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም የማያውቅ ቢሆንም፣ ቀሪውን ሕይወት ሥርዓት ማስያዝም የግድ ነው . . እኔ ተስፋ ማድረግ፣በጎውን መመኘትና መጠበቅ ነው ደስ የሚለኝ:: ተስፋ መቁረጥና በጎ በጎውን አለማየትን እጠላለሁ::

-ባልተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ ነኝ፣እሞታለሁ ብለህ ትጠብቃለህ?

-በእግዚአብሔር ፈቃድ ትኖራለህ፣በፍለጋ ጉዞህም ወደ መታደል ትደርሳለህ፤ከዚያ በኋላ የዓለማዊ ሕይወትንና የሞትን ትርጉም ትረዳለህ::

-‹‹ከሞት በኋላ ያለው ሕይወታችን›› የሚለው አገላለጽ ውብ አገላለጽ ነው:: በዚህ ላይ ነገ ካንተ ጋር እወያያለሁ:: ይቅርታ አድርግልኝና ላሳውቃት አሁን ለካትሪና ለመደወል እገደዳለሁ::

-ልክ ነህ . . ባለቤትህን ማማከር ይኖርብሃል:: አራዝሜብህ እንደሆነ አዝናለሁ፤እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን፣በሰላም ያገናኝን::

-አደም ላንተ ያለኝ አክብሮት ወሰን የሌውም፣ጧት እጠብቀሃለሁ፣ደህና ሁን::

የአደም ቃላት ጭንቅላቱ ውስጥ እየደወሉ የስልክ ጥሪውን አበቃ:: ‹‹ዕድሜ በእግዚአብሔር እጅ እንጂ በሐኪሞች እጅ አይደለም››፣‹‹እግዚአብሔር ከኛ ከራሳችን እንኳ ይበልጥ ለኛ ርህሩህ አዛኝ ነው››፣‹‹ተስፋ ማድረግ፣በጎውን መመኘትና መጠበቅ ነው ደስ የሚለኝ:: ተስፋ መቁረጥና በጎ በጎውን አለማየትን እጠላለሁ››፣‹‹በፍለጋ ጉዞህም ወደ መታደል ትደርሳለህ፤ከዚያ በኋላ የዓለማዊ ሕይወትንና የሞትን ትርጉም ትረዳለህ::›› የሚሉትን የአደም አባባሎች ሳያስብ ሲደጋግማቸው ራሱን አገኘ . . የአደም ቀላል ግን ጥልቅ ቃላት ውስጡን ለምን ሁሌ እንደሚያንቀጠቅጡ አያውቅም:: ምስጢሩ በራሳቸው በቃላቱ ምክንያት ነው? ወይስ እውነተኛ በመሆናቸው? ወይስ እንዴት እንደሚቆጣጠረው በማያውቀውና አሁን በሚገኝበት ያልተረጋጋ

ሁኔታው ምክንያት ይሆን? . .

ጆርጅ እየተግተለተሉ የመጡ ሀሳቦቹን ገታ አደረገ:: ለካትሪና ደውሎ ስለ ጉዳዩ ማማከር የግድ ነበር . .

-ሃሎ ካትሪና፣ናፈቅሽኝ፤ዛሬ ትመጪያለሽ ብዬ ጠብቄ ነበር::

-ልመጣ ነበር፣ዳሩ ቀላል ጉዳይ አጋጥሞኝ ቀረሁ እንጂ::

-በሰላም ነው?

-ሰላም ነው፣ሳሊ የቤት ሥራ ስለነበራት የኔ እገዛ አስፈልጓት ነው::

-አሁን የት ነሽ?

-እቤት ነኝ፣ጆርጅ ችግር አለ እንዴ?

-ኣይ፣አንድ ነገር ላማክርሽ ፈልጌ ነው:: እኔ ከተስማማሁበት ነገ የቀዶ ጥገና ሊደረግልኝ እንደሚችል ሐኪሙ ነግሮኛል::

-ነገ ነገ ! ጥድፊያው ምንድነው? የምን ቀዶ ጥገና ነው?

-ሐኪሙ የነገረኝ ነገ ምሽት ሁለት ሰዓት ላይ ማድረጉ ተመራጭ መሆኑን ነው::

-የኔ ፍቅር . . ምን እያሰብክ ነው? አሁኑኑ ወደ ሆስፒታል እመጣለሁ::

-ነገ ጧት ብትመጪ የሚሻል ይመስለኛል::

-ቀዶ ጥገናው የምንድነው?

-የአንጎል ቀዶ ጥገና ነው::

-የአንጎል!! አደገኛነት አለው?

-ምናልባት:: ዋናው ነገር የመሳካት ዕድሉ 60% ብቻ ቢሆንም መደረጉ ተመራጭ ነው የሚል አቋም አለው ሐኪሙ፤አንቺስ ምን ታስቢያለሽ?

-የምለውን አላውቅም፣ሌሊቱን በሙሉ ስላንተ እጸልያለሁ፤ማይክልና ሳሊን ይዤ ጧት እመጣለሁ::

-የኔ ፍቅር እጠብቅሻለሁ . . ደህና ሁኚ::

ካትሪና ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች ተከናንባ ተኛች:: የጆርጅን በድንገት ከሕይወቷ ውስጥ አለመኖር መሳብ ከበዳት . . ቀዶ ጥገናው ሳይሳካ ቢቀርስ? . . ዘላቂ አካለ ስንኩልነት ቢገጥመውስ? . . እንደገና ተነሳችና ለጆርጅ መጸለይ ጀመረች . .

ጆርጅም ስለ ካትሪና እና ስለ ሁለቱ ልጆች በማሰላሰል ተጠመደ:: በዋነኛነቱ ያሳሰበው የገንዘብ ጉዳይ ነው . . ለካትሪና እና ለልጆቹ ጠቀም ያለ ገንዘብ ሊሆን የሚችለውን የሕይወት መድህን ዋስትናውን ማደሱን አስታውሶ ፈገግ አለ:: ከሚሰራበት ኩባንያ ጋር የገባው የሥራ ውልም ጥሩ ገንዘብ ሊያስገኝ

www.path-2-happiness.com

የሚችል መሆኑና በተለይም ለሕመም የተጋለጠው ለኩባንያው ሥራ ጉዞ ላይ እያለ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን በማሰብ አሰበ፤ይሁን እንጂ ስለራሱ እንጂ ለማንም ግድ የሌለው ካኽ ከሞትኩ ምንም ነገር አይሰጥም የሚል ጥርጣሬረ አደረበት . . መሰል የሀሳብ ግጭቶችን በማስተናገድ ላይ እያለ እንቅልፍ ይዞት ሄደ . .

(2)

ጆርጅ አማልዶ ከእንቅልፉ ነቃ፤ባስተናገዳቸው የሀሳብና የጥያቄ ማእበሎች የተጨናነቀው ጭንቅላቱ እየከበደው ቁርሱን በላ፡፡ በአብዛኛው ቀዶ ጥገናው እንዲደረግ ወደ መወሰኑ ያደላ ቢሆንም ጭንቀት ጠበቅ እያለበት ነው . . ከቀዶ ጥገናው በፊት ምን ማድረግ ይኖርበታል? . . ካትሪና እና ልጆቹ ፈጽሞ ከአእምሮው ሊርቁ አልቻሉም . .

የጧቱ የሕሙማን መጠየቂያ ሰዓት እንደደረሰ አደም በፈገግታ ወደ ክፍሉ ከተፍ ሲል አየው . .

- የምሥራች ንገረኝማ . . እንዴት ነህ?
- ደህና ነኝ . . አዲስ ነገር የለም፤ምንም ነገር በርሱ እጅ ባይኖርም ሐኪሙን እየጠበቅሁ ነኝ፤ከአፍታ በኋላ ይደርሳል፡፡
- ልክ ነህ፣በሐኪም እጅ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የሰው ልጅ እጅ ምንም ነገር የለም፡፡
- ታዲያ ነገሮች ሁሉ በማን እጅ ናቸው?!!
- ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ናቸው፡፡
- አደም አምላክህ ማነው?
- የኔ አምላክ ያንተና የዓለማት ሁሉ አምለክ ነው፤አሁን ይህን ተወኝ፡፡
- እናም አንተ ፕሮቴስታንት ነህ ማለት ነው?!
- መታደልን ፍለጋ ፕሮጄክተህ ተሳክቶ ለመታደል ስትበቃ ካንተ ጋር እሆናለሁ፡፡
- ያ ከቀዶ ጥገናው በኋላ በሕይወት ተርፌ ከኖርኩ የሚሆን ነው!
- ተስፋ አድርግ . . በጎ በጎውን ብቻ አለማሰብ ያስጠላኛል!
- ዓለማዊ ሕይወት በቀቢጠ ተስፋ የተሞላች ናት፣ለምን አልቀበልም ትላለህ?
- ዓለማዊ ሕይወት በምንም ላይ ሳይሆን የቆመችው በተስፋ ላይ ብቻ ነው፤አፈተረቶቹን ወዲያ በላቸው፡፡

- እውነቱን ነገረኝና . . በቁጥር 13 ገደቢስነት አታምንም?
- በጭራሽ አላምንም፡፡ ዩኒቨርሱን የሚያቀነባብረውና የሚመራው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በነገራችን ላይ የቁጥሩ የንበት ድምጽ በነሱ ቋንቋ ‹‹መኖር አለብኝ›› ከሚል አገላለጽ ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ቁጥር 13 ቻናውያን ዘንድ የመልካም ዕድል ገድ ነው፡፡ የመጥፎ ገድ ነገር በጥቅሉ ከአፈተረትነት ያለለፈና ከእግዚአብሔር መንገድ ያፈነገጠ ጥመት ብቻ ነው፡፡
- ፕሮቴስታንት እንደመሆንህ የወሩ 13ኛ ቀን ዓርብ ላይ ቢውል እንኳ ቀኑን ገደቢስ አድርገህ አትወስደውም? በክርስትና ታሪክ ውስጥ ይሁዳ ክህደት ፈጽሞ አሳልፎ ሳይሰጣቸው ኢየሱስና ሐዋርያዎቹ በምስጢር የተሰበሰቡት ዓርብ ቀን መሆኑንና የተሰብሳቢዎቹም ቁጥር 13 መሆኑንስ አታውቅምን?
- እኔ በአፈተረቶች አላምንም፡፡ የመጣሁት ስለ ገደቢስነትና ስለገዳምነት ካንተ ጋር ለመከራከር ሳይሆን አንተን ለመጠየቅ ነው፡፡ ወዳጄ ሁሌ መልካም ገድንና ተስፋን ሰንቆ እንዲኖር ነው የምመኝለት፡፡
- የቀዶ ጥገናው የመሳካት ዕድል 60% ብቻ እየሆነ ተስፋ እንድሰንቅ እንዴት ትፈልጋለህ?!
- ጌታችን ርህሩህና ቸር አዛኝ ጌታ ነው፤ሁሉም ነገር በርሱ እጅ ነው፡፡ ሐኪሞች ምክንያት ብቻ ናቸው፡፡ ተስፋ ስታደርግ የበለጠ ደስተኛ ትሆናለህ፣የተሸለ ለመኖር ትችላለህ፤የቀዶ ጥገናው የመሳካት ዕድልም በጣም ጥሩ ነው፡፡ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ካደረብህ ግን ሁኔታህ የባሰ የከፋ ይሆናል፤ሕይወትህም የከፋ ይሆናል፣ርህሩሁ ፈጣሪ ጌታ የጻፈልህ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው፡፡ ጆርጅ ምን ነካህ በፊት እንደዚህ አልነበርክም'ኮ?
- አንተን ለመፈተንና የምትለውን ማወቅ ፈልጌ ነው፤ተስፋ ማድረግን ካንተ መማር ፈልጌ እንጂ እንደምታውቀው አፈተረትና አጉል አምልኮን አልወድም . . ይሁንና እኔ ባለሁበት ሁኔታ ላይ የሚገኝ ሰው ተስፋ መሰነቅ የሚችለው እንዴት ነው?

ካትሪና ማይክልና ሳሊን አስከትላ መጣች፣በሀዘን ተውጠው በጥድፊያ ወደ ጆርጅ አልጋ ደረሱ . .

- ጆርጅ አይዞህ፣አሁን እንዴት ነህ?
- ባባ እንዴት ነህ? በጣም አሳሰብከን፡፡
- ባባ ምን ሆነህ ነው?

ከቀዶ ጥገናው በፊት ቤተሰቡ ከአባታቸው ጆርጅ ጋር አብሮ የመሆን

www.path-2-happiness.com

ዕድል እንዲኖረው ለማድረግ አደም ክፍሉን ለቆ መሄድ መረጠ . .

-ፍቀዱልኝ እኔ ልሂድ፣ስለ ረበሽኳችሁ ይቅርታ::

-ኦህ . . መኖርህን አላስተዋልኩም ነበር፣ይቅርታ እንደምነህ አደም?

-የለም፣የለም አትሂድ፤ቸኩለህ ካልሆንክ በስተቀር እንድትቆይ ነው የምፈልገው::

-የሚያስቸኩለኝ ነገር እንኳ የለም፣እንዳላውካችሁ ስለፈለኩ ብቻ ነው::

-ምንም የሚያውከን ነገር የለም፣በመኖርህ ደስተኞች ነን::

ጆረጅ ማይክልና ሳሊን ቀረብ አድርጎ አልጋው ጫፍ ላይ አስቀመጣቸውና ስለ ትምህርት ቤትና ስለ ቤት ጠየቃቸው . .

-ባባ እኛ ደህና ነን፤መቼ ነው ወደ ቤት የምትመለሰው?

-እናቴ ከሦስት ቀን በኋላ ትመጣለህ ብላ ነበር፤ስትመጣ በቀጥታ ወደ ሮም እንደምንጓዝም ነግራን ነበር::

-የአይሮፕላን ትኬት ገዝቻለሁ፣የምንጓዘው ከአስር ቀናት በኋላ ነው::

-ትኬቶች ገዛሽ?! እንዴት?! ያለሁበት ሁኔታ ይህን የሚፈቅድልኝ አይመስለኝም::

-አትስጋ፣ድነህ ትሄዳለህ::

-አደም ምን ትላለህ?

-የተባረከ ውሳኔ ነው:: በእግዚአብሔር ፈቃድም እውን ይሆናል፤ይህ ለጥያቄህ መልስ ነው::

-የትኛው ጥያቄ?

-በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ተስፋ መሰነቅ እንዴት ይቻላል? ብለህ ጠይቀኸኝ አልነበረም?

-ነገሮችን ለቸሩ ርህሩህ ጌታ ሰጥቶ ሁሉንም ለርሱ መተው በሕይወታችን ደስተኞች እንድንሆን ያደርገናል::

-ካትሪና እንባ እየተናነቃት ፦ ሌሊቱን ሙሉ ሳለቅስና ስላንተ ስጸልይ ነው ያደርኩት፤እርግጥ ጸሎቴ እንጂ ለቅሶዬ ምንም እንደማይጠቅምህ አውቃለሁ:: ጧት ትንሽ የዘገየሁት የገዛሁትን የአይሮፕላን ትኬት የጉዞ ቀን ኦኬ ለማስደረግ ብዬ ነውን፤ጆርጅ ምን ትላለህ?

-ካትሪና ባንቺ ምን ያህል ደስተኛ እንደሆንኩ ልገልጽልሽ አልችልም፣ተስማምቶኛል . . ቆንጆዋ ሳሊ እስኪ ንገሪኝማ ፦ ወደ ሮም ለመሄድ ጓግተሻል?

-ባባ በጣም በጣም ነው የጓጓሁት:: የትሬቪን ፏፏቴ ማየት እፈልጋለሁ::

-የትሬቪ ፏፏቴ ደግሞ ምንድነው?!

-በጂኦግራፊ ትምህርት የተማርነው ትልቅ ፏፏቴ ነው::

-እኔ ደግሞ የቅዱስ አንጅሎን አምባ ማየት እፈልጋለሁ፤ለአጼዎቹ ቅሪተ አጽም ማሳረፊያ የተገነባ አምባ ሲሆን በጂኦግራፊ እንደተማርነው በኋላ ሙዝየም ሆኗል::

-እኔ ደግሞ የቅዱስ ጴጥሮስን ካቴድራል መጎብየት ነው ምፈልገው::

-ነገሮች በሚገባ የተቀነባበሩ ይመስላል፤እውን እንደሚሆኑመም ተስፋ አደርጋለሁ . .

ሕጻናቱ በደስታ ፈንድቀው አባትና እናታቸውን ላይ ተጠመጠሙ . . በጉጉትና በተስፋ ስለ ጉዞው መነጋገር ከቀጠለው ልዩ ቤተሰባዊ ቆይታ ራሱን ገለል ለማድረግ አደም ወደ ክፍሉ አንድ ጥግ ፈንጠር ብሎ ወንበር ላይ ተቀምጧል . . ካትሪና ሰዓቷን አየት አድርጋ ለሕጻናቱ እንዲህ አለች፦

-አሁን ሦስት ሰዓት ሆኗል፣ሾፌሩ ውጭ እየጠበቃችሁ ነው::

-እሺ . . ባባ ቻው ቻው፣ ደህና ሁን . .

-ውዶቼ በሰላም እንገናኝ፣ደህና ሁኑ . .

ጆርጅ ለብቻው ወደ ተቀመጠው አደም ፊቱን አዞረ . .

-አደም ይቅርታ፣አልተከፋህም?

-ምኑ?

-የሮም ጉዟችን፤አንተ ፕሮቴስታንት እንጂ ካቶሊክ አይደለህምና::

-አልከፋኝም፤እንዲያውም እንድትጓዝ ነው የማበረታታህ፤የክርስትናን ሃይማኖት ከተለያዩ ጎራዎቹና ጭፍራዎቹ ጋር በይበልጥ እንድታውቅ መሄድህ በጣም የሚደገፍ ነው::

-አደም አንተ እኮ የምትገርም ሰው ነህ!!

-በየመታደል መንገድ ፍለጋ ጥረታችን ላይ ፍጹም እውነተኞች ከሆን እያንዳንዱ ተጨማሪ ጥረትና ዕውቀት ለመንገዱ መገለጽ አንድ ዓይነት ማሳያ በመሆኑ ትኩረት ልንቸረው ይገባል:: ቀደም ሲል ወደ ሕንድና ኢየሩሳሌም እንድትጓዝ አበረታትችህ አልነበረም? ምን አዲስ ነገር አለ?

-አዲስ ነገር በኛና በካቶሊኮች መካከል በቀልና ጦርነት መኖሩ ነው . . እናንተ ፕሮቴስታንቶች በሰላሳ ዓመቱ ጦርነት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ካቶሊኮችን ገድላችሁ የለም?

-በዚህ ዓይነት አረመኔያዊ መንገድ መገዳደልን ማንም አይወደውም:: ደግሞም እኔን ፕሮቴስታንት ነው ያለህ ማነው? ምናልባት ካቶሊክ ሊሆን ስለሚችል ከጉዞህ መልስ እነግረሃለሁ::

-ካቶሊክ ትመስላለህ፤አንተና ካትሪና የምትጋሩት ነጥብ አለ . . በዚህ ሰሞኑ

www.path-2-happiness.com

ንባቤና በጉዞዬ ካቶሊካዊነትን በይበልጥ ለማወቅ ጥረት አደርጋለሁ:: የመጀመሪያ እምነቴ ግን እንግዳ የሆነ ጣዖት አምላኪነት አለበት የሚል ነው:: ልክ እንደ ጣዖት አምላኪዎቹ ቤተመቅደሶች በቅርጻ ቅርጾችና በሥዕሎች የተጨናነቁ ቤተክርስቲያኖቻቸውን አልወድም::

- ሰዎችን የሚገድለውን ፕሮቴስታዊነትን ግን ትወዳለህ::
- ይህ ካቶሊክ መሆንህን ያረጋግጥልኛል::
- ማለት የፈለኩት ይህን ሳይሆን በመታደል መንገድ ፍለጋ ጥረትህ ወቅት በየትኛውም ቡድንና በማንኛውም ፈለግ ውስጥ እውነትን ፈልግ፣መርምር ማለቴ ነው:: ይህን ስታደርግ መታደልን፣የሕሊና እርካታና መረጋጋትን ታገኛለህና::

ካትሪና ሁለቱን ሕጻናት ከሸኘች በኋላ ወደ ክፍሉ ተመለሰች . .

- በመዘግየቴ ይቅርታ፣ማይክልና ሳሊ ከሾፌሩ ጋር ከመሄዳቸው በፊት ጭማቂና ሳንድዊች ፈልገው አቆዩኝ::
- ካትሪና ለዚህ ጉዞ መሰናዶ በማድረግሽ ከልብ ነው የማመሰግነው፤አእምሮዬ ውስጥ የሚመላለሰው የሞት ፍራቻ ከኔ እንዲርቅ ለማድረግ ችለሻል::
- የሰው ልጅ መንፈሱ ሲጠራና ሲመጥቅ እውነታዎች ተገልጠው ከፊቱ ይዘረገፋሉ:: ሞት ምንጊዜም ከርሱ ጋር የሚኖርና በማንኛውም ወቅት ሊከሰት የሚችል እውነታ መሆኑንም ይገነዘባል:: በመሆኑም ለሕይወት መሸንገያዎችና ለመደሰቻዎቿ እስረኛ መሆኑ ያበቃል:: ሀሳቡና ትኩረቱ በዚህ ዓለም ጉዳዮች ተወጥሮ የሚያዝ አይሆንም . . የተፈጠረበትን ዓለማና መመለሻውን የሚያውቅ ሰው የሚኖረው ለመሞት፣የሚሞተውም ለመኖር መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይችላል::
- ‹‹ለመሞት እንኖራለን፣ለመኖርም እንሞታለን›› የሚለው ድንቅ ፍልስፍና ነው፤ግና ችግሩ ጣዕረ ሞትና ስቃዩ ነው::
- ኢየሱስ ለሰው ልጆች ብሎ ስቃይ ተቀብሏል፤ስቃይ ለዘላለማዊው መድህን መሰረታዊ ነገር ነው፤ስቃይን መቀበላችን ለኢየሱስ ላለን ፍቅር ማሳያ ነው::
- ታዲያ ዓለማዊ ሕይወት አስፈላጊነቱ ምኑ ላይ ነው?
- ጥቅሟ ጌታን ለማገልገልና ለማገልገል ብቻ እንድንጠቀምባት ነው::
- አደም በዚህ ላይ ምን ትላለህ?
- በየትኛው?
- ሕይወት በጥቅሉ ለአምላክ አገልግሎትና እርሱን ለማስደሰት ብቻ መሆን ይገባል በሚለው ላይ::

- ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ . . እግዚአብሔርን ማገልገል ግን መጸለይ ብቻ አይደለም::

ካትሪና በአድናቆት ፦

- በጣም ጥሩ፣በዚህ ላይ ቀሳውስትም ሳይቀሩ ብዙ ጊዜ እንዘነጋለን:: ሕይወታችን በሙሉ ለእግዚአብሔር መሆን የሚገባ አምልኮ ነው::

ጆርጅ በስላቅ እየሳቀ ፦

- ተደጋጋሚው ጥያቄ ግን ርህሩሁን አምላክ በፍጹምነት የሚያመልክ ሰው ማነው? ቁሳቁስ ወይም ጣዖትን አምላኩ አድርጎ የሚይዝ ማነው? የሚለው ነው::

አደም በቁርጠኝነት መንፈስ ፦

- ምናልባት ይህ በታሪክ ውስጥ አሳሳቢውና አደገኛው ጥያቄ ሳይሆን አይቀርም::
- ጆርጅ፣አምላክን በሚመለከት በኛ መካከል ስላለው ልዩነት ጠቆም ማድረግህ መሰለኝ::
- ምን ለማለት ነው የፈለግሽው?
- እኛ ሁሉም ክርስቲያኖች በሥላሴ ማለትም እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው በሚለው እምነት ላይ ሙሉ በሙሉ እንስማማለን:: ሥላሴዎቹም አንደኛው አብ ሁለተኛው ወልድ ሦስተኛው መንፈስ ቅዱስ ነው:: በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ባህርያት ላይ ልዩነቶች ቢኖሩንም በሥላሴ እምነት ላይ ልዩነት የለንም::
- ይህን ማለቴ አይደለም፣ይህን አላሰብኩም፣ላለማሰብም ነው የምጥረው:: ሦስቱ አንድ፣አንዱም ሦስት በባህሪ የሚለያዩ አማልክት እንዴት እንደሚሆኑ ሊገባኝ አይችልም!
- በክርስትና ውስጥ ከሁሉም አስቸጋሪው ጉዳይ ይህ ነው:: ሮም ስትሄድ በዚህ ላይ በስፋት እምድትወያይ ሀሳብ አቀርባለሁ፣እጅግ በጣም የተወሳሰበ አስቸጋሪ ርእስ በመሆኑ እዚህ ባለንበት ቦታ መተንተን አይቻልም::
- ሕይወታችንን ለርሱ አምልኮና ለአገልግሎቱ አሳልፍን የምንሰጠውን በሚገባ እንዴት እንደማናውቀውና እንዲያውም ማወቁ እንዴት አስቸጋሪ እንደሚሆን ሊገባኝ አይችልም:: ይልቁንም አንዳንዴ በኛና በጣዖት አምላኪዎች መካከል ምንም ልዩነት አላይም!!
- እመነኝ ከጥያቄው መሸሼ አይደለም፣የሚከተለው ቤተክርስቲያን የፈለገውን ቢሆን ይህ የያንዳንዱ ክርስቲያን ችግር ነው፤ስለዚህ ሮማ ላይ በጥልቀት እንወያይበታለን::

www.path-2-happiness.com

አደም በፈገግታ ፦

- እኔ በበኩሌ በካትሪና ሀሳብ እስማማለሁ፤ይህ ከባድ ርእስ ነው፣እንዲያውም ከሁሉም ጉዳዮች ዋነኛው ነው። ስለዚህም በዚህ ሁኔታ በችኮላ መወያየቱ ተገቢ አይደለም። አእምሮ ያለው ሰው ጣዖታዊ ነው ብሎ በሚያስበው ሃይማኖት ውስጥ መቀጠል የማይችል ሲሆን፣ አንድ መለኮታዊ ሃይኖትም ከጣዖት አምላኪ ሃይማኖቶች አንዱ ሊሆን አይችልም።
- እህህ፣ሁሉም ክርስቲያኖች አንዳንዴ ጣዖታዊነት ይጠናወታቸዋል የሚል እምነት ቢኖረኝም፣ እናንተ ሁለት ካቶሊኮች እኔም ከናንተ ጋር እስማማለሁ!

ካትሪና በመገረም ፦

- አደም አንተ ካቶሊክ ነህ እንዴ?
- አንዳንዴ ካቶሊክ ነህ ይለኛል፣ሌላ ጊዜ ደግሞ ፕሮቴስታንት ነህ ይለኛል።
- አሃ፣በቃ አሁን ካቶሊክ መሆኑን አረጋግጫለሁ . .

ጆርጅ በመሳቅ ላይ እያለ ሐኪሙ ገባ . . ፈገግ እያለ ወደ ጆር አልጋ ተጠጋ . .

- እንዲህ ነው እንጂ፣የነገርኩህ ነገር እንዳለ ሆኖ እንደዚህ ደስተኛ ሆነህ እንደማገኝህ እርግጠኛ ነበርኩ።
- ዶክተር ኖር እንኳን ደህና መጣህ፣እንደዚህ እርግጠኛ የሆንከው ግን ለምንድነው?
- ማንኛውም ምሁርና ሃይማኖተኛ የሆነ ሰው ከሌላው ይበልጥ ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ማስረከቡ የግድ ነው።
- ለመሆኑ እግዚአብሔር ማነው?
- ቀድሞውኑ አንተ ፈላስፋ ነህ ብያለሁ። እኔ ክርስቲያን ነኝና ይህን ርእስ እሸሻለሁ፣ከፍተኛ ጥረት ባደርግም ሊገባኝ አልቻለም። ርህሩህ ቸርና ቻይ የሆነ ፈጣሪ አምላክ ስለመኖሩ ግን እርግጠኛ ነኝ፣ይኸ በቂዬ ነው።
- እኔ ግን ይህ ብቻ በቂዬ ነው ብዬ ፈጽሞ አላስብም፣የማላውቀውን አምላክ እንዴት ነው የማመልከው?
- አንተ ትፈላሰፋለህ፣ለማንኛውም ቀዶ ጥገናው እንዲከናወንልህ በፊርማ አረጋግጠሃል?
- አላደረኩም፣ለመፈረም ግን ዝግጁ ነኝ፤ካትሪና እንደዚያ አይደለም እንዴ?
- የቀዶ ጥገናውን ስኬታማነት የበለጠ ከፍ የሚያደርጉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ? ወይም ቀዶ ጥገናውን ለማከናወን የተሻለ ቦታ ይኖር ይሆን?
- ይህን ቀዶ ጥገና ለማከናወን ተመራጩ ሆስፒታል ጀርመን አገር ነው

የሚገኘው፤ይሁን እንጂ አሁን ወደ ሌላ ሆስፒታል መዛወር የሚቻልበት ሁኔታ የለም። ቀዶ ጥገናው ዛሬውኑ መደረግ ይኖርበታል። ትናንት ጀርመን ከሚገኘው እሰቴሽያሊስት አማካሪ ጋር ግንኙነት አድርገን በጣም አበረታቶናል። የስኬታማነቱን ዕድል ከፍ የሚያደርገውን ነገር በተመለከተ ይህ ነው ብዬ መጥቀስ የምችለው የተለየ ነገር አላውቅም።

- ምን ትመክረናለህ?
- በአስቸኳይ ስምምነቱን እንድትፈርሙ ነው። የቀዶ ጥገናውን የመጨረሻ ምርመራ አስራ አንድ ሰዓት ላይ እንጀምራለን፣ቀዶ ጥገናው ዛሬ ሁለት ሰዓት ይከናወናል።
- ቀዶ ጥገናውን ማነው የሚደርገው?
- የቀዳጅ ሐኪሞች አምበል ዶክተር እስቲብ ማይክ ነው፣እስቴሽያሊስት አማካሪ ሐኪም ናቸው።
- እንፈርም ዘንድ ወረቀቱን ልትሰጠን ትችላለህ፣የምትመክረን ሌላ ነገር ካለም ጥሩ ነው።
- ሌላ ነገር የለም፣እስከ ቀዶ ጥገናው ድረስ እንዲሁ ደስተኛ ሆነህ እንድትቀጥል እሻለሁ፣በሳይንሳዊ መንገድ ባልተረጋገጠ ተሞክሮዬ እንደማውቀው ተስፋ በሰነቀ አዎንታዊ ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ላይ ያሉት ሰዎች ቀዶ ጥገና ከሌሎች ይበልጥ ስኬታማ ነው።
- መልካም ነው . . ተስፋ መሰነቅንና በጎ በጎውን በመጠበቁ ረገድ ከአደም ጋር ሳትስማሙ አትቀሩም።
- አንተንም ጨምሮ አርቆ አስተዋይ አእምሮ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በዚህ የሚስማሙ ይመስለኛል።
- ካትሪና ከቀዶ ጥገናው በኋላ ለምናደርገው ጉዞ ትኬቶችን ገዝታ የጉዞ ዝግጅቱን ያጠናቀቀችው ካትሪና በዚህ ረገድ ከሁላችንም ልቃ ሳትገኝ አልቀረችም።
- ግሩም ነው፣ከቀዶ ጥገናው በኋላ ለዕረፍትና ለክትትል ከአንድ ሳምንት ጊዜ በላይ አያስፈልግህም፤ከዚያ በኋላ መውጣት ትችላለህ . . ይሁን እንጂ ከቀዶ ጥገናው አስር ቀን በኋላ እንጂ ጉዞ ማድረግን አንመክርም።
- እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣የአይሮፕላን ቦታ የተያዘው ከዛሬ አስር ቀን በኋላ ነው፣ግምቴ በደንብ ይዞልኛል ማለት ነው . .
- አዎ፣ድንቅ ሥራ ነው የሰራሽው . . ጆርጅ የተባረከች ሚስትና ግሩም ድንቅ ወዳጆች አሉህ፣እንኳን ደስ አለህ እለሃለሁ። የሚፈረሙ ወረቀቶች ከአፍታ በኋላ ይደርሱሃል፤የቀዶ ጥገናውን ቅድመ ሂደቶች አሁን

www.path-2-happiness.com

እጀምራለሁ፤ፈጣን ፈውስም እመኝልሃለሁ::

ሐኪሙ ከወጣ በኋላ ጆርጅ ወደ ካትሪና ዞሮ እንዲህ አለ . .

- እንግዲህ ነገሮች ቀዶ ጥገናው ይደረግ ወደሚለው ያደሉ ይመስላል፤ከዚያ በፊት ያለው አጭር ጊዜ ብቻ በመሆኑ አንዳንድ ነገሮችን መልክ ማስያዝ ያስፈልገኛል::
- ጥሩ፣ምን ማድረግ ፈለክ?
- ከሞትኩ ሳይታወቁ ጠፍተው እንዳይቀሩ ያለኝን ንብረት ሁሉ በዝርዝር መዝግቤያለሁ፣ያለኝን ሀብት በሙሉ ላንቺና ለሁለቱ ልጆቼ ብቻ እንዲከፋፈል ነው የጻፍኩት::
- ጆርጅ እባክህ እንደዚህ አትበል . . ገና ትኖራለህ፣በሰላም ድነህ ትወጣለህም::
- በማቋረጤ ይቅርታ አድርጉልኝ፣ድነህ በሰላም እንደምትወጣ እርግጠኛና ባለ ሙሉ ተስፋ ከመሆኔም ጋር፣አሁን እርሱ የሚለው እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ይህን ባታደርግ ኖሮ ምናልባት ንብረትህ ሳይታወቅ ሊቀር ይችላል:: ከይቅርታ ጋር እንዲያውም አንዳንድ የቤተክርስቲያን መመሪያዎችን ተግባራዊ አድርገህ ቢሆን ኖሮ ባለቤትህን ተገቢ መብቷን ታሳጣት ነበር::
- የምትለውን መረዳት አልቻልኩም፣አንተ ሃይማኖተኛ እየሆንክ እንዴት እንዲህ ትላለህ?
- አባትና እናትህስ?
- ሳላያቸው አስር ዓመት ያህል ይሆነኛል::
- ይህን ለመናገር አሁን ጊዜው ላይሆን ይችላል . . ይሁን እንጂ ይህ ያለ ጥርጥር ጥፋት ነው::
- ካንተ ጋር እስማማለሁ፣ስለ ወላጆቼ ጉዳይ ካንድ ጊዜ በላይ ነግሬዋለሁ:: የኔ ወላጆች በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ እንዴት በተደሰትኩ ነበር::
- ዛሬ ሁለታችሁም በሁሉም ነገር በኔ ላይ የተስማማችሁ ይመስላል:: ከቀዶ ጥገናው በኋላ ስነቃ ከመኳዛችን በፊት ወላጆቼን ልጎበኛቸው ቃል ገብቼላችኋለሁ . . ቀዶ ጥገናው በሕይወቴ ውስጥ መለያ ነጥብ ሳይሆን አይቀርም::
- በኑዛዜህ ውስጥም ብትጠቅሳቸው መልካም ይሆናል::
- ልክ ነው፣መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እግዚአብሔር፡- አባትህንና እናትህን አክብር፤ . . ብሎአልና፤›› በማለት ለወላጆች ደግ እንድንሆን አዟል::
- የሚያሳዝነው የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዞች አንዳንዴ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ መሆናቸው ነው፤አሁን የጠቀስሽውን አንብቤ ‹‹ማንም ወደ እኔ

የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እህቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፣ደቀ መዝሙሬ መሆን አይችልም::›› የሚለውን ሉቃስ ወንጌል ውስጥ ሳነብ ግራ ይገባኛል::

- በኛ በካቶሊኮች ዘንድ አንተ አሁን የጠቀስከው ዓይነት ግጭት አእምሯችን ውስጥ ሲፈጠር ውሳኔ እንዲሰጡበት ጉዳዩ ወደ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ይተላለፋል፤ፕሮቴስታንቶች ግን በዚህ ላይ ብዙ ይቸገራሉ::
- ለጣዖታዊነት ወደ ቀረበውና አእምሮን አውልቆ ወዳስቀመጠው አስከፊ ፓፓዊ ሥርዓት ልትመልሽን ነው:: ዋናው ነጥብ ይህንን በኋላ እንመለስበታለን፣አሁን ይበልጥ ወደሚያሳስበንና ወደነበርንበት ጉዳይ እንመለስና ወላጆቼን በምክራችሁ መሰረት በዝርዝሩ ውስጥ እጨምራለሁ:: ከአፍታ በኋላም በምስክርነት ትፈርሙበት ዘንድ የኑዛዜ ወረቀቱን እሰጣችኋለሁ ::
- በእግዜአብሔር ፈቃድ በሰላም እንደምትወጣ እርግጠኛ ብሆንም ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው ::
- የሕይወት ዋስትና እንሹራንስ ውሌን ከአንድ ወር በፊት አሳድሻለሁ፣ከሞትኩ በኋላ ለናንተ ዋስትና ይሆናል ::
- የመድህን ዋስትና የሚሰጠው እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን ይህ ምክንያት ብቻ ነው ::
- ቤቱን በተመለከተ . .
- የምትፈልገውን ሁሉ በኑዛዜው ላይ ማስፈርህ አስፈላጊ ነው፤አሁን ከዚያ ይበልጥ አስፈላጊው እንዲፈውስህና ቀዶ ጥገናውን ስኬታማ እንዲያደርገው እግዚአብሔርን መለመንና መጸለይ ነው . . (ፈግ ብሎ ቀጠለና) ፦ ከሮማ ስጦታ እንድታመጣልኝ እንደምፈልግም እንዳትረሳ::

ካትሪና ሳትፈልገው ጥሶ መጉረፍ የጀመረውን እንባዋን ጠራረገችና በአደም የስጦታ ጥያቄ ፈገግ አለች . .

- ልክ ነህ . . ከሁሉም በላይ በጸሎታችን እግዚአብሔርን መለማመን ነው፤ከሮማ እንዲመጣልህ የምትፈልገው ስጦታ ግን ምንድነው ?
- እህህ፣እንግዲህ የሕንድም ይሁን የጣሊያን ዑድ ሽቶ ሮማ አይገኝ፣ከቫቲካን ካቶሊካዊ ስጦታዎችን አላመጣልህ . .
- ሁለቱንም አልፈልግም፤የምፈልገው ሁለት ስጦታዎችን ነው:: አንደኛው በጣም ግሩምና በጣም ርካሽ የሆነ የኪስ ቆዳ ቦርሳ ነው፤ርካሽ ካልሆነ ግን አልፈልገውም:: ሁለተኛው የኢጣሊያ እግር ኳስ ታላቅ ኮከብ የካርኒቫሮን ትልቅ ሬክላም እንድታመጣልኝ ነው::

www.path-2-happiness.com

-በጣም ግሩም የሆነ ውብና ርካሽ የቆዳ ቦርሳ! ይህ የማይመስል ነው . . እህህ፣ሙጢፅ አርረሕማንን ጣሊያን ውስጥ ካለገኘነው በስተቀር የሚቻል አይመስለኝም ።

-ሕንድ ውስጥ ሙጢፅ አረሕማንን የገራልህ ጌታ ጣሊያን ውስጥም ሌላ ሙጢፅን መቻችልሃል።

-ለመጀመሪያ ጊዜ እስፖርተኛ መሆንህን ማወቄ ነው!

-ካርኒቫሮ ያለፈው የዓለም ዋንጫ ኮከብ ተጫዋች ነው። እንደ ብዙዎቹ የጣሊያን ስፖርት ተንታኞች ግምት የቀድሞው ዝነኛ ኮከብ የፍራንኮ ባሬዚ ተተኪ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ለማንኛውም እኔ ስፖርትን ከመመልከት ይልቅ መስራትን ነው የምወደው፣ጥያቄዬ ግን ይኸው ነው።

-ከቫቲካን መስቀል እንዲመጣልህ ከፈለክ ጆርጅ ካላመጣልህ እኔ አመጣልሃለሁ።

-በኔ ላይ በቃ ሁሌም አንድ ናችሁ ማለት ነው።

-አመሰግናለሁ፣በወዳጄ እየቀለድኩ ነው፤እንድሄድ ትፈቅዱልኛላችሁ?

በዚህ አፍታ . . ቶም ደረሰና ክፍሉን የሞላውን ፈገግታና ሳቅ ተመለከተ . .

-ጆርጅ አዲስ ነገር የተገኘ ይመስላል፣እስቲ አብስረን።

-አዲስ ነገር እንኳ የለም፤ወዳጄ አደም በጣም ውብና በጣም ርካሽ የሆነ የጣሊያን የቆዳ ቦርሳ ስጦታ ከሮማ እንዳመጣለት ጠይቆኝ ስንስቅበት ነበር።

-ከሮማ?! ቀዶ ጥገናውን እዚያ ለማድረግ ወደ ሮማ ልትጓዝ ነው?!

-መጀመሪያ ከወዳጄ ከአደም ጋር ላስተዋውቅህ፤አደም ይህ ወዳጄ ሐኪም ቶም ነው . . ቀዶ ጥገናውን ዛሬ አድርጌ ከአስር ቀን በኋላ ከውድ ባለቤቴ ከካትሪና እና ከልጆቻችን ጋር ወደ ሮማ እንሄዳለን። ቦርሳውን እንዴት እንደማመጣለት ግን አላውቅም።

-እንዲህ ያለው ግሩም ድንቅ በተስፋ የተሞላ ብርቱ መንፈስ የትም የማይገኝ ነው፤ቀዶ ጥገናውን በተመለከተ የተለወጠ ነገር አለ?

-የለም፣የተለወጠ ነገር ቢኖር ካትሪና ይዛ ባመጣችልኝና ከአደም በተማርኩት በተስፋ የተሞላ ብርቱ የመንፈስ ጥንካሬ ለሕይወት ያለኝ አመለካከት ነው።

-በተስፋ የተሞላ መንፈስ ከምንም በላይ አስፈላጊያችን ነው፤የብዙዎቹ የአእምሮ ሕመሞችና የስነ ልቦና ችግሮች መፍትሔ በዚህ ውስጥ ነው ያለው። መማሩ ግን አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ ይሆናል።

-ከአደም ጋር ቁጭ በል፣በዚህ ረገድ ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ስላለው ያስተምረሃል።

-እናም የርሱ ተማሪ ሆኜ ከርሱ በመማር መታደል ይኖርብኛል።

-ግልጽ ለመሆን ካንተ ጋር ስቀመጥ ከምፈላሰፍባቸው መልሶች መካከል ብዙዎቹን የሚወስደው ወይ ከርሱ ነው፣ወይ ደገሞ ከካትሪና ነው . . ‹‹ነገሮችን ሳናካብዳቸውና ሳናወሳስባቸው ቀለል አድርገን መውሰድ አለብን›› የሚለውን ደጋግሜ ሳነሳልህ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ይህን የወሰድኩት ከአደም ነው።

-በጣም ግሩም ነው፣በተለይ ይህ አባባል ካንተ ከሰማሁት በኋላ አመለካከቴንና ባህሪዬን በከፊል ቀይሯል። ቀደም ሲል ተፈጥሮዬና ንባቤም ነገሮችን ወደ ማቅለል ሳይሆን ወደ ማወሳሰብ አቅጣጫ ያዘነበለ ነበር።

-አይምሰልህ ጆርጅ የወጣለት አሟካሽ ነው፣ከርሱ ለመማር አብሬው የምቀመጠው እኔ ነኝ፤እኔ ተራ የካፍቴሪያ አስተናጋጅ ስሆን እርሱ ግን አስተማሪዬና መምህሬ ነው።

ካትሪና በፈገግታ ፦

-ማሞካሻሸት ከጀመርን ዘንዳ ይህ ሁሉ የጆርጅን የግርታ ጥያቄዎች እንቆቅልሽ የፈታው የቶምም ጥረት ውጤት ነው።

ቶም በመገረም ስሜት ፦

-ይቅርታ . . እርግጠኛ ለመሆን ብቻ፣እውን ቀዶ ጥገናው ዛሬ ይካሄዳል?

-አላመንከኝም መሰለኝ፣ አዎ . . የተስፋ መሰነቅ ትምህርት መልመጃዎች አሁንም ገና የሚያስፈልጉህ መሰለኝ። ሁሉንም ነገሮች መልክ መልክ አስይዤለሁ፣የሚቀረኝ አንዳንድ ማስታወሻዎችን ለመጻፍ ግማሽ ሰዓት ብቻ ነው። ሞትም ሆነ ሕይወት ያለው በአላህ እጅ ብቻ ነው።

-ቀዶ ጥገናው መች ነው የሚደረገው?

-ሂደቱ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ይጀምራል፣ቀዶ ጥገናው ደግሞ ሁለት ሰዓት ነው።

አደም ሰዓቱን ተመለከተ . .

-አሁን ፍቀዱልኝ፣የግድ ወደ ካፌቴሪያው መሄድ አለብኝ።

-አደም የምስጋና ቃላት ያጥሩኛል፣አንተ ምርጥ ወዳጅ ነህ።

-አደም አንዴ፣ይህ ቢዝነስ ካርዴ ነው፣ ካንተ ጋር በደንብ መተዋወቅና ካንተ ጋር መወያየት ምኞቴ ነው።

-የግድ ልትገናኙ ይገባል . . አደም ሐኪም ቶም ቀደም ሲል ከነገርኩህ አሁን የተለወጠ ይመስላል።

www.path-2-happiness.com

-ካንተ ጋር በመተዋወቁ ክብር ይሰማኛል፣ቢዝነስ ካርድ ስለ ሌለኝ ግን ይቅርታ . .

ከኪሱ ቁራጭ ወረቀት አውጥቶ ስሙንና ስልክ ቁጥሩን ጻፈና ለቶም ሰጥቶት ተሰናብቶት ሄደ . .

-ከተዋወቅኩት አጭር ጊዜ ብቻ ቢሆንም አደም ከወዳጆቼ ሁሉ ምርጡ ወዳጅ ነው::

-በጣም ጨዋ የሆነ ሰው ነው:: አንተ ራስህን ስተህ በነበረበት ጊዜ ካኽ ሊጠይቅህ መጥቶ አደምን አስተናጋጅ በመሆኑ አፌዞበት ነበር፤እርሱ ግን ምንም ክፉ ቃል አልመለሰለትም፤ያለው ነገር ቢኖር ‹‹የኔ ማንነት ከውስጤ የሚመነጭ እንጂ ከውጭ የማመጣው አይደለም›› የሚል ብቻ ነበር::

-ላገኘውና ልተዋወቀው ይገባል . . አንተ ጆርጅ የኔን መለወጥ አምነህ መቀበልህም መልካም ነገር ነው::

የጆርጅ ስልክ ሲያቀጨል ቶምና ካትሪናን ይቅርታ ጠይቆ መነጋገሪያውን አነሳ:: አለቃው ካኽ ነበር . .

-አሁን ደህና ትመስላለህ፣ራስህን ስተህ በነበረበት ጊዜ ልጠይቅህ መጥቼ ነበር:: የካፌቴሪያ አስተናጋጁ አንተ ዘንድ ነበር፤አሁን እንዴት ነህ?

-እኔ ደህና ነኝ፣አስተናጋጁ ወዳጄ በመሆኑ ማንም ሰው የሚያስከፋውን ነገር እንዲናገር አልፈቅድም::

-እህህ፣የምሥራች ልንገርህ . . በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብቻ ሦስት ታላላቅ የውል ስምምነቶችን ለመፈረም በመቻልህ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንድትሸለም ወስኗል::

-አንተንም እነሱንም አመሰግናለሁ፤ሽልማቱ ምናልባት ጉቦ ስላቀበልኩ ሊሆን ይችላል::

-ይህን ተውና ሥራ መቼ ነው የምትጀምረው? የእረፍት ፈቃድ አልወሰድክም እኮ::

-አላወኩም፣ዛሬ የቀዶ ጥገና አደርጋለሁ፣ከዚያ ለዕረፍት ወደ ሮማ እሄዳለሁ:: ስመለስ የሥራ ፈቃድ እጽፍልህና ሥራውን መቀጠል አለመቀጠሌን እወስናለሁ::

-ስሜታዊ ወይ በጣም የተሰላቸህ ትመስላለህ፤እንዲዚህ ስትናገር ሰምቼህ አላውቅም::

-አዝናለሁ፣የራሴን መርህ ረግጬ ለቤንያሚን የጉቦ መሳሪያ ነው የሆንኩት::

-በቀዶ ጥገናው ምክንያት የተረጋጋህ አይደለህምና ሌላ ጊዜ እደውላለሁ፣ደህና ሁን::

-ደህና ሁን . .

-የኔ ፍቅር ምንድነው ነገሩ . . ?

-ያ ካኽ ነው፣የአደም ተጻራሪ ምስል፤አደብ የለው፣ጸባይ የለው፣መርህ የለው!

-ከልክ ባለፈ ቁሳዊነት፣በኤቲዝምና ከሃይማኖት በመራቃቸው ምክንያት በሕብረተሰባችን ውስጥ የርሱ ዓይነቶች እጅግ ብዙ ናቸው::

ቶም አከለ ፦

-በኔ እምነት የሰው ልጆች ዋነኛ ችግር ከእግዚአብሔር መራቃቸው ነው:: የጭንቀት የውጥረት የብክነትና የአደጋዎች ሁሉ ዋነኛ ምክንያትም ይኸው ነው::

-ይህን ከካትሪና ብሰማው እረዳለሁ፣ከቶም መስማቱ ግን እንግዳ ነገር ነው የሚሆንብኝ!!

-እህህ፣መለወጥህን ተቀብያለሁ ብለህ አልነበረም? በሌላ በኩል የከፋውን አደጋ የሚጋርጡት የሃይማኖት መሪዎች ነን ባዮች ስለሆኑ እንጂ ሁሉም ሳይንሳዊ ጥናቶች ያልኩትን ያረጋግጣሉ::

-የካቶሊኮችን ፓፓዊ አመራር ማለትህ ነው::

-አንደምታው ይገባኛል፣ለማንኛውም የመጣሁት ልጠይቅህ ነውና ፍቀዱልኝ ልሂድ፤ነገ መጥቼ አየሃለሁ::

-ቶም በጣም አመሰግናለሁ፤በጉብኝትህ እጅግ ረክቻለሁ::

ቶም እንደ ወጣ . . ካትሪና ወደ ጆርጅ ዞር አለችና . .

-እውነቱን ለመናገር ቶም በጣም ነው የተለወጠው!

-ልክ ነሽ፣ሃይማኖት በሰው ውስጥ ያለውን ሁሉንም ነገር ይለውጣል::

-ድንቅ ነው፣ጆርጅ አንተም'ኮ ተለውጠሃል

-ሊሆን ይችላል!

-ልጆቼ ዘንድ ወደ ቤት እሄድና ጊዜውን ለአንተ በመጸለይ አሳልፋለሁ፤አስራ አንድ ሰዓት ላይ ወዳንተ እመለሳለሁ::

-ወረቀቶቹን ጨርሼ ስለማስረክብሽ የግድ መመለስ ይኖርብሻል::

(3)

ጆርጅ ኑዛዜውን በማዘጋጀት ተጠምዶ ንብረቶቹን በዝርዝር አሰፈረ:: በአንድ ሰዓት ውስጥ ሁሉንም አዘጋጅቶ ጨረሰ . . በመቀጠል የሚደረግለትን የቀዶ ጥገና ሕክምና በመንገር በጸሎታቸው እንዲያስቡት ለሁሉም ወዳጆቹ

www.path-2-happiness.com

መልእክት ለመላክ ወሰነ:: ከመካከላቸው በትክክለኛውና በእውነተኛው መንገድ የሚጓዝ ሰው አምላክ ዘንድ ተሰሚነት ሊኖረው ይችላል ከሚል በመነሳት ጸሎቱ ከሁሉም ሃያማኖቶችና የእምነት ፈለጎች ተከታይ ወዳጆቹ እንዲሆን ወደደ . . ለሁሉም ኢ-ሜይል ላከ:: በተለይም ለካቶሊኩ ሐቢብ፣ለአይዳዊቱ ሌቪ . . ከወዳጆቹ መካከል ሙስሊም ስለ መኖሩ ሲያስብ ሙጢዕ አረሕማን ትዝ አላለው፣ለርሱም ጻፈ:: ሕንድን ሲያስታውስ ቡድሂስቷ ጆስቲና ትዝ አለችው፣ግና እነዚህ ጣዖታውያን ራሳቸው ጠፍጥፈው ወይም ጠርበው የሚሰሩት አምላካቸው ይጠቅማል ወይም ይጎዳል ብዬ አላምንም፣ጣኦታዊነት አስጠሊታ ነው . . ሲል ደምድሞ ኮምፒውተሩን ዘጋ::

ስልኩ ጮኸ፣እንግዳ ቁጥር ነበር፣አነሳው . .

- ሃሎ::
- ሃሎ ጆርጅ፣ስለ ጤንነትህ አጽናናን::
- ሃሎ ማን ልበል?
- ረሳኸኝ መሰለኝ፣ሌቪ ነኝ ከቴል አቪብ::
- ሌቪ እንደምነሽ . . እንዴት ልረሳሽ እችላለሁ፤ደግ የዋለችልኝን ብዙ ያስተማረችኝን ሰው እንዴት እረሳለሁ? ሌቪ ናፍቀሽኛል፤ድምጽሽን መለየት ባለመቻለ ይቅርታ፤ትደውያለሽ ብዬ አልጠበኩም ነበር::
- የቀዶ ጥገናው ነገር እንዴት ነው? በጣም ነው ያሳሰበኝ::
- ለበጎ ስሜትሽ ምስጋናዬ የላቀ ነው፤ቀዶ ጥገናው ዛሬ ይደረጋል፣ስኬታማ ይሆናል የሚል ትልቅ ተስፋ ሰንቋያለሁ፤የጻፍኩላችሁ እንድትጸልዩልኝ ብቻ ነው::
- እጸልይልሃለሁ፣ግና እያዘንኩ ጸሎቴ በአይሁዳዊነት መንገድ ነው::
- ለምን አዝናለሁ ትያለሽ?!
- ከአንተ ጉብኝት ወዲህ የመታደልን መንገድ ለመፈለግ በሃይማኖቶችና በእምነት ፈለጎች ላይ ንባብ እያካሄድኩ ነው:: ወደ የመታደል መንገድ ለመድረስ ምክርና መመሪያህን በመጠባበቅ ላይ ነኝ::
- ትንሽ ያጋነንሽው መሰለኝ፤ካንቺ የተማርኩት እኔ ነኝ፣በተለይም ግልጸኝነትንና ለራስ መታመንን ካንቺ ተምሬያለሁ . . በነገራችን ላይ የጓደኛችን የሐቢብ ወሬስ?
- ይኸው አጠገቤ ነው ያለው፣ሊያናግርህ ይፈልጋል::
- እህህ፣ጥበቃውና ዘበኝነቱ በስልክም ጭምር ነው በይው . . ሐቢብ ድንቅ ሰው ነው . . ሌቪ ጉድኝታችሁን ይበልጥ ለማጥበቅ ሞክሩ፣ለሰው ልጅ ጓደኛ በጣም ወሳኝ ነው::

- እህህ፣ ምናልባት ሐቢብ የሚነግርህ ነገር ሊኖር ይችላል . . ዋናው ነገር ሁላችንም ስላንተ እንጸልያለን:: ፈጣን ፈውስ እመኝልሃለሁ፣ቀዶ ጥገናው ከተጠናቀቀ በኋላ ደውልልን፣ሐቢብን እንካ::
- ሃሎ ጆርጅ፣ዘበኛው ነኝ፤ምንድነው ነገሩ? አሁን እንዴት ነህ?
- ዛሬ የቀዶ ጥገና ሕክምና ይደረግልኛል፤ተፈውሼ በመልካም ሁኔታ ላይ እሆናለሁ:: አንተስ እንዴት ነህ? ናፍቀሃለሁ::
- እኛ በጣም ደህና ነን፣እኛ የበለጠ ናፍቀንሃል፤ጉብኝትህ በእርግጥ የውይይት መክፈቻ ቁልፍ ነበር . .
- ዶክተር ይህ ያንተ ትህትና ነው . . ካንተ ብዙ ነው የተማርኩት፣ስለ ክርስትና የተለያዩ ፈለጎች የተናገርከው እስካሁን ጆሮዬ ውስጥ እንዳቃጨለ ነው:: በነገራችን ላይ የነገርከኝን ለማረጋገጥ በመጪው ሳምንት ሮምና ቫቲካንን እጎበኛለሁ::
- ግሩም ነው፣መታደልን የመፈለግ ጉዞህን ቀጥልበት፣የምትደርስበትን ውጤት እንደምታሳውቀን የገባህን ቃልም አትዘንጋ::
- ፈጽሞ አልረሳም፤የመታደል መንገድ ፍለጋው የት እንደደረሰ አሳውቃችኋለሁ፣ለሌቪም ቃል ገብቻለሁ::
- አስደሳች ዜና ልንገርህ . . ከሌቪ ጋር ሳንጋባ አንቀርም::
- ዋው! . . የተባረከ ይሁን፣እንኳን ደስ አላችሁ . . ካቶሊካዊ ወይስ አይሁዳዊ ጋብቻ?
- እህህ፣ጋብቻው ከወራት በኋላ እንጂ አይፈጸምም፣ገና ያልተፈቱ አንዳንድ ጉዳዮች አሉ:: አይሁዳዊም ይሁን ወይም ካቶሊካዊ ወይም ፕሮቴስታንታዊ ወይም ሌላ ግን ወደ መታደል መንገድ በሚያደርስ መንገድ ነው ሊሆን የሚችለው::
- ወደርሱ የሚያደርሰውን መንገድ ለማወቅ ይረዳን ዘንድ ፈጣሪ አምላክን እንለምነዋለን::
- ጌታ ካንተ ጋር ይሁን:: ስለ ጤንነትህና ስለ መታደል መንገድ ፍለጋው ለማወቅ በጉጉት እንጠብቃለን:: ደህና ሁን::

ጆርጅ የሆነ ነገር በማሰላሰል ላይ እያለ የነርሷ ድምጽ አቋረጠው . .

- አንዳንድ ምርመራዎችን ለማካሄድ አሁን መሄድ አለብን::

ጆርጅ ሰዓቱን ተመለከተ፤ልክ አስራ አንድ ሆኗል:: የተለያዩ ምርመራዎች ከተደረጉለት በኋላ ወደ ክፍሉ ተመለሰ . . ሰዓቱ አስራ ሁለት ተኩል ነው፣ካትሪና ገና አልመጣችም ነበረና ደወለላት:: ሆስፒታሉ መግቢያ በር ላይ መሆኗን ነገረችው:: ከደቂቃዎች በኋላ ካትሪና መኪናዋ ተበላሽቶ በሕዝብ

www.path-2-happiness.com

ማመላለሻ ለመጠቀም በመገደዷ ስለዘገየች እያዘነችና ይቅርታ እየጠየቀች ገባች::

-ስትቆዪ ምን አገኝቷት ይሆን ብዬ አሰብኩ::

-መኪናዋ መንገድ ላይ ስትበላሽብኝ የበለጠ እንዳልቆይ መንገድ ዳር አቁሜ በአውቶቡስ ተሳፈርኩ::

-ይህን ፖስታ ያዥው፣ክፋ ነገር ቢያጋጥም የሚያስፈልጉሽ ወረቀቶችና ሰነዶች ሁሉ ተካተውበታል::

-በእግዚአብሔር ፈቃድ ክፉ አያገኝህም፣ተፈውሰህ ትወጣለህ::

-አንድ ያልጻፍኩት ነገር አለ::

-ምንድነው?

-ላንቺም ይሁን ለልጆችሽ የመታደል መንገድ ፍለጋውን እንድትቀጥዪበት እፈልጋለሁ::

-የመታደል መንገድ ፍለጋውን አንተው ራስህ ታሚለዋለህ፤ወደምትፈልገውም ትደርሳለህ . . የመልካም ስነ ምግባርና የመርህ ባለቤት ነህና እግዚአብሔር ፈጽሞ አያሳፍርህም::

-እንባሽን ጥረጊ . . ካቲ ቃል ግቢልኝ::

-በእግዚአብሔር ፈቃድ ካንተ ጋር በመሆን የመታደል መንገድ ፍለጋ ጉዞውን እቀጥልበታለሁ፤ለዚህም ቃል ገብቼልሃለሁ:: የመጀመሪያው ፍለጋም አብረን ወደ ሮማ በምናደርገው ጉዞ ይሆናል::

-ካትሪና እወድሻለሁ . .

ወደርሷ ቀረብ ብሎ እቅፍ አደረጋት . . በለቅሶ ፈነዳች . .

-ጆርጅ እኔም እወደሃለሁ::

-እንደ ልማድሽ በተስፋ የተሞላሽ ሁኚ፤በሮም የምናርፍበትን ሆቴል ይዘሽልናል?

-አዎ::

ቀሪ ምርመራዎችን ያጠናቅቅ ዘንድ ጆርጅን ለመውሰድ ነርሷ መጣች . . የካትሪናን እጅ ጠበቅ አድርጎ በመያዝ ወደ ቤት እንድትሄድና እንድትጸልይለት ለመናት . .

-የኔ ፍቅር ወደ ቤት ሂጂ:: ከአፍታ በኂላ ለማደንዘዣ ይወስዱኛል፣ቀዶ ጥገናውም ሦስት ሰዓት ይወስዳል . . እናም እዚህ መቆየትሽ አስፈላጊ አይደለም:: ሁሉም ነገር ስለሚሳካ ተረጋጊ . .

-እንዲህ አትበል፣ጆርጅ እወደሃለሁ፣ካንተ ጋር ወደ ሮም እንጓዝና የመታደለን መንገድ እናገኘዋለን::

-የኔ እመቤት መሄድ ትችያለሽ፤ቁጥርሽ ስላለ ከቀዶ ጥገናው በኂላ እንደውልልሻለን::

-ጆርጅ እንግዲያውስ ጌታ ይጠብቅህ፣ዕድሜህንና ሕይወትንህም ይባርክ::

ለራሱ ፈጽሞ ፍርሃት የሚባል ነገር ዝር ባይልበትም ልቡ ለካትሪና እና ለልጆቹ በፍርሃት እየራደ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍሉ አመራ:: የእያንዳንዱ ሰው ጭንቀትና ሀሳብ ለገዛ ራሱ ብቻ ቢሆን ኖሮ ይህች ዓለም ምን ትሆን ነበር? ሲል ራሱን ጠየቀ:: በእርግጥ የማይታሰብ አደጋ ነበር የሚሆነው፣የሌሎችን ሕመም፣ሀሳብና ጭንቀት መጋራት የራስን ሕመምና ጭንቀት ለማቅለልና በተዕግስት ለመቋቋም አጋዥ ነው . . ሕይወትም እንደዚሁ፣ሰዎችን ለመጥቀም ለማስደሰት የሚኖር ሰው ደስተኛ ይሆናል፣መታደልንም ያገኛል:: ለራሱ ብቻ የሚኖር ሰው ደግሞ መንገዱን ይስታል . . እየተግተለተለ የሚመጣ ሀሳቡን ሐኪሙ አቋረጠው . .

-አሁን በከፍተኛ የመረጋጋትና የሕሊና ሰላም ላይ እንድትሆን እፈልጋለሁ:: የምርመራህ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት በጣም አመርቂ ስለሆነ ሁሉም ነገር ስኬታማ ይሆናል::

(4)

ቀዶ ጥገናው እኩለ ሌሊት ላይ ተጠናቀቀ፤አራት ሰዓት ነበር የፈጀው:: ካትሪና በየሰዓቱ ወደ ሆስፒታሉ ስትደውል ነበር የቆየችው:: ቀዳጅ ሐኪሙ ከቀዶ ጥገና ክፍሉ ወጥቶ እስከ ደወለላት ጊዜ ድረስ አልተረጋጋችም ነበር:: ነገሮች ሁሉ በተፈለገው መንገድ መከናወናቸውን፣ የቀዶ ጥገናው ውጤት ከአስራ ሁለት ሰዓቶች በኂላ የሚታይ መሆኑንና ከዚህ ጊዜ አካባቢ በፊት እንደማይነቃ ነገራት . .

-የኔ እመቤት አይዞሽ ተረጋጊ:: የስልክ ጥሪዎች ወደ ሆስፒታሉ እየጎረፉ ናቸውና ሌሎች የሚደውሉ ሰዎችንም አረጋጊያቸው::

-እነማን ናቸው የሚደውሉት?

-አደም፣ቶም . . የምታውቂያቸው ከሆነ እባክሽ ደውይላቸው::

-እሽ . . እንዲጸልዩለት እነግራቸዋለሁ::

በተከታዩ ቀን አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ . . ጆርጅ መንቃት ጀምሮ እጁን ባልተለመደ ሁኔታ እያንቀሳቀሰ ግልጽ ያልሆኑ ቅዥት መሰል ቃላትን እያሰማ ነው:: መንቃቱን ለመጠበቅ አጠገቡ ተቀምጠው የነበሩት ካትሪና አደምና ቶም በቅዠት ከሚናገራቸው ውስጥ . . የመታደል መንገድ፣ለምን ተፈጠርን . . ሕይወት . . ሞት . . የሚሉትን ከመሳሰሉ ውስን ቃላት

በስተቀር የገባቸው ነገር አልነበረም::

ጆርጅ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ሐኪሙ ሲመጣ ካትሪና በመጣደፍ ብድግ ብላ ተቀበለችው . . በፈገግታ ተቀበላት . .

-የኔ እመቤት ጭንቀትሽን እረዳለሁ . . ሁሉም የምርመራ ውጤቶች በጣም አመርቂ መሆናቸውን ላበስራችሁ እፈልጋለሁ፤ከአፍታ በኋላ ይነቃል ብለን እንጠብቃለን::

-ዶክተር . . የማይታወቅ ነገር ሲናገር ነበር!

-አታስቡ! ገና ሙሉ በሙሉ አልነቃም፤ይህ የተለመደ ነገር ነው:: የማደንዘዣው ተጽእኖ ሙሉ በሙሉ ከተወገደና ግልጽ የሆነ ነገር መናገር ከቻለ ለቀዶ ጥገናው ስካታማነት የመጀመሪያው ምልክት ነው:: ነገ መሳሪያዎቹን ከርሱ ማላቀቅ እንጀምራለን፤መንቀሳቀስና ተነስቶ መቆም ከቻለ ቀዶ ጥገናው መቶ በመቶ ስኬታማ ሆኗል ማለት ነው . . ሲነቃ በየሦስት ሰዓቱ የሕመም ማስታገሻ እንሰጠዋለን:: ከዚያ በኋላ ሙሉ ጤናማ ሆኖ ታገኙታላችሁና አይዟችሁ::

-እናመሰግናለን ዶክተር፣እግዚአብሔር ይጠብቀው::

-በነገራችን ላይ ቀዶ ጥገናው ከመጀመሩ በፊት በማደንዘዣው ወቅት ‹‹የመታደል መንገድ›› የሚል ቃል ይደጋግም ነበር፤ የመታደል መንገድ ምን ይሆን?

-ሁሉንም ነገር ትቶ ለማግኘት በፍለጋው ላይ የተሰመራበት መንገድ ነው::

-እዚህ ሆስፒታል ገብተው ከታከሙት ሰዎች ሁሉ ይበልጥ ደስተኛ ሰው እርሱ ነው፤የመታደልን መንገድ ለምንድነው የሚፈልገው?

-የመታደል መንገድ ፍለጋውን ሲጀምር እንጂ ደስተኛ አልሆነም::

-በሰላም ተፈውሶ ከተነሳ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዱን ያገኘዋል፤ፍቀዱልኝና ልሂድ::

ሐኪሙ እንደወጣ . . ቶም ከላዩ በተጠመዱ የሕክምና መሳሪያዎች ስር ወደ ተኛው ጆርጅ ፊቱን አዞረ . . በአዘኔታም አጉተመተመ . .

-አንተ ጆርጅ፣በእርግጠኝነት የመታደልን መንገድ ታገኘዋለህ፤እኔም ካንተ ጋር አገኘዋለሁ:: የመረገም መንገድ የሆነውን የኤቲዝምን መንገድ ሞክሬያለሁ፤ጭንቀትና ውጥረት ብቻ እንጂ ያተረፍኩት ነገር አልነበረም፤ይሁን እንጂ የፈጠረን ርህሩህ ጌታ እኛን ወደ ቀጥተኛው መንገድ ሊመራን እንደሚችል እርግጠኛ ብሆንም እስካሁኗ ደቂቃ ድረስ ግን የትኛውንም ሃይማኖት አምኜ አልተቀበልኩም::

-ቶም አንተም እንደምታገኘው እርግጠኛ ነኝ::

-አደም እንዴት ነው የማገኘው?

-አንተ ያልከውን ልድገምና ርህሩሁ አምላክ ወደርሱ ለመቅረብ የፈለገውን አያርቅም፤ስለዚህም እኔም አንተም ጆርጅም ለመፈለግ የምንጥረውን እናገኘዋለን::

-አንተም ጭምር በመታደል መንገድ ፍለጋ ላይ ነህ?

-ምናልባት!!

ጆርጅ ዓይኖቹን በግድ መክፈት ጀመረ . . ካትሪና አወቀችና ወደርሱ ቀረብ አለች . .

-ጆርጅ የኔ ፍቅር ትሰማኛለህ?

-አዎ::

-በሰላም በመንቃትህ ጌታ የተመሰገነ ይሁን:: በጣም ተጨንቀንልህ ነበር፤ይኸውና አደምና ቶም አንተን ለማየት መጥተው እዚህ ይገኛሉ::

-አመሰግናለሁ::

-ፈጣን ፈውስ እመኝልሃለሁ::

-እኔም ፈጣን ፈውስ እመኝልሃለሁ:: ሐኪሙ ቀዶ ጥገናው ስኬታማ መሆኑን አብስሮናል::

-የኔ ፍቅር የምትፈልገው ነገር ይኖራል?

-የለም::

-ጫና ልንፈጥርበት አይገባም፤በቀስታና በእርጋታ እንዲነቃ አሁን ልንተወው ይገባል::

-ልክ ነው . . ስለዚህም እኔና አደም እንሂድና አንቺ ከአጠገቡ ሁኚ::

-ሁለታችሁንም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፤እርሱ ራሱ ዛሬ ደውሎላችሁ ያለበትን ሁኔታ ይነግራችኋል::

-አደም መኪና አለህ ወይስ እንዳደርስህ ትፈልጋለህ?

-መኪና የለኝም፤አንተንም ማስቸገር አልፈልግም፤በሕዝብ ትራንስፖርት እሄዳለሁ::

-ካንተ ጋር ትንሽ ማውራት ስለምፈልግ ግባ አብረን እንሄዳለን . . ካትሪና ደህና ሁኚ::

-ደህና ሁኑ::

ቶምና አደም ከወጡ ከግማሽ ሰዓት ያህል በኋላ . . አጠገቡ ያለችው ካትሪና በሀሳብ ዓለም ጭልጥ እንዳለች ጆርጅ እንደገና ዓይኖቹን ከፈተ . .

-ካትሪና . .

www.path-2-happiness.com

- ጆርጅ የኔ ፍቅር . . አሁን እንዴት ነህ?
- ደህና ነኝ . . ቶምና አደምን ያየኋቸው መሰሎኝ ነበር ልበል?
- ሁኔታህ አስተማማኝ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ከአፍታ በፊት ነው የሄዱት፤ከማለዳ አንስቶ እዚህ ነበሩ . . የኔ ፍቅር አንተ እንዴት ነህ?
- አሁን ስንት ሰዓት ነው? . . ራስ ቅሌ ውስጥ ሕመም እየተሰማኝ ነው።
- ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አካባቢ ነው፤አትጨነቅ አሁኑኑ ሐኪም አስጠራለሁ። ነርሷ እንደጠራችው ሐኪሙ ወዲያውኑ ከተፍ አለ . .
- ጆርጅ ጥሩ ሁኔታ ላይ ነህ።
- ራስ ቅሌ ውስጥ ከባድ ሕመም ይሰማኛል።
- ችግር የለውም፤አሁን ማስታገሻ ትወስድና ይተወሃል፤የራስ ቅል በከፊል ተከፍቶ ስለነበር ይህ የተለመደ ነገር ነው። ነገሮች ሁሉ መልካምና አበረታች ናቸው።
- ትንሽ ከበድ ቢለውም በግልጽ መናገርም ጀምሯል።
- ይህ የቀዶ ጥገናው ስኬታማ መሆን ምልክት ነውና ሀሳብ አይግባሽ፤ጆርጅ አንተም ሀሳብ አይግባህ።
- አመሰግናለሁ።

ሐኪሙ የሕመም ማስታገሻ መርፌ ወጋው . . ወደ ካትሪና ዞሮ ጆርጅ ከመርፌው በኋላ በትንሹ ለሁለት ሰዓት የሚተኛ በመሆኑ ወደ ቤት እንድትሄድ መከራት . .

- እዚሁ ሆኜ እጠብቀዋለሁ።
- ከነቃ በኋላም ሁለት ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ የሚቆይ ሌላ መርፌ ይሰጠዋል፤ለማንኛውም ውሳኔው የራስሽ ነው።
- የኔ ፍቅር ሂጂ።
- ቀኑ ሙሉ ስላንተ ስጸልይ እውላለሁ።

ጧት አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ጆርጅ ነቅቶ ከነርሷ ጋር በጥሩ ሁኔታና በግልጽ ለመነጋገር ቻለ። ይሁን እንጂ ገና ምግብ አልተፈቀደለትም አሁንም የሚመገበው በግሉኮስ ነው . .

ለካትሪና ደውሎ በመነጋገር አጽናናት። ለአደምና ለቶምም እንዲደውል ጠየቀችውና ደወለላቸው፤ ከዚያም ለሌቪ ደወለ . . በመቀጠል ስለ መታደል መንገድ ፍለጋውና ስለ ሮም ጉዞው ማሰላሰሉን ቀጠለ . .

ወደ አብያተ ክርስቲያናት አገር . .

www.path-2-happiness.com

11 ወደ አብያተ ክርስቲያናት አገር . .

ወደ አብያተ ክርስቲያናት አገር . .

(1)

የጆርጅ ጤንነት ቀስ በቀስ መሻሻል እያሳየ ነው:: ለቀዶ ጥገናው ስኬታማነት ምልክቶች እየታዩ ነው:: ከማግስቱ ጀምሮ የሕክምና መሳሪያዎቹ ስለ ተነሱለት መንቀሳቀስ ችሏል:: በግሉኮስ ከሚሰጠው ፈሳሽ ምግብ ውጭ ግን ገና መብላት አልጀመረም . . ካትሪና እና ልጆቹ ሊያዩት መጡ:: በመልካም ጤንነት ላይ ሆኖ በደስታና በፍካት ሲያዋራቸው ስላገኙት በጣም ተደሰቱ:: ደስታው ትናንት መልእክት ልኮላቸው እንዲጸልዩለት ጠይቋቸው ለነበሩ ሁሉ የምስራች መልክት ማስተላለፉን አላስረሳውም:: ማን ያቃል ምናልባት ቀዶ ጥገናው የተሳካው በአንደኛቸው ጸሎት ምክንያት ሊሆን ይችላል . . ምናልባት !

ጆርጅ ስለ ክርስትና እና ስለ ተለያዩ ፈለጎቹና ጎራዎቹ በተቻለ መጠን የበዛ መረጃ ሰንቆ ለሮም ጉዞው ለመዘጋጀት ወደ ጥልቅ ንባቡ ተመልሷል:: ፕሮቴስታንት ሆኖ ተወልዶ ስለ ሃይማኖቱ የሚያውቀው እጅግ በጣም ጥቂት ብቻ መሆኑ ሁሌም ይገርመው ነበር:: ከሚያውቀው ውስጥ አብዛኛው ከካቶሊኳ ካትሪና ወይም ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ በነበረበት ጊዜ ከካቶሊኩ ሐቢብ ወይም ለመታደል መንገድ ፍለጋው ጥረት በቅርቡ ካደረጋቸው ንባቦች የተማረው ነው:: የማያውቁትን ሃይማኖት እንደሚከተሉት ብዙኃኑ ክርስቲያን መሰሎቹ ሁሉ ከዚህ ቀደም ይህ ነው የሚባል ሃይማኖትን የማጥናት አጋጣሚ ተመቻችቶለት አያውቅም:: እንዲያውም ብዙዎቹ እንደሱው ከስሙ ባለፈ ስለ ሃይማኖታቸው የሚያውቁት ነገር የለም::

በክርስትና ላይ ያደረገው ንባብ በተለይም በክርስትና ጎራዎችና ቡድኖች መካከል ያሉ እምነትን፣አፈጻጸምን፣አምልኮን የሚመለከቱ ከፍተኛ ልዩነቶች፣የተደረጉ ጦርነቶች እና ታላላቅ ግጭቶች በእጅጉ የሚያስደነግጡ ነበሩ:: ይህ ሁሉ ቅራኔና ልዩነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ? በሚለው ላይ ብዙ ያሰላስል ነበር:: ካቶሊካዊነት ቀዳሚ በመሆኑ ችግሩ የመጣው ከፕሮቴስታንት ነው ያለችው ካትሪና እውነቷን ይሆን? ሆኖም በክርስትና ታሪክ ኦርቶዶክስ ከካቶሊክ ቀዳሚ መሆኑን አስታወሰ:: በቅርበት መርህ ከተኬደ ለኢየሱስ ዘመን ይበልጥ የሚቀርበው የእምነቱ ጎራ በትክክለኛው መንገድ ላይ ነው

www.path-2-happiness.com

ተብሎ ይገመታል፤ይሁን እንጂ ወንጌሎች በኢየሱስ ሕይወት ዘመን ተጽፈው አልተቀመጡም . . ታዲያ የትኛው የክርስትና ጎራ ነው ትክክለኛው? በጉዳዩ ላይ ከሌላ ሰው ጋር የመነጋገር ፍላጎት አደረበትና ለኣደም ለመደወል ወሰነ . .

- ሃሎ ኣደም እንደምነህ?
- ሃሎ እንደምነህ ጃል . . እንኳን በሰላም ወጣህ::
- ኣደም አመሰግናለሁ፤በተቻለ መጠን በቅርብ ጊዜ ብንገናኝ ምኞቴ ነው::
- የሚመችህ ከሆነ ነገ መምጣት እችላለሁ::
- በጣም ጥሩ፣ግን ጥያቄ አለኝ፤ከቶም ጋር የጀመርኩትን ልግፋበት ወይስ ላቁም?
- ቀጥልበት የሚል ሀሳብ አለኝ፤ይሁንና ጥያቄው ለምን ተነሳ? ለምንስ አሁን?
- እኔ እንጃ፣ምናልባት አንዳንዴ ምንም አዲስ ነገር የለም የሚል ስሜት ስለሚሰማኝ ሊሆን ይችላል::
- አዲስ ነገር የለም ስትል?
- እንጃ፣እንዳው የሆነ እንግዳ ስሜት ነው በቃ::
- እኔም አላውቅም፤የማውቀው ነገር ቢኖር አዲስ ነገር ካልታየህ በስተቀር መቀጠል እንዳለብህ ነው:: በተለይም አንተ ብዙ እየተጠቀምክ ከመሆኑም በተጨማሪ እንደምትለው ቶም ራሱ ጥሩ መሻሻል አሳይቷል::
- ልክ ነህ፤ለምን እየተመቸኝ እንደመጣና እንደ ሐኪም ሳይሆን እንደ ወዳጅ ማየት ለምን እንደ ጀመርኩ አላውቅም:: ለማንኛውም ይህ የሚሰማኝ ነገር እንጂ ሌላ አይደለም:: ቀጠሮ ለመውሰድ እደውልለታለሁ:: መልካም ፈቃድህ ከሆነ ግን ከዚያ በፊት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ነገ ካንተ ጋር መወያየት እሻለሁ::

ጆርጅ የስልክ ጥሪውን አበቃና ለቶም ደውሎ ወደ ሮም ከመጓዙ በፊት ቀጠሮ እንዲይዝለትና ቦታው በሆስፒታሉ እንዲሆንለት ጠየቀው:: ቶምም ላስቸግርህ አልፈልግም በማለት እርሱ ራሱ ወደ ሆስፒታሉ ለመምጣት ተስማማ::

- ተነገወዲያ ጧት ይሁን:: ሐኪሙ ከሦስት ቀናት በኋላ ትወጣለህ ብሎኛል::
- ጆርጅ አንተን ደስ እንዳለህ ይሁን::

ጆርጅ በንባብ ተጠምዶ እያለ ካትሪና መጣች . . ፊቷ በደስታ ፈክቶ ከፍ ባለ ድምጽ ሰላምታ አቅርባ ወደ ክፍሉ ገባች:: ከጎኑ ቁጭ አለችና ጉንጬን

ሳመች . .

- በጣም ደስ ብሎኛል፣ሐኪሙ እንደ ነገረኝ የጤንነትህ ሁኔታ አመርቂ ነው::
- አዎ ደህ ነኝ፣የሮም ጉዞ ጉዳይስ?
- ከሞላ ጎደል ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው:: ትኬቶች ኦኬ ተደርገዋል፤ሆቴልም ተይዟል:: ከአንዳንድ ግለሰቦች ጋር የሚኖሩት ቀጠሮዎችና ከአስጎብኚዎች ጋር የሚደረጉ የጉብኝት ፕሮግራሞችም ተመቻችተዋል::
- በጣም ጥሩ፣ግና ከአንዳንድ ግለሰቦች ጋር የሚኖሩ ቀጠሮዎችን ስትይ ምን ማለትሽ ነው?
- የምትፈልገውን አውቃለሁ፤ከአንዳንድ ቀሳውስት ጋር ተገናኝተህ እንድትወያይና ቫቲካንን እንድትጎበኝ ተመቻችቷል::
- ይህ እኔ የምፈልገው ሳይሆን አንቺ የምትፈልጊው ነው::
- አዎ፣እኔ እምፈልገው ነው፤ፕሮግራም ያስያዝኩት ግን ያንተም ፍላጎት መሆኑን ስለማውቅ ነው::
- ልክ ነሽ፣የኔ ፍቅር አመሰግናለሁ::
- ከሐኪም ቶም ጋር ቀጠሮ የምትወስደው ከጉዟችን በፊት ነው ወይስ ከዚያ በኋላ?
- ከዚያ በፊት፣ነገ እዚህ ሆስፒታል እንዲሆን ተስማምተናል . . ለሕክምና ቀጠሮው ትኩረት የምትሰጭ ትመስያለሽ?
- ልክ ነህ፣ቶም ዘንድ ለሕክምና ቀጠሮ መሄድ ከጀመርክበት ጊዜ አንስቶ ይበልጥ ደስተኛ እንደ ሆንክ መስሎ ለምን እንደሚሰማኝ አላውቅም::
- በዚህ ምክንያት ብቻ ነው?!
- አዎ በዚሁ ምክንያት ብቻ . . ለምን እንደሆነ ባላውቅም ምናልባት ቶም ራሱም ከነበረበት ሁኔታው አሁን የተሻለ ሆኖ ስለሚሰማኝም ሊሆን ይችላል::
- እኔም እንደዚሁ ዓይነት ግንዛቤ ብኖረኝም እያጭበረበረኝ ነው የሚል ስጋት ግን አለኝ::
- ሁሉም ሊሆን ይችላል፣እኔ ግን እውነተኛ መለወጥ ነው ወደሚለው አደላለሁ::
- ይሁንና እያታለለን ከሆነ ዓላማው ምንድነው?
- እኛን በማታለል የሚያገኘው ጥቅም አለ ብዬ አልገምትም:: ለዚህ ነው መለወጡን እውነት ብዬ የማምነው::

www.path-2-happiness.com

- የቢሮው ኃላፊ በራድ ባይኖር እኔም እንደዚያ ነው እምነቴ::
- ያን ሰውየ በጣም እጠለዋለሁ:: ፈጽሞ የማይመች እኩይ ሰው አድርጌ ለምን እንደማየው አላውቅም::
- ቶም ራሱም እንዲሁ ተማርሮበታል!
- ሊሆን ይችላል ግን አሳማኝ አይደለም! ከሚማረርበት ከሥራ አሰናብቶት መገላገል ይችላል::
- ልክ ነው፤እኔ እንጃ ምናልባት ሌላ ምክንያት ሊኖር ይችላል! ለማንኛውም ከርሱ ጋር ያለኝን ሕክምና ለማቆም ሳስብ ነበር::
- ይህ ተገቢ መስሎ አይታየኝም . . ውሳኔው ግን ያንተ ነው::
- ሀሳብሽ በትክክል ከኣደም ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው:: አንዴ የጀመርከውን መንገድ መጨረስ ይጠበቅብሃል ነው የሚለኝ:: የቶምን መሻሻል እየጠቆመ መጥፎ በነበረበት ጊዜ አብረህ ቀጥለህ መሻሻልና መለወጥ ሲጀምር እንዴት ትተወዋለህ ባይ ነው::
- ሎጂካዊ አነጋገርና ጠንካራ መከራከሪያ ነው::
- ሁልጊዜ በሀሳብ መጣጣማችሁ ኣደምን ፕሮቴስታንት ሳይሆን ካቶሊክ ነው ብዬ እንድደመድም ያደርገኛል::
- እህህ፣ምናልባት ደግሞ ካቶሊካዊነት ከፕሮቴስታንትነት ይልቅ ለእውነት የቀረበ ለመሆኑ አስረጅ ሊሆንም ይችላል::
- ሊሆን ይችላል፤ሮም ላይ አንስተን እንወያይባቸዋለን ብዬ ብዙ ጥያቄዎችና ንጽጽሮችን ሰብስቤ አዘጋጅቻለሁ::
- ግሩም ሀሳብ ነው:: የምናመራው ወደ ካቶሊካዊነት ማዕከል ብቻ ሳይሆን ወደ ዓለም አቀፍ የክርስትና ማዕከል ነውና::
- ምናልባት የካቶሊካዊነት ማእከል ቢሆን እንጂ በእርግጠኝነት የክርስትና ማእከል ግን አይደለም:: በአሳዛኙ ጳጳሳዊ ሥርዓት እኛ አናምንም::
- እንዲህ ያለውን አባባል ሁለተኛ እንዳትናገር፤በተስማማነው መሰረት እነዚህን ርእሰ ጉዳዮች ሮም ስንደርስ እንወያይባቸዋለን:: ካቶሊካዊነት ላይ ጫን ያልክ አይመስልህም? በአፈንጋጬ ፕሮቴስታንት ላይ ያሉንን ትችቶች እንዳነሳ ነው የምትፈልገው?
- አፈንጋጬ!! ለፕሮቴስታንት ቆንጆ አገላለጽ ነው! አንቺ በተናገርሽው እኔ እንዳንቺ አለመቆጣቴን አታስተውይም?!
- እህህ፣ፕሮቴስታንትን የሚገልጽ ተጨባጭ አገላለጽ መሆኑን ስለምታውቅ ሊሆን ይችላል:: ሃማኖታችሁን እንዳሻችሁ አይደለም የምትደርሱትና እየጠፈጠፋችሁ የምትሰሩት? መጽሐፍ ቅዱስንም እንደ መሰላችሁ አይደለም የምትረዱት? ማለት የፈለኩት አፈንጋጭነትም ይኸው ነው!
- ምናልባት እንዳልሽው ሊሆን ይችላል፤አልያም ከሮማዋ ቤተክርስቲያን ጥመትና ከምትቸበችበው የምህረት ማስገኛ ምስክር ወረቀት ነጻ በመሆናችን ሊሆን ይችላል::
- ይህን ሁሉ ሮም ላይ ልንወያይበት ተስማምተናል:: እናም አሁን ክርክሩን ብናቆም ምን ይመስለሃል?
- እህህ፣ተስማምተናል:: በቀጠሮአችን መሰረት ለመጓዝ ምናልባት የሚፈለግ ነገር ካለ ሐኪሙን ጠይቀሽ እንድታረጋግጭ እፈልጋለሁ፤ለጉዞው በጣም ጓግቻለሁ::
- ኤጲስ ቆጶሱን ለመገናኘት ጓግቻለሁ ማለትህ ነው!!

ጆርጅ ተመቻችቶ ተቀመጠና ፈገግ ብሎ ፦

- አዎ፣ሃይማኖቱ የተሳሳተ መሆኑን እፊትሽ ላሳምነው::
- ያን ሹፈትህን የማውቀው ብሆንም በዚህ ጉዞ በእውነት ገለልተኛና ሚዛናዊ ለመሆን ከራሴ ጋር እታገላለሁ፤ ስለዚህ የኔ ፍቅር ልታግዘኝ ትችላለህ?
- የኔ ፍቅር መቼም ልቤን እንዴት እንደምታሸንፊው ታውቂያለሽ:: በማስረጃ ሳሸንፍሽ በፍቅር ትረቺኛለሽ:: አዎ፣የምችለውን ሁሉ እንደማደርግ እርግጠኛ መሆን ትችያለሽ::
- ጆርጅ እወደሃለሁ፤አሁን ስለ አንተ ሁኔታና ስለ ጉዞው ጉዳይ ሐኪሙን ለመጠየቅ ልሂድ::

ከአንድ ሰዓት በኋላ ካትሪና ስትመለስ ጆርጅን በንባብ ተጠምዶ አገኘችው . .

- ኦህ አምላኬ . . የምታነበው ነገር እስከዚህ ድረስ አስፈላጊ ነው ማለት ነው?!
- አዎ፣ስለ ማርቲን ሉተርና ስለ ጆን ካልቪን ነው የማነበው:: ሁለቱ በፕሮቴስታንት ላይ ተጽእኖ ካሳደሩት ሰዎች ዋነኞቹ ናቸው::
- የፕሮቴስታንትን ሃይማኖት ደረሱት፣ፈለሰፉት፤ማለትህ ነው?
- በአብዛኛው እውነት ተናግረሻል፤ይሁን እንጂ ያንን ያደረጉት ከካቶሊክ በሽታዎችና ከብልሹ ልማዶቹ ለመገላገል ሲሉ ነው . .
- እናም ፕሮቴስታንት ልቦለድ ድርሰት መሆኑን አምነህ ትቀበላለህ ማለት ነው?!
- አንዳንድ ሰዎች ዘንድ ሃይማኖትን ከኋላ ቀርነትና ከአእምሮ ዝግመት ጋር

www.path-2-happiness.com

የተያያዘ አድርገው እስከማየት ደረጃ ድረስ፣ካቶሊካዊነት በሚስጥሮቹና በጳጳሳዊ ሥርዓቱ የፈጠረውን የኢ-አማኝነት (ኤቲዝም) ማእበል ለመገደብ ሲባል የተደረገ በመሆኑ እያዘንኩ አዎ እልሻለሁ! በዚህ ላይ አሁኑኑ እንድንከራከር ትፈልጊያለሽ?

-ኦህ . . ጉዳዩ በቀጥታ በካቶሊካዊነት ላይ ነው የተደፈደፈው:: ፕሮቴስታንታዊነት ልቦለድ ድርሰትና የክርስትና ሃይማኖት ብረዛ መሆኑን አምነህ እስክትቀበል ድረስ ሮም ላይ እንከራከርበታለን::

-እውነትሽን ነው፤ፕሮቴስታንት ከካቶሊክ የተዛነፈና ያፈነገጠ ነው:: ለዚህም ነው አንዱ ሌላውን ከክርስትና የወጣ ከሃዲ አድርጎ የሚያየውና የሚዋጋው . . ሌላው ቀርቶ የፕሮቴስታንት ጎራዎችም አንዱ ሌላውን ከሃዲ አድርገው ይመለከታሉ:: የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያኖችና ጎራዎች ቁጥር ስንት እንደሆነ ታውቂያለሽ?

-አላውቅም፣ወደ መቶ ይደርሳሉ?

-ይህ ዜና ምናልባት ሊያስደምምሽ ይችላል:: የቤተክርስቲያኖቹና የጎራዎቹ ቁጥር ከሃያ ስምንት ሺህ እስከ አርባ ሺህ ነው::

-አርባ ሺህ ቤተክርስቲያኖችና ሰክቶች?!

ጆርጅ በመከፋት ስሜቱ ተለዋወጠ:: ፊቱን ቅጭም አደረገ፣ቀና ብሎ ተመቻችቶ በመቀመጥ እንዲህ አለ ፦

-በጣም እያዘንኩ አዎ፤ይህም መለኮታዊ ያልሆኑና ሕንድ ውስጥ ያየኋቸውን የመሳሰሉ ቡድኖችን እንዳስታውስ ያደርገኛል:: አሁንም እያዘንኩ ግልጽ መሆንና ለራስ መታመን በእውነት አስቸጋሪ ነገር ነው!

-የፕሮቴስታንት እምነት የፈጠራ ድርሰት ነው ብየህ የለ ! (ፈገግ ብላ ቀጠለችና) ፦ ይሁንና በስምምነታችን መሰረት ሮም ላይ ነው የምንከራከርባቸው::

-ከአንድ ጊዜ በላይ የፈለግሽውን እየተናገርሽ ሮም ላይ እንወያይባቸዋለን ትያለሽ:: (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ ግዴለም ላንቺ ሲባል ይሁንልሽ፤ሐኪሙ ምን አለ?

-ጆር እወደሃለሁ . . ሐኪሙ የነገረኝ የጤንነትህ ሁኔታ እጅግ በጣም ጥሩ መሆኑን፣የቀዶ ጥገና ሕክምናው መቶ በመቶ የተሳካ በመሆኑ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከሆስፒታል የምትወጣ መሆኑን፣ከወጣህ በኋላ ከሁለት እስከ ሦስት ቀናት ብቻ ዕረፍት ማድረግ በቂህ መሆኑንና ከዚያ መደበኛ ሕይወትህን መቀጠልም ሆነ ያለ ምንም ስጋት ጉዞውን ማድረግ

እንደምትችል ነው::

-በጉዞው ወቅት የሚደረጉ የተለዩ ጥንቃቄዎች አሉ?

-ጠይቄው ራስህን አለማንገላታትን ለአደጋና ለአስቸጋሪ ሁኔታ አለመጋለጥን ከመሳሰሉና ከቀዶ ጥገናው ጋር ግንኙነት ከሌላቸው አጠቃላይ የጤና ምክሮች ውጭ የተለዩ ጥንቃቄዎች ፈጽሞ አለመኖራቸውን ነግሮኛል::

-መልካም::

-ግሩም ድንቅ ጉዞ ይሆናል፤የትዳራችንን የመጀመሪያዎቹን ቀናት ዳግም እናድስበታለን::

-የጋብቻችን የመጀመሪያዎቹ ቀናት ድንቅ ነበሩ! እናድሳቸዋለን፤በጉዞውም ተደሳቾች እንሆናለን፤በተጨማሪም አዲስ ነገር ያለበት ጉዞም ይሆናል . .

-ምን አዲስ ነገር?

-የማይክልና ሳሊ ከኛ ጋር መኖር::

-ለነሱ ስንል የጉብኝቱን አንዳንድ ይዘቶች ለመለወጥ ብንገደድም ደስታችንን እጥፍ ድርብ ስለሚያደርጉ በጣም እወዳቸዋለሁ::

-እነሱን በሚመለከት ማድረግ የሚገባኝን እንዳላደረግሁ አውቃለሁ፤ሳላስበው ድንገት እንዳደጉ ነው የሚሰማኝ::

-የነፈግናቸውን በቂ ጊዜ ወደፊት እንክሳቸዋለን፤አይመስልህም?

-አዎ፣የማበረክትላቸው ከሁሉም የላቀ ስጦታ የመታደልን መንገድ እንዲያውቁ ማድረግ ነው የሚል እምነት አለኝ::

-አሁንም የመታደል መንገድ!

-ለሁለተኛም ለሦስተኛም ጊዜ እንጂ:: ወደዚያ ለመድረስ እንደተቃረብኩ ለምን እንደሚሰማኝ አላውቅም::

-ማን ያውቃል ሮም ውስጥ አብረን እንደርስበት ይሆናል::

-እህህ፣ሁላችንም እንደገና ካቶሊክ እንሆናለን ማለትሽ ነው?!

-ምናልባት . . ወይ ደግሞ ሌላ ሊሆንም ይችላል::

-ካቶሊካዊነትን ትለቅያለሽ ማለት ነው?!

-ማን ያውቃል? አንተ ራስህ ፕሮቴስታንትን ትለቅ ይሆናል::

-ሌላው ይሆናል ብለን እንገምትና ካቶሊካዊነትን የመልቀቅ ድፍረትና ወኔ ይኖርሻል?

-ይህን ለመወሰን ረዥም ጊዜና ትግል ጠይቆኛል . . ዛሬ ግን አስቸጋሪ ውሳኔ ቢሆንም አዎ ማለት እችላለሁ::

-የኔ ፍቅር ኮርቼብሻለሁ::

www.path-2-happiness.com

-ተልእኮህን ሳትወስን፣ለሕይወትህ ትርጉምና ዓለማ ሳታኖርለትና ለታላላቅ ጥያቄዎችህ ምላሽ ሳታገኝ ለመኖር ያልወደድክ በመሆንህ እኔ ነኝ እንጂ በአንተ የኮራሁት::

-እህህ፣እንግዲያውስ አንቺ ፕሮቴስታንቷ እንኳን ደስ አለሽ::

-እህህ፣አምነህ ወደ ግንዱ ወደ ጥንተ መሰረቱ ወደ ካቶሊካዊነት የተመለስከው አንተ አፈንጋጭ ፕሮቴስታንት እንኳ ደስ አለህ ልበል እንጂ::

(2)

ከካትሪና መሄድ በኋላ ጆርጅ ወደ ንባቡ ተመለሰ:: ስለ ማርቲን ሉተር ስለ ጆን ካልቪንና ስለሌሎቹም፣እንደዚሁም በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ ስለተስተዋሉ አዳዲስ ለውጦች የጀመረውን ንባብ ቋጨ:: በነርሷ ድምጽ እስከባነነ ድረስ ጊዜው አልታወቀውም ነበር . .

-ከወጣህ በኋላ ፈተና አለብህ?

-አዎ፣ወሳኝ ፈተና አለብኝ::

-በየትኛው የትምህርት እርከን?

-አላውቀውም::

-እንድንነጋገር የምትፈልግ አይመስለኝም፤ከንባብህ ስለ ረበሽኩህ ይቅርታ አድርግልኝ:: እኔ እንኳ የመጣሁት ግሉኮሱን ላላቅቅልህ ነው፤ከነገ ጀምሮ መደበኛውን አመጋገብ ትጀምራለህ::

-ይቅርታ፣ማለት የፈለኩት አንቺ እንደተረዳሽው አይደለም:: እውነቱን ለመናገር ፈተና ላይ መሆኔ ይሰማኛል፣ግን የትምህርት ፈተና አይደለም::

-የምትናገረው ምንም አልገባኝም !

-ሃይማኖትሽ ምንድነው?

-እኔ በሁሉም ሃይማኖቶች ብዙም አልተማመንም፤ሆኖም ግን ፕሮቴስታንት ነኝ . . ካልቪናዊ::

-የጆን ካልቪን ተከታይ ነሽ ማለት ነው?

-አዎ፣ይዞት የመጣው አዲስ ነገር ምን እንደሆነ ባላውቅም የርሱ ተከታይ ነኝ:: የማውቀው ነገር ቢኖር ለአእምሮ የቀረበ መሆኑን ብቻ ነው::

-ይዞት የመጣውን አዲስ ነገር ካላወቅሽ ይህን እንዴት አወቅሽ?

-እኔ ነርስ እንጂ መነኩሲት አይደለሁም:: በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መካከል የነበሩትን ደም አፋሳሽ ግጭቶች የፈታ መሰለኝ::

-የአንድ ሃይማኖት አማኞች ሆነው እርስ በርስ መፋጀትና መተላለቅ ለማሰብ አይከብድም?! እንደ ካልቪን ያለ አንድ ግለሰብ መጥቶ ሃይማኖትን ዳግም ጠፍጥፎ መስራቱስ ለማሰብ አያስቸግርም?!

-ለዚህ ነው በፕሮቴስታንትም ሆነ በካቶሊካዊነት ከነአካቴውም በሁሉም ሃይማኖቶች ላይ እምብዛም አልተማመንም ያልኩህ:: ሃይማኖት የሚያስፈልገኝ ባይሆን ኖሮ ፕሮቴስታንታዊነትን ባልተቀበልኩ ነበር::

-ይቅርታ አድርጊልኝና ሃይማኖት የሚያስፈልገኝ ባይሆን ኖሮ ስትይ ምን ማለትሽ ነው?

-ያለ ሃይማኖት መኖር አልችልም፤ሕይወት ያለ ሃይማኖት ስቃይና እርግማን ነው:: ኤቲስት ነበርኩ፤ከዚያ ወደ ዓለማዊነት (ሴኩላሪዝም) ተለወጥኩ:: ስመራው በነበረው የጭንቀት ሕይወት ምክንያት ራሴን ለማጥፋት ተቃርቤ ነበር:: ያለሁበት መንገድ የተሳሳተ መሆኑን ውስጤ ያውቀው ነበርና ያለ ምንም ዝርዝር ማብራሪያ ፕሮቴስታንት ለመሆን ወሰንኩ . . ካንተ ጋር ሀሳብ መለዋወጥ በጣም አስደሳች ነው፣ግና ሥራ ስላለብኝ ፍቀድልኝ ልሂድ::

-ንጹህ ሕሊናሽ አንቺ እንዳልሽው ፕሮቴስታዊነትን ያለ ምንም ዝርዝር ማብራሪያ እሽ ብሎ ይቀበላል? ከገዛ ራስሽ ለመሸሽ ያደረግሽው ነው የሚል እምነት አለኝ፣ግን ወዴት?

የጆርጅ አነጋገር ያሳደረባት ተጽእኖ ከፊቷ ጎልቶ ታየ:: ጭንቀቷንና መንፈሰ ባዶነቷን ለመሸሸግ እየሞከረች . .

-ምናልባት ልክ በነፋስ እንደሚነዳ ላባ ወደማላውቀው መሸሼ ሊሆን ይችላል፤ይሁን እንጂ አንድ ቀን ወደምፈልገው ለመድረስ እችል ይሆናል:: ደህና ሁን ልሂድ::

ጆርጅ በተከታዩ ቀን አማልዶ ከእንቅልፉ ተነሳ:: ከፍተኛ የሆነ ረሃብና የምግብ ፍላጎት አድሮበት ስለ ነበር ቁርስ እንደ ቀረበለት በጉጉትና በአምሮት በላና ወደ ንባቡ ተመለሰ:: የትናንቷ ነርስ ሙቀቱን ለመላካት መጣች . .

-በጣም ጥሩ ነው፣በጎ ሆነሃል::

-ትናንት ረብሼሽ ከሆነ ይቅርታ እጠይቃለሁ::

-አልረበሽከኝም፤ለትሕትናህ አመሰግናለሁ:: ያለ ምንም ግብ ከገዛ ራሴ በመሸሽ ላይ ስለመሆኔ የተናገርከው ነገር ትክክለኛ ይመስለኛል:: ታዲያ ኤቲዝምና ሴኩላሪዝም ስቃይ፣ሃይማኖተኛ መሆን ደግሞ ሽሽት ከሆነ ምን ማድረግ እችላለሁ?

www.path-2-happiness.com

- ሃይማኖተኛ መሆን ሽሽት አይደለም፤አንቺ ግን ከራስሽ ሃይማኖት ነው የምትሸሽው::
- ከእግዚአብሔር የተላለፈ ሳይሆን አንተ እንዳልከው የሚደረስ ፈጠራና ተጠፍጥፎ የሚሰራ ሃይማኖት በመሆኑ ነው:: በየጊዜው ሃይማኖቱ የተሻለ እንዲሆን ለማሻሻልና ለመከለስ የሚመጡ ሰዎች ይኖራሉ::
- ግንኮ መለኮታዊ ሃይማኖት ማለትም ከእግዚአብሔር የተላለፈ ነው::
- ከኔ ይበልጥ አንተ ስለ ሃይማኖት ታውቃለህ:: ይሁንና ካልቪን ወይም ሉተር ወይም ሌላው ሰው እንዳስፈለገው የሚለዋውጠው ሃይማኖት እንዴት ሆኖ ነው መለኮታዊ ሃይማኖት የሚሆነው?! እንዲያውም ኢየሱስ ራሱ አዲስ ኪዳን በጽሐፍ ከመጠናቀሩ በፊት የተገደለ በመሆኑ የተጻፈው በደቀመዛሙርቱ ደቀመዛሙርት አማካይነት ነው::
- የሃይማኖት ፈላስፋ ሳትሆኚ አልቀረሽም !
- እንዳልከኝ ሁሉ ከገዛ ራሴ የምሸሽ ፈርጣጭ ነኝ እንጂ::
- በአንቺ አመለካከት መፍትሔው ምንድን ነው?
- መፍትሔው አንተ የምትተችብኝ ከራስ መሸሽ ነው::
- ከችግሮች መሸሽ መፍትሔ ያስገኛል ብዬ አላስብም::
- ታዲያ በአንተ አመለካከት መፍትሔው ምንድን ነው?
- ወደ ሃይማኖት ዝርዝር ጉዳዮች ገብተን እውነታውን ማወቅ ነው ::
- ቀሳውስትና መነኮሳት ልንሆን?! እነርሱ ራሳቸው ትልቅ ጥርጣሬ አላቸው:: ለዚህ ነው በማያቋርጥ ሁኔታ በሃይማኖት ላይ ለውጥ የሚያካሄዱት::
- መንገዱን ማወቅ ማለት ቀሳውስትና መነኮሳት ሆን ማለት አይደለም:: እኔ ለቀሳውስትና ለመነኮሳት አክብሮት አለኝ፣ ከነሱ አንዱ መሆን ግን አልፈልግም:: ጥርጣሬ እርግማንን ሲያመጣ እርግጠኝነት ግን እርጋታን ያላብሳል::
- ካቶሊካዊ ትመስላለህ:: ለቀሳውስትና ለመነኮሳት ያለ ምንም ጥያቄ እጅ ሰጥተን እንድንገዛ ብቻ ሳይሆን፣ለራሳችን መጽሐፍ ቅዱስን አንብበን እንዳንረዳ ነው የሚፈልጉት::
- በኔና በፈጣሪ አምላኬ መካከል አገናኝ ሰው እንዲኖር ለማድረግ አእምሮዬን አውልቄ አሳልፌ መስጠት አይቻለኝም:: እኔ ፕሮቴስታንት ነኝ::
- ታዲያ አንተ እንደኔው ነህና ለምንድነው የምትተቸኝ?! ሉተራዊ ካልሆንክ በስተቀር::
- እህህ፣እውነቱን ለመናገር የካልቪን ወይም የሉተር ወይም የሌላው ተከታይ

ሆኜ እንደሆነ አላውቅም:: የማውቀው አባቴና እናቴ ፕሮቴስታንቶች ስለነበሩ ብቻ ፕሮቴስታንት መሆኔን ነው::
- እናም አንተ በትክክል እንደኔው ነህና ከራስ በመሸሽ እንዴት ነው የምትገልጸኝ?!
- እኔ ራሴ ከራሴ የሸሽሁ ፈርጣጭ በመሆኔ ነው::
- ወዴት ነው ሽሽትህ?
- ወደ መታደል መንገድ::
- እህህ፣ፈላስፋው ወዴት ነው መንገዱ?
- አላውቅም፣ግን አገኘዋለሁ::
- የፍልስፍናዊ እንቆቅልሾች ባለቤት ትመስላለህ:: በውይይቱ ደስተኛ ብሆንም ለመሄድ እገደዳለሁ:: በነገራችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ጽናትና ቁርጠኝነት ስላለህ እንደምታገኘው እኔም እርግጠኛ ነኝ፤ስታገኘው ግን አሳውቀን::
- ምኑን?!
- የመታደልን መንገድ !

ነርሷ ከሄደች ከአፍታ ቆይታ በኋላ የጤንነቱን ሁኔታ ለማየት ሐኪሙ ወደ ጆርጅ ክፍል መጣ:: በጥሩ ጤንነት ላይ ስለሚገኝ ከፈለገ ነገ ምሽት መውጣት እንደሚችል ነገረው::

- አመሰግናለሁ::
- ባለቤትህ ወደ ሮም እንደምትሄዱ ነግራኛለች:: እንኳን ደስ አለህ እለሃለሁ፤ውብና ታሪካዊት አገር ናት::
- አዎ፣እኔ አሷና ልጆቻችን አብረን ልንጓዝ ነው:: ከቀዶ ጥገናው በኋላ የምትሰጠኝ ተጨማሪ የጤና ምክር ይኖራል?
- ፈጽሞ የለም፤በጣም ጥሩ በሆነ የጤንነት ሁኔታ ላይ ነህ::

ከማምሸቱ ጥቂት ቀደም ብሎ አኣደም ደረሰ . . ጆርጅን በዙሪያው የሚሆን ነገር በማይሰማው ሁኔታ በተመስጦ ሲያነብ አገኘው:: ቀረብ ብሎ ሰላም አለው . .

- በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር እያነበብክ መሆን አለበት:: ሌላው ቀርቶ አጠገብህ ሰው መኖሩ እንኳን እየተሰማህ አይደለም !
- ኣደም! . . እንኳን ደህና መጣህ:: ምን ጊዜ ገባህ? ስለ ጥንታዊው የክርስትና ታሪክ ሳነብ ነበር::
- መልካም፣ምን አገኘህ::
- ስለ ጥንቱና አዲሱ የክርስትና ታሪክ ስታነብ በጣም አስገራሚ የሆነ

www.path-2-happiness.com

የመደናበር ሁኔታ ታስተውላለህ !

- ወደ ሮም እንኳ ከመጓዝህ በፊት ካቶሊካዊነትን ለመተቸት የተቻኮልክ አይመስልህም?
- እኔ ካቶሊካዊነትን አልተችም::
- ተረድቼ ካልሆነ ማለት የፈለከው ምንድነው?
- እኔ የምተቸው ካቶሊካዊነትን፣ፕሮቴስታንትነትንና ሁሉንም የክርስትና ሰክቶችንና ጎራዎችን ነው::
- ወደ ሮም መጓዝህ ነውና ከጉዞህ በኋላ ነገሮች የበለጠ ግልጽ ስለሚሆኑልህ አትቸኩል:: ማን ያውቃል ምናልባት አሁን አእምሮህ ውስጥ የሌለ አዲስ ነገር ሊታይህ ይችል ይሆናል::
- ላማክርህ የፈለኩትም ይህንኑ ነበር::
- አልገባኝም፣ልታማክረኝ የፈለከው ጉዳይ ምንድነው?
- በሰጠኸኝ ሀሳብ መሰረት ለቶም ደውየለት ነገ ለመገናኘት ቀጠሮ ወስጃለሁ፤ምን እንደሚለኝ ግን አውቃለሁ !
- በጣም ጥሩ፣ቀጥል ምን ሊል ይችላል?
- በሮም ጉብኝትህ ክርስትናን በደንብ አጥናው፣በቅርበት ለማወቅ ሞክር ይለኛል:: እኔ ግን ከንባቤም ሆነ ከኢየሩሳሌም ጉዞዬ ወይም ፕሮቴስታንት እንደ መሆኔ ከሕይወቴ በበቂ ሁኔታ አውቄዋለሁ የሚል ስሜት አለኝ:: ስለዚህም በጉዞዬ የምጨምረው አዲስ ነገር ይኖራል የሚል ግምት የለኝም::
- ጆርጅ ዕድሜህ ስንት ነው?
- ሰላሳ ሰባት ወይም ስምንት ነኝ፤ለምን ጠየከኝ?
- ሰላሳ ስምንት ዓመት ታግሰህ ኖረሃል፤ወደ ሮም ተጉዘህ በውሳኔህ እርግጠኛ ሆነህ እስክትመለስ መታገስ እንዴት ያቅተሃል? የተቻኮልክ አይመስልህም?
- ምናልባት ሊሆን ይችላል፤ግና ስለ ፕሮቴስታንት ቡድኖችና ጎራዎች ይበልጥ ባወቅሁ ቁጥር ይበልጥ እየተወኩትና እየጣልኩት ነው::
- እናም ምናልባት ወደ ካቶሊክ ወይም ወደ ኦርቶዶክስ ልትለወጥ ትችላለህ ማትለ ነው::
- አንተ ካቶሊክ ነህ ብየህ የለ? ግና እመነኝ ከጳጳሳዊው ካቶሊካዊነት ያለኝ ርቀት ከፕሮቴስታንታዊነት ካለኝ ርቀት የበለጠ ነው::
- ከጉዞው በኋላ ሀሳብህ ምናልባት ይለወጥ ይሆናል፤ለማንኛውም ከቅድመ

ውሳኔ ርቀን ሀሳቦችን በክፍትና ነጻ አእምሮ መመርመር አስፈላጊ ነው::

- ምንም ዓይነት ቅድመ ውሳኔ አልገደበኝም:: የካቶሊክና የፕሮቴስታንት መጽሐፎችና ሕትመቶቻቸውን፣ታሪካቸውንና ውጤታቸውን በጥልቀት አንብቤያለሁ፤ይሁን እንጂ ምንም አሳማኝ ነገር አላገኘሁም::
- መልካም፣ይበልጥ ነጻ ለመሆንና ይበልጥ አስተውለህ ለማስተንተን ሞክር እንጂ አትቸኩል:: ይህን ካደረክ ከጉዞህ በኋላ በምትወስደው ውሳኔህ የበለጠ እርግጠኝነትና የአእምሮ እርጋታ ይኖረሃል::
- ለመሆኑ ሃይማኖት ከአእምሮ ወይም ከሳይንስ ጋር ሊጋጭ ወይም ተጻራሪ ሊሆን ይችላል?
- በጭራሽ . . ሃይማኖቱ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ
- የተላለፈ ከሆነ ይህ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም::
- አንድ ሃይማኖት ከአእምሮ፣ከተጨባጭ እውነታ ወይም ከሳይንሳዊ ዕውቀት ጋር የሚጻረር መሆኑ እውነተኛ ሃይማኖት ላለመሆኑ ማስረጃ አይደለምን?
- ነው:: ይሁን እንጂ የሰው ልጅ አእምሮ ውስን በመሆኑ ያልደረሰክበት ነገር ሁሉ ከአእምሮ ወይም ከሳይንስ ጋር ይጻረራል ማለት አይደለም:: ይህ የሚያመለክተው የሰው ልጅ አእምሮ ውስን መሆኑን ነው::
- እንዴት ማለት? አብራራው::
- እግዚአብሔርን ፍጹማዊ የሆነ ዕውቀት አለማወቃችን እግዚአብሔር የለም ማለት አይደለም:: ይህ ማለት በተለመደው ሰብአዊ ድክመታችንና ውስንነታችን ምክንያት እውቀታችን ገደብ አለው ማለት ነው::
- ብዙ ብለፋና ብባዝንም አምላክ አንድም ሦስትም ነው የሚለውን የሥላሴ ጽንሰ ሀሳብ እስካሁን ድረስ መረዳት አልቻልኩም:: ቤተክርስቲያኗ ያለ ጥያቄና ያለ ክርክር እንዳምንበት የምትፈልገውና ከቤተክርስቲያን ምስጢሮች አንዱ የሆነ ካቶሊካዊ ምስጢር ይሆን?
- አንድን ነገር መገንዘብ ባለመቻልና ያ ነገር ከአእምሮ ጋር የሚጻረር በመሆን መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፤የትኛውን ማለትህ ነው?
- ሁለተኛውን ማለቴ ነው:: የሥላሴ ጽንሰ ሀሳብ ከአእምሮዬ ጋር ስለ ሚጻረር ልረዳውና ልተረጉመው አልቻልም::
- ቀጥተኛ፣ሚዘናዊና ትክክለኛ ከሆነ አእምሮ ጋር የሚጻረር ሃይማኖት ትክክለኛ ሃይማኖት ወይም እውነተኛው ሃይማኖት መሆን አይችልም::
- እናም በዚህ ኦርቶዶክስን፣ካቶሊክንና ፕሮቴስታንትን ውድቅ እናደርጋለን

www.path-2-happiness.com

ማለት ነው።

- ከሮም እስክትመለስ ድረስ ለምን አትታገስም?
- ይህንኑ ይገፎ የምመለስ ከሆነ ኤቲስት ወይም ሴኩላሪስት እሆናለሁ ማለት ነው።
- ኤቲዝምና ሴኩላሪዝም አንተ ዘንድ ከሰው አእምሮ ጋር አይጻረሩም ማለት ነው?
- ከአእምሮ ጋር በቀጥታ ይጻረራሉ፤ለዚህ ነው ትቼ ወደ ሃይማኖት የሸሸሁት። በመቀጠልም ከሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖት ወደ መለኮታዊ ሃይማኖት ሸሸሁ። ከዚያም አይሁዳዊነትን አሁን ባለበት ሁኔታው ጠላሁት። ክርስትናንም መጥላት ጀመርኩ፤የቀረኝ ቢኖር አሸባሪ ሙስሊም መሆን ብቻ ነው።
- ምናልባት ልትረዳና አሳማኝ ሆኖ ልታገኝ ስለምትችል ከሮም እስክትመለስ ውሳኔ ላይ አትድረስ።
- አሳማኝ ሆኖ ባላገኘውስ?
- ምናልባት የመታደል መንገድ እርሱ ሊሆን ስለሚችል እስላምን መርምር፣አጥናው !
- ታዲያ አንተ እስላምን አጥንተህ አሸባሪና ኋላ ቀር ሴት አሳዳጅ ለምን አልሆንክም ?
- አሁን የምንገኘው በክርስትና ጥናት እርከን ላይ ነው፤ከሮም ከተመለስክ በኋላ እንነግረሃለሁ።
- አንተና ካትሪና ሮም አእምሮዬን እንድጻረር የምታሳምነኝ፣ከሎጂክና ከሰብአዊ አእምሮ ጋር የሚጋጨውን እውነት ብዬ እንዳምን የምታደርገኝ ይመስል ለምን ሮም ሮም እንደምትሉ አላውቅም !
- እኔ አእምሮህን አውልቀህ አስቀምጥ፣ሎጂክን ተጻረር አላልኩህም። አትቸኩል፣አእምሮ አለህ ታስባለህና አሳማኝ ሆኖ ካላገኘህ የምትፈልገውን አድርግ ነው ያልኩህ። ደሞም እኔ የመጣሁት ባንተ ጥያቄ ነው፣ምንም ነገር አልጫንኩብህም፤እናም ይህ ውርጅብኝ በኔ ላይ ለምን ?
- ኣደም ይቅርታ፣እኔ በተፈጥሮዬ ችኩል ነኝ። እመነኝ ፍላጎቴ በተቻለ መጠን ቶሎ የመታደልን መንገድ ማግኘት ነው። ከቀዶ ጥገናው በፊት ይበልጥ ያስፈራኝ የነበረው ትልቁ ነገር የመታደልን መንገድ ሳላውቅ እንዳልሞት ነበር።
- በእግዚአብሔር ፈቃድ ትደርስበታለህ፣ታገኘዋለህ። አንተ ያልዘገየህ ብቻ

ሳትሆን በከፍተኛ ፍጥነት እየተጓዝክ ብትሆንም ጭራሽ ከማጣት ዘግይቶ ማግኘት የተሻለ ነው።

- ኣደም ደጋግሜ ይቅርታ እጠይቀሃለሁ። ምናልባት ችኩል ሆኜ ይሆናል፤ወይም ደግሞ በነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ተሰላችቼ ሊሆንም ይችላል።
- ቶሎ ለመድረስ በመጓጓት ተቻኩለህ ከሆነ አንድ ነገር ነው። መሰላቸት ግን ሳያጠናቅቁ መቆም ማለት በመሆኑ አደጋ ነው።
- አደጋ ! ትንሽ ያጋነንክ አይመስልህም ? !
- ጽናትና ቁርጠኝነት የሌለው ሰው የትም አይደርስም፣ምንም ነገር አያሳካም። መሰላቸት ማለት ደግሞ ቁርጠኛ አለመሆን ማለት ነው። የመጓጓትህ ውጤት የሆነው የችኩልነት ስነ ልቦና ከዚህ ጋር እንዳይጋጭብህ።
- እስማማለሁ፣ስሜትህ ግን ቶሎ ይገነፍላል፣ይህን አላስተዋልክም ?
- ሊሆን ይችላል፣ዓላማህ እኔን ለማስበርገግ መሆኑ ግን አልታየህም ?
- እህህ አልፎ አልፎ . . አንተ ቶሎ ቱግ ትላለህ።

በዚህ ወቅት . . ካትሪና ወደ አባታቸው አልጋ ከሚሮጡት ማይክልና ሳሊ ጋር ወደ ክፍሉ ገባች። በናፍቆት አቀፋቸው . . ለጥቂት ጊዜ ኣደምን ተወት አድርጎ ከነርሱ ጋር በማውራት ተጠመደ . . ኣደም ለደቂቃዎች ከጠበቀ በኋላ ለመሄድ ወሰነ . .

- አስተማማኝ ጤንነት ላይ መሆንህ አስደስቶኛል፣አሁን እንድሄድ ፍቀድልኝ።

ካትሪና ፈገግ ብላ ለኣደም ፦

- ይቅርታ ኣደም፣ማይክልና ሳሊ ከቀዶ ጥገናው በኋላ አባታቸውን አላዩም። ቀደም ሲልም ጉዞ ላይ ስለነበር ሳያገኙት ብዙ ጊዜ ሆኗቸዋል።
- ስለምን ይቅርታ ትጠይቂያለሽ?! ጭውውታችንን ጨርሰናል። ወዳጄ በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን አይቼ ተጽናንቻለሁ። እኔም ሥራ ስላለብኝ መሄድ እፈልጋለሁ።
- ኣደም ምስጋናዬ የላቀ ነው። ከመጓዜ በፊት አገኝሃለሁ?
- ካንተ ጋር መገናኘት ደስታዬ ነው፤ባንገናኝ እንኳ ቢያንስ እንደዋወላለን። ፍቀዱልኝ ልሂድ።

ኣደም ከወጣ በኋላ ካትሪና ሀሳብ ሰነዘረች ፦

- ይህን ወዳጅህን እዚህ ሆስፒታል እንጂ አላየሁትም፤ነገር ግን የላቀ ስነ ምግባር ያለው በጣም የተገራ ድንቅ ሰው ነው። ሲያዩት እኔ እንጃ በጣም ቀለል ያለና የሚመች ነው።

www.path-2-happiness.com

-ምናልባት እንዳንቺው ካቶሊክ ስለሆነ ሊሆን ይችላል !

-ሁሉም ካቶሊኮች የተገራ ጸባይ ያላቸው ድንቅ ሰዎች ናቸው፤ግና ቀደም ሲል ሃይማኖቱን እንደማታውቅ ነግረሽኝ ነበር::

-እስካሁንም ድረስ አላውቅም:: ይሁን እንጂ ወደ ሮም እንድሄድና ካቶሊካዊነትን በጥልቀት እንዳውቅ ያለው ጉጉት በአተያዩ መንገድ ሁሌ ካንቺ ጋር የሚስማማ መሆኑ ካቶሊክ መሆኑን ያረጋግጥልኛል:: ታውቂያለሽ ዛሬ ደግሞ ካቶሊካዊነትን ያለ ቅድመ ውሳኔ በነጻ አእምሮ እንዳጠናው ሊያሳምነኝ ይፈልጋል::

-እህህ፣መልካም ነው፣ምናልባት ስታጠናው ዝግ ሆነህ ይሆናል:: ምናልባት ደግሞ ከባለቤትህ ያላገኘሽውን መረጃ ከወዳጆችህ ታገኝ ይሆናል . . በነገራችን ላይ ወደ ሮም መጓዛችን መረጋገጡን ለልጆቹ አሳውቄአለሁ፤እነሆ ከፊትህ ናቸውና የሚፈልጉትን አዳምጣቸው::

-በሉ ጠይቁ . . ምንድነው የምትፈልጉት?

-ባባ ረሳህ እንዴ?

-ምንድነው የረሳሁት?

-የቅዱስ አንጅሎን አምባ ለማየት እንደምፈልግህ ነግረህ ነበር:: ሳሊ ደግሞ የትሬቪን ፏፏቴ ለማየት ነው የጠየቀችው::

-ይቅርታ፣እውነትም ረስቼ ነበር::

-ጉብኝቱ ሆቴል ቁጭ ብሎ ማንበብ፣ኮምፒውተር ላይ መስራትና ሙሉውን ጊዜ በመወያየት ማሳለፍ ብቻ እንዳይሆን ስጋት አለኝ::

-ለናንተ የተለየ ጊዜ እንደምሰጥ ቃል እገባላችኋለሁ::

-ባባ ቃል ነው?

-እናታችሁ ምስክር ነች፣ቃል ገብቻለሁ::

-እኤም ቃል እገባላችኋለሁ፣አባታችሁ ምስክሬ ነው::

ቤተሰባዊው ጭውውቱ ሞቅ ያለና አስደሳች ነበር:: የምሳ ሰዓት ሲደርስ ካትሪና ለልጆቹ እንዲህ አለች ፦

-አሁን ብንሄድና በጣሊያን ሬስቶራንት ምሳ ብጋብዛችሁ ምን ይመስላችኋል?

-ድንቅ ነው !

-በሉ እንሂድ::

ካትሪና ከልጆቹ ጋር ስትሄድ ጆርጅ ምሳውን በልቶ ወደ ንባቡ ተመለሰ . . ሆስፒታል ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በጥልቀት ሲያነበው የነበረውን ሲያስታውስ ሀሳብ ገባው . . ብዙ ባነበበ ቁጥር እርስበርስ የሚጋጩ ጉዳዮች እየበዙ

ይመጣሉ:: በተለይም እርሱ የክርስትና ጣያታዊነት፣ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱንና የሃይማኖት መሪዎችን አማልክት አድርጎ መያዝ ብሎ የሚጠራውን በተመለከተ ! ይህን ሁሉ ተቃርኖ በአንድ ጉዞ ማስወገድ ይቻላል . . ! ይህ እውን መሆን ከቻለ ምናልባት ጳጳሳዊው ሥርዓት ትክክለኛ ሊሆንና እሱም እንደ ካትሪና እና እንደ ኣደም ካቶሊካዊ ሊሆን ይችላል . . !

(3)

ጆርጅ ከእንቅልፉ አማልዶ ተነሳ:: ቁርሱን ከበላ በኋላ እንደ ልማዱ ወደ ንባብ ገባ:: ‹‹አይነኬ ትረካዎች በኦሪት›› የተሰኘና በጆናታን ክሪች የተደረሰ ሊነበብ የሚገባ አስፈላጊ መጽሐፍ ይዟል:: በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ ስለ መጽሐፉ የቀረበውን ሐተታ አነበበ ፦ ‹‹በዚህ አስገራሚ መጽሐፍ ውስጥ ደራሲው፣ብሉይ ኪዳን በምዕራቡ ዓለም ስነ ጽሑፍ ውስጥ አስደንጋጭ ትረካዎች በመሆናቸው በዘመን ርዝመት ምክንያት በተደበቁና ከሁሉም ይበልጥ አስበርጋጊና ግልጽ በሆኑ ትረካዎች የተሞላ መሆኑን ይነግረናል:: . . ›› ቀሳውስትና መነኮሳት ለሰው ልጅ ይበልጥ የሚበጀውንና የማይበጀውን ነገር ከእግዚአብሔር በላይ ያውቃሉ ተብሎ እንዴት ሊታሰብ ይችላል? በብሉይ ኪዳን ውስጥ የማያውቃቸው ታሪኮች የትኞቹ እንደሆኑ ራሱን ጠየቀ:: ትረካዎቹ ለምንና እንዴት ሊደበቁ ቻሉ? ቀደም ሲል ከሌቪ ጋር ከተነጋገሩባቸው ታሪኮች ይበልጥ በግድያና በአመጽ የተሞሉ ሊሆኑ ይችላሉ? ዛሬ ቀጠሮ ስላለው ቶም ከመምጣቱ በፊት ለማንበብ ወሰነ::

መጽሐፉ አንዳንድ ርእሰ ጉዳዮችን ለመደበቅ በትርጉም አማካይነት ማጭበርበር ብቻ ሳይሆን ከኦሪጂናሉ የዕብራይስጥ ቅጂ ለአንባቢ እንዲመች ተደርገው የቆርጦ መቀጠል ሥራዎች እንዴት እንደተከናወኑ በስፋት ያጋልጣል:: ይህን የሚያደርጉትም እነዚህን የወሲብ፣የእርቃነ ገላና የአመጽ ትረካዎች ሕጻናት እንዲያነቧቸው እንዴት እንተዋለን? በሚል ማመካኛ ነው:: ሌላ ጊዜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን አይልም፣ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው የሚለውን የሓኻሞች አባባል በምክንያትነት ያቀርባሉ:: ሁሉም ግን ታሪኮቹን ለመደበቅ ወይም ለማዛበትና ለማጭበርበር የሚደረግ ከንቱ ሙከራዎች ናቸው:: ታዲያ ይህን ሁሉ እነሱ ከፈጣሪ አምላክ ይበልጥ ያውቃሉ ማለት ነው? ወይስ መጽሐፉ ከእግዚአብሕር ዘንድ የተላለፈ አይደለም ማለት ነው? ወይ ደግሞ ያሁኑ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር የተላለፈው የጥንቱ ቅጂ የተበረዘ የተከለሰና የተምታታ አዲስ ቅጂ ወይም

www.path-2-happiness.com

ድርሰት ብቻ ነው?

ጆርጅ በከፍተኛ የመረበሽና የመደናገጥ ስሜት ውስጥ ሆኖ ንባቡን ቀጠለ። በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይ ኪዳን) ሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች (አይሁዳዊነት፣ክርስትና እና እስላም) ያምኑበታል። በመሆኑም መጽሐፉን መተቸት ሁሉንም መለከኮታዊ ሃይማኖቶች መተቸት ማለት ሊሆን ይችላል! በዚህ የጆናታን ክሪች መጽሐፍ ውስጥ ሰክሮ እርቃኑን ስለሆነው ኖሕ፣በሎጥና በሁለት ሴት ልጆቹ መካከል ስለ ተፈጸመውና እንዴት ተራ በተራ ከአባታቸው ጋር እንደተኙ ስለሚያወራው ወራዳ ወሳባዊ ትረካ፣በያዕቆብ ልጅ በሮቤል እና በአባቱ ቁባት መካከከል ስለ ተፈጸመው ወሲባዊ ቅሌት . . አነበበ። በሥጋ ዘመዳሞች መካከል እንኳ ሳይቀር የተፈጸሙ የወሲብ ቅሌቶችን የሚተርኩ ጥቅሶችን እያቅለሸለሸው አነበባቸው። ጤናማ ሰብአዊ አእምሮ የሚጠየፋቸው እነዚህ ወሲባዊ ቅሌቶች እንዴት ሆነው ስለ እግዚአብሔር ነብያትና መልእክተኞች የሚተርኩ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመጠየቅ ጆርጅ በእጅጉ ተገረመ። እነዚህን አጸያፊ ትረካዎች አንብቦ መጨረስ ፈተና ሆነበት . . እንደ ምንም ብሎ ፦ ‹‹ተለዋዋጭ ባሕርይ ያለው ባዙቃዊ አምላክ፣ሕይወት ሰጭ ከመሆን ይልቅ በአብዛኛው አውዳሚ የሆነ . . ›› በማለት የእግዚአብሔርን ባህርያት ወደሚገልጸው ክፍል ደረሰ። ተገቢ ያልሆኑ አስቸጋሪ ባሕርያት መሆናቸው ተሰምቶት እንዲህ ያለውን አምላክ ማምለክ ፈጽሞ አይቻልም ሲል ደመደመ ! እንዲህ ያለውን ድፍረት በፈጣሪ አምላክ ላይ መፈጸም እንዴት ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል?! መጽሐፍ ቅዱስ ፈጣሪ አምላክን ከሚያከብርና ከሚቀድሰው በበለጠ ላም የሚያመልኩ ወገኖች ላሚቱን አምላካቸውን ያከብራሉ፣ይቀድሳሉ።

ስለ ቅድስቷ ዝሙተኛ ስለ ታማራ ታሪክ እያነበበ ጆርጅ በጆርባው ተኝቶ ሳቁን ለቀቀው ! በቤተ መቅደስ ውስጥ እስከ ተፈጸመ ድረስ ዝሙት የተቀደሰ ተግባር መደረጉ አስገረመው። እንዳውም አንዳንዶች ቅድስት ዘማዊት መነኩሲት አልያም ይሁዳ ዝሙት የፈጸመባት የልጁ ሚስት ሳትሆን አትቀርም ይላሉ። ጆርጅ እያነበበ ያለው ነገር አቅለሸለሸው። እነዚህን የቅሌት ትረካዎች አንብቦ መጨረስ ተሳነው። በየጊዜው መገናኛ ብዙኃንን የሚያጣብቡና በካቶሊክ ካህናትና መነኩሴዎች የሚፈጸሙ የወሲብ ቅሌቶችን የሚመለከቱ ዜናዎች ትዝ አሉት።

መጽሐፉን ዘግቶ ኮምፒውተሩን ከፈተ። ወደ ዩትዩብ ድረገጽ ገባና ‹‹የቤተክርስቲያን ወሲባዊ ቅሌቶች›› ብሎ ጻፈ። በድምጽና በምስል ማስረጃዎች

ተደግፈው የመጡ የቤተክርስቲያን ወሲባዊ ቅሌቶች መረጃ ብዛትና ዓይነት አስበረገገው። ሁለቱ ካቶሊኮች ኣደምና ካትሪና እንደ መከሩኝ ወደ ሮም የማደርገውን ጉዞ ገፍቼበት የካቶሊክን ሕጸጾች መመርመሩን ልቀጥልበት? ወይስ ጉዞውን ለሽርሽር ብቻ አድርጌ የመታደልን መንገድ ልርሳ? ሲል ራሱን ጠየቀ። ይሁን እንጂ የመታደልን መንገድ ቢረሳ ወደ ነበረበት የእርግማንና የጥርጣሬ መንገድ እንደሚመለስ ወይም አእምሮንና እውቀትን በሚያወድም ኃይሉ የሰው ልጅ ሰብእና አውዳሚ ወደ ሆነው ኤቲዝም እንደሚያመራ ያውቃል። ሀሳቦች አእምሮው ውስጥ ሲፋጩ፣እያንዳንዱ ሀሳብ ሌላውን ሀሳብ አሸቀንጥሮ ከመጣሉ በፊት የገዛ ራሱን መንፈስና ልቦና አሸቀንጠሮ ሲጥልና ጥያቄዎቹን መልሶ ሲያመጣበት ተሰማው። ከሀሳቡ የባነነው በሐኪሙ ድምጽ ነበር ፦

- ጆርጅ . . ኧረ አንተ ጆርጅ ! አትሰማም እንዴ?
- ወይ . . አቤት፣ኖር ዶክተር።
- እኔ አናግረሃለሁ አንተ ሌላ ዓለም ውስጥ ነህ፤ስለ ምንድነው የምታስበው?
- የማልወደውንና የምጠላውን ርእሰ ጉዳይ እያሰብኩ ነበር።
- ምን ይሆን? !
- አርስበርስ የሚጋጩና ሎጂክና አእምሮን የሚጻረሩ ጉዳዮችን እጠላለሁ።
- እንዴት ማለት?
- ስለ ቀሳውስትና መነኩሳት ወሲባዊ ቅሌቶች ሰምተሃል? !
- ኦህ . . አዎ።
- ሕጻናት ላይ ወሲባዊ ጥቃት የሚፈጽሙና አስገድደው የሚደፍሩ ሰዎች ለእግዚአብሔር አምልኮና ለአገልግሎቱ ራሳቸውን በታማኝነት ማዋል ይችላሉ ተብሎ እንዴት ይታሰባል? !
- ጉዳትና አደጋውን እያወቀ አስካሪ መጠጥ ወይም አደንዛዥ እጽ እንደሚጠቀመው ሐኪም ማለት ነው !
- ሔሮዊን የሚጠቀም የጤና ባለሞያና ሐኪም እናንተ ዘንድ እንዴት ነው የሚታየው?
- በሥራው ስኬታማ ያልሆነ ሐኪም ነው። ከሞያውም ሊባረርና ሊጋለጥ ይገባል !
- ስለ ሐኪሞቹ ኃላፊነት ያለበት ክፍል ዕድገት የሚሰጣቸው፣የሚሸልማቸውና ጥፋታቸውን አይቶ እንዳላየ መሆን ብቻ ሳይሆን፣እነሱንና አደንዛዥ እጻቸውን የሚያስተዋውቅ፣ስልቱንም ጭምር የሚያስተምራቸው፣ሥርዓታቸውና

ሕጋቸው ይህንኑ የሚያበረታታ ከሆነሳ !

- ፈጽሞ ሊሆን አይችልም። ሆነ ብለን እንገምትና እንዲህ ያለው ተባባሪና እኩይ በመሆኑ ሰዎች ሐኪሞችን፣ሆስፒታሎችንና ሕክምናንም በጥቅሉ በጥርጣሬ ዓይን እንዲመለከቱ የሚያደርግ ነው። ምን ለማለት ፈለግህ?
- የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርቶች መነኩሳቱንም ጭምር ወሲብ፣ዝሙት፣ብልግና እና አስገድዶ መድፈርን አይደለም የሚያስተምሩት? መጽሐፍ ቅዱስ ነብያትንም ጭምር በሚያካትት መልኩ እንዲህ ባሉ ትረካዎች የተሞላ አይደለም ወይ?
- ምንም አልገባኝም፤ይበልጥ ትክክለኛ ልሁንና ካንተ ምንም ነገር እንዲገባኝ አልፈልግም። ታዲያ ኢአማኝ እንድንሆን ነው የምትፈልገው?! በሕክምናው ዓለም ብዙዎቹ ኤቲስት ሐኪሞች የላቀ ቦታ ያላቸውም ጭምር የስነ ልቦና ሕሙማን ወደመሆን የቀረቡ መሆናቸውን በሚገባ እናውቃለን፤ወይም ቢያንስ በሕይወታቸው ደስተኞች አይደሉም። የኔን ምክር የምትፈልግ ከሆንክ ከራስህ ሽሽ፣አሳማኝ ሆነው ብታገኘው እንኳ ከዚህ አመለካከት ራስህን አግልል። በሆነ መንገድ ሽሽ . . በጫወታ፣በመጠጥ፣በሴት፣በሥራ ወይም በሆነ ነገር፣ብቻ ሽሽ።
- ከራሳችን ሽሽተን ደስተኝነትን ማግኘት እንችላለን?!
- አዝናለሁ ያንን መታደል ፈጽሞ አይቻልም። ከኤቲዝምና ከእግዚአብሔር ከመራቅ መርገምት አንጻር ይሽኛው መርገምት ግን መታደል ተደርጎ ይወሰዳል . . አስደሳቹን ጭውውት በማቋረጤ አዝናለሁ። የመጣሁት ዛሬ ማምሻውን ስለምትወጣ ስለ ጤንነትህ ሁኔታ ብቻ ጥያቄዎች ካሉህ ለመመለስ ነው። በቀጣዮቹ ሁለት ቀናት የሰውነትህን የሙቀት መጠን እንድትከታተል እንመክረሃለን። ጥያቄ ይኖረሃል? ከሕክምና ጋር የተያያዘ ጥያቄ ብቻ ማለቴ ነው?!
- የለኝም አመሰግናለሁ . . ከሁለቱ ቀን በኋላስ የሙቀት መጠኑን መከታተል ያስፈልገኛል?
- አያስፈልግም . . ሁለቱ ቀናትም ለተጨማሪ ጥንቃቄ ብቻ ነው። የሙቀት መጠኑ ከተረጋጋ ጤንነትህ ሙሉ በሙሉ ተመልሷል ማለት ነው።

ቶም ገባ . . ለሐኪሙና ለጆርጅ ሰላምታ አቀረበ . . ሐኪሙ ወደ ሥራው ለመሄድ ለቆ ሲወጣ ሲል ጆርጅ ቀደመውና . .

- ከሕክምና ጋር ያልተያያዘ አንድ ጥያቄ እንዳቀርብ ትፈቅድልኛለህ?
- በፍጥነት መሆን አለበት፣ቀጥል።

- ሽሽት መታደልን የማያስገኝ መሆኑን የምታውቅ እስከሆንክ ድረስ ለምን ትሸሻለህ?
- ኤቲዝምን በመፍራት፤ቢያንስ በኔ አመለካከት ኢአማኝነት መርገምት ነው።
- ኤቲዝም ወይ ሽሽት?! ሌላ ሦስተኛ አማራጭ የለም?!
- እኔ አልደረስኩበትም እንጂ ሦስተኛ አማራጭ ምናልባት ሊኖር ይችላል። አንተ ከደረስክበት ንገረኝና ባለውለታዬ ትሆናለህ . . አሁን ልሂድ። ከመውጣትህ በፊት ጤና ነክ ጥያቄ ካለህ እንድትደውልልኝ ለነርሷ ንገራት፣ደህና ሁን።

ሐኪሙ ሲወጣ ቶም አይቶ ወደ ጆርጅ ፊቱን አዞረና . . .

- ጆርጅ በሁለታችሁ መካከል ሲካሄድ የነበረው ውይይት ምን እንደሆነ አላውቅም። የኤቲዝምን መርገምትነት፣የሚያስከትለውን ጭንቀትና ውጥረቱን ግን ከማንም በላይ አውቃለሁ።
- ኤቲዝም ለምን መርገምት ሆነ ትላላችሁ?
- የምትጠጋበትን፣ጉዳይህን ሰጥተኸው የምትመካበትንና የምትተማመንበትን አለማግኘት፣መንገድና አቅጣጫ እንዲያሳይህ የምትጠይቀውን አለኝታ ማጣት ከሁሉም በላይ አስቸጋሪ ነገር ነው።
- መንገዴን እንዴት ነው ከርሱ የማውቀው?
- ወደኛ በላካቸው ነብያት፣መልእክተኞችና መጽሐፎቹ አማካይነት ማወቅ ትችላለህ።
- ዝሙተኛ መነኩሲት ወይም አስገድዶ የሚደፍር ካህን ወይም መነኩሴ መንገዱን ይመሩኛል ብዬ እንዴት መጠበቅ እችላለሁ?
- አልገባኝም።
- ሰክሮ ዝሙት የሚፈጽም ነብይ ወይም በወሲባዊ ትረካ የታጨቀ ቅዱስ መጽሐፍ እንዴት መንገድ ይመራኛል?
- ጆርጅ ምን ነካህ? ዛሬ ለምንድነው እንዲህ የምትናገረው?
- ወዳጄ ቶም ታከተኝ፣ወደ ሮም ላለመጓዝ ከተጓዝኩም ለሽርሽር ብቻ እንዲሆን ከምር እያሰብኩበት ነው።
- ለምን . . ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ?
- አዲስ ነገር የለም፤በብሉይና አዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ወሲብና ስለ አመጽ ብዙ ብዙ ነገሮችን አነበብኩ፣አየሁ።
- ታዲያ ይኸ ካቶሊክን ብቻ የሚመለከት ነው?!

-ምን ማለትህ ነው?

-የፕሮቴስታንቶች የአመጽና የነውጥ ሥራ ተመሳሳይ እንዲያውም ከዚያ የከፋ አይደለም ወይ? በታሪክ ውስጥ ታይተው በማይታወቁ አስከፊ አረመኔያዊ ጭፍጨፋዎች የጀርመንና የሌሎች አገሮች ካቶሊክ ሕዝቦችን ማን እንደፈጀ ታውቃለህ?

-አዎ ፕሮቴስታንቶች ናቸው። ግና ታክቶኛል፣ምናልባት ፕሮቴስታንትነትም ጭምር ዋጋ ቢስ ነው።

-ጆርጅ እንዳስለመድከን ጠንካራ ሁን። ደካማ ተሸናፊ እንዳትሆን ተጠንቀቅ። ጽናትና ቁርጠኝነት ካለህ ወደ መታደል መንገድ ትደርሳለህ። ደካማ ተሸናፊ ከሆንክ ግን መድረሻህ ወደ ጭንቀትና ውጥረት እርግማን ይሆናል።

-ምን ላድርግ?

-እኔ እንጃ፣የማውቀው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ወደርሱ የሚያደርሰውን መንገድ የማይደብቅ መሆኑን ብቻ ነው።

-ይህ መንገድ የት ነው ያለው? ክርስቲያኖች ሙስሊሞችም በዚያ በወሲብና በአመጽ ትረካዎች በተሞላው መጽሐፍ በብሉይ ኪዳን ያምኑ የለም? ስለዚህ ጉዳይ ስትነግረኝ ሌቪን ማመን ቸግሮኝ ነበር። አሁን ግን በዓይኔ በብረቱ አይቼ የነገረችኝ ሁሉ እውነት መሆኑን አረጋግጫለሁ። ከብሉይ ኪዳን ማስረጃ እንድጠቅስልህ ትፈልጋለህ?!

-ፈጽሞ አያስፈልገኝም፤ይልቁንም ተጨማሪ ካስፈለገህ ከአዲስ ኪዳንም ጭምር ማስረጃ ልሰጥህ እችላለሁ።

-ታዲያ ሁለቱም በዚያው ተመሳሳይ መንገድ የሚሄዱ እስከሆኑ ድረስ ክርስትና እና እስላምን በመመርመር ለምን እንደክማለን?

-ከመጀመሪያው መንገዱን ፈልገን ለማወቅ ነው የተስማማነው። ወደ መንገዱ ለመድረስ መቃረባችን ለምን እንደሚሰማኝ አላውቅም። በእሽቅድምድሙ መጨረሻ ላይ እጅ አትስጥ . . ጆርጅ አንተ ለራስህ ብቻ አይደለም ፍለጋ የምታካሄደው። እኔም ንባቤና ምርምሬ ካንተ ጋር ሆኗል። እርግጠኛ ነኝ የመታደልን መንገድ እናገኘዋለን፣ግን እንዴት ብለህ አትጠይቀኝ።

-የኔም ስሜት ተመሳሳይ ነው፤ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ በራሴና በስሜቴ እየቀለድኩ ይሆን ብዬ እጠይቃለሁ። ሁሉም ማስረጃዎች መባዘንንና ከመንገድ መዛነፍን የሚያመለክቱ ቢሆንም በውስጤ ግን ከመንገዱ በቅርብ ርቀት ላይ መሆኔ ይሰማኛል።

-ወደ ሮም ተጓዝና ካቶሊካዊነትና ፕሮቴስታንታዊነትን በቅርበት መርምር። ያነበብካቸውን ጉዳዮች ተመልከት፤ተወይይባቸው። ሁሉንም መለኮታዊ ሃይማኖቶች በጥናት ከማዳረስህ በፊት የመጨረሻ ውሳኔ ላይ አትድረስ።

-እስላምንም እናጠናለን?!

-አዎ ያለ ምንም ጥርጥር። አንድን ነገር ማጥናትና መመርመር ማለት በዚያ ነገር ማመን ማለት አይደለም። ስለ ቡድሂዝም፣ህንዱይዝምና አይሁዳዊነት አንብበህ የለም? አጥንተህ የለም? ታዲያ ምኑ ነው አዲስ? ሁሉንም መለኮታዊ ሃይማኖቶች መርምረን ከማወቃችን በፊት ላለመወሰን ቀደም ብለን ተስማምተን የለም?!

-እቀጥልበታለሁ። የመታደልን መንገድ እንደማገኝ በውስጤ እርግጠኛ ብሆንም እስካሁን ባየኋቸው አመለካከቶችና ሃይማኖቶች ውስጥ ያጋጠሙኝ ተግዳሮቶች አፈተረት፣አመጽ፣ወሲብ፣መበረዝ፣መዛባትና እርስ በርስ መምታታት ናቸው።

-ወደ መታደል መንገድ ለመድረስ አሁንም አጥብቀህ አስብ። ፍለጋውና መድረሱ እንዲሁ ቀላል ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ጥረትና ድካም ባላስፈለገን ነበር!

-እደርስበታለሁ። ምናልባትም መፍትሔው ቀላልና ግልጽ ሆኖ ከአጠገቤ እያለ ለማየት ሳልችል በመቅረቴ እገረም ይሆናል።

-መንገዱ ምናልባት ካቶሊካዊነት ወይም ፕሮቴስታንታዊነት . . ወይም እስላም ሊሆን ይችላል።

-እነዚህ መንገዶች ሁሉ በአፈተረት፣በማጭበርበር፣ሃይማኖትን ለሥልጣን፣ለገንዘብና ለወሲብ በመገልገል የተሞሉ ናቸው የሚል እምነት ቢኖረኝም የፍለጋ ጉዞውን እንቀጥልበታለን። ለመሆኑ አንተ ምን ትመክረኛለህ?

-ብዙ አንብበሃል?

-አዎ ማንበቤ እንጂ ያታከተኝ ምን አለና! በነገራችን ላይ ካቶሊካዊነት ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ማብራሪያ ጋር ካልሆነ መጽሐፍ ቅዱስን እንኳ እንድናነብ አይፈልግም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ነገር መረዳት ያለብን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሱ በሚረዳበት መንገድ ብቻ ነው። አእምሯችንን አውልቀን እንድናስቀምጥ ይፈልጋሉ!!

-ልክ ነህ፤ፕሮቴስታንት ግን በሚፈልጉት መንገድ አዲስ ሃይማኖት ጠፍጥፈው መስራት ይፈልጋሉ። በሚፈልጉት መንገድም ይረዱታል።

www.path-2-happiness.com

በዚህ ምክንያት ነው ለዘመናት ብዙ ቦታ ሲከፋፈልና ሲሰነጣጠቅ የኖረው::

- ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በሚፈልገው መንገድም ሆነ እኛ በምንፈልገው መንገድ ብረዳው አዲስ ኪዳን በመሰረቱ ለመበረዝና ለመምታታት የተጋለጠና በስህተቶች የተሞላ በመሆኑ የተዛባ ነው:: እነዚህ ሃይማኖቶች አይረቡም፣አፈተረት ናቸው ብየህ አልነበረም?
- መልካም፣የበለጠ አንብብ፣የበለጠ እወቅ፣የበለጠ ተወያይ፣ ተከራከር፣የበለጠ ክፍትና ነጻ አእምሮ ይኑርህ:: ይህን ስታደርግ መንገዱ ይታየሃል::
- ካቶሊካዊነት ግን ለምን የሚል ጥያቄ በማይቀርብባቸውና ውይይት በማይካሄድባቸው ምስጢሮች ላይ የተመሰረተ ነው:: ከመነኮሳት ውጭ ማንም የማያውቃቸው ሰባቱ የቤተክርስቲያን ምስጢሮች!! አእምሮንና ሎጂክን የሚጻረሩ ከመሆናቸው ጋር እነዚህን መከራከር፣ማስተንተን ወይም መቃወም ከእምነቱ ጎራ የሚያስወጣ ክህደት ነው!!
- ፕሮቴስታንቶችም እንኳ ከሰባቱ ምስጢሮች በሁለቱ ያምናሉ::
- አንድ ነገር ባልኩህ ቁጥር ‹‹ፕሮቴስታንትም እንደዚ ነው›› ማለትህን አስተውልሃል? ከካትሪና ጋር ወደ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በመሄድህ ካቶሊካዊ ሆነሃል ልበል? የምትለውን ሁሉ በሚገባ አውቃለሁ፣የምናገረው ግን ስለ ካቶሊካዊነት ነው::
- ያለ ዕውቀትና ያለ ምክንያት በአንድ ሃይማኖት ላይ እንድትጫንና ወገንተኛ እንድትሆን አልፈልግም:: በዕውቀትና በምክንያት ላይ ተመስርተህ ከሆነ ግን ያለ አድልዖ በሚዛናዊነት የፈለከውን በል::
- የምናገረው በዕውቀትና በምክንያት ላይ ተመስርቼ ነው::
- እኔም እንደዚያው ነኝ፤የፈለኩት የበለጠ ሚዘናዊ እንድትሆን ብቻ ነው::
- ኦህ . . ልክ ነህ:: ስለነሱ የምናገራቸው አብዛኞቹ ጉዳዮች በአይሁዳዊነትና በፕሮቴስታንትም ውስጥ እያሉ ምናልባት በካቶሊካዊነት ላይ ይበልጥ ጠንከር ብዬ ይሆናል:: አስላም ውስጥም እንደዚሁ ወደፊት ያጋጥሙኛል ብዬ እጠብቃለሁ::
- ስለዚህም ነገሮች ግልጽ እስኪሆኑልን ድረስ የምርምርና የፍለጋ ጉዞአችንን እንደ ጀመርነው በተረጋጋ መንፈስ እናጠናቅቅ . . አንተ አይደለህም እንዴ ‹‹ሳይወሳሰብ ቀለል ባለ ሁኔታ›› የምትለኝ?
- አዎ፣ይህች የታወቀች የኣደም አባባል ናት::
- እናም የሰው ልጅ የተረጋጋ ሲሆን የበለጠ ሚዘናዊና የበለጠ ምክንያታዊ ይሆናል:: ከመጀመሪያው እንደ ነገርኩህ ነገሮች ግልጽ ሆነውልህ

እስከታውቃቸው ድረስ ወሳኔ ላይ እንዳትደርስ እጠይቀሃለሁ:: ምናልባት ውሳኔህ ለምሳሌ ያህል አይሁዳዊነት ሊሆን ይችላልና ለምን ትቸኩላለህ?

- በቀላሉ ልንገርህና በምንም ዓይነት ውሳኔዬ አይሁዳዊነት ሊሆን ይችላል የሚል እምነት የለኝም:: እኔ አመጽን እጠላለሁ፤ብሉይ ኪዳን ደግሞ በአመጻ ታሪኮች የተሞላ ነው:: ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሰፈሩትን እነዚህን ጥቅሶች እስኪ አስተውላቸው ፦ ‹‹ . . ሰይፉንም ከደም የሚከለክል ርጉም ይሁን::››፣‹‹እርሱም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦ የእናንተ ሰው ሁሉ ሰይፉን በወገቡ ላይ ይታጠቅ፣በሰፈሩም ውስጥ በዚህና በዚያ ከበር እስከ በር ተመላለሱ፣የእናንተም ሰው ሁሉ ወንድሙን ወዳጁንም ጎረቤቱንም ይግደል አላቸው::›› እስኪ ከዚህ የከፋ ምን ዓይነት ሽብርተኝነት ይኖራል?!
- ክርስቲያኖችና ሙስሊሞችም በብሉይ ኪዳን ያምኑ የለም?! እናም የበለጠ ተለሳለስና ነገሮች ሙሉ በሙሉ ፍንትው ብለው እስኪገለጹልህ ድረስ ውሳኔ አታስተላልፍ:: ወደ የመታደል መንገድ እንደምትደርስ እኔ እርግጠኛ ነኝ::
- በኔ ግምት ይህ ትልቁ ችግር ነው:: ክርስቲያኖች አዲስ ኪዳንን የብሉይ ኪዳን ማሟያ አድርገው ይወስዱታል:: ገና ባላጠናውም ሙስሊሞችም እንደዚያው ይመስሉኛል:: ስለዚህም ሁሉም የአመጽና የሽብር ሃይማኖቶች ናቸው::
- እዚህ ላይ ሁለት ነጥቦች አሉ ፦ አንደኛ በነዚህ ጉዳዮች ውስጥ የይሆናል ግምት ቦታ የለውም:: ሀሳብህ መመስረት ያለበት በዕውቀትና በማስረጃ ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል:: ሁለተኛ ይበልጥ እርግጠኛ እንድትሆን እፈልጋለሁ:: አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ማሟያ ነው ማለት ምን ማለት ነው? ያምኑበታል ማለት ነው ወይስ አይደለም?
- ባልከው ነገር እስማማለሁ:: ‹‹ይመስለኛል›› ግምት እንጂ ዕውቀት አይደለም:: የበለጠ ማንጓለልና ማንጠርም ከዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ነው:: አሳዛኙ ነገር ክርስቲያኖች ‹‹ማሟያ›› የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በሚገባና ግልጽ በሆነ ሁኔታ አላነጠሩትም፤ያላነጠርኩት እኔ አይደለሁም:: ለምሳሌ ያህል ካቶሊኮች ተከታዮቻቸው አዲስ ኪዳንን በቀጥታ አንብበው እንዳይረዱ ይከለክላሉ:: ለራሳቸው ተረድተው እንደ እኔና እንደ አንተ ላለው ተራ ሰው ማስረዳት የሚገባቸው መነኮሳት ብቻ ናቸው ብለው ያምናሉ:: ያለዚያማ የሚከተሉትን የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ማንም በቀጥታና በግልጽ ይረዳል

www.path-2-happiness.com

፦ ‹‹በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም፡፡›› የሚለውን ወይም ‹‹ነገር ግን እነዚያን በላያቸው ልነግስ ያልወደዱትን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡአቸው በፊቴም እረዱአቸው፡፡›› የሚሉ ጥቅሶቹ ግን ማንም ሊረዳው በሚችል ግልጽና ቀላል ቋንቋ የተጻፉ ናቸው፡፡

- ክርስቲያኖች ለነዚህ ጥቅሶች ቀጥተኛ ያልሆኑ ንጽጽራዊ ትርጉሞች እንዳላቸው መቼም ታውቃለህ፡፡
- ልክ ነህ ቀጥተኛ ያልሆኑ ንጽጽራዊ ትርጉሞች አሉን፡፡ ለነዚህ ጥቅሶች ተቃራኒ የሆኑና ለርህራሄና ለፍቅር ጥሪ የሚያደርጉ ጥቅሶችም አሉን፡፡ ቀጥተኛ ያልሆነ ንጽጽራዊ ትርጉም ሎጂካዊ ባይሆንም ከንጽጽራዊነት የሚያልፍ አይደለም፡፡ ተምሳሌታዊ ንጽጽራዊ ትርጉሞቹ በዚህ በተሞላው ብሉይ ኪዳን ካለን እምነታችን ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም፡፡ በሚያሳዝን መልኩ ከሌሎች ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በራሳችን መካከልም ተግባራችን ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለ አረመኔያዊ የጭካኔ ተግባሮቻችን ምሳሌዎችን እንድጠቅስልህ ትፈልጋለህ?
- ለአሁኑ ይህ ርእሳችን አይደለም፡፡ ነገሮችን በቦታቸው እናስቀምጥና ጠቅለል ባለ መልኩ እንመልከታቸው፡፡ ማንኛውንም ሃይማኖት ለማጥናት በአምላኩ፣በነብዩ፣በመጽሐፉ፣በእምነቶቹ፣በሕግጋቱ፣በታሪኩ እና በገሃዳዊ ሁኔታው ላይ ማተኮር ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ ጥናት ተመራጭ የሚሆነው በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ሳይሆን በአጠቃላይ መርሃዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ነው፡፡
- መልካም፣እንዴት ማለት ነው?
- በብሉይ ወይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአንድ የተወሰነ ጥቅስና በተምሳሌታዊ ትርጉሞቹ ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ከተአማኒነቱና በትክክል ከመተላለፉ አንጻር፣ከጸሐፊዎቹ እና ከትምህርቶቹ አንጻር፣እግዚአብሔርንና ነብያቱን አስመልክቶ ከሚያራምዳቸው እምነቶቹ አንጻር መጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ በሆነ እይታ እንመልከት፡፡ የተቀሩት ዝርዝር ጉዳዮች መሰረታዊውን ጉዳይ ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ምስክሮች እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም፡፡
- በጣም ጥሩ፤በዚህ ላይ ብዙ ያነበብኩ ቢሆንም የበለጠ እስካነብና የበለጠ እስክወያይባቸው ድረስ ማቆየት እችላለሁ፡፡
- የበለጠ ለማብራራት እንዳልከው የአይሁዳዊነት ጥናትህን ከብሉይ ኪዳን ጨርሰሃል እንበልና ትምህርቶቹ ምንድናቸው? ስለ እግዚአብሔር ነብያት ያለው አመለካከትስ ምንድነው?
- ከእግዚአብሔር የተላለፈ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡
- እግዚአብሔር ነው የጻፈው? ሙሴ ነው የጻፈው? አሮን ነው የጻፈው? ጸሐፊው ማን እንደሆነ ታውቃለህ?
- አዲስ ኪዳንን በተመለከተም ይህንኑ የምትጠይቅ ይመስለኛል?
- ያለ ጥርጥር፡፡ ባላደርግማ ሚዘናዊ አልሆንኩም ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የእሳቤ ስልት ወደ የመታደል መንገድ ሊያደርሰን የሚችልና ሰጥቶ መቀበልን በሚያስተናግዱ ዝርዝር ጉዳዮች እንዳንጠመድ የሚያደርገን ስልት ነው፡፡
- ግሩም ሀሳብ ነው፣እስማማበታለሁ፡፡
- ከሮም ከተመለስክ በኋላ ሁለት ዋና ዋና መለኮታዊ ሃይማኖቶችን ገምግመን ለመጨረስ እንችላለን፤የሚቀረን አንዱ ብቻ ይሆናል፡፡ እናም አጠቃላዩ ሥዕል ግልጽ ስለሚሆንልን የመታደል መንገድ ፍለጋ ጉዞአችንም ይጠናቀቃል ማለት ነው፡፡
- ሁሉም የማይረቡ መሆናቸው ግልጽ ቢሆንልንስ?!
- ቀደም ሲል በነበርኩበት ሁኔታ ላይ ብሆን ኖሮ ወደ ኤቲዝም እንመለሳለን እልህ ነበር፡፡ ይህን የፍለጋ መንገድ እንድትከተል የፈለኩት ዞረህ ወደ ኤቲዝም እንድትመለስ ነበር፡፡ አሁን ግን ሁሉም ሃይማኖቶች የማይረቡ ሆነው ቢገኙ እንኳ እንደገና ወደ ኋላ ተመልስን ሥራችንን ሙሉ በሙሉ እንገመግማለን፡፡ ሃይማኖት አስፈላጊ ነው? ከሆነ ሃይማኖትን የምንመርጠው እንዴት ነው? ብለን በመነሳት እንደ አዲስ እንጀምርና አሁን እስካለንበት ድረስ እንቀጥላለን፡፡ ይህን ስናደርግ ነገሮች የበለጠ ግልጽ ይሆኑልናል፡፡
- በጣም ረዥምም መንገድ ነው!
- እንደገና ወደ ኋላ አንመለስም ብዬ አስባለሁ፤ምኞቴም ነው፡፡ ጉዳዩ ከዕውቀት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ማለትም ዕውቀት በጨመርን ቁጥር አርቆ ማሰብና ግንዛቤያችን ይጨምራል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ብዥታዎች በጨመሩ ቁጥር አለማወቃችን ጨምሮ ከጥያቄዎቻችን ምላሽ የሚኖረን ርቀትም ይጨምርና ከመታደል መንገድም እንርቃለን፡፡ እንደምትደርስ እኔ እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ፤ግና ትንሽ ታገስ፡፡
- ያለ ምንም ጥርጥር እደርሳለሁ፡፡ (ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ ከሁሉም በላይ የሚያንገላታኝ ወደ መንገዱ የሚወስደውን መንገድ አለማየቴ ነው፡፡

www.path-2-happiness.com

- ወደ መንገዱ የሚያደርሰው መንገድ ግልጽ ነው፤ገና ያላየሽው ግን መንገዱን ራሱን ነው። ሰዎች ብዙ ጊዜ ወደ መንገድ የሚወስደውን መንገድ፣የሚፈልጉትና ያላዩት መንገድ አንዱ አካል አድርገው ያስባሉ።
- ጥሩ ፍልስፍና ነው። ወደ መንገድ የሚወስደው መንገድ እንዴት ግልጽ እንደሆነ ግን አብራራልኝ።
- ከመጀመሪያው አንስቶ የኤቲዝምንና የሴኩላሪዝምን መንገድ ውድቅ ማድረግህን ታውቅ የለም? ከዚያም የሰው ሰራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶችን መንገድ ውድቅ አድርገሃል። በመቀጠልም ከመለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥ አንዱን ለመምረጥ ማነጻጸርና ማመዛዘን ጀምረሃል። ልክ ነኝ?
- ሙሉ በሙሉ ልክ ነህ ። ለኔ ግልጽ ያልሆነልኝ ግን እንዴት ወደዚያ መድረስ እንደምንችል ነው።
- ያልኩህም ይህንኑ ነው። ያልተገለጠልህ ራሱ መንገዱ ነው እንጂ ወደ መንገዱ የሚያደርሰው መንገድ አይደለም።
- እህህ፣ደግ ነው፤ለማንኛውም ይህን እንለፈውና ለሮም ጉዞዬ ምን ትመክረኛለህ?
- በመጀመሪያ የምመክርህ በጉዞው ተደሳች እንድትሆንና ልጆቹንም በሽርሽር እንድታዝናናቸው ነው። አእምሮህን አሳርፈህ በንባብና በውይይት ያከማቸኸውን ግዙፍ መረጃህን ማቀናጀትና ማቀናበር ያስፈልገሃል። ሁለተኛ ንባብና ውይይትህን በነጻ አእምሮ ቀጥልበት። ትኩረትህን በቅርጻዊ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አድርግ። ሦስተኛ መረጃዎችህን ለማቀናጀትና ለመተንተን የሚያግዝህን የማስተዋል ስልት አብዝተህ ከተጠቀምክ በመሰረታዊ ጉዳች ላይ ብቻ ለማነጣጠር ይረዳሃል።
- መልካም፣በጣም ጠቃሚ ምክር ነው፤እጠቀምበታለሁ።ለጥያቄዎቼ መልስ ፍለጋ በመነሳቴ ብቻ እፎይታ ባገኝም በሂደቱ ውስጥ የበለጠ ስሜታዊ ሆኜ ነው ራሴን ያገኘሁት።
- የስሜታዊነትህ መንስኤ በአእምሮህ ላይ ያለው ተከታታይ ጫና ነው፤የመረጃዎችና በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ጫና ነው። ለዚህ ነው ጭንትህ የገዘፈው። እናም በነገርኩህ ራስህን የማዝናናት ምክሮች ጭነትህን አቃልል።
- እሽ አደርጋለሁ፤ለልጆቼም በዚህ ቃል ገብቻለሁ።
- መልካም ጉዞ እንዲሆንልህ ምኞቴ ነው። ከጉዞህ መልስ ጭነትህ ተቃሎ፣መረጃዎችህ ደርጅተውና ተቀነባብረው አእምሮህም የበለጠ ነጻ

ሆኖ እንገናኝ።
- ቶም፣የበራድ ነገርስ እንዴት ሆነ?
- ጉዳዩ መባባስ የጀመረ ይመስላል። እርሱ ዘንድ ባሉት ፎቶግራፎችና የቀረጻ ቅጂዎች በግልጽ እኔን ማስፈራራት ጀምሯል።
- አንተን ማስፈራራት!
- አዎ፣ኢሞራላዊ የሆኑ የኔና ያንዳንድ ታካሚ ሴት ደንበኞቼ የቆዩ ፎቶግራፎች በእጁ ይገኛሉ። ካንዳንድ ታካሚዎች ጋር ያደረኳቸው የሕክምና ምክክር ቅጂዎችንም ይዟል። በነዚህ በኔ ላይ ጫና መፍጠር ጀምሯል። ካልተደራደርኩ ለሕክምና ኮሚቴዎች ምክር ቤትና ለሕክምና ባለሞያዎች ማህበር አሳልፎ ለመስጠት እያስፈራራኝ ነው።
- ለሕክምና ማህበራቱ አሳልፎ ቢሰጥ ምን ጉዳት ያስከትልብሃል?
- ስሜ በአደባባይ ከመጉደፉም በላይ የሞያ ብቃት ምስክር ወረቀቴን እነጠቃለሁ።
- በምን ላይ ነው እንደራደር የሚልህ?
- ከርሱ ጋር እንድሰራ ለማድረግ።
- ከርሱ ጋር ምን መስራት?
- እህህ፣አደንዛዥ እጽ በመሸጥና ከኔ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ መፈጸም።
- የአደንዛዥ እጽ አሻሻጭ ከምትሆን ለሙያ ማህበራቱ ቢናገር ይሻላል።
- ልክ ነህ . . ግና ከሙያዬ መባረርም ከባድ አደጋ ነው።
- ታዲያ ምን ታደርጋለህ?
- አላወኩም፣ገና አስብበታለሁ። በል ደህና ሁን።

ጆርጅ ከቶም ጋር በነበረው ቆይታ ተዳሳች ሆኖ ወደ ንባቡ ተመለሰ . . ከርሱ ጋር ከተገናኘ በኋላ የመረጋጋትና የእፎይታ ስሜት ተሰምቶታል። በአነጋገሩም ተደስቷል። በተቻለው መጠን ምክሩን ተግባራዊ ለማድረግም ወስኗል። ይሁን እንጂ ከበራድ ጋር ባለው ችግር ቶምን እንዴት መርዳት እንደሚቻል በማሰብ አእምሮው ተጠምዷል . . በቶም መለወጥ እርግጠኛ ከሆነ በኋላ ችግር ሲገጥመው ብቻውን መተው አልፈለገም። ዳሩ ምን ማድረግ ይቻለዋል?

የቶምን ችግር በማሰላሰል ላይ እያለ . . ኢሜይሉን ከፈተና ከሐቢብና ከሌቪ ጤንነቱን ለመጠየቅ የተላኩ ሁለት መልእክቶችን አገኘ። ቀጣዩን መልስ ጻፈላቸው . .

‹‹ውድ ሐቢብ

www.path-2-happiness.com

የተሳካ ቀዶ ጥገና ተደርጎልኛል:: በመልካም ጤንነት ላይ መሆኔን አበስረሃለሁ:: ከሁለት ቀናት በኋላ ወደ ሮም እሳፈራለሁ:: እዚያ በሆንክና በዕውቀትህና በክፍት አእምሮህ ካቶሊካዊነትን አስመልክቶ የሚያጋጥሙኝን አንዳንድ ችግሮች ብታብራራልኝ እንዴት በወደድኩ::

ወዳጅህ ጆርጅ››

‹‹ወዳጄ ሌቪ

የተሳካ ቀዶ ጥገና ተደርጎልኛል:: በመልካም ጤንነት ላይ መሆኔን አበስርሻለሁ:: ከሁለት ቀናት በኋላ ወደ ሮም እሳፈራለሁ:: እዚያ በሆንሽና በዕውቀትሽና በክፍት አእምሮሽ ኦሪትንና አይሁዳዊነትን አስመልክቶ የሚያጋጥሙኝን አንዳንድ ችግሮች ብታብራሪልኝ እንዴት በወደድኩ::

ወዳጅሽ ጆርጅ››

የኢሜይል መልእክቶቹን በማገባደድ ላይ እያለ ካትሪና መጣች . .

- የመውጫ ሂደቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይጀመራል::
- ቤት፣ሰዎችና መኪኖችም ጭምር በጣም ናፍቀውኛል::
- ከኛ ተለይተህ ያሳለፍከው ቆይታ ለኔና ለልጆቼ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነበር . . አንተ እንኳ በንባብህና በውይይቶችህ ተጠምደህ ነበር:: ቶም ዛሬ መጥቶ ነበር እንዴ?
- አዎ፣ከርሱ ጋር ድንቅ ቆይታ ነበረን::
- አላልኩህም ነበር?
- ምክሮችሽ ሁሌም የሚመቹ ናቸው:: ዋናው ነገር መቼ ነው የምንወጣው?
- ከአፍታ በኋላ:: አንዳንድ ወረቀቶችን መጨረስ ብቻ ነው የቀረኝ:: አሁን እሄድና አጠናቅቄ እመለሳለሁ:: ዛሬ ባንተና በቶም መካከል የሆነውን መንገድ ላይ ታወጋኛለህ::

(4)

ቤተሰቡ ከበረራው ሁለት ሰዓት አስቀድሞ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ አመራ . . በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ ወደ ታሪካዊቱ ሮም ጉዞ ተጀመረ . . ለዚህ ጉዞ በጥንቃቄ ያቀደችው ካትሪና ከፒያሳ ናቮና አደባባይ ብዙ የማይርቀውን ራፋይል ሆቴል ነበር የያዘችው:: ሆቴሉ የሮምን ከተማ ገጽታ፣ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያንን እና የፓንቲኦን ቤተ መቅደስ ቁልቁል የሚያሳይ ነው:: ራፋይል ሆቴል ከአውቶቡስ መስመሮች ጋር በሚገባ የተሳሰረ ከመሆኑም ባሻገር አብዛኞቹ የሮም ከተማ ታሪካዊ የቱሪስት መስህብ ቦታዎችም በእግር

ጉዞ ከሆቴሉ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛሉ . .

- ካትሪና ምርጫሽ በጣም ድንቅ ነው::
- ማሚ አመሰግናለሁ፤ማየት ከምፈልገው አምባ የቀረበ ሆቴል ነው የያዝሽልን::
- ሳሊ ማየት ከምትፈልገው ፏፏቴም ብዙ አይርቅም::
- አሁን ከምሽቱ አንድ ሰዓት ነው:: ሆቴሉ ውስጥ ብንዝና እና እራታችን በልተን ብናርፍ ጧት የጉብኝት ፕሮግራማችንን በንቃት ለመጀመር ይረዳናል:: አይመስላችሁም?
- ባባ በጣም ጥሩ ነው . .

ቤተሰቡ በማለዳ ተነሳ . . ቁርሳቸውን በሆቴሉ ሬስቶራንት በሉ:: ከአስጎብኚ ጋር በታሪካዊ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ወደ ተሞላውና በአቅራቢው ወደሚገኘው አደባባይ አመሩ:: የሮምን ጥንታዊ ሕንጻዎችን፣ድንቅ ሐውልቶቿን፣የኪነ ሕንጻ ጥበብን፣ጥልቅ ታሪካዊነትና ግርማ ሞገስ የሚንጸባረቅባቸው የተዋቡ አብያተ ክርስቲያናትን . . ሲመለከቱ ወደር የሌለው ደስታና እርካታ አገኙ::

የምሳ ሰዓት ሲደርስ በጥንት ሮማውያን ሞዴል ወደ ተዘጋጀው የኢጣሊያ ሬስቶራንት ሄዱ . .

- ባባ የሮማውያን ሥልጣኔ ይህን ያህል ጥልቀትና ውበት አለው ብዬ አላሰብኩም ነበር !
- ማይክል፣የሮማውያን ሥልጣኔ ድንቅ የሆነ ጥንታዊ ሥልጣኔ ነው:: ከግሪክ ሥልጣኔ ቀጥሎ ታላቁ የአውሮፓ ሥልጣኔ ነው:: ከልደት በፊት በ275 መላውን የኢጣሊያ ባህረ ገብ ምድር የተቆጣጠረ ሥልጣኔ ነበር:: በቀጣዮቹ ሁለት ተከታታይ ምእተ ዓመታት ሮማውያን መላውን አውሮፓና ሰሜን አፍሪካን ያጠቃለለ፣የግሪክ ሥልጣኔ የሰረጸበትን ኢምፓይር መገንባት ችለዋል::
- ሮምን ልዩ የሚያደርጋት ውጭ ያሉት ሐውልቶችና ቅርጻቅርጾች ብቻ ሳይሆኑ ይህ ፒሳም ጭምር ነው::
- ማይክል በሐውልቶቹ ተደንቀሃል?
- አሰራራቸው ያምራል::

ከትሪና ፈገግ ብላ ፦

- የኢየሱስና የድንግሏ ሐውልቶች ምንኛ ያምራሉ !
- እነዚህ ሐውልቶችና የኢየሱስ ሐውልቶችም ጭምር በሕንድ ያየኋቸውን

www.path-2-happiness.com

የቡድሃና የሌሎች አማልክት ቅርጾችን እንዳስታውስ ለምን እንደሚያደርጉኝ አላውቅም:: ለኔ ሁሉም ተመሳሳይ ነገሮች ሆነው ይታዩኛል::

- አሁን ይህን ተወንና ምሳችንን ከበላን በኋላ ወደ ሌላኛው የአደባባዩ ክፍል እናመራለን::

ካትሪና በዚህ ጉዳይ ላይ ልጆቹ ፊት መከራከር እንደማትፈልግ የተረዳው ጆርጅ ሀሳቧን አክብሮ ተቀበለ:: ይሁን እንጂ አእምሮው የኢየሱስን ሐውልቶች ከቡድሃ ሐውልቶች ጋር ማስተሳሰር ብቻ ሳይሆን የጣዖት አምላኪዎችን እምነት ከካቶሊኮች እምነት ጋር አይይዞ መመልከቱን አላቆመም::

ቤተሰቡ የዕለቱን የጉብኝት መርሐ ግብር አጠናቆ ጸሐይ ከጠለቀች ከአጭር ጊዜ በኋላ ወደ ሆቴላቸው ተመለሱ:: እራታቸውን በሆቴሉ ሬስቶራንት አንድ ላይ በሉና ወደ መኝታ ክፍሎቻቸው አመሩ . . ጆርጅ ኢሜይሉን ከፈተና ከሐቢብ የተላከለትን መልእክት አገኘ ፦

‹‹ጆርጅ

ይህን መልእክት የምጽፍልህ ከሌቪ ጋር አብረን በመሆን ነው:: መልእክተህን አንብበን ቀዶ ጥገናው ስኬታማ በመሆኑ በእጅጉ ተደስተናል:: ቀዶ ጥገናው የተሳካልህ መሆኑን ምክንያት በማድረግም ከአፍታ በኋላ ከሌቪ ጋር የደስ ደስ ዝግጅት ይኖረናል:: ካቶሊካዊነትን ወይም አይሁዳዊነትን በተመለከተ ግልጽ ያልሆነልህን ነገር ካንተ ጋር ለመወያየት ደስተኞች ነን:: በፕሮቴስታንት እና በእስላምም ጭምር ለመወያየት ደስተኞች ነን:: በነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ካንተ ጋር ውይይት ለማድረግ ተዘጋጅተን እንጠብቃለን::

ሐቢብና ሌቪ››

ማሳሰቢያ ከሐቢብ ብቻ ፦ በቅዳሜ ዕለቱ ቅዳሴ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን መጎብኘት እንዳትረሳ::

መልስ ጻፈላቸው ፦

‹‹ሐቢብና ሌቪ ሠላም ለናንተ ይሁን

አሁን ያለሁት በካቶሊኮች አገር በሮም ነው:: ከካቶሊካዊት ቫቲካንም በቅርብ ርቀት ላይ እገኛለሁ:: ስለኔ በመደሰታችሁ ተደስቻለሁ:: ግልጽ ያልሆኑልኝን ነገሮች በሚመለከት አንዱን ጥቅስ ብቻ አስተላልፍላችሁና በጣም አጠር ያለ አስተያየት እንድትሰጡበት እጠብቃለሁ . . ‹‹አይነኬ ትረካዎች በኦሪት›› የተሰኘውና በጆናታን ክሪች ከተጻፈው መጽሐፍ አንዱን አንቀጽ እጠቅስላችኋለሁ:: አንቀጹ ስለ ኦሪት ወይም ብሉይ ኪዳን ሲናገር እንዲህ ይላል፦

ሚሽል ቪንቶራ እንዳስቀመጠው - ብሉይ ኪዳን ውስጥ በተመለከተው ነገር ስሜቱ ክፉኛ የተጎዳ ጋዜጠኛ ነው - ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስለ አፍራሽ አረመኔያዊ የጭካኔ አድራጎት የሚተርክ መጽሐፍ ነው:: ‹‹ዘንዶ የሚያገቡ ሴቶች፣እርስ በርሳቸው የሚገዳደሉ ወንድማማቾች፣ሙሉ በሙሉ የሚታረድና የሚፈጅ ሕዝብ፣በረሃ ውስጥ የሚንከራተቱ ነገዶች፣የሚጋዙ አራስ ሕጻናት፣ወንጀልን የሚያካትት ነብይነት፣ነብይነትን የሚያካትት ወንጀል፣የነብያት አንገት ተቆርጦ እንዲመጣላቸው የሚጠይቁ ሴት ዘፋኞች›› ቫንቱራ ሲያጠቃልል ኦሪትን ወደ ቅዱስ መጽሐፍነት ደረጃ ከፍ የሚያደርግ ማንኛውም ሕብረተሰብ ለእብደት የተጋለጠ ነው ይልና ‹‹ይህን በመሰለ መጽሐፍ ላይ የሚመረኮዝ ሥልጣኔ ሕብረተሰቡ አረመኔያዊ ጭካኔ የሌለውና አውዳሚ ያልሆነ ሕብረተሰብ ይሆናል ብሎ መጠበቅ›› አስቂኝ ነው በማለት ያክላል:: እናም ከቬንቱራ ጋር ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? ሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑ መሆናቸውን ግንዛቤ ውስጥ ከማስገባት ጋር አስተያየት ስጡበት::

ከአክብሮት ሠላምታና ከናፍቆቴ ጋር

ጆርጅ››

ጽሑፉን በአንድ መልእክት ለኣደምና ለቶምም ለመላክ ወሰነ . . ከዚያ ቁጭ ብሎ ማሰላሰል ያዘ . . እርሱ ራሱ ቬንቱራ በሚለው ነገር ይስማማል?! ካትሪና ባሰናዳችው መሰረት ነገ ከማገኛቸው ሰዎች ጋር ይህን ሀሳብ አንስቼ እወያይበታለሁ . .

ጧት ከቁርስ በኋላ ካትሪና ልጆቹን ይዛ ለግብይት ወጣች . . ጆርጅ ግን ካትሪና ባመቻቸች ቀጠሮ መሰረት የጃኖልካ ፍራንኳን መምጣት ቁጭ ብሎ ጠበቀ . . ጃኖልካ ካትሪና እንዳስተዋወቀችው በካቶሊካዊነትና በፕሮቴስታንት ላይ የጋዜጠኝነት ምርመራዎችን ያካሄደ ጣሊያናዊ ጋዜጠኛ ነው:: በተያዘለት ቀጠሮ ልክ ከጧቱ አምስት ሰዓት ላይ ከሆቴሉ ደረሰ:: ጆርጅ በሰላምታ ተቀበለው፤በትህትና ሰላምታውን መልሶ ፦

- ከቀሳውስት ወዳጆቼ ከአንደኛው በደረሰኝ መሰረት ለታላላቆቹ ጥያቄዎች ምላሽ ፍለጋ ላይ የተሰማራህ ተመራማሪ ነህ:: ካህኗ ባለቤትህ ለወዳጄ ለቄስ ሉዊጂ እስታቪኖ ደውላ ይህንኑ ነግራቸዋለች:: ለማንኛውም ራሴን ላስተዋውቅህ::
- ባለቤቴ ካህን አይደለችም:: ከአፍታ በኋላ ትመጣለች፤ካንተ ጋር መተዋወቅ ደስታዬ ነው፣እባክህን ቀጥል::

- እኔ ጣሊያናዊ ጋዜጠኛ ነኝ:: በዩኒቨርሲቲ ያጠናሁትን ፍልስፍና በጣም እወደዋለሁ:: የፈላስፋዎች - ፈገግ ብሎ ቀጠለና - በእርግጥ የብሩህ አእምሮ ባለቤቶችም ዋነኛ ጥያቄዎች የሕይወት ዋነኛ ጥያቄዎች ናቸው:: ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ስመራመር አያሌ ዓመታትን አሳልፌያለሁ::
- ካትሪና የደወለችላቸው ቄስ ለዚህ ነው አንተን ያናገሩት?
- አዎ::
- የዓመታት ምርምርህ ውጤት ምን ነበር?
- እህህ . . አስፈላጊ በሆኑ ውጤቶችና የተወሰኑ ነጥቦች ላይ ደርሻለሁ::
- በጣም ጥሩ፣ምንድናቸው?
- በቀላሉ . . ‹‹ምንም›› ነው መልሱ ! ያለኝ በአሳፋሪው የሃይማኖቶች ሁኔታ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች እንጂ የተቀናጀና ተሟልቶ የተጠናቀረ እሳቤ አይደለም::
- የምርምርህ ውጤት ‹‹ምንም›› ከሆነ ዘንዳ በምን ልትረዳኝ ትችላለህ?!
- እውነቱን ለመናገር አንተን ሊጠቅሙ የሚችሉ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ተሞክሮዎች አሉኝ:: እኔም በተራዬ ካንተ ልምድ መቅሰም እችላለሁ:: አዝናለሁ፣ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት ያደረኩት ጥረት ግን ውጤት አልባ ነው !
- መልሱ ‹‹መልስ የለውም›› ማለት ሊሆን ይችላል ብለህ ታምናለህ?
- አንተ ጥልቀትንና ማቅለልን አጣምረህ የተላበስክ ነህ፤ግሩም ነው አሟላው::
- ምኑን ነው የማሟላው? እኔ ጠያቂ ነኝ፣አንተ መልስ እንጂ::
- መልሱ ግልጽ ነው፤ስለሆነም መመለስ አያሻኝም:: መልሱ ‹‹መልስ የለውም›› ሊሆን የማይችል መሆኑ እርግጥ ነውና›› ቀጥል::
- እናም አንተ ያልደረስክበት መልስ ይኖራል ማለት ነው?
- አእምሮዬ መልስ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል ባይ ነው::
- አእምሮ መልስ ላይኖር ይችላል ብሎ ይገምታል የሚል እምነት የለኝም:: ይህ ማለት የሰው ልጆች በብኩንነት ውስጥ ይዳክራሉ ማለት ሲሆን፣ይህም በተራው ወደ ከንቱነትና ምንምነት መደዴ አመለካከት ያደርሳል::
- አንተ ድንቅ ፈላስፋ ነህ፤የኔም ሀሳብ ይኸው ነው:: ቅድም ያልኩህ ምን እንደምትል ለማየት ነው . . ይሁንና በአንተ አመለካከት ለጥያቄዎቹ ምላሽ የማገኘው ከወዴት ነው?
- በፍለጋ ላይ ነኝ፣እስካሁን አላገኘሁትም:: ያንተስ ሀሳብ?

- ብዙ ወዳጆቼ ኤቲስቶች ናቸው:: ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንደሌላት፣የጥያቄዎቹ ምላሽ በሳይንሳዊ ተግባራዊ ዘዴ ወይም በአጋጣሚ ብቻ ሊሆን እንደሚችል ሊያሳምኑኝ ይፈልጋሉ::
- መልካም፣ለጥያቄዎችህ መልስ ሰጡ?
- ኤቲዝም ወራዳ ፍልስፍና ነው:: በሳይንሳዊነትና በእሳቤነት ለመታየት ቢጥርም ከተራ አፈተረትና ከኋላ ቀር ቀባጣሪነት የሚያልፍ አይደለም:: እመነኝ ኤቲዝምን በሚገባ አውቃለሁ፤ከብዙ ኤቲስቶች ጋር ሰፊ ክርክር አድርጌያለሁ::
- በኤቲዝምና በሴኩላሪዝም አመለካከት ላይ ጫን ያልክ ትመስላለህ::
- ኤቲስት እንዳትሆን ስጋት አለኝ:: ለዚህ ነው መሰለኝ የምትከራከርላቸው:: ፍቀድልኝና እኔ ግን ካንተ ጋር በግልጽነትና በዝርዝር ነው የምናገረው:: እያንዳንዱ ኤቲስት ስህተተኛ መሆኑን በውስጡ አምኖ ይቀበላል:: እኔ ኤቲስት ነበርኩ፤ለተወሰነ ጊዜ ኤቲዝም ውስጥ ኖሬያለሁ:: ኤቲዝም ከሃይማኖቶች ችግር ለመራቅ የሚደረግ አንድ ዓይነት ሽሽት እንጂ ሌላ አይደለም:: ምንም ዓይነት ፍልስፍና፣ንድፈ ሀሳብ፣ሕሊናዊም ሆነ ሳይንሳዊ ማስረጃ የለውም:: ሴኩላሪዝም ግን በሃይማኖት ያምናል፤ነገር ግን ከኤቲዝም መነሻ በመነሳት ሃይማኖትን ከሰው ልጆች ሕይወት መነጠል ይፈልጋል::
- እንዴት?
- በሃይማኖትና በሳይንስ መካከል ያለው ቅራኔና ትግል ስር የሰደደ ዘመን ተሻጋሪ ችግር ነው:: በሁለቱ መካከል ግጭት ሲኖር በሰዎች ዘንድ የሳይንስ እውነታ ከሃይማኖት እውነታ የላቀ ነው::
- የኛ ዕውቀት ከእግዚአብሔር ዘንድ ከተላለፈው ዕውቀት የበለጠ ሊሆን ይችላል?
- በእርግጥ አይችልም:: ይሁንና ከእግዚአብሔር ዘንድ ስህተት ወይም ሊሆን የማችል ነገር ሊመጣ ይችላል?
- ምን ማለትህ ነው?
- ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምሳሌ ያህል ሌሎችን እንዲገድሉ ወይም ዝሙት እንዲፈጽሙ ወይም አስካሪ መጠጥ እንዲጠጡ የሚያበረታቱ ጥቅሶችን ሲያነቡ ወይም ሲሰሙ፣እነዚህ ነገሮች ከአእምሮ ከሞራልና ከዕውቀት አንጻር ጎጂዎች ለመሆናቸው እርግጠኞች እየሆኑ ምን እንዲያደርጉ ነው የምትፈልገው?

- እንግዲያውስ ከታላላቆቹ ጥያቄዎች መልስ ፍለጋ ድካም እፎይታ ለማግኘት ወደ ሴኩላሪዝም ደርሰሃል ማለት ነው።
- አዝናለሁ . . ሴኩላሪዝም ፈጽሞም እፎይታ አያስገኝም። እኔ የምናገረው ስለ ሴኩላሪዝም አማኝ ተከታዮች ነው። ሴኩላርዝም በሃይማኖትና በሳይንስ መካከል ያለውን ተቃርኖ እና የታሪክን ችግር ይፈታል። እንዲያውም እውነቱን ከፈለክ ሴኩላሪዝም ከክርስትና ሃይማኖት ጋር በብዙ መንገድ ይጣጣማል።
- መልካም . . የመጨረሻውን ነጥብ አብራራልኝ።
- ጳጳሳዊው ሥርዓት የምህረትና የስርየት ምስክር ወረቀቱን ላንተ ለመሸጥ ሲል የፈለከውን ነገር እንድትሰራ የሚፈቅድልህ መንገድ ነው። እናም ሃይማኖትን ወደ ጎን ብለህ ያሻህን ሰርተህ የስርየት ማረጋገጫውን ከቫቲካን መግዛት ብቻ በቂህ ነው።
- ፕሮቴስታንቶች ግን በዚህ አያምኑም፤አይደለም እንዴ?
- ያን የሚያደርጉት ግን ሃይማኖትን ከሰው ሕይወት ስለማይነጥሉ ሳይሆን ሃይማኖተኝነታቸው አነስ ያለ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ሃይማኖትን በይፋ ነው ከሰው ልጅ ሕይወት የሚነጥሉት። በኔ እምነት ለሱኩላሪዝምና ለኤቲዝም ዋነኛው መደላድል እና መረማመጃ ቤተክርስቲያን ነች !
- አንተ በምን ላይ ነህ?! የምን ሃይማኖት ተከታይ ነህ?! አንዴ ለኤቲዝም ትከላከላለህ፤አንዴ ደግሞ ለሴኩላሪዝም ትሞግታለህ፤ሌላ ጊዜ ለካቶሊካዊነት ትከራከራለህ !
- እኔ ምንም አይደለሁም። ውጤቱ ምንም አይደለም አላልኩህም ነበር? አንተስ ምንድነህ?
- አባትና እናቴ እንደዚያ ስለነበሩ እኔ ፕሮቴስታንት ነኝ። ከዚያም ምንም !
- እህህ . . እናም አንዳችን እንደሌላችን ነው ማለት ነው።
- ወደ ምንም ውጤት በደረስክ ጊዜ ደስተኛ ነበርክ? ደርሻለሁ ብለህስ ታስባለህ?
- ‹‹ምንም›› የሚደረስበት ነገር አይደለም ! ምናልባት እዚህ እኛ ዘንድ በምዕራቡ ዓለም የተለያዩ ከንቱና መደዴ አመለካከቶች፣ ጎራዎችና ሰክቶች እንዲነሱና እንዲስፋፉ መነሻ ምክንያቱ ይህ ሳይሆን አልቀረም።
- ከንቱና መደዴ አመለካከቶች?
- እህህ፣አዎ ሃይማኖታቸውን በምንም ላይ ወይም ከሃይማኖት በራቁ ተራ ነገሮች ላይ የሚመሰርቱ የአመለካከት ጎራዎች።

- እንግዲያውስ ይህን የ‹‹ምንም›› አደጋ ነው እንበላ?!
- ይልቅስ አደጋው የሕይወት ጥያቄ መልስ ያላገኘ መሆኑ ነው።
- ለምን ተዘናግተህ አትሸሸውም?
- አልቻልኩም፤አንድ ብልህ ወይም አርቆ አስተዋይ ሰው ይህን ማድረግ ይችላል ብዬ አላምንም።
- አብዛኛው ሰው እብድ ወይም ጅል ነው ማለትህ ነው?
- አብዘኞቹ ሰዎች ሕይወታቸው እየደፈረሰና ደስተኝነት እየራቃቸው ሊዘናጉት አይችሉም ማለቴ ነው።
- አንተ ፈላስፋ ነህ፤ግና ተስፈኛ አይደለህም። ወደ አልቦ ውጤት እንጂ የትም መድረስ አልቻልክም። ታዲያ መፍትሔው ምንድነው?
- ለኔ መፍትሔው ለጥያቄው መልስ እስክናገኝ ድረስ ፍለጋውን መቀጠል ነው . . አንተሳ መፍትሔው ምንድነው ትላለህ?
- መፍትሔው አንተ ያልከው ብቻ ነው። ካንተ የምለየው ግን በጣም ቅርብ በሆነ ጊዜ ውስጥ ወደ መልሱ እንደምደርስ የሚሰማኝ በመሆኑ ነው።
- ተስፋ መሰነቅ ከአምላክ የሚሰጥ ጸጋ ነው። ተስፋህ በተገቢ ቦታው እዲሆን ምኞቴ ነው። ይሁን እንጂ ተስፋ ለመሰነቅ አመላካች ነገር ሊኖርህ የግድ ይላል።
- አመላካች ማስረጃው መንገዱን ተስፋ ሳትቆርጥ በጽናት፣ያለማመንታትና ያላንዳች ጥርጣሬ በቁርጠኝነት መጓዝ ነው።
- ድንቅ ነው . . በጣም ግሩም ነው። በጉዞህ የት ደርሰሃል?
- ኤቲዝምንና ምድራዊ ሰው ሰራሽ ሃይማኖቶችን መርምሬ አልፌያለሁ። እንዳልከው ሁሉ የሚጠቅሙ አይደሉም። ከዚያ መለኮታዊ ሃማኖቶችን ተራ በተራ መመርመር ጀመርኩ። አሁን ክርስትናን በማጥናት ላይ እገኛለሁ።
- እኔ ከቤተሰብ መነሻ ካቶሊክ ነኝ፤ሆኖም ከካቶሊካዊነት ምኑንም እውነት ነው ብዬ አልቀበልም እለሃለሁ። ካቶሊካዊነት የግብስብስ ምስጢሮችና እርስ በርስ የሚጣረሱ ጉዳዮች ስብስብ ነው።
- ታዲያ ለምን ፕሮቴስታንት አትሆንም?
- አንተ ፕሮቴስታንቱ ይቅርታ አድርግልኝ፤በራሴ ሃይማኖት ነው የጀመርኩልህ። ፕሮቴስታንታዊነት ከካቶሊካዊነት ግብስብስ አፈተረቶችና ምስጢሮች ለመሸሽ የተደረገ ጥረት ነው። ይሁን እንጂ የተከታዩ ሃይማኖተኝነት እምብዛም የሆነ ያልተሳካ ጥረት ነው። በመሆኑም

www.path-2-happiness.com

የካቶሊካዊነትን ግብስብስ አፈተረቶችና ምስጢሮች ከፊሉን ልል ከሆነ ሃይማኖተኝነት ጋር ያጣመረ አዲስ ጎራ ነው።

- የበለጠ ብታብራራልኝ፤አንዳንዴ ድብቅ ትመስላለህ።
- ሁለቱም ማለቴ ካቶሊክና ፕሮቴስታንትም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይደለም የሚመረኮዙት? ብሉይና አዲስ ኪዳን ደግሞ የአፈተረቶችና የምስጢሮች መነሻ ናቸው።
- ከአምላክ ዘንድ ስለ ተላለፈው መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንዲህ ትናገራለህ ? !
- ልክ እንደ ቄሱ ወዳጄ ትናገራለህ። ለርሱ የሰጠሁትን መልስ ነው ላንተም የምሰጠው . . እስኪ በልበ ሙሉነት መልስልኝና አሁን በእጃችን የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ቃሉ መሆኑን ማረጋገጥ ትችላለህ? እኔ ግን ቢያንስ ከፊሉ ከእግዚአብሔር የተላለፈ ቃሉ አለመሆኑን በማስረጃ ላረጋግጥልህ እችላለሁ።
- እንዴት ነው የምታረጋግጠው?
- በብዙ ተጨባጭ ማስረጃዎች። ከነዚህ መካከል ከፊለክ መጽሐፍ ቅዱስ መቼ እንዴትና በነማን በጽሑፍ እንደ ተጠናቀረ ታሪኩን አንብብ። ከእግዚአብሔር የተላለፈ ቃሉ ነው ብሎ የሚያምን ሰው እንኳ ከታሪካዊ እውነታዎች ጋር ፊት ለፊት ይላተማል። በተለያዩ ቅጂዎች፣እትሞች፣ትርጉሞች መካከል ብቻ ሳይሆን በአንድ ተመሳሳይ ቅጂ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎችና የርስበርስ ግጭቶች አንብብ። ከእግዚአብሔር ዘንድ አለመሆናቸው ቁልጭ ብሎ የሚታዩ አንዳንዳንድ ትረካና ሁነቶቹን አንብብ። አምላክን በጨካኝ ተንኮለኛነት የሚገልጹ ትረካዎችን ተመልከታቸው . . ሌላ ማስረጃ ትፈልጋለህ? ዝርዝር ማስረጃዎችን ትሻለህ?
- በዚህና በሌላውም ጉዳይ ላይ የሚሉትን ለመስማት ከቄሱ ጋር መወያየት ፍላጎቴ ቢሆንም፣ባልከው ነገር በአብዛኛው እስማማለሁ።
- የምትደንቅ ሰው ነህ። ታዲያ በዚህ ላይ ለምን ትጨቀጭቀኛለህ?
- ሁኔታው አንተ እንዳልከው ከሆነ መፍትሔው ምንድነው?
- እኔ ምንም ውጤት ላይ አልደረስኩም ብየሃለሁ።
- ይቅርታ፣ምንም ነገር ስትል ምንም አለማወቅ ማለት ነው። እኔ የምፈልገው ዕውቀትና ግንዛቤ ያለውን ሰው ነው።
- የምትለው ነገር ትክክል ነው፤እኔ ግን የለኝም።
- ባንተ ግምት መልሱን መስጠት የሚችለው ማነው?

- ባውቅ ኖሮማ ድካሜ ከረዥም ጊዜ በፊት ባበቃ ነበር።
- መልካም ፈቃድህ ሆኖ ተጨማሪ ነገር ከቀሳውስት ማግኘት እፈልጋለሁ። ለነዚህና ለሌሎችም የሚሰጡትን ምላሽ መስማት እፈልጋለሁ።
- ቀሳውስት ወዳጆቼ ብዙ ናቸው። ዝግ የሆኑትን ወይስ ለሁሉም ነገር ክፍት የሆኑትን ነው የምትፈልገው? የዕውቀት ባለቤቶችን ወይስ ዐዋቂ መሰል ጥራዝ ነጠቆቹን?
- ማማረጥ የሚቻለኝ ከሆነ ያለ ጥርጥር ከዝጉ በክፍት አእምሮ የሚያናግረው የተሻለ ነው። ዋናው ግን የበለጠ ዕውቀት ያለው መሆኑ ነው። ዝግም ይሁን ክፍት እኔ የበለጠ ዕውቀት ያለውን ነው የምፈልገው።
- አይዞህ ተማመን፤ያንድ ሰው ዕውቀት በጨመረ ቁጥር ለተለያዩ ሀሳቦች ክፍትነቱ የበለጠ ይጨምራል። ባለቤትህ ካናገረችው ከወዳጄ ቄስ ሎዊጂ እስቲያቬኖ ጋር እንድትገናኝ ቀጠሮ እይዝልሃለሁ። ካየኋቸው ቀሳውስት ሁሉ የበለጠ እውቀት ያለውና ከሁሉም ይበልጥ በክፍት አእምሮ የሚናግር ቄስ ነው። ለነገ ወይም ለተነገ ወዲያ ቀጠሮ እወስድልሃለሁ።
- በጣም አመሰግናለሁ።
- የምትፈልገውን በሚገባ እገነዘባለሁ፤በምችለው ሁሉ ብረዳህ ደስተኛ ነኝ።
- ጆርጅ እየሳቀ ፦
- እንዳስቸገርኩህ ይሰማኛል፤ግና አንድ ጥያቄ አለኝ። እስላምን አጥንተሃል?
- አላጠናሁም . . እንዳው ጥቂት ንባብና አጭር ውይይት ብቻ እንጂ . . ።
- ለምን?
- እስላም የአመጽ፣የጦርነት፣የሴት ልጅ ጭቆና፣የኋላ ቀርነትና የመሳሰሉ ሌሎች ብዙ ነገሮች ሃይማኖት ነው።
- ታዲያ እስላምን አላጠናሁም፣አልመረመርኩም እያልክ ይህን ሁሉ እንዴት ማወቅ ቻልክ?
- ከመኖሪያ ቤታችን ጎረቤት ያለው ሬስቶራንት ባለቤት ግብጻዊ ሙስሊም ነው፤አንዳንዴ ከርሱ ጋር እወያያለሁ።
- ስለራሱ ይህንኑ ነው የሚናገረው?
- ስለራሱ ይህንን የሚናገር ማንም ሰው አይኖርም፤ግና እንደ ሌሎቹ ኋላ ቀር ሙስሊሞች ሳይሆን ስልጡን ሙስሊም ነው። ለሙስሊሞች ኋላ ቀርነት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ስጠይቀው ለግትርነት፣ተቃራኒን ለመግደል፣ሴትን ለማጨቆን እና ለመምታትም ጭምር ጥሪ የሚያደርግ በመሆኑ፣ምክንያቱ ሃይማኖቱ ራሱ መሆኑን ነው የነገረኝ።

-በጣም የሚገርም ነው፤እሱንም ማግኘት እችላለሁ?

-አንተ ራስህ በጣም ትገርማለህ:: ከርሱ ምን ትፈልጋለህ? ለማንኛውም ግን ቤታችን አቅራቢያ ባለው ሬስቶራንት በማንኛውም ቀን ምሳ ወይም እራት በልተህ ከርሱ ጋር ትንሽ ማውጋት እንችላለን::

-መልካም፣ከፈቀድክልኝ አሁንም ሌላ ጥያቄ አለኝ::

-እሺ ቀጥል::

-በካቶሊካዊነት ላይ ያለህን አቋም እያወቁ ቄሱ አንተን እንዴት ወደኔ ላኩህ?

-ክፍት አእምሮ አለው አላልኩህም? ብዙ ጊዜ እኔ የምናገራቸውን ነገሮች አሳማኝ ሆነው እንዳገኘው ይሰማኛል:: የተሻለው አማራጭ ግን ምን እንደሆነ አያውቅም !

-ብልጥ አቋም ነው:: ለጥያቄዎቻችን መልስ የምናገኝበት መንገድ ግልጽ ሳይሆንልን ከቀረ ከብኩንነትና ከባዶነት ያለንበት ነገር የተሻለ ይሆናል::

-ልክ ነህ:: እኔም ያለሁበት ብኩንነትና ባዶነት እንዳይሆን ተስፋ አደርጋለሁ፤ይሁን እንጂ አሁንም ፍለጋውን እንደቀጠልኩ ነኝ::

-ይቅርታ፣ፈጽሞ አንተን ማስከፋት አላሰብኩም::

-አውቃለሁ::

ካትሪና ከማይክልና ከሳሊ ጋር ተመለሰች:: ከጃኖልካ ጋር ተገናኝተው ሰላምታ ተለዋወጡ . .

-ጌታ የተመሰገነ ይሁን፤ከመሄድህ በፊት ደረስኩ:: ከተከበሩ ቄስ ሉዊጂ እስታቢኖ ዘንድ አይደለም የመጣኸው?

-አዎ፣እናም አንቺ የጆርጅ ባለቤት ነሽ ማለት ነው:: ምንኩስናን ባትቀበይም ከእንግሊዝ ሃይማኖት አጥባቂ ካቶሊኮች አንዷ መሆንሽን ነው ቄሱ የሚናገረው::

-ላንተም ለሉዊጂም ምስጋና ይድረሳችሁ:: የሚሰጡትን ትምህርቶች እና ሌክቸሮቻቸውን በማደማጥ የምከታተላቸው መምህሬ ናቸው::

-ለነገ ወይም ለተነገወዲያ ከርሱ ጋር እንድትገናኙ ቀጠሮ እይዝላችኂለሁ::

-ጆርጅ ከተስማማ ግሩም ነው::

-ጆርጅ ራሱ ነው ጥያቄ ያቀረበው፤ወደ አልፈኻማ ሬስቶራንትም ጎራ ትላላችሁ::

-በጣም ጥሩ ነው:: ከመምህሬ ጋር እገናኛለሁ . . ግን ያልከው ሬስቶራንት በተለይ ለምን ተመረጠ?

-ጃኖልካ ንገራት . .

-ከሙስሊሞች አንዱን ለማግኘት::

-ለምን?

-አላውቅም:: ግን ስለ እስላም ኂላቀርነትና ስለ አረመኔነቱ ከርሱ መስማት ይፈልጋል::

-ይህ ሙስሊም ያልነገረህን ብዙ ነገር እኔ እነግረሃለሁ:: የሃይማኖታቸውን ኂላ ቀርነት ለማወቅ ኂላ ቀር ሀገሮቻቸውን መመልከት ትችላለህ::

-ለማንኛውም ይህ የአድራሻ ካርዴ ነው:: ማንኛውም ዓይነት ሃይማኖታዊ ወይም ቱሪስት ነክ ጥያቄ ካላችሁ ብትደውሉልኝ ደስተኛ ነኝ:: ከወዳጅ ቄስ ሉዊጂ እስታቢኖ ጋር ቀጠሮውን አረጋግጬ እደውልላችኂለሁ፤ደህና ሁኑ::

ጃኖልካ ወጥቶ ሄደ፤ካትሪና እየሳቀች ወደ ጆርጅ ዞራ . .

-ውይይታችሁ እንዴት ነበር? በጊዜ ተመልሰን ባገኘው ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር::

-በጣም ጥሩ ነበር፤አመሰግንሻለሁ::

-እንዲህ ነውና . . ቄሱ ምሁርና ሃይማኖተኛ የሆነ ካቶሊክ ሰው እንጂ ሌላ አይደሉም::

-አዎ . . ፈላስፋና ምሁርም ነው:: እንዳልሽው አጥባቂ ካቶሊክ ሃይማኖተኛ ግን አይደለም::

-ይገርማል ! ወዳጃቸው መሆኑን ነው የነገሩኝ::

-ልክ ነው ወዳጃቸው ነው::

-አንድ ቄስ ሃይማኖተኛ ካልሆነ ግለሰብ ጋር ወዳጅነት ሊኖረው ይችላል?!

ዋናው ነገር ሊጠቅሙን ስለሚችሉ ከቄሱ ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ እንዲይዝልኝ ነው::

-ከማንኛውም ግለሰብ የሚጠቅም ነገር መቅሰም መልካም ነው፤በተለይም ቄስ ከሆነ:: ለመሆኑ ገበያ ሄዳችሁ ምን ሰራችሁ?

-አስደሳች ሽርሽር ነበር:: ሕጻናቱ በገበያው የመጫወቻ ስፍራ ተጫውተው ካበቁ በኂላ ለአጭር ጊዜ ተዘዋውረን አንዳንድ ነገሮችን ሸምተናል . . የመንገዱ መጨናነቅ ነው ያቆየን::

-ከከተማዋ የቱሪስት መዳረሻዎች ውስጥ የቱን ነው ዛሬ የምንጎበኘው?

-ለማይክል ስንል የቅዱስ አንጀሎን አምባ እንጎበኛለን:: በጣም ውብና በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ አምባ ነው:: እሱንና በአካባቢው ያሉትን

www.path-2-happiness.com

ለመጎብኘት ሙሉ ቀን ይወስድብናል።

-በሉ አሁን እንሂድ፣ማይክልና ሳሊ የት ናቸው?

-ክፍላቸው ናቸው። አዲሱን ጫማቸውን እያደረጉ ነው፣እንንቀሳቀስ።

ቤተሰቡ ወደ ቅዱስ አንጅሎ ለመሄድ ተያይዘው ወጣ . . ጆርጅ የቶምን ምክር ተግባራዊ ለማድረግ አእምሮውን ነጻ አድርጎ ከቤተሰቡ ጋር ለመንሸራሸርና ለመዝናናት ፈለገ። ስለ የመታደል መንገድ ፍለጋው ብዙ ላለማሰብና ለጥያቄዎቹ ምላሽ ወደሚያገኝበት መንገድ ለመድረስ ብዙ ላለመጨነቅ፣ጉዞውንም በእርጋታና በዝግታ ለማድረግ ወሰነ . .

ከቄሱ ጋር



www.path-2-happiness.com

12 ከቄሱ ጋር

ከቄሱ ጋር

(1)

ምሽት ላይ ቤተሰቡ ወደ ሆቴሉ ተመለሰ . . ጃንሉካ ለጆርጅ ስልክ ደውሎ ከቄስ ሉዊጂ ጋር ያለው ቀጠሮ ነገ ጧት አራት ሰዓት ላይ በቤተክርስቲያን መሆኑንና እርሱም እዚያ እንደሚጠብቃቸው ነገረው::

- ጃኖልካ ነው የደወለው፤ከቄሱ ጋር ያለን ቀጠሮ ነገ መሆኑን ነው የነገረኝ . . እናም ሕጻናቱን የት ነው የምንተዋቸው?
- ወይ ከኛ ጋር እንወስዳቸዋ፤ለን፣ወይ ደግሞ ከቤተክርስቲያኑ አቅራቢያ ባለው መናፈሻ እናቆያቸዋለን፣ውብ መናፈሻ ነው ያለው::
- መልካም፣ያ ይበልጥ የሚመች መሰለኝ::

ጧት ሁለት ተኩል ላይ ጆርጅና ካትሪና ከሕጻናቱ ጋር ከቤተክርስቲያኑ አቅራቢያ ወደሚገኘውና የተለየ የልጆች መጫወቻ ጥግ ወዳለው መናፈሻ አመሩ:: ለሕጻናቱ አስፈላጊው ሁሉ እንዲደረግላቸው ከጥጉ ኃላፊ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ማይክልና ሳሊን እዚያ እንዲቆዩ አደረጉ . . በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከቄሱ ጋር ለመገናኘት ወደ ቤተክርስቲያኑ አቀኑ . . ጃኖልካ ተቀበላቸውና ተያይዘው ሞቅ ያለ አቀባበል ወዳደረጉላቸው ቄስ ሉዊጂ አመሩ::

- ካትሪና እንኳን ደህና መጣሽ፣በእንግሊዝ አገር ስለምታደርጊው ከፍተኛ ትጥረትና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ እሰማለሁ፣ጌታ ይባርክሽ::
- ይህ ከርስዎ የተማርነውና ከርስዎ ዕውቀት ያገኘነው ነገር ነው::
- ጆርጅ እንኳ ደህና መጣህ . . ጃኖልካ ስለ ጥያቄዎችህና ስለ ብሩህ አእምሮህ ነግሮኛል:: የምትፈልገውን ማቅረብ ትችላለህ::
- ጊዜዎን አላባክንም፣አራት ጥያቄዎች አሉኝ:: አንደኛው እግዚአብሔር አንድም ሦስትም እንዴት እንደሚሆን አልገባኝም:: ብዙ አንብቤያለሁ፣ብዙ ትንተናዎችንም አዳምጫለሁ፤ምንም ውጤት ላይ አልደረስኩም:: ይቅርታ ደረግልኝና አንዳንዴ ክርስትና ከጣዖት አምላኪነት ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ነው የሚሰማኝ!

የቄሱ ፊት ተለዋወጠ፤የጃኖልካና የካትሪናን ፊት ተመለከቱና ቀጥለው

www.path-2-happiness.com

መሬት መሬት እያዩ . .

- ሁለተኛውስ?
- ኢየሱስ አምላክ ነው ወይስ ሰው ነው? አምልኮት የሚደረግለት አምላክ ነው ወይስ የተገደለ አገልጋይ ፍጡር ነው? የሰው ልጆችን ለማዳን አምላክ መሞት ያስፈልገዋል?! ሳይሞት በሕይወት እየኖረ ሰዎችን ማዳን አይቻልም?
- ሦስተኛውስ?
- መጽሐፍ ቅዱስን ብሉይ ኪዳንንም ሆነ አዲስ ኪዳንን ማነው የጻፈው? ማንስ ተረጎመው? ወደኛ ያስተላለፈውስ ማነው? በተለያዩ እትሞቹ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአንድ ተመሳሳይ እትም ውስጥ እርስ በርስ የሚጣረሱ ተጻራሪ ነገሮች ለምን ኖሩ? መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ብዙዎቹን ምንባቦች ለማንበብ ልጆቼን እንኳ የማፍር ከሆነ ፈጣሪዬን ዘንድ አሳፋሪነቱ እንዴት ነው የሚሆነው?
- አራተኛውስ?
- የሃይማኖቶችና የነብያት ታሪክ የግድያ፣የአመጽና የብልግና ታሪክ ነው? አመጽና ግድያን እጠላለሁ፤ለአመጽና ለግድያ ጥሪ የሚያደርገውን ሁሉ እጠላለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ለነብያትና ለእግዚአብሔር መልእክተኞች ያለው አመለካከት ግን ይገርመኛል፤የግድያ የዝርፊያና የወሲብ ጥቅሶችም እንዲሁ ይገርሙኛል!

ቄሱ ራሳቸውን ቀና አደርገው ወደ ጃኖልካ ከመዞራቸው በፊት ጆርጅንና ካትሪናን ዓይን ዓይናቸውን ተመለከቱ . .

- ጃኖልካ አስቀድመህ የርሱን ጥያቄዎች ለምን አልነገርከኝም?
- እርሱም አልነገረኝም ነበር!

ቄሱ ለአፍታ የጆርጅን ዓይኖች ትኩር ብለው አዩ . . ከዚያም የድከመትና የቁርጠኝነት ምልክቶች ተጣምረው በሚስተዋልበት ፊት ወደላይ ተመለከቱ፤በመቀጠል በጥልቀት ለመናገር ተመቻቹ . . .

- አየህ ልጄ የነዚህን ጥያቄዎች ምላሽ እንዲህ በቀላሉ መረዳት አትችልም፤ለማብራራትም ረዥም ጊዜ ይወስዳሉ። እናም ይህን ትተህ ወደ ጌታ አምልኮ ለምን አትሰማራም?
- ጌታዬ፣የመጣሁት ከርስዎ ተምሬ በዕውቀትዎ ለመጠቀም ነው። ረዥም ትንታኔ የሚያስፈልገውን ነገር ምሁራን ዐዋቂዎች አሳጥረው መግለጽ ይችላሉ።

- ደግ ነው ልጄ፣በሃይማኖታችን ውስጥ ልንወያይባቸውና ልንከራከርባቸው የማይገቡ ብዙ ምስጢሮች ይገኛሉ። አንተ ብቻህን በራስህ ልትረዳቸው የማይገቡ ብዙ ምንባቦችም እንደዚሁ አሉ።
- ጌታዬ፣ምስጢሮቹን በተመለከተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ ሃይማኖት እንድንከተል ታዘን ይህ ሃይማኖት ምስጢር ሊሆን እንዴት ይችላል? ለሁሉም ሰው ከእግዚአብሔር የተላለፉ ምንባቦችን ጥቂቶች ብቻ እንጂ ሌሎች የማይረዱት እንዴት ነው?!

በአነጋገሩ መከፋታቸው በቄሱ ፊት ላይ በግልጽ ታየ፤ወደ መሬት አዩና እንዲህ አሉ ፦

- ከጆርጅ ጋር ብቻዬን እንድሆን ሁለታችሁ ገለል ልትሉልን ትችላላችሁ?

የጃኖልካ ፊት ተለዋወጠ፣በአነጋገራቸው መከፋቱ በግልጽ ተስተዋለበት፤አርሱ ራሱ ካመቻቸው ፕሮግራም በገዛ ወዳጁ መባረሩ ሊዋጥለት አልቻለም . .

- እኔና ካትሪና እንድንወጣልዎ ነው ሚፈልጉት? ለምን ይህም ሌላው ምስጢር ይሆን እንዴ?!
- ለርሱ ብቻ መንገር የምፈልገው ነገር ስላለ ብትወጡልኝ አመሰግናችኋለሁ።
- ካትሪና ወደ ማይክልና ሳሊ ሂጂና እዚያ ጠብቂኝ፣ከአፍታ በኋላ እቀላቀላችኋለሁ።

ካትሪና ቄሱን ተሰናበተች፤ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከሚመሩት የቅዳሜ የቅዳሴ ሥርዓት እንዳትቀር አሳስበው በቡራኬ ሸኙዋት . . ከጃኖልካ ጋር ወደ መናፈሻው አመራች . . ሁለቱ ለቀው ሲወጡ ቄሱ ወደ ጆርጅ ፊታቸውን አዞሩ . .

- የኔ ልጅ አንተ በጣም ደፋር በጣም ጀግና ሰው ነህ፤ጀግንነት የጦር ሜዳው ሳይሆን ውስጣዊው ጀግንነት ነው።
- ጌታዬ አመሰግናለሁ።
- ልጄ ካንተ ጋር ስናገር እኔም ደፋር ጀግና ሆኜ ነው፤ምናልባትም የማትወደውን ነገር ከኔ ልትሰማ ትችላለህ።
- እሽ ይሁን፣ዋናው ነገር የምወደውን መስማቴ ሳይሆን የሚያስፈልገኝን መስማቴ ነው።
- ሊያስደንቅህ ይችል ይሆናል፣እያዘንኩ ለነዚህ ጉዳዮች ቁርጥ ያለ ምላሽ አይገኝም።
- ጌታዬ፣እምነትና ጥርጣሬ አንድ ላይ ሊሆኑ እንደማይችል አይታይዎትም?
- የምትናገረው ትክክል ነው። ቀርጥ ያለ መልስ ማግኘት ግን አልቻልኩም።

www.path-2-happiness.com

ዕድሜዬን በሙሉ አንተ የጠቀስካቸውንም ለሚያጠቃልሉ ብዙ ጉዳዮች ምላሽ ስፈልግ ቆይቻለሁ። የሆነ ነገር መልስ ነው ብዬ ልነግርህ እችል ነበር፤ግና ደፋርና እውነተኛ ለመሆን ቃል ስለ ገባሁልህ እውነቱን ልንገርህና እስካሁን ድረስ ቁርጥ ያለ ምላሽ አላገኘሁላቸውም።

- ታዲያ መፍትሔው ምንድነው?
- እኔ አሁን ካለሁበት የተሻለ ነገር ስላላገኘሁ አሁንም ቄስ ነኝ። ለኔ በሁሉም ነገር ተጠራጣሪ ከመሆን መልስ ያላገኘሁላቸው አንዳንድ ጉዳዮች መኖራቸው ይመረጣል፤አይመስልህም?
- ልክ ነዎት፤ይሁን እንጂ በላጩ መልስ ብናገኝላቸው ነው።
- እውነት ነው፤ምናልባት አንተ መልሱን ታገኝ ይሆናል፤የማረጋግጥል ነገር ቢኖር መልሱ ከቤተክርስቲያን በኩል እንደማይሆን ነው። በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ በቄስነት ሰላሳ ዓመታት አሳልፌያለሁ፣መልስ ግን አላገኘሁም። እኔ ዘንድ ያለው ይኸው ብቻ ነው።
- አንድ ጥያቄ እንድጠይቅ ይፈቅዱልኛል?
- ጠይቅ።
- ጃኖልካና ካትሪና እንዲወጡ ለምን ፈለጉ?
- በምነግርህ ነገር ትገረም ይሆናል! ይህን ያደረኩት ድፍረትና ጀግንነት ስለሚጎድለኝ ነው። ማንም ቢሆን በሌሎች ሰዎች ፊት በተለይም ዐዋቂ ነው ብለው በሚተማመኑበት ሰዎች ፊት ደካማ አላዋቂ ሆኖ መታየት አይፈልግም። በተጨማሪም ካቶሊካዊነትን ወይም ክርስትናን ከነአካቴው ቢተውት ምንድነው የሚሆኑት? ለምሳሌ ኤቲስት ሊሆኑ ይችላሉ። በኔ እምነት በጥርጣሬና በውዥንብር ዓለም ከመኖር የተወሰኑ ጥርጣሬዎችን ይዞ መኖር የተሻለ ነው።
- ይቅርታ ይደረግልኝና ለመሆኑ ከቀሳውስትና ከመነኮሳቱ መካከል እርስዎ የሚሉትን ነገር በይፋ ለመናገር ድፍረቱ ያላቸው የሉም ማለት ነው?
- በክርስትና ታሪክ ውስጥ ይህን ያደረኩ ቀሳውስትና መነኮሳት በተለያዩ ዘመናት ተነስተዋል፤ሁሉም ግን ወይ ይገደላሉ፣ወይ ይሰወራሉ፣ወይ ይሸሻሉ። መጽሐፍ ቅዱስና የቫቲካን መንበረ ፓትርያርክ ሥርዓት ጨካኞች ናቸው።
- እናም ኤሪክ ፊራቲኒ ‹‹ተቋሙ - የሰላይነት አምስት ምእተ ዓመታት›› በሚለው መጽሐፉ ውስጥ እንዳረጋገጠው በቫቲካንና በተለያዩ የዓለማችን የስለላ ድርጅቶች መካከል ያለውን ምስጢራዊ ግንኙነት እርስዎም ይደግፋሉ ማለት ነው?
- ፈጽሞ . . ይህ ትክክል አይደለም፤ከአሜሪካዊ ፕሮቴስታንት በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ የተሰነዘረ ስም ማጥፋት ነው።
- በመረጃ የተደገፉና ያነሳቸው እውነታዎችሳ?
- እያዘንኩ ብዞዎቹ እውነት ናቸው እለሃለሁ፤ዳሩ ግን ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን እና ርእሰ ሊቃነ ጵጵስናውን ለማሳጣት በሚያስችል አቀራረብ ሆን ተብለው የተቀነባበሩ ናቸው።
- የስለላ ተቋማት ወደ ቫቲካን መስረግ ወይም በሌላ አገላለጽ የቫቲካን የስለላ ተቋም በመላው ዓለም መሰራጨቱ ግን እውነት ነው። ልክ አይደለም?
- እያዘንኩ አሁንም አውነት ነው፤ብዙ ጊዜ የሚሆን ቢሆንም አጠቃላይ የሆነ ጉዳይ ግን አይደለም ።
- ቫቲካንና መንበረ ፓትርያርኩ ጭካኔና ጡጫውን በካህናትና በመነኮሳት በኩል በሕጻናት ጭምር ላይ በሚፈጸሙ የወሲብ ቅሌቶች ላይ ለምን አላየንም?
- ሊታይ አይችልም፤ይህ ነገር በመካከላቸው በሰፊው የተሰራጨ ነው። ታዲያ ለሕጻናት ተብሎ ቤተክርስቲያኒቱ ትሰንጠቅ ብለን እንዴት እንጠብቃለን?! ደግሞም ከነዚህ ወሲብ ነክ ጉዳዮች ከፊሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ውስጥ ጭምር የሚገኝ ነው። አንተ አንባቢ ምሁር ነህና የኔ ልጅ ችሎታህን በሚጠቅምህ ነገር ላይ ብታውለው የተሻለ ነው። ክርክሩን እዚህ ላይ ብንገታውስ?
- ጌታዬ ካቲሪና እና ጃኖልካ ለምን እንዳስወጧቸው ቢጠይቁኝ ምን ልበላቸው?

ቄስ ሎዊጂ በዝምታ ተውጠው እንዳቀረቀሩ ፦

- ሁሌም ቢሆን እውነት ተመራጭ ነው።
- ጌታዬ አመሰግናለሁ፤በጌታ ፈቃድ አድርገዋለሁ፤ከርስዎ ብዙ እውቀት ገብይቻለሁ።
- እኔም አመሰግናለሁ፣ጌታ ይባርክህ፤በተከበረው የቅዳሜ የቅዳሴ ሥርዓት ላይ እንደማገኝህ ተስፋዬ የጠበቀ ነው፤እርግጠኛ መሆን ከጥርጣሬ የተሻለ ነው።

ጆርጅ ተሰናብቶ ከወጣ በኋላ ካትሪና እና ጃኖልካ ወደሚጠብቁበት መናፈሻ አመራ። እንደ ደረሰ ጃኖልካ ጠየቀው ፦

- ለምንድነው እኛን ያስወጣን? ሎዊጂን ያልተገራ አድራጎት ሲፈጽም

www.path-2-happiness.com

ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነው !

የጃኖልካ ቁጣና መከፋት ግልጽ በመሆኑ ጆርጅ በማስወጣቱ ጉዳይ ላይ መነጋገር አልፈለገም . .

-የምሳ ሰዓት ተቃርቧል፤አብረን በልተን ለመጨዋወት እንድንችል፣ከቤትህ አቅራቢያ ካለው አልፈኻማ ሬስቶራንት በቅርብ ርቀት ላይ ነን?

-አዎ፣ከዚህ በእግር የአምስት ደቂቃ መንገድ ነው::

-እንግዲያውስ ፍቀድልኝ . . ከልጆቼ ጋር ተጫውቼ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ወደ ሬስቶራንቱ እንቀሳቀሳለን . . ካትሪና ምን ትያለሽ?

-ጥሩ ነው፣በግማሽ ሰዓቱ ውስጥ ባንተና በቄሱ መካከል ስለ ነበረው ቆይታ እንድትነግረን ምኞቴ ቢሆንም፣ይሁን ችግር የለውም:: ለማንኛውም ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሁሉንም ነገር ትነግረናለህ::

ጆርጅ ለጃኖልካና ለካትሪና ምን እላለሁ? ያበጠው ይፈንዳ የሆነውን ሁሉ ልንገራቸው? ምን ላድርግ? ብሎ ከራሱ ጋር እየተሟገተ ልጆቹ ወደሚገኙበት የመናፈሻው የሕጻናት ጥግ አመራ::

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ጆርጅ ከሕጻናቱ ጋር ተመልሶ መጣ . .

-በጣም ርቦናል፣በሉ ወደ ሬስቶራንቱ እንሂድ::

-በሉ እንሂድ::

(2)

ለአምስት ደቂቃ ያህል በእግር ከተጓዙ በኋላ ወደ አልፈኻማ ሬስቶራንት ደረሱ . . ጆርጆ ወደ ማይክልና ሳሊ ጎንበስ ብሎ ፦

-ውዶቼ . . ከተማውን እያያችሁ በሬስቶራንቱ ሰገነት ላይ ብትመገቡ ምን ይመስላችኋል?

-አንተና ማማ የት ልትመገቡ?

-እኛ የጠበቀ ቀጠሮ አለን:: እናንተ ለብቻችሁ ሆናችሁ እየተጨዋወታችሁና የከተማውን ውብ ገጽታ እያያችሁ ምሳችሁን ትበላላችሁ::

-በጣም ጥሩ፣ሳሊ በይ እንሂድ::

ጆርጅ ካትሪና እና ጃኖልካ መሀል ላይ ያለውን ጠረጴዛ ይዘው ተቀመጡ . . የምግብ ዝርዝሩን በማየት ላይ እያሉ ጆርጅ ፊቱን ወደ ጃኖልካ አዞረና . .

-ሙስሊሙ ወዳጅህ የት ነው?

-እሱም እኛን አስወጥቶን ካንተ ጋር ብቻ ለመነጋገር እንዳይጠይቅ እሰጋለሁ . . ለመንኛውም የምግብ ትእዛዞቹን ለመቀበል ከአፍታ በኋላ ይመጣል::

-ከቄሱ ጋር ትተኸኝ እንድትወጣ እኔ አልጠየኩህም፣የቄሱ ወዳጅህ ፍላጎት ነው::

-ይሁን እንጂ አንተም ወዲያው ነው የተስማማኸው::

-እህህ፣ታዲያ የሃይማኖት መሪዎችን መታዘዝ ግዴታ አይደለም እንዴ?! ዋናው ነገር . . ጥያቄዎቼ መልስ እንደሌላቸውና እናንተ ደግሞ ድክመቱንና አለማወቁን እንዳታዩ መፈለጉን ነው የነገረኝ::

ካትሪና ተከፍታ ወደ ጆርጅ ዓይኖች እየተመለከተች ፦

-ቄስ ሎዊጂ ዘንድ እንዲህ ላሉ ቀላል ጥያቄዎች ምላሽ ሊታጣ አይችልም !

-ምላሽ እንደሌሉትማ በሚገባ አውቃለሁ፣ይህንን እንደማውቅም ያውቃል:: የገረመኝ ለምን እንድንወጣ ፈለገ? በጉዳዩ ውስጥ ሌላ ነገር እንዳለ ነው የሚሰማኝ::

-ለማንኛውም ከኔ ይበልጥ ስለምትተዋወቁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ፤እንደሚመስለኝ ካትሪናን ብቻ ማስወጣት ስለአሳፈረው ነው::

ለአፍታ ዝምታ ሰፈነ . . ዓይኖቿ ልታፍነውና ልትደብቀው የምትሞክረው ነውጥ ውስጧ መኖሩን የሚያሳብቁ ይመስል ጆርጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በባዘነ የካትሪና እይታ ውስጥ ግራ መጋባትና ጥርጣሬ መኖሩን አስተዋለ:: ዝምታዋ ምናልባት የታፈነ እሳተ ገሞራ ዝምታ ዓይነት ሊሆን ይችላል:: የጆኖልካ ዝምታ ግን በግልጽ በሚያውቀው ጉዳይ ላይ ወዳጁ ይህን ማድረጉ አስገርሞት ቢሆንም ጆርጅ ከነገረው ውጭ ከጀርባው የሆነ ነገር አለ የሚል ጥርጣሬ አሁንም አልለቀቀውም::

ትእዛዝ ለመቀበል አስተናጋጅ መጣና አስፈሪውን የዝምታ ድባብ ሰበረው . . ጃኖልካ የሬስቶራንቱ ባለቤት ሰሊም መኖሩን ጠየቀውና ከተቻለ ከርሱ ጋር መነጋገር እንደሚፈልግ ነገረው . .

-ሰሊም ከወዳጆቹ ጋር እቢሮው ነው ያለው . . መልእክትዎን አደርሰዋለሁ . . ይቅርታ ለምሳ ምን ልታዘዛችሁ?

ትእዛዞቻቸውን ለአስተናጋጁ ተናገሩ:: ጆርጅ ማይክልና ሳሊ የት እንዳሉ ለአስተናጋጁ ነግሮ ትእዛዙን እንዲያደርስላቸው ጠየቀው . . ወደ ጃኖልካ እያየ ጥያቄ ሰነዘረ . .

-ሰሊም የነገርከኝ ሙስሊም ነው?

-አዎ፣ለመጀመሪያ ጊዜ ስታየው ጣሊያናዊ ሊመስልህ ይችላል . . በነገራችን ላይ እንግሊዝኛን ጥርት አድርጎ ይናገራል::

-መልካም፣ከአፍታ በኋላ ይመጣና እንሰማው ይሆናል::

ከረዥም ዝምታ በኋላ ካትሪና ተናገረች . .

- አሁን ወደ ቄሱ ጉዳይ እንመለስ . . ለጥያቄዎችህ መልስ መስጠት አልቻሉም ነው ምትለው !
- አዎ አልቻለም፣ይህም ብቻ ሳይሆን ዕድሜውን በሙሉ ለነዚህና ለሌሎቹም ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ሲጥር መኖሩንና አሳማኝ መልስ ማግኘት ያቃተው መሆኑን ነው የነገረኝ::
- ሊሆን የማይችል ነው !
- ካትሪና የምትናገሪው ቄስ ወዳጄ ነው፤መልሶቹን እንደማያውቅ በሚገባ አውቃለሁ:: በነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ በተደጋጋሚ ተከራክሬዋለሁ:: የገረመኝ ግን ለምን እንድንወጣ እንደፈለገ ብቻ ነው ! የማላውቀው ነገር ቢኖር ይኸኛው ብቻ ነው !
- ቄስ ሎዊጂ እስቲያቬኖ እርግጠኛ እንድሆን ካገዙኝ ሰዎች መካከል ዋነኛው ናቸው:: እንዴት ሆኖ ነው ይህ ጥርጣሬ እሳቸው ዘንድ ሊኖር የሚችለው?! ጆኖልካ ለመናገር ተመቻችቶ አንጋጦ ተመለከተና ፦
- የኔ ተሞክሮ እንዲህ ይላል ፦ የቄሱ ዕውቀት እየዳበረ በመጣ ቁጥር በግል በሚያደርገው ውይይት ይበልጥ እየተለሳለሰ ሲሄድ፣ለተራው አማኝ በጅምላ የሚሰጠውና የሚመጠናቸው ትምህርቱ ደግሞ ተጽእኖው እየጨመረ ይመጣ ነበር::
- ምን እያልክ ነው?
- አንቺ ከርሱ የሰማሽው ለተራው አማኝ የሚሰጠውን ትምህርት ነው:: ለግለሰብ በዝግ የሚናገረው ግን ከዚያ የተለየ ነገር ነው:: ለማንኛውም እኔ እረደዋለሁ፤ለሕዝብ በይፋ በሚሰጠው ትምህርት ምን እንዲል ነው የምትፈልጊው?! እኛ ጌታን አናውቅም፣ወይም መጽሐፍ ቅዱስ የተዛባ ወይም የሰዎች የገባበት ፈጠራ ነው እንዲል ትፈልጊ ኖሯል?!

ዓይኖቿ እንባ እየዘሩ ካትሪና እንዲህ አለች ፦

- አይደለም፣ቸሩ ርህሩሁ ጌታ ሦስት አካላት ቢኖሩትም አንድ ነው፤መጽሐፍ ቅዱስም ከርሱ የተላለፈ ቃሉ ነው እንዲሉ ነበር የምፈልገው::
- ጃኖልካ ካትሪናን በአዘኔታና በስስት ዓይን እያያት ፦
- መጽሐፍ ቅዱስ ከገዛ ራሱ ጋር እርስ በርሱ ሲጣረስ ምን ማድረግ እንችላለን? አሳማኝ በሆነ ሎጂካዊ መንገድ ሦስት አንድ፣አንድ ደግሞ ሦስት እንዴት እንደሚሆን ልታብራሪልኝ ትችያለሽ?! በቤተክርስቲያን የሚሉትን እንደማይለኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: ያንን ሺህ ጊዜ ሰምቻለሁ፣ሊያሳምነኝ

አልቻለም፤ይልቁንም ለብዙኃን ለሚሰጥ የጅምላ ትምህርት ብቻ እንጂ ለሌላ የሚረባ አይደለም የሚል እምነት አለኝ::

- ጆርጅ የካትሪና ከባድ ውስጣዊ ነውጥና በውስጧ በመፈንዳት ላይ ያለው እሳተ ገሞራ ተሰማው:: ለራሱ እንዲህ አለ ፦

ስለ ቄሱ የሰማችው ነገር ንዝረቱ አቅሟ መሸከም ከሚችለው በላይ ሆኖባት ሊሆን ይችላል አለና ርእሱን ለመለወጥ ሞከረ . .

- አሁን ወደኛ የሚመጣ ሰው ስላለ ውይይታችሁን ለሌላ ጊዜ ብታቆዩ ምን ይመስላችኋል?
- ኦ ሰሊም ነው . . ሰሊም እንኳን ደህና መጣህ፣ካንተ ጋር መተዋወቅ የሚፈልግ ሰው አለ::
- ሁላችሁም እንኳን ደህና መጣችሁ . . ጃኖልካ ከእንግዶችህ ጋር እንኳን ደህና መጣህ::
- ሁለቱ እንግዶቼ ከዚህ በፊት ከሙስሊም ሰው ጋር ተቀምጠው አውርተው ስለማያውቁ ካንተ ጋር ትንሽ ማውጋት ይፈልጋሉ::
- ደስ ይለኛል፤እኔ ከግብጽ ነኝ:: እናንተስ ከየት ናችሁ?
- ከእንግሊዝ ነን::
- በእንግሊዝ የሙስሊሞች ቁጥር በኢጣሊያ ካሉት በእጥፍ ይበልጣል::
- ልክ ነህ፤እኔ እንኳን የፈለኩት ስለ እስላም ካንተ ለማወቅ ነው:: ቅዱስ መጽሐፋችሁ በብሉ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ያምናል?
- ስእስላም ሃይማኖት እምነቶች ያለኝ ዕውቀት በጣም ውስን ቢሆንም ለማንኛውም የማውቀውን እመልስላችኋለሁ . . አዎ፣ያምንባቸዋል፤ግን ይቅርታ አድርጉልኝና - የተዛቡና የተበረዙ አድርጎ ይወስዳቸዋል::
- በሙሴና በኢየሱስ ታምናላችሁ?
- ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩ ነብያት ናቸው ብለን እናምንባቸዋለን::
- በጌታ ኢየሱስ ታምናላችሁ?
- አናምንም፣ሙስሊሞች የሚያምኑት ጌታ ሳይሆን የተከበረ የእግዚአብሔር ነብይ መሆኑን ብቻ ነው::
- ቅዱስ መጽሐፋችሁ ስሙ ምንድነው? እንዴት ነው ወደናንተ የደረሰው?
- ስሙ ቁርኣን ነው፤የደረሰን በነብዩ ሙሐመድ አማካይነት ነው . . ምንድነው የፈለጋችሁት?
- እስላምንና ትምህርቶቹን መተዋወቅ ነው የምንፈልገው::
- እኔ በበኩሌ እስላምን ብዙም አላወቅቀውም፤የማውቀው ንግድና ቱሪዝምን

www.path-2-happiness.com

ነው:: ለመሆኑ ከእስላም ምንድነው የምትፈልጉት?

- እናንተ ዘንድ ያለው አመጽና ሽብርተኝነት ስለሚያስገርመን ብቻ ነው::
- እኛ ዘንድ ያሉት አሸባሪ ሙስሊሞች በሃይማኖት ስም ሁሉንም ነገር ያወድማሉ::
- በሃይማኖት ስም ነው የምትለው? እንዲህ ያለ አመጽና ሽብር ያለበት ምን ዓይነት ሃይማኖት ነው?
- አዎ፣እስላም የሰላም ሃይማኖት እንጂ የሽብር ሃይማኖት አይደለም፤ሙስሊሞች ግን ኋላ ቀሮችና ግትሮች ናቸው::
- እንደገና ኋላ ቀሩ እስላም ነው ወይስ አሸባሪዎቹ ናቸው?
- እስላም ኋላ ቀር አይደለም፣ሙስሊሞች ግን ኋላ ቀር ናቸው:: ሙስሊሞች ብትሆኑ ሚስትህ እንደዚህ ከኛ ጋር ቁጭ ብላ እንዲህ ማውራት የማይቻል ነበር:: ታዲያ ይህ ኋላ ቀርነት አይደለም?
- ለምንድነው ከናንተ ጋር መቀመጥ የማይቻለኝ?
- መሸፋፈንና ከወንዶች መራቅ ስለሚኖርብሽ መቀመጥ አትችይም፤እውነቱን ለመናገር ግብጽን የተውኩት ከዚህ ኋላ ቀርነት ለመራቅ ነው::
- ዘመዶችህና መንግስትህም አቋማቸው ይህ ነው?
- እህህ . . አባቴ እናቴና ወዳጆቼ ሁሌም አመለካከትህ ከእስላም ያፈነገጠ ነው ይሉኛል::
- ለምን?
- እስላም ከክርስትና ሙለ በሙሉ ይለያል፤እናንተ ክርስቲያን ለመሆን አልፎ አልፎም ቢሆን በሳምንት አንድ ቀን ብቻ መጸለይ ይበቃችኋል:: እኛ ዘንድ ግን በቀን አምስት ጊዜ የማይሰግድ ሰው ከሃይማኖቱ ውጭ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል:: እናንተ ብሉይና አዲስ ኪዳንን መተቸት ትችላላችሁ፣በኛ ግን ቁርኣንን የተቸ ሰው ከእስላም እንደ ተቀለበሰ ይቆጠራል::
- ከቤተሰቦችህ ውስጥ እዚህ ጣሊያን ውስጥ የሚኖር ሰው አለ?
- ከአስር ዓመታት ወዲህ ጣሊያን ውስጥ ለብቻዬ ነው የምኖረው፤ወደ አገሬ መመለስ እምቢ ብያለሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከሳምንት በፊት ወንድሜ፣እናቴና አባቴ መጥተው እዚህ ይገኛሉ፣ከሦስት ቀናት በኋላ ተመልሰው ይሄዳሉ::
- ላገኛቸው እችላለሁ?
- አዎ ይቻላል፣ነገር ግን እናንተ እነሱ ዘንድ ከሀዲዎች በመሆናችሁ

አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ::

- እንዴት?
- አንተ እግዚአብሔር ሦስት ነው ትላለ፤ህ፣ይህ ደግሞ ከርሱ ጋር ባእድ አምላክ መያዝ በመሆኑ አንድ እግዚአብሔርን ክደሃል፣ካፍር ነህ ማለት ነው::
- ምን አዲስ ነገር አለው?! እኛም በኢየሱስ አምላክነት ስለማያምኑ ከሃዲዎች ናቸው እንላለን፣ብናገኛቸው ምንም ችግር የለውም::

ካትሪና አሁንም ከቄሱ ጋር በሆነው ነገር ክፉኛ እንደበረገገች ናት፤በመሆኑም ተጨማሪ አንቀጥቃጭ ነገር የሚሸከም አቅም እንደሌላት ይሰማታል ፦

- ጆርጅ ጊዚ የለንም፣ነገ የተከበረው የቅዳሜ የቅዳሴ ሥርዓት መሆኑን አትዘንጋ::
- እነሱ ጊዜ ካላቸው እኛ በቂ ጊዜ አለን . . መቼ ልናገኛቸው እንችላለን?
- ሙሉ ጊዜአቸውን ወይ ቤት ወይ እዚህ ሬስቶራንት ናቸው:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ይመጣሉ ብዬ አስባለሁ:: ሌላ ጊዜ እንዲሆን ከፈለክም እንዲጠብቁህ አደርጋለሁ . . እደግመዋለሁ ስለሚናገሩት ነገር እኔ ተጠያቂ አይደለሁም::

ጆርጅ ነገሩን የምር በመያዙ ካትሪና ፊት ላይ ገልጽ የመከፋት ስሜት ይነበባል፣በምሬት እንዲህ አለችው ፦

- ይቅርታ . . ጆርጅ ምን እንዳሰብክ አልገባኝም:: ሞቼ እገኛለሁ ካልክ ተመልሰን ወደ ሬስቶራንቱ ለመምጣት እንዳንገደድ ጥቂት ደቂቃዎች እንጠብቃቸው::
- ወደ ላይ ወጥቼ ማይክልና ሳሊን አይቻቸው እመለሳለሁ::
- ቆይ፣ይኸውና መጥተዋል፣ከኛ ጋር እንዲቀመጡ ወደዚህ ልጥራቸው?
- ወደዚህ ጥራቸው፤ልጆቹን አይቼ በፍጥነት እመለሳለሁ::
- እጠራቸዋለሁ፣የናንተ ጥያቄ ነውና ኃላፊነቱን የምትወስዱት እናንተ ናችሁ . . እናቴ፣አባቴ፣ኻሊድ ወደዚህ ኑ . . ከናንተ ጋር መገናኘት የሚፈልግ ሰው እዚህ አለ::
- ሳሊም ምድነው?
- ኻሊድ እነዚህ ወዳጆቼ ከናንተ ጋር መተዋወቅ ይፈልጋሉ:: ላስተዋውቃችሁ ይህ ወንድሜ ኻሊድ ነው፣እሷ እናቴ ነች፣ይሄ አባቴ ነው . . ኻሊድ እንግሊዝኛ ይናገራል፣እናቴና አባቴ ግን በመጠኑ ብቻ ይረዳሉ እንጂ አይናገሩትም:: ሁላችሁም ፍቀዱልኝና እኔ ከማዳመጥ ውጭ በውይታችሁ

www.path-2-happiness.com

ውስጥ ጣልቃ አልገባም፡፡

- ሁላችሁም እንኳን ደህና መጣችሁ፤ኻሊድ እባላለሁ የሕንጻ መሀንዲስ ነኝ፣ሰሊም ወንድሜ ነው፡፡ ይህ አባቴ ዐብዱላህ ነው፣እሷ እናቴ ዓእሻ ናት፡፡
- እኔ ጃኖልካ እባላለሁ በነጻ ንግድ ላይ የተሰማራሁ ኢጣሊያዊ ነኝ፡፡
- ስሜ ካትሪና ነው፣እንግሊዛዊት ነኝ፡፡
- ሁላችሁም እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡

ጆርጅ ከልጆቹ ዘንድ ተመልሶ መጣና ሰላምታ አቅርቦ ኻሊድና አባቱን ከጨበጠ በኋላ እናቲቱን ለመጨበጥ እጁን ሲዘረጋ ሳትጨብጠው ፈገግ ብላ ሰላምታውን መለሰችለት . .

- ይቅርታ . . እናቴ ወንዶችን አትጨብጥም፣ሰላም እንኳን ደህና መጣህ ትለሃለች፡፡
- እኔም ይቅርታ እጠይቃለሁ፣እንዲህ መሆኑን አላውቅም ነበር፡፡
- አንተ ከመምጣትህ በፊት ተዋውቀናል፤እኔ የሰሊም ወንድም ነኝ፣ስሜ ኻሊድ ነው፣የሕንጻ መሀንዲስ ነኝ፤እሷ እናቴ ነች፣ይህ አባቴ ነው፡፡
- እኔ ጆርጅ እባላለሁ፣የኮምፒውተር መሀንዲስ እንግሊዛዊ ነኝ፡፡ የጥንታዊ ታሪክ የሃይማኖትና የጥበብ አገር የሆነችውን ሮምን እንዴት አገኛችኋት?
- የሕንጻ መሀንዲስ እንደ መሆኔ በጥበቡ ልጀምር መሰለኝ፡፡ሮም በልዩ ጥበብ የተዋበች ናት፣አንዳንድ የማልወዳቸው ነገሮች ቢኖሩባትም የጥንታዊ ስልጣኔና የዘመናዊ ተሞክሮ ባለቤት የሆነች ግንባር ቀደም ከተማ ነች፡፡
- ምኗን ነው ያልወደድከው?
- ቅርጻ ቅርጽ ጣዖታትና ሰዎች በአክብሮትና በቅድስና የሚመለከቷቸው መሆኑ አያስደስተኝም፡፡ እንዲህ ያለው ነገር ካደግንበት ሃይማኖታችን ጋር አይጣጣምም፡፡ ይህ ጣዖታዊነትና ከአንድ አምላክ ሌላ ባዕድ አማልክት ማምለክ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ጆርጅ ሐውልትና ቅርጻ ቅርጾችን በመጥላቱ ረገድ ከሙስሊሞች ጋር መመሳሰሉን አስታወሰ . . የሕንዱዎችና የቡድሂስቶች ቅርጻ ቅርጽና ጣዖታት አማልክትም ትዝ አሉት . .

ኻሊድ ቀጠለ . .

- ይህ የሃይማኖት ጉዳይ ስለ ሮም ወደ ጠየከኝ ርእስ ይወስደኛል፡፡
- በማቋረጤ ይቅርታ፣ያደግንበት ሃይማኖታችን ስትል ምን ማለትህ ነበር?
- በእስላም ውስጥ እኛ ማንንም ምንንም ከእግዚአብሔር ጋር አናጋራም፡፡

ምንም ሸሪክ የሌለው አንድ አምላክ ብቻ መሆኑን አጥብቀን እናምናለን፡፡ ማንም ፍጡር ማንም ሰው ወደ አምላክነት ደረጃ ከፍ ሊል አይገባም፣ፈጽሞ አይችልምም፡፡ ለዚህ ነው ነብያችን ሙሐመድ (የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) ‹‹ከኔ በኋላ መቃብሬን የሚመለክ ጣዖት አድርጋችሁ አትያዙ፤እኔ የአላህ ባሪያና መልእክተኛው ብቻ እንጂ ሌላ አይደለሁምና›› ይሉ የነበረው፡፡

- ከአነጋገርህ እንደምረዳው እኛ ጣዖታውን አጋሪዎች ነን ማለት ነው?
- እግዚአብሔር ሦስት አምላክ ነው ብሎ የሚያምን ሰው እኛ ዘንድ በአላህ የሚያጋራ ሰው ነው፡፡

ቀስፎ የያዛትን ነገር የምታስተነፍስ ይመስል ካትሪና በከርክሩ ውስጥ ጣልቃ ገባችና . .

- ያንተ ታላቅ ሰሊም ግን ሀሳቡ ከዚህ የተለየ ነው፣አንተ የምትለውን ነገር አክራሪነት ነው ብሎ ነው የሚያምነው፡፡
- ወንድሜ ሰሊም ታላቁ ነው፣አከብረዋለሁ፣ሰው ፊት እርሱን መጻረር አልወድም፤እኔ በግሌ ግን ባልኩት ነገር አጥብቄ አምናለሁ፡፡

ጆርጅ አቋረጠና . .

- ይህ ማለት ሙሴና ኢየሱስ ውሸታሞች ናቸው ማለት ነው?
- እንዲህ ከማለት በአላህ እጠበቃለሁ ! እኛ በሙሴና በኢየሱስ (ሰላም በነርሱ ላይ ይሁንና) በፍጹምነት ነው የምናምነው፡፡ እናከብራቸዋለን፣እናልቃቸዋለንም፡፡ ከአላህ ዘንድ የተላኩ መልእክተኞች መሆናቸውንና ከአላህ ዘንድ መጽሐፎች የተላለፉላቸው መሆኑንም አጥብቀን እናምናለን . . ይልቁንም ብዙዎቹ የናንተ እምነቶች ደረጃቸውን አሳንሰው ያያሉ ብለን እናምናለን፡፡
- እኛ የወልድን የኢየሱስን ደረጃ ዝቅ እናደርጋለን !
- እናንተ በሰው እጅ ተገድሏል ብላችሁ ታምናላችሁ፤እኛ ግን አልተገደለም ብለን እናምናለን፡፡ አንዳንዶቻችሁ ዘንድ ደግሞ ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ተደርጎ ይታይ የለም? እናንተ አይደላችሁም ይህን ሁሉ የምታምኑት?
- እናንተስ . . በኢሱስና በድንግሏ ላይ ያላችሁ እምነት ምንድነው?
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ባሪያና መልእክተኛው መሆኑን እናምናለን፤ተመሳሰለባቸው እንጂ አልገደሉትም አልሰቀሉትም ብለን እናምናለን፡፡ አደም ያለ አባትና ያለ እናት እንደ ተፈጠረው ሁሉ ከእናቱ ከመርየም (ሰላም በርሷ ላይ ይሁንና) ያለ አባት በአላህ ተአምር የተወለደ

www.path-2-happiness.com

ነው፣ለዚህም ነው በአንቀልባ ሆኖ በአራስነቱ የተናገረው፣ብዙ ተአምራትን አላህ የሰጠው፣መናገር የተሳነውንና በለምጽ የተያዙትን ሕሙማን ያድን የነረው፣በአላህ ፈቃድም ሙታንን ያስነሳ የነበረው፣ሰዎች በቤቶቻቸው የሚበሉትንና የሚያስቀምጡትንም ይነግራቸው የነበረው።

- እናም ስለ ኢየሱስ የተሟላ እሳቤ አላችሁ፣ታምኑበታላችሁ፣በብሉይና አዲስ ኪዳንም ታምላችሁ ማለት ነው?
- አዎ፣በኦሪትና በወንጌል በመሰረቱ ከእግዚአብሕር ዘንድ የተላለፉ በመሆናቸው እናምናለን።
- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው !
- በመሰረቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፉ መሆናቸውን ነገር ግን የተዛቡና የተከለሱ መሆናቸውን እናምናለን። እናንተ ዘንድም በአንዳንድ ወንጌሎች ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም አምላክ ሳይሆን የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑ ተጠቅሶ የለም?
- የለም፣እንዲህ ያለ ነገር እኛ ዘንድ የለም።

ጃኖልካ ረዥም ጸጉሩን ወደኋላ መልሶ እጁን አነሳና ፦

- ስላቋረጥኳችሁ ይቅርታ፣የበርናባስ ወንጌል የሚባል ወንጌል አለ፣መኖሩ የታወቀው በአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ክርስትናን በከዳ ካቶሊካዊ መነኩሴ አማካይነት ነበር። ወንጌሉ ኢየሱስ ከርሱ በኋላ የሚመጣ ሌላ ተተኪ የእግዚአብሔር መልክተኛ ነብይ መኖሩን ያበሰረበትና ኢየሱስ የእግዚአብሔር መልክተኛና ነብይ መሆኑን የሚያስተምር በመሆኑ፣ የተለያዩ የክርስትና ቡድኖች ግን ወንጌሉን አይቀበሉትም።

ጆርጅ በአድናቆት ዓይኖቹን አፈጠጠና ፦

- እውነት ነው?! ታዲያ ካቶሊካዊ ቡድኖች ለምን ዕውቅና አልሰጡትም?!
- እርግጥ ነው ካቶሊኮችም ሆኑ ፕሮቴስታንቶች ባይቀበሉትም ሌሎች አንዳንድ የክርስትና ቡድኖች ተቀብለው አምነውበታል። ከዚያ በኋላ ብዙዎች እስላምን ተቀብለዋል፣በዚህ ምክንያትም ወንጌሉን የጻፈው ሙስሊም ነው ተብሎ ይተቻል።

ኻሊድ ፈገግ ብሎ ፦

- ወንጌሉ ከሌሎቹ ይበልጥ ለእውነት የቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃዎች አሉ።
- ይበልጥ ለእውነት የቀረበ ስትል ምን ማለትህ ነው? ትክክለኛ የሆነና ትክክለኛ ያልሆነ የሚባል ወንጌል አለ እንዴ?
- ከዓለማት ጌታ ከተላለፈው ወንጌል ጋር ይበልጥ የሚቀራረብ ማለቴ

ነው። ይህም አዲስ በተገኙ ጥንታዊ የብራና ጽሑፎች ወይም ግብጽ ውስጥ ከሚገኙ የበኒ መዛር ዋሻዎች በአንደኛው ውስጥ በተገኘው ወንጌል የተደገፈ ነው። ወንጌሉ ከነብዩ ሙሐመድ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) መምጣት በፊት በሦስተኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ የተጻፈ ሲሆን የይሁዳ ወንጌል ተብሎ ይጠራል፣በይዘቱ ከበርናባሳ ወንጌል ጋር ተመሳሳይ ነው።

ጃኖልካ በፌዝ ድምጸት ፦

- የምትናገረው ሁሉ ትክክል ነው፣አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ግን በዚህም ሆነ በዚያኛው ወንጌል አያምኑም።

ኻሊድ ወደ ንድሙ ወደ ሰሊም እያየ ፦

- ቅር አሰኝቻችሁ ከሆነ ይቅርታ አድርጉልኝ፣የምናገረው ነገር ሁሉ ለኢየሱስና (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) ወደርሳቸው ለተላለፈው መጽሐፍ ካለኝ ጥልቅ ፍቅር የመነጨ ነው።

ካትሪና ስሜቷ ተለዋወጠ፣ስለ ኢየሱስ ፍቅር ሲነሳ ዓይኖቿ እንባ አቀረሩ . .

- ሕይወቴ በሙሉ ለኢየሱስና ለፍቅሩ ቤዛ ይሁን፣ለዚህ ነው አዳኛችን በመሆኑ በርሱ የምናምነው፣ለዚህም ነው ክርስቲያኖች ተብለን የምንጠራው።
- እኔ የሕንጻ መሀንዲስ እንጂ የሃይማኖት ምሁር አይደለሁም፣ይሁን እንጂ ለዒሳ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) ያለሽ ፍቅር እውነተኛ ይመስላል። ‹‹ለኢየሱስ ያለኝ ጥልቅ ፍቅር ወደ እስላም መራኝ›› የሚለውንና በቬንዙዌላዊው ካቶሊክ ክርስቲያን በሳይሞን አልፍሬዶ ካራቢሎ የተጻፈውን መጽሐፍ አንብበሻል?
- እንዲህ የሚባል መጽሐፍ መኖሩንም ሰምቼ አላውቅም፣ለኢየሱስ ያለኝ ፍቅርም ከካቶሊካዊነት በስተቀር ወደሌላ ይመራኛል ብዬም አልገምትም።
- ብታነቢው ምን ይጎዳሻል?! በካቶሊካዊነትሽ ትተማምኚ የለም?!
- አላየሁትም እንጂ አነበው ነበር።
- ይኸው ይህ ከኔ የተበረከተልሽ የመጽሐፉ እትም ነው። ይቅርታ ይደረግልኝና ከዓለማዊ ሕይወት የራቁና የናቁ መስለው የኢየሱስን ፍቅር ለግል ጥቅማቸው መገልገያ እንዳደረጉ አንዳንድ ቀሳውስትና መነኮሳት ሳይሆን ለኢየሱስ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) ያለሽ ፍቅር ከልብ የመነጨ ሆኖ ለምን እንደሚሰማኝ አላውቅም።

www.path-2-happiness.com

-አመሰግናለሁ . . አነበዋለሁ፤ለኢየሱስ ባለኝ ፍቅር ላይም ሆነ በካቶሊካዊነቴ ላይ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ እርግጠኛ ነኝ።

-የሃይማኖት ምሁር አይደለሁም ትላለህ፣ስትናገር ግን የሃይማኖት ምሁር ቋንቋ ብቻ ሰይሆን ወደዚህ ሃይማኖት ጥሪ በሚያደርግ ሰው ቋንቋ ነው የምትናገረው።

-እስላም ሁላችንም ወደዚህ ሃይማኖት ጥሪ የምናደርግ ሰዎች እንደንሆን ይጠይቀናል። (ፈገግ ብሎ እናቱን አየና) እናቴ ወደዚህ አገር እንድመጣ ስታስገድደኝ እዚያ አገር ወደ እስላም ጥሪ የማድረግ አጋጣሚ ታገኝ ይሆናል ብላኝ ነበር፣እኔ ኢጣሊያንኛ ስለማላውቅ ለኔ ይህ የመጀመሪያ የደዕዋ አጋጣሚዬ ነው።

-ይቅርታ፣ሰው ሁሉ ወደዚህ ወደ ሰለጠነውና ወደ በለጸገው የምዕራቡ ዓለም ለመምጣትና ከኋላ ቀር አገሮች ለመውጣት ደስተኛ ነው። አንተ እንዴት ነው እናቴ አስገደደችኝ የምትለው?

-አውሮፓ ከኛ በጣም የሰለጠነች ናት። በየአገሮቻቸው በሚደርስባቸው ፖለቲካዊ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ጭቆና ምክንያት ስደተኞች ወደዚህ ሲደርሱ እንዲደሰቱ የሚያደርጋቸውም ይህ ነው። እኔ ግን በጥሩ ኩባንያ ውስጥ በመሀንዲስነት እሰራለሁ፣በቂ ገቢም አለኝ። እኛ ዘንድ በግብጽ አምባገነናዊው ሥርዓት ከወደቀ በኋላ ሁኔታችን ከበፊቱ የተሻለ ነው፣መጪው ጊዜ ደግሞ አላህ ካለ የበለጠ የተሻለ ይሆናል።

-እናንተ ዘንድ ላለው ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጭቆና መንስኤው ሃይማኖት አይደለም እንዴ?

-እስላም በምንም መንገድ የጭቆና ምክንያት ፈጽሞ ሊሆን አይችልም።

-በአሌግዛንደሪያ የሁለቱን ቅዱሳን ቤተክርስቲያን ያፈነዱት ሙስሊሞች አይደሉም?

-መጀመሪያ ላይ እንደዚያ ተብሎ ነበር፤ሁሉም ዓለም እኔም ጭምር በነገሩ ብገረምም እውነት ነው ብለን ተቀብለን ነበር። በምዕራባውያን ድጋፍ ሲገዛ የኖረው አምባገነኑ ሁስኒ ሙባረክ ከወደቀ በኋላ ግን ከፍንዳታው ጀርባ እሱና የስላላ ተቋማቱ እጅ እንደነበረበት ተረጋግጧል። የመጀመሪያውን ዜና ሰምተሃል፣በምዕራቡ ዓለም እንደተለመደው ሁለተኛውን ዜና አልሰማህም የሚል እምነት አለኝ።

-ይሁን እንጂ በሃይማኖታችሁ ምክንያት አሁንም ኋላ ቀሮች ናችሁ?

-የኻሊድ እናት (ዓእሻ) ምልክት አሳይተውት ፦

-ኻሊድ እንዲህ በለውማ ፦ የኔ ልጅ እኛ ወደኋላ የቀረነው በሃይማኖታችን ምክንያት ሳይሆን ከሃይማኖታችን በመራቃችን ምክንያት ነው!

ኻሊድ እናቱ ያሉትን ተርጉሞ ነገረው . . ምሳው ቀረበና ጠረጴዛ ላይ ተደረደረ፤ጆርጅ ግን የተጀመረውን ውይይት ለማስቀጠል ሞከረ . .

-አባትና እናትህ በመካከላችን የሚደረገውን ውይይት ይረዳሉ?

-አዎ፣በሚገባ ይረዳሉ፣እንግሊዝኛ መናገር ባይችሉም በሚገባ ይረዳሉ፤ሰሊም ከመጀመሪያው ነግሯችሁ ነበር፣ግና አንተ ከመምጣትህ በፊት ነው መሰለኝ።

-ጥያቄ ላቀርብላቸው እችላለሁ?

-እናቴ አቅርብ ትለሃለች፣መልሷን እኔ እተረጉምልሃለሁ።

-ኤቲስት ወይም አይሁዳዊት ወይም ክርስቲያን በሆንኩ ብለው አይመኙም?

-(እናት በኻሊድ ትርጉም) ፦ ልጄ በአላህ እጠበቃለሁ፣ብኩንነትንና ጥፋትን የሚመኝ ማንም ሰው አይኖርም።

-እኛ ያለንበት ጥፋትና ብክነት ነው ማለት ነው?

-(እናት በኻሊድ ትርጉም) ፦ ያ ጥፋትና ብክነት ካልሆነ ጥፋትና ብክነት ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፤እኔ በእስላም የተከበርኩ የታፈርኩ ኩሩና ደስተኛ ነኝ።

-ይህ ግን የርስዎ አመለካከት ብቻ ነው ወይስ የሁሉም ግብጻውያን አመለካከት ነው?

-(እናት በኻሊድ ትርጉም) ፦ ቢያንስ የኔ አመለካከት ነው። የሚያሳዝነው ግን ከኛም ዘንድ በናንተ ተጽእኖ ስር ወድቀቀው ሃይማኖትን ኋላ ቀርነት አድርጎ የሚመለከቱ አሉ።

ከዚያም ወደ ልጃቸው ወደ ሰሊም ተመለከቱ፣ራሱን አቀረቀረ . .

-ሴት ግን እስላም ውስጥ የተዋረደች ናት!

-(እናት በኻሊድ ትርጉም) ፦ ማነው እንዲህ ያለህ?! እኔ ዕድሜዬ ስልሳ አምስት ነው፣በዚህ ዕድሜም ልጄ ኻሊድ ሥራ የሚበዛበትና መምጣት የማይፈልግ ቢሆንም ትእዛዜን ተቀብሎ ከኔ ጋር እንዲመጣ ማስገደድ እችላለሁ። እርሱና ሴት ልጆቼም በየሳምንቱ ሦስትና አራት ጊዜ ይጠይቁኛል፣ስጦታዎች ያቀርቡልኛል፣እኔም ሆንኩ አባታቸው የሚያዛቸውን ነገር አንዲት ነገር መቃወም አይችሉም። እንዲህ ያለ አክብሮት አይተህ ታውቃለህ? አክብሮት ይህ ካልሆነ አክብሮት ሚባል ነገር የለም ማለት ነው።

-እኔ አባትና እናቴን ከሦስት ወራት ወዲህ አላየኋቸውም።

ኻለድ የናቱን ምላሽ ከሰማ በኋላ ትንሽ እንደ መሸማቀቅ አለና ግልጽ የመሸማቀቅ ስሜት ወደሚስተዋልበት ሰሊም ተመለከተ . .

-ምንድነው ያሉት . . ?

-ላስከፋህ አልፈልግም . .

-ፈጽሞ አልከፋም፣ንገረኝ።

-ከናንተ እንደተማረውና ጸባያችሁን እንደወረሰው ሰሊም ነህ ትላለች።

-እዚህ እኛ አገር የሚገኙት ግን ብዙዎቹ ጠጭዎች፣ስነ ምግባር የጎደላቸውና ያልተገሩ ናቸው!

-(እናት በኻሊድ ትርጉም) ፦ አቅጣጫ ጠቋሚ ጠፍቶባቸው የሚባክኑ ሰዎች ሁሉም ቦታ ይገኛሉ፣አቅጣጫቸውን ሲያውቁ ግን ተጸጽተው ወደ ፈጣሪያቸው ይመለሳሉ።

ማይክልና ሳሊ ምሳቸውን ካበቁ በኋላ ከሰገነቱ ወርደው መጡ . .

-ባባ ከሃያ ደቂቃ በኋላ እመለሳለሁ ብለህን ለአርባ አምስት ደቂቃ ጠበቅንህ፣ቃል በገባህልን መሰረት አንሄድም?

-ይቅርታ፣ልጆቻችሁን እንድትዘነጉ አደረግናችሁ።

-ኦህ፣ጊዜው መሄዱ ትዝ አላለኝም ነበር።

-ሰሊም፣ኻሊድ፣ዓኢሻና ዐብዱላህ በጣም ነው የማመሰግነው . . ብዙ ጊዜ ተሸማናችሁ። ይህ የኔ ቢዝነስ ካርድ ነው የናንተን ልትሰጡኝ ትችላላችሁ?

-አባቴና እናቴ ምን ካርድ ይኖራቸዋል?! የኔ ይኸውና፣ኢሜይሌ አለበት፣ካትሪና ስለ መጽሐፉ ያለሽን አስተያየት ትልክልኛለሽ ብዬ ተስፋ ላድርግ?

-እሞክራለሁ፣አመሰግናለሁ።

ኻሊድ ከናቱና ከአባቱ ጋር ከሄደ በኋላ ሰሊም ይቅርታ ሊጠይቃቸው ወደ እንግዶቹ ፊቱን አዞረ . .

-እንዳልኳችሁ በዝምታ ነው የቆየሁት፣ለተሰማችሁ ማንኛውም ቅሬታ ይቅርታ እጠይቃለሁ። እኔ ግን ከመጀመሪያው ተናግሬ አስጠንቅቄአችሁ ነበር፣እናንተ ናችሁ እምቢ ያላችሁ።

-በተናገሩት ነገር ብደናገጥም፣አቀራረባቸውም ትንሽ ጠንከር ያለ ቢሆንም ሁሉም ግን የተገራ አንደበት ያላቸው ጨዋዎች በመሆናቸው ምንም ይቅርታ መጠየቅ አያስፈልግህም . . እህህ፣ይልቅስ ለዓመታት ያልጎበኘሃቸውን ወላጆችህን ሄደህ ይቅርታ ጠይቅ።

ጃኖልካ ሁሉንም ተሰናብቶ ወደ ሥራው ሄደ። ጆርጅና ካትሪና ከሕጻናቱ ጋር ወደ ትሬቪ ፏፏቴ አመሩ . . በጣም ድንቅ የሆነ ፏፏቴ ነበር። በውብ እይታው በጣም ተማረኩ፤የዕለቱን ቀሪ ጊዜ በአካባቢው አሳለፉ . . ለቀው ከመሄዳቸው በፊት ካትሪና ሳንቲሞችን ወደ ፏፏቴው ወረወረችና ሳሊ ተገርማ ወደ እናቷ ተመለከተች . .

-በጣሊያኖች አፈተረት ሳንቲሞችን እዚህ የወረወረ ሰው ወደ ሮም ተመልሶ ይመጣል ይባላል።

-ባባ ሳንቲሞች ስጠኝ እኔም ልወረውር።

-የኔ ልጅ እውነት አይምሰልሽ፣ተረት ነው።

-አፈተረት መሆኑን አውቃለሁ፣ይሁንና ግን በትሬቪ ፏፏቴ ሳንቲም ወርወሬያለሁ ብዬ ለማውራት ብቻ ሳንቲም መወርወር እፈልጋለሁ።

-ይኸው ሳንቲሞች፣ ለራስሽና ለማይክልም ውሰጂለት። ካትሪና አንቺ ደግሞ አማኝ አፈተረተኛ እንዳትሆኚ ተስፋ አደርጋለሁ።

ካትሪናም ግልጽ በሆነ ምሬት መለሰች . .

-አንተም ውስብስብ ሰው እንዳትሆን ተስፋ አደርጋለሁ . . ነገሮችን አቅልላቸው፤ይህ ዝም ብሎ ሽርሽርና መዝናናት እንጂ ምንም አይደለም።

(3)

-ካትሪና ምን ሆነሻል?

-ምንም።

-ፏፏቴውና በአካባቢው ያለው መናፈሻ አላስደሰተሽም?! . . ዛሬ እንደ ልማድሽ ስትስቂና ስትጫወቺ አላየሁሽም።

-በጣም ቆንጆ ነበር ግን አእምሮዬ ትንሽ ውጥረት ውስጥ ሳይሆን አልቀረም።

-በምን?

-ከተገናኘናቸው ዓይነት ሙስሊሞች ጋር መገናኘት የምትፈልገው ለምንድነው?

-አፈተረታቸውንና ኋላ ቀርነታቸውን አውቄ ቶም ስለ ሙስሊሞች ሲጠይቀኝ መልስ ላዘጋጅለት ነው።

-ግና ለንግገራቸው በጣም ጥሩ አዎንታዊ አቀባበል ነበረህ።

ማይክል ፈገግ ብሎ የካትሪናን ዓይኖች እየተመለከተ ፦

-እኔ ነበርኩ አዎንታዊ አቀባበል የነበረኝ?!

ካትሪና ማለት የፈለገውን ተረድታለች . .

- እኛ ለኢየሱስ ባለን ፍቅር ላይ ሊጨረት ይፈልጋል::
- በእርግጥም ኢየሱስንና እናቱን ከልብ የሚያፈቅሩ ይመስላሉ::
- ምንድነው የምትለው?!
- ልዩነቱ በኢየሱስ አምላክነት ላይ ነው:: እነሱ ይህንን በእግዚአብሔር ማጋራት ባእድ አምልኮና ጣዖታዊነት አድርገው ነው የሚወስዱት::
- እኛ ግን የአምላክ አንድነትና አምልኮ አድርገን እንወስዳለን::
- እህህ፣መጽሐፉን ታነብዋለሽ?
- ማንበብ አልፈልግም::
- እህህ፣አነባለሁ ብለሽ ነው ቃል የገባሽለት፣አርሱ እንዳለሽ ሁሉ መጽሐፉን ለማንበብ ፍርሃት አለብሽ ማለት ነው?!
- ጆርጅ እንዴት እንዴት ነው ምትናገረው?! ምንም የማይጨምር ምንም የማይቀንስ መጽሐፍ ነው!
- ልክ ነሽ . . ታዲያ ለምን አታነቢውም? ምን ችግር አለው?
- ማንበብ ትፈልጋለች ያለህ ማነው?
- በማስረጃ አቀራረብና ከካቶሊካዊነት በመከላከል ረገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ደካማ ሆነሽ ነው ያገኘሁሽ፤ለመጀመሪያ ጊዜም በቀላል ንግግር ስትፍረከረኪ ማየቴ ነው::
- መጽሐፉን አላነበውም::
- መጽሐፉን እንደምትፈሪው ለራስሽ እያረጋገጥሽ ነው ማለት ነው::
- እንግዲያውስ አነበዋለሁ::
- ካትሪና ምን ነካሽ? የምን ደካማነት ነው?!
- እኔ እንጃ፣ከቄሱ ጋር ከተገናኘንበት ጊዜ አንስቶ ውስጤ የተረጋጋ አይደለም፤እውነትም መጽሐፉን ማንበብ ፈርቼ ሳልሆን አልቀረሁም::
- አልፈራሽም፣ጠንካራ ነሽ፣አንቺ እርግጠኛ በመሆን ረገድ ለኔ ምሳሌ ነሽ:: በጣም ትንሽ መጽሐፍ ነውና አሁኑኑ እንድታነቢ ነው የምጠይቅሽ፤ከትናንት ጀምሮ ስላላየሁ ኢሜይሌን አያለሁ::

ካትሪና ቁጭ ብላ መጽሐፉን ማንበብ ስትጀምር ጆርጅ በዓይኖቹ ካትሪናን እና በንባቡ ላይ ያላትን ተመስጦ እየተከታተለ ኢሜይሉን ከፈተ . . መልእክትና የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ልኮላቸው ከነበሩት ሰዎች አስተያየታቸውን የሰጡባቸውን ምላሾች አገኘ . . ጠቅለል አድርጎ በማሳጠር እንደገና ለሁሉም ላከላቸው::

ቶም ፦ ለበራድ ጭካኔ መነሻው ይህ ነው ማለትህ ነው?! ጥሩ አገላለጽ ይመስላል::

ሌቪ ፦ በዚህ አረመኔያዊ ጭካኔ ላይ ያለኝን አቋም የምታውቀው ቢሆንም ሁላችሁም ግን ታምኑበታላችሁ፤ብሉይ ኪዳንን የሚተች ሁሉንም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ይተቻል::

ሐቢብ ፦ ሙሉ በሙሉ እስማማበታለሁ፤ይሁን እንጂ የማልወዳቸውም ቢሆን ሙስሊሞች ግን በኦሪት ላይ ባላቸው እምነት ከሌሎች ይለያሉ::

አደም ፦ አደገኛ የሆነ አነጋገር ነው፤እንዲህ ያለው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ ሊሆን እንዴት ይችላል?

ቀጣዩን መልእክት ጻፈላቸው ፦

- ‹‹ዛሬ ሃሳብ የምትሰጡት በጥቅስ ላይ ሳይሆን በእሳቤ ላይ ነው ፦

በክርስትና ውስጥ ያለው የሥላሴ እምነት በእግዚአብሔር ሌላን ማሻረክ ነው፣ሊረዱት የሚያስቸግር ጽንሰ ሀሳብ ነው፤እግዚአብሔር አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ኢየሱስ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛው ነው:: አጠር ያለ ምላሽና ሀሳባችሁን እጠብቃለሁ::

ጆርጅ››

ጆርጅ ኮምፒውተሩ ላይ የሚሰራውን አበቃ . . በጥልቅ ተመስጦ መጽሐፉን ማንበብ ወደ ቀጠለችው ካትሪና ፊቱን አዞረ . .

- ጨረስሽ?
- አልጨረስኩም፣ትንሽ ጠብቀኝ::
- በአንዳንድ ርእሶች ላይ ካንቺ ጋር ሀሳብ መለዋወጥ ስለምፈልግ መጽሐፉን ለነገ አቆይው::
- ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፣ጨርሻለሁ::
- በመጽሐፉ በጣም የተመሰጥሽ ትመስያለሽ !
- መልካም ፈቃድህ ሆኖ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ::
- እንግዲያውስ እኔ እተኛለሁ::

ካትሪና መጽሐፉን አንብባ ጨረሰችውና አልጋው ላይ እንደተንጋለለ ወደ ጆርጅ ቀረብ አለች . .

- ይቅርታ ወደማገባደዱ አካባቢ ስለነበርኩ ልጨርሰው ብዬ ነው::
- አሳማኝ መጽሐፍ ይመስላል !
- በተወሰነ ደረጃ፣ማለፊያ ትረካ ነው::
- የነገው ሥራችንን ፊር ለማስያዝ ፈልጌ ነበር::
- ነገ ቅዳሜ ነው፤ቄሱ ነገ በቅዳሴ ሥርዓቱ ላይ እንድንገይ ጥሪ አድርጎልን

የለም?

-አዎ ጠርቶናል፣ግን እንሄዳለን?

-አዎ እንሄዳለን፣ከሁሉም በላይ ቅዱስ በሆነ ቤተክርስቲያን የሚደረገውን ቅዳሴ እንተዋለን?

-እህህ፣እናም ለኢየሱስ ያለሽ ፍቅር ወደ ቤተክርስቲያን እንጂ ወደ እስላም አልመራሽም ማለት ነው::

-መጽሐፉ በከፍተኛ ደረጃ አሳማኝ ቢሆንም ነገ ግን በቤተክርስቲን ተገኝቼ እጸልያለሁ::

-ልጆቹን የትነው የምናቆያቸው?

-ከኛ ጋር ወደ ቅዳሴው እንወስዳቸዋለን::

-ቄሶቹን አትፈሪላቸውም?

-አልገባኝም::

-ልጆቼን ወደ ቅዳሴው ልወስዳቸው አልችልም፣ቀሳውስቱን እፈራላቸዋለሁ::

-ምናቸውን ነው የምትፈራው?

-በተደጋጋሚ ብሉይና አዲስ ኪዳንን በማንበባቸው ምክንያት የቀሳውስቱን አረመኔያዊ የጭካኔ ድርጊት እፈራላቸዋለሁ::

-ዛሬ የምትናገረው ሁሉ እንቆቅልሽ ሆኖብኛል፣ማለት የፈለከውን ልታብራራልኝ ትችላለህ?

-ስለ አብያተ ክርስቲያናት ወሲባዊ ቅሌቶች አላነበብሽም? በታዳጊ ሕጻናት ቤተክርስቲያን ላይ ስለቀረቡት ክሶች አላነበብሽም? ሕጻናቱን አስገድደው ከደፈሩ ቀሳውስት መካከል ከአንደኛው ጋር የተደረገውን ቃለ መጠይቅ ሁሌም አልረሳም:: ቀሳውስትና መነኮሳቱ አውሬዎች እንጂ ሰዎች ናቸው ብሎ ማመን ያስቸግራል፤እናም ማይክልና ሳሊ እንዲህ ላለው ነገር እንዲጋለጡ አልፈልግም::

-ጆርጅ ምን ነካህ? እኔ በየሳምንቱ ከአንድ ጊዜ በላይ ወደ ቤተክርስቲን እሄዳለሁ፣እንዲህ ያለ ነገር ደርሶብኝ አያውቅም፣ይህ ሁሉ መረበሽ ለምን?

-ከዚህ በፊት በቤተክርስቲያን ስለሚፈጸሙ ወሲባዊ ቅሌቶች ተወያይተሽ ወይም አንብበሽ ታውቂያለሽ?

-አላውቅም::

-እንግዲያውስ ወደ ዩቲዩብ ግቢና በዚህ ላይ የተዘጋጁ ቪዲዮዎችን ተመልከቺና ነገ ልጆቹን ወደ ቅዳሴው መውሰድ አለብን ብለሽ ከጸናሽ እንወስዳቸዋለን::

-ላንተ ብዬ ቪዲዮዎቹን አሁን እመለከታቸዋለሁ፣ነገ ግን ሁላችንም ወደ ቤተክርስትያን ቅዳሴ እንሄዳለን . . ከኔ ጋርም የተገናኘነው ሙስሊም የሚጠቀመውን አነጋገር ስልት መጠቀም ጀምረሃል ማለት ነው!

-እህህ፣አነጋገሩ ተጽእኖ እንዳሳደረብሽ ሁሉ ቪዲዎቹም ተጽእኖ ያሳድሩብሻል፤የኔ ፍቅር ደህና እደሪ::

-ፍቅሬ አንተም ደህና እደር::

-በረዥሙ ተቃቀፉ፣ጆርጅ ሲያንቀላፋ የቤተክርስቲያን ወሲባዊ ቅሌቶችን የሚመለከቱ ፊልሞችንና ጽሁፎችን ስትከታተል ቆየች፤ከዚያ ወሲባዊ ወዳልሆኑ የቤተክርስቲያን ቅሌቶች ተሸጋገረች፣ሳይታወቃት ረዥም ጊዜ አሳለፈች . . እንደገና ‹‹ለኢየሱስ ያለኝ ጥልቅ ፍቅር ወደ እስላም መራኝ›› ወደሚለው መጽሐፍ ተመለሰችና አንዱን የመጽሐፉን አንቀጽ በድጋሜ አነበበችው፤ይህን አንቀጽ ለምን እንደ መረጠች ግን አታውቅም ፦

‹‹የቤዛነትና የስቅለት እምነት አእምሮንና ሎጂክን የሚጻረር ከመሆኑም ባሻገር፣መልካም ሥራን እርግፍ አድርጎ ለመተው፣ ኃጢአትና እንደ ግድያ፣ስርቆት፣አስገድዶ መድፈር፣ዝሙት ያሉና የመሳሰሉ እኩይ ተግባራትን ለመፈጸም በሩን ወለል አድርጎ የሚከፍት እምነት ነው:: ኢየሱስ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) ሊያሟሏቸው የመጡትንና ያስተማሯቸውን የሕግን፣የትእዛዛትንና የመልካም ሥራዎችን አስፈላጊነት ጳውሎስ አጣጥሏል:: በሮሜ ሰዎች መልእክቱ (3:28) እንዲህ ብሏል ፦ ‹‹ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና::›› አብርሃም (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) በሥራው አልጸደቁም (4:2):: ጳውሎስ መዳን የሚገኘው በኢየሱስ መሰቀል በማመን ብቻ ነው የሚል ይዞ መጣ:: የሰው ልጅ ጳውሎስን አምኖ ከተከተለው ፍጻሜው ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይከብዳል:: ለጳውሎስ መልስ ከሚሆኑት መካከል ኢየሱስ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) የተናገሩትና ማቴዎስ 5:19 ውስጥ የሰፈረው አንዱ ነው ፦ ‹‹እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤የሚያደርግ ግን ሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል::››

አንቀጹን ደጋግማ አነበበች . . ምሽቱ ወደ ንጋት መቃረቡ ትዝ ሲላት መጽሐፉን ከጎኗ እንደተከፈተ አስቀምጣ አልጋው ላይ ተዘረጋች፤ ወደ ሀሳብ ዓለም እንደገባች እንቅልፍ ይዟት ጭልጥ አለ::

www.path-2-happiness.com

ጆርጅ አማልዶ ከእንቅልፉ ሲነቃ ካትሪና አላወቀችም፡፡ ተነስቶ ገላውን ታጠበና ልብሱን ቀየረ . . ልቀሰቅሳት ወደ ካትሪና ቀረብ ሲል ማታ ስታነበው የነበረውን መጽሐፍ ባቆመችበት ገጽ እንደተከፈተ በአቅራቢያዋ አገኘው . . አነበበውና መጽሐፉን እንደ ተከፈተ በነበረበት ሁኔታ ደፍቶ አስቀመጠው፡፡

ወደ ልጆቹ ክፍል ሄዶ ተነስተው እንዲዘጋጁ ቀሰሳቸው፡፡ በመቀጠል ወደ ካትሪና ተመልሶ ቀሰቀሳት . . ለቁርስ ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ሲያመሩ ጆርጅ ወደ ካቲሪና ዞረና . .

- የዛሬ ጉብኝታችን ወዴት ነው?
- ከቦታዎች ሁሉ እጅግ ውብና እጅግ ምርጥ ወደ ሆነው ቦታ ነው፡፡
- ማማ ዛሬ ወዴት ነው የምንሄደው? ባባን ስጠይቅ የምንሄድበትን የምትመርጭው አንቺ ነሽ ብሏል፡፡
- ከአፍታ በኋላ ከአባታችሁ ጋር አስደሳች ነገር እንነግራችኋለን፡፡

ካትሪና ከጆርጅ ጋር ትንሽ ለመነጋገር ስለፈለገች ልጆቹ ቀድመው ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት እንዲሄዱ ጠየቀቻቸው . .

- ዛሬ ወዴትነው የምንሄደው?
- የቤተክርስቲያን ወሲባዊ ቅሌቶችን የሚመለከቱን አየሽ? አነበብሻቸው?
- ሁሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመሆኔ ጋር ያየሁትና ያነበብኩት ነገር ማሰብ ከምችለው በላይ ነው የሆነብኝ፡፡ ይህ እውነት ከሆነ እነዚህ ሰዎች ሳይሆኑ አራዊት ናቸው፡፡
- ይህ የሚሆነው እምነትን ከመልካም ሥራ በሚነጥሉ የጳውሎስ ትምህርቶች ምክንያት ነው፣ክርስትና የቤዛነትንና የመድህንን እምነት የፈጠረው ለዚህ ነው ብለሽ ታምኚያለሽ?
- መጽሐፉን አንብበሃል እንዴ?
- ተከፍቶ የነበረውን ገጽ ብቻ እንጂ አላነበብኩም፤ባነበው ችግሩ ምንድን ነው?
- ችግር የለውም . . ስለገረመኝ ብቻ ነው፡፡ ብታነበው ጥሩ ነበር፡፡ እኔ አልፈራሁም፤ምናልባት ያነበብከው አንቀጽ በተለይ ለኔ ችግር ሊፈጥርብኝ ይችል ይሆናል፣ለሁሉም ወደፊት እንነጋገርበታለን፡፡ ዋናው ነገር ዛሬ ወዴት ነው የምንሄደው? ምን አሰብሽ?
- በቤተክርስቲያኑ ቅዳሴ ላይ የግድ መገኘት ይኖርብናል፡፡
- ችግር የለውም፣ግና መጀመሪያ ወደ ቪላ ዶሪያ ባምቢሌ መናፈሻ ከሄድን በኋ ነው፤ከሮም መናፈሻዎች ትልቁ ብቻ ሳይሆን በውበትም ከዋነኞቹ

አንዱ ነው፡፡
- ከቅዳሴው እንዳንዘገይ እሰጋለሁ፡፡
- እህህ፣መነኮሲቷ አንዘገይም፡፡
- እንግዲያውስ ተስማምተናል፡፡

(4)

ቪላ ዶሪያ ባምቢሌ መናፈሻ ወደ ዘጠኝ ካሬ ኪሎ ሜትር በሚጠጋ ቦታ ላይ የተንጣለለ . . ውብና እጅግ የሚያስደስት ሰፊ አረንጓዴ ትእይንት ያለው . . ማይክልና ሳሊ አይተው የረኩባቸው ብዙ ዓይነት አእዋፍ ያሉበት ማራኪ መነፈሻ ነው . .

- ማማ ምርጫሽ እጹብ ድንቅ ነው፤የዛሬው ቀን ከቀናት ሁሉ ድንቅ ቀን ነው፡፡
- ቦታው በጣም ውብና እጅግ ማራኪ ነው፣ሳሊ አስደስቶሻል?
- አዎ በጣም ነው ያስደሰተኝ፡፡
- የጉብኝታችን ውበት ዛሬ ለቅዳሴ ወደ ቤተክርስቲያኑ ስንሄድ ደግሞ ይበልጥ የተሟላ ይሆናል፡፡

ማይክል ተነጫነጨና ፦

- እኔ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ አልፈልግም፡፡

ጆርጅ ትከሻውን ነቅንቆ ወደ ካትሪና አየና . .

- ይህ የእናትህ ምርጫ ስለሆነ እርሷን ጠይቃት፡፡
- ከመደበኛው የቱሪስት ጉብኝት በኋላ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ጉብኝት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡
- ማማ ይቅርታ፣እኔ ቤተክርስቲያን አልወድም !
- የፈጠረህን፣የመገበህንና የባረከህን አምላክህን ማምለክና ማመስገን አትወድም?
- አምላኬን ማምለክ እወዳለሁ፣ግን ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ሳይኖርብኝ ነው፡፡
- አንድ ሰው አምላኩን በማምለክና በማመስገን ወደርሱ ፊቱን ካልመለሰ ዓለም ትጠበዋለች፡፡
- አንቺ ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ቆርጠሻል?

ጆርጅ ክርክሩን ማለዘብ ወደደ . .

- ፈጣሪህን ባታመልከውና ባታመሰግነው መታደልን አታገኝም፤አምልኮ

www.path-2-happiness.com

ወደ ቤተክርስቲያን ከመሄድ ጋር የተሳሰረ ነው የሚል ግምት የለኝም፡፡

-የዚህን ውብ መነፈሻ ጉብኝት ከጨረስን በኋላ እንሄዳለን፣ጎብኝተህ ተዝናናበት፣የኔ ቆንጆ የፈጣሪህን አምልኮና ምስጋናውን ከመተው ግን ተጠንቀቅ፡፡

-ማማ አመሰግናለሁ፤ባባ አመሰግናለሁ፤ነገር ግን አምልኮ ከቤተክርስቲያን ጋር ብቻ የተሳሰረው ለምንድነው?!

ካትሪና ክርክሩን መቋጨት ፈለገች . .

-ሳሊ ነይማ ያችን እዚያ ዛፍ ላይ ያለችውን ወፍ አየሻት? . . ኑ ወደዚያ እንሂድ . .

ማይክልና ሳሊ ወፍዋን ተከትለው ሮጡ . .

-የማይክል አነጋገር በጣም ጥሩ ነው፡፡

-አዎ፣ግን ሕጻናቱ ለማይወዱት ነገር እኔን ምክንያት ለምን ታደርጋለህ?

-ወደ ቅዳሴው መሄድ ያንቺ ጥያቄ አይደለም?!

-አንተ ንጹሁ ፈላስፋ ንግግራችን አላበቃም ወደፊት ይቀጥላል፡፡

ቤተሰቡ የጧቱን ጊዜ በመናፈሻው ውስጥ አሳልፈው ምሳቸውንም እዚያው በሉ . . ካበቁ በኋላ ካትሪና ወደ ልጆቿ ዞር አለችና ፦

-አሁን ወደ ቅዳሴው እንሄዳለን፤በተመስጦ እንድትጸልዩና ራሳችሁን እንድትጠብቁ ይሁን፡፡

-ከምንድነው ራሳችንን የምንጠብቀው?

-ከሚያውካችሁ ወይም ከሚያስቸግራችሁ ማንኛውም ነገር ወይም ማንኛውም ሰው፡፡

-ምንን ከመሳሰለው?

-ከሚያውካችሁ ወይም ከሚያስቸግራችሁ ማንኛውም ነገር፤ማይክልና ሳሊ ያልኩት ግልጽ ነው?!

-ግልጽ ነው፣ ለምን እንደዚህ እንዳልሽን ግን አላውቅም?! ወደ ቤተክርስቲያን ነው ወይስ አጥቂ አራዊት ወዳሉበት መናፈሻ ነው የምንሄደው?!

ወደ ቤተክርስቲያኑ እንደተቃረቡ ካትሪና ወደ ጆርጅ ዘንበል ብላ በጆሮው አንሾካሾከች . .

-ተጠራጣሪ እንድሆን አደርገሀኛል፣ለማይክል ጥንቃቄ አድርግ እኔ ለሳሊ እጠነቀቃለሁ፡፡

-እስከዚህ ደረጃም አይደለም፤በጣም የተወሰወስሽ ትመስያለሽ . . ለማንኛውም እሺ አደርጋለሁ፡፡

ሁሉም ወደ ቤተክርስቲያኑ ገቡ፤አስፈሪው ቅዳሴ ተጀምሯል . . ጆርጅ ግን ግድ አልነበረውም፤ካትሪና በቅዳሴው ልቧ የተነካ ቢሆንም ጭንቀትና ደስተኛ ያለመሆን ስሜት ከፊቷ ይነበባል . .

እንደወጡ ማይክል በእናቱ ተንጠለጠለና . .

-ማማ አመሰግናለሁ፣ድንቅ የሆነ ቅዳሴ ነበር፤ኢየሱስን በጣም እወዳለሁ!

-ለኛ ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ልጅ ከኃጢአት መዳን ምክንያቱ እርሱ ነው፡፡

በሕጻን ንጽሕናና የዋህነት ሳሊ ጠየቀች . .

-ማማ . . ቸሩ አምላክ እኛን ከኃጢአቶቻችን ለማዳን ኢየሱስን ከመግደል ውጭ ሌላ መንገድ አልነበረውም እንዴ? በጣም ስለምወደው የኢየሱስ ወልድ ሞት በጣም ያሳቅቀኛል፤በርሱ ምክንያት በየዓመቱ የገና ስጦታዎች ይመጡልኛል፡፡

ማይክል አከለ . .

-ሳሊ እኔም እንዳንቺ ነኝ . . ምናልባት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ የማልወደው በዚህ ወይም ቀሳውስትና መነኮሳቱን ስለማልወዳቸው ሊሆን ይችላል፡፡

-ለኢየሱስ ያለህ ፍቅርህ ነው የሚያድንህና ነጻ የሚያወጣህ፡፡

-ማይክል መልካም መሥራትን አትርሳ፤ኢየሱስ ባስተማረን መሰረት ማመን ብቻ በቂ አይደለምና፡፡

የቅዳሴ ሥርዓቱ ካበቃ በኋላ ቤተሰቡ ወደ ሆቴሉ ተመለሰ፤ልጆቹ ወደ ክፍላቸው አመሩ . . በዚህ ጊዜ ጆርጅ መሰሪ ፈገግታ እያሳየ ለካትሪና እንዲህ አለ ፦

-ቤተክርስቲያን ውስጥ ውጥረት ይታይብሽ ነበር፡፡

-አንተ ደግሞ ግድ የለሽነት በግልጽ ይስተዋልብህ ነበር፡፡

-ልክ ነሽ፣አሳማኝ ሆኖ ባልታየኝ ነገር ግድ እንዲኖረኝ እንዴት ትጠብቂያለሽ? ዋናው ነገር የመልስ ጉዟችን ተነገወዲያ ነው፤ቀሪውን የጉብኝት ጊዜ ባለፈው እንዳደረግነው ሁሉ አስደሳች ሆኖ ማሳለፍ ይኖርብናል፡፡

-እኔ በጣም ደክሞኛል፤ትናንት በጣም ዘግይቼ ነበር የተኛሁት፤እናም አሁን እተኛለሁ፡፡

-እኔም ኢሜይሌን አይቼ እተኛለሁ፡፡ ሙስሊሙ ሰውየ የሰጠሽን መጽሐፍ ልትሰጭኝ ትችያለሽ?

-ልታነበው ነው?!

www.path-2-happiness.com

-ምናልባት፣ባነበው ምን ችግር አለው?
-ምንም፣እንካ . . ደህና እደር።

ጆርጅ ኮምፒውተሩን ከፍቶ ለላከላቸው መልእክት ባልደረቦቹ የላኩትን ምላሽ ለማየት ወደ ኢሜይሉ ገባ ፦

ሐቢብ ፦ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቼን የአምላክን ሦስትነት ከአንድነቱ ጋር (ሥላሴን) ለማስረዳት ብዙ ደክሜ ሳይሰካልኝ ቀርቷል፤ምናልባት እኔ ራሴ ስላልተረዳሁት ሊሆን ይችላል። የጠቀስከው በአጠቃላይ በጣም ጥንታዊ በሆኑ ወንጌሎች ውስጥ ይገኛል።

ቶም ፦ ማቴማቲክስ 3 ≠ 1 ይለናል። የሎጂክ ምሁራን ‹‹ያንድ ነገር ተከፋይ ክፍል በብያኔው የዋነኛው ክፍል ተከታይ ነው›› ይላሉ። አባቴ ‹‹ያልገባህን ነገር አትናገር›› ይል ነበር። እኔ ደግሞ ‹‹መልስ እንድሰጥህ ልረዳው የምችለውን ነገር ብቻ ንገረኝ›› ባይ ነኝ፣እህህ።

አደም ፦ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንጂ የእግዚአብሔር ሸሪክ ወይም ልጅ አይደለም ብንል ይህ ፈጽሞ የኢየሱስን ክብር ማሳነስ ማለት አይደለም።

ሌቪ ፦ ይህ እኛ ዘንድ በአይሁዳዊነት ውስጥ ‹‹ዕዝራ የእግዚአብሔር ልጅ ነው›› እንደሚባለው ዓይነት ነው። ሁለቱም መረዳት የማይቻል አነጋገር ነው የሚል እምነት አለኝ።

የተሰጡትን ሀሳቦች ስሞችን ሳይጠቅስ መልሶ ለሁሉም ላከላቸው። ከዚያም የሚከተለውን መልእክት ጻፈ ፦

-‹‹ሦስተኛው ዙር ፦ አዲስ ኪዳንን ያዛበውና የበረዘው ጳውሎስ ሊሆን ይችላል?
ጆርጅ››

-ቀሪዎቹን መልእክቶች በማየት ላይ እያለ የሚከተለውን ከካኽ የተላከ መልእክት አገኘ ፦

‹‹ውድ ወዳጄ ጆርጅ . . በመልካም ጤንነት ላይ እንደምትሆን ተስፋዬ የጸና ነው። ሁሉም ሠራተኞች እየጠበቁህ ነው፤በቅርቡ እንደምንገናኝ ተስፋችን ነው።››

ካኽ››

* ማስታወሻ እስካሁን ድረስ ከአንድ ሳምንት በላይ ከሥራ ቀርተሃል።››

ኮምፒውተሩን ለመዝጋት ሲያስብ የአደም የፌስቡክ ገጽ ትዝ አለው፤ሳይጎበኘው ረዥም ጊዜ ሆኖታል፤ወደ ገጹ ሄደና ስለሱ የተጻፈ አዲስ

መጣጥፍ አገኘ ፦ ‹‹መታደልን በመፈለግ ላይ ከተሰማራው ወዳጄ የሚቀሰሙ ትምህርቶች 3›› ፦

‹‹መታደልን በመፈለግ ላይ የተሰማራው ወዳጄን በዚህ ሰሞን እንግዳ የሆነ የጤና ችግር ገጥሞታል። ከርሱ የተማርኩትን ከማውሳቴ በፊት በሕመሙ ወቅት በተከሰተው ነገር ላይ ጥቂት ነጥቦችን ላስፍር ፦

1. በሽታ እንደ ተለመደው ድካም ማስከተሉ የታወቀ ነው፣ወዳጄንም ይኸው አጋጥሞታል። የመታደል መንገድ ፍለጋውን ከፍጻሜ አያደርስም የሚል ስጋት አድሮብኝ ነበር፤እርግጠኝነቱና ቁርጠኝነቱ ግን ስጋቱን በሰላም እንዲያልፍ አድርጎታል። በመሆኑም አስተዋይ ሰው ወሳኝ ትላልቅ ውሳኔዎችን በድክመት ሁኔታ ውስጥ በሚያልፍበት ወቅት መወሰን አይገባውም።
2. በአንድ ወቅት ላይ ድክመቱን ሳስተውል ሂደቱ ተራምጄ የመታደል መንገድ ይኸኛው ነው ብዬ ልነግረው ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር . . ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አተርፎኛል።
3. መጪው ወቅት ለወዳጄ ከሁሉም ይበልጥ በጣም አስቸጋሪው ወቅት እንደሚሆንበት እርግጠኛ ሆኛለሁ፣ውጤቱን ተከታታዬ አሳውቃችሁ ይሆናል።

ወደ ትምህርቱ ስንመለስ ወዳጄ የመታደልን መንገድ ፈልጎ ለማወቅ አሁንም ጽናትና ቁርጠኝነቱን እንደሰነቀ ነው። የሚከተሉትን ትምህርቶች ከርሱ መገብየት ችያለሁ ፦

1. በዙሪያህ የሚገኙ ሰዎች ወይ ተጽእኖ ታሳድርባቸዋለህ ወይ ባንተ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፣ወይም ደግሞ ትታገላቸዋለህ። ይህን የሚወስነው የእሳቤና የእምነት ትግሉ ነው። በወዳጄ ዙሪያ የሚገኙ ሰዎቹ ብዙዎቹ በርሱ ተጽእኖ ስር መዋል ጀምረዋል። ይህም የጽናቱንና የቁርጠኝነቱን ብርታት የሚያመለክት ነው። በጥቅሉ ሲታይ አሁን ካንድ በላይ የሆኑ በመታደል መንገድ ፍለጋ ላይ የተሰማሩ ሰዎች እንዳሉ ነው የምገምተው። ማን ያውቃል በቅርቡ ሁሉም የመታደልን መንገድ ለማወቅ መቻላቸውን ላበስራችሁ እችል ይሆናል።
2. በመታደል መንገድ ፍለጋ ጉዞ ላይ ለሁሉም አመለካከቶች ሚዛናዊ መሆንና ከስሜታዊነት መራቅ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፤አንዳንድ ጊዜ በጫናዎች ውስጥ ሲሆን የሚያጣው ቢሆንም ወዳጄ ይህን ሚዛናዊነት ታጥቋል።

www.path-2-happiness.com

3. የመማር አስፈላጊነት፤የምታውቀው ምናልባት ትክክል ላይሆን ስለሚችል፣ አውቃለሁ ብለህ የምታስበውን እንኳ ቢሆን መማር አስፈላጊ ነው። በወዳጄ ላይ አድናቆቴን የሳበው ከልጅነቱ ጀምሮ ያደገባቸውን ነገሮች እንኳ በክፍት አእምሮ ለመማር የሚያሳየው ቁርጠኝነት ነው።
4. የሚያሳዝነው ወዳጄ ሁነቶችን ንባቦቹንና ውይይቶችን እርስበርስ የማስተሳሰርና የማቀናጀት ችሎታው ውስን መሆኑ ነው። ይህ የተለያዩ እሳቤዎችንና አመለካከቶችን አነጻጽሮ የማየት ብቃት ወደ መታደል መንገድ ለመድረስ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

ወዳጄ የመታደልን መንገድ ለማወቅና ለታላላቆቹ የሕይወት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት በሚያደርገው ፍለጋ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል የሚል እምነት አለኝ። ለማንኛውም ቀጣዩን ትምህርት በቅርቡ ይዤላችሁ እመለሳለሁ።

አደም››

ጆርጅ ከፌስቡክ አንባቢዎች የተሰጡትን አስተየቶች አነበበ፤ያንደኛው አስተያት ትኩረቱን ሳበው ፦ ‹‹ወዳጅህን በጣም የምትወደው ትመስላለህ፤ለዚህ ነው አርአያ አድርገህ የምታቀርበው።›› የአደም መልስ እንዲህ የሚል ነበር ፦ ‹‹አዎ ለሰዎች ሁሉ በጎውን እንደምመኝ ለርሱም እመኝለታለሁ፤እግዚአብሕር ለሰው በጎውን እንድንወድላቸው ያዘናል።››

በመቀጠል ስለ አመለካከት ለውጥና ሽግግር በአደም የተጻፈ ሌላ መጣጥፍ አነበበ። የሚከተለው ነበር ፦

‹‹አንድን እሳቤና አመለካከት ትቶ ወደ ሌላ መሸጋገር አስቸጋሪ ነገር ቢሆንም ዛሬ ያጋጠመኝ ግን እንግዳ የሆነ ተሞክሮ ነው። ዛሬ በጣም ብልህና ብሩህ አእምሮ ያለው ፈላስፋ ከሆነ የስነ ልቦና ሐኪም ጋር ተገናኘሁ። ይሁን እንጂ በተለያዩ እምነቶችና እሳቤዎች መካከል ሲዘዋወርና ካንዱ ወደ ሌላው ሲሸጋገር ነው የኖረው። ክርስቲያን ነበር ወደ ኤቲስትነት ተለወጠ፤በስነምግባሩ የወረደ ኢአማኝ ሆነ። ቡድሂዝምን፣ሂንዱይዝምን፣አይሁዳዊነትንና ክርስትናንም አጥንቷል። አሁን እስላምን ለማጥናት ይፈልጋል። ሁለት ችግሮች ያሉበት ሲሆን አንደኛው ፦ ፍልስፍናን በሁሉም ነገር ላይ ፈራጅና መለኪያ አድርጎ ይወስዳል፤ፈራጅና መመዘኛው ዕውቀት እንጂ ያንተ ዘመናዊ የፍልስፍና መርህ አይደለም ስለው በአነጋገሬ እንደገና እንደሚያስብበት ቃል ቢገባም አምኖ መቀበል ግን አልቻለም። ሁለተኛ ችግሩ ፦ እያንዳንዱን ሃይማኖት የሚመለከተው ከኤቲስትነቱና ስለአጠናቸው ሃይማኖቶች የመዛባትና

የመምታታት ሁኔታ ያለው ጥልቅ ዕውቀቱ ካሳደረበት የሁሉም ሃይማኖቶች ጥላቻው መጥፎ ስሜት በመነሳት መሆኑ ነው። ከርሱ ጋር በሚኖረኝ ግንኙነት ምን ትመክሩኛላችሁ?

አደም››

የተባለው ሐኪም ቶም መሆኑን ጆርጅ አውቋል። የቶምን የፌስቡክ ገጽ ሲከፍት ግን ምንም አዲስ ነገር አላገኘም፤ይልቁንም ከአምስት ቀናት ወዲህ ቶም ገጹን ከፍቶ አያውቅም፣ይህ ደግሞ ልማዱ አልነበረም . . ኮምፒውተሩን ዘጋና መጽሐፉን አነሳ። እንቅልፍ ስለመጣበት ቶሎ ቶሎ አየት አየት አደረገ። አንደኛው ገጽ ላይ ዓኑይ ያረፈበት ጽሑፍ ትኩረቱን ሳበውና በተመስጦ አነበበው። ጽሑፉ የተለመደ ዓይነት ቢሆንም አርሱን ለምን እንዳስደነገጠው ግን አላወቀም። በአምልኮ፣መድህን በማግኘትና በሕይወት መካከል ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ሁኔታ ንጥጥሎሽ ባለበት ክርስትና ውስጥ እንዲህ ያለውን የማያውቀው በመሆኑ ይሆን? ወይስ ተናጋሪው ክርስቲያን በመሆኑ ብቻ ይሆን?

‹‹አሜሪካዊው ጸሐፊ ማይክል ኸርት በመጽሐፉ የታላላቆች ዝርዝር ውስጥ በቁጥር አንድ ላይ ካስቀመጣቸው በኋላ እንዲህ ይላል፦ መሐመድ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) በታሪክ ውስጥ በሁለቱም በሃይማኖታዊውና በዓለማዊውም መስኮች ጎልተው የወጡና በላቀ ደረጃ ስኬታማ የሆኑ ብቸኛው ሰው ነበሩ . . ይህ በዓይነቱ ልዩና አቻ የማይገኝለት ውህደትና ጥምረት ሙሐመድን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ከማንም በላይ ኃያል ተጽእኖ የሚፈጥር ታላቁ ሰብእና እንዲሆኖ ያስችላቸዋል።››

ጆርጅ በጀርባው ተኝቶ ለህሳብ ዓለም እጁን ሰጠ፤ራሱን ያወቀው ጧት ካትሪና እንዲህ ስትለው ብቻ ነበር ፦

- ተነስ ንቃ፣እህህ፣ይህ ሁሉ በመጽሐፉ ጦስ ነው።
- ኦህ . . የፈራሽልኝ ትመስያለሽ፣አይዞሽ ተረጋጊ መጽሐፉን ገና አላነበብኩትም።
- እህህ፣ ይህ ሁሉ መጽሐፉን ሳታነበው ከሆነ አንብበህ ቢሆን ኖሮ ምን ትሆን ነበር! በል ንቃ።

www.path-2-happiness.com

(5)

-በሉ ፈጠን በሉ . . ዛሬ ሮም ውስጥ የመጨረሻ ቀናችን ነውና በተቻለ መተን ብዙ ቦታዎችን መጎብኘት አለብን::

በሁነቶች የተሞላ ግሩም ቀን ነበር . . ቤተሰቡ መናፈሽዎችንና መዝናኛ ስፍራዎችን ጎብኝተዋል:: በሰው ሰራሽ ሐይቅ ላይ በጀልባ ተጉዘዋል . . ጉብኝታቸውን ያገባደዱት ወደ ገበያ ማዕከል በመሄድ ነበር . . ከገበያው ሲወጡ ጆርጅ ካትሪናን ድንገት ነካ አደረጋትና መልእክት ያለው ፈገግታ አሳያት ፦

-መስቀል ሳትገዢ ቀረሽሳ ! ኢየሱስን መውደድ ተውሽ?

-እንዳውም ፍቅሬ ጨምሯል፣ፍቅር ግን ትእዛዛትን በመፈጸምና መልካም በመሥራት እንጂ በመስቀል ብቻ አይደለም::

-እኔም ከረዥም ጊዜ አንስቶ ስነግርሽ የቆየሁት ይህንኑ ነው:: ፍቅር በመስቀል፣በሥዕልና በቅርጻ ቅርጽ፣በመነኮሳትም ሆነ በቀሳውስት አይደለም::

-አንተ አክራሪ ፕሮቴስታንት አሁን ይህን ተወን::

-መጽሐፉን ገና ያላነበብኩት ቢሆንም ማን ያውቃል ለኢየሱስ ያለኝ ጥልቅ ፍቅር አሸባሪ ሙስሊም ያደርገኝ ይሆናል::

-አሸባሪ ለመሆንም ሆነ ላም የሚያመልክ ህንዱ ለመሆን ብቁ ትመስለኛለህ::

-እህህ::

አመሻሹ ላይ ቤተሰቡ ቴቭራ ወንዝ ዳርቻ ወደሚገኝ ዝነኛ ሬስቶራንት አመሩ . . ማራኪውን የከተማይቱን ገጽታ እየተመለከቱ አስደሳችና አነቃቂ በሆነ አየር ውስጥ እራታቸውን በሉ . .

-ስለ ሃማኖት ስታወሩ ብዙ ጊዜ እሰማችኋለሁ፣ሃይማኖት ለሰው አስፈላጊ ነገር ነው?

-አዎ ማይክል፣ ያለ ጥርጥር አስፈላጊ ነው::

-አንድ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ግን ፦ ቀዳሚው መሰረት ኤቲዝም ነው፣እኛን የፈጠረን ተፈጥሮ ነው፤ሃይማኖታዊ እሳቤና ስለ ሃይማኖት ማሰብም ያረጀ ያፈጀ አፈተረት ነው፣ይላል::

-ያንተ ሀሳብስ?

-በሃይማኖት ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ነገሮች አፈተረት ናቸው ብዬ አስባለሁ::

-ሃይማኖት ራሱ አፈተረት በመሆንና በአንዳንድ ሃይማኖቶች ውስጥ አፈተረት በመኖር መካከል ልዩነት አለ::

-ጓደኛዬ እንደሚለው ግን በሃይማኖት ውስጥ ያሉት አፈተረታዊ ጉዳዮች ብዙ ናቸው::

-ማሙሽዬ ምን የመሳሰሉ ናቸው?!

-የትምህርት ቤት መምህሬ ብዙ ጊዜ ቢያብራራውም፣የሥላሴን እምነት ምንነት፣የኢየሱስን ቤዛነትም . . መረዳት አልቻልኩም::

-ምናልባት ዕድሜህ ትንሽ ስለሆነ ይሆናል፣ትልቅ በምትሆንበት ጊዜ ትረዳቸዋለህ::

-የነገርኩሽ ጓደኛዬ፣‹‹የምትጠይቀው ሰው ሁሉ አንተ ገና ትንሽ ልጅ ነህ ይለሃል፣ግን እመነኝ ሁሉም ለራሳቸው አይረዱትም›› ነበር ያለኝ፤አንቺ እነዚህን ነገሮች ትረጂያለሽ?!

-አዎ፣በተወሰነ ደረጃ::

-ባባ አንተሳ?

-እህህ፣አይገባኝም፣በተወሰነ ደረጃ አልረዳም::

-ነገሩ አስቸጋሪ እንደሆነ ነው የሚሰማኝ፤አምላክ እንድንረዳው እኛን ማድከም ይፈልጋል እንዴ?

ካትሪና ተቆጣች . .

-ኡፍ፣አንተ ደግሞ እንደ አባትህ ነገሮችን ታካብዳለህ፤ማሙሽዬ ነገሩ ከዚህ በጣም የቀለለ ነው::

ጆርጅ በቁርጠኝነት መንፈስ አከለ . .

-ግሩም ነው ማይክል፣እግዚአብሔር የሰው ልጅ አእምሮ መረዳት የሚሳነውን ነገር አያስተላልፍም:: እንደዚህ መስሎ የታየህ ነገር ካለ ለመረዳት የበለጠ መማር ያስፈልገሃል ማለት ነው:: ከዚህ ውጭ ነገሮች ወደማይታወቁ ሚስጥሮች ይለወጣሉ የሚለውን አትቀበል::

-እናም ባባ አንተ ከኤቲስቱ ጓደኛዬ ጋር ትስማማለህ ማለት ነው?

-ፈጽሞ አልስማማም፤ኤቲዝም ከአእምሮ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጋጭ

www.path-2-happiness.com

አፈተረት ነው፡፡

-ባባ አልገባኝም፡፡

-ዓለም በአጋጣሚ የተፈጠረ፣ሰዎችም በአጋጣሚ የተፈጠሩ እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ?!

-ባባ ኤቲስቶች እንደዚያ አይሉም፤አንዳንዶቹ በባዮሎጂ ትምህርት ስለተማርነው የዳርዊን ንድፈ ሀሳብ በሳይንሳዊ መንገድ ያወራሉ፡፡

-ልክ ነው፣የዳርዊን ንድፈ ሀሳብ ጊዜ ያለፈበት ንድፈ ሀሳብ ነው፤በአሁኑ ዘመን ግን ስህተተኛነቱ በሳይንስና በምክንያትም ተረጋግጧል፡፡

-እንዴት?

-የሳይንስ መምህርህን መጠየቅ ትችላለህ፤ከኔ በተሻለ ሁኔታ ዝርዝሩን ያውቃል፤ወይም ይህንን በዝርዝር የሚያስረዳ መጽሐፍ ልገዛልህ እችላለሁ፡፡ መመርኮዝ ያለብን ሳይንሳዊ መስለው ቢታዩ እንኳ በአፈተረቶች ላይ ሳይሆን በሳይንስና በዕውቀት ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡

-ችግሩ ግን ሃይማኖት ከሳይንስ ጋር የሚጋጭ መሆኑ ነው፡፡

-ሊሆን አይችልም፤አንደኛው ከሌላው ፈጽሞ መብቃቃት አይችልም፡፡

-እንዴት?

-ይህን በአይንስታይን አባባል ላጠቃልልህ እችላለሁ፦ ‹‹ሳይንስ ያለ ሃይማኖት አንካሳ ነው፤ሃይማኖምት ያለ ሳይንስ እውር ነው›› ይላል፡፡

-ኤቲስቶች ዕውቀታቸው አንካሳ ነው ማለትህ ነው?!

-እንዳውም ማይምነታቸው ከዕውቀታቸው የበዛ ነው፡፡ ሃይማኖት ያለ ሳይንስ ወደ አፈተረትና ወደ ምስጢሮች ሊለወጥ ስለሚችል የእውር መደናበር ነው . .

ማይክል ዝም ሲል ጆርጅ ከልጁ ዕድሜ በላይ የገዘፉ የሚመስሉትን እነዚህን ጥያቄዎች ሲያሰላስል ቆየ . . የአእምሮውን ብሩህነት የሚያመለክት ይሆን ወይስ የጥርጣሬ በሽታ ትንሹ ሥዕል?

ቤተሰቡ ወደ ሆቴሉ ሲመለስ ጃኖልካ እንግዳ መቀበያ ውስጥ እየጠበቃቸው ነበር፤ገና ሲያያቸው ተነስቶ ሰላምታ አቀረበላቸው . .

-ድንገተኛ ጉብኝት፣እንኳን ደህና መጣህ፡፡

-የቄሱ ወዳጅ እንደምነህ፣ቅዳሴው ላይ አላየንህም!

-ቅዳሴ ላይ መገኘት ከተውኩ ዓመት ሊሆነኝ ነው፡፡

-ታዲያ የቄሱን ወዳጅነት እንዴት መጠበቅ ትችላለህ?!

-ጥያቄዎችህን መመለስ ቢያቅተውም ቄሱ አንተ ዘንድ በጣም የተባረከ ሰው ይመስላል፤የሆነውን ነገር ከርሱ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

ጆርጅ በአንክሮ ፦

-ትዋሸኝ ነበር?

-በፍጹም፣ለማረጋገጥ ብዬ ነው፤የዚያ ቀን አድራጎቱ ለኔ በጣም እንግዳ ነገር ነበር፤ነገሩ አንተ እንዳልከው ነው፤ቄሱ ካትሪናን ብቻ ማስወጣት አልፈለገም ነበር፡፡

ካትሪና በመገረም አፈጠጠች . .

-በተለይ እኔን ለምን?!

-ሰውየው አንቺ አንዱ ተጠቃሚ የሆንሽውንና ለተራው ሕዝብ በይፋ የበሚናገረውና በዝግ በር ከምሁራን ጋር በሚናገረው መካከል ልዩነት ያደርጋል ብየሽ ለም? . . ለማንኛውም አላራዝምባችሁም፤ነገ ነው መሰለኝ የምትሄዱት?

-አዎ ነገ ነው፡፡

-ልሰናበታችሁ ነው የመጣሁት፤ግንኙነታችን እንዲቀጥል እሻለሁ፣ከናንተ ጋር በመገናኘቴ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡

-እኛም እንዲሁ ደስተኞች ነን . . እናመሰግናለን፡፡

-ትንሽ ጥያቄ አለኝ፣መጽሐፉን ልትሰጭኝ ትችያለሽ? ወዳጄን ጠይቄው የቀረው የመጨረሻ ኮፒ ላንቺ የሰጠው መሆኑን ነገረኝ፡፡

-መጽሐፉ እስከዚህ ድረስ አንተ ዘንድ አስፈላጊነት አለው ማለት ነው?!

-የዚያ ቀን ውይይታችሁ ስለ እስላም ከተራ ነገር ወይም ከዜና ዘገባዎች ባለፈ ውሃ የሚቋጥር ምንም ዕውቀት እንደሌለኝ አረጋግጦልኛል፡፡ ስለሆነም ይህን ሃይማኖት ለማወቅ ወስኛለሁ፤የመጽሐፉ ርእስም ስለሳበኝ ማንበብ ፈለግሁ፡፡

-ከልጆቹ ጋር ወደ ክፍላችን ልውጣና መጽሐፉን ይዤልህ እመለሳለሁ . . ማይክል፣ሳሊ በሉ ኑ፡፡

ጆርጅ ሳቅ እያለ . .

-እህህ፣እናም እስላምን ለማጥናት ወስንሃል ማለት ነው?

-አዎ ወስኛለሁ።

-ሙስሊም ትሆናለህ?

-ለምሳሌ እንደ ቀድሞው የሊብያ መሪ እንደ ቀዛፊ ይሆናል ብለህ ትጠብቀኛለህ? . . እኔ ያለ ምንም ልዩነት ሁሉንም አመለካከቶች አጠናለሁ። በዚያ ቀን ስለ እስላም ምንም አለማወቄን መገንዘብ ችያለሁ። በእስላም ላይ ብዙ ግርፍ መረጃዎች ቢኖሩኝም ሁሉም አስተማማኝ አይደሉም።

-እኔ ገና ስለ እስላም አላነበብኩም . . በሚቀጥለው ዙር እሱን አጠናለሁ። እያዘንኩ መጽሐፉንም አላነበብኩትም፣ለማንበብ ፍላጎት ነበረኝ።

-መጽሐፉ ለናንተ ይሁን፣ጥያቄዬን አነሳለሁ።

ካትሪና መጸሐፉን ይዛ መጣችና ለጃኖልካ ሰጠችው። መጻፊያውን አውጥቶ አንዳንድ መረጃዎችን ከመጽሐፉ ገልብጦ ከወሰደ በኋላ አመሰግኖ መጽሐፉን መልሶ ሰጣት . .

-መጽሐፉን አትፈልገውም እንዴ?

-መጽሐፉ የሚገኝበትን የኢንተርኔት ድረ ገጽ አድራሻ ወስጃለሁ፤ይህ በቂ ነው፣አመሰግናለሁ ደህና ሁኑ።

ጆርጅና ካትሪና ወደ ክፍላቸው ሄዱ . . ጆርጅ የወዳጆቹን ምላሽ ሲጠባበቅ ስለነበር ኮምፒውተሩን ከፈተ። ‹‹ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስን በተለይም አዲስ ኪዳንን በርዞታል፣አዛብቶታል ትላላችሁ?›› የሚል ትያቄ ልኮላቸው ነበር። ያልተጠበቀው አስገራሚ ጉዳይ ሁሉም መልሶች የመዛባትና የመምታታት አደጋ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ መከሰቱን በሙሉ ድምጽ የተስማሙበት መሆኑ ነው። የመበረዝና የማዛባት ድርጊቱ የተፈጸመበትን መንገድ በተመለከተ ግን ልዩነት አላቸው . . ሁሉንም ምላሾች እንደገና ጽፎ ለሁሉም ላከላቸው . .

ሐቢብ ፦ እያዘንኩ ከታሪክ አኳያ በትክክል ተከስቷል።

ቶም ፦ መዛባቱ፣መከለሱና መምታታቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ማን እንደፈጸመው ማወቅ ለኔ ቁምነገር የለውም።

አደም ፦ ፈንጂ ያዘለ ጥያቄ ነው። ማን እንዳዛበውና እንደ ለዋወጠው አላውቅም።

ሌቪ ፦ ታዲያ ብሉይ ኪዳንን ያዛባውና ያምታታው ማን ይሆን?! ምናልባት

ችግሩ የተከሰተው በገልባጮችና በጽሑፍ መዝግቦ የማጠናቀሩ ሥራ በጣም በመዝግየቱ እንጂ ሆን ተብሎ ለማዛባት ዓላማ ላይሆን ይችላል።

-የሚከተለውን ጻፈላቸው ፦

‹‹አራተኛው ዙር ፦ በግልጸኝነት ለመናገር እስላምን ለማወቅ እውነተኛ ፍላጎት አላችሁ? ከሆነስ ለምን?

መልካም ፈቃዳችሁ ሆኖ አጭር መልስ ነው የምፈልገው . . ነገ ምሽት ለንደን እገባለሁ።

ጆርጅ - ሮም››

-ለሁሉም ባልደረቦቹ ላከላቸው። በዚህ ዙር ካትሪናን እና ጃኖልካን በዝርዝሩ ውስጥ አካቷል . . ኢሜይሉን ማንበብ ቀጥሎ ከቶም የተላከለትን መልእክት አገኘ ፦

‹‹ይድረስ ለሁሉም ወዳጆቼ፣የፌስቡክ ገጼ የተሰረቀብኝ መሆኑን እሳውቃችኋለሁ፤እንዲመለስልኝ ከፌስቡክ አመራር ጋር በመደራደር ላይ ነኝ። በገጹ ላይ ሊታይ ለሚችል እኩይ የሆነ ማንኛውም ነገር አስቀድሜ ይቅርታ እየጠየቅሁ እኔን የማይወክል መሆኑን እገልጻለሁ።

ቶም››

ጆርጅ የቶምን ፌስቡክ ገጽ ሲከፍት ቶም ከበርካታ ሴቶች ጋር ኢሞራላዊ በሆነ አሳፋሪ ሁኔታ የሚታይባቸው ፎቶዎች ተለጥፈው አገኘ። በቶምና በበራድ መካከል ጦርነቱ ተጀመረ ማለት ነው? ሲል ራሱን ጠየቀ። አደም ስለ ሐኪሙ የአመለካከትና እሳቤ ሽግግርና ካንዱ ወደሌላው መረማመድ የጻፈው መጣጥፍ ወዲያው ትዝ አለውና አደም እውነቱን ነው ቶም ዝቅጠት ውስጥ ነበር አለ። ጆርጅ ፎቶዎቹን መመልከት ቀጠለ፣ከሴቶቹ ፎቶዎች መካከል ካትሪናን እየፈለገ መሆኑ ከአፍታ በኋላ ታሰበውና ይህ ለርሱም ሆነ ለርሷ ተገቢ ያልሆነ ጥርጣሬ እንደሆነ ተገነዘበ። ኮምፒውተሩን ዘግቶ አልጋው ላይ በጀርባዋ ወደተኛችው ካትሪና ሄደና ሳማት፤በእንቅልፍ ልቧ መልሳ ሳመችው፤ዓይኖቿን ከፍታ ፈገግ አለች . .

-እወደሃለሁ።

-እኔም እወድሻለሁ . . ወደኔ ቀረብ በይ።

www.path-2-happiness.com

ቀጣዩ ቀን በፍጥነት ነጎደ . . ወደ አይሮፕላን ማረፊያ ለመንቀሳቀስ የቀራቸው የተወሰኑ ሰዓታት ብቻ ናቸው . . ወደ ገበያ ሄዱና ካትሪና ስለ አደም ስጦታ ጆርጅን አስታወሰችው:: ከፍተኛ ጥራት ያለውና ዋጋው በጣም ርካሽ የሆነ የቆዳ ቦርሳ . . በግብይታቸው መሀል በአንዳንድ ምርቶቹ ላይ የማጣሪያ ሽያጭ በማካሄድ ላይ የሚገኝ ውድ የቆዳ ምርቶች መሸጫ ሱቅ በድንገት አጋጠማቸው:: ያንዳንድ ምርቶቹ የቅናሽ ዋጋ እስከ 80 በመቶ የሚደርስ ነበርና ጥራት ያለው የቆዳ ቦርሳ በርካሽ ዋጋ ለአደም ተገዛ . . በአስገራሚው የአደም ጥያቄና ፍላጎቱን እውን ለማድረግ ባስቻላቸው ያልተጠበቀ አጋጣሚ እየሳቁ ሱቁን ለቀው ወጡ::

ከገበያው ማእከል አቅራቢያ በሚገኝ ሬስቶራንት ምሳቸውን በሉና ሻንጣዎቻቸውን ለመውሰድ ወደ ሆቴሉ ተመለሱ . . ከዚያ ወደ አይሮፕላን ማረፊያው አመሩ::

ጭንብሉ ሲወልቅ

www.path-2-happiness.com

13 ጭንብሉ ሲወልቅ

ጭንብሉ ሲወልቅ

(1)

ጆርጅ ከሮም ጉዞው መልስ የበለጠ መነቃቃትና እፎይታ ተሰምቶታል። ብዙ ጭንቀትና ጫናዎች የተቃለሉለት ሆኖ የተሰማው ከመሆኑ የተነሳ የነበረበት ውጥረት በሥራ ብዛትና አብዛኛውን ጊዜውን ይወስድበት በነበረው ንባብ ምክንያት ይሆን? ወይስ ከወንጌልና ከአምላክ ጋር ብቻ ሳይሆን ከክርስትና እና ከሁሉም ፈለጎቹ ጋር በጥቅሉ በተያያዙ አሉታዊ እሳቤዎችና ግራ በመጋባት ምክንያት ይሆን? ብሎ ራሱን ጠየቀ። አልያም አሁን የተሰማው እፎይታ መጫወቻ አሻንጉሊቱን ሰብሮ ከሚደሰት ሕጻን ደስታ ያላለፈ ይሆን? ቤተክርስቲያን፣ ጳጳሳዊ ሥርዓቱና ወንጌሉ በውስጡ ከተንኮታኮቱ በኋላ ሌላ አዲስ መጫወቻ ከየት ያገኝ ይሆን?! ወይስ ለመንፈሱ ለሕይወቱና ለደስታው ምንም ትርጉም ያጣ ኤቲስት ሆኖ ይቀመጥ? ከዚያም ኦ አምላኬ ! ኦ አምላኬ ! ኦ አምላኬ ! ብሎ ጮኸ . .

ካትሪና እንኳ ሳትቀር ጉዞውን ወዳለች፤የተለየ መንፈስ ይዛ ነው የተመለሰችው . . ደስታዋ በባሏና በልጆቿ ደስታ በመደሰቷ ይሆን? ወይስ አጥልቃው የነበረውን ጭንብል በማውለቋ ሕይወትን ከተለየ አቅጣጫ መመልከት መጀመሯ ያሳደረባት ደስታ ይሆን? የቄሱን ግራ መጋባትና ደካማነቱን ስታውቅ የደረሰባትን ከባድ ድንጋጤ፣በግብጻዊው ሰውየና በሰጣት መጽሐፍ ፊት ተሸናፊ መሆኗን፣ጃኖልካንና ማስረጃዎቹን መሞገት የተሳናት መሆኑን . . ታስታውሳለች። መለስ ትልና ‹‹ግን እኮ ከአስፈሪ ጥርጣሬ የሚሻለውን እርግጠኝነት እውስጤ ይዣለሁ›› ትላለች። እንደገና ራሷን ‹‹ከበፊቱ ይበልጥ አሁን ለምን ደስተኝነት ይሰማኛል?!›› ስትል ትጠይቃለች።

ቤት ደርሰው እቃዎቻቸውን ካደራጁና ራሳቸውም ከተረጋጉ በኋላ፣የባልደረቦቹ ምላሾች መድረስ አለመድረሳቸውን ለማየት ጆርጅ ኢሜይሉን ከፈተ። የሁሉንም ምላሾች አገኘና ኮፒ አድርጎ ባለፈው ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ ለሁሉም መልሶ ላከላቸው።

ሌቪ ፦ አባቴን የገደሉ ሙስሊሞችን የምጣላቸው ቢሆንም እስላምን አጠናለሁ፤የማጠናው ግን የተሸከሙትን ክፋት ለማወቅና እንዴት ከዚያ መዳን እንደሚቻል ለመረዳት ስል ነው።

ሐቢብ ፦ አዎ መለኮታዊ ሃይማኖት ነውና አጠነዋለሁ፤ስለሱ ያለን መረጃ

www.path-2-happiness.com

ግን በጣም አናሳ ነው::

ቶም ፦ አዎ፣ሌላው ዘንድ ያላገኘሁትን ምናልባት እርሱ ዘንድ ላገኝ ስለምችል አጠናዋለሁ ነው::

አደም ፦ በእርግጠኝነት አዎ፤መርሃችንና ሚዘናዊነታችን ሁሉንም መለኮታዊ ሃይማኖቶች እንድንመረምር ያስገድዱናል::

ሐጃኖልካ ፦ አዎ እመረምረዋለሁ፣እኔ ሁሉንም ነገር መማርና ማወቅ ደስ ይለኛል::

ወደ ሮም ከሄዱበት ጊዜ አንስቶ ኢሜይሏን ከፍታ ስለማታውቅ ከመልሶቹ መካከል የካትሪናን አላገኘም . . አምስተኛውን ዙር ጻፈና ለሁሉም ላከ . .

‹‹አምስተኛው ዙር ፦ ምክንያታችሁ የተለያየ ቢሆንም የሁላችሁም መልስ ‹‹አዎ›› መሆኑ አስገራሚ ሆኖብኛል:: በመሆኑም የዛሬው ጥያቄ ፦ እያንዳንዱ ሰው በሦስቱ መለኮታዊ ሃይማኖቶች መጻሕፍት (ብሉይ ኪዳን፣አዲስ ኪዳንና ቁርኣን) መካከል ንጽጽሮሽ ያድርግ የሚል ነው::

ጆርጅ - ለንደን››

መልእክቱን ልኮ የተወሰኑ ደቂቃዎች ካለፉ በኋላ ስልኩ አቃጨለ፣ደዋዩ ቶም ነበር፤ድምጹ ውጥረትና ጭንቀት ውስጥ መኖሩን ያሳብቅበት ነበር . .

- ሰላም ነው አይደለም?
- ሰላም ነው መግባታችሁን ለማወቅ ፈልጌ ነው፤ላገኝህ እፈልጋለሁና መቼ መገናኘት እንችላለን?
- ገና ከ45 ደቂቃ በፊት ነው ቤት የደረስነው፣አሁን በጣም ስለመሸ ነገ ጧት ይመቸሃል? ካልሆነም አሁን መምጣት ትችላለህ::
- አዝናለሁ ጊዜው እንዲህ መምሸቱን ልብ አላልኩም ነበር፣ ይቅርታ:: ነገ ጧት አራት ሰዓት ላይ እቤት እመጣለሁ::
- እጠብቀሃለሁ፣አይዞህ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም ነገር በጎ ይሆናል::
- ጆርጅ አመሰግናለሁ፤ደግሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ::
- የቶም ጥሪ ያሳሰበው ጆርጅ የቶም የፌስቡክ ሂሳብ መሰረቁና ከበራድ ጋር ችግር ውስጥ መኖሩ ወዲያውኑ ትዝ አለውና ኮምፒውተሩን እንደገና ከፍቶ ወደ ቶም ፌስቡከክ ገጽ ሄደ:: ያጋጠመው ግን ያልጠበቀው ነበር . . ካትሪና በአስነዋሪ አለባበስ ከቶም ጋር ሆና የምትታይባቸውን ፎቶዎች ተለጥፈው አየ! አስተውሎ መመልከት ሞከረ፣በፎቶግራፎቹ ላይ ንጽሕናና የዋህነትን የተላበሰው የካትሪና ፊት በግልጽ ተለይቶ ይታያል:: ፎቶዎቹ የሮም ጉዞ ደስታውንና እፎይታውን የሚያስረሳው ከባድ ድንጋጤ

አሳደሩበት:: ለራሱ እንዲህ አለ ፦

- የዋህነትንና ንጽሕናን ጨምሮ ሁሉም ነገር ማታለልና ማጭበርበር ነው ማለት ነው !
- ለቶም መልሶ መደወል አሰበ፣ግን ምን እንደሚሆን ለማየት እስከ ነገ አራት ሰዓት መታገስን መረጠ . . ለመተኛት ሞከረ ግን አልቻለም:: ካትሪናን ከቶም ጋር ባየበት ሁኔታ ማየትን ማሰቡ አስጨንቆታል፤ትእይንቱን ከአእምሮው ፈጽሞ ማራቅ አልቻለም:: ቶምና ካትሪና ተስማምተው ስለ ንጽሕናቸው የዋሹትን ውሸት እንዴት አምኖ እንደ ተቀበለ ገርሞታል:: ሕይወት ገደል ትግባ . . ሰዎች ውሸታቸውን አሉ የሚሏቸው መልካም የስነ ምግባር እሴቶችም ገደል ይግቡ . . ጊዜውስ ምነው አልነቃነቅ አለ ! ጊዜ ራሱም ማጭበርበርና ማስመሰል አሳምሮ ያውቅበታል፣በሁለቱም ሁኔታ አንድ ቢሆንም ራሱን አንዴ ረዥም አድርጎ ሲያቀርብ ሌላ ጊዜ ደግሞ አጭር ሆኖ ይታያል::
- ካትሪና ጧት ሦስት ሰዓት ላይ ነቃች፤ጆርጅ ግን ያንቀላፋ መስሎ አደባ . . ወደርሱ ቀረብ ብላ ሳመችውና በጆሮው አንሾካሾከች ፦
- ውዴ የቤት አስቤዛ ለመግዛት መሄዴ ነው፤ለቤት የሚያስፈልጉን ነገሮችን ለመሸመት መሄዴ ነው ፍቀድልኝ::

ካትሪና ወጥታ እንደ ሄደች ጆርጅ ከመኝታው ተነስቶ ልክ አራት ሰዓት ላይ የደረሰውን ቶምን ጨፍገግ ባለ ፊት ተቀበለው . .

- ስለ ረበሽኩህ አዝናለሁ፣ነገሩ በጣም ቀላል ነው፣ግን በጣም አሳሳቢ ነው::
- በል ንገረኝ::
- ከበራድ ጋር ያለው ጦርነት በአስከፊ ሁኔታ ተጀምሯል::
- አልጠበቅክም ነበር?
- ጠብቄአለሁ፣ግና ቆሻሻ ጦርነት ነው::
- ከበራድ ከዚህ የተለየ ነገር ትጠብቅ ኖሯል?
- አልጠበቅኩም፣ፍቀድልኝና ልጨርስ:: ከአደንዛዥ እጽ አዘዋዋሪ ማፍያ ቡድናቸው ጋር ተባባሪ ሆኜ እንድሰራ አለበለዚያ ለውርደት እንደሚያጋልጠኝ አስጠንቅቆኝ አልተባበርም አልኩት:: ደጋግሞ ቢያስጠነቅቀኝም እምቢ አልኩት:: ከጥቂት ቀናት በፊት የፌስቡክ ሂሳቤን ለመክፈት ስሞክር አልከፈት አለኝ፣የቴክኒክ ችግር ይሆናል ብዩ ሳስብ ባልተጠበቀ ሁኔታ የፌስ ቡክ ገጼ ኢሞራላዊ በሆኑ የቀድሞ ፎቶዎቼ ተሞልቶ አገኘሁት::
- ይህ መቶ በመቶ ይሆናል ተብሎ የተጠበቀ ነው፣አይደለም እንዴ?

www.path-2-happiness.com

-እባክህን አስጨርሰኝ፣ፎቶዎቼን መለጠፍ ከጀመረ በኋላም እንድተባበረው ደጋግሞ ጠየቀኝ፣እኔም እምቢታዬን ደጋግሜ ነገርኩት:: በዚህ ጊዜ ነው ከበፊቱ ይበልጥ አስቀያሚ የሆነ ሥራ መስራት የጀመረው:: እውነት ያልሆኑ ፎቶዎችን በቴክኒካዊ ዘዴ እያቀነባበረና ቆርጦ እይገጣጠመ ገጼ ላይ መለጠፉን ተያያዘው::

-እናም ከኔ ምንድነው የምትፈልገው . . ?

-ምን እንደምልህ አላውቅም፤ቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነን ካትሪና ራቆቷን ሆና ከአጠገቤ የምትታይበትን ፎቶ አቀነባብሮ አስቀምጧል::

-በፌስቡክ ገጽህ ላይ ያሉት የክህደት ፎቶዎችህ እውነተኛ አይደሉም ማለት ነው የምትፈልገው?

-በእርግጥ እውነተኛ አይደሉም::

-የምትላት ሴት እኮ ባለቤቴ ነች፣ፎቶግራፎቹ የራሷ ስለመሆናቸው እርግጠኛ ነኝ::

-ልክ ነህ የራሷ ፎቶዎች ናቸው፣ግን በቴክኒክ የተቀነባበሩ እንጂ እውነተኛ አይደሉም::

-ቶም ይበቃል . . በኔ መሾፉ ይብቃህ !

-ፎቶዎቹን አስተውለህ መርምራቸው፣ከተለያየ ቦታ ተወስደው የተቀጣጠሉና በእጅ የተቀነባበሩ መሆናቸውን በግልጽ ማየት ትችላለህ::

-ከቤቴ ውጣልኝ . . ውጣልኝ !

-ጆርጅ እኔን በድለህ ካትሪናንም አትበድላት::

-ውጣ . . በቃ ውጣ::

ጆርጅ የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት በሳሎኑ ሶፋ ላይ ተዘረገፈ፣በከፍተኛ ስሜታዊ ሁኔታ ውስጥ ነበር . . ስልኩ ሲጮህ ቁጥሩን ተመለከተ፣አደም ነበር:: ሁሉም በኔ ላይ ድራማ እየተወኑ መሰለኝ፣በትወናው ውስጥ እኔ ብቻ ነኝ ሞኝ ተላላው . . ይህ ደግሞ አሁን ምን ይፈልግ ይሆን?! ብሎ አጉረመረመ::

-ሃሎ አደም !

-ሃሎ ጆርጅ ናፈቅከን እኮ::

-ምን ፈለግህ?

-ምንም፣እንዲሁ ሰላም ልበል ብዬ ነው::

-አመሰግናለሁ፣ደህና ሁን::

ከደቂቃዎች በኋላ ለምትመጣው ካትሪና ምን እንደሚላት

እያሰበ መነጋገሪያውን አስቀመጠ:: ውርደት ተሰምቶታል፤የክህደት ውርደት፣የማሞኘትና ድክመትን የመጠቀም ውርደት . . ካትሪና ፈገግ እያለች ስትመጣ ሲያይ ትንሽ ለመረጋጋት ሞከረ . .

-እንደ ሮሙ ሆቴል ዝግጁ የሆነ ቁርስ እዚህ የለም፤ቁርስ በልተሃል ወይስ የሆነ ነገር ላዘጋጅልህ?

-ምንም አልፈልግም::

-እንግዲያውስ አንድ ፍንጃን ወተት ወይም ሻይ ትጠጣለህ::

-አመሰግናለሁ::

-ትንሽ ነገርም ቢሆን ተጋራኝ::

-ምንም አልፈልግም አልኩሽ እኮ አይገባሽም?

-ጆርጅ ምን ተፈጠረ?

-ካትሪና ጭምብሉ ነው የተገለጠው፣ጭንብሉ ወልቋል::

-የትኛው ጭንብል?

የቶምን የፌስቡክ ገጽ ከፍቶ ከፊቷ አኖረ . . እየተራገመና እያጉረመረመ ወደ መኝታ ክፍሉ አመራ . .

-አንቺ አጥባቂ ሃይማኖተኛዋ፣ተመልከቺው፤አንቺ ትንሽቱ አውሬ እይውማ! ብትመነኩሽ ኖሮ እንደ ቤተክርስቲያን ቀሳውስትና መነኮሳት ሁሉ ትልቅ አውሬ በሆንሽ ነበር፤ተመልከቺ . .

ካትሪና ፎቶዎቹን ተመለከተች፤እያለቀሰች ጆርጅን ተከትላ ሄደች . .

-ቶም ውሸታም ባለጌ ሰው ነው፤ይህ በፍጹም እኔ አይደለም::

-አንቺ የተዋጣልሽ ተዋናይ አሁንም ድራማውን መቀጠል ነው የምትፈልጊው? ነገም አብራችሁ ልትተኙ . .

-እመነኝ እኔ ይህን ምስራ ሰው አይደለሁም፣ይህ የቶም ተራ ብልግና እና የርሱ ውሸት ነው:: ብዙ ጊዜ ስነ ምግባር የጎደለው ኤቲስት ሰው ነው ስትለኝ አልነበረም?

-ለሕክምና ወደርሱ እንድሄድ በተለይ የጎተጎትሽኝ አንቺ አልነበርሽም? ሃይማኖት ያስተማርሽውስ አንቺ አይደለሽም? ተለውጧል የምትይውስ አንቺ አይደለሽም? !

-እኔን ትጠረጥረኛለህ ብዬ ፈጽሞ አልጠበቅኩም ነበር . .

ካትሪና በለቅሶ ፈነዳች . . ከዚያ ራሷን ለማረጋጋት ሞከረችና ዳግም ወደ ኮምፒውተሩ ሄደች፤ቶምን እየተሳደበችና እተራገመች ፎቶዎቹን ትኩር ብላ በአስተውሎት አየቻቸው:: በዚህ ጊዜ ከተለያየ ቦታ ተወስዶ እንዲገጣጠም

www.path-2-happiness.com

የተደረገ መሆኑ በግልጽ በሚታይ አንድ ፎቶ ላይ ዓይኖቿ አረፉ:: በችኮላ ኮምፒውተሩን ይዛ ወደ ጆርጅ ሄደች . .

-ተመልከት፣ፎቶው ተቆርጦ የተቀነባበረና እውነተኛ አለመሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው:: አሁን እስኪ እንዴት ሆኖ ነው ይህ ራስ ከዚህ ደረት ጋር ሊጣጣም የሚችለው?!

-ይህ ልክ የቶም አነጋገር ነው፤‹‹ተቆርጦ የተለጣጠፈ ፎቶ›› የተውኔቱ አዲስ ምዕራፍ መሆኑ ነው?

-በደንብ አስተውለህ ተመልከተው::

-ምናልባት ሊሆን ይችላል፤ትወናችሁን ተቀብዬ በድጋሜ እንድታሞኙኝ ግን አልፈልግም !

-ቶም እርሱ ራሱ ገጹ ላይ ለጥፎ በውሸት የተቀነባበረ ፎቶ ነው እንዴት ማለት ይችላል?!

-ቶም ከአፍታ በፊት መጥቶ በራድ የፌስቡክ ሂሳቡን እንደ ሰረቀበትና እርሱን ለመበቀል ብሎ ፎቶዎቹን አቀነባብሮ የለጠፋቸውም ራሱ በራድ መሆኑን ነግሮኛል::

-በራድ ! ለምንድነው የሚበቀለው?

-የተውኔቱን ትረካ ለማሟላት ያህል፣አደንዛዥ እጽ ከነርሱ ጋር ተባብሮ ለመሸጥ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው::

-የምትናገረው ልገባኝ አልቻለም፤ለማንኛውም ግን ፎቶዎቹ ተቆራርጠው የተቀነባበሩ ብቻ ሳይሆኑ ውሸት መሆናቸው በግልጽ የሚስተዋል ስለመሆኑ ፍጹም እርግጠኛ ነኝ::

-በውሸት የተቀነባበሩ ሊሆኑ፣አውነትም ሊሆኑ ይችላሉ:: የፌስቡክ ሂሳቡ የተሰረቀበት መሆኑን የሚገልጽ መልእክት ቶም አልላከልሽም ነበር? ወይስ አሁንም የተውኔቱን ሌላ አዲስ ምዕራፍ መጀመራችን ይሆን?!

-ወደ ሮም ከተጓዝንበት ጊዜ ጀምሮ እኔ ኢሜይሌን ከፍቼ አላውቅም፤ኮምፒውተሩን ስጠኝና ከፍቼ ልረዳ::

ካትሪና ኢሜይሏን ስትከፍት ከቶም የተላኩ ሁለት መልእክቶችን አገኘች . . የመጀመሪያው ሂሳቡ መሰረቁን የሚገልጽ ሲሆን ሁለተኛው አስነዋሪ ፎቶ የያዘ ነበር:: በፌስቡክ ገጹ ላይ ያለው የቶም ፎቶ ራሱ ሆኖ ‹‹ይህ የንጽሕና እና የእውነተኝነት ማስረጃ ነው›› የሚል መግለጫ ከስሩ ተጽፎአል:: ፎቶውን አስተውላ ስትመለከት ከቶም ጎን ያለው ሰው እርሷ ሳትሆን ጆርጅ ነው . . !

-ይልቅስ አንተ ነህ ክህደት የምትፈጽምብኝ፤ናማ ፎቶውን ተመልከት::

-እኔ? ከማን ጋር ነው ክህደት የምፈጽምብሽ?!

-ከቶም ጋር፤ይኸ ፕሮቴስታንታዊ ግብረሰዶማዊነት አይደለም?!

ጆርጅ ፎቶዎቹን አስተውሎ ተመለከታቸው፤ተቆርጠው የተቀነባበሩ መሆናቸው በግልጽ የሚታይ ነበር . . ጆርጅ ለተወሰነ ጊዜ ራሱን አቀርቅሮ ቆየና ቀና ብሎ በተረበሸ ቅላጼ . .

-ቶምን ከቤት አባርሬው ነው የሄደው::

-ጆርጅ እኔን ትጠረጥረኛለህ?!

-ከቶም ጋር በመስማማት ትወናውን እያካሄደብኝ ነው ብዬ በማሰብ በአደም ላይም ስልክ ዘግቼበታለሁ !

-ጆርጅ ይህ ሁሉ ለምን?!

-በምናደድበት ጊዜ ወይም በድክመት ሁኔታ ላይ ሆኜ በአንድ ነገር ላይ እንዳልወስን አደም ከአንድ ጊዜ በላይ መክሮኛል:: አሁን ምን እንደማደርግ አላውቅም?! ካትሪና አጥፍቻለሁ ይቅርታ አድርጊልኝ::

-ከዚህ ሁሉ በኋላ ‹‹አጥፍቻለሁ ይቅርታ›› ብቻ ! !

-ምን እንዳደርግ ትፈልጊያለሽ?

-አላውቅም፣የይቅርታ ጥያቄው በጥፋቱ ልክ ነው የሚሆነው::

-ይቅር እንድትይኝ እማጸንሻለሁ፤ቶምና አደምን በተመለከተ ምን ማድረግ እንደምችል አስብበታለሁ::

-ካንተ ባማልጠብቀው ሁኔታ በጽኑ ያቆሰልከኝ ብትሆንም፣አሁን የተናገርከውን የአደም ምክር ከመተግበር ግዴታ ጋር ይቅር ብየሃለሁ::

-ካትሪና አመሰግናለሁ፣አንቺ ሁሌም ልብሽ የጠራ ሳፊ ነው:: እንዴት እንደማመሰግንሽና ያጠፋሁብሽን ትልቅ ጥፋት እንዴት እንደማስረሳሽ አላውቅም . . (ብሎ ተነስቶ አቀፋትና ቀጠለ) ፦ ከቶምና ከአደም ጋር ያለውን ነገር መፍትሔ ለመፈለግ ለአጭር ጊዜ ለብቻዬ እንድሆን ትፈቅጂልኛለሽ?

-ይሁንልህ፣ብቆስልም የጌታ ረድኤት ካንተ እንዳይለይ እጸልያለሁ::

ጆርጅ ኮምፒውተሩ አጠገብ ቁጭ አለ፤ኢሜይሉን ከፈተና የሚከተለውን መልእክት ጻፈ፦

‹‹ውድ ወዳጄ ቶም

በኔና በአንተ መካከል ሳናስበው በተፈጠረው ነገር ጥፋተኛ በመሆኔ ይቅርታ እጠይቀሃለሁ . . አንተ በበኩልህ ወደ ቤቴ መጥተህ ይቅርታ ጠይቀሃል፣ይቅር እንድልህም ጠብቀህ ነበር፤እናም በኔም ተመሳሳይ ነገር

www.path-2-happiness.com

አድርግ . . ከፈለግህ ወደ ክሊኒክህ እመጣና ብታባርረኝ ደስተኛ ነኝ . . ደጋግሜ ይቅርታ እንድታደርግልኝ እለምነሃለሁ።

ጆርጅ››

በመቀጠል ይቅርታ ለመጠየቅ በቀጥታ ለአደም ደወለ . .

- አደም፣ በጣም ምርጥና በጣም ርካሽ የሆነውን ቦርሳ አምጥቼልሃለሁ።
- አገኘህ? በዚህ መመዘኛ አግኝተህ አመጣህ?
- አዎ፣መቼ መጥተህ ትወስዳለህ?
- እህህ፣ዛሬ ባናገርከኝ ሁኔታ እንዳታናግረኝ ላንተ በሚመች ጊዜ።
- በተመቸህ ጊዜ አድርገው፤ቅድም ስትደውል በድክመትና በውጥረት ሁኔታ ውስጥ ስለነበርኩ ይቅርታ አድርግልኝ፣የሆነውን ነገር ሳገኝህ አጫውተሃለሁ።
- እንግዲያውስ እዚህ መጥተህ ሳትጎበኘኝ ረዝም ጊዜ በመሆኑ ወደ ካፌቴሪያው ብቅ በል።
- መልካም፣ዛሬ ወይም ነገ እጎበኘሃለሁ።

ጥሪውን ካበቃ በኋላ ቶም ምላሽ ጽፎለት ከሆነ ለማወቅ ወደ ኢሜይሉ ተመለሰ . . ቶም ለካትሪና ልኮት የነበረውን መልእክት ለርሱም ተልኮለት አገኘ፤በማንበብ ላይ እያለ ከቶም ምላሽ መጣለት . .

‹‹ይቅር እንድልህ ከፈለግህ አዳምጠህ ትእዛዞቼን ፈጽም ፦

1- ነገ ማታ አንድ ሰዓት ላይ ወደ ክሊኒኬ ትመጣለህ፣ከዚያ በኋላ አባርረሃለሁ አላባርርህም የሚለውን እኔ እወስናለሁ።

2- እንዲህ ያለውን ጋጠ ወጥ ድርጊት ዳግም ከመፈጸም ተቆጠብ።

3- ይህን እንዳነበብክ ለትእዛዞቹ ተገዢ መሆንህን የሚያረጋግጥ ቀጥተኛ መልእክት ጻፍ።

ዶክተር ቶም››

ምላሽ ጻፈለት . .

‹‹ውድ ወዳጄ ቶም ስመጣ ብታባርረኝ እንኳ ጥፋተኛ ስለሆንኩ ተስማምቻለሁ።

ጆርጅ››

መልሱን እንደ ላከለት ለቶም ስልክ ደወለ . .

- ሃሎ።
- ሃሎ፣በድጋሚ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤ተናድጄ ስለነበር ነው።
- ምንም አይደለም፤አንድ ሳልጠቅሰው የረሳሁትና ልትስማማበት የሚገባ

ግዴታ ግን አለ . .

- ምንድነው?
- እህህ . . ጆርጅ ቀልዴን ነው ሁሉም ነገር አልቋል፤ነገ በጣም አስፈላጊ የሆነ ቀጠሮ ይኖረናል።
- ቶም በጣም አመሰግናለሁ።
- ትቀርና ወየውልህ . . እህህ፣ተዘጋጅቼ እጠብቀሃለሁ።
- እንድታባርረኝ በቀጠሮው ከች እላለሁ . . አሁንም ደግሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

(2)

የስልክ ጥሪውን እንዳበቃ ከአደም ጋር ቀጠሮ እንዳለው አስታወሰ . .

- አሁን አደምን ለመጎብኘት ወደ ካፌቴሪያው እሄዳለሁ።
- አደም አስተዋይ ጥበበኛ ሰው ነው፤ጉዳዮች ባይኖሩኝ ኖሮ ካንተ ጋር በሄድኩ ነበር።
- ልክ ነሽ፣ከኔ በመወዳጀቱ ምን እንደሚጠቀም አላውቅም !
- ወዳጅነት ቁሳዊ መጠቃቀምን የማይሻ ራሱን የቻለ ትልቅ እሴት ነው።
- ለብቻው የሚኖር በመሆኑ አብረን ምሳ እንበላ ይሆናል፣ከኔ የሚያገኘው ነገር ካለ ምናልባት ይህች ብቻ ናት።

ጆርጅ ወደ ካፌቴሪያው ስደርስ አደም ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገለት። የሥራ ተራው ከግማሽ ሰዓት በኋላ እንደሚያበቃ ነግሮት እስከዚያ ድረስ ቡና እየጠጣ እንዲቆይ ነገረው። አደም ከሥራ ሲወጣ በቀጥታ ወደ ጆርጅ መጣና ምሳቸውን በሰዓዳ ሬስቶራንት ለመብላት ወስነው ሄዱ።

- ለደርሶ መልስ ጉዞና ምሳችን ለመብላት የአንድ ሰዓት ጊዜ አለንና የካቶሊኮች መናኸሪያና ማዕከላቸው እንዴት እንደነበረ አሁን ልታወጋኝ ትችላለህ?
- ብናገር አትቆጣም?
- ጆርጅ ስሜታዊ የሆንክ ትመስላለህ፣ምን ያስቆጣኛል?!
- ብሉይ ኪዳንን እውነት ነው ብዬ መቀበልም ሆነ በርሱ ማመን አልችልም፤በመሆኑም አይሁዳዊነት፣ካቶሊካዊነት፣ ፕሮቴስታንትነትም ሆነ እስላም ለኔ አመቺ አይደለም።
- አንደኛ - በብሉይ ኪዳን ላይ ይህን ሁሉ መጫንህ ለምንድነው? ለኛ በላክልን ጥቅሶች ምክንያት ነው?
- ይህ አንዱ ምክንያት ነው፤መጽሐፉ የተምታታና የተዛባ ስለ መሆኑ

www.path-2-happiness.com

ሌሎች መቶ ተመሳሳይ ምክንያቶች አሉኝ::

- አዲስ ኪዳንሳ?!
- ከብሉይ ሻል ያለ ቢሆንም ያው ተመሳሳይ ናቸው::
- ቁርኣንሳ?!
- በብሉይና አዲስ ኪዳንም የሚያምን እንደ መሆኑ እሱም እንደዚያው ነው::
- በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ችኩል እንዳትሆን ምኞቴ ነው::
- ከዚህ ሁሉ ጋር ለጥያቄዎቼ ምላሽ እንደማገኝ የሚሰማኝ እንጥፍጣፊ ስሜት አሁንም አለኝ::
- በእርግጠኝነት መልሱን ታገኘዋለህ::
- ችግሩ'ኮ አንዱም ሃይማኖት ትክክለኛ ሆኖ ካልተገኘ መፍትሔው ኤቲዝም ሊሆን ነው ማለት ነው !
- ኤቲዝም የመታደል መንገድና የሕይወት ጥያቄዎች ምላሽ ሆኖ አያውቅም፣ወደፊትም ሊሆን አይችልም::
- ታዲያ መንገዱ የቱ ነው?
- ፍለጋህን ቀጥልበት ታገኘዋለህ::
- እህህ፣ምናልባት እስላም ወይም የሽብር ሃይማኖቱ ይሆናላ !
- እስላምን ማጥናት እንፈልግ እንደሆነ በመጠየቅ መልእክት ስትልክልን የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ከመሆኑ ጋር የሁሉም መልስ ‹‹አዎ እንፈልጋለን›› የሚል ነበር፤አንተ ራስህ ግን እስላምን ማጥናት የማትፈልገው ለምንድነው?!
- እናንተ ከጠቀሳችኋቸው በሚበልጡ ብዙ ምክንያቶች፤ከሁላችሁም ይበልጥ እስላምን ለማጥናትና ለማወቅ የምጓጓው እኔ ነኝ:: እስላም ትክክለኛ ሆኖ ካልተገኘ ሌላ የትኛውም ሃይማኖት ትክክለኛ ሊሆን አለመቻሉ ብቻ በቂ ምክንያት ነው::
- የትኛውንም ሃይማኖት በዚህ መንገድ ማጥናት አይታየኝም !
- ወደ ሰዓዳ (መታደል) ሬስቶራንት ደርሰናል፣ወደ መታደል መንገድም ምነው በደረስን ! ለማንኛውም እንግባና ወጋችንን እንቀጥል::

የሚመች ጠረጴዛ መርጠው ሲቀመጡ አስተናጋጁ የምሳ ትእዛዛቸውን ተቀብሎ ሄደ . . አደም በቁርጠኝነት ስሜት ጆርጅን እያየ . .

- ከፈቀድክልኝ ስናገረው የነበረውን ልጨርስ፤ለሮም ጉዞ ስትዘጋጅና ስለ ክርስትና በጥልቀት ማንበብ ስትጀምር ምን ብየህ ነበር?
- ለሁሉም ሀሳቦች አእምሮህን ክፍት አድርገህ ያለ ምንም ቅድመ ውሳኔ

ነገሮችን መርምራቸው ነበር ያልከኝ::

- ዛሬም ያንኑ ደግሜ እለሃለሁ፤እስላምን ከዚህ ውጭ በሌላ መንገድ እንድታጠናው አልፈልግም::
- ገና አይሮፕላን ላይ እያለሁ ነው እስላምን ለማወቅ ማንበብ ስለሚገቡኝ መጻሕፍት ማሰብ የጀመርኩት::
- የኔን ምክር ትፈልጋለህ?! ከየትኛውም መጽሐፍ በፊት ቁርኣንን በማንበብ ጀምር::
- አይሁዳዊነትንና ክርስትናን ሳጠና ለምን በመጽሐፎቻቸው በብሉይና አዲስ ኪዳን አልጀመርኩም?
- አይሁዳዊነት ብሉይ ኪዳንን እንድታነብ የማይጠይቅህ ብቻ ሳይሆን ሆን ብሎ አንዳንድ ጥቅሶቹን እንዳይነበቡ ስለሚደብቃቸው ነው:: ክርስትናም መጽሐፍ ቅዱስን በቀጥታ ራስህ አንብበህ እንድትረዳ አይጠይቅህም፤ካህናትና ቀሳውስት በሚረዱበት መንገድ ብቻ መረዳት አለብህ ይላል::
- ቁርኣንስ?!
- እስላምን አልተረዳህም ብየህ የለም? እስላም ለሙስሊምም ሆነ ሙስሊም ላልሆነው የማስተማሪያ፣የማብሰሪያ፣የማስጠንቀቂያና የጥሪው ማድረሻ ዋነኛ መሰረት ያደረገው ቁርኣንን ነው::
- አደም ስለ እስላም ጥልቅ ዕውቀት ያለህ ትመስላለህ፣በሃይማኖቶች ጥናትና ምርምርህ ውስጥ አጥንተሃል ማለት ነው?
- አዎ::
- በግልጸኝነት በርሱ ላይ ያለህ አስተያየት ምንድነው?
- አንተን በመሰለ ሰው ላይ ማንም የራሱን ሀሳብ ሊጭንበት አይገባም፤ቁርኣንን ራስህ አንብበውና የራስህን ውሳኔ በራስህ ወስን::
- በግልጸኝነት ሃይማኖትህ ምንድነው? መጀመሪያ ላይ አይሁዳዊ መሰልከኝ፣ከዚያ ካቶሊካዊ፣አሁን ደግሞ ሙስሊም !
- ቡድሂዝምንና ሂንዱይዝምን እወቃቸው ባልኩህ ጊዜ ቡድሂስት ወይም ህንዱ ሊመስልህ እችል አልነበረም? የሰው ልጅ አእምሮውን ክፍት አድርጎ ከተቆለፈበት ሳጥን ራሱን አውጥቶ በነጻ ማሰብ እስካልቻለ ድረስ ፈጽሞ መሻሻል የማይችል መሆኑን ላረጋግጥልህ እፈልጋለሁ:: ሃይማኖቴንና የምከተለውን እምነትም የመታደልን መንገድ ለማግኘት የሚያስፈልግህን ሁሉ ካወቅህ በኋላ እነግረሃለሁ፤ምናልባት ይህ መንገድ

www.path-2-happiness.com

ሁሉንም ሃይማኖቶች የሚተካ ሊሆን ይችላል፡፡

- ሃይማኖቶችን ሁሉ የሚተካ እምነት ይኖራል ብዬ ፈጽሞ አስቤ አላውቅም፡፡
- ቁርኣንን አንብብ፤ቀጥለህ ስለ እስላምና ስለ እስላም ነብይ የተጻፉ መጽሐፎችን አንብብ፡፡ ሃይማኖቶችን ሁሉ በንጽጽር ለመመልከት ሞክር፡፡ ርእሰ ጉዳዮችንና መረጃዎችን የማገናዘብና የማነጻጸር ችሎታ ለስኬት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡
- ጉዳዮችን እንዴት ነው የማስተሳስራቸው?
- የምትጓዝበትን አቅጣጫ ላለመሳት በቡድሂዝም ወይም በህንዱ ሃይማኖት ውስጥ የጠላሃቸውን ነገሮች አስታውስና በአይሁዳዊነት ውስጥ ስለ አለመኖራቸው እርግጠኛ ሁን፤ከዚያም በክርስትና ውስጥ መኖር አለመኖራቸውን አረጋግጥ፡፡ በመጨረሻም እስላም ውስጥ ስለ አለመኖራቸው እርግጠኛ ሁን፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቡድሂዝም ውስጥ የወደድከው ነገር በአይሁዳዊነት በክርስትና ወይም በእስላም ውስጥ መኖር አለመኖሩን አረጋግጥ፡፡ በዚህ ሁኔታ ነው ርእሰ ጉዳዮችን በማነጻጸረና በማገናዘብ የምታያይዛቸው፡፡
- የምፈልገውንና የማልፈልገውን አያይዞ በማነጻጸር የሚያየው የተሟላ ወጥ ምልከታ ደስ ይለኛል፡፡
- በሃይማኖቶች መካከል ያሉትን ተመሳስሎና ልዮነቶቻቸውንም አስተውለህ መርምር፡፡
- የሚያሳዝነው በመካከላቸው ካሉት ልዩነቶች ይልቅ በመካከላቸው ያለው ተመሳስሎ ነው የሚታየኝ !
- ነገሮችን አገናኝቶ መመልከት አእምሮና አስተሳሰበን ያጎለብታል፡፡ ዝርዝር ጉዳዮችን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የሆኑትንም እርስ በርሳቸው አያይዘህ ማየትህን አረጋግጥ፡፡
- ተመሳስሎአቸውን በተመለከተ ሁሉም በብሉይ ኪዳን የሚየምኑ መሆናቸውን አስተውያለሁ፤በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ የሚየምን በእውነት እብድ ነው የሚል እምነት አድሮብኛል፡፡
- ክርስቲያኖች አዲስ ኪዳን የመጣው ብሉይ ኪዳንን ለማሟላት ነው ብለው ያምኑበታል፡፡ አይሁዶች ግን በአዲስ ኪዳን አያምኑም፡፡ ሙስሊሞች ደግሞ በመሰረቱ በሁለቱም የሚያምኑ ቢሆንም፣ሁለቱም የተዛቡና የተበረዙ በመሆናቸው ዛሬ ያሉት ከእግዚአብሔር የተላለፉ ነባሮቹ አይደሉም የሚል አቋም አላቸው፡፡ የሚያምኑት በቁርኣን ሲሆን ከበፊቱ የነበሩትን

መለኮታዊ መጽሐፎች ሁሉ የሚሽር ነው ይላሉ፡፡ ታድያ ልዩነቶቻቸው የሰፉ መሆናቸው አይታይህም?

- ልክ ነህ . . ልዩነቶቹ በጣም ሰፊ ናቸው፡፡ በተፈጥሮዬ ከልዩነቶች ይልቅ በሚመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ አተኩራለሁ፤ነገሮችን እምብዛም አያይዤ አልመለከታቸውም፡፡
- መልካም፣ችግርን ነቅሶ ማውጣት የመፍትሔው መጀመሪያ ነውና ወደ እልባቱ ደርሰሃል፣እናም በተሟላና በተሰናሰለ መልኩ ታየዋለህ ማለት ነው፡፡ በልተህ ጨርሰህ ከሆነ ከሥራ እንዳልዘገይ መንቀሳቀስ አለብኝ፡፡
- አዎ ጨርሻለሁ፤በል እንሂድ፡፡ በጣም ምርጡና በጣም ርካሹ ቦርሳህ መኪና ውስጥ ነው፣እንዳልረሳው፡፡
- ስጠይቅህ ስቀህብኝ የነበረ ቢሆንም በመመዘኛው መሰረት ነው ያመጣሽው፡፡
- በአጋጣሚ በአንዳንድ የቦርሳ ዓይነቶች ላይ የማጣሪያ ሽያጭ የሚያካሄድ መደብር ነበር፣በዚህ የጥራት ደረጃ በመደብሩ የቀረው የመጨረሻው ቦርሳ ይህ ነበር፡፡
- አጋጣሚ እግዚአብሔር ሊወስነው የሚችለውን ነገር የሰው ልጆች ማወቅ እንደማይችሉ ያመለክታል፡፡ የሚያሳዝነው ግን ‹‹አጋጣሚ›› የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ የምንጠቀመው አንድ ነገር እንዴት እንደ ተከሰተ ሳናውቅ በምንቀርበት ጊዜ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍጥረተ ዓለሙ ውስጥ ያለውን ሁሉ የምናውቅ ይመስል የማናውቀው ነገር ሲያጋጥመን ‹‹አጋጣሚ›› ነው ብለን እንወስዳለን ማለት ነው፡፡ እኛ ስላልደረስንበት ብቻ ዕውቀቱ የለም የማለት ያህል ሲሆን፣ ይህም የተወገዘው በራስ አጉል መመካትና መመጻደቅ መሆኑ ጥርጥር የለውም . . አልያም ልብ ሳንለው በኤቲዝም ተጽእኖ ስር ከመውደቅ የተነሳ ሊሆንም ይችላል፡፡
- በፍልስፍናህና በተራቀቁ ቴክኒካዊ ቃላትህ አንገላታሽኝ፡፡ እህህ፣የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ሆነና አንዱ ቦርሳ ብቻ ሲቀር ወደ መደብሩ ደረስኩ ማለት ነው፤ፈተናውን አልፌ ይሆን?
- እህህ፣ቦርሳው ከፍተኛ ጥራት ያለውና በጣም ርካሽ ከመሆን ግዴታ ጋር፡፡
- እንግዲያውስ አልፌአለሁ፣ቦርሳው ይኸውና ተቀበል፡፡
- በጣም ድንቅ ነው፣ፈተናውን አልፈሃል፡፡ ይህም አንዳንድ ጊዜ እውነታን በአእምሮአችን ብቻ ላንገነዘብ እንደምንችል የሚያመለክት ነው፡፡
- ይሁንና ተጨባጩ እውነታ ከአእምሮ እውነታ ጋር የማይጻረር እንደ መሆኑ፣እውነታ ከአእምሮ ጋር የሚቃረን መሆን አይችልም፤አለበለዚያ

www.path-2-happiness.com

ከሁለት አንዱ እውነታ አይደለም::
- ልክ ነህ፤የረቀቀ ልዩነት አለ፤ታድያ ፈላስፋው ማነው? !
- እባክህን ዛሬ ቶምን ከቤቴ አባርሬ አስቀይሜዋለሁ፤ይቅርታ ጠይቄው ይቅር ብሎኛል:: በነገራችን ላይ ነገ ከርሱ ጋር ቀጠሮ አለኝ::
- ከቤትህ አባርረህ ይቅርታ ጠየቅህና ይቅር አለህ ! ይህ የመጠቀ ስነ ምግባር ነው፣ምስጉን ጠባይ ነው:: ቶም በዚህ ፍጥነት እዚህ ደረጃ ይደርሳል ብዬ አልጠበኩም ነበር !
- ምን ማለትህ ነው?
- እንደ ነገርከኝ ቶም መሻሻልን እያሳየ ነው፤ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው ከወራዳነት ወደ ምጡቅ የስነ ምግባር ደረጃ በፍጥነት መነሳት አይችልም::
- በሆስፒታሉ ከተዋወቃችሁ በኋላ ከቶም ጋር አልተገናኘህም ነበር?
- ከአንድ ጊዜ በላይ ተገናኝተናል::
- ከአንድ ጊዜ በላይ?!
- አዎ፣እውነቱን ለመናገር ተመችቶኛል፣እኔም የተመቸሁት ይመስለኛል::
- እንዴት መዘንከው?
- ብልህ፣አስተዋይ፣በትልቅ የሽግግር ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ሰው ነው::
- ከዬት ወዴት ነው ሽግግሩ?
- ከነበረበት ሁኔታ ወደ ተሻለ ሁኔታ እየተሸጋገረ ነው::
- የተሻለ ሁኔታ ምንድነው?
- አንተ የተሰማራህበት የመታደልን መንገድ ፍለጋ ሊሆን ይችላል::
- እኔ አላገኘሁት . . እርሱ ያገኘዋል? !
- አንተም እንደሱ በከፍተኛ የሽግግር ጊዜ ውስጥ አይደለህም እንዴ? እንዳያገኝ የምትፈልግና የቀናህበት ትመስላለህ !
- ዋናው ነገር ከርሱ ጋር ያለኝ የነገው ቀጠሮ ምን መልክ መያዝ አለበት?
- እንደ ተለመደው መሆን አለበት::
- የተለመደው ምንድነው?
- ከኔ ይልቅ አንተ ታውቀዋለህ::
- የተለመደው ስለላፉት ንባቦችና ውይይቶች ይጠይቀኝና ቀጣዩን አዲስ ዙር እንጀምራለን::
- እናም የሚጠበቀውም ይህ ነው ማለት ነው::
- ስለ ተዛባውና ስለ ተበረዘው ክርስትና ከርሱ ጋር ትወያያለህ፣ ወይም ኋላ ቀሩን እስላም ስለ ማጥናት ከርሱ ጋር ትከራከራለህ ብለህ ትገምታለህ?

- አዎ ሁሉም ይሆናል የሚል ግምት አለኝ::
- ምድራዊ ሃይማኖቶችን፣አይሁዳዊነትንና ክርስትናን በተመለከተ እንዳደረኩት ሁሉ ሚዛናዊ በሆነ ተመሳሳይ ሁኔታ እስላምንም ለማጥት ወደ ቶራ ቦራ ተራሮች ልጓዝ? አደም ምን ነካህ?
- እህህ፣አዎ . . ምንም አልነካኝም፣ሌሎች ሃይማኖቶችን ለማጥናት እንደተጓዝክ ሁሉ እስላምን ለማጥናት መጓዝን አንተ እንዳልከው የፍትሐዊነትና የሚዘናዊነት ግዴታ ነው . . እህህ፣ይሁን እንጂ የግድ ወደ ቶራ ቦራ አይደለም::
- ሙስሊም ነኝ ብዬ አስመስዬ መሄድ ካልሆነ በስተቀር ወደ መካ መጓዝ እንኳ አልችልም::
- በውሸት ወደ መታደል መንገድ እደርሳለሁ ብለህ ታስባለህ? !
- እስላም ውስብስብ ከሆነ ምን ማድረግ እችላለሁ? ካቶሊክ ሳልሆን ወደ ሮም ሄጃለሁ፤ሌላው ቀርቶ ኤቲስት እንኳ ብትሆን ወደ ቫቲካን መግባት ትችላለህ::
- ማለት የፈለከው ይገባኛል፤ግና አንድ የመካ ነዋሪ የሆነ ሰው ለመግቢያ ቪዛ የሚጠየቁትን ነገሮች ሳያሟላ ወደ እንግሊዝ መግባት ይችላል?
- እኔም ማለት የፈለከው ገብቶኛል፤ግን ጉዳዩ የተለያየ ነው::
- ምንም ልዩነት የለውም፣የመግቢያ መመዘኛዎችን ሳታሟላ በዓለም ላይ የትም ቦታ መግባት አትችልም:: ምንም የሌለው ደሃ ወደ መታደል ሬስቶራንት ገብቶ እኛ እንደበላን መብላት ይችላል?
- ትክክል ነው . . ግና ሙስሊም የመሆን ግዴታ ላይኖርብኝ ይችላል::
- ማን ያውቃል፣ሊኖርብህ ይችል ይሆናል::
- ዛሬ ደግሞ በጣም የተለየህ ሰው ሆነሃል፤ወደ ካፌቴሪያው ተቃርበናል፣በቅርቡ ግን ካንተ ጋር ቀጠሮ ይኖረኛል::
- እህህ፣በደስታና በጉጉት ነው ስልክህን የምጠባበቀው . . አለዚያም ቶራ ቦራ እንገናኛለን::

www.path-2-happiness.com

(3)

ጆርጅ በቀጠሮው መሰረት ወደ ቶም ሲሄድ ክለኒኩ ተዘግቶ አገኘ፤በሩን አንኳኳና ቶም ከፍቶለት ሞቅ ካለ አቀባበል ጋር ተቀበለው።

- በል ግባ . . አዝናለሁ በራድ ያስነሳው አውሎ ነፋስና ችግሮቹ ጋብ እስኪሉ ድረስ ክሊኒኩ ተዘግቷል። በራድ ሁሉንም ግለሰባዊ፣ሞያዊና መንግስታዊ ባለ ድርሻዎችን አሁንም እያነሳሳብኝ ነው።
- ምን ማድረግ አሰብክ?
- አላወኩም፣እዚያም አለ እዚህ መፈታቱ አይቀርም።
- ለምን አትደራደርም?
- በምን ላይ ነው ከርሱ ጋር የምደራደረው?
- እኔ እንጃ፣ዋናው ነገር ከሸርና ተንኮሉ መገላገል ነው።
- እርሱ የሚፈልገውን ከመቀበል ሸርና ተንኮሉ ይመረጣል። በጣም የሚገርመው አብዝቶ ቢያስቸግረኝም፣የሰጠኝ አገልግሎትም ትልቅ ቢሆንም፣ቀደም ሲል ከነበረው አሁን በጣም ደስተኛ ነኝ !
- ሕይወት በተቃርኖና በአስደናቂ ነገሮች የተሞላች ነች። ዝሙት የሚፈጽም መነኩሴ፣ገበናውን የማይሸፍን የተራቆተ ነብይ፣ገዳይ የሆነ አምላክ፣ይህ ሁሉ ሆኖ ግን መቃወምና መተቸት አይፈቀድም !
- ይህን ትተን ወደ ጉዳያችን እንግባና በግልጸኝነት የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን እንዴት አገኘሃት?
- በግልጸኝነት እውነቱን ተናገር ካልከኝ የሰው አእምሮ ሊቀበለው በማይችል ሁኔታ ላይ ነው ያገኘኋት !
- ምናልባት ይህ ሊሆን የቻለው ፕሮቴስታንት በመሆንህ ይሆናል !
- የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንም በብዙ ነገር ተመሳሳይ ናት። ችግሩ በዚህ ወይም በዚያኛው ነው የሚል እምነት የለኝም ችግሩ . .
- ችግሩ ምኑ ላይ ነው?
- በግልጽ ለመናገር ችግሩ ጣዖት አምላኪነት ነው።
- ጣዖታዊነት? ! ባዕድ አምልኮ? !
- ይህን ማሰብ በጣም ጎድቶኛል፣እውነታው ግን ይኸው ነው። የጳጳሳዊ ሥርዓት ጣዖታዊነት፣የሥላሴ እምነት ጣዖታዊነት፣የቅርጻ ቅርጽና የሥዓሎች አምልኮ ጣዖታዊነት የ . . ጣዖት አምልኮ . .
- የችግሩ ምንጭና መሰረት ራሷ ቤተክርስቲያኗ ናት ማለት የፈለክ ትመስላለህ?
- አይደለም፣ተጨባጭ የሆነ እውነተኛ ችግር ያለው ብሉይና አዲስ ኪዳንን አጠቃሎ በያዘው በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ይህን ቋጠሮ ለመፍታት ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የታያት መፍትሔ ከቤተ ክርስቲያኗ መነኮሳትና ቀሳውስት ውጭ ሌላው ተራ አማኝ መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያነብ መከልከል ነበር። ካህናቱ ብቻ ናቸው መጽሐፉን መረዳት፣ማስረዳትና ማብራራት የሚችሉት። የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን መፍትሔ ደግሞ ማንበብና እንዳሻቸው ተገዥ አለመሆን ነው።
- የረቀቀ ትንተና ነው። በአንተ አመለካከት የዚህ መንስኤ ምን ይመስለሃል?
- ምክንያቱ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ወገን እንዳሻው የለዋወጠውና እንደ መሰለው ያሻሻለው መሆኑ ነው። ከዚ በኋላ ቀሳውስት በየዘመኑ እየተሰበሰቡ በተደጋጋሚና በቋሚነት ሲለዋውጡትና ሲያሻሽሉት መኖራቸው ነው። በመሆኑም አእምሯዊና ሎጂካዊ እውነታዎችን የሚጻረረውና እርስ በርሱ የሚፋለስ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ ቃሉ ሆኖ መቀጠል አልቻለም።
- ወንጌል በኢየሱስ ዘመን እንዲጻፍ ለምን አልተደረገም ነበር?
- በዘመኑ ክርስቲያኖች በከፍተኛ ጭቆና ውስጥ የነበሩ ተሳዳጆች ስለነበሩ ሊጻፍ አልቻለም። አዲስ ኪዳን ከኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት በኋላ ረዥም ዘመናት ቆይቶ ከታሪክ አንጻር በውል በማይታወቁና በማንነታቸው ላይ ከስምምነት ባልተደረሰ ግለሰቦች አማካይነት ነበር የተጻፈው። የተጻፈበት ቋንቋም ኢየሱስ ካስተማረበት ቋንቋ የተለየ ሌላ ቋንቋ ነበር። ዋናው ነገር ችግሩ ስር ሰደደና ፈጽሞ ሊፈታ የማይችል ቋጠሮ መሆኑ ነው። ለዚህም ነው በተለያዩ ቅጂዎቹ ውስጥ ብቻ ሳሆይን በራሱ በአንድ ተመሳሳይ ቅጂ ውስጥ እጅግ የበዙ መፋለሶችና የርስ በርስ ግጭቶች የሚስተዋሉት። አንዱ ትርጉም ከሌላው፣አንዱ እትም ከሌላው የሚጋጭ፣ከሰው ልጅ አእምሮ፣ከሎጂክ፣ከተጨባጭ እውነታና ከሳይንስ ጋር የሚጻረረውም በዚህ ምክንያት ነው . .
- ይኸ በቂ ነው፤ግና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጫን ያልክ ትመስላለህ !
- ፈጽሞ አልተጫንኩም፤እመነኝ እውነቱን ነው የምነግርህ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተገዥ ለመሆንና በርሱ ለመመራት ጥረት ባደርግም አልቻልኩም !
- እንዴት? አብራራልኝ።
- ሁለት ምሣሌዎችን ልስጥህ ፦ አንደኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፈው

www.path-2-happiness.com

ሁሉ አላምንም፤እዚያ በሰፈረው ሁሉ ማመን ማለት አእምሮዬን ውድቅ አድርጌ አውልቄ ማስቀመጥ ማለት ነው:: አእምሮዬን ውድቅ ካደረኩ ደግሞ ምንም መረዳት አልችልም ማለት ነው::

- ጥሩና ተጨባጭ የሆነ ፍልስፍና ነው . . ድንቅ እሳቤ ነው::
- ሁለተኛው ደግሞ ፦ አእምሮዬን ውድቅ አድርጌ ለመረዳትና ለማመን ብወስን እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እኔ ለአንተ አልሆንም ይለኛል !
- እንዴት ለአንተ አልሆንም ይላል? አብራራው::
- መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈረው የኢየሱስ ቃል ፦ ‹‹ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ::›› አይደለም የሚለው? እናም እኔ እስራኤላዊ ስላልሆንኩ ኢየሱስ በጭራሽ ለኔ የተላከ አይደለም::
- ስለዚህ አንተ ክርስቲያን አይደለህማ?!
- ሊሆን ይችላል፣አውነቱን ነው የምልህ አላውቅም . . በአንተ ምክንያት ኤቲስት እንዳልሆን እሰጋለሁ!
- ኤቲስት እንድትሆን ቀደም ሲል የዘየድኩት መላ ይህ ነበር፤ተሳክቶልኝ እንዳይሆን እፈራለሁ:: አሁን ግን ከነበረኝ አቋም ሙሉ በሙሉ ተለውጫለሁ:: ቢያንስ ኤቲዝምን በሚመለከት ከአንተ የበለጠ ዕውቀት ያለኝ ከመሆኑ አንጻር፣ከመሰል ጉዳዮች ለመገላገል የሚደረግ ሽሽት እንጂ የምር የሆነ ኢአማኝነት አለመኖሩን ደጋግሜ አረጋግጥልሃለሁ:: የከፋ ብልሹ ሕይወት ለመምራት ወደ ኤቲዝም፣አስካሪ መጠጥ፣ዝሙትና ወይም ሌላ ማንኛውም ነገር መሸሽ ማለት ነው:: ሽሽቱ ውስጣዊ አውነታ ከመሆን ይልቅ ከራሱ ከእውነታ የሚደረግ ፍርጠጣ ነው::
- ልክ ነውህ፣እያዘንኩ የዘየድከው መላ የያዘልህ ይመስላል፤ወደ መታደል መንገድ የመድረስ ተስፋዬ እንዳይጨልም ስጋት አለኝ::
- ምናልባት ባለማወቅ ሳንመረምረው ወይም ሳንረዳው ያለፍነው ነገር ሊኖር ይችላል:: ለማንኛውም ሳናጠናቅቅ ውሳኔ ላይ ላለመድረስ ተስማምተናል::
- ሳንመረምረው ወይም በደንብ ሳንረዳው የዘለልነው ነገር ሊኖር ይችላል ስትል ምን ማለት ነው?! ይህማ ራሱ የካቶሊኮች ሎጂክ ነው::
- በተወሰነ ደረጃ ትክክል ነው፤ይሁንና አእምሮና ሎጂክ እኛ የሳትነውን ሊቀበሉ ወይም ቢያንስ እኛ ለስህተት ልንጋለጥ አንችልም?
- ልክ ነው አእምሮ ያንን ሊቀበል ይችላል ብቻ ሳይሆን የዚህ ተቃራኒ ተቀባይነት የለውም:: ሁልጊዜ ትክክለኛው እኔ ነኝ ብሎ ማሰብ ራሱ ከአእምሮ ጋር የሚጻረር ነው::

- እህህ፣በጀ . . እናም ካቶሊካዊነት ከሰው ልጅ አእምሮ ጋር ይጣጣማል ማት ነዋ ! . . ዋናው ነገር ሳናጠናቅቅ ውሳኔ ላይ ላለመድረስ ተስማምተናል::
- እንደ ልማድህ እስላምን ማጥናት እንጀምር ለማለት ይህ መንደርደሪያ እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ::
- በትክክል ነው . . ይህንኑ ነው የምልህ፤እንድያውም እኔ በበኩሌ እስላምን ማጥናት ጀምሬአለሁ:: በነጻ አእምሮ ያለ ምንም ቅድመ ውሳኔ ለማጥናት ከራሴ ጋር እየታገልኩ ነው:: እኔም ካንተ ጋር በመታደል መንገድ ፍለጋ ላይ መሰማራቴን ነግሬህ የለም?

ጆርጅ አንደኛውን እጁ በሌላኛው መታና ፦

- ማለቂያ የሌለው መንገድ የጀመርን መሰለኝ::
- ከትናንት አንስቶ የሙስሊሞችን ቅዱስ መጽሐፍ ቁርኣንን ማንበብ ጀምሬአለሁ::
- እህህ፣እኔም ብሆን አደም እንዳነበው ሊያሳምነኝ ሞክሯል፣ግን መልስ አልሰጠሁትም፤ይሁን እንጂ ጊዜ እያባከንኩ እንደሆነ ነው የሚሰማኝ::
- የእንግሊዝኛ ትርጉሙን የሰጠኝ አደም ነው . . ካነበበ እስላምን ሊቀበል ይችላል ብሎ ይጠብቃል መሰለኝ::
- እስላምን እንድትቀበል ይፈልጋል! ብትቀበል እርሱ ምን ይጠቀማል?
- ሰዎች ሁሉ ወደየራሳቸው ሃይማኖቶችና አመለካከቶች ነው ጥሪ የሚያደርጉት::
- ማለት የፈለከው አልገባኝም::
- ምኑ ነው ያልገባህ? አደም ወደራሱ ሃይማኖት ሊያስገባኝ ይፈልጋል፤ግልጽ ያልሆነልህ ምኑ ነው?
- አደም ሙስሊም ነው ! ! !
- አዎና፣ዐረብ መሆኑን ገጽታውና ተክለ ሰውነቱ ይናገር የለም? ይህን አታውቅም ነበር?
- አዎ አላውቅም ነበር፤ስሙ የዐረብ ስም አይደለም፣የሕንድ ዝርያ ያለው ካቶሊካዊ ነው የሚል ግምት ነበረኝ፣አደም እያሾፈብኝ እንዳይሆን ፈራሁ::
- ስሙ እንኳ የመላው የሰው ልጆች አባት ስም ነው፣እኛ ዘንድም አለ፣ዐረቦች ዘንድም እንዲሁ የተለመደ ስም ነው:: ያሾፍብኛል ያልከው ገን ትክክል ኤመስለኝም፤ዋሽቶህ ያውቃል?! ጠይቀኸው እውነት ያልሆነ ነገር ነግሮህ ያውቃል?
- ካንዴም ሁለቴ ጠይቄው መልስ አልሰጠኝም:: ዋናው ነገር ወደ እስላም

www.path-2-happiness.com

ሲወስደኝ ከኋላ እየገፋፉኝና ወደዚያ ሲመራኝ ኖሯል? ሞኝ ተላላ መሆን አልፈልግም፡፡

- ወደራሱ ሃይማኖት ቢጠራህ ሞኝ ተላላ ትሆናለህ?!
- አልሆንም ግን . . እፈራለሁ፡፡
- ወደ እስላም መግባትን የምትፈራ ካልሆንክ በስተቀር ምንም የሚያስፈራህ ነገር የለም?!
- አዎ ያለ ዕውቀትና ያለ ማስተዋል ወደ አንድ ነገር መነዳትን እፈራለሁ፡፡
- ቀሳውስቱም ሆኑ ሌሎች ሲነዱህና ሲያሳምኑህ ያልቻሉትን አደም ነድቶህ እስከያሳምንህ ድረስ ደካማ ሆነህ ነው?! ወይስ አደም በከፍተኛ ደረጃ ጠንካራ በመሆኑ አስፈርቶህ ነው?

ጆርጅ በእጆቹ እያመላከተ ፦

- ሁለቱም አይደለም፤ግን ለምንድነው እንደዚህ የምታናግረኝ? !
- በሁሉም ሃይማኖቶች ላይ አንበሳ ከመሆን እስለምን ወደምትፈራ ጥንቸል ስለተለወጥክ፡፡
- ፈሪ አይደለሁም፤እስላምንም አጠናለሁ፣እመረምረዋለሁም . . ስለኔ መለወጥ ስትናገር ትዝ አለኝ፣አደም ስለ አንተ መለወጥና ሽግግር ይጽፋል፡፡
- ስለኔ መለወጥና ሽግግር? ! ከበራድ ጦስ ገና ሳልገላገል ይሸኛው ደግሞ ምን ጽፎ ይሆን?
- ወደ ፌስቡክ ገጹ ግባና የጻፈውን አንብብ፡፡
- እሽ አደርጋለሁ፣ይህን ተወውና ዋናው ነገር ከርሱ በፊት የነበሩትን እንዳጠናሃቸው ሁሉ እስላምን በክፍትና ነጻ አእምሮ ታጠነዋለህ?
- አዎ አጠናለሁ፣ተስማምተናል፡፡
- ከርሱ በፊት የነበሩትን እንደተቸህ ሁሉ ትተቸዋለህ?
- አዎ፣እንዲያውም ይበልጥ የጠነከረና የሰላ ትችት፡፡
- ይኸማ የምናወራው በክፍትና ነጻ አእምሮ ማጥናት አይደለም፡፡ ይበልጥ የጠነከረና የሰላ ትችት ማለትህ ከቅድመ ሁኔታ ባልጸዳ ዝግ አእምሮ ማለት ነው፡፡ ምድራዊ ሃይማኖቶችን፣አይሁዳዊነትንና ክርስትናን ባጠናህበት መንገድ ክፍት በሆነ ነጻ አእምሮ አጥናው፡፡
- እናም ሳልተቸውና የሰላ ሂስ ሳልሰነዝርበት እንድሰልም ነው የምትፈልገው? !
- ከቅድመ ውሳኔ ነጻ በሆነ ሚዛናዊ አእምሮ ለእውቀት ትኩረት ሰጥተህ ካጠናኸው በኋላ፣ልክ አይሁዳዊነትን፣ክርስትናን ወይም ቡድሂዝምን

እንደተቸሃቸው ሁሉ በሙሉ ልብ እንድትተች ነው ፍላጎቴ፡፡

- ባልካቸው እምነቶች ላይ ግን ጠንካራ ትችት አቅርቤ ቢያንስ ለኔ ስህተት ሆኖ የታየኝን ሁሉ ነው ያጋለጥኩት፡፡
- እኔ የምልህም ይህንኑ ነው፣የነሱን ስህተተኛነት እንዳጋለጥከው ሁሉ የእስላምን ስህተተኛነትም አጋልጥ፡፡ መማርንና ውሳኔን ከዚያ በኋላ ማድረግ ምርጫዬ ቢሆንም ያላሰብነውና አእምሯችን ውስጥ የሌለ ነገር ሊገለጥልን ይችል ይሆናል፡፡
- የእስላምን ስህተተኝነትና እርስ በርስ መጣረሱን ካጋለጥን በኋላ ምንድነው የምንሆነው? ወደ ኤቲዝም ነው የምንመለሰው? !
- እኔ እንጃ ! የማውቀው ነገር ቢኖር እንዳልኩህ ሁሉ ያልጠበቅነው ነገር ሊታየን ይችል ይሆናል የሚለውን ነው፡፡
- ቁርኣንን ማንበብ እንደመጀመርህ እስካሁን እንዴት አገኘሽው?
- ትናንት ነው የጀመርኩት፣እጅግ በጣም ትንሽ ነገር ብቻ ነው ያነበብኩት፣ግን አስደሳች ነው፡፡
- እህህ፣ኦህ መወስወስ የጀመርኩ መሰለኝ፣አንተም ሙስሊም እንዳትሆን እሰጋለሁ፡፡
- አይደለሁም . . እርግጠኛ መሆን ትችላለህ፣እኔ ሙስሊም አይደለሁም፡፡
- ታድያ አንተ ምንድነህ? !
- እኔ እንዳንተው ነኝ፤እኔ እንጃ በፍጥነት የምገለባበጥ ሆኖ ይሰማኛል፡፡
- አደምም ስለ አንተ ሲጽፍ ያለው በለውጥ ሂደት ውስጥ መሆንህን ነው፡፡
- ምናልባት ያለው ነገር እውነት ሊሆን ይችላል፣ዛሬ ስለኔ የጻፈውን አነባለሁ፡፡ ለመሆኑ ፌስቡክ ላይ እንዳገኘው ሙሉ ስሙ ማነው?
- ኢሜይሉ ስላለህ ሙሉ ስሙን ደብዳቤዎቹ ውስጥ ታገኛለህ፣በዚያም የፌስቡክ ገጹን ማግኘት ትችላለህ፡፡
- መልካም፣ዋናው ነገር እስላምን በነጻ አእምሮ እንመረምራለን፡፡
- እናም ወደ አፍጋኒስታን ወይም ወደ ቶራ ቦራ ያለ ቅድመ ውሳኔ በነጻ አእምሮ እንሄዳለና !
- ወደ ሙስሊምነት እንደምትለወጥ እርግጠኛ የሆንክ መስለህ ለምን እንደምትናገር እኔ እንጃ፡፡
- እየቀለድኩብህ ነው፡፡
- በነገራችን ላይ በካቶሊካዊነት ላይ ባለህ አቋም ምክንያት ከካትሪና ጋር አልተወዛገባችሁም?

- አልተወዛገብንም፣እጅ ሰጠች መሰለኝ::
- ወደ ቤተ ክርስቲያን በሄድኩበት ጊዜ እውነተኛ አምላኪና ለኢየሱስ ጥልቅ ፍቅር ያላት መሆኗን መገንዘብ ችያለሁ::
- የኔም ስሜት ይኸው ነው:: ከካቶሊካዊነትና ከእምነቶቹ በኩል ያጋጠማት አስደንጋጭ ሁኔታ ግን ብርቱ ነው . . ሮም ውስጥ ከአንድ ሙስሊም ጋር በተገናኘን ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ድንጋጤና የመፍረክረክ ሁኔታ ነበር ያሳየችው !! እምነትና እርግጠኝነትን ያስተማራት ቄስ ለኔ ጥያቄዎች መልስ መስጠት እንዳልቻለ ስታውቅም እንደዚሁ ተፍረክርካሎች !
- በሃይማኖት አጥባቂነቷ በጣም አደንቃታለሁ::
- ታድያ ወደ ካቶሊክነት ለምን አትለወጥም?
- እርስ በርስ መጋጨትንና ሳይንስን መጻረር በጣም ስለምጠላ::
- እህህ፣እንግዲያውስ ወደ እስላም ግባና ወደ ቶራ ቦራ ተራሮች አቅና::
- እስላምን አሳማኝ ሆኖ ባገኘውና የመግቢያ መመዘኛው ወደ ቶራ ቦራ መሄድ ቢሆን እንኳ በእርግጠኝነት አደርገዋለሁ::
- ጽኑ ቁርጠኝነትን እወዳለሁ፣ግና መውጫ መንገዱ አይታየኝም::
- እኔም እንዲሁ ነኝ፤ይሁን እንጂ በድንገትም ቢሆን መገለጹ አይቀሬ ስለመሆኑ ግን እርግጠኛ ነኝ፣እንዴት ብለህ አትጠይቀኝ፤በቃ እርግጠኛ ነኝ::
- እኔም ተመሳሳይ የሆነ የእርግጠኝነት ስሜት ነው ያለኝ::
- ለላክንልህ መልሶች እንዳስለመድከን ማጠቃለያ ለምን አልተላከለንም?
- ልክ ነህ . . በአንተ ፎቶዎች ምክንያት ትናንት ኢሜይሌን አላየሁም ነበር:: ዛሬ ሁሉንም አይና የአደም መልሶች ሙስሊም መልሶች መሆን አለመሆናቸውን ልብ ብዬ ለማየት እሞክራለሁ::
- ቀደም ሲል ከላካቸው መልሶቹ ውስጥ ግልጽ አልነበረም?
- ሊሆን ይችላል፤ሆኖም ልብ አላልኩም ነበር:: ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ነገሮችን፣ሁነቶችን፣ውይይቶችንና መረጃዎችን እርስ በርሳቸው አዛምጄ በማነጻጸር ያለ መመልከት ችግር እንዳለብኝ የጻፈው::
- ነገሮችን አዛምዶና አነጻጽሮ መመልከት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው::
- አነጋገርህ በትክክል ከአደም አነጋገር ጋር ተመሳሳይ ነው፤አድናቂው ሳትሆን አልቀረህም::
- አቋሙ ይህ መሆኑን አላውቅም ነበር፤እውነቱን ለመናገር አድናቆቴ ከዚህ አቋሙ ይበልጥ ለውስጣዊ ሚዘናዊነቱ ነው::

- ለውስጣዊ ሚዛናዊነቱ ያለህን አድናቆት እኔም እጋረሃለሁ፤የአመለካከቱ አድናቂም ነኝ:: በነገራችን ላይ በራድ ቢሮህ ውስጥ የተከለውን የስለላ ሲስተም አስወግደሃል?
- አዎ፣ከበራድና ከጣጣው ለመገላገል ያለኝን ጉጉት ልነግርህ አልችልም፤ከዚያ አስቂያሚ የቀድሞ ሕይወቴ ጋር ያስተሳስረኛል!
- በቅርቡ ትገላገለዋለህ፤እንድሄድ ትፈቅድልኛለህ??
- አዎ ትችላለህ፣የዛሬውን ጨርሰናል፣በኔ እምነት በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ከሆኑ ቀጠሮዎቻችን ይህ ዋነኛው ነው::
- እናም እስላምን ማጥናት እንጀምራለን፣ወደ ሥራ እመለስና ካኽን አገኘዋለሁ፣እንዴት እንደምጠላቸው ልነግርህ አልችልም!
- ምኖቹን ነው የምትጠላቸው?
- እሰላምና ካኽን::
- እንደገና ወደ ኢሚዛናዊነቱ ተመለስን!
- ኦህ . . ልብ አላልኩም ነበር፣ማለት የፈለኩት ካኽንና ሥራውን ነው::

(4)

ጆርጆ ማታ ወደ ቤቱ ከደረሰ በኋላ ኢሜይሉን ከፈተ . . ሦስቱ መለኮታዊ መጽሐፎችን በንጽጽር እንዲመለከቱ ለላከላቸው መልእክት ከባልደረቦቹ የተላኩትን ምላሾች አገኘ ፦

ሌቪ ፦ ቁርኣንን አላነበብኩትም፣ይሁንና ግን ሦስቱ ሃይማኖቶች በጣም ይመሳሰላሉ የሚል ግምት አለኝ::

ሐቢብ ፦ ሁሉም ከእግዚአብሔር ዘንድ ከመሆናቸው አንጻር ተመሳሳይ ናቸው:: ቁርኣን ግን ተአማኒነት ባለው መንገድ በጽሑፍ ተጠናቅሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ በመሆኑ ይለያል:: ይሁን እንጂ በጽሞና አላነበብኩትም::

አደም ፦ በመሰረቱ ሁሉም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፉ ናቸው፤የሚያሳዝነው ግን ብሉይ ኪዳንና ወንጌሎች የተዛቡና የተከለሱ መሆናቸው ነው::

ቶም ፦ ቁርኣንን ስላላነበብኩት ከኦሪትና ከወንጌል ጋር አላነጻጸርኩም::

ካትሪና ፦ ብሉይና አዲስ ኪዳኖች ከእግዚአብሔር የተላለፉ ናቸው:: እስካሁን ያላነበብኩት ቢሆንም ቁርኣን ግን እንደዚያ አይመስለኝም::

ጃኖልካ ፦ ትናንት ለመጀመሪያ ጊዜ ቁርኣንን ማንበብ ጀምሬለሁ፤በምን

www.path-2-happiness.com

እንደሆነ ባላውቅም ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን ይለያል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

ጆርጅ የአደምን ምላሽ ከወትሮው በተለየ ትኩረት አነበበ፣የሚጠቀመውን የአጻጻፍ ስልት አስተዋለ . . ሁሉም ወዳጆቹ ቁርኣንን እንዳላነበቡ ወይም በጨረፍታ ብቻ ያነበቡ መሆናቸውን በግልጽ ሲናገሩ ይህንን ያላለው አደም ብቻ ነበር፡፡ ሁሉንም መልሶች ለሁሉም ወዳጆቹ መልሶ ከላከ በኋላ የሚከተለውን ስድስተኛ ዙር ጻፈላቸው ፦

‹‹ስድስተኛው ዙር ፦ ከናንተ መካከል ቁርኣንን አንብቦ በመረዳት በተረጋገጠና ተኣማኒነት ባለው ሁኔታ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ አለመተላለፉን፣መዛበትና መከለስ የደረሰበት መሆን አለመሆኑን መመርመር የሚችል ሰው ያድርግ፡፡ ትችታችሁን በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ እጠብቃለሁ፡፡

ጆርጅ››

መልእክቱን ከላከ በኋላ በቀጥታ ለአደም ደወለ . .

- የተገናኘን ቢሆንም አሁንም ደግሜ ላገኝህ እፈልጋለሁ፤ነገ ይመችሃል?
- ችግር የለውም፤የሥራ ሰዓቴ ነገ እስከ ሁለት ሰዓት ስለሆነ የሚሆነው ግን ከዚያ በኋላ ነው፣እህህ እራት አብረን እንበላለን፡፡
- ይስማማኛል፣እኔም ነገ ወደ ሥራ የምመለስበት የመጀመሪያው ቀን ነው፤ከሦስት ሳምንታት ወዲህ የካኽን ፊት አላየሁም፡፡
- እንግዲውስ እጠብቀሃለሁ፣ደህና ሁን፡፡

ካትሪና ወደ ቤት ስትመለስ ጆርጅ ኮምፒውተሩ መስኮት ላይ እንዳፈጠጠ ቁጭ ብሎ አገኘችውና ስማው ትከሻውን መታ መታ አደረገች . .

- የኔ ፍቅር በመዘግየቴ ይቅርታ፣የሚያስፈልጉንን ነገሮች ለመሸመት ወደ ገበያ ማእከል ሄጄ ነው፡፡ ከጉዞ ከተመለስን ወዲህ ቤት ውስጥ ምንም አልነበረም . . ግሩም ትዝታ ጥሎ ያለፈ ጉዞ ነበር፡፡
- እውነትሽን ነው የማይረሳ ድንቅ ጉዞ ነበር፣ዋነኛው የጉብኝቱ ድንቅ ነገር ግን አንቺው ነሽ፡፡
- ለውብ አገላለጽህ አመሰግናለሁ፣ፈጥኖ ያለፈ ጉዞ ነበር፡፡
- ሁሉም መልካም ነገሮች የሚያልፉት በፍጥነት ሲሆን አሳዛኝ ጊዜያት ግን ረዥምና አሰልቺ ይሆናሉ፡፡ አስደሳች መጽሐፍ እንኳ አንዳንድ ጊዜ በአንዴ ተነቦ ያልቃል፣አሰልቺ መጽሐፍ ግን ብዙ ቀናት ወይም ሳምንታት እጅ ላይ ይቆያል . . ለዚህ ነው ኻሊድ የሰጠሸን መጽሐፍ በአንድ ምሽት ያነበብሽው፡፡

- ‹‹ለኢየሱስ ያለኝ ታላቅ ፍቅር ወደ እስላም መራኝ›› የሚለውን መጽሐፍ ማለትህ ነው?! በጣም አነጋጋሪ የመሆኑን ያህል አስደሳች አልነበረም፡፡
- ለዚህ ነው በላክሽው መልእክትሽ እንደጠቀስሽው ቁርአንን ለማንበብ የምታስቢው?
- በትክክል፤ለማንበብ ቆርጬ ትናንት የቁርኣን መጽሐፍ ገዝቻለሁ፡፡
- እህህ . . ኦ ካትሪና ይህማ መሰረታዊ ለውጥ ነው፣ካትሪና ቁርኣንን ልታነብ ! ሙስሊም ልትሆንም ትችላለች ማለት ነው?
- አነበዋለሁ፤ሂስ ልሰነዝርበት፣እንከኑንና እርስ በርስ መጣረሱን ለማጋለጥ ዓላማ አነበዋለሁ፡፡
- ሁላችንም ቁርአንን እንድናነብ የሚጠይቅ መልእክት ከአፍታ በፊት ለሁላችሁም ልኬ ነበር፤የሚገርም መገጣጠም ነው፡፡ እኔ የቁርአን መጽሐፉን ነገ ከአደም እወስዳለሁ፡፡
- ለምን በተለይ ከአደም?
- መጽሐፍ ቅዱሳቸው ስለሆነ፡፡
- አደም ሙስሊም ነው?! ካቶሊክ ነው ብለህ አልነበረም?!
- እውነቱን ለመናገር ሙስሊም መሆኑን ሳውቅ ነገሩ ለኔም ያልጠበኩት አስገራሚ ሆኖብኛል፡፡ በተለይ ለዚሁ ጉዳይ ብዬ ነገ ከርሱ ጋር ቀጠሮ ይዣለሁ፡፡
- በአደም ደስተኛ ብሆንም ሙስሊሞች ግን ፈጽሞ አያስደስቱኝም፡፡ ካቶሊክ ነው ብዬ ስላሰብኩ ይሆናል የተመቸኝ፡፡
- የምትናገሪው ነገር ከፍትሐዊነትና ከስነ አስተሳሰብ ጋር አይጣረስም? እምነቱን ትተን ማንነቱን መመዘን አይደለም ተገቢው?
- አይደለም፤ከመመዘኛ መስፈርቶች ሁሉ ዋነኛው ሃይማኖት ነው፡፡ አንድን አማኝ ካቶሊክ ከአንድ አሸባሪ ሙስሊም ጋር በአንድ ዓይን እንዳይ ነው የምትጠብቀው?! ምሁርን ከማይም በተለየ ዓይን እንመለከት የለም? በመልካም ስነ ምግባር ለታነጸው ከወራዳው በተለየ አክብሮት እንቸር የለም? እናም መልካም ስነ ምግባር፣ዕውቀትና ሃይማኖት የመመዘኛ መስፈርት መሆናቸው ጥርጥር የለውም፡፡
- ሊሆን ይችላል፤ይህ ትክክል የሚሆነው ግን ልክ እንደ መልካም ስነ ምግባርና እንደ ዕውቀት ሁሉ ሃይማኖትሽም ምንም ጥርጣሬ የሌለበት እውነት ቢሆን ኖሮ ነው፡፡ አይመስልሽም?
- በተወሰነ ደረጃ፤ይሁንና አንተ ዘንድ ሃይማኖት ከመልካም ስነ ምግባርና

www.path-2-happiness.com

ከላቀ እውቀት ያነሰ ደረጃ አለው ማለት ነው?! . . እህህ፣ጆርጅ አሁንም የኤቲዝም ብክለት ያለብህ ትመስላለህ::

-ምናልባት፣ግና ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ላይ ለሳሊና ለማይክል ለምን ነበር የፈራሽው? አንቺም የኤቲዝም ብክለት አለብሽ ማለት ነው?

-ምንም የፈራሁት ነገር አልነበረም፤አንተ እንዳው የሆነ ነገር ታስብና ራስህን ታሳምናለህ፤ደሞስ ምኑን ነው የምፈራው?

-እየቀለድኩ ነው፤ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለልጆቼ ስጋት አላደረብሽም፣ሙስሊሙ የሰጠሽን መጽሐፍ ማንበብም አልፈራሽም:: ለመሆኑ መጽሐፉ የታለ? እኔ አላነበብኩትም::

-አንደምታውን በሚገባ እረዳለሁ፤ማንም ሰው ቢሆን የሚሰማው፣የሚያነበውና የሚያስበው ነገር ተጽእኖ ያሳድርበታል::

-አንድ ጥያቄ እጠይቅሻለሁ፣በግልጽነት እንድትመልሽልኝ እፈልጋለሁ::

-ጠይቅ . .

-የካቶሊክ እምነትን መተው ትችያለሽ?

-ካቶሊካዊነት እተዋለሁ?! ትቼው ወዴት ልሄድ?

-ወደ ፕሮቴስታንት፣አይሁዳዊነት፣እስላም ወይም ወደ ማንኛውም እምነት::

-ከወር በፊት ጠይቀህ ቢሆን ኖሮ ያለ ምንም ማመንታትና በሙሉ ልብ አልተውም ባልኩህ ነበር . . አዝናለሁ አሁንም ቢሆን አልተውም እለሃለሁ:: ግና እምነቴ ከቀድሞው ለምን በጣም እንደ ደከመ አላውቅም:: አንተም በጥያቄዎችህ የምታፋጥጠኝ ብትሆንም ከራሴ ጋር ይበልጥ ግልጽ እንድሆን አድርግሀኛል::

-አንቺ ለኔ የእምነት ተምሳሌት ነሽ:: ያልሽው ለውጥ ምናልባት እምነትሽ ለመጨመሩ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: እኔ ፕሮቴስታንት እንጂ ካቶሊክ ባልሆንም የእምነትሽ ልባዊነት ይሰማኛል፣አንቺ ለኔ የመንገድ ፋና ነሽ::

-አንተ ነህ እንጂ የእውነት ፍለጋ ተምሳሌት፣ደሞም ትደርስበታለህ፤ጆርጅ እወደሃለሁ::

(5)

ጧት ላይ ጆርጅ ተለይቶት ወደ ነበረው ሥራው ሄደ፣ካኽን ማግኘት ስላልፈለገ በቀጥታ ወደራሱ ቢሮ አመራ . . በካኽ ላይ የጥላቻ ስሜት አድሮበታል:: ይሁዲ በመሆኑ፣በስግብግብነቱ፣ በወራዳ ጠባዩ ምክንያት ይሆን ወይስ ሁሉንም አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ? የሚያውቀው ነገር ቢኖር

ሃይማኖተኛ አይሁዳዊት ከመሆኗ ጋር ሌቪን የሚወዳት መሆኑን ነው . . በሚከተለው ሃይማኖት ምክንያት ማንንም አይጠላም፣የሚጠላው የሃይማኖቶችን መፋለስና አፈተረቶቻቸውን ብቻ ነው::

ለማንኛውም ግን ካኽን ማግኘት የግድ ነው፤በመሆኑም ካኽ መምጣቱን አውቆ ከመደወሉ በፊት ሊደውልለት ይገባል . . ስለ ካኽ በማሰላሰል ላይ እያለ ለኩባንያው ላበረከተው የላቀ አገልግሎት ጠቀም ያለ ጉርሻ የተፈቀደለት መሆኑን የሚገልጽ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ ከፊቱ ተቀምጦ ተመለከተ:: ወረቀቱ የፈጸማቸውን ስኬታማ ሥራዎች፣በሕንድና በቴል አቪብ ያደረጋቸውን የውል ስምምነቶች የሚዘረዝርና በካኽ የተፈረመ ነበር:: ለካኽ የነበረውን ጥላቻ ከልክ አሳልፎ ይሆን? ወይስ መሸለሙን ሲያውቅ ለርሱ የነበረውን ገንቢ ያልሆነ አስተያየት ለዘብ አድርጎ ይሆን? የተሰጠው ጉርሻ የበጎነቱ መገለጫ ይሆን? ወይስ እርሱ በኢየሩሳሌም ለብንያሚን ያቀረበው ዓይነት ጉቦ ይሆን?!

የቢሮ ስልኩ አቃጨለና መነጋገሪያውን አነሳ፤በሌላው ጫፍ ካኽ ነበር . .

-ሃሎ ጆርጅ፣መምጣትህን ሳውቅ ወደ ቢሮዬ ትመጣለህ ብዬ ጠብቄ ነበር፤ትመጣለህ ወይስ እኔ ልምጣልህ?

-ወረቀቶቼን እያስተካከልኩ ነበር፣ከደቂቃዎች በኋላ እመጣለሁ::

-እሺ እጠብቀሃለሁ::

ጆርጅ አንዳንድ ወረቀቶችን ሰብሰብ አድርጎ ለማስተካከል ቢችልም ካኽ ባሳየው አክብሮት የተጠመደ አእምሮውንና ሀሳቡን መሰብሰብ ሳይችል ወደ ካኽ ቢሮ አቀና:: ሲገባ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገለት . .

-ጆርጅ እንኳን ደህና መጣህ፣ናፈቅንህ እኮ እንደምነህ ጃል? ሮምስ እንዴት ነበረች? ቴል አቪብም ጭምር እንጂ?

-በጣም ደህና ነኝ፤ከሕመሙ ተፈውሻለሁ:: የቴል አቪቡን ጉዞ በተመለከተ ሁሉንም ውሎች አጠናቅቄ ልኬላችሃለሁ:: የሮሙ ጉዞ ግን ግሩም ድንቅ ነበር:: እናንተስ እንዴት ከረማችሁ? ኩባንያውስ?

-የቴል አቪቡ ውል ለኩባንያው ትልቅ የስኬት እርምጃ ተደርጎ የሚቆጠር ነው:: የአይሁዶች ሎቢ በብዙ አገሮች ውስጥ ስር የሰደደ ተጽእኖ ፈጣሪ ነው:: ከቴል አቪብ ጋር ውል መፈራረማችን የሁሉንም ያውሮፓ አገሮችና የአሜሪካን በር መክፈቻ ቁልፋችን ነው:: በዚህ ምክንያት የሥራ አመራር ቦርዱ የገንዘብ ጉርሻ እንዲሰጥህ ወስኗል፣አይተሃል?

-ካኽ ለዚህ በጎ አስተያየትህ አመሰግናለሁ፣የተለየ ነገር አልሰራሁም፣መፈጸም

ያለብኝን ነው ያደረኩት::

-መሰናክሎችን እንዴት ማለፍ እንደምትችል ሳስብ ይገርመኛል፤ድንቅ የሽያጭ ኤክስፐርትም ነህ !

-ምንም መሰናክል አልነበረም፣ወዲያው ነበር የተፈራረምነው::

-ለርሱ በግል የሚሰጠውን ገንዘብ አልጠየቀም ነበር? !

-ጉቦውን ማለትህ ነው? ወስዷል::

-ሌላ ነገር አልጠየቀም?

-ሌላ ምን?

-ተወው፣ከሌቪ ጋር ስንት ሌሊት አደርክ? ሃይማኖተኛ ስለሆነች አንዳንድ ጊዜ እምቢተኛ መሆኗን አውቃለሁ::

-ፈጽሞ አብሬአት አልተኛሁም፤ይህን ማድረግም አልችልም::

-ብንያሚን ቆሻሻ ነው . . አላግባባት ማለት ነው?

-ቆሻሻነቱ ግን ጉቦ በመቀበሉ ነው:: እንዲያግባባልኝ አልጠየኩትም:: ብንያሚን ከኔ ጋር ወሲብ እንድትፈጽም እንዲያስገድዳት እፈቅዳለሁ ብለህ ትጠብቃለህ? !

-እህህ፣ዋናው ነገር ውሉን መፈረሙ ነው:: አንተ እንድትደሰትና እንድትዝናና ነበር ምኞቴ፣አንተ ግን እሽ አላልክም:: ባንተ ቦታ ብሆን ኖሮ ከርሷ ጋር እንጂ አላድርም ነበር፤አልማረከችህም?

-ካኽ እኔ ባለትዳር ነኝ፣በባለቤቴ ላይ ክህደት እንድፈጽም ትፈልጋለህ? እኔ መርሆዎቼን መጣስ አልችልም::

-መርህ የምትለውን ነገር ወዲያ በልልኝ:: እኛ የምንጠቀምበት ከግቦቻችን ውስጥ አንዱን ማሳካት ስንፈልግ ብቻ ነው::

-ስለ መርህ ሳይሆን ስለ ሌላ ነገር እየተናገርክ ነው የሚመስለኝ፣መርህ ግን ሊጣስ አይችልም::

-ወደ ቴል አቪብ ስሄድ ሌቪ ሁሌ ከኔ ጋር ታድር እንደነበረ ታውቃለህ? እሷም ከማንም በላይ ነው ስለ መርህ የምትናገረው::

-ሰብአዊ ድክመት እንጂ ሌላ አይደለም::

-ይህ የመርህ ፍልስፍና ነው:: አንድን ዓለማ ማሳካት ስንፈልግ መርህ ነው እንላለን፤ሌላ ነገር ስንፈልግ ደግሞ የሰው ልጅ ድክመት ነው እንላለን::

የካኽ አነጋገር የጆርጅን ልቦና ነክቷል፤ትክክለኛ አነጋገር ነው:: እርሱ ራሱ ለብንያሚን ጉቦ አቀብሎ በሰብአዊ ድክመት አመካኝቷል፤እናም እርሱ ራሱ ካኽ በመርህ ላይ የሚከተለውን ንድፈ ሀሳብ ተከትሎ እየሄደ ይሆን?

-ሊሆን ይችላል፤ይሁን እንጂ ፍላጎቴን እስካላረካልኝ ድረስ መርህ ለምኔ የሚለው አቋም አደገኛ ነው:: መርህ የሌላት ሕይወት ከሁሉም የከፋች እኩይ ሕይወት ናት:: በዚህ ሁኔታ ከእንስሳት ብዙ የተለየን አንሆንም::

-እህህ፣ይቅርታ አድርግልኝና እንስሳት ከሰው ልጆች የተሻሉ ናቸው፤ከፈለግህ መርህ በለው የማይለወጡ ቋሚ ተፈጥሯዊ ነገሮች አሏቸው::

-ልክ ነህ . . መርህና ስነ ምግባራዊ እሴት የሌላቸው ሰዎች ከእንስሳትም የከፉ ናቸው:: ከሀብት፣ከወሲብና ከሥልጣን ውጭ ምንም ወደማያሳስባቸው አውሬነት ይለወጣሉ::

-የመርህ ጠበቃው፣ድንቅ ሌክቸር ነው:: አሁን ይህን እርሳውና ለሥራ ተሰናዳ፤ውል ለመፈራረም ወደ ስዊድን አዲስ ጉዞ ለማድረግ ዝግጁ ነህ?

-ወደ ስዊድን አዲስ ጉዞ?

-አዎ . . ከአንድ ሳምንት ያህል በኋላ:: የሥራ አመራር ቦርዱ ካንተ በስተቀር ሌላ ሰው እንዳይሄድ በሙሉ ድምጽ ተስማምቷል፤ለዚህ ነው አንተ እስክትመለስ ብሎ ካንድ ጊዜ በላይ ቀኑን ያራዘሙት::

-የምን ውል ነው?

-ከሞላ ጎደል ከቴል አቪቩ የኮንትራት ውል ጋር ተመሳሳይ ነው፤የሚፈረምበት ሁኔታም በጣም የተመሳሰለ ነው::

-እንዴት? አልገባኝም !

-ካንተ ዲፕሎማሲያዊ ክህሎት ጋር ለቴክኒካል መምሪያ ኀላፊው በግል የሚሰጥ ገንዘብ ይኖራል፤ነገሩ በዚሁ ያበቃና ስምምነቱ ይፈረማል::

-የፈለከው ገብቶኛል፤እዚያ ያለው የቴክኒክ መምሪያ ኀላፊ ሌላው ብንያሚን ነው ማለት ነው:: ግና ሌላ ሌቪ በስዊድን ትኖር ይሆን?

-እህህ . . ከሌቪ ጋር አልተዝናናሁም ብለህ የለም? ለምንድነው ሌላዋን የስዊድን ሌቪ የምትፈልገው? መርህስ የት ገባ?

-እንደዚያ ማለቴ አይደለም፣የሚያመሳስሉ ነጥቦችን መፈለጌ ነው::

-አዎ . . ስዊድንም ሌቪን የመሰለች አለችልህ፣ስሟ እንግሪድ ነው፤እርግጠኛ ሁን ልክ እንደ ሌቪ በጣም ውብ ቆንጆ ናት::

-መልካም፣እምቢታዬ በቆንጆዋ ምክንያት ነው ብለህ አታስብ::

-አልገባኝም::

-አልሄድም፤ችግሩን ግን ቀያይ የጭፈራ ምሽቶች አለመኖር አድርገህ እንዳትረዳ::

-ለምንድነው የማትሄደው?

www.path-2-happiness.com

-የመርህ ጠበቃ የሚል ስያሜ ሰጥተሀኝ የለም? ጉቦ ከኔ መርህ ጋር ይጻረራል።
-የመርህ ጠበቃው፣ውሉን እንዲፈርም ለብንያሚን ገንዘቡን ሰጥተሀ የለም? !
-አዎ፣ግን ተሳስቻለሁ፤ካሻህ ሰብአዊ ድክመት ነው በለው።
-ግቦቻችንን ለማሳካትና ጥቅሞቻችን ለማስከበር ብቻ ነው መርህን የምንገለገልበት አላልኩህም ነበር? ምንድነው የምትፈልገው?
-ምንም አልፈልግም፤በቃ መሄድ አልፈልግም።
-በቀጣይ የሚሰጥህ ጉርሻ ያለፈው እጥፍ ይሆናል ብልህስ? የሦስት ወር ደሞዝ ያህል ነው።
-ችግሩ እሱ ሳ . .
-አሁን መልስ እንድትሰጠኝ አልፈልግም። እንድታስብበት ሁለት ቀን ሰጥቼሃለሁ፤ይህን መልካም አጋጣሚ እንደማታበላሽ እርግጠኛ ነኝ።
-መልካም አጋጣሚው ምን ይሆን?
-ጉዞ፣ጠቀም ያለ ጉርሻና የሥራ እድገት።
-የሥራ እድገት? !
-አዎ፣በአዲሱ መዋቅር መሰረት - የስዊድኑን ውል ፈርመህ ከመጣህ - የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ትሆናለህ፣የኔን ቦታ ትይዛለህ። የሥራ አመራር ቦርዱ ለሥራ ክንውንህ ከፍተኛ አድናቆት አለው።
-አንተሳ? !
-የኩባንያችን ባለንብረት ለሆነው እናት ኩባንያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ልሆን እችላለሁ። ረጋ ብለህ አስብበት፤ይህን መልካም አጋጣሚ እንደማታበላሽ እርግጠኛ ነኝ። የጉዞ ሰሌዳውን እንደሚመችህ ማስተካከል ይቻላል። እህህ፣መርህ ማለትም የሚሰጠውን ገንዘብ ማድረስ ወይም በአንተ ትርጓሜ ጉቦውን መስጠት ይሆናል።
-ባልሄድስ? !
-በዚህ ኩባንያ በራስህ ላይ ወንጀል የፈጸምክ ትሆናለህ። አንተን የመሰለ አስተዋይ ይህን ያደርጋል ብዬ አላስብም። እመነኝ እኔ ራሴ ለመሄድ እፈልግ ነበር፤የሥራ አመራር ቦርዱ ግን በአንተ ላይ ከፍተኛ እምነት በመጣሉ ትላልቅ ኮንትራቶችን ለመፈራረም አንተ መሄድ አለብህ በሚል አቋሙ ገፍቶበታል።
-በቀናት ውስጥ መልስ እሰጥሃለሁ።

-በአእምሮህና በአስተዋይነትህ እተማመናለሁ፤በመሆኑም የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ ካሁኑ አስፈላጊውን የጉዞ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግልህ አዛለሁ። የኮንትራት ሰነዶቹና አስፈላጊ ወረቀቶች ከተሟላ ዝርዝር የውል ስምምነት ረቂቆች ጋር ወደ ቢሮህ ይደርሳሉ።
-ፍቀድልኝና ወደ ሥራ ልመለስ።

‹‹ ካኽ እንዳለው እውን መርህና መልካም ስነ ምግባር አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ የምንለዋውጣቸው መጠቀሚያና መገልገያ ናቸው? ወይስ የምንመራባቸውና መንገድ የሚያሳዩን ቋሚ የብርሃን ማማዎች ናቸው? እንዲህ ከሆነ ለብንያሚን በቴል አቪቭ ጉቦውን ለምን ሰጠሁ? የጉዞው ጉዳይ ካኽ ዘንድ በጣም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን በሥራው ለመቀጠል ወይም ለመልቀቅም ወሳኝ ነጥብ ሳይሆን አልቀረም . . መርሆ እውነት ዋጋ የለሽ ከሆነ እርስ በርሳቸው ወደሚባሉ አራዊትነት እንለወጣለን ማለት ነው። ዋይ . . ፈጣሪ እነዚህን ነገሮች ለምን አላደራጀም? ወይስ ሰዎች እርሱን አግልለው ጉዳዮቻቸውን በገዛ ራሳቸው እንዲያደራጁ ነው የተወላቸው?!››

ብሎ ራሱን እየጠየቀ ጆርጅ ወደ ቢሮው ተመለሰ።

በሀሳብ ተጠምዶ እያለ ጉዞውን የሚመለከቱ ሰነዶችና የጉዞ ወረቀቶች ተጠቃለው ወደ ቢሮው ተላኩለት። ለርሱ ይበልጥ አስፈላጊው ጉዳይ እጓዛለሁ ወይስ አልጓዝም? የሚለው ውሳኔ በመሆኑ ወረቀቶቹን በግድ የለሽነት አየት አየት አደረጋቸው። የማይጓዝ ከሆነ ለማንበብ ለምን ይደክማል?

ጆርጅ ወደ ቤት ተመልሶ በጉዞው ውሳኔ ላይ ካትሪናን ለማማከር፣ከተለመደው በላይ በጣም ረዝሞ የታየውን የዕለቱን የሥራ ሰዓት ማብቂያ ሲጠብቅ ቆይቶ ወደ ቤቱ ሄደ። ካትሪናን በከፍተኛ ተመስጦና በጢሞና በማንበብ ላይ ሆና አገኛት . .

-የምታነቢው መጽሐፍ በጣም አስደሳች ሳይሆን አይቀርም!
-በተወሰነ ደረጃ፣የሙስሊሞችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው የማነበው።
-ማንበቡን ጀመርሽ ማለት ነዋ!
-አዎ፣በጢሞና ያነበብኩትና የተረዳሁት ቢሆንም ያንዱን ምዕራፍ ትርጉም ካንድ ጊዜ በላይ ደጋግሜ ሳነብ ነው ራሴን ያገኘሁት።
-ለምን?
-እኔ እንጃ፤ምናልባት ከለመድኩት ዓይነት ሙሉ በሙሉ የሚለይ በመሆኑ ሊሆን ይችላል . . !
-መልካም . . ይህን ርእስና መጽሐፉን ለጊዜው ተወት እናድርግና

www.path-2-happiness.com

የማማክርሽ ብርቱ ጉዳይ አለኝ::

-መቀጠል ትችላለህ::

-ካኽ ሌላ አዲስ የሥራ ጉዞ እንዳደርግ ጥያቄ አቅርቦልኛል::

-በዚህ ኩባንያ ሥራ ከጀመርክበት ጊዜ ወዲህ የሥራ ጉዞዎች እንዲህ ተከታትለው ሲመጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፤ለመሆኑ ወዴት ነው?

-ወደ ስዊድን ነው::

-ስዊድን ማራኪ አገር ነች::

-ችግሩ ይኽ አይደለም::

-ታዲያ ችግሩ ምንድነው?!

-የኮንትራት ውሎችን ለመፈራረም ወደ ኢየሩሳሌም በተጓዝኩበት ወቅት እዚያ ለሚገኘው ኩባንያ ሥራ አስፈጻሚ ውሉን በቀላሉ ይፈርም ዘንድ ትልቅ ጉቦ ይዤለት ነበር የሄድኩት:: በዚህ የስዊድን ጉዞም ይህንኑ ዳግም እንዳደርግ ነው የሚፈልጉት::

-ጉቦን የማወግዝና የምጠላው ከመሆኑም ጋር ምኑ ነው አዲስ የሆነብህ?! ቀደም ሲል ሰጥተህ የለም?

-ይህማ ቃል በቃል የካኽ አነጋገር ነው::

-ያን አለቃህን እጠለዋለሁ፤ግና . .

-በመጀመሪያው ዙር ተሳስቼ ብሆን ስህተቱን አሁንም መድገም አለብኝ?! ሰዎች ከጥፋቶቻቸው መታረም የሚችሉበት መንገድ የለም እንዴ?

-በክርስትና ውስጥ ኢየሱስ ለሰው ልጆች ብሎ ራሱን በመሰዋቱ እኛን ከኃጢአት ነጻ አድርጎን አጸድቶናል::

-ይህ ለአንድ የተለየ ግለሰብ ሳይሆን ለአጥፊውም ለሌላውም ነው::

-አልገባኝም::

-ማለት ሁላችንም በኢየሱስ ደም አንዴ ከኃጢአት ነጻ ወጥተናል፤የመድህን ዋስትና እስከተሰጠን ድረስ ኃጢአት መሥራትን ለምን እንተዋለን?! ይህ ለምህረት ምስክር ወረቀት ንግድ ጥሩ መግቢያ ይመስለኛል::

-ማለት የፈለከው ገብቶኛል፤በክርስትና ዘንድ ነገሩ እንዲህ ነው:: በእስላም ዘንድ ግን በፈጸመው ኃጢአት ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ምህረት ያገኛል::

-እንዴት ያለ ፈጣን እርምጃ ነው? ስለ እስላም መናገር ጀመርሽ? ይህ ሁሉ አንድ መጽሐፍ ብቻ ካነበብሽ በኂላ?! ሙስሊሞች ንስሐ የሚገቡት በመነኮሳትና ቀሳውስቶቻቸው ዘንድ ነው? ከኀጢአት የመንጻት ቅዳሴ

የሚደረገው እንዴት ነው?

-ምንም ዓይነት ቅዳሴ የለም፤በቀጥታ ወደ ፈጣሪ አምላክ ተመልሰህ ምህረት እንዲያደርግልህ መለመን፣ኃጢአቱን እርግፍ አድርገህ መተውና ሁለተኛ ላትመለስበት በቁርጠኝነት መወሰን ብቻ ነው::

-እንዲህ በቀላሉ!

-አዎ::

-ይህን ሁሉ ያገኘሽው ሙስሊሙ ሰውዬ ሮም ላይ ከሰጠሽ መጽሐፍ ነው?!

-ቁርኣን ብለው ከሚጠሩት የሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ ነው እንጂ::

-መልካም፣ወደ ካኽ ጉዳይ እንመለስ::

-እኔ እንጃ፣አስቸጋሪ አመራጮች ናቸው፤መርህን ጥሰህ ያሉህን በመቀበል ለገዛ ህሊናህ ተጠያቂ ተወቃሽ መሆን ነው፣አልያም እምቢ ብለህ ሥራህን ማጣት ነው::

-አዎ አስቸጋሪ ምርጫ ነው፣ምላሽ ለመስጠት የሁለት ቀን ጊዜ አለኝ:: በኔ ቦታ ብትሆኚ ግን ምን ታደርጊ ነበር?

-እኔም በበከሌ እንዳንተው በግራ መጋባት ሁኔታ ውስጥ ነኝ፤እኔን በሚመለከት የግል ጉዳይ ላማክርህ ነበር፤ስለ ቀደምከኝ ግን በሁለት ግርታዎች ላስጨንቅህ አልፈልግም::

-እንዴት?

-ትምህርት ቤት የማስተምረውን ነገር እንደ በፊቱ አሳማኝ ሆኖ አላገኘሁትም፤በመሆኑም ሥራዬን ለመልቀቅ እያሰብኩ ነው::

-ሥራሽን ትለቂያለሽ?!

-አንተ መርህን መጣስ እንደማትወድ ሁሉ እኔም መርሆዬን መጣስ አልሻም:: በማስተምረው አብዛኛው ነገር እምነት አጥቻለሁ፣ወይ የማላምንበትን ነገር ለሌሎች በማስተማር መርሆዬን መጻረር፣አልያም የሥራ መልቀቂያ ማቅረብና ከነሱ የማገኘውን የወር ገቢ ማጣት ነው::

-ይህ ከፍተኛ ለውጥ ነው፣ባለፉት አስር ዓመታት ይህንኑ ስታስተምሪ አልነበረም? ምኑ ነው አዲስ? ሁለታችንም ሥራ ከለቀቅን በእንግሊዝም ሆነ በዓለም ደረጃ እየተባባሰ በመጣው የሥራ አጥነት ሁኔታ ውስጥ እንዴት መኖር እንችላለን?

-አዲሱ ነገር በካቶሊካዊነት ላይ ያለኝ እምነት የተናጋ መሆኑ ነው:: ይህን አይደለም የፈለከው?! ለማንኛውም ግን እስካሁን አልወሰንኩም::

-አስከፍቼሽ ከሆነ አዝናለሁ፣ለቀልድ ያህል ነው::

www.path-2-happiness.com

- ማስከፋት ሳይሆን በተቃራኒው ከዓይኔ ላይ ያለውን ግርዶሽ ነው ያስወገድክልኝ:: የበለጠ ግራ እንዳላጋባህ ልነግርህ አልፈለኩም ብየህ አልነበረም?
- ልክ ነሽ፣በግርታዬ ላይ ግርታ ነው የጨመርኩት . . ደጋግሜ አስብበትና በሁለት ቀናት ውስጥ እወስናለሁ:: አንቺም ከውሳኔ ላይ መድረስ አለብሽ:: እውነቱን ለመናገር ሕይወት በጥቅሉ ውሳኔ ናት . .
- ጆርጅ በዚህ ጉዳይ ላይ ሰዎችን ማማከር ይኖርብሃል::
- በሥራ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ከውስጥ መረዳት የሚችል ማን ይኖራል?
- ከወዳጆችህ መካከል አንድ ሊኖር ይችላል:: በመደበኛ የኢሜይል መልእክት ዝርዝር ለሁላችንም ለምን ጥያቄ አትልክልንም?
- ድንቅ ሀሳብ ነው፣አሁኑኑ እልካለሁ::

ጆርጅ ወደ ቢሮ ክፍሉ ሄዶ ኮምፒውተሩን ከፈተ፤ለወዳጆቹ ምክር ይለግሱት ዘንድ መልእክት ላከላቸው ፦

‹‹ሰባተኛው ዙር ፦ አንድ ችግር ስለ አጋጠመኝ ለስድስተኛው ዙር ምላሽ ከመስጠታችሁ በፊት ምክር እንድትሰጡኝ ወደድኩ:: ችግሩ በአጭሩ ፦ ቁሳዊ ሕይወቴ ቢጎዳም ለመርሆዎቼ ታማኝ ልሆን? ወይስ መርሆዎቼን ረግጬም ቢሆን ለጥቅሜ ትኩረት ልስጥ? ራሳችሁን በኔ ቦታ አድርጋችሁ በመውሰድ መልሳችሁ ግልጽና ቀጥተኛ እንዲሆን ምኞቴ ነው:: ግላዊ ጥቅሞችና መርሆዎች የማይጋጩበትና የሚጣጣሙበት መንገድ ይኖር ይሆን?

ጆርጅ››

መልእክቱን ከላከ በኋላ የቶምን የፌስቡክ ገጽ ከፈተ፤ወደ ቀድሞ ቦታው ተመልሶ አገኘው:: በገጹ ላይ ታትመው ለነበሩ ሐሰተኛና ቆርጦ ቀጠል ፎቶዎች ይቅርታ የሚጠይቅ ጽሑፍ ተለጥፎአል . . ቶም የፌስቡክ ሂሳቡን ለማስመለስና ከበራድ ጋር የነበረውን ችግር ለመፍታት የቻለ መስሎ ስለታየው ትንሽ እፎይታ ተሰማው:: ከዚያም የአደምን ገጽ ከፈተ፤‹‹የመታደልን መንገድ ለመገለግ ከተሰማራው ወዳጄ የሚቀሰሙ ትምርቶች 4›› በሚል ርእስ አዲስ መጣጥፍ ተለጥፎ አገኘ ፦

‹‹ወዳጄ ከሁሉም እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ወቅት ላይ ይገኛል::አሁን ባለበት የፍለጋ ደረጃ ላይ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስተዋል ይቻላል ፦

1. የሰው ልጅ ማወቅ የሚያስፈልገው ነገር ከማወቅ ይልቅ የማያስፈልገውን ነገር ማወቅ ይቀለዋል:: የመታደልን መንገድ ከማወቅም ያለ መታደልን መንገድ ማወቅ ይቀለዋል:: አዲስና መሰረታዊ ለውጥ ውስጥ ማለፍ

ለማንም ቢሆን አስቸጋሪ ነው::

2. የትኛውም ብርቱ ውሳኔ ድፍረትና ጀግንነትን ይጠይቃል:: ጀግንነት ለማንኛውም አመለካከታዊ፣ወታደራዊ ወይም ስነ ምግባራዊ ስኬት ወሳኝ ነጥብ ነው:: ወዳጄ ያለ ጥርጥር ጀግና ነው፣ነገር ግን አሁን ከቀድሞው የበለጠ ጀግንነት ያስፈልገዋል:: እናም እንደዚያ መሆን ይችል ይሆን?
3. ወዳጄና በዙሪያው ያሉት ብዙም ትኩረት በማይሰጡትና ልብ በማይሉት የለውጥ ሂደት ውስጥ ናቸው:: ይህም አስገራሚ ነገር ነው:: እስካሁን ድረስ እኔ ሙስሊም መሆኔን አያውቅም:: በጣም የሚቀርቡት ሰዎችም እንደሱ በከፍተኛ የለውጥ ሂደት ውስጥ መሆናቸውን ሲያውቅ መገረሙ አይቀሬ ነው::
4. ወዳጄ ለመማር ጉጉና ታታሪ ቢሆንም እስላምን የማወቅና የመመርመር ውሳኔ ላይ በቀላሉ አልደረሰም:: ምናልባት ለዚህ መንስኤው በመገናኛ ብዙኃን በእስላም ላይ የሚነዛው ሰፊ ውዥንብር ሊሆን ይችላል:: በከፊል ደግሞ ሙስሊሞች ራሳቸው ማድረግ የሚገባቸውን ባለ ማድረጋቸውና በስህተቶቻቸው ምክንያት ሊሆንም ይችላል::

አሁንም ቢሆን ወዳጄ በመታደል መንገድ ፍለጋ ጉዞውና ለትላልቆቹ የሕይወት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ላይ ነው የሚል እምነት አለኝ:: ቀጣዩን ትምህርት በቅርቡ ይዤላችሁ እመለሳለሁ::››

አደም››

ጆርጅ በአደም የተጻፈውን በድጋሚ በጢሞና አነበበው:: ‹‹አደም የመታደል መንገድ እስላም ብቻ ነው ብሎ ያምናል ማለት ነው?! ከሆነስ ከመነሻው ለምን አልነገረኝም ኖሯል? እያፌዘብኝ ይሆን? ወይስ እስላም በማታለል ላይ ይመሰረታል? እስላም እውን የመታደል መንገድ ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ ለምን ይደብቃል? ለምንስ ከኔ ይሸሽጋል?! የሚሸሹት አሳፋሪ ነገር ሆኖ ነው? ወይስ የቤተ ክርስቲያንን ሚስጥራት የመሰለ ሌላው የሃይማኖት ሚስጥር ይሆን?›› ሲልም ራሱን ጠየቀ:: በዚህ የሀሳብ ማዕበል ውስጥ እያለ ካትሪና መጣች . .

- ነይማ አደም ስለኔ የጻፈውን አንብቢ:: ይህን ግለሰብ መጠራጠር ጀምሬአለሁ::
- ምንድነው የጻፈው?
- ይኸው አንቢቢው::

ካትሪና መጣጥፉን በከፍተኛ ተመስጦ አነበበችውና ወደ ጆርጅ ዞር ብላ . .

-ጥርጣሬህ ምኑ ላይ እንደሆነ አልገባኝም !

-እርሱ ሙስሊም ነው፣ለኔ ታላላቅ የሕይወት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጠው የመታደል መንገድ እስላም ነው የሚል እምነት አለው።

-ልክ ነው፣ይኸ የተለመደ ነው፤የራሱን እምነት የመታደል መንገድ ነው ብሎ ማመኑ ተፈጥሯዊ ነው።

-ግና . . ለምን አስቀድሞ አልነገረኝም፣ለምን ያታልለኛል?

-ያልሆነ ነገር ነገሮህ አታልሎህ ያውቃል?

-የለም፣ግን ሃይማኖቱንና እምነቱን ከኔ ሸሽጓል።

-በግልጽ የነገረህ ይመስለኛል፣አንተ ነህ ልብ ያላልከው።

-እንዴት?

-በፌስቡክ ገጹ መረጃ ላይ ሃይማኖቱን ጽፎአል። ፈጽሞ አልደበቀም፣እንዲያውም ይኮራበታል። ሃይማኖት በሚለው ላይ ‹‹በእምነቱ የሚኮራ ሙስሊም›› ብሎ ጽፎታል።

-ታቂያለሽ ገጹን ብዙ ጊዜ እየከፈትኩ ይህን ልብ ብዬ አላውቅም። አደም እውነቱን ነው፣በበቂ ሁኔታ ነገሮችን አላገናዝብም።

-በላክልን መልእክት ሁላችንም ቁርኣንን አንብበን አስተያየት እንድንልክልህ ጠይቀህ አልነበረም? አንተ ራስህ ማንበብ ጀምረሃል?!

-ካኽ በችግሮቹ ወጥሮኝ ስለነበረ ገና አልጀመርኩም። ዛሬ ከአደም ጋር እገናኛለሁ፣ቁርኣንን ማንበብም ዛሬ እጀምራለሁ። በኩባንያው ሥራ መቀጠል አለመቀጠሌን ዛሬ ወይም ነገ ለመወሰን እሞክራለሁ።

-አደም ከኛ የተሻለ አዋቂ አይሆንም፣ይበልጥ ጠንከር ባለ ሁኔታ ምላሽ እንድንሰጠው ረጋ ብለህ የሚልህን አዳምጥ . . ምናልባት ሰልመን ከርሱ ጋር እስላምን እንድከተል ይፈልግ ይሆናልና ክርስትና ተነስቶ ከኛ ጋር እንዲሆን እናደርገው።

-ምናልባት ሊሆን ይችላል። አሁን ወደርሱ እሄድና በእርጋታ አዳምጬው ከርሱ ለመማር እሞክራለሁ፤እራትም አብረን ሳንበላ አንቀርም።

ለውጥና ሽግግር

www.path2-happiness.com

14 ለውጥና ሽግግር

ለውጥና ሽግግር

(1)

ጆርጅ አደምን ለማግኘት ወደ ካፌቴሪያው አመራ፣ግን አላገኘውም:: አስተናጋጁን ሲጠይቅ ዛሬ ያልመጣ መሆኑንና ለምን እንደ ቀረ እንደማያውቅ ነገረው . .

- ትናንት ተገናኝተን ለዛሬ ቀጠሮ ይዘን ነበር::
- ያወቅነው ነገር የለም:: አለመምጣቱ የሚገርም ነው፤ለማንኛውም ግን ነገ ይመጣ ይሆናል::

ጆርጅ ካፌውን ለቆ ሄደ፤በቀጥታ ወደ አደም ቤት በማምራት በሩን አንኳኳ፣የሚመልስ ሰው አልነበረም:: ስልክ ለመደወል ሲሞክር ሞባይሉ ዝግ ነው . . ነገሩ እያሳሰበው ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ . .

- ካትሪና . . አደም ጠፋ፣በሥራ ቦታውም ሆነ እቤቱም ሄጄ ሳገኘው አልቻልኩም፣ሞባይሉም ዝግ ነው::
- ይህ የመጀመሪያው አይደለም፣ትዝ ካለህ ከዚህ ቀደምም እንደዚሁ ጠፍቶብህ አልነበረም?
- ልክ ነሽ፣በሽብር ፍንዳታው ምክንያት በሀሰት ተጠርጥረው ታስረው ከነበሩት መካከል አንዱ ነበር መሰለኝ፣ነገር ግን ሙስሊም መሆኑን አላውቅም ነበር::
- ከአደም ጋር ብዙ አንተዋወቅም፣ግን በጣም ነው የማከብረው:: በታመምክ ጊዜ ላንተ የነበረውን አዘኔታና እንድትፈወስ የነበረውን ከፍተኛ ጉጉት አስተውያለሁ:: የካኽን ወራዳ ባህሪ ያስተናገደበትን ጨዋ ስነ ምግባሩንም ተመልክቻለሁ::
- አንቺ ስለ እርሱ የማታውቂውና እኔ በሚገባ የማውቀው ለኔ በጎውን የሚመኝልኝና የሚያስብልኝ ፍጹም ወዳጅ መሆኑ ነው:: ይህን ከአንድ በላይ በሆኑ አጋጣሚዎች ለማየት ችያለሁ፤ይህን ሁሉ ክብካቤና ፍጹምነት ለምን እንደሚሰጠኝ ሳስብ እገረማለሁ::
- ምኑ ነው የሚገርመው?!
- ክርስቲያን አለመሆኑን እስካወቅበት ጊዜ ድረስ የሚገርም አልነበረም::
- አልገባኝም፣ ለምን? !

www.path-2-happiness.com

-ወደ ቴል አቪቭ እንድሄድና አይሁዳዊነትን እንዳጠና ይገፋፋኝ የነበረው እርሱ ነው:: ክርስትናን እንዳጠናና ወደ ሮም እንድሄድ የገፋፋኝም እርሱ ነው:: ለራሱ ክርስቲያን ሳይሆን ይህን እንዴት ሊያደርግ ቻለ?

-ምናልባት ይህ በራስ የመተማመን ምልክት ሊሆን ይችላል::

-ወይም በስልቱ እርግጠኝነትና በሚከተለው መንገድ ካለው በራስ የመተማመን መንፈስ የመነጨ ሊሆን ይችላል::

- ሊሆን ይችላል፤በጥቅሉ ግን ቁርኣን በጣም ልዩ የሆነ መጽሐፍ ነው:: በመልክትህ እንደ ጠቀስከው በዚህ ሳምንት አታነበውም?

-ቀደም ብዬ እንደ ነገርኩሽ ማንበብ እፈልግ ነበር፣የካኽ ጉዳይ ነው የረበሸኝ፣አሁን ደግሞ የአደም መሰወር:: ለማንኛውም ወስጄ እንዳነበው አንብበሽ ጨረስሽ?

-አዎ ጨርሻለሁ፣አንዳንድ ነገሮችን ግን ደግሜ ማየት የግድ ይመስለኛል:: ሌላ ቅጂ እንዲገዛልህ ትፈልጋለህ?

-በመጽሐፍት መሸጫ መደብር ካለፍሽ አንድ ግዥልኝ:: በነገራችን ላይ ቁርኣን መጀመሪያ የተጻፈው በምን ቋንቋ ነው?

-በዐረብኛ ቋንቋ ብቻ ነው::

-ታድያ እንዴት ነው ያነበብሽው?

-ትርጉሙን ነው የማነበው::

-ብሉይና አዲስ ኪዳንንም ትርጉማቸውን አይደለም አነበብን የምንለው? ልዩነቱ ምኑ ላይ ነው?

-በላክልን ደብዳቤ በጠየቅከን መሰረት ጉዳዩን በዚህ ርእስ ላይ አንብቤ ለመመርመር ችያለሁ:: እናም ቁርኣን በታሪክ ውስጥ አቻ በሌለው የተአማኒነት ሁኔታ ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ መጽሐፍ ነው:: ከነብያቸው ከሙሐመድ ቁጥራቸው የበዛ ሰዎች ሰምተውና መዝግበው ለሌሎች አስተላልፉት፣በዚህ ሁኔታ ሲወርድ ሲዋረድ ነው እስከ ዛሬው ዘመናችን የደረሰው:: ምንም ዓይነት ስህተትም ሆነ የመለወጥ ችግር ፈጽሞ ሳይደርስበት ባለበት ተጠብቆ ለመኖር የቻለ መጽሐፍ ነው:: ትርጉሞቹ ግን ስህተት ሊኖሩባቸው ይችላል ::

-እንዴት?

-አያሌ ቀሳውስት የቁርኣንን ፍች የተረጎሙ ሲሆን ትርጉማቸው ግን በዘፈቀደ የተሰራ ነው:: አንዳንዶቹ ትርጉሞችም ስህተት አለባቸው::

-እናም . . ቁርኣን በተለይ ለዐረቦች ነው፣ከርሱ ውጭ ያለው ሁሉ የተዛባ

ነው ማለት ነው?

-ሊሆን ይችላል፣እኔ ግን እንዲህ አላልኩም ! ቁርኣን ራሱ ብዙ ቦታ ላይ ለዐረቦች ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ልጆች የተላለፈ መሆኑን ያመለክታል:: ብዙዎቹ ትርጉሞቹ በጣም ጥሩ ሲሆኑ ልዩነቶች ሲያጋጥሙ ግን ማመሳከሪያው የዐረብኛ ቅጂው ብቻ ነው:: የሚያስቀው ግን የዐረብኛው መጽሐፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈው በጽሑፍ መልኩ ወይም በቃል በመወጣት ብቻ ሳይሆን፣የተለየ የአነባበብ ስልቱም ጭምር በድምጽ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ መሆኑ ነው::

-ለትርጉም ትክክለኛነት መመዘኛው ምንድነው?

-ተርጓሚው የሚተረጉመው የቁርኣንን ፍች እንጂ ቁርኣንን አይደለም:: ቁርኣን በዐረብኛ ብቻ ነው ወደ ሌላ ቋንቋ የሚመለሰው ቁርኣኑ ሳይሆን ፍቺው ነው:: ለማንኛውም ስታነበው ይህንን ትረዳለህ::

-ስለ ደከመኝ መታኛት፣ስለራበኝም እራት መብላት እሻለሁ:: የአደም ነገርም ስለ አሳሰበኝ መረጋጋት፣ግራ ስለ ተጋባሁ ለካኽ ምላሽ መስጠትና ስለ ናፈቅኋት ፍቅሬንም ማግኘት እፈልጋለሁ:: አንቺ ደግሞ የቁርኣን ትርጉሞችን በማንበብ ተጠምደሻል !

ካትሪና ፈገግ አለች፤በመሽኮርመም ቅላጼ እንዲህም አለች ፦

-እንግዲያውስ በእራቱ እንጀምርና ከዚያ ፍቅሩን እናስከትል፤የተቀረውን ለሌላ ጊዜ እናቆይ::

ጆርጅ አማልዶ ከእንቅልፉ ተነሳና ወደ ሥራ ለመሄድ ተዘጋጀ:: እየከበደውና ጥላቻ እየተሰማው ወጣ:: ይህ ስሜት በካኽ ምክንያት ይሁን ወይም ገና እልባት ባላገኘለት የግራ መጋባት ሁኔታ? አያውቅም::

ወደ ቢሮው እንደገባ በቀጥታ ለአደም ደወለ:: ሞይባይሉ አሁንም እንደ ተዘጋ ነው:: አጭር የጽሑፍ መልክት ላከለት . . ከደቂቃዎች በኋላ ካኽ ደውሎ ወደ ቢሮው እንዲመጣ ጠየቀው . .

-የዓለምን ጣጣ ሁሉ በራስህ ላይ የተሸከምክ መሰልክ፣ምን ነክቶሃል?

-ምንም፣ትንሽ ድካም ተሰምቶኛል::

-ከፊትህ የሚነበበው ውጥረትስ !

-ምንም የለም፤ግን አንድ ውድ ወዳጄን አጥቼ እያፈላለኩት ነው፣መሰወሩ አሳስቦኛ ነው::

-በሥራ ቦታው፣በቤቱና በጓደኞቹም ዘንድ ፈልገሃል?

-አዎ፤የሚገርመው ነገር የካፌ የሥራ ባልደረባው አስተናጋጅ እንኳ

ባልተለመደ ሁኔታ አለመምጣቱን ሳይናገር መቅረቱ ያስገረመው መሆኑ ነው።

- እህህ፣ውዱ ወዳጅህ ! አንተ ዘንድ ሆስፒታል ያገኘሁት አስተናጋጅ ነው? !
- አዎ።
- ከሆስፒታሉ ላባርረው ምንም አልቀረኝም ነበር፤እንዴት ከካፌ አስተናጋጅ ጋር ትወዳጃለህ? !
- እንዲያውም ካትሪና ነበረች ትእቢትህን ስታሳየው ልታባርርህ ምንም ያልቀራት። አደም ከወዳጆቼ ሁሉ ምርጡ ወዳጄ ነው፤ስለርሱ በዚህ ሁኔታ ስትናገር አያስደስተኝም።
- አንተ ለኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ለመሆን የታጨህ ሰው ነህ፤እንዴት ስለ አስተናጋጅ ጓደኛ ትናገረኛለህ? በሥራ መስክ ሙያዊ ብቃትህ የላቀ ቢሆንም ማህበራዊ ብቃትህ ግን በጣም ደካማ እንዳይሆን ስጋት አለኝ። የሚያሳዝነው በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ላይ ማህበራዊ ብቃትና ክህሎት ከሥራ ብቃትና ክህሎት የበለጠ አስፈላጊነት ያለው መሆኑ ነው።
- ማህበራዊ ንቁነትና ብቃት ሰዎችን በግርድፍ አስነዋሪ አቀራረብ በትእቢት ማናገር ነው? !
- ገቢህንና የሥራ ዕድልህን የሚያሰፉልህን ሰዎች የመያዝ ብቃትና ክህሎት እንዲኖርህ ማለት ነው።
- ወዳጅነት ለአንተ ዕድሎችን መፍጠር፣ሀብትና ገቢን መጨመር ነው?
- አዎ፣ወዳጅነት ብቻ ሳይሆን ሕይወትም በሁሉም ገጽታዋ እንደዚያ ነች። ይህ መቼ እንደሚገባህ ግን አላውቅም?
- ማወቁንም አልፈልግም።
- ወዳጄ አታክርር፣መቼ ነው የምትጓዘው?
- ባንተ ወዳጅነት አልኮራም፤የአደም ወዳጅነት ግን ለኔ ከምንም በላይ ምርጥ ወዳጅነት ነው።
- እህህ፣እኔን የሚያሳስበኝ ሥራህ እንጂ ወዳጅነትህ አይደለም፤መቼ ነው ወደ ስዊድን የምትጓዘው?
- ነገ መልስ እሰጥሃለሁ፤ፍቀድልኝ ልሂድ።
- የአይሮፕላን ትኬት ገዝተንልሃል፣ከሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈጻሚው ከዊልያም መቀበል ትችላለህ . . እህህ፣ አስተናጋጁን ስታገኘው ግን የምስራቹን ንገረን።

ጆርጅ ራሱን እየወቀሰ ወደ ቢሮው ተመለሰ። መርሁን እንደማይጥስና እንደማይጓዝ ለካኽ በቀጥታ ለመንገር ለምን ድፍረት አነሰው? ሥራውን እንዳያጣ ፍርሃት አድሮበት ይሆን? እንግዲያውስ እርሱም ያው እንደ ካኽ ገንዘብ ያስጨንቀዋል ግን ከመርህ ጆርባ ይደበቃል ማለት ነው . . ከርሱ ይልቅ ካኽ ለገዛ ራሱም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ይበልጥ ግልጽ ነው ማለት ነው። ‹‹መርህን የሙጥኝ የምንለው ለግል ጥቅማችን የሚያገለግል ሲሆን ከጥቅማችን ጋር ሲጻረር ግን እንጥሳለን›› ሲል እውነቱን ሳይሆን አይቀርም . . ወደ ካኽ ተመልሶ ያበጠው ይፈንዳ ውሳኔውን ለመንገር አሰበ፣ግና መለስ አለና ይይቅርታ ደብዳቤ ለመጻፍ ወሰነ . . በዚህ መሀል የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ዊልያም ከተፍ አለ . .

- እንካ እነዚህ የአይሮፕላን ትኬቶች ከካኽ የተላኩ ናቸው።
- ፍላጎት ሳይኖረኝ እኔ እንድሄድ ካኽ እንዲህ ለምን እንደሚጓጓ በጣም ይገርመኛል . . እስከማውቀው ድረስ አንተ ወይም የሽያጭና ገበያ ሥራ አስኪያጁ እንዳትጓዙ የሚከለክል ነገር የለም፣እንዳውም በዋናነት የናንተ መደበኛ ሥራ እንጂ የኔ አይደለም !
- ተገዶ ነው እንጂ ራሱ ፈልጎት አይደለም።
- እንዴት? አልገባኝም !
- አንተ ቴል አቪቭ በነበርክበት ጊዜ የሥራ አመራር ቦርድ ወደ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት ከፍ እንድትልና ካኽ ወደ ሌላ እህት ኩባንያ እንዲዛወር በስብሰባ ወስኖ ነበር። ካኽ ይህ ውሳኔ እንዲዘገይ ለማድረግ ሲል የዘየደው መላ ካንተ በስተቀር ሌላ ሰው ሊያከናውነው የማይችል ተልእኮ መኖሩን መንገርና ውሳኔው እስከዚያ እንዲቆይ ቦርዱን ማሳመን ነበር።
- እኔ ተልእኮውን የማልፈጽም ከሆነስ?
- እኔ እንጃ፤እኔ መሄድ እፈልግ ነበር ግን አልተቀበለም። ቲኬቶቹን ያዛቸው፣ቦታ የተያዘልህ ከዘጠኝ ቀን በኋላ ነው።
- አሁን ነገሮች ግልጽ እየሆኑልኝ ነው፤ለምን ችክ እንዳለ አሁን ተረዳሁ። የስዊድኑን ደንበኛ ስልክና አድራሻ ልትልክልኝ ትችላለህ?
- ከአምስት ደቂቃ በኋላ ኢሜይልህ ላይ ታገኘዋለህ።
- የሁሉም የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ስልክና ኢሜይልም ላክልኝ።
- እልክልሃለሁ።
- ዊልያም አመሰግናለሁ።

ጆርጅ ደብዳቤውን መጻፍ ጀመረ፣አድራሻውን ለካኽ ማድረግ ትቶ ለሥራ

www.path-2-happiness.com

አመራር ቦርድ አደረገው ፦

‹‹የተከበራችሁ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

ለአስራ አራት ዓመታት ያህል የቆየሁበትን ኩባንያ በማገልገሌ ክብር ይሰማኛል። በኔ ላይ ለጣላችሁት እምነትም አክብሮቴ የላቀ ነው። ለዚህ የመታመን ደረጃ ተገቢው ሰው ሆኜ መገኘት ምኞቴ ነው። ኩባንያችንን ስኬታማ ማድረግ የሁላችንም ኃላፊነት ነው። ለኩባንያው ማበርከት የቻልኩትን እንዳበረክት ላስቻለኝ የዘውትር ድጋፋችሁ ያለኝን ከፍተኛ አክብሮትና ግምት እንድገልጽ ይፈቀድልኝ።

የሙያ ስነ ምግባሬንና የራሴን መርሆ የማልጥስ ከሆነ ከሥራ እንደምባረር ባልጠበቅሁት ሁኔታ ማስፈራሪያ ስለ ደረሰብኝ፣እናንተም ጥረቴን ግምት ውስጥ ታስገባላችሁ ብዬ በማሰብ የሥራ መልቀቂያ አቀርቤአለሁ። የሚገባኝ ሁሉ ተጣርቶ እንደሚሰጠኝም ተስፋ አደርጋለሁ። ሥራ መልቀቄ ለኔም ሆነ ለኩባንያው ስም ከመባረር የሚመረጥና መርሆዎቼንም በጥቅም ከመሸጥ የተሻለ ነው።

ላደረጋችሁልኝ ትብብርና መልካም አያያዝ ሁሉ ሁላችሁንም አመሰግናለሁ።

ጆርጅ ኒሶን››

ደብዳቤውን ጽፎ ሲጨርስ የተላከለትን የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን አድራሻ ኢሜይሉ ላይ አገኘ። ካኽንም ጨምሮ ደብዳቤውን ለሁሉም የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ላከላቸውና ወዲያውኑ ግቢውን ለቆ ወጣ . . ወደ አደም መኖሪያ ቤት ሄዶ ማንንም አላገኘም። ወደ ካፌው አመራ፤እዚያም አላገኘውም፤አስተናጋጅ ባልደረባውን ሲጠይቅ እንዲህ አለው ፦

- አንተ ነበርክ ትናንት የመጣህ? ዛሬም አልመጣም፤ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከአንድ ሰዓት ያህል በፊት ደውሎ የመኪና አደጋ ደርሶበት ሆስፒታል መሆኑንና ጤንነቱ በመሻሻል መሆኑን ነግሮናል።

(2)

ጆርጅ የሆስፒታሉን አድራሻ ጠይቆ በቀጥታ ወደዚያ ሄደ። እየሄደ ለካትሪና ደውሎ ነገራት . .

- ታምሜ ሆስፒታል ሳለሁ በአስገራሚ ሁኔታ ነበር ከጎኔ የቆመው፣እናም ውለታውን መመለስ ይኖርብኛል።
- በዚህ በኩል ብታልፍና አብረን ብንጠይቀው ምን ይመስለሃል?
- አሁን ወደ ሆስፒታሉ የተቃረብኩ ስለሆነ እኔ አሁን ልጎብኘውና አንቺ

በማታው የሕሙማን መጠየቂ ጊዜ ልትጠይቂው ትችያለሽ።

ጆርጅ ወደ ሆስፒታሉ ደርሶ የአደምን ክፍል ጠይቆ ወደዚያ አመራ። ወደ ክፍሉ ሲገባ አደምን እግሩ ሙሉ በሙሉ በጀሶ ተጠቅልሎና ብዙ ሰዎች ከበውት አልጋው ላይ ተኝቶ አገኘው . .

- አደም እንዴት ነህ . . ወዳጄ ምን አገኘህ?
- እንደምነህ ጆርጅ፣አዝናለሁ የአጭር ጽሑፍ መልክትህን ከአምስት ደቂቃዎች በፊት ነው ሞባይሌ ላይ ያየሁት፤ስልኬ ገና አሁን ነው የመጣልኝ፤አንተ እንዴት ነህ?
- ምንድነው የተከሰተው?
- ደረጃ ስወጣ ወድቄ ቅልጥሜ ላይ ስብራት ደረሰ፤ትናንት ወደዚህ ሆስፒታል አምጥተውኝ የአጥንት ቀዶ ጥገና ተደርጎልኛል፣አሁን በጎ ነኝ።
- ለምን አልደወልክልኝም?
- ጆርጅ አንተ ታማኝ ወዳጅ ነህ፣አመሰግነሃለሁ። እውነቱን ለመናገር ለማንም መደወል በምችልበት ሁኔታ ላይ አልነበርኩም። ወደ ሆስፒታል የወሰደኝ ወዳጄ ነው ለሚያውቃቸው ለነዚህ ወዳጆቼ የደወለላቸው። ከነሱ ጋር ላስተዋውቅህ ፦ አሕመድ የኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነር ከሶርያ፣አድሪያን ፋርማሲስት ከእንግሊዝ፣ዐሊይ የከፍተኛ ትምህርት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ከሰዑዲ ዐረቢያ፣ሸይኽ ባስም አልአዝሀሪ ከግብጽ የለንደኑ እስላማዊ ማዕከል ኢማም . . ከወዳጄ ከጆርጅ ጋር ላስተዋውቃችሁ የኮምፒውተር ሶፍትዌር ኢንጂነርና የተራቀቁ ሶፍትዌሮች ኩባንያ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ ነው . . ያደናቃችሁትን ምርጥ ቦርሳ ያመጣልኝ እርሱ ነው።
- እንኳን ደህና መጣችሁ፣የወዳጄን ወዳጆች ለመጀመሪያ ጊዜ መተዋወቄ ነው።
- ወዳጄ ጆርጅ ሥራ የሚበዛበትና ብዙ የሚጓጓዝ ሰው ነው።
- አደም እንዳላችሁ ቀደም ሲል የተራቀቁ ሶፍትዌሮች ኩባንያ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ ነበርኩ፤ከአደም በጣም ብዙ ብዙ ነገር ተጠቅሜያለሁ።
- ቀደም ሲል? ! ከመቼ ወዲህ ነው ኩባንያውን የለቀከው?
- ከአንድ ሰዓት ያህል በፊት የሥራ መልቀቂያዬን አቅርቤ ነው ወዳንተ የመጣሁት።
- ለምን?

- ታሪኩ ረዥም ነው፣ይህን እንርሳውና . . እግርህ አሁን እንዴት ነው? ሐኪሙስ ምን አለ?
- እግዚአብሔር ይመስገን . . በጎ ነኝ አሁን የሕመም ስሜቱ ጋብ እያለ ነው። ለአምስት ቀናት እዚህ ለመቆየት የምገደድ ሲሆን ለአንድ ወር ያህልም እቤት ማረፍ ይኖርብኛል፣ከዚያም ለአንድ ወር ያህል በምርኩዝ ተደግፌ እንቀሳቀሳለሁ።
- ሸይኽ ባስም አልአዝሀሪ ፈገግ ብሎ ፦ ጭውውታችሁን ማቋረጥ አልሻም፣የዙህር (ቀትር) ሶላት ሰግደን እንድንመለስ ፍቀዱልን።
- እጠብቃችኋለሁ።
- ሸይኽ ባስም ከልጅነቴ ጀምሮ መምህሬና አስተማሪዬ ናቸው።
- ወዴት ነው የሄዱት?
- የቀትርን ጸሎት ለማድረስ ነው የሄዱት።
- ዛሬኮ ማክሰኞ ነው፣የምን ጸሎት ነው?
- እኛ ሙስሊሞች ነን፤ሙስሊሞች በየቀኑ አምስት ጊዜ ወቅቱን ጠብቀው ይሰግዳሉ፣ጸሎት ያደርሳሉ።
- ሙስሊም መሆንህን አወቅሁ፣ለኔ ግን ያልጠበቅኩት ዱብዳ ነበር ! አስቀድመህ ለምን አልነገርከኝም ነበር?!
- ነገሮችን አያይዘህና አገናኝተህ አትመለከታቸውም ብየህ አልነበረም? ስሜና ውይይቶቼ ብቻ ሳይሆን መልኬና ተክለ ሰውነቴ ሙስሊም ዐረብ መሆኔን በግልጽ ያመለክታሉ፣ዋናው ነገር ካንተ የሸሸግሁት ነገር የለም። ካቶሊካዊ ነህ? ፕሮቴስታንት ነህ? እያልክ በመውቀስ ስትጠይቀኝ የነበርከው አንተ ነህ። ሆን ብዬ የደብቅሁህ መስሎ ተሰምቶህ ከሆነ ግን ደጋግሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ።
- በየቀኑ አምስት ጊዜ መስገድ አይደክማችሁም? !
- ሶላት ከዓለማዊ ሕይወት ልፋትና ከጣጣዎቿ እፎይታ ይሰጠናል፣አይደክመንም።
- እኛም እንደዚሁ በሳምንት አንድ ጊዜ በጸሎት እፎይታ እናገኛለን፣በቀን አምስት ጊዜ ግን አድካሚ ይመስለኛል !
- እኛ ግን በቀን አምስት ጊዜ ካልሰገድን ይደክመናል። የኛ ስግደት ብዙ ድካም የለበትም፣ወደ መሰጊድ መሄድ እንኳ ላያስፈልግ ይችላል።
- ወደ መስጊድ ትሄዳላችሁ?
- ወደ መስጊድ መሄድ ከተቻለ ተመራጭ ነው፣ካልተመቸ ግን በየትኛው

ቦታ መስገድ ይቻላል፤እኔም ከአፍታ በኋላ በተሽከርካሪ ወንበሬ ላይ ሆኜ እሰገዳለሁ።
- በዚህ የሕመም ሁኔታ ላይ እያለህ ትሰግዳለህ?!
- አዎ፣እንዳውም በዚህ ሁኔታ ላይ መሆኔ የበለጠ ለጸሎት እንድገፋፋ ያደርጋል። ፈጣሪ አምላኬ ረድኤቱ ሁሌም ያስፈልገኛል፣አሁን ባለሁበት ሁኔታ ላይ ደግሞ አስፈላጊነቱ የበለጠ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ የሕይወት ፈተናዎች የሰውን ልጅ መከራን የመቋቋም አቅም አሳጥተው ከመልካም ስነ ምግባርና ከመርህ እንዲዛነፍ ያደርጉት ነበር።
- ይህ እውነት ነው . . ለመርህ ታማኝ መሆን አድካሚ ነገር ነው።
- ለዚህም ነው ሶላትና ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት መፍጠር የሰውን ልጅ በትእግስትና በጽናት እንዲጎለብት የሚያደርግ የብርታትና የኃይል ምንጭ የሆነው።
- ቁርኣንን እንድታነቡ መልእክት ልኬላችሁ ነበር፣ለራሴ የትኛውን የቁርኣን ትርጉም እንደማነብ ግን አላውቅም።
- የዐረብኛ ቋንቋን አውቀህ እኛ የቁርኣንን ጥፍጥና እንደምናጣጥም አንተም እንድታጣጥመው ምኞቴ ነው። ለማንኛውም ሸይኽ ባስም ከተመለሱ በኋላ አንድ የትርጉም ቅጂ አበረክትልሃለሁ።
- እስላም የመጣው ለዐረቦች ብቻ ነው?
- ከምዕራቡ ዓለም ሌላ በዓለም ላይ የሚገኙ ሙስሊሞች ቁጥር በዐረብ አገሮች ከሚገኙት በብዙ እጥፍ ይበልጣል። እስላም አላህ ለነብዩ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ) እንዳለው ሁሉ ለመላው የሰው ዘር የተለገሰ እዝነት ነው ፦ ‹‹(ሙሐመድ ሆይ !) ለዓለማት እዝነት አድርግን እንጂ አልላክንህም።›› [አል አንቢያ፡107]
- እዝነት !
- አዎ እዝነት ነው፣በረከት ነው፣ጸጋ ነው . . ቁርኣንን ብታነበውና ብታጠናው ለዓለማት ሁሉ ምን ያህል እዝነትና ጸጋ እንደሆነ ልትደርስበት ትችላለህ።
- ካትሪና ስለ ካቶሊክ ስትናገር በምትናገረው ቃና ነው አንተም የምትናገረው።
- ካቶሊካዊነትን እንዳጠናህ ሁሉ . . እስላምን አጥናውና አሳማኝ ሆኖ ካላገኘኸው ወዲያ በለው።
- ላጠናወና ቁርኣንን በመቅራት ለመጀመርም ወስኛለሁ፤የማጠናው ግን በሂሳዊ መንገድ ነው።
- በጣም ጥሩና ተገቢም ነው። እስላም የዕውቀት ሃይማኖት ነው፤አስቀድመህ

ሳታውቅና ሳትረዳው እንድታምንበት አይጠይቅህም፡፡ ለዚህም ነው ከቁርኣን መጀመሪያ ለነብዩ የተላለፈው ቃል ‹‹አንብብ›› የሚል የሆነው፡፡

- በእስላም በጽኑ የምትተማመን ትመስላለህ . . ሮም ውስጥ ያገኘሁት አንድ ሙስሊም እንደኛ መሆንን እንደሚመኝ ነግሮኝ እስላምን እንዳላውቅ ነበር የመከረኝ፡፡
- ከሙስሊሞች መካከል ‹‹እስላም የኋላ ቀርነትና የሽብርተኝነት ሃይማኖት ነው›› የሚልህም ሊያጋጥምህ ይችላል፡፡
- ሰውየውም እንደዚያ ይል ነበር፡፡
- ከሙስሊሞች መካከል እስላም ሴቶችን ስለመጨቆኑና እምነቱን እንዲቀበሉ ሰዎችን የሚያስገድድ ስለመሆኑ የሚናገርም ልታገኝ ትችላለህ፡፡
- ሮም ውስጥ ያገኘሁት ሰው ያልከውን ሁሉ የሚናገር ነበር፡፡
- የማቴማቲክስ፣የምህንድስና፣የሕክምና ወይም የኮምፒውተር ሳይንስን የሚራገምና የሚተች ሰው ሊያጋጥምህ ይችል የለም?!
- በጣም ብዙ ናቸው፡፡
- ከነዚህ ሳይንሶች ደረጃ ምን የሚቀንሱት ነገር ይኖራል? ከሳይንሶቹ አስፈላጊነትና ጠቀሜታስ ምን ሊያጎድሉ ይችላሉ?
- በእርግጠኝነት ምንም አይኖርም፤ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ነገሩ ትንሽ ለየት ይላል፡፡
- በአስላም ላይ የተቀነባበረ የማጥላላት ዘመቻ ከመኖሩና በሳይንስ ላይ ይህን የመሰለ ዘመቻ ካለመኖሩ ውጭ ምንም ልዩነት መኖሩ አይታየኝም፡፡
- የተቀነባበረ የማጥላላት ዘመቻ ስትል ምን ማለትህ ነው?
- ‹ሙስሊሞች› ያደረሱትን የለንደኑን የሽብር ጥቃት ታስታውሳለህ?
- አዎ፣በኋላ ላይ ግን ፍንዳታው የሙስሊሞች የሽብር ጥቃት አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ያ የተረጋገጠው ግን ሚዲያዎቹ ለረዥም ጊዜ ስለ ሙስሊሞች አሸባሪነት ሲያወሩ ከከረሙ በኋላ ነበር፡፡ ማስተባበያውን ግን እንደ ተለመደው አንድ ጊዜ በጨረፍታ አውርተው ነው ያለፉት፡፡ በዚያ ፍንዳታ ምክንያት እኔ ራሴ ተይዘው ከታሰሩት መካከል አንዱ መሆኔንስ ታውቃለህ? ወንጀሌ ሙስሊም መሆኔ ብቻ ነበር፣ሙስሊም ስለሆንኩ በቃ ሽብርተኛ ነኝ ማለት ነው፡፡ የተሰበሰቡት ማስረጃዎች ሙሉ በሙሉ ሙስሊሞች ከወንጀሉ ጋር ምንም ግንኙነት እንደ ሌላቸው እንዳረጋገጡስ ታውቃለህ? የሚያሳዝነው ግን የምዕራቡ ዓለም ሚዲያ ሙስሊሞችን ለመወንጀል ሁሌም በተጠንቀቅ

ላይ መሆኑ ነው፡፡

- ይህ የሚሆነው ሙስሊሞች በተደጋጋሚ በሚፈጽሙት ተግባር ምክንያት አይመስልህም?
- በሁሉም ማህበረሰቦችና በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ ተስፈንጣሪዎች ይኖራሉ፡፡ ልዩነቱ ግን ከሙስሊሞች ጋር ያልተያያዘ ከሆነ ጉዳዩ እንደ ተራ ወንጀል ሲታይ፣ከነሱ ጋር ግንኙነት ካለው ግን የሽብር ወንጀል ተደርጎ መወሰዱ ነው ! ይህ አስቂኝ አይደለም?
- ለእስላም በጣም ስሜታዊ የሆንክ ወገንተኛ ትመስላለህ !
- ግልጽና ቀጥተኛ ልሆንልህና ሙስሊም እንዳትሆን ምንድነው የሚከለክልህ? ሰልመህ የመታደልን ሕይወት ለምን አትጎናጸፍም? !
- ያልጠበቅሁት ድንገተኛ ጥያቄ ነው፤መስለም ወይም እስላምን መቀበል እንዲሁ በቀላሉ የሚሆን ነው?!
- አዎ፣የቤተክርስቲያን ልዩ የጠመቃ ሥርዓት ወይም የአንዳንድ ሃይማኖቶች ዓይነት ውስብስብ ሂደት አያስፈልግህም፤በጣም ቀላል ነገር ግን ትልቅ ስር ነቀል ለወጥና ሽግግር ነው፡፡
- አደም እስላምን ተቀብዬ የሚሰልም ይመስለሃል?
- አዎ፣እንዲያም እጅግ በጣም ቅርብ ነህ ብዬ ነው የማምነው፡፡
- አደም ይቅርታ፣በሚገባ የምታውቀኝ አይመስለኝም፡፡ እኔ ከአእምሮዬ፣ከስነ አስተሳሰቤ፣ከእሳቤዬና ከመርሆዎቼ ጋር የማይጣጠምን ነገር የራሴ አድርጌ መያዝ የማልችል ሰው ነኝ፡፡
- ይቅርታ . . እንዲያውም አንተ ነህ እስላምን የማታውቀው !
- ማለት የፈለከው አልገባኝም፡፡
- ወደ እስላም መግባት በጣም ቀላል ነው፤ውስጥህ አሳማኝነቱን ሙሉ በሙሉ ከመቀበሉ በፊት ግን ወደ እስላም መግባት አትችልም፡፡ ተፈላጊው ነገር በአንደበት ‹‹ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ›› ማለት ብቻ ሳይሆን ይህ ጽንሰ ሀሳብ አስቀድሞ በተጨባጭ እውስጥህ መስረጽ ነው፡፡ በመሆኑም ዋናው ነጥብ ከአፍአዊ ቅርጻዊ ጉዳዮች በፊት ከልብህ ውስጥ የተተከሉ እምነታዊ ጉዳዮች ናቸው ማለት ነው፡፡
- አንድ ቀን ልሰልም እችላለሁ ብዬ ባላስብም የሚሆነውን ግን ማን ያውቃል? !
- እስላምን እንደምትቀበልና እንደምትሰልም ጽኑ እምነት ብኖረኝም ወደ

እስላም መግቢያ በርህ ግን የሳይንስና የዕውቀት በር ነው የሚል ግንዛቤ አለኝ:: ለዚህም ነው አንተ ሳይንስን፣ስነ አስተሳሰብን፣አእምሮንና መርህን የምትወድ በመሆንህ መጀመሪያ እስላምን ማወቅ አለብህ ከዚያ በኋላ ነው ሃይማኖቱን የምትቀበለው ብዬ የማምነው::

-በምትናገረው ነገር እኔን ወይም እስላምን ወይም ሁለቱንም? እያወደስክ እንደሆነ አላውቅም:: ለማንኛውም ግን ሮም ውስጥ ያገኘነው ሙስሊም ‹‹ለኢየሱስ ያለኝ ታላቅ ፍቅር ወደ እስላም መራኝ›› የሚል መጽሐፍ ለካትሪና ከማበርከቱ በፊት የተናገረውንና ከዚህ ጋር ተቀራራቢ የሆነውን ነገር አስታወስከኝ::

-ሮም ላይ ያገኛችሁት ሙስሊም ቅድም እስላምን የሚያጣጥል ነው አላልከኝም ነበር?

-የሚያስገርመው ነገር ይኸኛው ሙስሊም ቅድም የነገርኩህ ሙስሊም ወንድም ነው፣ሁለቱንም አንድ ላይ ነበር ያገኘናቸው::

-ባንተ አስተያየት ማንኛቸው ነው የሚሻለው?

-እኔ እንጃ፣የመጀመሪያው ታላቅ ሲሆን ሁለተኛውና ታናሹ ግን ለአባትና እናቱ የበለጠ አክብሮት አለው፣እነሱም በጣም ያከብሩታል:: ሁለቱን ማነጻጸር አላሳሰበኝም::

-ካትሪና መጽሐፉን አነበበች?

-አዎ፣ያውም ሁለቴ ነው ያነበበችው፤ከውስጥ እንደ አንቀጠቀጣትም አውቃለሁ::

-አንተስ አንብበሃል?

-አዎ አንብቤአለሁ፤አንተ ግን በቁርኣን እንድጀምርና ትርጉሙን እንደምታበረክትልኝ ነበር የነገርከኝ::

-እነ ሸይኽ ባስም ገና እየሰገዱ ነው መሰለኝ ትንሽ ዘገዩ፣አሁን ይመጣሉ:: ፍቀድልኝና አሁን እኔም ልስገድ . . ስለ እስላም መጠየቅ ከፈለግህ ሸይኽ ባስም ሊቅ ናቸው፣እኔ የርሳቸው ተራ ተማሪ ነኝ:: ላንተ ያበረከትኩልህ የቁርኣን ትርጉም መጽሐፍም ሸይኽ ባስም ዘንድ ነው::

-ከመጡ ጸሎትህን አድርሰህ እስክታበቃ እጠብቀሃለሁ፣አለዚያ እሄዳለሁ ፍቀድልኝ::

-መልካም::

ጆርጅ በአትኩሮት እየተመለከተው አደም ‹‹አላሁ አክበር›› ብሎ ሶላቱን ጀመረ:: በዚህ ወቅት ሸይኽ ባስምና ባልደረቦቻቸው ደረሱ . . ጆርጅ ፊቱን

ወደነሱ አዞረ . .

-የእስላም ሃይማኖት መሪ መሆንዎንና ያበረከተልኝን የቁርኣን መጽሐፍ ትርጉም ከርስዎ እንደምቀበል ነግሮኛል::

-እስላም ውስጥ የሃይማኖት መሪዎች የሚባል የካህናት ዓይነት መደብ የለም:: መጽሐፉ ውጭ መኪና ውስጥ ነው ያለው፣አብረን ሄደን ብሰጥህ ምን ይመስለሃል?

-መልካም . . ብዙ ስለ ዘገየሁ መሄድ ይኖርብኛል፣የማይረዝም ካልሆነ ግን አደም ጸሎቱን እስኪጨርስ እንጠብቅ::

-ሶላታችን እንደ ሃይማኖታችን ሁሉ ገርና ቀለል ያለ ነው፣ሁለመናው መታደል ነው፣ደስታ ነው::

-መታደል ነው፣ደስታ ነው? !

-አዎ . . የዛሬው ዓለማዊ ሕይወትና የወዲኛው ዘላለማዊ ሕይወት ተድላና ደስታ ነው:: የአደም ወዳጅ ሆነህ ይህን ሳይነግርህ መቅረቱ የሚገርም ነው:: ወዳጅህ ሆኖ ይህን ታላቅ ሃይማኖት ሳያስተዋውቅህ በመቅረቱ አደምን እወቅሰዋለሁ፣እስላምን ከማስተማር የተሻለ የሚያበረክትልህ ምንም ክቡር ስጦታ የለም:: ብዙዎቹ የሰው ልጆች ለመንፈሳዊና ዓለማዊ ሕይወታቸው የሚበጀውን ለመፈለግ በጥመትና በጥፋት መንገዶች ውስጥ ሲዳክሩ የአላህ ነብያትና መልክተኞች መደምደሚያ የሆኑትን ነብይ ሃይማኖት እንዴት ችላ እንዳሉ አታይም?

-ምናልባት እርስዎ ዘንድ ያለውን የቁርኣን ትርጉም መጽሐፍ ያበረከተልኝ ለዚህ ሊሆን ይችላል::

አደም ሶላቱን አብቅቶ ወደ ጆርጅና ሸይኽ ባስም ፊቱን አዞረ . .

-ሸይኽ ባስም አይውቀሱኝ፣እስላም የዛሬው ዓለም ሕይወትና የመጪው ዘላለማዊ ዓለም ሕይወት ተድላ መሆኑን ነግሬዋለሁ . .

-ሸይኽ ባስም ፈገግ እያለ ፦

-ጆርጅ እኛ ከያንዳንዱ ሶላት በኋላ የሕይወትን ሸክምና ጣጣ፣ ቻይ፣ቸር፣ርህሩህ፣ሰሚ ውስጠ ዐዋቂ በሆነው ፈታሪ ጌታ ላይ ስንጥል በዓለም ላይ ወደር የሌለው ደስታ ይሰማናል::

-ጆርጅ ሸይኽ ባስም የጠቀሱትን በዛሬው ዓለም ሕይወትና በመጪው ዘላለማዊ ዓለም ሕይወት መታደልን እመኝልሃለሁ::

-ተምሬ አውቄው አሳማኝ ሆኖ ካገኘሁትና በጥልቅ ሂሳዊ ምርምር ካጠናሁት በኋላ እንጂ ሃይማኖቴን መቀየር አልችልም:: አደም በሁሉም

www.path-2-happiness.com

ሃይማኖቶች ላይ በዚህ መንገድ አይደለም ጥናት ያካሄድኩት?

- ልክ ነው፤የኔ ጥያቄም በዚያው ተመሳሳይ መንገድ እንድትቀጥል ነው፤እንድትሰልም ብንጓም እስላም ግን ማወቅ ቀዳሚ መሆኑን ያስተምረናል።
- መጀመሪያ ማወቅና መማር አለብህ፤ወዳጄ ከዚያ በኋላ ካልሰለምክ ግን ማመካኛ አይኖርህም። አሁን እንሂድ?
- ካወቅኩት እስልምናን እንደምቀበል ያላችሁ ይህ ሁሉ በራስ የመተማመን መንፈስ ምንጩ ምን እንደ ሆነ አላውቅም።
- ምንጩ ከአላህ ዘንድ በመጣው እስላም ላይ ያለን ፍጹማዊ መተማመን ነው።
- እንግዲያውስ አየዋለሁ ! ! ቁርኣንን ለማንበብ ቃል እገባላችኋለሁ። ስለ እስላም ለማወቅ አነባለሁ፣እወያያለሁ፣በጥልቀት እመረምራለሁም። ከዚያ በኋላ እወስናለሁ።
- ግሩም ድንቅ ነው . . ተመራጩም ይኸው ነው።
- ሌሎች ሃይማኖቶችን ለማወቅ እንደተጓዝክ ሁሉ እስላምን ለማወቅና ለመመርመር መጓዝን አትርሳ።
- አሁን እንሂድ . . መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አነባለሁ፤ከዚያ የሚሆነው ይሆናል። አሁን ሥራ አልባ ሆኛለሁና ነገ ተመልሼ ልጠይቅህ እሞክራለሁ።
- ሥራውን መልቀቅህ ግን አስደንግጦኛል። የተቻኮልክ ትመስላለህና ነገ ካልመጣህ ስልክ እንደዋወል፤ፈጣሪ ካንተ ጋር ይሁን።

ጆርጅ የቁርኣንን ትርጉም ይዞ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ካትሪናን እቤት አላገኛትም፤ደወለላትና አደምን ለመጠየቅ ወደ ሆስፒታሉ በመሄድ ላይ መሆኗን ነገረችው . . የቁርኣን ንባቡን ለመጀመር ወሰነ። ከአደም በኩል የተቸረው ድንቅ አቀባበልና አያየዝ አስገርሞታል፣በተለይም እስላምን ከሚያስተዋውቁ ሌሎች መጽሐፎች ይልቅ በቁርኣን እንዲጀምር ማድረጉ። ከሁለት ሰዓት ያህል በኋላ ካትሪና ወደ ቤት መለሰች . .

- አደምን ጠይቄ መመለሴ ነው።
- የኔ ወዳጅ በመሆኑና እኔን ለማስደሰት ብለሽ እንጂ እንዳልሄድሽ አውቃለሁ።
- ግን በጣም የሚገርም ሰው ነው !
- እንዴት?
- እኔ እንጃ፣እርሱም ሆነ አብረውት ያሉ ሙስሊሞች ሁሉ ሴቶችን

አይጨብጡም፣በትህትና ይቅርታ ይጠይቃሉ። በአይዶች ወይም በክርስትያኖች ዘንድ ያለው ዓይነት በሴቶች ላይ የሚፈጸም መድልኦ ይሆን?

- ሊሆን ይችላል . . እኔ እንጃ። እኔ ከሁለት ሰዓት በፊት ስለ እስላም ማንበቤን በመጽሐፍ ቅዱሳቸው በቁርኣን ጀምሬአለሁ። እውነቱን ለመናገር እስካሁን ያነበብኩት ሴትን በፍትሐዊነት የሚመለከታትና አክብሮት የሚቸራት መሆኑን ነው።
- ልክ ነህ . . የቁርኣንን ትርጉም አንብቤያለሁ፤እንዳልከው ነው፤ያስገረመኝ ግን ያሳዩኝ አያያዝ ነው !
- ለምን ? ያስተዋልሽው አንቺን የማዋረድ ወይም የማንቋሸሽ ሁኔታ ነበር?
- ፈጽሞ አልነበረም፤እንዲያውም በጣም ትሁቶችና ተግባቢዎች ናቸው፣ግን አልጨበጡኝም፣ወደኔም አልተመለከቱም።
- ግን ትንሽ ቆይተሻል፣ሀሳብ አልተለዋወጣችሁም?
- ብዙ ተወያይተናል፤የምናገሩት በአብዛኛው ስለ እስላም ነው። አንዳንድ ቀሳውስትን እንዳስታውስ ለምን እንዳደረጉኝ አላውቅም።
- ምናልባት ባልደረባው ባስም የሃይማኖት መሪ ስለሆነ ይሆናል።
- አይደለም፣ባስም የሃይማኖት መሪ አይደለም፣ይህን አገላለጽም አይቀበልም። እስላም ውስጥ እናንተ ዘንድ እንዳለው ዓይነት የጵጵስና ሥርዓትና የሃማኖት መሪዎች የሚባል የካህናት መደብ የለም። ለማንኛውም ግን እርሱ የሃይማኖት እውቀት ያለው ምሁር ነው።
- አዎ . . ልክ ነሽ፤እርሱም ያለኝ ይህንኑ ነው፤ፈገግታ የማይለየው ትሁት አመለ ሸጋ ሰው ነው። እንዳንቆራረጥ ቢዝነስ ካርዱን ሰጥቶኛል። ታውቂያለሽ ሙስሊም እንድሆን ይፈልጋል ! ! ያላቸው በራስ መተማመን በእጅጉ ይገርመኛል !
- ካትሪና የሆነ ነገር ከትውስታ መዝገቧ ታነብ ይመስል ጣሪያ ጣሪያውን ተመለከተችና ፦ እንደ መነኮሳት ሙሉ ጊዜአቸውን ለአምልኮ የሚያውሉ ባይሆኑም ሁሉም ሰናይ ምግባር ያላቸውና አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚያበዙ ናቸው። የሚያስደንቀው ነገር ሥራቸውንም ሆነ ትምህርታቸውን አምልኮ አድርገው ይመለከታሉ፤እኛ ዘንድ እንዳለው ዓይነት ሕይወትን ከአምልኮተ እግዚአብሔር ነጥለው አይመለከቱም። ታቂያለሽ አደም አልጋው ላይ ሆኖ የጸሎት ሥርዓቱን አከናውኖ ‹‹እኛ በሁሉም ስፍራ እንጸልያን፣ሃይማኖት ገር ነው›› አለኝ።

www.path-2-happiness.com

-እኔ እያለሁም ሰግዶ በቀን አምስት ጊዜ እንደሚሰግዱና ስግደታቸው ተድላና ደስታ እንደሚያጎናጽፋቸው ነው የነገረኝ፡፡ ከፍተኛ በሆነ በራስ የመተማመን ስሜት የሚናገሩት ቢሆንም ያሉት ነገር አላሳመነኝም፡፡

-እውነት ነው . . ያላቸው በራስ የመተማመን ደረጃ በጣም ከፍ ያለ ነው፤ንግግራቸውም ትልቅ ተጽእኖ የሚያሳድር ነው፡፡ ለሰው ያላቸው አያያዝ፣ፈግገታቸውና ተግባቢነታቸውም ወደር የለውም፡፡

-በአድናቆታቸው የተያዝሽ ትመስያለሽ !

-ጉዳዩ የማድነቅ አለማድነቅ አይደለም፤ዋናው ጉዳይ ሙስሊሞች፣ቁርኣንና እስላም እኔ ከለመድኩት ሙሉ በሙሉ የተለየ ሥርዓትና ተፈጥሮ መሆኑ ነው፡፡

-ይበልጥ አብራሪው፤መጽሐፍ ቅዳሳቸውን ቁርኣንን ማንበብ ስጀምር ተመሳሳይ ስሜት ነው የተሰማኝ፡፡ በተሟላ ሁኔታ ምንነቱን ያልተረዳሁትን እንግዳ ስሜት ነው እውስጤ የፈጠረው፡፡ በተለይም የእግዚአብሔርን አንድነት፣እርሱን ማላቅና ማክበር፣ስሞቹንና ባህርያቱን በመሳሰሉት ርእሰ ጉዳዮችም ሆነ የነብያትን ታሪኮች በተለይም የኢየሱስንና የማርምን ታሪክ የሚመለከቱ ወይም ሞራልና ስነ ምግባርን የሚዳስሱ ጉዳዮች ልቤን ነክተዋል፡፡

-እኔም ተመሳሳይ ስሜት ነው ያሳደረብኝ፣ግና ለመወሰን መቸኮል የለብንም የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ ስለ ሃይማኖቱ ያለን ዕውቀት በጨመረ ቁጥር ነገሮች ግልጽ እየሆኑ ይሄዳሉ፣ደካማ ጎኑን፣እንከኑንና እርስ በርስ መጣረሱን ማወቅ እንችላለን፡፡ እንዲህ ያሉ ነገሮች እስላም ውስጥ ስለመኖራቸው ከኋላ ቀርና አምባገነናዊ የሙስሊሞች አገዛዝ ሁኔታ የበለጠ ማስረጃ አይኖርም፡፡

-ለአደም ትልቅ አድናቆት ቢኖረኝም፣ከአፍታ በፊት ቁርኣንን ሳነብ የሆነ ዓይነት እርካታ የተሰማኝ ከመሆኑም ጋር፣እስላምን የማወቅ ብርቱ ፍላጎት ያለኝ መስሎ አይታየኝም፡፡ ይሁን እንጂ ለማወቅ ከራሴ ጋር እታገላለሁ፡፡

-አውነቱን ለመናገር መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ማንበብ የተለየ ስሜት ይፈጥራል !

-የምሥራች ልበልሽ . . ዛሬ የሥራ መልቀቂያዬን አቅርቤያለሁ፡፡ መሰሪውን ውሽታም ካኽን አምርሬ ነው የምጠላው፡፡ የተሰጠኝን የሥራ ዕድገት ከኔ ሸሽጎ ወደ ስዊድን እንድሄድ ነው የመደበኝ፡፡ መልቀቂያውን ያቀረብኩት የሥራ አመራር ቦርዱን በሚያነሳሳ መንገድ ነው፤ምላሽ ካልሰጡኝ

የመጨረሻው መልቀቂያ ይሆናል፡፡

-እናም መርሆዎችህ በፍላጎትህና በጥቅሞችህ ላይ ድል ተቀዳጅተዋል ማለት ነው?

-ሊሆን ይችላል፤ግን ደሞ ለውሳኔ የገፋፋኝ የሥራ አመራር ቦርዱን ውሳኔና ካኽ የወሰደውን አቋም ማወቁ ሊሆን ይችላል፡፡ ተስፋ የማደርገው ተገቢ የሆነ አቋም ይወስዳሉ ብዬ ነው፡፡ ለማንኛውም ግን ገንቢ ያልሆነ ምላሽ ከነርሱ ካላገኘሁ ጉዳዩን ወደ ሠራተኞች ማህበር እወስዳለሁ፡፡

-እኔ ግን አሁንም በመርሆዬና በሥራዬ መካከል ሆኜ እየታገልኩ ነኝ . . ጥርጣሬዬን ሸፋፍኜ እሸሽ ነበር፣አንተ ነህ የተሸፋፈነው ሁሉ ይፋ ካልወጣ ብለህ የጸናህ፡፡

-ከተጋባንበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ በመጨረሻው ወር እንዳደረግሽው ፈጣን ለውጥና ሽግግር ስታደርጊ አይቼ አላውቅም፣በተለይም ከቴል አቪቭ ከተመለስኩ በኋላ !

-ለውጥና ሽግግር ሙሉ በሙሉ ክፉ ወይም ሙሉ በሙሉ በጎ አይደሉም፤የኔ መለወጥና ሽግግር ወደ በጎው እንዲሆን እመኛለሁ፡፡

-እህህ፣ከካቶሊካዊነት የተሻለ በጎ ይኖራል?

-በመድኃኒታችን በኢየሱስ ያለኝ እምነት እጅግ በጣም ጽኑ ነው፣በካቶሊካዊነት ላይም እንዲሁ ነው፣ከርሱ የተሻለ አለ ብዬ አልገምትም፣ግን ማን ያውቃል? !

-እህህ፣ዛሬ በጊዜ መተኛት እፈልጋለሁ፣ሆኖም የኢሜይል መልክቶችን በፍጥነት አነባለሁ፡፡

ጆርጅ ኢሜይሉን ከፈተ፤መርህን አስመልክቶ ልኮ ለነበረው መልክት አንዳንድ መልሶችን አገኘ፡፡ ሁሉንም አንድ ላይ ጠቅለል አድርጎ መልሶ ለሁሉም ላከላቸው፡፡ የሁሉም እርሱ ከደረሰበት ውሳኔ ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነበር፡፡

‹‹ጃኖልካ ፦ በቂ ድፍረት ላለው ሰው ያለ ጥርጥር መርህ ቀዳሚ ነው፤ግና ችግርና ድካም አለው፡፡

ሌቪ ፦ ትክክለኛው ነገር መርህ ይበልጥ አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ የኑሮ ጫናን የመቋቋም አቅም ስለሚያንሰን የግድ ሁላችንም ማድረግ እንችላለን ማለት ግን አይደለም፡፡

ሐቢብ ፦ መርህን ነው የምናስቀድመው፣አለዚያማ ወደ ዱር አውሬነት ተለወጥን ማለት ነው፡፡

www.path-2-happiness.com

ካትሪና ፦ መርህ ይቀድማል ተብሎ ነው የሚጠበቀው፣ ነገር ግን አስቸጋሪ ውሳኔ ነው።

ቀደም ሲል በቁርኣን ዙሪያ ለላኩላችሁ መልክት ምላሻችሁን በመጠባበቅ ላይ ነኝ።

ጆርጅ››

ኢሜይሉን ማየት ቀጥሎ ከጃናልካ የተላከ መልእክት አገኘ . .

‹‹ወዳጄ ጆርጅ . .

ከተዋወቅን አጭር ጊዜ ቢሆንም በአመለካከት መቀራረብ ብቻ ሳይሆን በመካከላችን መመሳሰል መኖሩን ነው የተገነዘብኩት። ስለዚህም ምናልባት ሊያስገርምህ በሚችል ጉዳይ ላይ ላማክርህ ወደድኩ።

እናንተ ከሄዳችሁ በኋላ ሙስሊሙ ሰውየ ለባለቤትህ የሰጣትን መጽሐፍ ከኢንተርኔት ላይ አግኝቼ አነበብኩ። ከዚያም የሕንጻ ዲዛይን ኢንጂነሩን ሙስሊም አግኝቼ ስወያይ መጀመሪያ የቁርኣንን ትርጉም እንዳነብ ጠየቀኝና ከአንድ ጊዜ በላይ ሙሉውን አነበብኩ። ከንባቤ በኋላ እንደገና ተገናኘተን ሀሳብ የተለዋወጥን ሲሆን ይህ መጽሐፍ ምን ዓይነት ምትሃት እንዳለው አላውቅም ! ስለ እስላም ዝርዝር ጉዳዮችን ጠይቄው ጥልቀት ያለው ዕውቀት የሌለው መሀንዲስ ብቻ መሆኑን ነገረኝ። ማን በዝርዝር ሊያስረዳኝ እንደሚችል ሲጠይቀው እንግዳ በመሆኑ ጣሊያን ውስጥ ይህን ማድረግ ማን እንደሚችል እንደማያውቅ አስረድቶኝ ስለ እስላም የበለጠ ለማወቅ ከፈለግሁ ሁለት መንገዶች እንዳሉ ጠቆመኝ ፦ ስለ እስላም የተጻፈውንና የተሰራጨውን ማንበብ መስማትና ማየት ሲሆን፣ይህም በቁጥር የበዛ ቢሆንም ከፊሉ በእስላም ጠላቶች የተጻፈ ነው። ሌላው መንገድ ጣሊያን ውስጥ የሚኖርና እስላምን በጥልቀት የሚያውቅ ሰው መፈለግ አለዚያም መሳፈር ነው። እናም ሁለቱንም መንገድ ወስኜ እናንተ ከሄዳችሁበት ጊዜ ጀምሮ በየቀኑ ከአምስት ሰዓት ላላነሰ ጊዜ ስለ እስላም በማንበብ ላይ እገኛለሁ። በቅርቡ ወደ ግብጽ ወይም ወደ ሊብያ ለመጓዝ እፈልጋለሁ። ምን ትመክረኛለህ?

ሰላምታዬ ላንተና ለካትሪና ይድረስ

ጃናልካ››

መልስ ጻፈለት . .

‹‹ወዳጄ ጃናልካ

ደብዳቤህን አንብቤ ድፍረትህና ጀግንነትህ በእጅጉ አስደንቆኛል። እኛ ከሄድን በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ደያረግከው ለውጥና ሽግግር ከፍተኛና

ከጠበቅኩት በላይ ነው። ሁለቱንም መንገዶች መከተልህን እደግፋለሁ። የደረስክበትን ውጤት እንድታሳውቀኝ እፈልጋለሁ፣ባንተና በንቁ ተመራማሪ አእምሮህ ብዙ እጠቀማለሁ።

ሰላምታዬ ይድረስህ

ጆርጅ››

(3)

ጆርጅ ከእንቅልፉ ሲነቃ ካትሪና ቁርስ አዘጋጅታ ነበር . . አብረው ቁርሱን በሉ . .

- ዛሬ ሥራ የለኝም፣ምን እንደማደርግ አላውቅም።
- ለሥራ መልቀቂያ ጥያቄህ ምላሽ ያልመጣ ስለሆነ መቅረትህ በሠራተኛ ማህበሩ ዘንድ ማስረጃ እንዳይሆንብህ ወደ ሥራ ሂድ።
- ይህን አላሰብኩም ነበር፣እውነትሽን ነው።
- አንተ እንኳ ቁርጥ አድርገህ ወስነሃል፤እኔም የራሴን ቁርጥ ያለ ውሳኔ ዛሬ ለመወሰን እሞክራለሁ።
- ቁርጥ ያለ ውሳኔ ! . . እንዴትና በምን?
- እኔ እንጃ፣ግን እሄድና ነገሩን ለመወሰን እሞክራለሁ።
- ትናንት በመርህና በጥቅም መካከል ያለውን ግጭት አስመልክቶ የተላከለኝን ማጠቃላያ ልኬልሻለሁ፤ውሳኔ ላይ ለመድረስ ምናልባት ሊረዳሽ ይችላልና አንብቢው።
- ከመወሰኔ በፊት አነበዋለሁ። እንዳይረፍድብኝ አሁን ልሂድ።
- እኔም አሁን ልሂድ።

ጆርጅ ወደ ሥራው አመራ፤ወደ ቢሮው እንደገባ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው በንዴት ገንፍሎ መጣ ፦

- ምንድነው ያደረከው?!
- ምንም አላደረግኩም፣ምን ተፈጠረ? !
- ትናንት አንተ ከሄድክ በኋላ ካኽ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ አስጠራኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነው እንዲህ ተናዶ ያየሁት። ጆርጅ የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን አድራሻ ከየት አገኘ? ብሎ አፋጠጠኝ፤አላውቅም አልኩት።
- እኔ ሰጠሁት ለምን አላልክም?!
- ሊያጠቃኝ ቢፈልግስ ብዬ ሰጋሁ ! ከግል ጥቅሙ ውጭ ምንም የማይታየው ግፈኛ መሆኑን መቼም ታውቃለህ።

www.path-2-happiness.com

-እንዲህ ነው እንግዲህ እርስ በርሳችን የምንፈራራው . . በጣም የሚገርም ነው . . የተቆጣበትን ምክንያት ግን ታውቃለህ?

-እንደሚመስለኝ የሥራ አመራር ቦርድ አባላቱ በአንተ ደብዳቤ ላይ ለመነጋገር በሦስት ቀናት ውስጥ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲደረግ ደውለው ጠይቀውታል፡፡

-ለምንድነው የሚሰበሰቡት?

-እኔ እንጃ፣የማውቀው ነገር ጉዳዩ ካንተ ጋር የተያያዘ መሆኑን ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው የጻፍከውን ደብዳቤ ይዘት የጠየቅሁህ?

-እናም ነገሩ በጣም አበረታች ነው ማለት ነው፣ይህን አልጠበቅሁም ነበር !

-አበረታች ! ምኑ ነው አበረታቹ?!

-ምንም አይደለም፣የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ነው የላኩላቸው፡፡ ለማንኛውም አድራሻዎቹን አንተ እንደ ሰጠኸኝ አንድም ሰው እንደማያውቅ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ፡፡

-አመሰግናለሁ . . ፍቀድልኝ ልሄድ፡፡

ጆርጅ በቀጣይ የሚወስደው እርምጃ ምን መሆን እንዳለበት በማሰላሰል ተጠመደ፡፡ የካኽን የማታለልና የመዋሸት ስልቶች አሳምሮ ያውቃል፡፡ ኩባንያውን መተው ስለማይፈልግ ስልቶቹን በቀላሉ በሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባ ላይ ሊጠቀምበት ይችላል፤በቦርዱ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ይጠይቃል ወይስ ዝርዝር መረጃዎችን ያቀርብላቸዋል? ምን ያድርግ? የሚገርመው ደግሞ ከሥራ አመራር ቦርድ አባላት መካከል እስካሁን ድረስ መልስ የሰጠው ሰው የለም! በመሆኑም የሚሰሙት ከካኽ ሊሆን ነው፣ይህ ፈጽሞ የማይፈልገው ነገር ነው፡፡ ቆም ብሎ አሰበበትና ለሥራ አመራር ቦርዱ በድጋሚ ደብዳቤ ለመጻፍ ወሰነ ፦

‹‹የተከበራችሁ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ፦

አስራ አራት ዓመታት የቆየሁበትን ኩባንያ በማገልገሌ ኩራት ይሰማኛል፡፡ በኔ ላይ የጣላችሁት እምነትም ለኔ የኩራት ምንጭ ሲሆን ለዚህ ተገቢው ሰው ሆኜ መገኘትም ምኞቴ ነው፡፡ ኩባንያችንን ወደፊት ማራመድ የሁላችንም ኃላፊነት መሆን ይገባል፡፡ ማስመዝገብ የቻልኩትን ስኬት እንዳስመዘግብ ያደረገኝ የናንተ ድጋፍና ትብብር በመሆኑ ለዚህ ያለኝን አድናቆትና ምስጋና እንድገልጽ ይፈቀድልኝ፡፡

በደሌን በመንገር የሥራ መልቀቂያ ያቀረብኩላችሁ ቢሆንም ከናንተ ያገኘሁት መልስ የለም፡፡ ይህ በደሌ እንደ ቀጠለ የሥራ መልቀቂያው ተቀባይነት

አግኝቷል ማለት ነው? ወይስ ፍትሕ አግኝቼ ሥራዬን እቀጥላለሁ ማለት ነው? ከሥራ አመራር ቦርዱ ጋር በቀጥታ የመወያየት ዕድል እንደሚሰጠኝ ተስፋዬ የጠበቀ ነው፡፡

ለመልካም ትብበራችሁና ለቀና አስተያየታችሁ ሁላችሁንም አመሰግናለሁ፡፡ ጆርጅ››

በዚህ ደብዳቤ ማስተላለፍ የፈለገው በሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ሁሉንም ነገር በግልጽ የማቀረብ ፍላጎቱን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ደብዳቤውን እንደላከ ወዲያውኑ የቢሮ ስልኩ አቃጨለ፤ደዋዩ ካኽ ነበር . .

-ባለ መርሁ ይህ ሁሉ ለመርህ ሲባል ነው ! አሁን ወደ ቢሮዬ መምጣት ትችላለህ?

-አዎ ለመርሆዬ ብዬ ነው፣ፈጽሞ በመርሆዬ ላይ አልደራደርም፡፡

-አሁን ወደኔ መምጣት ትችላለህ?

-አዎ አሁን እመጣለሁ፡፡

ጆርጅ ወደ ቢሮ ሲደርስ ካኽን ተቆጥቶ አገኘው . . በነገር ተቀበለው . .

-ጆርጅ ምንድነው የፈለከው?

-መርሆዬን አለመጣስ ነው የፈለኩት፡፡

-የኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅ መሆን የፈለግህ ትመስላለህ፡፡

-ለመሆን አልጓጓሁም፣ከመጣ ግን ብቁና ተገቢው ሰው ስለሆንኩ ችግር የለውም፡፡

-እናም ጉዳዩ የመርህ ጥያቄ ሳይሆን የሥልጣን ጥያቄ ነው ማለት ነው፡፡

-እንዳሻህ መረዳት ትችላለህ፤ለማንኛውም ግን እኔ መርሆዬን አልጥስም፡፡ የመጣሁት ደግሞ አንተ ስለጠየከኝና እንስማማለን ስላልክ ብቻ ነው፡፡ ካኽ እርግጠኛ ሁን እኔ መርሆዬን ፈጽሞ መጣስ አልችልም፡፡

-ጉዳዩ የስልጣን ሳይሆን አንተ እንደምትለው የመርህ ከሆነ የማቀርብልህ ሌላ ሀሳብ አለኝ፡፡

-ምንድነው?

-እኔ ወደ ስዊድን እጓዛለሁ፣ግን አንተ ከለንደን ወደሆነ ቦታ የመሄድ ግዴታ ይኖርብሃል፡፡

-ለምን?!

-ነገሩ ከራሴ የግል ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እኔ በዚህ ወቅት ኩባንያውን ለቅቄ ወደ ሌላ መዛወር አልፈልግም፤አንተ ለንደን ውስጥ ሆነህ የሥራ አመራር ቦርዱ ከተሰበሰበ ግን ለኔ እድገት ሰጥቶ ይህን ኩባንያ ለቅቄ ወደ

ሌላ እንድዛወር ይወስናል:: ለዚህ ነው ያንተን የስዊድን ጉዞ አስፈላጊነት ያሳመንኳቸው፤(ፈገግ ብሎ ቀጠለና) ፦ ስሜትህን ለመጠበቅና መርሆህን ለማክበር ስል እኔ እንዳለሁ፣አንተ ግን ውሳኔ መዘግየት እንዲችል በዚህ ጊዜ ከለንደን ውጭ መሆን ይኖርብሃል::

-ወዴት ነው የምሄደው?

-ወደፈለግህ ቦታ፣ጀርመን፣ዩክሬንና ግብጽ ሥራዎች አሉን::

-እምቢ ብልስ?

-ጉዳዩ የመርህ ሳይሆን የጥቅም ወይም የስልጣን ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ይሆናል ! ያ ከሆነ ደግሞ ሁሉንም እንደ አመጣጡ አስተናግዳለሁ::

-አስቤበት ነገ መልስ እሰጥሃለሁ::

-መልስ የምትሰጠው ለኔ ነው . . ለሁሉም የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አይደለም::

-እሺ ቃሌ ነው . .

ጆርጅ የኩባንውን ግቢ ለቆ ወጣ፤ወደ መኪናው ሲያመራ ለቶም ደወለ . .

-አሁን ብመጣ ይመቸሃል?

-አዎ መምጣት ትችላለህ::

-ከግማሽ ሰዓት በኋላ እደርሳለሁ፣መንገድ ላይ ነኝ::

ጆርጅ ወደ ቶም ክሊኒክ ደርሶ ሲገባ እንግዳ መቀበያው ውስጥ አዲስ ሠራተኛ ገጠመው፣ሠራተኛው እንኳን ደህና መጣህ ብሎ ተቀበለው . .

-ዶክተር ቶም አንተ እየጠበቀ ነው ግባ::

-ጆርጅ እንኳን ደህና መጣህ . . ክሊኒኩ ተመልሶ ከተከፈተ ወዲህ የመጀመሪያው ታካሚ ነህ፣ገና ዛሬ ነው የተከፈተው፤ከነገ ጀምሮ እንጂ ለማንም ደንበኛ ቀጠሮ አልሰጠንም::

-መልካም ዜና ነው፤ይቅርታ ነገሩን ሳልከታተል፣የበራድ ጉዳይ እልባት አገኘ? !

-ሳይመለስ ሄዷል::

-ወዴት ሄደ?

-ወደ እስር ቤት፤አደንዛዥ እጽ ሲሸጥ ተይዞ ታሰረ::

-እንዴት እጠላው መሰለህ !

-ለምንድነው የምትጠላው?

-መርህ የሌለው ግለሰብ ነው፤አንድ ሰው መርህ አልባ ሲሆን ከሰው ይልቅ ለዱር አራዊት የቀረበ ይሆናል::

-ፈተናዎች ብርቱ ናቸው ! ከፊቴ ሁለት አማራጮች ነበሩ፤መርሆዬን ረግጬ ሁሉንም ችግሮቼን ወዲያውኑ መፍታት ወይም በመርህ ጸንቼ ወደ ብርቱ ፈተና መግባት:: በመርሆዬ ለመጽናት ወስኜ ሁሉንም ነገር ለማጣት ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር:: በመርህ ላይ መጽናት መጨረሻው ያማረ ስለመሆኑ ግን እርግጠኛ ነበርኩ፣የሆነውም ይኸው ነው::

-የመጣሁበትን ጉዳይ ያወቅህ ትመስላለህ::

-ምንድነው?

ጆርጅ ከካኽ ጋር ስለሆነው ሁሉ ለቶም በዝርዝር ነገረው:: የጉዞውን ጉዳይም አንስቶለት ለመሄድ ማቅማማቱን አስረዳው . .

-ሳማክርህ ፈልጌ ነው አመጣጤ፣ኢሞራላዊ ቅድመ ግዴታዎቹን ሳልቀበል ጉዞውን ብቀበል መርሆዬን መጣስ ይሆናል ብለህ ታስባለህ?

-አልገባኝም፤ለሌላ ሥራ ነው የምትጓዘው እንዴት ነው መርሆህን የምትጥሰው?

-እግረ መንገዴን የካኽን እኩይ ዓላማ አሳካለታለሁ::

-ካኽን ሥራ አመራር ቦርዱ ፊት ይበልጥ ለማጋለጥም ትችል ይሆናል::

-እናም ሀሳብህ እንድጓዝ ነው?

-አዎ . . ወደ ግብጽ ተጓዝ::

-ለምን?

-ቀደም ሲል ባደረግነው ውይይት እስላምን ማጥናት እንዳለብን ተስማምተናል፤አሁን ደግሞ ይህ መልካም አጋጣሚ ተገኝቷል:: ክሊኒኩን ዛሬ ባልከፍት ኖሮ እኔ ራሴ ካንተ ጋር በሄድኩ ነበር::

-በቅርቡ ተከታታይ ጉዞዎች በማድረጌ መጓዝ አልወደድኩም፤መጓዝ ካለብኝ ደግሞ ወደ ጀርመን መሄድን ነው የምመርጠው::

-ውሳኔው የራስህ ነው፤እኔ ግን መጓዝህ አስፈላጊ ነው፣ሙስሊሞችን ከውስጥ ሆነህ ታያቸዋለህ፣እንከኖቻቸውንና ስህተቶቻቸውንም የማወቅ እድል ይኖረሃል ባይ ነኝ::

-አስብበታለሁ፤ለማንኛውም አንተ በዚህ ጉዳይ ላይ ያማከርኩት የመጀመሪያው ሰው ነህ:: የበለጠ አማክሬና አስቤበት የደረስኩበትን አሳውቀሃለሁ . . ፍቀድልኝ ልሂድ፤ዛሬ በክሊኒክህ ጉዳይ ተጠምደሃል . . በመርህ ላይ መጽናትህ ተገቢህ ነው . . ደህና ሁን::

እየሄደ ለአደም ደውሎ ሊያገኘው እንደሚፈልግ ነገረው:: አሁን ዶክተሩ አንዳንድ ምርመራዎችን እያደረገለት በመሆኑ እንደማይመቸው ነግሮት

www.path-2-happiness.com

ከይቅርታ ጋር በማታው የሕሙማን መጠየቂያ ሰዓት እጠብቀሃለሁ አለው . . ወደ ቤቱ አመራና የአደምን መጽሐፍ ቅዱስ ቁርኣንን ለማንበብ ወሰነ . .

በማንበብ ላይ እያለ ልጆቹ ማይክልና ሳሊ መጡ . .

- ባባ ዛሬ በጊዜ መጣህ !
- አዎ ሥራ ቦታ በጊዜ እንድመጣ የሚያደርገኝ ሁኔታ ስለነበረ ቶሎ መጣሁ::
- ባባ ምንድነው የምታነበው? በተመስጦ ነው ስታነብ የነበረው !
- የሙስሊሞች መጽሐፍ በመባል የሚታወቀውን መጽሐፍ ሳነብ ነበር::
- አሸባሪዎች ተብለው የሚጠሩ ሙስሊሞች?
- አዎ::
- በኛ ትምህርት ቤት የሕንድ ዝርያ ያለው ሙስሊም ተማሪ አለ፤በትምህርት ሰነፍ ሲሆን ጠባዩ በጣም የሚመች ነው፣አሸባሪ ግን አይደለም::
- ሽብርተኝነት ሃይማኖት የለውም፤የሚሉትን አትስማቸው፤ከሰዎች ጋር በመልካም ጸባያቸውና በጥሩ ስነ ምግባራቸው መሰረት ብቻ አብሮነት ይኑርህ::
- ከዐመለ ሸጋነቱ ጋር ግን ከኛ ትንሽ የመገለል ስሜት ይታይበታል::
- ለምን?!
- እኔ እንጃ ! ምናልባት በተደጋጋሚ አሸባሪ ነው ስለሚሉት ወይም አንዳንድ ተማሪዎች በመልኩና በቅርጹ ስለሚያፌዙበት ሊሆን ይችላል::
- ማነው እንደዚያ የሚለው?
- እኔ ግን እንደዚያ ማለት አልወድም:: አንዳንድ ተማሪዎች ግን ያደርጋሉ::
- የኔ ልጅ ሰዎችን ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርግ የሚገባው መርሃቸውና ስነ ምግባራቸው ብቻ ነው::
- እቅባልም ልክ እንደዚህ ነው የሚለው::
- እቅባል ማነው?
- የነገርኩህ ሙስሊሙ ሕንዳዊ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ነው::
- አዎ ቁርኣን ውስጥ ፦ ‹‹በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤›› (አልሑጁራት፡13) የሚል አንቀጽ ይገኛል:: እግዚአብሔርን በመፍራትና ትእዛዛቱን በመፈጸም ደረጃው ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው በቆዳ ቀለሙም ሆነ በዘሩ ምክንያት ከሌላው ሰው አይበልጥም::
- እስላም የዐረቦች ብቻ አይደለም? እቅባል ሙስሊም መሆኑን ሳውቅ በጣም ነው የተገረምኩት !

- የሙስሊሞች ቁጥር አንድ ቢሊዮን በተኩል ያህል ነው፤ከቻይና እስከ አሜሪካ ተሰራጭተው ይገኛሉ:: የሚገርመው ደግሞ 80% የሚሆኑ ሙስሊሞች ከዐረቡ ዓለም ውጭ ያሉ መሆናቸው ነው::
- እንዲህ ዓይነቱ እኩልነት እኛም ዘንድም ምነው በኖረ ብዬ ብዙ እመኛለሁ !
- እንዴት ማለትሽ ነው?!
- አንዳንድ ተማሪዎች ከናቴ በወረስኩት የፊቴ ቅርጽና በተክለ ሰውነቴ ምክንያት እንግሊዛዊት አይደለችም፣ሕንዳዊት ናት እያሉ ይንቁኛል::
- የኔ ልጅ ይህ የተከለከለ ነው፣ለአስተማሪሽ ልትነግሪያት ትችያለሽ::
- እነግራታለሁ፤አስተማሪዋ ፊት ብቻ እንጂ መናገራቸውን እንደማያቆሙ ግን አውቃለሁ::

ሕጻናቱ ለቀው ሲወጡ ጆርጅ ከራሱ ጋር አጉረመረመ . .

- ሳሊ እንኳ ሳትቀር በሞራል ሥርዓትና በጥሬ ሞራል መካከል ያለውን ልዩነት ትረዳለች ማለት ነው!

ካትሪና እስከመጣችበት ጊዜ ድረስ ጆርጅ ቁርኣን ማንበቡን ቀጠለበት . .

- ረዥም ቀን ነበር!
- መልካም ፈቃድሽ ከሆነ አንዴ ይቅርታ::
- ምንድነው ምታነበው?
- የሙስሊሞችን መጽሐፍ ነው የማነበው፤የጀመርኩትን እስካጠናቅቅ ጥቂት ትታገሽኝ?
- የት ደርሰሃል?
- ገና አልጨረስኩም::
- በጣም ሰብሰብ ብለህ በጽሞና እያነበብክ ነው ማለት ነው::
- እግዚአብሔር በሙስሊሞች መጽሐፍ ውስጥ የሚለውን አዳምጭማ ፦ ‹‹አ.ለ.ረ. (አሊፍ ላም ራ)፤ ይህች (አናቅጽ) ከመጽሐፉ አንቀጾችና ገላጭ ከኾነው ቁርኣን ነው:: እነዚያ የካዱት (በትንሣኤ ቀን) ሙስሊሞች በኾኑ ኖሮ ብብዛት ይመኛሉ:: ተዋቸው ይብሉ፤ይጠቀሙም፤ተስፋም ያዘናጋቸው በእርግጥም (መጥፎ ፍጻሜያቸውን) ያውቃሉ::›› [አልሑጁራት ፡1-3]
- በተለይ ይህን አንቀጽ ወይም ምንባብ ለምን መረጥክ?
- የዚህ መጽሐፍ አንዳንዶቹ ምንባቦች በተለይ ለኔ የተላለፉና እኔን የሚያናግሩኝ ሆነው ለምን እንደሚሰሙኝ እኔ እንጃ፤ከነዚህም ይሸኛው አንዱ ነው::

www.path-2-happiness.com

-በዚህ ምንባብ አንተን የሚያናግረው ምኑ ነው?!

-ገላጭ የኾነው መጽሐፍ . . የካዱ ሰዎች ሙስሊሞች በኾን ኖሮ ብለው አጥብቀው መመኘታቸው . . ከሃዲዎቹን መብላት መጠጣትና መደሰት ያዘናጋቸው መሆኑ . . ይህ ሁሉ እኔን በተለይ የሚያነጋግረኝ ሆኖ ለምን እንደሚሰማኝ አላውቅም?

-ሙስሊም ብሆን ኖሮ ብለህ ትቆጫለህ ማለት ነው?!

-አየሽ ይህ የማይሆን ነው . . ግና ለጥያቄዎቼ መልስ ማግኘት እፈልጋለሁ፤የመታደልን መንገድ ማወቅ እሻለሁ፤ከዚህ ሁሉ በመብላት በመጠጣትና በመዝናናት እንዳልዘናጋ እሰጋለሁ፤ለዚህ ነው አንዳንዶቹ አንቀጾች እኔን በግል የሚመለከቱኝ ሆነው የሚታዩኝ::

-የመታደል መንገድ እስላም ራሱ መሆን አይችልም?!

-እህህ፣ልክ የአደምን አነጋገር አመጣሽ፤ያ ይሆናል ብዬ ባልገምትም በሌሎች ሃይማኖቶች ላይ እንዳደረግሁት ሁሉ ለእስላምም በግምት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ሳይንሳዊ ምላሽ እሰጣለሁ::

-በነገራችን ላይ አደም እንዴት ሆኖ ይሆን?

-አንቺ ነሽ ከኔ በኋላ ያየሽው፣በሥራ ቦታ ብዙ ጉዳዮች ስለ ተፈራረቁብኝ ዛሬ አልጠየቅሁትም::

-የምስራች በለና፣ምን አዲስ ነገር ተገኘ?!

-መርሆዬን ሳልጥስ ወደ ጀርመን እንድጓዝ ካኽ አዲስ ሀሳብ አቅርቦልኛል::

-ተቀብለህ ችግሩ እልባት አግኝቷል ማለት ነው?

-አይደለም፣አስብበታለሁ ነው ያልኩት፤በዚህ ወቅት መሄድ ግን አልፈልግም::

-እናም አሁን ጉዳዩ የሀሳብ ልዩነት እንጅ ምንም ያህል የመርህ ችግር አይደለም ማለት ነዋ?

-ካኽም እንደዚህ ነው ያለኝ . . እውነቱን ለመናገር ግን ከዚያ በኋላ ሌላ ምክንያት ተፈጥሮ ነው፤ቶምን አማክሬ ስለነበር ሌላ ሀሳብ አቀረበ::

-የቶም ሀሳብ ምንድነው?!

-ወደ ግብጽ እንድጓዝ ነው የሚፈልገው::

-ጀርመን አላልከኝም ነበር?

-ካኽ ወደ ጀርመንን፣ግብጽ ወይም ዩክሬን የመጓዝ ሦስት አማራጮችን የሰጠኝ ሲሆን ቶም ግን ወደ ግብጽ እንድጓዝ እየጎተጎተኝ ነው::

-እናም ለጥያቄዎችህ ምላሽ ፍለጋ ነው ማለት ነው?

-አዎ፣እንደ ጀርመን ያለውን የሰለጠነ ጠንካራ አገር ትቼ ወደ ኋላ ቀር የአፍሪካ አገር መሄድ ግን አልፈልግም::

-ግብጽ እስላምና ሙስሊሞችን ከማወቅ ባሻገር የኮፕት ክርስቲያኖች፣የናይልና የፒራሚዶች አገርም ነች::

-ግብጽን በሚገባ የምታውቂ ትመስያለሽ!

-አዎና፣የቅብጥ ኦርቶዶክስ ክርስትና አገር፣ከዓለም አስደናቂ ነገሮች አንዱ የሆኑት የፒራሚዶች አገር፣በዓለም ረዥሙ ወንዝ ናይል የሚፈስባት አገር . . ናት:: ዘውትር ካቶሊካዊነቴን ከሚተች አንድ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ጋር ትውውቅ አለኝ . . እኛ እናንተ ፕሮቴስታንቶችን በለዘብተኝነትና በግድ የለሽነት እንደምንወቅሰው እርሱ ደግሞ ካቶሊኮችን በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ግድ የለሾች መሆናቸውን ይተቻል::

-እኛ ከእናንተ እንደተገነጠልን እናንተም በተራችሁ ከነሱ የተገነጠላችሁ ስለሆነ ነዋ! እናም አንቺም እንደ ቶም ሁሉ ከጀርመን ይልቅ ወደ ግብጽ መሄዴን ትደግፊያለሽ ማለት ነው?

-ሊሆን ይችላል፣ለማንኛውም ግን ውሳኔው ያንተ ነው:: እኔ የጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት የሆኑ አገሮችን እወዳለሁ፣አንተ ደግሞ ምናልባት በዘመናዊ ስልጣኔ የተራመዱ አገሮችን ትወድ ይሆናል:: በሕንድ ጉዞህ ግን ደስተኛ ነበርክ::

-በነገሩ ላይ አስብበታለሁ፤አንቺ ግን በመርህ ደረጃ ጉዞውን የደገፍሽ ትመስያለሽ::

-ከተከታታይ ጉዞዎችህ በኋላ ከኛ ጋር ቆይተህ ማረፍህን ብፈልግም፣መርሆውን መጣስ ለአንድ ሰው ራሱን ከማጣት የተለየ አይደለም:: በመርሆህ የሙጥኝ ብለህ መጽናት ምናልባት ሥራህን የማጣት ዋጋ ሊያስከፍልህ ይችል ይሆናል፤እናም ይኸኛው ላንተ ጥሩ መውጫ መንገድ ነው::

-አዎ፣ይህ የተሻለ አማራጭ ሳይሆን አይቀርም፤ለማንኛውም እስከ ነገ ድረስ ጊዜ ስላለኝ አስብበታለሁ:: ያንቺን በተመለከተስ አዲስ ነገር አለ?

-አዎ፣የኔም እልባት ሳያገኝ የቀረ አይመስለኝም::

-እልባት?! በምን ተደመደመ?

-የያዝነው ወር እነሱ ዘንድ የምሠራበት የመጨረሻው ወር ይሆናል ብዬ አስባለሁ::

-ከዚያስ?

www.path-2-happiness.com

- ሌላ ቦታ ለሥራ አመልክቼ በሂደት ላይ ነኝ፣የደረስኩበትን በተከታታይ ስለማሳውቅህ ምንም ልታስብ አይገባም። አሁን ለሳሊና ለማይክል ምሳ ላዘጋጅ።

(4)

በማታው የሕሙማን መጠየቂያ ሰዓት ጆርጅ አደምን ለመጠየቅ ወደ ሆስፒታሉ አመራ . . ወደ ክፍሉ ሲገባ ከሸይኽ ባስም ጋር እየተጨዋወቱ ሲስቁ አገኛቸው . .

- እንደምን ዋላችሁ፣ዛሬ ሁለታችሁም ደስተኞች ትመስላላችሁ።
- አልሐምዱሊላህ እኔ ሁሌም ደስተኛ ነኝ፣ከወንድሜ ከአደም ጋር በመሆኔ ደስታዬ ዛሬ ከወትሮው የበለጠ ሆኗል፣አንተስ እንዴት ነህ?
- ደህና ነኝ፣አደም እንዴት ነህ አሁን?
- እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን በጥሩ ሁኔታ ላይ ነኝ።
- አመጣጤ አንተን ለማየትና በሆነ ጉዳይ ላይ ላማክርህ ነበር !
- ደስ ይለኛል፣ቀጥል።
- ብዙ ሳላራዝምብህ ከመርሆዬና ከሥራዬ አንምዱን የመምረጥ ፈተና ውስጥ ገብቼ ከብዙ ትግል በኋላ መርሆዬን መርጫለሁ፣ነገሮች የተስተካከሉ ቢሆንም ካልተጠበቀ ድንገተኛ የጉዞ ግዴታ ጋር ነው።
- በመርሁ ላይ የሚጸና ማንኛውም ሰው ውድቀት የሚያጋጥመው መስሎ ቢታየው እንኳ በመጨረሻ ድል አድራጊ ይሆናል።

ባስም ፈገግ ብሎ ፦

- እኔም አንዳክልበት ፍቀዱልኝ፣ቁርኣን ውስጥ ነብያት በመርህ ላይ በመጽናታቸውና በትዕግስታቸው እንዴት ድል አድራጊዎች እንደሆኑ አላነበብክም?
- ቁርኣን ውስጥ እንደተመለከተው ሁሉ እናንተ ሙስሊሞች ዘንድ ሁሉም ነብዮች ድል አድራጊዎች ናቸው። እናንተ ዘንድ ዒሳ እንኳ ሳይቀር ድል አደረገ እንጂ አልተገደለም፣በእኛ ዘንድ ያለው ግን ኢየሱስ የሰው ልጆችን ለማዳን ነፍሱን ሰውቶ ተገደለ የሚል ነው።

ባስም በፈገግታ ፦

- እህህ፣ስለዚህም እስላም ለዒሳ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) የተለየ አክብሮት አለው፣ከናንተ ይበልጥ ይወዳቸዋል።

- ይሁን እንጂ ከሰብአዊ ፍጡርነት የወጣ ልዩ ባህሪ እንዳለውም ሆነ ለሰው ልጅ ቤዛ መሆኑን ግን አይቀበልም።
- እንዳውም ከዚያ የተሻለ አክብሮትና ልቅና ይሰጣቸዋል፣ቁርኣንን ያነበብክ አትመስልም፣የነብዩ ዒሳን (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) ታሪክ ቁርኣን ውስጥ ብዙ ቦታ ላይ አላነበብክም?
- ትርጉሙን ካንተ የወሰድኩት ገና ትናንት ነው፣ይሁን እንጂ አብዛኛውን አንብቤአለሁ፣የኢየሱስንም ታሪክ አንብቤአለሁ።
- አብዛኛውን ካነበብክ ዘንዳ በመርየም ምዕራፍ ውስጥ በዒሳ አንደበት የተነገረውን የአላህ ቃል ትርጉም አንብበሃል ብዬ አስባለሁ ፦ ‹‹በየትም ስፍራ ብሩክ አድርጎኛል፣በሕይወትም እስከ አለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል።›› [መርየም:21] ‹‹ሰላምም በኔ ላይ ነው፣በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን፣ሕያው ኾኘ በምቀሰቀስበትም ቀን፤›› [መርየም:33] በኣሊ ዒምራን ምዕራፍም እንዲህ ይላል ፦ ‹‹ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል፤(ይላልም) ፦ እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤በርሱም እተነፍስበታለሁ፤በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል። በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፣ለምጸኛንም አድናለሁ፤ሙታንንም አስነሳለሁ። የምትበሉትንና የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤የምታምኑ እንደ ኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ ታምር አለበት።›› [ኣሊ ዒምራን:49]
- አዎ የጠቀስካቸውን ሁሉ አንብቤአለሁ፤በጣም የሚደንቀው ግን ለክርስትና ያላችሁ አክብሮት ነው !
- ግልጽነትን ትወዳለህ?
- እህህ፣በእርግጠኝነት አዎ።
- እናንተ የኛን ያህል ለዒሳ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) ተገቢውን ክብር አትሰጡም።
- እንዴት?
- እናንተ ተስቅለዋል ብላችሁ ታምናላችሁ፣እኛ ግን አላህ ከጠላቶቻቸው ተንኮል አድኗቸው ከፍ አደረጋቸው እንጂ አልተገደሉም ብለን ነው የምናምነው። የሚከተለውን የአላህ ቃል አላነበብክም ፦ ‹‹ . . አልገደሉትም፤አልሰቀሉትምም፤ግን ለነሱ (የተገደለ ሰው በዒሳ) ተመሰለ፤ . . ›› [አል ኒሳእ:157]

www.path-2-happiness.com

- ልክ ነው፣አንብቤአለሁ::
- እናንተ ወይም ቢያንስ አንዳዶቻችሁ ንጽህቱ መርየም (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) አላህ ከእንዲህ ዓይነቱ አነጋገር ይጠብቀንና ዝሙት ፈጽማለች ብላችሁ ታምናላችሁ::
- እናንተስ የኢየሱስ አባት ማነው ብላችሁ ነው የምታምኑት?
- አባት የለውም፣አላህ አደምን ካለ አባትና ካለ እናት እንደ ፈጠረ ሁሉ ዒሳን ካለ አባት ከእናቱ ፈጥሮታል፤ለዚህ ነው ገና ጨቅላ ሕጻን ሆኖ የእናቱን ንጽሕና ለማረጋገጥ አላህ እንዲናገር ያደረገው::
- ከሰው ልጆች አባት ከአደም (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) ጀምሮ ላሉት መለኮታዊ ሃይማኖቶች ሁሉ የላቀ አክብሮት አለን፤ሁሉም ነብያት ጥሪ ያደርጉ የነበረው ለአንድ መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን እሱም ተውሒድ ወይም የአላህን አንድና ብቻ እውነተኛ አምላክነት ማረጋገጥ ነው:: እያንዳንዱ ነብይም ከርሱ ቀጥሎ ለሚመጣው ነብይ መንገድ በማመቻቸት መምጣቱን ያበስር ነበር:: በትርጉሙ ውስጥ የሚከተለውን አላነበብክም ፦ ‹‹የመርየም ልጅ ዒሳ ፦ የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ የማበስር ስኾን፣ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ::›› [አል ሶፍ:6] በናንተ መጽሐፍ ውስጥም ይህንኑ የሚያረጋግጥ አለ አይደለም?!
- የለም፣ያልከውን ነገር አላነበብኩም፤ምናልባት ገና ባላነበብኩት ቀሪ ክፍል ውስጥ ይኖር ይሆናል:: እኛ ዘንድም በአንዳንዶቹ መጽሐፎቻችን ውስጥ ብቻ ያልከው ነገር ሰፍሯል::
- የወንጌል ችግር ከኦሪጂናሉ መዛባቱ፣መከለሱና መለዋወጡ፣በተለያየ አጻጻፍ በተለይም ክርስቲያኖች በአይሁዶች እጅ ስቃይና መከራ ይደርስባቸው በነበረበት ዘመን በተደጋጋሚ መጻፉ ነው::
- ይህየሁሉምመለኮታዊመጽሐፎችችግርይመስለኛል፣ያልተዛባ፣ያልተከለሰና ሳይለወጥና ሳይምታታ ኦሪጂናል ቅጂውን እንደ ጠበቀ የሚገኝ አንድ መጽሐፍ እንኳ እስኪ አምጣልኝ::
- ቁርኣን ፈጽሞ አልተዛባም፣በጭራሽ አልተለዋወጠም፤ይህ በሙስሊሞች ዘንድም ሆነ ሙስሊም ባልሆኑትም ዘንድ የተረጋገጠ ነው:: ይህ ብቻ

ሳይሆን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ከቁርኣን ይበልጥ ጥንታዊነቱን ባለበት ጠብቆ ሳይጨምር፣ሳይቀንስና ሳይበረዝ በትክክል የተላለፈ ሌላ ሰነድ የለም፤ይህም ሙስሊም ባልሆኑ ወገኖች ዘንድም ተቀባይነት ያለው ይመስለኛል:: ከነብዩ ብዙ ሺ ሰዎች ናቸው ሰምተው ያስተላፉት፣እነሱም በተራቸው ለብዙ ሺ ሰዎች አስተላልፈዋል፤በዚህ ሂደት ውስጥ ያንዲት ፊደል ወይም ከዚያ ያነሰ ልዩነት እንኳ አልተፈጠረም::
- ከፊደል ያነሰ ምንድነው? !
- ቁርኣን የራሱ የሆነ የአነባበብ ስልትና የድምጽ አወጣጥ አለው:: ይህ እንኳ ሳይቀር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና በነበረበት ሁኔታ ተጠብቆ የኖረ ነው::
- በተለያዩ ቅጂዎቹ መካከል ምንም ልዩነት አይታይም ?
- ፈጽሞ የለም፣እርግጥ ነው ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ የተለያዩ የአነባበብ ስልቶች (ቅራኣት) ይገኛሉ፣ከዚህ ውጭ ሌላ ልዩነት የለም::
- ከአነጋገርህ እንደምረዳው ለምሳሌ ኢየሱስ በአንዱ የአነባበብ ስልት ተገድሏል፣በሌላው አነባበብ ደግሞ ራሱን አድኗል የሚል ሊሆን ይችላል?
- አይችልም ! ቁርኣን አንድና አንድ ብቻ ነው፣ምንም ልዩነት የለበትም:: ያልኩት የአነባበብ ዘዬ ልዩነት ብቻ ነው፤የንባብ ዘዬ ልዩነቱ በአብዛኛው ትርጉሙንም ሆነ ቃላቱንም እንኳ የማይነካ የድምጼ አወጣጥ ልዩነት ብቻ ነው::
- እስከዚህ ደረጃ ድረስ? ! ትንሽ ያጋነንክ መሰለኝ!
- የናንተ አውራፓውያን ተመራማሪ ሊቃውንት የሚሉትን ብታነብ ልክ አሁን ከምነግርህ ጋር ቃል በቃል የተጣጣመ መሆኑን መረዳት ትችላለህ::
- ግና . . ከሚገባው በላይ ያጋነንክ ወይም ትንሽ ስሜታዊ የሆንክ አይመስልህም?
- ምናልባት ሊሆን ይችላል አንተ ግን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ለጥያቄዎችህ ምላሽ ለማግኘት ፍለጋ ላይ መሆንህን አደም ነግሮኛል:: ሁሉንም ሃይማኖቶች ተራ በተራ የመረመርክ መሆንህንና እስላምን በማወቅና በመመርመር ሂደት ላይ እንደምትገኝ፣በእውነታ ላይ የተመሰረተ ሚዘናዊ ሳይንሳዊ አቀራረብ እንደምትወድም ነግሮኛል::

አደም ጣልቃ ለመግባት ተመቻችቶ ተቀመጠ ፦
- ድንቅ ውይይት ነው፤በማቋረጤ ግን ይቅርታ ይደረግልኝ . . ጆርጅ

ልታማክረኝ የነበረው በምን ጉዳይ ላይ እንደሆነ ንገረኝ::

-ባስም የመጣሁበትን ጉዳይ አስረሳኝ::

-ጆርጅ ይቅርታ አድርግልኝ::

-ዋነው ነገር . . በመርሆዬ ከጸናሁ በኋላ ወደ መስቀለኛ መንገድ ደረስኩ፤ከመርሆዬ ጋር የማይጻረር የሥራ ጉዞ ማድረግ ወይም ሥራዬን መልቀቅ እንደ አማራጭ ቀርቦልኛል:: ሀሳቤ ወደ መጓዙ ያጋደለ ቢሆንም አንዳንዴ ጉዞ የሰለቸኝ ሆኖ ይሰማኛል::

-ካንዱ ጉዞ ሳታርፍ ሌላ ጉዞ !

-ልክ ነህ፣እውነቱን ለመናገር በአሁኑ ወቅት የመጓዝ ፍላጎት የለኝም፤በሥራ መስክ ለገጠመኝ ቀውስ ግን ተመራጩ መፍትሔ ይመስለኛል::

-የአካል ድካም የራስን መርሆ ከመጣስ ይቀላል፤አንድ ሰው የራሱን መርሆ ከጣሰ ግን አካሉ ብቻ ሳይሆን ነፍሱም ትደክማለች:: ለመሆኑ ጉዞው ወዴት አገር ነው?

-ወደ ጀርመን፣ወደ ዩክሬን ወይም ወደ ሌላ አገር ነው::

-ወደ አንዱ እስላም አገር ቢሆን ምኞቴ ነበር፤ምድራዊ ሰው ሰራሽ ሃይማኖቶችን ለማወቅና ለመመርመር፣በመቀጠልም መለኮታዊ ሃይማኖቶችን - አይሁዳዊነትንና ክርስትናን - ለማወቅና ለመመርመር እንደ እንደ ተጓዝክ ሁሉ እስላምን በይበልጥ ለማወቅና በቅርበት ለመረዳት ጉዞ እንድታደርግ ስመኝ ነበር::

-ጀርመን፣ዩክሬን ወይም ግብጽ::

-አደም መሬት መሬቱን እያየ እጆቹን ለቀቅ አደርጎ ፦ ወይኔ ግብጽ እንዴት እንደናፈቀችኝ ልነግራችሁ አልችልም፤እኔና ሸይኽ ባስም ከግብጽ ነን፤ወደ ግብጽ ከተጓዝክ እስላምን በይበልጥ ማወቅ ትችላለህ ብዬ አስባለሁ::

-አንተ ግብጻዊ ነህ? !

-አዎ . . ከዚህ በፊት የነገርኩህ ይመስለኛል::

-ሊሆን ይችላል፣አላስታውስም::

-ወደ ግብጽ ከሄድክ ወዳጆቼ እዚያ አቀባበል እንዲያደርጉልህ እነግራቸዋለሁ፤አገሩን ያሳዩሃል፣ወደ ቱሪስት መዳረሻዎች ይወስዱሃል:: ባስም ደስታ በተሞላው ቅላጼ ፦

-ወንድሜ ካይሮ ውስጥ የፊዚክስ መምህር ነው፣የምትፈልገውን ሁሉ ሊያመቻችልህ ይችላል::

-ፍላጎቴ ወደ ጀርመን መሄድ ቢሆንም ያማከርኳቸው ሁሉ ወደ ግብጽ ሂድ እያሉኝ መሆኑ ነው የሚገባኝ፤ምናልባት ነገ ለካኽ ወደ ግብጽ እንደምሄድ አሳውቀው ይሆናል::

-እኔም ለወንድሜ ለመንገር ያንተን ምላሽ እጠብቃለሁ::

-ካንተ ጋር መጓዝ ብችል ኖሮ ግብጽ ናፈቃኛለች:: ሰዎቹ፣አገሩና ሁሉም ነገሯ ናፍቆኛል፤ከመጣሁ ሁለት ዓመት ያህል ሆነኝ::

-ታዲያ ከኔ ጋር ለምን አትጓዝም?

-በአላህ ፈቃድ ተነገ ወዲያ ከሆስፒታል እወጣለሁ፤የዩኒቨርሰቲ ፈተና ከሦስት ሳምንት በኋላ ነው::

-ደህና መሆንህ በራሱ በቂ ነው፤አንተና ባስም ከግብጽ እንዳመጣላችሁ የምትፈለጉትት ስጦታ ምንድነው?

-እህህ፣ ራሷን ግብጽን እንዳለች አምጣልኝ::

-እህህ::

ማታ ላይ ጆርጅ ኢሜይሉን ከፈተ፤ቁርኣንን አስመልክቶ ልኮላቸው ለነበረው መልክት ከወዳጆቹ የተላኩለት ምላሾች በተከታታይ ደርሰዋል:: ሁሉንም አንድ ላይ ጨምቆ ማጠቃለያውን ለሁሉም መልሶ ላከላቸው . .

‹‹ሌቪ ፦ ግልጽ መልስ የለኝም፤ከፊሉን ብቻ ነው ያነበብኩት፤ጊዜው በቂ አልነበረም::

ሐቢብ ፦ በአስተላለፉ ከተቀሩት መለኮታዊ መጽሐፍት ሁሉ የበለጠ ተአማኒነት ያለው ነው::

ቶም ፦ ይቅርታ . . በክሊኒኩ ጉዳይ ተወጥሬ ነበር፤ከሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ጥቂቱን ብቻ እንጂ አላነበብኩም፣ግን አነበዋለሁ::

ካትሪና ፦ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ ይመስለኛል::

ጃኖልካ ፦ ቁርኣን ያለ ምንም መዛባት ከሙሐመድ የተላለፈ መሆኑ በሳይንሳዊ መንገድ የተረጋገጠ ነው:: በሙሐመድ የሚያምን ሰው ቁርኣን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ መሆኑን አምኖ መቀበል ይኖርበታል::››

ዱብ ዕዳ የሆነበት ነገር ጃኖልካ በመልክቱ መጨረሻ ስሙን ካሰፈረ በኋላ ትሪፖሊ - ሊብያ ብሎ ማስከተሉ ነበር:: ከዚያም ለአዲስ ደብዳቤ ዊንዶ ከፈተ . . ለሁሉም የሚከተለውን ጻፈላቸው . .

‹‹ስምንተኛው መልክት ፦ እስላምን በይበልጥ እንድናውቅ እፈልጋለሁ፤ለአስቸኳይ ጉዳይ ወደ ግብጽ አገር ሳልሄድ አልቀርም::

www.path-2-happiness.com

በመሆኑም ፦

1. እስላምን ወይም ግብጽን ለማወቅ ዋቢ መጻሕፍትና መጣቀሻዎችን የሚጠቁመኝ ሰው ካለ፤
2. ለውይይት የሚቀርቡ ወይ ሊነሱ የሚገቡ ጥያቄዎች ያሉት ሰው ቢኖር፤
3. ማድረስ የሚገቡ መልሶች ያሉት ሰው ቢኖር፤

መልሶቻችሁን በሁለት ወይም ሦስት ቀናት ውስጥ እጠብቃለሁ። እንደ ተለመደው ጨምቄ ማጠቃለያውን መልሼ እልክላችኋለሁ።

ጆርጅ››

ስርቆቱ . .

www.path-2-happiness.com

15 ስርቆቱ . .

ስርቆቱ . .

(1)

-ካኽ ለጉዞ ዝግጁ ነኝ . . እንድትረዳልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር ጉዳዩ የመርሕ እንጂ የጥቅም አለመሆኑን ብቻ ነው።

-መልካም . . የምትገባው ግዴታ ግን ይኖራል!

-ግዴታ?! የምን ግዴታ?

-ለሥራ አመራር ቦርዱ ደብዳቤ ጽፈህ የሥራ መልቀቂያ ጥያቄህን መሰረዝህንና የቀረበልህን ጉዞ መቀበልህን ታሳውቃቸዋለህ።

-ለምን?

-ያስነሳኸው አውሎ ነፋስ የፈጠረው ችግር እንዲያበቃ።

-ጥሩ፣ ችግር የለውም። ጉዞው መቼ ነው?

-በአጭር ጊዜ ውስጥ ቦታ ሊያዝልህ ይችላል፤ግን ወዴት ለመሄድ ነው የመረጥከው?

-ወደ ግብጽ ለመሄድ ተስማምቻለሁ።

-እህህ . . አሁንም በደስተኝነት መንገድ ፍለጋው ላይ የጸናህ ትመስላለህ! ከአፍታ በኋላ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ትኬቶቹን ይዞልህ ይመጣል፤የመታደል ጉዞ ይሁንልህ።

-አመሰግናለሁ።

ጆርጅ ወደራሱ ቢሮ ሄዶ አስር ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ከተፍ አለ . .

-ለግብጽ ጉዞህ ለተነገወዲያ ኦኬ አስደርጌልሃለሁ። ይመችሃል?

-ጥድፊያው ለምንድነው?

-እኔ እንጃ፣ይህ የካኽ ፍላጎት ነው። ለማንኛውም መጓዝህ ከኛ ጋር መስራትን ትቀጥላለህ ማለት በመሆኑ አስደስቶኛል።

-አይቀጥልም ያለው ማነው?

-ካኽ ከሥራ ሊያስወጣህ እንደሚፈልግ በሠራተኛው መካከል በስፋት ሲወራ ነበር።

-ቀደም ሲል ፈርቼ ነበር። አሁን ግን አንዱ ሌላውን የሚያባርር ከሆነ እርሱን የማባርረው እኔ ነኝ የሚል እምነት ለምን እንዳሳደርኩ አላውቅም።

www.path-2-happiness.com

ለበጎ ስሜትህ አመሰግናለሁ::

-ካኽ ወረቀቶቹን በኢሜይል እንዲልክልህ አስታውሰው ብሎኛል::

-እኔን በጥርጣሬ ዓይን ማየት ጀምሯል፤ከአፍታ በኋላ የፈለገውን ኢሜይል እልካለሁ::

-ሰነዶቹና መረጃዎቹ ተሟልተውና ተቀናጅተው ዛሬ ይደርሱሃል:: ጉዳዩን በድንገት ስለ ሰማን ገና አልተዘጋጀንበትም ነበር::

-እጠብቃለሁ . . አመሰግናለሁ::

-ጆርጅ እንደ ወዳጅ የምመክርህ ነገር ቢኖር ካኽን አንድትጠንቀቀው ነው፤ፍቀድልኝ ልሂድ::

-አመሰግናለሁ፣መልካም ስነምግባርና በመርህ መጽናት፤ ማሴርንና ማጭበርበርን ድል እንደሚያደርጉ እርግጠኛ ሁን::

ስለ ጉዞው ለኣደም ለመንገር ጆርጅ የስልክ መነጋገሪያውን አነሳ . .

-ሃሎ . . አንተ ግብጻዊው፣ወደ አገራችሁ ልጓዝ ትኬቴን ኦኬ አስደርጌአለሁ::

-እንኳን ደስ ያለህ . . በእውነት ትልቅ የምስራች ነው:: ወንድማቸው አቀባበል እንዲያደርግልህ እንዲደውሉለት ለሸይኽ ባስምም እነግራለሁ፤እንደኔ ወንድም አይደለም እንግሊዝኛን አቀላጥፎ ይናገራል:: ጉዞው መቼ ነው?

-ተነገ ወዲያ ነው፤ጉዳዩ ከጠበቅሁት በላይ አጣዳፊ ሳይሆን አልቀረም::

-ሆስፒታል ውስጥ ብቻዬን ስለ ሆንኩ ዛሬ ወደኔ መምጣት ትችላለህ?

-የሚመችህ ከሆነ ከአፍታ በኋላ እመጣለሁ፤አሁኑኑ እንቀሳቀሳለሁ::

-በጣም ይመቸኛል . . እጠብቀሃለሁ::

ጆርጅ ወደ ሆስፒታሉ ደረሰ:: ኣደምን አልጋው ላይ ሆኖ ሲያነብ አገኘው . .

-ሰላም፣በንባብ የተጠመድክ ትመስላለህ፣ምንድነው የምታነበው?

-የአላህን መጽሐፍ ቁርኣንን ነው የማነበው::

-ከዚህ በፊት አላነበብከውም ነበር?

-በጣም ብዙ ጊዜ አንብቤዋለሁ፤በየቀኑ ማንበብ እወድለሁ::

-በየቀኑ?! አይሰለቻችሁም?!

-አዎ በየቀኑ የተቻለንን ያህል እናነበዋለን፤በዚህም ለዛውን እናጣጥማለን:: የዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ታምር በአላህ ፈቃድ ድዳ ሆኖ የተፈጠረውን ሰውና ለምጻምን ማዳን እንደ ሆነ ሁሉ፣የሙሐመድ ታምር ደግሞ ይህ ዘላለማዊ ሕያው መጽሐፍ ቁርኣን ነው::

-ዘላለማዊ ሕያው ስትል ምን ማለትህ ነው?

-ከመዛባትና ከመለዋወጥ የመጠበቁን ኃላፊነት አላህ ራሱ የወሰደው መሆኑን መግለጼ ነው:: የሚከተለውን አንቀጽ በቁርኣኑ ትርጉም ውስጥ አላነበብክም ፦ ‹‹እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፤እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን::›› [አልሒጅር:9] . . ስለ እውነት . . ይህን ስታነብ ታምራታዊነቱ አይሰማህም?

-እውነቱን ለመናገር . . ትርጉሙን እያነበብኩ ሳለሁ ትርጉሙን ሳይሆን በኦሪጂናል ቋንቋው ምነው ባነበብኩት ብዬ ተመኘሁ:: ትርጉሙን እያነበብኩም በአያሌ ጉዳዮች ላይ እኔን በተለይ የሚያናግረኝ ሆኖ ነው የሚሰማኝ::

-አንተን በይበልጥ የሚያናግሩ ርእሰ ጉዳዮችን አውቃቸዋለሁ::

-እንዴት አወቅህ?

-የአላህ አንድነት (ተውሒድ)፣ስሞቹና ባህርያቱ፣ኃያልነቱ፣ርህሩህነቱና ወዳድነቱ . . ማንኛውንም ሰው በከፍተኛ ደረጃ ጠልቀው የሚሰሙት ናቸው:: ይህን ለመንገር ትንቢት ማወቅ አያስፈልገኝም::

-ኦህ፣እውነትህን ነው:: በተጨማሪም እስላም ዓለማዊና መንፈሳዊ ሕይወትን ማጣጣሙና ልዩ የሆነ መንፈሳዊነቱ በጣም ከሚማርኩኝ ነገሮች መካከል ናቸው::

-እስላም የሰውን ልጅ ሕይወት በሁሉም ጎኖቹ የተሟላ እንዲሆን ያደርጋል:: ዓለማዊ ኑሮን ፈተው ምናኔ፣ምንኩስናም ሆነ ባህታዊነት፣ከፈጣሪ አምላክ መራቅም የለበትም:: የልቦና ፍጹምነት እስካለ ድረስ እስላም ሕይወትን በሙሉ አምልኮተ አላህ (ዕባዳ) አድርጎ ይመለከታል::

-ለማንኛውም ተነገወዲያ ወደ ካይሮ መጓዜ ነውና ምን ትመክረኛለህ?

-እህህ፣የዐባይን ውሃ እንድትጠጣ::

-የዐባይን ውሃ መጠጣትም እስላም ውስጥ አምልኮተ እግዚአብሔር ነው ትላላችሁ እንዴ?

-እህህ፣አይደለም እየቀለድኩብህ ነው:: በኛ በግብጻውያን ዘንድ ከዐባይ ውሃ የጠጣ ሰው ወደዚያ መመለሱ አይቀሬ ነው ተብሎ ይተረታል፣በአገሩ ውበትና ለሕዝቡ ደግነት ሲባል ማለታቸው ነው::

-ከአገር ሁሉ ላንተ እጅግ ተወዳጇ ግብጽ ናት!

-ያለ ምንም ጥርጥር ግብጽን እጅግ በጣም አብዝቼ እወዳታለሁ፤ወደዚያ የምመለስበትን ቀንም እናፍቃለሁ:: ከሁሉም በላይ የምወደው አገር ግን መካና መዲናን ነው::

-ይገርማል! ለምንድነው?

-የተወዳጁና ተፈቃሪው ነብይ የሙሐመድ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው

www.path-2-happiness.com

ላይ ይወረድ] አገር በመሆናቸው፡፡

- እኛ ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን እንደምንቆጥረው ነብያችሁ ሙሐመድን አዳኛችሁ አድርጋችሁ ትወስዳላችሁ?
- የአዳኝነት እሳቤ ከእስላማዊ እምነት ጋር ፈጼሞ ሊጣጣም የማይችል እሳቤ ነው፡፡ ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ከአላህ የተላኩ መልክተኛ ነብይ ናቸው፡፡ ሙሐመድም [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] እንዲሁ ከአላህ የተላኩ መልክተኛ ነብይ ናቸው፡፡ በመሆኑም በማመኑ ረገድ አንዱን የአላህ ነብይ ከሌላው የአላህ ነብይ አንለይም፡፡ እኛ በሁሉም የአላህ ነብያትና መልክተኞች እናምናለን፡፡ በኛ ዘንድ ማንኛውንም የአላህ ነብይ የዘለፈ ወይም ክብሩን የነካ ሰው ከሃይማኖት ጎራ ያፈነገጠ ከሃዲ ነው፡፡
- የአይሁድ ነብይ የሆነውን ሙሳ ወይም የክርስቲያኖች ነብይ የሆነውን ኢየሱስን ቢወርፍና ቢያንቋሽሽ እንኳ?
- አዎ፣ቁርኣን ውስጥ የሚከተለውን የአላህ ቃል አላነበብክም ፦ ‹‹ . . በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን . . ›› [አልበቀራ፡136]
- አንብቤአለሁ . . ቁርአን ውስጥ ልቤን በአድናቆት ከሞሉት አንዱ ይህ ነው፡፡ እናንተ ሙሴን፣ኢየሱስን፣ማርየምን፣ከተካታዮቻቸው በበለጠ ታከብራላችሁ፡፡ ሁለት ነገሮችን አስታወስከኝ ፦ አንደኛ ግብጻዊው ሰውየ ለካትሪና የሰጠውና ‹‹ለኢየሱስ ያለኝ ታላቅ ፍቅር ወደ እስላም መራኝ›› የሚለውን በቬንዙዌላዊው ጸሐፊ የተጻፈውን መጽሐፍ፣ሁለተኛ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱ ነብያትን፡፡
- ሁሉም ነብዮች የአላህን አንድነት በማረጋገጥ ለርሱ ብቻ አምልኮ እንዲደረግ ለማስተማር ነው የተላኩት፡፡ ይሁን እንጂ በሃይማኖቶች ላይ የደረሰው የመዛባትና የመበረዝ ሁኔታ ባእድ አምልኮ (ሽርክ) እንዲገባባቸው አደረገ፡፡
- ይቅርታ አድርግልኝ እና የራሳችንን ሃይማኖት አንተ አታስተምረንም፡፡ ከአይሁዶች ይበልጥ ስለ አይሁዳዊነት፣ከክርስቲያኖችም ይልቅ ስለ ክርስትና የምታውቅ አትሆንም፡፡
- ልክ ነህ፡፡ ምናልባት አይሁዶች ከኔ ይበልጥ ያሁኑን ሃይማኖታቸውን፣ክርስቲያኖችም እንዲሁ አሁን ያለውን ሃይማኖታቸውን ከኔ ይበልጥ ያውቁ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ከአላህ ጋር ሌሎች ባዕድ አማልክት መኖራቸው ግን አእምሮም ሆነ እውነተኛ ሃይማኖት ሊቀበለው የማይችል ነገር ነው፡፡
- እንዴት?

- አእምሮን በተመለከተ አላህ ስለ ምክንያታዊ አስረጅ የሚከተለውን ብሏል ፦ ‹‹በሁለቱ (በሰማያትና በምደር) ውስጥ ከአላህ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ በተበላሹ ነበር፤የዐርሹ ጌታ አላህም ከሚሉት ሁሉ ጠራ፡፡››]አል አንቢያ፡22[ዩኒቨርስ ሁለትና ከዚያ በላይ አቀናባሪዎች ወይም ጌቶች ቢኖሩት ኖሮ ስለሚጋጩና እርስ በርስ ስለሚናቆሩ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ በተናጋና ውጥንቅጡ በወጣ ነበር፡፡ አንዱ አንድ ነገር ሲፈልግ ሌላው ሲቃወም የሁለቱም እቅድ እውን መሆን አይችልም፡፡ በሁሉም ነገሮች ላይ መስማማታቸውም የማይታሰብ ነው፡፡ ስለዚህም ያለ ምንም ተቀናቃኝና ተቃውሞ የፈለገውን የሚያደርግና እቅዱን የሚያስፈጽም አንድ ብቸኛ ኃያል አድራጊ አምላክ የግድ መኖር አለበት፡፡ እሱም አሸናፊው ጌታ አላህ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው አላህ እንዲህ ያለው ፦ ‹‹አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፤ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም፤ያን ጊዜ (ሌላ አምላክ በነበረ) አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር፤ከፊላቸው በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር፤አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ፡፡››]አልሙእሚኑን፡91[
- ክርስትናን የሚቃረንና ሙሉ በሙሉ ከሥር የሚንድው ቢሆንም ድንቅ ፍልስፍናዊ ሎጂክ ነው!
- ፍልስፍናዊ ሳይሆን መለኮታዊ ነው፡፡ ነብዩ ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] የጠራ ተውሒድ ይዘው የመጡ በመሆናቸው፣ጣዖታዊነትን እና ባዕድ አምልኮን እንጂ ክርስትናንም አይንድም፡፡ ነብዩ ዩሱፍ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ሁለቱን የእስር ቤት ጓደኞቻቸውን የጠየቁትን ጥያቄ እንድጠይቅህ ፍቀድልኝ ፦ ‹‹(የእስር ቤት ጓደኞቼ ሆይ!) የተለያዩ (ከብር ከወርቅ ከእንጨት የተሰሩ) አምላኮች ይሻላሉን ወይስ አሸናፊው አንዱ አላህ? ከርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትግገዙም፤አላህ በርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም፣ፍርዱ የአላህ እንጅ የሌላ አይደለም፤እርሱን እንጅ ሌላን እንዳትግገዙ አዟል፤ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም፡፡››]ዩሱፍ፡39-40[ከተለያዩ ባዕድ አማልክትና ከብቸኛው እውነተኛ አምላክ ከአላህ የትኛውን ትመርጣለህ?!
- አላህ በዚህ ምንም አስረጅ አላወረደም የምትለው ግን እንዴት ነው?! አዲስ ኪዳን የኢየሱስን አምላክነት በሚናገሩ ጥቅሶች የተሞላ ነው!
- ካቀረብኩልህ ጥያቄ የሸሸህ ከመሆኑም ጋር ውይይታችንን እንቀጥላለን፡፡ አዲስ ኪዳን በስህተት የተሞላ መሆኑን ከኔ ይበልጥ አንተ ታውቃለህ፡፡ አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ቅጂዎችም የአላህን አንድነት የሚናገሩ

www.path-2-happiness.com

መሆናቸውን ከኔ በላይ አንተ ታውቃለህ:: ሌላው ቀርቶ ከተራ ምክንያት ብንነሳ እንኳ፣እርስ በርስ ሲቃረኑና ሲጋጩ የሚችሉ ከመሆናቸው አንጻር ዩኒቨርስና ስርዓቱ የሚፋለስና የሚበላሽ በመሆኑ ሁለት አማልክት መኖራቸውን አእምሮ በጀ ብሎ እንዴት መቀበል እንደሚችል አላውቅም:: አላህ ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል ፡- ‹‹በሁለቱ (በሰማያትና በምድር) ውስጥ ከአላህ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ በተበላሹ ነበር፤›› [አል አንቢያ፡ 22] ‹‹አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፤ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም፤ያን ጊዜ (ሌላ አምላክ በነበረ) አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር፤ከፊላቸው በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር፤››]አል ሙእሚኑን፡91[

- ይህ በጣም ትልቅ ጉዳይ ነው:: በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያኖች የሚገኙ ሥዕሎችን፣ቅርጻቅርጽና ምስሎችን አምርሬ እጠላለሁ:: አንድ ዓይነት ባዕድ አምልኮና የጣዖታዊነት መገለጫ መሆናቸው ይሰማኛል:: የመጣሁት ግን ይህን ለመነጋገር አይደለም!
- እስላም ውስጥ እንደ የአላህ አንድነት (ተውሒድ) ውበት፣አርኪነት፣አስደሳችነትና የሕሊና ሰላም አጎናጻፊነት ያለ የሚወደድ ነገር የለም::
- አስደሳችነቱ! አርኪነቱ! የሕሊና ሰላም አጎናጻፊነቱ!
- አዎ፣በአላህ ማጋራትና ባዕድ አምልኮ ልብን ጨምድዶ በመያዝ የሕሊና ሰላም ማጣትን ያስከትላል:: የሚከተሉትን አንቀጾች አላነበብክም ፡- ‹‹እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ፣እነዚያ ለነርሱ ጸጥታ አላቸው፤እነሱም የተመሩ ናቸው፤›› [አል አንዓም፡82] ‹‹(እነሱም) እነዚያ ያመኑ፣ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፤ንቁ አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ::›› [አል ረዕድ፡28] ‹‹ከግሣጼም የዞረ ሰው ለርሱ ጠባብ ኑሮ አልለው፤በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን::›› [ጣሃ፡ 124] . . ለዚህ አለመምጣትህን አውቃለሁ! ለማንኛውም አራዝሜብህ ይሆናልና ይቅርታ እጠይቃለሁ፤የጠየቅኸው ግን አንተ ነህ::
- ይህን ርእስ ከመዝጋታችን በፊት ቁርኣንን ሳነብ ብዙ ጊዜ አእምሮዬ ውስጥ ሲመላለስ የነበረውን ጥያቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ:: በመጨረሻው የቁርኣን አንቀጽ አንዳንድ ሰዎች በትንሣኤ ቀን ዓይነ ስውራን ሆነው እንደሚቀሰቀሱ ተወስቷል፤ይህ ጭካኔ አይመስልም?!
- አላህ ጥራትና ልቅና የተገባው ይሁንና ቁርኣን አላህን በኃያልነት እና በልዕልና በሚገልጹ፣ቸር፣ርህሩህ፣መሓሪ ይቅር ባይ፣ለጋስና አመስጋኝ . . መሆኑን፣ውብና የመጠቁ መልካም ስሞችና ባህርያት ያሉት መሆኑን

በሚገልጹ አንቀጾች የተሞላ ነው:: የውበትና የወዳድነት ባህርያት እንዳሉት ሁሉ የኃያልነትና የልዕልና ባህርያትም አሉት:: አላህ እንዲህ ብሏል ፡- ‹‹የግርማና የመከበር ባለቤት የኾነው ጌታህ ስም ተባረከ::›› [አል ረሕማን፡ 78]

- ምናልባት ይህ ወደ አእምሮዬ የመጣው ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሰፈሩትንና ለግድያ፣ለዘረፋና ለጭካኔ ሥራ የሚያዙ ጥቅሶችን ሁሌ ስለማስታውስ ሊሆን ይችላል::
- አዎ ይህ አንዱ ምክንያት ነው፤እኔ የምጨምረው ሌላ ምክንያት አለ:: ያም ክርስቲያኖች በኢየሱስ መገደል የመዳናቸውን ሀሳብ የለመዱት በመሆኑ በትንሣኤ ቀን የሚቀጣውና ገሀነም የሚገባው የምህረት ምስክር ወረቀቱን ከቤተክርስቲያን የመግዛት አቅም የሌለው ደሃ ብቻ ነው ብለው ማሰባቸው ነው::
- ማጥቃት ጀመርክ:: ካቶሊኮች እና ኦርቶዶክሶች ዘንድ እንዳለው እኛ ፕሮቴስታንቶች ዘንድ ለሽያጭ የሚቀርቡ የምህረት ማስገኛ ሰነዶች የሉንም:: በእርግጥ በኢየሱስ መሰቀል የኛ መዳን እምነት ግን ሁላችንም ዘንድ አለ::
- አንተ እንዳልከው የመዳን እሳቤ ድምዳሜ በሁሉም ጎኖቹ፣ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ሞተው ቤዛ የሆኑለት በመሆኑ ሁሉም ሰው ከኃጢአት ነጻ ሆነዋል የሚል ነው:: ይህ ደግሞ የፍርድ ቀንን ፋይዳ ቢስ ከማድረጉ በተጨማሪ በጎ ነገርና ትእዛዛትን መፈጸምም ሆነ አለመፈጸምን ትርጉም የለሽ ያደርጋል:: ኢየሱስ አንዴ ከኃጢአት ነጻ ስላደረገ ጽድቅ ሥራ ለምኔ ያሰኛል:: እናም ይህ ሁሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመጣስና ለመርህ ሳይሆን ለጥቅም መስራትን የሚያበረታታ አይመስልህም?
- ሊሆን ይችላል:: መርህ ስትል ካኽንና የመስሪያ ቤትህን ጉዳይ አስታወስከኝ፤ተነገ ወዲያ ወደ አገራችሁ ወደ ካይሮ መብረሬ ነውና ምን ዓይነት ዝግጅት እንዳደርግ ሀሳብ ታቀርባለህ?
- ከደወልክልኝ በኋላ ደውየ ስነግራቸው ከአንድ ሰዓት ያህል በኋላ እደርሳለሁ ስላሉኝ ሸይኽ ባስም አሁን መምጫቸው ነው ብዬ እገምታለሁ:: ወንድማቸው እዚያ ካንተ ጋር ይሆናል:: ከመጓዝህ በፊት ሁሉንም ነገር እንዲያመቻችልህ የምትፈልገውን ሁሉ ካንተ መስማት ይፈልጋሉ፤በምትፈልገው ነገር ሁሉ ለመተባበር ሁላችንም ዝግጁዎች ነን::

www.path-2-happiness.com

- እህህ፣ ለምን?!
- አልገባኝም!
- ለምንድነው የምትተባበሩኝ?! እኔን በማገልገላችሁ ምን ትጠቀማላችሁ?! ለጥያቄው ይቅርታ አድርግልኝ፣ግን ሁሌ ወደ አእምሮዬ ስለሚመጣ ነው::
- አንተ ወዳጄ በመሆንህ በተቻለኝ መንገድ አገለግለሃለሁ:: ሸይኽ ባስም ደግሞ ወዳጄ በመሆናቸው ለኔ ሲሉ ይተባበሩሃል:: ለጊዜው ማቆየት የምፈልገው ሌላ ምክንያትም ይኖራል::
- ይቅርታ አድርግልኝና ሌላውን ምክንያት ልትነግረኝ አትችልም?
- ግልጽ ልሁንልህና . . እኔና እሳቸውም ምናልባት ትሰልም ይሆናል የሚል ተስፋ ቋጥረናል:: በኛ ሃይማኖት አንድን ሰው በአላህ በማመንና እስላምን በመቀበል እንዲታደል ማድረግ ከምርጥ የአምልኮተ አላህ ተግባራት እንደ አንዱ ይቆጠራል::
- ኣደም ይቅር በለኝና እኔ እንድሰልም ከፍተኛ ጉጉት ቢኖርህም ፈጽሞ የምሰልም አይመስለኝም:: በመሆኑም እስላምን በማስተዋወቅም ሆነ እኔን በማገልገል በከንቱ አትድከሙ እላችኋለሁ::
- ለኛ አትፍራ፣አንተ ባትሰልም እንኳ በማሰባችንና ጥረት በማድረጋችን ብቻ እኛ ወሮታውን ከአላህ ዘንድ እናገኛለን:: የማቀርብልህ አገልግሎት ካለ ለወዳጅነትህ ስል ነውና በዚህም ከአላህ ምንዳ አገኛለሁ:: ሰዎችን ማገልገልና መጥቀምም እንዲሁ ከታላላቅ የአምኮልተ አላህ ተግባራት አንዱ ነው:: ከዚህ ሁሉ ጋር ግን አላህ መልካሙን ነገር የሻለትን ሰው ልቡን ለእስላም ክፍት ያደርግለታል የሚል እምነት አለኝ:: አንተ አስተዋይ አእምሮና ቀና መንፈስ ያለህ ሰው በመሆንህ እስላምን እንደምትቀበልም ጠንካራ አምነት አለኝ::
- ማን ያቃል ሊሆን ይችላል፤ግን አይመስለኝም:: በዚህ እንደማትከፋ ግን ተስፋዬ ነው፤ለመሆኑ ዘይቤህ ከበፊቱ ለምን ተለወጠ?
- ምን ማለትህ ነው?
- ስለ ሃማኖትህም ሆነ ስለ ቁርኣን ምንም ነገር አታነሳልኝም ነበር፤አሁን ግን ሙሉውን ጊዜ ስለዚሁ ብቻ ትናገራለህ:: በኔ ስትሳለቅና ስትሸነግለኝ ነበር?
- ሁሉንም ሃይማኖቶች እንደምትተውና ወደ እስላም እንደምትደርስ እርግጠኛ ነበርኩ:: ወደ እስላም በሚያደርስህ መንገድ ላይ ስትጓዝ ስለነበረ ለምን ላቋርጥህ? በአንዴ እንኳ ሀሳቤን አልለወጥኩም!
- መቼ ነበር?

- ታመህ ሳለህ ኦፕራሲዮኑ ሳይደረግልህ በፊት::
- ለምን?!
- ግልጽ ለመሆን ወደጄ ጀነት ውስጥ የኔ ባልደረባ እንዲሆን ስለምፈልግ እንዳትሞት ሰግቼ ነው . . ሸይኽ ባስም ይኸው መጡ፣ሸይኽ እንኳን ደህና መጡ::
- አሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱሏህ ወበረካቱህ::
- ወዐለይኩሙ ሰላም ወረሕመቱሏህ ወበረካቱህ::

ጆርጅ በመገረም መንፈስ ፦

- እንኳን ደህና መጡ፣የተለዋወጣችሁት አባባል ምንድነው?
- የኛ የሙስሊሞቹ ሰላምታ ነው:: አንዱ ለሌላው የሚያደርግ ጸሎት ነው፣ከቁሳዊና መንፈሳዊ እንከኖች ሁሉ እንዲጠብቀው አላህን መለመን ነው:: ቁሳዊ ሰላም የአካል የክብርና የንብረት ደህንነት ሲሆን፣መንፈሳዊው ደህንነት ደግሞ ሃይማኖትን ከእንከንና ከጉድለት ማዳን ነው:: ከዚያም የአላህን እዝነትና በረከቱን መለመን ነው:: ሃይማኖታችን የሠላምና የመተዛዘን ሃይማኖት ነው::
- በድጋሜ ወደ ሃይማኖት ውይይቱ ልትመልሱኝ ነው! እኔ ነገ መንገደኛ ነኝና ምን ዓይነት ፕሮግራም እንዲኖረኝ ነው ሀሳብ የምታቀርቡት?
- የፈለከውን ነገር:: ወንድሜ እዚያ ስለሆነ የምትፈልገውን ሁሉ ያመቻችልሃል::
- እዚያ ሄጄ ስለማከናውናቸው ሥራዎች እስካሁን ያወቅሁት ነገር የለም:: በኢሜይል ተልኮልኝ ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ:: ከመደበኛ ተልእኮዬ ውጭ የራሴ የግል ጉብኝት እንዲኖረኝ ስለምፈልግ የሚጎበኙ ቦታዎችንና ሌሎች ጉዳዮችንም እንድትነግሩኝ እፈልጋለሁ::
- ምን መጎብኘት ነው ምትፈልገው?
- ፒራሚዶችን፣የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና አንዳንዳንድ መሪዎቿን፣በተጨማሪም ሙስሊም የሃይማኖት ምሁራንንም ማግኘት እፈልጋለሁ::
- የጠቅስካቸው ነገሮች ሁሉ በጣም ቀላል ናቸው፤በደንብ ስለነገርኩት ወንድሜ ሁሉንም ያመቻችልሃል:: በተጨማሪ ግን ውሳኔው ያንተ ሆኖ አንዳንድ ተራ ዜጎችንም አግኝተህ ቀርበህ ብታናግራቸው መልካም ነው የሚል ሀሳብ አለኝ::
- በጣም ጥሩና አስፈላጊ ጉዳይ ነው . . የምታቀርቡልኝ ይህ የማስጎብኘት አገልግሎት ወጭ ምን ያህል ይሆናል?

www.path-2-happiness.com

- እኛ የቱሪስት አስጎብኚ ኩባንያ አይደለንም፡፡ እዚያ የሚጠየቀውን የቱሪስት አገልግሎት ክፍያ አንተ ራስህ ትከፍላለህ፡፡ ወንድሜን በተመለከተ ግን የእንግዳ መስተንግዶ አገልግሎት ነው፤እንግዳን ተቀብሎ ማስተናገድ እያንዳንዱ ሙስሊም እንዲፈጽም የሚፈለግ የአላህ አምልኮ አካል ነው፡፡
- ሁሉም ሙስሊሞች ይህንን ያደርጋሉ?
- እህህ፣በእርግጥ ሁሉም አይደሉም፡፡

ኣደም ቀና ብሎ እየቀለደበት . .

- ከሌቦችና ከኪስ አውላቂዎች ራስህን ጠብቅ፡፡ መቼም ፍጹም የሆነ ተምሳሌታዊ ማህበረሰብ በፈላስፎቹ አእምሮና በተምኔታዊ ዓለማቸው እንጂ በዚህ ዓለም ላይ የለምና ከአባይ ጠንቋች፣ከአምታታዎችና ከሌሎቹም ተጠንቀቅ፡፡
- እስላም ለመልካም ስነምግባር ጥሪ አያደርግም እንዴ?!
- ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ‹‹የተላክሁት መልካም ስነምግባራትን ምሉእ ለማድረግ ነው›› እንዳሉት ሁሉ መልካም ጸባይና ምሉእ ስነምግባር ማስፈን የተልእኮአቸው መሰረት ነው፡፡ ሙስሊሞች ለእስላም ይበልጥ ተገዥ በሆኑ ቁጥር ለመልካም ስነምግባራትም ይበልጥ ተገዥ ይሆናሉ፡፡ ጥሩ ስነምግባርና መልካም ጸባያት ከርሳቸው መላክ በፊትም ነበሩ፣እሳቸው የመጡት ግን የመጠቁና የተሟሉ ሊያደርጓቸው ነው፡፡ እያዘን አገራችን በኢኮኖሚም ሆነ በተቋማት ደካማና ኋላ ቀር ስለሆነች ጥንቃቄ አድርግ ማለት ፈልገን ነው፡፡

ባስም ቢዝነስ ካርድ አውጥቶ እጁን ዘረጋ . .

- እንካ ይህ የወንድሜን የተሟላ መረጃ የያዘ ካርዱ ነው፡፡ የመድረሻ ሰዓትህን ጠቅሰህ ኢሜይል ብትልክለት ወይም ብትደውልለት አይሮፕላን ማረፊያ ይጠብቀሃል . . ወንድሜ እንግሊዝኛ ስለሚናገር ምንም የሚያሰጋህ ነገር አይኖርም፡፡
- እኔም ከአፍታ በፊት ለወንድሜ ደውዬ እኛ ቤት እንዲያስተናግድህ ነግሬዋለሁ፣ግና እንግሊዝኛ ስለማይናገር ለአስጎብኚነት አይጠቅምህም፡፡
- ሁለታችሁንም አመሰግናለሁ፤ዛሬ ማከናወን የሚገቡኝ አንዳንድ ሥራዎች ስላሉኝ እንዳይረፍድብኝ አሁን ለመሄድ እገደዳለሁ፡፡ የጉዞ ዝግጅቱን ለማጠናቀቅ ነገ ሙሉውን ቀን ሥራ ቦታ አሳልፋለሁ፡፡ በሉ ግብጽ ስደርስ እደውላለሁ፤በጣም አመሰግናለሁ፣ደህና ሁኑ፡፡
- ግብጽም እየጠበቀችህ ናት፣ደህና ሁን፡፡
- እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን፡፡

(2)

ለግብጽ ተልእኮው ዝርዝር የሥራ መመሪያ ተልኮለት እንደሆነ ለማየት ጆርጅ ኢሜይሉን ከፈተ፡፡ ሁለት መልክቶችን አገኘ፡፡ አንደኛው ከጃኖልካ ሲሆን ሁለተኛው የሥራ ዝርዝሩን የሚመለከት ነበር፡፡ መጀመሪ የጃኖልካን ደብዳቤ ከፈተ . .

‹‹ውድ ወዳጄ ጆርጅ

- በሊብያ ቆይታ ከጠበቅሁት በላይ እየረካሁ ነኝ . . እርግጥ ነው በዚህ ሰሞን ሊብያ ውስጥ የጸጥታ ችግር አለ፣የአየሩ ሁኔታም እንዲሁ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በደረቁ በረሃ ውስጥ የለመለመ እርጥብ መንፈሳዊ ጉብኝት ላይ እንደሆንኩ ነው የሚሰማኝ፡፡

ስለራሴ በየጊዜው የደረስኩበትን አሳውቀሃለሁ፤ የመታደልን መንገድ እስክናገኘው ድረስ አንተም የደረስክበትን አሳውቀኝ፡፡

- ማስታወሻ ፦ ወደ ግብጽ እንደምትጓዝ ብትነግረኝ ኖሮ ወደ ሊብያ ከመምጣት ወደ ግብጽ እጓዝ ነበር፡፡

ጃኖልካ››

‹‹ውድ ወዳጄ ጃኖልካ

ወደ ግብጽ እንደምጓዝ ባለመንገሬ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤አልጠበኩም ነበር፣የተረጋገጠውም ገና ዛሬ ነው፡፡ ስሄድ ሁሉንም ነገር አሳውቀሃለሁ፡፡

ማስታወሻ፦ የለመለመ እርጥብ መንፈሳዊ ጉብኝት ስትል ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም፡፡ እውነቱን ለመናገር እኔ ግን በአሰልቺ የመንፈስ ድርቀት እንደተመታሁ ነው የሚሰማኝ፡፡

ጆርጅ››

በመቀጠል የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊውን ደብዳቤ ከፈተ፡፡ግብጽ ሲሄድ ማከናወን የሚገባውን ሥራዎች ዝርዝር በአትኩሮት አነበበ፡፡ የተሰጠው በጣም አስቸጋሪ ተልእኮ ሲሆን በካይሮ ውስጥ ለመካከለኛው ምስራቅ የቴክኒክና የንግድ ወኪል ማእከል የሚሆን ቢሮ መክፈት ነው፡፡ ካኽ ቶሎ ወደ ለንደን እንዲመለስ ስለማይፈልግ ተልእኮውን ሆን ብሎ አስቸጋሪ እንዲሆን ማድረግ ብቻ ሳይሆን የማይቻል አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ቀሪውን ቀንና ነገን ጨምሮ ካኽን ለማሳፈር የተሰጠውን የሥራ ተልእኮ በሚገባ ለመወጣት በጉዞው ዝግጅት ራሱን ለመጥመድ ወሰነ፡፡

ጆርጅ ግብጽ ውስጥ ከሚገኙ የቴክኒክ ሰራተኞች አስቀጣሪ ኩባንያዎች ጋር መላላክ ጀመረ፡፡ ከሁለት ቀናት በኋላ እንደሚመጣም፣አሳወቃቸው፡፡

www.path-2-happiness.com

የሚቀጠሩ ሥራ ፈላጊዎች በተቻለ መጠን ለኢንተርቪው ዝግጁ ሆነው እንዲጠብቁት እንደሚፈልግም ገለጸላቸው:: ቀሪዎቹን ቀናት ከባስም ወንድም ከጀማል ጋር በመመካከር ቦታ ለመፈለግ በማሰብ ለአንድ ሌሊት ብቻ የሚርፍበትን ትልቅ ሆቴል በኢንተርኔት እንዲያዝለት አደረገ:: ጉዞውን ለማሳካት የሚያግዙና የኮንትራት ውሎችን በተገቢው መንገድ ለማዘጋጀት የሚረዱ መረጃዎችን ከኢንተርኔት ላይ መፈለግ ጀመረ::

በሥራውና በተልእኮው ዝርዝር ጉዳዮች ተጠምዶ እያለ ካትሪና መጣች:: ከኻክ ጋር ከፍተኛ ፍጥጫ ውስጥ መሆኑንና በቀላሉ እንደማይለቀው ስለሚያውቅ ለሚጠብቀው ኃላፊነት በሚገባ መዘጋጀት የግድ ነው . .

- በጣም አስቸጋሪ ቀን ነበር፣ምን አዲስ ነገር አለ? የምስራች በለን::
- ተነገወዲያ ወደ ግብጽ እጓዛለሁ::
- ተነገወዲያ፣የምን ጥድፊያ ነው?!
- ረዥምና በጣም አስቸጋሪ ተልእኮ ይገጥ ነው የምሄደው፤ምናልባት ግብጽን በመምረጤ ተሳስቼ ይሆናል፣ወይም ካኽ በዚህ ሊበቀለኝና ስሜን ሥራ አመራር ቦርዱ ዘንድ ለማጠልሸት ፈልጎ ይሆናል::
- እርሱ ፈለገም አልፈለገ ተልእኮህን በሚገባ እንደምታሳካው እርግጠኛ ነኝ፣ጌታ ካንተ ጋር ነው::
- ካትሪና እወድሻለሁ፤ይህ ጉዞ ከኛው አህጉር ወጭ በሆነ የማላውቀው አገር ውስጥ ለቋንቋው፣ለሃይማኖቱ፣ለወጉ፣ ለልማዱና ለሥርዓቱም እንግዳ ሆኜ ከአንድ ወር በላይ እንዳይወስድብኝ እሰጋለሁ::
- ሊሆን ይችላል፤ይሁን እንጂ በዚህ ጉዞህ ተደሳች እንደምትሆን ከውስጤ ይሰማኛል::
- የኔም ምኞት ይህ ነው፤ኣደም አገሩ ውብና አስደሳች መሆኑን እያረጋገጠልኝ ነው፤ኣደም አገሩን በጣም የሚወድ ይመስላል::
- ሁሉም ሰው አገሩን ይወዳል!
- ልክ ነሽ፣ይበልጥ የሚገርመው ግን ከግብጽ ይበልጥ መካን የሚወድ መሆኑ ነው:: ምክንያቱ ደግሞ የነርሱ ነብይ ከአገሮች ሁሉ መካን የሚወድ በመሆኑ ነው! እንዲህ ያለው ምን ዓይነት ፍቅርና ምን ዓይነት ታዛዥነት ነው?! መነኮሳት ለኢየሱስ ያላቸውን ፍቅር አያስታውስሽም?
- ፈጽሞ፤ከዚያ የሚለይ ቢሆንም እንኳ ለኢየሱስ ያለንን ፍቅር ነው የሚያስታውሰኝ::
- በምንድነው የሚለየው?
- እኛ ኢየሱስን የምንመለከተው በአምላክነት ደረጃ ነው:: እነሱ ግን መልክተኛ ነብይ ብቻ አድርገው ነው የሚያዩት:: እኛ ለኢየሱስ ያለን ፍቅር እኛን ለማዳን ብሎ ራሱን ሰዋ በሚለው እምነት ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን፣የነርሱ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ መልካሙን ሁሉ ያስተማራቸው በመሆኑ ዙሪያ የሚሽከረከር ነው::
- የቱን መልካም ነገር ነው?
- እስላምን ነው፣ሁሉም መልካም ነገር የተካተተበት ነው ብለው ያምናሉ::
- ሁሉም መልካም ነገር!
- እንደዚያ ነው የሚያምኑት:: ለሁሉም የሕይወት ፈርጆች እስላማዊ ትንተና ያቀርባሉ:: ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተላለፉ ይናገራሉ::
- ‹‹ብለው ያምናሉ . . ይናገራሉ›› ስትል ማንን ማለትህ ነው?
- ሙስሊሞችን ማለቴ ነው::
- ቁርኣንን በሚመለከት በላክሽው የመጨረሻ ኢሜይል ‹‹ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ ይመስላል›› ብለሻል:: አባባልሽ በሁሉም መመዘኛ ለኔ ያልጠበኩት ዱብ እዳ ነበር::
- ያልተጠበቀው ዱብ እዳ ግን ቁርኣን በትክክል ከእግዚአብሔር የተላለፈ ስለመሆኑ እንዳጠና ያቀረብከው ጥያቄ ነው:: ይህ ዐረቦች የሚያነቡት መጽሐፍ ያለ ምንም መዛባትና መለዋወጥ በሙሐመድ አማካይነት የደረሳቸው ስለመሆኑ ምንም ጥርጠር የለም:: ጥያቄው ግን ሙሐመድ እውነተኛ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው::
- ከደብዳቤሽ እንደምረዳው እውነተኛ ነው የሚል እምነት እንዳለሽ ነው፣ለዚህ ነው ‹‹ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈ ይመስላል›› ያልሽው::
- የለም እንደሱ ማለቴ ሳይሆን እንደ ብሉይና አዲስ ኪዳን እርስ በርሳቸው የሚጋጩና የሚጣረሱ የተለያዩ ቅጂዎች የሉትም ማለት ነው የፈለኩት::
- ውይይቱ አስደሳች ቢሆንም ከመጓዜ በፊት ማጠናቀቅ የሚኖርብኝ ብዙ የዝግጅት ሥራዎች ስላሉኝ ለማቋረጥ እገደዳለሁ:: ለመሆኑ ልጆቹ የት ናቸው?
- በትምህርት ቤታቸው የሽርሽር ጉዞ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ሄደዋል፤ትናንት ነግረውህ አልነበረም፣ረሳህ?! ለማንኛውም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይመጣሉ፤በጣም ቢዘገይም ምሳውም ዝግጁ ይሆናል::
- ኦ ረስቼው፣በጣም ርቦኛል የኔ ፍቅር፣በጣም አመሰግናለሁ፤ምሳው እስኪቀርብ ድረስ ፍቀጅልኝና ሥራዬን ላጠናቅቅ::

www.path-2-happiness.com

(3)

ጆርጅ ካትሪናን እና ልጆቹን ተሰናብቶ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ አመራ . . አመሻሹ ላይ በአስራ ሁለት ሰዓት ካይሮ ደረሰ:: አስፈላጊውን ሂደት ጨርሶ ሻንጣውን ተረከበ:: ወደ እንግዳ መቀበያ ሳሎኑ ሲደርስ ‹‹ጆርጅ ኒሶን›› የሚል ስሙ፣ ጻሐፊው እንግሊዝኛን በደንብ የማውቅ መሆኑን በሚያሳብቁ ትላልቅ ፊደላት የተጻፈበት ሰሌዳ የያዘ አንድ ሰው አገኘ:: ወደርሱ አመራና ምልክት በማሳየት ፈገግ አለ:: ሰውየውም ጆርጅን እንኳን ደህና መጣህ ብሎ ተቀበለው . .

- እንኳን ወደ ግብጽ በደህና መጣህ:: እኔ የባስም ወንድም ጀማል ነኝ:: ይህ የአደም ወንድም ሙሐመድ ነው፣እንግሊዝኛ በደንብ ስለማይናገር ይቅርታ፣ግን አንተን ለመቀበል ጓግቶ ነው የተገኘው::
- ሁለታችሁንም አመሰግናለሁ . . ክፍል ስለያዝኩ ወደ አይሮፕላን ማረፊያው ሆቴል እንሂድ::
- እንዳልከው ግን ካይሮ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ያለባት በመሆኑ ሆቴሉ ከከተማው የራቀ ከመሆኑም በላይ በጣም ውድ ነው::
- ለአንድ ቀን ብቻ እንዲያዝልኝ ስላደረግሁ ነገ ብንለውጠው ችግር የለውም:: ለመሀል ከተማ ቅርበት ወዳለውና ከተማው ውስጥ ካሉት ትላልቅ ኩባንያዎች ያልራቀ ንጹህ ሆቴል እፈልጋለሁ::
- ብዙ ሆቴሎች ስላሉ ነገ አንተ ራስህ ሚመችህን ትመርጣለህ::
- እኔ ብዙ ሥራ ስላለብኝ ራስህ ነገ መርጠህ ያዝልኝ፣ደስ ካለኝ እቀጥልበታለሁ ካልሆነም እንቀይራለን::
- እሺ እንደ ፈለግህ . . ባስም እጅግ በጣም አጥብቆ ነው አደራ ያለኝ፣እናም ሙሉ ጊዜ ልታዘዝህ ዝግጁ ነኝ::
- ባስም ለኔ የሚያደርገው እንክብካቤ የሚገርም ነው!
- በብዙ ምክንያት ነው ፡ አንተ እንግዳ ነህ፣ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] እንግዳ እንድናስተናግድ አዘውናል:: አንተ እስላምን ለማወቅ የምትፈልግ ሰው ነህና እስላምን ልናሳውቅህ ግዴታ አለብን:: አንተ የወንድሜ ወዳጅ ነህ፤አላህ ደግሞ ውለታ እንድንመልስና በቃላችን እንድንገኝ አዞናል::
- አንደኛ ፡ አንድ ነገር በተናገርኩ ቁጥር . . ነብዩ . . ለምን ትሉኛላችሁ? ሁለተኛ እስላምን ለማወቅ እያጠና ነው ያለህ ማነው?
- አንደኛ ፡ ተወዳጁ ነብይ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ]

ዱካቸውን የምንከተል ታላቅ ምሳሌያችን ናቸው:: ሁለተኛ በደስተኝነት መንገድ ፍለጋ ላይ መሆንህን የነገረኝ ወንድሜ ባስም ነው::

- ደስተኝነትን ፍለጋ እንጂ እስላምን ፍለጋ አይደለማ !
- እስላም በሌለበት ደስተኝነት ስለማይኖር በሁለቱ መካከል ምንም ልዩነት የለም:: ይህ ባይሆን ኖሮማ እናንተ ምዕራባውያን ከማንም በላይ ደስተኞች በሆናችሁ ነበር:: ስዊድንን በመሰለ አገር 80% ያህሉ ሕዝብ ኤቲስት ወይም ሃይማኖት የለሽ መሆኑ ምስጢር አይደለም:: አገሪቱ ከዓለም ዋነኞቹ ባለ ጸጋ አገሮች አንዷ ብትሆንም በዓለም ላይ ራስን መግደል በከፍተኛ ደረጃ ከሚፈጽምባቸው አገሮች ዋነኛዋ ነች:: ራንስን ማጥፋት የደስተኝነት ማጣትና የተስፋ ቢስነት ዋነኛ መገለጫ አይደለም ወይ? !
- ሙስሊሞችም ራሳቸውን ያጠፉ የለም?
- አዝናለሁ ልክ ነህ ! ግና በከፍተኛ ልዩነት ቁጥራቸው ከሁሉም አነስተኛ ነው:: ሃይማኖት ራስን ከማጥፋት ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከቱና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተጠናቀሩ ሰነዶች ላይ በመመርኮዝ ዶክተር ጆስ ማንዌልና ተመራማሪ አሌሳንድራ ፊሊሽማን ባካሄዱት አጠቃላይ የሆነ ሳይንሳዊ ጥናት መሰረት፣ራስን የማጥፋት በከፍተኛ ቁጥር የሚፈጸመው በኤቲስቶች ዘንድ መሆኑን የደረሱበት ሲሆን፣ራሳቸውን ከሚገድሉ ሰዎች መካከል 25% ያህሉ ኤቲስቶች፣ከነሱ ቀጥሎ ቡድሂስቶች፣ከዚያ ክርስቲያኖችና ህንዱዎች ሲከተሉ ሙስሊሞች ከ1% ባነሰ ቁጥር መጨረሻ ላይ ይመጣሉ:: ይህም ብቻ ሳይሆን ‹‹የእስላም ሃይማኖት ራስን መግደል አጥብቆ የሚከለክል በመሆኑ በሙስሊም አገሮች ውስጥ ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች መቶኛ ከሌሎች አገራት በተቃራኒ ወደ ዜሮ የቀረበ ነው›› ብለዋል ሁለቱ ተመራማሪዎች::
- እስላም ራስን መግደል እርም አድርጎ ይከለክላል?
- በትክክል፣ይህ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ጎጂ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይከለክላል:: በጣም የሚገርመው ነብዩ (የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) በአኃዛዊ መረጃዎች መሰረት ራስን ማጥፋት ከሚፈጽምባቸው ነገሮች 90% ውን ቃል በቃል የተናገሩ መሆኑ ነው፤እንዲህ በማለት ፡ ‹‹ራሱን በብረት የገደለ ሰው፣ብረቱ በእጁ ሆኖ ሆዱን እየወጋና እየተሰቃየ ለዘላለም በገሀነም እሳት ውስጥ ዘውታሪ ሆኖ ይኖራል፤መርዝ ጠጥቶ ራሱን የገደለ ሰው መርዙን ፉት እያለ በገሀነም እሳት ውስጥ ዘውታሪ ሆኖ ይኖራል፤ከገደል አፋፍ ራሱን ወርውሮ የሞተ ሰው በገሀነም እሳት ውስጥ ራሱን ወደ ገደል እንደወረወረ ዘውታሪ ሆኖ ይኖራል::››

www.path-2-happiness.com

- ሙያህ ተጽእኖ ያሳደረብህ ትመስላለህ! ለዚህ ነው አኃዞችን በጣም የምትወደው!
- ለአስተያየትህ አመሰግናለሁ። በእርግጥ ወንድሜ እንደ ነገረህ ያጠናሁት ማቴማቲክስ ነው። ማቴማቲክስ ለሎጂካዊ አስተሳሰብ አጋዥ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ሳይንሳዊ ስልትን የተማርኩት ግን መጀመሪያ ከሃይማኖቴ ነው።
- ሁሉም ነገር ከነብዩና ከሃይማኖታችሁ ነው! ታበዙታላችሁ!
- ሊሆን ይችላል፤ይሁንና ሳይንሳዊው ስልት ያበዛሁት ምኑ ላይ መሆኑን ለይተህ ማስቀመጥን እንጂ በቀጥታ እኔን መውቀስ የማይጠይቅ መስሎ አይታህም?
- ተረትቻለሁ! ሃይማኖታችሁ ሳይንሳዊ ስልትን እንዴት ነው የሚያበረታታው?
- ከሳይንሳዊ ስልትና አቀራረብ ጋር ትስስር ያላቸው አንዳንድ የእስላም ጥሬ እውነታዎችን እንመልከት። ለምሳሌ ያህል እስላም ከጭፍን ተከታይነት ያስጠነቅቃል። ኃያሉ አላህ ስለ አጋሪዎች እንዲህ ይላል፦
- ‹‹ለነርሱም አላህ ያወረደውን ተከተሉ በተባሉ ጊዜ፣ አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን ይላሉ፣አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ እውነት) የማይመሩም ቢኾኑ (ይከተሉዋቸዋልን?)›› [አል በቀራ፡170]
- ያለ ሳይንሳዊ ስልት ግምትን መከተለን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፦ ‹‹ . . ጥርጣሬን እንጅ ሌላን አይከተሉም። እነርሱም የሚዋሹ እንጂ ሌላ አይደሉም።›› [አል አንዓም፡116]
- ሳይንስን፣ሎጂክን፣አእምሮንና ምርምርን ስለሚጻረረው የግል ዝንባሌ ተከታይነት እንዲህ ይላል፦ ‹‹ . . ብዙዎቹም ያለ ዕውቀት በዝንባሌዎቻቸው ያሳስታሉ፤›› [አል አንዓም፡119]
- ከፍትህ አስተካካይነት የሚያርቀውን ጥላቻ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፦ ‹‹ . . ሕዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ፤አስተካክሉ፤እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ የቀረበ ነው። አላህንም ፍሩ። አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።››]አል ማኢዳህ፡8[ስለ ሳይንሳዊ ተጨባጭነትም እንዲህ ይላል፦ ‹‹ከነዚያ ይሁዳውያን ከኾኑት ሰዎች ንግግሮችን ከስፍራዎቹ የሚያጣምሙ አልሉ፤ሰማንም አመጽንም . . ይላሉ፤›› [አልኒሳእ፡46] ወሰን ማለፍን፣ግፍንና ጥፋትን በመጻረር እንዲህ ይላል፦ ‹‹(የወቀሳ) መንገዱ በነዚያ ሰዎችን በሚበድሉት በምድርም

ውስጥ ያለ ሕግ ወሰን በሚያልፉት ላይ ብቻ ነው፤ . . ›› [አል ሹራ፡ 42] ለእውቀት መታመንን እና ፍትሐዊነትን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፦ ‹‹ . . በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ በትክክል እንድትፈርዱ (ያዛችኋል)፤›› [አልኒሳእ፡58] ፍትሕ ማስፈንን በሐቅ መመስከርንና አለማዳላትን በሚመለከትም እንዲህ ይላል፦ ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በትክክል (ፍትሕ) ቀዋሚዎች፣ በነፍሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢኾንም እንኳ ለአላህ መስካሪዎች ኹኑ።›› [አል ኒሳእ፡135] ማስረጃ የመጠየቅን አስፈላጊነት በሚመለከትም እንዲህ ይላል፦ ‹‹ . . እውነተኞች እንደ ኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው።›› [አል ነምል፡ 64]
- ስለ . .
- አሳማኝ ነው . . ይበቃኛል። አንተም እንደ ወንድምህ የሃይማኖት መሪ ነህ?
- እኔም ሆንኩ ወንድሜ እናንተ ዘንድ ባለው ዓይነት ቤተ ክህነታዊ ትርጉሙ የሃይማኖት መሪዎች አይደለንም። የወንድሜ የትምህርት መስክ እስላማዊ ጥናትና ምርምር ሲሆን የኔ ደግሞ ማቴማቲክስ ነው . . በነገራችን ላይ ከኣደም ወንድም ከሙሐመድ የእራት ግብዣ ተጠርተሃል . . የግብጽን የባህል ምግብ ወይም የፈረንጆችን ፈጣን ምግብ ትፈልግ እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋል።
- ቀለል ያለ የግብጽ ምግብ ይሁን።
- ‹‹ኮሽሪ›› የምንለው የምግብ ዓይነት አለን፤ይስማማሃል?
- ኮሽሪ! አላውቀውም፣ለማንኛውም እንሞክረው።
- ኮሽሪ ከፓስታ ከሩዝ ከሽንኩርት ከትማቲምና ከሌሎች ነገሮች የሚሠራ ምግብ ነው፤ለማንኛውም በጣም ጣፋጭና በጣም ታዋቂ የሆነ ምግብ ነው። እንሻአላህ አስደሳች ሆኖ ታገኘዋለህ፣ይህ ልዩ የሆነ ምርጥ የኮሽሪ ቤት ነው።
- የጀማል ምርጫ ያላስደሰተው ሙሐመድ ‹‹ጀማል ከውጭ የመጣ እንግዳችንን ኮሽሪ እንጋባዛለን! ምን ማለትህ ነው? ይህማ ተገቢ መስተንግዶ አይደለም›› አለው።
- አይደለም ሙሐመድ ይህ የራሱ ፍላጎት ነው . . ጆርጅ ሰማህ! ሙሐመድ እንዴት በተራና ርካሽ ሬስቶራንት እንግዳችንን እንጋብዛለን?ትልቅ ሬስቶራንት መምረጥ አለብን ይላል፣ምን ትላለህ?
- በጣም አመሰግነዋለሁ፣ይህን የመረጥኩት እኔ ነኝ፣በጣም ያስደስተኛል

በለው::

- ይኸው ነግሬህ የለ!
- ከይቅርታ ጋር ፍላጎትህን እናከብራለን፤እንግዳን ማክበርና ማስተናገድ ልማዳችን ነው፤ባህላችንና ሃይማኖታችንም በዚህ ያዘናል በለው::
- እናንተ ዘንድ ሁሉም ነገር በእስላም ወይም በሙሐመድ ምክንያት ነው! እናንተ ሙስሊሞች ከኛ ከክርስቲያኖች ይበልጥ ሃይማኖተኞች ሳትሆኑ አትቀሩም::
- እንዴት ማለት? አልገባኝም::
- እኛ በሳምንት አንድ ቀን እሁድ ብቻ በመጸለይ እንወሰናለን፣እናንተ ግን በቀን ከአንድ ጊዜ በላይ ትጸልያላችሁ:: ለሃይማኖታችሁና ለነብያችሁም ልዩ አድናቆትና ግምት ትሰጣላችሁ:: እኛ ዘንድ ግን ነብያት እንኳ በተጨባጭ አክብሮት አይቸራቸውም:: እናንተ ሃይማኖትን የተሟላ የሕይወት መመሪያ አድርጋችሁ ስትወስዱ እኛ ግን መንፈሳዊ ትስስር ብቻ አድርገን እናያለን::
- በምትለው ነገር ሙስሊሞችን እያወደስክ ነው ወይስ እየነቀፍከ ነው?
- እህህ፣ገለጻ ብቻ ነው:: እናንተ የተቀደሱ ነገሮቻችሁ ሲነኩ ትገነፍላላችሁ፤ቁጣችሁም ገደብ የለውም:: አሜሪካኖች መጽሐፋቸውን ሲያዋርዱና ሲያቃጥሉ አፍጋኖች የሰሩትን መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው!
- ለራሱ የተቀደሱ እሴቶች ግድ የሌለውና ነብዮቹን የማያከብር ምንም መሆን አይችልም:: እንግሊዞች መላእክትን ታከብሩ የለ? አሜሪካኖች መስራች ፕሬዚዳንቶቻቸውን ያከብሩ የለ? ኮሙኒስቶች ማርክስና ሌኒንን ያከብሩ የለ? ናዚዎች ሂትለርን ያከብሩት የለ? ሌሎችም . . እኛም ነብያትን በሙሉ እናከብራቸዋለን፣ይልቁንም ከክርስቲያኖች እንኳ በበለጠ ነብዩ ዒሳን [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] እናከብራለን፤ከናንተ ይበልጥም እንወዳቸዋለን:: ግን የአላህ አገልጋይና መልክተኛው ናቸውና ከዚህ ደረጃቸው በላይ አናስቀምጣቸውም::
- አዎ፣ልክ ነህ ግን ታጋንናላችሁ!
- ማጋነንማ እናንተ እንደምታደርጉት ዓይነት ሙሐመድ አምላክ ናቸው ብንል ኖሮ ነበር!
- ታጋንናላችሁ ስል ሃይማኖትን ከሁሉም የሕይወት ፈርጆች ጋር በማስተሳሰር ረገድ ማለቴ ነው::
- በእግዚአብሔርና በሕይወት መካከል ያለውን ትስስር በተመለከተ፣በፈጣሪ አምላክና በአገልጋዩ መካከል ያለውን ግንኙነት ጊዜያዊ የጸሎት ግንኙነት

ብቻ ነው፣የተቀረው የሕይወት ዘርፍ እግዚአብሔርን አይመለከተውም የሚል ሰው፣ሕይወትን ሃይማኖትንም ሆነ እግዚአብሔርን የማይረዳ ሰው ነው የሚል እምነት አለኝ:: ይቅርታ አድርግልንና እንዲህ ያለው ሰው መታደልን አያገኝም፤ሁሌም በጭንቀትና በውጥረት ውስጥ ይኖራል፤ፍጻሜው ከፍ ሲል የተጠቀሰው ዓይነት የራስን ሕይወት በገዛ እጅ ማጥፋት ይሆናል:: ቋሚ ትስስርና ግንኙነት በመካከከላቸው ከሌለ ሕይወት ሃማኖትም ሆነ አምላክ ትርጉም አልባ ይሆናሉ::

ኮሽሪ ወደሚያቀርብ ሬስቶራንት ገቡ፣የጆርጅን ትኩረት የሳበች አንዲት ጠረጴዛ መርጠው ተቀመጡ:: ሬስቶራንቱ በተመጋቢዎች የተጨናነቀ ሲሆን አስተናጋጆቹ የደንበኞቻቸውን ፍላጎት ለማሟላት ደፋ ቀና ይላሉ . . ሦስት ኮሽሪ አዘው በደቂቃዎች ውስጥ አስተናጋጁ ይዞላቸው መጣ . .

- ወዳጄ በአላህ ስም ይጀምሩት፣ኮሽሪው ቀርቧል::
- አስተናጋጁ ምን እያለ ነው?
- መብላት ከመጀመሬ በፊት በአላህ ስም እንድጀምር እያስታወሰኝ ነው::
- ለምን?!
- ቅድም የጀመርነውን ሀሳብ ለመቀጠል አንድ ሙስሊም ሕይወቱ በሙሉ የአላህ ነው ብሎ ስለሚያስብ መመገብ ከመጀመሩ በፊት ‹‹ብስምላህ›› ይላል:: በአላህ ስም ታግዤ በረከትና ረድኤቱን ከርሱ ጠይቄ እጀምራለሁ ማለቱ ነው::
- ግሩም ነው!
- እስላም ማንኛውንም ነገር ትንሹንም ትልቁንም የሚመለከት ድንጋጌ አሰፍሯል:: አላህ እንዲህ ብሏል፦
- ‹‹ . . በመጽሐፉም ውስጥ ምንም ነገር አልተውንም፤ . . ›› [አል ነምል፡ 38]
- ማንኛውንም ነገር!
- እህህ፣በነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ዘመን ስለሆነው ነገር የተላለፈውን ዘገባ አስታወስከኝ:: አንድ ሙስሊም ያልሆነ ሰው ወደ ነብዩ ባልደረቦች መጥቶ ‹‹ነብያችሁ ስለ ዓይነ ምድር እንኳ ሳይቀር ሁሉንም ነገር አስተምሯችኋላ!›› ሲል አሾፈባቸው:: ባልደረቦቹ ‹‹አዎ፣ከሽንት ወይም ከዓይነ ምድር በኋላ ቦታውን ለማጽዳት በቀኝ እጃችን እንዳንጠቀም ከልክለውናል፤በፋንድያ ወይም በአጥንት መጸዳዳትንም ከልክለዋል፤አንዳችሁ ከሦስት ባላነሱ ድንጋዮች አይጽዳዳ ብለዋልም::›› አሉት::

www.path-2-happiness.com

- የነብያችሁ ባልደረባ ያለው ነገር ትክክለኛ ነው ወይስ ሙስሊም ያልሆነውን ሰውየ ለመከራከር ብቻ እንዳው የተናገረው ነው?! እውን እስላም ውስጥ ዝርዝር የስነ ምግባር ስርዓቶች አሉ?
- አዎ ትክክለኛ ነገር ነው:: እርሱ የተመሰገነ ይሁንና አላህ ሃይማኖትን ምሉእ አድርጎታል:: አላህ እንዲህ ብሏል፦ ‹‹ . . ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ:: ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ:: ለእናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ . . ››]አል ማኢዳህ:3[ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] የተላኩትም መልካም ስነ ምግባራትን ምሉእ ለማድረግ ነው::
- የተሟሉ መልካም ስነ ምግባራት ባለቤቶች እናንተ ብቻ እንደ ሆናችሁ አድርጋችሁ የምታምኑት ለምንድነው?
- ልብ አላልክም ይሆናል እንጂ አሁን ጠቅሼልህ ነበር፤ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ፦ ‹‹የተላክሁት መልካም ስነ ምግባራትን የተሟሉ ለማድረግ ነው›› ብለዋል:: ማሟላት ማለት ቀደም ሲል በህዝቦች ዘንድ የነበሩትንና ሙሉ ያልነበሩትን መልካም ስነ ምግባራት ምሉእ ማድረግ ማለት ነው:: ይህም ከእስላም ልዩና ድንቅ ገጽታዎች አንዱ ነው::
- ምን ማለትህ ነው?
- እስላም መልካም ስነ ምግባራትን፣ሃይማኖቶችንና ሕግጋትን የማሟላት ትልእኮ ይዞ ነው የመጣው::የኣደምን የሙሳና የዒሳን [በሁሉም ላይ የአላህ ሰላም ይወረድ] መልእክት የሚያሟላ የማጠቃለያው የአላህ መልእክት ነው:: መልካም ጸባይና ውብ ስነ ምግባር እስላም ውስጥ ተራ ነገር ሳይሆን የሃይማኖታችን አቢይ አካል ነው::
- ኮሽሪም የሃይማኖታችሁ አብይ አካል ይሆን?
- እህህ፣ለእስላም ሳይሆን ለግብጽ አብይ ነገር ነው፤ለድሆችና ለሀብታሞችም የጋራ ምግብ ነው::
- ኦ ኮሽሪ እውነትም ጣፋጭ ምግብ ነው::
- መልካም እራት፣እንግሊዝኛ አጣርቶ ስለማይናገር በዝምታ የተዋጠውን ጋባዣችን ሙሐመድን እናመሰግናለን::
- ሙሐመድን በሚገባ አመስግንልኝ:: እስከ ዛሬ ከተመገብኳቸው ምርጥ ምግቦች አንዱ መሆኑንም ንገርልኝ::
- መህበሊያ በወተት ይቀራናል፣አዘዣለሁ::
- ሙሐመድ መህበሊያ በወተት ይቀራናል ይለሃል:: መህበሊያ ከግብጽ

ባህላዊ የጣፋጭ ዓይነቶች አንዱ ነው::

በልተው ከጨረሱ በኋላ ለጆርጅ ወደ ተያዘለት የአይሮፕላን ማረፊያ ሆቴል አመሩ:: ጆርጅ የሆቴሉን አስፈላጊ ፎርማሊቲ አጠናቆ ከገባ በኋላ ጀማል ነገ ጧት ተመልሶ እንደሚመጣ ነግሮት ተሰናብቶ ሄደ . .

ጆርጅ ወደ ክፍሉ ገብቶ እቃዎቹን ቦታ ቦታ ካስያዘ በኋላ ፈጣን ሻወር ወሰደ . . ከዚያም ኢሜይሉን ከፈተና ከወዳጆቹ የተላኩለትን ምላሾች አነበበ . . ጠቅለል አድርጎ ካዘጋጀ በኋላ ለሁሉም መልሶ ላከላቸው . .

‹‹የላካችሁልኝ መልሶች ለኔ አስደናቂና ጠቃሚ ነበሩ፤እነሱም የሚከተሉት ናቸው፦

ሐቢብ ፦ ብዙዎቹ የእስላም አቀራረቦች ሳይንሳዊ ቢሆኑም እስላምን አልወደውም፤እናም የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን እንድትጎበኝ እመክረሃለሁ::

ሌቪ ፦ ስለ እስላም ስንናገር ስለ ጭካኔ፣ስለ አክራሪነት፣ስለ ኋላቀርነትና ስለ አጥፊነት መነጋገር የግድ ይላል::

ካትሪና ፦ ይህ ሃይማኖት እንዲህ ያለ መስህብነት እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ምስጢሩ አይገባኝም! ምናልባት ለኢየሱስ ያላቸውን ፍቅርና ለሴቶች ያላቸውን አክብሮት አስረግጦ መናገር ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም::

ኣደም ፦ ከሁሉም በላጬ ዋቢ ማጣቀሻ የአላህ መጽሐፍ ቁርኣን ነው:: ከቁርኣን ያልተማረና ያላጠናው ሰው ስለ እስላም ባይናገር ምኞቴ ነው::

ጃኖልካ ፦ እስላም ጥልቀት ያለው ገርነት፣ቅለት ያለው ጥልቀትም ነው:: የዚህ እምነት ማራኪነትና መስህብነቱ ለመናገር የሚቸግር ነው:: ሚዛናዊ የሆኑ አንዳንድ ምዕራባውያን ስለ እስላም የጻፏቸውን ነገሮች ማንበብ ተመራጭ ነው::

እኔ ጆርጅ የሚከተለውን ላክሁላችሁ ፦ እሰላም ውስጥ አስገራሚ የሆኑ ምስጢራት ማለትም ተውሒድ፣አጠቃላይነት፣እርጋታ፣መንፈሳዊነት፣ሳይንሳዊነት፣ሽብር፣ሴት፣ዋቢነት፣ ተአማኒነትና ታሪክ ይገኛሉ::

ከዚህ የሚቀጥለው መልእክት በነዚህ በዘረዘርኳቸው ጉዳይ ዙሪያ ያለውን ጭጋጋማ ሁኔታ የሚያጠራ እንዲሆን ሀሳብ አቀርባለሁ:: ማብራሪያ ያለው ሰው ሀሳቡን ያካፍለን::

ጆርጅ››

ደብዳቤውን ከላከ በኋላ . . ከሌቪ የተላከ መልእክት አገኘ::

‹‹ወዳጄ ጆርጅ

በሰላም በጤና ወደ ግብጽ እንድትደርስ እመኛለሁ፤ቀደም ሲል አይሁዳዊነትንና ክርስትናን በተመለከተ ካደረግሃቸው ጥናቶች በተቃራኒ

www.path-2-happiness.com

በከፍተኛ ኃይልና በጠንካራ ጉልበት ወደ እስላም እየተንደረደርክ መሆንህ ይሰማኛል . . እባክህን እነዚህን ሙስሊሞች ተጠንቀቃቸው፤አደጋ እንዳያደርሱብህ አሰጋለሁ።

ሌቪ››

መልስ ላከላት . .

‹‹ወዳጄ ሌቪ

ለእውነተኛ ስሜትሽ ምስጋናዬ የላቀ ነው፤አስፈላጊውን ጥንቃቄ አደርጋለሁ። ያለውን ሁኔታም በየጊዜው አሳውቅሻለሁ። ያልሽውን መስየሽ ሊሆን ይችላል፣ግን እርግጠኛ ሁኚ ሙሉ በሙሉ አሳማኝ ሆኖ ሳላገኘው ወደ የትኛውም ሃይማኖት ፈጽሞ አልንደረደርም፣ከናንተ ጋር እመካከራለሁ፤ስለ በጎ አስተያየትሽ አመሰግናለሁ።

ጆርጅ››

ከካኽ መልእክት ደረሰው . . ከፍቶ አየው . .

‹‹ወዳጄ ጆርጅ

ከኩባንያው መራቅህና ተስማምተህ ከመቀበልህ በፊት የማታውቀውን ተልእኮ በመቀበልህ ደስተኛ ነኝ፤እንዲሳካልህ ምኞቴ ነው። ሁሉንም ነገር አመቻችቼልሃለሁ፤በስኬት ባትወጣው ግን ኃላፊነቱን አንተው ትሸከማለህ። ስኬትህን እጠባበቃለሁ።

ካኽ››

ጆርጅ ጧት አንድ ሰዓት ላይ ለቁርስ ከክፍሉ ወጣ፤በተለያዩ ዓለም አቀፍና የግብጽ የቁርስ ዓይነቶች የተሞላውን የሆቴሉን ቡፌ ወዶታል፤የማያውቃቸውን አዳዲስ ምግቦች መቀማመስ ያዘ . .

‹‹የሚያስፈልግዎት ነገር ይኖራል?›› አስተናጋጁ በተሰባበረ እንግሊዝኛ ጠየቀው . .

- በጣም አመሰግናለሁ . .
- ጌታዬ ከየት ነው የመጡት?
- ከእንግሊዝ አገር።
- አንተሳ?
- ከግብጽ . . ከእስክድርያ ነኝ።
- ስለ እስክድርያ ልትነግረኝ ትችላለህ?
- እስክድርያ ከግብጽ ታላላቅ ከተሞች አንዷ ስትሆን በመቄዶኒያዊው ታላቁ እስክንድር ከልደት በፊት በ332 ዓመት የተቆረቆረች ጥንታዊት ከተማ ነች።

- ጆርጅ እስክድር በስሙ እንዲትጠራ ስለ ፈለጋት ስለዚች ታሪካዊት ከተማ ያነበባቸው ነገሮች ታወሱት። እስክድር የቆረቆራት የንግድና የሄሌኒዝም ሥልጣኔ ማእከል እንድትሆን በማሰብ ሲሆን በኋላ ላይ ብዙ ዘመናትና ሥልጣኔዎች ተፈራርቀውባታል። በውስጧም ከጥንታዊው ዓለም አስደናቂ ነገሮች አንዱ የሆነው የእስክንድርያ የብርሃን ማማንና የእስክንድርያን ቤተ መጽሐፍት የመሳሰሉ ታሪካዊ ቅርሶችን ይዛለች። ክርስትና ወደ ከተማይቱ የደረሰው በ45 ዓመተ ልደት በሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ አማካይነት ነበር። ለክርስቲያኖች አንደኛዋ የትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል ከመሆኗም በላይ የአዲሱ ፍላጦናዊነት ፍልስፍና ፈለግ መገኛ በመሆኗ በፍልስፍና ረገድም የራሷ የሆነ አሻራ ነበራት። በዓለም ላይ የክርስትናን ነገረ መለኮትና እሳቤ የቀረጸው የእስክንድርያ ስነ መለኮት ትምህርት ቤት እምብርትም ነበረች . . ከእስላም መምጣት በኋላ የነበራትን ሚና ማስታወስ ሞከረ፤በዘመነ እስላምም የዕውቀት መናኸሪያ ሆና በመዝለቋ፣ወደ አገራቸው ተመልሰው ከመሄዳቸው በፊት የምዕራብና የአንዱሉስ ሊቃውንት ዕውቀት የሚቀስሙባት ማእከል ሆና አገልግላች . .

አስተናጋጁ አቋረጠው ፦

- ጌታዬ እኔን ረስተው በሀሳብ የነጎዱ ይመስላል፣ይፍቀዱልኝ ልሂድ . .

ጆርጅ ብንን ብሎ ከነጎደበት ዓለም ተመለሰና ፦

- አይደለም፣ስለ እስክድርያ ጥንታዊ ታሪክ ሳሰላስል ነበር።
- እኔ መሰረታዊ ትምህርት እንኳ አላጠናቀኩም፣የምጥፈውና የማነበበውም በግድ ነው። ይሁን እንጂ ግብጽን አወዳለሁ በተለይም እስክድርያን። እስክድርያ ያለ ጥርጥር የታሪክ ከተማ ናት። ከዚህ በፊት ጎብኝቷት ያቃሉ?
- እንድጎበኛት አጓጓኸኝ፤አንተ ሙስሊም ነህ?
- የለም፣ክርስቲያን ነኝ . .
- በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ያለው ግንኙነት እንዴት ነው? እስላም ወደ ግብጽ የገባው እንዴት ነው?
- በሙስሊሞችና በዘመኑ ግብጽን ይገዙ በነበሩት ቤዛንታውያን መካከል ጦርነት ተደረገ። የግብጽ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጎን ሆነው ይዋጉ ነበር።
- የግብጽ ክርስቲያኖች?!
- ኮፕቲኮች የግብጽ የመጀመሪዎቹ ነዋሪዎች ናቸው። ሁሉም ክርስቲያኖች

www.path-2-happiness.com

ናቸው ማለት ግን አይደለም . . ሙስሊሞች በድል አድራጊነት ወደ እስክድርያ ሲገቡ ነዋሪው ሕዝብ የእምነት ነጻነት ተጎናጸፈ:: ለአይሁድ ማህበረሰብም ነጻነቱን ጠብቆለት በሰላም ኖሩ:: በአንድም ቤተክርስቲያን ላይ ጥቃት አልሰነዘሩም::

-ለሙስሊሞች ይህን ያህል አድናቆት ካለህ ለምን አልሰለምክም?

-እንዲህ ሆኘ ነው የተወለድኩት:: ሃይማኖቴን ያባቴንና የአያቶቼን ሃይማኖት ለምን እለውጣለሁ? እርስዎ ሃይማኖትዎን መለወጥ ይችላሉ?

-ምን የሚከለክል አለ? ልለውጥ እችል ይሆናል . . በነበረው መጽናቱ ለአሳማኝነቱ እስካልሆነ ድረስ አሳማኝ ሆኖ ወዳገኙት መለወጥ የበለጠ ተገቢነት አለው::

-እኔ እንኳ መለወጥን አልወድም፤የሙስሊሞችን አስቸጋሪ ግዴታዎችም አልወድም::

-የሙስሊሞች አስቸጋሪ ግዴታዎች ስትል?!

-በቀን አምስት ጊዜ መስገድ፣ዘካ መክፈል፣የረመዷን ወር መጾም፣ወደ መካ ለሐጅ መሄድ . . አትዋሽ . . አትስረቅ . . አትቆጣ . . ዝሙት አትፈጽም . . ወዘተ.

-እነሱ ግን በዚህ ይደሰታሉ:: የላቀ ሕይወትና መታደል ነው ብለው ያምናሉ::

-እነሱ ይደሰቱበት ይሆናል:: ለኔ ግን አስቸጋሪ ነው፤ይቅርታ ብዙ አወራሁ::

-የለም፣እኔም ተመግቤ ጨርሻለሁ፣ለሰጠኸኝ ጊዜ አመሰግናለሁ::

ጆርጅ ከዚህ ሆቴል ወደ ሌላ ለመዛወር ወደ ክፍሉ ሄዶ ሻንጣዎቹን አዘጋጀ፤ሻንጣዎቹ እንዲወርዱለት ጠይቆ ወረዱ::እርሱም ጀማልን ለመጠበቅ ክፍሉን ለቆ ወደ እንግዳ መቀበያው ሄደ:: የመልቀቂያ ሂደቱን እንደጨረሰ ጀማል ደረሰ . .

-ዝግጁና ለሥራው ጉጉ ትመስላለህ::

-ልክ ነህ . . ዛሬ ማጠናቀቅ ያለብኝ ብዙ ሥራዎች አሉብኝ::

-መጀመሪያ ሻንጣዎችህን ወደ ሆቴሉ እናደርስና ከዚያ ወደምትፈልገው ቦታ እወስደሃለሁ::

-አዲሱ ሆቴል የት አካባቢ ነው?

-አልመዓዲ በሚባል አካባቢ አባይ ወንዝ ዳርቻ የሚገኝ ሆቴል ነው::

-ለሥራዬ ቅርበት ይኖረው ይሆን?

-ካይሮ ትልቅ ከተማ ነች:: ሥራህ በትክክል የት እንደሆነ አላውቅም፤እንኻ አሏህ ምቹና ለሥራህም ቅርብ ይሆናል፤ካልተመቸህም መቀየር ይቻላል::

ወደ አዲሱ ሆቴል ደርሰው ክፍል የመያዙን ሂደት አጠናቀቁ . .

-ወደ ክፍልህ ሄደህ አረፍ ብለህ እስክትመጣ እጠብቃሃለሁ::

-እረፍት እንኳ አያስፈልገኝም፤ወደ ክፍሉ ደርሼ ብቻ እመለሳለሁ::

ጆርጅ በፈገግታና በንቁ መንፈስ በፍጥነት ተመልሶ መጣ . .

-መልካም ፈቃድህ ከሆነ ወደዚህ አድራሻ መሄድ እፈልጋለሁ . . ከኛ ጋር ሲጻጻፍ የነበረ የሠራተኛ ኤጀንሲ ኩባንያ ነው::

-ኩባንያው አልጂዛ ውስጥ ስለሆነ ከዚህ ብዙ ርቀት የለውም፤ከፒራሚዶቹም ቅርብ ርቀት ላይ ይገኛል::

-መልካም፣ፒራሚዶቹንም ለማየት ከፍተኛ ጉጉት አለኝ::

-ልክ ነህ፤ግብጽን ጎብኝተህ ፒራሚዶችን ሳታይ መቅረት ተገቢ አይሆንም::

-ፒራሚዶቹም በሃይማኖታችሁ ምክንያት የተገኙ ናቸው?

-ፒራሚዶቹ የተገነቡት በፈረዖኖቹ ዘመን ነው፤ ነብያችንና ነብዩ ዒሳም [የአላህ እዝነትና ሰላም በሁለቱም ላይ ይወረድ] ከመላካቸው ረዥም ዘመናት አስቀድሞ ነው:: አንዳንዶቹ ፈርዖኖች በአላህ ያምኑ የነበሩ ሲሆን ከፊሎቹ ደግሞ ከሃዲዎች ነበሩ:: ለነብዩ ሙሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ‹‹እኔ ታላቁ ጌታችሁ ነኝ›› ያለውንና ቤተ እስራኤላውያንን ያሰቃየውን ፈርዖ ታውቁት የለም?

-የሚገርመው ታሪኩን በብሉይ ኪዳንና በቁርኣንም ውስጥ ያነበብኩት መሆኑ ነው::

-ግሩም . . እውነቱን ንገረኝና ከሁለቱ መጽሐፎች ለሙሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] የበለጠ ክበሬታ የሚሰጠው የትኛው ነው?

-ስለ እውነት . . የአይሁድ ነብይ ከመሆኑም ጋር ቁርኣን ነው የበለጠ ክበሬታ የሚሰጠው፤ይሁንና . .

-ይቅርታ፣እውነቱን ንገረኝና ከአዲስ ኪዳንና ከቁርኣን ለነብዩ ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] የበለጠ ክበሬታ የሚሰጠው የትኛው ነው?

-በአንድ መልኩ ካየን ወንጌል ነው፣በሌላ መልኩ ካየን ግን ቁርኣን ነው::

-እንዴት?

-ቁርኣን በኢየሱስ አወላለድ ትረካው፣ስለ ተሟላ ባህሪያው፣ከጉድለት በጠራና ክብሩን በጠበቀ መልኩ ባማቅረብ ረገድ የበለጠ ክበሬታ ይሰጠዋል:: አዲስ ኪዳን ደግሞ ከፍ አድርጎት የአምላክነት ደረጃ በመስጠት ያከብረዋል::

-የሰውን ልጅ አምላክ አድርጎ ማቅረብ ክበሬታ ነው ብለህ ታምናለህ ወይስ ያልሆነውን አድርጎ በማቅረብ በርሱ ላይ ቅጥፈት መንዛት ነው ትላለህ?!

-ማለት የፈለከውን በሚገባ እረዳለሁ፤በአንዳንድ የወንጌል ቅጂዎች

www.path-2-happiness.com

የእግዚአብሔር አገልጋ እንጂ አምላክ አለመሆኑ ተጠቅሷል። ይህንና ሌላ ሌላም ማለት ትችላለህ። ተገቢ መብትህም ነው፤ግና ሀሳቤን የጠየከኝ በተወሰነ ነጥብ ላይ ነው።

-‹‹ኢየሱስ ሙስሊም ነበርን?›› በሚል ርእስ አሜሪካ በሚገኘው የሉተር ዩኒቨርሲቲ የሃይማኖቶችና የእምነቶች ክፍለ ትምህርት ፕሮፌሰር በሆኑት ሮበርት ሽዲንገር የቀረበውን ጥናት አንብበሃል ብዬ እገምታለሁ።

-አዎ . . ገረፍ ገርፍ አድርጌ አይቸዋለሁ፤በጣም የተጋነነ ይመስለኛል። እስላም ከርሱ በኋላ የመጣ እየሆነ ኢየሱስ እንዴት ሙስሊም ሊሆን ይችላል?!

-ያልለመዳችሁትን የሚናገር ሰው ሁሉ፣ ወይ ያጋንናል ወይ ከሃዲ ነው፤ወይ ደግሞ ሳይንሳዊ አቀራረብን ይቃረናል ትሉታላችሁ። ሰውየው ታዋቂ በሆነ ዝነኛ ዩኒቨርሲቲ የስነ መለኮት ዴፓርትመንት ሊቀ መንበር ነው፤ቃሉን አላጠፋም ዩኒቨርሲቲውም ደግፎታል። እናም የሰው ልጅ ሕሊናዊ ነጻነትና ምሁራዊ ጀግንነት ኖሮት አንዳንድ ውሳኔዎች ላይ መድረስ አያስፈልገውም ትላለህ?!

-ምናልባት . . ባልከው ላይ በከፊል እስማማለሁ።

-መልካም አሁን ደርሰናል። ካንተ ጋር እንድገባ ትፈልጋለህ ወይስ እዚህ ቆይቼህ መቼ መጥቼ እንደምወስድህ ታሳውቀኛለህ?

-እኔ እንጃ . . ለማንኛውም አብረን እንግባና የሚሆነውን አይቼ እወስናለሁ። ወደ ዓለም አቀፉ የሰራተኛ ኤጀንሲ ኩባንያ ገብተው ሥራ አስኪያጁን ለማግኘት ጠየቁ። ሥራ አስኪያጁ ዶ/ር ገጊዮርጊስ ወጣ ማለታቸውንና ከሁለት ሰዓት ያህል በኋላ እንደሚመለስ ጸሐፊው ነጋራቸው . . ከሁለት ሰዓት በኋላ ተመልሰው እንደሚመጡ ነግረውት ወጡ . .

-ሁለት ሰዓቶች አለን፣የምንገኘው ከፒራሚዶች በቅርብ ርቀት ላይ ነውና በሁለቱ ሰዓት ውስጥ ትጎበኛቸዋለህ ወይስ ሌላ ቀጠሮ አለህ?

-ወደ ፒራሚዶቹ እንሂድና ተመልሰን እንመጣለን።

-መልካም ነው፣በነገራችን ላይ የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ እንዳንተው ክርስቲያን ነው፤ግን ፕሮቴስታንት ሳይሆን ኦርቶዶክስ ነው።

-እንዴት አወቅህ? ትተዋወቃላችሁ?

-አንተዋወቅም። ጸሐፊው እንደ ነገረን ከስሙ ነው ያወቅኩት። እኛ ዘንድ ጊዮርጊስ የሚለውን ስም የሚጠቀሙት ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው። ኦርቶዶክስ ነው ያልኩህ እዚህ ያሉት ብዙኃኑ ክርስቲያኖች ኦርቶዶክሶች እንጂ ፕሮቴስታንት ባለመሆናቸው ነው . . እርስ በርሳችሁ አንዱ

ሌላኛውን በክህደትና በመናፍቅነት እንደምትወነጃጀሉም አውቃለሁ።

-እስላም ውስጥ በክህደትና በመናፍቅነት የሚወነጃጀሉ ቡድኖች የሉም?!

-ያሳዝናል ግን አሉ።

-እንዴት ያሉት ናቸው?

-የቁርኣንን ምሉእነት የሚክዱ፣የነብዩን [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ባልደረቦችና ንጹሃት ባለቤቶቻቸውን የሚወነጅሉና የሚዘልፉ . . በብዙ መሰረት የለሽ አፈተረታዊ ተግባሮች ላይ የተሰማሩ ተስፈንጣሪዎች ይገኛሉ።

-የትነው የሚገኙት?

-በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ አነሶች ሲሆኑ መሰረታቸው በኢራንና እራቅ ሲሆን በሌሎች አገሮችም ይገኛሉ።

-ሺዓ ማለትህ ነው!

-በትክክለኛ ስማቸው ‹‹ራፍዷ› ወይም ሙሉውን ቁርኣንና ሙሉውን የነብዩን [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] ሱና ስለማይቀበሉ ‹‹እምቢተኞች›› ናቸው። ሌሎች ራሳቸውን ከእስላም ጋር ለማያያዝ የሚሞክሩ እንደ በሃኢዝም፣ቃድያኒዝምና የመሳሰሉ ቡድኖችም አሉ።

-እንግዲያውስ እንደኛው አንዱ ሌላውን ከሃዲ አድርጎ የሚመለከት ተጻራሪ ቡድኖች ሆናችኋል ማለት ነዋ?!

-የለም፤፣እንደ እናንተ እንኳ አልሆንም። ብዙኃኑ ሙስሊሞች ቁርኣን በአመጣጡ፣በአስተላለፉ፣በአረዳዱና በቃላቱ በተሟላና በተረጋገጠ መንገድ ወደኛ የደረሰ መሆኑን ሙሉ በሙሉ ይቀበላሉ። እናንተ ዘንድ ግን ኦርቶዶክሱም፣ካቶሊኩም፣ፕሮቴስታንቱም ሆነ የተቀሩት ቡድኖች ፈጽሞ ያልተበረዘና ያልተዛባ ወንጌል አለን ማለት አይችሉም፤ይህንን በሚገባ ታውቃላችሁ ብዬ አስባለሁ።

-የምትለውን ልየነት አውቃለሁ፣ግን የሚመሳሰሉበት መንገድ ይታየኛል። ዋናው ነገር ግብጽ ውስጥ ሺዓዎች አሉ?

-ለተወሰኑ ዘመናት ግብጽን ገዝተው የነበሩ ቢሆንም፣ዛሬ ግን የሉም ማለት ይቻላል።

-ከዚያ በኋላ ፈጃችኋቸው?

-እኛ እንደ እናንተ አይደለንም። ስርወ መንግስታቸውና ዘመናቸው አለፈ፣አበቃ። ብዙኃኑ ሕዝብ ግን በትክክለኛው ሱና ላይ ተፈጥሯዊ ንጽህናውን እንደጠበቀ ኖረ። የተቀሩትም ወደ ሱና እና ወደ እስላም ተመለሱ።

www.path-2-happiness.com

- ‹‹እኛ እንደ እናንተ አይደለንም›› ስትለኝ ምን ማለትህ ነው?
- ማለት የፈለኩትን በተሳሳተ መንገድ እንደማትረዳው ተስፋ አለኝ። ለምሳሌ ያህል ነባሮቹ የአውስትራሊያ ሕዝቦች የት ናቸው?! የአሜሪካ ነባር ነዋሪ ቀይ ሕንዶችስ የት ገቡ?!
- የበለጠ ልታብራራው ትችላለህ?
- ሕዝቦቹ እንዴት እንደ ተበደሉና ከነአካቴው እንዴት እንደ ተፈጁ ታውቃለህ! ነባር ህዝቦች በመጤዎቹ ነጮች እጅ ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል። እስላም ግን ግፍን አርም አድርጎ ፍትህ ማስፈንን ግዴታ አድርጎ ደንግጓል . . ተመልከት! ፒራሚዶቹ ከሩቅ መታየት ጀመሩ።
- እንዴት ይገዝፋሉ!
- ግዝፈታቸውና የኪነ ህንጻ ውበታቸው ስትቀርባቸው የበለጠ ጎልቶ ይታያል። እዚህ እንወርድና በፈረስ ጋሪ እንሳፈራለን፤የማሳስብህ ነገር ቢኖር ኪስህንና እቃህን በሚገባ እንድትጠብቅ ነው።
- ምን ማለትህ ነው?!
- የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች በብዙዎቹ የዓለም አገራት ውስጥ የስርቆትና የዘረፋ ቦታዎች ናቸው። እናም የስርቆቱ ዘዴ የተለያየ ቢሆንም ይህ የኛ ብቻ የተለየ ችግር አይደለም ማለቴ ነው።
- እናንተ እንደምትሉት ሙስሊሞች አይሰርቁም ተብሎ መገመት የለበትም?
- ሙስሊም ሰው እንጅ መልኣክ አይደለም። እንደ ሌላው ሁሉ የራሱ የሆኑ ስህተቶች፣ድክመቶችና ጉድለቶች ይኖሩታል። ይሁን እንጂ ሃይማኖቱ ከዚህ ሁሉ ይከለክለዋል፤ሌላውን ግን ሃይማኖቱ እነዚህን ነገሮች እንዲፈጽም ሊያበረታታው ይችላል።
- እንዴት?
- አንዳንድ ሃይማኖቶች - ስረ መሰረታቸው ትክክለኛ የነበረ ቢሆንም እንኳ- በሌሎች ላይ ግፍ እንዲፈጸም፣እንዲገደሉና እንዲሰረቁ ያዛሉ። እስላም ግን ይህን ሁሉ ሐራም አድርጎ አጥብቆ ይከለክላል። ሰዎች ግን ከሃይማኖታቸው በራቁ መጠንና ከእስላማዊ ስነ ምግባርና ከመንፈሱ በሚኖራቸው ርቀት ደረጃ ሃይማኖቱ በከለከላቸውና እንደ ስርቆት፣ዝሙት፣መጠጥ፣መዋሸት፣ቃልን ማጠፍና ራስ ወዳድነት በመሳሰሉ እኩይ ተግባራትና ባህርያት ውስጥ ይዘፈቃሉ . . ደረስን በል ውረድ።
- ድንቅና አስደሳች ጉዞ ሳይሆን አይቀርም።

በፒራሚዶቹ ስፍራ ለመዘዋወር ሚቀመጡባቸውን ሁለት ፈረሶች ጀማል ተከራየ . . ፈረሶቹን የሚመሩ ሁለቱ ሰዎች እንግሊዝኛ በደንብ የማይናገሩ

በመሆናቸው ጉብኝቱን በሁለት ሰዓት ውስጥ መጨረስ ይችሉ ዘንድ እንዲፈጥኑ እንዲነግራቸው ጆርጅ ጀማልን ጠየቀ . . ጉብኝቱ ሲጠናቀቅ ለቀጠሮው ለመድረስ ወደ መኪናቸው አመሩ . .

- ጀማል ከልብ ነው የማመሰግነው። በእውነት አስደሳች ጉዞ ነበር። ወደ ቅድሙ ቢሮ ተመልሰን መሄድ እንችላለን?
- ይቻላል፤ከፈለክም ወደ ሆቴልህ እንዲመጣ ደውልህ ልትነግረው ትችላለህ፤አሁን ሰባት ሰዓት ነው።
- መልካም፣እደውልለታለሁ።

የእጅ ስልኩን ለማውጣት ጆርጅ እጁን ወደ ኪሱ ሲከት ኪሱ ውስጥ የነበረው ገንዘብ የለም! በደንብ ቢፈልግም አላገኘውም . .

- ተሰረቅሁ መሰለኝ!
- እንሻ አሏህ በጎው ነው የሚሆነው፤ምናልባት ወድቆብህ ሊሆን ይችላል።
- አይደለም፣ፈረሱን ይመራ የነበረው ሰውየ ከፈረሱ ላይ ስወርድ ኪሴ ገብቶ ወስዶት ይሆናል። በጎው ነገር የክሬዲት ካርዶች ያሉበት ቦርሳዬ ያለበትን ሌላኛው ኪስ አለመግባቱ ነው።
- አላህ ይመስገን። ነቃ በል ተጠንቀቅ ብየህ አልነበረም!
- ብዙ ገንዘብ አይደለም፤ዋናው ነገር ለሰራተኛ ኤጀንሲ ኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ለዶ/ር ጊዮርጊስ ልደውል።

ከኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ጋር ስምንት ሰዓት ገደማ ላይ ሆቴል ለመገናኘት ተስማሙና ጆርጅ ይህንኑ ለጀማል ነገረው። ወደ ሆቴሉ ሲደርሱ ጭውውታቸውን ለመቀጠል አብሮት ወደ ክፍሉ እንዲሄድ ጀማልን ጠየቀው . .

- ከጊዮርጊስ ጋር የሥራ ስብሰባ ላይ ስትሆኑ ልረብሻችሁ አልፈልግም።
- አጭር ስብሰባ ይሆናል ብዬ ነው የምጠብቀው። ነገ ለሚኖረን ረዥም ስብሰባ ዝግጅት ብቻ ነው የሚሆነው። ጉዳይ ከሌለህ በጣም አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ ላይ ካንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ።
- ጉዳይ የለብኝም፣መቀጠል ትችላለህ።

ወደ ክፍሉ አብረው ሄዱ፤ጆርጅ ከክፍሉ የመስተንግዶ ባልኮኒ ሁለት ሲኒ ሻይ አዘጋጅቶ ቁጭ ብለው ለደቂቃዎች እየተነጋገሩ ከቆዩ በኋላ የክፍሉ ስልክ አቃጨለ። የአቀባበል ሰራተኛው የሠራተኛ ኤጀንሲ ኩባንያው ሥራ አስኪያጅ እየጠበቀው መሆኑን ለጆርጅ ነገረው።

ጆርጅ በችኮላ አንዳንድ ወረቀቶችን ወሳሰደና ጀማልን አስፈቅዶት ዶ/ር ጊዮርጊስን ለመገናኘት ወደ እንግዳ መቀበያ አመራ። ሲጠብቀው የነበረው

www.path-2-happiness.com

እንግዳ መካከለኛ ቁመና ያለውና በሃምሳዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ጆርጅ አስቀድሞ ሰላምታ በማቅረብ እንኳን ደህና መጣህ አለው . .

- የሚመችህ ከሆነ ለአፍታ ያህል አብረን እንቀመጥና ነገ በሚኖረን ስብሰባ ቅድመ ዝግጅት ላይ እንነጋገራለን::
- በጣም ይመቸኛል::
- በኢሜይል እንደጠቀስኩልህ እዚህ ካይሮ ሆነው የሚሰሩ ብዙ የቴክኒክ ባለሞዎችን ለኩባንያችን መቅጠር እፈልጋለሁ:: የምፈልጋቸው ባለሞያዎች ግን የላቀ ብቃት ያላቸው ብቻ መሆን ይኖርባቸዋል::
- ብዙ አመልካቾችን ያዘጋጀሁልህ ስለሆነ ከፈለግህ ነገ ቃለ መጠይቅ ልታደርግላቸው ትችላለህ::
- በናንተ በኩል በአመራረጡ ላይ ምን ልታግዙኝ ትችላላችሁ?
- የምታገኛቸው ካመለከቱት በርካታ ሰዎች መካከል እኛ የመረጥንልህ እጩዎች ናቸው::
- በምን መመዘኛ ነው የተመረጡት?
- በሙያዊ መመዘኛ መሰረት ነዋ! ማለት የፈለከው አልገባኝም::
- አንዱ መመዘኛ እንደኛው ክርስቲያን መሆን አልነበረም?

ጊዮርጊስ ፊቱን ቅጭም አደረገ . .

- በመጀመሪያ እኔ ክርስቲያን መሆኔን እንዴት አወቅክ? ሁለተኛ የኩባንያው ባለቤት ሙስሊም ሲሆን እኔ የኩባንያው ሥራ አስኪጅ ብቻ ነኝ:: ሦስተኛ ተመልማዮቹ አስር ሲሆኑ አንዱ ብቻ ክርስቲያን ሲሆን የተቀሩት ሙስሊሞች ናቸው:: አራተኛ . .
- ይቅርታ ምንም ፈልጌ አይደለም፣እንዳው በመካከላችሁ ውጥረት ብጤ ሊኖር ይችላል ብዬ ስለጠበቅኩ ብቻ ነገሮችን ለማጣራት ፈልጌ ነው::
- በመካከላችን ያለው ግንኙነት በጣም ጥሩ ነው:: በምዕራቡ ዓለም እንደምትገምቱት ወይም እንዲሆን እንደምትሹት አይደለም:: ለአናሳው የክርስቲያን ማህበረሰብ ከእስላማዊው አስተዳደር ይበልጥ በቂ ጥበቃ ያደረገ አልነበረም፤በዚህ የተነሳም ከታሪክ አንጻር ሁሌም ከሙስሊሞቹ ጦር ጎን ተሰልፈው ጠላትን በጋራ ሲዋጉ መኖራቸውን እንረዳለን::
- መልካም፣በአመራረጡ ላይ ወገንተኝነት መመዘኛ ላለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ስለፈለኩ ብቻ ነው::
- እርግጠኛ ሁን . . በቀረቡት እጩዎች መካከል የክርስቲያኖች መቶኛ ከተጨባጩ አኃዝ የበለጠ ከመሆኑ ውጭ ምርጫው የተካሄደው በሙያዊ መመዘኛ ብቻ ነው::

- እንዴት?
- ከአስር አንድ ማለት ክርስቲያኖች ከጠቅላላው ሕዝብ ከሚወክሉት መቶኛ የበለጠ ነው ማለት ነው:: ለማንኛውም ነገ በዚህ ረገድ ተጨማሪ ነገር እነግርህ ይሆናል . . ደስ ይልህ ወይም ያስከፋህ እንደሆነ ግን አላውቅም::
- በጣም ጥሩ፣አንድ ወዳጄ ላይ ክፍሌ ሆኖ እየጠበቀኝ ስለሆነ ለመሄድ እገደዳለሁ . . በነገራችን ላይ ይህ ወዳጄ ግብጻዊ ሙስሊም ነው:: ቀጠሮችን ነገ ሦስት ሰዓት በኩባንያው ቢሮ ነው:: ከመካከላቸው መምረጥ እችል ዘንድ በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎችን ማግኘት ምኞቴ ነው::
- መልካም፣ተስማምተናል:: ነገ እንጠብቀሃለን፣ እንሻአላህ የሚያረካህ ነገር ታገኛለህ:: ግብጽ ብቃት ባለው የሰለጠነ የሰው ኃይል የበለጸገች አገር ናት::

ጆርጅ ወደ ክፍሉ ወጣ፣በመዘግየቱ ጀማልን ይቅርታ ጠየቀው . . ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ሄደው አብረው ምሳ ለመብላት ጥያቄ አቀረበለት . .

- ቀጥተኛ የሆነ ጥያቄ ላቀርብልህ እችላለሁ?
- ጠይቅ::
- ለግልጽነቱ ይቅርታ አድርግልኝ . . ከኔ ጋር በመሆንህ፣እኔን በመኪና በማመላለስህና ከኔ ጋር በመልፋትህ የምታገኘው ጥቅም ምንድነው?
- የማገኘው ጥቅም ብዙና ግልጽ ነው::
- ምንድነው?
- በሃይማኖታችን ውስጥ ሰዎችን ማገልገልና መጥቀም ከፍተኛ ቦታ አለው:: ወደ አላህ ከሚያቃርቡ ምርጥ የትሩፋት ተግባራትም አንዱ ነው::
- የምታገኘው ጥቅም በቃ ይኸው ብቻ ነው ማለት ነው?!
- አይደለም፣የወንድሜን ወዳጅ ማገዝ የመሳሰሉ ሌሎች ጥቅሞችም አሉ:: ከዚህ ሁሉ የላቀ ነገርም አለበት፣እሱም አንተን ወደ እስላም መጥራት (ደዕዋ) ነው::
- ይቅርታ፣የመጨረሻውን ጥቅም በተመለከተ የሚኖር አይመስለኝም:: ግና ቁሳዊ ጥቅምህ ምንድነው? ለዚህ ሥራህ ስንት እንዲከፈልህ ትፈልጋለህ?
- እመነኝ ይህን ፈጽሞ አላሰብኩትም:: የምትፈልገውን ያህል ገንዘብ ወስን:: ግን መክፈል የምትጀምረው እንግዳ ከመሆንህ አንጻር መብትህ ከሆኑት ከመጀመሪያዎቹ የሦስት ቀናት ቆይታህ በኋላ ነው::
- ሰዓቱ ገና ቢሆንም የዛሬ ውሎ አስደሰች ነው:: ይሁን እንጂ ወደ ክፍሌ ገብቼ አንዳንድ ሥራዎችን ማጠናቀቅና በጊዜ መተኛት ይኖርብኛል:: በጣም ነው የማመሰግነው . . ቀጠሮችን ነገ ሁለት ሰዓት ነው:: ከጊዮርጊስ

www.path-2-happiness.com

ጋር ያለን ቀጠሮ ሦስት ሰዓት በመሆኑ አብረን ወደ ኩባንያው እንሄዳለን::

- መልካም ነው፣እንሻአላህ ይመቸኛል::

ሂሳቡን ለመክፈል ጆርጅ እጁን ወደ ኪሱ ሲከት ገንዘብ የያዘ ቦርሳውን አልነበረም . .

- ቦርሳዬን ላይ ረስቼ ሳልመጣ አልቀረሁም:: ሄጄ ይዤ ልመለስ ጥቂት ደቂቃዎች ትጠብቀኛለህ::
- አሁን ለምን ፈለከው?
- አገልግሎት ለሰጠን አስተናጋጅ ጉርሻ ነገር ልሰጠው እፈልጋለሁ::
- አሁን አስራ አንድ ሰዓት ገደማ ነው:: ጊዜህን ከማባከንና ወጥተህ በመውረድ ከምትለፋ፣የግብጽ ፓውንድም ስለማይኖርህ ይህን መቶ ፓውንድ ያዝና እንሻአላህ ነገ ዘርዝረን ትመልስልኛለህ::
- ጀማል በጣም አመሰግናለሁ::

(4)

ጆርጅ ወደ ክፍሉ ሄዶ ሥራዎቹን ለማከናወን ኮምፒውተሩን ከፈተ:: ቦርሳው ትዝ ብሎት ቢፈላልግ አጣ:: ክፍሉን ሙሉ በሙሉ ቢበረብርም ምንም ነገር ማግኘት አልቻለም:: ጠፍቷል ብሎ ስለቆረጠ በጭንቀት ተወጠረ:: ቦርሳው የክሬዲት ካርዶቹና ያለውን ጥሬ ገንዘብ ሁሉ የያዘ በመሆኑ ብዙ ከተረበሸ በኋላ ለጀማል ደወለ . .

- ቦርሳዬ የትነው ያለው?
- ክፍሌ ውስጥ ትቻለሁ ብለህ የለ?
- እባክህን የበለጠ ግልጽ ሁን:: ቦርሳዬንና አንተንም ክፍሉ ውስጥ ትቼ ነበር የሄድኩት፣ስመለስ ግን አላገኘሁትም::
- ምን ማለትህ ነው?
- በሰጠሽኝ መቶ ፓውንድ ልትሸነግለኝ አትሞክር:: አሁን ቦርሳዬን መልስልኝ::
- ይቅርታ እኔ አልወሰድኩም::
- ቦርሳው ክፍሉ ውስጥ ነበር:: ክፍሉ ወስጥ አንተን ብቻ ትቼ ነው የወጣሁት:: ታድያ ማን ወሰደው?
- እደግማለሁ እኔ ፈጽሞ አልወሰድኩም::
- ከአላህ ምንዳ አገኛለሁ፤የወንድሜን ወዳጅ አግዛለሁ ነው የምትለኝ:: አሁን ነገሮች ሁሉ በግልጽ ታዩ፤ሃይማኖታችሁ የስርቆት ሃይማኖት ሳይሆን አይቀርም መስለኝ:: በአንድ ቀን ሁለቴ ልሰረቅ!

- በእስላም ላይ ድንበር እንዳታልፍ እጠይቀሃለሁ፣እኔ ፈጽሞ አልወሰድኩም::
- ታድያ ዬት ሄደ? በኖ ጠፋ?!
- በዚህ ሁኔታ ለምንድነው የምታናግረኝ?!
- ቦርሳው ነገ ጧት ከሦስት ሰዓት በፊት ካልመጣልኝ ለፖሊስ አመለክታለሁ:: ደሞም ሰዎችን ማገልገል ሃይማኖታዊ ትእዛዝ ነው ትለኛለህ! እናንተ ዘንድ ስርቆት የሃይማኖት አንዱ አካል ነው መሰለኝ:: ለማንኛውም ጭቅጭቅ ሳላበዛ ቀጠሯችን ቦርሳዬን ይዘህ ነገ ሁለት ሰዓት ነው:: ይህ የመጨረሻ ቃሌ ነው::

ጆርጅ የስልክ ጥሪውን አቋረጠ:: ንድድ እያለውና ግራ እየተጋባ ወደ አልጋው ተወረወረ . .

- ካኽ በኔ ላይ ድል ሊቀዳጅ ነው መሰለኝ! ወደዚህ አገር ምን አመጣኝ? እስላምን የስርቆት ሃይማኖትን ለማወቅ? በአንድ ቀን ሁለት ጊዜ ተሰርቄአለሁ . . ጀማል ተብየው መጣና እንድትሰልም እመኛለሁ ይበለኝ!! ምን የሚሉት ሹፈት ይሆን?!!

ጆርጅ በከፍተኛ ንዴትና ውጥረት ተይዞ ስለነበር ለአንድ ሰዓት ያህል በሀሳብ ዋዠቀ:: ውጥረቱና ብሽቀቱ ከአስፈላጊነታቸውም ጋር ቦርሳው ውስጥ ባሉት ካርዶችና ገንዘብ ምክንያት ሳይሆን ሌሎች በሃይማኖት ስም እንደ ሕጻን ልጅ እየሸነገሉኝ ነው የሚል ስሜት ስላደረበት መሆኑን በእርግጠኝነት ይረዳል:: የክሬዲት ካርዶቹን ለማሳገድ ደብዳቤ ለመላክ አሰበ፤ግና ነገ ጀማል ይመልስልኝና ይህ ቆሻሻ ጨዋታ ያበቃል ብሎ ተስፋ ስላደረገ ሀሳቡን ቀየረ . . የነገውን ቀጠሮ አስታውሶ ከራሱ ጋር አወራ . .

- የነገ ቀጠሮዬ ከሙስሊም ጋር ሳይሆን ከክርስቲያን ጋር መሆኑ መልካም ነገር ነው:: ለኔ የበለጠ ቅንነት እንዲኖረው ያደርገዋል . . ለጊዮርጊስ ደውሎ የሆነውን ነገር ልነግረው ወሰነና ደወለ::
- ሃሎ፣ቀጠሮው ተለወጠ እንዴ?
- የለም አልተለወጠም:: ካንተ ጋር ለመገናኘት በመጣሁበት ጊዜ ክፍሌ ውስጥ ትቼ የነበረው ሙስሊሙ ወዳጄ ስርቆት ፈጽሞብኝ ምን እንደማደርግ ላማክርህ ነው የደወልኩት::
- እርግጠኛ ነህ እርሱ ነው የሰረቀህ?
- እያዘንኩ አዎ፤ቦርሳዬንና እርሱን ክፍሌ ውስጥ ትቼ ስመለስ ቦርሳውን አላገኘሁም::

www.path-2-happiness.com

- ክፍሉ ውስጥ በደንብ መፈለግ ሊኖርብህ ይችላል፤አሊያም ሆቴሉ ውስጥ ወድቆብህ ይሆናል፡፡
- እርግጠኛ ነኝ፤በሃይማኖት ስም ሲሸነግለኝ ምነኛ እንደ ተጃጃልኩ አላውቅም፡፡ ነገ ጧት ካላመጣልኝ ለፖሊስ እንደማመለክት አስጠንቅቄዋለሁ፡፡
- እንዲመጣልህ ምኞቴ ነው፡፡ ከአነጋገርህ እንደተረዳሁ ግን ማስረጃ ስለማይኖርህ የፖሊሱ ነገር እንኳ ምንም አይጠቅምህም፡፡
- ልክ ነህ፤ምንም ማስረጃ የለም፡፡ ታድያ መፍትሔው ምንድነው?
- ከርሱ ጋር የነገ ቀጠሮህ ስንት ሰዓት ነው?
- ሁለት ሰዓት ነው፡፡
- መልካም፤እኔ ደውዬ እንድሞክር የስልክ ቁጥሩን ልትሰጠኝ ትችላለህ?
- አዎ ይኸውልህ ቁጥሩ . .
- አሁን እረፍት ውሰድ፡፡ መሆን የሚችለውን ነገር ነገ እንመካከራለን፡፡ ለማንኛውም ግን ወስዶ ከሆነ ያመጣዋል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

ጆርጅ የስልክ ጥሪውን ሲቋጭ የተወሰነ እርጋታ ተሰማው . . ኢሜይሉን ከፈተና የሚከተለውን መልእክት ከጃኖልካ አገኘ ፦

‹‹ወዳጄ ጆርጅ

እኔ ሊብያ ውስጥ እንደተደሰትኩ አንተም በግብጽ ቆይታህ ደስተኛ እንደምትሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እዚህ ሕዝቡ እንግዳ ተቀባይና ሰው ወዳድ ነው፡፡ እጅግ በጣም በስነ ምግባር የታነጸና በጣም ሃይማኖተኛ ነው፡፡ ምናልባት በምዕራባውያኑና በነዚህ ዐረቦች መካከል ያለው ዋነኛው የባህሪ ልዩነት ስነ ምግባርና ግብረ ገብነት የሃይማኖታቸው አንድ አካል እንጂ እኛ ዘንድ እንደተለመደው ከሌሎች ዋጋና አጸፋ ጥቅም ሚጠበቅበት ነገር አለመሆኑ ነው፡፡ እንዴት ይዞሃል? ስለ ጤንነትህና ስለ ሁሉም ነገር ካንተ መስማት እንሻለን፡፡

ጃኖልካ››

መልስ ጻፈለት ፦

‹‹ወዳጄ ጃኖልካ

በሊብያ መደሰትህ አስደስቶኛል፤እነዚህን ሙስሊሞች ግና አጥብቀህ እንድትጠነቀቃቸው ምኞቴ ነው፡፡ እኔን በተመለከተ እስካሁን በግብጽ ሙስሊሞች ሁለት ጊዜ ስርቆት ተፈጽሞብኛል፡፡ አንደኛው ጊዜ ወደ እስላም

እንድገባ ጥሪ ሲያደርግልኝ በነበረ ሰው ሲሆን በችግሬ ጊዜ ከጎኔ የቆመው እንደኔ ያለው አንድ ክርስቲያን ብቻ ነው፡፡ ሥራዬን አጠናቅቄ ወደ እንግሊዝ ለመመለስ እንዴት እንደ ጓጓሁ ልነግርህ አልችልም፡፡

ጆርጅ››

በመቀጠልም ከሙስሊሞች እንዲጠነቀቅ በማሳሰብ ለላከችለት ደብዳቤ ምላሽ ለሌቪ ጻፈ ፦

‹‹ወዳጄ ሌቪ

- ያሳዝናል ያስጠነቀቅሽኝ ነገር አልቀረም ደርሶብኛል፤ግብጽ ውስጥ ስርቆት ተፈጽሞብኛል፡፡ ቀደም ሲል እንደጠቀስሽው ሁሉ በፍጥነት ወደ እስላም ስንደረደር የነበርኩ ቢሆንም አሁን ግን ስነ ምግባር የጎደለው ሃይማኖት መሆኑን እየተረዳሁ ነኝ፡፡ ምናልባት ይሁዳዊነትና ክርስትና የተዛቡና የተከለሱ ሊሆኑና እስላም ግን ያልተዛባና ያልተከለሰ ሊሆን ይችላል፤ግና ስነምግባራዊነት ፍጹም የጎደለው ሃይማኖት ነው፡፡ ስለ ሌላው ጉዳይ በቅርቡ እጽፍልሻለሁ፡፡ አሁን የጻፍኩልሽ በማስጠንቀቂያሽ አለመጠቀሜን በማስታወሴ ነው፡፡

ጆርጅ››

ኢሜይሉ ላይ ቀደም ሲል ለላከላቸው ጥቄዎቹ የተላኩለት ምላሾችን ቢያገኝም፣አንዱንም የማንበብ አምሮት ስላልነበረው ኮምፒውተሩን ዘጋ . . ለመተኛት በመሞከር አልጋው ላይ ቢዘረገፍም እንቅልፍ አልመጣልህ አለው፡፡ ብድግ ብሎ ቲቪውን ከፈተና የእንግሊዝኛውን ቢቢሲ ቻናል ዜና ጥቂት ከተከታተለ በኋላ ቻናሎችን ሲቀያይር በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚተላለፍ እስላማዊ ቻናል አጋጠመው፡፡

ፕሮግራሙ እስላም ውስጥ ስላለው መልካምና ምስጉን ባህርያት የሚወያራና ሙሐመድ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይወረድ] የተላኩት መልካ ስነ ምግባርን የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ መሆኑን የሚናገር ነበር . . ለራሱ እንዲህ አለ ፦

- እነዚህ እስላማዊ ሕዝቦች በሰብእና መከፋፈልና በጣምራዊነት የተጠቁ ሳይሆኑ አይቀሩም . . ጣምራ መስፈርት የሚጠቀመው ይህ ሃይማኖት እንዴት ያስጠላል!

የንዴቱ ብዛት ፕሮግራሙን እስከ መጨረሻው መከታተል አላስቻለውም፡፡ እንደገና ለማንቀላፋት ሞከረ፡፡ ሲገለባበጥ ከቆየ በኋላ እንቅልፍ ወስዶት

www.path-2-happiness.com

ጭልጥ አለ . . ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ከእንቅልፉ ብንን ብሎ ተነሳና ወደ መጸዳጃ ቤት ሄደ። ሲወጣ ፊት መታጠቢው አጠገብ ዓይኑ በጠፋ ቦርሳው ላይ አረፈ! ቀትር ላይ ዶ/ር ጊዮርጊስን ለመገናኘት ከመሄዱ በፊት መጸዳጃውን መጠቀሙ ትዝ አለው። ተቻኩሎ ስለ ነበር ሰነዶቹን ብቻ ወስዶ የገንዘብ መያዣ ቦርሳውን እዚያ መርሳቱን ልብ አላለም ነበርና በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ ሊገባ ቻለ!

ስሜቱ ክፉኛ ተጎድቶ አልጋው ላይ ቁጭ አለ። ያዞረውና ያጥወለውለው ጀመር . . ለሆነው ነገር ጀማልን ምን ብሎ ይቅርታ ይጠይቅ? ምንም ማረጋገጫ ሳይኖረው በስርቆት የወነጀለው በመሆኑ በድሎታል . . ኣደም ግልፍተኛ እንዳይሆንና በችኮላ እንዳይወስን ብዙ ጊዜ አስጠንቅቆታል . . አሁን ምን ማድረግ ይችላል?

(5)

ጧት ሁለት ሰዓት ላይ ጀማል ወደ ሆቴሉ ደርሶ የእንግዳ መቀበያው ሰራተኛውን ለጆርጅ እንዲደውልና መምጣቱን እንዲነግረው ጠየቀ . .

- እንግሊዛዊው ጆርጅን ነው?
- አዎ።
- ዛሬ ንጋት ላይ ደሙ በከፍተኛ ደረጃ ወርዶ በአንቡላንስ ወደ ሆስፒታል ተወስዶ ነበር።
- ተመልሷል?
- አዎ፣ከሁለት ሰዓት ገደማ በፊት ተመልሷል። ይተኛ አይተኛ ግን አላውቅም።
- እባክህን ደውልለትና ሊጠይቅህ የመጣ ጀማል የሚባል ሰው መምጣት ይፈልጋል በለው።

ሰራተኛው ደውሎ ሲነግረው ይምጣ አለውና ጀማል ወደ ክፍሉ ሲደርስ ድካምና መንገላታት ከፊቱ በጉልህ የሚስተዋለው ጆርጅ በሩን ከፈተለት . .

- ጆርጅ ይቅርታ አድርግልኝ፤ፈጽሞ አንተን የማስከፋት ፍላጎት አልነበረኝም። ይህ የባለቤቴ የወርቅ ማስቀመጫ ቦርሳ ነው። ባንኮች ተከፍተው ሄጄ ገንዘብ እስካመጣልህ ድረስ በአደራ አንተ ዘንድ ይቀመጥ። ያንተን ቦርሳ ላመጣልህ አልቻልኩም፣ ስንት እንዳለበትም አላውቅም!
- ይህ ሁሉ ለፖሊስ እንዳላመለክት በመፍራት ነው?

- በተከሰተው ነገር በጣም አዝናለሁ። ፖሊስ እንኳ ማድረግ የሚችለው ምንም ነገር አይኖርም።
- ታድያ የባለቤትህን ወርቅ ለምን ታመጣለህ?
- አንተ እንግዳ ነህ፤መስተንግዶ የማግኘት መብት አለህ። በተጨማሪም መንገደኛ እንግዳ ሆነህ ችግር የደረሰብህ ሰው ስለሆንክ ልናግዝህ ግዴታ ነው። በተጨማሪም ስለ እስላም የተዛባ እይታ እንዳይኖርህ እፈልጋለሁ።
- አሁንም እኔ አልወሰድኩም በሚለው ላይ እንደጸናህ ነው ማለት ነው?
- ያለ ምንም ጥርጥር እኔ አልወሰድኩም። ይሁን እንጂ እንዳይደክምህ አሁን ይህን ማንሳት አልፈልግም።
- በኔ ቦታ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?
- እውነቱን ለመናገር አላውቅም። ይህ ቦርሳው ለኔ በሚኖረው አስፈላጊነት ደረጃና በሚኖረኝ ስነ ልቦናዊ መረጋጋት ላይ የሚሞረከዝ ይሆናል። ምናልባት የሂሳብ ባለ ሞያነቴ ሁሉንም ነገር ወደ አኃዞች ለውጬ እንድመለከት ያደርገኝ ይሆናል።
- አንተ በኔ ቦታ ብትሆንና እኔ በአንተ ቦታ ብሆን ከኔ ምን ትጠብቃለህ?
- ይቅርታ አድርግልኝ መልስ አልሰጥም።
- አንተ ያደረከውን ያደርጋል ብለህ ትጠብቀኛለህ?
- እውነቱን ለመናገር አልጠብቅም፤ላንተ ግን ይገባሃል።
- ያደረኩትን ካደረኩ በኋላ ቦርሳዬን ባገኘው ለዚህ ሰው ምን ትለዋለህ?
- አግኝተሃል?!
- እንዲሁ ቢሆን ማለቴ ነው፣ይሆናል ብለህ አስበውና መልስልኝ።
- የግድ ወዳጄን ይቅርታ እጠይቀዋለሁ። ነገሩ በጣም ከባድና አስቸጋሪ በመሆኑ ተዝለፍልፌ ልወድቅም እችላለሁ ብዬ አምናለሁ።
- ይቅርታ ጠይቀህ አልቀበልም። ሥራህን አልረሳውም ቢልህስ?
- አላህ ይቅር ባይና ይቅር ባዮችን የሚወድ በመሆኑ፣ለሰው ልጅ ይበልጥ ተገቢው ነገር ይቅር ባይነትና ሆደ ሰፊነት ቢሆንም፣እንደዚያ ቢል እንኳ እውነት አለው።
- እንግዲያውስ እኔም ይቅርታ እጠይቃሃለሁ። ቦርሳዬን አግኝቻለሁ . . በዚህ ምክንያት ነው የደም ግፊቴ ወርዶ ወደ ሆስፒታል የተወሰድኩት፣ምን እንደማደርግ አላውቅም። እንዳልከው አላህ ይቅር ባይነትን የሚወድ ነውና

www.path-2-happiness.com

ደጋግሜ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ::

ጀማል ሳይፈልግ የወረደ እንባውን አባበሰ . .

- ይቅር ብየሃለሁ:: ልነግርህ የምችለው ነገር ቢኖር ከትናንት ጀምሮ እስካሁኑ ደቂቃ ድረስ እኔም ሆንኩ ባለቤቴ፣እንግሊዝ አገር የሚገኘው ወንድሜ ባስምም ሆነ ኣደም መተኛት ያልቻልን መሆናችንን ብቻ ነው::

- ነግረሃቸዋል ማለት ነው?!

- መሬት ጠባኝ መፍትሔ ፍለጋ ስኳትን፣የእስላም ስነ ምግባር ምን መሆን እንዳለበት ሲመክረኝና ሲያስተምረኝ ጊዮርጊስ ሲደውልልኝ ለአንተ መፈተኛ መሆን አልፈለኩም:: ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል ፦ ‹‹ጌታችን ሆይ! ለነዚያ ለካዱት ሰዎች መሞከሪያ አታደርገን፤ . . ››]አል ሙምተሒና፡5[

- እጅግ በጣም ነው የማዝነው::

- ነገሩ አሳማሚ ቢሆንም አልፏልና ምንም እንዳልተፈጠረ አድርገህ ቁጠረው:: አሁን ጤንነትህ እንዴት ነው?

- እኔ ደህና ነኝ፤ግን በአንተ ላይ ጥፋት ሰርቻለሁ፤ከባድ በደል ፈጽሜአለሁ::

- እኔ ይቅር ብየሃለሁ፣፤ግን ከግዴታ ጋር ነው::

- ምንድነው?

- የሆነውን ነገር እርግፍ አድርገህ ረስተህ ለራስህ ጤንነት ጥንቃቄ ከማድረግ ግዴታ ጋር ነው:: አለዚያ ይቅር አልልህም::

- ግዴታውን እቀበላለሁ፤ተስማመቻለሁ:: ግን አንተም ጥፋቴን እርግፍ አድርገህ ለመርሳት ቃል ከገባህልህኝ ነው::

- ተስማምተናል:: ቁርስ አድርገሃል?

- አላደረኩም::

- አብረን ቁርስ ለመብላት ራሴን ጋብዣለሁ፤ግን ከጊዮርጊስ ጋር ላለህ ቀጠሮ እንዳትዘገይ በፍጥነት መሆን ይኖርበታል:: ወደ ሬስቶራንቱ ቀድሜ ወርጄ ታች እጠብቀሃለሁ::

- በአምስት ደቂቃ ውስጥ ካንተ ጋር እሆናለሁ::

ግጭት . .

www.path-2-happiness.com

16 ግጭት . .

www.path-2-happiness.com

ግጭት . .

(1)

- ሰዓቱ ሁለት ተኩል ነው፣የጊዮርጊስን ቀጠሮ ማክበር እንችል ይሆን?
- ቁርሱን ቶሎ እንብላና እንቀሳቀሳለን፤መንገድ እንደ ጀመርን ትደውልለትና ጥቂት ልንዘገይ እንደምንችል ትነግረዋለህ:: ትናንት ትንሽ ጠንከር ቢልብኝም ጊዮርጊስ ጨዋ ሰው ነው፣ችግሩን ይረዳልናል::
- ትንሽ ጠንከር ቢልብኝም ነው ያልከው?!
- ስላንተ ጉዳይ ትናንት ደውሎልኝ ማለት የሚችለውን ሁሉ ነው ያለኝ::
- በተፈጠረው ነገር የተሰማኝን ሀዘን አሁንም ደጋግሜ እገልጻለሁ::
- ስምምነታችንን ማፍረስ ፈልገሃል ልበል?
- አይደለም፣ጀማል ከልብ አመሰግነሃለሁ፣ውለታህን መዘርዘር ይሳነኛል::

ጆርጅና ጀማል ወደ ዓለም አቀፍ ሠራተኛ ኤጀንሲ ኩባንያው ደረሱ:: ጊርጊስ መኖሩን ሲጠይቅ እየጠበቀው መሆኑን ጸሐፊው ነገረው:: አብረው ገቡና ጊዮርጊስ በሰላምታ ተቀበላቸው . .

- የምስራች ንገረና . . ወዳጅህ ቦርሳውን አመጣልህ?!
- ተወን መጀመሪያ እንቀመጥ፣ሁለተኛ በመዘየግቴ ይቅርታ አድርግልኝ::
- ጀማል የሚባለውን ወዳጅህን ትናንት እስከ አንገቱ ነው የነገርኩት:: እውነቱን ለመናገር ግን ከአነጋገሩ ጨዋ ሰው ስለመሰለኝ ይሰርቃል ብዬ አልገምትም፣ግን ብዙ ጫና አድርጌበታለሁ::
- አዝናለሁ፣አንተንም አልፍቻለሁ፤ይቅርታ አድርግልኝ፣ትምረናለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ጀማል ድንቅ ሰው ነው ይቅር ብሎኛል፤ቦርሳዬን ሆቴሉ መጸዳጃ ቤት ውስጥ አግኝቸዋለሁ!
- ወየው፣ጌታችን በእዝነትህ ድረስልን! አላህ ለኔም ላንተም ይቅር ይበለን እንጂ በሽካራ አቀራረብ ጀማልን ብዙ ተናግሬዋለሁ!
- ይህ ወዳጄ ጀማል ነው፣ተዋወቀው::
- ውይ! ወንድሜ ትናንት ለፈጸምኩብህ ነገር ይቅርታ እለምነሃለሁ::
- ችግር የለውም፣አላህ ይቅር ይበልህ . . በቃ ነገሩ አብቅቷል፣ረስተን ልንዘጋውና ላናነሳው ከጆርጅ ጋር ተስማምተናል::

-ጆርጅ ቦርሳውን ማግኘቱን መቼ ነበር ያወቅከው?
-በቦርሳው ምትክ የባለቤቴን ወርቅ ይዤለት ስመጣ ጧት ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ነበር።
-አላህ ሆይ ምህረትህን ለግስን፤ጀማል ደጋግሜ ይቅርታ እጠይቀሃለሁ። አላህ እንዲህ ብሏል እኮ ፦ ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስሕተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጻቾች እንዳትኾኑ አረጋግጡ።›› [አል ሑጁራት፡6]
-ይህ የምን ጥቅስ ነው?
-የቅዱስ ቁርአን ጥቅስ ነው።
-የአገሩ ክርስቲያኖችም ቁርአንን በቃላቸው ያውቁታል ማለት ነው?
-ትናንት ያስደስትህ ይሁን አይሁን ባላውቅም ነገ ያልተጠበቀ ነገር እነግረሃለሁ ብዬ አልነበረም! እኔ ከሰለምኩ ገና ስድስት ወሬ ነው።
-ክርስትናን ትተህ ሰለምክ?!
-አዎ . . ምን ያስገርማል? ብዙዎች ናቸው እስላምን ተቀብለው የሚሰልሙት። እንዳውም እስላም በዓለም ላይ ከሁሉም ይበልጥ በፍጥነት በመሰራጨት ላይ የሚገኝ ሃይማኖት ነው።
-የሚገርም ነገር የለውም፣ ግን ሙስሊም ያልሆነ ሰው ሲሰልም ማየት ለኔ ይህ የመጀመሪዬ ነው።
ጀማል በአድናቆት እጁን ራሱ ላይ አድርጎ . .
-ወንድሜ ስትለኝ ገርሞኝ የዜግነትና የሰብዓዊነት ወንድም ለማለት የፈለክ መስሎኝ ነበር፤ወንድሜ ለዛሬውና ለመጪው ዘላለማዊ ሕይወት መታደል በመብቃትህ እንኳ ደስ አለህ።
-ለዛሬውና ለወዳኛው ዘላለማዊ ሕይወት መታደል! የወዳኛውን ዘላለማዊ ሕይወት እንኳ አላውቅም፣በዛሬው ሕይወት መታደልን ማግኘት የሚቻለው ግን እኛ ዘንድ በምዕራቡ ዓለም ነው።
-ቁሳዊ ደስታና ብልጽግናን ለማለት ፈልገህ ከሆነ ልክ ነህ።ሕሊናዊ ደስታና መንፈሳዊ ተድላን በተመለከተ ግን ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እተባባሰና ችግሩ እየከፋ በመሄድ ላይ ነው። ለዚህ ነው በምዕራቡ ዓለም ራሳቸውን የሚያጠፉ፣በመንፈስ ጭንቀት የሚሰቃዩና ለተለያዩ የስነ ልቦና ችግሮች የሚጋለጡ ሰዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እያሻቀበ ሲሄድ የሚስተዋለው።
-ጀማል እኔን ማለትህ ነው?
-አልገባኝም! ከጠቀስኳቸው ነገሮች ጋር አንተን የሚያገናኝ ምን አለ?

-እኔም የዚህ የምትናገረው ምዕራቡ ዓለም አካል ነኝ።
-ጉዳዩ ስለ መታደል ምንነት ነው። ውስጣዊው ህሊናዊ ደስታ፣ደስታ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው። ከመንፈሳዊነት የተራቆተ ቁሳዊ ሕይወት የግንዛቤ ብዥታ የፈጠረ ይመስለኛል፤እናም ለአለመታደል ምክንያት ሆኗል።
-አላህ ይመስገን እንኳን ቦርሳህን አገኘህ እንጂ አሁን ጉዳያችን ስለ መታደል ሳይሆን ለቃለ መጠይቁ ስለሚጠብቁን ሰዎች ናውና ሥራ አለብን።
-ልክ ነህ . . ይቅርታ እኔ ትቻችሁ ልሂድ . . ጆርጅ መቼ ተመልሼ ልውሰድህ?
-ሥራው የሚያቆየኝን ይመስለኛልና ዛሬ አንተ እረፍና ስንጨርስ እኔ ራሴ ወደ ሆቴሉ አደርሰዋለሁ።
-አመሰግናለሁ . . ጀማል መልካም ፈቃድህ ከሆነ ነገ ሁለት ሰዓት ላይ ብንገናኝ ደስ ይለኛል።
-ተስማምተናል፤በሉ አሰላሙ ዓለይኩም ወረሕመቱሏህ ወበረካቱህ።
-ጀማል ድንቅ ሰው ነው፣ እንዴት ነው የተዋወቅከው?
-እንግሊዝ አገር በሚገኘው ወንድሙ በኩል ነው። በነገራችን ላይ ጠንክር ብለህ እንደተቀጣኸው ቢናገርም ከመምጣታችን በፊት ስለ አንተ ስናነሳ ግን ጨዋ የሆነ በጣም ጥሩ ሰው ነው ሲለኝ ነበር፣ክርስቲያን ነህ ብሎም ያስብ ነበር።
-እስላም ውስጥ ለጠላቶቻችን ቢሆን እንኳ ፍትሕ አስተካካዮች እንድንሆን ታዘናል። ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል ፦ ‹‹ . . ሕዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ፤አስተካክሉ፤እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ የቀረበ ነው። አላህንም ፍሩ። አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።››]አል ማኢዳህ፡8[አሁን ይህን እንተውና በመጀመሪያ ስለ ሥራ ውሎቹ መነጋገር ያስፈልገናል፣ከዚያ ቃለ መጠይቁን ትጀምራለህ። እንደ ተረዳሁት ያለህ ጊዜ አጭርና ጠባብ ነው።
-ልክ ነህ፣በኋላ ላይ ግን ስለ መስለምህ ጉዳይ ካንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ።
-በምሳ ሰዓት ወይም ወደ ሆቴሉ ስንመለስ መንገድ ላይ ሊሆን ይችላል።
ማታ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ጆርጅና ጊዮርጊስ በጊዮርጊስ መኪና ወደ ሆቴሉ ለመሄድ የሠራተኛ ኤጀንሲ ኩባንያውን ለቀው ወጡ። ያሳለፉት ቀን ምልምሎቹን ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ውሎችንና ስምምነቶች በመፈራረም

www.path-2-happiness.com

. . ሥራ የበዛበት ቀን ነበር::

- በአንድ ቀን ይህን ሁሉ ለመስራትና የቀረቡትን ሁሉ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ችለሃል:: ቃለ መጠይቁን እንዴት አገኘሽው?
- እውነቱን ለመናገር ከጠበቅኩት በላይ ጥሩ ሆነው ነው ያገኟቸው:: ከሙያዊ ጉዳዮች ባሻገርም ማህበራዊ ስነ ምግባራቸው አድናቆት ጭሮብኛል:: እንዲህ ያለውን ነገር እንግሊዝ ውስጥ አልለመድነውም፤በናንተ ጥረት ተልእኮዬ ቀላልና ስኬታማ የሚሆን ይመስለኛል::
- ቀጣይ እርምጃ ምንድነው የሚሆነው?
- መቻኮል አልፈልግም፣ነገና ተነገወዲያ ከሌሎች ሁለት ኤጀንሲዎች ጋር ሠራተኞችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ ይጠብቀኛል፤ከዚያ በኋላ ነው ተገቢውን የምወስነው::
- መልካም፣መቸኮል ደግ አይሆንም፣አይደለም እንዴ?
- በእውነቱ ችግሩን አስታወስከኝ . . ለጀማል ለዚህ ድንቅ ሰው ያለኝን አክብሮትና ባለውለታነቱን ተናግሬ አልጨርሰውም . . መቸኮል ጥሩም አይደለም ብለሃል፣ታድያ ለምንድነው ተቻኩለህ የሰለምከው?
- እህህ፣ለመፍረድ አትቸኩል! ቸኩሏል ያለህ ማነው? እንዲያውም በጣም ዘግይቻለሁ::
- እንዴት?
- እስላምን አምኜ እስክቀበል ድረስ በቂ ጊዜ ወስጄ አጥንቼዋለሁ:: ያሳመነኝም የዚህ ኩባንያ ባለቤት ነው፤ግና እንድሰልም ፈጽሞ ጫና አድርጎብኝ፣አዞኝም ሆነ ጨቅጭቆኝ አያውቅም:: እስከዚህ ደረጃ ድረስ አልዘገየሁም:: የዘገየሁት ሙሉ በሙሉ አሳማኝ ሆኖ ካገኘሁት በኋላ ሳልሰልም ስድስት ወር ሙሉ መቆየቴ ነበር፤በትክክልም ይህ መዘግየት ነው::
- እንዲህ ያለ ከባድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ስድስት ወር በጣም አጭር ጊዜ በመሆኑ ችኮላ ነው!
- በዚህ ጊዜ ውስጥ ብሞትና የዛሬውንና የወዳኛውን ሕይወት ውርደት ተከናንቤ ቢሆን ኖሮስ?!
- የዛሬውን ዓለማዊ ሕይወትና የወዳኛውን ሕይወት ሁሌ ማያያዛችሁ በጣም የሚገርም ነው፤ይሁንና የዛሬውና የወዳኛው ሕይወት ውርደት ምን እንደሆነ ልታብራራልኝ ትችላለህ?
- የዛሬው ዓለማዊ ሕይወት ውርደትን በተመለከተ፣እስከ ሰለምኩበት

ጊዜ ድረስ ውስጣዊ መረጋጋት፣ሕሊናዊ ሰላምና ደስታ ተሰምቶኝ አያውቅም:: በዚህ ልትገረም ትችል ይሆናል፣ ግን እውነታው ይህ ነው:: ተውሒድ የአላህ ፍጹማዊ አንድነት፣ለርሱ ብቻ ተገዥ መሆን፣ወደርሱ ብቻ መጠጋትና እርሱን ብቻ መማጸን . . ቁሳዊ ችግሮች ቢኖሩ እንኳ እውነተኛውን ውስጣዊ እርካታን ያጎናጽፋል፣ልቦናን ያጠራል:: በእርግጥ አንዳንድ ዘመዶቼ አርቀውኛል፣ከዚያም አልፈው ሊጎዱኝም ሞከረዋል::

- ተውሒድ - የአላህ ፍጹማዊ አንድነት - ውስጣዊ እርካታን ያጎናጽፋል? ልቦናን ያጠራል?!
- አዎ . . ጣዖታዊነት፣ሽርክና ፈጣሪ አምላክን አንድም ሦስትም ነው ብሎ ማመን ውስጣዊ ጭንቀትና የልቦና መታወርን እንደሚያወርሱ ሁሉ ተውሒድ ከዚህ ሁሉ ነጻ ያወጣል:: በመሆኑም ሌሎች ባእድ አማልክትን ከርሱ ጋር እያጋራሁ ሞቼ አላህን መገናኘት አልፈልግም:: አላህ በጣም ርህሩህና መሐሪ በመሆኑ ሁሉንም ኃጢያቶች የሚምር ቢሆንም በርሱ ማጋራትን -ሽርክን- ግን አይምርም:: ጌታዬ ለኔ ርህሩህና ቸር በመሆኑ ሳልሰልም እንድሞት አላደረገኝም::
- አነጋገርህ የሚገርም ነው!
- ምኑ ነው የሚገርመው?
- አሁን ወደ ሆቴሉ ስለደረስን ሬስቶራንቱ ውስጥ ጭውውታችንን እንቀጥላለን::
- ወደ ቤት ለመመለስ በጣም ስለ መሸብኝ እባክህን ይቅርታ አድርግልኝና ሌላ ጊዜ እንጫወታለን::
- እናም እራት ብቻየን እባላለሁ ማለት ነዋ!
- የማያስጨንቅህ ከሆነ::
- ግዴለም፣ደህና እደር::

(2)

ጆርጅ ወደ ክፍሉ ሄዶ እቃዎቹንና ሽዳንጣውን ካኖረ በኋላ በቀጥታ ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ተመልሶ መጣ:: በጣም ርቦት ነበር . . እራቱን በመብላት ላይ እያለ ወጣ ያለ እንግዳ ልብስ የለበሰ ሰው ከአጠገቡ ቆሞ አገኘው . .

- ራሚ እባላለሁ እንዳናግርህ ትፈቅድልኛለህ?
- ተቀመጥ::
- ትናንት በአንቡላስ ወደ ሆስፒታል የተወሰድከው አንተ ነህ?

www.path-2-happiness.com

-አዎ።
-እዚህ አገር ሌቦች ስለሚበዙ ተጠንቀቅ።
-አዎ . . ትናንት ስርቆት ተፈጽሞብኝ ነበር።
-አውቄአለሁ፣ለዚህ ነው ያስጠነቀቅኩህ።
-እንዴት አወቅክ?
-በመናፍስት አማካይነት ሁሉንም ነገር አውቃለሁ።
-የምን መናፍስት?
-ይህማ የማይነገር የኔ ምስጢር ነው።
-ነገ ምን እንደሚደርስብኝ ታውቃለህ?
-አዎ አውቃለሁ።
-ይህ አባባል ከሰብአዊ አእምሮና ከሃይማኖት ጋር አይጻረርም?
-ከኛ ይበልጥ ሃማኖታችንን ታውቃለህ፣አንተ ሙስሊም ነህ?
-አይደለሁም፣ግን በናንተ ቁርኣን ውስጥ ከህዋስ የራቀውን ነገር ከአላህ በስተቀር ማንም አያውቅም ይላል።
-ይህ ራሱን የቻለ ዕውቀት ነውና ሁሉንም ሃይማኖቶች ቻል በላቸው።
-እኔ ሙስሊም አይደለሁም፣ግን የምትለው ነገር አፈተረት እንጂ ዕውቀት አለመሆኑን አምናለሁ። እንዲህ ያለው ነገር እኛ ክርስቲያኖች ዘንድም አለ፤እናንተ ሙስሊሞች ዘንድ መኖሩን ግን አላውቅም ነበር!
-እህህ፣ጣሊያን የክርስቲያኖች አገር ናት፣እዚያ ያለው የጠንቋዮች ቁጥር ከሃይማኖት መሪ ካህናት ቁጥር ይበልጣል!
-የተነፈግነውን መንፈሳዊነት ለማግኘት በምናደርገው ፍለጋ ምክንያት አፈተረትና ጥንቆላ በምዕራቡ ዓለም በፍጥነት በመሰራጨት ላይ መሆኑን አውቃለሁ። ይሁን እንጂ አፈተረትና ጥንቆላ ነውና ይህን ዕውቀት ነው ብለህ ልታሳምነኝ ትችላለህ?
-አዎ።
-ትናንት ሁለት ጊዜ ነበር የተሰረቅኩት፤ማን እንደ ሰረቀኝ ታውቃለህ?
-እንዳነበው መዳፍህን ልትሰጠኝ ትችላለህ?
-እንካ።
-በሁለቱም ጊዜ የሰረቀህ ለአንተ በጣም ቅርብ የሆነ ሰው ነው።
-በጣም ጥሩ፣እውነትም ትንቢት የምታውቅ ትመስላለህ፤የተሰረቀብኝ ምንድን ነበር?
-ለአንተ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ነው የተሰረቅከው።

-ሰርቆት የት አስቀመጠው?
-ቅርብ ቦታ ነው . . ሩቅ ነው፤ቦታውን ለሚነግረኝ መንፈስ እንድሰጠው አስር ዶላር ብቻ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ።
-ከኔ የተሰረቀው ቦርሳዬ ያለበትን ቦታ ከነገርከኝ ከቦርሳው ውስጥ መቶ ዶላር እሰጠሃለሁ።
-መጀመሪያ አስሩን ዶላር ስጠኝና።
-አሁን ምንም የለኝም።
-አሁን አስሩን ዶላር ካልከፈልክ ከባድ ችግሮች እንደሚያጋጥሙህ ደጉ መንፈስ ነግሮኛል።
-እህህ፣አሁን ምግቤን ጨርሻለሁ፣ያንተ ደጉ መንፈስ ውሸታም መሆኑን ንገረው፣ቦርሳዬ ከኔ ጋር ነው፣አልተሰረቀም፣በአንተ መጫወት ስለ ፈለግሁ ብቻ ነው።

ጆርጅ አብሮት በነበረው አባይ ጠንቋይ እያሾፈና እየተዘባበተ፣ሮማ ውስጥ ያሉ ጠንቋዮች ከካህናቱ ቁጥር የመብለጣቸው እውነታ ለምን እንደሆነ እየተገረመ ወደ ክፍሉ ሄደ። ሃይማኖት ከስሮ ሎጂክን፣አእምሮንና ሳይንስን በመጻረሩ ረገድ ከአባይ ጠንቋዮችም መብለጡ ይሆን? ትናንት ሳያይ ያደረውን ኢሜይል ለማየት ኮምፒውተሩን ከፈተ . . ከጃኖልካ የተላከ ደብዳቤ አገኘ . .

‹‹ወዳጄ ጆርጅ

መልእክትህን አንብቤ የደረሰብህ ነገር በጣም አሳዝኖኛል።ሁለት ነገሮች ግን ግልጽ ሊሆኑ ይገባል። አንደኛ፦ ሃይማኖታቸው በዚያ ላይ የማያበረታታቸው እስከሆነ ድረስ፣የትኛውንም ሃይማኖት አመለካከትና ርእዮትን ከግለሰብ አቀንቃኞቹ ለይተን መመለከት ይኖርብናል። ሁለተኛ፦ እኔ እዚህ ከሙስሊሞች አብሬ እየኖርኩ ነው። በአጠቃላይ አነጋገር ድህነትና የጎሳ ልዩነቶች ቢኖሩባቸውም፣መንግስታዊ ተቋሞቻቸው ደካማ ቢሆኑም . . ወደዚያ የሚገፋፉ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም ከስርቆት በጣም የራቁ ሰዎች ናቸው። ይህን የሚያደርጉት መንግስትን በመፍራት ሳይሆን ሃይማኖታቸው ስለሚከለክላቸው ብቻ ነው። እኛን ግን ከዚህ የሚከለክለን በአብዛኛው ስርዓቱና ተቋማቱ እንጂ ግብረገብነት ወይም ሃይማኖት አይደለም። ህግና ሥርዓቱ ሲናጋ እኛ ዘንድ ስለሚፈጠረው መዓት ከኔ ይልቅ የምዕራቡን ተሞክሮ አንተ ታውቃለህ። በመጨረሻ ልነግርህ የምፈልገው ነገር ቢኖር ከአሻፈረኝ ባይነቴም ጋር ለመስለም በጣም የቀረብኩ መሆኔን ነው፤አንዳንድ ጥቃቅን ዝግጅቶችና ስጋቶች ብቻ ናቸው ለጊዜው ከመስለም ያቆሙኝ።

ጃኖልካ››

መልስ ጻፈለት ፦

‹‹ወዳጄ ጃኖልካ

ላሳየኸኝ አጋርነት አመሰግናለሁ። እውነታውን እንዴት እንደምነግርህ አላውቅም፤የተሰረቅኩ መስሎኝ ሙስሊም ወዳጄን በችኮላ ወንጅየው በደል ፈጸምኩበት። እርሱ ግን በድንቅ ሰብእናው፣በምሉእ ስነ ምግባሩ፣በአስደናቂ ትእግስቱና በትህትናው አሳፈረኝ። ለጅልነቴ እንዴት ብዬ ይቅርታ እንደምጠይቀው ማወቅ እንኳ አቃተኝ! መስለምን በሚመለከት በኔ በኩል ለምን እንደሆነ እንጃ አሁን አመቺ አይደለም የሚል ስሜት አለኝ፤አሁንም ድረስ ያልተመለሱልኝና የሴቶችን ጉዳይ፣ሰብዓዊ መብትንና ሃይማኖቱ ያለውን የሥልጣኔ ደረጃ የሚመለከቱ ነጥቦች ይቀሩኛል። በዚህ ረገድ የምትደርስበትን እንደምታስታውቀኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

ጆርጅ››

በመቀጠል ከሌቪ የተላከለትን ኢሜይል ከፈተ . .

ወዳጄ ጆርጅ

በደረሰብህ ነገር በጣም አዝኛለሁ፤አስጠንቅቄሃለሁ፣አሳስቤሃለሁም። የደረሰብህ ነገር ምናልባት ያንተንና የእጮኛዬን የሐቢብን ወደ እስላም በፍጥነት መንደርደር ለማርገብ መልካም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። ልንረዳህ የምንችለው ነገር ካለ አሳውቀን፤ወደ ቴልአቪብ ብትመጣ ለሁላችንም ትልቅ የምስራች ከመሆኑም በላይ ከአሸባሪዎቹ ሙስሊሞች እጅ አንተን መታደግ ይሆናል፤መምጣትህን በጉጉት እንጠብቃለን።

ሌቪ››

መልስ ጻፈላት፦

ወዳጄ ሌቪ

በጣም ናፍቄሻለሁ፣ምክሮችሽ ሁሌም ያስፈልጉኛል፤ እውነቱን ለመናገር ግን ምን እንደምልሽ እቸገራለሁ . . የሆነው ነገር ሳልሰረቅ የተሰረቅኩ መስሎኝ ሙስሊም ወዳጄን በችኮላ ጠርጥሬ በማስቀየም በደል ፈጸምኩበት። እርሱ ግን በድንቅ ሰብእናው፣በምሉእ ስነ ምግባሩ፣በአስደናቂ ትእግስቱና በትህትናው አሳፈረኝ። ለጅልነቴ እንዴት ብዬ ይቅርታ እንደምጠይቀው ማወቅ እንኳ አቃተኝ! ወደ እስላም አለመንደርደሬን ደግሜ ልገልጽልሽ እወዳለሁ። በእርግጥ በብዙ ሕግጋቱና እምነቶቹ በአድናቆት ብያዝም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ግን ገና ውሳኔ ላይ አልደረስኩም። ከሐቢብ ጋር

በመተጫጨታችሁ እንኳን ደስ አለሽ እላለሁ። እውነት እልሻለሁ በአእምሮ ብስለቱ በዕውቀቱና በሰፊ ግንዛቤው እሱን የመሰለ የትም አታገኚም። ከርሱ ጋር ስትወያዪ የትም ቦታ የማታገኚውን እርሱ ዘንድ ታገኚያለሽ። እናንተ ዘንድ ወደ ቴልአቪብ ብመጣ ደስታዬ ነበር፣ሆኖም ግን እዚህም እዚያ ያገኘሁት ዓይነት አቀባበልና መስተንግዶ እያገኘሁ ነው፤ምናልባት በቅርብ ጊዜ ውስጥ እጎበኛችሁ ይሆናል።

ጆርጅ››

ከዚያም ከደረሱት ደብዳቤዎች መካከል የካትሪናን አገኘ . .

‹‹ፍቅሬ ጆርጅ

ትናንት ወደ ሆስፒታሉ ስሄድ በባስም ወንድም የተፈጸመብህን ስርቆት ኣደም ነግሮኝ በጣም ተሰምቶኛል። ለማንኛውም እርሱ የሰረቀህ መሆኑን እርግጠኛ እንድትሆን እፈልጋለሁ። እስላምን እንዲያስተዋውቀኝ ባስምን በጎበኘሁበት ባለፉት ሁለት ቀናት ውስጥ በቅርበት ለማወቅ እንደቻልኩት፣ወንድሙ እንደ እርሱ ከሆነ ይህንን ይሰራል ብዬ አላምንም፤ለሁሉም ጻፍልን።

መልስ ጻፈላት . .

‹‹የኔ ፍቅር

ምንም ጥርጣሬ በሌለው ማስረጃ እርሱ ያልሰረቀኝ መሆኑን አረጋግጫለሁና አንቺም አርግጠኛ ሁኚ። የሆነው ነገር በኔ በኩል በተፈጸመ ስህተት ምክንያት ነውና ስለኔ ሆነሽ ባስምን ይቅርታ ጠይቂልኝ። በነገራችን ላይ ካቶሊካዊቷ ሃይማኖተኛ ካትሪና እስላምን ለማወቅ መፈለጓ እንዴት ሊታመን ይችላል?! ወይስ ቁርኣን ወይም ማንበቡን ትፈሪው የነበረውና ‹‹ለኢየሱስ ያለኝ ታላቅ ፍቅር ወደ እስላም ወሰደኝ›› የሚለው መጽሐፍ ተጽእኖ አሳድሮብሽ ይሆን?! የኔማ ፍቅር በጣም ናፍቄሻለሁ።

አፍቃሪሽ ጆርጅ››

ልኮላቸው ለነበረው ጥያቄ ከወዳጆቹ የተላኩለትን ምላሾች ሲያነብ ቆየና ሁሉንም አንድ ላይ ጨመቅ አድርጎ ለያንዳንዳቸው መልሶ ላከ . .

‹‹ሽብርተኝነትን በተመለከተ፦

ሐቢብ ፦ ሽብርተኝነት ፈጽሞ ሃይማኖት የለውም።

ሌቪ ፦ አባቴን የገደሉ ሙስሊሞች ሽብርተኞች ካልሆኑ ሽብርተኝነት ሌላ ትርጉም አለው ብዬ አላስብም።

ካትሪና ፦ እስላም ውስጥ ሽብርተኝነት የለም።

ኣደም ፦ ሽብርተኛ ሀብት ለመዝረፍ የሌሎችን አገር የሚወር ነው።

www.path-2-happiness.com

ቶም ፦ ሽብር ተቃዋሚዎችን ለማጥላላትና ለማጥቃት የሚያገለግል አዲሱ ስልት ነው።

ጃኖልካ ፦ ከሽብርተኝነት ዓይነቶች ሁሉ አደገኛው ርእዮተ ዓለማዊ ሽብርተኝነት ነው። ይህም በነጻ ማሰብንና የገዛ አእምሮ መጠቀምን እንኳ ማስፈራራትና መከልከል ነው። እስላም ግን በነጻ ለማሰብና ለማስተንተን ጥሪ ያደርጋል።

ጆርጅ ፦ በኛ በምዕራቡ ዓለም መገናኛ ብዙኃን በኩል ብቻ ካልሆነ በስተቀር፣በእስላምና በሽብርተኝነት መካከል እስካሁን ምንም ግንኙነት አላየሁም።

ሴቶችን በተመለከተ ፦

ካትሪና ፦ ስለ ሕጃብ እስካሁን መረዳት ባልችልም፣ሴት ልጅ እስላም ውስጥ በእጅጉ የተከበረች ናት።

ሌቪ ፦ ከአይሁዳዊነትም ሆነ ከክርስትና የከፋ አይደለም።

- ቶም ፦ በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር ማድረግ ያስፈልገኛል። ቁርኣን ውስጥ ‹‹ወንድም እንደ ሴት አይደለም፤››]ኣል ዒምራን:36[የሚል ጥቅስ ሰፍሯል።

ሐቢብ ፦ አልበደላትም።

ጃኖልካ ፦ በኛ ባህል ውስጥ በሁለቱ መካከል ግልጽ ልዩነቶች ከመኖራቸውም ጋር፣ተመሳሳይነት በሌለበት ፍጹማዊ እኩልነት አዳጋች መሆኑ እየታወቀ ለሴትና ወንድ እኩልነት ጥሪ እናደርጋለን። እስላም ግን ከተፈጥሯ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ተገቢ መብቷን በማክበር ፍትሐዊ አያያዝ ይደነግግላታል።

ኣደም ፦ ሴት እስላም ውስጥ የተጎናጸፈችውን ያህል ክብርና ደረጃ በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ አልተጎናጸፈችም። ከፈላጋችሁ ከየትኛውም መለኮታዊም ሆነ ምድራዊ ሃይማኖት ጋር አነጻጽሩት።

ጆርጅ ፦ ሕጃብን፣ለሰላምታ መጨባበጥን፣ውርስናንና ሌሎቹንም በተመለከተ አሁንም ብዥታዎች አሉብኝ። ስለዚህም የበለጠ ግልጽ እንዲሆኑልኝ ጥሪት አደርጋለሁ።

እስላምን በተመለከተ የሰጣችኂቸው መልሶች በአብዛኛው አዎንታዊ ከመሆኑ እውነታ በመነሳት ግልጽና ቀጥተኛ ጥያቄ አቀርብላችኂለሁ ፦ እስላምን ተቀብላችሁ ከመስለም ምን አገዳችሁ? ጥልቀትና ተጨባጭነት ያለው ምላሽ በሁለት ቀናት ውስጥ ላኩልኝ።

ወዳጃችሁ ጆርጅ››

የቶምን የፌስቡክ ገጽ ከፈተ፣ይህ ነው የሚባል ነገር አላገኘም። ወደ ኣደም ፌስቡክ ገጽ ተዛወረ፤‹‹የመታደልን መንገድ በመፈለግ ላይ ከተሰማራው ወዳጄ የሚቀሰሙ ትምህርቶች 5›› በሚል ርእስ አዲስ መጣጥፍ ሰፍሮ አገኘ ፦

‹‹ወዳጄ በመጨረሻዎቹ ደረጃዎች ላይ መሆኑን ካንድ ጊዜ በላይ ደጋግሜላችኂለሁ። የመታደሉ መንገድ እስላም መሆኑንና ያለ እስላም ለታላላቆቹ ጥያቄዎቹ ምላሽ የሚሰጥ አለመኖሩን በከፍተኛ ደረጃ አምኖ ተቀብሏል። ይሁን እንጅ ወደ ቅኑ መንገድ የመምራት ሥልጣን በአላህ እጅ ብቻ ነው። ባለቤቱ ትናንትና እስላምን ወድዳና በከፍተኛ ስሜት ውስጥ ሆና ታለቅስ ነበር፣ሰልማ ይሁን አይሁን ግን አላውቅም፤እያለቀሰች ነበር ወደ ቤቷ የተመለሰችው። አላህ ለዚህ ዓለምና ለወዳኛው ዓለም መታደል ያበቃት ይሆናል። ወዳጄን በተመለከተ ግን በአእምሮ ብስለቱና በግንዛባው ብቃት ብተማመንም ሙስሊሞችን እየፈራሁለት እስላምን በቅርበት ለማወቅ ወደ ግብጽ ሄዷል። የሚያሳዝነው ግን እዚያ ሆኖ በሙስሊሞች ስርቆት ተፈጽሞብኛል እያለ ነው። ይህን ፈተና ማለፍና ወደ እስላም መግባት የሚያስችል የልቦና ፍጹምነት አለው ብዬ ባምንም፣ስህተትና ችግሩ በእስላም በራሱ ምክንያት በመሆኑና በሙስሊሞቹ ምክንያት በመሆኑ መካከል ያለውን ልዩነት አልተረዳም። ትምህርቶቹን እንደሚከተለው ጠቅለል አድርጌ አቀርባለሁ ፦

1. እስላም ምሉእ፣አጠቃላይና ከጉድለት የጠራ ሲሆን በተቃራኒው ግን ሙስሊሞች እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ስህተትና ጉድለት ይኖርባቸዋል።
2. ወደ እስላም ለመግባት የሚደረገው ውሳኔ ከፍተኛ ጀግንነትና ድፍረትን እንዲሁም ጥልቅ ግንዛቤን የሚጠይቅ ሲሆን፣ምናልባትም እነዚህ ነገሮች ለወዳጄ በእጅጉ ያስፈልጉታል።

. ሰዎች በተሟላ ሁኔታ አሳማኝ ሆኖ እስኪገኙት ድረስ፣ወደ እስላም እንዲገቡና የመታደልን መንገድ እንዲይዙ ለማድረግ መጣደፍ አይገባም።

በሁሉም አንጻር የተሟላና በሁሉም አቅጣጫ አሳማኝ በመሆኑ፣በመታደል መንገድ ላይ የምንደብቀው ምንም ነገር የለም።

የመታደልን መንገድ ለማወቅ በአላህ የታደለ ሰው ሁሉ መንገዱን ለሌሎች በመልካም ሁኔታ ማብራራት ሲኖርበት ለዚያ የማብቃቱ (የህዳያ) ስልጣን ግን የአላህ ብቻ ይሆናል።

አላህ ልቡን ለመመራት ይከፍትለት ይሁን አይሁን በእርግጠኝነት

ባላውቅም፣ለወዳጄ መልካሙን ሁሉ እመኝለታለሁ!
ስድስተኛውን ትምህርት ተጠባበቁ . .
ኣደም››

ኣደም ስለ ካትሪና የተናገረው በጣም ረብሾታል:: ካትሪና ሰልማለች ብሎ ማሰብ እንዴት ይቻላል? ፈጽሞ ሊሆን አይችልም . . ምናልባት ኣደም በተሳሳተ መንገድ ተረድቷት ይሆናል:: እንዳውም ኣደም ለገጹ አንባቢዎች ካቶሊካዊት ሴት ወደ ሃይማኖቱ ማስገባት መቻሉን ዋሽቶ ለማሳየት እየጣረ ሊሆንም ይችላል:: በትናንቱ የመጨረሻ ደብዳቤዋ እንደምትሰልም አልነገረችውም . . የኣደም መጣጥፍ መቼ ፖስት እንደተደረገ ሲመለከት ከሁለት ሰዓት በፊት መሆኑን ተረዳ:: የካትሪና ደብዳቤ ግን ትናንት ጧት የተጻፈ ነበር:: ታድያ ትናንት ምሽት ሰለመች ብሎ ማሰብ እንዴት ይቻላል? ከሆነስ ለምን አልነገረችውም?

የካትሪና የመጨረሻዎቹ ደብዳቤዎች፣ሁሉም ስለ እስላም አዎንታዊ አመለካከት የያዙ ብቻ ሳይሆኑ የስርቆት ክስተቱን በተመለከተ እስላምና ሙስሊሞችን ለያይተው የሚመለከቱ ናቸው:: ታድያ ይህ ለመስለሟ ማስረጃ አይደለምን? ግን ደግሞ ካትሪና ሁሌም ለካቶሊካዊነት ተቆርቋሪ ናት፣ኢየሱስን ወደር በሌለው ሁኔታ ታፈቅራለች፣ለርሱም ብላ ነው ቤተክርስቲያን ለማገልገል ጉልበትና ጊዜዋን የምትሰዋው:: ይህን ሁሉ እርግፍ አድርጋ መተው የሚቻል ነው?

ጆርጅ ሌሊቱን በከባድ የአእምሮ ጭንቀትና ግጭት ውስጥ አሳለፈ:: አንዴ ባለቤቱ ያሻትን ማመን መብቷ መሆኑን ሲቀበል፣ሌላ ጊዜ ደግሞ በውስጡ በርሷ ላይ ሲቆጭ ይሰማዋል:: እንደገና ደግሞ የመስለሟን ወሬ ያስተባብላል . . ለራሱ መስለም ቢፈልግ ለርሷ መንገር ይኖርበት ነበር ወይስ ያሳደረው ስሜት የወንድና ሴትን እኩልነት ያለመቀበል አንዱ መገለጫ ይሆን? . . ካንዴም ሁለቴ ሊደውልላት አሰበ፣ግን ራሱን ያዝ አደረገ:: እርሷ ራሷ መደወል ወይም ቢያንስ ኢሜይል መጻፍ ትችል አልነበረም? እናም ካትሪና እንዲህ ያለውን ከባድ ውሳኔ ገና ያልወሰነች ሳትሆን አልቀረችም . .

(3)

ጆርጅ እየተጫጫነውና እየከባበደው ጧት አንድ ሰዓት ላይ ከእንቅልፉ ነቃ:: በችኮላ ሻወር ወስዶ ለቁርስ ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ሄደ:: ከዚያም ወደ ሠራተኛ ኤጀንሲው አብረው ለመሄድ እንግዳ መቀበያው ውስጥ ቁጭ ብሎ

የጀማልን መምጣት ጠበቀ::

ወደ ሠራተኛ ኤጀንሲው ኩባንያ ደርሰው ከሥራ አስኪያጁ ጋር ለመገናኘት ጠየቁ . .

- ከሚስተር ሙስጠፋ ጋር ትገናኛላችሁ አንዴ ቆዩኝ . .
- ጀማል፣የሥራ አስኪያጁ ስም ‹‹ሙስጠፋ›› ምን ማለት ነው?
- ከነብዩ ሙሐመድ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ስሞች አንዱ ሲሆን፣በአላህ የተመረጠ ተመራጩ ማለት ነው፤ሙስሊሞች በዚህ ምክንያት ይጠሩበታል::
- ሙስሊም ነው ማለት ነዋ!
- በመሳረቱ እንደዚያ ነው::

ከአፍታ በኋላ ሚስተር ሙስጠፋ እየጠባቃቸው መሆኑን ጸሐፊው ነገራቸው . .

- እንኳን ደህና መጣችሁ::
- እንግዲያውስ ፍቀዱልኛና እኔ ልሂድ፣ጆርጅ ስድስት ሰዓት ላይ እመጣልሃለሁ::
- ከሚስተር ሙስጠፋ ጋር ምን ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልገኝ አላውቅም::
- በኢሜይልህና በዝግጅታችን መሰረት ስምንት ሰዓት ላይ እንጨርሳለን ወይም ነገ በድጋሚ ትመጣለህ የሚል ግምት አለኝ::
- እንግዲያውስ ጀማል መልካም ፈቃድህ ከሆነ ስምንት ሰዓት ላይ እጠብቅሃለሁ::
- አንተ እንግዳችን ስለሆንክ ዛሬ ምሳ አብረን እንድንበላ እጠይቃለሁ::
- እናቴ ጆርጅን ዛሬ እኛ ዘንድ ምሳ እንድንበላ ይዤው እንድመጣ ጠይቃኛለች::
- በቃ እራት ከኔ ጋር ትበላለህ::
- ተስማምተናል፣ጀማል ስምንት ሰዓት ላይ እጠብቀሃለሁ::
- እኔ ደግሞ አንድ ሰዓት ላይ ወደ እራት እንድንሄድ ሆቴልህ ድረስ እመጣለሁ::
- ተስማምተናል፣በሉ ደህና ሁኑ::

ጀማል ወጣ፤ሙስጠፋ ፊቱን ወደ ጆርጅ አዞረ . .

- የቅርብ ወዳጆች ትመስላላችሁ::
- አዎ፣ከተዋወቅኩት ገና አጭር ጊዜ ቢሆንም ከሰውም ድንቅ ሰው ነው::
- ትውውቅህ የቅርብ ጊዜ እስከሆነ ድረስ ከነዚህ ሃይማኖተኛ እስላማውያን

www.path-2-happiness.com

እንድትጠነቀቅ አሳስበሃለሁ::

-ሃይማኖተኛ እስላማዊ መሆኑን እንዴት አወቅክ?!

-ከአኳኋኑ በግልጽ ይታያል::

-ከምኑ ነው የምታስጠነቅቀኝ?

-እንዳይገድልህ ወይም እንዳይሰርቅህና የመሳሰለውን እንዳይፈጽምብህ ነው የማስጠነቅቅህ:: ሊጠሉት የሚገባ ከሀዲ (ካፊር) ብቻ ሳትሆን መገደል ያለበት ሰው አድርገው ነው የሚመለከቱህ::

-ለምክርህ አመሰግናለሁ፤አንተ ከየትኛው የሙስሊሞች ጎራ ነህ?

-እኔ ሙስሊም ነኝ ግን ተራማጅና ዘመናዊ ነኝ፤ከፊል ሕይወቴን አሜሪካ ውስጥ ስለ አሳለፍኩ እስላማውያኑ ዘንድ የሌሉ አያሌ የሥልጣኔ ጉዳዮችን ተምሬአለሁ::

-እንዴት ያሉትን?

-ዴሞክራሲን፣የተለያዩ ሃሳቦች ማስተናገድ መቻልን፣የተለያየ ሃይኖት ካላቸው ጋር ተቻችሎ መኖርን፣ አንተ እንግሊዛዊ ነህና ከኔ ይበልጥ የምታውቃቸውን ሎሎች ነገሮችንም . .

-ይህ ያንተ ትህትና ነው፣ግን አነጋገርህ በጣም አስገርሞኛል፣እኛ ክርስቲያኖችም እኮ እናንተንም ኋላ ቀር ከሃዲዎች (ካፍር) አድርገን ነው የምንመለከታችሁ!

-ሙስጠፋ መጣፊያ አጣ፣ቀጠለና ‹‹እውነቱን ለመናገር አኛ ኋላ ቀሮች ነን፣በዚህ ረገድ ለኛ ያላችሁ አመለካከት ትክክለኛ ነው::›› አለው::

-ሊሆን ይችላል፣ለማንኛውም ሥራችንን እንጀምር::

-መልካም . . ሥራችንን እንጀምር፤ይሁንና ለሌሎች ሥልጣኔዎችና ባህሎች ክፍት አእምሮና ነጻ አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር መስራት ግን ለአንተ ስኬታማነት ዋስትና ነው፣ከማትፈልገው ነገርም የሚያርቅህ ነው::

-ያለ ምንም ጥርጥር፣በተለይ ደግሞ አገሩንና ማህበረሰቡን የሚወድ ከሆነ!

-አመሰግናለሁ፤በኢሜይልህ መስፈርት መሰረት ምልምል ሠራተኞችን አዘጋጅቼልሃለሁ::

-መልካም፣ስንት ናቸው? አንተስ እንዴት ገመገምካቸው?

-ለመጀመሪያ ዙር ስምንት ሰዎች ናቸው፣አብዛኞቻቸው ለዓለም የተለያዩ ባህሎችና የአነዋነዋር ዘይቤዎች ክፍት አእምሮና ነጻ አመለካከት ያላቸው ናቸው::

-ጥሩ፣ሙያዊና ክህሎታዊ ብቃታቸውስ?

-መጥፎ አይደለም . . አንተ ራስህ አግኛቸው፤ቃለ መጠይቁን እንጀምር እንዴ?

-ይቻላል፣ከመግባታቸው በፊት ግን በቅደም ተከተላቸው መሰረት ሲቪዎቻቸውን ትሰጠኛለህ::

-ይኸውና፣በዝርዝሩ መሰረት ጸሀፊው እንዲያስገባቸው እነግረዋለሁ፤አሁን ወደ ሰውብሰባ ክፍሉ እንሂድ፣አንተን አድርስና ወደ ቢሮዬ ተመልሼ እጠብቀሃለሁ::

በሙስጠፋ የቀረቡለትን ስምንቱን እጩዎች ተራ በተራ ተቀብሎ አነጋገራቸው፣ለስምንት ሩብ ጉዳይ ላይ ሥራውን አጠናቀቀ . .

-አመሰግናለሁ፣ቃለ መጠየቁን ጨርሻለሁ::

-እንዴት አገኘሃቸው?

-ጥሩ ናቸው፣የነገውን ዙር ሳጠናቅቅ ነው የምወስነው:: አሁን የጀማል መምጫ ነው፣ጨዋታችንን ማታ እራት ላይ ብንቀጥል ምን ይመስለሃል?

-መልካም ነው፣ምትወደውንና ምትደሰትበትን ሁሉ አዘጋጅቼልሃለሁ፤ጀማል እስኪደርስ ድረስ፣ ካነጋገርካቸው ስምንቱ ውስጥ ትኩረትህን የሳበ ወይም በሆነ ነገሩ ደስ ያለህ ሰው አለ?

-ትኩረቴን የሳበ ብዙ ነው፣ያስደነቀኝም ብዙ ነው::

-ዛሬ የሚያስደስትህን ሁሉ ታገኛለህ::

-እንዴት?

-እራት ላይ ይነገረሃል::

ጆርጅ ከኩባንያው ቢሮ ለቆ ሲወጣ ጀማል እየጠበቀው ነበር:: አብረው ወደ ጀማል ቤት አመሩ . .

-የዛሬ ውሎህ እንዴት ነበር?

-ምንም አይልም::

-ብዙም ያልረካህ ትመስላለህ!

-ፈጽሞ አላስደሰተኝም!

-ለምን?

-እኔ የምፈልገው ሙያተኛ ፕሮግራመሮችን ሲሆን እርሱ ያቀረበልኝ ግን ተራ የሰራተኞች ስብስብ ነበር::

-ምናልባት አንተ የፈለከውን አልተረዳ ይሆን?

-በሚገባ ተረድቷል፤ሥጋዊ ፍላጎቴን ብቻ ለማርካት የምፈልግ ሰው አድርጎኝ ነው የገመተው:: ታውቃለህ ከቀረቡልኝ ስምንት እጩዎች

www.path-2-happiness.com

መካከል አምስቱ ሴቶች ሲሆኑ ፕሮግራመሮች ሁለቱ ብቻ ናቸው:: ወንዶች ሦስት ሲሆኑ ሁለቱ ብቻ የኮምፒውተር ሙተያተኞች ናቸው::

- ታድያ በምን መስፈርት ነው ሰዎቹን የመረጠልህ?
- በአብዛኛው በቁንጅና፣በሽቅርቅርነትና በመናፍቅነት መስፈርት ነው!
- ማለት የፈለከው ገብቶኛል፣ይቅርታ እጠይቅሃለሁ፣እኛ ግብጻውያን ግን እንደዚያ አይደለንም!
- ሊሆን ይችላል፣ካነጋገርኳቸው መካከል ልዩ ብቃት ያላቸው አንድ ወንድና አንድ ሴት ቢኖሩም፣ሁለተኛ ባላገኘው ደስ ባለኝ ነበር::
- ቀጠሮ የሰጠኸው እንደ መሆኑ ዛሬ አብረህ እራት ብላና ልዩ ብቃት አላቸው ያልካቸውን ለማግኘት ጠይቀው::
- ይህ የነገውን ቃለ መጠይቅ ከጨረስኩ በኋላ የማደርገው ይሆናል::
- ነገሮች ሁሌ በሚፈለገው መንገድ ላይሳኩ ይችላሉ፤ወደ ቤት ለመድረስ ጥቂት ነው የሚቀረን፤አሁን ወደ ሰፈሩ እንገባለን:: ይቅርታ አድርግልኝና የምንኖረው በተራ ሰዎች ተራ ሰፈር ነው፣ባለ አምስት ወይም አራት ኮከብ ሆቴሎች የሉበትም::
- እኔ ይህንን ነው እምወደው፣አንተንና እናትህን ደጋግሜ አመሰገህናለሁ::
- እንደምታየው መንገዱ በጣም ጠባብ በመሆኑ ከዚህ በላይ በመኪና መግባት አንችልም፤በጣም ቅርብ ስለሆነ እስከ ቤቱ ድረስ ቀሪውን መንገድ በእግር እንጓዛለን::

እርጅና በሚስተዋልበት አሮጌ የመኖሪያ ሕንጻ ሦስተኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኘው የጀማል አፓርታማ ደረሱ:: ጀማል ለእንግዳ መቀበያነት ወደ ተዘጋጀችና በወግ ወደ ተያዘች ትንሽዬ ክፍል ጆርጅን ይዞ ገባ . .

- ግባ እንኳን ደህና መጣህ፣ለአፍታ ፍቀድልኝ፣መጣሁ::

ጆርጅ በክፍሏ ውስጥ ያሉ ተራ የቤት እቃዎችን እያስተዋለ ቁጭ አለ:: ተራና ቀለል ያሉ ነገሮችን የሚወድ ቢሆንም ወደ ሰፈሩ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጀማል አፓርታማ ክፍል ድረስ ባየው በጣም ተገርሟል:: እውን ይህ መኖሪያ ቤቱ ነው? ወይስ የሆነ ነገር አስቦብኝ ወደዚህ አምጥቶኝ ይሆን? ‹‹እነዚህ እስላማውያን ገዳዮች ሰራቂዎችና በቀለኝነት የተጠናወታቸው ናቸው . . ›› የሚለው የሙስጠፋ አባባል ትዝ አለው . . በእንግዳ ሀሳቡ ሳቀና በቦርሳው ስርቆት በወነጀለው ጊዜ ያሳየውን ታላቅ ስነ ምግባር አስታወሰ:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ጀማል የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች የተደረደሩበትን ትልቅ ሳፋ ይዞ መጣ፤ሳፋውን ከጆርጅ ፊት አስቀመጠ . .

- ቆይቼብህ ከሆነ ይቅርታ፣በል ብስምላህ ጀምር::
- አመሰግናለሁ፣ብዙ ለፋህ::
- ምንም አልለፋሁም፣ምግቡን እኔ ሳልሆን ያዘጋጀችው እናቴ ናት:: እርሷ ነች ለምሳ የጋበዘችህ፣ከአፍታ በኋላ መጥታ ሰላም ትለሃለች::
- እንግዳው ወደ ቤት ሲደርስ የጋባዡ አለመገኘት አስገራሚ ነው::
- ሴት በእስላም ውስጥ እናንተ ከምታስቡት በላይ ክቡር ነች፤የሚታዘዙላት ንግስት ነች፤የፈለገውን ቢሆን እናቴ የጠየቀችውን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ::
- የፈለገውን ቢሆን?!
- አዎ፣የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ::

ኡሙ ባስም መጥታ በሩ ላይ ቆመች፣ መሬት መሬቱን እያየች በግብጻዊ ቅላጼዋ ሠላምታ አቀረበች . .

- አሰላሙ ዐለይኩም የኔ ልጅ፣በመምጣትህ አክብረህናል አስደስተህናል፣ክብር ተሰምቶናል . . ባስም ሰላም ብሎህ አደራ ብሎናል . .
- ጆርጅ እናቴ እንኳን ደህና መጣህ ሰላም የኔ ልጅ፣በመምጣትህ አክብረህናል አስደስተህናል፣ክብር ተሰምቶናል . . ባስም ሰላም ብሎህ አደራ ብሎናል . . እያለችህ ነው::
- አመሰግናለሁ፣ለመናገር ቃላት ያጥሩኛል፣ለምን ከኛ ጋር አትሆንም . . እንብላ እንጂ::
- እናቴ የመጣችው እንኳን ደህና መጣህ ለማለትና አንተ ክብር እንግዳችን በመሆንህ ሁላችንም ልንታዘዝህ ዝጉጁ መሆናችንን ለማረጋገጥ ብቻ ነው::
- መስተንግዶአችሁና አቀባበላችሁ በጣም ከብዶኛል፤ይቅርታ አድርግልኝና ከኛ ጋር ለምን አልተቀመጠችም? ለምንስ አልጨበጠችኝም?
- እኛ ዘንድ ሴቶች የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከወንዶች ጋር አይቀመጡም:: በጋብቻ የማይገናኙ የቅርብ ዘመዶች ካልሆኑ በስተቀርም ወንዶችን አይጨብጡም::
- እንደነገርኩህ ዛሬ ለቃለ መጠይቁ አምስት ሴቶችን ያነጋገርኩ ሲሆን አራቱ ጨብጠውኛል፣አንደኛዋ ብቻ ልትጨብጠኝ ባለመፈለጓ በጣም ነው የተገረምኩት፤ሁሉም ግን አብሮኝ ቁጭ ብለዋል::
- ያልጨበጠችህ ምን ነበር ያለችህ?
- ወንዶችን እንደማትጨብጥ ገልጻ ይቅርታ ጠየቀችኝ::

- ያንተ አስያየትስ ምንድነው?
- ፍላጎቷን አከበርኩላት፣በተለይ ደግሞ ሁለቱ በአጨባበጣቸውም ሆነ በዓየኖቻቸውና በአካላዊ እንቅስቃሴአቸው ከጨዋ ስነ ምግባር ወጣ ያሉ ነበሩ።
- ወደ እንግሊዝ አገር ስሄድ ንግስቲቱን መጨበጥ ይፈቀድልኛል?
- ከዚህ ጋር ምን አገናኘው? በእርግጥ ንግስቲቱን ለመጨበጥ ሕጉ የሚፈቅድላቸው ለሰባት መደቦች ብቻ ነው።
- በኛ ሃይማኖት ውስጥ ሴት ልጅ የተከበረች ንግስት ናት ብየህ የለ?! እናም በትክክል ተለይተው ከተቀመጡ አስር መደቦች ውጭ ሌላ ወንድ እንዲጨብጣት እስላም አይፈቅድም። እነሱም አባት፣አያት፣ባል፣የባል አባት፣ልጅ፣ወንድም፣አጎት፣የወንድም ልጅና የእህት ልጅ ናቸው። እናንተ ንግስቲቱን ለማላቅና ለማክበር እንደምትከለክሉት ሁሉ እኛም ንግስታችንን ለማክበርና ከማይገቡ ነገሮች ልንጠብቃት ስንል እንከለክላለን።
- እህህ፣ የተከበረችና የታፈረች ንግስት! ታድያ ሴቶቹ ለምን ጨበጡኝ?
- ያሳዝናል፣ብዙ ሙስሊሞች በሃይማኖታቸው ጉዳ ላይ ችላ ባዮች ናቸው፤ሃይማኖቱ ግን ከነሱ ነጻ ነው።
- አሁን ገና ገባኝ፣ኣደም አንድም ጊዜ ካትሪናን ጨብጧት አያውቅም! ሴት በእስላም ውስጥ ስለምትይዘው ቦታ ብንወያይ ይከፋሃል?
- ስለ ንግስት ስትናገር እንዴት ይከፋዋል ብለህ ትጠብቃለህ?!
- እንግዳውስ ቀጥተኛ ጥያቄ ልጠይቅህ። የውርስ ድርሻዋን የወንድ ውርስ ድርሻ ግማሽ እየሰጣችኋት ንግስት ናት ትላላችሁ፤ንግስት ማድረጉን ትታችሁ ከወንድ ጋር እኩል አድርጓት።
- ለምትቀጥራቸው ሰራተኞች ሁሉ እኩል ደሞዝ ትከፍላቸዋለህ?
- ከርእሱ ለመውጣት የፈለክ ትመስላለህ!
- ፈጽሞ አልወጣሁም፣በርእሱ አንኳር ነጥብ ላይ እየተናገርኩ ነው።
- በእርግጥ እኩል አልከፍልም፣ለሥራ አስኪያጁና ለተላላከው እኩል ይከፈላል ብለህ ትጠብቃለህ?
- ለተላላኪው ከሥራ አስኪያጁ ያነሰ ስትከፍል ተላላኪውን በድለሃል ማለት ነው?
- አልበደልኩም፣ሁለቱንም በፍትሐዊ መንገድ ነው የማስተናግደው።
- እስላም በሴቶችና በወንዶች እንዲሁም በመላው የሰው ልጅ መካከል ፍትህን ለማስፈን ነው የመጣው እንጂ ሁሉንም በሁሉም ነገር እኩል

ለማድረግ አይደለም። ለዚህ ነው ሴት በውርስ ድርሻ የወንድ ግማሽ ስታገኝ የምናየው። በተቃራኒው ደግሞ ሴቷን ከቀለብና ከሁሉም ወጪዎች ነጻ አድርጎ ኃላፊነቱን በወንዱ ላይ ይጥላል . . ይህም የፍትሀዊነት የተሟላ መገለጫ ነው።
- ለምን . . ባለቤትህ የቤታችሁን ግማሽ ወጭ አታዋጣም?
- የቤት ወጭ ሙሉ በሙሉ የወንዱ ግዴታና ኃላፊነት ነው። ንግሥቲቱ ከነክብሯ እያዘዘች ነው የምትኖረው።
- ይቅርታ አድርግልኝማ . . ይህ ሴቲቱ እንዳትማር ወይም እንዳትሰራ አያደርጋትም?
- ማነው ያለው?! ልክ እንደ ወንዱ ሁሉ መማር ይኖርባታል፤አስፈላጊ ከሆነ መሥራትም መብቷ ነው . .
- የምታገኘው ደሞዝስ?
- የግል ንብረቷ ነው፣የቤት ወጭ ግዴታ የለባትም።
- እህህ፣እናም ከኢኮኖሚ አንጻር ከወንዶች ይልቅ ሴቶች አትራፊ ናቸው ማለት ነው።
- ከወንዶች በላይ በበለጠ ሳይሆን በፍትሐዊነት ነው፤ስነ ህይወታዊ ተፈጥሮዋ ከወንዱ እንደሚለይ ሁሉ፣የሚመለከቷት ድንጋጌዎችም በዚያው ልክ እንደ ባህሪዋና እንደ ሥራዋ ይለያያሉ።
- ስለ ፍትሐዊነት ውብ አገላለጽ ነው። በሌላ በኩል ግን ሕጃብ የተጣለባት ማህበራዊ በደል አይመስልህም?!
- መከበሪያና መታፈሪያዋ ነው እንጂ።
- በነዚህ ጨርቆች ተጠቅልላ ውበቷንና ሴትነቷን ስትሸፋፍን እንዴት ሆኖ?!
- ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት እናንተ ዘንድ የንግሥቶችና የልዕልቶች አለባበስ እንዴት ነበር?!
- ምን ለማለት ነው?!
- ጥያቄዬን መልስልኝ።
- ከነሙሉ መብታቸው ይኖሩ ነበር።
- አለባበሳቸው እንዴት ነበር?
- ዛሬ ሙስሊም ሴቶች የሚለብሱትን ዓይነት ልብሶች ይለብሱ ነበር ማለትህ ነው?
- ያለ ምንም ጥርጥር አዎ፤በተጨማሪም ይህ የደናግልት ልብስ አይደለምን?
- ይሁንና እኛ ስናድግና ስንሻሻል የሴቶቻችን አለባበስም አብሮ ሊሻሻልና

www.path-2-happiness.com

ሊለወጥ ችሏል::

-በመጀመሪያ የቤተክርስቲያን ሁኔታቸው - ለአባባሌ ይቅርታ- እየወረደ መጣ እንጂ እድገትና መሻሻል አላሳየም:: አለባበሳቸው ግን አልተለወጠም፤የሴቶች አለባበስም እንዲሁ - አሁንም ይቅርታ - እየወረደና እየዘቀጠ መጣ እንጂ እድገት ወይም መሻሻል አላሳየም:: የጾታዊ ትንኮሳ፣የዝሙት የውርጃና የሌሎችንም መዓቶች አኃዛዊ መረጃዎች አንብብ::

-እናንተ ዘንድም ያው ነው::

-ሰዎች ነንና እኛም እንሳሳታለን:: ግን እኛ ዘንድ ያለው ከናንተው ጋር ሲነጻጸር የውቅያኖስ ጠብታ ያህል ነው:: እሱም ቢሆን - አዝናለሁ - እናንተን ለመቅዳት ከናንተ የሚወሰድ ነው::

-እንዴት?

-አኃዛዊ መረጃዎችንና ጥናታዊ ዘገባዎችን ስለምወዳቸውና ስለሚያስደስቱኝ እንድጠቀማቸው ትፈቅድልኛለህ?

-አኃዛዊ መረጃ በጣም የተመጠነ ቋንቋ በመሆኑ ለኔ አሳማኝ ነውና መቀጠል ትችላለህ::

-ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአውሮፓና በአሜሪካ ካላገቡት ሴቶች መካከል 90% የሚሆኑት ዝሙትን ልቅ በሆነ ሁኔታ ወይም በየጊዜው ይፈጽማሉ:: በአሜሪካ ከጋብቻ ውጭ የሚያረግዙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወደ 48% ይደርሳል:: የአሜሪካ ኦፊሴላዊ ጥናቶችና የናሙና ዳሰሳዎች እንደሚያመለክቱት ከአጠቃላዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል 87.8% በሕይወታቸው ውስጥ ወሲብ ፈጽመው ያውቃሉ:: ከነዚህ መካከል 22% የሚሆኑት አስራ ሦስት ዓመት ሳይሞላቸው ወሲብ ፈጽሟል:: በስዊድን ደግሞ አዲስ ከሚወለዱ ሕጻናት መካከል 60% የሚሆኑት ያለ ምንም ትዳራዊ ትስስር ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ናቸው::

-ይበቃል . . የምዕራባዊውን ሕብረተሰባችንን ችግሮች ይህን ብቻ ሳይሆን የዚህን እጥፍ ድርብ አውቃለሁ:: ይሁን እንጂ ይህ በመላው ዓለም የተንሰራፋ ችግር ነው፤እናንተም ብትሆኑ እንደኛው አይደላችሁም?

-እያዘንኩ ቅድም እንደነገርኩህ ከኛም እናንተን በመከተል ብዙዎች በዚህ መንገድ እየተጓዙ ነው:: የሰው ልጅ ከሃይማኖት በራቀ ቁጥር እንዲህ ላለው ችግር ቅርብ ይሆናል፣ይሁን እንጂ በመካከላችን ያለው የቁጥር ልዩነት እጅግ በጣም ብዙ ነው::

-የናንተ የሃይማኖት መሪዎች እንደ ጳጳሳትና ደናግልት ይመነኩሳሉ አያገቡም ልትለኝ ትፈልጋለህ?

-ደጋግሜ ነግሬሃለሁ የሃይማኖት መሪና ካህን የሚባል ነገር በእስላም ሃይማኖት ውስጥ የለም:: ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] እንኳ አግብተዋል::

-ልክ ነህ ነብያችሁ ማግባቱን አንብቤ ተገርሜያለሁ! ይቅርታ፣ታድያ ባለቤትህ ዬት ናት? ባለትዳር ነህ አደለም?!

-ትምህርት ቤት ናት፤የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፊዚክስ መምህርት ናት:: የሥራ ሰዓቷ ከስድስት እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ነው፣ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልትመጣ ትችላለች::

-እውነቱን ንገረኝና ሕጃብ እንድትለብስ አስገድደሃታል?!

-ስለ እውነት ፈጽሞ አላስገደድኩም::

-ታድያ የሌሎችን ሴቶች ሕጃብ እንዲለበሱ ስታስገድዱ ሴቶቻችሁን ሕጃብ እንዲለብሱ ለምን አታስገድዱም? ሃይማኖትን ለግለሰባዊ ጉዳዮች መጠቀም እንዴት አስጠሊ ነው!

-ራሷ በገዛ ምርጫዋ ሕጃብ ለባሽ በመሆኗ እኔ አላስገደድኳትም:: ሃይማኖትን በግለሰባዊ ጉዳዮች ላይ በተሳሳተ መንገድ መጠቀምን በተመለከተ ካንተ ጋር እስማማለሁ ብቻ ሳይሆን ነብዩም [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ይህን ከልክለዋል::

-አንተ ሳታስገድዳት በገዛ ፍላጎቷ ሕጃብ ትለብሳለች ነው የምትለኝ?

-በትክክል::

-ሕጃብ እንድትለብስ የሚያደርጋት ምንድነው?

-ሃይማኖቷና የፈጣሪዋ ትእዛዝ፤ከዚያም ራሷን ለመጠበቅ::

-ከምንድነው ራሷን የምትጠብቀው?

-ቅድም የጠቃቀስናቸው አኃዛዊ መረጃዎች ሰለባ ከመሆን! እህህ፣ተጨማሪ አኃዛዊ መረጃዎችንና ቁጥሮችን መስማት ካሻህ ብዙ አሉኝ::

-የለም . . ይበቁኛል እኔ ዘንድም በጣም ብዙ ይኖራሉ:: ይቅርታ አድርግልኝና እንግሊዝ አገር ስለ ግብጻውያት ዘፋኞችና ተወዛዋዦች ብዙ እንሰማለን!!

-ልክ ነህ . . አዝናለሁ ከሃይማኖት እየራቅን በሄድን ቁጥር እናንተን እየቀዳንና እየተከተልን እንሄዳለን ብየሃለሁ::

-ማዘነህ ለምንድነው?

-ይቅርታ . . እናንተን ማስከፋት መፈለጌ አይደለም፤እናንተ ዘንድ ያለው

www.path-2-happiness.com

የሴቶች ሁኔታ የደረሰበት የዝቅጠት ደረጃ ብዙዎቹ አስተዋይ ሰዎቻችሁን ጭምር ያሳሰበና ሕብረተሰቡ እየተጓዘበት ያለውን አደገኛ አቅጣጫ ቆም ብሎ ማጤን አስፈላጊ መሆኑን ጮኽ ብለው እንዲናገሩ እያደረገ ነው።

- አደገኛ አካሄዶች ብዙ ናቸው፤የትኛውን አደጋ ማለትህ ነው?!
- አንድ ሰው የሚፈልገውን ሁሉ ከጋብቻ ውጭ በቀላሉ የሚያገኝ ከሆነ ትዳር ለምን ይፈልጋል? ይህ ደግሞ ቤተሰባዊ ስርዓትን የሚነድና ወድቅ የሚያደርግ በመሆኑ የትኛውንም የዓለም ጠንካራ ሕብረተሰብ የሚያንኮታኩትና ከነአካቴው የሚያጠፋ አደጋ ነው።
- በይበልጥ አብራራው።
- በጣም ግልጽ ለመሆን በብዙዎቹ ምዕራባውያን ዘንድ አንድን ውሻ ተንከባክቦ ማሳደግ አንድን ልጅ ወልዶ ከማሳደግ ተመራጭ አይደለምን?! ሴት ጓደኛ ከሕጋዊ ሚስት ይልቅ ወጭዋ አነስተኛ፣በየጊዜው ለመቀያየርና በየዓይነቱ ለማማረጥም የቀለለ አይደለምን?!
- ይህ እንኳ የተዛባ ተፈጥሮ ባላቸው ዘንድ ብቻ ነው።
- እውነት ብለሃል፣ይህ አንዳንድ ሕብረተሰቦች የደረሱበት ሁኔታ ነው። በአንዳንድ ሕብረተሰቦች ውስጥ ልጅ የመውለድ ሁኔታ በያንዳንዷ ሴት ከአንድ ሕጻን ያነሰ መሆኑን ታውቅ የለም? እነዚህ ሕብረተሰቦች ቶሎም ሆነ ዘግይተው ከስመው መጥፋታቸው አይቀሬ ነው።
- እህህ፣ ለዚህ ነዋ ከአውሮፓም ጭምር በቁጥር የበላይ የሆናችሁት።
- ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ‹‹አፍቃሪና ወላድ የሆኑትን አግቡ›› ይላሉ።
- በዚህ ዓይነቱ ዝርዝር ጉዳይ እንኳ ሳይቀር እስላም ጣልቃ ይገባል!
- እስላም እያንዳንዷን የሕይወት ዝርዝር ጉዳይ የሚያካትት አጠቃላይና የተሟላ የሕይወት መመሪያ ሃይማኖት ነው። ለዚህ ነው በእስላም ውስጥ ሕይወት ሚዘናዊ፣ነፍስን የሚያረካና አንዱ ጎን በሌላው ላይ ድንበር አልፎ የማያውክ አነዋነዋር የሆነው።
- የእስላም ዝርዝር ጉዳዮች አቤት ብዛታቸው! ለመሆኑ ይህ ድክመት እንጂ ጠንካራ ጎኑ ይመስለሃል?!
- እንዴት?!
- እነዚህን ረዥም ዝርዝሮች ተከታትሎ መፈጸም ለሰው ልጅ አድካሚ ነው። በሕይወት ላይ የተጣሉ ተጨማሪ ገደቦች ናቸው!
- እንደ እንግሊዝ ያለ ሕግ ያለበት አገር ወይስ ሕግ የሌለበትና ሥርዓተ

አልበኝነት የነገሰበት አገር ይሻላል?

- ማለት የፈለከው ገብቶኛል፤ይሁን እንጂ ጥሩ ሕግ ነው ለፈጠራና ለጥረት ሰፊ ቦታ የሚሰጠው።
- በትክክል እስላምን እየገለጽክ ነው! ለፈጠራ ለምናብና ለእሳቤ በጣም ሰፊ የሆ አድማስ ከፍቶልናል። ለዚህም ነው ቁርኣን ውስጥ አድማሳትን፣ታሪክን፣ተፈጥሮንና ሌሎችንም እንድንመረምርና አዝንድናስተነትን የሚጠይቁ አንቀጾችን የምናገኘው።
- ሰዎች ከተመራመሩና ካስተነተኑ የሃይማኖታችሁን ድክመት እንዳያውቁ አትፈሩም?
- ይህ ሊሆን የሚችለው በምድራዊ ሰው ሰራሽ ሃይማኖቶችና በተዛቡና ተአማኒነታቸውን በከሰመ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ዘንድ ብቻ የሚከሰት ነው። ሙስሊሞች ግን በተመራመሩና ባስተነተኑ ቁጥር እምነታቸው እርግጠኝነታቸውና ሃይማኖተኝነታቸው ይበልጥ እየጨመረ ይሄዳል። የሚያሳዝነው ግን መመራመርና ማስተንተን ባነሰ ቁጥር ሃይማኖኝነት የሚቀንስ መሆኑ ነው።
- በሃይማኖታችሁ ላይ ያላችሁ መተማመን አድናቆቴን ይስባል።
- አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እችላለሁ?
- ጠይቅ።
- እንዳትሰልም የሚያደርግህ ምንድነው?! እስላምን አሳማኝ ሆኖ አግኝተሃል የሚል ስሜት አለኝ!

ጆርጅ በጀማል ጥያቄ ትንሽ ተደናበረ . . ጣቶቹን በኃይል ጨበጥ አደረጋቸው . . ኣደም ስለ ካትሪና ማልቀስ ያሰፈረውና እርሱ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ሕሊናዊ ድፍረት እንደሚያስፈልገው የጻፈው ትዝ አለው። ጃኖለልካ በመጨረሻ ኢሜይሉ የጻፈለትንም አስታወሰ። በጥልቀት ወደራሱ ውስጣዊ ስሜት ተመለከተ . . እራሱ ለወዳጆቹ የላከላቸው ጥያቄም ይህ ራሱ መሆኑን አስታውሶ መልሱ ለምን እንደሚያስፈራው ራሱን ጠየቀ . . ድክመት ነው ወይስ ማመንታት? አለማወቅ ነው ወይስ አለመቸኮል?! ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ለጀማል መልስ ከመስጠቱ በፊት ለገዛ ራሱ መልስ መስጠት የግድ ነው . . ወደ ጀማል ፊቱን አዞረና . .

- አሁን መልስ እንዳልሰጥህ ትፈቅድልኛለህ?
- ውሳነው የራስህ ነው፣ይህን ያልኩህ መልካሙን ሁሉ ስለምወድልህ ብቻ ነው።

www.path-2-happiness.com

-አመሰግናለሁ . . በሁለት ወይም ሦስት ቀናት ውስጥ መልስ እሰጠሃለሁ::
-ለኔ መልስ መስጠት ብዙም አስፈላጊ አይደለም፣ዋናው ነገር ለገዛ ነፍስህና ለራስህ የሕሊና ጥሪ ምላሽ መስጠት ነው:: የሚያሳዝነው ቁሳዊው ሕይወት ወደ ቁሳዊ እቃነት ስለቀየረን ካሰብክና ካስተነተንክ ትደክማለህ፤ለዚህ ነው የሰው ልጅ ከመታደል ርቆ የሚኖረው::

‹‹ለገዛ ነፍስህና ለራስህ የሕሊና ጥሪ ምላሽ መስጠት . . ›› የሚለውን ሲሰማ ጆርጅ ተመቻችቶ ተቀመጠ፤መጀመሪያ ላይ አግኝቶት የነበረውን ሽማግሌ ቃል አስታወሰና እንዲህ አለው፦

-በትክክል እኔን እየገለጽከኝ ነው::
-ይቅርታ እንድትከፋ ፍላጎት ኖሮኝ አይደለም፣ይህ ግን ከአላህ በሚያፈነግጡበት ጊዜ የመላው የሰው ልጆች ባህሪ ነው:: ኃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል ፦ ‹‹ከግሣጼም የዞረ ሰው፣ለርሱ ጠባብ ኑሮ አለለው፤በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን::›› [ጣሃ:124] በተጨማሪም እንዲህ ብሏል ፦ ‹‹አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለእስላም ይከፍትለታል፤ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ቸጋሪ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል:: . . ››[አል አንዓም:125]
-የምትለው ነገር በጣም ከባድና ጭካኔ ነው!
-ይቅርታ . . ማክበድና መጨከን ፈልጌ ሳይሆን እውነታውን ብቻ መግለጼ ነው:: ከአላህ ከመዞርና ከማዘንበል የበለጠ ጭካኔ የለም:: ይቅርታ አሁን ብቻ ማለቴ ሳይሆን ሕይወትህን በሙሉ ማለቴ ነው!
-ምን ማለትህ ነው?
-ሰዎች በተለያዩ መንገዶችና ስልቶች ከራሳቸው ይሸሻሉ፤በጭፈራና በመጠጥ ከራሱ የሚሸሽግ አለ:: ከፊል የመንፈስ ረሀባቸውን በሚያስታግስ ሃይማኖታዊ ፋሽን ብቻ የሚረኩ ሰዎችም ይኖራሉ:: በደረቅ ፍልስፍና ውስጥ ራሳቸውን የሚደብቁም ይገኛሉ:: ተጨባጩን እውነታ መጋፈጥ ተስኗቸው ወዳልታወቀ አቅጣጫ ከራሳቸው የሚሸሹም አሉ:: ደግሜ ከልብ በመነጨ ፍቅር እለሃለሁ፦ ከዛሬው ሕይወትና ከነገው ዘላለማዊ ሕይወት መታደል የሚከለክልህ ነገር ምንድነው?
-በሁለት ወይም ሦስት ቀናት ውስጥ መልስ እሰጠሃለሁ ብየሃለሁ::

በመወያየት ላይ እያሉ የሚከፈት በር ድምጽ ሰሙ፤ጀማል ጆርጅን ይቅርታ ጠየቀ . .

-አንዴ ይቅርታ፣ባለቤቴ ዓእሻ መጥታለች::

-ከርሷም ጋር ጥቂት ብንነጋገር ትፈቅዳለህ?
-መጀመሪያ ላማክራትና ሀሳቧን ልስማ::
-ስለምን?
-ከወንዶች ጋር መነጋገር እንደማትወድ ስለማውቅ፣በማትፈልገው ነገር ለማስገደድ አልፈልግም፣አንዴ ይቅርታ::

ጆርጅን በመደመም ሁኔታ ውስጥ ትቶት ጀማል ክፍሉን ለቆ ወጣ:: ዛሬ የሆነው ነገር በጽኑ አንቀጥቅጦታል፤ምን እንደሚያደርግ የማያውቅ ሆኖ ብኩንነት ተሰምቶታል . . ወደ ግብጽ ምን አመጣኝ? ብሎ ቀኑን ሙሉ ራሱን ሲጠይቅ ውሏል:: የራሴ ታላላቅ ጥያቄዎች እንኳ እንቅልፍ ይንሱኝ! ምንድነው የምፈልገው? ለምንድነው የምኖረው? ይህ ሁሉ ድካም ስለምን? . . ወየው ጉዴ . .

በራሱ ጥያቄዎች ማእበል በመናጥ ላይ እያለ ጀማል ከባለቤቱ ጋር መጣ:: ቀና ብሎ ሲመለከታት ሕጻብ ለብሳለች፣ከፊቷ ተገልጦ የሚታየው በጣም አነስተኛው ክፍል ብቻ ነው . .

-ይኸውልህ ባለቤቴ እሷ ነች፤ምን መጠየቅ ትፈልጋለህ?
-መስለም እንደምትፈልግና ሴቶች በእስላም ውስጥ ስላላቸው ቦታ ጥያቄዎች እንዳሉህ ጀማል ነግሮኛል::
-ሴቶች በእስላም ውስጥ ስላላቸው ቦታ የማወቅ ፍላጎት ቢኖረኝም ፈጽሞ መስለም እፈልጋለሁ አላልኩም::
-መስለም የማትፈልግ ከሆነ ሴቶች በእስላም ውስጥ ስላላቸው ቦታ ለማወቅ ለምን ትፈልጋለህ?!
-እንዳው ለማወቅ ፈልጌ ነው::
-ሰውን የማይጠቅም ዕውቀት ዋጋ የለውም፤ባለቤቱን ከፍ የማያደርግ ዕውቀት ከንቱ ነው:: ዕውቀት ወደ አላህ ፍራቻ ይወስዳል:: ለዚህ ነው ኃያሉ አላህ እንዲህ ያለው ፦ ‹‹ . . አላህን ከባሮቹ ውስጥ የሚፈሩት ዐዋቂዎቹ ብቻ ናቸው፤›› [ፋጢር:28]
-ፍላጎቴ ማወቅ ብቻ ነው ማለቴ ነው፤ጥሬ ዕውቀት እናንተ ዘንድ ነውርና ስህተት ነው እንዴ?!
-እኛ ዘንድ ለተግባር የማይበቃ ባዶ ዕውቀት ዋጋ ቢስ ነው:: ከንቱነት፣ዓለማ የለሽነትና ግብ አልባነት የአእምሮም የሃይማኖትም በሽታ ስለመሆኑ በሚገባ ታውቁታላችሁ ብዬ አምናለሁ::
-እኛ ዘንድ ስትዪ ምን ማለትሽ ነው?!

www.path-2-happiness.com

-እኛ ሙስሊሞች ዘንድ ማለቴ ነው፤ተወኝና ወደምትፈልገው እንግባ፤መስለም ብትፈልግ እንጂ ጥያቄ እንደላቀረብክ እርግጠኛ ነኝ።

-እንዴት እርግጠኛ ሆንሽ?!

-እንደማላስከፋህ ተስፋ አደርጋለሁ፤ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ ‹‹እነዚያ የካዱት (በትንሣኤ ቀን) ሙስሊሞች በኾኑ ኖሮ በብዛት ይመኛሉ።›› [አል ሒጅር፡2] የአላህን አንድነት የማያረጋግጥና ለርሱ ተመሪ የማይሆን ብልህ ሰው የቅዠት ዓይነቶች፣የተዛቡና ተአማኒነት የጎደላቸው ሃይማኖቶች አእምሮው ውስጥ እርስ በርስ የሚፋጩበት፣አእምሮው ግጭቶችን የሚያስተናግድ ሰው ብቻ ነሆን አለበት።

-ብልህ ስትዩ ምን ማለትሽ ነው?!

-ደካማ አስተሳሰብ ያለው ሰው በሕይወቱ ውስጥ የሚያጋጥሙ የሃይማኖት ተቃርኖችንና ግጭቶችን፣ውስጣዊ የህሊና ጥሪዎችንና ጥያቄዎችን ችላ ብሎ ራሱን ወደሚጠምድበት ተራ ጉዳዮች ዘሎ ማለፍ ይችላል። ነገር ግን . .

-ነገር ግን ምን?!

-ነገር ግን ብሩህ አእምሮ ያለህ ብልህ መሆንህን፣ጀማል የባስምን አስተውሎ የጠቀሰለትን ወንድሙን ዋቢ በማድረግ ነግሮኛል።

-አመሰግናለሁ . .

-‹‹ሴቶች በእስላም ውስጥ ያላቸውን ቦታ›› ወደሚመለከተው ርእሰ ጉዳያችን እንግባና ከየት እንድንጀምር ትፈልጋለህ?

-ከፈለግሽበት ጀምሪ፤አስፈላጊ ሲሆን እኔ ጥያቄ አቀርባለሁ።

-እስላም ሲመጣ ዐረቦች ጨቅላ ሴት ሕጻናትን ሴት ሆነው በመወለዳቸው ብቻ ገድለው ይቀብሯቸው ነበር።

-የከፋ ኋላ ቀርነትና የጭካኔ ሥራ ነው!

-ልክ ነህ፤ይህ አስከፊ ሁኔታ ግን ዐረቦች ብቻ በተለይ የሚወቀሱበት አይደለም። በምዕራቡ ዓለምም ፈላስፎች በአንድ ከፍተኛ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ጉባኤ ይቀመጡ ነበር! በሚገርም ሁኔታ የመነጋገሪያ አጀንዳቸው ‹የሴት ነፍስ እንደ ወንድ ነፍስ ነው? ያላት የሰው ልጅ ነፍስ ነው ወይስ የእንስሳት ዓይነት ነፍስ ነው?!›› የሚል ነበር። የደረሱበት ማጠቃለያም ሴት ሰው ናት፣ያላት ነፍስና መንፈስ ግን በብዙ ደረጃዎች ከወንድ ያነሰ ነው የሚል ነበር። በተጨማሪም አንድ እንደ እቃ ሊሸጣትና ሊለውጣት ይችል ነበር። በሮማውያን ዘንድ የመፍታት የወለደችውን

ልጅ የራሴ ነው ብሎ ያለመቀበል መብት የወንዱ ብቻ ነው። በግሪኮች ዘንድ ሴት ልጅ ፈጽሞ አትወርስም። በናንተ እንግሊዞች ዘንድም የሴት ልጅ እስከ ቅርቡ ዘመን ድረስ የራሷ ንብረት ባለቤት የመሆን መብት አልነበራትም።

-በጣም የሚያሳዝን ነው፣አስቀያሚ ታሪክ ነው!

-ሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች በመሰረቱ ለሴቶች ፍትህ ይዘው የመጡ ቢሆንም፣በሚያሳዝን ሁኔታ አይሁዳዊነት ይህን አዛብቶታል። የተዛባውና የተጣመመው መጽሐፋቸው በወሲባዊ ምናቦችና በሴቶች ላይ በሚፈጸም መራራ ግፍ የተሞላ ነው።

-በዚህ ጉዳይ ላይ ከሌቪ ብዙ ሰምቻለሁ፤እኔም ብዙ አንብቤአለሁ።

-ሌቪ ማናት?!

-በጣም ድንቅ የሆነች ጨዋ አይሁዳዊት ሴት ነች።

-በእስላም መታደልን መከበርንና መታፈርን እንዲታገኝ እመኝላታለሁ።

-አይመስለኝም፣ለማንኛውም ቀጥይ።

-የልቦች መክፈቻ ቁልፍ ያለው በአላህ እጅ ነው። እንቀጥልና ክርስትናም እንዲሁ በሴቶች ላይ ፍትሕ አዛብቷል፣በሚያሳዝን ሁኔታም ሴቶችን በሚያንቋሽሹ ምንባቦች የተሞላ ሆኗል።

-ጥሩ የሀሳብ ፍሰት ነው።

-ከዚህ በኋላ እስላም መጣና በየትኛውም ሃይማኖት ያላገኘችውን ክብርና ፍትሐዊ አያያዝ አጎናጸፋት። እስላም ሳይዛባና ሳይከለስ ሲተላለፍ በነበረበት ሁኔታ ያለና የሚኖር ብቸኛው ሃይማኖት ነው፤ለጥበቃውም ከኃያሉ አላህ ዋስትና ተስጥቶታል።

-እስላም ያልተዛባና ያልተበረዘ ስለ መሆኑ በሚገባ አውቃለሁ፤አንዳንድ ጥያቄዎች ቢኖሩኝም መጀመሪያ የራስሽን እንድትቋጭው እፈልጋለሁ።

-ሴት በእስላም ውስጥ ያገኘችውን ከበሬታ መቼም ቢሆን አግኝታ አታውቅም። አውሮፓ ከሙስሊሞች ጋር በነበራት ንክኪ ስለ ሴት ልጅ ከበሬታ አንዳንድ ነገሮችን፣ዕውቀትንና ፍትሕ ማስፈን ተምራለች። ይህ ሁሉ ግን ከተዛቡና ከተከለሱ መጽሐፎቻቸውና ከቤተክርስቲያን ትምህርቶች ጋር ስለ ተላተመባቸው በቤተክርስቲያን ላይ አመጹ። የሚያሳዝነው ሳይሰልሙ ቀሩና ለሴት ከበሬታ የሚሰጥ ሥርዓት ለማግኘት ሲፈትሹ ሰብአዊ አእምሯቸው ወደ ጾታ እኩልነት መራቸው።

-ታድያ ሰብአዊ አእምሮ ከሃይማኖቶች ደረጃ አልፎ መጥቋል ማለት ነዋ?!

www.path-2-happiness.com

-በእርግጥ ባህሪዋን ተፈጥሯንና ሚናዋን ለውጠው ከወንዱ ተፈጥሯዊ ባህሪና ሚና ጋር ማጣጣም አዳጋች ሆነባቸው:: በመሆኑም ከራሷ ተፈጥሯዊ ባህሪና ሚና ጋር የወንዱንም ሥራ እንድትሠራ ወሰኑባት! የሚገርመው ግን ከራሷ ሥራ ጋር የወንዶችን ሥራ የምትሠራው ወንዱ ከሚያገኘው ደሞዝ ግማሽ ወይም ሩቡ ብቻ እየተከፈላት መሆኑ ነው! ከተፈጥሯና ከሚናዋ ውጭ ተመጣጣኝ ባልሆነ ክፍያ በማትችለው ነገር ላይ በማሰመራት ብቻ አልተወሰኑም፤ወደ ርካሽ ሸቀጥነት ለውጧት ዋስትና ያላት የተከበረች ሕጋዊ ሚስት ከመሆን ጊዜያዊ የወሲብ መገልገያ ‹የፍቅር ጓደኛ› እንድትሆን ፈረዱባት:: የጾታ እኩልነትና የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ይህን አስከፊ ሁኔታ ለመለወጥ ዘመቻ አድርገው ብዙም አልተሳካላቸውም::

-የምትናገሪው ሁሉንም ምዕራብና ሁሉንም ሁኔታ አይወክልም::

-ልክ ነህ፣ግን ብዙዎቹን ይወክላል:: ወደዚህ የከፋ ደረጃ ገና ያልወረዱ ይኖራሉ:: አደጋው ግን በእኩልነት፣በነጻነትና ከወንዶች የበላይነት በመገላገል ስም የሴት ልጅ ወደ ከፋ ልቅነትና ዋልጌነት እየተገፋች፣ሰብእናዋ ተገፎ ወደ እንስሳነት ደረጃ እንዲትዘቅጥ እየተደረገ መሆኑ ነው::

-ምን እያልሽ ነው?!

-አነጋገሬ ትንሽ ሻካራ ሆኖ ወይም እናንተን የሚያንቋሽሽ አድርገህ ተረድተህ ከሆነ ይቅርታ:: ማለት የፈለኩት በእኩልነት ስም የሴት ልጅ የወንዶች መጫወቻ፣ማሳሳቻና ማባበያ አሻንጉሊት ወይም የንግድ መስታወቂያ ሆናለች:: ይህ ባይሆን የወሲብ ቲቪ ቻናሎችን፣ፊልሞችን፣መጽሔቶችንና ሕጋዊ የወሲብ ንግድን . . እንዴት ልንተረጉማቸው፣ምን ልንላቸው ነው?

-ለዚህ ውብ ፍጡር የሚቸር አንድ ዓይነት የአድናቆት መግለጫ ነው ማለት ይቻላል!

-እናም ከወንዶች የተለየ ውብ ፍጠር መሆመኗን አምነህ ተቀብለሃል፣ስለዚህም ከወንዱ ጋር አንድና እኩል ናቸው ማለቱ ለርሷም ለርሱም በደል ማለት ነው:: እኔ ግን በነዚህ ህብረተሰቦች ውስጥ የሚገኘው ወንድ ቁሳዊ መብቶቿን ከነጠቃት በኋላ፣ራሱን አሳርፎ የርሱንና የራሷንም ሥራ አጣምራ እንድትሠራ በማድረግ ሰብአዊ ክብሯን ገፎ ወደ ተራ የመደሰቻና የመዝናኛ ሸቀጥነት ለውጧታል ብዬ ነው የምተረጉመው:: አለዚያማ በብዙዎቹ አገሮች ውስጥ በመጽሔቶች የፊት ሽፋን ላይ ልክ የቤት እቃ ወይም መኪና ወይም ሌላ ማንኛውም የሸቀጥ ማስታወቂያ

እንደሚወጣው ሁሉ የሴት ልጅ እርቃነ ገላዋን ሆና መቅረቧ ምን ሊባል ይችላል?!

-በእርግጥ ይህ በጣም የሚያስከፋ ነገር ነው፣በትክክል ግን ማህበረሰባችንን አይወክልም::

-እነዚህ ነገሮች ቢያንስ ሕጋዊ ከለላ የሚሰጣቸውና በተቀነባበረ መንገድ የሚካሄዱ ሲሆኑ፣በሌላ በኩል ግን የሚፈልጉ ሰዎች ሕጃብ እንዳይለብሱና ገላቸውን እንዳይሸፍኑ በሕግና በተደራጀ መልክ ይከለከላሉ:: ሥርዓቱ ሌላዋን ሴት ለሽያጭና ለግብይት የምትቀርብ ሸቀጥ እንዲትሆን ሲፈቅድ ሙስሊሟ ሴት ግን ሕጃብ እንዲትለብስ ግን አይፈቅድም::

-በአንዳንድ የአውሮፓ አገሮች የሚፈጽሙ የመብት ጥሰቶችን አወግዛለሁ፣አልቀበልም::

-እንግዳውስ በናንተው መስፈርት መሰረት አንተ አሸባሪ ነህ ማለት ነው:: . . አበዛሁባችሁ ይቅርታ፤ባለቤቴ ባጠይቀኝና ለመስለምህ ምናልባት ምክንያት ብሆንስ ብዬ ባላስብ ኖሮ አልመጣም ነበር::

-አንዴ በፍጥነት፣ለሌሎች ያቀረብኳቸው ጥያቄዎች አሉኝ፣ምላሻቸውን ከሴት ማግኘት እፈልጋለሁ::

-እሽ፣ጠይቅ::

-አንቺ ከኛ ዘንድ ወደ እናንተ ከመጡና ለእድገታችሁ አጋዥ ከሆኑ ዋነኛ ዘመናዊ ዕውቀቶች አንዱ የሆነው የፊዚክስ ባለሙያ ነሽ:: ከዚሁ ጋር ሕጃብ ትለብሽያለሽና ለመልበስ ተገደሽ ነው?! ወይስ እኛ ዘንድ እንዳለው ዓይነት የደናግልት አለባበስ ራስን ለመጠበቅ ሳይሆን ባህላዊ አለባበስ በመሆኑ ነው?! ወይስ የምትኖሩበት ሕብረተሰብ ሥጋዊ ፍላጎቱ ጣርያ የነካ በመሆኑ ለጾታዊ ትንኮሳና ለመሳሰሉ ችግሮች ላለመጋለጥ የግድ መልበስ ስላለብሽ ነው የለበስሽው?!

-እህህ፣አንደኛ ነገር ዕውቀት የመላው የሰው ልጅ ውርስ ነው:: እንደ ዛሬ ከናንተ ዘንድ ዕውቀት ወደኛ ከመምጣቱ አስቀድሞ እናንተ በድቅድቅ የማይምነት ጨለማ ውስጥ በነበራችሁበት ዘመን የተለያዩ ዕውቀቶች ከኛ ዘንድ ወደ እናንተ መጥተዋል:: ጾታዊ ትንኮሳ በከፊል እርቃነ ገላ በመሄድና የተወጣጠሩና ገላን የሚያስነብቡ ወሲብ ቀስቃሽ አለባበሶች ጋር በቀጥታ ግንኙነት እዳለው ታውቃለህ:: ይህን የሚደግፉ አኃዛዊ መረጃዎችን ከፈለክ መነጋገር እንችላለን:: እኔን በሚመለከት ግን ሕጃብ የምለብሰው በሃይማኖታዊ ትእዛዝነቱና ለዛሬውም ሆነ ለወዳኛው ሕይወቴ

መታደል መሆኑን በማወቄ ነው:: ለዛሬ ሕይወቴ እርካታና እርጋታ ሲሆን ለወዳኛው ሕይወቴ ደግሞ የቸሩ አላህ ችሮታና ምህረቱን ማስገኛ ነው::

- ‹‹በዛሬው ሕይወትና በወዳኛው ሕይወት መታደል›› የሚለውን ሁሌ ትደጋግማላችሁ::
- ልክ ነህ . . በተግባር የሞከረው ሰው እንጂ ሌላው የማያውቀው መታደል በመሆኑ ነው::
- ሊሆን ይችላል፣ግን ደግሞ ግልጽ ሁኚና ነብያችሁ እንዳደረገው ሁሉ ጀማል በአንቺ ላይ ሌላ ሚስት ቢያገባ ደስተኛ ትሆኛለሽ?!

ዓእሻ ከጎኗ በዝምታ ወደ ቆመው ጀማል ተመለከተችና ቀጠለች . .

- ጀማል ይህን ያደርጋል ብዬ አላስብም፣በኔ ላይ ባያገባ ምኞቴ ነው::
- ነብያችሁ ግን ብዙ ሚስቶች አግብቷል!
- ልክ ነህ፣ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ብዙ አግብተዋል፣ከእመ ምእመናን ሚስቶቻቸው መካከል አንደኛዋ ስማቸው እንደኔው ዓእሻ ነው::
- ታድያ ጀማል የነብዩን አርአያ በመከተል በአንቺ ላይ እንዲያገባ የማትፈልጊው ለምንድነው?!
- እስላም ሴት እንዳልሆን አልጠየቀኝም፣መቅናት መብቴ ነው:: እስላም ፍላጎቴንና የምወደውን ነገር መግለጽ የማልችል ደካማ እንድሆንም አልጠየቀኝም:: ከአንድ በላይ ማግባት ቅምጥ ፍቅረኞችን ከመያዝ የተሻለ መሆኑን ግን በእርግጠኝነት አውቃለሁ::
- በጥቅሉ ሲታይ ግን ከሁሉም ተመራጩ ከአንድ በላይ አለማግባቱ ነው . .
- ከአንድ በላይ ማግባት በአንዳንድ ወንዶች ተፈጥሮ ምክንያት የሰው ልጆች ባህሪ አንዱ ገጽታ ነው የሚል እምነት አለኝ:: በመሆኑም ከአንድ በላይ ማግባት በእስላም ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኝ ነው:: ልዩነቱ በቀደሙት ሃይማኖቶች ውስጥ በቁጥር ያልተገደበ ልቅ መሆኑ ሲሆን እንደምታውቀው ነብዩ ሱለይማን አንድ ሺ፣ኣደም አስራ ሦስት፣ነብዩ ዳውድ ስልሳ ዘጠኝ አግብተዋል:: እስላም ውስጥ ግን በአራት ብቻ የተገደበ ነው::
- በአሁኑ ዘመን ግን አንቀበለውም፣አብዛኞቹ ስርዓቶችም በሕግ ይከለክላሉ::
- መጽሐፍ ቅዱሳችሁ በዚህ የተሞላ ነው፤አንዳንዶቹ የናንተ ቀሳውስት ይህን ማብራራት ሲያቅታቸው አንዴ ይህ የሰው ልጆች ስህተት ነው

በማለት ነብዮቹን ይወቅሳሉ:: ሌሎቹ ደግሞ በአንድ የታሪክ ወቅት ላይ ጦርነቶች የበረቱ ስለነበር የሴቶች ቁጥር ከወንዶች የበዛ ስለነበረ ነው ይላሉ:: በዚህም ዛሬ ያለው የጦርነት ብዛትና ክፋት ከቀድሞው ዘመን የባሰ መሆኑን በመርሳት ከእውነታ ጋር ይጋጫሉ::

- ዋናው ነገር ከአንድ በላይ ማግባትን ለመከልከል ሲባል ሃይማኖታችንን፣ሥርዓቶቻችንን እና ሕጎቻችንን ያሻሻልናቸው መሆኑ ነው::
- ‹‹ሃይማኖታችንን አሻሽለናል›› መባሉ አስገራሚ ነው:: እውነተኛና የተሟላው ሃይማኖት መሻሻልም ሆነ ለውጥ የማይቀበል ለሁሉም ጊዜና ስፍራ ተስማሚና ተፈጻሚ የሚሆን ሃይማኖት ነው:: ለዚህ ነው ኃያሉ አላህ እስላምን አስመልክቶ እንዲህ ያለው፦ ‹‹ዛሬ ሃማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ:: ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ:: ለናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፤›› [አል ማኢዳህ:3] የተሟላና ማሻሻያ የማይቀበል ምሉእ በመሆኑ እኛ ሃይማኖታችንን አናሻሽልም::
- ጨቋኙን ከአንድ በላይ ማግባት ለመከልከል ስንል እኛ ግን አድርገነዋል::
- ልክ ነው፣በአብዛኞቹ የአውሮፓና የአሜሪካ አገሮች ከአንድ በላይ ማግባትን በግልጽና በይፋ የከለከላችሁ ሲሆን ቅምጥ ፍቅረኞችን በየዓይነቱ መያዝን ግን በግልጽና በይፋ ፈቅዳችኋል::
- ቁም ነገሩ ካንድ በላይ ማግባትን መከልከላችን ነው::
- የሰውን ልጅ ተፈጥሮና ማህበራዊ ሕይወት ከአንድ ሚስት በላይ ከሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ወንዶች ፍላጎት ጋር ለማጣጣም ስትሉ ብዙ የፍቅር ጓደኞችን መያዝ ፈቅዳችኋል:: ይበልጥ አስከፊው ደግሞ በአንዳንድ አገሮች ከብዙ ሚስቶች ይልቅ ብዙ ባሎችን ማግባት የሚፈቀድ መሆኑ ነው:: በቡድን ሆነው አንዲት ሴት ማግባትም ሲፈቀድ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ግን አይፈቀድም:: በመሆኑም ለአንዲት ሴት ባሏ በርካታ ቅምጥ ወዳጆችን ከሚይዝ ወይም በአስቀያሚው የቡድን ጋብቻ ላይ ከሚሳተፍ በሕጋዊ መንገድ ተጨማሪ ሚስት ማግባቱ ክብሯን ያስጠብቃል::
- መልካም፣የተማርሽውና በማስተማር ላይ ያለሽው ዘመናዊ ዕውቀት ግን ምናልባት ከሃይማኖታችሁ ትምህርቶች ጋር ብዙ ሊጋጭ ይችላል!
- ሳይንስ ከሃይማኖታችን ጋር ሊጋጭ! አንተ ሃይማኖታችንን አታውቅም ወይም ስለ ሳይንስ የምታውቀው ነገር የለም ማለት ነው:: ለማንኛውም

www.path-2-happiness.com

በሳይንስና በሃይማኖት መካከል ስላለው ግንኙነት ጀማል ከኔ ይበልጥ ያውቃል፤በሴቶች ጉዳይ ላይ እንዳናግርህ ነበር የጠየቀኝ፤ባልጠየቅ ኖሮና ሃይማኖትን ማገልገል ነው ብሎ በያሳምነኝ መናገር ፍላጎቴ አልነበረም:: መልካም ፈቃዳችሁ ከሆነ አሁን ልሂድና ልጄን ላስጠና::

ዓእሻ ወጥታ ሄደች . . በመደመም ስሜት ፈገግ እያለ ጆርጅ ፊቱን ወደ ጀማል አዞረ . .

-በባለቤትህ እንኳን ደስ አለህ እለሃለሁ፣ግና ወንድ እንጂ ሴት መሆን አይገባትም ነበር::

-እህህ::

-ምነው ምን አሳቀህ?!

-እንግዳውስ ወንድ እንደ ሴት አለመሆኑን ታረጋግጣለህ ማለት ነው:: ታድያ ለምንድነው ለጾታ እኩልነት ጥሪ የምታደርገው?! ከሚስት በላይ ለባል ታዛዥና ርህሩህ ማን አለና! ሃይማኖተኛ በመሆኗ ለባሏ ታዛዥ እንድትሆን ከነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] የተላለፈውን ትእዛዝ ታከብራለች::

-ዳግም ወደ ማበላለጡ ተመለስን፤ነብያችሁ አንተ ለርሷ ደግ እንድትሆን ለምን አላዘዘህም?

-በሚገባ አዘውናል፤[የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] እንዲህም ብለዋል፦ ‹‹በላጫችሁ ለቤተሰቡ ከሌላው ይበልጥ ጥሩ የሆነ ሰው ነው፣እኔ ከሁላችሁም ይበልጥ ለቤተሰቤ ጥሩ ነኝ::›› በውይይትህ በጣም ደስተኛ ነኝ፣አንዴ ሄጄ ዐስር እንድሰግድ ግን ፍቀድልኝ::

-አሁን አስር ሰዓት ተኩል ነው፤የሚመች ከሆነ አብረን እንውጣና አንተ እስክትሰግድ ድረስ እኔ ለአንድ ሰዓት ያህል ካይሮ ውስጥ ዞር ዞር እልና ከዚያ ወደ ሙስጠፋ ትወስደኛለህ፣ለምን እንደሆነ እንጃ ለእራት ቀጥሮኛል::

(4)

ጀማል ሰግዶ እስኪወጣ ድረስ ጆርጅ መኪና ውስጥ ቆየ፤ሶላቱ ካበቃ በኋላ ከመስጊድ የሚወጡ ሰዎችን ፊት ማስተዋል ያዘ፤አውሮፓዊ ገጽታ ያለው ሰው ተመለከተና ምልክት ሰጥቶት ሄዶ ሰላምታ አለው . . በተሰባበረ እንግሊዝኛ መለሰለት . .

-ሰላም፣ እኔ ዊልያም እባላለሁ፣ከየት አገር ነህ?

-ጆርጅ እባላለሁ፣ከእንግሊዝ ነኝ::

-እኔ ደግሞ ፒተር እባላለሁ፣ከጀርመን ነኝ::

-ከሙስሊሞቹ ጋር ስትሰግድ ነበር!

-ልክ ነህ ጀርመናዊ ሙስሊም ነኝ::

-ጀርመናዊ ወይስ ጀርመን የምትኖር ግብጻዊ?

-አውሮፓ ከሚገኙ ሙስሊሞች ግማሾቹ ነባር የአገሬው ሰዎች ሲሆኑ እኔም ከነርሱ አንዱ ነኝ:: በጀርመን የሙስሊሞች ቁጥር ከአራት ሚሊዮን የሚበልጥ ሲሆን ከሕዝቡ 5% ይሆናሉ::

-አውቃለሁ . . እኛ ዘንድ በአገረ እንግሊዝ ቁጥራቸው ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሲሆን ከጠቅላላው ሕዝብ 3% ይሆናሉ:: የኔ ጥያቄ ግን ክርስቲያን ነበርክ ወይ? ነው::

-አባቴና እናቴ ክርስቲያኖች ነበሩ፤እኔ ግን ኤቲስት ነበርኩ፤አላህ ይመስገን አሁን ሰልሜ መታደልን ተጎናጽፌያለሁ:: እዚህ የተገኘሁት እስላምን ለማጥናት ነው::

-ወደ እስላም እንድትገባ ያደረገህ ምንድነው?!

-ብዙ ጊዜ የሚቀርብልኝ ጥያቄ ነው:: ወደ እስላም የገፋፋኝን ነገር ጠቅለል ባለ መልኩ የሦስት ቃላት ፍለጋ ነው ማለት እችላለሁ፤እነሱም ፦ እውነታ፣መታደል እና ፍትሕ ናቸው::

-እስላም ውስጥ አገኘኻቸው?! እንዴትስ ማግኘት ቻልክ?

-አዎ አግኝቻለሁ፤ዝርዝሩን ማወቅ ከፈለክ በኋላ ብትጎበኘኝ ደስታዬ ነው፤አሁን ከአንድ ወዳጄ ጋር ቀጠሮ ሳለለብኝ ይቅርታ አድርግልኝ:: እንካ ይህ ሙሉ መረጃዬን የያዘ የአድራሻ ካርዴ ነው::

-አመሰግናለሁ፤በማስተጓጎሌ ይቅርታ::

ጆርጅ ወደ መኪናው ሲመለስ ጀማል እየጠበቀው ነበር . .

-መቼ ተመለስክ?

-ከሰውየው ጋር ስትነጋገር አይቸሃለሁ፣ላቋርጥ አልፈለኩም:: አሁን አስራ አንድ ተኩል ነው፣ለሙስጠፋ ቀጠሮ ምን ያህል ቀረህ?

-አንድ ሰዓት ያህል ይቀራል፤እውነቱን ለመናገር ግን በጣም ስለ ደከመኝ ወደ ሆቴል ሄጄ አረፍ ብል ደስ ባለኝ ነበር፤ዳሩ ግን በማላውቀው ምክንያት እንድገኝለት በጣም ጉጉ ስለነበር ቀጠሮ ሰጥቼዋለሁ፣ስለዚህም ማፍረስ አልፈልግም::

-መልካም ነው፤ቁርኣንና ነብዩም [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ

ይሁን] ቀጠሮ እንድናከብር አጥብቀው አሳስበዋል። ማን ያውቃል ለበጎ ነገር ሊሆን ይችላልና መሄድህ ተገቢ ነው። እስከዚያ ድረስ ግን በቀሪው አንድ ሰዓት ውስጥ በጀልባ አባይ ወንዝ ላይ ላንሸራሽርህ፣የቀጠሮህ ቦታም ለአባይ ቅርብ ነው።

-ድንቅ ሀሳብ ነው።

ወደ አባይ ወንዝ አመሩ፤ለአንድ ሰዓት ጀልባ ተከራዩና ለጆርጅ ትልቅ የእርካታና የእፎይታ ስሜት የሰጠ ረጋ ያለ አዝናኝና አስደሳች ሽርሽር አደረጉ። በጉዞው ላይ አእምሮው ውስጥ የሚጉላሉ የመረጃ ክምችቶች በድንገት እየተቀነባበሩ ፈርጅ ፈርጃቸውን ሲይዙ ተሰማው፤ከዚያም ወደ ሙስጠፋ ቀጠሮ ቦታ አቀኑ . .

-አመሰግናለሁ፣ወቅቱን የጠበቀ ድንቅ ጉዞ ነበር።

-እንሻአላህ ትንሽ እረፍት አግኝተሃል ብዬ አስባለሁ።

-ልክ ነህ፣ግን ትንሽ ዘና ባልኩ ቁጥር የትላልቆቹ ጥያቄዎቼ ጫና አሁንም እረፍት ይነሳኛል።

-የትኞቹ ጥያቄዎች?

-አንድ ጥያቄ እንድጠይቅህ ትፈቅድልኛለህ?

-ጠይቅ።

-ለምን ዓለማ ተፈጠርኩ ብለህ ራስህን ጠይቀህ ታውቃለህ?

-አዎ . . ብዙ ጊዜ እላለሁ . .

-ምን ብለህ ነው ለራስህ መልስ የምትሰጠው? ወይም ከጥያቄው እንዴት ነው የምትሸሸው?

-ቁልጭ ያለ ምላሽ እያለኝ ለምን እሸሻለሁ?!

-መልሱ ምንድነው?

-ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ ‹‹ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።›› [አል ዛሪያት:56]

-ለእግዚአብሔር ለመስገድና ለመጾም ብቻ ነው የተፈጠርኩት ልትለኝ ነው?!

-አይደለም . . በተሟላ አጠቃላይ ጽንሐሳቡና ግንዛቤው ለአምልኮት ነው የተፈጠርከው፤ጸሎትና ጾም ከአጠቃላዩ አምልኮ (ዕባዳ) አበይት ክፍሎች አንዱ አካል ብቻ ናቸው።

-እንዴት?

-አምልኮ የሕይወታችንን አጠቃላይ ፈርጆች ሁሉ የሚያካትት እንጂ በተለየ

ቀን ወይም ቦታ ወይም በተወሰነ እድሜ የሚገደብ አይደለም። ከዚህ አልፎ ነብያችን [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] አንድ ሰው ከባለቤቱ ጋር በመገናኘቱና በመደሰቱ እንኳ ከአላህ ምንዳ እንደሚያገኝ አስተምረውናል።

-እንዴት?

-ነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ይህን እንዲህ ሲሉ ነው ያብራሩት ፦ ‹‹ባልተፈቀደለት ሐራም ሁኔታ (በዝሙት) ፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ኃጢያት ይሆንበት አልነበረምን? እንደዚያው ሁሉ በሐላል በመፈጸሙ ምንዳ ያገኝበታል።›› በዚህ ሁኔታም ቅን ልቦና እና ፍላጎት እስካለ ድረስ ሕይወት በጥቅሉ አምልኮ (ዕባዳ) ነው። ጸሎት አምልኮ፣መኖርና መሞትንም ጨምሮ ሁሉም የአላህ ነው። ኃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል ፦ ‹‹ስግደቴ መገዛቴም፣ሕይወቴም፣ሞቴም፣ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል።›› [አል አንዓም:162]

-ለምንድነው የምትኖረው ?

-ያለፈውን ምላሽ ብሰጥህ እውነተኛ ነኝ። ምድርን ለማልማትና ለሰው ልጅ አገልግሎት ለመግራት፣ለሕይወት ምቹ ለማድረግ ብልህም አውነተኛ ነኝ። እውነቱን ለመናገር ምድርን ማልማት፣መኖርና ተፈጥሮን ለሰው ልጅ ኑሮ ምቹ አድርጎ መግራት ከአበይተ አምልኮዎች አንዱ ነው። ኃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል ፦ ‹‹ . . እርሱም ከምድር ፈጠራችሁ፤በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፤ . . ›› [ሁድ:61]

-አዝናለሁ ደረስን መሰለኝ . . ውይይታችንን ነገ እንቀጥላለን፤ጧት አራት ሰዓት ላይ እጠብቀሃለሁ። ከመጨረሻው ኩባንያ ጋር ቀጠሮዬ አምስት ሰዓት ነው፣እስከዚያ ማረፍ እፈልጋለሁ።

-ተስማምተናል።

ጆርጅ ሙስጠፋ ወዳለበት ገባ፣ሰላምታ ተለዋወጡ . .

-ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው፣እራቱ ከሆቴሎች አቅራቢያ በሚገኙ ሬስቶራንቶች በአንደኛው ይሆናል፤ሁሉም እዚያ እየጠበቁን ነው።

-መልካም . .

-የደከመህ ትመስላለህ . . የሚያዝናናህንና ንቃትህን የሚመልስልህን ሁሉ አዘጋጅተንልሃል። ያሳዝናል እኛ ግብጻውያን የአውሮፓ ወዳጆቻችን በሚጎበኙን ጊዜ የግብጻውያን አነዋነዋር ለአውሮፓውያኑ የማይመች መሆኑን እንረሳለን።

www.path-2-happiness.com

-እንዴት?

-እኔ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን የተከታተልኩት አሜሪካ ውስጥ ስለሆነ አነዋነዋራችሁን በሚገባ አውቃለሁ፤ዛሬ አስደሳች ነገር ታያለህ።

ሙስጠፋ መኪናውን አንዱ ሆቴል አጠገብ አቆመ፤ወርደው ትኩረት በሚስቡ ባለ ብዙ ቀለም መብራቶች ወደ አሸበረቀ አንድ የጎንዮሽ መግቢያ አመሩ። ቦታው በሙዚቃ ድምጽ ጫኸት የረበሸ በመሆኑ ሙስጠፋ እጁን በጆርጅ ትከሻ ላይ አድርጎ የሚነግረውን እንዲሰማ ወደ ጆሮው ቀረብ አለ . .

-ለኛ ብቻ እንዲበቃ ሆኖ በተለይ የተዘጋጀልን መድረክ አለን።

ወደ መድረኩ ደረሱ፤ጧት ቃለ መጠይቁ ላይ አግኝቷቸው ከነበሩ ሴቶች መካከል አራቱ እየጠበቁት ነበር . .

-ጧት የተዋወቅካቸው መሰለኝ፣አሁን ያመጣኋቸው በቅርበት ይበልጥ እንድትተዋወቃቸው ብዬ ነው . . ይህች ሰሚራ ናት፣ይህች መናል፣ይህች ዓእሻ ይህች ደግሞ ዳንያ ናት።

ሰሚራ ፈገግ ብላ እጇን ዘረጋች፣ጆርጅም ፈገግ ብሎ እጁን ዘርግቶ ጨበጣት፣የተቀሩትንም ጨበጣቸውና ተቀመጠ።

-ደግሜ ራሴን ላስተዋውቅ፣እኔ መናል ዐሊ ነኝ፣ዕድሜ ሃያ አራት፣አንተን ለማገልገል ነው የመጣሁት።

-መልካም . . ሁላችሁም መናል እንዳደረገችው ራሳችሁን ብታስተዋውቁ . .

-እኔ ሰሚራ ነዝሚ ነኝ፣ዕድሜዬ ሃያ ሦስት፣ላስደስትህ ነው እዚህ የተገኘሁት።

-እኔ ዓእሻ ኻሊድ ነኝ፣እድሜ ሃያ አምስት፣አንተን ብዬ መጥቻለሁ።

-እኔ ዳንያ ሳሚሕ ነኝ፣ ዕድሜ ሃያ አምስት።

-እንኳን ደህና መጣችሁ . . እኔ ጆርጅ ነኝ፣ዕድሜዬ ወደ አርባው እየተቃረበ ነው።

ሙስጠፋ ከመቀመጫው ብድግ አለ . .

ፍቀዱልኝ ከአጭር ጊዜ በኋላ እመለሳለሁ . . ጆርጅ በጊዜህ ተጠቀም፣ተደሰት።

-ግንኙነታችን ለኔ ያልተጠበቀ ዱብ እዳ ነው፣እዚህ እንደምንገናኝ አስቀድሜ አላወኩም ነበር።

-ለአንተ በገጸ በረከትነት እንደሚያቀርበን የነገረን ሙስጠፋ ነው።

-አልገባኝም።

-አንተ እዚህ ብቻህን ስለሆንክ አንተን ብለን ነው የመጣነው።

-አሃ . . ገባኝ፤ታድያ እስከምን ድረስ ነው እኔን ለማገልገልና ለማስደሰት የተዘጋጃችሁት?

-እህህ፣እስከ ጫፉ ድረስ።

-ያሻህን ነገር ጠይቅ፣የአገልግሎቱ ወሰን እስከምን እንደሆነ ለራስህ ታየዋለህ።

ጆርጅ የአራቱን ሴቶች ፊት እየተመለከተ ለአፍታ ዝም አለ። በእርግጥ ቆነጃጅት ናቸው፤ፈገግታቻው እስከ ማሳሳት ደረጃ ፈታኝ ነው . . ለርሱ ግን አስጠሊታዎችና ወራዶች ሆነው ነው የታዩት . . ዝምታውን ሰብሮ ሊያናግራቸው ወሰነ . .

-አንዳንዳንድ ነገሮችን ከናንተ እፈልጋለሁ፤በዓእሻ ልጀምር።

-ታዛዥህ ነኝ።

-ጥያቄ አለኝ፤ስምሽ ከነብያችሁ ሚስት ስም ጋር ተመሳሳይ አይደለም?

-አዎ፣ምነው ለምን ጠየቅህ?

-እናማ በምታድርጊያቸው ነገሮች ሁሉ የርሷን አርአያ ትከተያለሽ ማለት ነዋ?!

-ይህን ለምን ትጠይቃለህ? የምትፈልገውን ንገረኝ ፍላጎትህን አሟላለሁ።

-ፍላጎቴ መልስ እንድትሰጭኝ ነው . .

-ወደኔ ዙር . . እኔ ሰሚራ ክርስቲያን ነኝ፣ጓደኛዬን የሚያሸማቅቅ እንዲህ ያለ ጥያቄ ለምን ትጠይቃታለህ?

-ለርሷ እየተከላከልሽ ነው?!

-ጓደኛዬ ነችና አዎ፣የሚያሸማቅቅ ጥያቄህን ከርሷ መከላከል መብቴ ነው።

-አሁን ለርሷ ትከላከያለሽ፣ነገር ግን ኢየሱስ ከኃጢአቷ ስላላዳናት ገሀነም የምትገባ ከሃዲ (ካፊር) ናት ብለሽ ነው የምታምኚው!

-እኔ ክርስቲያን ነኝ፣ይሁን እንጂ ሴኩላሪስት ነኝ፣ለእውቀትና ለውጤቶቹ እንጅ ለሌላው ብዙ ትኩረት አልሰጥም።

-እንደምትዪው እውቀትን የምትወጂ ከሆንሽ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ቀርቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትሽን እንኳ አላጠናቀቅሽም፤የብቃትሽ መለኪያ ውበትሽ ብቻ ነው!

-ይህን ውበት ቀምሰህ ማየት ትፈልጋለህ? ልትደሰትበት ልትዝናናበት ትሻለህ?!

-ምናልባት፣ግን ጥያቄ አለኝ፤የምታደርጊው ነገር ከክርስትና ጋር የሚጻረር

www.path-2-happiness.com

አይደለምን?

-እኔ ሰኩላሪስት ነኝ ብየሃለሁ::

-ኤቲስት ማለትሽ ነው?

-ችግር የለውም፣በሁለቱ መካከል ብዙ ልዩነት መኖሩን አላይም::

-ውበትሽን መቅመስ ጨዋነትንና መልካም ስነ ምግባርን አይጻረርም?

-እዚህ አገር ያለውን ስርዓት እኛ ይበልጥ እናውቃለን፣ስነ ምግባርና ጨዋነትም አንጻራዊ ነገሮች ናቸው::

-እንዴት?

-በአንዱ ሰው ዘንድ መልካም ስነ ምግባርን ሚጻረረው ነገር በሌላኛው ዘንድ የመልካም ስነ ምግባር ቁንጮ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል::

-መርህ የሚባል ነገር ፈጽሞ አይኖርም ማለት ነው?

-የኔ ብቻኛው መርህ ጥቅሜ ነው::

-ይህ የብዙኃኑ ኤቲስቶችና የጥቅመኞችች መርህ ነው!

-አሁን ውበትን መጎንጨት የሚያስገኘውን ደስታ ማወቅ ትፈልጋለህ?

-አሁን ደግሞ ጥያቄዬ ለመናል ነው::

-እኔ ጥያቄህ አያስፈልገኝም፣እኛ አሁን የምናደርገው ነገር ችግራችንና ቆሻሻው ሙስጠፋ እንድንፈጽመው ያስገደደን ውርደትና ቅሌት ነው፤ዓእሻ ተነሽ እንሂድ::

-ቅሌትና ውርደት ከሆነ ለምንድነው የምትፈጽሙት?

ዓእሻና መናል ወጡ፤በከፍተኛ ጩኸት ቤቱን ከሚረብሻው የሙዚቃ ድምጽ ውጭ መድረኩ በዝምታ ተዋጠ፤ዝምታው የተሰበረው በአስተናጋጁ መምጣት ነበር . .

-ሙስጠፋ መጠጥ አዞላችሁ ምርጫቸውን ጠይቅ ብሎኛል፤ምን ልታዘዝ?

-ይቅርታ . . እኔ አልጠጣም::

-አልጠጣም! ከነኚህ ቆነጃጅት ጋር እዚህ የተገኘኸው ታድያ ለምን ይሆን? ለማንኛውም የዳንስ ምሽቱ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ይጀምራል:: እዚህ የተዋችሁ እንድትደሰቱ ብሎ መሆኑን እንድነግርህ ሙስጠፋ ጠይቆኛል፣ሁለት ተኩል ላይ የዳንስ ቅልጥፍናህን ለመመልከት ይመጣል:: ሀሳብህን ለውጠህ በመጠጥ ራስህን ማስደሰት ከፈለግህ ጥራኝ ከተፍ እላለሁ::

-አትጠጣም! አንተ ክርስቲያንም አውሮፓዊም አይደለህም ማለት ነው! ከጠጣህ በኋላ በውበት ለመደሰት የተሻለ አቀራረብ ይኖረሃል ብዬ ጠብቄ

ነበር!

-ለምን? መጠጣት የክርስቲያንነት አንዱ መስፈርት ነው?!

-በተወሰነ ደረጃ፤ካህናትና ቀሳውስት እንኳ ለአምልኮ እየጠጡ ለመጠጡ ቅድስና ይሰጡት የለ?

-መጠጣት የአውሮፓዊነት አንዱ መስፈርት ነው ያለውስ ማነው?

-በአብዛኛው አንዱ መስፈርታቸው ነው:: አውሮፓውያን አክራሪ ሙስሊሞች አይደሉም፤ምላሽህ እንዲህ ቅሌት የሚያከናንብ አሽማቃቂ መሆኑ ላይቀር ሙስጠፋ ዓእሻንና መናልን እዚህ እንዲመጡ ለማሳመን ብዙ ደክሟል:: አሁን በተከናነቡት ቅሌት ምክንያት ወደ አክራሪ ሙስሊምነት እንዳይለወጡ እሰጋለሁ::

-ኦህ . . እናም ለአክራሪ እስላም ጥሪ አድራጊና ሰባኪ ሆኛለሁ ማለት ነዋ!! ይህን ሁሉ ጊዜ ዲያና ብቻ ነበረች አንዲት ቃል ሳትተነፍስ ቁጭ ብላ የቆየችው:: ጆርጅ በመገረም ስሜት ፊቱን ወደርሷ አዞረ:: በቃለ መጠይቁ ላይ ጧት ከቀረቡት መካከል በኮምፒውተር ሙያ ብቸኛዋ እስፔሻሊስት ባለሞያ በመሆኗ ትኩረቱን ስባ ነበር . .

-አንቺሳ ምን ትያለሽ? አንቺ ብቻ ነሽ የተለየሽ!

-ለምንድነው እኔ ብቻ ከነሱ የተለየሁ የሆንኩት?

-የተማርሽ . . ምሁር . . ዝምተኛ!

-ነገር ግን እኔም እንደ እነሱው ለገጸ በረከትነት የቀረብኩ እቃ ነኝ::

-እቃ ለመሆን ለምን ተስማማሽ?

-ከራሴ ለመሸሽ ፈልጌ::

-እንዴት?

-ሕይወት ታክቶኛል፣መኖር አስጠልቶኛል፤በመዝናናትና በጫወታ ከስነ ልቦና ችግሬ እንደምወጣ አጎቴ ሙስጠፋን መክሮት ነው::

-ያንቺ አቋምስ?

-የመኖርን ትርጉም ባውቅ ኖሮ አቋም ይኖረኝ ነበር! ዳሩ ግን በነፋስ እንደሚቦን አቧራ ሕይወት ያለ ትርጉም የሚያቦነኝ ፍጡር ነኝ:: አጎቴ ከሙስጠፋ ጋር በማቀናጀት የዘየደው ዘዴ ምናልባት የተሻለ ሊሆን ይችላል!

-የተሻለው ዕድሜሽነንም አባክነሽ ከሕይወትሽ በመሸሽ ወደ ሽቀጥነት መለወጥ ነው?!

-ምናልባት የብኩንነትንና የዓላማ ቢስነትን ምንነት አታውቅም

ይሆናል፤ባይሆን ኖሮ እንዲህ አትለኝም ነበር:: አሁን ካለሁበት ራሴን ማጥፋት የተሻለ ነው::

- በሃማኖታችሁ መሰረት ግን ለምን እንደምትኖሩ ታውቃላችሁ፤ለምን እንደተፈጠራችሁም ታውቃላችሁ::
- እኔ አላውቅም፣ብትነግረኝ ምስጋናዬ ወደር የለውም::
- ሙስሊም ወዳጄ ዛሬ እንደ ነገረኝ የተፈጠራችሁት አላህን ለማምለክ ነው፤ድንቅ በሆነ ፍልስፍናዊ ገለጻ ነበር የአምልኮን አጠቃላይ ምንነት የተነተነልኝ::
- እኔ ግን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን እንጂ ሙስሊም አይደለሁም::
- ሁለቱ ሙስሊሞች ለቀው ሄደዋል፤አሁን በተሻለ ሁኔታ መደሰት ትችላለህ፣የዳንስ ምሽቱ ዝግጅት የሚጀምርበት ጊዜ እየተቃረበ ነው::
- ሁለታችሁም እንደኔው ክርስቲያኖች እንደመሆናችሁ ሌሊቱን አብረን ለመደሰት እስማማለሁ፣ነገር ግን ዲያናን አንድ ነገር እንዲታሳምነኝ ከማድረግ ግዴታ ጋር ነው::
- ምኑን ነው የማሳምንህ?
- መታደልን የማገኘውና ደስታን የምጎናጸፈው የሁለታችሁን ድንቅ ውበት በመጎንጨትና መጠጥ በመጠጣት ዓለምን ረስቼ ከአስከፊው ሕይወት ወደ መርሳት ደስታ በመሸሽ መሆኑን አሳምኚኝ::
- ከኔ ይበልጥ ሰሚራ ልታሳምንህ ትችላለች::
- ያስቀመጥኩት ግዴታ ግን አንቺ እንድታሳምኚኝ ነው::
- ሰሚራ ከግብጽ ምርጥ ቆነጃጅት ኮረዳዎች አንዷ ነች::ዓለምን በሙሉ የምታስረሳህ የተዋጣላት ተወዛዋዥም ናት፤በተለይ ደግሞ ከርሷ ጋር አንድ ብርጭቆ መጠጥ ከወሰድክ:: አሳመነህ?!
- ማመን እየጀመርኩ ነው፤ግን ለምንድነው ሰሚራ ሰሚራ የምትይው? ፍላጎቴ አንቺ መጀመሪያ እንድትጠጪና መጀመሪያ ካንቺ ጋር እንድንጨፍር ቢሆንስ?
- በሕይወቴ መጠጥ ጠጥቼ ባላውቅም ግን እስማማለሁ፤አሁን ከፍተኛ ጭንቀት ነው የሚሰማኝ፣ሕይወቴን ካጨለሙና ካወደሙ እነዚህ ጥያቄዎች መገላገል እፈልጋለሁ::
- የትኞቹ ጥያቄዎች?!
- ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የሚያናውጡኝ መገኘትን፣መፈጠርን፣የሕይወት ምንነትንና የመሳሰሉትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች::

- መጠጣት መጨፈርና ወሲብን መፈጸምሽ እንኳ ቢሆን እነዚህን ጥያቄዎች ያስረሱኛል ብለሽ ታምኚያለሽ?
- ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን እንኳ፣እኔ ለምትፈልገው ሁሉ ዝግጁ ነኝና አታካች ጥያቄዎችህን አታብዛ::
- እኔንም እንዳንቺው ጥያቄዎቹ አድክመውኛል፤ነገር ግን ከነሱ መሸሽ የጅላ ጅሎች ስልት መሆኑን ማረጋገጥ ችያለሁ:: ትክክለኛው አካሄድ መጋፈጥና ምላሽ ማግኘት ብቻ ነው::
- እኔም እንደዚያው ነኝ! ግና ታክቶኛል::
- አንቺ በዕውቀትሽ፣በጥበብሽና በብሩህ አእምሮሽ ውብ ነሽ:: እናም ይህን ሁሉ ውበት ለገላሽ ውበት ብለሽ አታበላሺ::
- አሁን እሄዳለሁ፤ላበረከትክልኝ ምክሮችህና ላከናነብከኝ ቅሌትም አመሰግናለሁ . . ደህና ሁኑ::
- እኔና አንተ ብቻ ቀረን፣እኔ ዝግጁ ነኝ:: እዚህ ወይስ እዚያ ሆቴል ነው እንድንጨፍርና እንድንዝናና የምትፈልገው?
- ሙስጠፋ የትነው ያለው?
- ሙስጠፋ እኛ በነጻ አብረን እንድንዝናና ነው ትቶን የሄደው፣በል እንሄድ::
- በይ ምሪን . .

ጆርጅ ከሰሚራ ጋር አብረው ተነሱ፣እርሷ ወደ መጨፈሪያ መድረኩ ስታመራ እርሱ ቤቱን ለቆ ለመውጣት ፊቱን አዙሮ ወደ በሩ አቀና . . ሊወጣ ሲል ሙስጠፋ አንዷን ኮረዳ ይዞ ቆሞ ተመለከተ . . በጨረፍታ አየት አድርጎ ፊቱን አዙሮ ወደ ውጭ መሄዱን ቀጠለ . .

- ጆረጅ ጠብቀኝማ . . ወዳጄ ምን ሆነሃል?
- ምንም . . ስለ ደከመኝ ወደ ሆቴል ሄጄ ማረፍ ፈልጌ ነው::
- አደርስሃለሁ ና ግባ::
- ጥሩ፣መልካም ፈቃድህ ከሆነ እባክህ ቶሎ በልልኝ::
- ኮረዶቹን እንዴት አየሃቸው?
- በጣም ቆነጃጅት ናቸው::
- በነጻ እንድትዝናኑና እንድትደሰትባቸው ብዬ ነው ትቼህ የሄድኩት::
- እስኪበቃኝ ተደስቼባቸዋለሁ::
- ይበልጥ ትኩረትህን የሳበች ማናት?
- ሁሉም ናቸው፤በነገራችን ላይ አንተ ሙስሊም ነህ?
- አዎ፣ስሜም ከነብዩ [የአላህ እዝነትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ስም

www.path-2-happiness.com

የተወሰደ ነው፡፡

- ዋይ የሙስሊሞች ቅሌት!
- ምን እያልክ ነው?
- ምንም፤አንተም እንደ ወዳጄ እንደ ጀማል ሙስሊም ነህ፣ግን ከርሱ በብዙ ነገር ትለያለህ፡፡
- እርሱ አክራሪ ነው፣ተስፈንጣሪ ነው ብየሃለሁ፤እኔ ግን በውጭ አገር የተማርኩና ክፍት አእምሮ ያለው ሰው ነኝ፡፡
- በጣም ስለደከመኝ ፈጠን በልልኝ፤ቶሎ ወደ ሆቴሉ ደርሼ ማረፍ እፈልጋለሁ፡፡
- ቀጠሯችን ነገ ስንት ሰዓት ላይ ነው?
- ለነገ ቀጠሮ የለንም፣እኔ ሌላ ቀጠሮ አለኝ፤ግን እንደዋወላለን፡፡

ጆርጅ በመገረምና በመደመም መዳፎቹን እያላተመ ወደ ሆቴሉ ገባ፡፡ በጣም ረዥምና በተቃርኖ . . በግጭትና ባልተጠበቁ ዱብ እዳዎች የተሞላ ቀን ነበር . . የሰራ አካላቱ ዝሎ ወደ ክፍሉ እንደደረሰ አልጋው ላይ ተዘረጋ . . ጥያቄዎቹ በተጠናከረ ሁኔታና በብርቱ ግፊት ሲመጡበትና ሲያስጨንቁት ተሰማው . . እንደሱው የጥርጣሬ ሰለባ ሆና ወደ ጭፈራና ጨዋታ የሸሸችው ምሁሯን ዲያና አስታወሰ . . ለወዳጆቹ በኢሜይል ልኮላቸው የነበረውንና ዛሬ ደሞ ጀማል ‹‹እስላምን ተቀብለህ ከመስለም ያገደህ ምንድነው?›› ሲል መልሶ ለርሱ ያቀረበው የገዛ ጥያቄው ትዝ አለው . .

የመንፈስ ሹክታ

www.path-2-happiness.com

17 የመንፈስ ሹክታ

የመንፈስ ሹክታ

(1)

ጆርጅ እየተጫጫነው ከእንቅልፉ ተነሳ:: የመሰላቸት ስሜት የሚሰማው በመሆኑ ቀኑን ሙሉ ከማንም ጋር ባይገናኝና ከክፍሉ ሳይወጣ ቢውል ምኞቱ ነው:: ዳሩ ግን ከካኽ ጋር ፍጥጫ ውስጥ በመሆኑ ሊያሸንፈውና አስቸጋሪ ተልእኮውን በስኬት ሊያጠናቀቅ ቆርጧልና ግላዊ ጉዳዮቹንና የሚጠናወቱትን የመሰላቸት፣የማመንታትና የመዛል ስሜቶች ማስወገድ የግድ ይላል፤ሥራውንና መጪ ዕድሉን እንዲያጨናግፉ መፍቀድ የለበትም::

ከጀማል ጋር ቀጠሮው ዛሬ አራት ሰዓት ላይ በመሆኑ ለቁርስና ኢሜይሉን ለማየት በቂ ጊዜ አለው:: ከክፍሉ ለመውጣት ስላልፈለገ ደውሎ ቁርስ ክፍሉ ድረስ እንዲመጣለት ጠየቀ፤ቁርሱ እስኪደርስ ቶሎ ተጣጥቦ ለመውጣት ባኞ ገባ . .

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ አስተናጋጁ ቁርሱን አምጥቶ ጠረጴዛው ላይ ደርድሮለት ወጣ . . ጆርጅ ቁርሱን እየበላ ኢሜይሉን ከፍቶ ማየት ሲጀምር ከካትሪና የተላከለትን ደብዳቤ አገኘ . .

‹‹ፍቅሬ ጆርጅ

ከሄድክ ገና አጭር ጊዜ ቢሆንም ለምን በጣም እንደናፈኩህ ብቻ ሳይሆን ከአጠገቤ እንድትሆን ለምን በጣም እንዳስፈለገኝ አላውቅም:: እስክትመጣ አንድ ወር መጠበቅ አይቻለኝም:: ብዙ ግራ የሚያጋቡ ችግሮች ስላሉብኝ በእጅጉ ታስፈልገኛለህ:: ግራ የመጋባቴን ደረጃ ለመጥቀስ ያህል እኔ ካቶሊካዊቷ ሃይማኖተኛ ቁርኣን የሚሉትን የሙስሊሞች ቅዱስ መጽሐፍ ትርጉም ሰምቼ አልቅሻለሁ እለሃለሁ:: እናም በጣም በተረበሸ ሁኔታ ውስጥ እየኖርኩ ነውና ታስፈልገኛለህ::

አፍቃሪህ ካትሪና››

መልስ ጻፈላት . .

‹‹ፍቅሬ ካትሪና

በቅርቡ እመለሳለሁ የሚል እምነት አለኝ:: ትናንትና የነበረኝ ቀጠሮ በጣም መጥፎና ስለ ሙስሊሞችም አፍራሽ ምስል የሚያንጸባርቅ ነበር:: ችግሩ ከራሳቸው ከሙስሊሞቹ ወይም ከሃይማኖታቸው ይሁን አይሆን ግን አላውቅም፤ትናንት ከርሱ ጋር ቀጠሮ የነበረኝን ሙስጠፋ ግን እጠለዋለሁ::

www.path-2-happiness.com

በቀናት ውስጥ ለመመለስ እሞክራለሁ። ከካኽ ጋር ባለኝ ፍጥጫ ተሸናፊ መሆን አልፈልግምና ጸልይልኝ።

አፍቃሪሽ ጆርጅ››

ከጃኖልካም ደብዳቤ ደረሰው . .

‹‹ወዳጄ ጆርጅ

ደብዳቤህ ደርሶኛል፤የሙስሊሞችን ስርቆት በተመለከተ ሀሳቤ ትክክለኛ በመሆኑ ተደስቻለሁ። ከእንግዲህ ከችኮላ መጠንቀቅ አለብህ። የሴቶችን ሁኔታ በሚመለከት ምንም ብዥታ የለብኝም፤ዋነኛው ብዥታዬ እስላም ውስጥ ነጻነት ያለውን ቦታ በተመለከተ ብቻ ነው፤ሀሳብ ወይም አመለካከት ካለህ አካፍለኝ።

ጃኖልካ››

ምላሽ ጻፈለት . .

‹‹ወዳጄ ጃኖልካ

በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀሳቤን በመቀየሬ ትገረም ይሆናል!! ልክ ነህ እስላም ውስጥ ሴቶችን የሚጨቁን ምንም ነገር የለም።ሥርዓቱ በአውሮፓዊ ሕብረተሰባችን ውስጥ ያልለመድነውና ሙሉ በሙሉ የተለየ ቢሆንም፣እስላም ከሴት ልጅ ተፈጥሮና ስነ ሕወታዊ አፈጣጠሯ ጋር የሚጣጣሙ ድንጋጌዎችን ይዟላት ነው የመጣው። ይህ በሴቶች ጉዳይ ላይ ሰፊ ጥናትና ብዙ ውይይት ካካሄድኩ በኋላ የደረስኩበት ማጠቃለያ ሲሆን በነጻነት ጉዳይ ላይ ግን ብዙ ንባብም ሆነ ውይይት ገና አላካሄድኩም። የደረስክበት ነገር ካለህ ላክልኝና ለሁሉም ስብስብ መልሼ እልካለሁ፣በተጨማሪም በርእሱ ላይ ንባብና ውይይት አካሄዳለሁ።

ጆርጅ››

የኢሜይል መልእክቶቹን በመከታተል ላይ እያለ የክፍሉ ስልክ ጮኸ . . አንድ እንግዳ እየጠበቀው መሆኑን ለመንገር የደወለው የእንግዳ መቀበያ ሰራተኛው ነበር . . ሰዓቱን ተመለከተ፤ገና ሦስት ተኩል በመሆኑ ገረመው . . ጀማል ከቀጠሮው ግማሽ ሰዓት አስቀድሞ እንዴት መጣ? . .

- ይቅርታ ማነው የሚጠብቀኝ?
- አንዲት ወጣት ልጅ ናት።
- ማን ናት?
- እርሱ ያውቀኛል ብላኛለች፣ስሟን ግን አልነገረችኝም።
- መልካም እንግዳውስ መጣሁ።

ጆርጅ ወደ እንግዳ መቀበያው አመራ፣የምትጠብቀው ዲያና ናት። ቀለል ያለ ተራ ልብስ ለብሳ ጸጉሯን ወደ ኋላ አስራለች።ፊቷ ላይ ምንም ዓይነት

ሜካፕ አይስተዋልም። በትናንቱና በዛሬ ሁኔታዋ መካከል ያለው ልዩነት በጣም ሰፊ ቢሆንም ከነተፈጥሮው ያለው የዛሬ ፊቷ ከትናንቱ ይበልጥ ውበትና ልስላሴን የተላበሰ ይመስላል። እይታዋ ብስለትና ጠንቃቃነቷን የሚያሳብቅ ሲሆን ትላልቅ ዓይኖቿ ጎላ ጎላ ብለዋል . .

ጆርጅ በሰላምታ ከተቀበላት በኋላ እንድትቀመጥ ጋበዛት . .

- ምን ትጠጭያለሽ?
- ምንም አልፈልግም፤ጊዜህን መውሰድ አልሻም በአንድ ጉዳይ ላይ ላነጋግርህ ፈልጌ ነው።

ሁለት ጭማቂ እንዲያመጣላቸው ጆርጅ አስተናጋጁን አዘዘ . . ከዚያም ወደ ዲያና ፊቱን አዙሮ ለምን እንደመጣች ጠየቃት . . ለመደበቅ ብትሞክርም ዓይኖቿ እንባ ማቅረራቸውን አስተውሏል . .

- እሺ . .
- ትናንት ከውስጥ ከሚያወድሟትና ከሚገድሏት ጥያቄዎች ለመሸሽ ስትፈልግ የነበረችዋ ልጅ ነኝ! እኔ ትናንት ያዋረድካት ልጅ ነኝ! እኔ ኦርቶዶክሷ ፈርጣጭ ነኝ! አንተ እንደምትለውም እኔ ዝምተኛዋ ጭምቷ ምሁር ነኝ፤እኔ የታከተኝ ፍጡር ነኝ! . .
- በሚገባ አስታውስሻለሁ፣ግን ከኔ የሚፈለገው ምንድነው?
- ቆንጆ አይደለሁም ወይ?!
- ቆንጆ ነሽ በጣም፣ያውም ልብ የሚያዋልል ምስራቃዊ ውበት የታደልሽ! ይሁንና ቆንጆ ነሽ እንድልሽ ነው የመጣሽው?!
- ታድያ ትናንት ለምን አዋረድከኝ?
- ስጠይቅሽና ሳዋይሽ ነበርኩ እንጂ እኔ አላዋረድኩሽም።
- ጥያቄዎቹ እንደኔው እንዳታከቱህ ነበር የተናገርከው! ሽሽት የጥያቄዎቹን ጉዳይ እንደማይፈታ ነው የጠቀስከው። እናም የነዚህን አድካሚ ጥያቄዎች መልስ ልትነግረኝ ትችላለህ?
- ለዚህ ነው የመጣሽው?
- አዎ!
- መልስ አላገኘሁም፣እንዳውም በነዚህ ጥያቄዎች ምክንያት ራሴን ለማጥፋት ተቃርቤ ነበር ብልሽስ?!
- ያልከው ነገር እውነት ከሆነ ይህ ብስለትህንና ብልህነትህን የሚያመለክት ማስረጃ ነው።
- ምላሽ አለማግኘቴ የብልህነቴ ማስረጃ ነው?!
- አለመሸሽህና መጋፈጥህ የብልህነት ማስረጃ ነው ማለቴ ነው።
- ታድያ አንቺ ለምንድነው የምትሸሸው?

www.path-2-happiness.com

-ሰዎች ነንና በድክመት ሁኔታዎች ውስጥ እናልፋለን::
-ስመሆኑ ለነዚህ ጥያቄዎች እውነተኛ መልሶች የሉምን?
-ያለ ጥርጥር አሉ::
-መልሶቹን ለማግኘትና ለማወቅ ያለኝን ጽኑ ፍላጎት ይህ ነው ብዬ ልነግርሽ አልችልም::
-እኔ ግን አውቃለሁ ግን ፈሪና ደካማ ነኝ::
-ታውቂያለሽ?!
-አዎ አውቃቸዋለሁ፤ይሁን እንጂ የሰው ልጅ የገዛ ራሱን ለመርታት በቂ ድፍረትና ጀግንነት ካልኖረው በስተቀር፣ህልውናውን ማረጋገጥ፣በሕይወቱ መታደልን ለማግኘትም ሆነ ራሱን ለመለወጥ አይችልም::
-የምትናገሪው ነገር አልገባኝም!
-አንዳንዴ ደሃ ደሃ ሆኖ የሚቀረው አንድ ሥራ ብጀምር እከስራለሁ ብሎ ስለሚፈራ ነው፤ላጤም አንዳንዴ እንደዚሁ ማግባትን ስለሚፈራ ላጤ ሆኖ ይቆያል፤ማይምም አንዳንዴ መማርን ስለሚፈራ ማይም ሆኖ ይቀራል::
-ትክክልና ግልጽም ነው፤ስለምን እንደምትናገሪ ግን አልገባኝም!
-ለነዚህ ጥያቄዎች አርኪና አሳማኝ መልስ አውቃለሁ፣ነገር ግን ልገደል ወይም ልታሰር እችላለሁ ብዬ ስለምሰጋ ባለሁበት ስቃይ ውስጥ እኖራለሁ::
-እኔ ግን ፈሪ አልሆንም! . . መልሱን ንገሪኝ፣ምንድነው?
-እስከዚህ ድረስ ጀግናና ደፋር ለመሆንህ እርግጠኛ ነህ?
-ምናልባት፤መልካም ፈቃድሽ ከሆነ ያለ ብዙ መፈላሰፍ ንገሪኝ::
-እኔም እንዳንተው እል ነበር፣በመጨረሻ ግን ፈሪ ሆኜ የምሸሸባቸውን መንገዶች ወደ ማሰላሰሉ ተመለስኩ::
-አንቺ የምትይውን ነገር አሳማኝ ሆኖ ካገኘሁት እስኪ ጀግንነቴን ልፈትሽበት! ለጥያቄዎቼ ምላሽ የማገኘው ከየት ነው?
-እኔ የመጣሁት ለጥያቄዎቼ እንዴት ምላሽ እንደማገኝ ካንተ ለማወቅ እንጂ አንተን ለማሳወቅ አይደለም::
-በተገላቢጦሽ እኔ ተማሪ ሆኛለሁና በይ ንገሪኝ::
-የምነግርህ ነገር ሊያስቆጣህ ይችል ይሆናል፤ዳሩ ግን ከረዥም ጥናትና ፍለጋ በኋላ ከርሱ በስተቀር ሌላ አላገኘሁም:: እናም ሙስሊም ከመሆን ምንድነው የከለከለህ?

ጆርጅ ወደ ሰማይ አንጋጠጠ:: ተመልሶ ለዲያና በደረቁ ፈገግ አለ:: የመታደልን መንገድ ለመፈለግ ከቆረጠበት ጊዜ አንስቶ ያለፈባቸውን ሁኔታዎች ማጠንጠን ጀመረ . . ከሪሙ፟ሏህ፣ኣደም፣ሸይኽ ባስም፣ጀማል . .

ያለፈበት ረዥም ጉዞ፣ያሳለፈው ብዙ ተሞክሮ፣ንባቡ፣ጥናቱና ውይይቱ . . የዚህ ሁሉ አድካሚ ጉዞ መዳረሻ እስላም ሊሆን? የመታደል መንገድ እስላም ራሱ ሊሆን?!

ደግሞስ የመታደልን መንገድ ካገኘ ያለ ምንም ማመንታት በቀጥታ እይዘዋለሁ፤እከተለዋለሁ ሲል የነበረውስ እርሱ ራሱ አልነበረምን? ኣደም ድፍረትና ሞራላዊ ጀግንነት ያስፈልገሃል ማለቱ ትክክል ይሆን እንዴ? እንዳለው ማሳየት የሚፈልገው ጀግንነትና ቁርጠኝነት ዝም ብሎ የማስመሰል ብቻ ይሆን? . .

-ረበሽኩህ መሰለኝ አዝናለሁ! ከዚህ የተለየ ሌላ ምላሽ አንተ ዘንድ ይኖራል የሚል ተስፋ ሰንቄ ነበር:: ዝምታህ እንደኔው የፍርሃትና ድፍረት የማጣት እንደማይሆን ምኞቴ ነው::
-ይቅርታ . . የለም እንዳው ሳስብ ነበር!
-ስለምን ስታስብ ነበር?
-ስለ ጥያቄሽ::
-መልሱን አስቀድሜ አውቃለሁ . . ፈርተሃል::
-ምኑን ነው የምፈራው?
-በዙሪያህ ያሉ ሰዎችን . . የገዛ ራስህን::
-የለም አልፈራሁም . . መጀመሪያ ግን አንቺ ራስሽ እስላምን እስከዚህ ድረስ መፍራትሽ ለምን እንደሆነ ልትነግሪኝ ትችያለሽ?
-እኔ እስላምን አልፈራሁም!
-ታድያ ምንድነው የፈራሽው?
-የፈራሁት ቤተሰቦቼን ነው፤አባቴ ስለሞተ የምኖረው ከእናቴ ጋር በወንድሟ ቤት ነው:: እኔ ብሰልም አጎቴ እብድ እንደሚሆን አውቃለሁ፤ሊገድለኝም ይችላል!
-ለምን?
-ቤተሰቦቼ ሙስሊሞች ያታልሉናል የሚል እምነት አላቸው::
-ይህ እንኳ ምናልባት እውነት ሊሆን ይችላል::
-አጎቴ ከክርስቲያኖቹ እንኳ ይልቅ ለሃይማኖታቸው ተገዥ ካልሆኑ ሙስሊሞች ጋር ብዙ ቅርርብ እንደኖረኝ ሁሌ ይጥራል:: በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር ስለምከራከር በሃይኖታችን ላይ ያለን እምነት እንዲሸረሽር ታደርጋለች ብለው ብዙ ጊዜ ይወቅሱኛል:: ለሃይማኖታቸው ተገዥ ያልሆኑ ሙስሊሞች ከክርስቲያኖቹም የባሱ በመሆናቸው አጎቴ ከነሱ ጋር እንድቀራረብ ግፊት ያደርግብኛል::
-እንደ ሙስጠፋ ካሉት ጋር ማለትሽ ነው?

www.path-2-happiness.com

-አዎ፣እንዴት እጠላው መሰለህ!
-ግን እርሱ አርአያነት ያለው ሙስሊም አይደለም እንዴ?!
-ሴኩላሪስት በለው ሊብራል፣ግራ ዘመም ነው ሰይጣናዊ . . የፈለከውን ስም ስጠው የብልሹ ጋጠ ወጦች ዓይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ ግን እንዳትሰልም የሚያደርግህ ምንድነው? መልስልኝ፡፡
-ይቅርታ በቅድሚያ የጀመርነውን መጨረስ እፈልጋለሁ፡፡ ብትሰልሚ አጎትሽ ሊገድልሽ የሚችለው ለምንድነው?
-ክርስትናን ለቆ የመሄዱ ሁኔታ ሁሌ እንዳይደጋገም ለመከልከልና ለመግታት፡፡
-ይህማ ከተራ የሃይማኖት ነጻነትና ከሰብአዊ መብት ጋር የሚጋጭ ነው!
-የምን ነጻነት! እኔ እንዳንተው ክርስቲያን ነኝ፡፡ እናም አእምሮህ በማይቀበላቸው የቤተክርስቲያን ሚስጥራት ያለማመን ነጻነት አለህ?! በአንዳንዶቹ ወንጌሎች ውስጥ እንደሰፈረው ኢየሱስ አምላክ አይደለም ብለህ የማመን ነጻነትስ አለህ?!
-አሁን እነዚህን ወደ ጎን ተይአቸው፡፡ እኔ አሁን ቀጠሮ አለብኝ፣ወዳጄ እዚያ ጥግ ቁጭ ብሎ እየጠበቀኝ ነው፣ውይይታችንን በኋላ ለመቀጠል እፈልጋለሁ! ፈቃደኛ ከሆንሽ ከሙስሊሙ ወዳጄ ጋር ላስተዋውቅሽ፡፡
-እንደኔው ድፍረትና ጀግንነት ስላነሰህ የጠየኩህን ጥያቄ ከመመለስ እየሸሸህ መሰለኝ፡፡ ለማንኛውም ውሳኔው የራስህ ነው . . ከወዳጅህ ጋር ለመተዋወቅ ግን ደስተኛ ነኝ፡፡

ጆርጅ ወደ ጀማል ሄዶ በመዘግየቱ ይቅርታ ጠየቀውና ስለ ዲያና ነገረው፣አብረው ወደሷ ተመለሱ . .
-ይህች መስለም የምትፈልገው ዲያና ናት፡፡
-ዲያና እንኳን ደህና መጣሽ፣ጀማል እባላለሁ ከእስክንድሪያ ነኝ፣መስለምሽ ያስደስተናል፡፡
-እኔም ከእስክንድሪያ ነኝ፣ግን ኦርቶዶክስ ነኝ፡፡ ለጆርጅ መስለም እፈልጋለሁ አልልኩትም፣ያልኩት ነገር የብዙዎቹ አሳሳቢ ጥያቄዎቻችን ምላሽ እስላም ውስጥ ይገኛል ነው፡፡
-መልካም . . ጭንቀትና ድብርትን የሚወድ ወይም ለጥያቄዎቹ ምላሽ ማግኘት የማይፈልግ ማንም ሰው ስለሌለ፣ይህ ራሱ አንቺ እስላምን ትፈልጊያለሽ ማለት ነው፡፡
-ትክክል ነው . . ለዚህም ነው ለምን አትሰልምም? የሚል ጥያቄ ለጆርጅ ያቀረብኩለት፡፡
-እኔም መልስ አልሰጠኋትም . . የግብጻውያን ጭካኔ ግን በጣም

አስበርግጎኛል፡፡ ዲያና ብትሰልም እንደምትታሰር ወይም እንደምትገደል ነው የምትናገረው!
ዲያና ብሶት እየተነፈሰች ቀና አለች . .
-አዝናለሁ . . ግብጾችን ብቻ እንዳትወቅስ እጠይቃለሁ! እናንተ አውሮፓውያንና አሜሪካውያን በጭካኔ ረገድ ከኛ በብዙ ደረጃ ትበልጣላችሁ፡፡ ኢራቅ ውስጥ በአቡ ጉረይብ የፈጸማችሁትን ረሳህ? ግፍ ጭካኔ ጥቃትና ማንአህሎኞነት በከፋ መልኩ እናንተ ዘንድ የተንሰራፋ ነው፣በተለይም በሴቶች ላይ፡፡ በምዕራቡ ዓለም ሴቶች ከወንዶች ይበልጥ በስድስት እጥፍ ለመመታትና ለጥቃት እንደሚጋለጡ መካድ ትችላለህ? በአሜሪካ 33% የሚሆኑ፣በእንግሊዝ 77% የሚሆኑ ባሎች ያለ ምንም ምክንያት ሚስቶቻቸውን እንደሚመቱ ማስተባበልስ ትችላለህ?
-የተናገርኩት ነገር ያስቆጣሽና የረበሸሽ ይመስላል!
-አይደለም፣ግን ግብጻዊት ነኝና ወቀሳህን ከአገሬ እከላከላለሁ፡፡
-አገርን መውደድ መልካም ነገር ነው . . በጣም ጥሩ ነገር ነው! ይሁን እንጂ መርህን መውደድ ይበልጥ ተገቢ ነው፡፡ እኛ ዘንድ በምዕራቡ ዓለም ትምክህትና ጭካኔ መኖራቸውን ብቀበልም እናንተም ዘንድ መኖራቸው ግን አስገርሞኛል፡፡ በሃይማኖትና በእምነት ነጻነት ረገድ ግን እኛ የተሻልን ነን፡፡ ያለ አንዳች ችግርና ባሰኘሽ ጊዜ ክርስቲያን፣ሙስሊም፣ይሁዲ ወይም ቡድሂስት . . መሆን ትችያለሽ፡፡
ጀማል ስቆ ቀጠለ . .
-እህህ፣ለዚህ ነዋ ሕጃብ ፈረንሳይ ውስጥ የተከለከለው!! አዛንና ሚናሬት መስራት ስዊዘርላንድ ውስጥ የተከለከለው በዚህ ነጻነት ነዋ!! ስለ የትኛው ነጻነት ነው የምታወራው?
-ጀማል ልክ ነህ፡፡ ግን እኛ አንድ ሰው መስለም ቢፈልግ አናስረውም ወይም አንገድለውም!
-እኛም ብንሆን መስለም የፈለገ ሰው አንገድልም!
-ጀማል ትክክል ነህ . . ይህ እኛ ዘንድ ያለው የክርስቲያናዊ ጠባብ ወገንተኝነት አካል ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይሁንና እስላምም እንደዚሁ በሰይፍና በጉልበት አይደለም የተስፋፋው?
-እስላምን በኢንዶኔዥያ፣በናይጄሪያ፣በኢትዮጵያ . . እንዲስፋፋ ያደረገ የጦር መሪ ማን ነበር? አብዛኞቹ የእስላም አገሮችና ሙስሊሞች በብዛት የሚኖሩባቸው አገሮች፣እስላምን ያለ ምንም ሰይፍ በደዕዋና በትምህርት ብቻ ነው የተቀበሉት፣ማንም ሰው እስላምን እንዲቀበል አልተገደደም፡፡ ይህ ታሪክ ያረጋገጠው እውነታ ነው . . ይቅርታ፣በብዙዎቹ የእስላም አገሮች

www.path-2-happiness.com

ውስጥ ክርስቲያኖች ለ1400 ዓመታት ያህል ክርስትናቸውን ይዘው ሲኖሩ እምነታቸውን እንዲለውጡ ማንም አላስገደዳቸውም። ሕንዶች ከአንድ ሺ ዓመታት በላይ በእስላም አስተዳደር ስር ሲኖሩ እስላምን እንዲቀበሉ ተገደው ያውቃሉ? ሙስሊሞች አንደሉስን ወይም የዛሬዋን እስፔይንን ሲገዙ እንዲሰልሙ ክርስቲያኖችን አስገድደው ያውቃሉ? በኋላ ላይ ግን በተቃራኒው ክርስቲያኖቹ ነበሩ ከመገደልና ክርስትናን ከመቀበል አንዱን እንዲመርጡ ሙስሊሞችን ያስገደዱት።

ውይይትና ክርክሩ ሰፍቶ እተንዛዛ መሆኑ የተሰማው ጆርጅ ከቀጠሮው እንዳይስተጓጎል ለመቋጨት ፈለገ . .

- በጣም ዘግይተናል፤እርስ በርሳችሁ እንድትተዋወቁ ፈልጌ ነው . . ዲያና ይህ ቢዝነስ ካርዴ ነው፣የስልክ ቁጥርሽን እፈልጋለሁ።
- ቢዝነስ ካርዴን እንካ፤ጀማል አንተም ያዝ።
- ችግር ከሌለው ምናልባት ዛሬ ወይም ነገ እደውልልሽና ውይይታችን እንቀጥልበታለን።
- ዋናው ነገር አጎቴ እንዳያውቅ ብቻ ነው። ካወቀ ግን እንደ ወፋእ ቆስጠንጢን፣ወይም ክሪስቲን መስሪ፣ወይም እንደ ሚርና ዓድልና እንደ ሌሎቹ መሆኔ ነው . . ልብ በል እስካሁን ጥያቄየን አልመለስክም!
- ዛሬ ወይም ነገ እደውልልሻለሁ፤ጥያቄው አስቸጋሪ ቢሆንም መልስ እሰጣለሁ! በይ አሁን ፍቀጅልን እኛ እንሂድ።

(2)

ወደ መኪና ከገቡ በኋላ ጆርጅ ወደ ጀማል ዞር ብሎ በአግራሞት ጥያቄ አቀረበለት . .

- ዲያና በመጨረሻ የደረደረቻቸው ስሞች ምንድናቸው?
- ወፋእ ቆስጠንጢን፣ክሪስቲንና ሚርናን . . እና የመሳሰሉትን ማለቷ ነው። ሁሉም የሰለሙ ክርስቲያኖች ሲሆኑ ታግተው ብዙ ሰቆቃ የተፈጸመባቸውና አንዳንዶቹም የተገደሉ ናቸው! የነርሱ እጣ ፈንታ እንዳይደርሳት ስጋቷን እየገለጸች ነው።
- ሽብርና ጭካኔ ነው። ለማንኛውም የካይሮ ቆይታዬን ነገ አበቃለሁ፤ለተወሰኑ ቀናት ወደ እንግሊዝ ሄጄ ወደ ካይሮ እመለሳለሁ። ባለቤቴ የኔን በአጠገቧ መገኘት በሚያስፈልጋት ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች።
- መልካም፣ዛሬ ከመጨረሻው ኩባንያ ጋር ቀጠሮ አለህ፤ከዚያ በኋላ የምትፈልጋቸውን ነገሮች ጠቅለል ባለ መልኩም ቢሆን መልክ መልክ አስይዛቸው።

- ልክ ነህ ይህንኑ ነው የማደርገው። ከሄድኩ በኋላ ሥራው ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግና ለክትትል የሚያመች የሥራ ማእቀፍ መፍጠርም ያስፈልገኛል።
- ከመጨረሻው ኩባንያ ጋር ከምታደርገው ግንኙነት በኋላ አንደኛቸውን ለዚህ ኃላፊነት ብቁ ሆኖ ልታገኝ ትችላለህ . . ደርሰናል፣መቼ እንድመጣልህ ነው የምትፈልገው?
- አብረን እንግባና ከዚያ በኋላ እንወስናለን።

ወደ ኩባንያው ሕንጻ ደርሰው ከሥራ አስኪያጁ ጋር ለመገናኘት ጸሀፊዋን ጠየቁ፤ባለ ቀጠሮዎቹ መድረሳቸውን ደውላ ነገረችው . .

- ዶክተር ኻሊድ እየጠበቃችሁ ነው ግቡ።

እንኳን ደህና መጣችሁ ብሎ ከተቀበላቸው በኋላ ወደ ስብሰባ ክፍሉ አስገባቸው . .

- በተጻጻፍነው መሰረት ዛሬ ማነጋገር የሚቻል ባለሞዎች ይኖራሉ ብዬ እጠብቃለሁ።
- አዎ ለዛሬ አራት ሰዎች አሉ። የቴክኒክ ሞያተኞችንና የዕውቀትና ቴክኖሎጂ አመራር ባለሞያዎችን በሁለት መደብ ስለ ከፈልኳቸው፣ሌሎቹን ከፈለክ ነገ ልታገኛቸው ትችላለህ።
- በጣም ጥሩ . . የዕውቀትና ቴክኖሎጂ አመራር ባለሞያዎችንስ?
- እንደ ነገርኩህ አራት ናቸው ዛሬ ለቃለ መጠይቅ ታገኛቸዋለህ፤ካመንክባቸው በኋላ እነርሱ ራሳቸው በአንተ ቦታ ሆነው የቴክኒክ ባለሞያዎችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ ይችላሉ ብዬ አስባለሁ። በመሰረቱ የቴክኒክ ሞያተኞችና ፕሮግራመሮች ሲሆኑ በተጨማሪም የቴክኒክና ፕሮግራሚንግ ኦፕሬሽን አመራር ትምህርት የቀሰሙና ክህሎትም ያላቸው ናቸው።
- መቼ ላገኛቸው እችላለሁ?
- ሻዩን ከጠጣህ በኋላ በነጠላ ወይም አንድ ላይ እንደፈለክ ማግንት ትችላለህ።
- መልካም ፈቃድህ ከሆነ አራቱንም አንድ ላይ ማግነት እፈልጋለሁ።
- እንዳሻህ፣ሻይ እስክትጠጣ ዝግጁ መሆናቸውን ላረጋግጥ . . ከቃለ መጠይቁ በፊት ልታውቃቸው ስለሚገባ እነዚህ ሲቪዎቻቸው ናቸው። ይቅርታ መጣሁ . .

ጆርጅ ሲቪዎቹን በችኮላ አያቸው። የሰዎቹ ልምድና ክህሎት ትኩረቱን ስቧል፤ይሁን እንጂ እስኪያነጋግራቸው ድረስ መቸኮል አልፈለገም። መረጃዎቻቸውን በትንሽ ወረቀት ላይ ጠቅለል አድርጎ አሰፈረ . .

ሙሐመድ ዐሊ - ሙስሊም - 38 ዓመት፣የግብብጽን የኤሌክትሮኒክስ መንግስት ፖርታል ፕሮጄክቶችን የመራ ሲሆን ፕሮግራሙ ግን ፍጻሜ

አላገኘም።

አሚር እስሐቅ - ክርስቲያን - 37 ዓመት፣የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የግብጽ መንግስት የቴክኖሎጂ የጋራ ፕሮጀክቶችን እንዲሁም የግብጽን የኢንፎርሜሽን ማእከል መርቷል።

ሰልዋ ሐሰን - 39 ዓመት - ሙስሊም፣በስማርት ፎን መስክ በተሰማራ ኩባንያ ውስጥ የቴክኖሎጂ ፕሮጄክቶችን መርታለች።

ማዝን ከማል - 39 ዓመት - ሙስሊም፣ሁለት የፕሮግራሚንግና የድረ ገጽ ዲዛን ኩባንያዎችን መርቷል።

ጽፎ እንደጨረሰ ዶክተር ኻሊድ ተመልሶ መጣ . .

- ጨርሰህ ከሆነ ወደ ስብሰባ ክፍል እንዲገቡ እጠራቸዋለሁ።
- ዝግጁ ነኝ።
- እሺ ጆርጅ፣እኔ መሄዴ ነው፣መቼ እንድመጣልህ ነው የምትፈልገው?
- ጀማል አመሰግናለሁ፣ከአንድ ሰዓት በላይ የሚያቆየኝ አይመስለኝም፣እጠበቀሃለሁ አብረን የምንሄድበት ቦታ አለ።
- መልክም፣ደህና ሁን።

ዶክተር ኻሊድ ባለ ሲቪዎቹን ጆርጅ ቁጭ ብሎ ወደ ሚጠብቃቸው ስብሰባ ክፍል እንዲገቡ ጠየቃቸው . .

- የናንተንም ሆነ የኢንጂነር ጆርጅን ጊዜ መሻማት አልፈልግም፣እርሱ የሚፈልገውን አብራርቼላችኋለሁ፣ሲቪዎቻችሁንም ተመልክቷል። ጊዜ ለማሳጠር ሲባል አንድ ላይ ነው የሚያነጋግራችሁ፤ጆርጅ መቀጠል ትችላለህ።
- የሁላችሁንም ሲቪዎች ተመልክቻለሁ፣ሁሉም በእጄ ይገኛሉ፤ለሁላችሁም አድናቆት አለኝ። እያንዳንዱ ሰው ለኩባንያችን ምን ማበርከት እንደምችልና ለምን እንደተስማማ ይንገረኝ።

የተናገሩትን አዳምጦ አብሯቸው ተወያየ፤ለሁሉም ያለውን አድናቆት ገልጾ የሚፈለግባቸውን ነገራቸው . . ከመካከላቸው ሦስቱን (አሚር፣ሰልዋና ማዝንን) ለመምረጥ መወሰኑን ገልጾ ሙሐመድ ሥራው ብዙ የማይመጥነው መሆኑን አስረዳ። ከመካከላቸው አንድ ሥራ አስኪያጅ እንዲመርጡ ጠይቋቸው አሚር እንዲሆን ወሰኑ . .

- ሥራ አስኪያጃችሁ ክርስቲያን በመሆኑ ችግር የለባችሁም?
- አንተም ክርስቲያን ነህ ምን ችግር አለው?
- አሚር ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ጓደኛዬ ነው፤እፊቱ እናገራለሁ፣የአመራር ብቃት አለው፤እንዲሰልም እመኝለታለሁ፤ባይሰልምም ግን ወዳጄ ሆኖ ይቀጥላል።

- የናንተ ዓይነቱን የምዕራባውያን ችግር እኛ ከሙስሊሞች ጋር የለንም፤እኔም ማዝን ከኔ የተሻለ የአመራር ብቃት አለው የሚል እምነት ነበረኝ።
- እኔ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቀጠሮ አለብኝ፣ስብሰባችሁን ቀጥላችሁ የኩባንያው የቢሮ ሥራ የሚጀመርበትን የተሟላ ዝርዝርና የመጀመሪያ ዓመት እቅድ እንድትነድፉ እፈልጋለሁ። በእቅዱ ላይ ተወያይተን ለማጽደቅና ሥራ ለመጀመር ነገ ጧት እንገናኛለን። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ሠራተኛ ኤጀንሲ ኩባንያ ዘንድ ምርጥ ከሆኑ የቴክኒክ ሠራተኞች ስብስብ ጋር ተገናኝቼ ቃለ መጠይቅ ማካሄዴን ስነግራችሁ በደስታ ነው።
- ዶክተር ጊዮርጊስ የሚመራውን ነው?
- አዎ አሚር . . ታውቀዋለህ እንዴ?
- ዶክተር ጊዮርጊስ ለኔም ለማዝንም ጓደኛችን ነው . . ምርጥና የሰለጠነ የሰው ኃይል ያቀርባል።
- እንደዚሁም በሌላ ኤጀንሲ ያገኘኋትና ዲያና ሳምሕ የምትባል በጣም ድንቅ የሆነች ፕሮግራመርም አለችኝ።
- እህህ፣ፕሮግራመርዋ ዲያና ሳምሕ?
- ታውቃታለህ?
- የእህቴ ልጅ ናት።
- አንተ አጎቷ ነህ ማለት ነው?
- አዎ።
- ሊሆን አይችልም!
- ምኑ ነው መሆን የማይችለው?!
- ዛሬ ማታ የግድ አንተን ማግኘት አለብኝ። ምሽት አንድ ሰዓት ላይ ለእራት ግብዣ ብጠራህ ትቀበላለህ?
- ሁላችንም ነው?
- አይደለም፣ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌለው የግል ጉዳይ ነው የፈለኩህ።
- መልካም፣የትነው?
- ባረፍኩበት ሆቴል ውስጥ፣አድራሻውን እንካ ያዝ።

www.path-2-happiness.com

(3)

-ወደ ሆነ ቦታ እንድትወስደኝ እፈልጋለሁ፣አትቃወም::
-ችግር የለውም፣ግን ወዴት ነው?
-ከድሆችና ከተራ ነዋሪዎች ጋር መቀመጥና መነጋገር እፈልጋለሁ::
-በጣም እንግዳ የሆነ ጥያቄ ነው፤አልቃወምም፣ለምን እንደሆነ ግን ማወቅ እችላለሁ?
-አንዳንድ ነገሮችን ከራሳቸው አንደበት መስማትና ሕይወትን እንዴት እንደሚመለከቱ ማወቅ እፈልጋለሁ::
-አሳማኝ ምክንያት ነው::
-በነገራችን ላይ ከሰለመች ሊገድላት ከሚችለው የዲያና አጎት ጋር ተዋውቄአለሁ፣የሆነ ነገርም አስቤአለሁ::
-የት ተዋወቅከው?
-የኩባንያችን ቢሮ ሥራ አስኪያጅ እንዲሆን ያጨሁት ሰው እርሱ ነው::
-እንዲህ ያለው ሰው ለዚህ ተገቢ አይደለም፣ጆርጅ ምነው ጭፍን ወገንተኝነት!
-ከተስማማሁና ሥራ አስኪያጅ እንዲሆን ከወሰንኩ በኋላ በአጋጣሚ እንጂ አጎቷ መሆኑን አላወቅኩም::
-ይሄ ሀሳብህን እንድትቀይር የሚያደርግ ነውርና የስነ ምግባር ሕጸጽ ነው::
-ልክ ነህ፣ይሄ የማደርገው ነገር ነው፤ግን ዛሬ ማታ አንተም ከምታየውና ከማደርገው ሙከራ በኋላ የሚሆን ነው:: ዛሬ በኔ ሆቴል አብረን እራት እንድንበላ ተጋብዘሃል::
-ምን አሰብክ?
-ማታ ታየዋለህ::
-መልካም፣እነሆ ወደ ተራ ሰዎች ሰፈር ደርሰናል . .
-የሆነን ሰው እቤቱ ድረስ ሄጄ መጎብኘት እፈልጋለሁ::
-እቤቱ ገብተህ መጎብኘት! ግድ የለም የማውቀው ሰው አለ፣ግን በዛኛው የመንገድ ጎን ነው:: እስኪ ልደውልለትና መኖር አለመኖሩንና ጉብኝታችንን ይቀበል እንደሆነም ላረጋገጥ::
-ጥሩ፣እኔም ለዲያና ልደውል::

ጆርጅ ለዲያና ደውሎ አንድ ሰዓት ላይ በሆቴሉ ለመገናኘት ቀጠራት . . ጀማልም ለጋሼ ሰዒድ ከጆርጅ ጋር እንደሚጎበኙት ለመንገር ደወለላቸው . .

-የተዘጋጀ ምግብ ገዝተን ይዘን መሄድ ይኖርብናል::
-ለምን?

-አስቀድሞ ቀጠሮ ሳይኖረን በምሳ ሰዓት እየሄድን በመሆኑና ጋሼ ሰዒድ እኛን ለማስተናገድ አቅም እንደሌላቸው ስለማውቅ ለምን እናሸማቅቃቸዋለን?
-መልካም ብለሃል፣በጣም ምርጥ የሆነ ምግበና ጣፋጮችን ከሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ጋር እንግዛ::

ወደ ጋሼ ሰዒድ ቤት ደረሱ:: በጣም ያረጀና ንጽሕናው ባልተሟላ ጠባብ ጎደና የሚገኝ ቤት ነው . . ጀማል በሩን አንኳኳ፤ጋሼ ሰዒድ እንኳን ደህና መጣችሁ ብለው በፈገግታ በሩን ከፍተው ተቀበሏቸው:: ምግብ፣አትክልትና ጣፋጮቹን ይዘው አብረው ወደ ውስጥ ገቡ . . በጣም ያረጀ ግን በጣም ንጹህ ወደ ሆነ አሮጌ ክፍል ወሰዷቸው:: የተዘጋጀው የመሬት መቀመጫ አሮጌ ፍራሽ ሲሆን መሀል ላይ ዳቦ፣ጥቂት አትክልትና አንድ ሳህን ሩዝ የተደረደረበት የምግብ መብያ ላስቲክ ተነጥፏል . .

-እባካችሁን አረፍ በሉና ጀምሩ::
-ምግብ ይዘን መጥተናል፣እንኩ ያዙ::
-አመሰግናለሁ፣አስፈላጊ አልነበረም፤እኔ ላስተናግዳችሁ ተዘጋጅቻለሁ፤እንዲያዘጋጁልን አንዴ ወደ ውስጥ ላስገባ::

ጋሼ ሰዒድ ወደ ውስጥ ገቡ:: ጆርጅ የተነጋገሩትን በትክክል እንዲነግረውና ጋሼ ሰዒድ የሚናገሩትን እያንዳንዱን ቃል እንዲተረጉምለት ጀማልን ጠየቀው፣አንድም ቃል ሳይተረጉምለት እንዳያልፍ አሳሰበው . . ከደቂቃዎች በኋላ ጋሼ ሰዒድ እንግዶቹ ያመጡት ምግብ በየሳህኑ የተደረደረበትን ትልቅ ሳፋ ይዘው ተመለሱ . .

-በሉ ጀምሩ፣አክብራችሁናል::
-ጀማል . . በዚች ዓለም ላይ ምኞታቸው ምን እንደሆነ ጠይቃቸው::
-የኔ ልጅ ከችግር መሰወርንና ጤንነትን ነው::
-በሕወታቸውስ ደስተኛ ናቸው?
-ልጄ ጌታችን የዋለልን ውለታ ከባድ ነው፣እቤት ውስጥ እኖራለሁ ልጆች አሉኝ፣የእለት ጉርሴን አገኛለሁ፤ከዚህ በላይ ምን እፈልጋለሁ?
-ገንዘብና ንብረት እንዲኖራቸው አይመኙም?
-ጌታችን ሲሳይ ይስጠን ይጨምርልን፤ግን ገንዘብ ብቻ አይደለም፣ገንዘብም ጤንነትም የሕሊና ሰላምና እርጋታም ይጨምርልን::
-የሕሊና እርጋታና ሰላም ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ ጠይቃቸው::
-ጀማል ወዳጅህን እንዴት እንደሚኖር ጠይቀው፤የሕሊና እርጋታን የማያውቅ ሰው ሕይወቱ የመከራ ሕይወት ነው::
-እንደገና ጠይቅልኝ፣እንዴትና መቼ ነው የሕሊና መረጋጋትና እፎይታ የሚሰማቸው?

-የሕሊና መረጋጋትና እፎይታ የሚሰማኝ ዐስር (አስር ሰዓት) አካባቢ ከልጆቼ ጋር ሻይ ስጠጣ፣የአምላኬን ትእዛዝ ሳልጥስ ውዬ፣ያለብኝን ግዴታ ተወጥቼ ማንንም ሳላውክ ለመተኛት ሌሊት ጎኔን ሳሰርፍና ነው:: ሶላት ከሰገድክ በኋላ የሕሊና መረጋጋትና እፎይታ አይሰማህም ወይ? በልልኝ::

ጀማል ያሉትን ሲተረጉምለት ጆርጅ አቀርቅሮ ለረዠም ጊዜ ዝም አለ . .

-አዝናለሁ፣እናንተ እንግዶቼ ናችሁና ልትከበሩ ይገባል፣ የማይገባ ተናግሬ አስቀይሜአችሁ እንዳልሆን::

-ይቅርታ መጠየቅ አያስፈልጋቸውም፣ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ መልስ ባለመስጠቴ እኔ ነኝ:: መልካም ፈቃዳቸው ከሆነ መልሱን ይለፉኝ:: የመጨረሻ ጥያቄ ላቀርብላቸው እፈልጋለሁ፣ለምንድነው የሚኖሩት?

-ጥያቄዎቻችሁ የሚገርሙ ናቸው! ለምን እንደሚኖር የማያውቅ ሰው አለ እንዴ?! ልጄ ጌታችን የፈጠረን እንድናመልከው ነው፤የሚመግበንና ሲሳይ የሚቸረንም እርሱ ነው፤ችሮታና ቸርነት በርሱ እጅ ነው:: እኔ የምለው ግን የክቡር ጉብኝታቸው ምክንያት ምንድነው?

-ክርስዎ ለመማርና ክርስዎ ጋር ለመተዋወቅ ነው በላቸው::

-አላህ ብሩክ ያደድርጋችሁ፣ተባረኩ::

ጋሼ ሰዒድ እነሱ ካመጡት ምርጥ ምግብ ይልቅ የራሳቸውን ቤት ያፈራውን ምግብ እየበሉ መሆናቸውን ጆርጅ አስተውሏል . .

-ጀማል እኛ ካመጣነው ምግብ ለምን እንደማይበሉ ጠይቃቸው::

-እናንተ እንግዶቼ በመሆናችሁ እናንተ ያመጣችሁት ቢሆንም ለናንተ ሰስቼ ነው . . እውነቱን ለመናገር ከተራው የኔ ምግብ እናንተ ከምግባችሁ የምታገኙትን ተመሳሳይ እርካታ አገኛለሁ:: አንድ ሰው ደስተኛና ጤነኛ እስከሆነ ድረስ ሁሉም ምግብ ጣፋጭ፣አላህ ይመስገንና ሁሉም ሕይወት ተድላ ነው::

በልተው ጨረሱና ጋሼ ሰዒድን ለመስተንግዷቸው አመስግነው ተሰነባብተው ወጡ . .

-መቼም ብዙ አስቸግሬሃለሁ፣አሁን ደግሞ ቤተክርስቲያን ወይም የተራ ክርስቲያን ሰው ቤት መጎብኘት እፈልጋለሁ!

-እንግዳውስ የጋሼ ሰዒድ ጎረቤት ክርስቲያን ነውና ወርደን እንዲያስፈቅዱልን እንጠይቃቸው?

-መልካም . .

ጀማል ደውሎ ነገራቸው፣ወዲያው ነበር ጋሼ ሰዒድ ፈገግ እያሉ የወጡት . .

-ኑማ ተከተሉኝ::

-ወዴት?

-ወደ ጎረቤቴ ቤት . . በር ላይ መሆናችሁን ነግሬው እንኳን ደህና መጣችሁ ግቡ ብሏል::

ጋሼ ሰዒድ በሩን ሲያንኳኩ ራሳቸውን በሻሽ የተሸፋፈኑና ፊታቸው ብቻ የሚታይ ትልቅ አሮጊት በሩን ከፈቱ . .

-ግቡ፣ሳብርን ከእንቅልፍ ቀስቅሼው ፊቱን እየታጠበ ነው::

-አንዴ ወደ ቤቴ ሄጄ የሆነ ነገር ይዤ እመለሳለሁ::

-ጀማል ይህ የክርስቲያን ቤት ስለመሆኑ እርግጠኛ ነህ?

-አዎ፣እንደነገሩን የክርስቲያን ቤት ነው::

-ታድያ ሴትየዋ ለምንድነው ጸጉራቸውን የሸፈኑት?

-መልሱን ባውቀውም ከራሳቸው ብትሰማ እመርጣለሁ::

ጋሼ ሰዒድ ቡና እና የሚበሉ ነገሮችን ይዘው ተመለሱና ከእንግዶቹ ፊት አኖሩ . .

-ሁሉም ነገር እኔ ዘንድ ዝግጁ ስለሆነ ጎረቤቴ ምንም ነገር ለማዘጋጀት እንዳይለፋ ነግሬዋለሁ፤ድንገት የመጣንበት በመሆኑ የርሱ እንግዳ የኔም እንግዳ ነው::

-ለምግቡ ለቡናውና እንግዶችን ይዘህ በመምጣትህ አመሰግናለሁ::

-ጀማል፣ሁለቱ ከመቼ ጀምረው ጎረቤቶች እንደሆኑ ጠይቅልኝ::

-አባቴና አባቱ ጎረቤታሞች ከነበሩበት ከ12 ዓመቴ ጀምሮ ሰዒድ ጎረቤቴ ነው

-የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ግን አይደላችሁም!

-ልክ ነው፣ግን ጎረቤታትና ወዳጆች ነን . . ሰዒድ ሁል ጊዜ እንድሰልም ይመክረኛል::

-ስለ እስላምና ክርስትና ያላቸውን አመለካከትና በሁለቱ እምነቶች መካከል ስላለው ግንኙነት ጠይቅልኝ::

-የኔ ልጅ ኢየሱስና መሐመድም ሁሉም የአላህ መልእክተኞች ናቸው:: እኔና ወላጆቼ ከድሮም ክርስቲያኖች ስንሆን ሰዒድና ወላጆቹ ደግሞ ከጥንቱ ሙስሊሞች ናቸው:: በመካከላችን ያለው ግንኙነትም ከጥንት ጀምሮ እጅግ በጣም ጥሩ ነው::

-ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን የሚያምኑ እስከሆነ ድረስ ለምን እንዳልሰለሙ ጠይቃቸው::

-እህህ፣ሰዒድም እኮ እንደዚሁ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን ያምናል፤እናም ለምን ክርስትናን አልተቀበለም?!

www.path-2-happiness.com

- ሙስሊሞች ዒሳ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን ስለሚያምኑና ክርስቲያኖች ግን ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን ስለማያምኑ ነው።
- ይህማ ራሱ ሰዒድ የሚናገረው ነገር ነው። ልጄ እውነቱን መስማት ትፈልጋለህ? አባቴና አያቶቼ የነበሩበትን መተው ስለምፈራ እንጂ ሰዒድ የሚለው ነገር አሳማኝ ነው፤ከአጎቶቼ ልጆች ይበልጥ እወደዋለሁ። እኔም ጥያቄ አለኝ፣ለመሆኑ አንተ ክርስቲያን ነህ ወይስ ሙስሊም?
- ለጊዜ ሲባል መልሱን ለራሴ ላቆይና ሌላ ጥያቄ አለኝ፣ባለቤትዎ እንደ ሙስሊሞች ለምን ይለብሳሉ?
- የኔ ባለቤት ብቻ ሳትሆን ሁሉም ግብጻውያት ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የሚለብሱት ነው።
- እኛ ዘንድ በአውሮፓ ክርስቲያኖች ጸጉራቸውን አይሸፍኑም።
- እኔ የማውቀው ግን እናንተ ዘንድ በአውሮፓም ሴቶች ጸጉራቸውን የሚሸፍኑ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎም ፊታቸውን ጭምር ይሸፍኑ እንደነበረ ነው። ሁኔታው የተለወጠው ከጥቂት ምእተ ዓመታት ወዲህ ብቻ ነው! እስኪ የሴት ቅድመ አያቶችህን ፎቶግራፎች ፈትሽ። እኛም እንደዚሁ ነን፤ነገር ግን ትናንሽ ክርስቲያን ልጃገረዶች እናንተን መከተል ይወዳሉ፣በመልካሙ ነገር ቢሆን ባልከፋ ግን በጭፍኑ እናንተን ይኮርጃሉ።
- ለምን ክርስቲያኖቹ ብቻ?
- በሙስሊሞች ዘንድ ሃይማኖት ሕይወትን ሙሉ በሙሉ የሚያጠቃልልና አሻራውን በማሳረፍ የሚለውጥ በመሆኑና ኃጢአትን የሚያስተሰርየው ተጸጽቶ መመለስና ንስሀ በመሆኑ ነው። በክርስቲያኖች ዘንድ ግን የሰውን ልጅ ሕይወት የሚለወጠው በቤተክርስቲያን በሚሆን ነገር ነው . . እኛ ዘንድ የትኛውም ስህተት ቢሰራ ኢየሱስ አንዴ ከኃጢአቶች ሁሉ ነጻ ስለ አወጣን ነገሩ ቀላል ነው።
- ለሁለቱም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርብልኝ፤ከሆቴሉ ቀጠሮ እንዳንዘገይ መሄድ ይኖርብናል።

ጋሽ ሰዒድንና ጋሼ ሳብርን ተሰናብተው ወጡ . . ወደ መኪናዋ አመሩ . .

- የፈለከውን ነገር አሳካህ?
- አዎ . . እኔ እንጃ፣አሁን ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ምንም ያህል አልቀረውም . . በውስጤ የሚፈነዳ እሳተ ገሞራ እንዳለ ሆኖ ይሰማኛል። ከዲያና እና ከአጎቷ ጋር ቀጠሮ ባይኖረኝ ኖሮ ከነዚህ ተራ ሰዎች ጋር ረዥም ጊዜ ለማሳለፍ እሞክር ነበር። ጥልቀት ባለው ቅለትና ተራ ሁኔታ ነው ስለ ሕይወት የሚገልጹት . . ጀማል ይቅርታ . . የመናገር አምሮቴ ጠፍቷል።

- መልካም።

የጆርጅ ጭንቅላት በአንድ ጥያቄ ‹‹አንተን ከመታደል መንገድ ከልክሎ የያዘህ ምንድነው?›› በሚለው ሊፈነዳ ተቃርቧል። ፈራህ እንዴ? ወይስ የመታደል መንገድ አሁንም ገና አልተገለጸልህም?! ወይስ አንተ ያወቅከው ማወቅ የምትፈልገውን ሳይሆን ማወቅ የማትፈልገውን ሆኖ ይሆን? በውስጡ በሚመላለሱ ግልጽ መረጃዎች ዓይነትና ብዛት የተነሳ መረጋጋት ከተሳነው አእምሮው የጥያቄው ጫና ምነው ፋታ በሰጠኝ ብሎ ተመኘ . .

(4)

- ወደ ሆቴሉ ተቃርበናል፤ዲያናንና አጎቷን ለእራት ጋብዣለሁ።
- ምን ማድረግ ነው የፈለከው?
- ልጅቷ እንድትሰልምና ከአጎቷ ችግር እንዲትገላገል አደርጋለሁ።
- በጣም ጥሩ፣ወደ እስላም ጥሪ የሚያደርግ ዳዒ ሆንክ ማለት ነው፣አንተ ግን የምትሰልመው መቼ ይሆን?
- ለጋሼ ሳብር እንዳልኩት ሁሉ . . መልሱን ለራሴ አቆያለሁ። ጭንቅላቴ በዚህ ጥያቄ ምክንያት ሊፈነዳ ነው፣ምናልባትም ከጥያቄው ለመሸሽ እፈልግ ይሆናል፣ማን ያውቃል . .
- አንተ ዳዒው እንዴት ብለህ ይሆን እንድትሰልም ጥሪ የምታደርግላት?!
- ለሹፈትህ አመሰግናለሁ! እሷ መስለም ትፈልጋለች፣ነገር ግን አጎቷን ትፈራለች። እናም ይህን ፍርሃት ነው የማስወግደው።
- እንዴት?
- ታየው የለ? አሁን ደርሰናል።
- ይልቅስ ከአጎቷ በኩል በዲያና ላይ ችግር እንዳትፈጥርባት።
- በጊዜ ነው የደረስነው፤ወጥቼ ሻንጣዬን አስቀምጬ ሬስቶራንቱ ውስጥ ቶሎ ከናንተ እቀላቀላለሁ።

ጀማል ወደ ሬስቶራንቱ ሲገባ ዲያና እና አጎቷ አንድ ጠረጴዛ ይዘው ጆርጅን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ፤አብሯቸው ቁጭ አለ . .

- ጆርጅ ሸንጣውን ለማስቀመጥ ነው ወደ ላይ የወጣው፣አሁን ይመጣል።
- ምን እንደሚፈልግ አላውቅም፣የዲያና አጎት መሆኔን እንዳወቀ ብቻ አብረን እራት ካልበላን አለኝ፤ምን እንደ ፈለገ ታውቃለህ?
- ምናልባት ዲያና ታውቅ ይሆናል! . .

www.path-2-happiness.com

-እኔ ምንም አላውቅም፣ለምን አልሰለምክም? ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ መልስ ሊሰጠኝ እንደሚደውል ብቻ የነገረኝ ቢሆንም የደወለው ግን ሳልጠብቅ ለእራት ግብዣ ነው!

ጆርጅ ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ደረሰ፣ዲያና ከሩቅ አይታው ምልክት ሰጠችው፣እነሱ ወደተቀመጡበት ጠረጴዛ አመራ . .

-ላስተዋውቃችሁ . . አሚር በግብጽ የኩባንያችን የቀጠና ሥራ አስኪያጅ ነው። ዲያና የኩባንያችን ምርጥ ፕሮግራመር ናት። ይሄ ሙስሊም ወዳጄ ደግሞ ፕሮግራመር ሳይሆን የፕሮግራሚንግ አባት የሆነው የማቴማቲክስ ባለሞያ ነው።

-አጎቴ የኩባንያችሁ ሥራ አስኪያጅ ነው?!

-ሙስሊም ባይሆንም፣በብቃትና በሁሉም ባልደረቦቹ ሙሉ ስምምነት የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ነው።

-ለጣልክብኝ እምነት አመሰግናለሁ።

-እስካሁን የሚገርመኝ ግን የሥራ ባልደረቦቹ ሙስሊሞች ሆነው እያለ እነሱ ራሳቸው ያጩት መሆኑ ነው!

ዲያና ፈገግ አለችና . .

-ምኑ ነው የሚያስደንቀው?!

-አስገራሚው አንዳንድ ክርስቲያኖች መስለም የሚፈልጉ ሰዎችን የሚከለክሉ መሆናቸው ነው።

አሚር በመደነቅ . .

-እስላምን በሚገባ ስላላወቁት ነው!

-አሚር፣አንድ ክርስቲያን ሰው ቢሰልም ችግር የለውም ትላለህ ማለት ነው?!

-ምናልባት መስማት የማትፈልገው ሊሆን ይችላል፣እኔ የማምንበትን ልንገርህ። ማንኛውም ክርስቲያን ፈልጎ ቢሰልም እኔ ምንም ችግር የለብኝም። ምናልባት ስለኔ የማታውቀው ከሦስት ሳምንታት ወዲህ ወደ አንድ እስላማዊ ማእከል እየተመላለስኩ መሆኤን ነው። ማን ያውቃል በቅርብ ጊዜ ውስጥ እሰልም ይሆናል!

-አጎትሽ ሊሰልም ይችላል፣እንግዳውስ አንቺን እንዳትሰልሚ የሚያደርግሽ ምንድነው?

-እህህ፣አሁን ገና ገባኝ።

-ምኑ ነው የገባሽ? ምን ነካሽ?

-አጎቴ አሚር የነገርኩህ አጎቴ አይደለም።

-እንዴት? የነገርሽኝ አጎትሽ ያንድ አባት ያንድ እናት ወንድም ነው ማለት አይደለም?

-አይደለም፣በምነግርህ ነገር ትገረም ይሆናል፣አያቴ ካንድ ሚስት በላይ ነበሩት።

-ክርስቲያን ሆኖ ከአንድ ሚስት በላይ?! ብዙ ማግባት ይፈቀዳል የሚል ክርስቲያን እኔ አላውቅም!

-ማነው ያለው? ወንጌል ከአንድ በላይ ማግባትን አይከለክልም የሚሉ ሰዎች አሉ፣ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ማርቆስ አምስተኛ የምእመናኑንና የከፊል ጳጳሳትን ፍላጎት በመጻረር ከአንድ በላይ ማግባትን በመቃወማቸው ታስረዋል። ሌላው ወገን እንደሚለው ይህ የሆነው በሙስሊሞች ተጽእኖ ምክንያትም ይሁን ወይም ከአንድ በላይ ማግባትን የሚደግፉ አንዳንድ ጳጳሳት እንደሚሉት ወንጌል የማይከለክለው በመሆኑ በመሆኑ፣አለዚያም ሚስቶች እንደሚሉት ቅምጥ ፍቅረኞችን ከመያዝ የተሻለ በመሆኑ . . ለማንኛውም አያቴ ሚስቱ ሞተችና ሌላ ሚስት አገባ። እናም አሚር አጎቴ ነው ግን የነገርኩህ አጎቴ ማርቆስ አይደለም፣ከአሚር ጋር በአባት ብቻ ነው የሚገናኙት።

-ይገርማል! ሕዝቡ ግን ከአንድ በላይ ማግባትን ይፈልጋል።

-እኔን ብቻ ለይተህ ለምን እንደጠራህ አሁን ገና ገባኝ። ዲያናን እንዳትሰልም የሚከለክለው አጎቷ እኔ መስየህ ኖሯል ማለት ነው።

-ልክ ነው።

ዲያና ከንፈሮቿን መጠጠችና በቁርጠኝነት ተናገረች . .

-እኔ ግን የጠራኸኝ ለምን እንዳልሰለምክ ልትነግረኝ ነው ብዬ ነበር ያሰብኩት።

ጀማል በመገረም . .

-ጣልቃ እንድገባ ፍቀዱልኝ፣ዲያና እርሱ እንዲሰልም መጓጓትሽ ትክክለኛ አቋም ነው፣አንቺ ራስሽ ግን ለምን አልሰለምሽም?

-ይህን ጥያቄ አቅርቤለት ከመመለስ ይሸሽ ስለነበረ መልሱን ሊነግረኝ ፈልጎ የጠራኝ መስሎኝ ነበር። አሁንሳ ልትነግረኝ ትችላለህ?

-ተገድጄ መመለስ እችላለሁ፣ብታልፉኝ ግን አመሰግናለሁ።

አሚር ፈገግ እያለ ቀጠለ . .

-እንግዳውስ አትመልስ:: መልስ እንፈልጋለን፣ነገር ግን ያለ ምንም መሸማቀቅ ከሆነ ብቻ ነው::

ዲያና ጣርያ ጣርያውን እያየች . .

-አንተ መግለጽ እስካልፈለክ ድረስ አልናገርም እንጂ እኔ መልስህን አውቃለሁ::

-ሁላችሁንም አመሰግናለሁ . . ግን እውስጤ ያለውን ማንም የሚያውቅ አይመስለኝም::

-አንተ ሰብአዊ ፍጡር ነህና መታደልን ትፈልገዋለህ፣እኔ አጎቴና አሚርም እንዲሁ:: ድፍረትና ጀግንነት ኖሮን ገልጸን ተናገርነው ወይም ፈርተን ከገዛ ራሳችን ሸሽተን ተደበቅን፣ እኛን እንዳናገኘው የሚከለክለን ነገር ራሱ ነው አንተንም የሚከለክለው:: እኔ ለምሳሌ እንቅፋት የሆነብኝ አጎቴ ማርቆስ ነው ብዬ በሁኔታዎች እያሳበብኩ ራሴን እሸነግላለሁ! ድፍረትና ነጻነት ቢኖረኝ ኖሮ ግን እወስን ነበር::

-ግራ አጋባሽኝ! ታድያ ምንድነው የከለከለሽ?

ዲያና ጸጉሯን እየነካካች ቀጠለች . .

-እውነቱን ለመናገር የሚከለክለኝ አንተንና አሚርንም የከለከለው ነገር ነው:: ውስጣዊ ግጭትህ እንዳይጋለጥ እንዳትነግረን እንደ ፈቀድንልህ ሁሉ አንተም በተራህ እንዳንናገር ለምን አትፈቅድልንም? እያንዳንዱ ሰው የየራሱን ቅራኔዎች፣ግጭቶች፣ዝንባሌዎችና ፍላጎቶች እውስጡ አምቆ ይዟል:: ለገዛ ራስ እውነተኛና ታማኝ መሆን ብዙ ያስቸግራል:: በተለይ ደግሞ ጉዳዩ ከሕይወት መሰረት ጋር፣ከሕልውና ምንነትና ከመኖር ዓላማ ጋር የተያያዘ በሚሆንበት ጊዜ:: ለዚህም ነው እኔ በፍርሃትና በሽንፈት እንደማደርገው ሁሉ፣ሰዎች በመጠጥና በጭፈራ . . ከዚህ የሚሸሹት!!

የዲያና አነጋገር ተጽእኖ ያሳደረበት አሚር በመደመም ስሜት ተውጦ ወደ ጫማው እየተመለከተ ቀጠለ . .

-የምትናገሪውን በሚገባ እረዳለሁ:: የሰው ልጅ ደስተኛ ሆኖ መኖር ይኖርበታል:: ፈጣሪ ጌታውን ለማወቅና ሕይወትን ለማጣጣም የመታደልን መንገድም ለራሱ ፈልጎ ማግኘት አለበት:: ይህ ግን ነጻነትና ጀግንነትን የሚጠይቅ ውሳኔ ነው:: ዲያና አንቺ ግን ከሁላችንም ይበልጥ ድፍረትና ጀግንነትን የተላበስሽ ነሽ፤ለዚህም ነው የተናገርሽውን መናገር የቻልሽው::

ጀማል ከመካከላቸው ሆኖ ግራ ቀኝ እየተመለከተ ግራ ተጋብቷል . .

-እኔ ምንም አልገባኝም፣ስለ የትኛው ጀግንነት ነው የምታወሩት?!

ዲያና ጥልቀት ባለው የተረጋጋ አነጋገር ቀጠለች . .

-ከሕሊና ደዌ የመላቀቅ ጀግንነት ነው:: ከሕይወት ውጣ ውረዶች፣ከግላዊ ፍላጎቶች፣ከስሜታዊ ዝንባሌዎች እና ከውዥንብሮች በላይ ሆኖ የመገኘት ድፍረት ነው:: የለመድከውን ወግና ልማድ ድንበር አልፎ የሚሄድ፣የሚነዙ ውዥንብሮችንና የሚሸረቡ ሴራዎችን በጣጥሶ የሚያልፍ ውሳኔ የመወሰን ጀግንነት ነው:: ልቦናህ በሚገባ እያወቀው አንደበትህ ድፍረት አንሶት መናገር የተሳነውን እውነታ የመናገር ጀግንነት ነው::

-አሁንም ለመረዳት እየሞከርኩ ነው!

-አንተ ሙስሊም ሆነህ የተወለድክ በመሆንህ ምናልት መረዳት ሊያስቸግርህ ይችላል፤እኔ ግን ዲያና ማለት የፈለገችውን ተረድቻለሁ፣ጆርጅም እንደዚሁ ተረድቷል ብዬ እገምታለሁ::

የዲያና ዓይኖች እንባ አቀረሩ . . መናገር ቀጠለች . .

-አርሱም መረዳት የማይፈልግ ወይም መረዳቱ እንዲታወቅበት የማይፈልግ ካልሆነ በስተቀር ተረድቷል:: ብዙ ሰዎች ደስተኞች መስለው ራሳቸውን ስለሚሸነግሉ ከራሳቸው ይሸሻሉ::

በፍለጋ ጉዞ ውስጥ ያለፈባቸው ደረጃዎች ሁሉ ጆርጅ አእምሮ ውስጥ በፈጣን ፊልም ሸው እያሉ አለፉ:: ከቁርኣን ያነበባቸውን አንቀጾች ሁሉ አስታወሰ:: ያሳለፋቸው ሁኔታዎች ሁሉ ከፊቱ ተደቀኑ:: መልስ ሊያገኝላቸው የለፋባቸው ቅራኔዎችና ግጭቶች ሁሉ ትዝ አሉት:: ግራ የተጋባ እይታው፣ በተቻለው ሁሉ ሊደብቀው ሞክሮ ባልተሳካለት ከባድ ፍንዳታ ውስጡ በመናጥ ላይ መሆኑን ያሳብቃል:: እናም በሁለት ቃላት ብቻ ለማሳጠር ወሰነ . .

-አዎ ተረድቻለሁ::

-እኔም የምታወሩትን እንቆቅልሽ ተረድቻለሁ:: የዛሬውን ዓለም ሕይወትና የወዳኛውን ሕይወት ተድላ ትጎናጸፉ ዘንድ፣መልካሙን ሁሉ ታገኙ ዘንድ፣የአላህን የተሟላ ሃይማኖት ተቀብላችሁ እንድትሰልሙ ለሁላችሁም እመኛለሁ:: አላህ እንዲህ ብሏል፦ ‹‹ዛሬ ሃማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ:: ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ:: ለናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፤›› [አል ማኢዳህ:3] በእስላም አማካይነት ጸጋ ሁሉ ተሟልቶ ሃይማኖትም ምሉእ ተደርጎ ተቋጭቷል::

-ለረዥም ጊዜ በፍለጋው ላይ የተሰማራሁትን ነገር በሚገባ የተረዳሁ ይመስለኛል::

www.path-2-happiness.com

-ስትፈልገው የነበረው ምንድነው?

-ራሴን ነበር ስፈልግ የነበረው:: የመኖሬን ምንነትና የተፈጠርኩበትን ዓለማ ለማወቅ ነበር ፍለጋ ላይ የተሰማራሁት . . የተውሒድን ብርሃን፣የሕይወትን ውበት ስፈልግ ነበር . . የመንፈስን የአእምሮንና የነፍስን ደስታ ለማግኘት መታደልን ፍለጋ ላይ ነበርኩ::

ዲያና እንባዋን እያደራረቀች ተናገረች . .

-እኔም ስፈልገው የነበረው ይኸው ነው!

-ውብ የእንቁ ጌጥ ይሆን ዘንድ የሕይወቴን ዕንቁዎች አንድ ላይ አደራጅቶ የሚያያይዘውን ገመድ አግኝቻለሁ:: አሁን ለምን እንደ ተፈጠርኩ፣ለምንስ ዓለማ እንደምኖር በሚገባ አውቄያለሁ!!

-እኔ ምንም አልገባኝም ! የገባህ ነገር ምን እንደሆነ ልትነግረኝ ትችላለህ?!

የዲያና ፊት በፈገግታዋ በራ . . ቀጠለች . .

-ስሜትህን እኔም በጥልቀት እጋራለሁ! ከሁላችንም ይበልጥ ነጻነትንና ጀግንነትን የተላበስክ ነህ:: ከገዛ ራስ ጋር እውነተኛና ታማኝ ሆኖ መገኘት ግሩም ድንቅ ብቃት ነው::

-የምፈልገውን ተረድቻለሁ:: አዳምንና ሙጢዕ አረሕማንን ተረድቻለሁ:: ሌቪን፣ቶምን፣ካትሪናን፣ሐቢብን፣ኦርሜላን፣ማይክልን፣ጃኖልካንና ካኽንም ተረድቻለሁ:: ከሁሉም በላይ ግን ጆርጅን ተረድቻለሁ . . የሕይወትን ትርጉምና ምንነት ተረድቻለሁ!

-ምንም አልገባኝም!! የጠቀስካቸው ስሞች ምንድናቸው?

አሚር ከእንባ ጋር እየተናነቀ . .

-ጆርጅ እኔም አሁን አንተን ተረድቻለሁ፤እጅግ በጣም ድንቅ ሰው ነህ!

-ሽማግሌው ስለ ደስተኝነት መንገድ፣ስለ መታደልን ፍለጋ የተናገረውን ተረድቻለሁ::

-ሽማግሌው?! የመታደልን መንገድ፣የደስተኝነትን ጎዳና ልታሳየን ትችላለህ?!

-መንፈሴ፣ነፍሴና ሕሊናዬ መልስ ሰጥተውኛል:: የመንፈስ ሹክታን፣የሕሊናን ጥሪ እነሆ አሁን ሰማሁ! . . ሁላችሁም ባለ ውለታዎቼ ናችሁ!

-መንፈስህ መልስ ሰጠህ?!

-አዎ፣ከመንፈሴ ተለይቼ ነበር፤አእምሮዬና እውቀቴ መንገዱን አውቀው መንፈሴ ግን ሩቅ ነበር::

አሚር በመገረም ዓይኖቹን ከፈተ . .

-እኔን እየገለጽከኝ ነው መሰለኝ፤መንፈስህ ምን አለህ?

-ዓለማዊ ሕይወት ከወዳኛው ሕይወት ጋር እንዴት እንደሚጣጣም፣ነፍስ ለሕይወት ትርጉም ከሚሰጠው ተውሒድ ጋር እንዴት እንደምትቀናጅ ነገረኝ::

ስሜቷ በጥልቅ የተነካው ዲያና እንባዋን እየጠራረገች ቀጠለች . .

-ዓለማዊ ሕይወት ከወዳኛው ሕይወት ይጣጣማል?!

-መንፈስ ከዕውቀት ከአእምሮና ከነፍስ ጋር ይጣጣሙና እርስ በርስ ከመታገልና ከመጻረር ፈንታ ይቀናጃሉ:: እርስበርስ መጻረራቸው የመከራዬ ምንጭ ነበር!

-ግሩም ነው፣የመንፈስ ጥራትና ምጥቀት የተሰማህ ጊዜ እጹብ ድንቅ ጊዜ ነው! መንፈስህ አሁን እንዴት ነው አብሮት የተቀናጀውና የተጣጣመው?

ጆርጅ ፊቱ እየበራና ፍልቅልቅ እያለ ቀጠለ . .

-የአካል ደስታ ከመንፈስ ደስታ ጋር ተገናኘ . . ቅለት ከጥልቀት ጋር ተጣመረ . . ዓለማዊ ሕይወት ከወዳኛው ሕይወት ጋር ተቀናጀ . . መርሕ ከጥቅም ጋር ተጣጣመ . .

-ድንቅ ነው . . እጹብ ድንቅ ነው . .

-ነገ ማታ ወደ ለንደን እጓዛለሁ:: የመታደልን መንገድ የማግኘቴን የምስራች እነግረዋለሁ:: ረዥም ጊዜ ራሴን በድያለሁ፤እድሜዬንም አባክኛለሁ::

-ለማነው የምትነግረው?

-የመታደልን መንገድ የሚያገኘው መንፈሴ መሆኑን ሳረጋገጠልኝ ሽማግሌ ነው የምነግረው::

-እዚህ የምትከፍተው ኩባንያ ጉዳይስ?

-ሂደቶቹን ነገ ጧት አጠናቅቃለሁ:: አይሮፕላን የያዝኩት ለተነገወዲያ ዓርብ ምሽት ሁለት ሰዓት ነው:: የህሊናዬን ጥሪ በማዳመጤና የመንፈሴን ሹክታ በመስማቴ፣ሕይወቴና መንፈሴ ተጣጥመውና ተጣምረው መቀናጀታቸውን . . ለሽማግሌው እነግረዋለሁ:: አሁን በዚህች አፍታ ከሁሉም ወዳጆቼ ጋር መገናኘት በጣም አምሮኛል:: እኔ እነሆ ደስተኛ ሆኛለሁ፣በእርግጥ ታድያለሁ፤መንገዱን አግኝቻለሁ::

-ጆርጅ እንኳን ደስ አለህ እለሃለሁ::

-ይቅርታ አድርጉልኝና አሁን በቀጥታ ወደ ክፍሌ መሄድ እፈልጋለሁ::

ጆርጅ ወደ ክፍሉ ሄዶ ለወዳጆቹ ኢሜይል ጻፈላቸው . .

‹‹ በደስተኝነት መንገድ ፍለጋዬ ላይ ከኔ ጋር የተጓዛችሁ ወዳጆቼ . . እነሆ የመታደልን መንገድ አግኝቸዋለሁ . . አግኝቸዋለሁ . . ደስታዬ ወሰን የለውም . . ለአስቸጋሪዎቹ ጥያቄዎቼ ምላሽ አግኝቻለሁ . .

ለናንተ ለሁላችሁም የልብ ፍካትና የህሊና ብርሃን ይገባችኋል . . ሁላችሁም የመንፈስ እርካታና የተውሒድ ጸዳል ይገባችኋል . .

ለናንተ ለሁላችሁም የመንፈስ ደስታና መነቃቃት ይገባችኋል . .

ለናንተ ለሁላችሁም የዓለማዊ ሕይወት ስኬትና የሕይወት ለዛ ይገባችኋል . .

ለናንተ ለሁላችሁም የዓለማዊ ሕይወትና የወዳኛው ሕይወት ተድላ ይገባችኋል . .

እኔ የታደልኩትን የደስተኝነት መንገድና መልካሙን ሁሉ እናንተም ታገኙ ዘንድ ጥልቅ ፍላጎቴ ነው። እኔ አግኝቼዋለሁ፣አዎ አግኝቼዋለሁ። መንፈሴ አእምሮዬና ነፍሴ ጥምረት ፈጥረው ተጣጥመዋል። ዓለማዊ ሕይወት ከወዳኛው ሕይወት ጋር ተጣጥሟል። የአካል ደስታ ከመንፈስ ደስታ ጋር ተገጣጥሟል። ነፍሴ ብዙ ከተበታተነች በኋላ ተሰባስባ አንድ ሆናለች። ጥያቄዎቼ ሁሉ ምላሽ አግኝተዋል . . ይህ የደስተኝነት መንገድ ነው፣ይህ የመታደል መንገድ ነው።

አንተ ቸሩና ርህሩሁ አምላክ ምስጋና ላንተ ይሁን

ወዳጃችሁ/ ጆርጅ ኒሶን››

የይዘት ማውጫ

www.path-2-happiness.com

የይዘት ማውጫ

ሽማግሌው	5
ግራ ያጋቡ ጥያቄዎች!	15
የክህደት ጥርጣሬ . .	35
ሕንድ . . የድንቃድንቅ አገር	55
ድክመት . . !	79
ቀጠሮ ከሽብርተኝነት ጋር . .	103
ኢየሩሳሌም የሃይማኖቶችና የፍጥጫ አገር	137
ሥጋዊ ፍላጎትና መርሕ . .	191
በሕይወትና በሞት መካከል . .	217
ተስፋና ስጋት	253
ወደ አብያተ ክርስቲያናት አገር . .	285
ከቄሱ ጋር	329
ጭንብሉ ሲወልቅ	369
ለውጥና ሽግግር	407
ስርቆቱ . .	443
ግጭት . .	483
የመንፈስ ሹክታ	527
የይዘት ማውጫ	551

www.path-2-happiness

使いやすいウェブサイト